

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች ቅጽ- 12

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
# ሰበር ችሎት ውሣኔዎች



ቅጽ- 12

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ፍርድ ቤት

www.chilot.me

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

## ቅጽ - 12

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጥናትና የሕግ ድጋፍ መምሪያ

ህዳር 2004 ዓ.ም

አዲስ አበባ

www.chilot.me



**<u>የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት</u>**

በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2/1/ ሥር በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሠጠው የሕግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅነት እንደሚኖረው ተደንግጓል፡፡ እነዚህን የሰበር ውሣኔዎች አሣትሞ ማሠራጨት ደግሞ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ኃላፊነት እንደሆነም ተመልክቷል፡፡

በዚሁ መሠረት ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ አስገደጅ የሕግ ትርጉም የተሠጠባቸውን የሰበር ውሳኔዎች ማሣተም የተጀመረ ሲሆን ካለፉት ሦስት ዓመታት ወዲህም ከቅፅ 5 እስከ ቅፅ 10 ያሉትን አሣትመን አሠራጭተናል፡፡ እነሆ አሁን ደግሞ ቅፅ 11 እና ቅፅ 12 የሰበር ውሣኔዎች ሊታተሙ በቅተዋል፡፡ ይህም አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሠጠባቸው የሰበር ውስኔዎቻችንን የማሣተሙ ሥራ ወቅቱን የጠበቀና ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲሆን የምናደርገው ጥረት ከጊዜ ወደጊዜ እየተሻሻለ መምጣቱን ያሣያል፡፡

ባለፉት እትሞች መልእክቴ እንደገለፅሁት እነዚህ ፍርዶች ምንም እንከን የላቸውም የሚባሉ እንዳልሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በፍርድ ቤቶቻችን በየትኛውም ደረጃ ላይ ባለን ዳኞች በአንፃራዊነት የልምድም ሆነ የብቃት ውስንነቶች ሊኖሩ ስለሚችሉ እነዚህ እጥረቶች በሰበር ፍርዶችና ውሳኔዎች ላይ አልፎ አልፎ ቢታዩ ሊገርመን አይገባም፡፡ የብዙ ዓመታት ተሞክሮ ያላቸው ሀገሮች ልምድም የሚያሣዩን ይህንኑ ነውና፡፡

የሀገራችን ፍርድ ቤቶች ውሣኔዎች ወጥና ተገማች እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ የሰበር ውሣኔዎች ሚና በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ ይህን አጠናክሮ ለመቀጠልና ውጤታማ ሥራ ለመሥራት ከሚደረገው ጥረት ጎን ለጎን በሰበር ውሣኔዎቻችን ላይ

በተለያዩ የሥራ መስኮች የተሠማሩ የሕግ ምሁራንና ተማሪዎች ገንቢ አስተያየቶችን እና ትችቶችን ሊሠጡበት ይገባል፡፡

እነዚህ አስተያየትና ትችቶች ከሌሎች በተመሣሣይ ጎዳና ካለፉ ሀገሮች ከምናገኛቸው ልምዶች ተደምረው አቅማችንን በማሣደግ የተጣለብንን ከፍተኛ ኃላፊነት ለመወጣት ጉልበት ስለሚሆኑን የሙያው ባለቤቶችና መላው ህብረተሰባችን ለጥረታችን መሣካት የሚጠበቅባቸውን ሀገራዊ ኃላፊነት እንዲወጡ በአክብሮት እየጠየቅሁ ውሳኔዎቻችንን በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረ ገፅ ላይ ማግኘት የሚቻል መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ማስታወስ እፈልጋለሁ፡፡

ተገኔ ጌታነህ ክፍሌ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት

# በ2003 ዓ.ም. የሰበር ችሎት

## የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **ውል** | | | | |
| 1. | አግባብነት ካለው የመንግስት አካል ፈቃድ ሳይኖር የከርሰ ምድር ቁፋሮ ሥራን ለመስራት የሚደረግ ውል ህጋዊና አስገዳጅ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ | 54249 | ጌታሁን አበበ ቦጋለ<br>እና ሐሰን ገአስ ሁመድ | ጥቅምት 16/2003 | |
| 2. | በህግ አግባብ ተመዝግቦ የሚገኝ የመያዣ ውል ተጠቃሚ የሆነ ወገን በህግ የተቀመጠው ጊዜ ከማለፉ በፊት ውሉ እንዲታደስለት ከጠየቀ የንብረቱ አስያዥ ፈቃድ መኖሩ ሳይረጋገጥ ውሉ ሊታደስና ሊመዘገብ ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3058/1/ እና /2,/ 1632/2/ | 40109 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ<br>እና<br>አቶ ተክሌ ዋከኔ | ጥቅምት 01/2003 | |
| 3. | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ከሚያስተዳድራቸው ቤቶች ጋር በተያያዘ በፍርድ ሃይል የኪራይ ውል እንዲዋዋል የሚደረግበት ህጋዊ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ | 42150 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና<br>እነ አቶ ዳንኤል ካሣ /ሀያ ሁለት ሰዎች/ | ጥቅምት 29/2003 | |
| 4. | ውልን በተመለከተ በህግ የተቀመጠውን ፎርም አልጠበቀም በሚል አቤቱታ ለማቅረብ ስለሚችለው ሰው /ወገን/<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1808/2/ | 47617 | ቄስ ገ/ሚካኤል አለምነው<br>እና<br>ወ/ሮ መልኬ ደምሴ | ህዳር 30/2003 | |
| 5. | የዋስትና ግዴታን ቀሪ ለማድረግ የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1925/2/ | 49041 | የአ/አ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መ/ቤት<br>እና አቶ ኤሣው መዓዛ /ሦስት ሰዎች/ | ህዳር 02/2003 | |
| 6. | ከመኪና ሽያጭ ጋር በተገናኘ ሽያጩ ከመከናወኑ በፊት በነበረ የፍ/ቤት እገዳ መነሻነት ገዢው በባለቤትነት መብቱ መገልገል ሳይችል ቢቀር በሻጩ ላይ የሚኖር ኃላፊነትና የጉዳት ካሣውን በመወሰን በኩል የገዢው ተነፃፃሪ ግዴታ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2341/2/ 2281, 2336, 2329, 2360, 1802, 1790 | 52106 | እነ አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>አቶ ታደሰ አደሬ | ህዳር 13/2003 | |
| 7. | እቃን ለመግዛት በጨረታ ማስታወቂያ ያወጣ ድርጅት ተወዳዳሪዎች በጨረታ ላይ ከተነገረው የተለየን ዕቃ በማቅረብ ከተወዳደሩ በኋላ ድርጅቱ ተወዳዳሪ የሆነው አካል በጨረታ ሰነዱ ላይ ሞልቶ ያቀረበውን እቃ መሰረት በማድረግ ውል የተዋዋለ እንደሆነ ይህንኑ ውል ለመፈፀም የሚገደድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1695/2/ | 53968 | እነ የምስራቅ ወለጋ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>አቶ ፀጋዬ ነጋ | ህዳር 13/2003 | |
| 8. | በማህበር አባላት ስምምነት የሚወጣ ደንብን አስመልክቶ በማህበሩ አባላት መካከል ብሎም በማህበሩ እና በአባላት መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን እልባት ለመስጠት በፍትሐብሔር ህጉ ውስጥ ስለ ውሎች በጠቅላላው የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1676/1/ | 54312 | አቶ ሃይላይ ተክላይ<br>እና<br>ውቁር የጨው አምራቾች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር | ህዳር 28/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 9. | ውል ጋር በተያያዘ ተዋዋይ የሆነ ወገን ውሉን የፈፀምኩት ተገድጄና ከፍላጐቴ ውጭ ነው በሚል የሚያደርገውን ክርክር ዳኞች (ፍ/ቤቶች) የዚህን ተዋዋይ ወገን እድሜ፣ ጾታ፣ የተዋዋይ ወገኖችን ልዩ ግንኙነት እና አጠቃላይ ተያያዥነት ያላቸው አኳኋኖች ጭምር መሰረት በማድረግ መወሰን ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1706/1/,1678/ሀ/,1809 | 55311 | ወ/ሮ ብርሃኔ አጥናፉ<br>እና<br>ኢንስፔክተር ዮሃንስ ተሲሳ | ህዳር<br>11/2003 | |
| 10. | ተዋዋይ ወገኖች በመካከላቸው ሊፈጠር የሚችለውን አለመግባባት በግልግል ዳኝነት ለመፍታት ከተስማሙ በኂላ አንደኛው ወገን ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ሌላኛው ተዋዋይ ስምምነቱ እንዲፈፀም ለፍ/ቤት የሚያቀርበው አቤቱታ የክስ ምክንያት የለውም ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1731<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33/2/, 231 | 56368 | ዶ/ር ሰለሞን ነጋሽ<br>እና<br>የባህርዳር ዩኒቨርስቲ | ህዳር<br>01/2003 | |
| 11. | የመያዣ ውል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ተደርጐ ለማስረጃነት ዋናውን ሰነድ ማቅረብ ባልተቻለ ጊዜ የዋናው ሰነድ ግልባጭ ስለመሆኑ ሥልጣን በተሰጠው አካል ተረጋግጦ የቀረበ የዋናው ሰነድ ኮፒ እንደ በቂ ማስረጃ ሊወሰድ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2011, 2008, 2009 | 56682 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>እነ አንዋር አብዱራህማን /ስምንት ሰዎች/ | ህዳር<br>14/2003 | |
| 12. | የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024/ረ/ እና 2023 ለውሃ ፍጆታ ክፍያ ተፈፃሚነት የሌላቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2023, 2024/ረ/ | 48857 | የአዲስ አበባ ውሀና ፍሳሽ ባለስልጣን<br>እና<br>የአዲስ አበባ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16/17 አስተዳደር ጽ/ቤት | ታህሳስ<br>12/2003 | |
| 13. | • የተሸጠለትን ነገር የተረከበ ገዢ የሽያጩን ዋጋ ወዲያውኑ የመክፈል ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>• ገዥ ለሻጭ /በሽያጭ/ ለማስረከብ በውል ከተስማማው መካከል የተወሰነውን ክፍል ያስረከበ መሆኑና ሻጭም በተረከበው መጠን ክፍያ ያልፈፀመ መሆኑ ለውሉ መፍረስ በቂ ምክንያት ሊሆን ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2278 | 49635 | ሂጦስ የገበሬዎች የህብርት ስራ ማህበር<br>እና<br>የምስራቅ ዱቄት ፋብሪካ | ጥር 23/2003 | |
| 14. | አንድን ዕቃ በውል የተረከበ ሰው የተረከበው ዕቃ ጉድለት አለው በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ በአንድ ዓመት ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2291, 2292, 2298/1/ | 55229 | ወ/ሮ መሃዳ ይመር<br>እና<br>የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የአርሲ ቅርንጫፍ | ጥር 09/2003 | |
| 15. | • የግንባታ ሥራን ለመንግስት ለመስራት ጨረታውን ያሸነፈ ሥራ ተቋራጭ ሥራውን ሙሉ በሙሉ ለሌላ ሥራ ተቋራጭ /ሰው/ በህጋዊ መንገድ ሊለቀቅ ወይም ሊያስተላልፍ የሚችልበት አግባብ<br>• ከአሰሪ ጋር ያልተደረገና ከሥራ ተቋራጭ ጋር የተደረገ የንዑስ ሥራ ተቋራጭነት ውልና የሚኖረው ውጤት<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3202/1/ እና /2/ 3205, 3206, 3244/1/, 2107 | 56252 | ተስፋዬ አበበ ሥራ ተቋራጭ<br>እና<br>ማዕረጉ ወርቁ ሥራ ተቋራጭ | ጥር 24/2003 | |
| 16. | • ውሎችን ህገ ወጥ ናቸው ወይም በህግ የተቀመጠውን መስፈርት አላሟሉም (Unlawful contracts or illegal contracts) በሚል ለመለየት የሚቻልበት አግባብ እና የሚያስከትሉት ውጤት<br>• በመያዣ ተይዟል በሚል ባለገንዘብ በሆነ ባንክ በሐራጅ ንብረቱ የተሸጠበት ሰው ባንኩ ንብረቱን ለመሸጥ መብት የለውም በሚል /ውሉ እንዲፈርስ/ የሚያቀርበው የመቃወም አቤቱታ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ | 43226 | ጌታ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | የካቲት<br>7/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 446,447<br>አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 6<br>አዋጅ ቁ. 216/92 | | | | |
| 17. | የከተማ ቦታ ውልን መሰረት በማድረግ በሊዝ የሚሰጥበትና ውሉ ሊቋረጥ የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 272/94 አንቀጽ 15/1/ /ለ/, 16 | 54596 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቦርድ<br>እና<br>ወ/ሮ ላቀች መንግስቴ | የካቲት 09/2003 | |
| 18. | ውልን መሰረት በማድረግ ቀብድ የተቀበለ ወገን የቀብዱን አጠፌታ በመክፈል ውሉ እንዲፈርስ ለመጠየቅ ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1885/2/ | 56794 | አቶ ሳህሉ ሙሉጌታ<br>እና<br>እነ አቶ ሰለሞን ኤፍሬም /ሦስት ሰዎች/ | የካቲት 07/2003 | |
| 19. | • ተዋዋይ ወገኖች ውል ባለመፈፀሙ አንዳቸው ለሌላቸው መቀጮ /ገደብ/ እንዲከፈል በማለት የሚደርሱበት ስምምነት ተፈፃሚ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ<br>• በውል በተወሰነ የገንዘብ ቅጣት ላይ የሚታሰብ የወለድ ክፍያ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1891, 1892/1/, 1889 | 58258 | ወ/ሮ ዮርዳኖስ ሃጐስ<br>እና<br>ወ/ሮ ሀይማኖት ተፈራ | የካቲት 21/2003 | |
| 20. | የእውቀት ሥራ /ግልጋሎት/ ውልን አሰሪ የሆነ ወገን በተናጠል ለማቋረጥ የሚችለው ባለሙያው ሥራውን ሙሉ በሙሉ አጠናቅቆ ለአሰሪው ከማስረከቡ በፊት ስለመሆኑና ባለሙያው ሥራውን አስመልክቶ በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችለው የሙያውን ደንቦች በመጣስ ጥፋት የፈፀመ እንደሆነ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2637/2/, 2636/2/ና/1/ | 60469 | ኮከብ ዱቄትና ፓስታ ፋብሪካ<br>እና<br>ሙሉ አለም የስራ አመራር አማካሪዎች | የካቲት 21/2003 | |
| 21. | ከመንግስት አስተዳደር መ/ቤት ጋር የሥራ ውል ያደረገ ወገን እንደውሉ ለመፈፀም ባልቻለ ጊዜ የአስተዳደር መ/ቤቱ ተዋዋዩ ለውል ማስከበሪያ (contract security) በሚል ካስያዘው ገንዘብ ላይ ውሉ ባለመፈፀሙ የደረሰበትን የጉዳት ኪሣራ መቀነስ የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 430/97 አንቀጽ 43<br>የመንግስት የግዢ መመሪያ ቁ. 117/5/ /ሀ-ሐ/ | 60951 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>ካንትሪ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር | ግንቦት 19/2003 | |
| 22. | • በሃዋላ የተላከን ገንዘብ ባንክ ለዕዳ ማስመለሻ በሚል ያለፍርድ መያዝ የማይችል ስለመሆኑ<br>• በፍትሐብሔር ግንኙነት እዳን ለማቻቻል ስለሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1838/1/, 1840, 1841 | 64203 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>አቶ መሐመድ ሙሳ /አራት ሰዎች/ | ግንቦት 15/2003 | |
| 23. | አንድን ስልጠና በአሰሪው ትብብር በውጪ አገር ተከታትሎ በምትኩ አገልግሎት ለመስጠት የተስማማ ሠራተኛ አስቀድሞ በውል የገባውን አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ባልተወጣበት ሁኔታ ሌላ /ተጨማሪ/ ስልጠና መጀመሩ በውሉ መሰረት ለመፈፀም ፈቃደኛ አለመሆኑን የሚያሳይና በኃላፊነት የሚያስጠይቀው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1731 | 46574 | ሐዋሳ ዩኒቨርስቲ<br>እና<br>እነ ዮናስ ካሣ /ሁለት ሰዎች/ | መጋቢት 09/2003 | |
| 24. | • ከመኪና ሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ ሻጭ ከመኪናው ጋር የተያያዙ አስፈላጊ ሰነዶችን ለገገር አሟልቶ ያስረከበ መሆኑ ከተረጋገጠ ገገር ስመ ሃብቱ በስሜ አልተዛወረም በሚል ምክንያት ብቻ ውሉ እንዲፈርስ የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>• ከመኪና ጋር በተገናኘ ስመ ሃብቱን ለማዞር አስፈላጊ ሁኔታዎችን አሟልቶ ስም እንዲዛወርለት ጥያቄ አቅርቦ መብቱ ሊረጋገጥለት ያልቻለ ሰው በሚመለከተው አካል ላይ በፍ/ቤት ክስ መስርቶ መብቱን ለማስከበር የሚችል ስለመሆኑ | 56569 | አቶ ዳዊት አሰፋ<br>እና<br>አቶ ተሻለ ደስታ | መጋቢት 23/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 25. | • በጽሁፍ እንዲደረጉ በህግ የተደነገጉ የውል አይነቶች ህጋዊና የተሟሉ ናቸው ለማለት መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች /መስፈርቶች/<br>• የቤት ሽያጭ ውል ምስክር ሳይኖርበት በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በመደረጉ ብቻ ህጋዊና የሚፀና ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723/1/, 1727/2/, 2877 | 57356 | ወ/ሮ መሠረት በቀለ<br>እና<br>ወ/ሮ ኤልሳ ሶሞኔሳ | መጋቢት 22/2003 | |
| 26. | ከግንባታ ሥራ ውል ጋር በተያያዘ የግንባታ ሥራ ፈቃድ የሚሰጠው ለባለቤት ወይም ለወኪሉ ስለመሆኑ<br>የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ ክትትልና ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 17, መመሪያ ቁ. 1/97 | 55359 | አቶ ተድላ ማሞ ጌታቸው<br>እና<br>እነ አቶ ፍስሐ ስመር /ሁለት ሰዎች/ | ሚያዝያ 21/2003 | |
| 27. | • ተዋዋይ ወገኖች ውል ለማድረግ ነፃ ቢሆኑም ህግ የወሰናቸውና የከለከላቸውን ነገሮች ባለመገንዘብ /ባለማክበር/ የሚደረጉ ውሎች የማይፀኑ እና የማይፈፀሙ ስለመሆናቸው<br>• በመንግስትና በህዝብ መሬት ላይ ግለሰቦች አንዱ ሰጪ ሌላው ደግሞ ተቀባይ በመሆን የባለቤትነት መብት ሊመሰርቱ የማይችሉ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1716 | 58157 | አቶ ዮሐንስ ታደሰ<br>እና<br>ወ/ሮ አማረች መንገሻ | ሚያዝያ 06/2003 | |
| 28. | ህጋዊ ባልሆነ የቤት ሽያጭ ውል አማካኝነት የተሰጠን ገንዘብ ለማስረዳት ህጉ የደነገገው ልዩ የማስረጃ አይነት የሌለና በማናቸውም ማስረጃ ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ/<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2472, 2001, 2019, 1808/2/, 1815, 2162, 2164 | 58636 | እነ አቶ ተሾመ ካሣ<br>እና<br>አቶ ቤዛ ኩሉ አዳም | ሚያዝያ 19/2003 | |
| 29. | • የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች በመያዣ (pledge) ለሌላ ሰው ተሰጥተዋል ለማለት የሚቻልበት ሁኔታ እና ውጤቱ<br>• መኪና በመያዣነት ተሰጥቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2825, 2832, 2830, 1186/2/, 2828, 1727, 2930, 2027, 2028, 2054 | 43582 | ራፒድ ኮንስትራክሽን ስራ ተቋራጭ ድርጅት<br>እና<br>ኦርቢስ ንግድና ቴክኒክ ክፍል ሊሚትድ | ሰኔ 28/2003 | |
| 30. | ጥሬ ገንዘብን በአደራ ከመስጠት ጋር በተያያዘ ክርክር የተነሳ እንደሆነ ገንዘቡ በአደራ መልክ መሰጠቱን ለማስረዳት ሊቀርብ ስለሚችል ማስረጃ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2742 2782 2779 | 60204 | አቶ ታደሰ ደምሬ<br>እና<br>አቶ ጌታሁን ለቻሞ | ሰኔ 14/2003 | |
| 31. | አንድን ሥራ ለሥራ ተቋራጭ የሰጠ የመንግስት መ/ቤት በራሱ ጥፋት ጉዳት አድርሶ ከሆነ ወይም የሥራ ተቋራጩን ሥራ መደበኛ አፈፃፀም ከባድ ያደረገበት እንደሆነ ለሥራ ተቋራጩ ኪሣራ የመክፈል ኃላፊነት የሚኖርበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3259 | 61110 | አል ናይል ቢዝነስ ግሩፕ ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና<br>የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን | ሰኔ 28/2003 | |
| 32. | የቤት ሽያጭ ውል ፈርሶ ወደ ነበርንበት እንድንመለለስና የከፈልኩት ገንዘብ ይመለስልኝ በሚል ክስ መስርቶ ፍ/ቤት ጥያቄውን በህግ ፊት የሚፀና ውል የለም በማለት ውድቅ ያደረገበት ወገን ያለአግባብ የተከፈለ ገንዘብ እንዲመለስልኝ በማለት የሚያቀርበው አቤቱታ ተገቢነት ያለውና ህጋዊ ስለመሆኑና በመጀመሪያው ክስ ተጠቃሎ መቅረብ የነበረበት ነው ሊባል የማይገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1815, 1880/2/, 2001-2019, 2162, 2164<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 216/2/3/ | 62134 | እነ ጣና ወ/ሰማያት<br>እና<br>ወ/ሮ አልማዝ አሰጋሽኝ | ሰኔ 28/2003 | |
| 33. | • የጠፋ ዕቃን ላገኘ ወይም ሌላ ነገር ለፈፀመ ሰው ሽልማት ይሰጠዋል ተብሎ በተለጠፈ /በተነገረ/ ማስታወቂያ ወይም በአደባባይ ሊታወቅ በሚችል ሌላ አይነት ማስታወቂያ መሰረት ዕቃውን አግኝቶ የመጣ ወይም የተባለውን ሥራ የፈፀመ እንደሆነ የተስፋ ቃሉን የሰጠው ሰው የተገለፀውን ሽልማት /የገባውን ቃል/ የመፈፀም ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>• በውል የተገባ ግዴታ ፍፁም የማይቻልና የማይሞከር ነው ለማለት ተዋዋይ ወገን ብቻ ሳይሆን | 62146 | ወ/ሪት ፍሬወይኒ ቴዎድሮስ<br>እና<br>ተርካንሬ ፕሮሞሽንና የማስታወቂያ ስራ ድርጅት | ሐምሌ 12/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ማንም ሰው ሊፈጽመው የማይችለው ግዴታ መሆን ያለበት ስለመሆኑ<br>• በአንድ ከተማ የሚገኝና መጠኑ ተለይቶ የታወቀ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ በሽልማት መልክ ለመስጠት በውል የተገባ ግዴታ ሊፈፀም የማይችል ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1715, 1741-1762, 1714, 1711, 1736, 1734, 1689 | | | | |
| 34. | የደንበኛን ጉዳይ /ክርክር/ በፍ/ቤት ክስ መስርቶ ሙያዊ አገልግሎት ለመስጠት የጥብቅና የውክልና ስልጣን የተሰጠው ጠበቃ በውል የገባውን ግዴታ በተገቢው ጊዜና ትጋት ለመወጣት አለመቻል በኃላፊነት የሚያስጠይቅና ለቅጣት የሚዳርግ ስለመሆኑ<br>ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 8/2//ለ/ 3<br>አዋጅ ቁ. 199/92 አንቀጽ 24/3/ /ለ-3/ | 66210 | አቶ ተስፋዬ ጉሳ<br>እና<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚ/ር | ሐምሌ<br>29/2003 | |
| 35. | • ከቤት ሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ የስም መዛወር የሚፈፀመው በመንግስት አስተዳደር ፊት እንጂ ሻጭ ነው የተባለው ወገን ሊፈጽመው የማይችልና ከህግ ወይም ከውል ይመነጫል ሊባል የማይችል ግዴታ ስለመሆኑ<br>• የስም ይዛወርልኝ አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለው ስለመሆኑ | 33945 | አቶ ሳልህ ሁሴን<br>እና<br>ደግፌ ደርቤ | ጥቅምት<br>20/2001 | |
| 36. | ስለ አስፈላጊ አደራ እና የማስረጃ አይነት<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2782,2800,2802,2472 | 64887 | አቶ አደም የሱፍ<br>እና አቶ አብዱሠላም ሙሐመድ | ሐምሌ<br>29/2003 | |
| 37. | የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1810/2/ ላይ የተመለከተው የይርጋ ገደብ ተፈፃሚ የሚሆነው ውል በፈቃድ ጉድለት ወይም በችሎታ ማጣት የተነሳ እንዲፈርስ ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1810 | 48012 | አቶ ኡመር ከድር<br>እና<br>አቶ በዳዳ ሰቦቃ /ሁለት ሰዎች/ | ጥቅምት<br>03/2003 | |
| 38. | ተዋዋይ የሆነ ወገን ወይም ጥቅም ያለው ማናቸውም ሰው ውሉ የተደረገበት ጉዳይ ወይም ምክንያት ከህግ ውጪ ነው ወይም ለህሊና ተቃራኒ ነው ወይም ለውሉ አፃፃፍ የተደነገገው ፎርም አልጠበቀም የሚል መከራከሪያ ምክንያት በማቅረብ ወሉ እንዲሰረዝ ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1808/2/ | 43379 | አበበ አበጋዝ<br>እና<br>ጥሩነሽ ተክሌ | ታህሳስ<br>25/2003 | |
| 39. | የንግድ መደብር ሽያጭ ውል በግዴታ እንዲፈፀም ለማድረግ የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2330, 2329, 1778/ | 44873 | አቶ ሰሚር ሱሩር<br>እና እነ ወ/ሮ ስንዱ ዱባለ | ጥር 13/2003 | |
| 40. | • በብድር ከተወሰደ ገንዘብ አከፋፈል ጋር በተያያዘ ብድር መክፈያ ጊዜው የዘገየ እንደሆነ ለአበዳሪው በኪሣራ መልክ የሚከፈለው ህጋዊ ወለድ ብቻ ስለመሆኑና ከዚህ ህጋዊ ወለድ በተጨማሪ በመቀጫ መልክ ለመክፈል የሚደረግ ስምምነት ፈራሽ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2006/2/, 2005/1/, 2489, 1889 | 59882 | ወ/ሮ አስገደች ዘርጋው<br>እና<br>አቶ አየለ ንዳኔ | የካቲት<br>21/2003 | |
| **ወንጀል** | | | | | |
| 41. | • ከ13 ዓመት እስከ 18 ዓመት ድረስ ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኝ ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ስለመሆኑ<br>• ድርጊቱን የፈፀመው ሠው ዕድሜ በዚሁ የእድሜ ክልል መገኘት የወንጀል ተጠያቂነቱን የማያስቀር ስለመሆኑ<br>የወ/ህ/ቁ. 626/1/, 211/1/, 48-56 | 46412 | የሐረሪ ክልል ዓቃቤ ሕግ<br>እና<br>ቦና አህመድ አሚን | ጥቅምት<br>30/2003 | |
| 42. | ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖር ሰዎችን ወደ ውጪ አገር በመላክ ወንጀል የተከሰሰን ሰው ጥፋተኛ ነው ለማለት እና ቅጣት ለመጣል የሚቻልበት አግባብ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 598/1/ /2/ | 54839 | አቶ ኢምራን ጉደሣ አብዲ<br>እና<br>የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ | ጥቅምት<br>30/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 43. | በህጋዊ መንገድ ወደ አገር ውስጥ የገባ የውጭ ምንዛሪን በህግ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ከአገር ይዞ ለመውጣት መሞከር የሚያስከትለው ኃላፊነት /ውጤት | 47935 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና ወ/ሮ እየሩሳሌም ወንዴ | ህዳር 30/2003 | |
| 44. | ከዋስትና መብት ጋር በተያያዘ ፍርድ ቤቶች የተከሳሽን የዋስትና መብት ለመንፈግ የተከሰሰባቸውን የወንጀል ክሶች ብዛትና ከባድነት መነሻ ሊያደርጉ ስለመቻላቸው<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.67/ሀ/ | 59304 | እነ አቶ አያሌው ተሰማ /ሦስት ሰዎች/<br>እና<br>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን | ህዳር 15/2003 | |
| 45. | በወንጀል የተከሰሰ ሰው የዋስትና መብት እንዲከበርለት ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ ትዕዛዙ ተነስቶ ዋስትናውን ሊከለከል ስለመቻሉ<br>የወ/መ/ሥ/ህ/ቁ. 74 | 59855 | ወ/ሮ ሊዊዛ ሮርቤታ<br>እና<br>አቃቤ ሕግ | ህዳር 28/2003 | |
| 46. | በሚያሽከረክረው መኪና ላይ ተሳፍሮ ሲሄድ የነበረ ሰው ወድቆ ለህልፈተ ህይወት የተዳረገበት ሾፌር በወንጀል ህግ ቁጥር 543/2/ ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 543/2/ | 52075 | አቶ ጌቱ ብርሃነ<br>እና<br>የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ | ታህሳስ 26/2003 | |
| 47. | • በወንጀል ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት ፍርድ የተሰጠ እንደሆነ ፍርድ የተሰጠበት ተከሳሽ የሚያቀርበው የይግባኝ አቤቱታ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችልበት አግባብ<br>• በይግባኝ ደረጃ ክስ የቀረበበት ተከሳሽ ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የተሰጠ የጥፋተኝነት ፍርድ እንደመጨረሻ ውሣኔ ተቆጥሮ በሰበር እንዲታረም ለማድረግ የማይቻል ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ሀ/ሥ/ሥ/ቁ. 193/2/, 197-202, 160, 164, 163, 195/2/ /ሀ/<br>የወንጀል ህግ ቁ. 522, 526<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 9, 10<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ | 57632 | ሰማኸኝ በለው<br>እና<br>የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ | ታህሳስ 25/2003 | |
| 48. | ዓቃቤ ሕግ ወንጀል ፈጽሟል በሚል የተጠረጠረና ምርመራ የተደረገበትን ሰው ተከሳሽ ከሚሆን ይልቅ ምስክር ቢሆን የተሻለ ነው ብሎ ካመነ ይህንኑ ለማድረግ የሚከለክለው ህግ የሌለ ስለመሆኑ | 57988 | ዮርዳኖስ አባይ አሰፋ<br>እና<br>የፌዴራል አቃቤ ሕግ | ጥር 10/2003 | |
| 49. | • ከወንጀል ጉዳዮች የክስ ሂደት ጋር በተገናኘ ዓቃቤ ሕግ ሊያከናውናቸው የሚገቡ ተግባራትና ኃላፊነቶች<br>• የጥፋተኛነት ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ ፍርድ ቤቶች ተከሳሽ በሆነ ወገን ላይ ቅጣት ሊጥሉ ስለሚችሉበት ሥርዓት /አግባብ/<br>የወ/መ/ሀ/ሥ/ሥ/ቁ. 136/1/, 148/1/ ,149 | 47755 | የፌዴራል አቃቤ ህግ<br>እና<br>አቶ ሚፍታህ ኑሪዲን | ግንቦት 05/2003 | |
| 50. | • በግድያ ወንጀል የተከሰሰ ሰው የወንጀል ቁጥር 540 ወይም 541ን መሰረት በማድረግ ጥፋተኛ አድርጐ ለመወሰን የወንጀል ድርጊቱ አፈፃፀምን እንዲሁም መነሻ ሁኔታዎች በአግባቡ መመልከት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ<br>• የወንጀል ህግ ቁጥር 78 "ን" ተፈፃሚ ለማድረግ ሊሟሉ ስለሚገባቸው መስፈርቶች<br>• ህጋዊ መከላከልን በማለፍ የተፈፀመ የነፍስ ግድያ በወንጀል ህግ ቁጥር 541 የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 78, 540, 541 | 57446 | ሃለቃ ገ/እግዚያብሔር ኃይሉ<br>እና<br>የኦሮሚያ ክልል ዓ/ሕግ | ግንቦት 19/2003 | |
| 51. | የወንጀል እና የፍ/ብሔር ክሶች ተጣምረው ሊታዩ የሚችሉት በወንጀል ህግ ቁጥር 101 አግባብ ብቻ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 101 | 59045 | የስልጤ ዞን ምርመራና ክስ ዓ/ሕግ<br>እና<br>እነ አቶ ጌታቸው አስራት /አምስት ሰዎች/ | ግንቦት 16/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 52. | በወንጀል ድርጊት በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ ሰው ከጉዳቱ በኂላ ተጉጂውን ወደ ህክምና ቦታ የወሰደው መሆኑ ብቻ በድርጊቱ የተፀፀተ መሆኑን ያሳያል በሚል ቅጣትን ከመነሻው በታች በመወረድ ቀልሎ እንዲወሰን ለማድረግ የሚያስችል ስላለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 543/3/, 59/1/, 575/2/, 82/1/<br>የትራንስፖርት ማሻሻያ ደንብ ቁ. 279/56 አንቀጽ 35 | 62332 | አቶ ዘለቀ ካሣዬ<br>እና<br>የፌዴራል ዓ/ሕግ | ግንቦት 29/2003 | |
| 53. | በወንጀል ተከስሶ የቀረበ ተጠርጣሪ በፍ/ቤት በሰጠው የእምነት ቃል መሰረት ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት ከተጣለበት በኂላ በተሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለማለት የማይችል ስለመሆኑ | 63741 | አቶ መሐመድ ሰኢድ አሊ<br>እና<br>የፌዴራል ዓ/ሕግ | ግንቦት 15/2003 | |
| 54. | ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ በሥር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ እውነታ የተጠቀሰውን ወንጀል የሚያቋቁም መሆን አለመሆኑ ጉዳይ የህግ ጭብጥ በመሆኑ በሰበር ችሎት ሊመረመር የሚችል ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 675/1/ | 64813 | ያሲን አሕመድ መሐመድ<br>እና<br>የፌዴራል ዓ/ሕግ | ግንቦት 17/2003 | |
| 55. | • የመወሰን ስልጣን የሌላቸውና የሙያ ግልጋሎት የመስጠት ኃላፊነት ብቻ ያላቸው ሰዎች /ሰራተኞች/ በወንጀል ጉዳይ በኃላፊነት ሊጠየቁ የሚችሉበት አግባብ<br>• የተቀጠረበትን የሙያ ሥራ በጥንቃቄና በአግባቡ አለመፈፀም በአዋጅ ቁ. 214/74 በስልጣን ያለአግባብ መገልገል የሙስና ወንጀል ያስጠይቃል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ | 43049 | አረጋኸኝ መርዕድ<br>እና<br>የፌ/ስ/ፀ/ሙ/ኮ/ዓ/ህግ | ግንቦት 26/2002 | |
| 56. | አንድ ተከሳሽ በወንጀል ህግ ቁጥር 427/3/ መሰረት የሙስና ወንጀል ፈጽሟል በሚል ሊጠየቅ የሚችልበት አግባብ<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 427/1/, /3/ | 55047 | አቶ ነብይ በድሩ ሽፋ<br>እና<br>የፌዴራል ሥ/ፀ/ሙ/ኮሚሽን ዓ/ህግ | መጋቢት 05/2003 | |
| 57. | ፍ/ቤት በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰን ሰው በተመለከተ አስቀድሞ የፈቀደውን የዋስትና መብት በራሱ አነሳሽነት ወይም በማናቸውም ባለጉዳይ አመልካችነት አዲስ ነገር ተከስቷል ብሎ ካመነ ዋስትናው እንዲነሳ ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችል ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 74 | 61275 | አቶ ኤልያስ ገረመው<br>እና<br>የኢት/ገ/ጉ/ባ/ዓ/ህግ | ሚያዝያ 18/2003 | |
| 58. | • በከባድ የሰው መግደል ወንጀል ተከስሶ ጥፋተኛ መሆኑ የተረጋገጠ ተከሳሽ ስለሚጠየቅበት አግባብ<br>• የተመሰረተበት ክስ በዓቃቤ ሕግ በኩል እንደክሱ አመሰራረት ያልተረጋገጠበት ቢሆንም ተከሳሹ የቀረበው ማስረጃ ከቀረበበት ክስ ባነሰ የወንጀል ድርጊት የሚያስጠይቅ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ተከሳሹ በነፃ እንዲሰናበት ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የማይኖር /የሌለ/ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 32/1/ /ሀ-ለ/, 539/1/ /ሀ/, 84, 86, 40, 445, 88<br>የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 113/2/<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 40, 445 | 45595 | የኦሮሚያ ክልል ዓቃቤ ህግ<br>እና<br>እነ ኢዮስያስ አበራ ገ/ሚካኤል /አምስት ሰዎች/ | ሰኔ 17/2003 | |
| 59. | • በወንጀል ተከስሶ ጥፋተኛነቱ የተረጋገጠበት ተከሳሽ ላይ የሚጣለውን የቅጣት አይነትና መጠን ለመወሰን ፍ/ቤቶች በህጉ ውስጥ ተካትተው የሚገኙትን የቅጣት ማቅለያ እና ማከበጃ ምክንያቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚችሉበት አግባብ<br>• የሞት ቅጣት ሊተላለፈ የሚችልበት አግባብ<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 117, 32/1//ሀ-ለ/, 539/1//ሀ/, 84/1//ሀ-ሠ/, 183, 179, 180, 182, 88/2/, 87/1/ | 47831 | እነ መስታወት ጌታነህ /አራት ሰዎች/<br>እና<br>የፌዴራል ዓቃቤ ህግ | ሰኔ 03/2003 | |
| 60. | “የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት” በሚል በወንጀል ህጉ ውስጥ የተመለከተውን የወንጀል | 67947 | አቶ አዱኛ አንበሉ | ሰኔ 15/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ድርጊት ለማቋቋም ቼኩ ለክፍያ ባንክ በቀረበበት ጊዜ በቂ ስንቅ የሌለው መሆኑን /ያለመኖሩ/ ማረጋገጥ ብቻ በቂ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 693/1/ | | እና<br>የፌዴራል አቃቤ ህግ | | |
| 61. | • በህጉ በጠቅላላ የቅጣት ማቅለያነት የተመለከተን ምክንያት ወንጀሉን ለማቋቋም የቀረበ በሆነ ጊዜ ፍ/ቤቶች ይህንን ምክንያት እንደ አንድ የቅጣት ማቅለያነት ሊጠቀሙበት የማይችሉ ስለመሆኑ<br>• ፍርድ ቤቶች በህጉ ለዳኞች የሚሰጠውን አመዛዝኖ ቅጣትን የመወሰን ስልጣን ሲጠቀሙ በቅጣት አወሳሰን ረገድ ህጉ ያስቀመጣቸውን መሰረታዊ መርሆዎች ሊጥሱ የማይገባ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 82/2/, 189,86, 180, 179, 182, 184, 82/1/, 88/2/ | 59356 | የፌዴራል ዓ/ህግ<br>እና<br>በሪሁን ፍቃዱ | ሰኔ 03/2003 | |
| 62. | በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ ክስ ከቀረበበት ሰው ጋር በተገናኘ በሚካሄድ የቅድመ ክስ ሂደት ጉዳዩን የሚያየው ፍ/ቤት እንደቀረበው የወንጀል አይነት በመመርመር ወደ ዋናው ክስ የመስማት ሂደት እንዲገባ በሚል ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችል ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 419<br>አዋጅ ቁ. 434/97 አንቀጽ 36/1//2/ | 57938 | እነ አቶ አደም አብዱ /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>የፌዴራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዓ/ህግ | ሐምሌ 14/2003 | |
| 63. | • በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ ክስ የቀረበበት ሰው በዋስትና ወረቀት ለመለቀቅ የሚያቀርበውን ጥያቄ ፍ/ቤቶች ተከሳሹ በቀረበበት የሙስና ወንጀል ክስ ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ ሊጣልበት የሚችለውን የቅጣት ጣሪያ መነሻ በማድረግ ውሣኔ ሊሰጡበት የሚገባ ስለመሆኑ<br>• ተከሳሹ የተከሰሰበት ወንጀል ከአስር ዓመት በላይ በእስራት ሊያስቀጣ የሚችል በሆነ ጊዜ በዋስትና ወረቀት እንዲለቀቅ ሊፈቀድ የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 434/97 አንቀጽ 4/1/<br>አዋጅ ቁ. 239/93 አንቀጽ 2<br>አዋጅ ቁ. 236/93<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 676/1/ | 63344 | የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/የሥ/ፀ/ሙ/ኮሚሽን<br>እና<br>እነ ላሉ ሰይድ አክሊታ | ሐምሌ 28/2003 | |
| 64. | ውልን /ስምምነትን/ መሰረት ባደረገ ግንኙነት አንድን ንብረት ወስዶ በውሉ መሰረት ለመመለስ ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል በሚል የወንጀል ክስ ሊቀርብበት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 23/2/, 24, 57, 58 | 65054 | ብሩክ ሚካኤል<br>እና<br>የፌዴራል ዓ/ህግ | ሐምሌ 14/2003 | |
| 65. | • ዓቃቤ ህግ በወንጀል በተከሰሰ ሰው ላይ የሚያቀርበው የወንጀል ክስ የወንጀሉን ዝርዝር ሁኔታ መያዝ እንዳለበት በተለይም ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ለይቶ አውቆ መልስ ለመስጠት እንዲችል ክሱ ወንጀሉንና ሁኔታውን መግለጽ ያለበት ስለመሆኑ<br>• አንድ ሰው ከሌሎች ሰዎች ጋር የወንጀል ተካፋይ ሆኗል የሚባለው በወንጀሉ አፈፃፀም የግዙፍ ተግባር የሃሳብና የህግ ሁኔታዎችን መተላለፍ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 112<br>የወንጀል ህግ ቁ. 32/1/ 23/2/ | 57644 | መ/ር አወት ተካ<br>እና<br>የትግራይ ዓ/ህግ | ሐምሌ 25/2003 | |
| 66. | ተጨማሪ ማስረጃን ከመቀበል ጋር በተያያዘ በወንጀል ህግ ቁጥር 143/2/ ሥር የተመለከተው ድንጋጌ ፍ/ቤቱ ለፍትህ አሰጣጥ ተገቢ ነው ብሎ ሲያምን ትዕዛዝ ሊሰጥበት የሚችል ስለመሆኑ በፈቃጅነት (permissive) የተቀመጠ እንጂ አስገዳጅ የህግ ድንጋጌ ስላለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 143/2/ | 66767 | አቶ ተስፋዬ ተሾመ<br>እና<br>የፌዴራል ዓ/ህግ | ሐምሌ 28/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 67. | በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰ ሰው የሚያነሳው የጤና ችግር ከዋስትና መብት አኳያ ሲታይ ስላለው ህጋዊ ጥበቃ | 68407 | ወ/ሮ ውልታ ደሳለኝ<br>እና<br>የኦሮሚያ ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዓ/ህግ | ሐምሌ 14/2003 | |
| 68. | • ወንጀልና የወንጀል ቅጣት የእያንዳንዱን ጥፋተኛ ግላዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ውሣኔ ሊሰጥባቸው የሚገባ ስለመሆኑ<br>• የጉምሩክ ህግን በመተላለፈ ጥፋተኛ የተባሉ ሰዎች /ተከሳሾች/ ላይ የሚጣለው የገንዘብ መቀጮ በእያንዳንዱ ጥፋተኛ ላይ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 41, 32/1/ሀ/<br>አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 73/1/<br>አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 73/1/ | 48956 | እነ ወ/ሮ ፍኖተ ፃድቅ አበራ<br>እና<br>የጉምሩክ ዓ/ህግ | መጋቢት 10/2002 | |
| 69. | አንድ ሰው በወር ደመወዝ ከሚያገኘው ገቢ ውጪ ሌላ ህጋዊ የገንዘብ ምንጭ እንዳለው ለማስረዳት ባልቻለበት ሁኔታ በሚሊዮን የሚቆጠር ሀብትና ንብረት ባለቤት መሆኑ ምንጩ ያልታወቀ ገንዘብ ይዞ በመገኘት የሙስና ወንጀል የሚያስጠይቀው ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 419 | 58514 | አቶ ሃንካራ ሃርቃ ሃያሞ<br>እና<br>የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ/ሥ/ፀ/ሙ/ኮ/ዓ/ህግ | ጥር 09/2003 | |
| 70. | የንግድ ፈቃድ መብትን መጣስ በአዋጅ ቁ. 501/98 መሰረት የወንጀል ተጠያቂነትን ስለሚያስከትልበት አግባብ | 69899 | እነ ዮሴፍ ሀይሉ ጠቅላላ ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ | ሐምሌ 29/2003 | |
| 71. | በአሽከርካሪነት ሥራው ማድረግ የነበረበትን ጥንቃቄ ሳያደርግ ቀርቶ በሌላ ሰው ላይ የሞት አደጋ ያደረሰ ሰው በወንጀል ህግ ቁጥር 543/2/ የሚጠየቅ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 543/1/, /2/, /3/, 59/1/<br>የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 113 | 55649 | ኤልያስ ዲጋ<br>እና<br>የፌዴራል ዓ/ሕግ | መጋቢት 06/2003 | |
| 72. | የወንጀል ክስ ቀርቦ ተከሳሹ እንዲከላከል በሚል በፍ/ቤት ብይን የተሰጠ መሆኑ ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ እንደተሰጠበት በመቁጠር የሰበር አቤቱታ ሊቀርብበት የማይቻል ስለመሆኑ | 59537 | አነዚር ኢብራሂም<br>እና የቤ/ጉ/ክ/ስ/ፀ/ሙስና ኮሚሽን | ሚያዝያ 19/2003 | |
| 73. | አንድ የወንጀል ድርጊት በእርግጥም ተጀምሯል /ተፈጽሟል/ ለማለት የሚቻለው የተደረገው ተግባር በማያጠራጥር ሁኔታና በቀጥታ ወንጀሉን ለመፈፀም ወደታሰበለት ግብ ለማድረስ የተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲቻል ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 27/1/ 540 555/ሀ//ለ/ | 63727 | ፋሲል ታምራት<br>እና<br>የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ መርማሪ ከሳሽ | ሰኔ 13/2003 | |
| **ፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት** | | | | | |
| 74. | በፍ/ቤቶች ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ትዕዛዝ የተሰጠው ተከራካሪ ወገን ጥሪ ተልኮለት ቀርቦ መልሱን አልሰጠም በሚል ምክንያት ከክርክሩ ውጪ እንዲሆን የሚሰጥ ትዕዛዝ በክርክሩ ውስጥ ያሉ ሌሎች ወገኖችን መብት የሚያጣብብና የሥነ-ሥርዓት ህግን የሚጥስ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70, 41/3/, 199 | 53844 | የወ/ሮ ቅጅነሽ አነስታል ወራሾች /ሦስት ሰዎች/<br>እና<br>የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ስራና ከተማ ልማት ቢሮ | ጥቅምት 18/2003 | |
| 75. | በፍርድ ለሌላ ሰው የተላለፈ ንብረት የእኔ ነው በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 418, 421, 455 | 50835 | እነ አቶ ምናሴ ኢትሶ /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>ወ/ሮ ፋንታዬ ተረፈ | ጥቅምት 16/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 76. | • የግልግል ዳኝነት ጉባኤ እንደ ፍ/ቤት የዳኝነት አካሄድ ሁልጊዜ ጥብቅ የሆነ የሙግት ሥርዓትን ተከትሎ ጉዳዩን ማየት የሌለበት ስለመሆኑ<br>• የግልግል ጉባኤ ጉዳዩን ለማየት ሊከፈል የሚገባውን የገንዘብ መጠን በተመለከተ ተገቢ ነው ብሎ ያመነበትን ያህል ሊወስን ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 318/5/, 317/1/<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3345 | 52942 | አቶ ገብሩ ኮሬ<br>እና<br>አቶ አመዲዮ ፌዴሬቼ | ጥቅምት<br>18/2003 | |
| 77. | ተከራካሪ ወገኖች የሚሟገቱበት ጉዳይ የልዩ አዋቂ ምስክርነትና ማብራሪያ የሚያስፈልገው ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ፍርድ ቤቶች ይህ እንዲፈፀም ማድረግ ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136/1/ | 48608 | ወጋገን ባንክ አ.ማ<br>እና<br>አቶ ሃብቶም ረዘነ | ህዳር<br>02/2003 | |
| 78. | • ተከራካሪ ወገኖች እንዲሰሙላቸው የሚቆጥሯቸው የሰው ማስረጃዎች የማስረዳት ብቃት ሊታወቅ የሚችለው ቃላቸው ከተሰማ በኂላ ስለመሆኑ<br>• የተቆጠሩ ማስረጃዎች የማስረጃ አግባብነትና ተቀባይነት መርህ (relevancy and admissibility) ካልከለከለ በስተቀር በዝርዝር ሊሰሙ የሚገባ ስለመሆኑ<br>• በሰው ማስረጃነት የተቆጠረ ኦዲተር በኦዲት ሪፖ`ርት ላይ ከተመለከተው ውጪ /የተለየ/ ሊያስረዳ አይችልም በሚል ምክንያት ሊሰማ አይገባም ሊባል የማይገባ ስለመሆኑ | 49502 | የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት<br>እና<br>እነ መርዕድ ተፈራ /ስድስት ሰዎች/ | ህዳር<br>01/2003 | |
| 79. | • መጥሪያ በጋዜጣ ጥሪ ሊደረግ የሚገባው ሌሎች አግባብነት ያላቸው የመጥሪያ አላላክ መንገዶች ቅደም ተከተላቸውን በጠበቀ መልኩ ከተከናወኑ በኂላ ስለመሆኑ<br>• መጥሪያ በአግባቡ ደርሷል ለማለት የሚላክለት ሰው ስም በተሟላ ሁኔታ ተገልጾ መላክ ያለበት ስለመሆኑ<br>• መጥሪያ በህጉ አግባብ እንዲደርሰው ሳይደረግ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ትዕዛዝ የተሰጠበት ወገን ትዕዛዙ እንዲነሳለት የሚያቀርበው አቤቱታ ተገቢነት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 94-110, 7870/ሀ/ | 53113 | እነ ወ/ሮ አበበች በጅጋ /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>ዶ/ር ተስፋዬ አካሉ | ህዳር<br>03/2003 | |
| 80. | በዋናው ክርክር ላይ በተሰጠ ፍርድ መብቱ የተነካበት ሰው በፍርድ አፈፃፀም ወቅት መብቱ ከተነካበት ሰው በተለየ ሥነ ሥርዓት ተቃውሞ ማቅረብ የሚገባው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 418, 419 | 53607 | የምጥን መንደር መኖሪያ ቤቶች የህብረት ስራ ማህበር<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ባየች አይገምት /ሦስት ሰዎች/ | ህዳር<br>14/2003 | |
| 81. | አስቀድሞ የተሰጠን ውሣኔ ለማስነሳት መቃወሚያ ማቅረብ የሚችል ወገን በክርክሩ መግባት የሚገባው ሆኖ ነገር ግን ተካፋይ ያልነበረ እንደሆነ ባልተካፈለበት ክርክር የተሰጠውን ፍርድ መቃወም የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 41 | 42714 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፍትህና ህግ ጉዳዮች ቢሮ<br>እና እነ የሸቀጣ ሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት /ሦስት ሰዎች/ | ህዳር<br>08/2003 | |
| 82. | ከሳሽ የሆነ ወገን ያቀረበው ክስ ውድቅ በተደረገበት ሁኔታ ተከሳሽ የዳኝነት ክፍያውን ለከሳሽ እንዲከፍል የሚደረግበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 215, 462 | 46281 | ወ/ሮ አበባዬ አቢ ደራወርቅ<br>እና<br>ይገረም ፈዬ | ታህሳስ<br>28/2003 | |
| 83. | • ልዩ ዕውቀትና ክህሎትን መሰረት በማድረግ አንድ ጉዳይ ተመርምሮ የተሰጠ የሙያ አስተያየት ሊስተባበል የሚችለው በጉዳዩ ላይ የተሻለ የሙያ እውቀትና ክህሎት ባለው ባለሙያ ጉዳዩን መርምሮ በሚሰጠው አስተያየት ስለመሆኑ<br>• አንድን ሰው ለማጓጓዝ ውል የተዋዋለ ሰው በጉዞ ወቅት በተጓዡ ላይ ለደረሰ ጉዳት ሊከፍል የሚገባው የካሣ መጠን ከብር 40,000 መብለጥ የሌለበት ስለመሆኑ | 47960 | አቶ ታከለ ባልቻ<br>እና<br>ወ/ሮ አዜብ ፀጋዬ | ታህሳስ<br>12/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | • የጉዳት ካሣ መጠኑ ከብር 40,000 ሊበልጥ የሚችለው በንግድ ህግ ቁ. 599 የተመለከተው መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136/1/<br>የንግድ ህግ ቁ. 597/1/ | | | | |
| 84. | • የበላይ ፍርድ ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሊሽር የሚችለው ህጋዊና በቂ ምክንያት ሲኖረው ብቻ ስለመሆኑ<br>• በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች የበላይ ፍርድ ቤት ውድቅ ለማድረግ የሚችለው የማይቀበልበትን ምክንያት በውሣኔው ላይ በግልጽ በማስፈር እንጂ በደፈናው "በተገቢው አልተረጋገጡም" የሚል ምክንያት በመስጠት ብቻ ስላለመሆኑና በዚህ መልክ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን በመሻር የሚሰጥ ፍርድ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 341 እና ተከታዮቹ | 58540 | ኪ.ድስ ሊንክ ኢንተርናሽናል<br>እና<br>ሲስተር ገነት ወንድሙ | ጥር 27/2003 | |
| 85. | ሁለት ተከራካሪ ወገኖች አንደኛው በሌላኛው ላይ የፍርድ ባለመብት ሆነው የአፈፃፀም አቤቱታው በተለያዩ ፍርድ ቤቶች በቀረበ ጊዜ በፍርድ የበሰለው ገንዘብ በመቻቻል እንዲፈፀም በሚል በአንድ ፍርድ ቤት ተጠቃሎ እንዲታይ ለማድረግ የሚሰጥ ትዕዛዝ አግባብነት ያለውና ህጋዊ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 397 | 57378 | ወ/ሮ አስቴር አርአያ<br>እና<br>ወ/ሮ አምሳለ ፀሐይ | ጥር 23/2003 | |
| 86. | በባንክ በኩል ከተላከ ገንዘብ ጋር በተገናኘ በአግባቡ ለተላከለት ሰው አልደረሰውም በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በላኪው ወይም በተላከለት ሰው ስም ክስ ቀርቦ ከተወሰነ በኋላ በሌላኛው /በላኪው/በተላከለት/ሰው/ ስም የሚቀርብ አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥህ/ቁ. 5 የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 | 51223 | ዳሽን ባንክ አ.ማ<br>እና<br>ወ/ሮ ሀመልማል መኮንን | የካቲት 24/2003 | |
| 87. | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418 አቤቱታ እንዲያቀርብ ተፈቅዶለት ክርክር ተካሂዶ ውሣኔ የተሰጠበት ወገን በድጋሚ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 447 "ን" መሰረት በማድረግ የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418, 447, 354 | 53421 | ወ/ሮ ወርቅነሽ ዋሴ<br>እና<br>አቶ ባንተይርጋ ወርቁ | የካቲት 22/2003 | |
| 88. | በመጀመሪያ በቀረበ የክስ መከላከያ መልስ ያልተካተተን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መልስ እንዲሻሻል በሚል ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መነሻነት ተካትቶ ሲቀርብ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 91, 244<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1856 | 55973 | ወ/ሮ አፀደ ኤዶ<br>እና<br>አቶ ትኩ ዋቅሹም | የካቲት 21/2003 | |
| 89. | • ሌሎች ሰዎች ተከራካሪ በሆኑበት ጉዳይ ንብረትን አስመልክቶ በፍርድ ቤቱ የተሰጠ የማገጃ ትዕዛዝ ይነሳልኝ በሚል አቤቱታ አቅርቦ ውድቅ የተደረገበት ሰው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሰረት ፍርድ ከተሰጠ በኋላ የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ<br>• አንድ ክርክር መጀመሩን ያወቀ ወገን የክርክሩን ውጤት ጠብቆ መብቱን የሚነካበት ሆኖ ባገኘው ጊዜ ከውሣኔው በኋላ የሚያቀርበው አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሰረት ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 153/3/, 418-421 | 56795 | አቶ ሙባረክ ከድር<br>እና<br>እነ ሚስተር ኑዋምባ ሲርር /አምስት ሰዎች/ | የካቲት 21/2003 | |
| 90. | ፍርድ ቤቶች ከውሣኔ ሊደርሱ የሚገባው የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት፣ የመከላከል ብሎም በእኩልነት መርህ የመዳኘት መብት በጠበቀ መልኩ ስለመሆኑ | 52546 | እነ አቶ በቀለ አማረ /ሁለት ሰዎች/<br>እና ወ/ሮ ብዙነሽ ግርማ | ታህሳስ 13/2003 | |
| 91. | ክስ ለመስማት ቀጠሮ ከተሰጠ በኋላ ያልቀረቡ ከሳሾችን ከክርክሩ ውጪ እንዲሆኑ በማለት ትዕዛዝ | 55078 | ማበርፋይድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር | ታህሳስ | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የሰጠ ፍ/ቤት /ችሎት/ በራሱ ተነሳሽነት አስቀድሞ የሰጠውን ትዕዛዝ በማንሳት ከክሱ ውጪ የሆኑትን ከሳሾች የክሱ አካል በማድረግ የሚሰጠው ውሣኔ ከሥነ ሥርዓት ህግ ውጪ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 73, 74, 78 | | እና<br>እነ አሸናፊ አለሙ /ዘጠኝ ሰዎች/ | 25/2003 | |
| 92. | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 377 ተፈፃሚ ሲደረግ የሚችልበት አግባብ | 52193 | የኮንስትራክሽን እና ቢዝነስ ባንክ አ.ማ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ መድህኒት ሃይሉ /ሁለት ሰዎች/ | ታህሳስ<br>27/2003 | |
| 93. | ክርክሩ በሌለበት እንዲቀጥል የተደረገበት ተከሳሽ በተከታዩ ቀነ ቀጠሮ ቀርቦ በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ ያለመቅረቡን ካስረዳ መከላከያውን አቅርቦ የመከራከር መብት የሚኖረው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 72, 78/1/ | 61846 | ወ/ሮ ፋጡማ ጀማል<br>እና<br>ወሮ ፋጡማ አስማን | ግንቦት<br>29/2003 | |
| 94. | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 እና 418 መሰረት በተሰጠ ፍርድ ላይ ተቃውሞ የሚቀርብበት ሥርዓት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 359, 418, 222, 223, 137/3/ | 55842 | የኦሮሚያ ከተሞች ፕላን ኢንስቲትዮት<br>እና<br>እነ አቶ ካሣ ጭርሳ /አራት ሰዎች/ | መጋቢት<br>23/2003 | |
| 95. | በፍ/ብሔር ክርክር ፍ/ቤት አንድን ጉዳይ /ጭብጥ/ ለማስረዳት የሚቀርብን የሙያ ምስክርነት (expert witness) ውድቅ በማድረግ ባለሙያ ባልሆኑ ምስክሮች የተሰጠ የምስክርነት ቃልን ሊቀበል የሚችለው ይህን ለማድረግ የሚያስችል በቂ እና አሳማኝ ምክንያት ሲኖር ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136/1/ | 65930 | የሱ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>እነ አቶ ደጀኔ በቀለ /ሁለት ሰዎች/ | ሰኔ 14/2003 | |
| 96. | ከኢትዮጵያ ውጪ በሚገኝ ፍርድ ቤት የተሰጠ ፍርድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች እውቅና ሊሰጠው ወይም ተቀባይነት ሊኖረው የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5, 456-461 | 59953 | ወ/ሮ አለምነሽ አበበ<br>እና<br>አቶ ተስፋዬ ገሰሰ | ሰኔ 02/2003 | |
| 97. | • በህግ የተቀመጠው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በኂላ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ እንዲፈቀድ የሚቀርብ አቤቱታ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ<br>• ይግባኙ በጊዜው ሊቀርብ ያልቻለው የባለጉዳዩ ጠበቃ፣ነገረፈጅ ወይም ወኪል የሆነው ሰው ባለመቅረቡ ወይም ከነዚህ ሰዎች ጋር በተያያዘ በተከሰተ ጉድለት መሆኑ ከታወቀ የማስፈቀጃ አቤቱታው በበቂ ምክንያት የተደረገ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 326/2/ /1/ 323/2/ 325 | 57360 | አፍሪካ ኢንሹራንስ አ.ማ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ሐምሌ<br>15/2003 | |
| 98. | በአንድ በመካሄድ ላይ ባለ የፍርድ ቤት ክርክር ተሳታፊ ለመሆን ጥያቄ አቅርቦ በብይን ውድቅ የተደረገበት እና በሌላ መዝገብ ክስ መስርቶ መብቱን እንዲያስከብር በሚል ትዕዛዝ የተሰጠበት ወገን በዚህ ትዕዛዝ መሰረት አዲስ መዝገብ በማስከፈት ወይም በሌላ መዝገብ በመግባት የክርክር ተሳታፊ ከመሆን የሚያግደው ነገር የሌለ ስለመሆኑ ወይም ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 | 62173 | ወ/ሪት ቤተልሄም ታደሰ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ሃና ታደሰ /ሦስት ሰዎች/ | ሐምሌ<br>11/2003 | |
| 99. | ግልጽነት የጐደለው ክስ /አቤቱታ/ በቀረበ ጊዜ ክሱ በተከራካሪዎች አነሳሽነት ወይም ፍ/ቤቱ በራሱ ክሱ እንዲሻሻል ሳይደረግ በደፈናው የቀረበን የይገባኛል ጥያቄ ላይ የሚሰጥ ፍርድ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 91/1/ | 63699 | አፔኖ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ድርጅት<br>እና<br>አቶ ጥሩነህ ይመር | ሐምሌ<br>15/2003 | |
| 100. | ፍ/ቤቶች በባንክ ለተሰጠ ብድር መያዣነት የተሰጠ ንብረትን በአዋጅ ቁ. 97/90 ባንኩ ሲረከበው በብድሩ ገንዘብ እና በንብረቱ ወቅታዊ የዋጋ ግምት መካከል ያለውን ልዩነት ማስላት አስፈላጊ | 61227 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ<br>እና | ሐምሌ<br>14/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | መሆኑን ባመኑ ጊዜ ይህንን ለማድረግ ልዩ የሂሳብ አዋቂ (expert witness) በመመደብ ለጉዳዩ እልባት ሊሰጡ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136/1//2/ | | እነ አቶ ኃይሉ አምቦ /ሁለት ሰዎች/ | | |
| 101. | • በፍርድ ቤት የእግድ ትዕዛዝ የተሰጠበትን የማይንቀሳቀስ ንብረት በተመለከተ የእግዱ ትዕዛዝ ተጥሶ ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት በተደረገ የሽያጭ ውል ለሦስተኛ ወገን በተላለፈ ጊዜ ሊኖር ስለሚችል ውጤት<br>• እግዱ ተጥሶ በተከናወነው ተግባር መብቱ የተጐዳበት ሰው የእግዱን ትዕዛዝ በጣሰው ወይም እንዲጣስ ምክንያት በሆነው አካል ላይ ተገቢውን አቤቱታ በማቅረብ መብቱን ለማስከበር የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 156<br>አዋጅ ቁ. 334/95 አንቀጽ 15/2/<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1204, 1206, 1184, 1185, 1195 | 61637 | ዶ/ር አልሑሴን በድልገዋድ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ገነት ሐድጐ /ሁለት ሰዎች/ | ሐምሌ<br>11/2003 | |
| 102. | በውጭ አገር የተሰጠ ፍርድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት እውቅና ካልተሰጠው በስተቀር በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የቀረበ አቤቱታ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ | 54632 | ወ/ሮ ራውዳ ሙሜ<br>እና አምባሳደር አብደላ አብድራህማን | ግንቦት<br>29/2003 | |
| 103. | የኤክስፐርት ማስረጃ ሙሉ እምነት ሊጣልበት የሚችል ማስረጃ ስላለመሆኑ | 43453 | አንበሳ የከተማ አውቶብስ አገልግሎት ድርጅት<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ዘነበወርቅ ከበደ /ሁለት ሰዎች/ | ህዳር<br>15/2002 | |
| 104. | የባለሙያ ማስረጃ ፍፁም ስላለመሆኑና ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር ተገናዝቦ ብቃቱና ተአማኒነቱ ሊመዘን የሚገባ ስለመሆኑ | 14981 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ<br>እና ወ/ሮ ሀዋ መሐመድ | ግንቦት<br>04/1998 | |
| 105. | በህግ /ፍርድ/ ኃይል የተወሰደ ንብረት ሊመለስ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 349/1/ | 44238 | አቶ ማሞ ደምሴ /ሦስት ሰዎች/<br>እና<br>እነ አቶ አያሌው ገ/እግዚአብሄር /ሦስት ሰዎች/ | ጥር 09/2003 | |
| 106. | ከሀራጅ ሽያጭ ጋር በተያያዘ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 447 እና 453 ትርጉምና ሊፈፀሙ የሚችሉበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 447, 453 | 56130 | ሲሲ ታነሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>እነ መአዛ አስፋው /ሦስት ሰዎች/ | ጥር 26/2003 | |
| 107. | • ክስ ለመስማት በተቀጠረበት ዕለት ለመቅረብ ያልቻለው በቂ ሊባል በሚችል እክል /ችግር/ ምክንያት መሆኑን ያስረዳ ተከሳሽ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ በሚል የተሰጠው ትዕዛዝ እንዲነሳለት የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ<br>• "በቂ ምክንያት" በሚል የሰፈረው ሃረግ ሊተረጐም የሚገባው ተከሳሹ ቀና ልቦና ያለው መሆኑንና የተለያዩ አግባብነት ያላቸው ነባራዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70/ሀ/, 72, 78/1/ | 54080 | እነ አቶ ላል ሮላንድ ቻፕ ማን<br>እና<br>አቶ ዜና ወ/ማሪያም | ጥቅምት<br>19/2003 | |
| 108. | የልዩ አዋቂ ምስክሮች በፍ/ቤት የሚሾሙበት፣ የሙያ ግዴታቸውን የሚያከናውኑበት እና ፍ/ቤቶችም የሚቀርበውን ሙያዊ ምስክርነት ሊቀበሉ የሚችሉበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136 | 44522 | ጭላሎ ስራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>አፍሪካ ኢንጂነርስ ኮንስትራክሽን | ታህሳስ<br>15/2003 | |
| 109. | ክስ የቀረበበት ጉዳይ ለቃል ክርክር /ለመስማት/ በተቀጠረበት ዕለት ከሳሽ የሆነ ወገን በመቅረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 73 መሰረት የተዘጋ መዝገብን መነሻ በማድረግ በቀጥታ ይግባኝ ለማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 73 74/2/ | 58487 | ወ/ሮ አባይነሽ ገ/ህይወት<br>እና<br>ወ/ሮ እታገኝ ደሳለኝ | መጋቢት<br>22/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 110. | በፍ/ቤት በተሰጠ ፍርድ ላይ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ የተቀመጠው የሥነ ሥርዓት ድንጋጌ ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበትና የቀን አቆጣጠር ስሌት ተፈፃሚ የሚደረግበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 323/2/ | 59085 | ወ/ሮ ብርሃኔ አዱላ<br>እና<br>ግርማ አብዲሳ | መጋቢት<br>05/2003 | |
| 111. | ተከራካሪ ወገኖች የሚያቀርቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ብይን ሳይሰጥ በማለፍ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 244/2/ ሠ, 234 | 59294 | አቶ በቀለ ጃፋር<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ሙሉነሽ ማሞ | መጋቢት<br>19/2003 | |
| 112. | አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ጉዳይ ጋር በተያያዘ "ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ" በሚል የተቀመጠው ሃረግ ትርጉም<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5, 244/2/ | 62330 | አቶ አዱኛ አጃው<br>እና<br>ቀስቅስ አየነው | ሚያዝያ<br>03/2003 | |
| **ባንክና ኢንሹራንስ** | | | | | |
| 113. | በባንክ ከተቀመጠ ገንዘብ ጋር በተያያዘ ትክክለኛው ገንዘብ አስቀማጭ ከሆነ ሰው ውጭ ለሆነ ሰው ገንዘብ ወጪ ተደርጐ የተከፈለ እንደሆነ ባንኩ በሃላፊነት ሊጠየቅ የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ ያላደረገ ወይም የባንኩን የተለመደ አሰራር ሳይከተል የሰራ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ | 41535 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>እነ ግሎሪ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር /አራት ሰዎች/ | ጥቅምት<br>03/2003 | |
| 114. | በንግድ ህጉ የመድን ሰጪን ግዴታና ኃላፊነት በተመለከተ የቀረቡ ድንጋጌዎች መድን ሰጪው ከመድን ገቢዉ ጋር አንዳንድ ኃላፊነቶችን ለማስቀረት በሚል ከተስማሙባቸው ድንጋጌዎች ጋር ተገናዝበው ሥራ ላይ መዋል ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁጥር 664/1/ | 50199 | ግሎባል ኡንሹራንስ ኩባንያ<br>እና<br>አቶ አያሌው ወርቁ | ታህሳስ<br>27/2003 | |
| 115. | • ባንኮች ላበደሩት ገንዘብ በመያዣነት የያዙትን የማይንቀሳቀስ ንብረት በዕዳ መክፈያነት በሐራጅ ለመሸጥ የተሰጣቸውን ስልጣን በተግባር ሲያውሉ ህግን በመተላለፍ በባለዕዳው ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂነት ያለባቸው ስለመሆኑ<br>• በመያዣነት የተያዘውን ንብረት በሐራጅ ለመሸጠም የፍርድ ቤት ውሣኔ ወይም ፈቃድ የማያስፈልጋቸው ስለመሆኑ<br>• አበዳሪ የሆነ ባንክ በአዋጅ ቁ. 97/90 የተሰጠውን ስልጣን /መብት/ ትቷል (waive) ሊባል ስለሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 394-449<br>አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 3, 6 | 65632 | ህብረት ባንክ አ.ማ<br>እና<br>አቶ አሊ አብዱ | ሐምሌ<br>13/2003 | |
| 116. | መድን ገቢ የሆነ ወገን ጉዳት የደረሰበትን መድን የተገባለት ንብረቱ ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ ሊጠገንለት /ሊካስ/ ያልቻለ መሆኑን በተረዳ ወቅት በዚህ ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን የጉዳት ኪሣራ ለመቀነስ አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን የመፈፀም ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1802 | 47076 | አፍሪካ ኢንሹራንስ /አ.ማ/<br>እና<br>ወ/ሮ ጣይቱ አመዴ | መስከረም<br>25/2003 | |
| 117. | ግዴታውን ለመፈፀም ያልቻለን ተበዳሪ ንብረት አበዳሪ ባንክ በአዋጅ ቁ. 97/90 በንብረቱ ግምት ከተረከበ በኋላ ቀሪውን ዕዳ በተመለከተ የሚያቀርበው ጥያቄ በይርጋ ይታገዳል ለማለት የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1846 | 56010 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>እነ ቃድሮ ኑሬ | ሐምሌ<br>29/2003 | |
| **የዳኝነት ስልጣን** | | | | | |
| 118. | • የሊዝ ውል እንዲቋረጥ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ እና ሊከተል የሚችለው ውጤት | 54697 | አዲስ ኢንተርናሽናል አካዳሚ | መስከረም | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | • የሊዝ ውል ጋር በተያያዘ የሚቀርብ የመብት ጥያቄ በአ.አ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች የሚታይ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 455/97 አንቀጽ3/2/<br>አዋጅ ቁ. 272/94 አንቀጽ 2/7/, 15/1/ /ለ/ | | እና<br>እነ አቶ ሃይማኖት አበበ /ዘጠኝ ሰዎች | 24/2003 | |
| 119. | • ከአዋጅ ውጪ የማይንቀሳቀስ ንብረት ተወስዶብኛል በሚል በቀረበ አቤቱታ መነሻነት የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በህጉ አግባብ የሚሰጠው ውሣኔ እንደ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሊቆጠር የሚችልና ለአፈፃፀም የሚቀርብ ስለመሆኑ<br>• አንድን ጉዳይ የማየት ስልጣን ከፍርድ ቤት ውጪ ለሆነ አካል የተሰጠ በመሆኑ በዚህ አካል እየታየ ባለበት ተመሳሳይ ወቅት በፍርድ ቤት ሊታይ የማይገባ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 110/87<br>አዋጅ ቁ. 193/92<br>አዋጅ ቁ. 572/2000<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 8 | 48316 | ወ/ሮ ዘነበች ተመስገን<br>እና<br>የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | ጥቅምት<br>04/2003 | |
| 120. | • የፌዴራል ጉዳይን በውክልና ስልጣን ተመልክቶ በክልል ፍርድ ቤት ውሣኔ የተሰጠበትን ጉዳይ መሰረት በማድረግ የይግባኝ አቤቱታ ማቅረብ ስለሚቻልበት ሁኔታ /አግባብ/<br>• የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ በሚነሳ ክርክር ላይ እንደ ፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ብሎም በይግባኝ ደረጃ ባለ ክርክር ደግሞ እንደ ፌዴራል ይግባኝ ሰሚ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሆኖ የፌዴራል ጉዳዮችን ለማስተናገድ የሚያስችል የውክልና ስልጣን ያለው ስለመሆኑ<br>• አዋጅ ቁ. 322/95 የተወሰኑ የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች በህገ መንግስቱ ተሰጥቷቸው የነበረውን የፌዴራል ጉዳዮችን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣናቸው የማስተናገድ የውክልና ስልጣንን ብቻ የሚያስቀር እንጂ በይግባኝ ያላቸውን ስልጣን ጭምር የሚያስቀር ስላለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/2/, /5/<br>አዋጅ ቁ. 322/95 | 54577 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና<br>አቶ ሰለሞን ያቆብ | ህዳር<br>01/2003 | |
| 121. | የአ.አ. ከተማ አስተዳደር ማኀበራዊ ፍ/ቤቶች የፌዴራል ተቋማት ተከራካሪ የሆኑበትንና የገንዘብ መጠናቸው ከ5000 ብር ያልበለጠ የፍ/ብሔር ጉዳዮችን ለማስተናገድ ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 361/95<br>አዋጅ ቁ. 25/88 | 56118 | የኢትዮጵያ ቴሌ ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን<br>እና<br>ወ/ሮ ወርቅነሽ ወ/ማርያም | ህዳር<br>16/2003 | |
| 122. | በውጭ አገር መንግስት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን የማየት የዳኝነት ስልጣን ያለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 12/1/<br>የወንጀል ህግ ቁ. 263, 71 | 55299 | ዓለም ገብሩ<br>እና<br>የትግራይ ዓቃቤ ህግ | መጋቢት<br>19/2003 | |
| 123. | • የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች በአዋጅ ቁ. 67/89 ሥር የተደነገጉ የወንጀል ድርጊቶችን የተመለከቱ ክርክሮችን አይቶ ለመወሰን ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ<br>• ያለ ንግድ ፈቃድ በመነገድ ወንጀል የተከሰሱ ሰዎችን በተመለከተ የቀረበ ክርክርን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች ለማየት ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ<br>• ሺሻ ጋር በተገናኘ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ወንጀሎችን አይቶ ለመወሰን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 67/89 አንቀጽ 46 | 56893 | የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አቤቱታና ምርመራ ክስ አቀራረብ ንዑስ የስራ ሂደት<br>እና<br>እነ ወ/ሪት ፍሬህይወት ፍቃዱ /አስራ ሁለት ሰዎች/ | መጋቢት<br>22/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41/2/, 52 | | | | |
| 124. | • የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች ንብረትነታቸው የከተማው አስተዳደር ለመሆናቸው ክርክር በማይቀርብባቸው ቤቶች ላይ የሚነሱ የይዞታ፣ የኪራይ እና ሌሎች ክርክሮችን አይተው ለመወሰን ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ<br>• የሁከት ይወገድልኝ ክስ ከከተማው መሪ ፕላን ጋር እስካልተያያዘ ድረስ በከተማው ፍ/ቤቶች የሥረ ነገር ስልጣን ሥር የሚወድቅ ስላለመሆኑ<br>• የሥረ ነገር ስልጣን ሳይኖር የሚሰጥ ፍርድ እንዳልተሰጠ የሚቆጠርና ህጋዊ አስገዳጅነት የሌለው ስለመሆኑ<br>• ከቤት ይዞታ ጋር በተገናኘ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች የተሰጣቸው ስልጣን ሁከት ይወገድልኝ በሚል የሚቀርብ የዳኝነት ጥያቄን መሰረት ባደረገ መልኩ ሲቀርብ ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41/1//4//ረ/<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 9 231 /1/ /ለ/ | 64703 | ሻምበል ለታይ ገ/መስቀል<br>እና<br>በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 1 አስተዳደር ጽ/ቤት | ሐምሌ 29/2003 | |
| 125. | • የፖለቲካ ተሿሚ የሆነ ሰው ከሥራ ኃላፊነቱ መነሳቱን ተከትሎ ያለውን ቅሬታ የመንግስት ሰራተኞች አዋጅን መሰረት በማድረግ ለአስተዳደር ፍ/ቤት ጉዳዩን አቅርቦ ሊስተናገድ የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>• ፍ/ቤቶች በዚህ መልኩ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ተቀብሎ ለማስተናገድ የሥረ ነገር ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 12/2/<br>የቤንሻንጉል ብ/ክ/መ/የሲቪል ሰርቪስ አዋጅ ቁ. 29/95 አንቀጽ 71 | 63417 | አቶ ትዕዛዙ አርጋው<br>እና<br>የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ ም/ቤት | ሐምሌ 15/2003 | |
| 126. | • የኢትዮጵያ የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ከአዋጅ ውጩ የተወሰዱ ንብረቶችን በተመለከተ የቀረበን ጉዳይ አከራክሮና አጣርቶ የመወሰን ስልጣን በህግ የተሰጠውና ከፍ/ቤት ውጪ ያለ የዳኝነት አካል ስለመሆኑ<br>• ውሣኔውን ለማስፈፀምም አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ የሚችልና የሚሰጠውን ትዕዛዝ ለማስፈፀምም ማንኛውም የመንግስት አካል ተገቢውን ትብብር ማድረግ ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 110/87 አንቀጽ 74/ሐ/ 7 4 /ሐ/<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 371/1/<br>አዋጅ ቁ. 146/91 አንቀጽ 26/2/ 28/2/ | 63627 | ሼህ አሽራቅ ሰይድ<br>እና<br>የቡታጅራ ከተማ ቀበሌ 02 አስተዳደር | ሐምሌ 14/2003 | |
| 127. | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) አዋጅን በመተላለፍ የሚፈፀሙ የወንጀል ጉዳዮችን ለማየት ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 52/4/ /5/ 41/2/<br>አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 96<br>አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 49<br>የወንጀል ህግ ቁ. 349/1/ | 59723 | አብዱልፈታህ መሐመድ<br>እና<br>ኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ፍትህ ጽ/ቤት | ሰኔ 16/2003 | |
| 128. | • የንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን ያልተገባ የንግድ ውድድርን በሚመለከት የሚነሳውን ክርክር የመዳኘት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ<br>• ከንግድ ምልክት ጋር በተያያዘ አንድ ድርጊት ያልተገባ የንግድ ውድድር ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 329/95 አንቀጽ 10/2/ /ሀ/, 11, 15 | 55162 | ዩኒሊቨር ፒ.ኤል.ሲ..ፖርት ሰንላይት ሚራል ማርሲ. ሳይድ<br>እና<br>ጌት እሽት ዲተርጀንት ማምረቻ እና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር | የካቲት 22/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁ. 501/98<br>የንግድ ህግ ቁ. 133 | | | | |
| 129. | • አንድን ጉዳይ ተመልክቶ ዳኝነት ለመስጠት ሥልጣን የተሰጠው ለሌላ የዳኝነት አካል ከሆነ ፍ/ቤቶች ጉዳዮን የማየት ስልጣን የማይኖራቸው ስለመሆኑ<br>• የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ስልጣን ሥር የሚወድቅ አይደለም በሚል በኤጀንሲው የተረጋገጠ ጉዳይን ጉዳዩን የማየት ስልጣን ለሌላ የዳኝነት አካል የተሰጠ ነው በሚል ክርክር እስካልቀረበ ድረስ ፍ/ቤቶች ተቀብለው ማስተናገድ የሚችሉ ስለመሆናቸው<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231/1//ለ/, 9/2/, 244/3/ እና 328/3/<br>አዋጅ ቁ. 110/87<br>አዋጅ ቁ. 47/67 | 37964 | እነ አቶ መሐመድ ሁሴን የእነ አቶ መሐመድ ሁሴን ወራሾች /ሦስት ሰዎች/<br>እና<br>እነ የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ /ሁለት ሰዎች/ | ጥር 27/2003 | |
| 130. | • በአስተዳደራዊ ጉዳይ የመጨረሻ ውሣኔ እንዲያገኙ በህግ ተለይተው የተቀመጡ ጉዳዮችን በተመለከተ ፍ/ቤቶች የመዳኘት ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ<br>• የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሰረት ከሥራ የተሰናበተ ሰራተኛ በየትኛውም የፍርድ አካል ውሣኔ ወደ ሥራ የመመለስ መብት የማይኖረው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 578/2000 አንቀጽ 19/1/ /ለ/<br>ደንብ ቁ. 155/2000 አንቀጽ 37/1/ /2/ | 51790 | እነ ወልዳይ ዘሩ /ስልሳ አንድ ሰዎች/<br>እና<br>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓ/ህግ | ግንቦት 16/2003 | |
| 131. | • የንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን ያልተገባ የንግድ ውድድርን በተመለከተ የሚነሳ ክርክርን የመዳኘት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ<br>• የንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን ተግባርና ኃላፊነት<br>አዋጅ ቁ. 329/95 አንቀጽ 10/2/ /ሀ/, 3, 15<br>አዋጅ ቁ. 501/98 አንቀጽ 49 | 47682 | አም.ኤ ሽሪፍ ኃ.የተ.የግ.ማህበር<br>እና<br>ታደሰ ኃ.የተ.የግ.ማህበር | መጋቢት 06/2003 | |
| **የንግድ ህግ** | | | | | |
| 132. | በቼክ ላይ የተፃፈለትን ገንዘብ በህጉ በተቀመጠው ጊዜ ክፍያ ያልጠየቀበት ሰው ወይም በይዞታው እያለ የታገደበት እንደሆነ ይህንኑ ቼክ እንደ ተራ ሰነድ በማስረጃነት በማቅረብ ያላግባብ የመበልፀግ ክስ ሊመሰርት የሚችል ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 799 | 40173 | አምባሰል የንግድ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>አቶ አብዱልቃድር ጁሃር | ጥቅምት 05/2003 | |
| 133. | የሐዋላ ወረቀት በይርጋ ስለሚታገድበት አግባብ<br>የንግድ ህግ ቁ. 817/1/ /2/, 825 | 48242 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና እነ ቦጋለ መስቀሌ /ሁለት ሰዎች/ | ጥቅምት 04/2003 | |
| 134. | የአክስዮን ማህበር መሥራቾችና የአክሲዮን ድርሻ መብት ጋር በተያያዘ በሚቀርብ አቤቱታ ላይ የንግድ ህግ ቁ. 416/2/ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 416/2/ | 52269 | እነ አቶ ከድር ሀድ ሁሴን /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>አቶ ጁሀር አልይ | ጥቅምት 17/2003 | |
| 135. | • ቼክ ጋር በተያያዘ የሚቀርብ የፍትሐብሔር ክስ ለቼኩ መፃፍ /መውጣት/ ምክንያት ከሆነው ውል ጋር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባ ስለመሆኑ<br>• ውልን መሠረት በማድረግ የተፃፈ ቼክ ሌላው ወገን የውል ግዴታውን በአግባቡ አልተወጣም | 55077 | ወ/ሮ ጥሩወርቅ ዘገኑ<br>እና<br>አቶ ግደይ አብርሃ | ህዳር 28/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በሚል ምክንያት ብቻ ቼኩን የፃፈው ወገን በቼኩ ከመጠየቅ ነፃ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ<br>የንግድ ሕግ ቁጥር 717 | | | | |
| 136. | በባህር ላይ በሚደረግ የዕቃ ማጓጓዝ ለደረሰ ጉዳት የሚከፈል የጉዳት ካሣ አወሳሰን የባህር ህግ ቁ. 198/1/ /3/ | 52667 | ኒያላ ኢንሹራንስ አክስዮን ማህበር<br>እና የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ | ታህሳስ 12/2003 | |
| 137. | • የአክስዮን ማህበር አባል በመሆን የሚገኝ መብትና ጥቅም ለሌላ ሰው ሊተላለፍ የሚችልበት አግባብ<br>• ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ባለአክሲዮን የሆነ ሰው ላለበት የግል ዕዳ አክሲዮኖቹ /በወቅቱ የገበያ ዋጋ/ ተሸጠው እንዲከፈል ለማድረግ የሚቻል ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 522-524 | 57288 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>እነ አቶ አሸብር ታደሰ /አምስት ሠዎች/ | መጋቢት 19/2003 | |
| 138. | በባህር ላይ በሚደረግ የዕቃ ማጓጓዝ ለሚደርስ ጉዳት የአጓጓዡ የኃላፊነት አድማስ<br>የባህር ህግ ቁ. 196, 138, 205, 197, 180/3/ | 56480 | የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ<br>እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት | ሰኔ 14/2003 | |
| 139. | • የአክስዮን ማህበር ወይም የኩባንያ ሥራ አስኪያጅ የሆነ ሰው ድርጅቱ የሚያዝበት ገንዘብ እንደሌለው እያወቀ በድርጅቱ ስም በሚያወጣው/ በሚሰጠው/ ቼክ በኃላፊነት ሊያስጠይቀው የሚችል ስለመሆኑ<br>• የኩባንያ ሥራ አስኪያጅ በንግድ ህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ወይም የኩባንያውን መተዳደሪያ ደንብ በመጣስ መስራቱ የተረጋገጠ እንደሆነ ከድርጅቱ ጋር በአንድነት ወይም እንደነገሩ ሁኔታ በተናጠል ሊጠየቅ ስለመቻሉ<br>የንግድ ህግ ቁ. 530 | 57932 | ተክሉ ካሣ ገብረየስ<br>እና<br>ማርኮ ባርዚ | ሰኔ 30/2003 | |
| 140. | የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የንግድ ሥራ ፈቃድ ለመስጠት የቀረበው የንግድ ስም ቀደም ሲል ከተመዘገቡ የንግድ ስሞች ጋር አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይና አሳሳች አለመሆኑን እንዲሁም ለመልካም ጠባይ ወይም ሥነ ምግባር ተቃራኒ አለመሆኑን ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 67/89 አንቀጽ 16/2/ 14 20<br>አዋጅ ቁ. 376/96<br>የንግድ ህግ ቁ. 137,138 | 58931 | የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር<br>እና<br>ታይገር ሎጀስቲክ እና የንብረት ጥበቃ<br>ኃ/የተ/የግል ማህበር | ሐምሌ 15/2003 | |
| 141. | • ከቼክ ጋር በተያያዘ “የግል ግንኙነት” በሚል የተቀመጠው ሀረግ ሊተረጉም የሚችልበት አግባብ<br>• በቼክ የሚገደዱ ሰዎች ላይ አውጭው ክስ ለማቅረብ የሚችለው ቼኩ ከተፃፈበት ቀን አንስቶ እስከ አንድ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ስለመሆኑ<br>• በቼክ በተከሰሰና ሰነዱን ይዞ በመጣው ሰው መካከል ያለን “የግል ግንኙነት” በመቃወሚያነት ለማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ<br>• ቼክ የሚሰጥበት ምክንያት በሰጪውና በተቀባዩ የሚወሰን እንጂ በህጉ የተዘረዘረ ባለመሆኑ ቼኩን የፃፈው ሰው ቼኩን የሰጠሁት ለዋስትናነት ነው በሚል ቼኩን ይዞ በመጣው ሰው ላይ “የግል ግንኙነትን” መሠረት በማድረግ የሚያቀርበው መቃወሚያ ቼክ በዋስትና ሊሰጥ የማይችል ነው በሚል ውድቅ ሊደረግበት የማይገባ ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 717/1/-/3/, 855, 881/1/, /ሀ/, 854, 640,868,752,850,827 - 840 | 24435 | ሀጂ መሃመድ አደም<br>እና<br>አቶ ፍፁም ግርማ | የካቲት 04/2000 | |
| 142. | • ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አባል የሆነ ሰው ከአባልነቱ ለመውጣት የሚችልበት ብሎም ማህበሩ ሊመሰረትና ሊፈርስ የሚችልበት አግባብ<br>• የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 244/2/ /ረ/ ተከራካሪ ወገኖች አለመግባባታቸውን በሽምግልና ስምምነት ከመፋታት ጋር ተፈፃሚ የሚደረግበት አግባብ | 50537 | ሲ/ር መአዛ ዮሴፍ<br>እና<br>ዶ/ር ዮሴፍ ደነቀው | ግንቦት 02/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የንግድ ህግ ቁጥር 510/2/<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 244/2/ /ረ/ | | | | |
| 143. | • በንግድ ህጉ ቁጥር 683 "ወኪሎች" በሚል የተመለከተው የእቃ አስተላላፊነት ሥራን ለጥቅም የሚሰሩ ወገኖችን የማያካትት ስለመሆኑ<br>• መድን ሰጪው ክስ ሊያቀርብባቸው የማይችላቸው ወገኖች ከመድን ገቢው ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያላቸውና ለራሳቸው ጥቅም ሳይሆን ለመድን ገቢው ጥቅም የሚሰሩ ወገኖችን ስለመሆኑ<br>የንግድ ሕግ ቁ. 683/3/ | 49295 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና<br>እነ የቻይና ዋንቦ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን<br>/ሁለት ሰዎች/ | መጋቢት<br>22/2003 | |
| **አእምሯዊ ንብረት** | | | | | |
| 144. | የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የንግድ ምልክት እና የንግድ ስምን አስመልክቶ ፈቃድ በሚሰጥበት ወቅት የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማያዛባና ያልተገባ የንግድ ውድድር እንዳይከሰት ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ መሆን ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 329/95 አንቀጽ 10/1/, /2//ሀ/, እና /ሐ/<br>አዋጅ ቁ. 501/98<br>አዋጅ ቁ. 320/95 አንቀጽ 6/1/ | 57179 | ኢትዮ ሴራሚክ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>እነ የኢትዮጵያ አእምሮአዊ ንብረት ጽ/ቤት<br>/ሁለት ሰዎች/ | የካቲት<br>22/2003 | |
| 145. | • የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በሚሰጣቸው ውሣኔዎች ላይ ቅሬታ አለኝ የሚል ወገን ያለው መብት ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች ይግባኝ ማቅረብ ነው እንጂ የቀጥታ ክስ ማቅረብ ስላለመሆኑ<br>• የፌ/ጠፍ/ቤት ሦስት ዳኞች በሚሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሰጠው ትዕዛዝ /ውሣኔ/ አስገዳጅ ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 454/97 አንቀጽ 2/1/<br>አዋጅ ቁ. 25/88<br>አዋጅ ቁ. 501/98 አንቀጽ 6, 17, 36, 49<br>አዋጅ ቁ. 320/95<br>አዋጅ ቁ. 410/96 | 59025 | የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረቶች ጽ/ቤት<br>እና<br>አቶ ጥበበ አየለ | ግንቦት<br>19/2003 | |
| **ውክልና** | | | | | |
| 146. | • አንድ ሰው ለሌላ ሰው በሰጠው ፍፁም የውክልና ስልጣን መሰረት የተከናወነውን ተግባር ለማፍረስና መከራከሪያው ሊያደርገው የሚችለው ወካዩ ራሱ ስለመሆኑ<br>• የወካይ ወራሾች ወኪሉ የውክልና ስልጣን ወሰኑን ሳያልፍ የስራውን ተግባር የሚቃወሙበት ህጋዊ መሰረት ስላለመኖሩ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2189/1/ እና /2/ | 38721 | ካፕቴን ዮናስ ሕሉፍ<br>እና<br>እነ አቶ እስጢፋኖስ ኪዳኔ /አራት ሰዎች/ | ህዳር<br>27/2003 | |
| 147. | የውክልና ስልጣን መስጫ ሰነድ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል ቀርቦ ካልተረጋገጠና ካልተመዘገበ በስተቀር ህጋዊ ውጤት የማይኖረው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 334/95 አንቀጽ 5/1//ለ/ | 59568 | አቶ ቴዎድሮስ ተስፋዬ<br>እና<br>አቶ ሙሉ አርጌ /ሁለት ሰዎች/ | ሚያዝያ<br>05/2003 | |

# ውል


www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 54249

ጥቅምት 16 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ጌታሁን አበበ ቦጋለ - ጠበቃ ገመዳ ጎንፋ - ቀረበ፡፡

**ተጠሪ፡-** ሐሰን ገአስ ሁመድ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ውልን መነሻ በማድረግ የተጠየቀውን የገንዘብ ክፍያ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአፋር ብ/ክ/መ/ በዞን አንድ /የአውሲረሲ/ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ ተጠሪው በመልካች ላይ ክስ የመሠረተው የከርሰ ምድር ቁፋሮ ሥራ በጋራ ለመሥራት ውል የተዋዋልን ሲሆን፣ ተከሣሽ /የአሁን አመልካች/ ሥራውን መጀመር ሲገባው ይህን አላደረገም፡፡ በመሆኑም ውሉን በማፍረሱ ግዴታ የገባበት ብር 200.000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ውሉ በስህተት የተደረገ ነው፡፡ ስህተቱም የሁለቱ ወገኖች ነው፡፡ ከዚህ የተነሣም የክልሉ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ውሉን ሰርዞአል የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ክሱን ውድቅ አድርጎአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ውሣኔውን በመቃወም ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ የተሠማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በከፍተኛው ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በመሻር አመልካችን ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች መጋቢት 14 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች እንደ ውል አፍራሽ በመቁጠር ክስ የቀረበበትን ገንዘብ እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ካሰሙት ክርክር እና አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ የተደረገውን የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር እና የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ ክርክሩን በመጀመያ ደረጃ የሰማው የአውሲረሲ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተጠሪን ክስ ወድቅ ያደረገው ለክሱ መሠረት የተደረገው ውል ተከሣሽን ለማስገደድ የሚችል ሕጋዊ ውል አይደለም እሚል መደምደሚያ ላይ በመድረሱ እንደሆነም ከውሳኔው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡



www.chilot.me

ተጠሪ የከርሰ ምድር ቁፋሮ ከሌሎች ሰዎች ጋር ለመሥራት የሚያስችል ፈቃድ ሳይኖረው ውሉን እንደተዋዋለና በዚህ ምክንያት የክልሉ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ውሉ ሕጋዊ ውጤት እንዳይኖረው እንዳደረገው በፍሬ ነገር ረገድ እንደተረጋገጠም ተመልክተናል፡፡ ይግባኙን የሰማው የአፋር ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሲሆን ውሉ በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ስለመሠረዙ ግንዛቤ እንደወሰደ በውሣኔው አመልክቶአል፡፡ በከፍተኛው ፍ/ቤትም የተሰጠውን ውሣኔ የሻረውም ውሉ በቢሮው አልተሰረዘም በማለት ሳይሆን፣ ውሉ በክልሉ ፍትሕ ቢሮ ፊት የተደረገ ነው፡፡ ተዋዋይ ወገኖችም ወደውና ፈቅደው ያደረጉት ነው፡፡ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮው ውሉን የመሠረዝ ሥልጣን የለውም የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ነው፡፡

በበኩላችን እንደምናየው የከርሰ ምድር ቁፋሮ ለማድረግ በቅድሚያ ከሚመለከተው የመንግሥት ተቋም ወይም መሥሪያ ቤት ፈቃድ ሊኖር ይገባል፡፡ የመሬት ይዞታ እና በመሬት ውስጥ ያሉት ማዕድናት የመንግሥት እና የሕዝብ ሃብቶች እንደመሆናቸው /የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ /3/ ይመለከተዋል/ ከመንግሥት በግልጽ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖር የከርሰ ምድር ቁፋሮ ለመሥራት ግለሰቦች ቢዋዋሉ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ውል ተዋውለዋል ሊባል አይችልም፡፡ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በዚህ ረገድ የሚመለከተው አካል አይደለም አልተባለም፡፡ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተደርጎ የነበረውን ውል ሰርዣለሁ ያለውም በዚህ ምክንያት ማለትም ከቢሮው የተሰጠ ፈቃድ ስለሌለ ነው፡፡ በአጠቃላይ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ተደርጎአል የተባለው ውል ተግባራዊ ሊሆን ይችል የነበረው ፈቃዱ ተሰጥቶ ቢሆን ነበር፡፡ ውሉ በዚህ ምክንያት ተግባራዊ ሊሆን ካልቻለ ደግሞ ለውሉ አለመተግበር አመልካች ብቻውን ኃላፊ የሚሆንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም የአፋር ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 1098 ጥር 10 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. በአፋር ብ/ክ/መ/ የዞን አንድ /አውሲረሲ/ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 1220 የካቲት 11 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
   ስለዚህም አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ እንዲከፍል አይገደድም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 40109

ጥቅምት 1 ቀን 2003

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጲያ ልማት ባንክ - ነ/ፊጅ አክሊሉ ተስፋዬ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ተክሌ ዋከኔ -- ዋከኔ ቶላ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የመያዣ ውል የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው ክስ የቀረበው በተጠሪ ነው፡፡ የክሱ ምክንያት በአበዳሪ /አመልካች/ እና ተበዳሪ በአቶ ሽፈራው ቡሎ መካከል በ24/12/1987 ዓ.ም በተደረገ የብድር ውል የቤት ቁጥር 870 የሆነውን መኖሪያ ቤት ለብድር አከፋፈል ዋስትና መያዣ ያደረገ መሆኑን ጠቅሶ የብድር ውሉም ሆነ የመያዣ ውሉ ሳይታደስ አሥራ ሦስት /13/ ዓመት ስለሆነ የመያዣ ውሉ በፍ/ብ/ሕግ/ ቁጥር 3058 መሠረት ቀሪ ሆኖ አመልካች የያዘውን የቤቱን ካርታና ፕላን እንዲመልስ እንዲወሰን የሚል ነበር፡፡

አመልካች ሥር ፍ/ቤት ያቀረበው ክርክር ታህሳስ 19 ቀን 1988 የተፈረመው የመያዣ ውል ጥቅምት 9 ቀን 1998 ዓ.ም ለነቀምቴ ከተማ አስተዳደር በተፃፈ ደብዳቤ ለቀጣይ 10 ዓመት እንዲታደስ የተደረገ መሆኑን ጠቅሶ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የዳኝነት ሥልጣን ያከራከረው የምሥራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለ ውሉ መታደስ ከማዘጋጃው መግለጫ ከጠየቀ በኂላ ውሉ የታደሰው ከሳሹ /ተጠሪ/ በሌለበት ነው በማለት ይህ የዋሱን ሃላፊነት የሚለወጠው ያለእሱ እውቅና የተደረገ ነው በሚል የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1928/2/ን በመጥቀስ የመያዣ ውሉ እንደታደሰ አይቆጠርም በማለት የመያዣ ውሉ ሳይታደስ 10/አሥር/ ዓመት አልፎበታል በሚል ተጠሪ የዋስትና ሃላፊነት የለበትም ሲል ፈርዷል፡፡

አመልካች በውሳኔው ቅር ተሰኝቶ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

ለዚህ ሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ነ/ፈጅ ለሰበር የቀረበው አቤቱታ ይዘት ባጭሩ አመልካች ለሰጠው ብድር ተጠሪ መያዣ መስጠቱን፣ የመያዣ ውል ከሰው ዋስትና



www.chilot.me

የተለየ መሆኑን የሥር ፍ/ቤቶች ባለመገንዘብ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1928/2/ን ጠቅሰው መወሰናቸው ስሕተት ስለመሆኑ እና የመያዣ ውሉ የተጠሪን ስምምነት ሳይጠይቅ ሊታደስ መቻሉን የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 3058/2/ ድንጋጌ ባለማገናዘብ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት እንዲሻር አመልክተዋል፡፡ የሰበር ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የተጠሪን ስምምነት ሳያገኝ ውሉ መታደሱ ተቀባይነት የለውም ሲሉ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ ስለመሆኑ ለመመርመር ሲባል ተጠሪ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪም ግንቦት 11 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ቀርበው ክርክራቸውን አሰምተዋል፡፡ የክርክራቸው ይዘትም ማዘጋጃ ቤቱ የመያዣ ውሉን አላደሰም የሚልና ቀርበው ስምምነት ያልሰጡ መሆኑን ጠቅሰው የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከትነው ሆኖ እኛም ጉዳዩን ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡ በዚህ ሰበር ችሎት ውሳኔ የሚያስፈልገው ጭብጥ የመያዣ ውልን ለማደስ የተጠሪው ስምምነት አስፈላጊ ነው ወይስ አይደለም; የሚለው ነው፡፡ከመዝገቡ መረዳት እንደቻለው አመልካች ለአቶ ሽፈራው ቡሎ ለሰጠው ብድር ተጠሪ በነቀምት ከተማ ቀበሌ 04 ክልል የሚገኘው ቁጥሩ 870 የሆነ መኖሪያ ቤቱን በዋስትና መያዣ መስጠቱን አላከራከረም፡፡

የመያዣ ውሉም በክፍሉ አስተዳደር ተመዝግቦ የቆየ ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የመያዣ ውል ተመዝግቦ ካለ ለቀጣይ አሥር ዓመት ያህል ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 3058/1/ ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ ይህ ጊዜ ከማለፉ በፊት ለተጨማሪ ጊዜ ውጤት እንዲኖረው ለማድረግ ውሉን ማደስ አስፈላጊ እንደሆነም የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 3058/2/ ይጠቅሳል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የመያዣ ውሉ እንዲታደስ የአሥር ዓመት ጊዜ ከማለፉ በፊት አመልካች ለክፍሉ መሬት አስተዳደር /ማዘጋጃ ቤት/ በደብዳቤ ያሳወቀ ስለመሆኑ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት ይህንን ፍሬ ነገር ካረጋገጠ በኂላ የመያዥ ውሉ እንዲታደስ የአስያዡ ፈቃድ አልተገለፀም በሚል ምክንያት መያዣ ውሉ እንደታደሰ አይቆጠርም በማለት ውሉን ውጤት አልባ ማድረጉን ተረድተናል፡፡

የመያዣ ውል ከተመዘገበ ይህው ውል እንዲታደስ ጥያቄ የሚቀርበው በመያዣ ውሉ መብት ተጠቃሚ በሆነው ወገን መሆኑን መረዳት አዳጋች አይደለም፡፡ የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 3058/2/ መንፈስ መረዳት የሚቻለውም ይኸው ሀሳብ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ይበልጥ ግልፅ የሚሆነው የመያዣ ውል ከመዝገብ ሊሰረዝ የሚቻልባቸው ሁኔታዎች እና የሥልጣኑን ጉዳይ አስመልክቶ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1632/2/ ጋር በማገናዘብ ሲታይ ነው፡፡

እነዚህ ድንጋጌዎች የሚያስገነዝቡት የተመዘገበው መብት ጊዜ ተወስኖለት የተደረገ እንደሆነ ጊዜው ሲያበቃ ይኸው እንዲሰረዝ አቤቱታ ሊቀርብ ሳያስፈልግ ባለሥልጣኑ ከመዝገብ መሠረዝ እንደሚችል ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል በተመዘገበው መብት ተጠቃሚ የሆነው ወገን ይኸው የተወሰነ ጊዜ ከማለፉ በፊት እንዲታደስለት ከጠየቀ ውል እንዲታደስ መመዝገብ የሚችል መሆኑን ያመለክታል፡፡



www.chilot.me

ከእነዚህ ድንጋጌዎች አቀራረፅና ይዘት መረዳት የሚቻለው የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዥ ውል አንዴ ከተመዘገበ ይህንኑ ውል የማደስ ተግባር ለመፈጸም የአስያዡ ፈቃድ እንደገና መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ የሚያሣይ አንቀጽ አለመሆኑን ነው፡፡

ስለሆነም አመልካች የመያዣ ውሉ እንዲታደስ ለማዘጋጃ ቤቱ በሕጉ በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ ጥያቄ ማቅረቡ እስከተረጋገጠ እና ማዘጋጃ ቤቱም ይህንኑ መፈፀሙ እስከታመነ ጊዜ ድረስ ተጠሪ ውሉ እንዲታደስ ፈቃዱን አለመግለፅ የመያዣ ውሉን ጊዜ ሊያራዝም አይችልም በማለት የሥር ፍ/ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ የሕጉን መንፈስና ይዘት በአግባቡ ያላገናዘበ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህም የመያዣ ውሉ የአሥር አመት ጊዜ አልፎበታል ከዚያ በኂላም አልታደሰም በማለት የተጠሪን ክስ ተቀብለው የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የምሥራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 13190 በ4/7/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 64740 በ4/11/2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሸሯል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የመያዣ ውል ለተጨማሪ 10 ዓመት ጊዜ የታደሰ በመሆኑ የተጠሪ ክስ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፍ/ዘ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 42150

ጥቅምት 29 ቀን 2003 ዓ.ም

***ዳኞች፡-*** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

***አመልካች -*** የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ነ/ፈጅ ወንድወሰን ጥሩነህ ቀረቡ

***ተጠሪዎች -*** እነ አቶ ዳንኤል ካሣ /ሃያ ሁለት ሰዎች/ - ቀረቡ

- የ22ኛ ተጠሪ ጠበቃ ይሁን ፀሐይ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የኪራይ ውል ይሞላልን ጥያቄን መሠረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ ተጠሪዎች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአሁኑ አመልካች ላይ የካቲት 27 ቀን 1999 ዓ.ም በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- አመልካች የሚያስተዳድራቸውን የመንግስት ቤቶች ያለውል በቁልፍ ሽያጭ ወይም በውክልና በመያዝ ከሶስት እስከ አስር አመት ድረስ በቤቶቹ ቤተሰብ አፍርተው እየኖሩ እንደሚገኙ የኪራይ ቤቶች አስተዳደር የስራ አመራር ቦርድ 94ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ በተጠሪዎች ሁኔታ የሚኖሩ ግለሰቦች ሕጋዊ ተከራይ እንዲሆኑ ውሣኔ ማሳለፉን፣ የተጠሪዎች ሁኔታ ውሣኔ ያረፈበት በመሆኑ የኪራይ ውል አመልካች እንዲያስሞላቸው ቢጠይቁ ከሰባት መቶ ሁለት ሰዎች ዝርዝር ውስጥ የሌላችሁ በመሆኑ ውል አላስሞላችሁም በማለት የመለሳቸው መሆኑን ተጠሪዎች ከእነዚህ ሰባት መቶ ሁለት ከተባሉ ግለሰቦች ጋር ሲመዘገቡ አቅርቡ የተባሉትን ማስረጃ ሲያቀርቡ ቆይተው በአመልካች ድርጅት አስተዳደራዊ ችግር ባለመመዝገባቸው ሁሉንም ዜጋ እኩል ያላስተናገደና ተጠሪዎችን የጎዳ መሆኑንና የአመልካች ድርጅት ድርጊት ኢፍትሐዊና አድሎ ያለበት በመሆኑ ሊታረም እንደሚገባው ገልፀው ጥቅምት 03 ቀን 1998 ዓ.ም በተሰጠው ውሣኔ መሠረት ተጠቃሚ መሆናቸው እንዲረጋገጥ በኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች በኩል የተከሰተው አፈፃፀም ችግር የተጠሪዎችን በሕግ ፊት በእኩል የመታየት ሕገ መንግስታዊ መብት የጣሰና የመልካም አስተዳደር መርህን ያልተከተለ አሰራር ነው ተብሎ በአመልካች ቤቶች ላይ ሕጋዊ ውል እንዳይሞሉ የተደረገው ክልከላ ተነስቶ በቦርዱ ውሣኔ መሠረት ሕጋዊ ውሉ እንዲሞላ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ክስ ለመመስረት የሚያስችላቸው ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ መብት የሌላቸው መሆኑን ተጠሪዎች ሰባት መቶ ሁለት ሰዎች በመባል ውል እንዲሞሉ ከተፈቀደላቸው ሰዎች መሐል ስማቸው



www.chilot.me

እንደማይገኝ በተደረገው 105ኛ ስብሰባ በኤጀንሲው ሰባት መቶ ሁለት ሰዎች በመባል ከሚታወቁት ባለጉዳዩች በቀር ሊስተናገዱ እንደማይገባ በመወሰኑ የተጠሪዎችን ጉዳይ ማስተናገድ እንደማይቻል፣ ተጠሪዎች ከፊሉ ከመጋቢት 04 ቀን 1997 ዓ.ም በፊት ጉዳያቸው ውሣኔ ያገኘ በመሆኑ 94ኛ ስብሰባ በተደረገው ውሣኔ መሠረት ሊስተናገዱ የማይገባ ከፊሉ ደግሞ ውዝፍ ኪራይ ባለመክፈላቸው ምክንያት ውሣኔ ያገኘ በመሆኑ በአንድነት ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት እንደሌለው እንዲሁም ውል አመልካች ሊዋዋል የሚችለው በሙሉ ፍላጎት እንጂ ተገዶ አለመሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

የስር ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ በመመርመር የአመልካችን ክርክር በከፊል ውድቅ አድርጐ የአሁኑ ተጠሪዎች ጥቅምት 03 በቀን 1998 ዓ.ም በተሰጠው ውሣኔ መሠረት ተጠቃሚዎች በመሆናቸው በውሣኔው መሠረት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሲል ወስኗል በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረፈጅ ታህሣሥ 03 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፉት ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩ ተመርምሮም አመልካች ከተጠሪዎች ጋር የኪራይ ውል ማድረግ አለበት ወይስ የለበትም? የሚለው ነጥብ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል ጉዳይ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ የግራቀኙ የቃል ክርክርም ጥቅምት 23 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰምቷል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የተጠሪዎች የዳኝነት ጥያቄ አመልካች በቤቶቹ ላይ ውል አስሞልቷቸው የተከራይነት መብት እንዲረጋገጥላቸው ሲሆን ለጥያቄው መሠረት ያደረጉትም የአመልካች ቦርድ ውሣኔ ተጠቃሚ የሚያደርጋቸው መሆኑን አመልካች ከተጠሪዎች ጋር ተመሳሳይ ሁኔታ ያላቸውን ሌሎች በርካታ ሰዎችን የኪራይ ውል እንዲሞሉ ሲያደርግ ተጠሪዎችን በሕገ መንግስቱ የተጠበቀላቸውን የእኩልነት መብት ግንዛቤ ውስጥ ባላስገባ መልኩ አድሎ ፈጥሯል የሚሉትን ምክንያቶችን መሆኑን ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ ተጠሪዎች ተመሳሳይ ሁኔታ ያላቸው ሰዎች የኪራይ ውል እንዲሞሉ ተደርጓል የሚሉት ለተጠሪዎች መብት የማይሰጥ መሆኑንና የቀድሞው የቦርድ ውሣኔ በሌላ ውሣኔ መተካቱን እንዲሁም የኪራይ ውል መደረግ ያለበት በተዋዋይ ወገኖች ሙሉ ፈቃድ እንጂ በግዴታ አለመሆኑን ጠቅሶ የተጠሪዎች የዳኝነት ጥያቄ የህግ ወይም የውል መሠረት የለውም በማለት መከራከሩን ተገንዝበናል፡፡

በመሠረቱ በፌዴራልም ሆነ በክልል የዳኝነት ስልጣን የፍ/ቤቶች ብቻ ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 79/1/ ተደንግጓል የሕገመንግስቱ አንቀጽ 37 ድንጋጌ ሲታይ ደግሞ ፍ/ቤቶች በማናቸውም ጉዳይ ገደብ የለሽ ስልጣን የሌላቸው መሆኑን ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት የሕገመንግስቱ አንቀጽ 79/1/ እና 37 አንድ ላይ ሲታዩ ፍ/ቤቶች አንድን ጉዳይ ተቀብለው ለማየትና ለመወሰን ሥልጣን የሚኖራቸው ጉዳዩ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው /Justiciable matter/ ሆኖ ከተገኘ ብቻ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 1 “ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት



www.chilot.me

ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሣኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው፡፡" በሚል ከተደነገገው "..... ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል..." የሚለው፣ እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 4 በሌላ አኳኋን እንዲፈፀም በህግ ካልተገለፀ፣ ክሱን ተቀብሎ ለማከራከር ሥልጣን ያለው ፍ/ቤት ብቻ ነው በሚል መደንገጉ በፍርድ ሊወሰን በሚችለው ጉዳይ ፍ/ቤቶች ብቸኛ ስልጣን የሌላቸው መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቶች አንድን ጉዳይ ተቀብለው ማየት የሚችሉት ጉዳዩ በፍርድ የሚያልቅ ሲሆንና በሌላ አኳኋን እንዲታይ በሕግ እስካልተወሰነ ጊዜ ድረስ ብቻ ነው፡፡ ጉዳዩ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል ነው ሊባል የሚችለው ደግሞ የክርክሩ መሠረት በሕግ ጥበቃ ያገኘ መብት ወይም ግዴታ ሲሆን ወይም ለመብቱ ወይም ግዴታው መሠረት የሚሆን ውል መኖሩ ሲረጋገጥ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር የመሠረቱት ሕጋዊ ውል የሌላቸው መሆኑን ራሳቸው ክሱን ሲመሠርቱም ቢሆን አረጋግጠው የቀረቡት ጉዳይ ሲሆን አመልካች የሚያስተዳድረውን ቤት የኪራይ ውሉ ከተጠሪዎች ጋር እንዲገባ ይደረግላቸው ዘንድ ዳኝነት የሚጠይቁት አመልካች ከተጠሪዎች ጋር ተመሳሳይ ሁኔታ ያላቸውን ሰዎች ኪራይ እንዲሞሉ በቦርድ ተወስኖ በቁጥር ሰባት መቶ የሆኑት ሰዎች የውሣኔው ተጠቃሚ ሲሆኑ ተጠሪዎች ላይ አድሎ በመፈፀም በቦርዱ ውሣኔ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ማድረጉ ከመንግስት መስሪያ ቤት የማይጠበቅ ነው በሚል ነው፡፡

በመሠረቱ አመልካች የራሱ የሆነ ሕጋዊ ስልጣን ያለው፣ የመንግስት ቤቶችን የማስተዳደር ኃላፊነት የተሰጠው ሲሆን እንደማንኛውም ባለሃብት ቤቶቹን ለፈለገው ሰው የማከራየት ሕጋዊ መብት ያለው አካል መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የራሱን ሥርዓት በመዘርጋት የሚያስተዳድራቸውን ቤቶች ለሕብረተሰቡ በተከራይነት እንዲጠቀሙ የሚያደርግ መሆኑ ይታመናል፡፡ ኪራይ ደግሞ ውል ከሚባሉት ሕጋዊ ተግባራት አንዱ ሲሆን በሕግ ጥበቃ የሚደረግለት የኪራይ ውል የውል አመሰራረት መሠረታዊ ነጥቦችን አሟልቶ መገኘትን የግድ ይላል፡፡ ለውል አመሰራረት መሠረታዊ ነጥቦች ናቸው ከሚባሉት መካከል ደግሞ አንዱ የመዋዋል ነፃነት /Freedom of contract/ ነው፡፡ የመዋዋል ነፃነት ሲባልም ተዋዋይ ወገኖች በሙሉ ፈቃዳቸውና ፍላጎታቸው ውል የማድረግ መብት ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ሕግ ጥበቃ የሚያደርገው በሕጉ አግባብ የተመሰረተን ውል እንጂ ከመነሻው ተዋዋይ ወገኖች በግድ በውል ግዴታ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግን አለመሆኑን ነው፡፡

የተጠሪዎች ጥያቄ ሲታይም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 25፣ 41፣ 89 እና 90 ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መንፈስ የሚጠቅስ ቢሆንም አመልካች በሕጉ ከተሰጠው ሥልጣን እና ተግባር እንዲሁም ከውሉ አመሰራረት መሠረተ ሃሳቦች አንፃር ሲታይ የተጠሪዎች የእኩልነት እና መጠለያ የማግኘት መብት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የተያያዘ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ከሁሉም በላይ ከተጠሪዎች ጋር ተመሳሳይ ሁኔታ ያላቸውን ሰዎች የኪራይ ተጠቃሚነት ወሰነ የተባለው የአመልካች መስሪያ ቤት የስራ አመራር ቦርድ የተጠሪዎች ጥያቄ ከሰባት መቶ ሰዎች ጋር ተመሳሳይ አለመሆኑን በ105ኛው መደበኛ ስብሰባ አረጋግጦ የወሰነ ሲሆን ተጠሪዎች ጉዳዩ ተመሳሳይ ነው፣ ወይም ተመሳሳይ እንዳይሆን በአመልካች የአስተዳደር ችግር ተፈጥሯል የሚሉ ከሆነም ጥያቄውን ማቅረብና መስተናገድ ያለባቸው በፍርድ ቤት ክስ በመመስረት ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም የተጠሪዎች ጥያቄ በሕግ አግባብ የተቋቋመ የኪራይ ውል አፈፃፀም ጋር የተገናኘ ባለመሆኑ አመልካች ከተጠሪዎች ጋር በፍርድ ኃይል የኪራይ ውል እንዲዋዋል የሚደረግበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ሲሆን ጉዳዩ በፍርድ ሊያልቅ የማይችል ሆኖ እያለ



www.chilot.me

የበታች ፍርድ ቤቶች ክሱን በመቀበል ውሣኔ መስጠታቸው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል

*ው ሣ ኔ*

1. በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 84204 ሕዳር 03 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 61531 ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት በድምፅ ብልጫ ተሽሯል፡፡

2. ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር ያቋቋሙት ሕጋዊ የኪራይ ውል በሌለበት ሁኔታ አመልካች ከተጠሪዎች ጋር የኪራይ ውል ለማድረግ በፍርድ ኃይል የሚገደድበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት*

*የሃሣብ ልዩነት*

እኔ በአምስተኛው ተራ ቁጥር ስሜ የተጠቀሰው ዳኛ አመልካቾችና ተጠሪዎች በዚህ መዝገብ የተከራከሩበት ጉዳይ /ጭብጥ/ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል አይደለም አመልካቾችን በፍርድ ለመጠየቅ የሚያስችላቸው ተጠሪዎች ከውል የመነጨ ወይም በህግ ዕውቅናና ጥበቃ የተሰጠው መብት የላቸውም በማለት አብላጫው ድምፅ በሰጠው የህግ ትርጉምና ውሣኔ ያልተስማማሁ በመሆኔ ለልዩነት ምክንያት የሆኑኝን ነጥቦች ከዚህ ቀጥሎ ገልጫለሁ፡፡

1. አብላጫው ድምፅ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት ከሚለው መደምደሚያ ላይ የደረሰበት የመጀመሪያው ምክንያት ጉዳዩ በፍርድ የሚያልቅ /Justiciable matter/ አይደለም በማለት ነው፡፡ "ፍትህ የማግኘት መብት" በአገራችን የማናቸውም ሰው መሠረታዊ መብት መሆኑ በህገመንግስቱ አንቀጽ 37 የተደነገገ ሲሆን ማናቸውም ሰው በፍርድ ሊያልቁ የሚችሉ ጉዳዩችን ለፍርድ ቤት ወይም በህግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው ሌላ አካል የማቅረብና ፍትህ የማግኘት መብት ያለው መሆኑን በሕገመንግስቱ አንቀጽ 37/1/ ተደንግጓል በእኔ እምነት ይኸ ህገመንግስታዊ ድንጋጌ በተፈጥሯዊ ባህሪያቸው ፍርድ ቤት ወይም ሌላ የዳኝነት ሥልጣን በህግ የተሰጠው አካል በፍትህ ጠያቂው ወይም አቤቱታ አቅራቢው የቀረበለትን ማመልከቻና ማስረጃ ለማመልከቻው መልስ የመስጠት ግዴታ ያለበት የተፈጥሮ ወይም የህግ ሰው የሚሰጠውን መልስና ማስረጃ በመቀበል በመስማትና በመመርመር ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ውሣኔ ሊያስተላልፍባቸው የሚችሉ ጉዳዩች በፍርድ ሊያልቁ የሚችሉ ጉዳዩች ወይም /Justiciable matter/ እንዲሆኑና ማናቸውም ሰው ለፍርድ ሰጭ አካል በማቅረብ ለመጠየቅና የእሱን ጥያቄ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ የሚያደርግ ወይም ለጥያቄው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ዕውቅናና ጥበቃ የሚሰጥ ውሣኔ የማግኘት መብት ያለው መሆኑን የሚደነግግ እና ሰፊ ትርጉምና ማዕቀፍ ያለው ድንጋጌ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ አንድ ጉዳይ በፍርድ የሚያልቅ ጉዳይ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን የህገ



www.chilot.me

መንግስቱ አንቀጽ 13/2/ በሚደነግገው መሠረት አገሪቱ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶችና የሌሎች አገሮች ፍርድ ቤቶች ተሞክሮና ልምድና ለዳኝነት የቀረበውን ጉዳይ መሠረታዊ ባህሪ መመርመር ያስፈልጋል።

አንድ ጉዳይ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል ነው የሚባለው የክርክሩ መሠረታዊ ባህሪ በፍርድ ለመጨረስ አመች የሆነ ሲሆንና ተከራካሪዎቹ የሚከራከሩበት ጉዳይ ንድፈ ሃሳባዊ ወይም ምናባዊ የፈጠራ ታሪክ ላይ የተመሠረተ ሣይሆን በነባራዊ ዕውነታና ተጨባጭ በሆነ ችግር ወይም ክስተት መሠረት ያደረገ የመብት ወይም የሃላፊነት ጥያቄ ሲሆን እንደሆነ በህግ መዝገብ ቃላት “Justiciable matter“ ለሚለው ቃል ከተሰጡት ትርጉም ለመረዳት የሚቻል ሲሆን በህገመንግስቱ አንቀጽ 37 የተደነገገው ፍትህ የማግኘት መብት አገራችን ካፀደቃቻቸው ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀፅ 1 እና የአፍሪካ የሰዎችና የህዝቦች መብት ቻርተር አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘትና ትርጉም ጋር በተጣጣመ መንገድ ግንዛቤ ሊያዝበት የሚገባው ነው። በተለይም የህገ መንግስቱ አንቀጽ 37 የተደነገገው ፍትህ የማግኘት መብት የአፍሪካ የሰዎችና የህዝቦች መብት ቻርተር “Every individual Shall have the right to have his cause heard. This comprisises the right to appeal to competent national organs against acts of violating his fundamental rights as recognized and guaranteed by conventions, laws, regulations and custom in force“ በማለት በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ ከተደነገገው ድንጋጌ ጋር በተጣጣመ መንገድ ግንዛቤ ሊያዝበትና ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው ነው የሚል ሃሳብ አለኝ።

ከዚህ አንፃር ስመረምረው አመልካችና ተጠሪዎች የሚከራከሩበት ጉዳይ ተጠሪዎች በተከራይነት ወይም ተከራዩችን በመወከል ለረዥም ጊዜ ይዘው ሲጠቀሙባቸው የነበሩና ንብረትነታቸው የአመልካች የሆኑ ቤቶች የአመልካቹ ድርጅት ሥራ አመራር ቦርድ በ94ኛ መደበኛ ስብሰባው ባሣለፈው ውሣኔ መሠረት በሙሉ ተከራይነት የመያዝና ከአመልካች ጋር የኪራይ ውል የመዋዋል መብት አላቸው ወይስ የላቸውም? አመልካች የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ 94ኛ መደበኛ ስብሰባ ያሣለፈውን ውሣኔ ሲያስፈፅም ተጠሪዎችን በእኩል ደረጃ ከሌሎች በተመሳሳይ ውሣኔ ተጠቃሚ ከሆኑ ሰዎች በመለየት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ በማስፈፀም ሂደት የፈፀመው አድሎ አለ ወይስ የለም? የሚለው ጭብጥ ነው ይህ ክርክር በመሠረታዊ ባህሪው የፖሊሲ ጥያቄ የማያስነሣና ፖለቲካዊ የሆነ ጉዳዩችን ያላካተተ በተቃራኒው የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርዱ የሰጠው ውሣኔ አመልካች ያለአድሎ ወጥነት ባለው ሁኔታ አስፈፅሟል ወይስ አላስፈፀመም ተጠሪዎች በሥራ አመራር ቦርድ 94ኛ መደበኛ ስብሰባ በሰጠው ውሣኔ ተጠቃሚ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚሉትን ነጥቦች የማጣራትና አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በመመርመርና በመመዘን ውሣኔ ሊሰጥበት የሚችል ጉዳይ ነው። አመልካች ድርጅት የመንግስት የልማት ድርጅት መሆኑ አመልካችና ተጠሪዎች የሚከራከሩበትን ጉዳይ “በፍርድ የማያልቅ ጉዳይ” “non Justiciable matter“ አያደርገውም። ስለሆነም የተጠሪዎችን ክስ በመቀበል በአመልካች በኩል የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ በመስማትና በመመዘን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ መስጠታቸው ጉዳዩ በመሠረታዊ ባህሪው በፍርድ የሚያልቅ / Justiciable matter/ በመሆኑ ትክክል ናቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በሚል ምክንያት ከሙያ ባልደረቦቹ በሃሳብ ተለይቻለሁ።

2. ሁለተኛው ነጥብ ተጠሪዎች አመልካችን በፍርድ የሚጠይቁበት ከህግ ወይም ከውል የመነጨ መብት የላቸውም በማለት አብላጫው ድምፅ የሰጠው ትርጉም በተለይ አመልካች ከተቋቋመበት ዓላማና መሠረታዊ ባህሪ አንፃር መታየት ያለበት ነው የሚል እምነት አለኝ።



www.chilot.me

ተጠሪዎች የአመልካችን ቤት የያዙት አመልካች በህጋዊ መንገድ ላከራያቸው ሰዎች ገንዘብ በመክፈልና የተከራይ ተከራይ በመሆን ወይም የተከራዩቹ ወኪል በመሆን እንደሆነ በበታች ፍርድ ቤቶች በተጠሪዎችና በአመልካች በኩል ከተደረገው ክርክርና ፍርድ ቤቶቹ ከደረሰቡት መደምደሚያ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በግለሰቦች መካከል የተደረገው የቤት ኪራይ ውል ወይም የቤት ተከራይ የሚያደርገው አከራይ ውል ወይም በግለሰብና በአንድ የንግድ ድርጅት መካከል የሚደረግ የቤት ኪራይ ውልና የተከራይ አከራይ ውል እና የኪራይ ውሉን ተፈፃሚነት በተመለከተ ተከራዩ በወኪል ስለሚፈፅማቸው ተግባራት በአራከዩና በተከራዩ ወይም በአከራዩና የተከራይ ተከራይ በሆነው ሰው መካከል አለመግባባት ቢፈጠር ወይም በአከራዩ እና በተከራዩ ወኪል መካከል አለመግባባት ቢፈጠር አለመግባባቱን አግባብነት ያላቸውን ስለቤት ኪራይና ስለእንደራሴነት የሚደነግጉትን የፍታብሔር ህግ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ እልባት የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ የተጠሪዎች ጥያቄ በፍታብሔር ህጉ ስለ እንደራሴነትና ስለቤት ኪራይ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ የማይወሰንበት ዋነኛው ምክንያት አመልካች የመንግስት ልማት ድርጅት መሆኑና አመልካች የተቋቋመበት ዋናው ዓላማ እንደማንኛውም የግል የንግድ ድርጅት ያሉትንና የሚሰራቸውን ቤቶች ከፍተኛ ዋጋ ለሚያቀርብለት ሰው እያከራየ ገንዘብ መሰብሰብ ሣይሆን የመንግስት መሠረታዊ የፖሊሲ ሃሳብና መመሪያን መሠረት በማድረግ ያለውን የቤት እጥረት ለማቃለል የተቋቋመ መሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 59/1968 ና በአዋጁ ከተደነገገው የድርጅቱ መሠረታዊ ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም አመልካች የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት የሚችሉ ግልፅ የአሠራር ሥርዓቶችን በመቀየስ የቤት ኪራይ ግልጋሎት የሚሰጥባቸውን መመዘኛዎች በማውጣት መመዘኛውን ለሚያሚሉ ሰዎች በቅደም ተከተል ክፍት ቤት ሲኖረው የማስተናገድ ግዴታና ሃላፊነት አለበት፡፡ አመልካች በሕዝብና በመንግስት ሃብት የተቋቋመ የልማት ድርጅት በመሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 3 እና በህገመንግስቱ አንቀጽ 13/2/ መሠረት በአፍሪካ የሰዎችና የህዝቦች መብት ቻርተር አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀጽ 3 "Every individual Shall have the right to access to public property and service in strict equality of all persons before the law" በማለት ከሚደነግገው ድንጋጌ ጋር በተጣጠመ መንገድ ግልፅ የሆነ አሰራርና መመዘኛ መሠረት በማድረግ መመዘኛውን የሚያሟላ በቅድም ተከተል የማስተናገድና እኩል ግልጋሎት የመስጠት ግዴታ ይኖርበታል የሚል እምነት አለኝ፡፡

አመልካች ቤት በኪራይ ማግኘት የሚፈልጉ ሁሉንም ዜጎች ጥያቄ ለማስተናገድ አቅም የሌለው መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ሆኖም አመልካች ያሉትን ቤቶች የሚያከራይበትንና የተከራዩ ሰዎችንም የሚያስለቅቅበትን ግልፅ የሆነ መስፈርትና የአሠራር ሥርዓት መዘርጋትና የአሠራር ሥርዓቱ ቤት እንዲከራዩ የሚፈቅድላቸውና መመዘኛ መስፈርቱን የሚያሟሉ ሰዎች በቅድም ተከተል በእኩል ደረጃ የኪራይ ግልጋሎት እንዲያገኙ የማድረግ የመመዘኛ መስፈርቱን የማያሟሉ ሰዎች ያገኙት የነበረውን የኪራይ ግልጋሎት የማቋረጥ ግዴታና ኃላፊነት አለበት፡፡ ይህም ማለት አመልካች የኪራይ ውል ሲዋዋልም ሆነ የኪራይ ውሉን ሲያቋረጥ ግልፅ የሆነ የአሠራር ሥርዓትና የመመዘኛ መስፈርቶችን የመጠቀምና በቅደም ተከተል መስፈርቱን የሚያሟሉትን በእኩል ደረጃ የማስተናገድ ግዴታ አለበት፡፡ አመልካች እንደማንኛውም የግል የንግድ ድርጅት የመዋዋል ነፃነት /Freedom of contract/ አለኝ በማለት የሚያቀርበው ክርክር ድርጅቱን መሠረታዊ ባህሪና የተቋቋመበትን ዓላማ እንደዚሁም የህገመንግስቱን አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 3 እና የህገመንግስቱ አንቀጽ 13/2/ መሠረት በማድረግ በአፍሪካ የሰዎችና የህዝቦች መብት ቻርተር አንቀጽ 13 /3/ በማክበር አገሪቱ የገባችው ቃልኪዳን ጋር የሚጣጣም ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በህገመንግስቱ አንቀጽ 12 ንዑስ ቁጥር 1 እና 2 የተደነገገውን የግልፅነትና የተጠያቂነት

መርህ አገልግሎቱን በሚሰጥበት ጊዜ ሁሉ ሊያከብርውና ሊመራበት የሚገባው ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

ከላይ የገለፅኳቸውን መሠረታዊ ሃሰቦች ይህ የአመልካችና የተጠሪዎች ክርክርና በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሣኔ ስመረምረው አመልካች የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ ጥቅምት 3 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት ከተጠሪዎች ቤት በያዙበት ተመሳሳይ ሁኔታ ቤት ይዘው የሚገኙና ተመሳሳይ መስፈርት የሚያሟሉ ሰባት መቶ ሁለት ሰዎች የያዙትን ቤት በቋሚነት ተከራይተው ለመኖር እንዲችሉ በመፍቀድ የኪራይ ውል ተዋውሏል፡፡ ተጠሪዎች የሥራ አመራር ቦርዱ ጥቅምት 3 ቀን 1998 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያወጣቸውን መስፈርቶች የሚያሟሉና አመልካች በቦርዱ ውሣኔ ለመፈፀም ባለመፈለጉ ብቻ ተጠሪዎች እንደ ሌሎቹ ሰባት መቶ ሁለት ሰዎች የኪራይ ግልጋሎት የማግኘት መብታቸውን በእኩል ደረጃ ሳይከበርላቸው የቀረ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ በማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ያለበቂ ምክንያት ተጠሪዎች እንደሌሎቹ ሰባት መቶ ሁለት ሰዎች የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ ጥቅምት 3 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ መከልከሉ ከላይ የጠቀሳቸውን የህገመንግስት ድንጋጌዎች የሚጥስና የድርጅቱን ተፈጥሯዊ ባህሪና ዓላማ የሚቃረን አድሏዊ የሆነ አሠራር ነው፡፡

አመልካች የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ ጥቅምት 3 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት ተጠሪዎች ከሌሎቹ ሰባት መቶ ሁለት ሰዎች ጋር በእኩል ደረጃ ማስተናገድና ግልጋሎት እንዲያገኙ ማድረግ ሲገባው ተጠሪዎችን ያለበቂ ምክንያት ሲያጉላላ ቆይቶ ከአንድ ዓመት በኃላ የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ ጥቅምት 10 ቀን 1999 ዓ.ም በ105ኛ መደበኛ ስብሰባው ያስተላለፈውን ውሣኔና መስፈርት አያሟሉም በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ ድጋፍ ያለው አይደለም፡፡ ስለሆነም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች የሥራ አመራር ቦርዱ ጥቅምት 3 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ የድርጅቱን ቤቶች የተከራይ ተከራይ በመሆን ወይም የተከራይ ወኪል በመሆን ይዘው ለረዥም ጊዜ የኖሩ ሰዎች በህጋዊ ተከራይነት የአመልካችን ግልጋሎት የሚያገኙበትን መስፈርትና መመዘኛ የሚያሟሉ ሆነው እያለ ተጠሪዎችን ከሌሎቹ ሰባት መቶ ሁለት ሰዎች ጋር በአኩል ደረጃ አለማስተናገዱ ህጋዊ አይደለም ተጠሪዎችን ከሌሎቹ ሰባት መቶ ሁለት ሰዎች ጋር በእኩል ደረጃ ማስተገድ ይኖርበታል በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም የሚል እምነት ስላለኝ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

በአጠቃላይ ጉዳዩ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል / Justiciable matter/ በመሆኑና የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች ከተጠሪዎች ጋር ተመሳሳይ መመዘኛና መስፈርት የሚያሟሉ ሰባት መቶ ሁለት ሰዎች የሥራ አመራር ቦርዱ ጥቅምት 3 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት አስተናግዶ ተጠሪዎችን የቤት ኪራይ ግልጋሎት እንዳያገኙ ያለበቂ ምክንያት የከለከላቸው መሆኑን በማጣራትና በማስረጃ በማረጋገጥ አመልካች አገልግሎቱን ለተጠሪዎች በእኩል ደረጃ እንዲሰጥ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም የሚል እምነት ስላለኝ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

**የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት**

ም.አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 47617

ህዳር 30 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ቄስ ገ/ሚካኤል አለምነው - ጠበቃ ታደሰ ወ/ጊዮርጊስ ቀረበ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ መልኬ ደምሴ ቀረበች

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከሕግ ውጪ የተያዘብኝ ቤት ይለቀቅልኝ በማለት ተጠሪ በአመልካች ላይ በመሠረተችው ክስ መነሻነት የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ በተጠሪ ክስ እንደተገለጸው አመልካች ቤቱን አለቅም ያለው ከተጠሪ አውራሽ ላይ በውል ገዝቼ ነው የያዝኩት በማለት ነው፡፡ ተጠሪ ይህን ሁኔታ በማወቅዋም ውሉ በሕጉ የተመለከተውን መስፈርት /ፎርማሊቲ/ አሟልቶ የተደረገ አይደለም የሚል የመከራከሪያ ነጥብ በክስዋ አንስታለች፡፡ በመጨረሻም የጠየቀችው ዳኝነትም ውሉ በሕግ ውጤት የለውም እንዲባል እና አመልካችም ቤቱን እንዲያስረክቧት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ለክሱ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የስረነገር የመከራከሪያ ነጥቦችን አንስቶአል፡፡ ከመቃወሚያዎቹ አንዱ ክሱ በፍ/ብ/ሕግ ቁ.1000 መሠረት በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የሚል ሆኖ ሥረ ነገርን በሚመለከትም ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም፡፡ የገዛሁት ጅምር ቤት ስለነበር በእንጨት ተሰርቶ የነበረውን ጅምር በማፍረስ ህንፃ ሠርቻለሁ፡፡ እንደከሳሽ ጥያቄ ቤቱን አስረክብ ብባል የማስረክበው የገዛሁትን ሳይሆን በራሴ ገንዘብ የሠራሁትን ህንፃ ነው የሚሉትን መከራከሪያዎች አቅርቦአል፡፡ ይህን የመሰለ ክርክር የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአንድ በኩል ለይርጋ መቃወሚያው አግባብነት አለው ተብሎ የተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1000 በወራሾች መካከል ለሚነሳ ክርክር ነው አግባባነት የሚኖረው በማለት በሌላ በኩል ደግሞ የሺያጭ ውሉ በተደረገበት እና ክሱ በቀረበበት መካከል ያለው ጊዜ ሰባት ዓመት በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1845 ከተቀመጠው የጊዜ ወሰን አንፃር ሲታይ ይርጋው አላለፈም የሚል ምክንያት በመስጠት የአመልካችን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በሥረ ነገር ረገድ የቀረበው ክርክር የሽያጭ ውሉ በፍ/ሕ/ቁ. 1723 የተመለከተውን መስፈርት ወይም /ፎርም/ አያሟላም የሚል ምክንያት በመስጠት ብቻ ውድቅ አድርጐታል፡፡ በእርግጥ አመልካች በቤቱ ላይ ወጪ አድርጌአለሁ ካለ ወጪው እንዲመለስለት ስለ አላግባብ መበልፀግ በሚመለከቱት የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የመጠየቅ መብቱ ተጠብቆአል የሚል ትችት በውሳኔው መጨረሻ ላይ አስፍሮአል፡፡ በመጨረሻም



www.chilot.me

በክሱ የተመለከተውን ቤት አመልካች ለተጠሪ እንዲያስረክብ ወስኖአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔውን አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሐምሌ 17 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው አመልካች የገዛሁትን ጅምር ቤት በመገንባት ህንፃ ሠርቻለሁ በማለት ያቀረበው ክርክር እና ማስረጃ የመታለፉ አግባባነት ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

እንደምንመለከተው ክርክሩ የተነሳው በወራሾች መካከል ባለመሆኑ እና ክሱም የቀረበው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1845 የተመለከተውን የይርጋ ወሰን ከማለፉ በፊት ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ረገድ በመረጋገጡ አመልካች ያቀረበው የይርጋ መቃወሚያ በሥር ፍ/ቤቶች ውድቅ የተደረገው በአግባቡ ነው፡፡ ወደ ጉዳዩ ሥረ ነገር ስንመጣ ተጠሪ ቤቱን ልረከብ የምትለው የቤት ሺያጭ ውሉ ሕጋዊ አይደለም ወይም የተደረገው ከሕግ ውጪ ነው በማለት እንደሆነ ነው የምንገነዘበው፡፡ ውሉ ውጤት የለውም ለማለት የሰጠችው ምክንያትም በፍ/ብ/ሕግ ቁ.1723 የተመለከተውን የውል አጻጻፍ ፎርም አያሟላም በማለት ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሕጉ አራተኛ መጽሐፍ አንቀጽ 12 በምዕራፍ 3 ሥር ስለግዴታዎች መቅረት በሚመለከት ዝርዝር ድንጋጌዎች ተቀምጠዋል፡፡ የዚህ ምዕራፍ ክፍል 1'ም' ውሎችን ስለመሰረዝና ስለማፍረስ በሚል የተደነገገ ሲሆን በዚህ መዝገብ ለያዝነው ጉዳይ አወሳሰን ተገቢነት ያለው በዚህ ክፍል ሥር ከተካተቱት ድንጋጌዎች አንዱ የሆነው በቁጥር 1808 የተመለከተው ድንጋጌ እንደሆነም እንገነዘባለን፡፡ በዚህ ድንጋጌ ንኡስ ቁ(2) እንደተመለከተው ውሉ ለውሉ አጻጻፍ የተደነገገውን ፎርም አልጠበቀም የሚል መከራከሪያ ያለው ተዋዋይ ወገን ወይም ማንኛውም ከውሉ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ጥቅም ያለው ሰው ውሉ እንዲሰረዝ ለመጠየቅ ይችላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ በእርግጥ ተጠሪ ውሉ ይሰረዝልኝ የሚል ክስ ባትመሰርትም የውሉን መኖር ተገንዝባ ለውሉ አጻጻፍ የተደነገገውን ፎርም አልጠበቀም የሚል መከራከሪያ አንስታለች፡፡ አመልካች ደግሞ ውሉ ሳይነካ በራሴ ጥረት እና ገንዘብ የሠራሁትን ቤት ይገፔ መቅረት አለብኝ በማለት ተከራክሮአል፡፡ በዚህ ምክንያትም አመልካች ቤቱን ለተጠሪ ሊያስረክብ ይገባል ወይስ አይገባም በሚለው ነጥብ ላይ ውሳኔ ከመስጠት በፊት ውሉ የሚሰረዝ ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ጭብጥ ላይ ውሳኔ መስጠት አግባብ ይሆናል፡፡ በዚህ አካሄድ በመጨረሻ ውሉ ይሰረዛል የሚባል ቢሆን እንኳ አመልካች ቤቱን አስረክበህ ሂድ የሚባልበት አግባብ ይኖራል ማለት አይደለም፡፡ በፍ/ብ/ሕግ/ቁ 1815 (1) እንደተደነገገው ውል ሲሰረዝ ወይም ሲፈርስ ተዋዋዮቹ በተቻለ መጠን ውሉ ከመደረጉ በፊት እንደነበሩት ሁኔታ እንዲመለሱ የግድ ነው፡፡ በዚህ መንገድ መፈፀም ካልተቻለም በፍ/ብ/ሕግ ቁ1817 የተመለከተውን ደንብ መከተል እንደሚገባ ሕጉ ያመለክታል፡፡

ጉዳዮን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የፌዴራል መጀመያ ደረጃ ፍ/ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት ከጅምሩ ውል እንደሌለ በመቁጠራቸው የውልን መፍረስ ወይም መሠረዝ ተከትሎ ስለሚኖረው ውጤት በተመለከተ ውሳኔ ሊሰጡ አልቻሉም ተጠሪ ልረከብ የምትለው ቤት እኔ የሰራሁት ነው የሚለው የአመልካችን ክርክር በጭብጥነት ይዘው በማስረጃ ሳያጣሩ ያለፉትም በዚህ ምክንያት ነው የሚመስለው፡፡ እንደ ሕጉ ከሆነ ግን ክርክሩ የውል መፍረስ ወይም መሠረዝንም የሚመለከት በመሆኑ ቀጥሎ ስለሚመጣው ውጤት በተመለከተ ተገቢውን መወሰን ይቻል ዘንድ በእርግጥ ቤቱ አመልካቹ የሠራው ነው? ቤቱ በጅምር የነበረ ነው ከተባለስ አመልካች ምን ያህሉን ሠራ፣ ወዘተ የሚሉትን ነጥቦች አስቀድሞ በማስረጃ ማንጠር አስፈላጊ ነው የሚሆነው፡፡ ይህ ሁኔታ



www.chilot.me

በሕጉ አግባብ ውል ይፈርሳል ወይም ይሰረዛል የሚል ውሳኔ ቢሰጥ ሊከተል ስለሚገባው ውጤት ወሳኝ ሚና የሚኖረው የፍሬ ነገር ጉዳይ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ክርክሩን በዚህ አግባብ አልመሩም፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በሕጉ አተገባበር /አተረጓጐም/ ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 08007 ሚያዝያ 7 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 80087 ሐምሌ 7 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክሩን በተከፈተው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት ሠርቼ ያጠናቀቅሁት እኔ ነኝ በማለት አመልካች ያቀረበውን ክርክር ተጠሪ ከምታቀርበው ክርክር ጋር በማገናዘብ እንዲያጣራ በመቀጠልም በፍሬ ነገር ረገድ ያጣራውን መሠረት በማድረግ በአጠቃላይ የክርክሩ ውጤት ላይ ተገቢውን ይወስን ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 343(1) መሠረት መልሰንለታል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 49041

ኀዳር 2 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሓጐስ ወልዱ

ሻገረ ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የአ/አ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መ/ቤት ነ/ፈጅ ማህሌት ዳዊት ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1ኛ. አቶ ኤሣው መዓዛ

2ኛ. አቶ ዘርሁን ሙላት

3ኛ. ወ/ሮ ተስፋነሽ ተሰማ

} ጠ/መስፍን ደምሴ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የዋስትና ግዴታን የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው ክስ የቀረበው በአመልካች በኩል ነው፡፡ የክሱ ይዘት ባጭሩ ሲታይ 1ኛ ተጠሪ የአመልካች ሰራተኛ ሁኖ ለ7 ዓመታት ያህል ትምህርት እንዲከታተል እና ትምህርቱን ሲያጠናቅቅ ለ6 ዓመት ያህል ለማገልገል ግዴታ ገብቶ ለ5 ዓመታት ያሕል ትምህርቱን ከተከታተለ በኂላ ባልታወቀ ምክንያት ትምህርቱንና ሥራውን ስላቋረጠ ለትምህርት የወጣውን ወጪ እንዲተካ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች (ተጠሪዎችም) ለዚሁ ውል አፈፃፀም እስከ ብር 50,000 ድረስ የዋስትና ግዴታ የገቡ ስለሆነ ክስ የቀረበበትን ብር 29,497.03 ባልተነጣጠለ ሃላፊነት እንዲከፍሉ እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ የመረመረው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ(ተጠሪ) ክስ የቀረበበትን ገንዘብ እንዲከፍል ሲወስን፣2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የዋስትና ግዴታ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1925/2/ መሰረት አስቀድመው አስቀርተዋል በሚል ከክሱ በነፃ እንዲሰናበቱ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካራከረ በኂላ የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ በፍርድ አጽንቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የሥር ፍ/ቤቶች የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1925/2/ የሰጡት ትርጉም መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ነው በማለት እንዲታረም ጠይቋል፡፡



www.chilot.me

የሰበር ችሎቱም አቤቱታውን መርምሮ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1925/2/ መሰረት ከዋስትና ግዴታቸው ነፃ ናቸው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ አዝዟል፡፡

የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጠበቃ የካቲት 29 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ በይዘቱም ተጠሪዎች የገቡት ግዴታ ወደፊት ይደርሳል ተብሎ ለሚታሰብ ሁኔታ ስለመሆኑ ጠቅሶ ይህ ሃላፊነት ከመድረሱ በፊት የዋስትና ግዴታቸውን ማውረዳቸው በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1925/2/ የሚሸፈን ስለመሆኑ በመግለጽ በዝርዝር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የዚህ ሰበር ችሎት ውሳኔ የሚያሳየው ነጥብ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የዋስትና ግዴታ አውርደዋል ተብሎ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 125/2/ ተጠቅሶ የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ወይንስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ከግራ ቀኙ ክርክር ላይ እንደተረዳነው 1ኛ ተጠሪ በአመልካች እስፖንሰርንት ከፍተኛ ትምህርት ተከታትሎ አጠናቆ ሲመለስ ለ6 ዓመት ለማገልገል፣ ይህንን ካልፈፀመ ደግሞ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ያወጣውን የትምህርት ወጪዎች ሊተካ የውል ግዴታ የገባ ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችም 1ኛ ተጠሪ በውል የገባውን ግዴታ ካልፈፀመ እስከ ብር ሃምሣ ሺህ ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ለመክፈል የዋስትና ግዴታ መፈረማቸውም አላከራከረም፡፡

በዚሁ አግባብ አመልካች ይህንኑ ውለታ መነሻ በማድረግ 1ኛ ተጠሪ እንደውሉ ግዴታውን ባለመፈፀሙ ተጠሪዎች በአንድነትና በነጠላ ብር 29,497.03 እንዲከፍሉ እንዲወሰን ዳኝነት በመጠየቁ የሥር ፍ/ቤትም 1ኛ ተጠሪን ሃላፊ በማድረግ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

በሌላ በኩል 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የዋስትና ግዴታ ውል የገቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1925/2/ መሰረት የዋስትና ግዴታቸውን አስቀድመው አውርደዋል በሚል ከክሱ በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡

የሥር ፍ/ቤት ለውሳኔው ምርኩዝ ያደረገው የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1925/2/ ወደፊት ስለሚሆን ወይም በአንድ ዓይነት ሁኔታ ስለሚመጣ ግዴታ ዋስ ስለመሆን አስመልክቶ የዋስትና ግዴታው ለስንት ጊዜ እንደሚረጋ በስምምነቱ ያልተመለከተ እንደሆነ የዋናው እዳ ተጠያቂነት ከመድረሱ በፊት ዋሱ ዋስትናውን ሊያስቀር እንደሚችል ያመለክታል፡፡

ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መረዳት የሚቻለው ዋናው ግዴታ ወደፊት ሊደርስ ወይም ላይደርስ በሚችል ሁኔታ ላይ (uncertain event) የተመሰረተ በሆነ ጊዜ ዋሱ ዋናው ግዴታ ከመድረሱ በፊት የዋስትና ግዴታውን ማስቀረት የሚችልበት አግባብ ስለመኖሩ ነው፡፡

የዚህ ድንጋጌ መንፈስ ዋናው ግዴታ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ሊፈጸም የሚችል ስለመሆኑ ከይዘቱ መረዳት ይቻላል፡፡



www.chilot.me

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የአመልካች ግዴታ 1ኛ ተጠሪ ከሥራ ውጪ ሆኖ ትምህርት እንዲከታተል መፍቀድ እና ለትምህርቱም አስፈላጊውን ወጪ መሸፈን ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ደግሞ ትምህርቱን ተከታትሎ እንዳጠናቀቀ በውሉ ለተመለከተው ጊዜ ያሕል ለአመልካች አግልግሎት መስጠት አሊያም ለትምህርት የወጣውን ወጪ መተካት ስለመሆኑ ከግራ ቀኙ ክርክር መረዳት ተችሏል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የዋናው ውል ግዴታ ወደፊት በሚደርስ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ እርግጠኛ ያልሆነ (uncertain event) ሁኔታ ላይ የተንጠለጠለ ነው ተብሎ በፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 1925 ሥር የሚሸፈን አለመሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው ዋና ግዴታ ወደፊት ሊደረስ ወይም ላይደርስ የሚችል ሁኔታ (conditional) ነው የማይሰኝ ነው ከተባለ ደግሞ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የዋስትና ግዴታ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1925/2/ መሰረት የዋናው ግዴታ ተጠያቂነት ከመድረሱ በፊት አስቀርተዋል ተብሎ ተቀባይነት ሊያገኝ አይችልም፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች 2ኛ ና 3ኛ ተጠሪዎች የዋስትና ግዴታ የ1ኛ ተጠሪ ግዴታ ከመድረሱ በፊት ቀሪ ሆኗል በሚል ምክንያት ተጠሪዎች አላፊነት የለባቸውም ሲል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1925/2/ በመጥቀስ የሰጠው ፍርድ የድንጋጌውን ይዘትና መንፈስ በአግባቡ ያላገናዘበና የግራ ቀኙን የውል ግዴታ በውል ያላመነ ስለሆነ ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

ስለሆነም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 110168 በ01/09/2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 70425 በ16/10/2000 ዓ.ም የተሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በገቡት የዋስትና ግዴታ ውል መሰረት ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ለአመልካች የመክፈል ግዴታ አለባቸው ብለናል፡፡
3. የሥር ፍ/ቤት በዚሁ መሰረት ያስፈጽም፡፡ ይፃፍ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 52106

ህዳር 13/2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማህበር ነ.ፈጅ አቶ ብርሃኑ ልኪሣ ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- አቶ ታደሰ አደሬ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ አንድ የተሸጠ የሚንቀሣቀስ ንብረት ከመሸጡ በፊት በነበረ የፍ/ቤት ዕገዳ ምክንያት ገዥው በባለቤትነት መብቱ መገልገል ሣይችል ቢቀር በሻጩ ላይ ሊኖር የሚችለው ኃላፊነት ምንድን ነው የሚለውን ነጥብ በሚመለከት በሻጭና በገዥ መካከል በተነሣው የሕግ ክርክር ላይ ያተኮረ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ በኦሮሚያ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ባጭሩ፡

ሳምሶን ነጋሽ በሚባል ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን ፊያት የጭነት መኪና ሚያዚያ 28 ቀን 1998 ዓ.ም በብር 58,000.00 ሸጠልኛል፡፡ ሆኖም የፍ/ቤት ዕግድ ስላለበት የንግድ ፈቃድ፣ ቦሎ እና ታርጋ በማውጣት እንደባለቤት በንብረት አገልግሎት ማግኘት አልቻልኩም ጥቅም ተቋርጦብኛል፡፡ ስለሆነም የተቋረጠ ጥቅም በወር 7000.00 /ሰባት ሺህ ብር/ እንዲከፍለኝና ስመሐብትነቱንም ወደ እኔ ይዙርልኝ የሚል ክስ አቅርቦበታል፡፡

የአሁን አመልካችም በተከሣሽነት ቀርቦ ባለቤትነትን የሚያረጋግጡ ሰነዶችንና ሊብሬውን አስተላልፈናል፡፡ በከፍተኛው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን የዕግድ ትእዛዝ ያስነሳን ሲሆን በወረዳው ፍ/ቤት የነበረውን ግን ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ለማስነሣት አልቻልንም የሚለውንና ከይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የውሣኔ ግልባጭ መረዳት እንደሚቻለውም በዕገዳ ምክንያት መኪናው ያለሥራ አልቆመም፤ ዕግድ ያለበት መሆኑንም እያወቀ ስለገዛ ኃላፊነት የለብንም የሚሉትን ከኃላፊነት ጋር የተያያዙ ክርክሮችን ካቀረበ በኋላ ስለተቋረጠ ጥቅም መጠን አስመልክቶ ደግሞ የተቋረጠው ጥቅም መጠን በማስረጃ ያልተረጋገጠ በመሆኑ አይታመንም በማለት ግልጽ መልስ ሰጥቷል፡፡



www.chilot.me

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ተቋረጠ ስለተባለው ጥቅም ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ ይችል ዘንድ ከበከልቻ ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር ማረጋገጫ እንዲቀርብ ካደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ፣

ተከሣሽ የአሁን አመልካች ለተቋረጠ ጥቅም ኃላፊነት አይኖርብኝም ሲል ያቀረባቸው ምክንያቶች ተቀባይነት የላቸውም የተቋረጠ ጥቅምን በሚመልከት የትራንስፖርት አክሲዮን ማህበሩ ከሣሽ ከገለፀው መጠን በላይ ሆኖ ስለተገኘ ከሣሹ ያቀረበውን መጠን የስሌት መነሻ በማድረግ የሽያጭ ውሉ ከተደረገበት ሚያዚያ 28 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ስመ ሀብትነቱ ወደ ከሣሽ ዞሮ ሥራ እስከሚጀምርበት ጊዜ ድረስ በወር 7000.00 /ሰባት ሺህ ብር/ ተከሣሽ ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በይግባኝ ደረጃ የሁለቱንም ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ

የሽያጭ ውሉ ከተደረገበት ከሚያዚያ 28 ቀን 1998 ዓ.ም በፊት ግንቦት 23 ቀን 1994 ዓ.ም የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ መኖሩን ከተረጋገጠ ሻጭ ቀድሞውኑ የዕግድ ትእዛዝ እንዳለበት ያውቃል፡፡ ስመሀብት የማዛወር ግዴታ ባይኖርበትም ይህንን ዕገዳ እያወቀ መሸጡ፡ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ነው በሽያጭ ውል ላይ ሻጭ አስፈላጊውን ትብብር ሁሉ ያደርጋል በሚል መገለፁ በሻጭ ላይ ያለውን ከሕግ የመነጨ ግዴታን የሚያስቀር አይሆንም መኪናው ስለመቆሙ አልተረጋገጠም ቢልም ስመሐብትነቱ በገዥው ስም እስካልዞረ ድረስ ያለስራ እንደቆመ ይቆጠራል ስለሆነም ኃላፊ ነው መባሉ ተገቢ ሲሆን፤ የደረሰውን የጉዳት መጠንንም ቢሆን በገለልተኛ ወገን የተረጋገጠው ከሣሹ ከጠየቀው በልጦ በመገኘቱ የተነሣ በከሣሽ በኩል የቀረበው መጠን መወሰዱ ስህተት አይደለም የሚሉትን መነሻ በማድረግ ውሣኔውን አጽንቷል፡፡

የሰበር ቅሬታ የቀረበውም በእነዚህ በየደረጃው የተሰጡት ውሣኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው ናቸው ይታረምልን በሚል ሆኖ የመከራከሪያ ነጥቡም በሥር ፍ/ቤቶች አቅርቧቸው ከነበረው በይዘቱ የተለዩ አይደለም፡፡

ተጠሪም በኃላፊነትም ሆነ በጉዳት ካሣ መጠን ረገድ የሰጠው ዳኝነት ሕግን መሠረት ያደረገ ነው ለሚለው ክርክሩ ውሉን አብራርቶ አቅርቧል፡፡

እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2341/2/ ላይ በተመለከተው መሠረት ከኃላፊነት ለመዳን ሲል ገዥው በንብረቱ ላይ የዕገዳ ትእዛዝ ያለበት መሆኑን እያወቀ ገብቷል የሚለውን ክርክር ያቅርብ እንጂ ይህ ክርክር ለሻጭ ጠቃሚ የሚሆነው ገዥው ተከስተ ባለው ጉድለት ሣቢያ የሽያጭ ውል  ይፍረስልኝ በሚል ክስ የቀረበበት እንደሆነ ስለመሆኑ በንዑስ ቁጥር 1 ላይ ተመልክቷል፡፡ የገዥ የአሁን ተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ ውል ይፍረስልኝ የሚል ሣይሆን ሻጭ ግዴታውን ከኪሣራ ጋር ይፈጽም የሚል ስለሆነ ቀጥተኛ አግባብነት የለውም፡፡ ገዥው የሚጠይቀው ዳኝነት አስገድዶ ማስፈፀምም ይሁን የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ይህ የሻጭ መከራከሪያ ነጥብ በሁለቱም ዓይነት ዳኝነቶች ያገለግላል እንኳ ቢባል ገዥ የአሁኑ ተጠሪ ንብረቱን በገዛበት ጊዜ በፍ/ቤት በተሰጠ ዕገዳ ምክንያት ሻጩ የእኔ ነው ከሚሉ ሦስተኛ ወገኖች መብት ሁሉ ነፃ የሆነ መኪና ለገዥው ማስረከብ የማይችል መሆኑን ያውቅ ነበር ወይስ አልነበረም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ተይዞ በሥር ፍ/ቤት በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ አይደለም በዚህ ነጥብ ላይ ማስረጃችንም አልታየልንም የሚል የሰበር ክርክርም የለውም፡፡ ገዥ ያውቅ ነበር በሚል በአባባል ደረጃ ከመግለጽ አልፎ ይህንን አባባል በማስረጃ አስደግፎ ማስረዳት

ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም በዚህ ሰበር ደረጃም ቢሆን ገዥ ያውቅ ነበር በሚል ብቻ ተወስኖ የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

እንዲሁም አመልካች አከራካሪ የሆነው የዕግድ ትእዛዝ በእሷ መዝገብ ላይ ስላልተሰጠ፤ የወረዳው ፍ/ቤትም ስለእግድ ጉዳይ ሲጠየቅ ዕግድ የለም በሚል ስለአረጋገጠ እና ገዥውም ዕገዳ ያለበት መሆኑን አስቀድሞ የማረጋገጥ ግዴታ ነበረበት የሚሉትን ነጥቦች በመጠቀስ ኃላፊነት የለብኝም ሲል ያቀረባቸው ክርክሮች ሻጩ የተሸጠው ንብረት ላይ የማያስነካ መብት ለገዥው ለማስተላለፍ አስፈላጊ ተግባሮችን ለመፈፀም ግዴታ ይኖርበታል በሚል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2281 እንዲሁም ውጤቱ የውል ማፍረስን ጉዳይ የሚመለከት ቢሆንም የገዛውን መብት በሚነካ ጉድለት ምክንያት ሻጭ የእኔ ነው ከሚሉ ሦስተኛ ወገኖች መብት ሁሉ ነፃ የሆነ ነገር ለገዥው የማስረከብ ግዴታ አለበት በሚል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2341 የተጣለበትን ከሕግ የመነጨ ግዴታ ያገናዘቡ ክርክሮች ባለመሆናቸው የሕግ መሠረት የላቸውም፡፡

አከራካሪው መኪና በፍ/ቤት ዕግድ ምክንያት ያለ ሥራ ቆሟል ወይስ በሥራ ላይ ነበረ የሚለውን ጉዳይ አስመልክቶ አመልካች በሰበር ደረጃ የተብራራ ክርክር ያቀረበ ቢሆንም ይህ የፍሬ ነገር ጉዳይ ለሥር ፍ/ቤት በማስረጃ ተደግፎ ሊያጥር የሚችል እንጂ የሕግ ክርክርን የሚያስነሳ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት አመልካች በሸጠው ንብረት ላይ አስቀድሞ በነበረ የፍ/ቤት ዕገዳ ምክንያት በገዥው ላይ ደረሰ ለተባለው የጥቅም መቋረጥ ኃላፊ ነው በሚል በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሆኖም በዚሁ በሻጭ የግዴታ ጉድለት በገዥው ላይ ደርሷል የተባለውን የጉዳት መጠን በሚመለከት የተሰጠው ውሣኔ በተጓዳኝ ገዥ እንዲህ ያለ ጉዳይ ባጋጠመ ጊዜ እርሱም በተቻለ መጠን ሊደርስ የሚችለውን ለይቶ የመቀነስ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ ከተመለከተው ድንጋጌ ጋር ተካቶ ሊታይ የሚገባው ነጥብ ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ የመኪና ሽያጭ ውል የተደረገው ሚያዚያ 28 ቀን 1998 በሕግ ገዥው ጉዳት ደረሰበኝ ካሣ ይከፈለኝ ሲል ክስ ያቀረበው ደግሞ መጋቢት 26 ቀን 1999 ዓ.ም ነው፡፡ ጉድለት ያለበት ንብረት ወይም ደግሞ ሙሉ የባለቤትነት መብት ለመገልገል የሚያስችል ጉድለት ያለበት ንብረት የተረከበ ገዥ ያለው የማስተካከያ መብት በፍ/ብ/ሕግ ከቁጥር 2336 ቀጥሎ ባሉት ድንጋጌዎች ተቀምጧል፡፡ ገዥው ወዲያውኑ ክስ አቅርቦ ውሉን ማስፈረስ ወይም ደግሞ ከቁጥር 2329 ጀምሮ ባሉት ድንጋጌዎች የተጓደለው ነገር ተሟልቶ ይፈፀም ዘንድ ወዲያውኑ መጠየቅ ከዚህ ጋር ጎን ለጎንም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2360 እንደተመለከተው ከላይ ከተመለከቱት የሕግ መፍትሄዎች በሻጭ ግዴታ መጓደል ምክንያት የደረሰበትን ጉዳት በገንዘብ አስልቶ መጠየቅ እንደሚገባው ተመልክቷል፡፡ በዚህ ጉዳይ ገዥው ይህንን በሕግ በተሰጠው መብቱ ሳይገለገል ለአንድ ዓመት ያህል እንደቆዩ መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ይህንንም ማድረግ መብቱ የሆነውን ያህል ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት በመቀነስ ረገድ ከባከነው ጊዜ አንፃር ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1802 እንደተመለከተው ግዴታው ይሆናል፡፡ ከዚህ አንፃር የደረሰውን የጉዳት ልክ አወሳሰን ከተያዘው ጉዳይ አንፃር በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1790፣1802 የተመለከተውን መሠረት በማድረግ ሊወስን ሲገባ ይህንን በገዥው በኩል የታየው የጥንቃቄ ጉድለት ሳይታይ የሽያጩ ውል የተደረገበትንና ዕግዱ የተነሣበትን ጊዜ መነሻ በማድረግ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091



www.chilot.me

በተመለከተው ድንጋጌ ብቻ በማየት ውሣኔ መስጠቱ በሥር ፍ/ቤቶች በጉዳት ካሣው አወሳሰን ረገድ ስህተት መፈፀማቸውን ተገንዝበናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1/ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት እንደቅደም ተከተሉ በመ/ቁ. 05183 21/6/2000 በመ/ቁ. 64263 በ22/04/02 የሰጡትን ውሣኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ አሻሽለን ወስነናል፡፡

2. አመልካች በተጠሪ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት ብለናል፡፡

3. የተከሰተውን ጉዳት በጊዜው እንዲስተካክል ማድረግ ሲገባ ይህን ካልፈፀመ ከተያዘው ጉዳይ አንፃር ጊዜ በረዘመ ቁጥር የጉዳቱ ስሌት በዚሁ ልክ እያደገ እንደሚሄድ ማወቅ ሲገባው ይህንን ሣያደርግ ያሳየውን የጥንቃቄ ጉድለት ሁሉ በማየት ለደረሰበት የጉዳት ልክ በርትዕ ብር 21,000.00 /ሃያ አንድ ሺህ/ ብር ይከፈለው ብለናል፡፡

በሥር ፍ/ቤት የተወሰነው ወጭና ኪሣራ ስሌቱ መሠረት ይኸው የጉዳት ገንዘብ ይሁን፤ በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ስለተሰጠው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 53968

ህዳር 13 ቀን 2003 ዓ.ም

***ዳኞች*** - ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

***አመልካቾች*** - 1. የምሥራቅ ወለጋ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ነገፈጅ አቶ በቀለ መንገሻ ቀረቡ

2. የምስራቅ ወለጋ ዞን ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ነገረፈጅ ድንቀለም ይኖሩ

***ተጠሪ፣*** አቶ ፀጋዬ ነጋ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

***ፍ ር ድ***

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የምስራቅ ወለጋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ስላመለከቱ ነው ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አንደኛው አመልካች በአዲስ ዘመን ባወጣው ጨረታ ተሣትፌ በማሸነፌና ሌሎች ፎርማሊቲዎችን በማሟላት ለጤና ኬላ የሚውሉ መሣሪያዎችን ሳቀርብ ተከሣሹ ዋጋቸውን ሊከፍል ውል ተዋውለናል፡፡ ሆኖም ተከሣሹ /አንደኛ አመልካች ሀምሌ 27 ቀን 1997 ዓ.ም ባደረግነው ውል መሠረት ላቀረብኩለት አስራ አራት ፍሪጅ ዋጋውን ከነተጨማሪ እሴት ታክሱ እንዲከፍለኝ ጠይቄ እስካሁን ያልከፈለኝ በመሆኑ ብር 340,621.96 /ሶስት መቶ አርባ ሺ ስድስት መቶ ሃያ አንድ ብር ከዘጠና አንድ ሣንቲም/ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ተጠሪ ክስ አቅርቧል፡፡ አንደኛ አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ ፍሪጁን ተረክቦ ለሁለተኛው ተጠሪ ያስረከበ መሆኑን ከገለፀ በኃላ ገንዘብ ያልከፈልነው ተጠሪ ያቀረበው ፍሪጅ በጨረታ ተወዳድሮ ያሸነፈበት ሣይሆን ሌላ አይነት ፍሪጅ በማቅረቡ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛው አመልካች በጨረታው ጣልቃ ገብ ተከራካሪ ሆኖ ቀርቦ ተጠሪው "Cibir Type " የሚባል ፍሪጅ ማቅረብ ሲገባው "Zero applience" የተባለ ፍሪጅ ነው ያቀረበው ሊከፈለው አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኃላ ተጠሪ ባቀረበው የጨረታ ሰነድ "Zero applience" የሚባለውን ፍሪጅ በመሞላት የተወዳደረ በመሆኑ በውሉ አስፈላጊው ሪፍሪጅሬተር የሚል አሻሚ ቃል ያለ በመሆኑ ተጠሪ ለማቅረብ የተስማማው "Zero applience" የተባለውን ፍሪጅ ነው ይህንን ፍሪጅ በውሉ መሠረት ያቀረበ በመሆኑና አስራ አራት ፍሪጅ ከሣሽ

/ተጠሪ/ ያስረከበ ስለሆነ ብር 340,621.95 ብር አመልካቾች ለተጠሪ እንዲከፍሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል አንደኛ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የአንደኛ አመልካችን ይግባኝ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሠርዞታል አመልካቾች የሰበር አቤቱታ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ሰበር ችሎት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካቾች መጋቢት 7 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በጨረታው ያቀረበው ስፔስፊኬሽንና አመልካቾች እንድንረከበው የጠየቀው ዕቃ አንድ አይነት አይደሉም ከዚህ በተጨማሪ በዋጋ ማቅረቢያው ተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት መሆኑን ሣያሣውቅ ከነተጨማሪ እሴት ታክሱ የዕቃውን ዋጋ እንድንከፍል ተወስኖለታል፡፡ ስለሆነም የክልሉ ፍርድ ቤቶች በየደረጃው የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል ተጠሪ በበኩሉ የአመልካቾች አቤቱታ የህግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑ የሰበር አቤቱታቸውን በመሰረዝ የሰበር ችሎት እንዲያሰናብተኝ የሚል ይዘት ያለው መልስ ያቀረበ ሲሆን አመልካቾች  የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራቀኙ በፅሑፍ ያቀረቡት ክርክር ይዘት በአጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካቾች ተጠሪ ያቀረበውን አስራ አራት ፍሪጅ በሙሉ ባለቤትነት በመቀበል ለተጠሪ የፍሪጁን ዋጋ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር እንዲከፍሉ የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ለተያዘው ጭብጥ እልባት ለመስጠት በመጀመሪያ የሥር ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍሬ ጉዳይ ደረጃ የደረሱበትን መደምደሚያ ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በጨረታ ሰነድ ሞልቶ ያቀረበው “Zero applience“ የሚባለውን ፍሪጅ መሆኑን ሁለተኛው አመልካችም “Zero applience” የሚባለው ፍሪጅ ተገቢውን አገልግሎት መስጠት የሚችልና ከተያዘው በጀት ጋር ዋጋው ተመጣጣኝ መሆኑን ገልፆ ለጨረታ ኮሚቴው ደብዳቤ የፃፈ መሆኑን በመዘርዘር ተጠሪ የተዋዋለው “Zero applience“ የተባለው ፍሪጅ በመሆኑና ይህንኑ ፍሪጅ በቁጥር አስራ አራት ያስረከበ በመሆኑ የፍሪጁን ዋጋ ከነተጨማሪ እሴት ታክስ አመልካቾች እንዲከፍል ወስኗል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት አመልካቾች ከተጠሪ ጋር ውል የተዋዋሉት “Zero applience“ የሚባለውን ፍሪጅ ለመግዛት መሆኑን በመግለፅ ትዕዛዝ ሰጥቷል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ተጠሪ በውሉ የተገለፀውን ዕቃ ያቀረበ መሆኑን በማረጋገጥ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አንደኛ አመልካች በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ለጨረታ የወጣው “Cibir Type“ የተባለውን ፍሪጅ ለመግዛት ነው የሚል ክርክር ያቀረበ ቢሆንም ተጠሪ በጨረታ ሰነዱ ሞልቶ ያቀረበው “Zero applience“ የሚባለውን ፍሪጅ ለማቅረብ እንደሆነ በየደረጃው ባሉ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ይህም ተጠሪ በሀራጅ ማስታወቂያው የተገለፀውን ፍሪጅ ሣይሆን ሌላ አይነት ፍሪጅ ለተጠሪ ለማቅረብ የጨረታ ሰነዱን ሞልቶ ሲያቀርብ አዲስ ድርድር እንዲደረግ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1694 መሠረት ሀሳቡን እንደገለፀ የሚያስቁጥር ሲሆን የጨረታ ኮሚቴው የሁለኛውን አመልካች ሃሳብና ስምምነት ከተቀበለ በኃላ ተጠሪን የጨረታው አሸናፊ መሆኑን በማረጋገጥ ውል መዋዋሉ ተጠሪ ያቀረበውን አዲስ ድርድር የተቀበለና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1695 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ውል የተዋዋሉ መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡

ስለሆነም ተጠሪ የጨረታ ሰነዱን የሞላው “Zero applience “ የሚባለውን ፍሪጅ መሆኑና አመልካቾችም ይህንኑ አውቀውና አምነውበት ተጠሪን ዕቃውን እንዲያቀርብ ውል የተዋዋሉ መሆኑና ተጠሪ በውሉ መሠረት አሥራ አራት “Zero applience“ ፍሪጅ ማስረከቡን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪዎች ይህ በክልሉ ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ ተገቢነት የለውም በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ለሰበር ችሎት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 የተሰጠውን ሥልጣን ያላገናዘበና የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካቾች ተጨማሪ እሴት ታክስ እንድንከፍል መወሰኑ አላግባብ ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር የአዋጅ ቁጥር 285/1994 ድንጋጌዎች እንደተሻሻለው ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባና የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ በአጠቃላይ አመልካቾች ከተጠሪ ጋር ባደረጉት ውል መሠረት የተረከቧቸውን አስራ አራት ሪፍሬጅሬተሮች ዋጋ ከነተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲከፍሉ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎትና ሰበር ችሎት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ሚያዚያ 13 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

ም.አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 54312

ኀዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ኃይላይ ተክላይ - ጠበቃ አቶ ገ/አምላክ ገ/ጊዮርጊስ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ሙቁር የጨው አምራቾች ኃላ/የተወ/የግል ማህበር ጠበቃ አቶ ሙሉጌታ ገብሩ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው በተጠሪ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 16 ላይ ስለ ውዝግብ አፈታት በሚል የተቀመጠው የደንብ ክፍል በማህበሩ አባላት መካከል የተነሣን ክርክር ብቻ ለመሸፈን ታስቦ የተቀረፀ ነው ወይስ በአባሉና በማህበሩ መካከል የሚነሳውንም ውዝግብ ሊጨምር የሚችል ነው? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ጋር በተያያዘ የአንቀፁ የተፈፃሚነት ወሰን በሚመለከት አግባብነት ያለውን ትርጉም ለመስጠት ሲባል ነው፡፡

የጉዳዩ መነሻ የአሁን አመልካች የማህበሩ አባል በማህበር ላይ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ሲሆን ይዘቱም ማህበሩ በንግድ ሕግ ባለበት ኃላፊነት መሰረት የማህበሩን የሂሳብ ሚዛን ለአባላት አላቀረበም፤ትርፍና ኪሣራም አላሳወቀም፡፡ በመሆኑም ማህበሩ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ያደረገውን እንቅስቃሴ የሚያሳዩ የሂሳብ ሪፖርት እንዲያቀርብ ትርፍና ኪሣራ ታይቶ ድርሻዬ ይሰጠኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 16 ላይ ማህበር ነክ አለመግባባት በግልግል እንደሚታይ የተደነገገ ሲሆን ይህ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡

የአሁኑ አመልካችም የፍ/ቤቱን ሥልጣን አስመልክቶ በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በግልግል እንዲታይ የተስማማነው በማህበርተኞች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን እንጂ በማህበሩ ላይ የቀረበውን ክስ የሚመለከት አይደለም፡፡ ስለሆነም ሥልጣኑ የፍ/ቤት ነው በሚል ይዘት ማስተባበያውን በቃል ክርክር አቅርቧል፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም በማህበርተኞች መካከል የሚነሱ ማህበር ነክ አለመግባባቶች የሚለው የመተዳዳሪያ ደንቡ አንቀጽ በማህበሩና በማህበርተኞች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን ሁሉ የሚመለከት በመሆኑ በግልግል ከሚታይ በቀር ፍ/ቤቱ ክርክሩን ለማየት ሥልጣን የለውም የሚል ዳኝነት ሰጥቶበታል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት ፍ/ቤትም በዚሁ ነጥብ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ብይን አጽንቷል፡፡

ይህ ሰበር አቤቱታ የቀረበውም ክርክር ያስነሳው ጉዳይ በፍ/ቤት ቀርቦ ሊታይ የሚችል ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ለመለየት በሥር በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶች በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 16 የተመለከተውን የደንብ ክፍል በአግባቡ አልተረጐሙትም፤የሚል ሆኖ በምክንያትነትም ክርክሩ የተነሣው በማህበርተኞች መካከል ሳይሆን በማህበርተኛ እና በማህበሩ መካከል ስለሆነ ደንቡ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል አይደለም፡፡ ጉዳዩ በፍ/ቤት ሊታይ የሚችል ነው፡፡ በሚል የተጠቀሰው ይገኝበታል፡፡

እንዲሁም ወጭና ኪሣራን አስመልክቶ የአሁን ተጠሪ አቅርቦት የነበረው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ከተደረገ ተረቺ በመሆኑ የወጭና ኪሣራ መብታችን ሳይጠበቅ በአንፃሩ በሥልጣን ምክንያት የእኛን ክስ ውድቅ ሲያደርግ ለተጠሪ መብቱን መጠበቁና በተመሳሳይ መንገድ የእኛን መብት መንፈጉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 463 የተመለከተውን ድንጋጌ የሣተ የሕግ ስህተት ነው የሚለውንም ቅሬታ አቅርቧል፡፡

ተጠሪም የሥር ፍ/ቤቶች ሥልጣንን አስመልክቶ የሰጡት ዳኝነት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት መሆኑን ለማስረዳት የበኩሉን መልስ ዘርዝሮ ያቀረበ ሲሆን፤አመልካችም በመልሱ መልስ ላይ የጠበቃውን በጥብቅና ለመከራከር ያለውን የውክልና ሥልጣን የፀና አይደለም ስለሆነም መልሱ ዋጋ ያለው ባለመሆኑ የክርክሩ አካል ሊሆን አይገባም የሚለውን ሁሉ ጨምሮ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን፤እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ለትርጉም መነሻ የሆነው፣በማህበሩ መተዳዳሪያ ደንብ አንቀጽ 16 ውዝግብ ለመፍታት በሚል ርዕስ በማህበርተኞቹ መካከል የሚነሱ ማህበር ነክ አለመግባባቶች በኢትዮጵያ የፍ/ብሔር ህግና የሥነ-ሥርአት ሕግ ስለግልግል በተመለከተው ደንብ መሰረት ይወሰናል፡፡ ውሳኔው አስገዳጅና የመጨረሻ ነው "በሚል ከተቀመጠው አንቀጽ" በማህበርተኞቹ መካከል የሚነሱ ማህበር ነክ አለመግባባቶች …" የሚለው ሐረግ በቀጥተኛው የሐረግ ትርጉም (literal meaning) የሚገደብ ነው ወይስ የተነሳው አለመግባባት ማህበር ነክ መሆኑ እስከተገለፁ ድረስ ከማህበሩ የሚመነጭ ማህበር ነክ አለመግባባት በማህበርተኞቹ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን በማህበሩና በማህበርተኞቹ መካከል አለመግባባት መነሳቱ አይቀሬ በመሆኑ "በማህበርተኞች መካከል" የሚለው ሐረግ በስፋት ታይቶ ሊተረጐም ይገባል ወይ? የሚለውን ጥያቄ ስለሚያስነሳ ለትርጉም በር በማይከፍት ሁኔታ የተቀረፁ አንቀጽ ሆኖ አልተገኘም፡፡

የትርጉም ሥራ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከሚመራበት ደንብ የመነጨ በመሆኑ እና ይህ ደንብም በማህበርተኞች ስምምነት የሚወጣ በመሆኑ እንደማናቸውም በሕግ ፊት የፀና ውል እንደሚተረጐመው ይህም ደንብ ስለውሎች በጠቅላላው ሕግ በተቀመጠው የመነሻ_አተረጓጐም መርህ ሊታይ የሚችል ከመሆኑም

በላይ ይህን መሰል ደንብ ለመተርጐም ሊመራን የሚችል የተለየ ሕግ እስከሌለ ድረስ የስምምነት ዓይነት ምንም ይሁን ምን ስለውሎች በጠቅላላው የተመለከቱት ደንቦች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1676/1/ የተመለከተ በመሆኑ ጭምር ነው፡፡

በመሆኑም ማህበር ነክ አለመግባባት በማህበርተኞች መካከል ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በማህበሩና በማህበሩ አባላት መካከል ጭምር የሚነሳ በመሆኑ አንቀጹን ቃል በቃል ካየነው በማህበሩና በማህበርተኞች መካከል ከማህበሩ የመነጨ አለመግባባት የተነሣ እንደሆነ እንዴትና በማን ይታያል? የሚል ጥያቄ ከተነሣ በክፍተትነት የሚቀር በመሆኑ ይህንኑ በሚመለከት ጥያቄ ቢነሳ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1734 እንደተመለከተው በዚህ ነጥብ ላይ የማህበሩ አባላት የሐሳብ አንድነት (common interest of the members) ምን ሊሆን ይችላል? እንዲሁም ማህበር ነክ አለመግባባት የሚል ጠቅላላ አነጋገር በዚሁ አንቀጽ ላይ ተጠቅሶ እያለ ከማህበሩ ሊመነጭ የሚችለውን የአለመግባባት ዓይነት ወሰን የሚያጠብ "በማህበርተኞች መካከል" የሚል ቃል ቢገኝም ማህበርተኞቹ ማህበር ነክ አለመግባባት የሚለውን ቃል ሲጠቀሙ የነበራቸው ሐሳብ ምን ነበር? የሚለውን ሁሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1735 ከተመለከተው አንፃር ማየት የሚያስፈልግ በመሆኑ ይህ ክርክር ያስነሳው አንቀጽ ከነዚህ ማዕዘኖች አኳያ ታይቶ ሊተረጐም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ዝርዝር ይዘቱን ማየት እንደሚቻለው ማህበር ነክ ጉዳዮችን በተሟላ አኳኋን እንዲሸፈን ተደርጐ የተቀረፀ ሲሆን፣በስተመጨረሻ ከዚህ መሰል መተዳደሪያ ደንብ ሊመነጭ የሚችልን ውዝግብ እንዴት  መፍታት እንደሚቻል አስቀድሞ ለማየት የደንቡ አካል በማድረግ በአንቀጽ 16 ላይ ከማህበሩ የመነጨን ማናቸውም ውዝግብ ለፍርድ ቤት በማቅረብ ፍትህ የማግኘት መብቱ በሕገ-መንግስቱም ሆነ አከራካሪ በሆነው በንግዱ ሕጉ ላይ የተከበረ መሆኑ እየታወቀ ውዝግቡ በሕግ መሰረት በግልግል እንዲታይና ይህም በግልግል ታይቶ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ መሆኑን በመግለጽ ማካተታቸው ማናቸውም ጉዳይ በአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ እንዲያልቅ ሐሳብ የነበራቸው መሆኑን የደንቡ ይዘት እና አቀራረጽ ስለሚያስረዳ፤

እንዲሁም ከማህበሩ የሚመጬት ውዝግቦች በማህበርተኞች መካከል ወይም በማህበሩና በአባላቱ መካከል ሊሆን እንደሚችል እየታወቀ የውዝግቡን ዓይነት በሁለት በመክፈል በማህበሩና በአባላት መካከል ከሆነ ግን ወደ ፍ/ቤት እንዲሄድ አስበው ነው ለማለት የተለዩ የግምት መነሻ የሆኑ ምክንያቶች ባለመገኘታቸው፣

በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 16 ላይ ማህበር ነክ ውዝግብ የሚለው አባባል በማህበሩና በአባላቱ መካከል ጭምር ሊነሳ የሚችልን ክርክር ሁሉ የሚያጠቃልል ሊሆን ይገባል በሚል የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዳኝነት በውል አተረጓጐም ረገድ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል የዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ትርጉም ለመስጠት መነሻ ያደረገው በአመልካች የሰበር አቤቱታ እና በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ትርጉም መሰረት በማድረግ እንጂ የተጠሪን መልስ በመመርኮዝ ባለመሆኑ፣

እንዲሁም ስለተጠሪ ሆኖ ለመከራከር ለጠበቃው የውክልና ሥልጣን ሰጡ የተባሉት ሥራ አስክያጅ በማህበሩ ቃለ ጉባኤ ተሰጥቷቸው የነበረው የሥራ ዘመን አልቋል እንጂ በሌላ ሥራ አስኪያጅ ተተክተዋል በማለት ባለመሆኑ፤ ይልቁንም አመልካች ያቀረቡት ማስረጃ በግልጽ እስካሁን

ድረስ በሌላ ሥራ አስኪያጅ የአለመተካታቸውን የሚያስረዳ በመሆኑ ከጥብቅና ውክልና ጋር በተያያዘ ያነሱት ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ስለወጭና ኪሣራ ጉዳይ ማን እንደሚከፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 462 እንደተመለከተው ለይቶ ለመወሰን ሥልጣኑ የፍ/ቤቱ በመሆኑና ይህንኑ ሥልጣኑን በዘፈቀደ የተጠቀሙበት ለመሆኑ ጠቋሚ እና አስረጂ በሆነ አኳኋን የቀረበ ክርክር ባለመሆኑ ወጭና ኪሣራ ማን ይክፈል የሚለውን በመወሰን ረገድም የሕግ ስህተት የተፈፀመ ሆኖ ስላላገኘው የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንደቅደም ተከተሉ በኮ/መ/ቁ. 6204 በ27/6/2001 እና በመ/ቁ. 79390 በ22/4/2002 የሰጡትን ብይን እና ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348 መሰረት አጽንተናል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም ብለናል፡፡
   ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 55311

ህዳር 17 ቀን 2003 ዓ.ም

***ዳኞች -*** ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

***አመልካች -*** ወ/ሮ ብርሃኔ አጥናፉ ጠበቃ መኮንን አራጋው ቀረቡ

***ተጠሪ -*** ኢንስፔክተር ዩሐንስ ተሲሳ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በምስራቅ ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግንቦት 11 ቀን 2001 ዓ.ም ባቀረበው የክስ ማመልከቻ እና በተከሣሽ ማለትም በአሁን አመልካች መካከል በነበረን የተለየ ግንኙነት ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺ.ህ ብር/ በብድር እንድሰጣት ጠይቃኝ አበድሬያታለሁ፡፡ ተከሣሽ ግንቦት 16 ቀን 2000 ዓ.ም የብድር ውል የፈረመች ሲሆን እስከ ሚያዚያ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺ ብር/ ቀሪውን ብር 100,000 /መቶ ሺ ብር/ እስከ ሚያዚያ 5 ቀን 2002 ዓ.ም ሊከፍሉ ተስማምተዋል፡፡ በውሉ መሠረት ያልከፈሉ በመሆኑ በብድር የወሰዱትን ገንዘብ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርባ ከከሣሽ ጋር እንደባልና ሚስት በመሆን አብረን ስንኖር መግባባት ስላልቻልን ለመለያየት ስንወሰን ገንዘብ ካልሰጠሽኝ በስተቀር በማለት በእኔና በንብረቴ ላይ አደጋ እንደሚያደርስ ስላስፈራራኝ ገንዘብ ሣልበደር በግዳጅ ገንዘብ እንደተበደርኩ አድርጌ ፈርሜለሁ ስለሆነም ከከሣሽ /ተጠሪ/ የተበደርኩት ገንዘብ ስለሌለ እንድከፍል የምገደድበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ሁለት ምስክሮችን ሰምቷል፡፡ አንደኛው ምስክር በመጀመሪያ አመልካችና ተጠሪ ሲከራከሩ እንደነበር ከዚያም ሣይስማሙ በመቅረታቸው ከጠበቃ ጋር ሄደው ሲጮሁ እንደነበርና አመልካች የእኔ ድርሻ ለተጠሪ እንዳይደርሰው ስትል እንደነበርና ተጠሪ የአንቺ ድርሻ እንዳይደርሰኝ ፈርሚ ሲል የነበረ መሆኑንና በመጨረሻ አመልካች ብር 200,000 ከተጠሪ ተበድሬለሁ በማለት እንደፈረመች በመቅረቱ ተጠሪ ለአመልካች ብር 200,000 እንዳልሰጣት የመሰከረ መሆኑን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሣኔው በግልፅ ያሰፈረ ሲሆን ሁለተኛው ምስክር አመልካችና ተጠሪ እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ



www.chilot.me

እንደነበር የብድር ውል በተፈራረሙበት ቀን አመልካች ተጠሪን ከድርሻየ ጋር እንድትደርስ ስትል ተጠሪ አብረን ያፈራነውን ንብረት ድርሻየን እንዳገኝ ነው በማለት ይናገር እንደነበር ከዚያ በኃላ አመልካች የብድር ውል የፈረሙለት መሆኑን በመግለፅ እንደመሰከረ ከከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካችን እንደባልና ሚስት በኖርንበት ጊዜ ያፈራነውን የጋራ ንብረት ስጭኝ በማለት ሲጠይቅ የነበረ መሆኑንና አመልካች ከተጠሪ በደረሰባት ግፊትና ተፅዕኖ የተበደረችው ገንዘብ ሣይኖር ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺ ብር/ ተበደሬአለሁ ብላ የፈረመች መሆኑ በአመልካች ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ይህም በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1706 በተደነገገው ሁኔታ የተደረገ ውል በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት የለውም በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ተጠሪ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል የክልሉ ጠቅላይ ፍድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በፈረመችው ብድር ውል መሠረት ተጠሪ ክስ ያቀረበበትን ገንዘብ ከነወለዱ የመክፈል ግዴታ አለባት በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የአመልካችን አቤቱታ አልተቀበለውም፡፡

አመልካች ሚያዚያ 20 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ እኔና ተጠሪ እንደባልና ሚስት በነበረን ግንኙነት አብረን የኖርን ሲሆን አስራ አንድ ዓመት የሆናት መክሊት ዩሐንስን ወልደናል፡፡ ሆኖም በመካከላችን በነበረው አለመግባባት ግንኙነታችንን ለማቋረጥ ስንወስን ገንዘብ ካልሰጠሽኝ በማለት በሥራው ምክንያት መንግስት ባስታጠቀው መሣሪያ በተለያየ ጊዜ እያስፈራራ ስላስቸገረኝ በብድር የወሰዱኩት ገንዘብ ሣይኖር ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺ ብር/ እንደተበደርኩ በመግለፅ በፍራቻ ፈርሜለሁ ገንዘብ በወቅቱ ያልተበደርኩ መሆኔን በውሉ ላይ በምስክርነት የፈረሙት የተጠሪ ሁለት ምስክሮች ለሥር ፍርድ ቤት አስረድተዋል፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ያላግባብ ተጨማሪ ማስረጃ በመቀበል የሰጠውና ህግን መሠረት ያላደረገ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በይግባኝ ሰሚው ችሎት የተፈፀመውን የህግ ስህተት ሣያርም ማለፉ ተገቢ ባለመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው አመልካች ውሉን ሲፈፅሙ የሀይል ተግባር የተፈፀመባቸው መሆኑን አላስረዱም አመልካች የፍታብሔር ህግ ስለብድር በሚደነግገው መሠረት ገንዘብ በብድር የወሰዱ መሆኑ በውሉ ሰነድ የተረጋገጠ በመሆኑ ብድሩን ላለመክፈል የሚያቀርቡት ክርክር የህግ ድጋፍና መሠረት የለውም፡፡ ስለዚህ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ እንዲያደርግልኝ የሚል ይዘት ያለው መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች ተጠሪ ማስፈራራትና ዛቻ የፈፀመው ውሉ በተፈረመበት ቀን ሣይሆን ከዚያ በፊት አመልካች ላይ ከዚያ በፊት ሥነ ልቦናዊ ተፅኖ የሚያሣድሩ ተግባራትን በመፈፀም ነው አመልካች ያልተማርኩ በመሆኔና ተጠሪ የፖሊስ መኮንን በመሆኑ እኔን ስጋት ላይ የሚጥል ተግባር ሲፈፅም የቆየ ሲሆን ውሉ በሚፈረምበት ወቅትም በእኔና በአመልካች መካከል ጭቅጭቅ የነበረ መሆኑ በማስረጃ ስለተረጋገጠ ውሉን በሙሉ ፈቃድና ፍላጎቴ ያላደረግሁት በመሆኑ ልገደድበት አይገባም በማለት የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር በግራቀኙ መካከል የተደረገው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው በአመልካችና በተጠሪ መካከል ግንቦት 16 ቀን 2000 ዓ.ም ያደረጉት የብድር ውል ህጋዊ ውጤትና አስገዳጅነት አለው ወይስ የለውም የሚለው ጭብጥ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡



www.chilot.me

ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመመለስ አንድ ውል ህጋዊ ውጤት የሚኖረው በምን መንገድ ሲፈፀም ነው የሚለውን ነጥብ ማየት ያስፈልጋል፡፡ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በህግ ፊት የፀናና ህጋዊ ውጤት ሊኖረው የሚችለው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1678 የተደነገጉትን ሶስት መሠረታዊ ሁኔታዎችን ሲያሟላ መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1678 "የሚፀና ውል ነው ለማለት ሶስት ሁኔታዎች ያስፈልጉታል" በማለት ሁኔታዎቹን ከ"ሀ" እስ "ሐ" በዝርዝር ደንግጓል፡፡ በህግ ፊት የፀና ውል ለማቋቋም አስፈላጊ ከሆኑ ሁኔታዎች አንደኛ ውሉ ችሎታ ባላቸው ሰዎች መካከል የተደረገና ተዋዋዩቹ ጉድለት በሌለው ሁኔታ የተስማሙበት ሲሆን እንደሆነ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1678 /ሀ/ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺ ብር/ ብድር የወሰዱ መሆኑን በመግለፅ ግንቦት 16 ቀን 2000 ዓ.ም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማጣሪያ ምስክርነት ጠርቶ ቃላቸውን የተቀበላቸው ጠበቃ ባዘጋጁት የብድር ውል ላይ በማጣሪያ ምስክሩ ቢሮ ውስጥ መፈረማቸውን አልካዱም፡፡ አመልካች የሚከራከሩት በወቅቱ ብር 200,000 እንደተበደርኩ በሚገልፀው ሰነድ ላይ የፈረምኩት በሙሉ ፍላጎቴና ፈቃዴ አይደለም፡፡ ከተጠሪም ውሉን በምፈርምበት ጊዜም ሆነ ከዚያ በፊት በብድር የወሰድኩት ገንዘብ የለም ፡፡ ብድሩን የፈረምኩት ተጠሪ ሰነዱን ካልፈረምኩ በህይወቴና በንብረቴ ላይ የማይቀር አደጋ ወይም ጉዳት የሚያደርስብኝ መሆኑን በመግለፅ በተለያየ ጊዜ የማስፈራራትና የማስገደድ ተግባራትን ስለፈፀመብኝ ነው በማለት ነው፡፡

የማስገደድ ወይም የሀይል ሥራና ተግባር ስለተፈፀመበት አንድ ሰው አንድን ውል ለመዋዋል የተስማማ በሆነ ጊዜ ለውሉ የሰጠው ስምምነት ጉድለት ያለበት ስምምነት ተደርጎ እንደሚወስድና በህግ ፊት የፀና መብትና ግዴታ ለማቋቋም የማይችል ስለመሆኑ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1678/ሀ/ እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1706 እና የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1809 ድንጋጌዎችን በጣምራ በማንበብ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

አንደኛው ተዋዋይ ወገን ሌላውን ተዋዋይ ወገን ራሱን ወይም ወላጆቹን ወይም ተወላጆቹን ወይም ባልን ወይም ሚስትን ከባድና የማይቀር አደጋ በህይወቱ በአካሉ በክብሩ ወይም በንብረቱ እንደሚያመጣበት ያሳመነው በመሆኑ ምክንያት ውሉን ለመዋዋል የተስማማ እንደሆነ ውሉን በማፍረስ በቂ ምክንያት እንደሆነ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1706 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ እዚህ ላይ ሌላውን ወገን ውል እንዲፈፅም የሚያስገድደው ሰው የማስገደድ ተግባሩን የፈፀመውና ሌላውን ተዋዋይ ወገን ስጋት ላይ የሚጥሉ ተግባራትን የፈፀመው ውሉ በሚፈፀምበት ዕለት ወይም ከዚያ ውሉ ከተፈፀመበት ዕለት በፊት ሲሆን እንደሚችል ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1706 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1706 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ የጣምራ ንባብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ አንደኛው ተዋዋይ ሌላውን ተዋዋይ ወገን በውሉ ካልተስማማ በህይወቱ ወይም በንብረቱ ላይ የማይቀር አደጋ የሚያደርስበት መሆኑን ለማሳመን የሚችሉ የተለያዩ የማስገደጃና የማስፈራሪያ ተግባራትንና ዘዴዎች በመጠቀም በአእምሮው ተደላድሎ የነበረው ተዋዋይ ወገን ሌለው ተዋዋይ ከባድና የማይቀር አደጋ ሊያደርስብኝ ይችላል በሚል ስጋት ውሉን እንዲዋዋል ለማድረግ የሚችልባቸው በርካታ መንገዶች አሉ፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ውሉ ከመደረጉ በፊት የተፈፀሙ መሆኑን አለመሆኑን አንደኛ ተዋዋይ ወገን ሌላው ተዋዋይ ከባድና የማይቀር አደጋ ሊያደርስብን ይቻላል በሚል ስጋት ለውሉ ስምምነቱን የሰጠ መሆኑን ዳኞች በመገደድ ስምምነቱን የሰጠውን ሰው እድሜውን ፆታውንና አኳኋኑን በማመዛዘን ውሣኔ መስጠት እንደሚገባቸው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1706 ንዑስ አንቀጽ 3 ይደነግጋል፡፡



www.chilot.me

አመልካች ከተጠሪ ብር 200,000 መበደራቸውን የሚገልፅ ውል ግንቦት 16 ቀን 2000 ዓ.ም የፈረሙት በእርግጥ ከተጠሪ ተበድረው የወሰዱት በውሉ መጠኑ የተገለፀው ገንዘብ ስላለ ነው? ወይስ ተጠሪ የማይቀርና ከባድ አደጋ በህይወታቸውና በንብረታቸው የሚያደርስባቸው መሆኑን እንዲያምኑና ስጋት ላይ እንዲወድቁ ለማድረግ የሚችሉ የተለያየ ተግባራትና ዘዴ በመፈፀሙ ነው? የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረውን ልዩ ግንኙነትና ባህሪ የአመልካችን ፆታ የትምህርት ደረጃና የተጠሪውን ግላዊ ሁኔታና እና ሥልጣንና ኃላፊነት መመርመርና መመዘን እንደሚያስፈልግ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1706 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ እንችላለን፡፡

ከላይ ያስቀመጥናቸውን መሠረታዊ ሁኔታዎች ስንመዝን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማጣሪያ ምስክርነት የሰማቸው ሁለት ሰዎች አመልካች በተጠሪ ምንም አይነት የማስገደድ ተግባር ሣይፈፀምባቸው እኛ ባለንበት የብድር ውሉን ፈርመዋል በማለት ውሉ በተፈረመበት ወቅት ብቻ ስለነበረው ሁኔታ የሰጡትን የምስክርነት ቃል መሠረት በማድረግ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች አልተገደዱም የሚል መደምደሚያ ላይ መድረሱ ከላይ የጠቀስነውን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1706 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን ያልመዘነና ያልመረመረ መሆኑን የሚያሣይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሉ ከመፈፀሙ በፊት በተጠሪና በአመልካች መካከል የነበረውን ግንኙነትና የተጠሪ ምስክሮች አመልካችና ተጠሪ ወደ ሁለተኛው የማጣሪያ ምስክር ቢሮ ከመሄዳቸው በፊት ሲለዋወጡት የነበረው ሃሳብና ንግግርን መመዘንና መመርመር ይገባው ነበር አመልካችና ተጠሪ እንደባልና ሚስት አብረው ለረዥም ጊዜ የኖሩ እና የአስራ አንድ ዓመት ሴት ልጅ ወልደው ያሣደጉ መሆናቸው በግራቀኙ የተካደ ፍሬ ጉዳይ አይደለም እንደባልና ሚስት በመተማመን የኖሩት አመልካችና ተጠሪ በመካከላቸው በተፈጠረው አለመግባባት ግንኙነታቸውን ለማቋረጥ ለየብቻቸው ለመኖር ሲወስኑ በመካከላቸው አለመግባባትና ቅሬታ ተፈጥሮ የነበረ በመሆኑ የብድር ውሉ ተፈረመ በተባለበት ግንቦት 16 ቀን 2000 ዓ.ም የዕርቅ ስምምነት ውል አድርገው የነበሩ መሆኑና በውሉም በጋራ በቆየንበት ጊዜ የተፈራ የጋራ ሀብት በውርስ ወይም በስጦታ ያገኘነው ንብረት የለም በማለት ተስማምተው የነበረ መሆኑ አመልካችና ተጠሪ ካቀረቡት ክርክር ለመገንዘብ ችለናል፡፡ አመልካችና ተጠሪ ወደ ሁለተኛው የፍርድ ቤት የማጣሪያ ምስክር ቢሮ ከመሄዳቸው በፊት የእኔን ድርሻና ንብረት እንዳትወስድ እያለች አመልካች ትናገር የነበረ መሆኑና አመልካች ብር 200,000 ተበድሬያለሁ ብላ ከመፈረሟ በፊት ይከራከሩና ሃሳብ ይለዋወጡ የነበሩት ስለብድር ገንዘብ ሣይሆን ስለጋራ ንብረት እንደነበር የከፍተኛው ፍርድ ቤት የምስክርነት ቃላቸውን የሰማቸውና የሰጡትን የምስክርነት ቃል ተዓማኒነት ያለው መሆኑን በማረጋገጥ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በውሣኔው በግልፅ አስፍሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ብር 200,000 ተበድሬአለሁ ብላ ከመፈረሟ ውጭ በዕለቱ ተጠሪ በብድር የሰጣት ጥሬ ገንዘብ ቼክ ወይም ሐዋላ የሌለ መሆኑ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ቃላቸውን የሰማቸው የተጠሪ ምስክሮችና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰማቸው የማጣሪያ ምስክሮች አረጋግጠዋል፡፡

ተጠሪ መርማሪ ፖሊስ በመሆኑ አመልካችን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሰማቸው የማጣሪያ ምስክሮች ፊት ውሉን ፈርሚ ብሎ ለማስገደድ የሚሞክርበት ሁኔታ የለም ምክንያቱም ተጠሪ ድርጊቱ በህግ ፊት የሚያስትለውን ህጋዊ ውጤት ጠንቅቆ የሚያውቅ ከአመልካች የተሻለ የህግ ዕውቀትና ግንዛቤ ያለው በመሆኑ ከአመልካች ጋር እንዳባልና ሚስት ስንኖር ያፈራነው የጋራ ሀብት አለ ብሎ በህግ ፊት ተከራክሮ ለመፍታት የሚያስችለው ማስረጃ አለመኖሩን በመረዳት



www.chilot.me

አመልካች የብድር ውል እንዲፈፅሙ ያደረገ መሆኑን ከላይ ከገለፅናቸው ሁኔታዎች ለመገንዘብ ይቻላል የብድር ውሉ አመልካች ከሚኖሩበት ከተማ ውጭ መደረጉ የአመልካችን ክርክር የሚያጠናክር ነው፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ውሉን ስትፈርም ተጠሪ አላስገደዳትም ወይም አላስፈራራትም የሚለውን የማጣሪያ ምስክሮች ቃል በመስማት ብቻ አመልካች የብድር ውሉን ተጠሪ እንድትፈፅም አላስገደዳትም ከሚለው መደምደሚያ ላይ የደረሰው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1706/3/ በሚደነግገው መሠረት ውሉ ከመፈረሙ በፊት አመልካችና ተጠሪ ያደረጉትን የዕርቅ ስምምነት እንደዚሁም ወደ ሁለተኛው ማጣሪያ ምስክር ቢሮ ከመሄዳቸው በፊት ሃሳብ እየተለዋወጡ ሲከራከሩ የነበሩት በብድር ስለተወሰደ ገንዘብ ሣይሆን አብረው ሲኖሩ በጋራ ያፈሩት ንብረት አለ ወይም የለም በሚለው ነጥብ ላይ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ የማያስገባ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪ አመልካች የማስፈራራትና የማስገደድ ተግባራት የተፈፀመባት መሆኑን አላስረዳችም በማለት ያቀረበውን ክርክር ስንመለከተው አመልካች የብድር ውሉ በህግ ፊት የማይፀናና ፈራሽ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ እንዳለባቸው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2001 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገ ቢሆንም በህግ ፊት የሚፀናና ጉድለት የሌለበት የብድር ውል ያለ መሆኑን ለማስረዳት ተጠሪ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2001 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ያቀረባቸው ምስክሮችና በአጠቃላይ ሌሎች የአካባቢ ሁኔታዎች አመልካች ከተጠሪ ብር 200,000 በሙሉ ፍላጎትና ፈቃዳቸው ያልተበደሩና በተቃራኒው ተጠሪ አብረን ስንኖር ያፈራነው የጋራ ገንዘብ ያለኝ በመሆኑ በብድር መልክ ድርሻየን ፈርሚ በማለት የተለያዩ የማስገደጃና የማስፈራራት ተግባራትን በመፈፀም የብድር ስምምነቱን እንዲፈርሙ ያደረጉ መሆኑን የሚያረጋግጡ መሆናቸውን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1706 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገጉትን ሁኔታዎች በማመዛዘን ከድምዳሜ ላይ የደረሰ በመሆኑ ተጠሪ በዚህ በኩል ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ አመልካች የብድር ውሉን ለማፍረስ በሁለት ዓመት ያልጠየቁ መሆኑን ገልፆ የተከራከረ ቢሆንም ይኸ የተጠሪ ክርክር ውሉን ለመፈፀም እንቢ ለማለት የማይፈልገው ወገን ውሉ የማይረጋ መሆኑን በማናቸውም ጊዜ መቃወሚያ ሊያደርገው እንደሚችል በግልፅ የሚደነገግውን የፍታብሔር ህገ ቁጥር 1809 መሠረት ያላደረገ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ በአጠቃላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት እና ሰበር ችሎት በአመልካችና ተጠሪ በመካከላቸው የነበረውን ልዩና ጥብቅ ግንኙነት አመልካችና ተጠሪ በመካከላቸው የነበረውን ግንኙነት ለማቋረጥ ያደረጉትን ስምምነትና ውሉ የአመልካች መኖሪያ በሆነው ቢሸፍቱ ከተማ ሣይሆን የተጠሪ መኖሪያና የሥራ ቦታ በሆነው አዳማ ከተማ የተደረገ መሆኑን የአመልካችን ፆታና የትምህርት ደረጃና የተጠሪን የትምህርት ደረጃ ሙያና ስልጣንና ሀላፊነት እንደዚሁም የብድር ውሉን ከማፀፋቸው በፊት ሲከራከሩበት የነበረውን መሠረታዊ ጉዳይ የፍታብሐር ህግ ቁጥር 1706 ንዑስ አንቀጽ 3 በሚደነግገው መሠረት ሣያመዛዝኑ አመልካች ለተጠሪ ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺ ብር/ ከነወለዱ እንዲከፍሉ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

***ው ሣ ኔ***

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሰበር ችሎት እና የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንተነዋል፡፡
3. አመልካችና ተጠሪ ግንቦት 16 ቀን 2000 ዓ.ም የተፈራረሙት የብድር ውሉ ተጠሪ በሙሉ ፈቃዳቸው ስምምነታቸውን ያልሰጡበት ጉድለት ያለውና በህግ ፊት የማይፀናና ውጤት የሌለው ነው በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

ም.አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 56368

ህዳር 1 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፣** ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች -** ዶ/ር ሰሎሞን ነጋሽ ዶ/ር ዘውድነህ በየነ ቀረበ

**ተጠሪ -** የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ሙሳት ያዛቸው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ ሰበር ችሎት እንዲወሰን ለቀረበው አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ ቀደም ሲል በተደረገው ውል መሠረት የግልግል ዳኛ በፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲመረጥ አመልካች አቅርቦት የነበረውን ጥያቄ የሚመለከት ነው አመልካች ጥያቄውን ያቀረበው ለምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ፍ/ቤቱ ተጠሪን አስቀርቦ መልስ እንዲሰጥ ከማድረጉ በፊት ጥያቄው በፍ/ቤት የሚስተናገድ አይደለም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 231 የተመለከተውን ድንጋጌ በመጥቀስ መዝገቡን ዘግቶአል ጉዳይ በይግባኝ የቀረበለት የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤትም ይግባኝ የተባለበት ትዕዛዝ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ግንቦት 14 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው ለአመልካች ክስ መሠረት የሆነው በሁለቱ ወገኖች መካከል የተደረገ ውል መሆኑ እስካላከራከረ ድረስ እንደውሉ ጉዳዩ በግልግል ያልቅ ዘንድ የፍ/ቤትን እገዛ በመጠየቅ የቀረበው ክስ በማያስከሰስ ነገር ላይ የቀረበ ነው በማለት ሳይስተናገድ የመቅረቱን አግባብነት ለመመርመር ነው በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ትዕዛዝ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለጸው አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሠረተው በመሃከላቸው የተደረገውን ውል መነሻ በማድረግ ነው ውሉ ነሐሴ 28 ቀን 2000 ዓ.ም የተደረገ የማማከር አገልግሎት የመስጠት እንደሆነም በክርክሩ ተመልክቶአል በሌላ በኩል ደግሞ የውሉን አፈፃፀም በሚመለከት በመሃከላቸው አለመግባባት ቢፈጠር እና አለመግባባቱን በድርድር መፍታት ካልተቻለ ሁለቱ ወገኖች በሚያቋቁሙት የግልግል ዳኝነት እንደሚታይ ስምምነት ስለመደረጉ ግራቀኝ ወገኖች አልተካካዱም አመልካች ወደክስ ያመራው ተጠሪ በውሉ መሠረት ለመገዛት ፈቃደኛ አልሆነም



www.chilot.me

በማለት ሲሆን የጠየቀው ዳኝነትም ተጠሪ በውሉ በገባው ግዴታ መሠረት የግልግል ዳኛ እንዲመርጥ ይገደድልኝ የሚል ነው፡፡

እንደሚታየው አመልካች እና ተጠሪ በመሃከላቸው ያቋቁሙትን መብት እና ግዴታ የሚገዛ ውል አድርገዋል፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁ 1731 እንደተደነገገው በሕጉ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች ባቋቋሙዋቸው ሰዎች ላይ ሕግ ናቸው ከሣሽ የሆነው ወገን ተጣሰብኝ የሚለውን መብት ለማስከበር ዳኝነት የሚጠይቀው የመብቱን ምንጭ ወይም መሠረት ውል ወይም ህግ እንደሆነ በማረጋገጥ ስለመሆኑ  የሚያከራክር አይደለም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 33/2/ አነጋገር ከሣሽ ከተከሣሽ ላይ የሚጠይቀውን ጥቅም ወይም መብት በማረጋገጥ አቤቱታውን ያቀርብ ዘንድ ይጠበቅበታል ሲባልም የመብቱ መሠረት ሕግ ወይም ውል መሆኑን በግልጽ ማሳየት አለበት ማለት ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች ተጠሪ ይፈጽምልኝ የሚለው ግዴታ መሠረቱ ውሉ እንደሆነ አሳይቶአል ተጠሪም ለአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰጠው መልስ እንደገለጸው ስለውሉ መደረግም ሆነ ስለይዘቱ የሚክደው ነገር የለም፡፡ ክርክሩ ተከሣሽ የመንግስት መሥሪያ ቤት በመሆኑ ጉዳዩን በግልግል እንዲጨርስ በሕግ አይገደድም የሚል እንደሆነም ከዚሁ መልሱ ይዘት ተገንዝበናል፡፡

ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የክሱን መዝገብ የዘጋው ተጠሪን ሳያስቀርብ እንደሆነ ከላይ ተገልጾአል፡፡ መዝገቡን ሊዘጋ የቻለውም አመልካች የክስ ምክንያት የለውም በማለት ነው ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት ፍ/ቤትም በተመሳሳይ ሁኔታ ይግባኙን ሰርዞአል በመሆኑም ይህ የሰበር ችሎት በዚህ ደረጃ ሊያይ የሚገባው አመልካች ያቀረበው ክስ የክስ ምክንያት የለውም በማለት የተሰጠው ትዕዘዝ አግባብነት ያለው ነው ወይ? የሚለውን ጭብጥ በመሆኑ ተጠሪ በግልግል ዳኝነት ጉዳዩን እንዲጨርስ የሚለውን የሥረ ነገር ክርክር የምንመረምርበት አግባብ የለም፡፡ ወደያዝነው ጭብጥ ስንመለስም አመልካች በክሱ ላይ የገለጸው ጉዳይ /ነገር/ የክስ ምክንያት የሌለው /የማያስከስስ/ ነው የሚባል ባለመሆኑ አቤቱታ የቀረበበት ትዕዛዝ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ 39576 ሚያዚያ 21 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና በአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/መ/ቁ 29491 ግንቦት 12 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ውሉን መሠረት በማድረግ ያቀረበው ክስ የክስ ምክንያት የለውም በማለት ሳይስተናገድ መቅረቱ በአግባቡ አይደለም ብለናል፡፡ ስለዚህም የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱን ለተጠሪ እንዲደርስ በማድረግ እና ግራቀኝ ወገኖች በክሱ ስረ ነገር የሚያቀርቡትን ክርክር ከሰማ በኃላ ተገቢውን ይወሰን ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 341/1/ መሠረት ወስነናል፡፡
3. ግራቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት***

የሰ/መ/ቁ. 56682

ህዳር 14 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

**ተጠሪዎች** ፡- 1ኛ አንዋር አብዱራማን

2ኛ አብዱልቃድር አብዱራማን

3ኛ መሐመድ አብዱራማን

4ኛ ከሊፍ አብዱራማን

5ኛ አይሻ አብዱራማን

6ኛ ሂቦ አብዱራማን

7ኛ ሳሚያ አብዱራማን

8ኛ ናሬሳ አብዱራማን

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ ግራ ቀኙ ከቀጠሮ በፊት ካቀረቡት የጽሑፍ ክርክር ጋር መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ ግራ ቀኙ የመያዣ ውል አደራረግ ሥርዓትን አስመልክቶ ያቀረቡትን የህግ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ የአሁኑ ተጠሪዎች አባታችን ሳያውቀው በድብቅ የተደረገ የመያዣ ውል ስለሆነ ያስረክብልን ይሰረዝልኝ ይለቀቅልን የሚል ክስ በአሁን አመልካች ላይ በምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት በማቅረባቸው ሲሆን የአሁን አመልካችም ባንኩ ለዮሴፍ አብርሃም ለሰጠው የብድር ገንዘብ ከአባታቸው ጋር ሐምሌ 14 ቀን 1987 ዓ.ም በተደረገ የመያዣ ውል መነሻ እንጂ ከሳሾች እንደሚሉት አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ ይህ አከራካሪ የሆነ የመያዣ ውል በኦሮሚያ ከተማ አስተዳደር ተመዝግቦ እንደማይገኝ የከተማው አስተዳደር ምንም ዓይነት ማስረጃ እንደሌለ አረጋጋጧል፡፡ አከራካሪ በሆነው የመያዣ ውል ላይ የተቀመጠውን ፊርማ የአባታቸው ስለ መሆኑ ማረጋገጥ እንዳይቻል ባንኩ የአሁን አመልካች ማገናዘብያ የሚሆን የተለያዩ ማስረጃ ለማቅረብ አልቻለም፡፡ ዋናውን የመያዣ ውል ማቅረብ ባለመቻሉ ያቀረበው ኮፒ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2011 ሥልጣን ባለው አካል ፊት ካልተረጋገጠ ተቀባይነት የለውም፡፡

ስለሆነም የመያዣ ውሉ በፍ/ብ/ስ/ሕ/ቁ 1723 መሠረት በአዋዋይ ፊት ያልተረጋገጠ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3052 መሠረት በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ላይ ስላልተመዘገበ አደራረጉ የሕግ መስፈርትን አላሟላም በመሆኑም ውድቅ ነው፡፡ ካርታው ይመለስ በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ የተጠሪዎች አባት በህይወት እያሉ እኔ ሳላውቀው ካርታ ይዞብኛል በማለት ከአሁን አመልካች ጋር ስለተከራከረ የመያዣ ውል ምዝገባ ሥርዓት አስፈላጊ አልነበረም በህይወት እያሉ በመያዣ ውሉ ላይ አልፈረምኩም በማለት ስለተከራከሩ ዋናው አከራካሪ ነጥብ ፈርመዋል ወይስ አልፈረሙም የሚለው ነበር ይህንን ነጥብ ለመለየት የአሁን አመልካች ዋናውን ሰነድ አላቀረበም የእራሱን ሰነድ በሥርዓት መያዝ ግዴታው ነው ያቀረበው ኮፒ ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚቻልበት መንገድ የለም፡፡ የሚለውን ተችቶ በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠውን ወሳኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከዚህ በላይ በአጭሩ እንደተገለፀወው በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤቶች የተሰጡት ውሳኔዎች መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በሚል ነው ያቀረበውም ምክንያት ዋናው የመያዣ ውል ሊገኝ ባይችልም ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ኮፒ አቅርበናል፡፡ በዚህ ሰነድ ላይ የሰፈረን ፊርማ መካድ እንደማይቻል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2011 ተደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ በአግባቡ አልተተረጐመም የሚለውን ነው፡፡

ተጠሪዎችም ለዚህ የሰበር ቅሬታ መልሳቸውን በጽሑፍ ያቀረቡ ሲሆን በግራ ቀኙ መካከል ለተነሣው አከራካሪ ነጥብ መነሻ የሆነውን የኮፒ ሰነድ ጉዳይን አስመልክቶ የአሁን አመልካች በሰበር ቅሬታው ላይ ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት የተረጋገጠ ኮፒ አቅርቤያለሁ ለሚለው ክርክር ዋናውን ቅጅ ማቅረብ እንደማይቻል በዚህ ሰበር ደረጃም አረጋግጧል፡፡ ቢኖረው ኖሮ በሚመለከተው ማዘጋጃ ቤት ይቀመጥ ነበር እራሱም ዋናውን መያዝ ነበረበት ይህ ሁሉ ሳይሆን በሰጡት ሰነድ ይወሰንልኝ  ማለቱ አግባብ አይደለም በማለት ተከራክረዋል ፡፡

እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡ እንደተመለከትነውም በዚህ ሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ እንዳደረጉት ክርክር የአሁን አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ጉዳዩን ለማስረዳት ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት የተረጋገጠ ኮፒ አቅርቦ እንደነበር የሚያስረዳ ሲሆን ይህንንም የሚያጠናክረው በሥር በሁለቱም ደረጃ በተደረገው ክርክር አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2008 መሠረት አከራካሪ የሆውን የመያዣ ውል ሰነድ ኮፒ አቅርቦ እንደነበረ በሁለቱም ውሳኔዎች ተመዝግቦ የመገኘቱ ጉዳይ ነው፡፡ የዚህን ክርክር ያስነሳው የመያዣ ውል ዋናው ኮፒ ቀርቦ ቢሆን ኖሮ ተጠሪዎች ሦስተኛ ወገን ናቸው እንኳ ቢባል ይህ የመያዣ ውል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት እስከተረጋገጠ ድረስ የሰነዱን ይዘቱና ፊርማን ጨምሮ በማናቸውም መንገድ ቢሆን ሊቃወሙት እንደማይችሉት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2009 ላይ ተመልክቷል ይህ ዋናው ሰነድ መቅረቡ ቀርቶ የዚህ ሰነድ ትክክለኛ ቅጅ ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ተረጋግጦ ከቀረበ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2011 እንደተመለከተው በማስረጃ



www.chilot.me

ዋጋነቱ እንደ ዋናው የተረጋገጠ የመያዣ ሰነድ የሚያገለግል እንጂ ክርክር የቀረበለት ፍ/ቤት ዋናውንና ቅጂውን ሁለቱንም በማስቀረብና በማስተያየት ቅጅው ያለውን የማስረጃ ዋጋ የሚመረምርበት የህግ አግባብ የለም በዚህ መንገድ የማረጋገጥ ተግባሩ አይከናወንም፡፡ ዋናውና መሠረታዊ የሆነው ጉዳይ ለማስረጃነት የቀረበው ኮፒ ከዋናው ጋር በማገናዘብ ሥልጣን ባለው አካል ፊት ትክክለኛ ግልባጭ ስለመሆኑ በኮፒው ላይ ተገልፆ የመገኘቱ ሁኔታ ነው፡፡

በመሆኑም የመያዣ ውል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ተደርጎ ለማስረጃነቱ ዋናው ሰነድ ባልተገኘ ጊዜ በምትኩ ኮፒ ሲቀርብ የዚህ የዋናው ሰነድ ግልባጭ ስለመሆኑ እራሱ ሰነዱ ሥልጣን በተሰጠው አካል ማረጋገጫ ተደርጉበት የሚናገርሆኖ ከተገኘ ከላይ በተጠቀሰው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2011 መሠረት በእራሱ በቂ ማስረጃ ሆኖ እያለ ለዚህ ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ተረጋግጦ የቀረበን ኮፒ ብቸኛው ማረጋገጫ ዋናው ሰነድ እንደሆን ተደርጎ የተሰጠው ትርጉም መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

የምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት እንደቅደም ተከተሉ በመ/ቁ 9452 በ19/12/2000 እና በመ/ቁ 84422 በ29/18/2002 የሰጡትን ፍርዶች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕቁ 348(1) መሠረት ሽረናል፡፡

ሐምሌ 14 ቀን 1987 ዓ.ም በተፃፈ የተደረገው የመያዥ ውል በተጠሪዎች አባት ስለመደረጉ አመልካች በህግ መሠረት ያረጋገጠ ስለሆነ ዋጋ ያለው በመሆኑ በዚሁ በአንድ ላይ የተገለፀው ንብረት ካ ርታ ለተጠሪዎች ሊለቀቅ አይችልም ብለናል፡፡

በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ላደረጉት ክርክር ወጪና ኪሣራውን በየእራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡን ዘግተናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 48857

ታህሳስ 12 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ነ/ፈጅ ፈያራ ገለታ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአዲስ አበባ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16/17 አስተዳደር ጽ/ቤት የቀረበ የለም፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውሃ አገልግሎት ሂሳብ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካች ክስ ይዘትም ባጭሩ፡- ተጠሪ በቀድሞ ወረዳ 07/ቀበሌ 27 አስተዳደር በቤት ቁጥር 436 ነዋሪና ባለቤት የነበሩት አቶ ግርማ ወ/ሚካኤል በ15/07/1950 በውል ቁጥር 12085 ከአመልካች መስሪያ ቤት ጋር ባደረጉት የውል ስምምነት አገልግሎት እያገኙና የውሃ ሂሳብ ሲከፍሉ የቆዩ መሆኑን የተጠቀሰውን ቤት ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ወርሶ በቀድሞው ባለሃብት እግር በመተካት የውሃ አቅርቦት አገልግሎት ሲጠቀም የቆየ ቢሆንም የህዳር ታህሳስና ከሐምሌ 1992 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሳስ 1993 ዓ.ም ድረስ የተጠቀመበትን የውሃ ፍጆታ ክፍያ አለመክፈሉን ገልጾ ብር 556.79 (አምስት መቶ ሃምሳ ስድስት ብር ከሰባ ዘጠኝ ሳንቲም) እንዲከፍል ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ በመልሱም አመልካች ክስ ለመመስረት የሚያስችለው የውል ወይም የሕግ ግንኙነት የሌለው መሆኑን ክሱም በይርጋ የሚታገድ መሆኑንና ሂሳቡ ካልተከፈለ ደንበኝነቱን ሳያቋርጥ ቆይቶ ክስ መመስረቱ አግባብ አለመሆኑን ጠቅሶ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤትም የተጠሪን የክርክር ነጥቦች ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግ ተጠሪን ለክሱ ኃላፊ አድርጐ ለክሱ መሠረት የሆነውን ገንዘብ (ብር 556.79) እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የውሃ ፍጆታ ክፍያ ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) መሠረት ተቀባይነት የለውም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ ጉዳዩ በሰበር አቤቱታ የቀረበለት የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎትም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡



www.chilot.me

የአመልካች ነገረ ፈጅ ጳጉሜ 05 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 ድንጋጌና የደንብ ቁጥር 31/1994 ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸው መሆኑን በመዘርዘር ውሳኔው እንዲሻር እና ተጠሪ የውሃ ፍጆታ ሂሳቡን እንዲከፍል ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚየሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጐለት ቀረቦ በነገረ ፈጁ አማካኝነት የፁሑፍ መልሱን ሰጥቷል፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅም የመልስ መልሱን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ዋናው የህግ ትርጉም የሚያስፈልገው ጉዳይ፡- የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ድንጋጌ ለውሃ ፍጆታ ሂሳቡ(ገንዘብ) አግባብነት አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ መስጠት ይቻል ዘንድ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ድንጋጌን በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 በጠቅላላው ሲታይ በሕግ የሕሊና ግምት የሚሸፈን የፍሬ ነገር ነጥብ (Legal Presumptions) የሚመለከት ሲሆን ዓይነቱም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2025 እና 2026 ድንጋጌዎች ጋር ተዛምዶ ሲታይ ውስን የሆነ የማስተባበያ ማስረጃ የሚቀርብበት (not freely rebuttable or rebuttable but in a limited way) የሕግ የህሊና ግምት ነው፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 የተለያዩ የክፍያ አይነቶችን የሚዘረዝር ሆኖ በጠቅላላው ሲታይ ግን በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊከፈሉ የሚገቡ ክፍያዎች (እዳዎች) በዚሁ የሁለት አመት ጊዜ ውስጥ ሳይጠየቁ የቀሩ እንደሆኑ ክፍያውን (እዳውን) የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ወገን የተባለውን ክፍያ (እዳ) እንደከፈለ የሕግ ግምት እንደሚወሰድበት ያስገነዝባል፡፡ ድንጋጌው የውሃ ፍጆታ ሂሳቡን ለይቶ አላስቀመጠም፡፡

ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነትና ተፈጻሚነት ያለው ድንጋጌ ተብሎ በተጠሪ የሚጠቀሰውን በስር የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ሆነ ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀባይነት ያገኘው በፍ/ሕ/ቁጥር 2024 ድንጋጌ በፊደል (ረ) ስር የተመለከተው የክፍያ ግምት ሲሆን ሙሉ ይዘቱም በሚከተለው መልኩ የተቀመጠ ነው፡፡

ቁ. <u>2024 በሁለት አመት የተወሰነ ጊዜ</u>

እዳው እንዲከፈል መጠየቅ ከሚገባበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ሳይከፈል የቀረ ገንዘብ እንደተከፈለ የሚቆጠረው፡-

(ረ) በብድር ለተሰጠ፣ የገንዘብ ወለድና በጠቅላላውም የዓመት ጊዜ ተወስኖለት በየዓመቱ ወይም ከዚህ ባነሰ የጊዜ ውሳኔ ውስጥ ሊከፈል የሚገባው ዕዳ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡ የዚሁ ድንጋጌ የእንግሊዝኛ ቅጂም፡-

Art. 2024 presumption of payment after two years

The following debts shall be deemed to have been paid where two years have elapsed since they fell due:

(f) interest on loans and generally any sum payable annually or at shorter periodical intervals. በሚል ተቀምጧል፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው ድንጋጌ ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው የድንጋጌው መጀመሪያ ፖራግራፍ የመክፈያ ጊዜያቸው ከደረሰ ጊዜ አንስቶ ሁለት አመት ያለፋቸው እዳዎች (ክፍያዎች) እንደተከፈሉ ይቆጠራሉ የሚል ሲሆን በተከታይ የተዘረዘሩት ንዑስ ድንጋጌዎች ደግሞ የሚወሰንባቸውን የክፍያ (እዳ) ዓይነቶችን የሚዘረዝር ነው፡፡ በድንጌጋው ፊደል (ረ) ስር የተመለከተው ሲታይ በብድር የተሰጠ ወይም ለማናቸውም የአከፋፈል ሁኔታ በየአመቱ ወይም ከአመት ባነሰ ጊዜ እየተከፈለ እንዲያልቅ ጊዜ ተቆርጦለት የተሰጠ ገንዘብ ላይ የሚታሰብ ወለድ እዳው ከበሰለበት ወይም በየተወሰነ ጊዜ የሚከፈል ገንዘብ ከሆነ ደግሞ ገንዘቡ ተከፍሎ ማለቅ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት ያለፈ እንደሆነ በእነዚህ ክፍያዎች (እዳዎች) ላይ ሊጠየቅ የሚችለው የወለድ ክፍያ እንደተከፈለ የሕግ ግምት የሚወሰድ መሆኑን ያሳያል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚነት የሚኖረው በብድር ለተሰጠ የገንዘብ ወለድ ላይ ሲሆን ዋናው የብድር ገንዘብን የማይጨምር መሆኑን የድንጋጌው ይዘትና አቀራረጽ ያስገነዝባል፡፡ ምክንያቱም ድንጋጌው ዋናውን የብድር ገንዘብ የሚጨምር ቢሆን ኖሮ የብድር ገንዘብና ወለድ በማለት ያስቀምጠው ነበር እንጂ ለብቻው ነጥሎ የብድር ገንዘብ ወለድን በማለት አይጽፈውም ነበር፡፡ ይህ ስለመሆኑም ይህ ችሎት በሰመ/ቁጥር 29181 እና የሠ/መ/ቁጥር 35758 በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) መሠረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ድንጋጌ አግባብነት የሚኖረው ለብድር ገንዘብ ወለድ እንጂ ለዋናው የብድር ገንዘብ አይደለም፣ የውሃ ፍጆታ ሂሳብም ብድር ባለመሆኑ ከመነሻውም ድንጋጌው አግባብነት ሊኖረው አይችልም፡፡

ሌላው ስለክፍያ ግምት የሚያወሳው ድንጋጌ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2023 ሲሆን ይህ ድንጋጌ የስድስት ወር ጊዜ ማለፉ ክፍያው እንደተፈጸመ ያስቆጥራል በሚል የተቀመጠ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ የስድስት ወር ማለፍ ገንዘቡ እንደተከፈለ የሚያስቆጥርባቸው ሁኔታዎችን ለይቶ አስቀምጧል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ስር የወርሃዊ የውሃ ፍጆታ ሂሳብ አልተመለከተም፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2023 ድንጋጌ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ እንዲሁም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2022 ድንጋጌ ሲታይም የተከፈለው እዳ ወለዶችን ወይም በተወሰነው ጊዜ የሚከፈሉትን ሌሎች የክፍያ ድርሻዎችን የሚመለከት እንደሆነ የተከፋዩን አይነት ለይቶ ሳይገልጽ ለአንዱ የክፍያ ደረሰኝ የሰጠ ባለገንዘብ ያለፈውንም ድርሻ እንደተቀበለ ይቆጠራል በማለት በንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ ያስቀመጠ ሲሆን ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ በዚህ ድንጋጌ መሠረትም ሲታይ የሚገባው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሌላው ተጠሪ ለክርክሩ መሠረት ያደረገው የደንብ ቁጥር 31/1994 አንቀጽ 19(1) ድንጋጌን ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት በክፍያ ምክንያት የውሃ አቅርቦት ከተቋረጠበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ደንበኛው የአገልግሎት ክፍያ ካልፈጸመ የደንበኘነት ውሉ ተሰርዞ ደንበኛው ለዋስትና ያስያዘው ተቀማጭ ገንዘብ ለአመልካች መስሪያ ቤት ገቢ የሚደረግበትን አግባብ ተመልክቷል፡፡ ድንጋጌው በአመልካችና በደንበኛው መካከል ስለሚኖረው የወደፊት ግንኙነትና አመልካች ሊወስደው ስለሚችለው እርምጃ ከሚያሳይ በስተቀር ደንበኛው ለተጠቀመበት የውሃ አገልግሎት ያልተከፈለ

ሂሳብ ካለ አመልካችን ለመጠየቅ አይችልም የሚል መንፈስ የለውም፡፡ በመሆኑም ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የሌለው ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የውሃ ፍጆታ ሂሳብ ከመሰረቱ ብድር አይደለም፣ የብድር ባህሪም የለውም፡፡ የውሃ ፍጆታ ሂሳብ አመልካች ለህብረተሰቡ በሚያቀርበው አገልግሎት መሠረት የሚከፈል ሲሆን መሰረቱም ውል ነው፡፡ አመልካች ክስ ያቀረበው በክሱ ላይ በተመለከተው ቤት ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት እያስተዳደረው በመሆኑ በቤቱ ለተጠቀመበት ውሃ ተጠሪ ክፍያ እንዲፈጽም ነው፡፡ ተጠሪ ቤቱን በተጠቀሰው ሕግ ተረክቤ አላስተዳድርም የሚል ክርክር የሌለው ሲሆን በቀድሞው ባለቤት ስም የገባው የውሃ ቆጣሪ ሲነሳም ችግሩ እንደደረሰበት ገልጾ ቆጣሪው እንዲመለስለት ጠይቆ ቆጣሪው የተመለሰለት መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ የተጠሪ ክርክር ከአመልካች ጋር የውሃ አቅርቦት ውል አልፈፀምኩም የሚል ሲሆን ከላይ እንደተመለከተው በስር ፍርድ ቤት ቤቱን በሕግ ተረክቦ የሚያስተዳድረው መሆኑ ካለመካዱም በተጨማሪ የውሃ ቆጣሪውን አመልካችን ጠይቆ መውሰዱ የተረጋገጠ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 235 መሠረት ጉዳዩ እንደታመነ የሚቆጠር ነው፡፡ በመሆኑም የውሃ አቅረቦቱ ተጠሪ ቤቱን በሕግ አግባብ ተረክቦ የሚያስተዳድረው እስከሆነ ድረስ መብትና ግዴታው በሕግም ሆነ በውል ለተጠሪ መተላለፉ የተረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪ ለውሃው ፍጆታ የማይጠየቅበት አግባብ የለም፡፡ ክፍያውን ስለመክፈሉ ደግሞ ተጠሪ ገልፆ የተከራከረው ነገር የለም፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜ ደግሞ ተጠሪ የክፍያ ግምት ተጠቃሚ የሚሆንበት ምክንያት የለም፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ለውሃ ፍጆታ አገልግሎት ሂሳብ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) እና የደንብ ቁጥር 31/1994 ድንጋጌዎችን መሠረት ማድረጋቸው ያላግባባ በመሆኑ እና ተጠሪም በሕጉ አግባባ ለሚያስተዳድረው ቤት የውሃ ፍጆታ ክፍያውን ለመክፈል ከሕግና ከውል የመነጨ ግዴታ ያለበት በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 03172 ሚያዝያ 05 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 10318 ሐምሌ 17 ቀን 2001 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08/09 ቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 2602 ጥቅምት 18 ቀን 2001 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
3. የውሃ ፍጆታ ሂሳብ ይከፈለን ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2022 መሠረት የክፍያ ደረሰኝ ያልቀረበበት ከሆነ በይርጋ ደንብ የሚገዛ እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር በተመለከተው የሕሊና ግምት የሚሸፈን አይደለም ብለናል፡፡
4. ተጠሪ ብር 556.79 (አምስት መቶ ሃምሳ ስድስት ብር ከሰባ ዘጠኝ ሳንቲም) ለአመልካች እንዲከፍል ብለናል፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 49635

ጥር 23 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች ፡-** ሂጦስ የገበሬዎች የህ/ሥ/ማህበር - የቀረበ የለም

**ተጠሪ ፡-** የመሥራቅ ዱቄትና ፋብሪካ - "

መዝገቡ የተቀጠረው ለጉዳዩ አወሳሰን እንዲረዳ ይቅረብ የተባለው የሥር የመጀመሪያ ደረጃ መዝገብ ቁጥር 6059 አለመቅረቡን አስመልክቶ ተገቢውን ትዕዛዝ ለመስጠት በሚል ነበር፤ ይሁን እንጂ ይኸው መዝገብ ዘግይቶም ቢሆን የቀረበ ስለሆነ ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## <u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው ግራ ቀኙ እንደአደረጉት የስንዴ ሽያጭ ውል ሳይፈፀም የቀረው በየትኛው ተዋዋይ ወገን ጉድለት ነው የሚለውን ነጥብ በውሉ ከተመለከተው የሻጭና የገዥ መብትና ግዴታ፣ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ግራ ቀኙ ስለጉዳዩ ካቀረቡት ክርክርና ማስረጃ አንፃር ለይቶ ከሚያስከትለው ውጤት ጋር ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት ሲባል ነው፡፡

ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነው የአሁን አመልካች የሂጦስ ገበሬዎች የህ/ሥ/ማህበር ያቀረበው ክስ ሲሆን፤ ይዘቱም

ታህሳስ 26 ቀን 1997 ዓ.ም በተደረገ የስንዴ ግዥና ሽያጭ ውል መሠረት በየጊዜው ለማስረከብ ከገባነው 4000(አራት ሺ.ህ) ኩንታል ስንዴ ውስጥ እስከ ጥር 27 ቀን 1997 ዓ.ም ድረስ በድምሩ 1020(አንድ ሺ.ህ ሃያ) ኩንታል አስረክበናል፡፡ ለዚሁ ለተረከበው ገዥ ዋጋውን አልከፈለም፡፡ እኛም የማስረከቡን ተግባር በማቆም ክፍያ እንዲፈፅም ብንጠይቀው እንደጥያቄው ባለመፈፀሙ ርክክቡ ዘገየ፡፡ የስንዴም ዋጋ በነዳጅ ዋጋ ጭማሪ የተነሣ ጨመረ፡፡ ይህንም የስንዴ ዋጋ ጭማሪ እራሱ በሰጠን ማስታወቂያ ጭምር አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም በእራሱ የክፍያ ግዴታ ባለመፈፀም ተግባር ውሉ ቀሪ ሆኖ ላስረከብነው የስንዴ ዋጋ ብር 168,300(አንድ መቶ ስድሳ ስምንት ሺ.ህ ሦስት መቶ ብር) ከእነ ወለዱ ጋር ይክፈል የሚል ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በተከሳሽነት የሰጠው መልስ የክፍያ ጥያቄ አቅርቦ አልተከለከለም፡፡ ውሉ ከተደረገበት ስንዴውን እስከሚያስረክብበት ድረስ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ አልተደረገም ለማስረከብ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አልቻልኩም በማለት የገለፃቸው ምክንያቶች በህጉ መሠረት እንደአቅም በላይ የሆኑ ምክንያቶች አይቆጠሩም፡፡ ስለሆነም ስንዴውን

ለማቅረብ እንቢተኛ ሆኖ ያስረከበውን ስንዴ ዋጋ ክፍያ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት መልሷል፡፡

እንደገናም የተከሳሽ ከሳሽ ሆኖ ተከሳሽ እንደውሉ ለማስረከብ በገባው ግዴታ መሠረት ባለማስረከቡ ባልተረከብነው 2980 ኩንታል ልክ የስንዴ ዋጋ በዚያው ጭማሪ የብር 447,000(አራት መቶ አርባ ሰባት ሺህ ብር) በልዩነት ጉዳዩ ደርሶብናል፡፡ ስለሆነም ቀሪውን 2980 ኩንታል ያስረክበን፤ ወይም ይህንኑ የዋጋ ልዩነት በጉዳት ኪሣራ ይክፈለን የሚል አቤቱታ አቅርቧል፡፡

የአሁን አመልካች ለዚሁ የተከሳሽ ከሳሽ አቤቱታ የሰጠው መልስ ፍሬ ቃል

ለማስረከብ የገባሁት ስንዴ እኔ የማመርተውን ሳይሆን ከማህበሩ አባላት ወይም ከአርሶ አደሩ በግዥ የሚገኘውን ነው፡፡ ለተረከበው የስንዴ ዋጋ ባለመክፈሉ ምክንያት የስንዴ ዋጋ በመጨመሩ ምክንያት የቀሪውን የማስረከብ ተግባር እንዲያቆም ተገዷል፡፡ በውሉ አንቀጽ 13 አንደኛው ወገን የገባውን ግዴታ ሳይፈፅም ቢቀር ወይም ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥም ውሉን ማፍረስ ይቻላል፡፡ ለተረከበው 1020 ኩንታል ስንዴ በወቅቱ ክፍያ ለመፈፀም ባለመቻሉ ጊዜው ተራዘመ ጊዜው ሲራዘም የስንዴ ዋጋና የነዳጅ ዋጋ በመጨመሩ ለዚሁ ጭማሪ ምክንያት የሆነው እራሱ የተከሳሽ ከሳሽ ነው፡፡ ስለሆነም ለውሉ መፍረስ ምክንያት የሆነው እራሱ በመሆኑ በተከሳሽ ከሳሽነት ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም፡፡ የጠየቀውም የጉዳት ኪሣራ መጠን በማስረጃ የተደገፈ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ክርክሩ የቀረበለት ፍ/ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ የአሁን ተጠሪ የተረከበውን 1020(አንድ ሺህ ሃያ) ኩንታል ስንዴ ዋጋ ክፍያ ያልፈፀመ መሆኑን ስላመነ ዋጋውን ብር 168,300.00(አንድ መቶ ስድሳ ስምንት ሺህ ሦስት መቶ ብር) ከጥር 20 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ለከሳሽ ይክፈል፤

በሌላ በኩል የአሁን አመልካች ቀሪውን ስንዴ ላለማስረከብ በምክንያትነት የጠቀሰው የስንዴና የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ ናቸው በሚል ስለመሆኑ እራሱ ለተከሳሽ በ10/6/97 ዓ.ም የፃፈው ደብዳቤ አስረጂ በመሆኑ ምክንያት ከክፍያ መዘግየት ጋር የሚያያዝ አይደለም፤ በተጨማሪም የክፍያ መዘግየት ለውል ማፍረስ ምክንያት የሚሆነው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1788 እንደተመለከተው የክፍያው መዘግየት የውሉን መሠረታዊ ስምምነት የነካ ሲሆን ነው፡፡ በውላቸው አንቀጽ 8 ላይም የክፍያ መዘግየት የውሉን መሠረታዊ ስምምነት የሚነካ መሆኑ አልተመለከተም፡፡ ስለሆነም የክፍያ መዘግየት ውሉን ያፈርሳል የሚለውን ክርክር ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም፤ በውሉ መሠረት ቀሪውን 2980(ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ) ኩንታል ስንዴ ያስረክብ፤ ወይም ደግሞ በአሁን ጊዜ ለአንድ ኩንታል ብር 150.00(አንድ መቶ ሃምሣ ብር) ስለመጨመሩ በቀረበው መረጃ መሠረት ለ2980 ኩንታል ብር 447,000.00(አራት መቶ አርባ ሰባት ሺህ ብር) ተከሳሽ ለከሳሽ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ወሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካች ያቀረበው የይግባኝ ክርክር በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተቀባይነት ባለማግኘቱ ለዚህ የሰበር መዝገብ መነሻ የሆነውን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

ሁለቱም ወገኖች በዚህ በሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ ያቀረቡት ክርክር ይዘት ከላይ ባጭር ባጭሩ በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡትን ለመግለፅ ከተጠቀሰው በይዘቱ የተለየ አይደለም፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርመረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአሁን አመልካች በከሳሽ ለውሉ መፍረስ ምክንያት የሆነው ገዥ መሆኑ ታውቆ ውሉ ይፍረስ ላስረከቡት ስንዴ ዋጋ ይክፈለኝ በሚል እና የአሁን ተጠሪም በተከሳሽ ከሳሽነት እንደ ውሉ ቀሪውን ስንዴ ያስረክበኝ፤ የማያስረክብ ከሆነ በሻጭ ጉድለት ምክንያት የስንዴ ዋጋ በመጨመሩ የተነሳ የታየውን የዋጋ ጉድለት በጉዳት ኪሣራ ይክፈለኝ በሚል ይከራከሩ እንጂ ሁለቱንም ወገኖች የሚያከራክራቸውን ነጥብ ለይቶ ለጉዳዩ ውሳኔ ለመስጠት አከራካሪው ነጥብ አንድ ነው፡፡ ይኸውም

እንደ ውሉ ሊፈፀም ያልቻለው በየትኛው ተዋዋይ ወገን ጉድለት የተነሣ ነው የሚለው ነው፡፡ ከዚህም ጭብጥ በመነሳት በታመነው እና የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሠረት በማድረግ ከውላቸው አንቀጾች እና አግባብነት ካለው ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደተመለከትነው ፡-

የአሁን ተጠሪ በሁለት ተከታታይ ጊዜ ለተረከበው 1020(አንድ ሺህ ሃያ ኩንታል) ስንዴ ዋጋ ያለመክፈሉን የካደው ጉዳይ አይደለም ስላልጠየቀኝ እንጂ ጠይቆ ክፍያ አልተከለከለም የሚል ክርክር ያቀርብ እንጂ በውሉ እንደተመለከተው በየጊዜው ለሚረከበው ስንዴ ዋጋውን የመክፈል ግዴታ የተጣለበት ከመሆኑ በቀር የመክፈል ግዴታው በክፍያ ጥያቄ ላይ የተመሠረተ አይደለም፡፡ በመሆኑም ሻጭ በየጊዜው የተባለውን የስንዴ መጠን የማስረከብ ግዴታ ያለበትን ያህል ተጠሪም በገዥነት በየጊዜው ለሚረከበው የስንዴ መጠን ዋጋውን የመክፈል ተነፃፃሪ ግዴታ አለበት፡፡ ይህም የሻጭና የገዥ እንደቅደም ተከተሉ በየጊዜው የተሸጠውን ነገር የማስረከብና ዋጋውን የመክፈል ግዴታቸው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በውላቸው ላይ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ይህ በየጊዜው ለሚረከበው ስንዴ ዋጋ የመክፈል ግዴታ መዘግየቱ ካላከራከረ የገዥ ብቸኛ ግዴታ በሽያጭ ለተረከበው ስንዴ ዋጋ መክፈል እንደመሆኑ መጠን ይህ የክፍያ መዘግየት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1784 በተደነገገውም ቢሆን የውሉን መሠረታዊ ስምምነት የነካ ነው ከሚባል በቀር የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ትርጉም የሚከተል አይደለም፡፡ እንደውሉ አነጋገር ክፍያ የመፈፀም ግዴታ በየጊዜው በሚደረገው ርክክብ መሠረት እንጂ ገዥ ክፍያ ሳይፈፀም በውል ማብቂያ ጊዜ አጠቃሎ የመክፈል መብት ያለው ይመስል ከፊል ክፍያ የውሉን መሠረታዊ ስምምነት ሊነካ አይችልም ወደ ሚለው መደምደሚያ የሚያደርስ አይደለም፡፡ በተለይም ሻጭ የሚሸጠውን ስንዴ ከማህበሩ አባል ከሌሎች አርሶአደረሮች በመሰብሰብ በሽያጭ የሚያስተላለፍ መሆኑን ገልፆ ሲከራከር ለዚህ ማስተባበያ ክርክር ተጠሪ አለማቅረቡ በየጊዜው ለሚደረገው ርክክብ በወቅቱ ክፍያ የማግኘት መብትና ክፍያ የመፈፀም ግዴታ የውሉ መሠረታዊ የስምምነት ክፍል መሆኑን አመላካች ነው፡፡

በውላቸው አንቀጽ 8 ላይ ገዥው በየጊዜው ለሚረከበው ስንዴ ዋጋውን የመክፈል ግዴታ ያለበት በመሆኑና አንደኛው ወገን የገባውን ግዴታ ሳይፈፅም በቀረ ጊዜ ለውል ማፍረሻ ምክንያት እንደሆነ በውሉ አንቀጽ 13 ላይ የተመለከተ በመሆኑ የገዥ ግዴታ አለመፈፀም ምን ውጤት እንደሚያስከትል በውላቸው ላይ የተቀመጠ ሲሆን፤ ይህ ስለመሆኑ በውላቸው በግልፅ አልሰፈረም እንኳ ቢባል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2278 እንደተመለከተው የተሸጠን ነገር የተረከበ ገዥ የሽያጩን ዋጋ ወዲያውኑ የመክፈል ግዴታ ያለበት በመሆኑና የሽያጩ ዋጋ ያልተከፈለው ሻጭ የተሸጠውን ነገር ሳያስረክብ በእጁ የማቆየት መብት የሚሰጠው ለመሆኑ የዚሁ ድንጋጌ ግልባጭ ንባብ ስለሚያስረዳ በተለይም ግራ ቀኙ ከያዙት ውል አንፃር ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ባለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2351(1) እንደተመለከተው ሻጭ በተከታታይ ለሁለት ጊዜ የተሸጠውን ስንዴ ሲያስረክብ በተንዳኝ ገዥ የክፍያ ዋጋውን አለመክፈሉን እንዳረጋገጠ፤ በተከታይ ለሚያስረክባቸውም ነገሮች ስለመከፈሉ ተገቢውን ስጋት የሚያሳድርና በዚህም የተነሣ ውሉን የማፍረስ መብት የሚሰጠው እንጂ ተጠሪ እንደሚለው

ተገዶ ቀሪውን ስንዴ እንዲያስረክብ ወይም ደግሞ ይህንኑ የማስረከብ ግዴታ የማይዋጣ ከሆነ የዋጋ ልዩነትን የመክፈል ግዴታ የሚጥልበት አይደለም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት ግራ ቀኙ እንደገቡት የሽያጭ እና ግዥ ውል እንዳይፈፀም ምክንያት የሆነውን የግዴታ መጓደል የፈፀመው ገዥ እንጂ ሻጭ ያለመሆኑ ግራ ቀኙ ባቀረቡት ክርክር ማስረጃ ማረጋገጡን የሥር ፍ/ቤት ተቀብሎ ሆኖም ይህ የክፍያ ግዴታ አለመሟላት ዋናውን የስምምነት አካል የነካ አይደለም በሚል መነሻ ለውሉ መፍረስ ሻጭን ኃላፊ በማድረግ የሰጠው ትርጉም ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ከላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች አፈፃፀም በአግባቡ ያላገናዘበ በመሆኑ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት እንደቅደም ተከተሉ በኮ/መ/ቁ 6059 በ8/8/2000 እና በኮ/መ/ቁ 68877 ሐምሌ 09 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ እና ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡
2. የግራ ቀኙ የሽያጭ ውል በገዥ በኩል የሚጠበቀውን የክፍያ ግዴታ ባለመፈፀም ምክንያት መፍረሱ ስለተረጋገጠ ሻጭ የአሁን አመልካች በሽያጭ ላስረከበው 1020(አንድ ሺህ ሃያ) ኩንታል ስንዴ ዋጋ ብር 168,300.00(አንድ መቶ ስድሳ ስምንት ሺህ ሦስት መቶ ብር) ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር ገዥ /የአሁን ተጠሪ/ ይክፈል ብለናል፡፡
3. ለስንዴው ሽያጭ እና ግዥ ውል መፍረስ ምክንያት ሆኖ የተገኘው ገዥ ለተረከበው 1020 ኩንታል ዋጋ ክፍያ በጊዜው ባለመክፈሉ የተነሣ በመሆኑ እንጂ በሻጭ በኩል በታየ የግዴታ አለመፈፀም ምክንያት ባለመሆኑ ሻጭ የአሁን አመልካች ለገዥው ለአሁን ተጠሪ ቀሪ ስንዴውን የማስረከብም ሆነ ቢያስረክብ ታዩ የተባለውን የዋጋ ልዩነት በጉዳት ኪሣራ መልክ የመክፈል ግዴታ የለበትም ብለናል፡፡

በዚህ ሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ ያደረጉት ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

የሥር ፍ/ቤቶች መዝገቦች በመጡበት ሁኔታ ይመለሱ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡***

ራ/ታ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ/55229

ጥር 09 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- ወ/ሮ መሐዳ ዑመር

**ተጠሪ** ፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የአርሲ ቅርንጫፍ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለሰበር የቀረበውን ጉዳይ በተመለከተ በመጀመሪያ ያየው የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበሩት የአሁኗ አመልካች የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ዕዳውን ሳይከፍል ከቀረ የገበሬ ማህበር ተረክቦ ለእኔ ያስተላለፈልኝ ማሽን ጉድለት የሌለበት መሆን ሲገባው ከጉድለቱ ጋር ስላስተላለፈልኝ ተከሣሹ ባንክ ከእኛ የወሰደውን ብር 40,000 /አርባ ሺህ ብር/ መመለስ ይገባዋል በሚል ባቀረቡት ክስና ክርክር መሠረት ተከሣሹ ገንዘቡን ለከሣሽ መመለስ ይገባዋል በማለት የወሰነ ሲሆን በባንኩ /በአሁኑ ተጠሪ/ የይግባኝ አቤቱታ መነሻ ጉዳዩ ቀርቦለት የተመለከተው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ደግሞ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ መርምሮ ባንኩ የክስ መቃወሚያ አድርጐ ያቀረበውን የይርጋ ክርክር የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሳያየው አልፎ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ መክፈል አለበት ብሎ የወሰነው ያለአግባብ ነው፡፡ ከተነሣው የይርጋ ክርክር አንፃር ሲታይ ክሱ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1845 መሠረት በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ሽሮታል፡፡

የአሁኗ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን ሊያቀርቡ የቻሉ ቢሆንም ጠቅላይ ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የሰበር አቤቱታው በዚህ ምክንያት የቀረበ ነው፡፡

አመልካች ክሱ በ10 ዓመት ይርጋ ይታገዳል በሚል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶች ሚያዚያ 18 ቀን 2002 ዓ.ም. በተጻፈ ማመልከቻ ገልፀው አቅርበዋል፡፡



www.chilot.me

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ይታይ በመባሉ ማመልከቻው ለተጠሪው ተልኮ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

በተጠሪው በኩል በጽሑፍ በቀረበው መልስ ላይ አመልካችም የመልስ መልስ ሰጥተውበት ተከራክረዋል፡፡

ይህ ችሎትም ጉዳዩን መርምሯል፡፡

የአሁኑ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ላይ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪ በይግባኙ ያላነሳውን የይርጋ ክርክር እራሱ በማንሳት ውሣኔ ሰጥቷል በሚል የገለፁትን በተመለከተ ከዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጀምሮ የይርጋው ክርክር መቅረቡን ውሣኔው ስለሚያስረዳ ተቀባይነት የለውም፡፡

በአሁኑ ተጠሪ በኩል የይርጋ ክርክር መቅረቡ ስለተረጋገጠ የአሁኗ አመልካች በተጠሪው ላይ ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል የተባለው በአግባቡ መሆን አለመሆኑ ሲመረመር፡-

የአሁኗ አመልካች ተጠሪው ለእኔና ለባለቤቴ መጭመቂያ ማሽን አስተላለፈልን የሚሉት ነሐሴ 14 ቀን 1985 ዓ.ም. በተደረገ ውል ሲሆን ተጠሪው ከሌላ ገበሬ ማህበር በዕዳ ምክንያት የተረከበውን ማሽን ስለዋጋው አከፋፈል በውሉ ላይ በማመቻቸት ከፍለን የራሳችን በማድረግ እንድናስቀረው አስተላለፈልን በማለት የሚገልጹት ሽያጭ እንጅ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው አይደለም፡፡ አመልካች በውል ተላልፎልኛል የሚሉትን ማሽን እንደተረከቡ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2291 መሠረት በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲመረመር በማድረግ ጉድለት ያለበት ሆኖ ከተገኘ በዚሁ ሕግ ቁጥር 2292 መሠረት ለተጠሪው ማስታወቅ ነበረባቸው፡፡ ካስታወቁ በኋላም በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2298/1/ ላይ በተገፀው መሠረት ክስ ማቅረብ ይችሉ የነበረው ካስታወቁበት ቀን አንስቶ እስከ አንድ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ክስ ካላቀረቡ ዕቃው ጉድለት ያለበት ነው ብለው የመክሰስ መብታቸውን ያጣሉ፡፡ አመልካች በማሽኑ ላይ ጉድለት ስለመኖሩ በሕጉ መሠረት በአጭር ጊዜ ለተጠሪው አስታውቀው በተወሰነው የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ክስ ማቅረብ ቀርቶ የፈፀሙት አንድም ነገር ሣይኖር ከአሥራ ሁለት ዓመት ቆይታ በኋላ ተጠሪው ያስረከበን ማሽን ጉድለት ስላለበት የከፈልነውን ብር 40,000 /አርባ ሺህ ብር/ ይመልስልን የሚል ክስ አቅርበዋል፡፡ አሥር ዓመት ወደሚለው የይርጋ ክርክር መሄድ ሳያስፈልግ አመልካች ማሽኑን እንደተረከቡ በአጭር ጊዜ እንዲመረመር አድርገው ጉድለት ያለው ስለመሆኑ ለተጠሪው በማሳወቅ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ማሽኑ ጉድለት ያለበት ነው የሚለውን ክስ ያላቀረቡ ስለሆነ የመክሰስ መብታቸውን አጥተዋል፡፡

የይርጋው ጊዜ ተቋርጦ ቆይቷል በሚል ያነሱትን ክርክር በሚመለከት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ በሚያይበት ጊዜ እንዲህ ዓይነት ክርክር ያላቀረቡ ሲሆን የይርጋው ጊዜ ተቋርጦ ቆይቷል የሚለውን ክርክር ያነሱት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ባቀረቡት ይግባኝ ላይ ነው፡፡ ጠቅላይ ፍ/ቤቱም በሥር ፍ/ቤት ያልቀረበ አዲስ ክርክር በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 329 መሠረት ሊታይ የሚችል አይደለም ብሎ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ ፍ/ቤቱ በዚህ ረገድ ፈጽሟል የሚባለው የሕግ ስህተት የለም፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጉዳይ የአሁኗ አመልካች ተጠሪው አስተላልፎልን የነበረው ማሽን ጉድለት ስላለበት የከፈልነውን ገንዘብ ብር 40,000 ይመልስልን በሚል ያቀረቡት ክስ በይርጋ የታገደ ነው በሚል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የሰበር አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 56252

ጥር 24 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች** ፡- ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- ተስፋዬ አበበ ሥራ ተቋራጭ - አልቀረቡም

**ተጠሪ** ፡- ማዕረጉ ወርቁ ሥራ ተቋራጭ - ጠበቃ ተካ ዳባ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ በስር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ በምዕራብ አርሲ ዞን በገደብ አሣሣ ወረዳ ጥጆ ዋቄንጥረ ከሚባለው ሥፍራ የሚሰራውን የጤና ኬላ ለመገንባት በጨረታ ተወዳድሮ አሸንፏል፡፡ ተጠሪ ይህንን ግንባታ ራሱ ለማከናወን ስላልፈለገ ህንፃውን እኔ ሙሉ በሙሉ እንድሠራለት በተወካዩ በኩል ተዋውሏል፡፡ እኔም ለተጠሪ ኮሚሽን ብር 50,000 /ሀምሣ ሺህ ብር/ ከፍዬ ውሉን በተዋዋልንበት ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ.ም. የግንባታ ቦታውን አስረክቦኝ ሥራውን ሠርቻለሁ፡፡ ሆኖም ተጠሪ ለተሠራው ሥራ ከምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ የተከፈለውን ብር 240,000 /ሁለት መቶ አርባ ሺህ ብር/ ከተቀበለ በኂላ ለእኔ መስጠት ሲገባው ራሱ የወሰደ በመሆኑ ይህንን ገንዘብ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የእኔ ወኪል የዚህ አይነት ውል ለመዋዋል ሥልጣን የለውም፡፡ አመልካች የውክልና ሥልጣን ከሌለው ሰው ጋር አደረግሁ የሚለው ውል ህግን የሚቀረን ነው፡፡ አመልካች ህንፃውን አንድም ቀን አልሠራም፡፡ የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በራሱም ሆነ በወኪል አማካኝነት በራሱ ለመገንባት ተጫርቶ ያሸነፈውን የህንፃ ሥራ ውል ለአመልካች አሣልፎ የመስጠት ሥልጣን የለውም፡፡ በውሉ ላይ አሠሪው የህንፃው ባለቤት የምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ አልተስማማም፡፡ ስለሆነም አመልካች /ከሣሽ/ ያቀረበው ክስ ህጋዊ መሠረት የለውም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ግንቦት 17 ቀን 2002 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በጨረታ ተወዳድሮ ያሸነፈውን ጤና ኬላ ሠራተኛ ቀጥሬና የሚያስፈልገውን የግንባታ ዕቃ አሟልቼ እንድሠራ በወኪሉ አማካኝነት ውል በመፈረምና ብር 50,000 /ሀምሣ ሺህ ብር/ ኮሚሽን በመቀበል ተዋውሏል ውሉን ስንዋዋል የአሠሪው የምዕራብ አርሲ ጤና መምሪያ ተቆጣጣሪ መሀንዲስ የነበረ ሲሆን ተቆጣጣሪ መሐንዲሱ ባለበት የግንባታውን ቦታ ተረካክበናል፡፡ ለስራው በተሰጠው ንድፍና ቢል ኦፍ ኳንቲቲ መሠረት ስራውን የሠራሁት እኔ ስሆን አሠሪውም የተሠራውን ሥራ ሲያፀድቅ ቆይቷል፡፡ ሠራተኛ ቀጥሬ የግንባታ ዕቃዎችን በራሴ ወጭ አቅርቤና አሟልቼ የሠራሁትን ሥራ ለአሰሪው በማስረከብ የክፍያ ሰርተፍኬት የተቀበለው ተጠሪ ወኪሉ የግንባታውን ሥራ ለሌላ ለማሳለፍ ስልጣን የለውም በማለት ያቀረበውን ክርክር በመቀበል የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ስለግንባታ ሥራ ውል የተደነገጉ መሠረታዊ የአሠራር መመሪያን የሚፃረርና የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ውሉ ሥልጣን በሌለው ተወካይ በኩል የተደረገ ነው፡፡ አመልካች የግንባታ ሥራውን የሠራ መሆኑን የሚያስረዱ ማስረጃዎችን ያላቀረበ መሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ተገጋግሟል፡፡ ስለዚህ አመልካች ክርክሩን በማስረጃ በአግባቡ ሣያስረዳ በሰበር አቤቱታው አዲስ ክርክር ማቅረቡ ተገቢ አይደለም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ጥቅምት 22 ቀን 2003 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ በሰበር አቤቱታው ያነሣቸውን የመከራከሪያ ነጥቦች በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ያቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ለግንባታ አስፈላጊ የሆነውን የግንባታ ዕቃ በማሟላትና ሠራተኛ በመቅጠር ለሠራሁት ሥራ ተጠሪ ክፍያውን ሊሰጠኝ ይገባል በማለት የቀረበው ክስ የህግ ድጋፍ እና መሠረት የለውም በማለት የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ በአግባቡ ለመወሰን በመጀመሪያ በአመልካችና በምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ እንደዚሁም በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተደርጓል የተባለውን ውል መሠረታዊ ባህሪና በህግ የሚያስከትለውን ውጤት መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ የወጣውን ጨረታ በማሸነፍ ተጠሪ በገደብ አሰሳ ወረዳ ጥጃዋቄንጥራ ከሚባለው ሥፍራ ላይ በአሠሪው በተሰጠው ንድፍና ኘላንና ቢል ኦፍ ኳንቲቲ መሠረት የጤና ኬላ ሠርቶ ለማስረከብ የግንባታ ሥራ ውል ተዋውሏል፡፡ ይህም በአሠሪው /የምዕራብ አርሲ ዞን የጤና መምሪያ/ እና በሥራ ተቋራጩ /ተጠሪ/ መካከል በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3244 ንዑስ አንቀፅ 1 በሚደነግገው መሠረት የመንግስት የሥራ ውል የተዋዋሉ መሆኑን ነው፡፡

አመልካች በእኔና በተጠሪ መካከል ተደርጓል የሚለው ውል ተጠሪ በጨረታ ያሸነፈውን የህንፃ ሥራ ሙሉ ለሙሉ ለእኔ በመልቀቅ ሥራውን እንድሠራና ዋጋው መጨረሻ ለእኔ ሊከፈል ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ.ም. ተዋውለናል የሚል ክርክር ያቀርባል፡፡ ይህ የአመልካች ክርክር በአሠሪው /በምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ/ ፈቃድና ዕውቅና ተጠሪ የህንፃውን ሥራ ለእኔ አስተላልፎልኛል የሚል ይዘት ያለው አይደለም፡፡ የግንባታ ሥራ ውል በአሠሪው ዕውቅናና ፈቃድ ሙሉ በሙሉ ለሌላ ሰው የሚለቀቅበት ወይም ለንዑስሥራ ተቋራጭ የሚሰጥበት ሁኔታ ማለትም “Nominated Assignment or Nominated sub contract” የሚደረግበት ሁኔታ እንዳለና በእኛ አገር አስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ጋር የተደረገን የሥራ ውል ሙሉ በሙሉ ለሌላ ሰው ለመልቀቅ ወይም ለንዑስ



www.chilot.me

የሥራ ተቀራጭ ለመስጠት የአስተዳደሩ መሥሪያ ቤት ፈቃድ አስፈላጊ እንደሆነ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3202 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 2 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአስተዳደሩ መስሪያ ቤት ሙሉ ዕውቅናና ፈቃድ የህንፃ ሥራ ውሉን ለሌላ ሰው በሚለቀቅበት ጊዜ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3205 የተደነገገው ውጤት የሚያስከትል መሆኑን በአስተዳደሩ ሙሉ ዕውቅናና ፈቃድ ሥራው ለንዑስ ሥራ ተቋራጭ የተሰጠ ሲሆን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3206 የተደነገገውን ውጤት የሚያስከትል መሆኑ ተደንግጓል፡፡ የአስተዳደሩ መስሪያ ቤት ተቋራጩ ሥራውን ሙሉ በሙሉ ለሌላ ሰው እንዲለቅ ለመፍቀድ ወይም ሥራውን በከፊል ለንዑስ ሥራ ተቋራጭ እንዲሰጥ ለመፍቀድ የሚችለው ውሉን ለመዋዋል ሥልጣን ባለው ባለሥልጣን በኩል መሆን እንዳለበት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3202 ንዑስ አንቀፅ 2 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ስናየው አመልካች ከተጠሪ ጋር ውል የተዋዋልኩት የአሠሪው /የምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ/ ተቆጣጣሪ መሀንዲስ ባለበት ስለሆነ የህንፃ ሥራ ውሉን ለተጠሪ ለመልቀቅ የተስማማው በአሠሪው ዕውቅናና ፈቃድ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ ድጋፍና መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ውሉ በአመልካችና በተጠሪ መካከል በአግባቡ ተደርጓል ወይስ አልተደረገም የሚለው ጭብጥ ወደፊት የሚታይ ሆኖ በአመልካችና ተጠሪ መካከል ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ.ም. ተደርጓል ተብሎ የአመልካች መከራከሪያ የሆነው ውል በባህሪው ከአሠሪው ማለትም የአስተዳደር መሥሪያ ቤት ከሆነው የምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ ፈቃድ ውጭ የተደረገ የህንፃ ሥራን የመልቀቅ ውል / Unnominated Assignment of Contract of work / ነው፡፡ ተቋራጩ የአስተዳደር መሥሪያ ቤቱ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3202 ንዑስ አንቀፅ 2 በሚደነግገው መሠረት ሣይፈቅድለት የህንፃውን ሥራ ሙሉ በሙሉ ለሌላ ሰው ቢለቅ ውጤቱ ምን ይሆናል የሚለውን ጥያቄ መልስ ማግኘት ያለበት ነው፡፡ የሥራ ተቋራጩ ከአሠሪው ፈቃድ ውጭ ሥራውን ሙሉ በሙሉ ለሌላ ሰው ቢለቅ ወይም ለንዑስ ሥራ ተቋራጭ ቢሰጥ፣ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3205 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3206 የተደነገጉትን ህጋዊ ውጤቶች በተቋራጩና በሌላ ሶስተኛ ወገን መካከል የሥራ ውልን ለመልቀቅ ወይም ንዑስ የሥራ ውል ለመዋዋል የተደረገው ውል በአስተዳደሩ መሥሪያ ቤት ላይ ግዴታ የሚያስከትልበት አይደለም፡፡ የአስተዳደሩ መስሪያ ቤት መብቱን የሚጠይቀውም ሆነ ግዴታውን የሚወጣው ለሥራ ተቋራጩ ሲሆን የአስተዳደሩ መሥሪያ ቤት ግንኙነት ከሥራ ተቋራጩ ጋር ብቻ የሚወሰን መሆኑን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 3205 እና ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 3206 የተቃርኖ ንባብና ትርጉም " Acontrario reading and Interpretation " ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ ተቋራጩ አሠሪ የሆነው የአስተዳደር መሥሪያ ቤት ሣይፈቅድለት ሥራውን ለመልቀቅ ያደረገው ውል ወይም ለንዑስ ተቋራጭ ጋር ያደረገው ንዑስ የሥራ ውል በአስተዳደሩ መሥሪያ ቤት ላይ መከራከሪያና መቃወሚያ ሊሆን እንደማይችል በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3204 ንዑስ አንቀፅ 1 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ በተቃራኒው የሥራ ተቋራጩ የአስተዳደር መሥሪያ ቤቱ ሣይፈቅድለት የሥራ ውሉን ለሌላ ሰው ለመልቀቅ በመዋዋሉ ወይም ንዑስ የስራ ውል መዋዋሉ እንደ ጥፋት ተቆጥሮ የአስተዳደር መሥሪያ ቤቱ ውሉን ለማፍረስ የሚያስችለው በቂ ምክንያት እንደሆነ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3204 ንዑስ አንቀፅ 2 በግልፅ ይደነግጋል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አሰሪው የምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3202 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ሣይፈቅድ ተጠሪና አመልካች ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ.ም. አደረጉት የተባለው ውል አመልካች በአሠሪው በምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ ላይ በቀጥታ



www.chilot.me

መከራከሪያ አድርጎ ሊያነሣው የማይችል መሆኑ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 3204 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አሠሪው የምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ የሥራው ተቋራጭ ከሆነው ከተጠሪ ጋር አድርጎት የነበረውን የህንፃ ሥራ ውል ለማቋረጥ የሚያስችለው በቂ ምክንያትና ጥፋት እንደሆነ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3204 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ የአሠሪው ፈቃድና ስምምነት አለመኖር ከላይ ከተገለፀው ሁኔታ አልፎ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተደርጓል የተባለውን ውል በመካከላቸው አስገዳጅነትና ምንም አይነት ህጋዊ ውጤት የማያስከትል ውል አያደርገውም፡፡ ስለሆነም በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተደርጓል የተባለውን ውል በመካከላቸው አስገዳጅነትና ምንም አይነት ህጋዊ ውጤት የማያስከትል ውል አያደርገውም፡፡ ስለሆነም በአመልካችና በተጠሪ መካከል ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ.ም. ተደርጓል የተባለው ውል ላይ አሠሪው /የምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ/ ፈቃድና ስምምነቱን አለመስጠቱ ውሉ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ምንም አይነት መብትና ግዴታ የማይፈጥር ፈራሽና ውጤት አልባ ያደርገዋል በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የህግ ትርጉምና ውሣኔ ከላይ በዝርዝር ያየናቸውን ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ እና የሚያስከትሉትን ህጋዊ ውጤት ያላገዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. የጤና ኬላው ህንፃ አሠሪ የሆነው የምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ ከሥራ ተቋራጩ ተጠሪ ጋር በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3244 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ያደረገውን ህንፃ ሥራ ውል የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3204 ንዑስ አንቀፅ 2 በሚደነግገው መሠረት አላፈረሰም፡፡ በአንፃሩ አሠሪው የተሠራውን የጤና ኬላ በመረከብ ለሥራ ተቋራጩ/ተጠሪ/ የክፍያ ሰርተፊኬት በመሥራት ብር 240,000 /ሁለት መቶ አርባ ሺህ ብር/ የከፈለ መሆኑን ከግራ ቀኙ ክርክር ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ተጠሪ የህንፃ ሥራውን ለአመልካች ለመልቀቅ ከአሠሪው ፈቃድ ውጭ ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ.ም. አድርጎታል የተባለው ውል አመልካች በማናቸውም መልኩ አሠሪውን የምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ ለመጠየቅ የማያስችለው ቢሆንም ውሉ መኖሩና በአግባቡ መፈጸሙ ከተረጋገጠ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1731 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የህግ አስገዳጅነት ያለው ነው፡፡

ተጠሪ ከአመልካች ጋር የጤና ኬላ ህንፃ ሥራ ውሉን ለመልቀቅ የተደረገ ህጋዊ ውል ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ.ም. አላደረግሁም፡፡ የእኔ ተወካይ ይህንን ውል የተዋዋለው ከተሰጠው የውክልና ሥልጣን ውጭ ነው በማለት በሥር ፍርድ ቤት የተከራከረ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤት ይህንን ምክንያት የአመልካችን ክስ ውድቅ ለማድረግ ጠቅሶታል፡፡ ሆኖም ተጠሪ ተወካይ ከውክልና ሥልጣኑ ውጭ ነው የተዋዋለው የሚለውን የህንፃ ሥራ የመልቀቅ ውል ተጠሪ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2107 ድንጋጌዎች መሠረት የማፅደቅ ግዴታ አለበት ወይስ የለበትም? የሚለው ጭብጥ የበታች ፍርድ ቤቶች የግራ ቀኙን ክርክር ማስረጃና የግንባታ ሥራን ልዩ ባህሪ መሠረት በማድረግ ጭብጥ መመሥረትና መወሰን ይገባቸው የነበረ መሆኑን ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 248 ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ይህንን መሠረታዊ ጭብጥ ሣይመሠርቱና ውሣኔ ሣይሰጡበት አልፈዋል፡፡ ይህንን ጭብጥ በአግባቡ ለመወሰን፣ አመልካች ለተጠሪ በኮሚሽን መልክ ከፍየዋለው የሚለው ብር 50,000 /ሀምሣ ሺህ ብር/ ተጠሪ ተቀብሏል ወይስ አልተቀበለም? ተጠሪ የግንባታ ሥፍራውን ሙሉ በሙሉ ለአመልካች አስረክቦ ነበር ወይስ አልነበረም? ለጤና ኬላው ግንባታ የሚያስፈልገውን ሠራተኛ በመቅጠርና ለግንባታው አስፈላጊ የሆነውን ዕቃ በማሟላት ግንባታውን ያከናወነው አመልካች ነው ወይስ አይደለም? አመልካች የሠራው የግንባታ ሥራ አለ ከተባለ ተጠሪ አመልካች የሠራውን ሥራ አሠሪው የምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ እንዲረከበው በማድረግ ክፍያ እንዲፈፀምለት አሠሪውን



www.chilot.me

ጠይቋል ወይስ አልጠየቀም የሚሉት ነጥቦች ፍርድ ቤቱ በተከራካሪ ወገኖች የሚቀርቡ ማስረጃዎችንና እውነቱን ለማውጣት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 145/1/ በማስቀረብ ጭምር በማጣራት ውሣኔ ሊሰጥባቸው የሚገቡ ነጥቦች ናቸው፡፡ በያዝነው ጉዳይ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመወሰን አስፈላጊ የሆኑትን ከላይ የተገለፀውን ጭብጥ ሣይመሰርትና ፍሬ ጉዳዩን ሣያጣራ ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ.ም. የተደረገውን ውል የተዋዋለው የተጠሪ ወኪል ከሥልጣኑ ውጭ የፈፀመው ተግባር ነው የሚለውን ነጥብ ብቻ በማየት የሰጠው ውሣኔ በውሉ መሠረት አመልካች ግዴታውን ፈፅሞና የግንባታ ሥራ ሠርቶ ከሆነ ውጤቱ ምን ይሆናል ለሚለው መሠረታዊ ጥያቄ እልባት ያልሰጡ በመሆኑ ውሣኔው መሠታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አከራካሪውን የጤና ኬላ የሰራው ማን ነው? የሚለውንና ከላይ በዝርዝር ያስቀመጥናቸውን ነጥቦች ዙሪያ አመልካችና ተጠሪ የሚያቀርቡትን ክርክርና ማስረጃ በመቀበልና ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልስን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

ጽ/ሽ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 43226

የካቲት 7 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገብረሥላሴ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ጌታ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ ስላቀረበ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በከሣሽነት ቀርቦ በሥር ተከሣሽ የነበረው ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 97/1990 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የአዲስ አበባ ዱቄት ፋብሪካን ለመሸጥ የሐራጅ ማስታወቂያ አውጥቶ ነበር፡፡ በሐራጅ ማስታወቂያው መሠረት ተወዳድሬ ጨረታውን በማሸነፌ ታህሣሥ 23 ቀን 1993 ዓ.ም በተፃፈ ሽያጭ ውል ፋብሪካውን በብር 42,500,100.99/አርባ ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ አንድ መቶ ብር ከዘጠና ዘጠኝ ሣንቲም/ ገዝቻለሁ፡፡ አከፋፈሉን በተመለከተ ብር 10,625,025.50 /አስር ሚሊየን ስድስት መቶ ሃያ አምስት ሺ ሀያ አምስት ብር ከሀምሣ ሣንቲም/ ተከፍሏል፡፡ ቀሪው ብር 31,825,025 /ሠላሣ አንድ ሚሊየን ስምንት መቶ ሃያ አምስት ሺ ሀያ አምስት ብር/ ተከሣሽ በሚሰጠው ብድር ለመክፈል የካቲት 17 ቀን 1993 ዓ.ም ከተከሣሽ /ተጠሪ/ ጋር የብድር ውል ተዋውለናል፡፡ ከተከሣሽ /ተጠሪ/ ለተወሰደው ብድር ከሣሽ ሠላሣ ሠባት መኪናዎችን በመያዣ ውል አስይዟል፡፡ ሆኖም የፋብሪካው ሽያጭ የባንኩን አሻሻጥ ደንብ የተከተለ አይደለም በማለት የባንኩ ኢንስፔክተሮች ሐምሌ 23 ቀን 1993 ዓ.ም ባቀረቡት ሪፖርት ፋብሪካው በተጠሪ በመያዣነት ያልተያዘ መያዣውም የተመዘገበ አይደለም ተብሎ የተከሣሽ /ተጠሪ/ ድርጅት ሥራ አስኪያጆችና የከሣሽ /አመልካች/ ድርጅት በወንጀል ተከሰው የከሣሽ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ በነፃ ተሰናብተዋል፡፡ ስለዚህ የሽያጭ ውል የማይፀናና ውል ለመዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት ያልተደረገ በመሆኑ የብድርና የመያዣ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ ይወሰንልን በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በተከሣሽነት ቀርቦ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለውም፡፡ ሽያጩ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት ያለው የተሸጠው ንብረት ባለቤት የሆኑት አስር አለቃ ወ/ሃይማኖት ስርቋ እንጅ ከሣሽ /አመልካች/ ክስ የማቅረብ መብት የለውም፡፡ ከሣሽ /አመልካች/ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስልኝ በማለት ጥያቄ ያቀረበው በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት



www.chilot.me

ሕግ ቁጥር 447/1/ የተደነገገው የሁለት ወር ጊዜ ካለፈ በኋላ ነው፡፡ ጥያቄው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1810 የተደነገገው የሁለት ዓመት የይርጋ ገደብ ካለፈ በኋላ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡

አመልካች ተጠሪ/ ተከሣሽ/ ፋብሪካ የሸጠልን በመሆኑና የሸጠልኝ የፋብሪካ ላይ ሽያጭ ውል ሊፈፀም የማይችል በመሆኑ ክስ የማቅረብ መብት አለኝ፡፡ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አለው የሚል ሰፊ ክርክር አቅርቧል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ከሰማና ያቀረቡትን የጽሑፍ ክርክርና የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ክስ ተቀብሎ የማከራከርና ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን አለው፡፡ ከሣሽ /አመልካች/ ክስ ለማቅረብ መብት አላቸው በማለት ብይን የሰጠ ሲሆን በተጠሪ በኩል የቀረበውን የሁለት ወር የይርጋ ጊዜ መቃወሚያ በመቀበል በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 6 ባንክ በመያዣ ሲሸጥ ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 394-449 የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ተፈፃሚነት እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡ ከሣሽ መብት የሌለውን ንብረት ነው የሸጠልኝ በማለት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 446 መሠረት ሽያጩ እንዲሰርዝ የሚያቀርቡት ጥያቄ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 447/1/ የተደነገገው የሁለት ወር ጊዜ ካለፈ በኋላ የቀረበ በመሆኑ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን በድምጽ ብልጫ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ታህሣሥ 1 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ከተጠሪ ጋር የተደረገው የፋብሪካ ሽያጭ ውልና የመያዣ ውሉ ቀሪ እንዲሆንና የጠየቅሁት የባንክ ኢንስፔክሽን ተጠሪ ንብረቱን የሸጠው የመያዣ መብት ሣይኖረው ነው በማለት በጽሑፍ የሰጠውን ማረጋገጫ በማስረጃነት በመያያዝ ነው፡፡ ውሉ ሕግን የሚቃረን ውል ከሆነ በይርጋ የማይታገድ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለሕግ ተቃራኒ የሆነ ውል ቀሪ እንዲሆን የሚቀርብ ጥያቄ በይርጋ የማይታገድ መሆኑን ሣይገነዘብ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ማጽናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 344 እስከ ፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 449 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ለጉዳዩ ተፈፃሚ የሚሆኑት በመጀመሪያ ተጠሪ በንብረቱ ላይ የመያዣያ መብት ሲኖረው ነው፡፡ ተጠሪ በንብረቱ ላይ የመያዣ መብት ሣይኖረው የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ሆነ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አብላጫው ድምጽ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 447/1/ን በመጥቀስ የሰጡት ውሣኔ የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ስለዚህ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ሐምሌ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ለአመልካች በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት የዱቄት ፋብሪካውን የሸጥነው የፋብሪካው ባለቤት ለሆኑት አስር አለቃ ወልደሀይማኖት ስቋር የሰጠነው ብድር ባለመከፈሉና የፋብሪካውን ሕንፃ በመያዣነት በክልል 14 መስተዳድር ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ አስመዝግበን ስለያዝነው ነው፡፡ ማሽነሪዎቹንና ተሽከርካሪዎቹን በተመለከተ በመያዣነት የያዛቸው አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ በሰጠን ውክልና መሠረት ሸጠናል፡፡



www.chilot.me

ስለዚህ አመልካች በዚህ በኩል የሚያቀርበው ክርክር ተገቢ አይደለም ይህም በመሆኑ ለጉዳዩ የአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 6 በሚደነግገው መሠረት ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 339 እስከ ፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 449 የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ተፈፃሚነት አላቸው፡፡ ስለሆነም የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ሆነ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ግራ ቀኙ ለሰበር ችሎት በጽሑፍ ካቀረቡት ክርክር በተጨማሪ ችሎቱ የአመልካችንና የተጠሪን የቃል ክርክር ሐምሌ 15 ቀን 2001 ዓ.ም የሰማ ሲሆን የቃል ክርክሩ ወደ ጽሑፍ ተቀይሮ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ የአመልካችና ተጠሪ የቃል ክርክር በይዘቱ በጽሑፍ ካቀረቡት ክርክር ጋር ተመሣሣይነት ያለው ሲሆን አመልካች ሕገወጥ የሆነ ውል እንዲፈርስ የሚቀርብ ጥያቄ በጊዜ ገደብ አይታገድም የሚል መሠረታዊ የሕግ መርህ አለ፡፡ለምሣሌ በዚህ ዘመን የባሪያ ንግድ አይፈቀድም፡፡ ባሪያ ነግዳለሁ ብሎ ተዋውሎ ቢገኝ በሁለት ዓመት ይርጋ ታግዷል ሊባል አይችልም የሽያጭ ውሉ ሕገወጥ ስለሆነ፡፡ በዚህ ጉዳይም ተጠሪ የሱ ያልሆነውንና በአዋጅ ሊሸጠው የማይችለውን መሸጥ አይችልም፡፡ አንድ ውል ሕገወጥ ውል ነው የሚባለው በሕግ የተከለከለ ሲሆን ነው፡፡ ስለዚህ የይርጋ ክርክርና የይርጋ የሕግ ድንጋጌዎች በዚህ ጉዳይ ተጠቃሽነትም ሆነ ተፈፃሚነት የላቸውም የሚል ይዘት ያለው ሰፊ ክርክር አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የሸጥነው በመያዣ የያዝነውን ንብረት ነው ገዥ ፋብሪካውንም ተረክበው እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡ ውሉ ሕገወጥ ነው መባሉ ተገቢ አይደለም የሚል ይዘት ያለው መልስ በቃል ክርክር ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር በግራ ቀኙ በኩል የቀረበው የጽሑፍና የቃል ክርክር ይዘት ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካች ጥያቄ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 447/1/ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ያልቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጡት ውሣኔና የሕግ ትርጉም ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው መሠረታዊ ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካች ከተጠሪ ጋር የተደረገው የፋብሪካ ሽያጭ ውል ሕገወጥ የሆነ ውል /unlawfull contract/ ነው፤ ሕገ ወጥ የሆነ ውል ቀሪ ለማስደረግ የሚቀርብ ክስ በማናቸውም ጊዜ ለመቅረብ ይችላል፡፡ ሕገወጥ የሆነ ውል ቀሪ ለማድረግ በሚቀርብ ክስ ላይ በፍታብሔር ሕግም ሆነ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ የተደነገገው የጊዜ ገደብ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የላቸውም በማለት ከተጠሪ ጋር ያደረገውን የዱቄት ፋብሪካ ሽያጭ ውል ሰውን ከመሸጥና ከባሪያ ንግድ ጋር በማመሣሰል ያቀረበው ክርክር ተገቢና ሕጋዊ መሠረት ያለው መሆኑን መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሀ/ ሕገ ወጥ ውል /unlawfull contract/ ማለት በሕግ እንዲደረግ ያልተፈቀደ የሕግ ክልከላ ያለበት ውል ማለት ነው፡፡ አንድ ውል ሕገወጥ ውል ነው የሚባለው ተዋዋዮቹ የተዋዋሉበት መሠረታዊ ጉዳይ ዓላማ በመሠረታዊና ሞራላዊ ይዘቱ ተዋዋይ ወገኖች ስምምነት በማድረግ መብትና ግዴታ እንዲፈጥሩበት በሕግ ያልተፈቀደ ወይም በሕግ ክልከላ የተደረገበት ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ለምሣሌ አመልካች እንዳለው በሕገ መንግሥቱም ሆነ በአገሪቱ የወንጀል ሕግ እንደዚሁም በዓለም አቀፍ የወንጀል ሕግ ማንኛውንም ሰብዓዊ ፍጡር በግዴታ አገልጋይነት መያዝ ወይም በሰው መነገድ የተከለከለ በመሆኑ ሰውን በግዴታ አገልጋይነት ለመያዝ ወይም በሰው ለመነገድ የተደረገ



www.chilot.me

ውል በመሠረታዊ ባህሪውና ሞራላዊ ይዘቱ ሕገወጥ ውል /unlawfull contract/ ነው፡፡ አንድ ውል የተመሠረተበት መሠረታዊ ጉዳይ “object of contract” በሕግ ክልከላ የተደረገበት በሆነ ጊዜ ውሉ በሕግ ፊት እንደሌለና ምንም አይነት ሕጋዊ ውጤት የማያስከትል /void contract/ ነው፡፡ አንድ ውል በማናቸውም ሰው ወይም አካል ፈቃድና ስምምነት ሕጋዊ ውጤት እንዲኖረው ማድረግ የማይቻልና በማናቸውም መንገድ ለማስተካከልና ሕጋዊ ውጤት እንዲያገኝ ለማድረግ የማይቻል በሆነ ጊዜ ውሉ ከጅምሩ በሕግ ፊት እንዳልተደረገና እንደሌለ “Null or void contract” እንደሚሆን በዘርፉ ከተደረጉ ጥናቶች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በእኛ አገር የሕግ ሥርዓት አንድ ውል የፀና ውል ለመሆን ማሟላት ከሚገባው አንደኛው መሠረታዊ ነጥብ ውሉ ሕጋዊ በሆነ ጉዳይ ላይ የተመሠረተ መሆን የሚገባው እንደሆነ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1678 ንዑስ አንቀጽ /ለ/ ይደነግጋል፡፡ ይህንን ነጥብ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1678 ንዑስ አንቀጽ “ለ” የእንግሊዝኛው ቅጅ “The object of the contract is sufficiently defined and is possible and lawful” በማለት ከአማርኛው ቅጅ በተሻለ አገላለጽ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የውሉ መሠረታዊ ባህሪና ጉዳይ በሕግ ያልተፈቀደና ክልከላ የተደረገበት በሆነ ጊዜ ማለትም ውሉ ሕገወጥ /unlawful contract/ በሆነ ጊዜ በሕግ ፊት ውጤት እንደማያስከትል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1716 ተደንግጓል፡፡ በውጤት ደረጃ ዳኞች የውሉ መሠረታዊ ዓላማ ሕገወጥ መሆኑን ከውሉ ቃል ወይም ውሉ እንዲፈፀምለት የሚጠይቀው ተዋዋይ ካቀረበው ጽሑፍ በተረዱበት በማናቸውም ጊዜ ውሉ እንዲፈፀም የቀረበላቸውን ጥያቄ ውድቅ ለማድረግና አንቀበልም ለማለት የሚችሉ መሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1718 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የውሉ መሠረታዊ ዓላማ ወይም ጉዳይ በሕግ ያልተፈቀደና የተከለከለ ሆኖ ሲያገኙት ዳኞች ሕገወጥ /unlawful/ የሆነው ውል በቀረበላቸው በማናቸውም ጊዜ ሕጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት የለውም በማለት ለመወሰን እንደሚችሉና ሕገወጥ የሆነውን ውል ውድቅ ለማድረግ በሕጉ የተደነገገው የይርጋ የጊዜ ገደብ መቃወሚያ ሊሆን እንደማይችል ከላይ ከተጠቀስናቸው የሕግ ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ለ/ ውሉ ሲደረግ በጠቅላላ የውል ሕግና በልዩ የውል ሕግ ድንጋጌዎች ወይም በሌሎች ህጎች የተደነገገውን መስፈርት የማያሟላና ጉድለት ያለበት ሆኖ መገኘቱ ውሉ የሕጉን መስፈርት የማያሟላ “illegal contract” ያደርገዋል እንጅ ውሉን ሕገወጥ ውል /unlawfull contract/ ነው ብሎ ለመደምደም የሚያስችል አይደለም፡፡

ከባለሀብቱ በቂ የሆነ የውክልና ሥልጣን ሣይኖረው ወይም ንብረቱን ለመሸጥ የሚያስችል መብት በሌለው ሰው የተደረገ የሽያጭ ውል፣ ውሉ በሕግ የተደነገጉ አስገዳጅ መስፈርቶችን የማያሟላ ነው የዚህ ጉድለት ውሉን በፍርድ ቤት እንዲፈርስ መቃወሚያና ክርክር ሊቀርብበት የሚችል /invalid contract/ የሚያደርግ አይደለም፡፡

በሕገወጥ ውል /unlawful contract/ እና የሕጉን መስፈርት ሣያሟላ በተደረገ ውል /illegal contract/ መካከል በጽንሰ ሀሣብ ደረጃ ሰፊ ልዩነት እንዳለ በሥነ ሕግ ዙያ በተደረጉ ጥናቶች ብቻ ሣይሆን በብላክስ ሎው መዝገበ ቃላት ውስጥ “The principal distinction between the terms of lawful and legal is the former contemplates the Substance of a law, the latter the form of law.. To say an act “lawful” implies that it is authorized, sanctioned or at any rate not forbidden by law. To say it is “legal” implies that it is done or performed in accordance with the forms and usage of law, or in a technical manner;



www.chilot.me

in this sense illegal approaches the meaning of invalid” በሚል *መንገድ ተገልጾ* እናገኘዋለን፡፡

*ከላይ የተገለጸውን የሕግ ጽንሰሀሳብ እና የፍታብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት* በማድረግ በአመልካችና በተጠሪ *መካከል የተደረገው የዱቄት ፋብሪካ ሽያጭ* ውል በ*መሠረታዊ* ባህሪው ሞራላዊ ይዘቱና ዓላማው በሕግ ክልከላ የተደረገበት ሕገወጥ ውል /unlawfull contract/ *ነው ብሎ ለመደምደም* አይቻልም፡፡ አንድ የማይንቀሣቀስ ንብረት ሀብቱን በሽያጭ የማስተላለፍ የውክልና ሥልጣን በባለሀብቱ ባልተሰጠው ሰው ወይም ንብረቱን በሽያጭ ለማስተላለፍ በማይችል ሰው ቢሸጥ ውሉን በመሠረታዊ ባህሪው በሞራላዊ ይዘቱና ዓላማው ሕገ ወጥ ውል /unlawfull contract/ አያደርገውም፡፡ በአንጻሩ ይህ ጉድለት መኖሩ ቢረጋገጥ ውሉ ባለሀብትነትን በሽያጭ ለማስተላለፍ የተደነገጉትን አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች የማያሟላ “Illegal or invalid contract” የሚያደርገው ጉድለት ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ፋብሪካውን የሸጠልኝ ንብረቱ ላይ ሕጋዊ የመያዣ መብት ሣይኖረውና ንብረቱን በአዋጅ ቁጥር 97/1990 ለመሸጥ የሚያስችል መብት ሣይኖረው ነው፡፡ ስለዚህ ውሉ ሕገወጥ ውል /unlawfull contract/ በመሆኑ ከጅምሩ ውሉ እንደሌለ የሚቆጠር /null or void contract/ ነው በማለት የሚያቀርበው ክርክርም ከሕጉ መሠረታዊ ሀሣብ ጋር የማይሄድ ነው፡፡ የውል ሕግ ወይም ሌሎች የሕግ ማዕቀፎች የደነገጉትን መስፈርት ሣያሟላ የተደረገ ውል በሙሉ /null or void contract/ና ሕገወጥ ውል ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ አይቻልም፡፡

አንድ ውል ከጅምሩ እንዳልተደረገ /null or void contract/ የሚቆጠረው በማናቸውም መንገድ ሕጋዊ ውጤት ለማስገኘት የማይችልና ጉድለቱ ሊስተካከል የሚችልበት ምንም ዓይነት አማራጭ ወይም መንገድ የሌለ ሆኖ ሲገኝ መሆኑን “An instrument or transaction which is wholly in effective, in operative and incapable of ratification and which thus has no force or effect so that nothing can cure it” በሚል መንገድ ተገልፃ የምናገኘው ሲሆን የውሉን ጉድለት በማቃናት ህጋዊ ውጤት እንዲኖረው ለማድረግ የሚቻልበት መንገድና ሁኔታ ሲኖር ውሉ (null or void contract) ሣይሆን ጉድለት ያለበትና ፈራሽ ሊሆን የሚችል ውል “voidable or invalid contract” እንደሚሆን Variable exists when an imperfection or detect can be cured by an actor confirmation of him who could take advantage of it” በሚል መንገድ በብላክስ ሎው እና በሌሎች ጽሑፎች የተሰጡ ትንታኔዎችን በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በእኛ አገር የህግ ሥርዓት አንድን ንብረት በሽያጭ ለማስተላለፍ መብት ወይም የውክልና ሥልጣን በሌለው ሰው ሽያጭ ሲፈፀም የንብረቱ ባለቤት ሽያጩን ካፀደቀውና ከተቀበለው ውሉ በሕግ ፊት የፀናና ውጤት ያለው እንደሚሆን ከፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 2190- 2192 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሽያጭ ሊያስተላልፈው የሚችለው የባለሀብትነት መብት ከሌለው ሰው ንብረት የገዛ ገዥ ንብረቱ የእኔ ሀብት ነው የሚል ሶስተኛ ወገን ሲመጣበት ሻጭ በዋቢነት /መድንነት/ እንዲቀርብለት ለመጠየቅ እንደሚችልና የሽያጭ ውሉን ለማፍረስ የሚያስችለው በቂ ምክንያት እንደሆነ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2875፣የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2884፤ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2341 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2342 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎችን በጣምራ በማንበብ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪ በሽያጭ ሂደቱ ፈፅሞታል በማለት የሚዘረዝራቸው ጉድለቶች በተጠሪ ሙሉ በሙሉ የተካደና በፍርድ ያልተረጋገጠ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ጉድለቱ መኖሩ ቢረጋገጥም እንኳን አመልካች እንደሚለው ውሉን ከጅምሩ ሕገ ወጥ ውል/unlawfull contract/ ና ከጅምሩ

እንዳልተደረገ የሚያስቆጥር (null or void contract) የሚያደርግ ሣይሆን የሽያጭ ውሉን ጉድለት ያለበትና በፍርድ ቤት መቃወሚያና ክርክር ሊቀርብበትና ፈራሽ ሊሆን የሚችል ውል መሆኑን (voidable or invalid contract) የሚያሣዩ መሆናቸውን ከላይ ከዘረዘርነው የሕግ መሠረተ ሀሣብ የፍታብሔር ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የሽያጭ ውል በመሠረታዊ ባህሪው በሞራላዊ ይዘቱና ዓላማው ከሰው ከመነገድ ጋር የሚነፃፀርና ሕገወጥ ውል /unlawful contract/ ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በሽያጭ ውሉ ላይ አመልካች አሉ በማለት የሚዘረዝራቸው ጉድለቶች ውሉን ከጅምሩ እንዳልተደረገና ሕጋዊ ውጤት የሌለው /null or void contract/ የሚያደርጉ አይደለም፡፡ አመልካች የሚዘረዝራቸው የሕግ ጉድለቶች መኖራቸው ቢረጋገጥ እንኳን ውሉን ጉድለት ያለበትና በፍርድ ቤት ሊፈርስ የሚችል /voidable or invalid Contract/ ሊያደርግ የሚችል ጉድለት ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በጽሑፍና በቃል ባቀረቡት ክርክር የሽያጭ ውሉ ሕገወጥ የሆነ ውል/unlawful contract/ በመሆኑ ከጅምሩ እንዳልተደረገ መቆጠር የሚገባው(null or void contract) ነው በማለት ያቀረበውን ክርክር ከላይ በዘረዘርናቸው ምክንያቶች አልተቀበልነውም፡፡

2.የሽያጭ ውሉ ሲደረግ በተጠሪ በኩል አልተሟሉም በማለት አመልካች የሚያነሣቸው የሕግ መከራከሪዎች በተጠሪ የተካዱና በፍርድ ያልተረጋገጡ መሆናቸው እንዳለ ሆኖ ጉድለቶቹ ሙሉ በሙሉ እውነት መሆናቸው ቢረጋገጥ እንኳ ውሉን ለማፍረስ ምክንያት የሚሆኑ /avoidable contract) የሚያደርጉ ናቸው፡፡ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1718 በግልጽ እንደተመለከተው ዳኞች ሕጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑን ገልፀው አንድ ውል ተፈፃሚ እንዲሆን የሚቀርብን ጥያቄ ውድቅ የሚያደርጉት ውሉ ሕገ ወጥ ውል /unlawfull contract/ ሆኖ ሲያገኙት ነው፡፡ ውሉን በፍርድ ቤት ተከራክሮ ለማፍረስ የሚቻል /invalid contract/ ከሆነ ውሉ ጉድለት አለበት የሚለው ወገን ውሉን ለማስፈረስ ጥያቄውን የሚያቀርብበትን የጊዜ ገደብ ሕግ አውጭው በሕግ ይደነግጋል፡፡

ተጠሪ ለአመልካች የዱቄት ፋብሪካውን የሸጥኩት በአዋጅ ቁጥር 97/1990 እና በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 216/92 በተደነገገው መሠረት ለብድር በመያዣነት የያዝኩትን ንብረት ነው፡፡ የሽያጩ ሥርዓትም በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 6 እና 5 የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 423 በሚደነግጉት መሠረት ሐራጁን ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ማስታወቂያ በማውጣት የተከናወነ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ ባወጣው የሐራጅ ሽያጭ ስርዓቱ ተሣትፈው አሸናፊ በመሆን አመልካች የዱቄት ፋብሪካውን የያዙ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ተጠሪ በሐራጅ ንብረት ሲሸጥ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 394 እስከ አንቀጽ 449 የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው ተፈፃሚነት የሚኖራቸው ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 6 ተደንግጓል፡፡ አመልካች ተጠሪ ባወጣው ሐራጅ ሽያጭ ተሣትፎ ያደረገው ውል እንዲፈርስለት የሚጠይቀው ተጠሪ ንብረቱን በአግባቡ በመያዣነት ያልያዘ ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 97/1990 መሠረት ንብረቱን የመሸጥ መብት ሣይኖረው ነው የሸጠልኝ በማለት ነው፡፡ ተጠሪ ንብረቱን ለመሸጥ የሚያስችለው መብት በዱቄት ፋብሪካው ላይ እንዳለው በመግለጽ የሚከራከር ሲሆን ተጠሪ ንብረቱን ለአመልካች የሸጠው በአዋጅ ቁጥር 97/1990 መሠረት ንብረቱን ለመሸጥ የሚችልበት መብት እያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካች የሐራጅ ሽያጭ ውሉ እንዲፈርስለት ጥያቄ ያቀረበው በሕግ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ መወሰን ያስፈልጋል፡፡



www.chilot.me

አመልካች የሐራጅ ሽያጩ እንዲፈርስለት የሚጠይቀው ተጠሪ የንብረቱን ባለሀብትነት በሽያጭ ለማስተላለፍ የሚያስችለው መብት የለውም በማለት መሆኑን በተደጋጋሚ ተገልጿል፡፡ በተሸጠው ንብረት ላይ የፍርድ ባለእዳው መብት የሌለው መሆኑ ሲረጋገጥ ሽያጩ እንዲፈርስለት ገዥ ማመልከት እንደሚችል የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 446 ይደነግጋል፡፡ አመልካች ተጠሪ ንብረቱን በሽያጭ ለማስተላለፍ የሚያስችል መብት የለውም የሚል በመሆኑ የአመልካች ክርክር በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 446 ድንጋጌ ሥር የሚታቀፍ ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 446 የተደነገገውን መሠረት በማድረግ የሐራጅ ሽያጭ እንዲፈርስለት የሚጠይቅ ገዥ ውሉን ለማስፈረስ ጥያቄውን ከሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ማቅረብ እንዳለበት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 447 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም አመልካች ውሉ እንዲፈርስ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ያልጠየቀ በመሆኑና ከስድስት ዓመት በኋላ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት የከፍተኛ ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል ሕገወጥ ውል /unlawfull contract/ አለመሆኑን ከግንዛቤ ያስገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ውሣኔው በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል ከጅምሩ እንዳልተደረገና እንደሌለ የሚቆጠር /void contract/ ሣይሆን በፍርድ ቤት ውሣኔ ሊፈርስ የሚችል /voidable or invalid contract/ ነው የሚል ይዘት ያለው መቃወሚያና ክርክር በአመልካች የቀረበበት መሆኑና የአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 6 የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 446 እና በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 447 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው መሆኑን በማገንዘብና የእነዚህን ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘት መንፈስና ዓላማ መሠረት ያደረገ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ብይንና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ይህ ውሣኔ ተጠሪ የሸጠለትን የዱቄት ፋብሪካ የእኔ ነው ባይ ሰው የመጣበት እንደሆነ አመልካች ተጠሪ በዋቢነት እንዲቀርብለት ከመጠየቅ የሚገድበው አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ መዝገብ ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡
4. የከፍተኛው ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 54596

የካቲት 09 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቦርድ ጽ/ቤት ነ/ፈጅ ተስፋዬ ዘውዴ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ ላቀች መንግሥቴ - ጠበቃ ዶ/ር ንዋይ ዘርጌ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ከሊዝ ውል አፈፃፀም ጋር የተያያዘ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ በአሁኑ አመልካችና በሌሎች ሁለት የመንግሥት ተቋማት ላይ በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፤ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 13 ክልል ውስጥ የሚገኙ ቁጥራቸው 1055 እና 1056 የሆኑ ቤቶች ያረፉበትንና ስፋቱ 3139 ካ.ሜትር የሆነ ቦታ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የካቲት 20 ቀን 1992 ዓ.ም በተፈረመ የሊዝ ውል ቦታውን ወስደው በእለቱ የቦታ ይዞታ ምስክር ወረቀት ተሰጥቷቸው ቦታው በከፊልም ቢሆን በእጃቸው እንዳለ የሊዝ ውሉ እንዲሰረዝ አቤቱታ ቀርቦበት ሊሰረዝ አይገባም ተብሎ ጥቅምት 18 ቀን 2000 ዓ.ም በሊዝ ቦርዱ ውሣኔ ከተሰጠ በሁዋላ በመንግሥት ቤቶች እና በፍትህ ሚኒስቴር አመልካችነት የሊዝ ውሉ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል እንዲሰረዝ ጥያቄው ለሊዝ ቦርድ ቀርቦ የካቲት 05 ቀን 2000 ዓ.ም የሊዝ ውሉ እንዲሰረዝ ከሕግ ውጪ ቦርዱ መወሰኑን ገልፀው በሊዝ ውሉ የመጠቀም መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የሊዝ ውሉ ሊሰረዝ የቻለው በአዋጅ ቁጥር 20/1997፣ 34/2000 እና 272/1994 መሠረት መሆኑን ጠቅሶ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን እንደሌለው እና የዳኝነት ጥያቄውም ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልፆ ተከራክሯል፡፡ በስር ፍርድ ቤት እንደየቅደም ተከተላቸው ሁለተኛ እና ሶስተኛ ተከሣሽ የነበሩት የፍትህ ሚኒስቴርና የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ የሊዝ ውሉ እንዲሰረዝ አቤቱታ ለማቅረብ በሕጉ አግባብ ሥልጣንና መብት ያላቸው መሆኑን ጠቅሰው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የሊዝ ውሉ ሊሰረዝ አይገባም ተብሎ ከተወሰነ በሁዋላ እንደገና ታይቶ መሠረዙ ከአዋጅ ቁጥር 20/1997 አንቀጽ 5/11/ ድንጋጌ ውጪ ነው፣ ተጠሪ በቦታው ላይ ግንባታውን ያላከናወኑት ቦታው ሙሉ በሙሉ ነፃ

ሁኖ ሣይረከቡት በመቅረታቸው ከመሆኑም በላይ የሊዝ ውሉ ሊፈፀም ይገባል ተብሎ በፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሣኔ አግኝቶ ባለበት ሁኔታ የሊዝ ውሉ እንዲሰረዝ መደረጉ ያላግባብ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 272/1994 አንቀጽ 15/ለ/ መሠረትም የሊዝ ውሉን ለመሠረዝ የሚያስችል የሕዝብ ጥቅም ስለመኖሩ ተረጋግጧል ለማለት አይቻልም የሚሉትን ምክንያቶች በመያዝ ተጠሪ በሊዝ ውሉ የመጠቀም መብታቸው ሊጠበቅላቸው ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረፈጅ መጋቢት 28 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ስምንት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው መሠረታዊ ይዘትም ባጭሩ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 34/2000፣ 272/1994፣ 455/97፣ 555/2000 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 27604 እና 46052 የሰጣቸውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉሞችን ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የሊዝ ውሉ እንዲሰረዝ አመልካች መወሰኑ ተገቢነት የለውም ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሰጠቱ ከአዋጅ ቁጥር 272/1994 እንዲሁም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 27604 ከሰጠው የሕግ ትርጉም ጋር ተገቢነቱን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ጥር 05 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ሰባት ገጽ ማመልከቻ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡ የመልሣቸው መሠረታዊ ይዘትም በጉዳዩ ላይ የተለያዩ ክርክሮች ቀርበውበት በፍርድ ቤት ውሣኔ ተጠሪ የሊዝ ውል መብት የተረጋገጠላቸው ከመሆኑም በላይ በዚህ በውሉ ጊዜ ግንባታውን ያላከናወኑትም ቦታው ሙሉ በሙሉ ነፃ ሁኖ ባለመረከባቸው መክንያት በመሆኑና ይህም በፍርድ ቤት ውሣኔ ጭምር የተረጋገጠ መሆኑን፣ እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 34/2000 ተብሎ የሚጠቀሰው ሕግም በሕግ አግባብ የታወጀ ስለመሆኑ የሚያመላክት ነገር በሌለበት ሁኔታ የአመልካች እርምጃ በዚሁ አዋጅ መሠረት የተከናወነ ነው በማለት ክርክር መቅረቡ እውነት የሌለው መሆኑን ጠቅሰው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለውም ተብሎ ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች ነገረፈጅም ጥር 23 ቀን 2003 ዓ.ም በፃፉት አራት ገጽ የመልስ መልስ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ለበርካታ ጊዜያት በጉዳዩ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች በተሰጠው ውሣኔ የፍርድ ባለመብት የሆኑ ከመሆኑም በላይ የሊዝ ቦርዱም ጉዳዩን ተመልክቶ የሊዝ ውሉ ሊሰረዝ እንደማይገባ በቃለ ጉባዔ ቁጥር 6/2000 አረጋግጦ ከወሰነ በሁዋላ የካቲት 05 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ የሊዝ ውሉን ለሕዝብ ጥቅም ሲባል መሠረዙ አግባብ መሆኑን ገልፆ የቀድሞውን ውሣኔ ሽሮ ቦታው ለመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ እንዲሸጥ የወሰነ መሆኑን ነው፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ የሊዝ ቦርዱ የካቲት 05 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ ሕጋዊ ነው በማለት የሚከራከሩት አዋጅ ቁጥር 34/2000 "ን"

መሠረት ያደረገ ነው በማለት ነው፡፡ ይህ አዋጅ በሕጉ አግባብ የታወጀ አይደለም በማለት ተጠሪ ለአቀረቡት ክርክርም አዋጁ በነጋሪት ጋዜጣ ያልታወጀ መሆኑን በመልስ መልሣቸው ላይ የአመልካች ነገረፈጅ አምነው አዋጅ አለ ለማለት ይቻላል በማለት የሚከራከሩት ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ በአስተዳደሩ አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት ለሚመለከታቸው አካላት በደብዳቤ ተልኳል፤ ተገልጿል የአስተዳደሩ የሕግ አወጣጥ ስርዓትም ለየት ያለ ነው በማለት ነው፡፡ ይህ ችሎትም አለ የተባለውን አዋጅ ኮፒውን አስቀርቦ የተመለከተ ሲሆን የአመልካች ነገረ ፈጅ እንደአረጋገጡት በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ የወጣ ስለመሆኑ የሚያሣይ ነገር የሌለው መሆኑን ተገንዝቧል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 20/1997 አንቀጽ 5/11/ መሠረት ቦርዱ በሊዝ ውል ጉዳይ ላይ በሚሰጠው ውሣኔ የሚነሣ ቅሬታን መርምሮ ተገቢነት ካለው ውሣኔውን ለአንድ ጊዜ ብቻ ማሻሻል እንደሚችል በግልጽ የተደነገገ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ በቃለ ጉባዔ ቁጥር 6/2000 በቀድሞው ውሣኔ ላይ የቀረበውን ቅሬታ መርምሮ የቀድሞውን ውሣኔ መሻሻል እንደሌለበት የወሰነ ሲሆን የካቲት 05 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጠ የተባለው የሊዝ ውልን የሚሰርዝ ውሣኔ አዋጅ ቁጥር 20/1997 አንቀጽ 5/11/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የሚሰርዝ በሕጉ የወጣ አዋጅ በሌለበት ሁኔታ ነው፡፡ አዋጁ ቁጥር 34/2000 ተብሎ የሚጠቀሰው ሰነድ በሕጉ አግባብ የወጣና ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ ያልተረጋገጠ ሲሆን አዋጁ በስራ ላይ ውሏል ቢባል እንኳ የሊዝ ውሉ ሊሰረዝ አይገባም ተብሎ ውሣኔ ከተሰጠ በሁዋላ በድጋሚ የሊዝ ውሉ ይሰረዝልኝ ጥያቄ ቀርቦ ውሉ እንዲሰረዝ የተሰጠው ውሣኔ አዋጁ ተፈፃሚነት አለው ከተባለበት  ከአንድ ቀን በሁዋላ መሆኑ ከውሉ አፈፃፀም ሁኔታ ጋር ያለው ተገቢነቱ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ ተጠሪ በሊዝ ውሉ መሠረት ቦታውን ሙሉ በሙሉ እንዲረከቡ ይወሰንላቸው ዘንድ ጥያቄ አቅርበው ከስር ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እስከ ፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቦታውን እንዲረከቡ ውሣኔ ተሰጥቷቸው በጉዳዩ ላይ የፍርድ ባለመብት በመሆን በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 92111 የአፈፃፀም ጥያቄው አቅርበው ያልተፈፀመላቸው መሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መረጋገጡ ተጠሪ በሊዝ ውሉ መሠረት በአንድ ዓመት ከስድስት ወር የጊዜ ገደብ ሕንፃውን የመገንባት ግዴታቸውን ያልተወጡት በራሣቸው ችግር ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት አለመኖሩን የሚያሣይ ነው፡፡ ሌላው የአመልካች ነገረፈጅ አጥብቆ የሚከራከሩት የሊዝ ውሉ በአዋጅ ቁጥር 272/1994 አንቀጽ 15 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት የሊዝ ውሉን የመሠረዝ ስልጣን የአስተደደር አካል የሆነው የሊዝ ቦርድ ነው፣ ፍርድ ቤቶች ሊመለከቱ አይገባም በማለት ነው፡፡ በመሠረቱ  ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወስን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሣኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ የኢ.ፌዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 37/1/ ድንጋጌ በግልጽ የሚያሣየው ጉዳይ ነው፡ ከዚሁ የሕገ መንግሥት ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ ፍርድ ቤቶች አንድ ጉዳይ /አቤቱታ/ ተቀብለው ውሣኔ መስጠት የሚችሉት ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በሕግ ለሌላ አካል ያልተሰጠ ጉዳይ /አቤቱታ/ ተቀብለው ውሣኔ መስጠት የሚችሉት ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በሕግ ለሌላ አካል ያልተሰጠ ጉዳይ በሚሆንበት ጊዜ እንደሆነ መሆኑን ነው፡፡ በሕግ ተለይተው በአስተዳደራዊ ውሣኔ እንዲቋጩ በተባሉ ጉዳዮች ላይ መደበኛ ፍርድ ቤት የመዳኘት የስረ ነገር ሥልጣን ስለሌለው በሕጉ መሠረት ለአንድ አስተዳደር አካል ቀርቦ አስተዳደራዊ ውሣኔ የተሰጠበትን ጉዳይ ወይም ለአስተዳደር መቅረብ የሚገባውን ጉዳይ ፍርድ ቤት ሊያስተናግደውም ሆነ አከራክሮ ውሣኔ ሊሰጥበት አይችልም፡፡ ለአንድ የመንግሥት አካል በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን የሚሰጡት ሕጎች መጠበቅና መከበር ያለባቸው ሲሆን የዳኝነት አካል ስልጣንም በሕግ የተወሰነ ስለሆነ ሕግ የተመርጎም ስራው በሕጉ በተመለከተው አድማስ የሚመራ ይሆናል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 4 ድንጋጌ የሚያሣየውም ፍርድ ቤቶች በሌላ ሕግ በግለጽ በታገዱ ጉዳዮች ላይ አከራክሮ የመወሰን ስልጣን የሌላቸው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በአስተዳደራዊ ውሣኔ

የመጨረሻ እልባት እንዲያገኙ በሕግ ተለየተው የተቀመጡ ጉዳዮችን ፍርድ ቤቶች የመዳኘት ስልጣን የሌላቸው መሆኑ ሊስተዋል የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ /ክርክር/ መሠረት ያደረገው ከአመልካች ጋር ባደረጉት የሊዝ ውል የተሰጠውን ቦታ የሊዝ ውሉ ከውሉ አፈፃፀም መሠረታዊ ባህርያትና ከሕግ ውጪ ተሰርዞ ቦታው ለመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ እንዲሰጥ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 272/1994 የሊዝ ቦታ የሚሰጥበትና ውሉ የሚቋረጥበትን አግባብ ዘርግቷል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 15፣16 እና 17 ድንጋጌዎች ሲታዩ የሊዝ ውል የሚቋረጥበትንና ካሣ የሚከፈልበትን አግባብ፣ ጉዳዩን ሊመለከቱ የሚችሉ ወገኖችንና የይግባኝ አቀራረብን ሥርዓት ደንግገው እናገኛለን፡፡

በተያዘው ጉዳይ የሊዝ ውል እንዲቋረጥ ተደርጓል የሚባለው ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ነው በሚል ምክንያት በመሆኑ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያላቸው የአዋጅ ቁጥር 272/94 ድንጋጌዎች አንቀጽ 15/1/ለ/ እና 16 ናቸው፡፡ የአንቀጽ 15/1ለ/ ድንጋጌ የከተማ ቦታ የሊዝ ይዞታ ቦታው ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ለሌላ ስራ ወይም አገልግሎት እንዲውል ሲወሰን ሊቋረጥ እንደሚችል የተመለከተ ሲሆን በአንቀጽ 16/1/ ደግሞ አግባብ ያለው አካል ለሕዝብ ጥቅም ይውላል ተብሎ በሚወስነው መሠረት ለሚመለከተው አካል የማስለቀቂያ ትእዛዝ ወይም ማስጠንቀቂያ በጽሑፍ በመስጠት የሚገለገለውን የከተማ ቦታ ማስለቀቅና መረከብ እንደሚችል አስቀምጧል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 17/1/ ድንጋጌ ሲታይም በአንቀጽ 16 መሠረት የማስለቀቅ ትእዛዝ የደረሰው ወይም ትእዛዝ በተሰጠበት ንብረት ላይ መብት ወይም ጥቅም አለኝ የሚል ወገን የካሣም ሆነ ማንኛውንም ለፍርድ ሊቀርብ የሚገባው ሌላ አቤቱታ ከዝርዝር ምክንያቱ እና ማስረጃው ጋር ትእዛዙን ለሰጠው አካል የማቅረብ መብት እንዳለው ያስገነዝባል፡፡ በዚህ መልኩ ቀርቦ የታየ ጉዳይም በአንቀጽ ንዑስ ቁጥር ሁለት ስር የተመለከተውን ተገቢ ዳኝነት የሚሰጥበት ሲሆን በውሣኔው የማይስማማ ሰው ለጉባዔው ይግባኙን ማቅረብ እንደሚችል በአንቀጽ 18/1/ ስር ተደንግጎ ያለ ከመሆኑም በላይ ይህ አካል የሚሰጠው ውሣኔ ካሣ አነሰኝ ወይም ካሣ በዛብኝ ወይም ካሣ ተከለከልኩ በሚል ክርክሮች ላይ ካልሆነ በስተቀር በሕግም ሆነ በፍሬ ነገሮች ላይ የመጨረሻ ውሣኔ ስለመሆኑ የጠቀሰው አንቀጽ ንዑስ ቁጥር ሦስት ድንጋጌ ያሣያል፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለው በሊዝ የተሰጠ ቦታን የሚመለከተው አካል ማስለቀቅ የሚችለውና ጉዳዩ ላይ ጉባዔው የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ እና በፍርድ ቤት ሊቀርብ የማይገባው ቀድሞ የቦታ ማስለቀቁ እርምጃ የተወሰደው ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 272/94 አንቀጽ 2/7/ ስለሕዝብ ጥቅም ትርጉም አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሠረት የሕዝብ ጥቅም ማለት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሕዝቦች በመሬት ላይ ያላቸውን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና የከተማ ልማትን በቀጣይነት ለማጎልበት አግባብ ያለው አካል በመሪ ፕላን ወይም በልማት እቅድ የሕዝብ ጥቅም ብሎ የሚወስነው ነው በሚል ትርጓሜ የተቀመጠ ሲሆን አዋጅ ቁጥር 455/97ም ተመሣሣይ ይዘት ያለውን ትርጉም በአንቀጽ 2/5/ ስር ይዞ እናገኛለን፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ጉዳዩ ከሕዝብ ጥቅም ጋር የተገናኘ ነው በሚል ያቀረበው ክርክር በበታች ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያላገኘው የሊዝ ውሉ የተሰረዘበት መንገድ ሕጉ ከደነገገው ስርዓት ውጪ ነው ከሚል ምክንያት በተጨማሪ ቀድሞውንም ቢሆን የሊዝ ውሉ የሚሰርዝበት ምክንያት የለውም ተብሎ በመወሰኑ፣ በአዋጅ ቁጥር 555/2000 ስር ለመንግሥት ቤቶች የተሰጠው ስልጣንም ጉዳዩን የማይማለከተው መሆኑን፣ በአዋጅ ቁጥር 471/1998 መሠረት ለፍትህ ሚ/ር የተሰጠው ስልጣንም ለሕዝብ ጥቅም ሲባል አቤቱታ ማቅረብ የሚችል መሆኑን ቢያሣይም በተያዘው ጉዳይ ግን ከሕግ

የበላይነት መርህ ጋር በሚጋጭ መልኩ የፍርድ ቤትን ውሣኔ ውጤት ሊያሣጣ የሚችል ሁኖ ተገኝቷል በሚሉት ምክንያቶች መሆኑን ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ከላይ እንደተመለከተውም ተጠሪ በተለያዩ የክርክር መስመሮችና ደረጃዎች በሕጉ አግባብ በተቋቋመ የሊዝ ውል የቦታው ሕጋዊ ባለይዞታ መሆናቸው ተረጋግጦላቸዋል፡፡ ስለሆነም የፍርድ ቤት ውሣኔ ስለአለ ብቻ ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ንብረት አይወስድም ለማለት የማይቻል ቢሆንም ከተያዘው ጉዳይ ልዩ ባሕርይ አንፃር ሲታይ ግን የአመልካች እርምጃ ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ የተወሰደ ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሌላው የአመልካች ነገረፈጅ አጥብቀው የሚከራከሩትና ሰበር ችሎቱ እንዲመለከተው የተያዘው ጭብጥ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 27604 ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጋር ስላለው ተገቢነት የሚመለከት ነው፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 27604 የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የቦታ ምስክር ወረቀት ይሰጠኝ ጥያቄን በሚመለከት የተነሣን ክርክር መሠረት ያደረገ ሲሆን በችሎቱ የተሰጠው ትርጉምም እንዲህ አይነት የቦታ ወይም ይዞታ ይሰጠኝ ጥያቄዎችን በመቀበል እየመረመረ ለቦታ ጥያቄዎች ቦታ የመመደብ፣ የይዞታ ምስክር ወረቀት የመስጠት የከተማው አስተዳደር ተግባርና ኃላፊነት እንጂ በፍርድ የሚያልቅ ጉዳይ አይደለም የሚል ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ክስ የመሠረቱት ከሊዝ ውል አፈፃፀም ጋር የተያያዘ እንጂ የቦታ ወይም የይዞታ ይሰጠኝ ጥያቄ አይደለም፡፡ ስለሆነም የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄና የአመልካች ክርክር በመ/ቁጥር 27604 በተያዘው ጉዳይ ካለው ፍሬ ነገር እና የሕግ ክርክር ሙሉ በሙሉ ግንኙነት አለው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ምክንያቱም የተጠሪ ክስ መሠረቱ የሊዝ ውል ሆኖ ውሉ ተጥሷል በሚል ዳኝነት የጠየቁ ስለመሆኑ የሚያሣይ ነውና፡፡ ሌላው የአመልካች ነገረፈጅ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 46052 የሰጠው የሕግ ትርጉም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ሲታይም የሊዝ ውሉን ከከተማው አስተዳደር ጋር አደረጉ የተባሉት ግለሰብ ቦታውን ሙሉ በሙሉ ተረክበው በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግንባታውን ባለማከናወናቸው የሊዝ ውሉ የተሰረዘ ስለመሆኑ ስለሚያሣይ ሲሆን አሁን በእጃችን ባለው ጉዳይ ግን መሠረታዊ ክርክሩ የሊዝ ውሉ ያላግባብ ተሰርዟል የሚል ቢሆንም ቦታውን ተጠሪ በከፊል በመረከባቸው ምክንያት በገቡት ግዴታ መሠረት ግንባታውን ሊያከናውኑ ያልቻሉ መሆኑ በፍርድ ቤት ውሣኔ ጭምር የተረጋገጠ በመሆኑ በመ/ቁጥር 46052 ከተያዘውና የሊዝ ውሉን ከከተማው አስተዳደር ጋር አደረጉ የተባሉት ግለሰብ ቦታውን ሙሉ በሙሉ ተረክበው በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግንባታውን ባለማከናወናቸው የሊዝ ውሉ የተሰረዘ ስለመሆኑ ከሚያሣይ ውሣኔ ጋር በፍሬ ነገር ደረጃ ጉልሕ ልዩነት ያለበት በመሆኑ የመ/ቁጥር 46052 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ነው ተብሎ ለዚህ ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2/4/ መሠረት የሚጠቀስበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ክርክር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለልም የተጠሪ ጥያቄ የአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቦርድ ጽ/ቤት በሊዝ የተወሰደ ቦታን ከሕግ ውጪ የሊዝ የምስክር ወረቀትን በመሠረዝ ሕገ ወጥ እርምጃ ወስዷል በማለት በዚህ ውል ያገኙት የንብረት መብታቸው /የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40/6 ይመለከቷል/ በፍርድ እንዲጠበቅላቸው የሚጠይቅ በመሆኑ በፍርድ ቤት ሊስተናገድ የሚገባው እና ውሣኔ የሚሰጥበት ጉዳይ ሁኖ ክርክሩ ሲጀመር የክርክሩ ተሣታፊ ከነበሩት አካላት ማንነት አንፃር ጉዳዩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች መቅረቡም ሆኖ የአመልካች ክርክር ውድቅ ሁኖ ተጠሪ በሊዝ ውሉ የመጠቀም መብታቸው እንዲጠበቅ በማለት የተሰጠው ውሣኔ ከአዋጅ ቁጥር 272/94፣ 20/1997፣ 555/2000፣ ከአዋጅ ቁጥር 471/1998 ድንጋጌዎች እንዲሁም ከውል አፈፃፀም መሠረታዊ

መርሆዎች ጋር ተዛምዶ ሲታይ ሕጋዊ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህ ምክንያት በውሣኔው ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1/ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 66717 ጥር 27 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 46194 ጥር 07 ቀን 2002 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

2/ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 56794

የካቲት 07 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ሳህሉ ሙሉጌታ - ጠበቃ ወንድም ጌታሁን ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1. አቶ ሰለሞን ኤፍሬም

2. አቶ ጌታቸው ኤፍሬም

3. አቶ መስፍን ኤፍሬም

} አቶ ደረጀ ወርቁ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የከፍተኛው ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት ተጠሪዎች ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪዎች አመልካች ታህሣስ 19 ቀን 1999 ዓ.ም. በተጻፈ የሽያጭ ውል በአዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 11/12 የሚገኙ ቁጥራቸው 595 እና 596 የሆነ ቤቶች በብር 1,330,000 /አንድ ሚሊዮን ሦስት መቶ ሠላሳ ሺህ ብር/ ለመሸጥ ተስማምቶ ብር 206,000 /ሁለት መቶ ስድስት ሺህ ብር/ ቀብድ ተቀብሏል፡፡ ተከሣሽ /አመልካች/ የቤት ሽያጭ ውሉን መሠረዙን በደብዳቤ የገለፀ ሲሆን እኛም በሽያጭ ውሉ መሠረት ቤቱን እንዲያስረክበን ማስጠንቀቂያ ሰጥተነዋል፡፡ ተከሣሽ/አመልካች/ ቤቱን ተገድዶ እንዲያስረክበን እንዲወስንልን ይህ ቢታለፍ በውሉ የተቀመጠውን የገደብ መቀጫና የቀብዱን ገንዘብ አጠፌታ አድርጎ እንዲመልስ ይወሰንልን በማለት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ ከከሣሾች/ተጠሪዎች/ ጋር በሕጉ አግባብ ያደረግሁት የቤት ሽያጭ ውል የለም፡፡ ተጠሪዎች/ከሣሾች/ ያቀረቡት ውል በውል አዋዋይ ፊት ወይም በፍ/ቤት መዝገብ ሹም ፊት ያልተደረገ በመሆኑ ከረቂቅነት አልፎ ሕጋዊ አስገዳጅነት የሌለው በመሆኑ የከሣሾች/ተጠሪዎች/ ክስ ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን የቃልና የጽሑፍ ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ በከሣሾች/ተጠሪዎች/ እና በአመልካች/ተከሣሽ/ መካከል የቤት ሽያጭ ውል አለ ወይስ የለውም? ተከሣሽ/አመልካች/ የቤት ሽያጭ ውሉን ተገድዶ መፈፀም አለበት ወይስ የለበትም? የሚሉትን ጭብጦችና ሌላ ሦስተኛ ጭብጥ ከመሠረተ በኋላ በከሣሾችና/በተጠሪዎች/ና በአመልካች/ተከሣሽ/ መካከል ሕጋዊ አስገዳጅነት ያለውና የፀና የቤት



www.chilot.me

ሽያጭ አለ በማለት ስለ ቀብድ የተደነገጉ የፍታብሔር ሕግ ድንጋጌዎችና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰበር መዝገብ ቁጥር 36887 መሠረት በማድረግ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ተከሣሽ/አመልካች/ የቤት ሽያጭ ውሉን በፍርድ ተገዳጅ ይፈፅም ከሣሾች/ተጠሪዎች/ ቀሪውን የቤቱን ዋጋ ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቀርቧል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች ግንቦት 16 ቀን 1992 ዓ.ም. በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የሥር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት በውል አዋዋይ ወይም በፍ/ቤት መዝገብ ሹም ፊት ያልተረገ ውል ሕጋዊ አስገዳጅነትና የፀና ውል ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723/1/ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 21448 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ከተጠሪዎች ጋር ያደረግሁት የቤት ሽያጭ ውል የለም እንጅ አለ ቢባል እንኳን ተጠሪዎች በውሉ አደራረግ ወቅት የተለያዩ ተፅዕኖ ያደረጉ በመሆናቸውና ጉድለት የሌለ በመሆኑ አላግባብ የገደብ መቀጮና ቀብዱ አጠፌታ ሆኖ እንዲከፈል ያቀረቡት ጥያቄ ተገቢ አይደለም፡፡ የሥር ፍ/ቤት ውሉ እንዲፈፀም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው ጥር 4 ቀን 2003 ዓ.ም. በተጻፈ መልስ አመልካች ቤቶቹን አልሸጥኩም የሚል ክርክር አላቀረቡም፡፡ አመልካች የሽያጭ ውሉን መኖሩን አምኖ በሚከራከርበት ሁኔታ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723/1/ በመጥቀሱ ብቻ የውሉ አስገዳጅነት እንደማይቀር የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት የሕግ ትርጉም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 36887 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉምና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1883 ድንጋጌን መሠረት ያደረገ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ተገቢነት የለውም፡፡ የሽያጭ ውሉን አመልካች እንዲፈፅሙ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔም የሕግ ስህተት የለበትም፡፡ በሥር ስለ ቀብድና መቀጮ የተሰጠ ውሣኔ በሌለበት ሁኔታ አመልካች የሰበር አቤቱታ ማቅረባቸው ተገቢ አይደለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የፀና የቤት ሽያጭ ውል አለ ወይስ የለም? በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የፀና የቤት ሽያጭ ውል አለ የሚባል ቢሆን የአመልካች ግዴታና ኃላፊነት ምንድን ነው? የሚሉትን ጭብጦች መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር ታህሣስ 19 ቀን 1999 ዓ.ም. በተጻፈ የቤት ሽያጭ ውል በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 11/12 የቤት ቁጥር 595 እና የቤት ቁጥር 596 በብር 1,330,000 /አንድ ሚሊዮን ሦስት መቶ ሠላሳ ሺህ ብር/ እንደገዙና አመልካች ከቤቶቹ ዋጋ ብር 206,000 /ሁለት መቶ ስድስት ሺህ ብር/ ቀብድ እንደወሰዱ ለሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት የክሥ ማመልከቻ ገልጸዋል፡፡ አመልካች ተጠሪዎች በቀብድ መልክ ወስደዋል በማለት የገለፁትን ብር 206,000 /ሁለት መቶ ስድስት ሺህ ብር/ አልወሰድኩም በማለት በግልፅ ክደው ያልተከራከሩ መሆኑን የሥር ፍ/ቤት ከሰጠው ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ይህም አመልካች ከተጠሪዎች የቤት ሽያጭ ቀብድ ገንዘብ የተቀበሉ መሆኑን እንዳመኑ እንደሚቆጠር በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 234 ንዑስ አንቀጽ 1/ሠ/ እና በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 235 ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ አመልካች የቤት ሽያጭ ውሉን መነሻ በማድረግ ብር 206,000

/ሁለት መቶ ስድስት ሺህ ብር/ መቀበላቸውን በግልፅ ክደው ያልተከራከሩና ይህም የቀብድ ገንዘብ መቀበላቸውን እንዳመኑ ከላይ በተገለፁት የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የሚቆጠር ነው፡፡ አንዱ ወገን ለአንዱ ወገን ቀብድ መስጠቱ በማያከራክር ሁኔታ ውሉ መደረጉን እንደሚያረጋግጥ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1883 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በሥር ክርክሩን አይቶ የወሰነው የከፍተኛ ፍ/ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 36887 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በተዛባ መንገድ በመረዳት ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚ አድርጓል በማለት አመልካች ሰፊ ክርክር አቅርበዋል፡፡ በእኛ በኩል የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን የወሰነው በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል በጽሑፍ የተደረገውን የሽያጭ ውል ብቻ መሠረት በማድረግ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የሥር ፍ/ቤት በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የፀና የቤት ሽያጭ ውል አለ ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰው በመካከላቸው ተደርጓል የተባለውንና ይህንኑ ፎርም አላሟላም የሚል ክርክር በቀረበበት የጽሑፍ ውል ላይ ብቻ በመመራት እና በመመልከት ሣይሆን ተጠሪዎች ለአመልካች የቀብድ ገንዘብ የከፈሉ መሆኑንና አመልካችም የቀብድ ገንዘቡን ከተጠሪዎች የተቀበሉ መሆናቸውን ማመናቸው በሕግ በኩል ያለውን ውጤት በመመዘን ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች የቀብድ ገንዘብ መቀበላቸውን ያልካዱና የቀብድ ገንዘብ እንደተቀበሉ የሚቆጠር በመሆኑና ይህም የቤት ሽያጭ ውሉ መደረጉን በማያከራክር ሁኔታ እንደሚያረጋግጥ ፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1883 በግልጽ የተደነገገ መሆኑን አመልካች ውሉን በተናጥል ያፈረሰ መሆኑን በመግለጽ ማስጠንቀቂያ የጻፈ መሆኑን ክዶ ያልተከራከረ መሆኑን በማገናዘብ የሥር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በዚህ መዝገብ ያለውን ልዩ ሁኔታ የቀብድ ገንዘብ ክፍያ የሽያጭ ውሉ መኖሩን በማረጋገጥ በኩል የሚኖረውን የአስረጅነት ዋጋ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1883 የተደነገገውን መሠረት ያደረገና የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ የሥር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች የቤት ሽያጭ ውሉን እንዲፈጽም የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ሲሆን ይህንንም ለመወሰን በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የተደረገውን የቤት ሽያጭ ውል መሠረታዊ ባህሪና አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መመርመር ያስፈልጋል፡፡ አመልካችና ተጠሪዎች ታህሣስ 19 ቀን 1999 ዓ.ም. ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል የቤቱ ሻጭ የተባሉት አመልካችና የቤቱ ገዥ የሆኑት ተጠሪዎች ቀብድ የተቀባበሉበት ውል መሆኑ በሽያጭ ውሉ በግልፅ የተመለከተ መሆኑን ከሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ከተጠሪዎች የቀብድ ገንዘብ የተቀበሉ መሆኑን በማመን ተጠሪዎች የውል ግዴታቸውን ስላልተወጡ ውሉን በተናጠል ያፈረሱ መሆኑን በመግለፅ ጥቅምት 22 ቀን 2001 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ ለተጠሪዎች አሳውቀዋል፡፡ አመልካችና ተጠሪዎች ባደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ተጠሪዎች የከፈሉትን ቀብድ በመልቀቅ ውሉን የማፍረስ መብታቸውን ቀሪ ያደረጉ መሆኑና በተመሣሣይ ሁኔታ አመልካች የተቀበሉትን የቀብድ ገንዘብ አጠፌታ በመክፈል ውሉን የማፍረስ መብታቸውን ቀሪ ያደረጉ ስለመሆኑ በአመልካችም ሆነ በተጠሪዎች የቀረበ ማስረጃ እንደሌለ ከሥር ፍ/ቤትና በሰበር ከተደረገው ክርክር ለመገንዘብ ችለናል፡፡

በውላቸው ሌላ ስምምነት ከሌለ በቀር ቀብድ የተቀበለው ወገን የተቀበለውን ቀብድ አጠፌታ በመክፈል ውለታውን ማፍረስ እንደሚችል በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1885 ንዑስ አንቀጽ 2 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ አመልካች ይህን የሕግ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ውሉን የማፍረስ መብታቸውን ቀሪ የሚያደርግ ተቃራኒ ስምምነት ያደረጉ መሆኑን ተጠሪዎች እስካላስረዱ ድረስ አመልካች በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1885 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን በማሟላት የሽያጭ ውሉን የማፍረስ መብት አላቸው፡፡ ተጠሪዎች አመልካች የሽያጭ ውሉን ለመፈፀም ፈቃደኛ ካልሆኑ በአማራጭ የቀብዱን ገንዘብ አጠፌታ አድርገው እንዲከፍሉ እንዲዋሰንላቸው ያቀረቡት ክስ አመልካች ቀብዱን

አጠፌታ በመክፈል ውሉን የማፍረስ መብታቸውን ቀሪ የሚያደርግ ተቃራኒ ስምምነት ያላደረጉ መሆኑን የማያመላክት ነው፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤትና የጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል የቀብድ ገንዘብ የተከፈለበት ውል በመሆኑ ውሉን በማፍረስ በኩል አመልካችም ሆነ ተጠሪዎች ያላቸውን መብትና ውሉን ሲያፈርስ በሕግ የተጣለባቸውን ግዴታና ኃላፊነት ከግንዛቤ ውስጥ ሣያስገቡ አመልካች ቤቶቹን ለተጠሪዎች እንዲያስረክቡና የሽያጭ ውሉን እንዲፈፅሙ የሰጡት ውሣኔ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1885 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም የከፍተኛው ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች የቤት ሽያጭ ውሉን እንዲፈጽምና ቤቶቹን እንዲያስረክብ የሰጡትን ውሣኔ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት በማሻሻል አመልካች ከተጠሪዎች የተቀበለውን ቀብድ ብር 206,000 /ሁለት መቶ ስድስት ሺህ ብር/ አጠፌታ አድርጎ ብር 412,000 /አራት መቶ አሥራ ሁለት ሺህ ብር/ ለተጠሪዎች በመክፈል የሽያጭ ውሉን ማፍረስ ይችላል በማለት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1885 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

3. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
4. አመልካች ከተጠሪዎች የተቀበለውን የቀብድ ገንዘብ አጠፌታ ማለትም ብር 412,000 /አራት መቶ አሥራ ሁለት ሺህ ብር/ ለተጠሪዎች ይክፈል በማለት ወስነናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ



www.chilot.me

የሰ.መ.ቁ. 58258

የካቲት 21 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- ወ/ሮ ዮርዳኖስ ሐጉስ አልቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- ወ/ሮ ሐይማኖት ተፈራ ጠበቃ አቶ ፋንታሁን አባተ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ ለሰበር የቀረበው ጉዳይ ተዋዋይ ወገኖች በውላቸው የወሰኑት መቀጫ/ገደብ/ እንዲፈፀም የሚያስገድድ ሆኔታ መኖር አለመኖሩን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1889-1895 ካሉት ድንጋጌዎች አንፃር መመርመርን የሚጠይቅ ነው፡፡

ለክርክሩ መነሻ ሆኖ የተገኘው የካቲት 19 ቀን 2000 ዓ.ም የተደረገ የቤት ኪራይ ውል ነው፡፡ በዚህ ውል የአሁኗ አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ ካልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 ክልል ውስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥሩ አዲስ የሆነ ቤት ለትምህርት ቤት አገልግሎት ይውላል ተብሎ ለአሁኗ ተጠሪ በወር ብር 10,000 የኪራይ ሂሣብ ለ5 ዓመት ለማከራየት ተስማምተዋል፡፡ የቅድሚያ ክፍያ ብር 60,000 ከተከራይዋ ወስደዋል፡፡ በኪራይ ውሉ አከራይ ቤቱን አጥረው ነሐሴ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ለተከራይዋ ለማስረከብ ግዴታ ገብተዋል፡፡ በውሉ መሠረት ባይፈጽሙ መቀጮ/ገደብ/ ብር 50,000 ለመክፈል ተስማምተዋል፡፡

በኪራይ ውሉ መሠረት ቤቱን አጥረው ሊያስረክቡኝ አልቻሉም ማስጠንቀቂያም ተጽፎላቸው በውሉ መሠረት ሣይፈጽሙ ቀርተዋል ቤቱንም ለታሰበለት አገልግሎት ለማዋል ስላልተቻለ ውሉን አፍርሰዋል ስለዚህ በቅድሚያ የተቀበሉትን ብር 60,000 ከወሰዱበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲሁም ቤቱን ባለማስረከብ ውሉን ስላፈረሱ በውሉ ላይ የተወሰነውን መቀጫ/ገደብ/ ብር 50,000 አከራይዋ የአሁኗ አመልካች ሊከፍሉኝ ይገባል በሚል ወደ ፍርድ ቤት ክስ ያመሩት ተከራይ የሆኑት የአሆኗ ተጠሪ ናቸው፡፡ ተከሣሽዋ የአሁኗ አመልካች ክሱ ደርሷቸው በሰጡት መልስ የውል ግዴታዬን ለመወጣት በመንቀሳቀስ ላይ እያለሁ የቀበሌ መስተዳድር ያጠርኩትን አጥር አፍርሶብኛል እንዳላጥርም ከልክሎኛል ውሉ ሣይፈፀም የቀረው በተከሣሽ ጥፋት አይደለም ቤቱም ለትምርት ቤት አገልግሎት ሊውል አይችልም ተብሏል፡፡ ውሉ በእኔ ጥፋት ስላልፈረሰ ገደብና ወለድ ሊከፍል አይገባም ኪሣራ በሌለበት ገደብና ወለድ በክሱ የተጠየቀው ያለ አግባብ ነው፡፡ ውሉ እንደማይፈፀም ከታወቀ በኃላ ከሣሽ ገንዘባቸውን እንዲወስዱ

ተጠይቀው ፈቃደኛ ስላልሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚሉትን ክርክሮች አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክሱን የግራቀኙን ክርክሮችና ማስረጃዎች መርምሮ በሰጠው ፍርድ አከራይዋ ቤቱን እንዳላጠሩ የቀበሌ መስተዳድር ከልክሎኛል የሚለውን ለማስረዳት ያቀረቡት ቀበሌው የፃፈው ደብዳቤ ከይዞታቸው ውጪ የያዙት የመንግሥት መሬት መኖሩን የሚያስረዳ ነው፡፡ ከራሣቸው የካርታ ይዞታ ውጭ ያለ ቦታ አጥረው ለከሣሽ ለማስረከብ መንቀሳቀሳቸው ህጋዊ አይደለም በዚህ ምክንያት ለከሣሽ ማስረከብ የነበረባቸውን ቤት ሣያስረክቡ መቀረታቸው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በውሉ መሠረት ሣይፈጽሙ ቀርተዋል ሊባል አይችልም አንድ የትምህርት ቢሮ ተወካይ ማህተም በተደረገበት ደብዳቤ መፃፃፍ ሣይሆን በቃሉ ቤትና ቦታው ለትምህርት ቤት አገልግሎት ሊውል አይችልም ብሉ ከልክሏል የተባለውም ተቀባይነት የለውም አከራይ የዉል ግዴታቸውን ባለመፈፀማቸው ምክንያት የኪራይ ውሉ ፈርሷል፡፡ በቅድሚያ የተቀበሉትን ብር 60,000 ማስጠንቀቂያ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ /9%/ ጋር እና በኪራይ ውሉ መሠረት ባለመፈፀማቸው በውሉ ላይ የተስማሙበትን ብር 50,000 ፍርዱ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ አለቀ ድረስ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለከሣሽዋ ለአሁኗ ተጠሪ ሊከፍሎ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኗ አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን አቅርበው ያስረቀርባል ተብሎ ግራቀኙ ቀርበው ክርክሩ ከተሰማ በኃላ ከፍተኛው ፍ/ቤትም መርምሮ በሰጠው ፍርድ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ምክንያት አልተገኘም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የአሁኗ አልካች በኪራይ ውሉ ላይ የተመለከተውን መቀጫ ብር 50,000 ፍርዱ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር ለአሁኗ ተጠሪ እንዲከፍሉ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በሚል በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት የቀረበ ነው፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመወሰኑ ማመልከቻው ለአሁኗ ተጠሪ ተልኮ ቀርበው መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

በዚህም መሠረት የተጠሪ ጠበቃ በጽሑፍ በሰጡት መልስ ውሉ ሣይፈጽም የቀረው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው የሚያሰኝ ነገር አለመኖርን ውሉ እንዳይፈፀም ያደረጉት አመልካች ራሣቸው እንደሆኑ ፣ በውሉ ወሉን አፍራሹ ወገን መቀጫ ብር 50,000 ለመክፈል ግዴታ ስለመግባቱ እና አመልካችም በውሉ መሠረት ሣይፈጽሙ መቅረታቸው በውሉ የተወሰነውን መቀጫ በክሱ እንዲከፍሉ ተጠይቆ የሥር ፍ/ቤት በሕጉ አግባብ አይቶ እንዲከፍሉ ስለመወሰኑ በመዘርዘር ተከራክረዋል፡፡

አመልካች በተጠሪ በኩል በተሰጠው መልስ ላይ የመልስ መልስ መስጠት አያስፈልገኝም ብለዋል፡፡

ጉዳዩም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በአሁኗ አመልካችና ተጠሪ መካከል የካቲት 19 ቀን 2000 ዓ.ም በጽሑፍ የቤት ኪራይ ውሉ ተደርጓል፡፡ አመልካች የቤቱ አከራይ ሲሆኑ ተጠሪ ደግሞ ተከራይ ናቸው፡፡ ተከራይ ቤቱ



www.chilot.me

በውሉ የተከራዩት ለትምርት ቤት አገልግሎት ሊጠቀሙበት ነው። ተከራይ ለቤቱ ኪራይ በየወር ብር 10,000 የሚከፍሉ ሆኖ በቅድሚያ ብር 60,000 ለአከራይ ከፍለዋል። ቤቱ በተከራይዋ በኩል ለተፈለገበት ለትምህርት ቤት አገልግሎት እንዲውል ከነቦታ ይዞታው መታጠር ያለበት ስለመሆኑ በውሉ አምነውበት አከራይዋ አጥረው ለማስረከብ ግዴታ ገብተዋል። ውሉን የካቲት 19 ቀን 2000ዓ.ም ተፈራርመው ማስረከቢያው ከ5 ወር በኃላ ነሐሴ 1 ቀን 2000ዓ.ም እንዲሆን የተስማሙትም በዚህ ጊዜ ውስጥ አከራይ የአጥሩን ሥራ ለማጠናቀቅ እንዲችሉ ታስቦ ነው።

የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2900 አከራይ ያከራየውን የማይንቀሳቀስ ሀብት ከተጨማሪ ዕቃዎቹና በውሉ መሠረት ወይም በሀብቱ ተፈጥሮ መሠረት ለተመደበበት ጉዳይ ሊያገለግል በሚችልበት ሁኔታ አሟልቶ ለተከራዩ ማስረከብ እንዳለበት ደንግጓል።

በዚህ ጉዳይ ቤት አከራይ የሆኑት የአሁኗ አመልካች ቤቱ በውሉ ለተመደበበት ጉዳይ ሊያገለግል በሚችልበት ሁኔታ አጥረውና አሟልተው በውሉ በተወሰነው የማስረከቢያ ግዜ ለተከራይዋ ለአሁኗ ተጠሪ ሣያስረክቡ ቀርተዋል።

አመልካች በኪራይ ውሉ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ አሟልተው ቤቱን ለተከራይ የማስረከብ ግዴታቸውን ባለመፈፀማቸው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1784 መሠረት ውሉ ቀሪ እንዲሆን ተደርጓል።

አመልካች በውሉ መሠረት ሊፈጽሙ ባለመቻላቸው ውሉ ቀሪ መሆኑ ከተረጋገጠ በውሉ ላይ የተወሰነውን መቀጫ /ገደብ/ ብር 50,000 ለተከራይዋ ለአሁኗ ተጠሪ ለመክፈል ይገደዳሉ ወይንስ አይገደዱም; የሚለውን ዋናውን የክርክር ጭብጥ በተመለከተም አመልካች በውሉ መሠረት ያልፈፀምኩት የቀበሌ መስተዳዳር ቤቱን እንዳላጥር በመከልከሉና ያጠርኩትንም በማፍረሱ ስለሆነ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም አመልካች ራሣቸው በጽሑፍ ማስረጃነት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት የቀበሌ መስተዳድር የፃፈው ደብዳቤ እንዳያጥሩ የተደረገው ከይዞታቸው ውጭ የመንግሥት ቦታን ጨምረው በመከለል በመያዛቸው ምክንያት መሆኑን እንደሚያስረዳ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ የሚያሣይ በመሆኑና አመልካችም በስር አቤቱታቸው ላይ ቀበሌው ይህንን አላለም በሚል የገለጹት ነገር ስለሌለ በሕጉ ከአቅም በላይ የሚል ትርጉም የሚሰጠው አይደለም። ሁለተኛውን ምክንያት በሚመለከት ቤትና ቦታው ለትምርት ቤት አገልግሎት ሊውል የሚችል አይደለም ተብሏል የሚለውን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከቀበሌው የትምህርት ቢሮ በጽሑፍ ተገልጾ የቀረበ ማስረጃ አለመኖሩንና ተወካዩ በቃል ተናግሯል የተባለው በቂ አለመሆኑን በመግለጽ ሣይቀበለው ስለቀረ በሰበር ደረጃ የሚመረመር አይደለም። ስለዚህ የአሁኗ አመልካች በውሉ መሠረት ያልፈፀምኩት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በሚል ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም። ለውሉ መፍረስ ተጠያቂ የሚሆኑት አመልካች ናቸው።

የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1889 አንደኛው ወገን ግዴታውን ያልፈፀመ እንደሆነ ወይም አንድሎ ወይም አዘግይቶ የፈፀመ እንደሆነ የሚከፈለውን መቀጮ ተዋዋዮች አስቀድመው በውላቸው ለመወሰን እንደሚችሉ ያስረዳል።

በተያዘው ጉዳይም በዚሁ ሕግ መሠረት የአሁኗ አመልካች በውሉ መሠረት ግዴታቸውን ካልፈፀሙ መቀጮ ብር 50,000 ለመክፈል ተስማምተዋል።



www.chilot.me

የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1891 ባለገንዘቡ መቀጫ /ገድብ/ ሊቀበል የሚገባው ውሉ ባለመፈፀሙ ኪሣራ ለመጠየቅ በሚችልበት ጊዜ ሁሉ እንደሆነ ይገልፃል፡፡

ከዚህ ሌላ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1892/1/ ላይ የተመለከተውም ሲታይ ባለገንዘቡ ኪሣራ ባይደረስበትም የተዋዋለው መቀጫ/ገደብ/ ሊከፈለው የሚገባ ስለመሆኑ የሚደነግግ ነው፡፡

አመልካች ተጠሪዋ በውሉ አለመፈፀም ምክንያት የደረሰባቸው ኪሣራ ስለሌለ መቀጫ ሊከፈላቸው አይገባም በሚል ያቀረቡት ክርክርም ከፍሲል በተጠቀሰው ድግጋጌ መሠረት ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡

በሕጉም መቀጫውን ለመቀነስ የሚያስችል ምክንያት አልተገኘም፡፡

በመሆኑም የአሁኗ አመልካች በውላቸው የተወሰነውን መቀጫ /ገደብ/ ብር 50,000 ለአሁኗ ተጠሪ እንዲከፍሉ በመወሰኑ የሚታይበት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም፡፡

በሌላ በኩል ግን እንደ ውሉ ባለመፈፀሙ በተወሰነው የቅጣት ገንዘብ ላይ ህጋዊ ወለድ ታስቦ እንዲከፈልበት የተወሰነው በሕጉ የሚደገፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ከፍርዱ በኋላም ቢሆን በመቀጫ ገንዘብ ላይ ህጋዊ ወለድ /9%/ ታስቦ እንዲከፈል መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ መታረም የሚገባው ነው፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 14189, በ22/10/2001, በመቀጫው ብር 50,000 ላይ ወለድ 9% እንዲከፈልበት የወሰነው እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 84660, በ28/10/2002 ይህንኑ ያፀናበት ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሎ የአሁኗ አመልካች የመቀጫውን ገንዘብ ብር 50,000 ያለ ወለድ ለአሁኗ ተጠሪ እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡
2. በዚህ የሰበር ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

ቅ/መ



www.chilot.me

*የሰ/መ/ቁ. 60469*

*የካቲት 21 ቀን 2003 ዓ.ም*

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- ኮከብ ዱቄትና ፓስታ ፋብሪካ - ጠበቃ ነቅዓጥበበ በየነ ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- ሙሉ ዓለም የሥራ አመራር አማካሪዎች - ሙሉሸዋ ወልደ ማርያም ሥራ አስኪያጅ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው የክስ ማመልከቻ ሲሆን ተጠሪም በበኩሉ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በአመልካች ላይ አቅርቧል፡፡

በሥር ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበት መሠረታዊ ጉዳይ የሙያ ሥራ አገልግሎት ውል አፈፃፀም የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ የድርጅቱን መዋቅር ለማስጠናት ያወጣሁትን ጨረታ አሸናፊ በመሆን የድርጅቱን መዋቅር በስልሣ ቀን ውስጥ ሰርቶ ለማስረከብ ታህሣሥ 4 ቀን 1999 ዓ.ም የውል ግዴታ ገብቷል፡፡ ተጠሪ በውሉ መሠረት ብር 8,625 /ስምንት ሺህ ስድስት መቶ ሀያ አምስት ብር/ ከአመልካች የቅድሚያ ክፍያ ተቀብሎ ወስዷል፡፡ ሆኖም ተጠሪ ጥናቱን በወቅቱና በጥራት ሰርቶ ያላስረከበ ሲሆን ከአመልካች የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ በማካተት ሠርቶ አላስረከብም፡፡ ስለዚህ በቅድሚያ ክፍያነት የወሰደውን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲመልስ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ መሰረቷል፡፡ ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ በውላችን መሠረት ጥናቱን ሰርተን ሁለት ጥራዝ ለአመልካች አስረክበናል፡፡ ስለዚህ የአመልካች/ከሳሽ/ ክስ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ በአመልካች ላይ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርቧል፡፡ የተጠሪ የተከሳሽነት ክስ ይዘት ከአመልካች/ከከሳሽ/ ጋር ባደረግነው ውል መሠረት ጥናቱን አጠቅቀን አስረክበናል፡፡ ስለሆነም ያልከፈለን ቀሪ ክፍያ ብር 20,125 /ሀያ ሺህ አንድ መቶ ሀያ አምስት ብር/ ለመልካም ሥራ አፈፃፃም ዋስትና ያስያዝነውን 2,250 /ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሀምሣ ብር/ የጉዳት ካሣ በርትእ 10,000/አስር ሺ. ብር/ ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ የሚል የተከሳሽ ከሳሽነት



www.chilot.me

ክስ አቅርቧል። አመልካች በሥር በከሳሽ ተከሳሽነት ቀርቦ ተጠሪ ሥራውን በውሉ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ያላጠናቀቀና ያጠናውም ጥናት በተሰጠው ቢጋር መሠረት ያልተሰራና ከድርጅቱ የተሰጠውን ማሻሻያ መሠረት በማድረግ አስተካክሎ ባለማቅረቡ ቀሪውን ክፍያ ለመፈፀም አልገደድም። አስር ሺህ ብር ተጠሪ የጠየቀው ከህግ ውጭ ነው የሚል ክርክር አቅርቧል።

የሥር ፍርድ ቤት በአመልካች በኩል ያቀረበውን ክስና ተጠሪ ያቀረበውን ክርክር እንደዚሁም በተጠሪ በኩል ያቀረበውን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስና አመልካች በከሳሽ ተከሳሽነት ያቀረበውን ክርክር እንደዚሁም ግራ ቀኙ የየበኩላቸውን ክርክር ለማስረዳት ያቀረቧቸውን ማስረጃዎች ከመረመረ በኃላ አመልካች ጥናቱ እስከ ሰኔ 7 ቀን 1999ዓ.ም ተጠሪ ጥናቱን አጠናቆ እንዲያቀርብ ደብዳቤ የፃፈ መሆኑንና ተጠሪ ሰኔ 11 ቀን 1999ዓ.ም ሁለት ጥራዝ ጥናት ለአመልካች መላኩ በማስረጃ ተረጋግጧል። ስለሆነም አመልካች የጥናቱን ማስረከቢያ ጊዜ ለማራዘም በፃፈው ደብዳቤ መሠረት ተጠሪ ጥናቱን ያሰረከበ በመሆኑ አመልካች በውሉ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተጠሪ ጥናቱን ሰርቶ አላስረከበም በማለት ያቀረበው ክርክር ተገቢ አይደለም። ተጠሪ ጥናቱን አጠናቅቆ ያስረከበ መሆኑ ተረጋግጧል። አመልካች ተጠሪ ያቀረበው ጥናት ጉድለት ያለበት ነው በማለት የሚከራከር ቢሆንም ጥናቱ ጉድለት ያለበት ስለመሆኑ በማስረጃ ስላላስረዳ አመልካች በቅድሚያ ክፍያ የከፈለው ገንዘብ እንዲመለስለት ያቀረበው ክስ ተገቢ አይደለም በማለት የወሰነ ሲሆን የተጠሪን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በተመለከተ የሙያ ግልጋሎት ክፍያው ብር 29,750 መሆኑ በውሉ በግልፅ የተመለከተ በመሆኑና ተጠሪ ለመልካም ሥራ አፈፃፀም 2,250 /ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሀምሣ ብር/ ያስያዘ መሆኑ ስለተረጋገጠ እንደዚሁም ተጠሪ ጥናቱን በውሉ መሠረት ሰርቶ ያስረከበ ስለሆነ ቀሪ ያገልግሎት ክፍያ 20,125 /ሀያ ሺህ አንድ መቶ ሀያ አምስት ብር/ ለመልካም ሥራ አፈፃፀም የተያዘው ብር 2,250 /ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሀምሣ ብር/ ከህጋዊ ወለድ ጋር አመልካች ለተጠሪ የመክፈል ሀላፊነት አለበት። ተጠሪ ጉዳት የደረሰበት መሆኑ ስላልተረጋገጠ ብር 10,000 የጉዳት ካሣ እንዲከፈለው ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል።

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅረቧል። የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ የሚነቀፍበት የፍሬ ጉዳይ ወይም የህግ ስህተት የሌለ መሆኑን በመግለጽ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል።

አመልካች መስረከም 13 ቀን 2003 ዓ.ም ተጠሪ አመልካች በሰራው ቢጋር መሠረት ድርጅቱን ከኃላቀርነት ወደ ዘመናዊ አሠራር የሚያሸጋግር ጥናት ለማቅረብ የውል ግዴታ የገባ ቢሆንም የተጠሪ ጥናት አስራ ሁለት የሚደርሱ ጉድለቶች እንዳሉበት በአመልካች የሥራ አመራር ቦርድ ያደረገውን ውይይት ቃለ ጉባኤ በማስረጃነት አቅርበን እያለ የሥር ፍርድ ጥናቱ ጉድለት ያለበት ስለመሆኑ አያስረዳም በማለት መወሰኑ መሠረታዊ ህግ ስህተት ያለበት ነው። ከተጠሪ ጋር ያደረግነውን የሙያ ግልጋሎት ውል በማናቸውም ጊዜ በተናጠል የማፍረስ ሥልጣን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2637 ንዑስ አንቀፅ 1 በግልፅ ተደንግጎ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ይህንን ድንጋጌ በመተለለፍ ውሉ የተፈፀመ በመሆኑ ቀሪ ክፍያ ለተጠሪ ይከፈለው በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት የሰበር አቤቱታ አቅረቧል። ተጠሪ በበኩሉ ጥናቱን ሙሉ በሙሉ አጠናቅቄ ለአመልከች ማስረከቤን የሥር ፍርድ ቤት በማስረጃ አረጋግጧል። አመልካች በጥናቱ ላይ ከሙያ አንፃር ጉድለት ያለ መሆኑን ያላስረዳ ሲሆን ቀሪውን የሙያ አገልግሎት ክፍያ ላለመክፈል ያቀረበው መከራከሪያ የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ይደረግልኝ የሚል ይዘት ያለው መልሰ አቅርቧል። አመልካች የመልስ መልስ ሰጥቷል።

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ በውሉ መሠረት ግዴታውን ስለተወጣ አመልካች ቀሪውን የሙያ አገልግሎት ክፍያ ይክፈል በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ይህንን መሠረታዊ ጭብጥ ለመወሰንና በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገውን ውል ልዩ ባህሪና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎችን ይዘት መንፈስና ዓላማ ማገናዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረገውን የሙያ ግልጋሎት ውል በማናቸውም ጊዜ በተናጥል የማፍረስ መብት አለኝ በማለት የሚከራከረው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2637 ንዑስ አንቀጽ 1 በመጥቀስ ነው፡፡

የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2637 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ቃል በቃል ሲነበብ አሠሪው በማናቸውም ጊዜ ውሉን ማፍረስ ይችላል የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ ሆኖም ይህ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው መቼ ነው የሚለው ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የዕውቀት ሥራ ለመስራት ከአሠሪው ጋር ውል የተዋዋለ ሰው የዕውቀት ሥራውን ሙሉ ለሙሉ አጠናቆ ለአሠሪው ካስረከበ በኃላ በአሠሪውና የዕውቀት የሥራ ውሉን በሠራው ሠው መካከል የሚነሳው ክርክር የዕውቀት የሥራ ውሉን የሠራው ሰው ፣ የሙያ ሥራውን በልምድና የሙያ ሥራ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ የአመልካችን ጥቅም በሚያረጋግጥ አኳኃን የሙያ ሥራውን ከልብ ስርቷል ወይስ አልሰራም; የሙያ ሥራውን የሠራው ሰው የዕውቀት ሥራውን የሙያውን ደንቦች በጠበቀና በሚያሚላ ሁኔታ ፈፅሟል ወይስ አልፈፀመም የሚሉት ነጥቦች መሆናቸውን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2636 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2636 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይችላል፡፡ ስለሆነም አሠሪው በተናጠል የዕውቀት ግልጋሎት ውሉን ለማቋረጥ የሚችለው የዕውቀት የሥራ ውሉን የተዋዋለው ሰው የዕውቀት ሥራውን ሙሉ በሙሉ አጠናቅቆ ለአሠሪው ከማስረከቡ በፊት እንደሆነ ከላይ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎችና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2637 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

የሙያ ሥራ ለመሥራት የተዋዋለው ሰው የሙያ ሥራውን ሙሉ በሙሉ በማጠናቀቅ ለአሠሪው ካስረከበ በኃላ የኪነጥበብ ደንቦችን ማለትም የሙያውን ደንቦች በማፍረስ ጥፋት መፈፀሙ ካልተረጋገጠ በቀር በኃላፊነት እንደማይጠየቅ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2636 ንዑስ አንቀፅ 2 በግልጽ የተደነገገ ሲሆን የፍ/ህ/ቁ.2632 ንዑስ አንቀጽ 2 የእንግሊዘኛው ቅጅ “He shall not be liable to his client, unless he commits an error, having regard to the rules of his profession” በሚል መንገድ ከአማርኛው ቅጅ በቀላልና ግልፅ በሆነ አገላለፅ ደንግጐታል፡፡ ተጠሪ ጥናቱን ሙሉ በሙሉ ለማጠናቀቅ ለአመልካች ሰኔ 11 ቀን 1999 ዓ.ም ሁለት ጥራዝ የጥናት ሰነድ ያስረከበ መሆኑ የሥር ፍርድ ቤት በማስረጃ ያረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡

አመልካች በውሉ መሠረት ቀሪውን የሙያ ግልጋሎት ክፍያ የማይከፍልበት በቂ ምክንያት ያለው መሆኑን በተለይም ተጠሪ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2636 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የውል ግዴታውን ያልተወጣና ተጠሪ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2636 ንዑስ አንቀፅ 2 በሚደነግገው መሠረት የሙያውን ደንብ ያልጠበቀና የዕውቀት ሥራው ስህተት ያለበት መሆኑን የማስረዳት ግዴታ (Burdon of proof) አለበት፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች ተጠሪ ያቀረበው የጥናት ሰነድ በድርጅቱ የሥራ አመራር ቦርድ ታይቶ ጉድለት የተገኘበት መሆኑን የሚያሣይ ቃለ ጉባኤ በማስረጃነት ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበ መሆኑን በመግለፅ የሚከራከር ቢሆንም ይህ ማስረጃ በተጠሪ ተጠንቶ የቀረበው ሁለት ጥራዝ የጥናት ሰነድ ሙያዊ ጉድለትና ስህተት ያለበት መሆኑን

የሚያስረዳ ማስረጃ እንዳልሆነ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባለው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡

ስለሆነም አመልካች በተጠሪ ተሠርቶ በቀረበው የጥናት ሰነድ ላይ ተፈፅመዋል የሚላቸውን የሙያውን ደንብና አሠራር የሚጥሱ ጥፋቶች የማስረዳት ሸክሙን (Burdon of proof) ካልተወጣ ተጠሪ ለሰጠው ሙያዊ ግልጋሎት መክፈል የሚገባውን ቀሪ ክፍያ እንዲከፍል የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2634 ንዑስ አንቀፅ 2ን መሠረት ያደረገና የህግ ስህተት የሌለበት ነው፡፡ አመልካች በተጠሪ ተጠንቶ የቀረበው ሰነድ ሙያዊ ጉድለት ያለበት መሆኑን ይህ ሰበር ችሎት በማጣራት እንዲወስንላቸው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ለሰበር ችሎት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 የተሰጠውን ሥልጣን ያላገናዘበና የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ ከላይ በዝርዝር በገለፅነው ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ፀንቷል
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

ቅ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 60951

ቀን 19/9/2003

ዳኞች፣ ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሀመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** - የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ነገረ ፈጅ አቶ ሳሙኤል ተገኜ፣ ቀረቡ

**ተጠሪ** - ካንትሪ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር ፣ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለው ፍርድ ሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አመልካች በስር የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከሳሽ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ ነው፡፡ ክሱም ለመንገድ ስራ የሚያገለግሉትን የተለያዩ የአስፖልት ውጤቶችን እስከ ተከሳሽ ሳይቶች ድረስ ለማቅረብ ተከሳሽ መ/ቤት ያወጣውን ጨረታ ተወዳድሬ በማሸነፍ የሥራ አፈፃፀም ዋስትና (contractual security) የጠቅላላ ሥራ ዋጋ 10% ብር 9,559,525.37 ከወጋገን ባንክ የተሰጠ ዋስትና አስይዤ ስለእቃውም አቅርቦት ከተከሳሽ መ/ቤት ጋር እንደ አውሮፖ አቆጣጠር ሰፕቴምበር 20/2007 ውል የገባን ሲሆን ከሳሽ ከገባሁት ግዴታዎች የአስፖልት ውጤቶችን አቅርቤ Ac 60/70 ተብሎ ከሚታወቀው የአስፖልት አይነት ማቅረብ ከሚገባኝ 8.276 ሜትሪክ ቶን ውስጥ 3,829.5 ሜትሪክ ቶን ብቻ አላቀረብኩም፡፡ ምክንያቱም በውሉ ይደርሳሉ ተብሎ ያልተገመቱ ጉዳዮች ውሉን በከፍተኛ ሁኔታ በማናወጣቸዉ ሲሆን ከተከሳሽ ጋር በመወያየት በቅድሚያ የተቀበልኩትን 10,224,989.13 ብር ተመላሽ በማድረግ ውሉ ተቋርጧል፡፡ ሆኖም ተከሳሽ መ/ቤት ለመልካም አፈፃፀም ዋስትና ካስያዝኩት ፋይናንሻል ጋራንቲ ቦንድ ውስጥ ላላስረከብኩት የአስፖልት ውጤት መጠን ብር 3,557,729.34 በመቁረጥ ቀሪውን ገንዘብ እንደሚመልስልኝ ገልጿል፡፡ ስለሆነም ተሰካሽ ብር 3,557,729.34 ያስቀረብኝና ለተከሳሽ ባቀረብኳቸው የአስፖልት ውጤቶች ብር 497,735 ኪሣራ የደረሰብኝ በመሆኑ የተጠቀሰው ገንዘብ ወጪና ኪሳራ ተጨምሮ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ለክሱ ተከሳሽ የሰጠው መልስ ከሳሽ ኪሳራ ገጥሞኛል ይበል እንጂ ደረሰብኝ የሚለው ኪሣራ አስቀድሞ ሊገመት የሚችል ነው፡፡ ተከሳሽ መ/ቤት ለሚሰራው እና ለሚያስጠግነው መንገድ በእቅድ የሚሠራ በመሆኑና ከሳሽም ማቅረብ የሚገባውቸውን የአስፓልት ውጤቶች በግዜ ካለማቅረቡ የተነሳ በተከሳሽ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል፡፡ Ac 60/70 ከተባለው የአስፓልት ውጤት ውስጥ 3829.5 ሜትሪክ ቶን እስካሁን ድረስ አላቀረበም፡፡ ተከሳሽም ለደረሰበት ጉዳት ከሳሽ ለመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ካስያዘው ገንዘብ ውስጥ ብር 3,557,927.34 መውሰዱ አግባብነት አለው ይህ

ለመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና የተያዘው ገንዘብ ለሚደርሰው ጉዳት እንደሚውል በውላችን የተስማማነው ጉዳይ ነው፡፡ በውሉ ምክንያት ኪሳራ ብር 497,735 ደርሶብኛል በማለት እንዲከፈለው የጠየቀውም ቢሆንም ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም በውላችን በማናቸውም ሁኔታ የዋጋ ማስተካከያ እንደማይደረግ ተስማምተናል በማለት የከሳሽ ክስ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡

የግራ ቀኙን ክርክር የመረመረው የሥር የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ከሳሽ ለማቅረብ የውል ግዴታ ከገባው የአስፓልት ውጤት ውስጥ 3829.5 ሜትር አለማስረከቡን አምኗል፣ ውሉም በግራ ቀኙ ስምምነት የተቋረጠ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም፣ ከሳሽ ከአቅም በላይ የሆኑ ምክንያቶች ናቸው በማለት የዘረዘራቸው ምክንያቶች በፍ/ህ/ቁ 1792/2/አንፃር ሲታዩ ከአቅም በላይ የሆኑ ምክንያቶች ናቸውየሚባሉ አይደሉም፣ተከሳሽ በደብዳቤ እንደገለፀው የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘብ ቀንሶ ያስቀረው ከሳሽ ያስረከበውን እና ያላስረከበውን መጠን በማመጣጠን ሲሆን ይህን ተከሳሽ በራሱ መወሰኑ ተገቢነት ያለው አይደለም፡፡ የተከሳሽ መ/ቤት ኪሳራ ደርሶበታል ቢባል እንኳን በፍ/ቤት ክስ ቀርቦ ከሚያስወስን በስተቀር የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ለደረሰበት ኪሣራ መቀነስ የለበትም ሲል ቀንሶ ያስቀረውን የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘብ ብር 3,557,927.34 ለከሳሽ እንዲመልስ ሲወስን ከሳሽ በተጨማሪ ኪሣራ ገጥሞኛል ሲል የጠየቀውን የኪሳራ ገንዘብ ብር 497,735 ተከሳሽ ሊጋራ አይገባውም ብሏል፡፡

የሥር ተከሳሽ በሥር የፌ/ከ/ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም ሲል በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት አጽንቷል፡፡

በሥር ፍ/ቤት ውሳኔ አመልካች መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት የቅሬታ ነጥቦች ለዚህ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን በዋናነት የጠቀሣቸውም ለዚህ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው የመንግስት የግዥ ስርአት ለመወሰን የወጣው የአዋጅ ቁጥር 430-97 ሆኖ እያለ ፍ/ቤቱ አግባብነት የሌለውን የፍትሃብሔር ህግ ቁጥር 1790/1/ እና 1799 ለውሳኔው መሰረት ማድረጉ ተገቢነት የለውም፣ ለውሳኔው አግባብነት አለው እንኳን ቢባል የበሰለ የጉዳት ካሳ (liquidated Damages) በተመለከተ በውሉ ጠቅላላ ክፍልና ልዩ ሁኔታ አንቀጽ 27 የተስማማንበት ጉዳይ ስለሆነ የፍትሐብሔር ህግ ቁ. 1894 እንደተደነገገው አመልካች ስምምነት በተደረሰበት ጉዳይ ላይ የጉዳቱን ልክ ሆነ መጠን የማስረዳት ሀላፊነት የለበትም፡- ስለሆነም ተጠሪው ካስያዘው የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘብ በስምምነቱ መሰረት ቆርጦ የመውሰድ መብት አለው፡፡

ይህ ሆኖ ሳለ ይህንኑ ገንዘብ አመልካች በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ማስወሰን አለበት የተባለው በፍ/ህ/ቁ 1731፤ በውሉ አንቀፅ 18/2/ እና በመንግስት እቃ ግዢ መመሪያ አንቀፅ 11/14/2 መሰረት ተቀባይነት የለውም የሚሉ ናቸው፡፡

ለሰበር አቤቱታ ተጠሪው በሰጠው መልስ ከአመልካች ጋር የነበረው ውል በመቋረጡ ላስረከበው እቃ ለሚደርሰው ጉዳት ማካካሻ የሚከፈለውን ካሳ ስምምነት ያላደረገ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ያልቀረበውን እቃ በተመለከተ የካሳ መጠን አመልካች ክስ አቅርቦ ከሚያስወስን በቀር ጉዳት መኖሩንም ሆነ የካሳውን ልክ ራሱ ወስኖ ሊወስድ እንደማይችል የሰጡት ውሳኔ በፍ/ህ/ቁ 3200 መሰረት ህጋዊ ነው፣ አመልካች ተጠሪ በውሉ አንቀፅ 27 መሰረት የተስማሙትን ዘግይቶ ለቀረበ ዕቃ የሚከፈል መቀጫን እንጂ ውሉ በመቋረጡ ላልቀረበ ዕቃ የሚደርስ ጉዳትን በተመለከተ አይደለም፣ ተጠሪ ላስረከበው ዕቃ የተረጋገጠ ጉዳትም ቢሆን ኪሳራ ሊከፍል አይገባም፣ አመልካች



www.chilot.me

በውሉ አንቀፅ 27 መሰረት ሊከፍለኝ የሚገባውን መቀጫ በውሉ አንቀፅ 18 መሰረት ከዉል ማስከበሪያ ላይ የመቀነስ መብት አለኝ በማለት ያቀረበው ቅሬታ የህግ መሰረት የለውም በማለት የሥር ከፍ/ፍ/ቤትም ሆነ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት አመልካች ከዘረዘራቸው የቅሬታ ነጥቦች አንፃር የፈፀሙት የህግ ስህተት የለም ሲል ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ የቀረበው ሲሆን እኛም ተጠሪው ለመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ካስያዘው ገንዘብ ውስጥ ባልፈፀመው የውል ግዴታ መጠን አመልካች ቀንሶ ማስቀረቱ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ለዚህ ለተያዘው ጭብጥ ከአመልካች በኩል የቀረበው ክርክር በአዋጅ ቁጥር 430/97፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሐምሌ 1997 ባወጣው የመንግስት ዕቃ ግዥ መመሪያ በአመልካችና ተጠሪ መካከል በተደረገው ውል መሰረት ተጠሪው ለመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ካስያዘው ገንዘብ ውስጥ ባልተፈፀመው የውል ግዴታ መጠን የመቀነስ መብት አለኝ የሚል ነው፡፡ ተጠሪው ግን አመልካች ለመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ከተያዘው ገንዘብ ውስጥ በራሱ ስልጣን ቀንሶ ለማስቀረት አይችልም ሲል ተከራክሯል፡፡ ተጠሪው ለዚህ ክርክር አግባብነት አለው በማለት በዋናነት የጠቀሰውም የፍ/ብ/ህ/ቁ 3200 ነው፡፡ የተጠቀሰው የፍ/ብ/ህ/ቁ 3200 ከአስተዳደር መ/ቤቶች ጋር የሚደረገውን ውል የሚመለከት ሲሆን ድንጋጌው በመርህ ደረጃ የቅድሚያ ልዩ መብት እንደማይኖር የሚናገር ነው፡፡ በዚሁ ህግ መሰረትም የአስተዳደር መ/ቤቱም ተዋዋዩ ውሉን ባለመፀሙ የሚያስቀጣ ጥፋት አድርጓል በማለት በገዛ ራሱ አንድ ውሳኔ ለማድረግ ወይም በተዋዋዩ ግዴታ አለመፈፀም ወይም ለመፈፀም በመዘግየቱ ምክንያት የሚፈለግበትን ኪሣራ ልክ በገዛ ራሱ ለመወሰን አይችልም፡፡

ይሁን እንጅ ለዚህ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያላቸው የመንግሰት የግዥ ሥርአትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 430/97 እና የመንግስት የግዢ መመሪያ እንዲሁም ግራ ቀኙ የገቡት ውል እንጅ የተጠቀሰው የፍትሀብሔር ህግ ድንጋጌ አይደለም፡፡ ምክንያቱም በህግ አተረጓጎም ረገድ ለዚህ ለተያዘው ጉዳይ የፍ/ህጉ አጠቃላይ ህግ ሲሆን የመንግስት የግዥ ሥርአትን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 430/97 ልዩ ህግ በመሆኑ ከግዥ ጋር ተያይዞ ለሚነሳ ክርክር ተፈፃሚ የሚሆነው ይኸው አዋጅ ነው፡፡

አዋጅ ቁጥር 430/97 አንቀፅ 43 ስለ ውል ማስከበሪያ (contract security) የሚደነግግ ሲሆን አቅራቢው በውሉ መሰረት ባለመፀሙ በግዢ ፈፃሚው አካል ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ማካካሻ የሚውል ማስከበሪያ ለግዥ ፈፃሚው አካል መስጠት አለበት ይላል፡፡ የግራ ቀኙ ተዋዋዮችም ይህንኑ አስገዳጅነት ያለውን የህግ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ በውላቸው የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ያካተቱ ሲሆን ተጠሪው በውሉ መሰረት ማስረከብ የሚገባውን Ac 60/70 የተባለውን የአስፋልት ውጤት ቀንሶ በማስረከቡ በአመልካች ላይ ጉዳት መድረሱን ክርክሩ ያመለክታል፡፡ ይህ በመሆኑ አመልካች በውሉ አንቀፅ 18/2/ እንደተጠቀሰው በውሉ መሰረት ተጠሪው ግዴታውን ባለመፈፀሙ የተነሳ ለተፈጠረው ጉድለት መያዣ ከነበረው ከመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘብ ቀንሷል፡፡ ሐምሌ1997 የገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ያወጣው የግዥ መመሪያ አንቀፅ 11/5/ም ቢሆን አቅራቢው ዕቃውን አጠናቅቆ ባለማስረከቡ ርክክቡ ባልተፈፀመበት ግዢ ላይ በየቀኑ 0.1 ወይም 1/1000 መቀጫ እንደሚከፍል ይናገራል፡፡

መመሪያው መቀጫ የውሉን ዋጋ 10% የሚበልጥ በሚሆንበት ጊዜ ግዥ ፈፃሚው ውሉን የመሰረዝ መብት እንዳለው እና የውሉ አፈፃፀም መዘግየት በግዥ ፈፃሚ ስራ ላይ ችግር የሚያስከትል ከሆነ ግዥ ፈፃሚው የመቀጫውን መጠን 10% ሳይጠብቅ ውሉን መሰረዝ እንደሚችል ጭምር በቁጥር 11.7/5/ /ለ//ሐ/ ይገልፃል፡፡

በመሆኑም ከአዋጁ አንቀፅ 43፣ ከመመሪያው ቁጥር 11.7/5/ /ሀ-ሐ/ እንዲሁም ከውሉ አንቀፅ182፣27.1 ይዘት አንፃር ሲታይ አመልካች ለመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ከተያዘው ገንዘብ ባልተፈፀመ ውል ግዴታ መጠን ቀንሶ መውሰዱ አግባብነት አለው፡፡ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና የሚያዘውም አቅራቢው በውሉ መሰረት ግዴታውን ባለመፈፀም የተነሳ ግዥ ፈፃሚው ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ተገቢውን መቀጫ አቅራቢው ከዚሁ ገንዘብ እንዲከፍልና ውሉን አክብሮ በውሉ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ግዴታውን እንዲፈፅም ታስቦ ነዉ፡፡ ስለሆነም አመልካች ለመልካም ስራ አፈፃፀም ተጠሪው ያስያዘውን ገንዘብ ራሱ ቀንሶ የአስፋልት ውጤቱ ባለመቅረቡ የተነሳ ለተፈፀመው ጉድለት ማስቀረት አይችልም በማለት በስር ፍ/ቤት የተወሰነዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 79497 በቀን 30/4/2002 በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እንዲሁም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 52052 በቀን 24/1/2003 የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል፡፡

2. ተጠሪው ለመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ካስያዘው ገንዘብ አመልካች ቀንሶ ያስቀረውን ብር 3,557,929.34 /ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ አምሳ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃያ ዘጠኝ ከሰላሳ አራት ሳንቲም /ለተጠሪው ሊመልስ አይገባም ብለናል፡፡

3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ አመልካችና ተጠሪ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ ይሁን፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሂአ/



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 64203

ግንቦት 15 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

***አመልካች*** ፡- የኢት/ንግድ ባንክ አልቀረበም

***ተጠሪዎች*** ፡- 1. አቶ መሐመድ ሙሳ

2. ወ/ሮ ሐሊማ ሃብቤ

3. ወ/ሮ ነኢማ ዩያ

4. ወ/ሮ ሽኩር ዋቃዩ

(ከ1-4 ላሉት) ተወካይ አቶ መሐመድ ሙሣ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ተጠሪዎች በስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሳሾች ሲሆኑ አመልካች 2ኛ ተከሳሽ፣ እንዲሁም የኢት/ መንገዶች ባለሥልጣን 1ኛ ተከሳሽ፣ የሚጨታ ከተማ አስተዳደር ደግሞ 3ኛ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ ክሱም በሚጨታ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ በ1226 ካሬ ሜትር ላይ የሰፈረውን ግምቱ 250,000 ብር የሚያወጣውን የከሳሾች ቤት 1ኛ ተከሳሽ በብር 162,306 ብቻ በመገመት ይህንኑ ገንዘብ 1ኛ ተከሳሽ ለ2ኛ ተከሳሽ ሰጥቶ 2ኛ ተከሳሽም ከከሳሾች ጋር ምንም ዓይነት የዋስትናም ሆነ የብድር ውል ሳይኖር ገንዘባችንን የያዘብን ሲሆን 3ኛ ተከሳሽ ደግሞ የተለያዩ መብታችንን የሚጋፉ ደብዳቤዎች የሰጠ ስለሆነ ተከሳሾቹ የቤታችንን ግምት ብር 250,000 ከወጪና ኪሳራ ጭምር እንዲከፍሉ ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

የሥር 1ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በስር ፍ/ቤት በተደረገ ክርክር ከክሱ የወጡ ሲሆን የ2ኛ ተከሳሽ መልስ 1ኛ ከሳሽ በ23/7/1986 ዓ.ም ከባንኩ ጋር በተደረገ ውል ብር 40,000 ተበድሮ ባለመክፈሉ የተነሳ ወለድ ተጨምሮበት ብር 71,398.67 እዳ አለበት፣ እንዲሁም ወንድሙ ሶፍያን ሙሳ የተባለው ከባንኩ ጋር በተደረገ ውል ገንዘብ ሲበደር ከሳሽም የአንድነትና ነጣላ ዋስትና የገባ ሲሆን ከተበዳሪው የሚፈለገው ብር 19,583.53 በመሆኑ ከሳሽ ገንዘቡን የመክፈል ግዴታ ስላለበት በአጠቃላይ ከ1ኛ ከሳሽ ብር 90,583.59 የሚፈለግበት በመሆኑ ይህው ገንዘብ ተቀንሶ ቀሪውን ብር 71,727.27 ከሳሾች እንዲወስዱ ቢነገራቸውም ለመውሰድ ፈቃደኞች አይደሉም የሚል ሲሆን 1ኛ ከሳሽ የፈረመውን የብድር ውል እና የዋስትና ሠነድ አያይዞ አቅርቧል፡፡



www.chilot.me

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የመረመረው የስር ከፍተኛ ፍ/ቤትም ባንኩ በብድር ውሉ አንቀጽ 15 መሠረት በርሱ ዘንድ የተቀመጠውን ገንዘብ ለሚፈለገው የብድር እዳ እንዲቻቻል ከሚያደርግ ውጪ በሐዋላ አገልግሎት የተላከውን በእንቅስቃሴ የሚገኘውን ገንዘብ ለእዳው ማቻቻል አይችልም በማለት 1ኛ ተከሳሽ ማለት የኢት/መንገዶች ባለሥልጣን የላከውን የከሳሾች ገንዘብ ብር 162,306.90 ይመልስ በማለት ፈርዷል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በበኩሉ ክርክሩ በይግባኝ ቀርቦለት ከመረመረ በኋላ ቤቱ በዋስትና የተያዘ ስለመሆኑ ውሉ የሚያመለክት አይደለም፡፡ ይግባኝ ባይ /ያሁን አመልካች/ ውሉን መሠረት አድርጐ ክስ አቅርቦ እዳውን ማስከፈል ከሚችል በቀር የመ/ሰጪዎችን ገንዘብ መያዙ አግባብነት የለውም፡፡ በስር ከፍተኛ ፍ/ቤትም ቢሆን ስለ ብድር ውል አንቀጽ 15 የሰጠው ትርጉም አግባብ ሆኖ አላገኘሁም በማለትና የውሳኔውን ድምዳሜ በመቀበል ይግባኝ ባይ ለመልስ ሰጪዎች የያዘውን ገንዘብ ይመልስ መባሉ የሚነቀፍ አይደለም ተብሏል፡፡

በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ቅር የተሰኘው የአሁን ሰበር አመልካችም ባቀረበው ቅሬታ አመልካች በግልጽ ከተጠሪዎች ጋር ባደረገው የብድር ውልና የአንድነትና የነጠላ ዋስትና ውል መሠረት ገንዘቡ ባለመከፈሉ ዕዳውን ለማቻቻል በማንኛውም መልኩ በባንኩ ዘንድ በባለእዳዎች ስም የተቀመጠውን ገንዘብ መውሰድ የሚችል ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤቶች ለተጠሪዎች እዳ ገቢ የተደረገውን ገንዘብ አመልካች እንዲመልስ መወሰናቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው ብሏል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሰጡት መልስ ከአመልካች ጋር የተፈራረምነው የብድርም ሆነ የአንድነትና የነጠላ ዋስትና ውል የለም፣ በፍትሐብሔር ህግ አንቀጽ 1832 እና 1833 መሠረትም የእዳ ማቻቻያ የሚያስደርጉ ምክንያቶች የሉም በማለት የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጐ የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ እንደተገለፀው የቀረበ ሲሆን እኛም አመልካች ለተጠሪዎች የቤት ግምት የተላከውን ገንዘብ ለእዳ ማቻቻያነት መያዙ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በፍታብሔር ህጋችን እዳን ለማቻቻል የሚቻለው በሶስት መንገዶች ሲሆን 1ኛው መንገድ በፍታብሔር ህግ አንቀጽ 1838/1/ እንደተጠቀሰው ባለእዳውን እንዲቻቻልለት መፈለጉን ለባለገንዘቡ ሲያስታውቅ ወይም ባለእዳው እዳው እንዲቻቻልለት ስምምነቱን ሲገልጽ ነው፡፡ 2ኛው የማቻቻያ መንገድ ደግሞ ሁለቱ ወገኖች በውል ፈቃዳቸውን ሲገልጹ መሆኑን የፍ/ህ/ቁ 1840 ያመለክታል፡፡ 3ኛው የእዳ ማቻቻያ መንገድ ደግሞ በፍ/ህ/ቁ 1841 መሠረት በፍ/ቤት የሚደረገው ማቻቻያ ነው፡፡

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የማቻቻያ መንገዶች አመልካች ጠቅሶ የሚከራከረው የእዳ ማቻቻያ መንገድ ማለትም የብድሩንና የዋስትና ውሎች ሲሆን ውሎቹም በፍ/ህ/ቁ 1731 መሠረት በመካከላቸው ህግ ሆነው ይገዛሉ በሚል ነው፡፡ በዚህም መነሻ ለእዳው ማቻቻያነት ገንዘቡ የተያዘው ተገቢ ነው ይላል፡፡

የአመልካች እና ተጠሪዎች የእዳ ማቻቻያ ክርክርን ለመወሰን የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት መሠረት ያደረገው ተያይዞ የቀረበለትን የብድር ውል አንቀጽ 15 ነው፡፡ ይህ የተጠቀሰው የውሉ አንቀጽ "ተበዳሪው በዚህ ውል ላይ የተገለፀውን ማናቸውንም ግዴታ ያልፈፀመ እንደሆነ በባንኩ ዘንድ ያስቀመጠውን ገንዘብ ወጪ በማድረግ ለእዳው ለማቻቻል ባንኩ መብት አለው" ይላል፡፡ ይህ

የውል ድንጋጌ የሚናገረው በባንኩ ዘንድ ባለእዳው ያስቀመጠውን ገንዘብ ነው፡፡ አመልካች ግን 1ኛ ተጠሪ በአመልካች ባንኩ ያስቀመጠውን ገንዘብ ሳይሆን በስር 1ኛ ተከሳሽ የተላከለትን ገንዘብ ነው፡፡ በተጠቀሰው የውል አንቀጽም በባንኩ ከተቀመጠ ገንዘብ ውጪ በሌሎች መንገዶች የተገኙ የባለዳውን ገንዘቦች ለእዳው ማቻቻያነት የሚያዙ ወይም ገቢ የሚደረጉ ስለመሆናቸው አልተገለፀም፡፡ በመሆኑም አመልካችና ተጠሪ የገባነው ውል በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1731 መሠረት አስገዳጅ ነው በሚል ብቻ በውሉ ውስጥ ባልተካተተ ጉዳይ በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ አመልካች ለእዳው ማቻቻያ ማድረጉ የህግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘንም፡፡ በመሆኑም በስርፍ/ቤት አመልካች የያዘውን ገንዘብ ለተጠሪዎች ይመልስ በሚል በተሰጠ ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 15734 በቀን 25/10/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔና የስር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 106858 በቀን 25/4/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለባቸው ስለሆኑ ፀንተዋል፡፡
2. ይህ ውሳኔ አመልካች ከተጠሪዎች የሚፈለግባቸው እዳ ካለ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ክስ አቅርቦ የማስወሰን መብቱን የሚያስቀርበት አይሆንም፡፡
3. አመልካች የያዘውን የተጠሪዎች ገንዘብ እንዲመልስ ተወስኗል፡፡
4. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የየራሳቸው ይችሉ፡፡
5. ከዚህ በፊት በዚህ ጉዳይ በመ/ቁ 17488 ተጀምሮ የነበረው አፈፃፀም እንዲታገድ የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
6. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ ይሁን፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡***

ም/አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 46574

መጋቢት 9 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

**አመልካች ፡-** ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ - ይሁንልኝ ቡሎ ቀረበ

**ተጠሪዎች ፡-** 1. ዮናስ ካሣ አልቀረበም

2. ወ/ሮ በለጡ አጎታለም ቀረበች

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ ሰበር መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ ለትምህርት (ለስልጠና) የተደረገው ወጪ በውሉ መሠረት ይመለስልኝ በማለት አመልካች የመሠረተውን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው 1ኛ ተጠሪ በውሃ (ወተር) ኢንጂነሪንግ የማስትሬት ዲግሪ ትምህርቱን በአመልካች ድጋፍ እና ትብብር ፈቃድ ወደ ቤልጂየም ሀገር ሄዶ እንዲማር እና ተምሮ ሲመለስም ለተማረበት ሁለት ዓመት ሦስት እጥፍ ማለትም ስድስት ዓመት አመልካችን ለማገልገል፣ ይህን ማድረግ ካልቻለ ደግሞ ለትምህርት የወጣውን እና ለቤተሰቡ የተከፈለውን ደመወዝ በጠቅላላው ብር 190,470.00 ለአመልካች እንዲከፍል ስምምነት ተደርጎአል፡፡ 2ኛ ተጠሪም 1ኛ ተጠሪ ግዴታውን ባይወጣ ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ገንዘቡን ለመክፈል ግዴታ ገብታለች፡፡ ሆኖም 1ኛ ተጠሪ በገባው ግዴታ መሠረት ተመልሶ ለማገልገል ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለዚህም ሁለቱም ተጠሪዎች ገንዘቡን ይከፍሉ ዘንድ ይወሰንልኝ በማለት ነው አመልካች ክሱን የመሠረተው፡፡ ክሱ የቀረበለት የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት ተጠሪዎች የሰጡትን መልስ ካየ በኋላ፣ 1ኛ ተጠሪ በአሁኑ ጊዜ በመማር ላይ እንደሆነ ማስረጃ ቀርቦልኛል የሚል ምክንያት በመስጠት ክሱን ሰርዞአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች የተሰጠውን ትዕዛዝ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ የተሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ይግባኝ የተባለበትን ትዕዛዝ አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 4 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ ስህተቱ ይታረምለት ዘንድ ጠይቆአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በግራ ቀኝ ወገኖች የተገባውን ውል መሠረት ያደረገ



www.chilot.me

ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ጭብጡን ግራቀኝ ወገኖች ካሰሙት ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ግራ ቀኝ ወገኖች ካቀረቡት ክርክር መገንዘብ እንደቻልነው ለክሱ መነሻ የሆነው ውል በግራቀኙ መካከል ስለመደረጉ እና 1ኛ ተጠሪም ወደቤልጅየም ሃገር ሄዶ የማስተርስ ዲግሪውን ስለማግኘቱ አልተካደም ወይም አከራካሪ አልሆነም፡፡ ተጠሪዎች ክሱን የተቃወሙት 1ኛ ተጠሪ የማስተርስ ዲግሪውን ካገኘ በኋላ ወደ አሜሪካን ሃገር በመሄድ ለፒ.ኤች. ዲግሪ ትምህርት በመቀጠል ላይ ስለሆነ በውሉ መሠረት ተመልሶ አመልካችን ሊያገለግል አልቻለም በሚል ገንዘቡን እንዲከፍል አይገደድም የሚል ምክንያት በመስጠት ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም ይህን በተጠሪዎች የቀረበውን የመከራከሪያ ነጥብ እንዳለ በመቀበል ነው ክሱን ውድቅ ያደረጉት፡፡ አመልካች 1ኛ ተጠሪ የቀጠለውን ትምህርት ጨርሶ ሲመለስ ክሱን ማንቀሳቀስ ይችላል በማለትም ነው ክሱን የሰረዙት፡፡ አመልካች በዚህ መልኩ የተሰጠውን ውሳኔ የተቃወመው በመሃከላችን የተደረገውን ውል እና ሕጉን መሠረት ያደረገ አይደለም በማለት ነው፡፡

በበኩላችን እንደምናየው እና እንደምንገነዘበው ክርክሩ ሊወሰን የሚገባው በግራቀኝ ወገኖች የተደረገውን ውል እና አግባብነት ያለውን ሕግ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ከሁሉ በፊት የውሉን ይዘት እንደዚሁም ውሉ ለተዋዋይ ወገኖች የሰጠውን መብት እና የጣለውን ግዴታ መመርመር ተገቢ ይሆናል፡፡ በክርክሩ እንደተገለጸው አመልካች 1ኛ ተጠሪን በማስተርስ ዲግሪ ለማስተማር ግዴታ የገባ ሲሆን፣ ተጠሪዎች ደግሞ በውሉ ለተመለከቱት ዓመታት አመልካችን ለማገልገል፤ ይህ ካልተፈጸመ ደግሞ ለትምህርቱ የወጣውን ወጪ ለአመልካች ለመተካት ግዴታ ገብተዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በውሉ መሠረት ትምህርቱን ጨርሶ የማስተርስ ዲግሪውን ያገኘ ቢሆንም፤ ወደ አገሩ በመመለስ ለአመልካች አገልግሎት አልሰጠም ወይም ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ይህም ማለት ውሉ በሰጠው መብት የተጠቀመ (ትምህርቱን የተማረ) ሲሆን፣ ግዴታውን ግን አልፈጸመም፡፡ የፒ.ኤች ዲግሪ ትምህርት እንዲቀጥል የሚያስችለው ተጨማሪ ስምምነትም ከአመልካች አላገኘም፡፡

በሕጉ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች ባቋቋሙዋቸው ሰዎች ላይ ሕግ ስለመሆናቸው በፍትሐብሔር ሕግ ቁ.1731 በተቀመጠው ድንጋጌ ተመልክቶአል፡፡ ውለታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ግልጽ ሆኖ ከሚሰማው በመራቅ ወይም ከዚሁ በመውጣት በፍ/ቤት ሊተረጎሙ እንደማይችሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁ.1733 ተደንግጎአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ለክርክሩ መሠረት የሆነው ውል ግልጽ ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ ተመልሶ አመልካችን ለማገልገል ግዴታ የገባው የማስተርስ ዲግሪውን ካገኘ በኋላ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ትምህርቱን ጨርሶ ዲግሪውን እንዳገኘ ተረጋግጠአል፡፡ በመሆኑም የማገልገል ግዴታውን መወጣት የሚችለው በኋላ የጀመረውን የፒ.ኤችዲ ድግሪ ትምህርቱን ከጨረሰ በኋላ ነው ለማለት የሚቻልበት የውልም ሆነ የሕግ አግባብ የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ወደሌላኛው ጫፍ (ትምህርቱን ጨርሶ ከተመለሰ በኋላ ክሱ ይቀጥል ወደሚለው) የሄዱት ግልጽ የሆነውን ውል ግልጽ ሆኖ ከሚታየው በመውጣት እንደሆነ ነው መገንዘብ የቻልነው፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ በዚህ መሠረትም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የሐዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት በመ.ቁ 03288 ጥር 26 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 64401 መጋቢት 11 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. የሐዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት ክርክሩን በተከፈተው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ በጉዳዩ ሥረ ነገር ገብቶ አመልካች ባቀረበው የክፍያ መጠን ላይ ክርክር እንዲሰማ፤ በመጨረሻም ተገቢውን ይወስን ጉዳዩ ይመለስለት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.341(1) መሠረት ወስነናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

ራ/ታ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 56569

መጋቢት 23 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች** ፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- አቶ ዳዊት አሠፋ - ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- አቶ ተሻለ ደስታ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለው ፍርድ ሠጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አመልካች የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ጭብጥ ተመሥርቶ ለሰበር የቀረበ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ የመኪና ሽያጭ ውልን የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ በከሣሽነት ቀርበው ተከሣሽ /አመልካች/ ለከሣሽ /ተጠሪ/ና በሥር ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ ተከራካሪ ለነበሩት ወ/ሮ ደብሪቱ በየነ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-07999 ኦ.ሮ የሆነውን መኪና በብር 250,000 /ሁለት መቶ ሀምሣ ሺ ብር/ ሸጠዋል፡፡ ከመኪናው ዋጋ ውስጥ ገዥዎች ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺ ብር/ የከፈልን ሲሆን ሻጭ /አመልካች/ ውል ክፍል ቀርበው ውሉን ባለመዋዋላቸው የመኪናው ባለሀብትነት ሊተላለፍልን አልቻለም፡፡ የመኪናው ባለሀብትነት ለገዥዎች ባለመዛወሩ መኪናውን ለማስመርመርና ቦሎ ማድረግ ስላልተቻለ ከመጋቢት 2000 ዓ.ም. ጀምሮ መኪናው ሥራ አልሰራም ስለሆነም ከሣሽና ጣልቃ ገብ በወር ብር 8000 /ስምንት ሺ ብር/ ገቢ ያጣን በመሆኑ ብር 20000 ጨምረው ተከሣሽ እንዲከፍሉ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተከሣሽነት ቀርበው ሻጭ የሽያጭ ውሉን በአግባቡ ፈፅሜአለሁ፡፡ የመኪናውን ይዞታ ለገዥዎች አስተላልፈዋል፡፡ የመኪናውን ባለቤትነት ለማስተላለፍ የሚያስፈልጉትን ሰነዶች ለገዥዎች አስተላልፈዋል፡፡ የመኪናውን ባለቤትነት ለማስተላለፍ የሚያስፈልጉትን ሰነዶች ለገዥዎች ሰጥተዋል፡፡ የመኪናውን ስመሀብት የማዞር የእኔ የሻጭ ግዴታና ሀላፊነት አለመሆኑ እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተከራክረን ውሣኔ ተሰጥቶበታል፡፡ ውሉ እንዲፈርስ የቀረበው ክስ የህግ መሠረትም የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የመኪናውን ሻጭ የሆነው ተከሣሽ /አመልካች/ የመኪናውን ባለሀብትነት ለገዥዎች /ተጠሪ/ ለማስተላለፍ አስፈላጊ የሆነውን የመኪና ሽያጭ ውል በውል አዋዋይ ፊት ለመፈረም ፈቃደኛ አይደለም ስለዚህ ተከሣሽ ግዴታውን ያልፈፀመ በመሆኑ ውሉ ሊፈርስ ይገባዋል፡፡ ተከሣሽ /አመልካች/ ከሣሽና /ለተጠሪና በሥር ጣልቃ ገብ ተከራካሪ ለሆኑት ለእያንዳንዳቸው ብር 112,500 /አንድ መቶ አሥራ ሁለት ሺ አምስት መቶ ብር/ በድምሩ ብር 250,000 /ሁለት መቶ ሀምሣ ሺ ብር/ ይክፈል፡፡ ከሣሽ /ተጠሪና/ ጣልቃ ገብ መኪናውን ለተከሣሽ /ለአመልካች/ ያስረክቡ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የሥር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 121731 ጥቅምት 28 ቀን 2001 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅረበዋል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ሻጭ /ይግባኝ ባይ/ መኪናውን የሚመለከቱ አስፈላጊ ሰነዶችን ለገዥዎች /ለመልስ ሰጭዎች/ አስረክቧል፡፡ መኪናውን ለገዥዎች አስረክቧል የመኪናውን ባለሀብትነት ወደ ገዥዎቹ የማዛወር ኃላፊነት የሻጭ /ይግባኝ ባይ/ እንዳልሆነ ከዚህ በፊት ግራ ቀኙ እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባደረጉት ክርክር የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35601 ውሣኔ ሰጥቶበታል የመኪና ሽያጭ ውል በውል አዋዋይ ፊት እንዲደረግ የሚያስገድድ የህግ ድንጋጌ የለም፡፡ ሻጭ /ይግባኝ ባይ/ የመኪና ሽያጭ ውሉን አሟልቶ የፈፀመ ስለሆነ ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ግንቦት 25 ቀን 2002 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 45360 ሚያዝያ 29 ቀን 2002 ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ የወሰነው ከዚህ በፊት ተጠሪ የመኪናውን ሽያጭ ውል እንዲፈፅም ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርበው ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተከራክረን ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35601 የሰጠውን ውሣኔ የሚሽርና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ አንድ ውል የማይፈፀመው ውሉ ሣይፈፀም የቀረ ወይም ውሉ ሊፈፀም የማይችል ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ አመልካች ከሶስት ዓመት በፊት የሽያጭ ውሉን ፈፅሜአለሁ፡፡ ስለዚህ የመኪናው ባለሀብትነት ወደ ገዥዎች አላዛወርክም በማለት ውሉ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ መኪናው የቆመው ለፍርድ ማስፈፀሚያነት ስለተያዘ ነው የመኪናው ዲፕሪሼሽን ዋጋና ገዥዎች በመኪናው በመጠቀም ሲሰበስቡት የነበረው ገቢ ሣይታሰብ መኪናውን በመውሰድ ገንዘባቸውን ይክፈላቸው በማለት የተሰጠው ውሣኔም መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው ጥቅምት 19 ቀን 2003 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ እኔና አመልካች ከዚህ በፊት የተከራከርንበት ጭብጥ የሚያስነሳው የህግ ጥያቄ አሁን ከምንከራከርበት ጉዳይ የተለየ በመሆኑ አመልካች ጉዳዩ ከዚህ በፊት የተወሰነ ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የህግ መሠረት የለውም፡፡ የሽያጭ ውሉ አልተፈፀመም፡፡ አመልካች በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2281 የተጣለባቸውን ግዴታ አልተወጡም፡፡ መኪናውን ያሣገዱትም አመልካች ናቸው ስለዚህ ውሉ ፈርሶ ወደ ነበርንበት እንድንመለስ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

አመልካች በቅንነት የሸጥኩት መኪና በገዥዎች ሥም እንዲዛወር የካቲት 12 ቀን 1999 ዓ.ም. ከተጠሪ ጋር በመሆን በፅሑፍ ለምስራቅ ሸዋ ዞን ንግድ ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ጽ/ቤት ማመልከቻ አቅርቤአለሁ፡፡ የመኪናውንም ክሊራንስ ለተጠሪ አስረክቤአለሁ፡፡ ስለዚህ በእኔ በኩል የሚፈፀም የሚገባኝን ማናቸውንም ግዴታ ተወጥቼ እያለ ውሉ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የመኪና ሽያጭ ውል ፈርሶ ተዋዋዮቹ ወደነበሩበት ይመለሱ በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ይህንን ጭብጥ ለመመለስ በመጀመሪያ ተጠሪ ከዚህ በፊት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 43008 ባቀረበው ክስ መነሻ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሰኔ 23 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በይግባኝ በማየት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57891 ታህሣሥ 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ በይግባኝ በማየት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35601 የሰጠውን ውሣኔ ይዘት መመልከቱ አስፈላጊ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ መዝገብ ቁጥር 35601ን በማስቀረብ ተመልክተናል፡፡

ተጠሪና አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 43008 የተከራከሩት ሻጭ አመልካች መኪናውን ከዕዳና እገዳ ነፃ በማድረግ ስም እንዲያዛውሩ በማለት ተጠሪ በመክሰሳቸውና አመልካች መኪናው ከዕዳና እገዳ ነፃ መሆኑን የካቲት 29 ቀን 1999 ከጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 09/15 እና ከኢንሹራንስ ማስረጃ በማምጣት የሰጠ መሆኑን በማንሣት ተከራክሮ የአመልካች ማስረጃ ተዓማኒነት የለውም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የወሰነ መሆኑን ተረድተናል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበው ከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ሻጭ የሸጡትን መኪናና ሊብሬ ለገዥዎች አስተላልፈዋል ስሙ እንዲተላለፍላቸውም ለሚመለከተው አካል የተለያዩ ደብዳቤዎችን አቅርበዋል የመኪናው ዕዳ እስከ የካቲት 30 ቀን 1999 ዓ.ም የተከፈለ ለመሆኑም ማጣሪያ አቅርበዋል፡፡ የመኪና ሽያጭ ውል የተለየ ፎርም የለውም የመልስ ሰጭዎች ጠበቃ እንደገለፁት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1723 መሠረት የመድረግ ግዴታ የለበትም የመኪና ሽያጭ ውል ከተደረገ በኋላ ስመሀብቱ የሚተላለፍበት ሁኔታ በህግ ማስታወቂያ ቁጥር 360/6/ ላይ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በዚሁ መሠረት የሽያጭ ውሉና ሊብሬው ሲቀርብለት የሚመለከተው የመንገድ ትራንስፖርት ስመሀብቱን በገዥው ስም ያዛውራል ሻጭ በህግ ለመንግስት መሥሪያ ቤት የተሰጠውን ስም የማዛወር ግዴታ ሊወስዱ አይችሉም የሚል ዝርዝር ምክንያት በመስጠት ተጠሪ አመልካች የመኪናውን ስም ያዛውርልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ የክስ ምክንያት የሌለውና ሻጭ (አመልካች) መኪናውን በማስረከብ ስም እንዲዛወርላቸው ደብዳቤ በማስገባት፣ የመኪናው ዕዳ መከፈሉን ማረጋገጫ በማቅረብ ግደታቸውን የተወጡ መሆኑን በውሣኔው ውስጥ በግልፅ በማስፈር ውሣኔ የሰጠ መሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 57891 ታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በማየት ለመረዳት ችለናል፡፡ ተጠሪ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57891 በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ይዘቱ ከላይ የተገለፀውን የከፍተኛው ፍርድ ቤት

የሰጠውን ውሣኔ ያፀናው መሆኑን በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 35601 ግንቦት 6 ቀን 2000 ዓ.ም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከሰጠው ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57891 የሰጠው ውሣኔና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 35601 ያፀናው ውሣኔ መሠረታዊ ይዘት የመኪናው ሻጭ የሆኑት አመልካች በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2274 በተደነገገው መሠረት የሸጡትን መኪና ለገዥዎች ያስረከቡ መሆኑንና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2281 በተደነገገው መሠረት የተሸጠውን መኪና ባለሀብትነት ለገዥዎች (ለተጠሪና በሥር ጣልቃ ገብ ተከራካሪ ለነበሩት) ለማስተላለፍ አስፈላጊ የሆኑ ተግባሮችን የፈፀመ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ አመልካች በሽያጭ ውሉ መሠረት በእሳቸው በኩል መፈፀም የሚገባቸውን ተግባራት ሙሉ በሙሉ የፈፀሙና ቀሪው ሥራ ሥልጣን ያለው የአስተዳደር ክፍል መሆኑን በማረጋገጥ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57891 እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35601 ውሣኔ ሰጥተውበታል፡፡

ተጠሪ ከላይ ቁጥራቸው በተገለፀው መዛግብት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡትን ውሣኔ ግልባጭ የመኪናውን ስመሀብት ከሻጭ ወደገዥ የማዛወር ሥልጣን ላለው አካል በማቅረብ የመኪናው ስመሀብት እንዲዛወርላቸው መጠየቅና አስፈላጊም ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል ላይ ክስ በማቅረብ መብታቸውን ማስከበር ይገባቸዋል፡፡ ተጠሪ በሽያጭ ውሉ መሠረት ግዴታቸውን ሙሉ በሙሉ አሟልተው የፈፀሙ መሆኑ በፍርድ የተረጋገጠላቸውን አመልካችን በሽያጭ ውሉ መሠረት ግዴታውን አሟልቶ ያልፈፀመ ስለሆነ ውሉ ፈርሶ ወደነበርንበት እንድንመለስ ይወሰንልን በማለት መክሰሳቸው የህግ መሠረት የለውም፡፡ ይህን ክስ በመቀበል የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 121731 ውሉ እንዲፈርስ የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 45360 የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔን በማፅናት የሰጠው ውሣኔ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 5 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረታዊ ድንጋጌ የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተጠሪ አሁን በቀረበው ክስና በፊት ከአመልካች ጋር ተከራክረው ውሣኔ ያገኘው ጉዳይ መካከል ግኑኝነት የሌለው የተለያዩ ጭብጦች መሆናቸውን በማንሣት የተከራከሩ ቢሆንም አመልካች በሽያጭ ውሉ መሠረት ግዴታቸውን አሟልተው ተወጥተዋል ወይስ አልተወጡም? የሚለውን ነጥብ በመመርመር አመልካች በሽያጭ ውሉ መሠረት ግዴታቸውን አሟልተው የተወጡ መሆኑን በመግለፅ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57891 የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35601 ውሣኔ ሰጥተውበታል ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በሽያጭ ውሉ መሠረት ግዴታውን ስላልተወጣ ውሉ ፈርሶ ተዋዋዮች ወደ ነበሩበት ይመለሱ በማለት በመዝገብ ቁጥር 45360 የሰጠው ውሣኔ ከዚህ በፊት የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበትን ጭብጥ በድጋሜ በማየት የተሰጠው ከዚህ በፊት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የተሰጠ ውሣኔ በመሆኑ ተጠሪ ያቀረቡት ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመሆኑም አመልካች በሽያጭ ውሉና ስለ ሽያጭ ውል በተደነገጉት የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ግዴታቸውን አሟልተው የተወጡ መሆኑንና ቀሪው ሥራ ጉዳዩ የሚመለከተው የመንግስት አካል መሆኑን በማረጋገጥ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57891 የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35601 የሰጠው ውሣኔ በሰበር ታይቶ ሣይሻሻል ወይም ሣይሻር አመልካች በሽያጭ ውሉ መሠረት



www.chilot.me

ግዴታውን አሟልቶ ያልፈፀመ በመሆኑ የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ ይገባዋል በማለት ተጠሪ ያቀረበውን ክስ በመቀበል የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 5(1)ን የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 121731 ጥቅምት 28 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በማፅናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 45360 በሚያዝያ 29 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 73449 መጋቢት 8 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

ጽ/ሽ



www.chilot.me

የሰ.መ.ቁ 57356

መጋቢት 22 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፣** ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች -** ወ/ሮ መሠረት በቀለ ጠበቃ አቶ ታየ ገብረመድህን ቀረቡ

**ተጠሪ -** ወ/ሮ ኤልዛ ሶሞኔላ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ተገልፆ ለሰበር ችሎት ስለቀረበ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ተጠሪ/ከሣሽ/ ተከሣሽ/አመልካች/ አውሊያቸውን ተለማምነው በጠና ታሞ የነበረውን ባለቤቴን እንደሚያድኑት ገልፀው የሽያጭ ውል የተደረገ በማስመሰል በድሬደዋ ከተማ በካርታ ቁጥር 1813 የተመዘገበውን ቤት በነፃ በስጦታ ወስደዋል ውሉ ህገወጥ በመሆኑ እንዲፈርስ ይህ የሚታለፍ ቢሆን ውሉ በአስገዳጅነት ማሟላት እንዳለባቸው በህግ የተደነገገውን መስፈርት የማያሟላ በመሆኑ እንዲፈርስልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርበው ውሉ በሙሉ ፈቃድና ስምምነት ከሣሽ ቤታቸውን የሸጡልኝ በመሆኑ ውሉ ለህግ ተቃራኒ አይደለም፡፡ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት የተደረገ በመሆኑ አስገዳጅ መስፈርቶችን የሚያሟላ ውል በመሆኑ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ ከሣሽ /ተጠሪ/ እና ተከሣሽ /አመልካች/ ሰኔ 25 ቀን 1996 ዓ.ም ያደረጉት ውል ተዋዋዮቹ ብቻ የፈረሙበት ሰነድ ነው፡፡ በውልና ማስረጃ የተደረገ ቢሆንም በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1727 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በሁለት ምስክሮች የተፈረመ አይደለም ስለዚህ ውሉ እንደረቂቅ የሚታይና ፈራሽ ነው በማለት ከሣሽ /ተጠሪ/ ከተከሣሽ የወሰዱትን ብር 23,000 /ሃያ ሶስት ሺህ ብር/ ለተከሣሽ ይመልሱ ተከሣሽ /አመልካች/ በድሬዳዋ ከተማ በካርታ ቁጥር 4813 በ800 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈውን የድርጅት ቤት ተከሣሽ /ተጠሪ/ ያስረክቡ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ



www.chilot.me

ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች ሰኔ 15 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በድሬዳዋ ውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ፊት የተደረገ ነው፡፡ ውሉ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1723/1/ የተደነገገውን ፎርማሊቲ ያሟላል፡፡ ውሉ በፅሑፍ የተደረገ በመሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2877 የተደነገገውን ፎርማሊቲ ያሟላል ውሉ በሁለት ምስክሮች አለመፈረሙና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1727/2/ የተደነገገውን ፎርማሊቲ አላሟላም በማለት ውሉ እንዲፈርስ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ቤቱን ከገዛሁ በኃላ ከብር 300,000 /ሶስት መቶ ሺ.ህ ብር በላይ ወጭ በማድረግ የማስፋፊያ ግንባታ አድርጌለሁ ስለዚህ ውሉ ፈርሶ ወደነበራችሁበት ተመለሱ በማለት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ጥር 13 ቀን 2003 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት መልስ የውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ባለሥልጣን ውሉን ተቀብሎ ከመመዝገቡ ውጭ ውሉን ስንፈራረም አላየም ውሉን መንደር ውስጥ ነው የተፈራረምነው በውሉ ላይ ምስክሮች እንዲኖሩ ያልተደረገው አመልካች እኔን በውሉ ላይ ያስፈረሙኝ አውሊያው አዞሻል የሚልና ሌሎች የማስፈራሪያ ቃሎችን በመጠቀም ያስፈረሙኝ በመሆኑ ነው፡፡ ውልና ማስረጃ መደረጉ የምስክሮችን ፎርማ አስፈላጊነት ቀሪ አያደርግም ስለዚህ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክረዋል አመልካች ጥር 30 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ የተጠሪ ባለቤት ከዚህ ዓለም በሞት የተለያት ጥር 13 ቀን 1995 ዓ.ም በመሆኑና ተጠሪ ቤቱን የሸጡልኝ ሰኔ 25 ቀን 1996 ዓ.ም ተጠሪ አመልካች አስፈራርታኝ ነው የፈረምኩት በማለት ያቀረቡት ክርክር ዕውነትነት የሌለውና በክፉ ልቦና የቀረበ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት ውል በሁለት ምስክሮች ፊርማ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ውሉ ፈርሶ ተዋዋዬች ወደነበሩበት ይመለሱ በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አንድን ውል የፀና ውል ለማድረግ ከሚያስፈልጉ ሶስት መሠረታዊ መስፈርቶች አንደኛው የውሉ አፃፃፍ በህግ የታዘዘ በሆነ ጊዜ ውሉ በህጉ የተመለከተውን ልዩ ፎርም በሚያሟላ ሁኔታ መደረጉ እንደሆነ በፍታብሐር ህግ ቁጥር 1678/ሐ/ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ተጠሪና አመልካች ያደረጉት የማይንቀሳቀሥ ንብረት ሽያጭ ውል ነው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውሉ በፅሑፍ ሊደረግ የሚገባው መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2877 “የውሉ ፎርም” በሚል ርዕስ ሥር ተደንግጓል፡፡ ህጉ በግልፅ የሚያስገድድ በሆነ ጊዜ ውሉ በህጉ የታዘዘውን ልዩ ፎርም ማሟላት የሚገባው መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1719 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገ ሲሆን ውሉ በፅሑፍ እንዲደረግ በህግ የተደነገገ ግዴታ ሲኖር ልዩ በሆነ አሰራር ተገልፆ በውሉ ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ውሉን መፈረም እንዳለባቸው የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1727 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ ውሉ በፅሑፍ እንዲሆን ህግ የሚያስገድድ በሆነ ጊዜ በፅሑፍ በተደረገው ውል ላይ ተዋዋዬች መፈረማቸው ብቻውን ህጉ የፀና ውል እንደማያደርገው በሁለት ምስክሮች ፊት ካልተረጋገጠ አይፀናም በማለት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1727 ንዑስ አንቀጽ 2 በግልፅ ደንግጓል፡፡

ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1727 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ውሉ መደረጉን የሚያረጋግጡ ምስክሮች አካለመጠን ያልደረሱና ያልተከለከሉ መሆን እንደሚገባቸው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1729/1/ ተደንግጓል፡፡ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1723/1/ መሠረት የማይንቀሳቀሥ ሽያጭ በውል አዋዋይ ወይም በፍርድ ቤት መዝገብ ሹም ፊት እንዳደረገ የተደነገገው በፍታብሐር ህግ ቁጥር 1727 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1729

ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን አስገዳጅ ፎርም ህግ አውጭው ለማስቀረት ወይም ለመተካት በማሰብ አይደለም፡፡ በአንፃሩ የማይንቀሳቀሥ ንብረት በውል አዋዋይ ፊት ወይም በፍርድ ቤት መዝገብ ሹም ፊት ሲደረግ ውሉን የሚያዋውለው ባለሥልጣን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1678 የተደነገጉት ሶስት መሠረታዊ ሁኔታዎች መሟላታቸውንና በተለይም በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1727 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገጉት ፎርማሊቲዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ ተዋዋዩች ውሉን እንዲፈራረሙ ያደርጋል የሚል ሀሳብ ስለነበረው ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪና አመልካች ሰኔ 25 ቀን 1996 ዓ.ም ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል በፍታብሐር ህግ ቁጥር 1678 /ሐ/ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2877 እና በፍታብሐር ህግ ቁጥር 1727 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን አስገዳጅና ልዩ የውል ፎርም የማያሟላ በመሆኑ ውሉ ሊፈርስ ይገባዋል በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች ቤቱን ከገዙ በኃላ ከፍተኛ የሆነ የማስፋፊያ ግንባታ ሥራ እንደሰሩ በሰበር አቤቱታቸው በማንሳት ተከራክረዋል፡፡ ሆኖም አመልካች ይኸንን ለሰበር ችሎት ያቀረቡትን መከራከሪያ ለሥር ፍርድ ቤት አንስተው ያልተከራከሩበትና በሰበር ደረጃ የቀረበ አዲስ የፍሬ ጉዳይ ክርክር መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ግልባጭ ተገንዝበናል በመሆኑም አመልካች ቤቱን ከገዙ በኃላ ተጨማሪ ግንባታ እንደገነቡ በማንሣት በሰበር ያቀረቡት ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ያልተነሣና የፍታብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 329 ንዑስ አንቀጽ 1ን በሚጥስ መንገድ ለሰበር ችሎት የቀረበ አዲስ ክርክር በመሆኑ ህጋዊ መሠረትና ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ስለሆነም ከላይ በዝርዝር የገለፅናቸውን መሠረታዊና አስገዳጅ የህግ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪና አመልካች ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል እንዲፈርስ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት መስከረም 26 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
3. ግራቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት***

ም.አ



www.chilot.me

የሠ/መ/ቁ 55359

ሚያዝያ 21 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አቶ ተድላ ማሞ ጌታቸው ጠበቃ አቶ ጌታቸው በለጠ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1- አቶ ፍስሐ ሱመር ቀረቡ

2- አቶ ስዩም ተክለማርያም አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ተገልፆ የቀረበ ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አንድ በኩል አመልካች ከሣሽ ተጠሪዎች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪዎች የተከሣሽ ከሣሾች አመልካች የከሣሽ ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካች ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪዎች ጋር መስከረም 27 ቀን 1996 ዓ.ም የግንባታ የሥራ ውል እንደተዋዋለና ለሥራው ብር 715,625/ የሰባት መቶ አሥራ አምስት ሺ ስድስት መቶ ሃያ አምስት ብር/ ለመክፈል የተስማማ መሆኑን ተጠሪዎች በሶስት ጊዜ ክፍያ ብር 322,345.75 /ሶስት መቶ ሃያ ሁለት ሺ ሶስት መቶ አርባ አምስት ብር ከሰባ አምስት ሣንቲም/ የወሰዱ መሆኑን ገልፆ ተጠሪዎች የግንባታ ሥራውን ከጀመሩ በኋላ ብር 94,905.40 /ዘጠና አራት ሺ ዘጠኝ መቶ አምስት ብር ከአርባ ሣንቲም/ ዋጋ ያለው ሥራ ከሠሩና ብር 6068.40 ዋጋ ያለው የግንባታ ዕቃ በቦታው በመተው ሥራውን አቋመዋል፡፡ ስለሆነም ተጠሪዎች ከወሰዱት ክፍያ ውስጥ ሥራ ላይ ያላዋሉትን ብር 221,369.95 /ሁለት መቶ ሃያ አንድ ሺ ሶስት መቶ ስልሣ ዘጠኝ ብር ዘጠና አምስት ሣንቲም/ ከነወለዱ ሊመልሱልኝ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ግንባታው በወቅቱ ባለመጠናቀቁ ቤቱን ለመሥራት የሚጠይቀው ተጨማሪ ወጭ ብር 335,012.70 /ሶስት መቶ ሰላሣ አምስት ሺ አስራ ሁለት ብር ከሰባ ሣንቲም/ ሊከፍሉ ይገባል፡፡ ግንባታው በመዘግየቱ ብር 71,562.50 መቀጫ የመክፈል ሀላፊነት አለባቸው፡፡ በአጠቃላይ ተከሣሾች /ተጠሪዎች / ብር 637,623.88 /ስድስት መቶ ስላሣ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሃያ ሶስት ብር ከሰማኒያ ስምንት ሣንቲም/ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች በተከሣሽነት ቀርበው ከሣሽ /አመልካች/ ያቀረበው ክስ ተገቢ አይደለም፡፡



www.chilot.me

የግንባታ ሥራው በወቅቱ ያልተጠናቀቀው ከሣሽ የግንባታ ፈቃድ የሌለው በመሆኑና ግንባታውን እንድናቆም የቀበሌ አስተዳደር ስላስገደደን ነው፡፡ የዋጋ ጭማሪውም በዚህ ምክንያት የደረሰ ነው፡፡ የግንባታውን ሰማኒያ አምስት ፐርሰንት አጠናቀናል፡፡ ከሣሽ ግምቱ ብር 100,000 የሆነ የግንባታ ዕቃ ወስዷል፡፡ ስለሆነም የከሣሽ ክስ ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

2. ተጠሪዎች በበኩላቸው የግንባታውን ሰማኒያ አምስት ፐርሰንት የሠራን ሲሆን ከሣሽ ሊከፍለን የሚገባውን የሶስተኛ ዙር ክፍያ አልከፈለንም ከሣሽ የግንባታ ዕቃ ዋጋ በመጨመሩ ምክንያት የመጣውን የዋጋ ለውጥ የመሸፈን ግዴታ ያለበት ቢሆንም የዋጋ ለውጡን አልከፈለንም ከዚህ በተጨማሪ ከሣሽ ለዕቃ ኪራይ የከፈልነውን በቦታው የነበረውና የወሰደውን የግንባታ ዕቃ ዋጋ በድምሩ ብር 33,594.56 /ሶስት መቶ ሰላሣ ሶስት ሺ አምስት መቶ ዘጠና አራት ብር ከሀምሣ ስድስት ሣንቲም/ ሊከፍለን ይገባል በማለት የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በተከሣሽ ከሣሽነት ቀርቦ ተከሣሾች/ ተጠሪዎች/ የሠሩት የግንባታ ሥራ አስራ አራት ፐርሰንት ብቻ ስለሆነ ተጨማሪ ክፍያ የጠየቁት አላግባብ ነው፡፡ ከሣሾች የዋጋ ጭማሪ ክፍያና የግንባታ ዕቃ ዋጋ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ የህግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአመልካችን ክስና የተጠሪዎችን የመከላከያ መልስ እንደዚሁም የተጠሪዎችን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስና የአመልካችን የከሣሽ ተከሣሽነት ክርክርና ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ማስረጃ በመስማትና በመመርመር የግንባታ ፈቃድ የማውጣት ኃላፊነት ያለባቸው ተከሣሾች /ተጠሪዎች/ በመሆናቸው ለግንባታው መዘግየት በሀላፊነት የሚጠየቁት ተከሣሾች /ተጠሪዎች/ ናቸው፡፡ ስለተሠራው የግንባታ ሥራ መጠን የተሻለ ማስረጃ ያቀረበው ከሣሽ /አመልካች/ በመሆኑ ተጠሪዎች/ ተከሣሾች/ በቅድሚያ ክፍያ ከወሰዱት ገንዘብ ውስጥ ብር 221,369.95 ለከሣሽ /አመልካች/ ሊመልሱ ይገባል፡፡ የግንባታ ሥራው በወቅቱ ላለመጠናቀቁ ሀላፊነት ያለባቸው ተጠሪዎች ስለሆኑ በግንባታው መዘግየት ለተከሰተው የዋጋ ጭማሪ የተከሣሽ ከሣሾች ሊከፍሉ ይገባል በማለት ተጠሪዎች ብር 556,382.65 / አምስት መቶ ሃምሣ ስድስት ሺህ ሶስት መቶ ሠማኒያ ሁለት ብር ከስልሣ አምስት ሣንቲም/ ለአመልካች ከሣሽ ይክፈሉ በማለት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

3. ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የግንባታ ፈቃድ የማውጣትና ኘላኑን የማፅደቅ ሀላፊነት ያለበት ተዋዋይ ወገን ማንኛቸው እንደሆኑ አመልካች ተጠሪዎች ያደረጉት የግንባታ ሥራ ውል አይገልፅም፡፡ ተጠሪዎች የግንባታ ፈቃድ ለማውጣትና ኘላን ለማፀደቅ በውሉ በግልፅ ሀላፊነት ያልወሰዱ ከመሆኑና የግንባታ ፈቃድና ኘላን የሚሰጠው ለባለቤቱ ወይም ለህጋዊ ወኪል ብቻ እንደሆነ የየካ ክፍለ ከተማ የመሠረተ ልማትና ቤቶች ጉዳይ ጽ/ቤት የግንባታ ፈቃድ ክትትልና ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 17 እና የመመሪያ ቁጥር 1/97ን በመጥቀስ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት በፅሑፍ ማብራሪያ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪዎች የአመልካች ወኪል መሆናቸው አልተረጋገጠም ስለዚህ ግንባታ ፈቃድ የማውጣትና ኘላን የማፅደቅ የአመልካች ሀላፊነት ነው፡፡ አመልካች ለተጠሪዎች በኘላኑ መሠረት የተከናወነውን የግንባታ ሥራ በማረጋገጥ ክፍያ የመክፈል ሀላፊነት ያለበት መሆኑ አመልካችና ተጠሪዎች መስከረም 27 ቀን 1996 ዓ.ም ባደረጉት ውል አንቀፅ 3 በግልፅ ተመልክቷል፡፡ አመልካች ለተጠሪዎች የከፈለው የመጀመሪያ ክፍያ የግንባታ ሥራውን ለማስጀመር ሁለተኛው ክፍያ ደግሞ ሥራው የተሠራ መሆኑ ተረጋግጦ የተከፈለ መሆኑ ተጠሪዎች ባቀረቡት የሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪዎች ለአመልካች ብር 221,369.95 የመመለስ ግዴታ የለባቸውም፡፡ አመልካች የግንባታ ፈቃድ ባለማውጣቱና ኘላን ባለማፀደቁ ምክንያት የግንባታ ሥራው በመዘግየቱ ምክንያት

የመጣን የግንባታ ዕቃ ዋጋ ጭማሪ ተጠሪዎች ለአመልካች የመክፈል ግዴታ ያለባቸውም በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡ የተጠሪዎችን የከሣሽነት ክስ በተመለከተ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ ይወስን በማለት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 341/1/ መሠረት ለከፍተኛው ፍርድ ቤት መልሶለታል፡፡

4. አመልካች ሚያዝያ 18 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪዎች አመልካች ጋር የቤት ግንባታ ውል የተዋዋሉት የግንባታ ፈቃድ አውጥተውና ኘላኑን አፀድቀው በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ግንባታውን ጨርሰው ለአመልካች ለማስረከብ ነው ተጠሪዎች የግንባታ ፈቃድ ሣይኖርና ኘላን ሣይፀድቅ ቤቱ ሊገነባ እንደማይችል ያውቃሉ፡፡ የግንባታ ፈቃድ ሣይወጣና ኘላኑ ሣይፀድቅ ሥራ መጀመራቸው ጥፋት ነው፡፡ ስለዚህ ለግንባታው መዘግየት ተጠሪዎች ሀላፊነት ያለባቸውም በማለት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪዎች የወሰዱትን ገንዘብ የሚመጥን የግንባታ ሥራ ሠርተዋል ወይስ አልሠሩም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኞችን ክርክርና ማስረጃ በመመዘንና በማጣራት መወሰን ሲገባው በገለልተኛ ባለሙያ ተገምቶ የቀረበውን ማስረጃ ውድቅ በማድረግ ክፍያው የተፈፀመው ለተሠራው ሥራ መጠን ነው በማለት መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ለውሉ መዘግየት ሀላፊ መሆናቸውንና የግንባታ ዕቃ ዋጋ በመጨመሩ ምክንያት የመጣውን ልዩነት መክፈል ሀላፊነት ወስኖ እያለ የተጠሪዎችን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ውሣኔ አልሰጠበትም በማለት ጉዳዩን መመለሱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪዎች ታህሣሥ 1 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጡት መልስ ስለግንባታ ፈቃድ ማመልከቻ አቀራረብ አሰጣጥና ቁጥጥር በወጣው አዋጅ ቁጥር 316/79 ግንባታ ፈቃድ የሚጠየቀው ሲፈቀድም የሚሰጠው ለባለቤቱ ወይም ለወኪሉ ስለመሆኑ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ይህንኑ ነጥብ በተመለከተ ማብራሪያ እንዲሰጠው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሰጥቶ የሚመለከተው አካል ግልፅ ምላሽ በፅሑፍ ሰጥቶ እያለ ይህንን በማለፍ የከፍተኛው ፍርድ ቤት መወሰኑ ተገቢ ባለመሆኑ በይግባኝ ሰሚው ችሎት መሻሩ ተገቢ ነው፡፡ አመልካች የግንባታ ፈቃድ ያወጡት ከአንድ ዓመት በኋላ በመሆኑ ግንባታው በመዘግየቱ ምክንያት ለደረሰው የግንባታ ወጭ ጭማሪ ተጠሪዎች የመካስ ሀላፊነት የለብንም፡፡ የግንባታ ሥራውን ዋጋ ክፍያ የወሰድነው የተሠራው ሥራ መጠንን በተመለከተ አሠሪው /አመልካች/ እና የሥራ ተቋራጮች የሆኑት ተጠሪዎች ጥር 28 ቀን 1996 ዓ.ም በተፃፈ መተማመኛ ተፈራርመው በመሆኑ የምንመልሰው ገንዘብ የለም፡፡ ተጠሪዎች 85% እንደሠራንና አመልካች ለሠራነው ሥራ ክፍያ ያልፈፀመ በመሆኑን ገልፀን ያቀረብነው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ሣያጣራና ሣይወሰን የከፍተኛው ፍርድ ቤት ያለፈው በመሆኑ ጉዳዩን ይግባኝ ሰሚው ችሎት መመለሱ ተገቢ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ጥር 27 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ ሁለት ገፅ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ይዘት በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ የተያዘውን ጭብጥ ማለትም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪዎች የግንባታ ፈቃድ የማውጣትና ኘላን የማስፀደቅ ሀላፊነት የሌለባቸው በመሆኑ ግንባታው በመዘግየቱ ምክንያት የግንባታ ዕቃ ዋጋ በመጨመሩ የደረሰውን የዋጋ ጭማሪ ለመክፈል ሀላፊነት የለባቸውም በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከላይ የተገለፀውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተለያየ መደምደሚያ ላይ የደረሱበትን ምክንያት መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ግንባታ ፈቃድ የማውጣትና ኻላን የማስፀደቅ ሀላፊነት አለባቸው ከሚለው መደምደሚያ ላይ የደረሰው አመልካችና ተጠሪዎች የግንባታ ሥራ ውል ለመዋዋል ሲነጋገሩ ተጠሪዎች የግንባታውን ፈቃድ ከሚመለከተው የመንግስት አካል በማውጣትና ኻላኑን በማስፀደቅ ግንባታውን በስድስት ወር ውስጥ አጠናቅቀው ለማስረከብ ለአመልካች ገልፀውላቸዋል በማለት የአመልካች ምስክሮች ቃል ለሰጡት የምስክርነት ቃል ታዓማኒነትና ክብደት ያለው ማስረጃ መሆኑን በመግለፅና ተጠሪዎች የግንባታ ፈቃድ ሣይኖር ሥራ መጀመራቸው ከሙያቸው አንፃር ሲታይ ጥፋታቸው ነው በማለት መሆኑን በውሣኔው በግልፅ አስፍሮታል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ አመልካችና ተጠሪዎች መስከረም 27 ቀን 1996 ዓ.ም የተዋዋሉት የግንባታ ሥራ ውል ተጠሪዎች የግንባታ ፈቃድ የማውጣትና ኻላን የማስፀደቅ ሀላፊነት ያለባቸው መሆኑን አይገልፅም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የግንባታ ሥራ ፍቃድ የሚሰጠው ለንብረቱ ባለቤት ወይም ለህጋዊ ወኪሉ ብቻ መሆኑ አግባብነት ባላቸው የህግ ማዕቀፎችና የአሠራር መመሪያዎች ተመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች የአመልካች ወኪሎች ስለመሆናቸው የቀረበ ማስረጃ የሌለ በመሆኑ ተጠሪዎች የግንባታ ሥራ ፈቃድ ለማውጣት የሚችሉ አይደለም፡፡ ስለሆነም የግንባታ ሥራ ፈቃድ ባለመውጣቱ ምክንያት የግንባታ ሥራ ለመዘግየቱም ሆነ በዚህ ምክንያት ለተከሰተው የዋጋ ለውጥ ተጠሪዎች በሀላፊነት አይጠየቁም በማለት ነው፡፡

ከዚህም የምንረዳው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካችና ተጠሪዎች መስከረም 27 ቀን 1996 ዓ.ም በፅሑፍ ያደረጉትን የግንባታ ሥራ ውል ይዘትና አግባብነት ባላቸው የህግ ማዕቀፎች መሠረት የግንባታ ሥራ ፈቃድ ማውጣት የሚችለው ማንኛው ወገን ነው የሚለውን ነጥብ መሠረት ማድረግ ውሣኔ የሰጠ መሆኑን ነው፡፡ የአንድ ሰው ግዴታ ሀላፊነት ከውል ወይም ከህግ የሚመነጭ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር ሲደራደሩ የግንባታ ፈቃድ ለማውጣትና ኻላኑን ለማስፀደቅ እንደሚችሉ እንደገለፀ በአመልካች ምስክሮች የተገለፀ ሲሆን አመልካችና ተጠሪዎች ያደረጉት የግንባታ ሥራ ውል ስምምነት ውስጥ ተጠሪዎች የግንባታ ሥራ ፈቃድ ለማውጣትና ኻላኑን አፅድቀው ሥራ ለመጀመር በግልፅ ያልተዋዋሉም መሆኑን ፍሬ ጉዳይ በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን የሥር ፍርድ ቤት የፈፀመውን ስህተት በይግባኝ አይቶ የማረም ሥልጣን ባለው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች የግንባታ ሥራ ከመጀመራቸው በፊት የግንባታ ሥራ ፈቃድ የተሰጠ መሆኑን የማረጋገጥና የፀደቀ ኻላን መኖሩን የማረጋገጥ ሙያዊ ሀላፊነት አለባቸው በማለት የወሰነው ውሣኔ የግንባታ ፈቃድ አሠጣጥ ክትትልና ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 17 እና ከመመሪያ ቁጥር 1/97 አንፃር ሲታይ ተገቢነት የሌለው መሆኑን፣ የግንባታ ሥራ ፈቃድ የሚሰጠው ለባለቤቱ ወይም ለወኪሉ ብቻ መሆኑን በማረጋገጥ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የከፍተኛ ፍርድ ቤት በህግ አተረጓጎም ረገድ የፈፀመውን ግድፈት እንዳረመ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

የግንባታ ሥራ ፈቃድ የማውጣት ሀላፊነት ያለበት ማን ነው? የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ መፍታት ያስፈለገው የግንባታ ሥራ ፈቃድ ባለመውጣቱ ምክንያት ለግንባታ ሥራው መዘግየትና የግንባታ ዕቃዎች ባሣዩት የዋጋ ጭማሪ ምክንያት የወጣውን ተጨማሪ ወጭ የመሸፈን ሀላፊነት ያለበት አመልካች ነው ወይስ ተጠሪ ነው የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች



www.chilot.me

በግንባታ ሥራ ውሉ በግልፅ ተጠሪዎች ግዴታ ያልገቡበትንና ከላይ በተገለፁት አግባብነት ባላቸው የህግ ማዕቀፎችና የአሠራር መመሪያዎች የአመልካች ወይም የአመልካች ህጋዊ ወኪሎች ተግባርና ሀላፊነት መሆኑ የተደነገገውን ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ምክንያት የግንባታ ሥራው የዘገየ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባለው ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተረጋግጧል፡፡

ተጠሪዎች ከውል ወይም ከህግ የመነጨ የግንባታ ሥራ ፈቃድ የማውጣትና ኘላን የማስፀደቅ ሀላፊነት የሌላባቸው በመሆኑ የግንባታ ሥራው የግንባታ ሥራ ፈቃድ ባለመወጣቱ ምክንያት ለመዘግየቱና የግንባታ ሥራው በመዘግየቱና ምክንያት ለተከሰተው የግንባታ ዕቃ ዋጋ ጭማሪ ተጠያቂ የሚሆኑበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያሌለበት በመሆኑ በዚህ በኩል አመልካች ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

አመልካች ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪዎች የሠሩት የግንባታ ሥራ መጠንና ከአመልካች የወሰዱትን የገነዘብ መጠን ተመጣጣኝ መሆኑን በማጣራት መወሰን ሲገባው ተጠሪዎች ለአመልካች የሚመልሱት ገንዘብ የለም በማለት መወሰኑ የህግ ስህተት አለበት በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በሰበር በጭብጥነት የተያዘ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የፌደራል ጠቅለይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ለአመልካች ብር 221,369.95 እንዲመልሱ በማለት የሰጠውን ውሣኔ የሻረው ተጠሪዎች ለገነቡት የግንባታ ሥራ አመልካች ክፍያ ስለሚፈፅምበት ሁኔታ በግንባታ ሥራ ውሉ የተስማሙበትን የውል ሀይለ ቃልና አመልካች ተጠሪዎች ጥር 25 ቀን 1996 ዓ.ም በመተማመን የተፈራረሙበትን ሠነድ ይዘት ታዓማኒነትና ክብደት በመመዘን እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመዘን ውሣኔ የተሰጠበት በመሆኑና የሰበር ችሎት ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን የሌለው መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 የተደነገገ በመሆኑ በዚህ በኩል አመልካች ያቀረቡት ክርክር የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተጠሪዎችን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አጣርቶ እንዲወስን ጉዳዩን መመለሱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑን በመግልፅ አመልካች የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የከሣሽን ክስና ማስረጃ በመቀበል ተጠሪዎች በሀላፊነት ይጠየቃሉ ብሎ ስለወሰነ የተጠሪዎችን የተከሣሽ ከሣሽነት ጥያቄ በጥቅሉ ውድቅ አድርጎባቸው የነበረ መሆኑን ውሣኔው ያሣያል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪዎች ለአመልካች ክስ ተጠያቂ አይደሉም በማለት ወስኖ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡ ይህም በመሆኑ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ከዚህ በፊት በዝርዝር አጣርቶ ያልወሰነውን የተጠሪዎች የተከሣሽ ከሣሽነት ጥያቄ አጣርቶ እንዲወስን ጉዳዩን መልሶታል፡፡ ይህ ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ከመሆኑም በላይ ገና በሂደት ላይ ያለና የመጨረሻ ውሣኔ ያልተሰጠበት በመሆኑ አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አጣርቶ እንዲወሰን ይግባኝ ሰሚው ችሎት መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ያቀረበውን አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡

ከላይ በዘረዘርናቸው ምክንያቶች የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 58157

ሚያዚያ 06 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሤ

**አመልካች**፡- አቶ ዮሐንስ ታደሰ - ቀረበ

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ አማረች መንገሻ ጠበቃ አቶ ምክሩ ወ/አረጋይ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የአሁኑ አመልካች ለሥር የመ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ፍሬ ቃሉ ተከሳሽ /ያሁን ተጠሪ/ የአደረግነውን የወሰን ምልክት ስምምነት በመጣስና በውላችን በተስማማንበት መሠረት ባለመፈፀም ከፍ/ቤት የተሰጠ ትዕዛዝ ሳይኖር ሀሰተኛ የአጥር ፈቃድና ህገ ወጥ የይዞታ ማረጋገጫ በመያዝ አጥሬን በማፍረስ፣ የወሰን ምልክት በማጥፋትና ቀደም ሲል ከወ/ሮ ይርግዱ ሳሙኤል ወራሾች ከነ ወልደየስ አምባዬ በግዥ ካገኘችው ቦታ አልፋ በንብረቶቼ ላይ ጉዳት ያደረሰችና አዲስ አጥር ስላጠረች በህገ ወጥ መንገድ ያጠረችውን አጥር አፍርሳና የራሴን ያፈረሰችውን አጥር መልሳ በመሣጠር ቀደም ሲል በገባነው ውል መሠረት እንደትፈጽም ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የሥር ተከሳሽም በሰጠችው መልስ ይዞታው የከሳሽ ስለመሆኑ ማስረጃ ስለሌለው ክስ የማቅረብ መብት የለውም፣ በዚህ ጉዳይ ለአምስት ተደጋጋሚ ጊዜያት በተለያዩ መዛግብት ክስ ሲያቀርብ የቆየ በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 መሠረት ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል፣ ከሳሽ እነደሚለው ሣይሆን ቦታውን ያጠርኩት ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድርና ከሥራና ከተማ ልማት ጽ/ቤት በተሰጠኝ ፈቃድ ሲሆን ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ ታጥሮ ያለ የግል ይዞታዬ ነው፣ በንብረቱም ላይ ያደረስኩት ጉዳት የለም፡፡ ነገር ግን ዛፍ ተቆረጠብኝ ለሚለው ዛፉ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑ ታውቆ የደን ሚኒስቴር እና ፖሊስ ያስቆረጡ ስለሆነ አይመለከተኝም፣ ከዕርቅ ስምምነት ውጪ ስለመሥራቴም ከሳሽ ያቀረበው ማስረጃ ካለመኖሩም ሌለ ከሳሽ የተከሳሽን ይዞታ 2x4 ሜትር የሆነውን አልፎ በመያዝ በጉልበት እየተጠቀመበት ስለመሆኑ የካርታ ቁጥሩ ጂ አይ ኤስ 5556 የሆነ ያረጋግጣል በማለት የከሳሽ ክስ ውድቅ ተደርጎ ኪሣራ ከፍሎ መዝገቡ እንዲዘጋ አመልክታለሁ ብላለች፡፡

የሥር የመ/ደ/ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኂላ በ24/10/2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ፍርድ በአዋጅ ቁጥር 361/95 መሠረት ካርታ የመስጠትና የመሠረዝ ሥልጣን የክፍለ ከተሞች ነው፡፡ በመሆኑም ከሳሽ ካርታው የተሰጣት ያለአግባብ ነው የሚል ከሆነ ካርታውን



www.chilot.me

የሰጠውን ክፍል እንዲሰርዝ ከሚጠይቅ ውጪ ጥያቄውን ለፍ/ቤት ማቅረብ የለበትም በማለት የከሳሽን ክስ ውድቅ አድርጕበታል፡፡ ከሳሽ አላአግባብ ተከሳሽን በመክሰሱ ምክንያት ለወጣው የጠበቃ አበል ብር 10,000/አሥር ሺህ/ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

በዚሁ በሥር የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት የአሁኑ አመልካች ለሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ከፍተኛው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ወገን ካከራከረ በኋላ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሠረት የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን በማጽናት ለሥር መ/ሰጪ የወጪና ኪሣራ የመጠየቅ መብት ጠብቆላታል፡፡ በዚሁ መሠረት የሥር መልስ ሰጪ የወጪ ዝርዝር ጥያቄ ለከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርባ በመዝገብ ቁጥር 82975 በቀን 24/12/2002 በተሰጠ ፍርድ ብር 6,000/ስድስት ሺህ/ ይግባኝ ባይ /ያሁን አመልካች/ ለመልስ ሰጪ /ለአሁኗ ተጠሪ/ እንዲከፍል ተወስኗል፡፡

የሰበር አመልካችም የሥር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገሩም ሆነ በወጪ ዝርዝር ላይ በሰጡት ውሣኔ ቅር በመሰኘት አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡ በዋነትም አመልካች የጠቀሳቸው የቅሬታ ነጥቦች፡-

እኔ ለሥር ፍ/ቤት ያቀረብኩት ክስ እንደውሉ እንዲፈፀምልኝ ሆኖ ሳለና ካርታ ይሠረዝልኝ በሚል ተቀጥሮ ክሱ ውድቅ መደረጉ፣ እንዲሁም በሥር መ/ደ/ፍ/ቤት ብር 10,000 የጠበቃ አበል እንድከፍል መወሰኑና ከፍተኛ ፍ/ቤትም ድጋሚ ኪሣራ እንድከፍል መወሰኑ ያለአግባብ ነው የሚሉ ናቸው፡፡ ተጠሪዋ በጠበቃ አማካይነት በሰጠችው መልስ አመልካች የተጠሪው ይዞታ 500 ካ.ሜ ሲሆን 900 ካ.ሜ ካርታ ድንበሩን በመግፋት ያወጣችው ህገ ወጥ ካርታ ይሠረዝልኝ በማለት በተደጋጋሚ የሚከራከር ሲሆን ህገ ወጥም ሆነ ህጋዊ ካርታን ለማሠረዝ የሚቀርበው አቤቱታ በአዋጅ ቁጥር 361/95 ሥልጣኑ የክፍለ ከተማ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ የሚነቀፍ አይደለም፣ አመልካችና ተጠሪ ቦታን በሚመለከት ያደረግነው ስምምነት የለም፣ አለ ቢባል እንኳን ከ1985 ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ድረስ በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ የሚሆን ነው፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1727 መሠረት በምስክሮች ፊት ያልተረጋገጠ፣ በውል አዋዋይ ቀርቦ ያልተመዘገበና ተጠሪ ያልፈረምኩበት በአመልካች ብቻ የቀረበ ውል ተቀባይነት የለውም በማለት በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈፀመ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ወጪና ኪሣራ የመጠየቅ መብት ተጠብቆ መዝገቡ እንዲዘጋ ጠይቃለች፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ በተገለፀው አኳኋን የቀረበ ሲሆን እኛም የሚከተሉትን ጭብጦች በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

1. ውሉ ሊፈፀም የሚችል ነው ወይስ አይደለም;
2. አመልካች በሁለቱም የሥር ፍ/ቤቶች እንዲከፍል የተወሰነበትን የጠበቃ አበል በሙሉ መክፈል አለበት ወይስ የለበትም;

1ኛን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች ይፈፀምልኝ በማለት ከክሱ ጋር አይይዞ ያቀረበው ሚያዝያ 04 ቀን 1991 ዓ.ም አመልካችና ተጠሪ በቀድሞ አጠራር በወረዳ 17 ቀበሌ 14 አስተዳደር ጽ/ቤት ስምምነታቸውን የገለጹበት ማመልከቻ ሲሆን ፍሬ ቃሉም የአሁኑ አመልካች እና ይዞታውን ላሁኗ ተጠሪ ሸጠዋል የተባሉት እነ ወልደየስ አምባዬ የሚፈጽሙትን የወሰን መግፋትና የፍርድ ቤት ክስ በመተው ከአስፋልት መንገድ ጀምሮ ነባር አጥር ታጥሮ በኀላን ታይቶ የተነሣው የወ/ሮ ይርገዱ ሣሙኤል የካርታ ቦታ ኀላን የወሰን ድንጋይ ከታች በአቶ ደስታ መሐመድ አጥር መሠረት ቀጥታ ሆኖ የፈረሰው የአመልካች ነባር አጥር በነበረበት መሠረት ድንበራችን መሆኑን ለቀበሌ እናረጋግጣለን የሚል ነው፡፡



www.chilot.me

ተዋዋይ ወገኖች ሁሉ የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደመሰላቸው የመወሰን መብት ያላቸው ሲሆን ሕግ የወሰናቸውንና የከለከላቸውን ነገሮች ግን ሊያከብሩ እንደሚገባ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1716 ይደነግጋል፡፡ ህግ የወሰናቸውንና የከለከላቸውን ነገሮች ባለመገንዘብ ወይም ባለማክበር የሚደረጉ ውሎች የማይፀኑና የማይፈፀሙ ናቸው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩት በከተማ መሬት ነው፡፡ የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት ደግሞ የመንግስትና የሕዝብ ብቻ መሆኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 40/3/ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም በመንግሥትና በህዝብ መሬት ላይ ግለሰቦች አንዱ ሰጪ ሌላው ተቀባይ በመሆን የባለቤትነት መብት ሊመሠርቱ አይችሉም፡፡

በሌላ በኩል የሚያከራክረው ቦታ የከተማ ቦታ እስከሆነ ድረስ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 11/2//ሰ/ መሠረት ተጠሪዎች የአመልካችን ይዞታ አልፋ ስለመያዟ በከተማው ክልል ውስጥ የሚገኘውን መሬትና የተፈጥሮ ሀብት በሕግ መሠረት ለማስተዳደር ሥልጣን ለተሰጠው የከተማው አስተዳዳር ማመልከት ነበረበት፡፡ ይህን መብቱን ለመጠየቅ ደግሞ አመልካች ተጠሪዋ አልፋ ይዛብኛለች በሚለው ቦታ ላይ የባለይዞታነት መብት ያለው ስለመሆኑ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ካርታ ሊኖረው ይገባል፡፡

ተጠሪም በህገ ወጥ መንገድ የባለ ይዞታነት ማረጋገጫ ካርታ ተሰጥቷታል ለሚለውም ህገ ወጥ መሆኑንና አለመሆኑን መመርመርና ህገ ወጥነቱ ሲረጋገጥ መሠረዝ የሚችለው ይኸንኑ ማስረጃ ለመስጠት በህግ መብት የተሰጠው የከተማው አስተዳደር አካል መሆኑን ከዚህ በፊት ይህ ችሎት በሰበር መ/ቁ. 22719 ጥቅምት 14 ቀን 2000 ዓ.ም በአመልካች የአ/አ ከተማ አስተዳደር ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ተተኪ የመሬት ልማትና አስተዳደር ባለሥልጣንና በተጠሪ አቶ ነጋሽ ዱባለ መካከል በተደረገው ክርክር ከሰጠው የህግ ትርጉም መገንዘብ ይቻላል፡፡ የሰበር ችሎቱም የሚሰጠው የህግ ትርጉም በተመሣሣይ ጉዳዮች ላይ በየትኛውም ፍ/ቤት የአስገዳጅነት ባሕሪ ያለው መሆኑን አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1/ ስለሚደነግግ የሥር ፍ/ቤት ይኸንኑ የህግ ትርገም መሠረት በማድረግ ካርታ ማሰጠትም ሆነ ማሠረዝ የፍ/ቤት ሥልጣን አይደለም በሚል የወሰነው ከዚህ በላይ በተገለጹ ምክንያቶች የተነሣ አመልካች እንዲፈፀምለት ያቀረበው ውል የማይፈፀምና ካርታ የማሰጠትም ሆነ የማሠረዝ ሥልጣን የፍ/ቤት ሳይሆን የአስተዳደር መሥሪያ ቤት በመሆኑ በውሣኔው ላይ ይህን ጭብጥ በሚመለከት የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

2ኛው ጭብጥ የጠበቃ አበልን በሚመለከት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ነው፡፡ በመ/ደ/ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር አመልካች ለተጠሪ የጠበቃ አበል ብር 10,000/አሥር ሺህ/ ፣ በከፍተኛ ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ደግሞ ብር 6,000.00 /ስድስት ሺህ/ እንዲከፍል ተወስኖበታል፡፡ በጠቅላላው አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የተወሰነበት ብር 16,000/አሥራ ስድስት ሺህ ብር/ ነው፡፡

ለሥር መ/ደ/ፍ/ቤት የሥር ከሳሽ /አመልካች/ ክሱን በ24/03/2001 ዓ.ም ያቀረበ ሲሆን ተጠሪዋም ፍ/ቤት ቀርባ ለክሱ መልስ የሰጠችው በ4/07/2001 ዓ.ም መሆኑንና ፍ/ቤቱም የሥረ ነገር ሥልጣን የለኝም በሚል የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረገው በ24/10/2001 መሆኑን የሥር ፍ/ቤት መዝገብ ያመለክታል፡፡ ተጠሪዋ ፍ/ቤት ቀርባ ክርክር ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ በጉዳዩ ፍርድ እስከተሰጣት ጊዜ ተጠሪዋ ጠበቃዋ ፍ/ቤት የተመላለሠበት ጊዜ አጭር ነው፡፡ ፍርዱም ብዙም



www.chilot.me

ለውሣኔ የሚረዱ ማስረጃዎችን መመርመር ሳያስፈልግ በሥር ነገር ሥልጣን መዝገቡ የተዘጋበት ነው፡፡

ከፍተኛው ፍ/ቤትም ቢሆን ያስቀርባል በሚል ካከራከረ በኋላ በፎርም የፍትሐብሔር ሥ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ን በመጥቀሥ የሥር መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔን አጽንቷል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የተጠሪ ጠበቃ በፍ/ቤት ቀጠሮዎች በዚህ ጉዳይ ለብዙ ጊዜ በመመላለስ ተጉላላቷል የሚያሰኝ አይደለም፡፡

በመሆኑም ጠበቃው ዕውቀቱን ሥራ ላይ ለማዋል ላበረከተው አስተዋጽኦ እንዲከፍለው የተወሰነው የጠበቃ አበል ከሰጠው አገልግሎት አንፃር ሲታይ ከፍ ብሎ ተገኝቷል፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2635 'ም' ከመጠን በላይ የሚደረገውን የሥራ ዋጋ ዳኞች ሊቀንሱ እንደሚችሉ የተደነገገውም ተዋዋይ ወገኖች ለሙያው ሥራና ተግባር እንዲሁም ክብር ተቃራኒ የሚሆን የሥራ ዋጋ ስምምነት እንዳያደርጉ ለመከልከል ታስቦ ነው፡፡

የሥር ፍ/ቤቶችም ቢሆኑ የቀረበውን የወጪ ዝርዝር ጥያቄ በሚመረመሩበት ጊዜ የቀረበውን የወጪ ዝርዝር ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው የፍትሃብሔር ሕግ ድንጋጌና ሌሎች አግባብነት ካላቸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. ድንጋጌዎች አንጻር መርምረው መወሰን አለባቸው፡፡ ይህ ታልፎ አመልካች ከፍ ያለውን የጠበቃ አበል እንዲከፍል መወሰናቸው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ነው፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የሥር የመ/ደ/ፍ/ቤት ኮ/መ/ቁ. 132135 በቀን 24/10/2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች የጠበቃ አበል ብር 10,000 /አሥር ሺህ/ እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔና የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ኮ/መ/ቁ. 82975 በቀን 24/12/2002 አመልካች ብር 6,000/ስድስት ሺህ/ እንዲከፍል የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል አመልካች በሁለቱም ፍ/ቤቶች ለወጣው የጠበቃ አበል ብር 2,000/ሁለት ሺህ/ ለተጠሪ እንዲከፈል ወስነናል፡፡
2. አመልካች እንደውሉ ይፈፀምልኝ በማለት ያቀረበው ውል ሊፈፀም የሚችል አይደለም ብለናል፡፡
3. የሥር የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 132135 በቀን 24/10/2001 ዓ/ም በዋለው ችሎት ካርታ የማሠረዝ ክስ የፍ/ቤት ሥልጣን አይደለም በማለት የሥር ከሳሽን ክስ ውድቅ ያደረገውና ከፍተኛው ፍ/ቤትም በመ/ቁ. 82975 በቀን 09/10/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ን በመጥቀስ ያፀናው በአግባቡ ስለሆነ አጽንተናል፡፡
4. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ አመልካችና ተጠሪ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቅ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 58636

ሚያዝያ 19 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** እነ አቶ ተሾመ ካሣ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ቤዛ ኩሉ አዳም የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ በሽያጭ ምክንያት ተከፈለ የተባለ ገንዘብ ይመለስልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካቶች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- አመልካቾች ከመኖሪያ ቤታቸውና ከይዞታቸው በመቀነስ በግምት 270 ካ.ሜትር የሆነና ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤት ብር 40,000/ አርባ ሺህ/ ሸጠውላቸው ብር 10,000.00 /አስር ሺህ / በውሉ እለት የከፈሏቸው መሆኑን ብር 20,000.00/ሃያ ሺህ ብር/ ደግሞ አመልካቾች ቤቱን አድሰው ለተጠሪ ሲያስረክቡ እንዲከፈላቸው የተሰማሙ ቢሆንም አመልካቾች ቤቱን ባለማደሳቸው ተጠሪ በራሳቸው ገንዘብ እንዲያድሱ ስምምነት ላይ በመደረሱ ምክንያት ተጠሪ ብር 20,000.00 /ሃያ ሺህ/ ወጪ በማድረግ ቤቱን አድሰው የተረከቡ መሆኑን ከዚህም በተጨማሪ ተጠሪ ብር 51,000.00/ሃምሳ አንድ ሺህ ብር/ ወጪ በማድረግ ደረጃውን የጠበቀ አምስት ክፍል ቤት የሰሩ መሆኑን ተጠሪ በአመልካች ላይ የቤት ሽያጭ ውሉን በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ቀርበው እንዲያስመዘግቡ በፍርድ ቤት ክስ መስርተው ክርክሩ ሲካሄድ ቆይቶ ፍርድ ቤት በሕግ ፊት የሚፀና ውል የለም በማለት ውሣኔ መስጠቱን በመዘርዘር በማይጸና ውል የተወሰደውና ለግንባታ የወጣው ወጪ በድምሩ ብር 81,000.00/ሰማንያ አንድ ሺህ ብር / እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾች በበኩላቸው ተጠሪ ወደ ቤቱ የገቡት በኃይል መሆኑን በተጨማሪነት የገነቡት ግንባታም አለመኖሩን የሽያጭ ውሉም የተጭበረበረ መሆኑን በውሉ ደረሰኝነት ብር 10,000.00 ብቻ መቀበላቸውን ገልፀው ይኸው ገንዘብ ተከፍሏቸው ግራ ቀኙ ወደነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ ሊደረግ ይገባል ሲሉ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም አመልካቾች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውንና ተያያዥ ጭብጦችን በመያዝ የግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮችን ቃል መርምሮ አመልካቾች ለተጠሪ ብር 61,000.00 ውሣኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን



www.chilot.me

ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ፀንቷል፡፡

አመልካቾች ሐምሌ 22 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የቤት ሽያጭ ስለመኖሩ በሕግ መሠረት በጽሑፍ የተደረገና በሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ፊት የተፈረመ የቤት ሽያጭ ውሉ በሌለበት ሁኔታ ለቤቱ እድሳት የወጣ ገንዘብ ለተጠሪ ሊመለስላቸው ይገባል መባሉ እንዲሁም ተጠሪ ተጨማሪ ግንባታ አከናወንኩ የሚል ክርክር ሳይኖራቸውና በማስረጃም ባልተደገፈበት መንገድ ለብር 61,000.00/ስልሳ አንድ ሺህ ብር / ሃላፊ ተደርገን ውሣኔ መሰጠቱ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በማይፀና ረቂቅ ውል አመልካቾች የተቀበሉትን ብር 10,000.00 እንዲመልሱ ከመደረጉ በተጨማሪ ተጠሪ የግንባታ ፈቃድ እንኳን ሳይኖራቸው ሰራሁት ለሚሉት ቤት የምስክሮች ቃል ብቻ መሠረት ተደርጎ አመልካቾች ለተጠሪ የግንባታ ወጪ እንዲከፍሉ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ጭብጥ፡- አመልካቾች ለተጠሪ ገንዘቡን እንዲመልሱ ተብሎ የተወሰነው በሕጉ ተቀባይነት ያለውን ማስረጃ መሠረት ባደረገ መንገድ ነው? ወይስ አይደለም? የሚል ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ክስ የመሰረቱት አመልካቾች ቤት ሸጠውልኝ የተወሰነ ገንዘብ ከፍዬአለሁ የተወሰነውንም የአመልካቾችን ግዴታ ለመወጣት ስል ወጪ አድርጌ ቤቱን በመረከብ ተጨማሪ ግንባታ አከናውኼ ባለበት ሁኔታ በፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር በሕግ ፊት የሚጸና ውል የለም ስለተባለ ገንዘቡ ሊመለስልኝ ይገባል በማለት መሆኑን በግራ ቀኙ መካከል የቤት ሽያጭ ውል አለ የለም የሚለው ክርክርም በፍርድ ቤት ታይቶ ሕጋዊ የሆነ የቤት ሽያጭ ውል የሌለ መሆኑ መረጋገጡን ነው፡፡ የቤት ሽያጭ ውል የሌለ መሆኑ የተረጋገጠው ተጠሪ አመለካቾች የቤት ሽያጭ ውሉን ውል አዋዋይ ፊት ቀርበው ሊያስመዘግቡልኝ ይገባል በማለት በመሰረቱት ክስ አመልካቾች በሕግ ፊት የሚጸና ውል የለም በማለት በመከራከራቸው ምክንያት መሆኑንም ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ ችለናል፡፡ ተጠሪ ለአሁኑ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን ጉዳይ ያቀረቡትም የቤት ሽያጭ ውል የለም ተብሎ ውሣኔ ከተሰጠ በሁዋላ ሲሆን አመልካቾች ገንዘቡን ስለመቀበላቸው ያቀረቡትና ያሰሙት ማስረጃ የሰው ምስክሮችንና የሰነድ ማስረጃ ነው፡፡ አመልካቾችም የሰው ምስክሮችን አቅርበው ያሰሙ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት የውሣኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካቾችን ለክሱ ኃላፊ ያደረገው ገንዘቡን ከተጠሪ ስለመቀበላቸው ተጠሪ በተገቢው ማስረጃ አስረድተዋል አመልካች ግን በምስክሮቻቸው ሊያስተባብሉ አልቻሉም በሚል ምክንያት ነው፡፡ እንግዲህ ከላይ የተመለከቱት ነጥቦች በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጡት ሲሆን አመልካች የስር ፍርድ ቤት የስነ ሥርዓት ግድፈት ፈጽሟል በማለት የሚያቀርቡት አንዱ ነጥብ ተጠሪ ሕጋዊ የሆነ ቤት ሽያጭ ውል አለ በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ሳያገኝ በቤት ሽያጭ ውል የተከፈለው ገንዘብ እንዲመለስ ተብሎ መወሰኑ ለጉዳዩ መቅረብ ከሚገባው ማስረጃ አይነት አንፃር ተገቢነት የሌለው ነው በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የቤት ሽያጭ ውልን አስመልክቶ ክርክሩ የቀረበበት አግባብ በተጠሪ በኩል የቀረበው የቤት ሽያጭ ውል



www.chilot.me

በውል አዋዋይ ፊት እንዲመዘገብ የሚል ክስ በመቅረቡ በመሆኑና በሕጉ አግባብ የተደረገ የቤት ሽያጭ ውል የለም ተብሎ ድምዳሜ የተደረሰ በመሆኑ ተጠሪ በሽያጩ ምክንያት ለአመልካቾች የሠጡትን ገንዘብ ሊመለስልኝ ይገባል በማለት ጥያቄ ከማቅረብና በማናቸውም ማስረጃ ከማስረዳት የማይከለከል መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1808/2/ ፣ 1815 ፣ 2001 እስከ 2019 እንዲሁም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2162 እና 2164 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የቀረበውን የማስረጃ አይነት መሠረት በማድረግ መቃወሚያ የሚቀርብበት ጉዳይ አይደለም። በመሆኑም በዚህ ረገድ አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም።

አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩትና በዚህ ሰበር ችሎት እንዲታይ የተያዘው ጭብጥ በጉዳዩ ላይ የቀረበው ማስረጃ በሕጉ ስላለው ተቀባይነት ነው። ተጠሪ ሕጋዊ አይደለም በተባለው የቤት ሽያጭ ውል መሠረት ለአመልካቾች ከፍያለሁ የሚሉት የገንዘብ መጠን ብር 10,000.00/አስር ሺህ ብር / ሲሆን ሌላው ብር 51,000.00 ከቤቱ ርክክብ በሁዋላ ለተደረገ ግንባታ የወጣ ወጪ ነው። አመልካቾች ለጉዳዩ የቀረበው ማስረጃ ተቀባይነት የሌለው ነው የሚሉት ይህንኑ የገንዘብ መጠን በሰው ማስረጃ ሊረጋገጥ አይገባም ተጠሪ በማስረጃም ክርክራቸውን አላስደገፉም በማለት ነው። ይሁን እንጂ የአመልካችና የተጠሪ ግንኙነት የብድር ውል ሳይሆን ሕጋዊ ያልሆነ የቤት ሽያጭ ውል ስለመሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። በመሆኑም ጉዳዩ በሰው ምስክር ሊረጋገጥ አይገባም ተብሎ በአመልካቾች የቀረበው ክርክርም ሆነ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2472 ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ነው። ጉዳዩ መገዛት ያለበት ስለሽያጭ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በተለይ በመመልከት ወይም ስለጠቅላላው ውል የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በማየት ነው። በዚህም መሠረት ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ያላቸው ድንጋጌዎች በጠቅላላው የውል ሕግ ሲሆን በዚህ የውል ሕግ አንድን ነገር ለመግዛት ገንዘቡን የከፈለ ሰው ግዥው ሕጋዊ አይደለም ተብሎ ውሣኔ ከተሰጠው ገንዘቡ እንዲመለስለት ጥያቄ ቢያቀርብና ክሱን በሰው ምስክር ቢያስረዳ የሰው ምስክሮች ቃል ተቀባይነት የለውም ሊባል እንደማይችል ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2001 እስከ 2019 ድረስ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ያስረዳሉ። በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረቧቸውን የሰው ምስክሮች ቃል በመቀበል ውሣኔ መስጠቱ ከላይ ከተመለከቱት የጠቅላላ ውል ሕግ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንፃር ሕጋዊ እንጂ የሚነቀፍ ሁኖ አልተገኘም። ተጠሪ በቦታው ላይ ግንባታውን ያከናወኑት በአመልካቾች በኩል ተቃውሞ እየቀረበ ባለበት ሁኔታ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ያልተረጋገጠ ሲሆን የግንባታ ፈቃድ ሳያወጡ ግንባታው መከናወኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1178 እና 1179 ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ የተጠሪን የግንባታ ወጪ ይተካልኝ ጥያቄን ህጋዊ አይደለም ለማለት የሚያስችል አይሆንም። በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶቹ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ሁኖ አግኝተናል። በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል።

**ው ሣ ኔ**

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል።
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል። መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 43582

ሰኔ 28 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ራፒድ ኮንስትራክሽን ስራ ተቋራጭ ድርጅት - ጠበቃ አብዱወሀብ ረቢ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ኦርቢስ ንግድና ቴክኒክ ክፍል ሊሚትድ - ጠበቃ ግርማ ስላሴ አርአያ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የመኪና ሽያጭ ውል ጋር ተያይዞ የተነሳውን መኪናና ሊብሬ ልረከብ እንዲሁም የተቋረጠ ጥቅም ይከፈለኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡-አመልካች የሰሌዳ ቁጥር 3-07539 እና 3-09190 የሆኑ ሁለት መርቸዲስ ከባድ የጭነት ገልባጭ መኪናዎችን በ15-10-1993 ዓ.ም በተፈረመ የሽያጭ ውል ከተጠሪ ላይ በብር 1,620,000.00 (አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሃያ ሺህ ብር) ገዝቶ አብዛኛውን ገንዘብ ከከፈለ በሁዋላ ቀሪውን ብር 486,000.00 በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ከፍሎ ለማጠናቀቅ ይችል ዘንድ ቀናቸው ወደፊት ተደርጎ የተፃፉ ሁለት ቼኮችን ለተጠሪ በመስጠት ሁለቱን መኪኖች የተረከበ መሆኑን ፣ አመልካች ገዝቶ የተረከባቸው መኪኖች 50,000.00 (ሃምሳ ሺህ) ኪሎ ሜትር ከመጓዛቸው ወይም አመልካች ከተረከባቸው ከአንድ አመት በፊት ቴክኒካል የሆነ ብልሽት ስለገጠማቸው ተጠሪ በውሉ መሰረት መኪኖቹን ለመጠገን ባለበት ግዴታ መሰረት መኪኖቹን ለጥገና ከጋራዡ ገብተው ተገቢው ጥገናም የተደረገላቸው መሆኑን ፣ ተጠሪ ለጥገና ከተረከባቸው ሁለቱ መኪኖች ውስጥ የሰ.ቁጥር 3-09190 አ.አ የሆነውን መኪና ጠግኖ ለአመልካች ሲያስረክብ የሠሌዳ ቁጥር 3-07539 የሆነውን መኪናና የሁለቱን መኪኖች ሊብሬ ለአመልካች መልሶ ለማስረከብ ፈቃደኛ ሆኖ አለመገኘቱንና ለዚህ ተግባሩም የሰጠው ምክንያት ቀናቸው ወደፊት ተደርጎ በአመልካች በኩል የተጻፉት ቼኮች የመክፈያ ጊዜ የደረሰ ስለሆነ በቼኮቹ ላይ የሰፈረውን ገንዘብ ሳይከፈለኝ ሊብሬዎቹንም ሆነ መኪናውን አላስረክብም የሚል መሆኑን ፣ ሊብሬዎቹና መኪናው እንዲመለስለት አመልካች ማስጠንቀቂያ የሰጠ ቢሆንም ተጠሪ ፈቃደኛ አለመሆኑን ፣ ተጠሪ በቼኮቹ ላይ የሠፈረው ገንዘብ እንዲከፈለው በፍርድ ቤት ክስ መስርቶም ያስወሰነ መሆኑን ፣ ተጠሪ አንዱን መኪና ከእነ ሊብሬው እንዲሁም ሌላኛውን መኪና ሊብሬ አላግባብ በመያዙ ምክንያት የሠ/ቁጥር 3-07539 አ.አ የሆነው ገልባጭ መኪና ለጥገና በተጠሪ ጋራዥ ከገባበት ከሚያዝያ 06 ቀን 1995 ዓ/ም ጀምሮ በስር ፍርድ ቤት ክስ እስከ ቀረበበት እስከ ታህሳስ 15 ቀን 1997 ዓ/ም

ድረስ እንዲሁም የሰ/ቁጥር 3-09190 የሆነው መኪና ሊብሬ በተጠሪ በመያዙ ምክንያት ለስምሪት ከከተማው ለመውጣት የሚያስችለውን ፈቃድ አጥቶ ለዘጠኝ ወራት ያህል ስራ በማቆሙ ምክንያት በድምሩ ብር 1,402,741.00 (አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ አርባ አንድ ብር) ገቢ ያጣ መሆኑን ዘርዝሮ ሊብሬውንና የተያዘውን መኪና ለአመልካች እንዲያስረክቡ ፣ የተቋረጠውን ጥቅምም እንዲከፍል ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በተከሳሽነቱ ቀርቦ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃሚያ ነጥቦችንና የፍሬ ነገር ክርክሮችን በማንሳት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ በመጀመሪያ ደረጃ ያነሳው ነጥብ አመልካች ክስ የመሰረተው ቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ስለመሆኑ የሚገልፅ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ የመኪኖቹን ዋጋ ቀሪ ሂሳብ ለመክፈል የተጠሰው ቼክ ካልተከፈለ ተጠሪ መኪኖቹን ወዲያውኑ በእጁ አስገብቶ ለሕዝብ በሐራጅ ለመሸጥ ይችላል በሚል በግራ ቀኙ መካከል ውል መደረጉን ፣ ሊብሬውንም በመያዣነት ተይዞ አመልካች ክላውዶ ለማስደረግ ሲፈልግ ሲሰጠው የነበረ በመሆኑ በገቢ መቋረጥ ላይ ተጠሪ የፈፀመው ድርጊት የሌለ መሆኑንና ሌሎች ነጥቦችን በመዘርዘር ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለተከው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በተጠሪ በኩል በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የቀረበውን መከራከሪያ ነጥብ ውድቅ አድርጎ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ መኪኖቹንና ሊብሬዎቹን በሕግ አግባብ በመያዣነት የያዛቸው መሆኑ ተረጋገጧል በሚል ምክንያት የአመልካችን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ወሳኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ የካቲት 11 ቀን 2001 ዓ/ም በፃፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሚል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ፤ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በሕግ አግባብ የተደረገ የመያዣ ውል በሌለበት ሁኔታ የተሠጠ ፤ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2825 ፣ 2828 ፣ 2830 እና 2846 ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ጥቅምት 17 ቀን 2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ሁኖ የተገኘው፡-በአመልካችና በተጠሪ መካከል በሕግ አግባብ የተደረገ የመኪኖች የመያዣ ውል አለ ወይስ የለም? የሚለው ሲሆን ሌሎች ነጥቦች ከዚሁ ነጥብ ጋር ተያይዘው ምላሽ ሊሰጣቸው የሚገባቸው ናቸው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ ሰኔ 15 ቀን 1993 ዓ/ም የሁለት መኪኖች ግዥ ውል ማድረጋቸውን ፣ የመኪኖቹ ዋጋ ብር 1,620,000.00 (አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሓያ ሺህ ብር) ሁኖ ገዥው ከዚሁ ገንዘብ ውስጥ አብዛኛውን ከፍሎ ብር 486,000.00 (አራት መቶ ሰማኒያ ስድስት ሺህ ብር) የቀረበትን ይህንኑ ገንዘብም በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ከፍሎ ለማጠናቀቅ ይችል ዘንድ ቀናቸው ወደፊት ተደርጎ የተፃፈ ሁለት ቼኮችን ለሻጭ በመስጠት



www.chilot.me

መኪኖቹን ሰኔ 08 ቀን 1994 ዓ/ም ገዥው ተረክቦ የመኪኖቹን ሊብሬም በዚሁ ቀን መረከቡን ፣ መኪኖቹ በተጠሪው ጋራዥ ሚያዚያ 06 ቀን 1995 ዓ/ም መግባታቸውን ፣ ከዚህም በሁዋላ ለቀሪው እዳው መክፈያነት በአመልካች ለተጠሪ የተሰጡት ቼኮች ውስጥ 1ኛው የሚመነዘረው ሰኔ 02 ቀን 1995 ሲሆን ሁለተኛው ቼክ ደግሞ ሰኔ 30 ቀን 1995 ዓ/ም ሁኖ በእነዚህ ጊዜያት ለባንክ ቀርበው በቂ ስንቅ የላቸውም ተብሎ በመመለሳቸው ምክንያት ተጠሪ በአመልካች ላይ ቼኮቹን መሰረት አድርጎ ክስ መስርቶ የፍርድ ባለመብት መሆኑ መረጋገጡን ፣ ይህ ሁኖ እያለም ተጠሪ ለጥገና የገቡትንና ለአመልካች ከሸጣቸው መኪኖች ውስጥ የሰ/ቁጥር 3-0990 የሆነውን መኪና ሊብሬ ፣ የሰ/ቁጥር 3007539 የሆነውን መኪና ደግሞ ሊብሬውንና መኪናውን በመያዝ ለአመልካች ሊሰጥ ፈቃዳኛ ሊሆን ያልቻለ መሆኑን ፣ ይህ መብት ከሽያጭ ውሉ ያገኘው ስለመሆኑ ተጠሪ ጠቅሶ የሚከራከር ሲሆን አመልካች ደግሞ በሕግ አግባብ የተደረገ የመያዣ ውል የለውም በማለት የሚከራከር መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2825 ስር በግልጽ እንደተመለከተው የሚንቀሳቀስ ፣ ንብረት ፣ መያዣ ፣ (Pledge) መሰረተ ሐሳብ በዋናነት የአንድን ተንቀሳቃሽ ንብረት ይዞታ አሳልፎ በመስጠት ዋስ መሆን የሚቻልበት የግዴታ ዓይነት ነው፡፡ የዚህ አይነት ዋስትና (ፕሌጅ) አንድ ሰው ለራሱ ወይም ሌላ ሦስተኛ ወገን ለሚገባው ግዴታ ተፈጻሚነት ሊኖረው ይችላል፡፡ የዚህ አይነት ዋስትና ተፈጻሚነት ያለው በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ መሆኑ ከማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ (Mortgage) መለያ መንገዱ መሆኑም የሚታወቅ ነው፡፡ በመሆኑም  በመርህ ደረጃ ፕሌጅ ሊመሠረት የሚችለው የሚንቀሳቀሰውን ንብረት በማስተላለፍ ስለመሆኑ በዚህ ረገድ የተደነገጉት ድንጋጌዎች በግልፅ የሚያሳዩን ነጥብ ነው፡፡ የድንጋጌዎቹ ቅርጽ ፣ ይዘትና መንፈስ የንብረቱ ይዞታ ካልተላለፈ ፕሌጅ አልተቋቋመም ሊባል ሁሉ እንደሚችል ያስረዳል፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2832 በሕጉ ላይ ተገልጾ ካልተፈቀደ በቀር በመያዣ ተሰጥቶ ተይዘዋል የተባለው ዕቃ ከባለዕዳው እጅ ሳይወጣ በመያዣ እንደ ተሰጠ ሆኖ ሊቆጠር እንደማይችል  መደንገጉም ከላይ የተነሳውን ምክንያት የሚያጠናክር ነው፡፡ በሕግ ከተፈቀደው በቀር መያዣው በባለዕዳው እጅ ይሆናል ብለው ቢዋዋሉ እንኳን ውሉ እንደማይጸና ጨምሮ  ሕጉ ደንግጓል፡፡ ሆኖም ሕጉ ሲፈቅድ በልዩ ሁኔታ /As an exception/ የንብረቱ ይዞታ ሳይተላለፍ ፕሌጅ ሊመሠረት የሚችልበት የሕግ አግባብ አለ፡፡ ይህም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2830 ላይ የተመለከተው ሲሆን ፣ በተለይ በዕቃው ለማዘዝ የሚያስችሉት ሰነዶች ከተሰጡት ባለገንዘቡ መያዣውን እጅ እንዳደረገ ያህል ይቆጠራል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ንብረቶች ባለቤትነታቸው ያለምዝገባ ወረቀት (Title deed) ሊተላለፍ ስለማይችል የንብረት ይዞታ መተላለፍ ሳያስፈልግ ፕሌጅ ሊፈጸም ይችላል፡፡ እነዚህ ዓይነት ዋስትና ሊሰራባቸው የሚችሉት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1186(2) የተጠቀሱት ፣ ልዩ ተንቀሳቃሽ ፣ ንብረቶች ፣ እንደ ፣ መኪናና ፣ የአክሲዮን ፣ የዕቃ ፣ ማከማቻ ፣ ደረሰኝ ፣ ዓይነት ፣ ንብረቶች ፣ ናቸው፡፡ ንብረቱን ለባለገንዘቡ ከማስተላለፍ (Dispossession) በተጨማሪ የሚንቀሳቀስ ንብረት መያዣ በሕጉ በተቀመጠው የአሠራር ሁኔታ ፎርም መሠረት ካልተፈጸመ በሕግ ፊት የጸና አይሆንም፡፡ ይህ የፎርም መስፈርት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2828 ላይ የተደነገገ ሲሆን ፣ ዋስትና የተሰጠበት ግዴታ ከፍተኛው ገንዘብ ምን ያህል እንደሆነ በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን በግልጽና በጥንቃቄ  በመያዣው ውል ውስጥ መመልከት ይገባዋል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ውሉ ፈራሽ እንደሚሆን ሕጉ በግልጽ ደንግጓል፡፡ በተጨማሪም የመያዣው ውል ከብር 500.00 (አምስት መቶ ብር) በላይ የሆነ እንደሆነ ውሉ በጽሑፍ ካልተደረገና ይኸውም እርግጠኛ ቀን ካገኘበት ዘመን ጀምሮ ካልሆነ በቀር አይጸናም፡፡ ስለዚህ ከብር 500.00 (አምስት መቶ ብር) በላይ የሆነ የሚንቀሳቀስ ንብረት መያዣ በጽሑፍ እንዲፈጸም ሕጉ  በአስገዳጅ ሁኔታ ያስቀመጠው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እንዲህ ዓይነት የመያዣ ውል  በጽሑፍ እንዲደረግ ሕጉ ግዴታ ካስቀመጠ



www.chilot.me

በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1727 መሠረት በውሉ ፣ ግዴታ ፣ ያለባቸው ፣ አስያዡና ፣ መያዣ ፣ ተቀባዩ ፣ መፈረም ፣ እንዳለባቸውና ፣ ሁለት ፣ ምስክሮች ፣ ፊትም ፣ መረጋገጥን የግድ ይሏል ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ካልተሟላ ውሉ በሕግ ፊት የሚፀና አለመሆኑን ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎችን ፣ በአንድ ላይ ስናነብ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ የሚንቀሳቀስ ንብረት መያዣ ውል( Pledge) አቋቁሜአለሁ በማለት ተከራክሮ የበታች ፍርድ ቤቶችም ውሉ መያዣ ነው ከሚባል በስተቀር ሌላ ምክንያት ሊሰጠው የሚችለው አይደለም በማለት ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ ይሁን እንጂ ሰኔ 15 ቀን 1993 ዓ/ም በተደረገው ውል ለውሉ መያዣነት የተያዙት የማይንቀሳቀሱት ንብረቶች አሁን ክርክር ያስነሱ ስለመሆኑ ፣ የዋስትናው መጠን ምን ያህል እንደሆነ በግልፅ ያልተመለከተ ሲሆን የበታች ፍርድ ቤቶች ውሉ መያዣ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱት "ገዥው ግዴታውን የማያከብር ሁኖ ሲገኝ ወይም ቼኩ ክፍያ ሳይፈጸምበት ከተመለሰ ያልተከፈለው ውዝፍ ሂሳብ በሙሉ ወዲያውኑ ተገቢ ሂሳብና ተከፋይ ይሆናል፡፡ በዚህ ጊዜም ሻጩ ወዲያውኑ መኪናውን በእጁ አግብቶ ያላአንዳች ሌላ አይነት አሰራር መኪናውን ለሕዝብ በሐራጅ የመሸጥ ስራውን ይቀጥላል፡፡" በሚል በውሉ ውስጥ የተቀመጠውን ዐረፍተ ነገር በመያዝ ነው፡፡ ሆኖም ከላይ እንደተጠቀሰው በሽያጭ ውሉ ውስጥ የመያዣ ውሉ በግልጽ የተጠቀሰና በሥርዓቱ መሰረት የተደረገ የመያዣ ውል አይደለም፡፡ ይልቁንም ተጠሪ ከመኪናዎቹ ውስጥ አንዱን በውሉ ባለው ግዴታ መሰረት ለጥገና ሲገባ የያዘው መሆኑ ሲታይ የሚንቀሳቀስ ንብረት መያዣ ውል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2828 እና 2930 ድንጋጌዎችን ባከበረ መልኩ ተደርጓል ለማለት የሚያስደፍር አይደለም፡፡ ተጠሪ በአንድ በኩል የሚንቀሳቀስ ንብረት መያዣ ውል ያለው መሆኑን ጠቅሶ ከመኪኖቹ አንዱንና የሁለቱን መኪኖች ሊብሬ በይዞታው ስር ያደረገ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ለእዳው መክፍያ እንዲውል የተሰጠውን ቼክ መሰረት በማድረግ ክስ አቅርቦ የፍርድ ባለመብት መሆኑ ሲታይ የመኪናው ሽያጭ ውል ሰኔ 15 ቀን 1993 ዓ/ም ሲደረግ መያዣውን አስመልክቶ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ሐሳብ ግልፅነት የሌለው መሆኑን የሚጠቁም ሲሆን በቼኩ ላይ በፍርድ ቤት ክስ መስርቶ መብቱን ከውሉ መደረግ በሁዋላ ማስከበሩ ከፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1734 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አንፃር ሲታይ የመያዣ ውል ሰኔ 15 ቀን 1993 ዓ/ም በተደረገው ውል መሰረት ያለመቋቋሙን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች የመኪኖቹን ሊብሬ ለተጠሪ መስጠቱ ያልተካደ ፍሬ ነገር ሲሆን ይህ መሆኑ ተጠሪ መኪኖቹን በራሱ ስልጣን እንዲሸጥ መብት የሚሰጠው ሳይሆን መኪኖቹ እዳው ከመከፈሉ በፊት ለሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፉና የተጠሪን ቅድሚያ መብት የሚያስገኝ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ ተጠሪ የሚንቀሳቀስ ንብረት የመያዣ ውል በመኪኖቹ አቋቋሜአሁ በማለት አንዱን የአመልካች መኪና በቁጥጥር ስር ማዋሉን ከውሉ የመነጨና ሕጋዊ ጥበቃ ሊደርግለት የሚገባው እርምጃ አይደለም፡፡ አመልካች ሊብሬውን ለመያዣነት መስጠቱን በክርክሩ ሂደት ያረጋገጠው ጉዳይ በመሆኑ ተጠሪ በመኪኖቹ ሊኖረው የሚችለው መብት ሊብሬውን በመያዝ የቅድሚያ መብት ማስከበር ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ መኪናውን ይዞ ቁጥጥር ስር ያደረገው በመያዣ ውሉ መሰረት ነው በማለት የደረሱበት ድምዳሜ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2825 ፣ 2828 እና 2830 እንዲሁም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1727 ድንጋጌዎችን ባገናዘበ መልኩ ሁኖ ስላላገኘን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሌላው ተጠሪ የአመልካችን መኪኖች በራሱ ይዞ ቁጥጥር ስር ለማዋል የሚችልበት በሕግ አግባብ የተደረገና በሕጉ መሰረት ጥበቃ የሚደረግለት የሚንቀሳቀስ ንብረት መያዣ ውል የለም ከተባለ መኪናውን ለጥገናው በቂና ተገቢ ጊዜ ነው ከሚባለው ምክንያታዊ ጊዜ በላይ ከሕግ ውጪ



www.chilot.me

በመያዙ በአመልካች ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ የማይሆንበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም መኪኖቹ ወደ ተጠሪ ጋራዥ የገቡት ለጥገና ነው የሚለው ፍሬ ነገር የተረጋገጠ ቢሆንም ለጥገናው ጊዜ ያስፈልግ የነበረው ጊዜ ምን ያህል ነው ፣ ከሕግ ውጪ የተያዘው የሠሌዳ ቁጥር 3-07539 የሆነውን መኪና በወቅቱ ተጠግኖ ለአመልካች ቢሰጥ ኑሮ ይገኝ የነበረው ሕጋዊ ገቢ ምን ያህል ነው የሚለው እና ሌላ ከገቢ ጋር ተያይዞ የሚነሳ ክርክር በፍሬ ነገር ደረጃ በስር ፍርድ ቤት ያልነጠረ በመሆኑ በዚህ ችሎት መቋጫ ሊሰጠው የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ለመኪናው ጥገና የሚያስፈልገውን ምክንያታዊ ጊዜ በተገቢው መንገድ በማጣራት እንዲያረጋግጥና ከዚህ ጊዜ ውጪ ላለው የመኪና መያዝ ደግሞ ተጠሪ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2027 ፣ 2028 እና 2054 ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በመገንዘብ አመልካች ሊያገኝ ይችል የነበረውን የገቢ መጠን በተመለከተ የግራ ቀኙኝ ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ሊወስነው የሚገባ ጉዳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡ አመልካች የመኪኖቹን ሊብሬ ተጠሪ በመያዙ ምክንያት ጥቅም ተቋርጧል ለሚለው ክርክር የስር ፍርድ ቤት አመልካች በፈለገ ጊዜ ሊብሬውን እየፈረመ ወስዶ ይመለስ የነበረ መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠ ቢሆንም ሊብሬው በመያዙና የሰ/ቁጥር 3-09190 የሆነው መኪና ክላውዶ ባለመደረጉ በአመልካች ላይ ደርሷል በማለት አመልካች በጠየቀው ዳኝነት ላይ ግልፅ ውሳኔ አልሰጠበትም፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው በሕግ አግባብ የተቋቋመ የሚንቀሳቀስ ንብረት መያዣ ውል አለ የሚል ድምዳሜ የስር ፍርድ ቤቱ በመድረሱ ምክንያት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ነገር ግን ከላይ እንደተመለከተው በሕግ አግባብ የተቋቋመ የመያዣ ውል ባይኖርም ሊብሬዎቹን አመልካች ለተጠሪ አሳልፎ መስጠቱ ተጠሪ የቅድሚያ መብቱን ለማስከበር የሚያስችለው ይሆን የነበረ ሁኖ በየጊዜውም ሊብሬውን ለአመልካች አሳልፎ ይሰጥ የነበረ መሆኑን ተጠሪ በምስክሩ ማረጋገጡን ፣ አመልካች ሊብሬውን በየጊዜው እየፈረመ ያለመውሰዱን ከመግለጽ ውጪ በተገቢው ማስረጃ በማስገደፍ ክርክሩን ያለማቅረቡን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰ/ቁጥር 3-09190 መኪና ሊብሬው በተጠሪ ለአመልካች በየጊዜው ይሰጥ የነበረ መሆኑን እንደተረጋገጠ ፍሬ ነገር በመውሰድ በሕግ አተገባበር ወይም አተረጓጎም ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ካለ ብቻ ማረም ስልጣኑ መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ))እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌ መገንዘብ የምንችለው ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች የሰ/ቁጥር 3-09190 የሆነ መኪና ሊብሬ በተጠሪ በመያዙ ምክንያት ጥቅም ተቋርጦብኛል በማለት ያቀረበው ክርክር በተገቢው ማስረጃ የተደገፈ ባለመሆኑ ተቀባይነት ያለው ሁኖ አላገኘውም፡፡ እንዲሁም የመኪኖቹን ሊብሬ በተመለከተ አመልካች ለተጠሪ በራሱ ፈቃድ አሳልፎ መስጠቱ የተረጋገጠ ጉዳይ በመሆኑ አመልካች ቀሪ እዳውን ለተጠሪ እስካልከፈለው ድረስ ተጠሪ ሊብሬዎቹን በዚህ የክርክር ደረጃ እንዲመልስ የሚያስገደደው ሕጋዊ ምክንያት የሌለ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካች ጥያቄ የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

በአጠቃላይ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የሽያጭ ውል ተጠሪ መኪኖቹ ላይ የቅድሚያ መብት እንዲኖረው ከሚያደርግ በስተቀር መኪኖቹን በራሱ ሥልጣን በመያዝና ቁጥጥር ስር በማዋል ራሱ እንዲሸጥ መብት የሚያጎናፅፍ አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት የሠሌዳ ቁጥር 3-07539 የሆነውን የአመልካች መኪና ለጥገና ከሚያስፈልገው ምክንያታዊ ጊዜ ውጪ በመያዙ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት ያለበት ሲሆን የጉዳት መጠኑ በስር ፍርድ ቤት ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባ ሁኖ የሰ/ቁጥር 3-09190 የሆነውን መኪና ሊብሬ በመያዙ በአመልካች ላይ ጉዳት ደርሷል ፣ ሊብሬዎቹን ተጠሪ ሊመልስ ይገባል በማለት አመልካች ለአቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ግን ተጠሪ ኃላፊ

ሊሆን የሚችልበት አግባብ የሌለ ሁኖ ስለአገኘነው የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊሻሻል የሚገባው ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 35917 ጥቅምት 21 ቀን 1999 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 28219 ህዳር 15 ቀን 2001 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል ሰኔ 15 ቀን 1993 ዓ/ም የተደረገው የመኪኖች ሽያጭ ውል ተጠሪ መኪኖቹን በራሱ ሥልጣን በመያዝና ቁጥጥር ስር በማዋል ራሱ እንዲሸጥ መብት የሚያጎናፅፍ አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህም ምክንያት የሠሌዳ ቁጥር 3-07539 የሆነውን የአመልካች መኪና ለጥገና ከሚያስፈለገው ምክንያታዊ ጊዜ ውጪ በመያዙ ለደረሰው ጉዳት ተጠሪ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን የጉዳት መጠኑ በስር ፍርድ ቤት ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው በመሆኑ ለመኪናው ጥገና የሚያስፈልገው ምክንያታዊ ጊዜ ምን ያህል እንደሆነ እና ለጥገናው ከሚያስፈለውገው ምክንያታዊ ጊዜ ውጪ መኪናው ሊያስገኝ ይችል የነበረው ገቢ መጠን ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሰምቶና በተገቢው መንገድ አጣርቶ ተገቢውን ሊወስንበት ይገባል በማለት በዚሁ ነጥብ ላይ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1)መሰረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. ተጠሪ የሠሌዳ ቁጥር 3-07539 የሆነውን የአመልካች መኪና ለአመልካች ሊመልስና ሊያስረክብ ይገባል ብለናል፡፡
5. የሰ/ቁጥር 3-09190 የሆነውን መኪና ሊብሬ በመያዙ በአመልካች ላይ ጉዳት ደርሷል በማለት አመልካች ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
6. አመልካች ሊብሬውን ለክላውዶ የሚያስፈልገው መሆኑን ሲያረጋግጥ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጎ ከሚሰጥ በስተቀር እዳው እስከሚከፈለው ድረስ ሊብሬዎቹን ተጠሪ ለአመልካች እንዲያስረክብ አይገደደም ብለናል፡፡
7. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ውጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ/ 60204

ሰኔ 14 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሒጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አቶ ታደሰ ደሞሬ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ጌታሁን ለቻሞ - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገንዘብ ክርክር ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ ተጠሪ ሕዳር 26 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፋው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ሰኔ 05 ቀን 1997 ዓ/ም ለአመልካች ብር 180,000.00(አንድ መቶ ሰማኒያ ሺህ) ለጊዜው በአደራ አስቀማጭነት መኪና ተገዝቶ አብረው ለመጠቀም ተነጋግረው የሠጡ መሆኑን ገልፀውና በዚህ አጋጣሚ ወደ አመልካች እጅ ገንዘቡ ከገባ በሁዋላ ገንዘቡን ለመመለስ አመልካች ሲጠየቁ ሊመልሱ ያልቻሉ መሆኑን ጠቅሰው ገንዘቡን ከእነ ወለዱ እንዲመልሱላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸው የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም ተጠሪ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ በአደራ ያልሰጧቸው መሆኑን ገልጸውና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች በተጠሪ በኩል ያልቀረቡባቸው መሆኑን ጠቅሰው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ጉዳዩን በመመርመር አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ ከነሕጋዊ ወለዱ(9%) ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች መስከረም 04 ቀን 2003 ዓ.ም በፃፉት በ2/ሁለት/ገፅ የሠበር ማመልከቻ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሚል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡-ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ በአደራ የሠጡ መሆኑ እየተገለጸ ለጉዳዩ መቅረብ የሚገባው ማስረጃ ሳይቀርብ በሰው ምስክሮች ቃል ለክሱ ኃላፊ ተደርገው መወሰኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2782፣2472 እና በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2471 እስከ 2489 ድረስ የተደነገጉትን የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓቶች ፣ እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 248 ስር ስለጭብጥ አመሰራረት



www.chilot.me

የተደነገገውን ሥርዓት ባላገናዘበ መልኩ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የሠበር አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ ለአመልካች ብር 180,000.00(አንድ መቶ ሰማኒያ ሺህ ብር) በአደራ መስጠታቸው ስለተረጋገጠ ይክፈሉ ተብሎ መወሰኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2472 እና 2782 ድንጋጌዎች አንፃር ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሠበር ችሎቱ ሊቀርብ ይገባዋል በመባሉ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ሕዳር 27 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ 2/ሁለት/ ገፅ ማመልከቻ፡- ገንዘቡ በአደራ ለአመልካች ተሰጠ ተብሎ ክሱ ሲመሰረት የተገለፀው የአገላለፅ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር አደራ ተብሎ አልተረጋገጠም ፣ ገንዘቡ ለአመልካች የተሰጣቸው መኪናውን በጋራ ገዝቶ ለመጠቀም በሚል ሃሳብ ሁኖ ይኸው ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ ምንም አይነት የሕግ ግድፈት የሌለበት በመሆኑ ሊጸና ይገባል ሲሉ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡ አመልካችም ታህሳስ 20 ቀን 2003 ዓ.ም በፃፉት 2/ሁለት/ገፅ ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን ሠጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጹሁፍ እና የቃል ክርክር የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል እንደመረመውም አመልካች ለክርክሩ መነሻ ለሆነው ገንዘብ ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ መወሰኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2472 እና 2782 ድንጋጌዎች አንፃር ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በመሠረቱ የፍትሐብሔር ግዴታ ከውል ወይም ከህግ ከሚመነጭ ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ክስ አቅራቢው ወገን ደግሞ ይህንኑ በአግባቡ በመለየትና በመግለጽ የሚጠይቀውን ዳኝነት በዝርዝር የማቅረብ እንዲሁም የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡ በተያዘው ጉዳይ በአመልካችና በተጠሪ መሀከል የተፈጠረው ግንኙነት ምን እንደነበረ ከላይ በተመለከተው መልኩ የጥሬ ገንዘብ አደራ ሲሆን አመልካች በክስ አቤቱታቸው በዝርዝር ለይተውና ገልፀው ለተጠሪ ገንዘቡን በአደራ የሰጡ መሆኑን በማሳየት ክሱን መስርተዋል ፣ ክርክርም አድርገዋል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ከአመልካች ጋር አለኝ የሚሉትን ግንኙነት በሕጉ አግባብ ሊቀርብ በሚገባው ማስረጃ የማስረዳት ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ገንዘብ አመልካች ከተጠሪ ወሰዱ የተባሉት በአደራ ሲሆን አመልካች ደግሞ ይኸው ግንኙት ከተጠሪ ጋር የለኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ስለሆነም የተጠሪ ክርክር መሠረት ያደረገው አደራ ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ እንግዲህ ግንኙነቱ አደራ ነው ከተባለ በዚህ ረገድ የቀረበው ክርክርም ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች በመመልከት ሊስተናገድ የሚገባው ይሆናል፡፡

በመሠረቱ የፍትሐብሔር ግንኙነት ዓይነት የተለያየ ሲሆን እያንዳንዱ ግንኙነት የሚቋቋምበት ፣ ግንኙነቱ ክርክር ቢያስነሣ ተከራካሪዎቹ የሚለያዩባቸውን ነጥቦችን ለማስረዳት መቅረብ ያለበት የማስረጃ ዓይነት በህጉ የተወሠነ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ግንኙነቱ ክርክር ሲያስነሣ ተከራካሪዎቹ የሚለያዩባቸውን ነጥቦች የማስረዳት ሸክም በተከራካሪ ወገኖች በሚቀርበው የክርክር ይዘት አግባብነት ባለው ህግ የተወሰነ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ የፍትሐብሔር ግንኙነቶች ክርክር ሲያስነሱ በምስክር ወይም በተለየ ማስረጃ መረጋገጥ ያለባቸው መሆኑ በህግ ተለይተው ተመልክተዋል፡፡ በመሆኑም ለእያንዳንዱ የፍታሐብሔር ግንኙነት የማስረዳት ሸክም ያለበት ወገን በቀጥታ አግባብነትና ተፈፃሚነት ባለው በፍትሐብሔር ህጉ በታዘዘው የማስረጃ ዓይነት ማረጋገጥ


www.chilot.me

አለበት፡፡ አደራ የፍታሐብሔር ግንኙነት የሚቋቋምበት አንዱ ተግባር ነው፡፡ይህ ተግባር ክርክር ሲያስነሣ የግንኙነቱን መኖር ማስረዳት የሚቻልበትን መንገድ ህጉ ለይቶ ወስኗል፡፡ የአደራ ጉዳይን በተመለከተ አግባብነት ያላቸው የፍታሐብሔር ህግ ድንጋጌዎች ቁጥር 2779 እና ተከታዬቹ ናቸው፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2782(1) ድንጋጌ የገንዘብ አደራ ሁኖ ሲገኝ ሊቀርብ የሚገባውን የማስረጃ አይነት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2472"ን" በማጣቀስ ምላሽ ይሠጣል፡፡ በዚህም መሰረት ለአደራ ተቀባዩ የተሰጠው እቃ ጥሬ ገንዘብ የሆነ እንደሆነ አደራ ተቀባዩ እንዲገለገልበት ፣ ተፈቅዶለት ከሆነ ስለእንደዚህ ያለው ጉዳይ የአላቂ ነገርን ብድር የሚመለከቱ ደንቦች ተፈጻሚ እንደሚሆኑ ይገልፃል፡፡ በመሆኑም በአደራ የተሰጠው እቃ አደራ ተቀባዩ እንዲገለገልበት የተፈቀደለት ገንዘብ ከሆነ ይህ ግንኙት የሚገዛው የአላቂ ነገር ብድርን በሚመለከቱ ደንቦች ይሆናል ማለት ነው፡፡ አደራ ሠጪው አደራ ተቀባዩ በገንዘቡ እንዲገለገልበት በግልፅ ሊፈቅድለት የሚችል ሲሆን ግልፅ ስምምነት ባይኖርም ገንዘቡ ለአደራ ተቀባዩ የተሰጠው ሳይታሸግና ሳይዘጋበት ከሆነ ተቀባዩ እንዲገለገልበት እንደተሰጠው የሚቆጠር መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2782(2) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ተጠሪ ለአመልካቹ የሰጡት ጥሬ ገንዘብ ሲሆን ገንዘቡን ተጠሪ አሽገው ወይም ዘግተው ለአመልካች የሰጡ መሆኑንም የተነሳ ክርክር የሌለ በመሆኑ አመልካቹ ገንዘቡን እንዲገለገሉበት በተጠሪ እንደተፈቀደ የሚቆጠር ነው፡፡ እንዲሁም ተጠሪ ገንዘቡ ለመኪና መግዣ ተሰጠ ይበሉ እንጂ በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር 180,000.00(አንድ መቶ ሰማኒያ ሽህ ብር) ቆጥረው ለአመልካች በአደራ የሰጡ ስለመሆኑ ማስረጃ አቅርቤ አሰማለሁ በማለት ባቀረቡት ክርክር ማስረጃዎቹን አቅርበው በአደራ የሰጡ ስለመሆኑ ማስመስከራቸውን የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ በግልፅ የሚያሳይ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ እንዲህ ከሆነ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው ግንኙነት የሚገዛው የአላቂ ነገር ብድርን በሚመለከቱ የፍትሐብሔር ሕግ ደንቦች መሆኑ ግልፅ ይሆናል፡፡

ወደ ሕጉ ስንመጣም የፍ/ህ/ቁ 2472(1) በብድር የተሠጠ ገንዘብ ከብር 500.00/አምስት መቶ ብር/ በላይ ሲሆን የብድሩን ውል በጽሁፍ ወይም በፍርድ ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ወይም መሃላ ካልሆነ በቀር ለማስረዳት አይቻልም በማለት የሚደነግግ ሲሆን ለብድር ውሉ ሌላ ማናቸውም ዓይነት ማስረጃ ማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ ደግሞ የተጠቃሹ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ በአስገዳጅ ሁኔታ ደንግጓል፡፡ ስለሆነም ከብር 500.00 በላይ የሆነ የገንዘብ ብድር ውል ለማስረዳት ተቀባይነት ያለው ማስረጃ በጽሁፍ ወይም በፍርድ ቤት በተደረገ እምነት ቃል ወይም መሃላ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ከእነዚህ ማስረጃዎች ውጪ ሌሎች የማስረጃ ዓይነቶች ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑ በህጉ ተለይቶ መቀመጡን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ ጉዳይ የተጠሪ ክርክር ብር 180,000.00 ለአመልካች ለጊዜው በአደራ ሰጥቼው ነው የሚል ሆኖ ይህንኑ በተመለከተ በህጉ አግባብ ተቀባይነት ያለውን የማስረጃ ዓይነት የማቅረብ ግዴታ የተወጡ ሁነው አልተገኙም፡፡ ተጠሪ ጉዳዩን ለማስረዳት ያቀረቡት የሰው ማስረጃዎችን ሲሆን የሰው ማስረጃ ደግሞ ለጉዳዩ ተቀባይነት ያለው(Admissible) ማስረጃ አይደለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተጠሪ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ ሊመልሱ ይገባል ወደ ሚለው ድምዳሜ የደረሱት ተቀባይነት የሌላቸው ማስረጃዎች የሰጡትን የምስክርነት ቃል በመያዝ በፍ/ህ/ቁ 2782 ፣ 2472(1) እና (2) ድንጋጌዎች ስር የተቀመጠውን ሁኔታ ባላገናዘበ መልኩ ነው፡፡ ሲጠቃለልም ተጠሪ ገንዘቡን ለአመልካች ሠጠሁ የሚሉበትን ምክንያት ተቀባይነት ያለውን የማስረጃ ዓይነት /admissible evidence/ በማቅረብ ያላስረዱ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ወስነናል፡፡



www.chilot.me

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 12455 ግንቦት 21 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 82022 ሐምሌ 04 ቀን 2002 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348 (1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ ብር 180,000.00/አንድ መቶ ሰማኒያ ሺህ ብር/ ሊከፍሉ የሚችሉበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. በክርክሩ ሂደት የወጡትን ወጪዎችንና ኪሣራዎችን ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**ሃ/ዲ**



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 61110

ሰኔ 28 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አል ናይል ቢዝነስ ግሩኘ ኃ/የተ/የግል ማህበር ጠበቃ አቶ ዓለማየሁ ተፈሪ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ነገረ ፈጅ ብርሃነ ደስታ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ በመዝገብ ቁጥር 81664 ያቀረበውን ክስና አመልካች በተጠሪ ላይ በመዝገብ ቁጥር 85281 ያቀረበውን ክስ በማጣመር በመዝገብ ቁጥር 81664 በማየት ሰኔ 12 ቀን 2002 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

1. ተጠሪ በአመልካች ላይ በመዝገብ ቁጥር 81664 በሥር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ከሣሽ ለሚያሠራው የመንገድ ሥራ አገልግሎት የሚሰጡ አስር የውሃ ጉድጓዶች እንዲቆፈርለት አመልካች /ተከሣሽ/ ጋር ህዳር 15 ቀን 1999 ዓ.ም ውል ተዋውለናል፡፡ ውሉ ሁለት ክፍል ያለው ሲሆን በውሉ የመጀመሪያ ክፍል ተከሣሽ በደገሀቡር አካባቢ ጥልቀታቸው ሁለት መቶ ሀምሣ ሜትር የሚሆኑ ሁለት ጉድጓዶችን በመቆፈር በአንድ መቶ አምስት ቀናት በማጠናቀቅ ለከሣሽ ግንቦት 15 ቀን 1999 ዓ.ም ለማስረከብ ተስማምቷል፡፡

በውሉ ሁለተኛው ክፍል ተከሣሽ ከደገሀቡር እስከ ቀብራደሀር ከቀብራደሀር እስከ ሰላዩ ባለው ቦታ ጥልቀታቸው ሁለት መቶ ሀምሣ የሆኑ ስምንት ጉድጓዶች ቆፍሮና አጠናቅቆ በመቶ ሰማኒያ ቀን ውስጥ ማለትም ግንቦት 29 ቀን 1999 ዓ.ም ለከሣሽ ለማስረከብ ተስማምቷል፡፡ ተከሣሽ ቆፍሮ ያጠናቀቀው ሁለት ጉድጓድ ሲሆን እነርሡም ቢሆኑ በውሉ መሠረት የተሠሩ አይደሉም፡፡ ተከሣሽ ያለከሣሽ ፈቃድ ሥራውን ለንዑስ ተቋራጭ በመስጠቱ ውሉ ተቀርጧል፡፡ ስለሆነም ተከሣሽ በገባው የውሀ ጉድጓድ ቆፋሮ ሥራ ውል መሠረት ግዴታውን ያልፈፀመ በመሆኑ ከከሣሽ የወሰደውን ብር 1,838,592.27/አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰላሣ ስምንት ሺ አምስት መቶ ዘጠና ሁለት ብር

ከሃያ ሰባት ሣንቲም/ እንዲመልስ እንዲወሰንልኝ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የስራ ውሉን በአግባቡ ባለመፈፀሙ ምክንያት ከሣሽ ጨረታ አውጥቶ ሥራውን ለሌላ ተቋራጭ ሰጥቷል፡፡ ሥራው ለሌላ ተቋራጭ ሲሰጥ ብር 2,708,219/ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ ስምንት ሺ ሁለት መቶ አሥራ ዘጠኝ ብር/ ከበፊተኛው ውል ብልጫ ያለው ገንዘብ ለመክፈል ተገድደናል፡፡

ስለዚህ ተከሣሽ ይህንን በልዩነት የተጠየቅነውን ገንዘብ እንዲከፍል ይወሰንልን እንዲሁም ተከሣሽ በውሉ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ሥራው ለዘገየበት አንድ ፐርሰንት በየቀኑ መቀጫ ለመክፈል የተስማማ በመሆኑ ብር 1,057,070.93/አንድ ሚሊዮን ሀምሣ ሰባት ሺህ ሰባ ብር ከዘጠና ሶስት ሣንቲም/ የመክፈል ከውል የመነጨ ግዴታ አለበት፡፡ ስለሆነም ተከሣሽ በድምሩ ብር 5,603,532.52/አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሶስት ሺ አምስት መቶ ሰላሣ ሁለት ብር ከሀምሣ ሁለት ብር ከሀምሣ ሁለት ሣንቲም/ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ተገቢ ናቸው የሚላቸውን ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡

አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ ከሣሽ ሥራውን በወቅቱ ያላስረከበና ሥራው እንዲጀመር ሁኔታዎችን ያላመቻቸ በመሆኑ ተከሣሽ መቀጫ እንዲከፍል ያቀረበው ጥያቄ ተገቢነት የለውም፡፡ ተከሣሽ በውሉ መሠረት በውሉ ክፍል አንድ የተገለፁትን ሁለት ጉድጓዶች በወቅቱ ቆፍሮ አጠናቅቋል፡፡ በውሉ ሁለተኛው ክፍል ከተገለፁት ጉድጓዶች አንድ ጉድጓድ ቆፍሯል፡፡ ሶስተኛው ጉድጓድ ሁለት መቶ ሃምሣ ሜትር ጥልቀት ተቆፍሯል፡፡ ውሃ ላይ ለመድረስ አስተላለፊ ቱቦ እንዲገባለት ተከሣሽ ለከሣሽ ሃሣብ ያቀረበለት ቢሆንም አልተቀበለውም፡፡ የዲዛይን ሥራ ለንዑስ ተቋራጭ የሰጠነው ከሣሽ አውቀትና ፈቃደኛ በመሆኑ ነው፡፡ ሰባት ጉድጓዶች አልተሠሩም፡፡ ሰባት ጉድጓዶች ያልተሠሩት በወቅቱ በአካባቢው የፀጥታ ችግር ስለነበረና ከሣሽ ሥራውን በቅርበት የሚከታተል ክፍያ የሚያፀድቅ መሀንዲስ ባለመመደቡ ነው፡፡ አመልካች ውሉን ያፈረሰው በራሱ ምክንያትና ጥፋት በመሆኑ ለተጨማሪ ዋጋ ክፍያ እንዲሸፍን ያቀረበው ጥያቄ ተገቢነት የለውም በማለት የተከራከረ ሲሆን ተገቢ ነው የሚላቸውን ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡

2. በመዝገብ ቁጥር 85285 አመልካች ከሣሽ ተጠሪ ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ከሣሽ/አመልካች/ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ከተከሣሽ ጋር በነበረኝ የውሀ ጉድጓድ ቁፋሮ ውል መሠረት በውሉ ክፍል አንድ የተመለከቱትን ሁለት ጉድጓዶች ሙሉ በሙሉ ቆፍሬ አጠናቅቄያለሁ፡፡ በውሉ ሁለተኛ ክፍል ከተገለፁት ስምንት ጉድጓዶች አንድ ጉድጓድ በውሉ መሠረት ቆፍሬአለሁ፡፡ ተከሣሽ ለሠራሁት ሥራ ክፍያ ያልፈፀመልኝ ሲሆን በወቅቱ ኢንጅነር አልመደበም፡፡ ተከሣሽ የውሉ ጊዜ ካለቀ ከስድስት ወር በኋላ የመደበው ኢንጅነር ሥራው በአግባቡ አልተሠራም በማለቱ ክፍያ ለመፈፀም ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ኢንጅነሩ ጋር እንድንነጋገር ያቀርብነውን ጥያቄ ተከሣሽ አልተቀበለውም፡፡ ስለሆነም ከሣሽ ለቆፈርኳቸው የሶስት ጉድጓዶች ዋጋ ብር 2,776,728.22 /ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ሰባት መቶ ሃያ ስምንት ብር ከሃያ ሁለት ሣንቲም/ ተከሣሽ እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ፡፡ ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ከሣሽ ብር 1,838,298.12 ቅድሚያ ክፍያ ወስጃለሁ፡፡ ስለዚህ ተከሣሽ ብር 938,435.95/ዘጠኝ መቶ ስላሣ ስምንት ሺህ አራት መቶ ስላሣ አምስት ብር ከዘጠና አምስት ሣንቲም/ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ በተከሣሽነት ቀርቦ ከሣሽ የሥራ ኘላንና ኘሮግራም ሣያወጣ ሥራውን ጀምሯል፡፡ ከሣሽ ሁለት ጉድጓድ የቆፈረ ቢሆንም በውሉ መሠረት በአግባቡ አልተሠሩም፡፡ ተከሣሽ ተቆጣጣሪ መሃንዲስ አለመመደቡ ከሣሽ ሥራውን በውሉ መሠረት እንዳይሠራ የሚያደርግ ምክንያት

አይደለም፡፡ ውሉ የተቋረጠው በከሣሽ ጉድለት ነው ስለዚህ ከሣሽ ያቀረበው ክስ የህግ መሠረት የለውም በማለት መልስ አቅርቧል፡፡

3. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሁለቱ መዝገቦች በተከራካሪዎች የተቆጠሩ ምስክሮችን ከሰማና በግራ ቀኙ በኩል የቀረቡትን ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ ውሉ የተቋረጠው በሥራ ተቋራጩ/አመልካች/ ጥፋት ምክንያት በመሆኑ አሠሪው /ተጠሪ/ ሥራውን በሌላ ሥራ ተቋራጭ ለማሠራት ያወጣውን ተጨማሪ ክፍያ የመክፈል ግዴታና ሀላፊነት አለበት፡፡ ሥራ ተቋራጩ/አመልካች/ ለሥራው መዘግየት ሊከፍል የሚገባውን የመቀጫ ገንዘብ የመክፈል ሀላፊነት ያለበት በመሆኑ አሠሪው/ተጠሪ/ በክሱ የገለፀውን የመቀጫ ገንዘብ አመልካች ለተጠሪ ይክፈል፡፡ አመልካች የቆፈራቸው ሁለት ጉድጓዶች በውሉ መሠረት ያልተሠራ መሆኑን አሠሪው/ተጠሪ/ የገለፀ በመሆኑ ሥራ ተቋራጩ በቅድሚያ ከወሰደው ገንዘብ እንዲቀናነስለት ያቀረበው ክስ ተገቢነት የለውም፡፡ ስለዚህ አመልካች ከተጠሪ የወሰደውን ቅድመ ክፍያ ሙሉ በሙሉ ለተጠሪ የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡ በአጠቃላይ አመልካች ብር 5,603,532.52/አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሶስት ሺህ አምስት መቶ ስላሣ ሁለት ብር ከሃያ ሁለት ሣንቲም/ ለተጠሪ ይክፈል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

4. አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች በአካባቢው በነበረው የፀጥታ ችግር ምክንያት ነው ቀሪዎቹን ጉድጓዶች ያልቆፈርኩት በማለት ያቀረበውን ክርክር ውድቅ አድርጎታል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ አመልካች በፅሑፍ ላቀረበው ጥያቄ ምላሽ አለመስጠቱና ሥራውን የሚከታተል መሀንዲስ ባለመመደቡ ለውሉ በአግባቡ አለመፈፀምና መቋረጥ አስተዋፅኦ እንዳበረከተ በመዘርዘር አመልካች ለመዘግየቱ ሊከፍል ከሚገባው የመቀጫ ገንዘብ ግማሹን ማለትም 528,520.47/አምስት መቶ ሃያ ስምንት ሺህ አምስት መቶ አስር ብር ከአርባ ሰባት ሣንቲም/ እንዲከፍል በማለት አሻሽሎ ወስኗል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የሁለት ጉድጓድ ዋጋ በውሉ መሠረት ለአመልካች የመክፈል ግዴታ አለበት በማለትም ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ሥራውን ለሌላ የሥራ ተቋራጭ ሲሰጥ የተጠየቀውን የዋጋ ብልጫ ማለት ብር 2,708,219 አመልካች ሙሉ በሙሉ ሊከፍል ይገባዋል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

5. አመልካች ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ለውሉ በአግባቡ አለመፈፀም የአመልካች ጥፋት ብቻ ሣይሆን የተጠሪም ጥፋትና አስተዋፅኦ እንዳለበት በማረጋገጥ የመቀጫው ገንዘብ በግማሽ እንዲቀነስ ከወሰነ በኋላ ተጠሪ ለሌላ ተቋራጭ ሥራውን ሲሰጥ ተጠይቄአለሁ የሚለውን አብላጫ የሥራ ዋጋ ሙሉ በሙሉ አመልካች እንዲሸፍን መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ተጠሪ ከሌላ የሥራ ተቋራጭ ጋር ውል መዋዋሉ ብቻውን ሥራውን ለማሠራት ተጨማሪ ገንዘብ የተጠየቀና የከፈለ መሆኑን የሚያስረዳ አይደለም፡፡ በውሉ መሠረት የመቀጫ ገንዘብ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ከተወሰነ በኋላ በውሉ አለመፈፀም ምክንያት ተጨማሪ የጉዳት ካሣ አመልካች እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ መሠረት የለውም፡፡ አመልካች በሥራ ውሉ መሠረት የተወሰኑ ጉድጓዶችን ቆፍሮ አስረክቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካች ምንም አይነት ሥራ እንዳልተሠራ አድርጎ በማስላት ያቀረበውን የካሣ ጥያቄ በመቀበልና አመልካች የሠራውን ሥራ ሣያቀናንስ ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ጥቅምት 5 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልክቷል፡፡



www.chilot.me

ተጠሪ በበኩሉ ጥር 19 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ በሥራው መዘግየት የሚከፈለው የመቀጫ ገንዘብ በሥራ ውሉ ላይ በግልፅ የተወሰነና ተጠሪ ውሉ ባለመፈፀሙ ለደረሰበት እርግጠኛ ጉዳት ከሚጠይቀው ገንዘብ የተለየ ነው፡፡ አመልካች የውል ግዴታውን ባለመፈፀሙ የተቋረጠው የቀሪ ጉድጓድ ሥራ ሌላ ተጫራች እንዲያጠናቅቀው ተጠሪ የሰጠው አመልካች ጋር በተደረገው ውል ሣይሰሩ ለቀሩት 7/ሰባት/ ጉድጓዶች ብቻ ነው፡፡ በአመልካች የተሠሩት በሁለተኛው ጨረታ አልተካተቱም በመሆኑም አመልካች ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሠራሁትን ሥራ ግምት ውስጥ ሣያስገባ ካሣ እንዲከፍል ወስኖብኛል በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተገቢነት የሌለው ነው፡፡ አመልካች መቀጫው ከተቀነሰ ጉዳቱንም እኔ ብቻ እንድከፍል መወሰኑ ስህተት ነው በማለት ያቀረቡት አቤቱታ የፍርድ ቤቱ ሥልጣንን ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የካቲት 4 ቀን 2003 ዓ/ም በተፃፈ የመልስ መልስ የዋጋ ልዩነት የታየው በወቅቱ ባለው የዋጋ ንረት ምክንያት በመሆኑ አመልካች ተጠያቂ ሊሆን አይገባውም፡፡ የዋጋ ልዩነቱን አመልካች ይክፈል እንኳን ቢባል ተጠሪ ለውሉ አለመፈፀም አስተዋፅኦ ያለው መሆኑን ይግባኝ ሰሚው ችሎት ያረጋገጠ በመሆኑ እንደሀላፊነቱ መጠን ኪሣራው ሊቀነስ ይገባዋል በማለት ተከራክሯል፡፡

6. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ የቀሪዎቹን ሰባት የውሃ ጉድጓዶች ሥራ ለሌላ የሥራ ተቋራጭ በጨረታ አወዳድሮ ሲሰጥ የተጠየቀውን ተጨማሪ ገንዘብ አመልካች ሙሉ በሙሉ መሸፈን አለበት በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከላይ የያዝነውን ጭብጥ በአግባቡ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካችና ተጠሪ ህዳር 15 ቀን 1999 ዓ.ም አድርገውት የነበረውን የውሃ ጉድጓድ ሥራ ውል አፈፃፀም ለማስረዳት ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር ይግባኝ ሰሚው ችሎት በፍሬ ጉዳይ ደረጃ የደረሰባቸውን መደምደሚያዎችና አመልካችና ተጠሪ በሰበር ደረጃ የማይካካዱባቸውን ነጥቦች በዝርዝር ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

6.1 የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረግኩትን የሥራ ውል በአግባቡ ያልፈፀምኩት በአካባቢው የፀጥታ ችግር የነበረ በመሆኑና ተጠሪ በውሉ መሠረት ተቆጣጣሪ መሀንዲስ ባለመመደቡ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች ለውሉ መዘግየትም ሆነ ቀሪው የውሉ ክፍል አለመፈፀም ምንም አይነት ተጠያቂነት ስለሌለብኝ የመቀጫ ገንዘብም ሆነ ኪሣራ ለተጠሪ የመክፈል ሀላፊነት የለብኝም በማለት ያቀረበውን ክርክር ሙሉ በሙሉ አልተቀበለውም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ለሥራ ውሉ አፈፃፀም መዘግየትና መቋረጥ የአመልካች ጥፋትና አስተዋፅኦ ያለበት መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣኑን በመጠቀም እንዳረጋገጠ በውሣኔው በግልፅ አስፍሮታል፡፡ በሌላ በኩል ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሥራ ውሉ በአግባቡ አለመፈፀምና ለውሉ መቋረጥ አመልካች ብቻ ሣይሆን በተጠሪ በኩል የተፈፀመ ጥፋትና አስተዋፅኦ ያለ መሆኑን በተለይም አመልካች በሥራ ውሉ መሠረት ተቆጣጣሪ መሃንዲስ እንዲመድብለት በተደጋጋሚ በፅሑፍ ላቀረበለት ጥያቄ ተጠሪ መልስ ያልሰጠ መሆኑን በማስረጃ እንዳረጋገጠ በውሣኔው ገልፆል፡፡ በሌላ አገላለፅ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተደርጎ የነበረው የውሀ ጉድጓድ ሥራ ውል አፈፃፀም ለመዘግየቱም ሆነ ለውሉ መቋረጥ አመልካችና ተጠሪ የየበኩላቸውን አስተዋፅኦ ያበረከቱ መሆኑን በግራ ቀኙ የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ በመመዘን በውሣኔው አረጋግጧል፡፡ በዚህ ምክንያት ለውሉ አፈፃፀም መዘግየት በሥራ ውሉ መክፈል የሚገባውን



www.chilot.me

የመቀጫ ገንዘብ ሙሉውን ሳይሆን ግማሹን /ሃምሣ ፐርሰንቱን/ ብቻ የመክፈል ግዴታና ሀላፊነት አለበት በማለት የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ ብር 1,057,070.93 የመቀጫ ገንዘብ ይክፈል በማለት የሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል አመልካች ግማሹን ብቻ ማለትም ብር 528,510.47 የመቀጫ ገንዘብ ለተጠሪ የመክፈል ግዴታና ሀላፊነት አለበት በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የሚከራከረው ለውሉ አለመፈፀምና መዘግየት የተጠሪ ጥፋትና አስተዋፅኦ እንዳለበት በፍሬ ጉዳይ ደረጃ ከተረጋገጠ፣ ውጤቱ የመቀጫ ገንዘብ በመቀነስ ብቻ የሚወሰን አይደለም በማለት ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ሥልጣኑ የዳኞች በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የመቀጫውን ገንዘብ በመቀነስ ብቻ መወሰኑ ተገቢ ነው የሚል መከራከሪያ አቅርቧል፡፡ በእኛ በኩል አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበትን ይህንን መሠረታዊ ነጥብ የፍታብሔር ህጉ የመንግስት ሥራዎችን በተቋራጭ ስለማሥራት የተደነገጉትን ልዩ የህግ ድንጋጌዎችና ሌሎች አግባብነት ካላቸው የህግ ማዕቀፎች መሠረት በማድረግ መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አንድን ሥራ ለሥራ ተቋራጭ የሰጠ የመንግስት መሥሪያ ቤት በራሱ ጥፋት ጉዳት አድርሶ እንደሆነ ወይም ተቋራጩ ውሉን ለጊዜው እንዳይፈፅም አግዶት እንደሆነ የሥራ ተቋራጩ ኪሣራ የማግኘት መብት ያለው መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3259 ንዑስ አንቀፅ 2 ይደነግጋል፡፡ ከሁሉም በላይ የሥራው አሠሪ የሆነው የመንግስት መሥሪያ ቤት ጥፋት ወይም የመብት መተላለፍ ባያደርግም አድራጎቱ የሥራ ተቋራጩን ሥራ መደበኛ አፈፃፀም ከባድ ያደረገበት እንደሆነ ለሥራ ተቋራጩ ኪሣራ የመክፈል ሀላፊነት እንዳለበት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3259 ንዑስ አንቀፅ 3 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ በሥራ ውሉ መሠረት ሥራውን የሚከታተል መሀንዲስ ባለመመደቡና አመልካች በፅሑፍ ለጠየቃቸው ጥያቄዎች ወቅታዊ ምላሽ ባለመስጠቱ ለሥራ ውሉ መዘግየትና ለውሉ አለመፈፀም የበኩሉን አስተዋፅኦ እንዳበረከተ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ ህጋዊ ዉጤትም በመቀጫ ገንዘብ ብቻ የሚወሰን እንዳልሆነና ተጠሪ ለአመልካች ካሣ የመክፈል ሀላፊነት ያለበት መሆኑን ከላይ የተጠቀሱትን ልዩ የህግ ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 85295 በተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ተጠሪ ለውሉ አፈፃፀም መዘግየትና ለውሉ መቋረጠ የበኩሉን አስተዋፅኦ ያበረከተ ስለሆነ ኪሣራ ወይም ካሣ ሊከፍለኝ ይገባል የሚል የዳኝነት ጥያቄ አላቀረበም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በተጠሪ በኩል ተፈፅሟል የሚላቸውን ጥፋቶችና ጉድለቶች በመዘርዘር ተጠሪ ላቀረበው የኪሣራ ጥያቄ ሀላፊ ልሆን አይገባኝም በማለት የተከራከረ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤትና ከይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሣኔ ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡

ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ችሎት ለውሉ በአግባቡ አለመፈፀምና መዘግየት የተጠሪ ጥፋትና አስተዋፅኦ አለበት በማለት በፍሬ ጉዳይ ደረጃ ከደመደመ በኋላ የዚህን መደምደሚያውን የአመልካችን የመከላከያ መልስ ህጋዊ ውጤት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3259 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀፅ 3 ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ አለመመዘኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

አመልካች የሥራ ውሉ በመዘግየቱና ባለመፈፀሙ የመቀጫ ገንዘብ እንዲከፍል ተወስኖብኛል፡፡ ይህ ከሆነ ለተጠሪ ኪሣራ የመክፈል ሀላፊነት የለብኝም በማለት የተከራከረ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የመቀጫ ገንዘብ እንዲከፍል መወሰኑ ውሉ ባለመፈፀሙ ተጠሪ የደረሰበትን ኪሣራ ከመክፈል ነፃ አያደርገውም በማለት ተከራክሯል፡፡ ይህም የአመልካችና የተጠሪ ክርክር የመንግስት ሥራዎችን ለመሥራት ስለመቋረጥ ከተደነገጉት ልዩ ድንጋጌዎችን አንፃርና መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በተለይም የአመልካች ክርክር ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 3261

ድንጋጌዎችን አንፃር መሠረት በማድረግ መታየት ያለበት ሲሆን ከሥራ ውጭ የተደረገው ሥራ ተቀራጭ ሥራው ለአዲስ ተቋራጭ በጨረታ የተሰጠ ሲሆን አዲሱ የሥራ ውል በመሥሪያ ቤቱ የሚያስከትለውን ከባድ የሆነውን ወጭ መቻል እንዳለበት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3261 ንዑስ አንቀፅ 2 በግልፅና አስገዳጅነት ባለው ሁኔታ ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም አመልካች ለሥራው መዘግየትና አለመፈፀም መቀጫ እንድከፍል የተወሰነ ስለሆነ ቀሪው ሥራው ለሌላ ሥራ ተቋራጭ ሲሰጥ ተጠሪ የደረሰበትን ኪሣራ የመክፈል ግዴታ ያለብኝም በማለት ያቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀውን ድንጋጌ ያላገናዘብ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

ከላይ በዝርዝር እንደገለፅነው ተጠሪ የሥራ ውሉ ለመዘግየቱና ውሉ በአግባቡ ላለመፈፀሙ ላደረገው አስተዋፅኦ የመቀጫ ገንዘብ በመቀነስ ብቻ የሚወሰን ሣይሆን ተጠሪን ተጨማሪ ሀላፊነት የሚያስከትልበት ስለመሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3259 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀፅ 3 ተደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል ለውሉ አለመፈፀምና መዘግየት ጥፋትና አስተዋፅኦ ያበረከተ መሆኑ የተረጋገጠበት አመልካች ተጠሪ ሥራውን ለሌላ ተቋራጭ ሲሰጥ የወጣውን ወጭ የመጋራት ወይም መሸፈን ግዴታ እንዳለበት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3261 ንዑስ አንቀፅ 2 ተደንግጓል፡፡ አመልካች ተጠሪ ሥራውን ለሌላ ሥራ ተቋራጭ ሲሰጥ የደረሰበትን ኪሣራ ሙሉ በሙሉ እንዲሸፍን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3261 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የሚገደደው ለሥራ ውሉ መዘግየትና አለመፈፀም ተጠሪ ያበረከተው አስተዋፅኦ አለመኖሩ ሲረጋገጥ እንደሆነ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3259 ንዑስ አንቀፅ 3 ድንጋጌ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3261 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ የጣምራ ይዘት ተፈፃሚነትና ውጤትን በማገንዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች ለውሉ አለመፈፀምና መዘግየት ብቸኛ ተጠያቂና ሀላፊ አለመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣኑን በመጠቀም ካረጋገጠ በኂላ በውሉ አለመፈፀም ምክንያት በተጠሪ ላይ የደረሰውን ኪሣራ ሙሉ በሙሉ አመልካች እንዲሸፍን የተሰጠው ውሣኔ ከላይ የተገለፁትን የህግ ድንጋጌዎች ይዘትና ድንጋጌዎቹ በአንድ ላይ ሲፈፀሙ የሚያስከትሉትን ውጤት ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል አመልካች ሊከፍል የሚገባው ተጠሪ ቀሪውን ሥራ ለሌላ ተቋራጭ ሲሰጥ የደረሰበትን ኪሣራ ማለትም ብር 2,708,219/ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ ስምንት ሺ ሁለት መቶ አስራ ዘጠኝ ብር / ሣይሆን የዚህን ግማሽ/ሀምሣ ፐርሰንት / በሌላ አነጋገር ብር 1,354,109.50 /አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሃምሣ አራት ሺ አንድ መቶ ዘጠኝ ብር ከሀምሣ ሣንቲም / ብቻ ነው በማለት ወስነናል፡፡

6.2 አመልካች የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ኪሣራው ለተጠሪ እንዲከፈል የወሰነው አመልካች ምንም አይነት ሥራ እንዳልሠራ በመቁጠርና አመልካች ሠርቶ ለተጠሪ ያሥረከባቸውን የተወሰኑ ሥራዎች ከግንዛቤ ውስጥ ሣያስገባና ሒሳቡን ሣያቀናንስ ነው በማለት ክርክር በሰበር አቤቱታው አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ለዚህ ሰበር ችሎት ጥር 19 ቀን 2003 ዓ.ም በፅሑፍ በሰጠው መልስ ጨረታ ወጥቶ ለሌላ የሥራ ተቋራጭ የተሰጡትን የውሀ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ መጠን በተመለከተ በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ካቀረበው ክርክር የተለየ መልሥ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ ለሰበር ችሎት በሰጠው መልስ በተራ ቁጥር 3 ላይ ለሌላ የሥራ ተቀራጭ በጨረታ የተሰጠው የሰባት /7/ ውሀ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ መሆኑንና ይህም በአመልካች የቁፋሮ ሥራ የተሠራላቸውን የውሃ ጉድጓዶች እንደማይጨምር በመግለፅ ተከራክሯል፡፡

ይህም የተጠሪ ክርክር አመልካች በሥራ ውሉ መሠረት ጥልቀታቸው ሁለት መቶ ሃምሣ ሜትር የሆነ የሶስት የውሀ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ ሠርቻለሁ በማለት አመልካች ከሥር ጀምሮ ያቀረበውን ክርክር በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 235 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት እንዳመነ የሚያስቆጥረው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች ሁለት የውሀ ጉድጓድ በመቆፈሩ እንጅ ሶስት የውሀ ጉድጓድ በውሉ መሠረት የቆፈረ መሆኑን አላስረዳም በሚል ምክንያት ተጠሪ ለአመልካች ሁለት የውሀ ጉድጓድ የቆፈረበትን ዋጋ ይክፈል በማለት የሰጠውን ውሣኔ ተጠሪ በሰበር ካቀረበው ክርክር አንፃር በመመዘንና በማሻሻል ተጠሪ አመልካች ሶስት የውሃ ጉድጓድ የቆፈረበትን ዋጋ በውሉ መሠረት የመክፈል ሀላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

6.3 በሥር ፍርድ ቤት በይግባኝና በሰበር በተሰጠው ውሣኔ መሠረት አመልካች ለተጠሪ ሊመልስ የሚገባው በቅድመ ክፍያ የወሰደውን ገንዘብ ያለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በሰጠው ውሣኔና በዚህ ሰበር ችሎት በተሰጠው ውሣኔ መሠረት አመልካች ለተጠሪ መክፈል የሚገባው የመቀጫ ገንዘብና ኪሣራ /ካሣ/ እንዳለ በውሣኔው ተገልፆል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ አመልካች ለሠራው የሶስት ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ በውሉ መሠረት ተገቢውን ዋጋ እንዲከፍል ይህ ሰበር ችሎት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በውሣኔው አመልካች ከተጠሪ እንደዚሁም ተጠሪ ከአመልካች የሚጠይቁት የገንዘብ ዕዳ ያለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ዕዳውን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 236 መሠረት በማቻቻል ተራፊ ገንዘብ የሚጠይቀውና በዚህ ፍርድ የፍርድ ባለመብት የሚሆነውን ወገን ለመለየት ፍርዱ ለአፈፃፀም ምቹ በሚሆንበት መንገድ ለመስጠት ይቻል ዘንድ ጉዳዩን በዝርዝር ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ሀ/ አመልካች ለተጠሪ መክፈል ያለበት ገንዘብ</u>

- አመልካች ከተጠሪ ብር 1,838,292.27 /አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰላሣ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና ሁለት ብር ከሃያ ሰባት ሣንቲም/ በቅድሚያ ክፍያ የወሰደ መሆኑን ያልካደና በማመን የተከራከረ በመሆኑ ይህንን ገንዘብ አመልካች ለተጠሪ የመመለስ ግዴታና ሀላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡
- አመልካች ለሥራ ውሉ መዘግየትና ለውሉ አለመፈፀም በከፊል ሀላፊነት ያለበት መሆኑን በማረጋገጥ ለተጠሪ ብር 528,520.47 /አምስት መቶ ሃያ ስምንት ሺህ አምስት መቶ አስር ብር ከአርባ ሰባት ሣንቲም/ ለተጠሪ እንዲከፍል ይግባኝ ሰሚው ችሎት በሰጠው ውሣኔ መሠረት የመክፈል ሀላፊነት አለበት፡፡
- ተጠሪ ለውሉ መዘግየትና አለመፈፀም የበኩሉን አስተዋፅኦ ያደረገ መሆኑ በፍሬ ጉዳይ ደረጃ ስለተረጋገጠ አመልካች በሥራ ውሉ መሠረት ያልሠራውን ቀሪ ሰባት የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ ተጠሪ ለሌላ ተቋራጭ ሲሰጥ ከደረሰበት ኪሣራ ግማሹን ብቻ አመልካች የመሸፈን ሀላፊነት እንዳለበት ይኸ ሰበር ችሎት የይግባኝ ሰሚውን ውሣኔ በማሻሻል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም አመልካች ብር 1,354,109.50/አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሃምሣ አራት ሺህ አንድ መቶ ዘጠኝ ብር ከሃምሣ ሣንቲም/ ለተጠሪ ካሣ ይክፈል በማለት ወስነናል፡፡ በአጠቃላይ አመልካች ብር 3,720,918.09 /ሶስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃያ ሺህ ዘጠኝ መቶ አሥራ ስምንት ብር ከዜሮ ዘጠኝ ሣንቲም/ የመክፈል ሀላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

ለ/ **ተጠሪ ለአመልካች የሚከፍለው ገንዘብ**

አመልካች ሶስት የውሃ ጉድጓዶችን በውሉ መሠረት የሠራ መሆኑን ተጠሪ በማረጋገጡ አመልካች የሶስት ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ ዋጋ ለአመልካች የመክፈል ሃላፊነት እንዳለበት በዚህ ችሎት በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ሶስቱን ጉድጓዶች ለሠራበት ተጠሪ በውሉ መሠረት ሊከፍለው የሚገባው ብር 2,776,728.22/ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ሰባት መቶ ሃያ ስምንት ብር ከሃያ ሁለት ሣንቲም/ እንደሆነ በሥር ፍርድ ቤት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ ዋጋው በውሉ መሠረት ተሰልቶ የቀረበ አይደለም የሚል ክርክር አላቀረበም፡፡

ስለሆነም ተጠሪ ከላይ መጠኑ የተገለፀውን ገንዘብ ለአመልካች የመክፈል ሃላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

በአጠቃላይ አመልካች ለተጠሪ ከሚከፍለው ብር 3,720,918.09 /ሶስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃያ ሺ ዘጠኝ መቶ አሥራ ስምንት ብር ከዜሮ ዘጠኝ ሣንቲም/ ውስጥ ተጠሪ ለአመልካች የሚከፍለው ብር 2,776,728.22 /ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ሰባት መቶ ሃያ ስምንት ብር ከሃያ ሁለት ሣንቲም/ ተቀንሶ ፣ /ተቻችሎ/ የሚቀረውን ብር 944,189.87/ዘጠኝ መቶ አርባ አራት ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ብር ከሰማኒያ ሰባት ሣንቲም/ አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ለአመልካች መክፈል ያለበት ገንዘብ አመልካች ለተጠሪ ከሚከፍለው ገንዘብ ላይ ከላይ በውሣኔው በተገለፀው መሠረት ከተቀናንሶ የቀረውን ብር 944,189.89 /ዘጠኝ መቶ አርባ አራት ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ብር ከሰማኒያ ሰባት ሣንቲም / አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኑ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ.መ.ቁ 62134
ሰኔ 28 ቀን **2003** ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች -** እነ ጠና ወ/ሰማያት - ከጠበቃ ሀይሉ አግዘው ጋር - ቀረቡ
**ተጠሪ -** ወ/ሮ አልማዝ አሰጋኸኝ - ከጠበቃ አሰፋ ንጉሴ ጋር - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በሽያጭ ምክንያት ተከፈለ የተባለ ገንዘብ ይመለስልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካቾች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- አመልካቾች የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል መመዘኛና መስፈርት ባላሟላ ሰነድ ቤት ሽያጭ ውል ተዋውለዋል በማለት ነሐሴ 20 ቀን 1997 ዓ/ም በተጻፈ ከተጠሪ ላይ ብር 80,000.00 (ሰማኒያ ሺህ ብር) መቀበላቸውን ፤ ይህ ረቂቅ ውል እንጂ የሚፀና ውል ባለመሆኑ ተጠሪ ያገኙት ቤት ወይም ጥቅም የሌለ መሆኑንና ገንዘቡንም ሊመልሱላቸው ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ገልጸው ያላግባብ የተወሰደባቸውን ገንዘብ ከወሰዱበት ጊዜ ጀምሮ ከታሰበው ብር 24,300.00 ሕጋዊ ወለድ ጋር በድምሩ ብር 104,300.00 (አንድ መቶ አራት ሺህ ሶስት መቶ ብር) ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካቾች በበኩላቸው ተጠሪ በጉዳዩ ላይ ክስ አቅርበው የመጨረሻ ፍርድ በተሰጠበት ጉዳይ ላይ በድጋሚ ክስ ለማቅረብ የማይችሉ መሆኑን ፤ ጉዳዩም ያላግባብ መበልፀግ ነው የሚል በመሆኑ በሁለት አመት ይርጋ ቀሪ ሊሆን እንደሚገባ ገልፀው በእነዚህ የመጀመሪያ ደረጃ መቃሚያ ነጥቦች ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም አመልካቾች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሱትን የይርጋ ጊዜ የተጠሪ ዳኝነት ጥያቄ ያላግባብ የተወሰደ ገንዘብ ይመለስልኝ የሚል በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143(1) መሰረት የሚገዛ ነው በማለት በሁለት አመት የይርጋ ጊዜ ቀሪ ነው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ጉዳዩ በሁለት አመት የይርጋ ጊዜ የማይታገድ መሆኑን በመግለፅ በዚህ ረገድ በስር ፍርድ ቤት የተያዘውን ምክንያት በመሻር ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የአስር አመት የይርጋ ጊዜ ነው በማለትና ክሱ የቀረበውም ይኸው ጊዜ ሳይልፍ መሆኑን አረጋግጦ እንዲሁም አከራካሪውን ገንዘብ አመልካቾች ከተጠሪ መቀበላቸው በፍሬ ነገር ደረጃ በስር ፍርድ ቤት መረጋገጡን ጠቅሶ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሮ ብር 80,000.00 (ሰማኒያ ሺህ ብር) ከግንቦት 24 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር አመልካቾች ለተጠሪ እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ



www.chilot.me

ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካቾች ጥቅምት 29 ቀን 2003 ዓ/ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የይርጋው ጊዜ ወደ አስር አመት ተብሎ መተርጎሙም ሆነ ተጠሪ የቤት ሽያጭ ስለመኖሩ አለመኖሩ በነበረው ክርክር አጠቃልለው ማቅረብ ይችሉ የነበረውን ክርክር ነጥለው በኋላ አቅርበው ተቀባይነት ማግኘታቸው ክስን ነጣጥሎ ማቅረብ የማይቻል መሆኑን የሚደነግገውን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 216 ድንጋጌን ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም ተጠሪ ቀደም ሲል ክስ አቅርቦ ባስወሰነበት መዝገብ አጠቃልለው ማቅረብ የነበረባቸውን ነጣጥለው አቅርበዋል በማለት አመልካቾች ያቀረቡት ተቃውሞ መታለፉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ጭብጥ፡- አመልካቾች ለተጠሪ ገንዘቡን እንዲመልሱ ተብሎ የተወሰነው በሕጉ ተቀባይነት ያለውን ማስረጃ መሰረት ባደረገ መንገድ ነው? ወይስ አይደለም? የሚል ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአመልካቾች ላይ መጀመሪያ ክስ የመሰረቱት ውል እንዲፈርስና ገንዘባቸው ተመልሶላቸው ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ የሚል ሲሆን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሉ ረቂቅ ስለሆነ የክስ ምክንያት የለውም በማለት መዝገቡን መዝጋቱን ፣ ለአሁኑ ክርክር መሰረት የሆነውን ክስ ተጠሪ የመሰረቱት በረቂቅ ውሉ መሰረት የተከፈለ ገንዘብ እንዲመለስላቸው መሆኑን ፣ ቤቱ ከአመልካቾች እጅ ያልወጣና በተጠሪ እጅ ያልገባ መሆኑን ነው፡፡

በመሆኑም ተጠሪ አመልካቾች ቤት ሽጠውልኝ ብር 80,000.00 ከፍዬአለሁ ፣ ውል ይፍረስልኝ፤ወደ ነበርንበት እንድንመለስ ይደረግ የሚል ጥያቄ አቅርበውም ውሉ ረቂቅ በመሆኑ የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሰጠቱ ምክንያት ሁለተኛ ክስ ሊያቀርቡ የቻሉት በፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር በሕግ ፊት የሚጸና ውል የለም (ረቂቅ ነው) ስለተባለ ያላግባብ የተከፈለ ገንዘብ ሊመለስልኝ ይገባል በማለት መሆኑን ፣ በግራ ቀኙ መካከል የቤት ሽያጭ ውል አለ የለም የሚለው ክርክርም በፍርድ ቤት ታይቶ ሕጋዊ የሆነ የቤት ሽያጭ ውል የሌለ መሆኑ መረጋገጡን ከክርክሩ ሂደት በግልጽ ተረድተናል፡፡ ተጠሪ ለአሁኑ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን ጉዳይ ያቀረቡትም የቤት ሽያጭ ውል የለም ተብሎ ውሳኔ ከተሰጠ በሁዋላ ሲሆን አመልካቾች ገንዘቡን ስለመቀበላቸው በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካቾችን ለክሱ ኃላፊ ያደረገው ገንዘቡን ከተጠሪ ስለመቀበላቸው ተጠሪ በተገቢው ማስረጃ አስረድተዋል ፣ አመልካቾች ግን አላስተባበሉም በሚል ምክንያት ነው፡፡ እንግዲህ ከላይ የተመለከቱት ነጥቦች በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጡት ሲሆን አመልካቾች የስር ፍርድ ቤት የስነ ሥርዓት ግድፈት ፈጽሟል በማለት የሚያቀርቡት አንዱ ነጥብ ተጠሪ ሕጋዊ ያልሆነ የቤት ሽያጭ ውል ይፍረስልኝ ፣ ወደ ነበርንበት እንድንመለስ ይወሰንልኝ በማለት ክስ ሲያቀርቡ ገንዘቡን ያላግባብ ለአመልካቾች የከፈሉ መሆኑን ገልጸው ገንዘቡ እንዲመለስላቸው በአማራጭ ዳኝነት መጠየቅ ሲገባቸው እና ተጠሪ ቀደም ሲል በተመሳሳይ ጉዳይ ክስ ሲመሰርቱ ይህንኑ ክስ አጠቃልለው ሊከሱ ሲገባ ቀንሰው ባስቀሩት ገንዘብ ላይ ድጋሚ ክስ እንዳይመሰርቱ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 216 ይከለክላቸዋል



www.chilot.me

የሚል መቃወሚያ አቅርበው መታለፉን ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ በተያዘው መሰረት የተጠሪ ክስ በተጠቀሰው የሥነ ሥርዓት ድንጋጌ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ወይ? የሚለውን ጭብጥ ፍ/ቤቱ መርምሯል፡፡ ለዚህ ይረዳ ዘንድ ድንጋጌውን መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 216 በአጠቃላይ ስለ ክስ አቀራረብና አገላለፅ የሚመለከት ድንጋጌ ነው፡፡ በተለይ ከተያዘው ጉዳይ ጋር አግባብነት ያለው የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር 2 እና 3 ነው፡፡ የንዑስ ቁጥር 2 የመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር አንድ ከሳሽ ክስ ሲያቀርብ ለክሱ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች በሙሉ አጠቃሎ ማቅረብ እንደሚገባ የሚናገር ሲሆን ንዑስ ቁጥር 3 ደግሞ አንድ ከሳሽ ሊከስበት ሲችል ሆነ ብሎ በመቀነስ ባስቀረው ሃብት ምክንያት እንደገና ሌላ ክስ ለማቅረብ እንደማይፈቀድለት ይገልፃል፡፡ በመሆኑም ከሳሽ ክስ ሲያቀርብ ክሱን ለማቅረብ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች በሙሉ አጠቃሎ ማቅረብ የሚጠበቅበት ሲሆን ማቅረብ ሲችል ሆነ ብሎ **ቀንሶ ባስቀረው** ሃብት ላይ ግን ድጋሚ ክስ ሊያቀርብ እንደማይችል ከድንጋጌዎቹ መረዳት ይቻላል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣ የቤት ሽያጭ ውልን አስመልክቶ ክርክሩ የቀረበበት አግባብ በተጠሪ በኩል የቀረበው የቤት ሽያጭ ውል ይፍረስልኝ ፣ ወደነበርንበት እንድንመለስ ይደረግልኝ የሚል ክስ በመቅረቡ በመሆኑና በሕጉ አግባብ የተደረገ የቤት ሽያጭ ውል የለም ፣ ዉሉ ረቂቅ ስለሆነ የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድምዳሜ ላይ የተደረሰ በመሆኑ ተጠሪ በሽያጩ ምክንያት ለአመልካቾች የሠጡትን ገንዘብ ሊመለስልኝ ይገባል በማለት ጥያቄ ከማቅረብና በማናቸውም ማስረጃ ከማስረዳት የማይከለክል መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1808(2) ፣ 1815 ፣ 2001 እስከ 2019 እንዲሁም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2162 እና 2164 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ በመሆኑ በክስ አቀራረብ ሥርዓት ላይ መሰረታዊ የሆነ የሥነ ስርዓት ግድፈት ተፈጽሟል ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ ተጠሪ ቀድሞ ከመሰረቱት የክስ ይዘትና ከጠየቁት ዳኝነት አንፃር ውሉ ረቂቅ በመሆኑ የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከተሰጠው ውሳኔ አኳያ ሲታይ የሽያጭ ገንዘቡን ሆነ ብለው ትተዋል ፣ ወይም በክሱ ሊጠቃለል የሚችል ሀብት ቀንሰው አስቀርተው ሌላ ጊዜ ክስ መስርተዋል ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 62146

ሐምሌ 12 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሪት ፍሬወይኒ ቴዎድሮስ የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** ተርካንፌ ፕሮሞሽን የማስታወቂያ ስራ ድርጅት - ጠበቃ ነፃነት ጌታሁን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የውል ይፈፅምልኝ ጥያቄን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት ሚያዚያ 07 ቀን 2002 ዓ/ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ተጠሪ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የደቡብ ክልል ሁሉም ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች የሚሳተፉበትን የደቡብ ሚስስ ቱሪዝም የቁንጅና ውድድር በኮንሶ ልዩ ወረዳ ካራት ከተማ መስከረም 09 ቀን 2001 ዓ/ም እንደሚያዘጋጅና ተወዳዳሪዎች እንዲመዘገቡ ባወጣው ማስታወቂያ መሰረት መመዝገባቸውን ፣ በማስታወቂያውም ላይ በውድድሩ አሸናፊ ለሆነች ወጣት በክልሉ ርዕሰ ከተማ ሐዋሳ መኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ፣ በክልሉ በሚገኙ ታላላቅ ኮሌጆች ውስጥ ነፃ የትምህርት እድል እና የብር 5000.00(አምስት ሺህ) የገንዘብ ስጦታ ለመስጠት አመልካች በሚኖሩበት የዳውሮ ዞን በፋክስ የማስታወቂያ ደብዳቤ ቃል መግባቱን ፣ በውድድሩም አመልካች ተወዳድረው አንደኛ በመውጣት የደቡብ ሚስስ ቱሪዝም ማዕረግ ያገኙ መሆኑን ፣ ተጠሪ በገባው ቃል መሰረት በኮሌጅ የነፃ የትምህርት እድሉን እና ብር 5000.00 ለአመልካች የሰጣቸውና አመልካችም የተቀበሉ ሁኖ የቤት መስሪያ ቦታ ግን በገባው ቃል መሰረት ያልፈፀመላቸው መሆኑን ዘርዝረው ተጠሪ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እንዲሰጣቸው ፣ ቦታውን መስጠት የማይችል ከሆነ ደግሞ በወቅቱ በነበረው የከተማው የሊዝ ዋጋ ተመን መሰረት የሁለት መቶ ካሬ ሜትር ዋጋ ብር 360,000.00 (ሶስት መቶ ስልሻ ሺህ ብር) እንዲከፍል ይወስንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም በማስታወቂያው ላይ የተገለፀው እድል የሚለው ቃል የሚያመላክተው የሥጦታ ተስፋ ቃል እንጂ ሽልማት ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥ 2435 መሰረት ግዴታ የሚጥል አይደለም ፣ የስጦታ ተስፋ ቃል በሕግ ፊት ተቀባይነት የሌለው ከመሆኑም በላይ ፎርማሊቲውንም የጠበቀ አይደለም ፣ የውሉ ጉዳዩ በግልፅ ያልተመለከተና የሚቻል ውል ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1714 መሰረት ሕጋዊነት የለውም ፣ እንዲሁም መሬት የመንግስትና የሕዝብ በመሆኑ ልገደድበት አይገባም በማለት ክሱ ውድቅ

ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ማስታወቂያው የሚያሳየው የስጦታ ተስፋ ቃል መሆኑን ፤ ይህ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2435 መሰረት ግዴታ የሚጥል አለመሆኑን ፤ የውሉ ጉዳይም በሕዝብና በመንግስት መሬት ላይ የተደረገ በመሆኑ ተጠሪ ሊፈፀመው የሚችለው አይደለም ፤ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1689(1) ለጉዳዩ አግባብነት የለውም  የሚሉትን ምክንያቶችን በመያዝ የአመልካችን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ በማስታወቂያው ላይ ከገለፃቸው ሽልማቶች መካከል ሁለቱን ፈጽሞ እያለ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ለመሸለም ቃል አልገባሁም በማለት ያቀረበው ክርክር በበታች ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ማግኘቱ የውል አተረጓጐም ደንቦችን ስለውል አፈፃጸም የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በይዘቱ በስር ፍርድ ቤት ከአቀረበው መከራከሪያ ነጥብ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ክርክር ያቀረበ ሲሆን አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች ያቀረቡት ክስ ውድቅ መደረጉ ባግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ነው፡፡

ከላይ እንደተገለፀለው አመልካች በተጠሪ በተደረገው ጥሪ መሰረት ተወዳድረው የደቡብ ሚስስ ቱሪዝም ማዕረግ ማግኘታቸው ፤ በጥሪው ጊዜም ለአሸናፊ ሊሰጡ የሚገባቸው ሽልማቶች መገልፃቸው የተረጋገጠ ሲሆን ከሽልማቶች መካከል በክልሉ በሚገኙ ታላላቅ ኮሌጆች መካከል የነጻ ትምህርት እድልና ብር 5000.00 (አምስት ሺህ ብር) ተጠሪ ለአመልካች የፈጸመላቸው ሽልማቶች መሆናቸው ተረጋግጠዋል፡፡ አሁን ግራ ቀኙን እያከራከሩ ያለው የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ከሽልማቶች መካከል የሚገኝ መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡ ተጠሪ በዚህ ረገድ አጥብቆ የሚከራከረው በማስታወቂያው ላይ "በሐዋሳ ከተማ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እና በክልል የሚገኙት ታላላቅ ኮሌጆች ውስጥ ነጻ የትምህርት እድል---"በሚል ከተቀመጠው አረፍተ ነገር ውስጥ እድል የሚለው ቃል የስጦታ የተስፋ ቃል እንጂ ሽልማት አይደለም ፤ የስጦታ የተስፋ ቃል ደግሞ አስገዳጅ ግዴታ የማይጥል ነው በማለት ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ የተጠሪን ክርክር ተቀብለዋል፡፡ ይህን የስር ፍርድ ቤቶችን ድምዳሜ በፍ/ሕ/ቁጥር 2427 ስር ከተመለከተው የስጦታ ትርጓሜ አንፃር ማየቱ ተገቢ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ ስጦታ ማለት አንድ ወገን ተዋዋይ ማለት ሰጪ ተቀባይ ተብሎ ለሚጠራው ለሌላ ሰው ችሮታ በማድረግ አሳብ ከንብረቶቹ አንዱን የሚለቅበት ወይም ግዴታ የሚገባበት ውል ስለመሆኑ የተመለከተ ሲሆን በተቀባዩ በኩል የሚገባ ግዴታ የለም፡፡ በሌላ አነጋገር ስጦታ በስጦታ ሰጪ ለስጦታ ተቀባዩ በችሮታ(gratuitously) የሚደረግ ውል ነው፡፡ አመልካች እና ተጠሪ ያደረጉት ውል ግን አመልካች የቁንጅና ውድድሩ አሸንፈው የደቡብ ሚስስ ቱሪዝም ማዕረግ ከአገኙ ሽልማቱን ተጠሪ የሚሰጣቸው መሆኑን የሚገልፅ  በመሆኑ የውሉ ጉዳይ ሲታይ አንዱ ተዋዋይ ለሌላኛው አንድ ነገር ለማድረግ ወይም ለመስጠት የተስማማበትና በሕጉ አግባብ የተቋቋመ መሆኑን የሚስገነዝብ ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ከመነሻው ጉዳዩ በስጦታ ውል የሚሸፈን

መሆን ያለመሆኑን ግራ ቀኙ ከአቋቋሙት ውል የግራ ቀኙን ግዴታ በመለየት ስጦታ መሆን ያለመሆኑን ሳይለዩ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2435 ድንጋጌን ለውሳኔአቸው ዋቢ ማድረጋቸው አግባብነት ያለውን ሕግ በመለየት ረገድ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈፀማቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሕግ ፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1689 ሲሆን በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ አንድ ድንጋጌ መሰረት የጠፋ እቃ ሳገኝ ወይም ሌላ ነገር ለፈጸመ ሰው ሽልማት ይሰጠዋል ተብሎ በተለጠፈ ማስታወቂያ ወይም በአደባባይ ሊታወቅ በሚችል ሌላ ዐይነት ማስታወቂያ ወጥቶ ቃል ከተሰጠ በኋላ የጠፋውን ዕቃ አግኝቶ ቢያመጣ ወይም እንዲፈጽም የተባለውን ስራ ፈጽሞ ቢገኝ ይህን ያደረገው ሰው የወጣውን ማስታወቂያ ሳይውቅ ቢቀርም የተሰጠውን የተስፋ ቃል እንደተቀበለ እንደሚቆጠር የተደነገገ ሲሆን በአንቀፁ ንዑስ ቁጥር ሁለት ደግሞ ቃል ሰጪውም በበኩሉ የሠጠውን የተስፋ ቃል የመፈጸም ግዴታ እንዳለበት በኃይለ ቃል ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ሌላ ነገር መፈፀም በሚል ከተቀመጠው ሐረግ መረዳት የሚቻለው የውድድር አሸናፊንም የሚያካተት መሆኑን ሲሆን ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ድንጋጌ ይኸው ድንጋጌ እንጂ የስጦታ ውልን በሚመለከት የተቀመጡት የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች አይደሉም፡፡

ሌላው የበታች ፍርድ ቤቶች ለውሳኔው መሰረት ያደረጉት የግራ ቀኙ ሐሳብን የሚመለከት ነው፡፡ በመሰረቱ በውል ውስጥ የተጠቀሱት ቃላትና ድንጋጌዎች ግልጽ ባልሆኑ ጊዜ ከፍ/ሕ/ቁጥር 1732 ፣ 1735-1738 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ስር በሰፈሩት ደንቦች መሰረት መተርጐም የተፈቀደ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያላቸው ደንቦች የፍ/ሕ/ቁጥር 1734 እና 1736 ሲሆኑ ተዋዋዮች ውላቸውን ከመዋዋላቸው አስቀድሞ ወይም ከተዋዋሉ በኋላ የነበሩበትን ሁኔታዎች ፣ የፈጸሙትን ተግባር በማመዛዘንና ሐሣባቸው ምን እንደነበር ለማወቅ መሞከር እና የውሎችን ቃሎች አንዱን ከአንዱ ጋር እያዛመዱ በመመልከት ለውሉ ጉዳይ አግባብ ያለውን ትርጉም በመስጠት አዎንታዊ ውጤት እንዲኖረው ማድረግ ተገቢ ስለመሆኑ ተጠቃሽ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች በተጠሪ በኩል የቀረበው የውል አቀባበል ማስታወቂያ በ19/12/2000 ዓ/ም የተጻፈ መሆኑን የገለፁ ሲሆን ተጠሪም ይህንኑ ደብዳቤ ስለመኖሩ ሳይክድ አጥብቆ የሚከራከረው በይዘቱና መንፈሱ ላይ ነው፡፡ ለክርክሩ መሰረት የሆነው የደብዳቤው ክፍል " **….አሸናፊ የሆነች ወጣት በክልሉ ርዕስ ከተማ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እና በክልሉ የሚገኙት ታላላቅ ኮሌጆች ውስጥ ነጻ የትምህርት እድል ሲኖራት የብር 5000.00 (አምስት ሺህ ብር) ገንዘብ ሽልማትም ታገኛለች**" በሚል የተቀመጠ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ በግልጽ ያሳያል፡፡ ከዚሁ የደብዳቤ ይዘት የነፃ ትምህርት እድልና የብር 5000.00 ሽልማት ለአመልካች በተጠሪ የተፈጸሙ ግዴታዎች ናቸው፡፡ ተጠሪ በደብዳቤው <u>….እድል ሲኖራት…</u> የሚለው ሐረግ አመልካች የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ሽልማት ይሰጣታል ወይም ታገኛለች የሚል ግልጽ የሆነ የተስፋ ቃል የለም ፣ ቃሉ መኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ልታገኝ የምትችልበት ሁኔታ መኖሩን ከሚያመላክት አልፎ በእርግጠኝነት ይህ ቦታ በሽልማት የሚሰጥ መሆኑን አያሳይም በማለት ተከራክሮ የስር ፍርድ ቤቶችንም ይሕንኑ የተጠሪን ክርክር ተቀብለዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከላይ እንደተመለከተው የውል ቃሎች ግልፅነት የሚጎድላቸው ከሆነ ሕጉ የአተረጎጎም ደንቦችን ያስቀመጠ ሲሆን ዳኞቹም ይህንኑ የአተረጎጎም ደንብ ሊከተሉ እንደሚገባ የግድ ይላል፡፡ ተጠሪ ለአመልካች የነጻ ትምህርቱን የሰጠውና ብር 5000.00 የከፈለው ከውሉ በሁዋላ ሲሆን ይህን ግራ ቀኙ ከውሉ በሁዋላ የፈጸሙትን ተግባር በማመዛዘንና ሐሣባቸውን ምን እንደነበር ለማወቅ ሲሞከር ተጠሪ ለአመልካች የመኖሪያ ቤት መስሪያ ለመሸለም የተስፋ ቃል መስጠቱን የሚገልፅ ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ለአመልካች የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ለመሸለም የገባው ግዴታ የለም በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1734 እና 1736 ድንጌጋዎችን መሰረት ያላደረገ

ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች በግራ ቀኙ መካከል የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ሽልማት ቃል አልተገባም ለማለት በምክንያትነት የያዙት ጉዳይ የውሉን ጉዳይና ሊፈፀም የሚችል መሆን ያለመሆኑን የሚመለከታው ነጥብ ነው፡፡ እንደሚታወቀው የውል ጉዳይ የሚያሳየው ተዋዋይ ወገኖች ለመፈጸም የገቡትን ግዴታ ሲሆን ይህ የሚቋቋመው ግዴታም አንዱ ተዋዋይ ለሌላኛው አንድ ነገር ለማድረግ ወይም ለመስጠት አለበለዚያ አንድን ማድረግ ይችል የነበረውን ከማድረግ ለመቆጠብ የሚስማማበት ነው፡፡ ይህ የተባለው ነገር እንዲደረግለት የሚፈልገው ሌላኛው ወገንም በበኩሉ ሌላ ግዴታ ይገባል፡፡ ይህ ግዴታ የሚያሳየው የውሉን ጉዳይ ሲሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1711 ላይ እንደተመለከተው ሕግ ከከለከለው በስተቀር ተዋዋዮቹ ሁሉ የሚዋዋሉትን ጉዳይ እንደመሰላቸው የመወሰን መብት አላቸው፡፡ የውል ጉዳይ አወሳሰን ከመዋዋል ነጻነት(Freedom of Contract)ጋር በእጅጉ በቀጥታ የተገናኘና ለተዋዋዮች ግላዊ ምርጫ የተተወ ስለመሆኑ የጠቅላላ ውል ፅንሰ ሐሳቦች የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ተዋዋይ ወገኖች የራሳቸውን መብትና ግዴታ ገልፀው የሚፈልጉትን ባግባቡ ለይተው ካመለከቱ በመካከላቸው በሕግ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ ውል ተመስርቷል ለማለት የሚቻል መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1715 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የሚሳየን ጉዳይ ሲሆን ግዴታዎቹ በትክክልና በሚበቃ ሁኔታ ሊገለፁ እንዲሚገባም የዚሁ ድንጋጌ ይዘት ያስረዳል፡፡ እንዲሁም የአንደኛው ተዋዋይ ወገን ግዴታ ሊፈፅሙት ፍጹም የማይቻልና የማይሞከር ጠባይ ያለው ሆኖ ከተገኘ ፈራሽ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1714 የተመለከተው ድንጋጌ የሚያስገነዝብ ሲሆን ይኸው ድንጋጌ ፍፁም የማይቻልና የማይሞከር ጠባይ ያለው ግዴታ ሲባል ተዋዋይ ወገን ብቻ ሳይሆን ማንም ሰው ሊፈፅመው የማይችለው ግዴታ መሆን እንዲሚኖርበት የሚያስረዳ ሲሆን ሊፈጸም እስከቻለ ድረስ አስቸጋሪነቱ ግዴታውን ሊያፈርሰው እንደማይችል የተጠቃሹ ድንጋጌ መንፈስና ይዘት በግልጽ ያሳያል፡፡ ውል ሕጋዊ ውጤት ያለው ተግባር እንደመሆኑ መጠንም እያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን በውሉ የተጣለበትን ግዴታ መፈፀም የሚገባው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1740 እስከ 1762 ድረስ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የበታች ፍርድ ቤቶች የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ በእርግጠኝነት በተጠሪ እጅ የሚገኝ መሆኑ ፣ ስፋቱ እና አቀመማጡ የተለየ እና የታወቀ መሆኑ በትክክል እና በግልጽ በሚበቃ መልኩ አልተመለከተም በማለት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1714(1)ን በመጥቀስና ተጠሪ የከተማ ቦታን በስጦታም ሆነ በሽልማት የመስጠት ስልጣንም ሆነ ችሎታ የለውም በማለት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1715 ድንጋጌ ጋር በማዛመድ ውሉ በሕግ ግዴታን የሚፈጥር አይደለም በማለት የደረሱበት ድምዳሜ ሲታይ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታዎች በከተሞች ለሰዎች የሚሰጡበትን ስርዓት ፤ የማዘጋጃ ቤትን ስልጣንና የሊዝ ሕጎችን ፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1711፣1713፣1714 እና 1715 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ ነው፡፡ መሬት የመንግስትና የሕዝብ መሆኑ በፌዴራልም ሆነ በክልል ሕግጋተ መንግስታት የተደነገገ ሲሆን በከተማ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታዎች ለሰዎች የሚሰጡበትና ስራው የሚያከናውነው የክፍሉ ማዘጋጃ ቤት መሆኑን ስራ ላይ ያሉት ሕጎች የሚሳዩን ሲሆን መጠኑን በተመለከተም ሕግና ሥርዓት የተዘረጋለት ጉዳይ ነው፡፡የከተማ ቦታን የመስጠት ስልጣን የከተማው ማዘጋጃ ቤት ስልጣን መሆኑ በሕጉ በተደነገገበት ሁኔታ ተጠሪ ቦታ ለአመልካች እሸልማለሁ ብሎ የገባው ቃል ስልጣኑ ሲኖረው የሚፈጽመው ግዴታ መሆኑን አውቆ ያደረገው ሳይሆን ቦታ የሚገኝበትን ሥርዓት ተከትሎ ለአመልካች ለማስረከብ ግዴታ መግባቱን የሚያሳይ ነው፡፡ የከተማ ቦታ ከሚገኝባቸው መንገዶች አንዱ ደግሞ የሊዝ ስርዓት ነው፡፡ ቦታ በሊዝ የሚገዛው ደግሞ በሕጉ ፣ ደንቡና በመመሪያው መሰረት ተመንና የውሉ ጊዜ ወጥቶለት ነው፡፡ ተጠሪ የቦታ ሽልማት ውሉን

በወቅቱ በነበረው የሊዝ ተመንና በሕጉ አግባብ በሊዝ ገዝቶ የሚፈጸመው ጉዳይ እንጂ ፍጹም የማይቻልና የማይሞከር ጉዳይ አይደለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የመሬቱን አቀማመጥና ተይዞ የሚገኝበትን ሁኔታ እንዲሁም ቦታ በሽልማት የመስጠት ስልጣንን በምክንያትነት በመያዝ በሕግ ጥበቃ ሊደረግለት የሚችል ውል የለም ብሎ መደምደሙ ከፍ/ሕ/ቁጥር 1715 ድንጋጌ አንፃር ሲታይ ሕጋዊ መሰረት የሌለው ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በከተማ የመኖሪያ መስሪያ ቦታ የሚገኝበትን የሕግ ስርዓት እያወቀ ያደረገው ውል መሆኑ እየታወቀ በሕግ ጥበቃ ሊደረግለት አይችልም በማለት መደምደም በተዋዋዮች መካከል ሊኖር የሚገባውን የቅንነትንና የመተማማን ግንኙነት መሰረት በማድረግና በጉዳዮቹ ውስጥ ያለውን ልማዳዊ ሥርዓት በመከተል ውሎች በቅን ልቦና ሊተረጎሙ ይገባል ተብሎ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1732 ስር የተደነገገውን ድንጋጌ ውጤት አልባ የሚያደርግ ነው፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1689(1) ድንጋጌ ሁኖ እያለ አግባብነት የሌለውን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2435 ድንጋጌ መሰረት በማድረግ የደረሱበት ድምዳሜ የውል አተረጎጎም ደንቦችንና የውል ውጤትን መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. በአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 08045 ሰኔ 30 ቀን 2002 ተሰጥቶ በደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 44079 ጥቅምት 10 ቀን 2003 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተቋቋመው የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ በሕግ ጥበቃ ሊደረግለት የሚችል ውል ነው ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ለአመልካች በሐዋሳ ከተማ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ በሕጉ አግባብ ገዝቶ እንዲሰጣት ወይም ውሉ ሲደረግ በነበረው የከተማ የሊዝ ዋጋ መሰረት አንድ መኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ሊገዛ ይችል የነበረውን ዋጋ በሊዝ ሕጉ ፣ ደንቡና መመሪያው መሰረት አስልቶ ለአመልካች እንዲከፍል ብለናል፡፡
4. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 66210

29/11/ 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አቶ ተስፋዬ ጎላ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የአሁኑ ተጠሪ መ/ቤት የዲስኘሊን ኮሚቴ የሰጠው የዲስኘሊን ውሣኔ ለተጠሪ መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ቀርቦ ይፈፀም በመባሉ ምክንያት አመልካች ይግባኛቸውን በደንብ ቁጥር 57/1992 አንቀጽ 29 መሰረት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ከፍተኛው ፍ/ቤትም መልስ ሰጪውን መጥራት ሳያስፈልግ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሠረት የይግባኙን መዝገብ በመዝጋት አመልካችን በማሰናበት በመወሰኑ አመልካች በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት የካቲት 28 ቀን 2003 ዓ/ም በተፃፈ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን ስለአቀረቡ ነው፡፡

ለዲስኘሊን ኮሚቴ ውሣኔ መነሻ የሆነውን አቤቱታ ለተጠሪ መ/ቤት ያቀረቡት አቶ ጽጌ ጌታነህ ሲሆኑ የአቤቱታውም ፍሬ ቃሉ ከአዲስ አበባ ቴኒስ ክለብ ጋር በተፈጠረው ያለመግባባት ክለቡን በሕግ ፊት አመልካች አቅርበው እንዲፋረዱላቸው አመልካችን ጠይቀው አመልካችም ፈቃደኛ ሆነው የጥብቅና ሙያ ውል እንደአደረጉና አመልካች ለሚሰጧቸው አገልግሎትም ብር 2,000.00 ለመክፍል፣ አከፋፈሉም በቅድሚያ ብር 1,000.00፣ ቀሪው ብር 1,000.00 ደግሞ ጉዳዩ እንደተከናወነ እንደሚሆን ተስማምተው ቅድሚያ ክፍያውን አመልካች ተቀብለው አመልካች እንደስምምነቱ ሳይፈፅሙ ለእንግልት የዳረጓቸው መሆኑን ገልጸው የዲስፕሊን እርምጃ እንዲወሰድባቸውና የተወሰደባቸው ገንዘብ እንዲመለስላቸው መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች ክሱን ሊያቀርቡ ያልቻሉት አስተዳደራዊ መፍትሔዎችን ለመጨረስ ተገቢውን ሲያደረጉና ክለቡ ሕጋዊ ሰውነት ስለሌለው በፍርድ ቤት ሊከሰስ የሚችል አለመሆኑን እንዲሁም ክሱ የሚቀርበው አስተዳደራዊ መፍትሔዎች ሲያልቁ በመሆኑ በዲስፕሊን ሊያስጠይቃቸው የማይችል መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡ የሥር የዲስኘሊን ኮሚቴውም የአሁኑ አመልካች የፌዴራል ፍ/ቤቶች የጠበቆች ሥነ ምግባር ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 8/2/ለ/ የተደነገገውን የሥነ ምግባር ድንጋጌዎች በመጣስ የደንበኛቸውን በአፋጣኝ



www.chilot.me

ፍትህ የማግኘት መብት ጎድተዋል፣ ይህም ሕብረተሰቡ ለሌሎች የሕግ ባለሙያዎች ያለውን እምነት የሚሸረሽር ነው የሚለውን ምክንያት በመስጠት በአዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 24(3(ለ(3)) መሰረት በብር 10,000 /አሥር ሺህ/ እንዲቀጡ የውሳኔ ሃሳብ ለበላይ ኃላፊ ያቀረበ ሲሆን የበላይ ኃላፊውም የኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ አጽድቀውታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ከግል ተበዳይ ጋር በተደረገው የጥብቅና ውል መሰረት ሙያው የሚጠይቀውን እየፈጸሙ ያሉ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ በጉዳዩ ላይ ክስ ሳያቀርቡ ዘግይተዋል ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች የዲስፐሊን ግድፈት ፈፅመዋል ተብሎ ብር 10,000.00 እንዲቀጡ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት ተይዞ ለሰበር ችሎቱ ጉዳዩ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦም አመልካች በዲሲፐሊን ግድፈት ሊጠየቁ የቻሉት ከግል ተበዳይ ጋር ባደረጉት የጥብቅና ውልና ተገቢ ያልሆኑ ተግባራትን መፈፀማቸው በመረጋገጡ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት በፅሑፍ መልሱን አቅርቧል፡፡ አመልካችም የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ የተገለፀ ሲሆን እኛም አመልካች በተከሰሱበት የዲስኘሊን ክስ ጥፋተኛ ናቸው ተብለው በገንዘብ የተቀጡት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በመሰረቱ የጥብቅና ሙያ ለእውነት፣ ለፍትህ እና ለሕግ የበላይነት መስፍን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑ እሙን ሲሆን ይህንን ግብ ላይ ለማድረስ ደግሞ ሙያው ከባለሙያው የሙያ ኃላፊነቱን በታማኝነት፣ በቅንነት፣ በታታሪነትና በብቃት እንዲወጣ የሚጠይቀው ጉዳይ ይሆናል፡፡ ይህንኑ ግዴታ ያለመወጣት ደግሞ ምግባረ ብልሹነት ሲሆን ተጠያቂነትን የሚያስከትል ነው፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ምዝገባና ፍቃድ አሰጣጥ አዋጅ ቁጥር 199/92 መግቢያው እንዲሁም አንቀጽ 30 ስር ለተመለከቱት ድንጋጌዎች እና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 3፣8(2(ለ)) እና ሌሎች ድንጋጌዎች ይህንኑ ግንዛቤ ውስጥ ያስገቡና ተጠያቂነት መቼ ሊከተል እንደሚችል የሚያሳዩ ድንጋጌዎችን ይዘው እናገኛለን፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ሲመጣ አመልካች የዲስፐሊን ግድፈት ፈጽመዋል የተባሉት ከአቶ ጽጌ ጌታነህ ጋር ባደረጉት የጥብቅና ውክልና ስልጣን መሰረት የቅድሚያ ክፍያ ወስደው ጉዳያቸውን በተገቢው ጊዜ ለሚመለከተው ፍርድ ቤት አቅርበው ሳያስወስኑ አዘገይተዋል ተብለው ሲሆን ይህ ስለመሆኑ የዲሲፐሊን ኮሚቴው በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ ሲሆን አመልካችም ቢሆኑ ጉዳዩን አስተዳደራዊ መፍትሔ እንዲሰጥበት ለማድረግ ለሚመለከተው አካል ጥያቄ በማቅረብ እየተከታተሉት ያለና ወደ ፍርድ ቤት ለመሄድም አቶ ጽጌ ጌታነህ እንዲከሰስላቸው የሚፈልጉት አካል ሕጋዊ ሰውነት የሌለው በመሆኑ የተቸገሩ መሆኑን ገልፀው የሚከራከሩ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ አመልካች ከአቶ ጽጌ ጌታነህ ጋር ያደረጉት የጥብቅና ውል ይዘት ሲታይም እኔ አገልግሎት ተቀባይ ከአዲስ አበባ ቴንስ ክለብ ጋር በተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት የክለቡ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ከጥቅምት 23 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ያገደኝ በመሆኑ አገልግሎት ሰጪው አቶ ተስፋዬ ጎላ ጥሩነህ ባላቸው የጥብቅና ሙያ ከስራ አስኪያጅ ኮሚቴው ጋር ተከራክረው የእኔን የክለብ አባልነት መብቴን እንዲያስጠብቁልኝ የሚል ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የደንበኛቸውን ጉዳይ በፍርድ ቤት ክስ ለመመስረት ያልቻሉበት ምክንያት በጉዳዩ ላይ



www.chilot.me

አስተዳደራዊ መፍትሔ ለማግኘት ነው የሚል የሚገኝበት ሲሆን ይህ ምክንያት ጉዳዩን ለመጨረስ አንዱ አካሄድ ነው ቢባልም አስተዳደራዊ መፍትሔ ለማግኘት ሲባል ግን ጉዳዩ በፍርድ ቤት በተገቢው ጊዜ ክስ ሳይቀርብበት እንዲቆይ የሚያደርግ አይደለም፡፡ የስር የዲስፕሊን ኮሚቴውም አስተዳደራዊ መፍትሔ መፈለግ ተገቢነቱን አምኖ አመልካችን ከተጠያቂነት ሊድኑ አይችሉም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው አመልካች በትጋትና በታማኝነት ጉዳዩን ያልተከታተሉ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል በማለት ሲሆን አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት የማስተባበያ ማስረጃ የሌለ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ ሌላው አመልካች በምክንያትነት የሚያቀርቡት ነጥብ ደንበኞቸው እንዲከሰስ የሚፈልጉት አካል ሕጋዊ ሰውነት የሌለው መሆኑ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ምክንያት ጠበቃው የሙያው ስነ ምግባሩን መሰረት በማድረግ በሙያው ሕጋዊ ነው የሚለውን አስተያየት የማቅረብ ሙያዊ ነፃነት ያለው መሆኑ ቢታወቅም ይህንኑ ነፃነቱን ደግሞ የደንበኛውን ፍላጎት ማዕከል በአደረገ መልኩ ሊወጣው የሚገባው ከመሆኑ ጋር ተዳምሮ ሲታይ ደንበኞቸው እንዲከሰስ የሚፈልጉትን አካል ከሰው ይኸው አካል የሕግ ሰውነት ያለው መሆን ያለመሆኑ ጉዳይ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት እንዲወሰን ማድረግ የሚችሉት ነጥብ በመሆኑ ክስ ላለማቅረብ እንደ በቂ ሕጋዊና ሙያዊ ምክንያት ሊወሰድ የሚችል አይደለም፡፡ በአጠቃላይ አመልካች ከደንበኞቸው ጋር ያደረጉት የጥብቅና ውክልና ስልጣን ሰነድ ይዘቱ ሲታይ አመልካች ክሱን በተገቢው ጊዜ በፍርድ ቤት እንዲያቀርቡና የደንበኞቸውን መብት እንዲያስጠብቁ ግዴታ የሚጥልባቸው መሆኑና አመልካች ይህንኑ ግዴታቸውን በተገቢው ጊዜና በትጋት ሳይወጡ ቀርተው ጉዳዩን ያዘገዩ መሆኑ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የዲስፕሊን ኮሚቴውና የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተስማሙት ጉዳይ በመሆኑ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ከተሰጠው የመሰረታዊ ሕግ ስህተት የማረም ስልጣን አንፃር ሲታይ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ጉዳይ የሚነቀፍበትን አግባብ አላገኘንም፡፡ በፍሬ ነገር ረገድ የተረገጋጠው ነጥብ ከላይ የተጠቀሰው ከሆነ አመልካች በደንብ ቁጥር 57/92 አንቀፅ 8(2(ለ)) እና አዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀጽ 24(3(ለ-3)) ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ ተብለው በብር 10,000.00(አስር ሺህ) መቀጣታቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 33945

ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** አቶ ሣልህ ሁሴን ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ደግፌ ደርቤ ከጠበቃ ጣሰው ማሞ ጋር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ከሣሽ የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ ተከሣሽ ነበሩ፡፡

አመልካች ግንቦት 05 ቀን 1997 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ተጠሪ በስማቸው ተመዝግቦ የሚታወቀውንና በቀድሞው አጠራር ከፍተኛ 09 ቀበሌ 07፣ በአሁኑ አጠራር በአራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 የሚገኘውን ቁጥሩ 207 እና 206 የሆነ ቤት በመያዣነት አስይዘው ብር 12000.00 /አስራ ሁለት ሺህ/ ተበድረው ቤቱን እንዳስረከቧቸው፤ በስምምነቱ ወቅት የማይንቀሳቀስ ንብረት መሸጥና መለወጥ ችግር ስለነበር ገንዘቡ የ10 ዓመት መክፈያ ጊዜ ተወስኖለት ኀዳር 20 ቀን 1990 ዓ.ም. ማብቃቱን፤ ኀዳር 20 ቀን 1980 ዓ.ም. በተፃፈ የብድርና የዋስትና ውል ቤትን መሸጥና መለወጥ በመንግሥት ሲፈቀድ አመልካች ብር 5000.00 /አምስት ሺህ/ ለተጠሪ በመጨመር ከወሰዱት ብር 12000.00 ጋር ተደምሮ በብር 17000.00 /አስራ ሰባት ሺህ ብር/ ቤቱን በሽያጭ ለማስተላለፍ ተጠሪ ውል መፈረማቸውን፤ የቤቱን የእድሣት ወጪዎችም አመልካች እንዲሸፍኑ ተጠሪ ፈቃዳቸውን በውሉ የገለጹላቸው ሆኖ ተጠሪ ከወሰዱት የቤቱ መያዣ ብድር ጋር የእድሣት ወጪ ሲደመር ድምሩ ብር 18787.90 /አስራ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሠማኒያ ሰባት ብር ከዘጠና ሣንቲም/ መሆኑን፤ የቤት ሽያጭም ከ1982 ዓ.ም. ጀምሮ በመንግሥት መፈቀዱን ዘርዝረው ተጠሪ በስምምነቱ መሠረት የብድሩን ገንዘብ በወቅቱ ካለመመለሣቸውም በላይ የቤቱን ስመ ንብረት በሽያጭ ለማስተላለፍ በአማራጭ የገቡትን ግዴታ ስላልፈፀሙላቸው አመልካች ብር 5000.00 /አምስት ሺህ/ ለተጠሪ ጨምረውላቸው የቤቱ ስም በአመልካች እንዲዛወር ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ለማስረጃነትም የጽሑፍና የሰው ምስክሮችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡

የአሁኑ አመልካች የክስ ማመልከቻና ማስረጃ ለተጠሪ እንዲደርስ ተደርጎም ተጠሪ በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ፍ/ቤቱም

የአመልካችን ክስና ማስረጃ መርምሮ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገ ውል የመያዣ ውል ሣይሆን የወለድ አገድ ውል ነው፤ ውሉ በተደረገበት ወቅት የወለድ አገድ ግንኙነት የሚገዛው በአዋጅ ቁጥር 47/67 ስለነበር ይኸው አዋጅ የወለድ አገድ ውልን የሚከለክል በመሆኑ ውሉ ሕገወጥ ስለሆነ ፈራሽ ነው፤ ተዋዋዮች ወደ ነበሩበት ይመለሱ፤ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት አመልካች ያስረክቡ፤ ተጠሪ ከአመልካች የወሰዱትን ገንዘብና የቤት ማደሻ ብር በገቡት ውል መሠረት ለከሣሽ ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚሉባቸውን ምክንያቶች ኀዳር 16 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የበታች ፍ/ቤቶች ተጠሪ ቀርበው ባልተከራከሩበት እና የተጠየቀ ዳኝነት በሌለበት ሁኔታ ቤት እንዲረከቡ መወሰናቸው ያላግባብ በመሆኑ ውሣኔው ተሽሮ ኀዳር 20 ቀን 1980 ዓ.ም. በውል ያገኙት መብት ተጠብቆ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በጉዳዩ ከተጠየቀው ዳኝነት በተለየ ሁኔታ የተሠጠውን ውሣኔ የሕግ አግባብነት ለማጣራት ተጠሪ እንዲቀርብ ተደርጎ ጥር 29 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት፣ የፍ/ሕ/ቁ. 1815 ድንጋጌን ያገናዘበ፣ የአመልካች ጥያቄ ግን በፍ/ሕ/ቁ 2851 ድንጋጌ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አመልካች የካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት የመልስ መልስ ማመልከቻ ተጠሪ ወደ ዋናው ጉዳይ ገብተው ለመከራከር ሥነ ሥርዓቱ የማይፈቅድላቸው መሆኑን ገልፀውና የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ይህንኑ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱ ምላሽ የሚያስፈልጋቸው ጭብጦች፡-

1ኛ/ የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች ከጠየቁት ዳኝነት በተለየ ሁኔታ የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? እና

2ኛ/ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የክስ ምክንያት አለው ወይስ የለውም? የሚሉት ሁነው ተገኝተዋል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡- አመልካች ከተጠሪ ጋር ተደርጓል በሚሉት ስምምነት አከራካሪውን ቤት ተረክበው በይዞታቸው ሥር አድርገው እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑን ገልፀው የሚከራከሩ ሲሆን የጠየቁት ዳኝነትም ቀሪውን ብር ለተጠሪ ጨምረው የቤቱ ስመንብረት እንዲዛወርላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ነው፡፡ ይህንኑ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የአሁኑ ተጠሪ ፍ/ቤት ቀርበው ከስር ያልተከራከሩበት ሆኖ የስር ፍ/ቤት ግን የውሉን ሕጋዊነት በራሱ ጊዜ በማንሣት ሕገ ወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት አመልካች ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው የስር ፍ/ቤት ውሣኔ የሰጠው የአሁኑ አመልካች በግልጽ ባላመለከቱት እና ባልጠየቁት ዳኝነት ላይ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 182/2/ ድንጋጌ ሥር የተመለከተውን የመጀመሪያ

ደረጃ ፍ/ቤት የዳኝነት አሠጣጥ የስልጣን አድማስ በግልጽ የሚገረር ነው፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም በይግባኝ ሠሚነቱ ስልጣን የስር ፍ/ቤትን የውሣኔ አሠጣጥ ማረም ሲገባው በተመሣሣይ ምክንያት ተቀብሎ ማጽናቱ የዳኝነት አሠጣጥ ሥርዓቱን ያላገናዘበ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት ስለውሉ ሕጋዊነት ክርክር ባልተነሣበት ሁኔታ በራሱ ጊዜ ማንሣቱም የክርክር አመራር ስርዓቱ በሚፈቅድለት ሁኔታ አይደለም፡፡ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ሣይቀርቡ ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ ከተወሰነ በኋላ አሁን በሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር ሥነ ሥርዓታዊ አይደለም፡፡ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ሣይቀርቡ ታይቶ በተሰጠው ውሣኔ ለበላይ ፍ/ቤት ሊያቀርቡ የሚችሉት ክርክር ከስር ክስ ተያይዘው የቀረቡትን የከሣሽን ማስረጃዎች አግባብነት፣ ተቀባይነት እና ጥንካሬ ያገናዘብ መሆን ያለመሆኑን መሠረት በማድረግ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በዚሁ የክርክር ደረጃ ያነሱት ክርክር ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ አልፈነዋል፡፡ በዚህም መሠረት የስር ፍ/ቤት የውሣኔ አሠጣጥ ከተጠየቀው ዳኝነት በተለየ ሁኔታ መሆኑ ከላይ የተጠቀሰውን የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡- በመጀመሪያው ጭብጥ እንደተገለፀው የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ስመ ንብረቱ እንዲዞርላቸው ይወሰን ዘንድ ነበር፡፡ የስር ፍ/ቤትም የዚህኑ ጥያቄ አግባብነት በመመርመር ውሣኔ መስጠት እየተገባው ከተጠየቀው ዳኝነት በተለየ ሁኔታ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የአመልካች ጥያቄ ተገቢነት ያለው መሆን ያለመሆኑን የስር ፍ/ቤት በጭብጥነት ይዞ በሕጉ አግባብ የሰጠው ውሣኔ ባይኖርም ከተጠየቀው ዳኝነት ይዘት በሰበር ችሎቱ ከዚህ በፊት በተመሣሣይ ጉዳይ ከተሰጠው የሕግ ትርጓሜና ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ዓላማ አኳያ ሲታይ በዚህ ችሎት ለጉዳዩ እልባት መስጠቱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የሚያስከስስ ሊሆን ይችላል አይችልም? የሚለው ነጥብ ምላሽ የሚያስፈልገው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከአመልካች ክስና ክርክር ማረጋገጥ የተቻለው ከተጠሪ ጋር በተደረገው ስምምነት ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት አመልካች ተረክበው ለረጅም ጊዜያት በይዞታቸው ስር አድርገው የሚገኙ መሆኑን፣ ቤቱን የሚመለከቱ አስፈላጊ ሰነዶችም በተጠሪ እጅ ይገኛሉ ተብሎ በክሱ አለመገለጹንና የዳኝነት ጥያቄ ያልቀረበበት መሆኑን በተጠሪ በኩል መፈፀም አለበት የተባለው የቤቱ ስመ ንብረት ማዞር ብቻ መሆኑን ነው፡፡ የስም ዝውውር ተግባር የሚፈፀመው በመንግሥት አስተዳደር ክፍል ፊት እንጂ ሻጭ ነው የተባለው ወገን ሊፈጽም ይገባል ተብሎ ከሕግ ወይም ከውል ያመነጫል ሊባል የማይችል ግዴታ ነው፡፡ የስም ዝውውር ጥያቄ የሚስተናገደው የባለ ሀብትነት የምስክር ወረቀት በሚሠጥ የመንግሥት አስተዳደር አካል ገዢው ውልና አስፈላጊ ሠነዶችን ይዞ ሲቀርብ እንጂ በፍ/ቤት ክስ ቀርቦ ዳኝነት የሚሰጥበት አይደለም፡፡ አንድ ክስ ሊቀርብ የሚገባው የክስ ምክንያት ሲኖረው ሲሆን የክስ ምክንያትም ተከሣሽ ለከሣሽ ሊፈጽመው የሚገባው ግዴታ መኖሩ ጋር ተያይዞ ሊነሣ የሚችለውን ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ መስጠት የሚቻልበት ሁኔታ ስለመኖሩ ሲረጋገጥ የሚታወቅ ነው፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች ተጠሪ የስም ዝውውሩን እንዲፈጽሙ ይወስንልኝ ብለው ዳኝነት መጠየቃቸው በተጠሪ በኩል ሊፈፀም የሚገባ የሕግ ወይም የውል ግዴታ የሌለ መሆኑን ስለሚያሣይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 231/1/ሀ/ መሠረት ፍሬ ነገሩ የማያስከስስ ነው ተብሎ መወሰን ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡



www.chilot.me

**ው ሣ ኔ**

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13295 ጥቅምት 16 ቀን 1999 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 51107 ኅዳር 03 ቀን 2000 ዓ.ም. የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የስም ዝውውር ጥያቄ ታይቶ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው እያለ ከተጠየቀው ዳኝነት በተለየ ሁኔታ ውሉ ሕገወጥ ነው ተብሎ ቤቱን እንዲያስረክቡ መባሉ የዳኝነት አሰጣጥ ሥርዓትን የተከተለ አይደለም ብለናል፡፡
3. የአመልካች የስም ይዛወርልኝ ጥያቄ የሚያስከስስ ምክንያት የለውም ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 48012

ጥቅምት 3 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ዑመር ከድር ቀረቡ

**ተጠሪዎች**፡- 1/ አቶ በዳዳ ሰቦቃ

2/ ወ/ሮ አበበች ተካ ጠ/ሰለሞን ሀብቴ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የቤት ሽያጭ ውልን መነሻ ያደረገ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪዎች ጅምር ቤት ከ1057 ካ.ሜ. ይዞታ ጋር ሸጠውለት ሳለ ክ/ከተማው ቦታውን ለልማት የወሰደ መሆኑን ጠቅሶ ሽያጭ የተፈፀመው የሻጮች ይዞታ ባልሆነ ቦታ ላይ ነው ሲሉ ሽያጩ ዋጋ የለውም ተብሎ ወደነበሩበት እንዲመለሱ እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቋል፡፡ ተጠሪዎች የይርጋ ክርክር በማቅረባቸው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሽያጭ ውል ከተፈፀመ ከሁለት ዓመት በላይ ይሆናል በማለት የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1810/2/ እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሥ/ሕግ 244/2/ሠ እና 245 በመመረኮዝ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ይህንኑ ብይን አጽንቷል፡፡

የአመልካች ጠበቃ ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረቡት አቤቱታ ውሉ በሕጉ አላግባብ ያልተፈፀመ ስለመሆኑ እና ተጠሪዎች መብት የሌላቸውን ቦታ የሸጡላቸው መሆኑን ዘርዝረው የሥር ፍ/ቤት ለጉዳዩ አወሳሰን ትክክለኛ ጭብጥ ሣይዝ የሰጠው ብይን እንዲታረም አመልክቷዋል፡፡

ሰበር ችሎቱም አቤቱታውን መርምሮ በዚህ ጉዳይ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1810/2/ ተፈፃሚነትን አስመልክቶ ለመመርመር ሲል ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ አዝዟል፡፡

የተጠሪዎች ጠበቃ በ14/5/2002 ዓ.ም ጽፎ ባቀረቡት መልስ የአመልካች ክስ ውል ማሰረዝ ይሁን ማፍረስ ግልጽነት የሚጎድለው ስለመሆኑ ጠቅሰው ተጠሪዎች ያደረጉት የሽያጭ ውል ዋጋ የለውም እንዲባልና ወደነበርንበት እንመለስ የሚለውም ውሉ ከተደረገ ከ9 ዓመት በኋላ የቀረበ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1810 በይርጋ ቀሪ መደረጉ በአግባቡ ነው በማለት የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡



www.chilot.me

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል የተመለከተው ሆኖ እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት የተቻለው በግራ ቀኙ መካከል ነሐሴ 12 ቀን 1990 ዓ.ም በተደረገ ውል ተጠሪዎች ጅምር ቤት ለአመልካች መሸጣቸው እና በዚሁ አግባብም በግራ ቀኙ መካከል በውሉ መሠረት የተፈፀመ ስለመሆኑ ነው፡፡

አመልካች ውሉ ዋጋ የለውም ተብሎ ግራ ቀኙ ከውሉ በፊት ወደነበሩበት እንዲመለሱ እንዲወሰን ዳኝነት የጠየቀው ለአመልካች የተሸጠው ይዞታ የሻጮች አልነበረም በሚል መነሻ ስለመሆኑም የሥር መዝገብ ያስረዳል፡፡ ከዚህ መረዳት  የሚቻለው የውሉ ጉዳይ ሕጋዊነት አከራካሪ ሆኖ የቀረበ መሆኑን ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1711 በግልጽ እንደተደነገገው የውልታው ጉዳይ /Object of the Contract/ የመወሰን መብት የተዋዋዮች ቢሆንም በሕግ የተወሰኑ ወይም የተከለከሉ ጉዳዮች የተጠበቁ መሆናቸውን ያስገነዝባል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ያቀረበው ክስ መሠረት ያደረገው ተጠሪዎች የሸጡት ቤትና ይዞታው የራሣቸው አይደለም በሚል ነው፡፡

ስለዚህ የውልታው ጉዳይ ተጠሪዎች ሕጋዊ ባለይዞታ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለው በፍሬ ነገር ክርክር እና ማስረጃ የሚጣራ በመሆኑ በዚህ ደረጃ የምንመረምረው አይደለም፡፡ የሥር ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1810/2/ን በመመርኮዝ ክሱን በይርጋ ደንብ ስለዘጋው የዚህን አቋም አግባብነት ብቻ እንመረምራለን፡፡

ውል የማፍረስ /invalidation/ መነሻ ምክንያቶች በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1808 ተዘርዝረዋል፡፡ እነዚህም ውሉ አመሠራረት ላይ የፈቃድ ጉድለት መኖር ከተዋዋይ ወገኖች አንዱ ችሎታ ማጣት፤ የውልታው ጉዳይ ሕገወጥነት ወይም ኢምራላዊነት ወይም የውሉ አቀራረጽ /ፎርም/ በሕግ የተደነገገውን ሥርዓት አለመጠበቅ የሚሉ ናቸው፡፡

ከእነዚህ ምክንያቶች በአንዱ ወይም በሌላው መነሻ ውሉ እንዲፈርስ ጥያቄ በማንና መቼ መቅረብ እንዳለበትም በሕጉ ተመልክቷል፡፡

ከዚሁ አንፃር በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1810 ሥር እንደተመለከተው የውሉ መፍረስ ምክንያት ከተዋዋይ ወገኖች ፈቃድ ጉድለት ወይም ችሎታ ማጣት ጋር የተያያዘ ከሆነ ውሉ እንዲፈርስ ጥያቄ መቅረብ ያለበት በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ መሆን እንዳለበት ያመለክታል፡፡

የጊዜውም አቆጣጠር ውሉ የማይረጋበት ምክንያት ከቀረበት ጊዜ ወይም አካለመጠን ከደረሰ ጊዜ ጀምሮ መሆኑንም ተመልክቷል፡፡ ይህ የድንጋጌው ይዘት ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ምክንያቶች የተወሰኑትን ብቻ ለይቶ ያስቀመጠ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም ከፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1808/1/ ድንጋጌ ይዘት ጋር ተገናዝቦ ሲታይ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1810/1/2/ የተመለከተው የጊዜ ገደብ የሚያገለግለው ውሉ በፈቃድ ጉድለት ወይም በችሎታ ማጣት መነሻ እንዲፈርስ የሚቀርብ ጥያቄን በሚመለከት ብቻ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ ሌላ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1808/2/ ሥር የተዘረዘሩትን ምክንያቶች መነሻ በማድረግ ውል እንዲፈርስ የሚቀርብ የዳኝነት ጥያቄ በፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 1810 መሠረት በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ እንዲቀርብ ሕጉ አላስገደደም፡፡ ስለዚህም የውልታው ጉዳይ ሕጋዊነትን አስመልክቶ የቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1810 መሠረት በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ አልቀረበም ሲል የሥር ፍ/ቤት

የደረሰበት ድምዳሜ የሕጉን ይዘት በአግባቡ ያገናዘበ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የውለታውን ጉዳይ ሕጋዊነት አስመልክቶ የሚያቀርብ ክስ የይርጋ ጊዜ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1810 ሥር የሚሸፈን ሣይሆን እንደማናቸውም የውል ጉዳዮች ክርክር በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1845 በተደነገገው የአሥር ዓመት ጊዜ የሚታይ ይሆናል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግራ ቀኙ መካከል የሽያጭ ውል የተደረገው ነሐሴ ወር 1990 ዓ.ም ሲሆን ክስ የቀረበው ግንቦት 26 ቀን 2000 ዓ.ም ስለመሆኑ ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ ጊዜው ሲሰላ ደግሞ አሥር ዓመት /10/ እንዳላለፈው ተገንዝበናል፡፡

ስለሆነም የውለታው ጉዳይ ሕጋዊነትን አስመልክቶ አመልካች ያቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1810/2/ መሠረት በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ አልቀረበም በሚል የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ብይን ሊታረም የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13325 መስከረም 28 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 72117 በ02/11/2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ የሚሸፈን አይደለም ብለናል፡፡
3. ክሱ የአሥር ዓመት ይርጋ ጊዜ አላለፈበትም ብለናል፡፡
4. ስለሆነም በግራ ቀኙ የቀረበውን የፍሬ ነገር ክርክር መርምሮ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ብለን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341/1/ መሠረት መዝገቡን ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡
5. ግራ ቀኙ የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 43379

ታህሳስ 25 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች ፡-** አበበ አበጋዝ ቀረበ

**ተጠሪ ፡-** ወ/ሮ ጥሩነሽ ተክሌ ቀረበች

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ ቀደም ሲል በቤት ላይ ተደርጎ የነበረው የሽያጭ ውል እንዲፈርስ በተወሰነው መሠረት ቤቱን ያስረክቡኝ፣ የአሁኑ አመልካችም ቤቱን ይዞ ስለሚገኝ እስኪያስረክበኝ ድረስ ኪራይ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ተጠሪ በአሁኑ አመልካች እና ሃይሉ ታደሰ በተባለ ግለሰብ ላይ ያቀረበችውን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ክሱ የቀረበው ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም የተከሳሾቹን መልስ ካየ እና ክርክሩን ከሰማ በኋላ በወቅቱ 1ኛ ተከሳሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት ለቆ ለተጠሪ እንዲያስረክብ፤ በውሉ መፍረስ ምክንያት ለደረሰበት ጉዳት 2ኛ ተከሳሽ የነበረውን ሃይሉ ታደሰን ከሶ የመጠየቅ መብት አለው በማለት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ ፍ/ቤቱም ቀደም ሲል ተሰጠ የተባለው ውሳኔ የስር ከሳሽ ቤቱን እንድትረከብ የሚያስችላት አይደለም የሚል ምክንያት በመስጠት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮአል፡፡ ከዚህ በኋላም ተጠሪ ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረብዋ በዚህ ደረጃም ክርክሩ የተሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች የካቲት 3 ቀን 2001ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ከክርክሩ አነሳስ እና ቀደም ሲል ተሰጥቶ ነበር ከተባለው ውሳኔ አንፃር ሲታይ ያለው አግባብነት ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡



www.chilot.me

ከሥር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር እና በየደረጃው የተሰጡትን ውሳኔዎች ይዘት በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ ከዚህም በቅድሚያ መገንዘብ የቻልነው ተጠሪ በ2ኛ ተከሳሽነት ተመዝግቦ የነበረው ሃይሉ ታደሰ የተባለው ሰው ሚስት እንደሆነች እና ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት ከኔ ፈቃድ ውጭ ነው የተሸጠውና የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ይወሰኝልኝ በማለት ተጠሪ ባልዋን ጨምራ መክሰስዋን ነው፡፡ ይህን የመሰለውን ክስ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ክርክሩን ከሰማ በኂላ፣ ውሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1723 የተመለከተውን መስፈርት አያሟላም፤ በሕግ ፊት የፀና አይደለም የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ክሱ የክስ ምክንያት የለውም የሚል ውሳኔ እንደሰጠም ተመልክተናል፡፡ ተጠሪ ቤቱን ልረከብ፤ ኪራይም ይከፈለኝ በማለት አዲስ ክስ የመሠረተችውም ከዚህ በኂላ ነው፡፡

እንደምንመለከተው በአመልካች እና በተጠሪ ባለቤት መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ይፍረስልኝ በማለት ተጠሪ ክስ ብትመሠርትም ክስዋ የክስ ምክንያት የለውም በሚል ትዕዛዝ ነው የተዘጋው፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ለክሱ መነሻ የሆነው ውል ሊፈርስ የሚገባው ነው ወይም አይደለም? በሚለው የሥረ ነገር ጭብጥ ላይ ክርክር ተደርጎ ውሳኔ አለመስጠቱን ነው፡፡ በእርግጥ ቀደም ሲል ቀርቦ በነበረው ክስ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት ተወስኖ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ አመልካች ይግባኝ ባይነት ጉዳዩ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ክርክር ከተካሄደበት በኂላ ተሽሮ ክርክሩ እንደገና ተሰምቶ ይወሰን ዘንድ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተመልሶአል፡፡ ከዚህ በኂላም ነው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክሱ የክስ ምክንያት የለውም በማለት ክሱን ሳያስተናግድ መዝገቡን የዘጋው፡፡ በዚህ ላይም ማንኛውም ተከራካሪ ወገን ይግባኝ አላለም፡፡

ቀደም ሲል እንዳየነው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት የክስ ምክንያት የለም በማለት የተሰጠው ትዕዛዝ ከጅምሩ የቤት ሽያጭ ውል የለም እንደማለት ነው በሚል እሳቤ ነው አመልካች ቤቱን ለተጠሪ ያስረክብ በማለት የወሰኑት፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግን የክስ ምክንያት የለም በመባሉ ተጠሪ ቤቱን ልትረከብ ችላለች ማለት አይቻልም የሚል አስተሳሰብ ነው የያዘው፡፡ በእርግጥ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተጠሪን የውል ይፍረስልኝ ክስ የክስ ምክንያት የለውም ለማለት የሰጠው ምክንያት ውሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1723 የተመለከተውን መስፈርት /ፎርም/ ያላሟላ እና ከጅምሩ ውል ሳይኖር የውል ይፍረስ ክስ ሊቀርብ አይችልም የሚል ስለመሆኑ ከውሳኔው ይዘት ተገንዝበናል፡፡ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤትም ይህን አካሄድ በመከተሉ ነው በአመልካች እና በተጠሪ ባለቤት መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ፈራሽ ሊሆን የሚገባው ነው ወይም አይፈርስም? በሚለው የሥር ነገር ጭብጥ ላይ ክርክር ሳይሰማ ተጠሪ ቤቱን ትረከብ ዘንድ የወሰነው፡፡

ለፍ/ቤት የቀረበ የፍትሐብሔር ክስ የክስ ምክንያት አለው ወይስ የለውም? ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የዳኝነት ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚሉት ጥያቄዎች መልስ የሚያገኙት ወይም የሚወሰኑት ፍ/ቤቱ ወደ ክሱ ሥረ ነገር ከመግባቱ በፊት ነው፡፡ ይህንንም የሚያደርገው ፍ/ቤት በራሱ አነሳሽነት እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33/2/ እና 231/1/ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ዋነኛው ጉዳይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች አግባብ የክስ መዝገብ ሲዘጋ ወይም ክስ አይስተናገድም ሲባል ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ሥረ ነገር ላይ ጭብጥ ይዞ በማከራከር ያልወሰነ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ከያዝነው ጉዳይ ጋር አገናዝበን ስንመለከተው በአመልካች እና በተጠሪ ባለቤት መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ይፈርሳል ወይስ አይፈርስም? የሚለው ነጥብ የክሱ ሥረ ነገር ጭብጥ ነው፡፡ ይህ የሥረ ነገር ጭብጥ በየትኛውም ደረጃ በተደረገው ክርክር ተይዞ በተከራካሪዎች መካከል ንጥጥር አልተደረገበትም፡፡



www.chilot.me

በመሆኑም ምንም የተደረገ ውል የለም የሚለው የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት መደምደሚያ የሕግ መሠረት የሌለው ነው፡፡ ተደጋግሞ እንደተገለፀው የቤት ሽያጭ ውል ስለመኖሩ አላከራከረም፡፡ ለዚህም ነው ተጠሪ የውል ይፍረስልኝ ክስ የመሠረተችው፡፡ "የግዴታዎች መቅረት "በሚለው በፍትሐብሔር ሕጉ አራተኛ መጽሐፍ አንቀጽ 12 በምዕራፍ 3 ሥር" ውሎችን ስለመሰረዝና ስለማፍረስ" የሚል ክፍል አለ፡፡ በዚህ ክፍል ሥር ከተቀመጡት ድንጋጌዎች አንዱ በሆነው በቁ.1808/2/ እንደተመለከተው ውሉ የተደረገበት ጉዳይ ወይም ምክንያት ከሕግ ውጭ ነው ወይም ለሕሊና ተቃራኒ ነው ወይም ለውሉ አጻጻፍ የተደነገገውን ፎርም አልጠበቀም የሚል መከራከሪያ /ምክንያት/ ያለው ተዋዋይ ወይም ማንኛውም ጥቅም ያለው ሰው ውሉ እንዲሰረዝ ለመጠየቅ ይችላል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ ውሉ መፍረስ አለበት የሚል እምነት ስላላት የውል ይፍረስ ክስ መስርታለች፡፡ ውሉ የሚፈርስበት የሕግና የፍሬ ነገር ምክንያት አለ ወይስ የለም የሚለው የሥረ ነገር ክርክር በዝርዝር የሚታየው ክሱ በቀረበለት ፍ/ቤት እንደሆነም ግልጽ ነው፡፡ በእርግጥም ውሉ የሕጉን ፎርም አልጠበቀም የሚል ክርክር የሚነሳ ቢሆን የሚታየው ከፍ ሲል ከጠቀሰነው ድንጋጌ አንፃር ነው፡፡ በዚህ አግባብ ውሉ ፈራሽ ነው ካልተባለ ደግሞ ተጠሪ በቀጥታ ቤቱን ትረከብ ዘንድ መወሰን የሚቻልበት አካሄድ የለም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ቤቱ ተሸጦአል መባሉን በመቋወም ክስ እስከ መሠረተች ድረስ ክርክሩ እስከመጨረሻው ድረስ ተኪዶ ሳይታይ ከወዲሁ ልትሰናበት አይገባም፡፡ ነገሩን አጠቃለን ስንመለከተው የሥር ፍ/ቤቶች ወደ ድምዳሜ የደረሱት ክርክሩ መመራት ባለበት አግባብ ሳይመሩ ተገቢም ጭብጥ ሳይዙ ነው ለማለት ችለናል፡፡ ይህ ደግሞ ከሕጉ አተገባበር አንፃር ሲታይ መሠረታዊ ስህተት ነው፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 01887 መጋቢት 20 ቀን 96ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 31308 ሐምሌ 22 ቀን 2000ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 40132 ጥር 4 ቀን 2001ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሸረዋል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክሩን በተከፈተው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ በቅድሚያ ለተጠሪ የክስ መነሻ የሆነው ውል ይፈርሳል ወይስ አይፈርስም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ፤ ግራ ቀኝ ወገኖች በዚህ ረገድ የሚያቀርቡትን የሕግና የፍሬ ነገር ክርክር ከሰማ በኂላ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ሶ/በ**



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 44873

ጥር 13 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ሰሚር ሱሩር - ጠበቃ በፀሎት መኮንን ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1. ወ/ሮ ስንዱ ዱባለ - አልቀረቡም

2. አቶ መርሀፅድቅ ድጋፌ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካች በአዲስ አበባ በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 05/08 በቤት ቁጥር 441 በንግድ ፈቃድ ቁጥር 03/01/3/00/69/95 የሚያካሂዱትን የንግድ ድርጅት በብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) ተጠሪዎች ጥቅምት 28 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የውል ሰነድ ሸጠውልኛል ተጠሪዎች ብር 40,000(አርባ ሺህ ብር) በቼክ ተቀብለው ወስደዋል፡፡ ቀሪውን ብር 160,000(መቶ ስልሳ ሺህ ብር) የንግድ ድርጅቱን ሽያጭ በውልና ማስረጃ ፈርመውና ባለሀብትነቱን ተጠሪዎች ሲያስተላልፉ ሊከፈላቸው ተስማምተናል፡፡ ሆኖም ተጠሪዎች (ተከሳሽ) በውሉ መሠረት ለመፈፀም ፈቃደኛ ሣይሆኑ በመቅረታቸው ተከሳሾች (ተጠሪዎች) የሸጡት ድርጅት ከዕዳና ዕገዳ ነፃ አድርገውና ማናቸውም አስፈላጊ ፎርማሊቲ አጠናቀው እንዲያስረክቡና መቀጫውንም እንዲከፍሉ ውሣኔ ይሰጥልን በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀርበው ከሳሽ (አመልካች) በውሉ ላይ አልፈረሙም ውሉም ሲደረግ አልነበሩም፡፡ የቅድሚያ ክፍያው በወቅቱ አልተፈፀመም፡፡ ውሉ በውል አዋዋይ ፊት ያልተደረገ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የለውም፡፡ ከሳሽ የበኩላቸውን ግዴታ እንዲወጡ በደብዳቤ ተጠይቀው ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ውሉ መፍረሡን አሣውቀናቸዋል፡፡ ከሳሽ ውሉን በግድ የማሣወቅ ሀሳብ ያላቸው መሆኑን አስቀድመው ያላሣወቁን በመሆኑ ውሉ በግዴታ ይፈፀምልኝ በማለት ክስ ማቅረብ አይችሉም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ አመልካች በውሉ ላይ በወኪላቸው በአቶ ሰብሀ ሱሩር አማካኝነት የፈረሙ ስለሆነ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ውል አለ፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ አመልካች



www.chilot.me

ፅፈው የሰጧቸውን ቼክ ባንክ ወስደው መንዝረዋል፡፡ ስለዚህ የንግድ ድርጅት ሽያጭ ውል ተዋዋዮች ስምምነታቸውን የሰጡበት ውል ነው፡፡ ውሉ በፅሑፍ የተደረገ ስለሆነ በህጉ የተቀመጠውን ፎርም ያሟላ ነው፡፡ ሆኖም ከሳሽ አመልካች በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2331 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ውሉ በግዴታ እንዲፈፀምለት የሚያስገድድ ስለመሆኑ ለሻጭዎች (ተጠሪዎች) ያልገለፀ በመሆኑና ውሉ የተለየ ጥቅም የሚያስገኝ መሆኑን ያላስረዳ በመሆኑ የንግድ ድርጅት ሽያጭ ውሉ እንዲፈፀምለት ከሳሽ (አመልካች) የመጠየቅ መብት የለውም በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ የህግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት የለበትም በማለት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

አመልካች መጋቢት 18 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪዎች የንግድ ድርጅቱን የሚያስረክቡት እስከ ህዳር 28 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ ነው፣ የአመልካች ወኪል ተጠሪዎች ገንዘቡን ተቀብለው የንግድ ድርጅቱን እንዲያስረክቡ በምስክሮች ፊት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎች ታህሣሥ 10 ቀን 2000 ዓ.ም ውሉን አፍርሠናል በማለት ደብዳቤ የፃፉት መጀመሪያም ያሰቡበት ጉዳይ ነው፡፡ የውሉ መፈፀሚያ የጊዜ ገደብ ስለሚታወቅ ማስጠንቀቂያ መስጠት አስፈላጊ አልነበረም፡፡ የተከፈለው ብር 40,000 አላግባብ በዝምታ ታልፏል፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሉን በግዴታ ለመፈፀም ለመጠየቅ አመልካች አይችልም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው በቃል ባቀረቡት ክርክር የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ውሉ በግዴታ ለመፈፀም ልዩ ጥቅምና ፍላጎት ያላቸው መሆኑን አለማስረዳታቸውንና ውሉ በግዴታ እንዲፈፀም ለመጠየቅ የሰጡት ማስጠንቀቂያ አለመኖሩን በማረጋገጥ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች በቃል የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሑፍና የቃል ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች የንግድ ድርጅት ሽያጭ ውል በግድ እንዲፈፀም አመልካች ለመጠየቅ አይችሉም በማለት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም ውሉ በግዴታ አይፈፀምም ቢባል አመልካች ለተጠሪዎች የከፈሉት ብር 40,000 (አርባ ሺህ ብር) በተመለከተ ውሣኔ ሣይሰጡ ማለፋቸው ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉት ጭብጦች መፈታት ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

1. የመጀመሪያውን ጭብጥ ለመፍታት የሽያጭ ውልን በግዴታ ስለመፈፀም የተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና አላማ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመርህ ደረጃ ገዥ ሻጭ የሽያጭ ውሉን በግድ እንዲፈፅምለት ለመጠየቅ የሚችለው ውሉ ልዩ የሆነ ጥቅም የሚያስገኝለት ሆኖ ሲታየው እንደሆነ የፍታበሔር ህግ ቁጥር 2329 ይደነግጋል፡፡ ገዥው በሽያጭ ውሉ ላይ ልዩ ጥቅም አለው የሚባለውና የሽያጭ ውሉን ሻጭ በፍርድ ሀይል ተገድዶ እንዲፈፅም ፍርድ ቤቶች ለመወሰን የሚችሉት የሽያጭ ስምምነት የተደረገበት ዕቃ በልማድ ምትክ ሊገዛበት የማይቻል የሆነ እንደሆነ ወይም የተባለውን ምትክ ለመግዛት ገዥው ላይ ከፍ ያለ ወጭና ችግር የሚያስከትልበት የሆነ እንደሆነ መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2330 ይደነግጋል፡፡ አመልካች የንግድ ድርጅት ሽያጭ ውሉ ልዩ ጥቅም የሚያስገኝላቸው መሆኑንና የንግድ ድርጅቱ ምትክ ሌላ የንግድ ድርጅት መግዛት የማይችሉ ስለመሆናቸው ወይም ሌላ የንግድ ድርጅት ለመግዛት ቢሞክሩ ከፍተኛ ወጭና ችግር የሚያስከትልባቸው ስለመሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት በክሳቸው እንዳልገለፁ ማስረጃ በማቅረብም እንዳላስረዱ የሥር ፍርድ ቤት በሰጠው



www.chilot.me

ውሳኔ አረጋግጧል፡፡ አመልካች የሽያጭ ውሉ በግድ እንዲፈፀም ለመጠየቅ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2329 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2330 የተደነገጉት ሁኔታዎች መኖራቸውን የማስረዳት ግዴታ ያለባቸው ሲሆን አመልካች ይህንን ግዴታቸውን ያልተወጡ መሆኑን በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ውለታን በግድ ስለመፈፀም በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1778፣ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2329 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2330 ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገ በመሆኑ በዚህ በኩል አመልካች ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የንግድ መደብር ሽያጭ ውሉ እስከ ህዳር 28 ቀን 2000 ዓ.ም የሚፈፀም ስለመሆኑ የአመልካችና ተጠሪዎች ባደረጉት ውል የተገለፀ ቢሆንም የሽያጭ ውሉ በግዴታ እንዲፈፀምለት የሚፈልግ ገዥ ውሉ በግዴታ እንዲፈፀምለት የማስገደድ ሀሳብ ያለው መሆኑን ለሻጭ ካልገለፀ ውሉን በፍርድ ሀይል ተገድዶ ሻጭ እንዲፈፅም ቢደረግ መብቱን እንደሚያጣ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2330 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ አመልካች በዚህ ድንጋጌ መሠረት ማስጠንቀቂያ ያልሰጠ መሆኑንና ይልቁንም ተጠሪዎች ውሉን አፍርሰናል በማለት ቀድመው ለአመልካች በፅሑፍ ያሣወቁ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአመልካችና በተጠሪ ውል ላይ የተገለፀው የጊዜ ገደብ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2331 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን ጥብቅ መሥፈርት የሚያሟላ አይደለም፡፡ ይኸም በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የንግድ ድርጅት ሽያጭ ውሉ በግዴታ እንዲፈፀምላቸው አመልካች የመጠየቅ መብት የላቸውም በማለት የሰጡት ውሣኔና የደረሱበት መደምደሚያ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

2. ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች በቼክ ብር 40,000 (አርባ ሺህ ብር) ለተጠሪዎች የከፈሉና ሁለተኛው ተጠሪ ቼኩን በገንዘብ መንዝረው ከባንክ የወሰዱ መሆናቸው በሥር ፍርድ ቤት አንስተው አመልካች የተከራከሩበት ሲሆን ተጠሪ ይህንን በመካድ የሰጡት መልስ የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ብር 40,000 የከፈሉ መሆኑን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 235 መሠረት ያመኑ መሆኑን ግራቀኙ ካደረጉት ክርክር ለመገንዘብ ችለናል፡፡ የሽያጭ ውሉ በግዴታ ሊፈፀም አይገባውም ከተባለ ተከራካሪዎች ውሉ ከመደረጉ በፊት ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ማድረግና ለውሉ አለመፈፀም ኃላፊ የሆነው ተዋዋይ ሌላኛው ተዋዋይ ወገን የደረሰበትን ኪሣራ የመተካት ኃላፊነት እንደሚኖርበት ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1815 እና ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1790 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡

አመልካች ውሉ በግዴታ የማይፈፀም ከሆነ በአማራጭ ውሉ ባለመፈፀሙ የደረሰበትን የኪሣራ መጠን በመግለፅ ተጠሪዎች ኪሣራ እንዲከፍሉት የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ የለም፡፡ በዚህ በኩል አመልካች ያልጠየቁት ዳኝነት በመሆኑ በውሉ መሠረት ባለመፈፀሙ ተጠሪዎች የሚከፍሉት ካሣ የለም፡፡ ሆኖም ተጠሪዎች ከአመልካች በቼክ ተቀብለው የወሰዱትን ብር 40,000 (አርባ ሺህ ብር) ለአመልካች የመመለስ ግዴታ ያለባቸው መሆኑ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1815 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ የተደነገገ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎች ከአመልካች የወሰዱትን ብር 40,000(አርባ ሺህ ብር) እንዲከፍሉ አለመወሰናቸው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ይህንን የውሣኔ ክፍል ብቻ በማሻሻል ተጠሪዎች ለአመልካች ብር 40,000(አርባ ሺህ ብር) የመክፈል ግዴታና ሀላፊነት አለባቸው በማለት ወስነናል፡፡



www.chilot.me

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪዎች የንግድ ድርጅት ሽያጭ ውሉን በግዴታ እንዲፈፅሙ አይገደዱም በማለት ወስነናል፡፡
3. ተጠሪዎች ለአመልካች ብር 40,000(አርባ ሺህ ብር) ይክፈሉ በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ



www.chilot.me

*የሰ/መ/ቁ. 59882*

*የካቲት 21 ቀን 2003 ዓ.ም*

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ አሰገደች ዘርጋው ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ አየለ ንዳኔ ጠበቃ አቶ ዘነበ አሰፋ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የሰበር ማመልከቻ ስላቀረቡ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረቡት የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርቦ ተከሳሽ /አመልካች/ መጋቢት 19 ቀን 2000 ዓ.ም በተደረገ የብድር ውል ስምምነት ብር 105,000 /አንድ መቶ አምስት ሺህ ብር/ ወስደዋል፡፡ ተከሳሽ /አመልካች/ የተበደሩትን ገንዘብ እስከ ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ ሊከፍሉ በዚህ ጊዜ ውስጥ ካልከፈሉ ቅጣት ብር 30,000 /ሰላሣ ሺህ ብር/ ጨምረው ሊከፍሉ ተስማምተዋል፡፡ ተከሳሽ የብድር ገንዘቡን በውሉ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ያልከፈሉ በመሆኑ ብር 135,000 /አንድ መቶ ሰላሣ አምስት ሺህ ብር/ ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀረበው ከከሳሽ /ተጠሪ/ ጋር የብድር ውል ያደረግሁ መሆኑ አይካድም፡፡ ሆኖም ከሳሽ /ተጠሪ/ ውሉን ካስፈረሙኝ በኃላ የውሉን ኮፒ ላምጣ ብለው ገንዘቡን ሣይሰጡኝ በመሰወራቸው ጉዳዩን በሽምግልና ስከታተል ቆይቼ አሁን በወንጀል ከስሼ መያዣ ወጥቶባቸዋል፡፡ ስለሆነም ከሳሽ /ተጠሪ/ የብድር ውሉ ገንዘቡን ተቀብያለሁ ብዬ ከፈረምኩ በኃላ ገንዘቡን ሣይሰጠኝ የተሰወረ በመሆኑ ውሉ ፈራሽ ተደርጎ ክሱ ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ተከሳሽ /አመልካች/ ብር 105,000 በብድር ከከሳሽ /ተጠሪ/ የወሰዱ መሆኑን በመግለፅ መጋቢት 19 ቀን 2000 ዓ.ም በተደረገው የብድር ውል ላይ ፈርመዋል፡፡ ስለሆነም ተከሳሽ /አመልካች/ በውል ወስጃለሁ ብለው በፅሑፍ ያረጋገጡትን ገንዘብ ተጠሪ /ከሳሽ/ ያልሰጠኝ መሆኑን በሰው ምስክር ላስተባብል በማለት ያቀረቡት ክርክር የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2005/1/ እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2006 ድንጋጌዎችን የሚቃረን በመሆኑ የህግ መሠረት የለውም፡፡ ውሉ በተንኮል የተደረገ አይደለም ውሉ ለሞራልና ለህግ ተቃራኒ አይደለም፡፡ ስለሆነም ተከሳሽ /አመልካች/ የተበደሩትን ብር 105,000 በውሉ የተስማሙትን የቅጣት ገንዘብ ብር 30,000 በድምሩ



www.chilot.me

135,000 /አንድ መቶ ሰላሣ አምስት ሺህ ብር/ ከሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ይከፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል አመልካች ነሐሴ 17 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በእኔና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል በተንኮል ላይ የተመሠረተና ተጠሪ ግዴታቸውን ያልተወጡበት ውል ነው፡፡ በውሉ የተገለፀውን ገንዘብ ያልሰጡኝ መሆኑን በምስክሮች ለማስረዳት ያቀረብኩት ጥያቄ የበታች ፍርድ ቤቶች ውድቅ ማድረጋቸው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1704 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2009/1/ን ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው አመልካችና እኔ ያደረግነው የብድር ውል ገንዘቡን መውሰዳቸውን ያረጋግጣል፡፡ አመልካች ተዋዋይ እንጅ ሶስተኛ ወገን ባለመሆናቸው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2009 በጉዳዩ አግባብነት የለውም፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች የፍታብሔር ህግ አንቀፅ 2005 እና አንቀፅ 2006ን መሠረት በማድረግ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ የሰበር አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት ህዳር 29 ቀን 2003 ዓ.ም በፅሑፍ ባቀረቡት መልስ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ታህሣሥ 14 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ ተጠሪ ውሉ መፈረሙን እንጂ ውሉ መፈፁሙን አላስረዳም፡፡ እኔ ውሉ ከተፈረመ በኃላ የብድር ገንዘቡን ያለሰጠኝ መሆኑን በማስረጃ ለማስተባበል ያቀረብኩት ጥያቄ አላግባብ ተከልክያለሁ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ብር 105,000 /አንድ መቶ አምስት ሺህ ብር/ የብድር ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍሉ የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም; የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ብር 30,000/ሰላሣ ሺህ ብር/ እና ወለድ ለተጠሪ እንዲከፍሉ የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚሉት ጭብጦች መታየት ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

1. የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች ከተጠሪ ብር 105,000/አንድ መቶ አምስት ሺህ ብር/ በብድር ከተጠሪ ተቀብለው የወሰዱ መሆኑን አመልካችና ተጠሪ መጋቢት 19 ቀን 2000 ዓ.ም ባደረጉት የብድር ውል አረጋግጠው ፈርመዋል፡፡ አመልካች ውሉ በተንኮል የተደረገ ነው፡፡ ተጠሪ ከፈረምኩለት በኃላ በውሉ ላይ የተጠቀሰውን ገንዘብ አልሰጠኝም፡፡ ውሉ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ስለሆነ ፈራሽ ነው የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ አመልካች ከተጠሪ በውሉ የተገለፀውን ገንዘብ ለመበደር ወደውና ፈቅደው የብድር ውል ስምምነት ያደረጉ መሆኑንና በብድር ውሉ ላይ የፈረሙ መሆኑ በአመልካች የተካደ ፍሬ ጉዳይ አይደለም፡፡ ከዚህ የምንረዳው አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት የብድር ውል በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1698 በተደነገገው መሠረት መሠረታዊ ስህተት የሌለበት በመሆኑና ውሉ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1704 በሚደነግገው መሠረት በተንኮል የተደረገ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ያልቀረበበት በመሆኑ አመልካች ውሉ ፈራሽ ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የህግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የአመልካች ክርክር በባህሪው የብድር ውል ስምምነት ሲደረግ ውሉ ጉድለት አለበት የሚል ሣይሆን ተጠሪ በብድር ውሉ መሠረት የብድር ገንዘቡን አልሰጠኝም በውሉ የተገለፀውን ግዴታውን አልተወጣም የሚል ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው አመልካች የብድር ገንዘቡን የተቀበሉ መሆኑን በነፃ ፈቃዳቸው አንብበው ተስማምተው በፊርማቸው ያረጋገጡ መሆኑን መጋቢት 19 ቀን



www.chilot.me

2000 የተደረገው የብድር ውል አስረጅ ነው፡፡ ስለዚህ አመልካች ገንዘብን አልተቀበልኩም በማለት የሚያቀረቡት ክርክር ተገቢ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችና ተጠሪ መጋቢት 19 ቀን 2000 ዓ.ም ያደረጉት ውል አመልካች በውሉ ሰነድ የተገለፀውን ገንዘብ ከተጠሪ ተቀብለው የወሰዱ ስለመሆኑ ሙሉ እምነት የሚጣልበት በቂ መስረጃ እንደሆነ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2005 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገ በመሆኑና አመልካች በብድር ውሉ ላይ ከተጠሪ ገንዘብ የተቀበሉ መሆኑን የሚገልፀውን ህግ በሰው ምስክር ወይም በህሊና ግምት ማስረጃ በማቅረብ ለማስተባበል እንደማይፈቅድላቸው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2006 ንዑስ አንቀፅ 2 አስገዳጅ ድንጋጌ የተደረነገገ በመሆኑ አመልካች ገንዘቡን ያልተቀበልኩ መሆኑን በምሰክር እንዳላስረዳ የበታች ፍርድ ቤቶች አላግባብ ከለከሉኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ የህግ መሠረትና ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ አመልካች በብድር ውሉ ገንዘብ እንደተቀበሉ የሚገልፀውን ሀይለ ቃል ለመቃወም የሚችሉት ተጠሪ ቃለ መሀላ እንዲፈፅም በመጠየቅ እንደሆነ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2006 ንዑስ አንቀፅ 1 ተደንግጓል፡፡ አመልካች ተጠሪ ቃለ መሀላ እንዲፈፅምላቸው ያቀረቡት ክርክር ያሌለ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ አመልካች የተበደሩትን ብር 105,000 /መቶ አምስት ሺህ ብር / ለተጠሪ እንዲከፍሉ የሰጡት ውሣኔ ከላይ የተገለፁትን የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገና የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ የአመልካችን አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡

2. ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች መጋቢት 19 ቀን 2000 ዓ.ም በብድር የወሰዱትን ገንዘብ እስከ ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም ለመመለስ የብድር ገንዘቡን እስከ ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም ካልመለሱ መቀጫ ብር 30,000 /ሰላሳ ሺህ ብር/ ለተጠሪ ለመክፈል ተስማምተዋል፡፡ አንደኛው ወገን ግዴታውን ያልፈፀመ ወይም አጉድሎ ወይም አዘግይቶ የፈፀመ እንደሆነ የሚከፍለውን መቀጮ ተዋዋዬቹ አስቀድመው በውላቸው ለመወሰን እንደሚችሉ በመሠረታዊ መርህነት በፍታሔር ህግ ቁጥር 1889 ተደንግጓል፡፡ ሆኖም ከዚህ ጠቅላላ መርህ የሚገድቡ በልዩ ሁኔታ የተደገነጉ ድንጋጌዎች ተዋዋዬች የሚያደርጉትን የመቀጫ ስምምነት መጠን የሚገደቡና የሚከለክሉ በሆነ ጊዜ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1889 ድንጋጌ ተጠቃሽና ተፈፃሚ የሚሆንበት ምክንያት የሌለ መሆኑን ተቀባይነት ካለው የህግ ድንጋጌዎች አተረጓጎም ለመረዳት ይቻላል፡፡ የብድር ገንዘብ አመላለሱን አስመልክቶ ተበዳሪው የብድር ገንዘቡን በውሉ በተጠቀሰው ጊዜ ከመክፈል የዘገየ እንደሆነ ለአበዳሪው በኪሣራ መልክ የሚከፍለው በፍታብሔር ህጉ በተደነገገው መሠረት የወለድ ገንዘብ እንደሆነ በፍታብሐር ህግ ቁጥር 2489 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገ ሲሆን በህግ ከተፈቀደው የወለድ መጠን በላይ ተበዳሪው መቀጫ እንዲከፈል የሚደረግ ስምምነት ፈራሽ እንዲሆን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2489 ንዑስ አንቀፅ 2 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች በተጠሪ በብድር የወሰዱትን ገንዘብ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ማለትም እስከ ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም ካልመለሱ ብር 30,000 /ሰላሣ ሺህ ብር/ ለተጠሪ ለመክፈል ያደረጉት ስምምነት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2489 ንዑስ አንቀፅ 2 አስገዳጅ ድንጋጌን የሚጥስና ህጋዊ ውጤት የሌለው ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በመቀጫ መልክ በተጠሪ ብር 30,000 /ሰላሣ ሺህ ብር/ ለመክፈል ያደረጉት ስምምነት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1889 ከተደነገገው ጠቅላላ መርህ በተለየ ሁኔታ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2489 ንዑስ አንቀፅ 2 ክልከላ የተደረገበት መሆኑን ሣያገናዝቡ የሰጡትና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ አመልካች በብድር ውሉ መሠረት ገንዘቡን በወቅቱ ባለመመለሳቸው መቀጫ ለተጠሪ ብር 30,000 /ሰላሣ ሺህ ብር/ እንዲከፍሉ በወሰኑት የበታች ፍርድ



www.chilot.me

ቤቶች በተደራቢነት አመልካች የዋናውን ብድርና የመቀጫ ገንዘቡ ከሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ የሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ እንዲከፍሉ የሰጡት ውሣኔ ህጋዊ መሠረት የሌለውና የአመልካችና የተጠሪን የብድር ውል ስምምነት መሠረታዊ ይዘትና የሚያስከትለውን ህጋዊ ውጤት ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተጠሪ ብር 105,000 /አንድ መቶ አምስት ሺህ ብር/ የሆነውን የብድር ገንዘብ ብድሩ መመለስ ካለበት ከሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርስንት ወለድ ጋር እንዲከፍሉ የሰጡት ውሣኔ የህግ ስህተት የለበትም፡፡ ሆኖም አመልካች ለተጠሪ መቀጫ ብር 30,000 /ሰላሣ ሺህ ብር/ ከሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርስንት ወለድ ጋር እንዲከፍሉ የሰጡት ውሣኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2489 ንዑስ አንቀፅ 2 አስገዳጅ ድንጋጌን የሚጥስና መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2009 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌን በመጥቀስ በብድር ውሉ ላይ ገንዘብ ተቀብያለሁ በሚል አገላለፅ የተፃፈው ቃል ሀሰተኛ መሆኑን በምስክር ለማስተባበል ያቀረቡት ጥያቄ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2009 ንዑስ አንቀፅ 1 ይዘትና ተፈፃሚነት ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2009 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በውል ሰነድ የተፃፈን ቃል ሀሰተኛ መሆኑን በማናቸውም አይነት ማስረጃ ለማስተባበል ሰነዱን የፃፈው ወይም የተቀበለው የመንግስት መሥሪያ ቤት ባለሥልጣን አለመሆኑን በውሉ ላይ የተፃፈውን ቃል ለማስተባበል ጥያቄ ያቀረበው ሰው የውሉ ተዋዋይ ሣይሆን ሶስተኛ ወገን ተከራካሪ መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚገባ በግልፅ ይደነግጋል፡፡

በያዝነው ጉዳዩ የአመልካችና የተጠሪ ውል በመንግስት መሥሪያ ቤት ባለስልጣን የፃፈው ወይም የተቀበለው ሰነድ አለመሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም በውሉ ውስጥ ያለውን ቃል ሀሰተኛነት ለማስተባበል የጠየቁት አመልካች የብድር ውሉ ተዋዋይ ወገን እንጂ ሶስተኛ ወገን ተከራካሪ አይደሉም፡፡ ስለሆነም አመልካች የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2009 ድንጋጌዎችን በመጥቀስ የውሉን ቃል ሀሰተኛነት በምስክር ለማስረዳት ያቀረቡት ጥያቄ የህግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤት ብር 30,000 /ሠላሣ ሺህ ብር/ መቀጮና ለዚህ የመቀጮ ገንዘብ ከሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ የሚታሰብ ወለድ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ የሰጡት የውሣኔ ክፍል ብቻ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትና በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ሊሻሻል የሚገባው ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ብር 105,000 /መቶ አምስት ሺህ ብር/ ከሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ለተጠሪ ይክፈሉ በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች የመቀጫ ገንዘብ ብር 30,000 /ሰላሣ ሺህ ብር/ እና ይህ የመቀጫ ገንዘብ የሚወልደውን ወለድ ለተጠሪ የመክፈል ግዴታና ኃላፊነት የለባቸውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቅ/መ

# ወንጀል



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 46412

ጥቅምት 30 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- የሐረሪ ክልል ዐቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም፡፡

**ተጠሪ** ፡- ቦና አህመድ አሚን - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ እድሜአቸው አስራ ሦስት ዓመት በሆነና አስራ ስምንት ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የሚፈፀም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ተጠሪ ሕዳር 07 ቀን 2000 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 4፡00 ስዓት በሚሆንበት ጊዜ በሐረሪ ክልል በቀበሌ 19 ልዩ ስሙ ንደ ጎቤ ተብሎ በሚጠራ ስፍራ የግል ተበዳይ የሆነችውን የ15 ዓመት ሕፃን ዘሙ አህመድን በመኖሪያ ቤት ውስጥ በር ዘግቶባት መብራት አጥፋቶ አፏንና አፍንጫዋን በማፈን እንዳትጮህ በማድረግ ለመከላከል በማትችልበት ሁኔታ ውስጥ ካደረገ በሁዋላ አስገድዶ የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመፈፀሙ በ1996 ዓ.ም በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 620 ስር የተመለከተውን ተላልፏል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም ክሱ ተነቦለት እንዲረዳው ከተደረገ በሁዋላ በክሱ ላይ ተቃውሞ የሌለው መሆኑን ገልጾ ስለድርጊቱ አፈፃፀም ግን የክህደት ቃል ሰጥቷል፡፡ ከዚህም በኋላ አቃቤ ሕግ እንደክሱ ያስረዱልኛል ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅረቦ ከአሰማ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ከግል ተበዳይ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸመው በኃይል ተግባር ሳይሆን በግል ተበዳይ መልካም ፈቃድ ስለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ተጠሪን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 141 መሠረት በነፃ አሰናብቶታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በሁዋላ ተጠሪ የግል ተበዳይ ላይ የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀማቸው በአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች መረጋገጡን እንደስር ፍርድ ቤት አባባል ተቀብሎ ድርጊቱ በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕግ አንቀጽ 620 ስር የሚሸፈን መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ ተጠሪ እድሜው 16 አመት የግል ተበዳይ ደግሞ እድሜዋ 15 አመት መሆኗንና እንደዚህ አይነት ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ ምን መሆን እንዳለበት የወንጀል ሕጉ ምንም የሚሰጠው ምላሽ የሌለ መሆኑ በመጥቀስ እና በማመሳሰል ደግሞ ተጠያቂነትን ማስከተል እንደማይቻል ሕጉ በአንቀጽ 2(3) ስር ያስቀመጠው መርህ መሆኑን በዋቢነትይዞ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪን በነፃ በማሰናበት የሠጠውን ውሳኔ በውጤት ደረጃ ተገቢ

መሆኑን በመቀበል አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሳኔ ባለመስማማት ነው፡፡

አመልካች አቃቤ ሕግ ሚያዝያ 28 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ሦስት ገጽ የሰበር አቤተታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2(3)፣ 56፣211 እና 626ን እንዲሁም የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁጥር 113(2) ድንጋጌዎችን መንፈስና ይዘት ያላገናዘበ መሆኑን በመዘርዘር ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 626(1) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ መተላለፉ ተረጋግጧል ተብሎ እንዲከላከል ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታመኑ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጉለት ቀርቦ መጋቢት 14 ቀን 2002 ዓ.ም በጠበቃው አመካኝነት በተጻፈ ማመልከቻ መልሱን ሰጥቷል፡፡ አመልካችም የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪው የወንጀል ተጠያቂነት የሚከተልበት አይደለም ተብሎ ከክሱ ነፃ መባሉ ሕጋዊ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ እድሜዋ አስራ አምስት አመት ከሆናት ሕፃን ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀሙ መረጋገጡን ሁለቱም የስር ፍርድ ቤቶች የተቀበሉት ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡ የተጠሪ ጠበቃ በዚህ ችሎት ባቀረቡት የፁሑፍ መልስ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈፀመ መሆኑ አልተረጋገጠም በሚል ተከራክረዋል፡፡ ሆኖም ይህ ችሎት በዚህ ረገድ የበታች ፍርድ ቤቶች የደረሱበትን የማስረጃ ምዘና ድምዳሜ ለመመልከት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕግ መንግሥት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት ስልጣን የሌለው በመሆኑ የተጠሪ ጠበቃ ክርክር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ተጠሪ ከግል ተበዳይ ጋር ግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈፀመ በተባለበት ጊዜ እድሜው አስራ ስድስት አመት የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከወንጀሉ ነፃ ነው የተባለውም የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 626(1) የግል ተበዳይና የድርጊቱ ፈፃሚ እድሜው በአስራ ሶስት አመትና በአስራ ስምንት አመት ክልል ውስጥ ከሆኑ ሕጉ ምላሽ አይሰጥም በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የድንጋጌው አቀራረጽ ሲታይ ማንም ሰው ተቃራኒ ጾታ ካላትና እድሜዋ ከአስራ ሦስት ዓመት በላይ ሆኖ አስራ ስምንት ዓመት ካልሞላት ልጅ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈፀመ ወይም ይህችው ልጅ እንዲህ አይነቱን ድርጊት ከእርሱ ጋር እንድትፈጽም ያደረገ እንደሆነ በሚል የተቀመጠ ሲሆን “ማንም ሰው….የሚለው የሕጉ አገላለጽ የወንጀል ሐላፊነትን በተመለከተ የተደነገጉትን የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎችን ማለትም ከአንቀጽ 48 እስከ 56 ድረስ የተመለከቱትን ግንዛቤ ውሰጥ ባስገባ መልኩ መታየት ያለበት መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 56 ድንጋጌ በተለይም ሲታይም እድሜአቸው ከአስራ አምስት ዓመት በላይ ከ18 ዓመት በታች ያሉ ወጣት ወንጀል አድራጊዎች ከተጠያቂነት የሚድኑ አለመሆኑን የሚያሳይ ሆኖ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ እድሜው ሲታይ ከወንጀል ተጠያቂነት ነፃ የሚሆንበት ህጋዊ ምክንያት የለም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 626(1) ስር የተቀመጠው ድንጋጌ ትኩረት የሚያደርገው የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም ወይም እንድትፈጽም ማድረግ የወንጀል ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡ አስራ ሶስት አመት በሆናትና



www.chilot.me

አስራ ስምንት አመት ካልሞላት ልጅ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ያደረገ ወንድ እድሜው በዚሁ የእድሜ ክልል መገኘት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 211(1) መሠረት ታይቶ የግል ተበዳይን ተጠያቂነት ከማያመጣ በስተቀር ተጠሪን ከወንጀሉ ነፃ የሚያደርገው አይደለም፡፡ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚፈጽሙ ወንድና ሴት እድሜያቸው በአስራ ሶስት አመትና በአስራ ስምንት አመት መካከል መገኘት ሁለቱንም የወንጀል ተጠያቂነት ያስቀርላቸዋል ብሎ መደምደም የሕጉ አላማ አይደለም፡፡ በዚህ እድሜ መካከል ያሉት ሕፃናት ተገቢ ላልሆነ ድርጊት እንዳይጋለጡ መከላከል የሕጉ አላማ ነው ተብሎም ይታመናል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤት የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 2(3)ን የጠቀሰው ያለቦታው ሆኖ አግኝተናል፡፡ ተጠሪ እድሜዋ አሥራ አምስት አመት ከሆናት ሕፃን ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀሙ ተረጋጋጧል ከተባለና ድርጊቱ በአቃቤ ሕጉ የክስ ማመልከቻ ስር ከተጠቀሰው ድንጋጌ ያነሰ ሁኖ ከተገኘ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 113(2) መሠረት ተጠሪ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 56 እና 626(1) ድንጋጌ አንጻር እንዲከላከል መደረግ ነበረበት፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪን ሳይከላከል የወንጀል ተጠያቂነት የለበትም በማለት የሰጡት ውሳኔ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 56፣211 እና 626(1) ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ እንዲሁም የወንጀል ሕጉን ዓላማ ያላገናዘበ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2)(ሀ) መሠረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ በ1996ቱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 626(1) ስር በተመለከተው ሁኔታ ድርጊቱን መፈጸሙን አቃቤ ሕጉ ያስረዳ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች የተቀበሉት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ መከላከያ ካለው እንዲያቀርብ አድርጉና ማስረጃዎቹን ሰምቶ ተገቢውን እንዲወሰን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2(ሀ) መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 54839

ጥቅምት 30 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- አቶ ኢምራን ጉደሣ አብዲ ጠበቃ ገዛኸኝ ፍቅሬ ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ፍርድ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡

የክርክሩ መሠረታዊ ነጥቦች የፌዴራል ዐ/ሕግ በአመልካች ላይ ያቀረባቸው ሁለት የወንጀል ክሶች ናቸው፡፡ ዐቃቤሕግ አመልካች በወንጀል ህግ አንቀጽ 598(2) የተመለከተውን በመተላለፍ ሴቶችን ወደ ውጭ ለመላክ የሚያስችል ህጋዊ ፈቃድ ሣይኖረው ሰኔ 22 ቀን 2001 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03/02 ክልል ውስጥ ወ/ሮ መቅደስ ንጉሴን ኩዌት ከሚባል ሀገር በሠራተኝነት እልክሻለሁ ብሎ ብር 2000 /ሁለት ሺህ ብር/ ተቀብሎ ልኳት በሣምንት አንድ ቀን ጽዳት ትሠሪያለሽ ተብላ ከተቀጠረች በኋላ ሥራው በጣም ስለከበዳት ወደ አገሯ ለመመለስ ስትጠይቅ ሁለት ወር ከአስር ቀን የነፃነት መብቷ በአንድ ክፍል ውስጥ በመገደብ ሰብዓዊ ክብር አጥታ ለከፍተኛ እንግልት የተዳረገች በመሆኗ ዜጐችን ያለ ፈቃድ ወደ ውጭ የመላክ ወንጀል ፈጽሟል፡፡

እንደዚሁም በሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተከሳሽ ከነበረው ሰው ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)ሀ እና አንቀጽ 692(1) የተመለከተውን በመተላለፍ በአዲስ አበባ ከተማ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ከከፈተው ጽ/ቤቱ ውስጥ እነ ሀያት መሐመድ የተባሉትን አስራ ሁለት የግል ተበዳዮች ብር 6000 እስከ 6500 ብር ኩዌት ዱባይና ሣውዲአርቢያ እልካችኋለሁ በማለት ሀሰተኛውን ነገር እውነት አስመስለው ገንዘብ ተቀብለው የወሰዱና የግል ተበዳዮችን ያልላካቸው በመሆኑ የማታለል ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ክስ አቀርቧል፡፡

አመልካች የተለያዩ የክስ መቃወሚያዎችን አቅርቦ የሥር ፍርድ ቤት ውድቅ ያደረገበት ሲሆን በሁለቱም ክሶች ወንጀሉን አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ



www.chilot.me

አንደኛውን ክስ ለማስረዳት የግል ተበዳይን ለምስክርነት አስቀርቦ ያስመሰከረ ሲሆን በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ በመቀበል አመልካችን ወደ ኩዌት አገር እንደላካትና እና አመልካች ከነገሯት በላይ የከበደ ሥር እንድትሰራ ስለተደረገች ይህንኑ ለአመልካች መናገሯን በኋላም መሐመድ ሩሄን የሚባል ኤጀንሲ 475 ዶላር ደመወዟን ቀምቶ ሁለት ወር ከአስር ቀን በአንድ ክፍል እንድትቆይ እንዳደረጋትና ነፃነቷን እንዲገደባት በመጨረሻ ቡታ ጋር አፈነዳለሁ ብላ ቢላ ይዛ በመጋበዟ ወደ አገሯ አሳፍረው እንደላኳት የመሠከረች ሲሆን ሌሎች ሁለት ምስክሮች የምስክሯን ቃል የሚያጠናክር የምስክርነት ቃል እንደሰጡ ከሥርፍርድ ቤት ውሳኔ ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ ሁለተኛውን ክስ ለማስረዳት አስራ አንድ ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ መሆኑንና ምስክሮቹም የግል ተበዳዮች እንደሆኑ አመልካችና በሥር ሁለተኛ ተከሳሽ የነበረው የማነ ወይም አሚር ገብረማርያም እያንዳንዳቸው ዱባይ ሣውዲአረቢያ ኩዌት እንልካችኋለን በማለት ብር 6000 እስከ 6500 የተቀበላቸው መሆኑን መሥክረዋል፡፡ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ የሥር ፍርድ ቤት በሰጠውብይን መሠረት አንደኛውን ክስ በተመለከተ በህግ በተሰጠኝ ፈቃድ ትኬት ቆርጬ ከመስጠት ውጪ የግል ተበዳይን ወደ ውጭ አልላኩም በሁለተኛው ክስ የተመለከተውን ተግባርም ያልፈፀምኩ ስለመሆኔ ያስረዳልኛል በማለት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ማስረጃቸውን ከመዘነ በኋላ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበውን ሁለት ክሶች የተጠቀሰውን የወንጀል ተግባር አመልካች የፈፀመ መሆኑን በበቂ ማስረጃ አስረድቷል፡፡ የአመልካች የመከላከያ ማስረጃ ታዓማኒነት የሌለውና የተጠሪን ክስ የሚያስተባብል አይደለም በማለት አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 598(2) እና አንቀጽ 692(1) የተመለከተውን በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት በአስራ ሁለት ዓመት ጽኑ እስራትና በብር 17,000 /አሥራ ሰባት ሺህ ብር/ እንዲቀጣ ፍርድ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ፍርድ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለበት ነው በማለት ይግባኙን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡ አመልካች ሚያዚያ 1 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ላቀረበብኝ አንደኛ የወንጀል ክስ በአስር ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ወስኖብኛል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በወንጀል ህግ ቁጥር 598(2) የተመለከተውን በመተላለፍ ጥፋት ፈጽሟል በማለት የሰጠው የጥፋተኛነት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተተ አለበት፡፡ ምክንያቱም የግል ተበዳይ በህይወት ወይም በአካሏ ላይ የደረሰባት ጉዳት ያለ ስለመሆኑ በሰጣቸው የምስክርነት ቃል አልገለፀችም አየር በማይገባበትም ቤት ተቆልፌ ነበር ያለችውም ስልክ እየደወለች ዘመዶቿን ታገኝ የነበረ በመሆኑ በህጉ ድንጋጌ የተገለፀውን ፍሬ ጉዳይ ያልተሟላ መሆኑን ያሣያል፡፡ ስለዚህ በወንጀል ህግ አንቀጽ 598(1) ጥፋተኛ መባል ሲገባኝ በፍሬጉዳይ ደረጃ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በወንጀል ህግ አንቀጽ 598(2) ጥፋተኛ ተብዬ የተጣለብኝ ቅጣት መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የግል ተበዳይ ለሰባ ቀናት በውጪ አገር ሰብዓዊ ክብሯ ተጥሶ በአንድ ክፍል ውስጥ ተቆልፎባት የቆየች መሆኑን የመሰከረች በመሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 598(2) የተመለከተው ሁኔታ ተሟልቷል ስለዚህ የአመልካች ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 598(2)ን የተላለፈ ጥፋተኛ ነው በማለት የሰጠው የጥፋተኛነት ውሳኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ ለማጣራት መዝገቡ ለሰበር ችሎት የቀረበ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በፍሬ



www.chilot.me

ጉዳይ ደረጃ አመልካች የተጠሪ አንደኛ ምስክርና የግል ተበዳይ የሆነችው ወ/ሮ መቅደስ ንጉሴ ፈቃድ ሣይኖረው ለቤት ሠራተኛነት ወደ ኩዌት የላከ መሆኑን የግል ተበዳይ ኩዌት ሄዳ ሥራ ከጀመረች በኂላ አሠሪዎቿ ከባድ ሥራ ያለእረፍት እንድትሠራ ያስገደዷት መሆኑን በመጨረሻም ሥራውን ለቅቃ ስትወጣ መሀመድ ሩሄን የሚባል ኤጀንሲ የወር ደመወዟን 475 ዶላር በመውሰድ በቂ አየርና ምግብ ልታገኝ በማትችልበት ሁኔታ ለሁለት ወር ከአስር ቀን ነፃነትና መብቷን በመገደብ በአንድ ክፍል ውስጥ እንድትቀመጥ አስገድዷት መሆኑንና በመጨረሻም ከዚህ ክፍል እንድትወጣ የማይፈቀድላት ከሆነ ስሊንደር እንደምታፈነዳ ቢላ ይዛ ስትናገር ወደ አገሯ የላኳት መሆኑን በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ይህ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬጉዳይ በየትኛው የወንጀል ህግ ድንጋጌ በሀላፊነት እንደሚያስጠይቅ ለመወሰን አግባብነት ያላቸውን የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች ይዘት መመርመር ያስፈልጋል፡፡

እኛም ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 598 ድንጋጌዎች መርምረናል፡፡ ማንም ሰው ፈቃድ ሣይኖረው ወይም በማናቸውም ሌላ ህግ ወጥ መንገድ ኢትዮጵጳያዊ ዜጋን ለሥራ ወደ ውጪ አገር የላከ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት ሊደረስ በሚችል ጽኑ እሥራት እና ከሀያ አምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ እንደሚቀጣ" የወንጀል ህግ አንቀጽ 598 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ አንድ ሰው ጥፋተኛነህ ተብሎ የሚቀጣው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 598 ንዑስ አንቀጽ 2 ከተዘረዘሩት የማክበጃ ምክንያት አንደኛው ያልተሟላ ሲሆን መሆኑን ከህጉ ድንጋጌ አንቀጽና ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ሆኖም አንድ ሰው ፈቃድ ሣይኖረው ወይም በማናቸውም ህገ ወጥ መንገድ ወደ ውጭ አገር የላካት ኢትዮጵያዊት ሰብአዊ መብቷ በህይወቷ ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት የደረሰባት እንደሆነ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት ጽኑ እሥራት እስከ ሀያ አመት የሚደርስ ጽኑ እሥራትና ከሀምሣ ሺ ብር የማይበልጥ መቀጮ እንደሚሆን የወንጀል ህጉ አንቀጽ 598 ንዑስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡ አመልካች የግል ተበዳይዋ በአካሏ ወይም በህይወቷ ላይ የደረሰባት ጉዳት ስለሌለ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 598 ንዑስ አንቀጽ 2 ጥፋተኛ መባሌ የህግ ስህተት አለበት በማለት ይከራከራል፡፡ ሆኖም የወንጀል ህግ አንቀጽ 598 ንዑስ አንቀጽ 2 የተላከችው "ኢትዮጵየዊት የሰብአዊ መብቷ በህይወቷ ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት የደረሰባት እንደሆነ" በሚል መንገድ የተደነገገ ሲሆን አጥፊው በዚህ የህግ ድንጋጌ ጥፋተኛ ነው ተብሎ ፍርድ የሚሰጠው የተላከችው ኢትዮጵያዊት በሰብአዊ መብቷ መደፈር ደርሶባት እንደሆነ ወይም በህይወቷ ላይ ጉዳት የማድረሥ መከራ ተደርጐ እንደሆነ ወይም በህይወቷ ላይ ጉዳት ደርሶባት እንደሆነ ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት የማድረስ የሙከራ ወንጀል ተፈጽሞባት ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት ደርሶባት እንደሆነ መሆኑን ከህጉ ድንጋጌ ይዘትና አቀራረጽ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በወንጀል ሕግ አንቀጽ 598 ንዑስ አንቀጽ 2 አንድ ሰው በሀላፊነት የሚጠይቀው ከላይ ከተዘረዘሩት አንደኛው ወደ ውጭ በላካት ኢትዮጵያዊት ላይ መፈፀሙ የተረጋገጠ እንደሆነ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስናየው የግል ተበዳይ የሆነችው አንደኛ የተጠሪ ምስክር መሐመድ ሩሄን በሚባል ኤጀንሲ በአንድ ክፍል ውስጥ ታግታና የነፃነትና የመንቀሣቀሥ መብቷ ተገድቦ ለሰባ ቀናት የቆየች መሆኑና በዚህም ወቅት ከፍተኛ የሆነ የሥነ ልቦናና የአካል መጎሳቆል ጉዳት ደርሶባት የነበረ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የግል ተበዳይ በህይወቷ ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት የማድረስ ሙከራ ያልተፈፀመባት ወይም ጉዳት ያልደረሰባት ቢሆንም በነፃነት የመንቀሣቀሥና ወደ አገር የመመለስ መብቷ በአንድ የንግድ ድርጅት

ለሰባ ቀናት ያህል ተገድቦ በአንድ ጠባብ ክፍል ውስጥ እንድትቆይ የተገደደችና ሰብአዊ መብቷ የተጣሰ መሆኑ ስለተረጋገጠ የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ተጠሪ ባቀረበው አንደኛ ክስ የተጠቀሰውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 598 ንዑስ አንቀጽ 2 በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት የሰጡት ፍርድና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 (2(-2) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ፍርድ የፀና መሆኑን በማወቅ ተከታትሎ እንዲየስፈጽም ለማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 47935

ህዳር 30 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገብረሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥለጣን - ግርማ ወልደማሪያም ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ እየሩሣሌም ወንዴ ጠበቃ አቶ የሺጥላ አሰፋ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት አመልካች ስለጠየቀ ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ተከሣሽ ተጠሪ ከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ተጠሪ ከአሜሪካን አገር ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ 12,500 የአሜሪካን ዶላር ይዘው የመጡ መሆኑን በዴክራላሪስዮን ቁጥር ሲ-5-7119 ሐምሌ 29 ቀን 1999 ዓ.ም እንዳስመዘገቡ ገልፀው ጥቅምት 14 ቀን 2001 ዓ.ም ወደዱባይ ሊሄዱ ሲሉ 2500 የአሜሪካን ዶላር ብቻ የመለሱልኝ ሲሆን 10,000 የአሜሪካን ዶላር አስቀርተዋል፡፡ ስለዚህ ዶላሩን በአይነቱ ወይም በኢትዮጵያ ብር ምንዛሬ እንዲከፍል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች አንድ ኢትዮጵያዊ ከ45 ቀናት በላይ የውጭ ገንዘብ መያዝ አይችልም ለጊዜያዊ ጉብኝት የመጣ ሰው ቢሆንም እንኳን ያመጣውን የውጭ ምንዛሬ ይዞ እንዲወጣ የሚፈቀድለት በአንድ መቶ ሰማኒያ ሶስት ቀናት ውስጥ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ 10,000 የአሜሪካን ዶላር ይዘው እንዳይወጡ መከልከሉ ተገቢ ነው ሆኖም ዶላሩን በኢትዮጵያ ብር መንዝሮ የማይከፍልበት ምክንያት የለም በማለት 10,000 የአሜሪካን ዶላር የካቲት 18 ቀን 2001 ዓ.ም በነበረው የምንዛሬ ተመን መሠረት በኢትዮጵያ ብር መንዝሮ ከየካቲት 18 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ አመልካች የይግባኝ ቅሬታ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን ቦሌ ቅርንጫፍ በላከው መመሪያ ኢትዮጵያ ውስጥ በጊዜያዊነት ለጉብኝት የመጡ ወይም ለንግድ ወደ አገር ውስጥ የገቡ ሰዎች ለጊዜው በእጃቸው የያዙትን የውጭ ምንዛሬ ለጉምሩክ አስመዝግበው ማስረጃ ከያዙ ለአንድ መቶ ሰማኒያ ሶስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ይዘውት የመጡትን የውጭ ምንዛሬ ይዘው ለመውጣት ፈቃድ አያስፈልጋቸውም የሚል በመሆኑ የተጠሪ ዶላር



www.chilot.me

የተያዘው በዚህ መመሪያ መሠረት ነው፡፡ ስለዚህ የተያዘው ዶላር በኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ እንዲከፈላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው 10,000 ዶላሩን ጉምሩክ በሰጠኝ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ /Temporary Receipt for Deposit/ ቁጥሩ 176828 ገቢ ያደረግሁት በመያዣ ስም መሆኑንና ደረሰኙም ከአንድ መቶ ሰማኒያ ቀን በኋላ እንደማያገለግል ይገልፃል፡፡ ስለዚህ አመልካች በሕጋዊ መንገድ አሣውቀው ያስገቡትን ዶላር እንዳይወጣ ከሚከለክል በስተቀር የሚወርስበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ብሔራዊ ባንክ ያወጣውን መመሪያ በመጣስ ዶላሩን ሊያወጡ ሲሉ የተያዘ በመሆኑ የመውረስ ሥልጣን አለን በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን ተጠሪ ከአሜሪካን ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ የግል ንብረታቸው የሆነውን 12,500 /አሥራ ሁለት ሺህ አምስት መቶ/ የአሜሪካን ዶላር አመልካች እንዲያውቀው በዲክራላሲዩን ያስመዘገቡ እና በጊዜያዊ የመያዣ ማስቀመጫ ደረሰኝ 176828 ያስያዙ መሆኑን በግራ ቀኙ ክርክር ተገልፆአል፡፡ ተጠሪ ከአሜሪካን አገር ይዘው የመጡትንና ለአመልካች በግልጽ ያሣወቁትን ዶላር ከመቶ ሰማኒያ ቀን በኋላ ይዘው ለመውጣት የሞከሩ መሆኑንና አመልካች የብሔራዊ ባንክ ያወጣው መመሪያ ያለ ፈቃድ አንድ ሰው ለንግድ ወይም ለጉብኝት ወደ አገር ይዞት የገባውን ዶላር ከመቶ ሰማኒያ ሶስት ቀን በኋላ ይዞ መውጣት የማይፈቀድለት መሆኑን በመግለጽ 10,000 የአሜሪካን ዶላር ተጠሪ ይዘው እንዳይወጡ የከለከለና ዶላሩን የያዘ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ አመልካች ተጠሪ ለመንግሥት አሣውቀው ይዘው የገቡትን 10,000 የአሜሪካን ዶላር ከአንድ ዓመት ከአራት ወር በኋላ ያለ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ይዘው መውጣት እንደማይችሉ በመግለጽ መከልከሉ ተገቢነት ያለው ተግባር ቢሆንም ተጠሪ የውጭ ምንዛሬውን ይዘው የመወጣት መብታቸውን ከሚያጡ በስተቀር ዶላሩ በኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ እንዳይሰጣቸውና በሕጋዊ መንገድ ከአገራቸው ይዘውት የመጡትን ገንዘብ እንዳይጠቀሙ የሚያደርግ የወንጀል ተግባር ያልፈፀሙ በመሆኑ ገንዘቡን በኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ እንዲከፈላቸው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ምንም አይነት የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 59304

ኅዳር 15 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** 1. አቶ አያሌው ተሠማ

2. አቶ ጌታቸው አጎናፍር

3. ዶ/ር መሐሪ መኮንን

ጠበቆች፡-

1. ታምሩ ወንድምአገኘሁ ቀረቡ፡፡

2. ደሣለኝ ዓለሙ ቀረበ፡፡

3. ገ/እግዚአብሔር ተስፋዬ ቀረበ፡፡

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓቃቤ ሕግ

1. እሸቱ ወ/ሰማያት
2. ወንድወሰን ደሣለኝ
3. አውግቸው ክብረት

ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የወንጀል ድርጊት ተፈጽሟል በሚል የቀረበውን ክስ ተከትሎ የተነሣውን የዋስትና ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ በጉዳዩ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሣሽ የሆነው የተጠሪው ባለሥልጣን ዓቃቤ ሕግ በአመልካቾች ላይ ክስ መስርቷል፡፡ በአሁኑ 1ኛ አመልካች ላይ አስራ አንድ ክሶች በሁለተኛ አመልካች ላይ አምስት ክሶች በአራተኛ አመልካች ላይ ስድስት ክሶች መመስረታቸውን የሥር ፍርድ ቤት ብይን ይገልፃል፡፡ አመልካቾች የዋስትና ጥያቄ ያቀረቡት በክሶቹ የተመለከቱት የወንጀል ድርጊቶች የዋስትና መብት የሚያስነፍጉ አይደሉም በማለት ሲሆን ዓቃቤ ሕግ ደግሞ ይህንኑ የአመልካቾችን ጥያቄ የተቃወመው በአመልካቾች ላይ የተመሠረተው ክስ ከአስራ አምስት ዓመታት በላይ ሊያስቀጣ ይችላል፤ አመልካቾች በዋስ ቢለቀቁ ግዴታቸውን አክብረው ፍርድ ቤት አይቀርቡም ሌላ ወንጀል ሊፈጽሙ ይችላሉ፤ ምስክሮችን በመግዛት ወይም በማባበል ወይም አስረጂ የሚሆኑበትን ያጠፋ ይሆናል በሚሉ ምክንያቶችና የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 63፣ 67/ሀ/፣ /ለ/ እና /ሐ/ በዋቢነት በመጥቀስ ነው፡፡ ከዚህም በኋላ የሥር ፍርድ ቤት ከሁለቱም ወገኖች የቀረበውን ክርክር መርምሮ አመልካቾች የተከሰሱባቸው የወንጀል ክሶች ከባድ ተደራራቢ በመሆናቸው አመልካቾች የዋስትና መብታቸው ቢከበርላቸው ግዴታቸውን ሊያከብሩ ይችላሉ የሚል



www.chilot.me

እምነት ሊያሳድሩ የሚችሉ አይደሉም የሚል ምክንያት በመስጠትና የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 67/ሀ/ን ብቻ በዋቢነት በመጥቀስ የአመልካቾችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

እኛም የአመልካቾች ጠበቆች ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም. ጽፈው ያቀረቡትን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን በጽሁፍ እንዲያደርጉ አድርገናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የአመልካቾችን የዋስትና ጥያቄ የሥር ፍርድ ቤት ውድቅ ሲያደርግ በምክንያትነት የያዛቸው ነጥቦች በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 67/ሀ/ ሥር የተመለከተውን ነጥብ የማቋቋሚያ ነጥብ መሆን አለመሆናቸውን ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የአመልካቾች ጠበቆች እና ዓቃቤ ሕግ ያቀረቡትን የጽሁፍ ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡

የሥር ፍርድ ቤቶች በአመልካቾች ላይ የተጠቀሱባቸው ድንጋጌዎች በራሳቸው ዋስትና የሚከለክሉ አለመሆናቸውን የተቀበሉት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ በመሆኑም አመልካቾች ዋስትና ይፈቀድ ዘንድ ክሱን ለሚያየው ፍርድ ቤት ጥያቄ /አቤቱታው/ አቅርበዋል፡፡

በመሠረቱ የዋስትና መብት በሕገ መንግሥት ጥበቃ ከተደረገላት የተያዙ ሰዎች መሠረታዊ መብቶች አንዱ ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 19/6/ ሥር የተያዙ ሰዎች በዋስትና የመፈታት መብት ያላቸው መሆኑን በመርህ ደረጃ ያስቀመጠ ሲሆን ይህ በሕገ መንግሥቱ የተከበረው "መሠረታዊ" መብት ሊነፈግ፣ ሊገደብ ወይም በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ የሚደረገውም አግባብነት ባላቸው ሌሎች ዝርዝር ሕጎች መሠረት በልዩ ሁኔታ ስለመሆኑ ይኸው የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የዋስትና መብት መሠረታዊ የሆነ ሕገ መንግሥታዊ መብት ቢሆንም ፍጹም መብት ሳይሆን በሕጉ አግባብ ሊነፈግ የሚችል ነው፡፡ ስለሆነም የዋስትናው ጥያቄ ተቀባይነት አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ላይ ውሣኔ የሚሰጠው ፍርድ ቤት እንደመሆኑ መጠን በዚህ ረገድ አግባብነት ያለውን ልዩ ሕግ መሠረት አድርጎ ጉዳዩን ሊመዝነውና ተገቢውን ውሣኔ ሊሰጥ እንደሚገባ ግልጽ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካቾች ያቀረቡት የዋስትና ጥያቄ የተስተናገደው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 67 መሠረት ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በዋስትና ወረቀት የመለቀቅ ማመልከቻ ለመቀበል የማይቻልባቸውን ሁኔታዎችን አስቀምጧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች የአመልካቾችን የዋስትና ጥያቄ ያልተቀበሉት በተጠቀሰው ድንጋጌ ፊደል "ሀ" ሥር የተመለከተውን ሁኔታ በመጥቀስ ነው፡፡ በእርግጥም ድንጋጌው በዋስትና ወረቀት የተመለከቱትን ግዴታዎች አመልካቾች የሚፈጽሙ የማይመስሉ እንደሆነ ጥያቄውን ውድቅ ለማድረግ እንደሚቻል ያሳያል፡፡ እዚህ ላይ ሊስተዋል የሚገባው ዋናው ጉዳይ ግን ድንጋጌውን በመተግበር ረገድ ፍርድ ቤቱ ግንዛቤ ውስጥ ሊያስገባው የሚገባው ምክንያት ምንድነው? የሚለው ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ዋስትናውን ለመከልከል ግምቱን መነሻ የሚያደርግባቸው ሁኔታዎች በተጠቀሰው ድንጋጌ በግልጽ አልተመለከቱም፡፡ እንዲህ ከሆነ አንድ ተከሣሽ የዋስትና መብት ቢከበርለት ግዴታውን የሚፈጽም የማይመስል ነው ተብሎ ግምት የሚወስደው በቂና ሕጋዊ ሊባሉ በሚችሉ ምክንያቶች ሊሆን ይገባል ተብሎ የሚታመን ሲሆን ምክንያቶች በቂና ሕጋዊ ናቸው የሚለው ጉዳይ ከተለያዩ ከባባዊ ሁኔታዎችና ከጉዳዩ ልዩ ባሕርይ አንፃር ፍርድ ቤቱ ሊገነዘበው የሚችለው ነጥብ ነው ተብሎ የሚታሰብ ነው፡፡ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 67 ድንጋጌ አቀራረጽና ይዘት በጠቅላላው ሲታይ ፍርድ ቤት የዋስትና

መብትን የሚነፍግባቸውን ሁኔታዎች የሚያስገነዝብ ሲሆን ምክንያቶቹን ፍርድ ቤቶች ከተለያዩ ሁኔታዎች አንፃር እየተመለከቱ ሊመዝኗቸው የሚገባቸው ናቸው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካቾችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ያደረጉት በዋስትና ቢወጡ የዋስትናውን ግዴታ አክብረው ይገኛሉ ለማለት የሚቻል አይደለም በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይህ ግምት መሠረቱ በአመልካቾች ላይ የተመሠረቱት የክሶች ብዛትና የወንጀሎች ከባድነትና ሊያስከትሉ የሚችሉት ውጤት ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ወንጀሎቹ ከባድና ተደራራቢ መሆናቸውን ለግምቱ መነሻ አድርጓል፡፡ ፍርድ ቤቱ በእነዚህ ምክንያቶች ላይ በመመስረት ዋስትናውን ነፍጎአል፡፡ ይህን ምክንያት ለግምቱ መነሻ እንዲያደርግ ደግሞ በሕጉ የተከለከለ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ ሕጉ ለፍርድ ቤቱ ስልጣን የሰጠው ስለመሆኑ የሚታመን ከሆነ የሥር ፍርድ ቤት ሕጋዊ ምክንያት መሠረት ሳያደርግ ውሣኔ የሰጠ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ይህ ሰበር ችሎትም በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት የተሰጠው ሥልጣን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሣኔ ማረም ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 19/6/ እና የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ሕግ 67/ሀ/ መሠረት የሰጡት ውሣኔ ሕጉ የሰጣቸውን ሥልጣን መሠረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር በሕጉ አተረጓጎምና አተገባበር ረገድ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 91837 ሚያዝያ 19 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 55696 ግንቦት 24 ቀን 2002 ዓ.ም. የጸናው ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 75/2/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 59855

ህዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ሊዊዛ ፎርቤታ የቀረበ የለም፡፡

**ተጠሪ፡-** ዓቃቤ ህግ የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የዋስትና መብት ይከበርልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአመልካችና በሌሎች ሦስት ግለሰቦች ላይ በመሰረተው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ክሱ በፍርድ ቤት መታየት ከቀጠለ በሁዋላም አመልካች የተከሰሱበት የወንጀል ጉዳይ የዋስትና መብት የማይከለክል በመሆኑ የዋስትና መብታቸው ተከብሮላቸው ቆይቷል፡፡ ከዚህ በሁዋላም ዓቃቤ ሕግ የተፈቀደውን የዋስትና መብት ሊያስነሳ የሚችል አዲስ ነገር መገኘቱን ገልጾ ለአመልካች የተከበረላቸው የዋስትና መብት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 74 መሰረት እንዲነሳ አመልክቷል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሲመለከት የነበረው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ ለአመልካች የተከበረላቸውን የዋስትና መብት የሚያስነሳ ፍሬ ነገር ተገኝቷል የሚል ምክንያት በመያዝ ቀድሞ የሰጠውን ትዕዛዝ በመቀየር የአመልካችንና የሌሎችን ተከሳሾች የዋስትና መብት ነፍጓል፡፡ ከዚህም በኂላ አመልካችና ሌሎች አብሯቸው የተከሰሱና የዋስትና መብት በማክበር የተሰጠው ትዕዛዝ የተነሳባቸው ሰዎች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኂላ የስር ፍርድ ቤት በድጋሚ የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሮ የዋስትና መብት ተከብሮላቸዋል፡፡ ከዚህም በኂላ አቃቤ ሕግ አመልካችና ሌሎች አብሯቸው የተከሰሱ ሰዎች የዓቃቤ ህግ ምስክር የሆነውን ሰው ሌላ ሰው ልከው አስፈራርተዋል፣ የዋስትና መብት በማክበር የተሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 74 መሰረት ተነስቶ ጉዳያቸውን ማረሚያ ቤት ሁነው እንዲከታተሉ ሲል ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታውን አቅርቧል፡፡ ፍርድ ቤቱም ተስፈራራ የተባለውን የዓቃቤ ህግ ምስክር በችሎት አስቀርቦ በመስማትና ምስክሩ በጉዳዩ ላይ በተከሰሱ ሰዎች መስፈራራቱን መመስከሩን በማረጋገጥ ቀድሞ የአመልካችን የዋስትና መብት በማክበር የሰጠውን ትዕዛዝ በማንሳት ጉዳያቸውን በማረሚያ ቤት ሁነው እንዲከታተሉ ሲል ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ነሐሴ 20 ቀን 2002 ዓ.ም. በጻፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ተስፈራራ የተባለው የአቃቤ ሕግ ምስክር አመልካች በላኩት ሰው የተስፈራራ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የዋስትና መብቱ አዲስ ነገር ተገኝቷል ተብሎ መነሳቱ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ በመታመኑ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ሕዳር 13 ቀን 2003 ዓ.ም. በተጻፈ ማመልከቻ መልሱን ሰጥቷል፡፡ በመልሱም ላይ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው ሥነ-ሥርዓቱን ጠብቆ ያለመሆኑንና የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትእዛዝ በማስረጃ በተረጋገጠ ፍሬ ነገር ላይ የተመሰረተ መሆኑን ገልፆ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ እንዲሆን ተከራክሯል፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው ተስፈራራ የተባለው የዓቃቤ ሕግ ምስክር በዋናው ጉዳይ ላይ የምስክርነት ቃሉን ሰጥቶ ያበቃ መሆኑን በመጨመር የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ሰበር ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ሥነ ሥርዓቱን ጨርሶ የቀረበ መሆን ያለመሆኑን ስንመለከተው የአመልካች የዋስትና መብት መጀመሪያ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከተሰጠ በኋላ አዲስ ነገር ተገኝቷል በሚል ምክንያት በአቃቤ ሕግ አቤቱታ አቅራቢነት በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኘ ሲሆን በዚህ ትዕዛዝ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው የስር ፍርድ ቤት የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 74 ድንጋጌን መሰረት በማድረግ የሰጠውን ትዕዛዝ የተሻረ ቢሆንም አቃቤ ህጉ ለዚሁ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አዲስ ነገር ተገኝቷል በሚል በድጋሚ የአመልካች የዋስትና መብት እንዲነሳ አመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ምስክር ሰምቶ በአቃቤ ሕግ በኩል የተገለጸው ፍሬ ጉዳይ በማስረጃ መረጋገጡን በመያዝ የአመልካችን የዋስትና መብት በማክበር የሰጠውን ትዕዛዝ አንስቶታል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው በውጤት ደረጃ ሁለቱም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ ተመሳሳይ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ መቅረቡ ሥነ ሥርዓቱን ሳይጠብቅ ነው ለማለት የሚያስችል ባለመሆኑ በዚህ ረገድ ተጠሪ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አለተገኘም፡፡

አመልካች የተከሰሱበት የወንጀል ድርጊት የዋስትና መብት የማይከለከል ሲሆን የዋስትና መብታቸው ከተከበረላቸው በኋላ ሊከለከል የቻለው የዓቃቤ ሕግ ምስክርን በሌላ ሰው አስፈራርተዋል በሚል ምክንያት ነው፡፡ ዋስትና የተፈቀደለት ሰው በዋስ ከወጣ በኋላ አዲስ ነገር ከተገኘ ፍርድ ቤቱ በማናቸውም ጊዜ ቢሆን በስልጣኑ ወይም በማናቸውም ባለጉዳይ አመልካችነት በዋስትና ወረቀት የተለቀቀው ሰው የተለቀቀበትን ሁኔታዎች (ግዴታዎች) እንደገና ተመልክቶ የተለቀቀው ሰው አዲስ ዋሶችን እንዲያመጣ ወይም በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ለማዘዝ የሚቻል ስለመሆኑ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 74 ድንጋጌ በግልፅ ያሳያል፡፡ የአመልካችን የዋስትና መብት በማክበር የተሰጠው ትእዛዝ በስር ፍርድ ቤት እንደገና የታየውም በአቃቤ ሕግ ምስክር ላይ የማስፈራራት ተግባር ፈፅመዋል በሚል ምክንያት ነው፡፡ ምስክሩ የተስፈራራ ስለመሆኑ ደግሞ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡ በዚህ ረገድ የአመልካች ጠበቃ አጥብቀው የሚከራከሩት ምስክሩ በአመልካች በቀጥታ ወይም አመልካች ራሳቸው በላኩት ሰው ስለመስፈራራቱ አልተረጋገጠም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይኸው የአመልካች ጠበቃ ክርክር የፍሬ ነገር ክርክር ሲሆን ፍሬ ነገርን



www.chilot.me

የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕግ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት የተሰጠው ስልጣን ፍሬ ነገርን የማጣራት ወይም ማስረጃን መመዘን ባለመሆኑ በዚህ ችሎት ሊታይ የሚገባው አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የአመልካች ጠበቃ ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡ በዚህም መሰረት የአቃቤ ሕግ ምስክር መስፈራራቱ ከተረጋገጠ ምክንያቱ እንደአዲስ ነገር መገኘት የሚታይ ሲሆን የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 67(ለ) እና (ሐ) ድንጋጌዎች መንፈስ ጋር ተዳምሮ ሲታይ ለአመልካች የተከበረውን የዋስትና መብት እንደገና ለማንሳት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት የለም፡፡

ሌላው የአመልካች ጠበቃ በዚህ ችሎት በመልስ መልሳቸው ላይ ያነሱት ክርክር ተስፈራራ የተባለው ምስክር በጉዳዩ ላይ የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተው ጉዳዩ አብቅቷል የሚለው ሲሆን ይህ ነጥብ በዚህ ችሎት የተነሳ አዲስ ነጥብ ሲሆን ችሎቱ መመርመር ያለበት የስር ፍርድ ቤቶችን የውሳኔ ግልባጭ መሰረት በማድረግ በሕግ አተረጓጎም ወይም አተገባበር ረገድ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መኖሩ ሲረጋገጥ ከመሆኑ አኳያ ሲታይ የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ለማለት የሚያስችል የክርክር ነጥብ አይደለም፡፡ የአመልካች ጠበቃ ተስፈራራ የተባለው ምስክር በጉዳዩ ላይ መስክሮ ጉዳዩ አብቅቷል የሚሉ ከሆነም አዲስ ነገር መገኘቱን መሰረት በማድረግ የዋስትና መብቱን ለከለከለው ፍርድ ቤት ጥያቄአቸውን ከሚያቀርቡና በሚሰጠው ትእዛዝም ቅሬታ ካላቸውም ተዋረዱን ጠብቀው የይግባኝ ቅሬታቸውን ወይም የሰበር አቤቱታቸውን ከሚያቀርቡ በስተቀር በዚህ ችሎት ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 72(2) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፤

ዘቢ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 52075

ታህሳስ 26 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገብረሥላሴ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ጌቱ ብርሀኑ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ዐቃቤ ህግ - ወርቅነህ ዘነበ ቀርበዋል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የበታች ፍርድ ቤት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ አመልካች በወንጀል ህግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 2 የተመለከተውን በመተላለፍ ግንቦት 22 ቀን 1998 ዓ.ም ከጧቱ ሁለት ሠዓት የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02/03 የሰሌዳ ቁጥር 3-17408 አ.አ የጭነት መኪና ከአየር ጤና ወደ ቃሊቲ አቅጣጫ በማሽከርከር ላይ እንዳለ ገብሬል ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት ሲደርስ ከመኪናው ላይ አሣፍሮት የነበረው ታምራት ሰማኸኝ ከመኪናው ወድቆ በመሞቱ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል ፈፅሟል በማለት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች ጥፋተኛ አይደለሁም ብሎ በመከራከሩ ተጠሪ ሁለት ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ የተጠሪ ምስክሮች ሟች አመልካች የቆመለት መስሎት ለመውረድ ሲሞክር አመልካች መኪናውን በማሽከርከሩ ሟች ወድቆ የሞተ መሆኑንና አመልካች ከላይ የተጫነው ሰው ሁኔታ በስፖኪ ሣያይና ሣያረጋግጥ ማሽከርከሩ በሙያው ማድረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ያላደረገ መሆኑን ያሳያል በማለት መስክረዋል፡፡ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ የሌለው መሆኑን ለሥር ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች የወንጀል ህግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 2ን በመተላለፍ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት አመልካች በአንድ ዓመት ከሶስት ወር ቀላል እስራትና በብር 4500 መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካችን ይግባኝ አልተቀበለውም፡፡

አመልካች ጥር 10 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የተጠሪ ምስክሮች ቃል በአይናቸው ያረጋገጡት ፍሬ ጉዳይን የመሰከሩ ሳይሆኑ የራሳቸውን ሀሳብ የገለፁ ናቸው፡፡ አመልካች ሟችን በሚያሽከረክረው መኪና ላይ አልጫነም ሀላፊነት ወስጄ ያልጫንኩትን ሰው ህይወት ደህንነት ጥንቃቄ ላደርግ አልችልም ስለዚህ የአመልካች ድርጊቱ በወንጀል ህግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 2



www.chilot.me

የሚሸፈን አይደለም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ሟች ተጠሪ ሲያሽከረክረው ከነበረው መኪና ላይ ወድቆ የሞተ መሆኑን በማስረጃ አስረድተናል፡፡ አመልካች ሟችን አለመጫኑን በመከላከያ ማስረጃ አላረጋገጠም፡፡ የአመልካች አድራጎት የትራንስፖርት ደንብ ቁጥር 279/56ን የሚጥስና በሙያው ማድረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ባለማድረጉ የሟች ህይወት ለህልፈት የበቃ መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በፈፀመው ጥፋት የሆነ ቸልተኝነት ከሚያሽከረከረው መኪና ላይ አሣፍሮት የነበረው ሟች ታምራት ሰማኸኝ የሞት አደጋ የደረሰበት መሆኑን ተጠሪ በቂ ማስረጃ በማቅረብ ያረጋገጠ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የከፍተኛው ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የተጠሪን ማስረጃ ለመከላከል ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ፍሬ ጉዳይ በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን ሂደት ፈፅመውታል የሚለውን ስህተት ይህ ሰበር ችሎት እንዲያርምላቸው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ለሰበር ችሎት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 3(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 የተሰጠውን ሥልጣን ከግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ አመልካች ከመኪናው ላይ አሳፍሮት የነበረው ሟች ከመኪናው እየወረደ እያለ መኪናውን ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ በማሽከርከሩ ሟች ከመኪናው ላይ ወድቆ ለህልፈት የተዳረገ መሆኑን በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የአመልካች አድራጎት በወንጀል ህግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገውን መሥፈርት የሚያሟላ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195(1/ለ-2) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ውሣኔው የፀና መሆኑን አውቆ ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለአዲስ አበባ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ይፃፍ፡፡

   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡***

ራ/ታ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 57632

ታህሣስ 25 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ሰማኸኝ በለው - ባለቤቱ ነኝ ብለው ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ - ወርቅነህ ዘነበ ቀረቡ

መዝገቡ የቀረበው ለምርመራ ሲሆን መርምረን በአብላጫ ድምፅ ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው በአመልካች ላይ ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በወ/ይ/መ/ቁ. 48189 መጋቢት 30 ቀን 2002 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚልበትን ምክንያት በመግለፅ አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ ሲሆን ተጠሪ የፌዴራል ዐቃቤ ሕግም የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሣኔ በሕግ መሠረት የተሰጠ መሆኑን ገልፆ ተከራክሯል፡፡

አመልካች በሰበር ሰሚው ችሎት እንዲታረምለት የሰበር አቤቱታ ያቀረበበት የጥፋተኝነት ውሣኔ በይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 193/2/ መሠረት የአሁን አመልካች በመልስ ሰጭነቱ ተጠርቶ ሊቀርብ ባለመቻሉ ምክንያት በሌለበት ይግባኙን በመስማት በመሆኑ በዚህ አኳኋን የተሰጠን የጥፋተኝነት ውሣኔ ይህ ሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር የማረም ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለው የሥልጣን ጉዳይ በቅድሚያ ሊታይ የሚገባው ነጥብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ለጉዳዩ አወሳሰን እንዲረዳ የጉዳዩን አመጣጥ ባጭሩ ለመግለፅ ያህል ለዚህ ለሰበር መ/ቁ. 57632 መነሻ የሆነው ውሣኔ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ክ/ቁ. 20464 ሰኔ 18 ቀን 2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የተሰጠው ፍርድ ሲሆን ይዘቱም፡-

ተከሣሽ /የአሁን አመልካች/ በወ/መ/ሕ/ቁ. 522/1/ሀ/ የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ሟች አርቲስት ግሩም ተስፋዬን በግፍ ገድሏል፣ ህይወቱ እንዲያልፍ አድርጓል በማለት የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ከእነ ሙሉ የወንጀል ዝርዝሩ በቀረበው ክስ መነሻ ተከሣሽ /የአሁን አመልካች/ ቀርቦ እንዲከራከር ተጠርቶ ሊቀርብ ያልቻለ፣ በጋዜጣም ቢጠራ ያልቀረበ መሆኑን በማየት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 163/1/ መሠረት ጉዳዩን ተከሣሹ በሌለበት እንዲታይ ካደረገ በኋላ፤ ከሣሽ ዐቃቤ ሕግ እንደ የወንጀል ክሱ አቀራረብ ተከሣሹ የወንጀሉን ድርጊት ሆን ብሎ አስቦ የፈፀመ

ስመሆኑ አላረጋገጠም፡፡ ስለሆነም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 163/3/ መሠረት ከክሱ ነፃ ነው የሚል ፍርድ የተሰጠበት ነው፡፡

በዚህ ፍርድ ላይ የአሁን ተጠሪ ቅር ተሰኝቶ ባቀረበው የይግባኝ ቅሬታ መነሻ ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት ለዚህ የሰበር መዝገብ ምክንያት የሆነውን በወ/ይ/መ/ቁ. 48189 መጋቢት 30 ቀን 2002 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የአሁን አመልካች በሌለበት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

በዚሁ ፍርድ ላይ የአሁን አመልካች በሌለበት ሊታይ የቻለበትን ምክንያትም እንደሚከተለው አስፍሮታል፡፡

ተከሣሽ የሆነው የአሁኑ አመልካች በመልስ ሰጪነት እንዲቀርብ የይግባኙ ማመልከቻና መጥሪያ ምርመራውን ባጣራው የፖሊስ ክፍል በኩል እንዲደርሰው ተልኮ የአ/አበባ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽን የትራፊክ መቆጣጠሪያና ምርመራ መምሪያ መልስ ሰጭ ከኢትዮጵያ ውጭ ሄዷል የሚል ጥቆማ እንደደረሰው በመግለፅ ያላገኘው መሆኑን በጽሑፍ በማሳወቁና መዝገቡም ሲታይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም መልስ ሰጭ ተፈልጐ ባለመገኘቱ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጐለት ባለመቅረቡ ክሱ በሌለበት የታየ ሆኖ በመገኘቱ እንደገና ተጨማሪ በጋዜጣ ጥሪ ማድረግ ሳያስፈልግ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 193/2/ መሠረት ይግባኙ መልስ ሰጭ በሌለበት ታይቶ እንዲወሰን ተበይኗል፡፡

በዚህ መሠረትም የሥር ፍ/ቤት ፍርድና የይግባኝ ባይ ዐቃቤ ሕግ ቅሬታ ከህጉ ጋር በማገናዘብ ከመረመረ በኋላ፡-

በይግባኝ የቀረበለት መዝገብ ከአሁን አመልካች ጉዳይ ጋር በተያያዘ ለሦስተኛ ጊዜ የቀረበ መሆኑንና የአመጣጡንም ሂደት እንደሚከተለው ገልፆታል፡፡

በመጀመሪያ የአሁን አመልካች በተባለው ጊዜና ቦታ ሟችን በቸልተኝነት ገድሏል በሚል የወ/መ/ሕ/ቁ. 526/1/ ተጠቅሶ በቀረበበት ክስ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከሣሹን መከላከል ሳያስፈለገው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 141 መሠረት በብይን በማሰናበቱ የተነሣ የይግባኝ ክርክር ቀርቦበት በወ/ይ/መ/ቁ. 26293 ታህሣስ 16 ቀን 1999 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሥር ፍ/ቤት የተሰማው ማስረጃ ተከሣሹ እንዲከላከል የሚያበቃ መሆኑን ጠቅሶ ይከላከል ሲል መመለሱን፡፡

በዚህ መሠረት መዝገቡ ከተመለሰ በኋላ ዐቃቤ ሕጉ የድርጊቱ አፈፃፀም በቸልተኝነት የተፈፀመ ሳይሆን ሆን ብሎ የፈፀመው መሆኑን ስለተረዳን ክሱን እንድናሻሽል ይፈቀድልን በማለት ጥያቄ ቢያቀርብም የከፍተኛው ፍ/ቤት ይህንን ጥያቄ ባለመቀበል የተከሳሹን ቃል በመከላከያ ማስረጃነት ተቀብሎ ጥር 23 ቀን 2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ተከሣሹ የአሁን አመልካች በወ/መ/ሕ/ቁ. 526/1/ ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ ድርጊቱን የፈፀመ መሆኑን አረጋግጦ የጥፋተኝነት ውሣኔ ከሰጠ በኋላ ለዚሁ ጥፋት በብር 3000.00 /ሦስት ሺህ ብር/ የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

ዐቃቤ ሕግ በዚህ ውሣኔ ለሁለተኛ ጊዜ በወ/ይ/መ/ቁ. 36932 በክስ ማሻሻል ጥያቄው ላይ አተኩሮ የይግባኝ ክርክሩን ሲያቀርብ በዚህ መነሻ መልስ ሰጭ የነበረው የአሁን አመልካች እንዲቀርብ ተፈልጎ ሊገኝ ባለመቻሉ እንዲሁም በጋዜጣ በተደረገው ጥሪ ባለመቅረቡ የይግባኝ ጉዳዩን



www.chilot.me

በሌለበት ሰምቶ ዐቃቤ ሕግ ከፍርድ በፊት የክስ መሻሻል ጥያቄ ለማቅረብ የሥነ-ሥርዓቱ ሕጉ አይከለክለውም ከፍርዱ በፊት በማናቸውም ጊዜ ክስ የማሻሻል መብቱን የሥር ፍ/ቤት ሳይቀበለው መቅረቱ አግባብ አይደለም በማለት ቀደም ሲል የሰጠውን የጥፋተኝነት እና የብር 3000.00 /ሦስት ሺህ ብር/ የገንዘብ መቀጮ ቅጣት ውሣኔ ሽሮ ተዘጋጅቶ በሚቀርበው አዲስ ክስ መሠረት ጉዳዩ እንዲታይ መልሶታል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ ውሣኔ መሠረት ያንኑ የኮ/መ/ቁ. 20464 የሆነውን መዝገብ አንቀሳቅሶ በዚሁ መዝገብ ላይ ተሻሽሎ የቀረበውን ክስ መነሻ በማድረግ ተከሣሽ /የአሁን አመልካች/ ቀርቦ ባለው የመከራከር መብት እንዲከራከር ተጠርቶ ያለመቅረብ እና በጋዜጣ ጥሪም ተደርጐለት አለመቅረቡን በማየት ከላይ በመግቢያው ላይ እንደተገለፀው ሰኔ 18 ቀን 2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የአሁን አመልካች በክሱ ላይ የተገለፀውን ድርጊት እንደ ተከሰሰበት ድንጋጌ ሆን ብሎ የፈፀመው ለመሆኑ በማስረጃ አልተረጋገጠም፡፡ ስለሆነም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 163/3/ መሠረት በነፃ ይሰናበታል በማለት ለመጨረሻ ጊዜ በጉዳዩ ላይ ፍርድ የሰጠ መሆኑን ጠቅሶ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በይግባኝ ሥልጣኑ የዚህኑ ፍርድ አግባብነት እንደሚከተለው መርምሮ የእራሱን ፍርድ መልስ ሰጭ የነበረው የአሁን አመልካች በሌለበት በአብላጫ ድምፅ ሰጥቷል፡፡

የድርጊቱ ሆን ተብሎ የተፈፀመ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ዐቃቤ ሕግ ባቀረበው የሰውና የሠነድ ማስረጃ ሊያረጋግጥ አልቻለም፡፡ በሌላ በኩል ይህ የአሁን አመልካች በዚሁ ድርጊት የተነሣ በቸልተኝነት ጥፋተኛ ተብሎ የብር 3000.00 /ሦስት ሺህ ብር/ የገንዘብ መቀጮ ተቀጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ከክስ ማሻሻል ጥያቄ ጋር በማያያዝ ይግባኝ የጠየቀበት ዐቃቤ ሕግ እንጂ ተከሣሹ አይደለም፡፡ ስለሆነም ድርጊቱ የተፈፀመው ሆነ ተብሎ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጉዳይ ከሚያከራክር በቀር የድርጊቱ ፈፃሚ ተከሣሹ መሆኑ የታወቀ ጉዳይ ነው፡፡

በመሆኑም ማስረጃው በወ/መ/ሕ/ቁ. 522/1/ሀ/ በተመለከተው መሠረት ጥፋተኛ ለማድረግ ደካማ ሆኖ ቢገኝም የፈፀመው አድራጐት በቸልተኝነት የግድያ ወንጀል ነው ለማለት በቂ ሆኖ ስለተገኘ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 113/2/ መሠረት በወ/ሕ/ቁ. 526/2/ የተመለከተውን ተላልፎ የተገኘ ጥፋተኛ ነው ሊባል ስለሚገባው የሥር ከፍተኛው ፍ/ቤት ሰኔ 18 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠውን ፍርድ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195/2/ሀ/ መሠረት ተሰርዞ በወ/ሕ/ቁ. 526/2/ ጥፋተኛ ነው ካለ በኋላ ከዐቃቤ ሕግ በኩል ከቀረበው የቅጣት አስተያየት አንፃር በማየት የአሁን አመልካችን በአራት ዓመት እሥራት እንዲቀጣ በማለት ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት መጋቢት 30 ቀን 2002 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በአብላጫ ድምፅ ወስኗል፡፡

የይግባኝ መዝገቡ በዚህ አኳኋን ከተቋጨና ከተዘጋ በኋላ የአሁን አመልካች የይግባኝ ክርክር በቀጠሮ ጊዜ ውጪ ሀገር ነበርኩኝ ክሱ ስለመቀጠሉ አላወቅኩም መጥሪያም አልደረሰኝም የሚሉትን ምክንያቶች በመጥቀስ በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ፍርድ ውድቅ ሆኖ ጉዳዩ ባለበት እንዲታይ ይደረግለት ዘንድ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 197 አቤቱታ በማቅረቡ በዚህ መነሻ ዐቃቤ ሕግ እንዲቀርብ አድርጎ ጉዳዩን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 201 መሠረት ከሰማ በኋላ የወንጀል ክሱ ተሻሽሎ በወ/ሕ/ቁ. 522/1/ሀ/ መሠረት በከባድ ወንጀል ክስ ሲታይ ሊቀርብ ባለመቻሉ ጥሪ ተደርጐም ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት መወሰኑን መዝገቡ ያስረዳል፡፡



www.chilot.me

በመጀመሪያው ክስ በነፃ ከተሰናበተ በኋላ ዐቃቤ ሕግ ባቀረበው የይግባኝ መነሻ በይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት ቀርቦ ተከራክሯል፡፡ ይከላከል ተብሎ መዝገቡ ከተመለሰ በኋላም በከፍተኛው ፍ/ቤት በጠበቃ ታግዞ ተከራክሯል፡፡

በዚሁ የወንጀል ጉዳይ ከአንዴም ሁለቴ በይግባኝ ሰሚውና በሥር ፍ/ቤቶች በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ለመቅረብ ስላልቻለ በሌለበት ተፈርዷል፡፡

ከአገር ወጥቷል ለተባለ ሰው መጥሪያ በግንባር ማድረስ ስለማይቻል ጥሪው በጋዜጣ መደረጉ ሥነ-ሥርዓታዊ ነው፡፡

ወደ ውጭ አገር ለምን እንደሄደና ከአንድ ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ምን ይሠራ እንደነበርና ለምን ወደ አገር ውስጥ ሳይመለስ የቆየበትን ምክንያት እንኳን አልገለፀም፡፡

በቀረበበት በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል እየቀረበ ሲከራከር ከቆየ በኋላ ክሱ ወደ ከባድ ወንጀል ከተቀየረበት ጊዜ ጀምሮ ከአገር መውጣቱና ክርክሩ በከፍተኛው ፍ/ቤት ሲቀጥል ያን ያህል ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ሳይመለስ መቆየቱ በተሻሻለው ወንጀል ምክንያት የዋስ መብቱ ስለማይፈቀድ ታስሮ ክርክሩን የሚቀጥል መሆኑን በመረዳት ከፍርዱ ሂደት መሸሹን ስለሚያመለክት ባለቤቱ በየቀጠሮው እየቀረበች ጉዳዩን ትከታተል ነበር፤ ለዚህም ማስረጃ አለኝ በማለት ዐቃቤ ሕግ ያቀረበውን ክርክር አለመካዱ ሁሉ ሲታይ አመልካች በዚህ መዝገቡ ቀርቦበት የነበረውን የወንጀል ይግባኝ ክርክር አያውቅም ነበር ለማለት አያስችልም፡፡ ስለሆነም ከከባድ የወንጀል ክስ በመሸሽ አገር ጥሎ በመውጣት ሳይመለስ በመቅረቱ ምክንያት በሌለበት ሊታይ የቻለ ሆኖ ስለተገኘ በሌለበት የተሰጠው ፍርድ ውድቅ የሚሆንበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት አቤቱታውን ውድቅ አድርጎታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ይህን ሲመስል አመልካቹ ይህን የሰበር አቤቱታው ያቀረበው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እኔ በሌለሁበት የሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ እና የቅጣት አወሳሰን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚልበትን በክርክር አካሄድ ተፈፀመ የሚላቸውን የሥነ-ሥርዓት ጉድለቶችን በቸልተኝነት ወንጀል ተፈፀመ ለማለት በሕግ የሚጠይቀውን ሚሚያ የመሳሰሉትንና በቅጣት አጣጣል ረገድ እንደ ሕጉ አልተፈፀመም የሚላቸውን በመጥቀስ የተከራከረ በመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት አንድ ፍርድ ተከሳሽ /ይግባኝ ባይ/ በሌለበት ታይቶ የተሰጠ መሆኑ ሲታወቅ እርሱ ባለበት ክርክሩ ታይቶ እንዲወሰን የማድረግ መብቱን ሳያስጠብቅ በቀጥታ ያንኑ በሌለበት ታይቶ የተሰጠውን ውሣኔ በሰበር ለማሳረም የሚያስችል ሥልጣን አለው ወይስ የለውም የሚለውን ጥያቄ ሊያስነሳ ችሏል፡፡

የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80/3/ እና ይህንኑ ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ተከትሎ ከወጣው ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 የሚመነጭ በመሆኑ እንደ ሕገ መንግሥቱ እና አዋጁ ሥልጣን ያለው መሆኑንና አለመሆኑን ከሌላው ተከራካሪ ወገን በክርክር መልክ ባይቀርብለትም በእራሱ መርምሮ የመለየት ግዴታ አለበት፡፡ ከዚህም አንፃር ይህንኑ ጉዳይ ተመልክተናል፡፡

እንደተመለከትነውም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት የሥልጣን ምንጭ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80/3/ሀ/ የተመለከተው ድንጋጌ ሲሆን ይዘቱም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

ማናቸውንም የመጨረሻ ውሣኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን ይኖረዋል ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል የሚል ነው።

ከዚህም ድንጋጌ "... የመጨረሻ ውሣኔ ..." የሚለው ሀረግ አንድ ጉዳይ በሀገሪቱ በተዋቀሩት ፍ/ቤቶች ታይቶ እንዲወሰን ከታች ወደ ላይ ስንት የክርክር ደረጃ ማለፍ አለበት። ስንት የክርክር ደረጃ ሊፈቀድ ይገባል የሚለውን አስመልክቶ በወጣው ሕግ መሠረት የክርክሩ ደረጃውን አሟጦ የጨረሰ መሆኑን የሚያመለክት ነው። የዚሁ ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌን አፈፃፀም አስመልክቶ በወጣው አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 9 እና 10 የተመለከተውም የመጨረሻ ውሣኔ ማለት በፍ/ቤቶች አደረጃጀት አንፃር አንድ ጉዳይ ከታች ወደ ላይ እስከምን ያህል ደረጃ መዝለቅ ይችላል የሚለውን መሠረት በማድረግ የተቀመጠ የክርክር ደረጃ ወሰን መሆኑን እስረጂ ነው።

አሁን የተያዘውን አንድ የወንጀል ጉዳይ ተከሣሽ በሌለበት ታይቶ ፍርድ በተሰጠ ጊዜ በዚህ ፍርድ ላይ ይግባኝ የማሰማት መብት ያለው መሆኑንና አለመሆኑን አስመልክቶ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 202 የተመለከተው ድንጋጌ ከላይ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 9 እና 10 የተመለከተውን የክርክር ደረጃ ወሰን የሚያመለክት ሳይሆን የተለየ ዓላማ ያለው ነው።

በዚሁ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ አንድ ፍርድ ተከሣሽ በሌለበት ታይቶ ከተፈረደ በኋላ ፍርደኛው ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 197 ቀጥሎ ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት ፍርዱ ውድቅ ሆኖ የመከራከር መብቱ እንዲጠበቅለት ያቀረበው ማመልከቻ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቶ ውድቅ እንዲሆን ከተደረገ ይግባኝ ማለት አይቻልም። ነገር ግን ስለተፈረደበት ቅጣት ብቻ ማመልከቻው ውድቅ እንዲሆን ከተወሰነበት ቀን አንስቶ በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ ይግባኝ ማለት አይከለክልም በማለት በጥፋተኝነት ውሣኔው ላይ ይግባኝ ማለት እንደማይቻል በግልፅ ተደንግጓል።

በሌለሁበት ታይቶ የተሰጠው ፍርድ ይነሳ ለማለት በምክንያትነት የሚቀርቡት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 199/ሀ/ እና /ለ/ የተመለከቱት የመጥሪያ አደራረስ እና ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ለመቅረብ አለመቻል ናቸው። እነዚህን ምክንያቶች ማስረዳት የቻለ ፍርደኛ ፍርዱን ውድቅ አድርጎ እንደገና እርሱ ባለበት ክርክሩ እንዲሰማ የማድረግ መብት ያለው ሲሆን ከእነዚህ ሁለት ምክንያቶች አንደኛውን ለማስረዳት ያልቻለ ተከሣሽ ወይም ፍርደኛ ከፍትህ ርቆ ወይም ሸሽቶ የነበረ (considered as a convicted perform who was actually seeking to evade justice) መሆኑን የሚያስረዳ ነው።

ከወንጀል ጉዳዮች የትኞቹ ተከሣሽ በሌለበት ሊታዩ የሚችሉ ስለመሆኑ በሌለበት እንዲታይ ከመደረጉ በፊት ስለሚፈፀመው ሥርዓት በመዘርዝር አንድ የወንጀል ክስ ጉዳይ ተከሣሽ በሌለበት እንዲታይ ማድረግ ስለሚቻልበት ሁኔታ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 160 እስከ 164 መደንገጉም ጥሪ ተደርጎለት አለመቅረቡ ቢታወቅም በወ/ሕ/ቁ. 1 እንደተመለከተው የተከሣሽ አለመቅረብ የወንጀልን ሕግ ግብ አፈፃፀም ሊያሰናክል የሚችል እና ሕጉም ተገቢ ባልሆነ ምክንያት ወደ ሕግ ሊቀርቡ የማይችሉን ያለማበረታት ቀዳሚ ግብ ያለው መሆኑንና በዚህም የተነሣ ተጐጂዎች ከሚፈልጉት ፍትህ የማግኘት መብት አንፃር ታይቶ የተዘረጋ ሥርዓት ሲሆን፤ በአንፃሩ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 2/ሀ//1/ እንደተደነገገው የተከሰሰ ሰው ካለው መሠረታዊ መብት አንዱ የመሰማት መብት እንደመሆኑ መጠን በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 13/2/ እንደተመለከተው ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ህግጋት አንዱ በሆነው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት



www.chilot.me

/ኢ.ኤ.አ. 1966/ አንቀጽ 14/3/መ/ ተከሣሽ ባለበት የመዳኝትና እራሱን የመከላከል መሠረታዊ መብት ያለው በመሆኑ እና ይህም በማናቸውም ምክንያት በሌላ ሕግ ሊገደብ ስለማይችል በዚህ መብቱ ለመገልገል እንዳይችል ጥሪ በሚገባ ያልተደረገላቸው ከሆነ ጥሪ ቢደረግላቸውም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በክርክሩ ጊዜ መቅረብ ያልቻሉ ወገኖች ካሉ ይኸው ከላይ በተቀመጠው ሕገ መንግሥታዊ መብት መጠቀም እንዲችሉ ሥርዓቱ በወ/ሕ/ቁ. 197-202 ተዘርግቷል፡፡

ስለሆነም ከእነዚህ ምክንያቶች አንዱን ያላስረዳ ፍርደኛ ፍርዱን ውቅድ የማስደረግ መብት ያለው ሲሆን ይህንን ለማስረዳት ያልቻለው ግን በሕገ መንግሥቱ በተሰጠው በሕግ መሠረት የመዳኘት መብት /The right to fair trial) ለመጠቀም ሳይፈልግ ከሕግ ለመራቅ ያቀደ ከሕግ ርቆ የቆየ በመሆኑ ግምት የሚወሰድበት ስለሆነ በተሰጠው የቅጣት ውሣኔ ላይ ካልሆነ በቀር በተሰጠው ጥፋተኝነት ውሣኔ ላይ ይግባኝ የማቅረብ መብት የሌለው መሆኑን በመግለፅ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 202 ተደንግጓል፡፡ በዚህም መሠረት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 202 መሠረት በጥፋተኝነቱ ውሣኔ የይግባኝ መብት አይኖረውም በሚል መደንገጉ ከላይ ከተቀመጠው ምክንያት አንፃር የመከራከር መብቱን የነፈገ እንጂ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የይግባኝ አቤቱታ ማቅረብ አይቻልም መባሉ ፍርዱን የመጨረሻ አድርጎታል የሚል ትርጉም ለመስጠት የሚቻል አይደለም፡፡

ስለ ወንጀል ይግባኝ ጉዳይ አስመልክቶ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 193/2/ በዐቃቤ ሕግ ይግባኝ መነሻ በነፃ የተሰናበተውን ተከሣሽ ጉዳይ በሌለበት እንዲታይ ለማድረግ በሚያስችል አኳኋን መደንገጉም በይዘቱም ሆነ በዓላማው የመጀመሪያ ደረጃ ክስን ተከሣሽ በሌለበት እንዲታይ ከማድረግ ተለይቶ የሚታይ ስለሆነ መልስ ሰጭ በሌለበት የተሰጠውን ፍርድ እርሱ ባለበት ክርክሩ እንዲታይ ፍርዱን ውድቅ ካላደረገው በቀር በሌለበት ታይቶ የተሰጠውን ፍርድ እንደመጨረሻ ፍርድ ተቆጥሮ በሰበር እንዲታረም ለማድረግ የሚያስችል መብት አይሰጥም ፍርዱም እንደመጨረሻ ፍርድ ስለማይቆጠር ሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር የማረም ሥልጣን የለውም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት በአሁን አመልካች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የተቋጨ እንጂ በሰበር ሊታይ የሚችል ጉዳይ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በቅጣት ውሣኔ ረገድ የሰበር ጉዳዩን መመርመር የሚቻል በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን ክርክር እንደተመለከትነውም በቅጣት አጣጣል /አወሳሰን/ ረገድ የሥር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የፈፀመው የሕግ ስህተት አልተገኘም፡፡

ስለሆነም የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን የጥፋተኝነት ውሣኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80/3/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 9 እና 10 እንዲሁም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 202 መሠረት ከክርክሩ ደረጃ ወሰን አንፃር በማየት እንደተቀመጠ የመጨረሻ ውሣኔ ሆኖ ባለመገኘቱ ይህ ሰበር ችሎት ለማየት ሥልጣን የሌለው በመሆኑ በሰበር ሊታረም የሚችል አይደለም፡፡

የቅጣት አወሳሰኑም ቢሆን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ብለናል፡፡ በዚህም መነሻ የሚተለውን ውሣኔ በአብላጫ ድምፅ ሰጥተናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ኮ/ቁ. 20464 ሰኔ 18 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ የተሻረ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በወ/ይ/መ/ቁ. 48189 መጋቢት 30 ቀን



www.chilot.me

2002 ዓ.ም. የሰጠውን ፍርድ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195/2/ለ/2/ መሠረት በተለየም ምክንያት ቢሆን አፅንተናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## የልዩነት ሀሳብ

ስማችን በአራተኛውና በአምስተኛው ተራ ቁጥር የተገለፀው ዳኞች አብላጫው ድምፅ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ይግባኙን አይቶ አመልካች በሌለበት የሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ ላይ አመልካች የሰበር አቤቱታ እንዲያቀርብ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 3 የሚፈቀድ አይደለም በማለት በሰጠው የሕግ ትርጉምና በደረሰበት መደምደሚያ ያልተስማማን በመሆኑ በሀሳብ ተለይተናል፡፡ ከሥራ ባልደረቦቻችን የተለየንበት የመጀመሪያው ምክንያት ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ አቫሸሎ ያቀረበውን የወንጀል ክስ ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 አመልካች በሌለበት አይቶ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በሌለበት ሁኔታ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 202 የተደነገገው ሥርዓት በጠቅላላውና የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 3 በልዩ ሁኔታ ለጉዳዩ አግባብነትና ተፈፃሚነት ያለው የሕግ ድንጋጌ እንደሆነ አድርጎ በመተርጎም አብላጫው ድምፅ በሰጠው ውሣኔ የማንስማማ በመሆናችን ሲሆን ሁለተኛው ለጉዳዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 202 የተደነገጉት ድንጋጌዎች በጠቅላላውና የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር አንቀጽ 202 ንዑስ አንቀጽ 3 በልዩ ሁኔታ ለያዝነው ጉዳይ ተፈፃሚነት አላቸው የሚባል ቢሆን እንኳ እነዚህ ድንጋጌዎች አመልካች ይግባኝ ሰሚው ችሎት በሰጠው ፍርድ ላይ ተፈፅሟል የሚለውን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በሰበር ታይቶ እንዲታረምለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ከመጠየቅ የሚገድብ አይደለም የሚል አቋም ያለን በመሆኑ ነው፡፡

1. ከላይ ለልዩነታችን ምክንያት አድርገን በመጀመሪያ የገለፅነውን ነጥብ ለመረዳት በመጀመሪያ በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን ፍርድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአብላጫ ድምፅ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ጉዳዩ ያለፈበትን ሂደት መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህ መዝገብ አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበት ጉዳይ በተደጋጋሚ ለሦስት ጊዜ ያህል በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የታየና በተለያየ ጊዜ የተለያየ ውሣኔ የሰጠበት ሲሆን በይግባኝም በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለሦስት ጊዜ ያህል የታየና የተለያዩ ውሣኔዎች የተሰጠበት መሆኑን መዛግብቱን በመመርመር ለመርዳት ችለናል፡፡

አመልካችና ተጠሪ በዚህ መዝገብ የሚከራከሩበት ጉዳይ መነሻ ተጠሪ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሚያዚያ 14 ቀን 1995 ዓ.ም. ጽፎ ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ያቀረበው ክስ ይዘትም ተከሣሹ/አመልካች/ በ1949 ዓ.ም. የወጣውን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 526 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን በመተላለፍ ሐምሌ 7 ቀን 1994 ዓ.ም. በግምት ከሌሊቱ አሥር ሰዓት ሲሆን የመለያ ቁጥር 2-72538 አ.አ. የሆነ መኪና ባለመጠንቀቅና ጥፋት በሆነ ቸልተኝነት

ሲያሽከረክር የመኪናውን መንገድ ወደ ቀኝ በመልቀቅ ባምቢስ ድልድይ ውስጥ ገብቶ በመገልበጡና በአደጋው በመኪናው ውስጥ ተሣፍሮ የነበረው አቶ ግሩም ተስፋዬ ላይ የሞት አደጋ ያደረሰበት በመሆኑ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡ አመልካች/ተከሣሽ/ ሚያዚያ 14 ቀን 1995 ዓ.ም. ጽፎ ተጠሪ ያቀረበውን የወንጀል ክስ አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት በመከራከሩ ተጠሪ ክሱን ያስረዱልኛል የሚላቸውን ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት የተጠሪን ማስረጃ ከሰማና ከመረመረ በኋላ የተጠሪ ማስረጃ አመልካች በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 526 ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል የፈፀመ መሆኑን በአጥጋቢ ሁኔታ አላስረዳም በማለት አመልካች የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልገው በነፃ እንዲሰናበት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 20464 ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም. ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ የከፍተኛው ፍ/ቤት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 141 መሠረት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይገባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የተጠሪንና የአመልካችን ክርክር በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 26293 ከሰማ በኋላ ተጠሪ ሚያዚያ 14 ቀን 1995 ዓ.ም. ያቀረበውን የወንጀል ክስ በአጥጋቢ ሁኔታ ያስረዳ በመሆኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከሣሽን/አመልካችን/ በነፃ ማሰናበቱ ተገቢ አይደለም በማለት የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሣኔ በመሻር የከፍተኛው ፍ/ቤት የአመልካችን መከላከያ ማስረጃ በመስማት ጉዳዩን እንዲወስን በማለት ታህሣስ 16 ቀን 1999 ዓ.ም. በመወሰን ጉዳዩን ለከፍተኛው ፍ/ቤት መልሶ ልኮታል፡፡

በዚህ ውሣኔ መሠረት የከፍተኛው ፍ/ቤት ጉዳዩን ማየት ቀጥሏል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት አመልካች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ የሌለው በመሆኑ ፍ/ቤቱ የክሱን ቃል እንዲሰማው የጠየቀ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ አመልካች በቸልተኝነት ሳይሆን አስቦና ሆነ ብሎ ሟችን የገደለው መሆኑን የሚያስረዳ አዲስ ማስረጃ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 522 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ክሳችንን አሻሽለን እንድናቀርብ ይፈቀድልን በማለት አመልክተዋል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ የወንጀል ክሱን ለማሻሻል ያቀረበውን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ አመልካች በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 526 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን በመተላለፍ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት አመልካች በብር 3000 /ሦስት ሺህ ብር/ መቀጮ እንዲቀጣ ጥር 23 ቀን 2000 ዓ.ም. ውሣኔ ሰጥቶ አመልካች የገንዘብ መቀጮውን የከፈለ መሆኑን ከመዝገቡ ለመረዳት ችለናል፡፡

ተጠሪ ያቀረብነውን የወንጀል ክስ በማሻሻል ለማቅረብ ያቀረብነውን ጥያቄ የከፍተኛው ፍ/ቤት ውድቅ ማድረጉ ተገቢ አይደለም፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት ለማሻሻል ጥያቄ ያቀረብንበትንና ሚያዚያ 14 ቀን 1995 ዓ.ም. ጽፈን ያቀረብነውን የወንጀል ክስ መሠረት በማድረግ የሰጠው የጥፋተኝነት የቅጣት ውሣኔ ተገቢ አይደለም በማለት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለሁለተኛ ጊዜ የይግባኝ ቅሬታውን አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ አመልካች ይግባኙ በሚሰማበት ቀነ ቀጠሮ እንዲቀርብ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኙ በሚሰማበት ቀነ ቀጠሮ ያልቀረበ በመሆኑ ይግባኙን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ጉዳዩን መልስ ሰጭ/አመልካች/ በሌለበት አይቶ ተጠሪ ከፍርድ በፊት የወንጀል ክሱን የማሻሻል መብት ያለው መሆኑ በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ተደንግጎ እያለ የከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ ክሱን ለማሻሻል ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ አይደለም በማለት የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በመሻር የከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ አሻሽሎ

የሚያቀርበውን የወንጀል ክስ በመቀበልና ክርክሩን በስማት እንዲወሰን በማለት ጉዳዩን ለሁለተኛ ጊዜ መልሶ ልኮለታል፡፡

የከፍተኛው ፍ/ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ጥቅምት 26 ቀን 2001 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ መሠረት ተጠሪ አመልካች የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 522 ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ ሟች ግሩም ተስፋዬ ላይ ከባድ የሰው መግደል ወንጀል ፈፅሟል በማለት ጥር 12 ቀን 2001 ዓ.ም. አሻሽሎ ያቀረበውን የወንጀል ክስ በመቀበል ጉዳዩን ለሦስተኛ ጊዜ ለመስማት ተጠሪና አመልካች /ተከሣሽ/ እንዲቀርቡ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ሆኖም አመልካች ባለመቅረቡ መጥሪያው በጋዜጣ እንዲወጣ ካደረገ በኋላ ወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 በተደነገገው መሠረት ተከሣሽ/አመልካች/ በሌለበት በ(default) የተጠሪን ማስረጃና ክርክር በመስማትና በመመርመር ተጠሪ የወ/መ/ሕ/ቁ. 522/1/ በመጥቀስ ጥር 12 ቀን 2001 ዓ.ም. አሻሽሎ ባቀረበው የወንጀል ክስ መሠረት አመልካች ከባድ የሰው መግደል ወንጀል የፈፀመ መሆኑን የሚያረጋግጥ አጥጋቢ ማስረጃ አላቀረበም በማለት ተከሳሽ /አመልካች/ን ተሻሽሎ ከቀረበው የወንጀል ክስ በነፃ እንዲሰናበት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 163 ንዑስ አንቀጽ 3 እና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 141 መሠረት ወስኗል፡፡

ከላይ በአጭሩ የገለጽነው ክርክሩ ያለፈባቸው ሂደቶች ተከሣሹ/አመልካች/ በሌለበት (default) ክሱ ታይቶ ጉዳዩን በመጀመሪያ ባየው የከፍተኛው ፍ/ቤት በአመልካች ላይ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ያለ መሆኑን የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡ ተጠሪ ያቀረበው የተሻሻለ የወንጀል ክስ ተከሳሹ/አመልካች/ በሌለበት (default) በከፍተኛው ፍ/ቤት የታየ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት አመልካች በነፃ እንዲሰናበት ፍርድ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በነፃ እንዲሰናበት ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ እንዲታረም ለማድረግ ዐቃቤ ሕግ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 181 እና በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 185 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ይግባኝ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በማቅረብ ጉዳዩ በይግባኝ እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ በእኛ እምነት የከፍተኛው ፍ/ቤት አመልካች በሌለበት (default) በማየት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ባለመኖሩ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ 160 እና ተከታዮቹ አንድ ተከሣሽ በሌለበት የተሰጠውን ፍርድ ውድቅ እንዲደረግለት ስለሚያመለክትበትና ጉዳዩ ፍርዱን በሰጠው ፍ/ቤት በድጋሚ ስለሚታይበት ሥርዓት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 202 የተደነገጉት ድንጋጌዎች በጠቅላላውና የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 202 ንዑስ አንቀጽ 3 በልዩ ሁኔታ ለጉዳዩ አግባብነትና ተፈፃሚነት ያላቸው ድንጋጌዎች አይደሉም፡፡

2. ከፍተኛው ፍ/ቤት ተከሣሹ በሌለበት (default) ተጠሪ ያቀረበውን የተሻሻለ የወንጀል ክስ በማየት አመልካች/ተከሣሽ/ በክርክሩ ተሣታፊ ያልነበረ ቢሆንም ከቀረበበት ክስ በነፃ እንዲሰናበት የሰጠውን ፍርድ በመሻር በአመልካች ላይ የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የሰጠው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ መልስ ሰጭ/አመልካች/ በሌለበት አይቶ ለመወሰን የተከተለው ሥርዓት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 የተደነገገውን ልዩ ሥርዓት (special procedure in cases of default) አይደለም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት አንቀጽ 181 እና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር አንቀጽ 185 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ያቀረበውን ይግባኝ በሚሰማበት ጊዜ መልስ ሰጭው ባለመቅረቡ የተከተለው ሥርዓት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን (absence of a resepondant to the appeal) ሥርዓት ነው፡፡ በእኛ እምነት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 160 እስከ 163 በተደነገገው የdefault procedure እና በይግባኝ መልስ ሰጭ በሚቀርበት ጊዜ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሚከተለው



www.chilot.me

የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 193 ንዑስ አንቀጽ 2 መካከል ሠፊና መሠረታዊ ልዩነት አለ፡፡

በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 የተደነገጉት የ(default procedure) ጉዳዩን በመጀመሪያ የሚያየው ፍ/ቤት አሥራ ሁለት ዓመትና ከዚህ በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት የሚያስቀጡ የወንጀል ክሶችን ተከሣሹ በሌለበት አይቶ ለመወሰን የሚከተለውን ልዩ ሥርዓት የሚደነግግ ሲሆን የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 በማናቸውም ጉዳይ የሥር ፍ/ቤት በሰጠው ፍርድ ቅር በመሰኘት ተከሣሹ ወይም ዐቃቤ ሕግ ያቀረቡት ማናቸውም ይግባኝ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሚሰማበት ጊዜ መልስ ሰጭ ካልቀረበ ተፈፃሚ የሚሆን ሰፊ ሥርዓት ነው፡፡

የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 በጥቅል አገላለጽ የተደነገገና በበርካታ ጉዳዮች ሰፊ ተፈፃሚነት ያለው ሥርዓት ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በዚህ ሥርዓት መሠረት አይቶ የሰጠው ውሣኔ መልስ ሰጭ ውድቅ እንዲሆንለትና ይግባኙ መልስ ሰጭ ባለበት ታይቶ እንዲወሰን ማመልከቻ የሚያቀርብበት ሥርዓት አይደለም፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የቀረበለትን ይግባኝ መልስ ሰጭ በሌለበት አይቶ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገጉት ድንጋጌዎች መሠረት የሰጠው ፍርድ እንዲሰረዝና ውድቅ እንዲሆን በማድረግ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 202 መሠረት በማድረግ መጠየቅም ሆነ ማመልከት አይቻልም፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 202 የተደነገገው ሥርዓት ጉዳዩን ተከሣሹ በሌለበት (default) በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 በተደነገገው መሠረት አይቶ የተሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ውድቅ ለማስደረግ የሚያገለግል እንጂ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ይግባኙን መልስ ሰጭ በሌለበት አይቶ የወሰነውን ውሣኔ በድጋሚ አይቶ ውድቅ ለማስደረግ የሚያገለግል ሥርዓት አይደለም፡፡ ስለሆነም አብላጫው ድምፅ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 202 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ይግባኝ ሰሚው ችሎት ይግባኙን አመልካች/መልስ ሰጭ/ በሌለበት አይቶ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ መሠረት የሰጠውን ፍርድ ለማሰረዝ አግባብነትና ተፈፃሚነት እንዳላቸው አድርጎ በሰጠው ትርጉም ያልተስማማን በመሆኑ በሀሳብ ተለይተናል፡፡

3. የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 በሚከተሉት ሁኔታዎች ሁሉ ተፈፃሚነት ያለው ሥርዓት ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በዚህ ሥርዓት መሠረት መልስ ሰጭ በሌለበት ይግባኙን አይቶ የሰጠው ውሣኔ ላይ የተፈፀመ የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት ሊታረም የሚቻለው በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው የይግባኝ ሥርዓት በመጠቀምና ይህ የይግባኝ ሥርዓት በሌለበት ሁኔታ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ በሰበር ታይቶ እንዲታረም በመጠየቅ መሆን አለበት የሚል እምነት አለን፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው ሥርዓት መሠረት ይግባኙ መልስ ሰጭ በሌለበት ታይቶ የሚወሰነው፡-

- ተከሣሽ የወንጀል ክሱን በመጀመሪያ በሚሰማበት ጊዜ ቀርቦ ተከራክሮ የሥር ፍ/ቤት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ሲወስን፣ ተከሣሹ የጥፋተኝነቱን ውሣኔ ወይም የቅጣቱን ውሣኔ ወይም የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔውን በመቃወም ያቀረበው ይግባኝ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሚሰማበት ጊዜ መልስ ሰጭው /ዐቃቤ ሕግ/ ያልቀረበ በሆነ ጊዜ፣
- ተከሣሹ የተወሳሰቡትን የወንጀል ድርጊት የፈፀመና ጥፋተኛ መሆኑን በማመን ክሱን ለሚሰማው ፍ/ቤት በሰጠው የዕምነት ቃል መሠረት የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ

የተሰጠበት በሆነ ጊዜና ተከሣሹ የቅጣት ውሣኔውን በመቃወም በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 185 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ያቀረበው ይግባኝ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሚሰማበት ጊዜ መልስ ሰጭ/ዐቃቤ ሕግ/ ያልቀረበ በሆነ ጊዜ፣

- ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው ፍ/ቤት የወንጀል ክሱንና ክርክሩን ተከሣሹ በሌለበት (default) በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 መሠረት አይቶ በተከሣሹ ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የሰጠ ሲሆንና ተከሣሹ በሌለበት የተሰጠውን ፍርድ ለማሰረዝ ያቀረበው ማመልከቻ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 201 በተደነገጉት ድንጋጌዎች መሠረት ከታየ በኋላ ማመልከቻው በአንቀጽ 202 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ተቀባይነት ያላገኘ ተከሣሽ በሌለበት የተሰጠውን የቅጣት ውሣኔ በመቃወም በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ያቀረበው ይግባኝ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሚሰማበት ጊዜ መልስ ሰጭ /ዐቃቤ ሕግ/ ያልቀረበ ሲሆን፣
- ተከሣሽ ባለበት ጉዳዩን ያየው ፍ/ቤት ተከሣሽ ለጊዜው እንዲለቀቅ ወይም በነፃ እንዲሰናበት የሰጠውን ፍርድ በመቃወም ዐቃቤ ሕግ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 181 እና አንቀጽ 185 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ያቀረበው ይግባኝ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሚሰማበት ጊዜ መልስ ሰጭ/ተከሣሹ/ ያልቀረበ ሲሆን፣
- ተከሣሽ ባለበት ጉዳዩን ያየው ፍ/ቤት በተከሣሽ ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የወሰነ ሲሆንና ዐቃቤ ሕግ ፍርድ ቤቱ የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ ወይም የቅጣት ውሣኔ ወይም የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔውን በመቃወም በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 181 እና አንቀጽ 185 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ያቀረበው ይግባኝ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሚሰማበት ጊዜ መልስ ሰጭ/ተከሣሽ/ ያልቀረበ ሲሆን፣
- የወንጀል ክሱን በመጀመሪያ ያየው ፍ/ቤት የወንጀል ክሱን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 በተደነገገው መሠረት ተከሣሹ በሌለበት (default) በማየት ተከሣሹ በነፃ እንዲሰናበት የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ዐቃቤ ሕግ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 181 እና አንቀጽ 185 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ያቀረበው ይግባኝ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሚሰማበት ጊዜ መልስ ሰጭ/ተከሣሽ/ ያልቀረበ ሲሆን፣
- የወንጀል ክሱን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 በተደነገገው ሥርዓት መሠረት ተከሣሹ በሌለበት ያየው ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ ወይም የቅጣት ውሣኔ ወይም የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በመቃወም ዐቃቤ ሕግ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 181 እና አንቀጽ 185 ንዑስ አንቀጽ 2 ያቀረበው ይግባኝ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሚሰማበት ጊዜ መልስ ሰጭ/ተከሣሽ/ ያልቀረበ ሲሆን፣
- ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መልስ ሰጭ ባለበት ወይም በሌለበት ይግባኙን አይቶ በሰጠው ፍርድ ላይ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ሁለተኛ ይግባኝ ማቅረብ የሚቻል በሆነ ጊዜ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በመቃወም ዐቃቤ ሕግ ወይም ተከሣሹ ያቀረቡትን ይግባኝ ለማሰማት በተያዘው ቀን ቀጠሮ መልስ ሰጭ ሳይቀርብ ሲቀር በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 አንቀጽ 2 ተፈፃሚነት አለው፡፡

4. ከላይ በተገለፁት ሁኔታዎች ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መልስ ሰጭው በሌለበት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ይግባኙን መርምሮ በወንጀለኛ



www.chilot.me

መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2 ከተደነገጉት ድንጋጌዎች በአንደኛው የተመለከተውን ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን አለው፡፡ በያዝነው ጉዳይ የከፍተኛው ፍ/ቤት ተከሣሹ አመልካች በሌለበት የወንጀል ክሱን በማየት ተከሣሽ በነፃ እንዲሰናበት የሰጠው ፍርድ ላይ ተጠሪ ያቀረበውን ይግባኝ መልስ ሰጭ/አመልካች/ በሌለበት ሰምቶ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ መሠረት የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔን በመሻር በአመልካች ላይ የጥፋተኝነትና የጥፋት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኙን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ 193 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በማየት የሰጠውን ፍርድ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ጉዳዩን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 202 በተደነገገው ሥርዓት መሠረት አይቶ ፍርዱን ውድቅ እንዲያደርግለት ያቀረበው ማመልከቻ የሕግ መሠረት የለውም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ይግባኙን መልስ ሰጭ በሌለበት አይቶ የሰጠውን ፍርድ ውቅድ እንዲያደርግለት አመልካች በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 202 በተደነገገው ሥርዓት መሠረት ያቀረበውን ማመልከቻ በመቀበል የአመልካችንና የተጠሪን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች በቂ ምክንያት ያላቀረበ በመሆኑ ፍርዱ አይሰረዝም በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 2ን በመጥቀስ ሰኔ 7 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ የሕግ መሠረት የለውም፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በማናቸውም ምክንያት የቀረበለትን ይግባኝ መልስ ሰጭ በሌለበት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 ሰምቶ የሰጠው ፍርድ ውድቅ እንዲደረግ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 202 በተደነገገው ሥርዓት መሠረት ለመመልከት የሚፈቅድ የሕግ ድንጋጌ የለም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መልስ ሰጭ በሌለበት አይቶ የሰጠው ፍርድ ላይ የተፈፀመ የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት የሚታረምበት ሥርዓት በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው መስፈርት የተሟላ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ የተዘረጋውን የይግባኝ ሥርዓት በመጠቀም ነው፡፡ ጉዳዩ ከላይ በተገለፀው የሕግ ድንጋጌ የተዘረጋውን መሥፈርት የማያሟላ ሲሆን ወይም በዚህ መዝገብ እንደተያዘው ጉዳዩን ለሁለተኛ ጊዜ በይግባኝ አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው ፍ/ቤት ወይም ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሌለ ጊዜ ስህተቱ የሚታረመው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 የተዘረጋውን የሰበር ሥርዓት በመጠቀም ነው፡፡

ከላይ ከደረስንበት መደምደሚያ ላይ ለመድረስ ከዚህ በፊት በሰፊው ከገለፅናቸው ምክንያቶች በተጨማሪ የአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 አቀራረፅ እና የቃል በቃል ንባብ መገናዘብ አለበት የሚል እምነት አለን፡፡ "የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሥልጣን" የሚል ርዕስ ያለው የአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 "የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሚከተሉትን ጉዳዮች በይግባኝ የማየት ሥልጣን ይኖረዋል"

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ ውሣኔ የሰጠባቸው ጉዳዮች፣

2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ የተለየ ውሣኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች በማለት ይደነግጋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች በሌለበት አይቶ በነፃ እንዲሰናበት በተሰጠው ውሣኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ወስኗል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 10 መሠረት የሰበር አቤቱታ ለማቅረብ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ይግባኙን በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት መልስ ሰጭ ባለበት አይቶ ውሣኔ መስጠቱ በመስፈርትነት አልተደነገገም፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ችሎት መልስ ሰጭ በሌለበት ይግባኙን



www.chilot.me

ሰምቶ በሰጠው ውሣኔ የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ ከሻረ ወይም ካሻሻለ መልስ ሰጭ ያለው ብቸኛ አመራጭ የሰበር አቤቱታ ማቅረብ መሆኑን የሚደነግግ የሕግ ድንጋጌ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ አሻሽሎ ያቀረበውን የወንጀል ክስ ተከሳሹ/አመልካች/ በሌለበት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 በተደነገገው መሠረት አይቶ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተከሣሹ/አመልካች/ በነፃ እንዲሰናበት የሰጠውን ፍርድ በመቃወም ተጠሪ ያቀረበውን ይግባኝ መልስ ሰጭ/አመልካች/ በሌለበት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 192 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በማየትና የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ መሠረት በመሻር በአመልካች ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሣኔ ይግባኝ የሚያይ ሌላ ችሎት ወይም ፍ/ቤት የለም ይህም በመሆኑ አመልካች ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኙን በሌለበት አይቶ በሰጠው ውሣኔ ላይ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ይግባኝ ለማቅረብ አይችልም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች/መልስ ሰጭ/ በሌለበት ይግባኙን በማየት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በይግባኝ የማይታይ ወይም ከሰበር ውጭ በሌላ መንገድ ሊታይም የማይችል የመጨረሻ ውሣኔ ነው፡፡

ስለሆነም አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ ያቀረበውን ይግባኝ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት መልስ ሰጭ/አመልካች/ በሌለበት አይቶ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ በመሻር በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 195 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ መሠረት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ሲወስን ፈፅሞታል የሚለውን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በሰበር ታይቶ እንዲታረምለት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ በሰበር ችሎቱ እንዳይታይ የሚገድብ ወይም የሚከለክል ግልፅ የሆነ የሕግ ድንጋጌ የለም፡፡ በዚህ በኩል አብላጫው ድምፅ ጉዳዩ በሰበር የሚታይና የሚታረም አይደለም ከሚለው መደምደሚያ ላይ የደረሰው በጉዳዩ የተሰጠ "የመጨረሻ ውሣኔ" የለም በማለት ሲሆን በእኛ በኩል ጉዳዩ በይግባኝ ሰሚ ችሎት የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበትና በሰበር ሊታይ የሚችል ውሣኔ በመሆኑ ተጠሪ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ያቀረበለት ይግባኝ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በማየት የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ መሠረት በሰጠው ፍርድ ላይ ተፈፅሟል የሚለውን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በሰበር ታይቶ እንዲታረምለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት የሰበር አቤቱታ እንዳያቀርብ የሚገድብ ወይም የሚከለክል የሕግ ድንጋጌ የለም፡፡ በዚህ በኩል አብላጫው ድምፅ ጉዳዩ "የመጨረሻ ውሣኔ" አላገኘም በማለት የሰጠውን የሕግ ትርጉም ከላይ በዝርዝር በገለጽነው ምክንያት አልተቀበልነውም፡፡

5. አብላጫው ድምፅ ጉዳዩ በሰበር የሚታይ አይደለም ከሚለው መደምደሚያ ላይ የደረሰው በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ድንጋጌ መሆኑን በመዘርዘር ነው፡፡ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ አቀራረፅና የቃል በቃል ንባብ "ማመልከቻው ፍ/ቤቱ ሣይቀበል ቀርቶ ውድቅ እንዲሆን በመወሰኑ ይግባኝ ማለት አይቻልም ነገር ግን ስለተፈረደበት ቅጣት ብቻ ማመልከቻው ውድቅ እንዲሆን ከተወሰነበት ቀን አንስቶ በአሥራ አምስት ቀን ጊዜ ውስጥ ይግባኝ ቢል አይከለከልም" የሚል ነው፡፡

ይህ ድንጋጌ የወንጀል ክስ ተከሣሹ በሌለበት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 በማየት ወንጀል ክሱን ተከሣሹ በሌለበት (default) ያየው ፍ/ቤት በተከሣሽ ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የሰጠ በሆነ ጊዜ ብቻ ተፈፃሚነት ያለው የሕግ ድንጋጌ ነው፡፡ ድንጋጌው ሁለት ደንቦች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው የወንጀል ክሱ በሌለበት የታየ ተከሣሽ በሌለበት የተሰጠው ፍርድ ውድቅ እንዲሆንለት ያቀረበው ማመልከቻ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 201 በተደነገገው ሥርዓት ከታየ በኂላ ማመልከቻው ተቀባይነት የለውም ተብሎ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የተወሰነበት ተከሣሽ የሥር ፍ/ቤት አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ በሰጠው ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ማለት የማይችል መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡ ሁለተኛው ደንብ በሌለበት የወንጀል ክሱ ታይቶ ፍርድ የተሰጠበት ተከሣሽ ፍርድ ውድቅ እንዲደርግለት ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት ያቀረበው ማመልከቻ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት አቤቱታው ተቀባይነት ያላገኘ ተከሣሽ ፍ/ቤቱ ክሱን በሌለበት አይቶ በሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔን በመቃወም ይግባኝ ለማቅረብ የማይችል መሆኑንና በቅጣት ውሣኔ ላይ ብቻ ይግባኝ የማለት መብት ያለው መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡ ይህ የሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 202 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ገዥ ደንብ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 181 በወንጀል ፍርድ ላይ ይግባኝ ስለሚቀርብበት ሁኔታ ከደነገገው ጠቅላላ መርህ በልዩ ሁኔታ የተደነገገ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የወንጀለኛ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 3 በይዘቱም ሆነ በሚያስከትለው ህጋዊ ውጤት ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 185 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ጋር ተመሣሣይነት ያለውና በሌለበት የወንጀል ክስ ታይቶ የተሰጠን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ውድቅ ለማስደረግ ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት ያላገኘ ተከሣሽ በቅጣት ውሣኔው ላይ ብቻ ይግባኝ ማለት እንደሚችል ግልጽ የሚያደርግ ነው፡፡

የቀረበበትን የወንጀል ክስ በሙሉ በማመኑ ምክንያት በዕምነቱ መሠረት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 134/1/ መሠረት የጥፋተኝነት ውሣኔ የተሰጠበት ሰው የቅጣት ውሣኔውን በመቃወም ካልሆነ በስተቀር በጥፋተኝነቱ ውሣኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ እንደማይቻል የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 185 ንዑስ አንቀጽ 1 ከደነገገው በተጨማሪ ተከሣሽ የጥፋተኝነት ውሣኔውን በመቃወም ይግባኝ የማያቀርብበት ሁኔታ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው ሁኔታ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ በአምስተኛው መጽሐፍ በሁለተኛው አንቀጽ ተከሣሹ በሌለበት ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ከአንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 ታይቶ የተሰጠውን ፍርድ ውድቅ ለማድረግ በሚቀርብ ማመልከቻ ላይ ብቻ ተፈፃሚነት ያለው ነው፡፡ ድንጋጌው በሥነ-ሥርዓት ሕጉ አምስተኛው መጽሐፍ አንደኛ አንቀጽ የወንጀል ፍርድ በይግባኝ ስለሚታረምበት ሁኔታ ከአንቀጽ 181 እስከ አንቀጽ 196 በደነገገው ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት የሌለው በመሆኑ አብላጫው ድምፅ ጉዳዩ በሰበር የሚታይ አይደለም በማለት የተሰጠው ትርጉም ተገቢ ሆኖ አልታየንም፡፡

6. በወንጀለኛ መቀጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 202 የተደነገጉት ድንጋጌዎች በጠቅላላውና የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 3 በዚህ መዝገብ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነትና ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑን ከተራ ቁጥር 1 እስከ ተራ ቁጥር 5 ዘርዝረናል፡፡ አብላጫው ድምፅ እንደተረጎመው እነዚህ ድንጋጌዎች ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ይግባኙን መልስ ሰጭ በሌለበት በማየት በሰጠው በጥፋተኝነትና በቅጣት ውሣኔ ላይ ተፈፃሚነት አላቸው የሚባል ቢሆን እንኳን የሰበር ችሎቱ አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ

ውሣኔ ከመስጠት እነዚህ ድንጋጌዎች በጠቅላላው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 3 ሁኔታ የሚከለክሉ ወይም የሚገድቡ አይደሉም፡፡

ለዚህም የመጀመሪያው ምክንያት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 202 ያሉትን ድንጋጌዎች ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መልስ ሰጭ በሌለበት አይቶ በሰጠው ፍርድ ላይ የማመሳሰል የሕግ አተረጓጎም ዘዴን በመጠቀም ተፈፃሚ ሲሆኑ ጥብቅና ጠባብ የሆነ ትርጉም ሊሰጣቸው የሚገባ መሆኑ ነው፡፡ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ድነጋጌዎች የሙግት ሂደትን በአግባቡ ለመምራትና የተከሣሹን መሠረታዊ መብቶች የሚከበሩበትን ሥርዓት የሚደነግጉ ናቸው፡፡ ስለሆነም አንድ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌ በሚተረጎምበት ጊዜ ሠፊና የተለጠጠ ትርጉም በመስጠት መሠረታዊ መብቶችንና ነፃነቶችን በሚያሣጣ መንገድ ሊተረጎም አይገባውም፡፡ የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎችን በጥብቅና በጠበበ መንገድ በመተርጎም በህገ መንግሥቱ እና በሌሎች የሕግ ማዕቀፎች የተደነገጉ የስህተት ማረሚያ ሥርዓቶች ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ የማያሠናክል ወይም አላስፈላጊ ገደብ በማይጥል መንገድ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል የሚል እምነት አለን፡፡

የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 3 ተከሣሹ በሌለበት የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ ላይ ይግባኝ እንዳያቀርብ ገደብ የሚጥል ነው፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 181 እስከ እስከ አንቀጽ 196 የተደነገገው የይግባኝ ሥርዓት የሰበር ችሎት በሚጠቀምበት ጊዜ በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 የተዘረጋውን የሰበር ሥርዓት ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ የማያጣብብና ዜጎች መሠረታዊ የሕግ ሥህተት አለበት የሚሉትን የመጨረሻ ውሣኔ በሰበር እንዲታረምላቸው የመጠየቅ እድላቸውን በማያጣብብ ሁኔታ መተርጎምና ተፈፃሚ መሆን አለበት፡፡

ሁለተኛው ምክንያት በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 የተዘረጋው የሰበር ሥርዓት መሠረታዊ ዓላማና ግብ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ማናቸውም የመጨረሻ ውሣኔ በሰበር ታይቶ ሊታረም የሚችልበትን እድል በመፍጠርና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትን ውሣኔ በሰበር አይቶ በማረም በአገሪቱ ውስጥ ወጥ የሆነ የሕግ አተረጓጎምና ተፈፃሚነት እንዲቀር ማድረግ ነው፡፡ ሌላው የሰበር ዓላማ ህጋዊ ያልሆነ ውሣኔ እንዳይፀና ማድረግ ሲሆን ከይግባኝና ከሌሎች ሥርዓቶች የተለየ መሆኑን ይህ የሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 42239 ጥቅምት 29 ቀን 2003 ዓ.ም. በሰባት ዳኞች በተሰየሙበት በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አቋም የያየዘበት ነው፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መልስ ሰጭ/አመልካች/ በሌለበት በማየትና የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ መሠረት በመሻር በሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ላይና የአመልካችና የተጠሪ ክርክር ባለፈባቸው ሂደቶች ተፈፅሟል የሚለው የሕግ ስህተት እንዲታረምለት አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ መመርመር የሰበር ሥርዓት ከተዘረጋበት መሠረታዊ ዓላማና ግብን መሠረት ያደረገ ሆኖ እያለ ጉዳዩ ለሰበር ቀርቦ እንዳይታይ የሚከለክል የሕግ ድንጋጌ በሌለበት ጉዳዩ በሰበር የሚታይ አይደለም መባሉ ተገቢ ነው የሚል እምነት የለንም፡፡

7. አብላጫው ድምፅ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 199/ሀ/ እና /ለ/ን በመጥቀስ አመልካች ከፍትህ ርቆ ወይም ሸሽቶ የነበረ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 ይግባኙን በሌለበት አይቶ የሰጠው ፍርድ ውድቅ እንዲደረግለት ያቀረበውን አቤቱታ ያልተቀበለው መሆኑን በመግለጽ የሰጠው ምክንያት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ክርክር ያለፉበትን ረዥምና ውስብስብ ሂደት ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ምክንያቱም ተጠሪ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 526 ንዑስ አንቀጽ 1ን በመጥቀስ ያቀረበው የወንጀል ክስ ሲሰማ አመልካች ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ተከራክሮ

ፍ/ቤቱ በብይን በነፃ አሰናብቶታል፡፡ ተጠሪ በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሲያቀርብ አመልካች በይግባኝ ሰሚው ችሎት ቀርቦ ተከራክሮ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሣኔ በመሻር የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን መከላከያ ሰምቶ እንዲወስን የሰጠውን ውሣኔ በማክበር በከፍተኛው ፍ/ቤት ቀርቦ ከተከራከረ በኂላ የከፍተኛው ፍ/ቤት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 526 ንዑስ አንቀጽ 1ን የተላለፈ ጥፋተኛ ነው በማለት የወሰነበትን የገንዘብ መቀጮ ከፍሏል፡፡

የከፍተኛው ፍ/ቤት አመልካች በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 526 ንዑስ አንቀጽ 1ን በመተላለፍ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት ፍርድ የሰጠው ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪ ክሱን የማያስረዳ ማስረጃ ስላቀረበ የአመልካችን መከላከያ ሰምተህ ወስን በማለት የሰጠውን ፍርድ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ የወንጀል ክስ ከተጀመረበት 1995 ዓ.ም. ጀምሮ የከፍተኛው ፍ/ቤት ጥር 13 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ አመልካች እስከፈፀመበት ጊዜ ድረስ ረዥም ጊዜ አመልካች በክርክር የቆየ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ተጠሪ ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 119 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ውጭና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪ በክሱ በጠቀሰው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 526 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የአመልካችን መከላከያ ማስረጃ ሰምቶ የከፍተኛው ፍ/ቤት እንዲወስን በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 26293 የሰጠውን ፍርድ በማያስለውጥ ሁኔታ ተጠሪ አቅርቦት የነበረውን የወንጀል ክስ በመተው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 522 ንዑስ አንቀጽ 1ን በመጥቀስ ክሱን ለማሻሻል ያቀረበውን ጥያቄ የከፍተኛው ፍ/ቤት ውድቅ ያደረገው በመሆኑ ተጠሪ ይግባኝ አቅርቦ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የከፍተኛው ፍ/ቤት የተጠሪን የተሻሻለ ክስ ተቀብሎ አከራክሮ እንዲወስን በሰጠው ውሣኔ መሠረት የተሻሻለው ክስ ሲሰማ አመልካች ያልቀረበ መሆኑን በመዝገቡ የተደረገው የክርክር ሂደት ያሣያል፡፡ ይህ ሂደት አመልካች ከፍትህ ርቆና ሸሽቶ የኖረ መሆኑን አያሣይም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 26293 የሰጠውን ፍርድ በሚለውጥና የሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 119 ከሚደነግገው ሥርዓት ውጭ ተጠሪ ክሱን እንዲያሻሽል በመፍቀዱ ምክንያት በክርክሩ ሂደት ችግሮች የተፈጠሩ መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱን ግብ ለማሣካት የሚቻለው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 22 እና በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 2 የተደነገገውን የህጋዊነት መርህ በሚያከብር ሁኔታ የፍትህ አካላቱ ኃላፊነታቸውን ሲወጡ ነው የሚል እምነት አለን፡፡ ሰበር በወንጀል ጉዳይ በተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ በህገ መንግሥቱና በወንጀል ሕጉ የተደነገጉ መሠረታዊ መርሆች መከበራቸው የሚረጋገጥበት ሥርዓት ነው፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች በሌለበት የሰጠው ፍርድ ላይ አለ በማለት በሰበር አቤቱታው የገለፃቸው የሕግ አተረጓጎም የወንጀል ሕጉን ግብ የማያሣካ ነው የሚል እምነት የለንም፡፡

8. አብላጫው ድምፅ የአመልካች ጉዳይ በሰበር የሚታይ አይደለም በማለት የሰጠውን ውሣኔ ለማጠናከር የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አገሪቱ ያፀደቀችውን የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 3/መ/ በዋቢነት ጠቅሷል፡፡ በእኛ በኩል ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 14 በጠቅላላውና ንዑስ አንቀጽ 3/መ/ በልዩ ሁኔታ በአቀራረቡም ሆነ በይዘቱ የወንጀል ክስ ተከሣሽ ባለበት መታየት ያለበት መሆኑን የሚደነግግና በወንጀል የተከሰሰ ሰው ሊከበርለት የሚችል ሰፊ መብት ያለው መሆኑን በዝርዝር የሚደነግግ እንጅ የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ቀርቦ ሊታይ የሚችልበት ሁኔታ በማናቸውም መንገድ የሚያጣብብ ይዘት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡



www.chilot.me

ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ የተጠቀሰው የሲቪልና የፖለቲካ መብት ቃል ኪዳን ስምምነት ድንጋጌ መተርጎም ያለበት መብትን በሚያሣጣ ወይም በሚያጣብብ መንገድ መሆን አይገባውም፡፡ ይህ ድንጋጌ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች መብት በሚያሣጣ ወይም በሚያጣብብ መንገድ ሊተረጎም የማይገባው መሆኑን ዓለም አቀፍ ህብረተሰብ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 1948 ዓ.ም. ባወጀው የሰብዓዊ መብቶች ሁለንተናዊ መግለጫ /The Universal Decleration of Human Rights) አንቀጽ 30 የደነገገውን የአተረጓጎም መርህ መሠረት ባደረገ ሁኔታ ትርጉም ሊሰጠው ይገባዋል የሚል እምነት አለን፡፡

በአጠቃላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ ተራ ቁጥር 8 በተጠቀሱት ምክንያቶች የሰበር ችሎት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታና ተጠሪ ያቀረበውን መልስና ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የሰጠውን ውሣኔ በመመርመር መዝገቡ ለሰበር ሲቀርብ በተያዘው ጭብጥ መሠረት ውሣኔ እንዳይሰጥ የሚከለክለው ሕግ በሌለበት ሁኔታ ጉዳዩ በሰበር የሚታይ አይደለም በማለት አብላጫው ድምፅ በሰጠው ውሣኔ ያልተስማማን በመሆናችን በሀሳብ ተለይተናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 57988

ጥር 10 ቀን 2003 ዓ.ም

*ዳኞች፣* ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

*አመልካች፣* ዬርዳኖስ አባይ አሰፋ የቀረበለት የለም

*ተጠሪ፣* የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የአሁኗ አመልካች በተከሰሰችበት የስርቆት ወንጀል በክሱ ላይ ተላልፋለች ተብሎ በተጠቀሰባት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 665/1/ መሠረት ጥፋተኛ ተብላ በ2 ዓመት ቀላል እሥራትና በብር 2500 የገንዘብ መቀጮ እንድትቀጣ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በሚል በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 80/3//ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10/3/ መሠረት የቀረበ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ሆነ በይግባኝ ቀርቦለት የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በጥፋተኛነቱም ሆነ በቅጣት አወሳሰኑ ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ግንቦት 5 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ይታይ በመባሉ ማመልከቻው ለተጠሪው ተልኮ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት አድርጓል ተጠሪው በጽሑፍ የሰጠው መልስ ለአመልካች ጠበቃ ደርሷቸው በጽሑፍ የመልስ መልስ ሰጥተውበታል፡፡

ይህ ችሎትም ጉዳዩን መርምሯል፡፡

እንደመረመረውም የአሁኑ አመልካች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 665/1/ን በመተላለፍ የስርቆት ወንጀል ፈጽማለች ተብላ የተከሰሰችው ከሌሎች ዋና የወንጀል አድራጊዎች ጋር በመሆን ቀን የግል ተበዳይዋ ቤት ገብተው ቁምሣጥን በመስበር በርካታ መጠን ያለው ገንዘብ የተለያዩ የወርቅ ጌጣጌጦች እና ሌሎች ቁሳቁሶችን ሰርቀው ወስደዋል በሚል ምክንያት መሆኑን መዝገቡ ያስረዳል፡፡

የአሁኗ አመልካች ክሱን ክዳ ብትከራከርም ዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች አቅርቦ አስረድቷል፡፡

ዐቃቤ ሕግ ካቀረባቸው ማስረጃዎች መካከል አንዱ የጽሑፍ ሲሆን የጽሑፍ ማስረጃውም የአሁኗ አመልካች በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 35 መሠረት ፍ/ቤት ቀርባ የስርቆቱን ድርጊት ስለመፈፀሟ በማመን ሰጥታለች የተባለው ቃል ነው፡፡ ይህንንም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 44948 በ14/11/2001 ዓ.ም በሰጠው የጥፋተኛነት ውሣኔ ላይ ገልጾታል፡፡ የአመልካች ጠበቃ በሰበር አቤቱታቸው ላይ እንዲህ አይነት የጽሑፍ ማስረጃ አልቀረበባትም አላሉም፡፡ ሚስጥር ሰለሞን የተባለችው የግል ተበዳይ ልጅ ከአሁኗ አመልካች ጋር በዚሁ የስርቆት ወንጀል አንደኛ ተከሣሽ መሆኗን ተከሳ እያለ የዐቃቤ ሕግ ምስክር እንድትሆን ተደርጐ ቀርባ ዐቃቤ ህግ በእርሷ ላይ አቅርቦት የነበረውን ክስ በማንሣት ምስክር እንድትሆን አድርጓል ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን ወንጀሉን ፈጽሟል ተብሎ ምርመራ ተጣርቶበት ክስ እንዲቀርብበት የተደረገው ሰው ተከሣሽ ከመሆን ይልቅ ምስክር መሆኑ ይጠቅመኛል ብሎ ዐቃቤ ሕግ በእርሱ ላይ አቅርቦት የነበረውን ክስ ማንሣት ምስክር እንዲሆን ማድረግን የሚከለክለው ሕግ ስለሌለ በዚህ ጉዳይ በ1ኛም ተከሣሽ ላይ አቅርቦት የነበረውን ክስ በማንሣት ምስክር አድርጐ ማቅረቡ የሚጥሰው ሕግ የለም፡፡ በአሁኗ አመልካች ላይ የቀረበባት ማስረጃ ምስክሯ ብቻ ሣትሆን ከፍ ሲል እንደተገለፀው የፅሑፍ ማስረጃም ቀርቦባታል አመልካች ወንጀሉን መፈፀሟ ተረጋግጦባታል የተባለው በእነዚህ ሁለት ማስረጃዎች ስለሆነ የአመልካች ጠበቃ ምስጥር ሰለሞን ክሱ ሣይነሣላት በተከሣሽነት ደረጃ እንዳለች እርሷ ብቻ ቀርባ እንዳመሰከረችባት አድርገው የገለጹት ትክክል አይደለም፡፡

የአሁኗን አመልካች በሚመለከት በማስረጃ የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ስለሥርቆት ወንጀል የሚያሣዩ አይደሉም በሚል የተነሣውን ክርክር በተመለከተም በማስረጃ የተረጋገጡበት ፍሬ ነገሮች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 665 ላይ የተመለከተውን የስርቆት ወንጀል በሚገባ የሚያቋቁሙ ሆነው ስለተገኙ በዚህ የሕግ አንቀጽ መሠረት ጥፋተኛ በመባሏ የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም፡፡

የተወሰነባትን ቅጣት በሚመለከት ፍ/ቤቱ በርካታ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች መኖራቸውን በቅጣት ውሣኔው ላይ ከገለፀ በኃላ ሁለተኛውን አማራጭ እስከ አምስት አመት የሚደርሰውን የጽኑ እሥራት ቅጣት በመተው የቀላል እሥራቱን ቅጣት በመከተል በ2 ዓመት ቀላል እሥራት እንድትቀጣ መወሰኑ ዕድሜዋ 17 አመት ነው የተባለውን ግምት ውስጥ ያስገባ የሚባል እንደሆነ እንጂ ያለአግባብ ከብዶባታል የሚያሰኝ አይደለም፡፡ በመሆኑም በቅጣት አወሳሰኑም ረገድ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም፡፡ ስለሆነም የሚከተለው ተወስኗል፡፡

## *<u>ው ሣ ኔ</u>*

1. በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ለ/2/ መሠረት ፀንቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት***

ም.አ



www.chilot.me

የሰበር መ/ቁ 47755

ግንቦት 5 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፣ ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፣ የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ዐቃቤ ሕግ ወርቅነህ ዘነበ ቀረበ

ተጠሪ፣ አቶ ሚፍታህ ኑረዲን ጠበቃ ግርማ ደጀኔ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው። ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው። በሥር ፍርድ ቤት አመልካች በተጠሪና በዚህ ክርክር ተካፋይ ባልሆኑ ሌሎች ሁለት ሰዎች ላይ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና አንቀጽ 346 የተመለከተውን በመተላለፍ በተጠሪ በተመዘገበ የንግድ ድርጅት /ሱቅ/ ውስጥ ተጠሪ ፈቃድ ሣይኖረው የውጭ አገር ገንዘብ በመመንዘርና የዘጠኝ የውጭ ሀገር ገንዘብ አከማችቶ የተገኘ ሲሆን ሌሎች ተከሣሾች የወንጀሉ ሥራ ተካፋይ በመሆናቸው የውጭ አገር ገንዘብ በህገወጥ መንገድ የመመንዘር ወንጀል ፈፅመዋል በማለት ክስ አቅርቧል። አመልካች ካቀረበው የወንጀል ክስ ጋር በተጠሪ ሱቅ ውስጥ

1. የኢትዮጵያ ብር 1,275,159 /አንድ ሚሊዬን ሁለት መቶ ሰባ አምስት ሺህ ብር አንድ መቶ ሃምሣ ዘጠኝ ብር/
2. የአሜሪካን ዶላር 6,042 /ስድስት ሺህ አርባ ሁለት የአሜሪካን ዶላር/
3. የአውሮፖ ህብረት ዩሮ 920 /ዘጠኝ መቶ ሃያ ዩሮ/
4. የእንግሊዝ ፖውንድ 40 /አርባ የአንግሊዝ ፖውንድ/
5. የአረብ ኢምሬት 205 /ሁለት መቶ አምስት AED/
6. የሳውዲ አረቢያ ሪያል 2,261 /ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ስልሣ አንድ ሪያል/
7. የስዊዝ / CHF/ 1400 /አንድ ሺህ አራት መቶ የስዊዝ CHF/
8. የኳታር ገንዘብ 7.00 /ሰባት የኳታር ገንዘብ/
9. የካናዳ ዶላር 2.00 /ሁለት የካናዳ ዶላር በኤግዚቢትነት የተያዘ መሆኑን ከአቀረበው የወንጀል ክስ ጋር በመዘርዘር አቅርቧል። ተጠሪ ወንጀሉን አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም ብለው



www.chilot.me

ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የአመልካችን ማስረጃ ከሰማ በኃላ ተጠሪ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ የተጠሪን የመከላከያ ማስረጃ ሰምቷል የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኃላ ተጠሪ በወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና አንቀጽ 346 የተመለከተውን በመተላለፍ በህገወጥ መንገድ የውጭ አገር ገንዘብ የመነገድ ወንጀል ፈፅሟል በማለት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሣኔ ከሰጠ በኃላ አመልካችና ተጠሪ የቅጣት ውሣኔ አስተያየት እንዲሰጡ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ፍርድ ቤቱ ተጠሪን ሊያርምና ሊያስተምር የሚችል የቅጣት ውሣኔ እንዲሰጥለትና በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተገኙት የውጭ አገር ገንዘቦች ውርስ ሆነው ለመንግስት ገቢ እንዲሆኑ የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ እንዲሰጥለት የቅጣት አሰተያየት አቅርቧል፡፡ ተጠሪም 4 ገጽ የቅጣት አስተያየት በፅሑፍ አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት ከመረመረ በኃላ ተጠሪ በሁለት ዓመት ፅኑ እስራትና በብር 30,000 /ሰላሳ ሺህ ብር/ እንዲቀጣ ወስኖ የፅኑ እስራት ቅጣቱን በሁለት ዓመት የሙከራ ጊዜ እንዲገደብ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዙት የውጭ አገር ገንዘቦች በመንግስት እንዲወረሱ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዘው የኢትዮጵያ ገንዘብ እንዲወርስ ትዕዛዝ ሣይሰጥ ማለፉ የወንጀል ህጉን አንቀጽ 346 እና አንቀጽ 48 የሚጥስ ነው ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዘው የኢትዮጵያ ገንዘብ እንዲወረስ ትዕዛዝ ሣይሰጥ በዝምታ ማለፉ ተገቢ ባለመሆኑ በይግባኝ ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የይግባኝ ቅሬታ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የቅጣት ውሣኔና ትዕዛዝ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ሀምሌ 11 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በይግባኝ ያነሳቸውን የቅሬታ ነጥቦች በማንሣት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ተጠሪ በህገወጥ መንገድ የውጭ አገር ገንዘብ የመመንዘር ወንጀል የፈፀመ መሆኑ ተረጋግጦ ጥፋተኛ ተብሏል፡፡ ስለዚህ የወንጀሉ ድርጊት የሥራ ፍሬ የሆነውና በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዘው የኢትዮጵያ ገንዘብ እንዲወረሱ ትዕዛዝ ሣይሰጥ የሥር ፍርድ ቤት በዝምታ ማለፉና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ሚያዚያ 19 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ባደረግነው ክርክር ከተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዘው የኢትዮጵያ ብር እንዲወረስ ትዕዛዝ ይሰጥልኝ በማለት አላመለከተም፡፡ በተቃራኒው አመልካች እንዲወረስ ትዕዛዝ እንዲሰጥለት የሚፈልገው የውጭ አገር ገንዘቦችን ብቻ መሆኑንና በተጠሪ ሱቅ የተያዘውን ገንዘብ እንደማይጨምር በግልፅ አስተያየት ሰጥቷል፡፡ ስለዚህ በስር ያልተከራከረበትን ፍርድ ቤቱ አለፈብኝ በማለት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ የህግ መሠረት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ሚያዚያ 20 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

ግራቀኙ በፅሑፍ ካደረጉት ክርክር በተጨማሪ ችሎቱ ሀምሌ 15 ቀን 2002 ዓ.ም የግራቀኙን ክርክር ሰምቷል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ ሱቅ የተገኘው የኢትዮጵያ ብር እንዲወረስ አስተያየት መስጠቱን በማንሣት የተከራከረ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው አመልካች የኢትዮጵያ ገንዘብ እንዲወርስ በሥር ፍርድ ቤት አልተከራከረም፡፡ አመልካች የመወረስ ትዕዛዝ የኢትዮጵያን ብር እንዲጨምር እንደማይፈልግ በመግለፅ ነው አስተያየት የሰጠው የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ ግራቀኙ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በሰጠው የቅጣት አስተያየት በተለይም በተጠሪ

ሱቅ ውስጥ ስለተያዘው የኢትዮጵያ ገንዘብ አመልካች ባቀረበው ክርክር ይዘት ላይ ሰፊ ልዩነት ያላቸው በመሆኑ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ ሶስተኛ የወንጀል ችሎት የአመልካችንና የተጠሪን ክርክር ከመቅረፀ ድምፅ ያቀረቡትን ካሴት እንዲልክ ችሎቱ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 124880 ያደረጉት ክርክር የተቀረፀን ካሴት በፖስታ በማሸግ ህዳር 8 ቀን 2003 በተፃፈ መሸኛ ልኳል፡፡ ይህ የሰበር ችሎትም አመልካችና ተጠሪ ያቀረቡትን የቅጣት አስተያየትና ክርክር የተቀረፀበትን ካሴት ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ.ም በቴፕ ሪከርደር ሰምቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዘው የኢትዮጵያ ብር እንዲወረስ ትዕዛዝ ሣይሰጡ ማለፉ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ይህንን ጭብጥ ለመወሰን አመልካች የተጠሪ ሱቅ ውስጥ ስለተያዘው የኢትዮጵያ ገንዘብ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረበውን አስተያየትና የውሣኔ ሃሣብ ትክክለኛ ይዘት መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና ለሰበር ችሎት የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተገኘው የኢትዮጵያ ገንዘብ እንዲወረስ ትዕዛዝ ሣይሰጥ በዝምታ ማለፉ የወንጀል ህግ አንቀጽ 346 እና የወንጀል ህግ አንቀጽ 98ን የሚጥስ መሆኑን በመጥቀስ በሰፊው የሚያቀርበውን ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ባቀረበው የቅጣት አስተያየትና የውሣኔ ሃሣብ በማንሣት እንዳልተከራከረ በመቅረፀ ድምፅ ከተቀዳው የአመልካች የቅጣት አስተያየትና የውሣኔ ሃሣብ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ላይ የጥፋተኝነት ውሣኔ ከሰጠ በኃላ አመልካች የቅጣት አስተያየትና የውሣኔ ሃሣቡን እንዲያቀርብ እድል ሲሰጠው ፍርድ ቤቱ ተጠሪን ሊያርምና ሊያስተምር የሚችል የቅጣት ውሣኔ እንዲሰጥለት የጠየቀ መሆኑንና በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተገኙ የውጭ ገንዘቦች እንዲወረሱ ውሣኔ እንዲሰጥለት የጠየቀ መሆኑን በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዘው የኢትዮጵያ ገንዘብ እንዲወረስ ያቀረበው የቅጣት አስተያየትና የውሣኔ ሃሣብ እንደሌለ ተገንዝበናል፡፡ በተቃራኒው አመልካችን በመወከል ለችሎቱ የቅጣት አስተያየትና የውሣኔ ሃሣብ ያቀረቡት ዐቃቤ ሕግ በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዙት የውጭ ገንዘቦች እንዲወረሱ ያቀረቡት የውሣኔ ሃሣብ እንደተጠበቀ ሆኖ የመወረስ ትዕዛዙ በተጠሪ ሱቅ የተያዘውን የኢትዮጵያ ገንዘብን የማይጨምር መሆን እንዳለበት በግልፅ አስተያየትና የውሣኔ ሃሣብ ያቀረበ መሆኑን ችሎቱ በትዕዛዝ አስቀርቦ ከሰማውና በመቅረፀ ድምፅ የተቀረፀው የቅጣት አስተያየትና ይህንን አስተያየት በፅሑፍ በመገልበጥ በሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ጋር ከተያያዘው ሰነድ ተገንዝበናል፡፡

አመልካች በወንጀል ክሱ በኤግዚቢትነት ዘርዝሮ ያቀረበውና ከተጠሪ የንግድ ሱቅ ውስጥ የተገኘው 1,275,159 /አንድ ሚሊዩን ሁለት መቶ ሰባ አምስት ሺህ አንድ መቶ ሃምሣ ዘጠኝ ብር/ ተጠሪ ጥፋተኛ ከተባለበት የወንጀል ድርጊት ጋር ግንኙነት አለው የሚልበትን ምክንያት በመግለፅ ይህ የኢትዮጵያ ገንዘብ እንዲወረስ የውሣኔ ሃሣብና ክርክር በሥር ፍርድ ቤት አላቀረበም፡፡ አመልካች ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው የመውረስ ትዕዛዝ በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዘውን የኢትዮጵያ ገንዘብ እንዲጨምር ክርክር የማያቀርብ መሆኑን የውሣኔ ሃሳቡን በግልፅ አስመዝግቧል አመልካች የተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዙት የውጭ ገንዘቦች እንዲወረሱና የኢትዮጵያ ገንዘብ እንዳይወረስ በግልፅ የቅጣት አስተያየትና የውሣኔ ሃሣብ ከቀረበ በኃላ የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዘው የኢትዮጵያ ገንዘብ እንዲወረስ ውሣኔ ሣይሰጥ አልፎብኛል በማለት ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና


www.chilot.me

ለሰበር ችሎት ያቀረበው ክርክር ምንም አይነት የህግ መሠረት የሌለውና በሙግት ሂደት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ አሰጣጥ ሂደት ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ነፃና ገለልተኛ ሆነው የመምራት የመመርመርና የመመዘንና ውሣኔ የመስጠት ህገመንግስታዊ ሃላፊነት ያለባቸው መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ክርክር ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

የአገሪቱን ህዝብና የፌዴራሉን መንግስት በመወከል በጉዳዩ ተከራካሪ ሆኖ የቀረበው አመልካች በክስ መከፈትና በመሰማት ሂደት ያለበት ግዴታና ሃላፊነት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 136 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የጥፋተኝነት ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ሊፈፅመው ስለሚገባው ተግባር በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 148 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ፍርድ ቤቱ የጥፋተኝነት ውሣኔ ከሰጠ በኃላ አመልካች ፍርድ ቤቱ ቅጣት ከመወሰኑ በፊት ሊመረምራቸው አስፈላጊም ከሆነ በማስረጃ አረጋግጦ ውሣኔ ሊሰጥባቸው የሚገቡ ነጥቦችና ክርክሩን ሊያስረዱለት የሚችሉ ማስረጃዎችን በመዘርዘር የቅጣት አስተያየትና የውሣኔ ሃሣብ የማቅረብ ሃላፊነት እንዳለበት በወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 149 ንዑስ አንቀጽ 3 ተደንግጓል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት አመልካች በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 149 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ያቀረበውን የቅጣት አሰተያየትና የውሣኔ ሃሣብ ከተቀበለና ተጠሪም የአመልካችን የቅጣት አሰተያየት የውሣኔ ሃሣብ መሠረት በማድረግ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 149 ንዑስ አንቀጽ 4 ያቀረበውን ክርክር ከተቀበለ በኃላ ጉዳዩን ነፃና ገለልተኛ ሆኖ በመመዘን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 149 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 149 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ግልፅ ክርክርና የውሣኔ ሃሣብ ያላቀረበበትን በተቃራኒው በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዘው የኢትዮጵያ ገንዘብ እንዲወረስ ክርክር የማያቀርብ መሆኑን በግልፅ አስተያየቱን ያስመዝገበበትን ጉዳይ የኢትዮጵያ ገንዘብ እንዲወረስ የሥር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ በዝምታ አልፎብኛል በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ከላይ የተደነገጉትን የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ያላደረገና አመልካች ለሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ ሱቅ ውስጥ ስለተገኘው የኢትዮጵያ ገንዘብ ያቀረበውን የውሣኔ ሃሣብ ትክክለኛ ይዘት የማያንፀባርቅ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዙት የውጭ አገር ገንዘቦች ብቻ እንዲወረሱ የሰጠው ውሣኔ በወንጀለኛ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 149 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት አመልካች ያቀረበውን የቅጣት አስተያየትና የውሣኔ ሃሣብ መሠረት ያደረገና ምንም አይነት የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ሀምሌ 24 ቀን 2001 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ይፃፍ፡፡
3. ከበታች ፍርድ ቤቶች የመጡትን መዝገቦችና ከሥር ፍርድ ቤት የመጣው ካሴት ይመለስ፡፡
4. መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

ም.አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 57446

ግንቦት 19 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አደነ ንጉሴ

**አመልካቾች፡-** ሃለቃ ገ/እግዚአብሔር ኃይሉ -ጠበቃ ፈቃዱ ያሚ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ**፡- የኦሮሚያ ክልል ዓ/ሕግ - በሌለበት የሚታይ ነው፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካች በተከሰሱበት የወንጀል ድርጊት የበታች ፍ/ቤቶች በሠጡት ጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ነው፡፡

አመልካች የተከሰሱት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 የተመለከተውን በመተላለፍ በቀን 02/06/2001 ዓ.ም ከምሽቱ 2፡30 ሰዓት ላይ የደን ጠባቂ ሆኖ ሲሰራ መንግስት ባስታጠቀው ክላሽ ጠመንጃ ሶስት ጥይት ተኩሶ ሟች አቶ ግደይ ትኩእ የተባሉትን መትቶ ገድሎታል በሚል ሲሆን አመልካች ስለድርጊቱ አፈፃፀም ክደው በመከራከራቸው ዐቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስጃዎችን በማቅረብ አስምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች እንዲከላከሉ ብይን ተሰጥቶ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ የሌላቸው መሆኑን በማረጋገጣቸው በዐቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበባቸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ተብለው በ20 /ሃያ አመት/ ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ተወስኖባቸዋል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለትግራይ ማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ የሰጠውን የጥፋተኛነት ውሳኔ በማጽናት ቅጣቱን ብቻ በማሻሻል 15/ አስራ አምስት ዓመት/ ጽኑ እስራት እንዲቀጡ በማለት ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ጉዳዩ በሰበር አቤቱታ የቀረበለት የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በጉዳዩ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በሚል ምክንያት አቤቱታውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አበቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው መሠረታዊ ይዘትም አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት ያላግባብ ከመሆኑም በላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበት ድንጋጌም በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችን ያላገናዘበ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚየሳይ ነው ፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ

መታየት ያለበት መሆኑ ታምኖበት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት መጥሪያ ደርሶት ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን እኛም ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር እና የሥር መዝገብ ውሳኔ ይዘት ከመረመረ በኋላ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ምላሽ የሚያሻው የሕግ ጥያቄ ሆኖ ያገኘው አመልካች ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በወ/ሕ/ ድንጋጌ አንቀጽ 540? ወይንስ 541? የሚለውን ነው፡፡ የህንኑ ለመፍታት የጉዳዩን አፈፃፀም እና መነሻ ሁኔታዎች በአጭሩ መመልከት ተገቢ ነው፡፡

ከሥር ፍ/ቤት መዝገብ መረዳት የተቻለው ፍሬ ነገር ወንጀሉ ተፈፀመ በተባለበት ቀን ሌሊቱን አመልካች ደን ለመጠበቅ ተቀጥረው ባለበትና መሳሪያውንም ለዚሁ አላማ ለማዋል በያዙት ሁኔታ የስር አቃቤ ሕግ ምስክሮችና ሟቹ ወደ ደኑ በመሄድ ዛፍ በመቁረጥ ላይ እያሉ በተፈጠረው አለመግባባት አመልካች ሁለት ጥይቶችን ከተኮሱ በኋላ ሶስተኛውን ጥይት በመተኮስ ሟችን በመምታት ለሕልፈት የዳረጉት መሆኑ በክርክሩ ሂደትና በአቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል ጭምር ከተነገረው የአመሰካከር ይዘት መስፈሩን ነው፡፡

በሌላ በኩል አመልካች የተከሰሱበትን ወንጀል ስለመፈጸማቸውም አምነው ክደው የሚከራከሩት የአፈጻጸሙን ሁኔታ ስለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የውሳኔ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ እንግዲህ አጠቃላይ የወንጀሉ አፈፃፀም ሁኔታ ይህንን የሚመስል ሲሆን አመልካች ለወንጀል ድርጊቱ ኃላፊነት የለብኝም በማለት እስከዚህ ችሎት አጥብቀው የተከራከሩ ቢሆንም ስለወንጀሉ አፈፃፀም እና የማስረጃ ምዘና ጉዳይ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን የሚታይ ባለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር እንዳለ በመቀበል በህግ ረገድ የሚኖረውን ውጤት ብቻ መመልከቱ ተገቢ መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪፑብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80/3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ በመሆኑ ጉዳዩን በሚከተለውን መልኩ አይተናል፡፡

አመልካች የተከሰሱበትን የወንጀል ድርጊት በሕዝብ ደን ላይ አደጋ ለመከላከል እንደሆነ ከፍ ሲል የተመለከተውን ፍሬ ነገር እና ከወንጀሉ አፈፃፀም ከባቢያዊ ሁኔታ መረዳት ይቻላል፡፡

ድርጊቱ ወንጀል ነው ቢባልም በሕግ በተመለከተ ልዩ ሁኔታ በሕግ በተፈቀዱ ድርጊቶች የማያስቀጡ እና ይቅርታ የሚያሰጡ ሁኔታዎች በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተመለከተውን ድንጋጌ ከተያዘው ጉዳይ ጋር ማየት ተገቢ ሆኖ አግኝተናል፡፡ ለተያዘው ጉዳይ ቀጥታና አግባብነት ያለውን የወንጀል ሕግ ድንግጋጌ ቁጥር 78 እንመለከታለን፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሠረት የራሱን ወይም የሌላውን ሰው መብት ሕገወጥ ከሆነ ጥቃት ወይም በቅርብ ከሚደርስ ሕገ ወጥ ጥቃት ለማዳን ጥቃቱ እንዳይደርስ ለማድረግ ሌላ መንገድ ሳይኖር ከሁኔታው መጠን ባለመለፍ የተፈፀመ ድርጊት አያስቀጣም ተብሎ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ተከሳሹ ከቅጣት ነፃ የሚሆነው ሕገወጥ ጥቃት በራሱ ወይም በሌላው ሰው መብት ላይ የተሰነዘረ ወይም በእርግጠኛነት ሊደርስ የሚችል ጥቃት ስለመኖሩ ይህንንም ለማስወገድ ወይም ለመከላከል ሌላ አማራጭ የሌለው ስለመሆኑ እና የወሰደው የመከላከል ወይም ጥቃቱን የማስወገድ እርምጃ ከተሰነዘረው ጥቃት ጋር ተመጣኝ ኃይል የተጠቀመ መሆኑን ማስረዳት ሲችል ብቻ ነው፡፡ ይህንኑ የሕጉን መንፈስ እና ይዘት መሰረት አድርገን የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከት በስር አቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል የተረጋገጠው ፍሬ ነገር በሕዝብ ደን ሟችና የአቃቤ ሕግ ምስክሮች በሌሊት



www.chilot.me

ሰዓት የዛፍ መቁረጥ ተግባር መፈፀማቸው አመልካችም ለደኑ ጥበቃ ከመንግስት የታጠቁትን መሣሪያ በወቅቱ ይዘው በጥበቃ ላይ የነበሩ ስለመሆኑ አመልካች ደኑን ለማስከበር ያደረጉትን ጥረት በሟች ጥቃት ተሰንዝሮባቸው የነበረ ስለመሆኑ እና በደኑ ላይ አደጋ ሲሰነዘር አመልካች ሟች ከሁለት ጥይት ተኩስ በኋላ በሶስተኛው ጥይት የመቱት መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ይህ ፍሬ ነገር የሚያስገነዝበን በደኑ የተቃጣ ሕገወጥ ጥቃት ስለመኖሩ ነው፡፡ ይህንን ጥቃት ለማስወገድ አመልካች ተኩሰው ሰው መግደላቸው እና ማቁሰላቸው ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን ተከትሎ የሚነሳው ጥያቄ አመልካች የተሰነዘረውን ጥቃት ለማስወገድ ሌላ አመራጭ ያልነበራቸው ስለመሆኑ እና የወሰዱት አማራጭም ተመጣጣኝ ስለመሆኑ አስረድተዋል ወይ? የሚለው ነው፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቧቸው መከላከያ ማስረጃዎች የሉም፡፡ አመልካች ሕገወጥ ጥቃትን ለማስወገድ እርምጃ ስለመውሰዳቸው የተመለከተ ቢሆንም እርምጃው ሌላውን አማራጭ የጨረሱ ስለመሆኑ እና ተመጣኝ ስለመሆኑ ለማስረዳት ያልቻሉ ስለሆነ በወ/ሕግ አንቀጽ 78 የተመለከተውን ድንጋጌ ይዘት አሟልተዋል ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም ፡፡ ስለዚህም ድርጊታቸው ሕገወጥ ጥቃትን ለማስወገድ ነው የሚያስብል መነሻ ቢኖረውም የፈፀሙት የነፍስ ግድያ ወንጀል በሕጉ ከተመለከተው መጠን በማሳለፍ መሆኑን መገንዘብ ችለናል፡፡

ሕጋዊ መከላከልን ከመጠን በማሳለፍ የተፈፀመ የወንጀል ድርጊት ደግሞ ከቅጣት ነፃ የማያደርግ ስለመሆኑ የወ/ሕ ድንጋጌ ቁጥር 79/1/ ያመለክታል፡፡ ይልቁንም ይህ አድራጎት የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ስለመሆኑ የዚህ ድንጋጌ ቁጥር 79/1/ ይገልፃል፡፡ይህንን መሠረታዊ ጉዳይ ከተረዳን የአመልካች ድርጊት ጥፋተኛ ሊያሰኝ የሚገባው በየትኛው የወ/ሕጉ ድንጋጌ ነው የሚለውን መሠረታዊ ጭብጥ ወደ ማየት ስንመለስ የአመልካች ድርጊት ህጋዊ መከላከልን ከመጠን ማሳለፍ መሆኑን መሠረት በማድርግ የወ/ሕጉ ልዩ ክፍል በዚህ ጊዜ ተፈፃሚ የሚሆን ድንጋጌ እንዳለው እንረዳለን፡፡ ይኸውም በወ/ሕጉ አንቀጽ 541/ሀ/ ሥር ከተመለከቱት የድንጌጋው ማቋቋምያ ምክንያቶች አንዱ ሕጋዊ መከላከልን ከመጠን በማሳለፍ የተፈፀመ የነፍስ ግድያ ወንጀል እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከትነው የወ/ሕጉ አንቀጽ 79/1/ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አድርጐ በገለፀው አኳኋን አንቀጽ 541/ሀ/ ሁለተኛው ሐረግ ደግሞ ወንጀሉን ለማቋቋም እንደሚችል ደንግጓል፡፡

እንዲህ አይነት ሁኔታ በተፈጠረ ጊዜ ደግሞ በወ/ሕጉ አንቀጽ 82/2/ እንደተደነገገው ድርጊቱን ለማቋቋም የተደነገገው ልዩ ክፍል ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡ ይህንን ለማለት የወንጀል ሕጉን ድንጋጌ ቁጥር 82/2/ እና 84/2/ ይዘት እና አቀራረጽ አገናዝቦ መመልከት ተገቢ ነው፡፡

ስለሆነም አመልካች የፈፀሙት የወንጀል ድርጊት የወ/ሕጉን አንቀጽ 540 የሚያቋቁም ነው በማለት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ የድርጊቱን አፈፃፀም ከባቢያዊ ሁኔታና ምክንያት በአግባቡ ባለማገናዘብ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን መረዳት ችለናል፡፡

ስለሆነም አመልካች የፈፀሙት የወንጀል ድርጊት የሕዝብ ደን ላይ ሊደርስ ይችል የነበረን ሕገወጥ ጥቃት ለማስወገድ እና ለመከላከል ቢሆንም ድርጊቱ የተፈፀመው ሌሎች አማራጮችን ሁሉ አሟጠው ሳይጨርሱ መሆኑን አፈፃፀሙ ሲታይ ሕጋዊ መከላከልን ከመጠን በማሳለፍ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ የድርጊቱ አፈፃፀም የወ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 541/ሀ/ን የሚያቋቁም ይሆናል፡፡

ስለዚህም አመልካች በ540 ሥር ጥፋተኛ መባላቸው አግባብ ሆኖ ስላላገኘው ይህንኑ የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበትን ድንጋጌ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 113/2/ መሠረት ለውጠን አመልካች በወ/ሕግ ቁጥር 541/ሀ/ ሥር ጥፋተኛ ናቸው ብለናል፡፡

ቅጣትን በተመለከተ አመልካች በዚህ ፍ/ቤት ጥፋተኛ የተባሉበት አንቀጽ አስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት እንደሚያስቀጣ ድንጋጌው ያመለክታል፡፡ በመሠረቱ ቀላል እስራት በመደቡ የሚጣለው ከአሥር ቀን እስከ ሦስት ዓመት የሚደርስ ስለመሆኑ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 106/1/ ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ ቀላል እስራት ቅጣት ከዚህ መደብ ጣሪያ ከፍ ብሎ አምስት ዓመት ሊደርስ የሚችለው በዚሁ አንቀጽ ሥር የተመለከቱት ምክንያቶች ወይም ሁኔታዎች ውሰጥ ቢያንስ አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ ስለመሆኑም ተደንግጓል፡፡ ይህንኑ በማገናዘብ አመልካች ላይ ሊፈፀም የሚገባውን ቅጣት እንደሚከተለው ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ032878 ሚያዝያ12 ቀን 2002 ዓ.ም የፀናው የበታች ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በ195/2/ለ/2/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. በዚሁ መሠረት አመልካች በወ/ሕግ 541/ሀ/ ድንጋጌ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ የግድያ ወንጀል የፈጸሙ ጥፋተኛ ናቸው ብለን ወስነናል፡፡
3. አመልካች በዚህ ጉዳይ እጃቸው ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ በአመስት /5/ ዓመት ቀላል እስራት እንዲቀጡ ብለናል፡፡
4. የጥፋተኛነት አንቀጽ እና ቅጣቱ የተሻሻለ መሆኑን እንዲያውቀው የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ይፃፍ፡፡
5. ማረሚያ ቤቱ በዚህ ችሎት በተሻሻለው ቅጣት መሠረት እንዲያስፈጽም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡***

እ/ብ



www.chilot.me

የሰ.መ/ቁ. 59045

ግንቦት 16 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የስልጤ ዞን ምርመራና ክስ ዐቃቤ ህግ ቃሲም ባዴ - ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-**1. አቶ ጌታቸው አስራት - ቀረቡ

2. አቶ አመነ ድሪባ - ቀረቡ

3. አቶ ሰንበቶ ጃራ - አልቀረቡም

4. አቶ ፋንታሁን ዘውዴ - አልቀረቡም

5. አቶ አድነው ያዕቆብ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በዳሎቻ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ ለወረዳው ፍ/ቤት የወረዳው መርማሪ ከሣሽ ዐቃቤ ህግ ተጠሪዎች በወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና በወንጀል ህግ አንቀጽ 686 ንኡስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን በመተላለፍ በዳሎቻ ከተማ 01 ቀበሌ ልዩ ስሙ ሰሊም ሰፈር ከሚባለው አንደኛ ተከሣሽ ለመኖሪያ ቤት የተፈቀደለትንና የሰራውን ቤት አላግባብ ለመሰረተ ክርስቶስ አማኞች በመጸለያነት እንዲጠቀሙበት በመስጠቱ በርካታ የእምነት ተከታዩች ተሰባስበው ከግንቦት 22 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት 30 ቀን 2001 ዓ.ም ከቀኑ ሁለት ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ ሶስት ሰዓት ከፍተኛ ጩኸት በማሰማትና በድምጽ ማጉሊያ መሣሪያ በመጠቀም የሁከት ማድረስ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪዎች ክሱን ክደው ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤት ዐቃቤ ህግን ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተጠሪዎች መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ብይን ሰጥቷል፡፡ ተጠሪዎች የመከላከያ ምስክሮቻቸውን አቅርበው አሰምተዋል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ዐቃቤ ህግ በክሱ የተጠቀሰውን የወንጀል ህግ ድንጋጌ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 113 ንኡስ አንቀጽ 2 መሠረት በመለወጥ ተጠሪዎች በወንጀል ህግ አንቀጽ 815 ንኡስ አንቀጽ 1



www.chilot.me

የተመለከተውን የደንብ መተላለፍ ጥፋት የፈጸሙ ጥፋተኞች ናቸው በማለት ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው በብር 80 /ሰማኒያ ብር/ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ ተጠሪዎቹ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የክልሉ መርማሪ ከሣሽ የሰጠው አስተያየትና የቀረበውን ክርክር ተቀብሎ ከመዘነ በኂላ የክልሉ መርማሪ ከሣሽ የተጠሪዎችን የሰበር አቤቱታ በመደገፍ የተከራከረ መሆኑን በውሣኔው በገጽ 9 ካሰፈረ በኂላ የወረዳው ፍ/ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር በወረዳው ፍ/ቤት በትዕዛዝ የተዘጋው የጸሎት ቤት እንዲከፈት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ሐምሌ 26 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በዳሎቻ ወረዳ ፍ/ቤት የወረዳው መርማሪ ከሣሽ ያቀረበው የወንጀል ክስ በወንጀል መዝገብ ቁጥር 02395 ቀርቦና ክርክር ተደርጐበት ፍ/ቤቱ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በተጠሪዎች ላይ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን የወንጀል ይግባኝ የስልጤ ዞን በመዝገብ ቁጥር 05761 በማየት የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

ተጠሪዎች የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡት የወንጀል ሰበር አቤቱታ በሰበር መዝገብ ቁጥር 36352 ሲታይና ክርክርና አስተያየት የተደረገበት እንደሆነ በየደረጃው የተከፈቱትን መዛግብትና አመልካች ያቀረበውን ክርክር ይዘት በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል የዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ከአንደኛው ተጠሪና ከአምስተኛው ተጠሪ ጋር የከተማዋን ፕላን መከበር ማዕከል ያደረገ ክስ የፍታብሔር ክርክር ለዳሎቻ ወረዳ ፍ/ቤት አቅርቦ ጉዳዩ ከወረዳው ፍ/ቤት የመዝገብ ቁጥር 02428 ክርክር ከተደረገበት በኂላ አንደኛና አምስተኛ ተጠሪ የመኖሪያ ቤት እንዲገነቡ በተሰጣቸውና በሰሩት ቤት ከመኖሪያነት ውጭ ለሆነ አገልግሎት ማዋል የሌለባቸዉ መሆኑ ተወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አንደኛና አምስተኛ ተጠሪ የፍታብሔር ይግባኝ ለስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የአንደኛና የአምስተኛ ተጠሪን የፍታብሔር ይግባኝ በመዝገብ ቁጥር 05607 በማየት የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የህግም ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት የሌለ መሆኑን ገልጾ ይግባኙን በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ አንደኛና አምስተኛ ተጠሪ የወረዳው ፍ/ቤት በፍታብሔር መዝገብ ቁጥር 02428 የሰጠውን ወሣኔ የዞኑ ከፍተኛው ፍ/ቤት በፍታብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 05607 ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑን በመግለጽ ራሱን የቻለ የሰበር አቤቱታ አቅርበው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 35808 ሲመረምር ከቆየ በኂላ የፍታብሔሩን ጉዳይ የወንጀሉ ጉዳይ ከሚታይበት የሰበር መዝገብ ቁጥር 36352 ጋር በማጣመር ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ከህግ ውጭ ሁለቱን መዛግብት በማጣመርና አግባብነት የሌላቸዉን የህግ ድንጋጌዎች በመጥቀስ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው ጥር 9 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ መልስ በወንጀሉ መዝገብም ሆነ በፍታብሔር መዝገብ  የሚነሣው ክርክርና የሚያዘው ጭብጥ ተመሣሣይ በመሆኑ የክልሉ ሰበር ችሎት ሁለቱን መዛግብት በማጣመር መርምሮ ውሣኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም፡፡ አመልካች የመኖሪያ ቤት በመስራት እንድትገለገሉበት በተፈቀደ ቦታ ላይ ለአምልኮ አገልግሎት አውለዋል በማለት ያቀረበው ክስ በህገመንግስቱ የተረጋገጠልንን የሀይማኖትና የእምነት ነጻነት የሚጋፋ ነው፡፡ አገሪቱ ኋላ ቀር አገር በመሆኑ የመኖሪያ ሰፈር የኢንዱስትሪ ሰፈር የሚባል የሌላት ሲሆን ቤተክርስቲያንና መስጊዶችን በመኖሪያ ቤት ውስጥ ማግኘት የተለመደ ነው፡፡ ስለዚህ በመኖሪያ ሰፈር ለጸሎትና የአምልኮት ማከናወን አይቻልም በማለት አመልካች ያቀረበውን ክርክር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ጥር 20 ቀን 2003 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡ በመልስ መልሱ ከተማዋ እድገቷን የምትመራበት ፕላን አለ፡፡ በከተማዋ ፕላን መሠረት መስጊዶች ፣ ቤተክርስቲያንና የጸሎት ቤቶች መገንባት ሲያስፈልግ የሚገነቡበት ቦታ ተለይቷል፡፡ በፕላኑ መሠረትም የጸሎት ቤት መገንቢያ ቦታ ተሰጥቷቸው እያለ የመኖሪያ ቤታችን ተቀይሮ የጸሎት ቤት ሊሆን ይገባል በማለት ያቀረቡት ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የወንጀል መዝገብ ቁጥር 36352 እና የፍታብሔር መዝገብ ቁጥር 35808 ጋር በማጣመር ተጠሪዎች የፈጸሙት የሁከት ተግባር የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ጉዳዩን እንደመረመርነው በወረዳው ፍ/ቤት በወንጀል ተከሣሽ የነበሩት ሶስቱም ተጠሪዎች የነበሩ መሆኑንና ተጠሪዎች በወረዳው ፍ/ቤት የወንጀል መዝገብ ቁጥር 02395 በዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁ. 05761 ይግባኝ ባይ በመሆን የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ በመሆኑና የወረዳውና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከላይ ቁጥራቸው በተገለጸው ሁለት መዛግብት የሰጡትን የወንጀል ፍርድ በመቃወም የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 36352 ማቅረባቸውን ተገንዝበናል፡፡ ስለዚህ የወረዳው ፍ/ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡትን የወንጀል ፍርድ በመቃወም በክርክሩ ተሣታፊ የሆኑት አምስቱም ተጠሪዎች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል የመኖሪያ ቤት ለመስራት የተፈቀደላቸውን ቦታና ለመኖሪያነት የሰሩትን ቤት ለአምልኮት አገልግሎት ለዘላቂነት እንዲውሉ ማድረጋቸው ተገቢ አይደለም፡፡ ከዚህ ድርጊታቸው እንዲታቀቡ ውሣኔ ይሰጥልን በማለት የፍታብሔር ክስ የመሠረተው የዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ነው፡፡ የዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ክስ ያቀረበው በአምስቱ ተጠሪዎች ላይ ሣይሆን በአንደኛ ተጠሪና በአምስተኛው ተጠሪ ላይ ብቻ ነው፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት በማዘጋጃ ቤቱ የቀረበውን የፍታብሔር ክርክር በፍታብሔር መዝገብ ቁጥር 02428 በማየት ውሣኔ የሰጠ ሲሆን አንደኛና አምስተኛ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን ይግባኝ የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍታብሔር መዝገብ ቁጥር 05607 በማየት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አንደኛና አምስተኛ ተጠሪዎች የወረዳውና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት አቅርበው የሰበር አቤቱታቸው በሰበር መዝገብ ቁጥር 35808 ሲመለከት የቆየ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡



www.chilot.me

የፍታብሔር ክርክር ከወንጀል ክርክር ጋር ሊጣመር የሚችልበት መሠረታዊ ሁኔታ በወንጀል ህግ አንቀጽ 101 የተደነገገ ሲሆን የፍታብሔር ክርክሩ የወንጀል ሰለባ የሆነ ሰው የሚያቀርበው የካሣ ጥያቄ በሆነ ጊዜ ከወንጀል ክስ ጋር ተጣምሮ እንዲወሰንለት ማመልከት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የፍታብሔር ክርክር በወንጀሉ ጉዳት ደርሶብናል የሚሉ ሰዎች ካሣ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በወንጀል የሚደረገው ክርክርና በፍታብሔር በሚደረገው ክርክር የሚያዘው ጭብጥና የሚቀርቡ ማስረጃዎች እንደዚሁም የማስረጃ አመዛዘን ሥርዓቱ የተለያየ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በወንጀል መዝገብና በፍታብሔሩ መዝገብ ተከራካሪ የሆኑት ሰዎች የተለያዩ ናቸው፡፡

በፍታብሔር መዝገብ ተከራካሪ የሆነው የዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሲሆን አመልካች የሚከራከረው የዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤትን በመወከል ነው፡፡ የዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የሚከራከረው ከአምስቱ ተጠሪዎች ጋር ሣይሆን ከአንደኛውና ከአምስተኛው ተጠሪ ጋር ብቻ ነው፡፡ በወንጀሉ መዝገብ ከስር ጀምሮ የመርማሪ ከሣሽና በአምስቱ ተጠሪዎች ተከራካሪ መሆናቸውን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤት እና አንደኛና አምስተኛ ተጠሪ በፍታብሔር የሚከራከሩበትን የሰበር መዝገብ ቁጥር 35808 አመልካችና ተጠሪዎች ከሚከራከሩበት የወንጀል መዝገብ ቁጥር 36352 ጋር በማጣመር ማየቱ የወንጀል ህግ አንቀጽ 101 መሠረታዊ የህግ ድንጋጌ የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

2. ተጠሪዎች ከግንቦት 22 ቀን 2001 ዓ.ም እስከ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ጸሎት እንዲደረግ ሁኔታዎችን በማመቻቸት በአካባቢው ህብረተሰብ ላይ የድምጽ ሁከት የመፍጠር የደንብ መተላለፍ ጥፋት ፈጽመዋል በማለት የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ የሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ገልጾ አመልካች አስተያየትና ክርክር ያቀረበ መሆኑን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 36352 በሰጠው ውሣኔ በግልጽ አስፍሯል፡፡ አመልካች ተጠሪዎች የደንብ መተላለፍ ጥፋት እንዳልፈጸሙ የክልሉ ሰበር ችሎት በሰጠው አስተያየትና ባቀረበው ክርክር የተከራከረ በመሆኑ ተጠሪዎች በወንጀሉ ጥፋተኛ ተብለው የተወሰነባቸውን ቅጣት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሻረው አግባብ ነው በማለት የቀረበው የሰበር አቤቱታ የህግ መሠረት የለውም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ሰበር ችሎት የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የሻረው የአመልካችን ክርክርና አስተያየት መሠረት በማድረግ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የወንጀሉን ጉዳይ በተመለከተ በሰበር መዝገብ ቁጥር 36352 የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በመሻር የሰጠውን ውሣኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 195 ንኡስ አንቀጽ 2/ለ/1 መሠረት አጽንተናል፡፡

በአጠቃላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ክርክር የያዘውን የሰበር መዝገብ ቁጥር 35808 ከወንጀል መዝገብ ቁጥር 36352 ጋር በማጣመር አይቶ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የወንጀሉን ጉዳይ በተመለከተ በመዝገብ ቁጥር 36352 የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡



www.chilot.me

## ው ሣ ኔ

1. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በዳሎቻ ወረዳ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 02395 የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔና የስልጤ ዞን በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 05761 የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ተጠሪዎች ከቀረበባቸው የወንጀል ክስ በነጻ እንዲሰናበቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 36352 የሰጠው ውሣኔ ጸንቷል፡፡
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አንደኛ ተጠሪና አምስተኛ ተጠሪ የዳሎቻ ወረዳ ፍርድ ቤት ከዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ጋር የነበራቸውን የፍታብሔር ክርክር በማየት በፍታብሔር መዝገብ ቁጥር 02428 የሰጠው ውሣኔ የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ በፍታብሔር መዝገብ ቁጥር 05607 ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት በሰበር መዝገብ ቁጥር 35808 ያቀረቡትን ክርክር የወንጀሉ ጉዳይ ከሚታይበት የሰበር መዝገብ ቁጥር 36352 አጣምሮ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ተሽሯል፡፡
3. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪና አምስተኛ ተጠሪ በሰበር መዝገብ ቁጥር 35808 ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አመልካች የዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤትን በመወከል ያቀረበውን ክርክር የወረዳ ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍታብሔሩን ጉዳይ በተመለከተ የሰጡትን ውሣኔና ለውሣኔያቸው መሠረት ያደረጓቸውን የህግ ድንጋጌዎች በመመርመር ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 391/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ፍርድ የወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

የሰ.መ/ቁ. 62332

ቀን 29/9/ 2003 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** ፡- አቶ ዘለቀ ካሣዬ - አልቀረቡም

**ተጠሪ** ፡- የፌዴራል ዐ/ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የወንጀል ክስ ሲሆን በፌ/ከ/ፍ/ቤት ቀርቦ የነበረው በቸልተኝነት ሰው በመግደል የሚል ነበር፡፡ ዐቃቤ ሕጉ አቅርቦት የነበረው ክስ ተከሳሽ /የአሁን አመልካቹ / የትራንስፖርት ማሻሻያ ደንብ ቁ . 279/56 አንቀጽ 35 እና የ1996 ዓ/ም ወ/መ/ህግ አንቀጽ 543 /3/ የተመለከተውን ተላለፎ የሚያሽከረክረው ታርጋ ቁ 1-10432 አ/አ የሆነውን መኪና ታህሳስ 20/01 ዓ/ም ከጥዋቱ አንድ ሰዓት ተኩል ላይ በዮሐንስ ቤተክርስቲያን ልዩ ስሙ ሰባራ ባቡር እየተባለ በሚጠራው አካባቢ በእግረኛ ማቋርጫ ዜብራ ላይ ቅድሚያ ባለመስጠት ተክሉ ጌታሁን የተባለውን በቸልተኝነት ገጭቶ ገድሎአል የሚል ነበር ፡፡

ክሱን የሰማው የፌ/ከ/ፍ/ቤት ተከሳሽ የቀረበበትን ክስ ድርጊቱን መፈፀሙን አምኖ ግን ጥፋቱ ያለመሆኑን ስለካደ የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቶ በወ/መ/ሕግ አንቀፅ 59/1/ /ሀ/ እና 543/3/ ስር ጥፍተኛ ነው በማለት የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብሎ በአንድ አመት ከ6 ወር ፅኑ እስራትና ብር 10,000 / አስር ሺህ/ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የፌ/ዐቃቤ ሕግ ቅር በመሰኘት ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅረቦ ፍ/ቤቱም ካከራከረ በኃላ ቅጣቱ በአምስት አመት ፅኑ እስራት ከፉ አድርጐ የወሰነ እና የገንዘብ መቀጮውን ባለበት ያልተነሳ መሆኑን ወሰኗል ፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች በጠበቃው አማካኝነት ህዳር 14 ቀን 2003 ዓ/ም 3 ገፅ ማመልከቻ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ የተለያዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን በማቅረባችን የከፍተኛው ፍ/ቤት ከግምት አስገበቶ ቅጣት የቀለለና ከመነሻው ዝቅ ብሎ መቅጣቱ ግልፅ ሆኖም እያለ ጠቅላይ ፍ/ቤት ተጐጅን ወደ ሕክምና ቦታ መውሰድ በሕግ ማለትም በወ/መ//ሕግ ቁ . 575/2/ ሥር የተጣለበትን ኃላፊነት መወጣቱ እንጅ ፅኑ እስራት እንዲቀጣ መወሰኑ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ዐ/ ሕግ በቀን 10/6/2003 ዓ/ም በ2 ገፅ መልስ ስጥቷል ፡፡ የመልሱ ፍሬ ሀሳብ የተባለው የቅጣት

ማቅለያ መክንያት ቅጣቱን ከመነሻው ዝቅ የሚደርግ ባለመሆኑ የጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ በመሆኑ እንዲፀና በማለት ተከራክሯል፡፡

የአመልካች ጠበቃ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡ በግራ ቀኙ የቀረበው ክርክር በአጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን በአቤቱታውም የቀረበውን ክርክር ከተያዘው ጭብጥና አግብበነት ካላቸው ሕጉ ጋር በማገናዘብ መርመሮታል ፡፡ እንደመረመረውም በዚህ ጉዳይ የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ከመነሻ ቅጣት / አምስት ዓመት ፅኑ እስራት / በታች የሚቀጣበት ምክንያት የለም የማለቱን አግባብነት በመመልከት መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል ፡፡ በዚሁ መሰረት በሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ያስቀርባል ሲባል አመልካች ግጭቱን ካደረሰ በኋላ ማለትም የሐኪም ዕርዳታ እንድታገኝ ማደረጉ በወ/መ/ሕግ አንቀጽ 82/1/ /ሠ/ መሰረት ቅጣቱን ሊያቀለው የሚገባ ነው ወይስ አይደለም ? የሚል በመሆኑ ችሎቱም ከዚህ ጭብጥ አኳያ ብቻ በመመልከት መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝቶታል፡፡ በመሠረቱ አንድ ጉዳት የደረሰበት ስው ወይም በአደጋ ላይ የሚገኘውን ሰው አለመርዳት የወንጀል ኃላፊነት የሚያስከትል መሆኑ በወ/መ/ሕግ ቁ 575 ሥር የተደነገገ ከመሆኑም በላይ ጉዳቱን ያደረሰው ተከሳሽ ራሱ በሆነበት ጊዜ ደግሞ የበለጠ የወንጀል ኃላፊነት የሚጥል ስለመሆኑ ከወ/መ/ ሕግ ቁጥር. 575 /2/ ሥር መረዳት ይቻላል ፡፡ ይሄንን ኃላፊነት ያልተወጣ ተከሳሽ ለዚህም ተጨማሪ የወንጀል ኃላፊነት በተደራራቢነት ሊጠየቅ እንደሚችልና አመልካች ወደ ሕክምና ማዕከል ማድረሱ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የተጣለበትን ኃላፊነት መወጣቱን የሚያመለክት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 82/1/ /ሠ/ መሰረት ተከሳሽ በእዉነት የተፀፀተ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ሲገነዘብ ቅጣት ሊያቀልለት እንደሚችልና በእውነት ስለመፀፀቱ ከመገልጫዎቹ አንዱ በደል ለደረሰበት ሰው አስፈላጊውን እርዳታ ማድረጉ ሊሆን እንደሚችል ተቀምጧል ፡፡ ይሄ ማለት ግን ተከሳሽ ተበዳይን ወደ ሕክምና ማዕክል ማድረሱ ብቻ በፈፀመው ድርጊቱ በእውነት ተፀፅቷል የሚያሰኝ ሳይሆን ጉዳዬን በመጀመሪያ ደረጃ ወይም በይግባኝ ያየው ፍርድ ቤት አጠቃላይ የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማትና በማመዛዘን የሚደርስበት መደመደሚያ ነው፡፡

አመልካች ተበዳይን ወደ ሕክምና ማዕክል ማድረሱ አጠቃላይ የክሱን ሂደት ከግምት በማስገባት አመልካች በእውነት ተፀፅቷል የሚያሰኝ ነው ወይስ አይደለም ? የሚለው ነጥብ የማስረጃ ምዘና በመሆኑና የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን ደግሞ በሕግ መንግስቱ አንቀፅ 10 መሰረት መሰረታዊ የህግ ስህተት ማረም እንደመሆኑ መጠን የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበትን መደምደሚያ መቀበሉ ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች ተበዳይን ለሕክምና ማዕከሉ ማድረሱ ሌላ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በአመልካች ላይ የተጣለውን ኃላፊነት መወጣቱን እንጂ ቅጣቱን ለማቅለል የሚያበቃ አይደለም ማለቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘንም፡፡ በዚሁ መሰረት ቀጥሎ የተመለከተው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ው ሳ ኔ**

የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 54154 በቀን 24.2.2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195/2/ /መ/ መሰረት ፀንቷል፡፡ መዝገቡ ተዝግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመልስ ፡፡

ስ/ረ                                                  የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 63741

ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- አቶ መሐመድ ሰይድ አሊ - ጠበቃ እሸቱ ዓሊ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ - በሌሉበት የሚታይ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>**ፍ ር ድ**</u>

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በ1996 ዓ/ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪፑብሊክ ወንጀል ህግ አንቀጽ 27 እና 593ን በመተላለፍ በሕገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊያንን ወደ ውጪ አገር ለመላክ መሞከር ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ አመልካችም ፍርድ ቤት ቀርበው የአቃቤ ሕግ የክስ ቻርጅ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ የእምነት ክህደት ቃላቸውን ሲጠየቁ የወንጀል ድርጊቱን መፈፀማቸውን በዝርዝር በማመናቸው በእምነታቸው መሠረት በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበበት አንቀጽ ሥር ጥፋተኛ ተብለውና የቅጣት አስተያየት ቀርቦ ከተመዘገበ በኋላ በቅጣት መመሪያው መሠረት በሁለት ዓመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራት እና በብር 100 (አንድ መቶ) እንዲቀጡ ተወስኗል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ብቻ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195 /2/መ/ መሠረት ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ታህሳስ 25 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፉት ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው መሠረታዊ ይዘትም አመልካች ድርጊቱን እንደአመኑ ተደርጎ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ያላግባብ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ተጠሪን ያስቀርባል ተብሎ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ተጠሪ ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመለኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካችን ቅሬታ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ሲታዘዝ ከተያዘው ጭብጥ ከድርጊቱ

አፈፃፀም እንዲሁም አመልካች ላይ ከተጣለው የቅጣት መጠን አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት ኢትዮጵያዊያኑን ከሕግ ውጪ ወደ ውጭ አገር ሊልኩ ሲሉ ተይዘዋል በሚል ሲሆን ይህንኑ ደርጊት መፈፀማቸውን በዝርዝር አምነዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ድርጊቱን በዝርዝር ማመናቸውን መሠረት በማድረግም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 134/1/ መሠረት የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጠቷል፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት ጉዳዩን በዝርዝር ማመናቸው ተረጋግጦ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በእምነቱ መሠረት በሚሰጠው የቅጣት ውሳኔ ሕጋዊነት ላይ ይግባኝ ማለት ከሚቻል በስተቀር በእምነት መሠረት በሚሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ሊቀርብ የማይችል ስለመሆኑ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 185/1/ ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል ፡፡ አመልካች ይህንኑ በመገንዘብም ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሲያቀርቡ በስር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ላይ ይግባኝ አለማቅረባቸውን በሰበር አበቱታቸው በግልጽ የገለፁት ከመሆኑም በላይ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ይህንኑ በሚገባ ይረጋገጣል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጠር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት የተሰጠው ስልጣን በማናቸውም የመጨረሻ ፍርድ ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሲኖር ማረም ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች በጥፋተኘነት ውሳኔ ላይ ያቀረቡት ቅሬታ የእምነት ቃላቸው በዝርዝር የተሰጠ ነው ተብሎ በስር ፍርድ ቤት ከተመዘገበው ይዘት ውጪ በመሆኑና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ካለው ሥልጣን አንፃር ሲታይ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ በሕጉ አተገባበርና በውጤት ደረጃ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195/2/መ/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ብ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 64813

ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ያሲን አሕመድ መሐመድ አልቀረበም፡፡

**ተጠሪ፡-** ፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ባምላኩ አንዳርጌ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች በሥር ፍ/ቤቶች የተላለፈበትን የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚል ቅሬታ ስላነሳ ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው አመልካች የተከሰሰው በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675(1) የተመለከተውን በመተላለፍ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሞአል ተብሎ ነው፡፡ ድርጊቱም ብር 10,000(አስር ሺህ ብር) የሚያወጣ ቆርቆሮ ገዝቼ አመጣለሁ በማለት ከግል ተበዳይ ገንዘቡን የወሰዱና ቆርቆሮውን ግን ሳያመጣ መቅረቱን የሚያመለክት ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ድርጊቱን አለመፈጸሙን በመግለጽ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ከዚህ በኋላም ክሱን የሰማው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መጀመሪያ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮችን ሰምቶ አመልካች ሊከላከል ይገባል የሚል ብይን ሰጥቶአል፡፡ በመቀጠልም የአመልካችን የመከላከያ ማስረጃ የሰማ ሲሆን በመጨረሻም አመልካች በዐቃቤ ህግ ክስ የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት የፈጸመ መሆኑን አረጋግጫለሁ በማለት የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም የጥፋተኛነት ውሳኔውን እንዳለ በማፅናት በሥር ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን የአንድ ዓመት ከሁለት ወር ጽኑ እስራት ወደሰባት ወር ቀላል እስራት ዝቅ በማድረግ ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ጥር 25 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው አመልካች ዐቃቤ ሕግ (ተጠሪ) ባቀረበበት ክስ መሠረት ጥፋተኛ መባሉ በአግባቡ ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ግራቀኝ ወገኖች ይህን ጭብጥ መሠረት በማድረግ ያሰሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ በዝርዝር እንዳመለከትነው በዐቃቤ ሕግ ክስ የተመለከተውን ድርጊት አልፈጸምኩም በማለት አመልካች ቢከራከርም፣ ክሱን የሰማው ፍ/ቤት ግን ድርጊቱን ስለመፈጸሙ በማስረጃ አረጋግጦአል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የሰማው ፍ/ቤትም እንደዚሁ የተሰማውን ማስረጃ በመመዘን በድርጊቱ መፈጸም እርግጠኛ ሆኖአል፡፡ እንደሚታየው ድርጊቱ ተፈጽሞአል ወይስ አልተፈጸመም የሚለው የፍሬ ነገር ጭበጥ በመሆኑ የሚነጥረው (የሚጣራው) በማስረጃ ነው፡፡ የፍሬ ነገር ጭብጥን በማስረጃ የማጣራት እና የተሰማውን ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩን በዚህ መልክ በመምራት መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል፡፡ በዐቃቤ ሕግ ክስ የተመለከተው ድርጊት በአመልካች መፈጸሙን በማረጋገጣቸውም ድርጊቱ ከተጠቀሰው የወንጀል ሕጉ ድንጋጌ ጋር አገናዝበው የጥፋተኛነት ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡

በበኩላችንም እንደምናየው አመልካች በዐቃቤ ሕግ ክስ የተመለከተውን ድርጊት ፈጽሞአል ወይስ አልፈጸመም የሚለውን የፍሬ ነገር ጭብጥ የማጣራት ሥልጣን ለሰበር ችሎቱ የተሰጠ ባለመሆኑ በዚህ ደረጃ የምንመረምረው አይደለም፡፡ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው እውነታ በክሱ በተጠቀሰው ድንጋጌ የተመለከተውን ወንጀል ያቋቁማል ወይ የሚለው ነጥብ ግን የሕግ ጭብጥ በመሆኑ ተመልክተነዋል፡፡

አመልካች የተከሰሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 675(1) የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፎ ወንጀል ፈጽሞአል ተብሎ እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል፡፡ ድንጋጌው የሚለው

"ማንም ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልጽናግ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ፣ የሌላ ሰው የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ፣ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ ወይም ይህን የመሳሰለውን ማናቸውንም አድራጎት የፈጸመ እንደሆነ፣"

ጥፋተኛ ተብሎ በሕጉ የተመለከተውን ቅጣት ይወስንበታል ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው አመልካች የግል ተበዳይ ለቆርቆሮ መግዣ በማለት የወሰደውን ገንዘብ ወስዶ አስቀርቶአል፡፡ ገንዘቡ ቆርቆሮውን አልገዛበትም ወይም ለሰጠው የግል ተበዳይ አልመለሰም፡፡ ይህ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጦበታል፡፡ ገንዘቡን እስካልመለሰ ወይም ለተባለው አገልግሎት ስለማዋሉ እስካላስረዳ ድረስ ደግሞ በድንጋጌው የተመለከተውን ወንጀል ፈጽሞአል ለማለት ነው የሚቻለው፡፡ በሌላ አነጋገር አመልካች የፈጸመው በማስረጃ የተረጋገጠበት ድርጊት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675(1) የተመለከተውን ወንጀል የሚያቋቁም ነው፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የምንልበት ምክንያት የለም፡፡ በዚህ መሠረትም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ 102615 ጥር 16 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕግ ሥ/ሥ/ቁ 195(2)(ለ)(2) መሠረት ፀንቶአል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

ራ/ታ *የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 43049

ግንቦት 26 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አረጋሽኝ መርዕድ - ጠበቃ ግሩም አየለ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ህግ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 34393 የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ እያለ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መፅናቱ ተገቢ ባለመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ጥር 24 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካችና በሌሎች አራት ሰዎች ላይ የሙስና ወንጀል ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው የክስ ይዘትም አመልካች የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ የህግ ኤክስፐርት ሆኖ በሚሠራበት ጊዜ ንብረትነቱ የወ/ሮ ኤስሚንግ አግኑያ የሆነውንና በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 20 ቀበሌ 29 ቁጥሩ 214 የሆነውን መኖሪያ ቤት በከፍተኛው ፍርድ ቤት አራተኛ ተከሳሽና አምስተኛ ተከሳሽ የነበሩትንና ክሳቸው የተቋረጠውን አቶ አብዲሣ ሁሪሣና አቶ ሳምሶን ጋርቮልድ አላግባብ ብልፅግና እንዲያገኙ በማሰብ የአባታችን ቤት አላግባብ የተወረሰብን ስለሆነ ይመለስልን በማለት ለኤጀንሲው ያቀረቡትን አቤቱታ የሚያረጋግጥ የይዞታ የምስክር ወረቀት መብራትና ውሀ ያስገቡበት ውልና የቤት ሥራ ፈቃድ ሣያቀርቡ በቀበሌ ፍርድ ሸንጎና በምስክር የተረጋገጠ ስለሆነ እንዲመለስላቸው የሚል የውሣኔ ሀሳብ በሥር አንደኛና ሶስተኛ ተከሳሾች ለነበሩት የፕራይቬታይዜሽን የሥራ ኃላፊዎች በማቅረብ በወንጀል ህግ 33 እና 32(1)ሀ እና በተሻሻለው ልዩ ወንጀለኛ መቅጫ ህግ 214/74 አንቀፅ 23 የተደነገገውን በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት በሥልጣን አላግባብ የመገልገል ወንጀል ፈፅመዋል በማለት ነው፡፡

አመልካች ወንጀሉን አልፈፀምኩም ብለው የተከራከሩ ቢሆንም ከላይ መለያው የተገለፀውን ቤት በሚመለከት በሳምሶን ጋርቮልድ ስም ሁለት ሺህ ካሬ ሜትር ካርታና ፕላን፣ በወ/ሮ ኤስሚንግ አግኑያን ስም አንድ ሺህ ካርታና ፕላን በማስረጃነት ቀርቦ የአዲስ አበባ ከተማ ልማት ቢሮ ተጠይቆ ቢሮው ቤቱ ያረፈው በወ/ሮ ኤስሚንግ አግኑያን ቦታ ላይ እንደሆነ አረጋግጦ መፃፉን፣ ቤቱ የገባው

የውህና የመብራት ቢል የወ/ሮ ኤስሚንግ አግኑያን ስም መሆኑን እንደሚያረጋግጥና አመልካች የውሣኔ ሀሳብ ለማቅረብ የምስክርነት ቃላቸውን ያሰማቸው ምስክሮች ቤቱ ከአዋጅ ውጭ የተወረሰ መሆኑን ለማስረዳት የቀረቡ ቢሆንም የተጠሩበትን ጭብጥ የሰጡት ምስክርነት የሌለ መሆኑና ከመጡበት ጭብጥ ውጭ ቤቱ የሳምሶን ጋርልቮልድ ነው በማለት መመሥከራቸውንና ይህንን መነሻ በማድረግ አመልካች ቤቱ ለሳምሶን ጋልቮልድ ወራሾች እንዲመለስ የውሣኔ ሀሳብ በሥር አንደኛና ሁለተኛ ተከሳሽ ለነበሩት የኤጀንሲው ሀላፊዎች ማቅረባቸው በዐቃቤ ህግ አንደኛ ምስክርና በሌሎች የሰነድ ማስረጃዎች ተረጋግጧል በማለት አመልካች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ብይን ሰጥቶ፣ አመልካች ከአንደኛና ሶስተኛ ተከሳሾች ጋር በጋራ ሶስት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ ከመዘነ በኋላ አመልካች በዐቃቤ ህግ ክስ የተጠቀሰውን ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኛ ናቸው በማለት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥቶ አመልካች በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በከፍተኛው ፍርድ ቤት በተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ችሎት የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195(2)ለ(2) መሠረት አፅንቶታል፡፡

አመልካች ለሰበር አቤቱታው የውሣኔ ሀሳብ ያቀረቡት የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ከሥራና ከተማ ልማት ሚኒስትር ከአዲስ አበባ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የተፃፈውን ደብዳቤና ማህደር በማየት ነው፡፡ ካርታው እውነተኛ መሆኑ ተረጋግጧል ይህ የተሣሣተ ከሆነ ፍርዱ እንዲታረም በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 6 ከሚጠየቅ በስተቀር እኔ በወንጀል መጠየቄ ተገቢ አይደለም፡፡ ተጠያቂም የምሆን ከሆነ በኢፌዲሪ የወንጀል ህግ 420(1) የሙያ ግዴታን ጥሰሀል በሚል መሆን ሲገባው በሥልጣን አላግባብ ተገልግሏል ተብዬ ጥፋተኛ መባሌ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ የዐቃቤ ህግ ማስረጃ ወንጀል መሥራቴን ከተገቢው ጥርጣሬ ውጭ አላስረዱብኝም፡፡ ምስክርነት መስማት በአዋጅ ቁጥር 110/87 እና በመመሪያ ቁጥር 001/88 የተፈቀደ ነው በወንጀል ሊያስጠይቀኝ አይገባም ስለዚህ የህግ አስተያየት ስለሰጠሁ ብቻ ወንጀል ሠርተሀል ተብዬ የተወሰነብኝ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ቤቱ በሥር አራተኛና አምስተኛ ተከሳሽ ለነበሩ ሰዎች እንዲመለስ የውሣኔ ሀሳብ የቀረበው ማስረጃ ሣይቀርብለትና ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ ነው፡፡ ስለሆነም በግብረአበርነት መከሰሳቸውና ጥፋተኛ መባላቸው ተገቢ ነው፡፡ የዐቃቤ ሕግ በሰውና በፅሑፍ ማስረጃ አመልካች ተገቢውን ማጣራት ማድረግ የነበረባቸው መሆኑን አስረድተዋል በአጠቃላይ አመልካች በሰበር ያቀረቡት የህግ ሣይሆን የፍሬ ጉዳይ ክርክር በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ፍርድ እንዲፀናልን በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች ፈፀመ የተባለው አከራካሪው ቤት በተመለከተ በአራተኛና አምስተኛ ተከሳሽ በነበሩት ሰዎች በኩል ያቀረቡትን ማስረጃዎች በማገናዘብ የሙያ አስተያየትና የውሣኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡ አመልካች አከራካሪው ቤት ለአራተኛና ለአምስተኛ ተከሳሾች ቢመለስ የህግ ድጋፍ ያለው ነው የሚል የውሣኔ ሀሳብ ከማቅረብ ውጭ በጉዳዩ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣንና ኃላፊነት የለውም፡፡ ይኸም በመሆኑ አመልካች በዐቃቤ ህግ ማስረጃ



www.chilot.me

የተዘረዘሩትን ስህተቶች የፈፀመው በሥር አራተኛና አምስተኛ ተከሳሽ የነበሩትን አላግባብ ለመጠቀምና ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና እንዲያገኙ ነው ወይስ እንደማንኛውም ባለሙያ የሙያ ሥራውን በሚሰራበት ወቅት ተገቢውን የሙያ ትጋት እና ጥንቃቄ ባለማድረጉ ነው የሚለውን ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ አመልካች ለመኖሪያ ቤቱ የሙያ ግልጋሎት ሲሰጥ ሊመራባቸው በሚገቡት የሕግ ማዕቀፎች ማለትም አዋጅ ቁጥር 110/87 እና ይህንኑ አዋጅ ለማስፈጸም ከወጣው መመሪያ 001/88 ከሚፈቅዱት ውጭ በመውጣት በሥር አራተኛና አምስተኛ ተከሳሾች የነበሩትን ሰዎች ጥቅም ለማስገኘት ሲል የፈፀመው ተግባር ያለ መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ አመልካች የሚመራባቸውን የህግ ማዕቀፎችን መሰረት በማድረግ ተገቢውን ሙያዊ ማጣራት ሲያደርግ ሁሉንም ማስረጃዎች በአግባቡ ያላገናዘበ በተለይም የአራተኛና አምስተኛ ተከሳሾች ቤት ነው የተባለው ሰው በተመለከተ ካርታና ፕላን የቀረበለት ቢሆንም የመብራትና የውሀ ቢል በግል ተበዳይ ወ/ሮ ኤስሚንግ አግኑያን ስም የሆነበትን ትክክለኛ ምክንያት ሣያገናዝብና ሣያጣራ የውሣኔ ሀሳብ በሥር ፍርድ ቤት ሶስተኛ ተከሳሽ ለነበሩት የመምሪያ ኃላፊውና ለአንደኛ ተከሳሽ ማቅረቡ ነው፡፡ የመወሰን ሥልጣን የሌላቸውና የሙያ ግልጋሎት የመስጠት ኃላፊነት ብቻ ያለባቸው ሰዎች ግልፅ በሆነ ሁኔታ አንድን ሰው ለመጥቀም ወይም ራሳቸውን ለመጥቀም በማሰብና ኃላፊዎቻቸውን ለማሣሣት የፈፀሙት ጉልህ ተግባር መኖሩ እስካልተረጋገጠ ድረስ በሥልጣን አላግባብ የመገልገል ወንጀል ፈፅመዋል ተብለው ሊጠየቁ አይገባም፡፡ ስለሆነም አመልካች የሙያ ተግባሩንና ሥራው በአግባቡና በጥንቃቄ ባለመፈፀሙ ምክንያት በመንግስትና በግል ተበዳይ ላይ ዐቃቤ ህግ በክሱ የገለፀው ጉዳት ቢኖርም አመልካቹ ጥፋተኛ መባል የሚገባው በልዩ ወንጀለኛ መቅጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 214/74 አንቀጽ 23(1)ሀ መሆን ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ አንፃር የከፍተኛው ፍርድ ቤት በአብላጫ ድምፅ የሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔና የጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

አመልካች የፈፀመው የተቀጠረበትን የሙያ ሥራ በጥንቃቄና በአግባቡ አለመፈፀም ወንጀል ነው፡፡ ይህ ወንጀል ከሶስት ዓመት በማይበልጥ እስራት እንደሚያስቀጣ በአዋጅ ቁጥር 214/74 አንቀፅ 25 ተደንግጓል፡፡ ሆኖም ከአዋጅ ቁጥር 214/74 በኋላ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ በአዋጅ ቁጥር 414/1996 የተደነገገ በመሆኑና በወንጀል ህጉ የሥራ ሀላፊነትን አለመወጣት ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከስድስት ወር በማይበልጥ እስራት የሚያስቀጣ መሆኑ በወንጀል ህግ አንቀፅ 420 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገ በመሆኑና በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 22 ንዑስ አንቀፅ 2 ወንጀሉ ከተፈፀመ በኋላ የወጣው የወንጀል ህግ ተከሳሹን የሚጠቅም ሆኖ ሲገኝ ተፈፃሚ እንደሚሆን የሚደነግግ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን የጥፋተኝነት ውሣኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 113/2/ እና በህገ መንግስቱ አንቀፅ 22 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት በመለወጥ አመልካች በወንጀል ህግ አንቀፅ 420 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገውን በመተላለፍ የሥራ ሀላፊነትን ያለመወጣት ወንጀል ፈፅሟል በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

የቅጣቱን መጠን በተመለከተ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ቅጣቱን አቅልሎ ለመወሰን የሚያስችሉ ምክንያቶች ያሉ መሆኑን በቅጣት ውሣኔው የመዘገባቸውን ነጥቦችና አመልካች ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘበት የወንጀል ህግ አንቀፅ 420 ንዑስ አንቀፅ 1 ከስድስት ወር በማይበልጥ እሥራት የሚያስቀጣ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባትና በወንጀል ህግ አንቀፅ 88 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የአመልካችን ግላዊ ሁኔታዎች ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በሶስት ወር እስራት እንዲቀጣ በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195(2)ለ2 መሠረት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በማሻሻል ፍርድ ሰጥተናል፡፡



www.chilot.me

## ው ሣ ኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች የሥራ ሀላፊነትን ባለመወጣት ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ በሶት ወር እስራት እንዲቀጣ ወስነናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 55047

መጋቢት 5 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ነብይ በድሩ ሽፋ ጠበቃ ማርቆስ ወ/ሰንበት - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ሥ/ፀ/ሙ/ኮሚሽን ዐቃቤ ሕግ ዋልተ ንጉስ ፍቅሬ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 66890 የሰጠው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ይግባኝ ችሎት የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 51161 ማፅናቱ በሰበር የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ጭብጥ ተይዞ በመቅረቡ ነው፡፡

በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ አመልካችና በሥር ሁለተኛ ተከሣሽ የነበረው አቶ ቶውፊቅ ሹፌ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሠ/ እና /ለ/ በአንቀጽ 427 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 3 ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ ግብረ አበር በመሆን የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን መረጃና ክትትል ሠራተኛ የሆነውን አቶ ሰለሞን ታደሠን በሥራው ኃላፊት ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ በማሰብ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ባለመክፈል የማታለልና የሙስና ወንጀል ተጠርጥረው ለመያዝ ይደረግባቸው የነበረውን ምርመራና ክትትል እንዲቋረጥ አድርግልን በማለት መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም. ከቀኑ አሥራ አንድ ሰዓት ከፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ህንፃ ቢሮ ቁጥር 207 ድረስ በመግባት ብዛቱ አሥራ አምስት እሽግ የሆነ እያንዳንዱ አሥር ሺህ ብር የያዘ በሁለተኛው ተከሣሽ አማካኝነት ለአቶ ለለሞን ታደሠ የሰጡ በመሆናቸው በግብረአበርነት በመላ ሀሳባቸውና አድራጎታቸው ሙሉ ተካፋይ በመሆን የሙስና ወንጀል ፈፅመዋል በማለት ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት ግራ ቀኙ የቅድመ ክስ ክርክር እንዲያደርጉ ካደረገ በኋላ የተማመኑበት ነጥብ የሌለ በመሆኑ የተጠሪን ምስክሮች ሰምቷል፡፡

የመጀመሪያው የዐቃቤ ሕግ ምስክር የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን የክትትል ሠራተኛ መሆኑን ገልፆ፣ መጋቢት 17 2000 ዓ.ም. ከጧቱ ሦስት ሰዓት ሲሆን ሁለተኛ ተከሣሽ አቶ ቶፊቅ ሹሬ አቶ ታደሠ ከሚባል ሰው ጋር ከቢሮ ድረስ መጥተው ሁለተኛ ተከሣሽ የአጎቴ ልጅ አንደኛው ተከሣሽ በኮሚሽኑ ምርመራ እየተደረገበት ነው፡፡ ቤተሰብ እየተጨነቀ ነው፡፡

በአንደኛው ተከሣሽ ላይ የተጀመረውን ክትትልና ምርመራ አቋርጥልን ለአንተም ትጠቀማለህ ብር 150,000 /አንድ መቶ ሀምሣ ሺህ ብር/ እንሰጥሀለን፡፡ ሁለተኛ ተከሣሽ 18/07/2000 ብሩን ይዞ እንዲመጣ ከቀኑ አሥራ አንድ ሰዓት ቀጠርኩት፣ ሁለተኛ ተከሣሽ ብር ይዞ እንደሚመጣና በአንደኛ ተከሣሽ ላይ የሚደረገው ምርመራና ክትትል እንዲቋረጥለት እንደሚፈልግ፣ ይህ ከሆነ አንደኛ ተከሣሽ ከተቀበለለት እንደሚመጣ ለኮሚሽነሩና በየደረጃው ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎችና የሥራ ባልደረቦች ሪፖርት አደረግሁ፡፡ ከሁለተኛ ተከሣሽ ጋር ሣደርግ የነበረውን ንግግር በመቅረፀ ድምፅ ቀረፅኩ፡፡ ሁለተኛ ተከሣሽ 18/07/2000 ብሩን በፌስታል ይዞ መጥቶ ዘበኞች አናስገባም ሲሉ እንዲያስገቡት ነገርኳቸው፡፡ አሥራ አምስት ባለ አሥር ሺ ብር ጥቅል ገንዘብ አመጣ ንግግራችንን ቀረፅኩት፡፡ አንደኛ ተከሣሽ ምርመራው የሚቋረጥለት ከሆነ እንደሚመጣ ነገረኝ፡፡ መጋቢት 21 ቀን 2000 ዓ.ም. ከቀኑ አሥራ አንድ ሰዓት አንደኛ ተከሣሽን ይዞ ለመምጣት ተቀጣጠርን፡፡ 21/07/2000 ከቀኑ አሥራ አንድ ሰዓት ይዞት መጣ፡፡ አንደኛ ተከሣሽ 21/07/2000 ዓ.ም. ከሁለኛ ተከሣሽ ጋር ቢሮዬ ድረስ መጥቶ በጉምሩክ ማጭበርበር እንደተከሰሰ ለእኔ ብር 150,000 የላከልኝ መሆኑን ምርመራውና ክትትሉ ከተቋረጠለት ወደፊት ውለታ እንደሚውልልኝና ሌሎች ዝርዝር ነገሮችን አወራ፡፡ እኔም በመቅረፀ ድምፅ ቀረፅኩት፡፡ ከዚያ በኋላ ወጥተው ሲሄዱ አንደኛ ተከሣሽና ሁለተኛ ተከሣሽ በቁጥጥር ሥር ዋሉ፡፡ ገንዘቡ በኃላፊዎች ትዕዛዝ ባንክ ገቢ ሆኗል በማለት መሥክሯል፡፡ ሌሎቹ ምስክሮች ሁለተኛ ተከሣሽ በፌስታል ገንዘብ ይዞ ሊገባ ሲል በመፈተሽ አናስገባም ብለው በአንደኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ትዕዛዝ ገንዘቡን ይዞ የገባ መሆኑንና አንደኛና ሁለተኛ ተከሣሾች አንደኛ ዐቃቤ ሕግ ምስክር ጋር ቀጠሮ አለን ብለው ከገቡ በኋላ ሲወጡ የያዟቸው መሆኑን መስክሯል፡፡ አመልካች በ18/07/2000 አገር ውስጥ ያልነበሩ መሆኑን በማስረዳት ፓስፖርት ያቀረቡ መሆኑን ከበታች ፍ/ቤት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ የሥር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሣሽ /አመልካች/ በሁለተኛ ተከሣሽ በኩል ሲደራደሩ ቆይተው የዐቃቤ ሕግ አንደኛ ምስክር የሆነው የኮሚሽኑ የክትትልና ምርመራ ሠራተኛ በሥራ ኃላፊነት ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ ብር 150,000 በሁለተኛ ተከሣሽ በኩል ከሰጡ በኋላ መጋቢት 27/2000 ዓ.ም. በግንባር ከሁለተኛው ተከሣሽ ጋር ከአንደኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ጋር በመቅረብ ገንዘቡን የላኩት እሳቸው መሆናቸውንና ወደፊትም ውለታ እንደሚውሉለት መግለፃቸውና ገንዘቡ ከጉምሩክ ቀረጥ በማጭበርበር የተገኘ መሆኑን ያረጋገጡ መሆናቸው በማስረጃ ስለተረጋገጠ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 427/1/ እና /3/ የተመለከተውን በመተላለፍ የሙስና ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኞች ናቸው ብሎ አመልካች በሰባት ዓመት ፅኑ እሥራትና በብር አሥር ሺህ ብር መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ፍርድ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኙ የሚጣራ ሕግ ወይም የፍሬ ነገር ነጥብ የሌለው መሆኑን ገልፆ የአመልካችን ይግባኝ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195/1/ መሠረት ሠርዞታል፡፡ አመልካች በኮሚሽኑ እንደሚፈለግ መጥሪያ በተጻፈበት መጋቢት 12 ቀን 2000 ዓ.ም. ከአንደኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ጋር ሁለተኛው ተከሣሽ ጉቦ ለመቀበል ተደራድረዋል በተባለበት መጋቢት 17 ቀን 2000 ዓ.ም.፣ ሁለተኛ ተከሣሽ ገንዘቡን ለአንደኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ሰጥተዋል በተባለበት መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም. አመልካች በኢትዮጵያ ውስጥ አልነበሩም ስለዚህ በወንጀሉ ተካፋይ ነው ተብሎ የተሰጠብኝ የጥፋተኝነት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ጉቦ ተቀባይ ሣይኖር ጉቦ የመስጠት ወንጀል ሊፈፀም ስለማይችል አንደኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ጉቦ ተቀባይ ነው ባልተባለበት ሁኔታ ጉቦ የመስጠት ወንጀል ፈፅመሀል ተብዬ ጥፋተኛ መባሌ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ አመልካች

የጉምሩክ ቀረጥ ባለመክፈል ወንጀል ተጠርጥሮ ክትትል ይደረግበት የነበረው ወንጀል ክስ በተመሠረተበት ሂደት ላይ ይገኛል፡፡ ስለዚህ ፍ/ቤቱ በዚህ ጉዳይ የጥፋተኝነት ውሣኔ ወስኖ የቅጣት ውሣኔውን እንዲያቀይልን ያቀረብነውን ጥያቄ ባለመቀበል ቅጣት መወሰኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 63 እና አንቀጽ 184 ያልተከተለና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ አመልካች ጥፋተኛ መባል አይገባኝም እንጂ ጥፋተኛ እንኳን ብባል በወንጀል ሕግ አንቀጽ 27/1/ እና በአንቀጽ 427/1/ መሆን ሲገባው ወይም በአናሣው ድምፅ ውሣኔ መሠረት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 427/1/ ጥፋተኛ መባል ሲገባኝ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 427/1/ እና /3/ ጥፋተኛ ነው በማለት የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ታህሣስ 6 ቀን 2003 ዓ.ም. በተጻፈ መልስ አመልካችና በሥር ፍ/ቤት ሁለተኛ ከሣሽ የነበረው ሰው ያሰቡትን ውጤት ያላገኙ ቢሆንም ጉቦ የመስጠት ወንጅሉን ሙሉ በሙሉ ፈፅመው አጠናቀዋል፡፡ ስለዚህ ወንጀሉ የሞራላዊ ግላዊና ሕጋዊ መስፈርቶችን በማያሟላ መልኩ የተፈፀመ ሆኖ እያለ ሙከራ ነው እንዲባል የቀረበው የሰበር አቤቱታ የሕግ መሠረት የለውም፡፡ አመልካች ከአሥራ ሦስት ሚሊዮን ብር በላይ የቀረጥ ማጭበርበር ፈፅሞ ይደረግበት የነበረው ክትትል እንዲቋረጥለት ለማድረግ የፈፀመው ድርጊት በአዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀጽ 2/9/ በተሰጠው "ከባድ ሙስና" ትርጉም የሚካተት ነው፡፡ ስለዚህ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 427/1/ ጥፋተኛ መባል ይገባኝ ነበር በማለት ያቀረቡት አቤቱታ የሕግ መሠረት የለውም፡፡ የቅጣት ውሣኔውን በተመለከተ አመልካች ያቀረቡት መከራከሪያ የበታች ፍ/ቤቶች መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የፈፀሙ መሆኑን የሚያሣይ አይደለም፡፡ በአጠቃላይ የአመልካች ክርክርና አቤቱታ የበታች ፍ/ቤቶች መሠረታዊ የሕግ ስህተት የፈፀሙ መሆኑን የሚያረጋግጥ ባለመሆኑ አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ እንዲያሰናብተን በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ጥር 26 ቀን 2003 ዓ.ም. በተጻፈ የመልስ መልስ አመልካች ከመጋቢት 2 ቀን እስከ መጋቢት 19 ቀን 2000 በአገር ውስጥ ስላልነበረ በወንጀሉ ተካፋይ መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ የኮሚሽኑ ሠራተኛ ጉቦ የመቀበል ወንጀል ከፈፀመ አመልካች ጉቦ የመስጠት ወንጀል ፈፅሟል በማለት ለማጠቃለል አይችልም፡፡ የወንጀል ሕጉ ቅጣት ተጠቃልሎ የሚወስንበትን ሁኔታ ያስቀመጠ ስለሆነ አመልካች በሌላ ወንጀል ተከስሶ እያለ በዚህ መዝገብ ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ ተገቢ አይደለም የሚል ይዘት ያለው ክርክር አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የከፍተኛው ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ፍርድ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የጉምሩክ ቀረጥ የማጭበርበርና የሙስና ወንጀል ፈፅሟል በሚል ምክንያት ተጠርጥሮ በፌዴራል ሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ክትትል እና ምርመራ እየተደረገበት የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች በኮሚሽኑ የሚደረግበት ክትትል እንዲቋረጥለት ለማድረግ የኮሚሽኑ የክትትልና የምርመራ ባለሙያ የሆነውን አንደኛ የተጠሪ ምስክር ጋር በሥር ሁለተኛ ተከሣሽ በሆነው አቶ ቶውፊቅ በኩል መጋቢት 17 ቀን 2000 ዓ.ም. ገንዘብ ለመስጠት ሀሳብ ያቀረበ መሆኑን፣ ከዚያም በኋላ በስልክ አንደኛውን የተጠሪ ምስክር በስልክ ካነጋገረና ገንዘብ በሁለተኛው ተከሣሽ በኩል እንደሚልክ ከነገረው በኋላ መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም. 150,000 /አንድ መቶ ሀምሣ ሺህ ብር/ በመላክ ገንዘቡ ለአንደኛ የተጠሪ ምስክር ከተሰጠ በኋላ በኮሚሽኑ የሚደረገው ክትትልና ምርመራ ተቋርጧል በሚል ዕምነት መጋቢት 21 ቀን 2000



www.chilot.me

ዓ.ም. ከአንደኛው የተጠሪ ምስክር ቢሮ ድረስ ከሁለተኛው ተከሣሽ ጋር የመጣና ገንዘቡን የላከው እሱ መሆኑን ወደፊትም ውለታ እንደሚውልለት ካረጋገጠለት በኂላ ሁለቱም በቁጥጥር ሥር የዋሉ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አንደኛው የተጠሪ ምስክር ከአመልካቾች ጋር በስልክና በአካል ያደረጋቸው ንግግሮች በመቅረፀ ድምፅ የተቀዳ መሆኑን መሥክሯል፡፡ በአጠቃላይ አመልካች በወንጀሉ ሥራ በመላ ሀሳቡ ሙሉ ተካፋይ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የከፍተኛው ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተረጋግጧል፡፡

አንድ ሰው ጉቦ የመስጠት ወንጀል ፈፅሟል የሚባለው አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ ወይም ማድረግ የማይገባውን እንዲያደርግ ጥቅም ወይም ጥጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ ሆኖ በተገኘ ጊዜ እንደሆነ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 427 ንዑስ አንቀጽ 1 በግልፅ ይደነግጋል፡፡ አመልካች በመላ ሀሳቡና ድርጊቱ ሙሉ ተካፋይ በመሆን የተጠሪ አንደኛ ምስክር የሆነው የክትትልና የምርመራ ሠራተኛ በአመልካች ላይ የሚደረገውን ክትትል እንዲያቋርጥ ለማድረግ ብር 150,000 /አንድ መቶ ሀምሣ ሺህ ብር/ በመደለያነት ያቀረበ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ከውጭ አገር የገባሁት መጋቢት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. ነው በማለት ፓስፖርቱን በማስረጃነት ያቀረበ ቢሆንም አንደኛው የተጠሪ ምስክር በአመልካች ላይ የሚያደርገውን ክትትል ቢያቆም የሚጠቀምና ገንዘብ የሚሰጠው መሆኑን በሁለተኛው ተከሣሽ በኩል ሀሳብ ካቀረበበት መጋቢት 17 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ አመልካችና ሁለተኛ ተከሣሽ ጋር ከሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ቢሮ እስከተያዘበት መጋቢት 21 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/ለ/ በሚደነግገው መሠረት በመላ ሀሳቡና አድራጎቱ በወንጀሉ ድርጊት በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ መሆኑ በተጠሪ ማስረጃና አንደኛው የተጠሪ ምስክር ጋር በስልክ ካደረጋቸው ንግግሮችና በሁለተኛ ተከሣሽ በኩል ከፈፀሙ ተግባራትና መጋቢት 21 ቀን 2000 አንደኛው የተጠሪ ምስክር ጋር ካደረጋቸው ንግግር ከፈፀማቸው ተግባራት የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ያቀረበው ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

አመልካች የሙስና ወንጀል ክትትል ሠራተኛ የሆነው አንደኛ የተጠሪ ምስክር የሚያደርገውን ክትትል እንዲያቋርጥለት የሚፈልገውና የተጠረጠረበት ወንጀል ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ያለው የጉምሩክና ቀረጥ ገንዘብ የማጭበርበር ወንጀል ፈፅሟል በሚል ምክንያት መሆኑ በተጠሪ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች አንደኛውን የዐቃቤ ሕግ ምስክር ለመደለል ያቀረበው የገንዘብ መጠንም ከፍተኛ ብር 150,000 /አንድ መቶ ሀምሣ ሺህ ብር/ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ከሆነ የአመልካች አድራጎት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 427 ንዑስ አንቀጽ 3 የሚሸፈን መሆኑን "ወንጀል አድራጊው ያቀረበው ጥቅም ወይም ስጦታ ከፍተኛ እንደሆነ ወይም ድርጊቱ በመንግሥት ወይም በህዝብ ወይም ግለሰብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አስከትሎ እንደሆነ" የሚለውን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 427/3/ ድንጋጌ ይዘት በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም አመልካች ጥፋተኛ መባል የሚገባኝ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 427/1/ መሆን ይገባዋል በማለት ያቀረበው ክርክር የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

አመልካች ለአንደኛው ተጠሪ ማድረግ የሚገባውን የወንጀል ክትትል እንዲያቆምለት ብር 150,000 /አንድ መቶ ሀምሣ ሺህ ብር/ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የወንጀሉን ድርጊት የፈፀመ በመሆኑ ጥፋተኛ መባል የሚገባኝ በሙከራ ወንጀል መሆን ይገባዋል በማለት ያቀረቡት ክርክር በወንጀል ህግ ቁ. 27/4/ እና /3/ ድንጋጌ ይዘት፣ መንፈስና ዓላማ ጋር የሚጣጣም ሆኖ አላገኘነውም፡፡ አመልካች የቅጣት አወሳሰኑን በተመለከተ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ የበታች ፍ/ቤቶች መሠረታዊ የሕግ ስህተት የፈፀሙ መሆኑን የሚያመላክት አይደለም፡፡

ከላይ በዘረዘርነው ምክንያት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/ለ/ እና አንቀጽ 427/1/ እና /3/ የተመለከተውን በመተላለፍ ከባድ የሙስና ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት የሰጡት የቅጣት ውሣኔ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 23 እና ሌሎች መሠረታዊ መርሆችና ከላይ የገለፅናቸውን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ የተሰጠና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ፍርድ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡
2. ፍርዱ የፀና መሆኑን እንዲያውቀው ለፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 61275

ሚያዝያ 18 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አቶ ኤልያስ ገረመው - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** የኢት/ገ/ጉ/ባ/ዐ/ህግ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አመልካች በስር የመ/ደ/ፍ/ቤት 3ኛ ተከሣሽ የነበረ ሲሆን ፍ/ቤቱም የቀረበለትን የዋስትና ጥያቄ ከመረመረ በኋላ አመልካች ለብር 300,000 /ሶስት መቶ ሺህ/ የሚበቃ ዋስትና እንዲያቀርቡ በመ/ቁ 167550 በቀን 18/10/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ብይን የሰጠ ሲሆን የስር ከሣሹ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 74ን በመጥቀስ አዲስ ነገር የተገኘ ስለሆነ ቀደም ሲል የተፈቀደው የዋስትና መብት እንዲነፈግ በማመልከቱ ፍ/ቤቱም የስር ከሣሽን አቤቱታ በመቀበል የተፈቀደው ዋስትና ቀሪ እንዲሆንና አመልካች /የስር 3ኛ ተከሣሽ/ በማረሚያ ቤት ሆኖ ክርክሩን እንዲቀጥል ማዘዙን የስር ፍ/ቤት መዝገብ ያመለክታል፡፡

የሰበር አመልካችም የተፈቀደለትን ዋስትና በመከልከሉ ምክንያት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ከፍተኛው ፍ/ቤትም የስር መ/ደ/ፍ/ቤት የፈቀደውን ዋስትና እንደገና መከልከሉ ተገቢ አይደለም ሐምሌ 7/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች በዋስ እንዲወጣ አዟል፡፡ ይሁን እንጂ ያሁን ተጠሪ አዲስ ነገር ተገኝቷል በማለት የአመልካች የዋስትና መብት እንደገና እንዲነፈግ በመጠየቁ ከፍተኛው ፍ/ቤትም አዲስ ነገር መገኘቱንና አለመገኘቱን ለማጣራት ማስረጃ የሰማ ሲሆን ለማስረጃነት የቀረበውም የማስፈራራት ድርጊት ተፈጽሞበታል የተባለው ሰው ነው፡፡

የስር ከፍተኛ ፍ/ቤትም የቀረበውን ምስክር ቃል ከመረመረ በኋላ የተጠሪን አቤቱታ በመቀበል በመ/ቁ 96273 በቀን 12/12/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተፈቅዶለት የነበረውን ዋስትና ከልክሏል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ በከፍተኛ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ሲሆን የዘረዘራቸውም ዋና ዋና የቅሬታ ነጥቦች፣

አመልካች የተከሰሰበት ወንጀል ዋስትናን አያስከለክልም፣

በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 74 መሠረት አዲስ ነገር ተገኝቷል በሚል በቀረበው አቤቱታ መነሻ ቀርቦ የምስክርነት ቃሉን የሰጠው የተጠሪ ምስክር ለቀረበለት መስቀለኛ ጥያቄ ሲመልስ ማን እዳስፈራራው እንደማያውቅ ተናግሮ እያለ አዲስ ነገር ተገኝቷል በሚል የተፈቀደው ዋስትና መነፈጉ ተገቢነት የለውም የሚሉ ናቸው፡፡

ተጠሪው በበኩሉ በሰጠው መልስ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74 መሠረት አዲስ ነገር የተገኘ እንደሆነ ፍ/ቤቱ በማንኛውም ጊዜ በዋስትና ላይ የሰጠውን ውሣኔ መሻር ይችላል፣ ፍ/ቤቱም አዲስ ነገር ስለመገኘቱ ማስረጃ ሰምቶ አረጋግጧል፣ በማስረጃ ዙሪያ በሰበር ደረጃ ክርክር ሊደረግ አይገባም፡፡ በመሆኑም የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ህግን መሠረት ያደረገ ስለሆነ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ እንደተገለጸው አጥሮ የቀረበ ሲሆን እኛም የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት የፈቀደውን ዋስትና አዲስ ነገር ተገኝቷል በሚል በሰጠው ትዕዛዝ መከልከሉ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚያሰኝ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 19/6/ በተደነገገው መሠረት የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት ያላቸው ሲሆን በህግ በተደነገጉ ሁኔታዎች ግን ፍ/ቤት ዋስትናን ላለመቀበል ይችላል፡፡ ዋስትና ከተፈቀደ በኋላም ቢሆን አዲስ ነገር የተገኘ እንደሆነ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74 መሠረት ፍ/ቤቱ በማናቸውም ጊዜ ቢሆን በስልጣኑ ወይም በማናቸውም ባለጉዳይ አመልካችነት ተከሣሹ በዋስትና ወረቀት የተለቀቀበትን ሁኔታዎች እንደገና ለማየት ይችላል፡፡ በዚሁ መሠረት ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ በዋስትና ከተለቀቀ በኋላ የከሣሽ ምስክር የሆነውን ግለሰብ ማስፈራራቱን ምስክሩ ለስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሰጠው የምስክርነት ቃል መመልከት ይቻላል፡፡

አመልካች በዋስትና ከተለቀቀ በኋላ የፈጸመው ድርጊት ደግሞ አዲስ ድርጊት ስለሚሆን ፍ/ቤቱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74 ከተቀመጡት ሁለት አማራጮች ማለትም ተከሣሽ አዲስ ዋስ እንዲያመጣ ወይም በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ይደረጋል ከሚሉት ሁለተኛውን አማራጭ በመውሰድ የዋስትና መብቱን በመከልከል ማረፊያ ቤት እንዲቆይ አድርጓል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች የቀረበው የተጠሪ ምስክር ለቀረበለት መስቀለኛ ጥያቄ ማን እንዳስፈራራው እንደማያውቅ ተናግሯል በማለት የተከራከረውም ቢሆን በዚህ በሰበር ደረጃ መጣራት የሌለበት የፍሬ ነገር ክርክር በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡

በአጠቃላይ ይህ ችሎት በሰበር መ/ቁ 59855 በቀን 28/3/2003 ዓ.ም በአመልካች ወ/ሮ ሊዊዛ ፎርቤታ እና በተጠሪ ዐ/ሕግ መካከል በተደረገው የዋስትና ክርክር ችሎቱ በኢ/ፌ/ዲ/ሪ/ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ /ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት የተሰጠው ስልጣን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃ መመዘን ባለመሆኑ በዚህ ችሎት ሊታይ አይገባም በማለት እና በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74 መሠረት አዲስ ነገር ሲገኝ የተፈቀደው ዋስትና ሊከለከል ስለመቻሉ የሰጠው ትርጉም በዚህ በተመሣሣይ ጉዳይ አስገዳጅነት ስላለው በዚህ በተያዘውም ጉዳይ በስር ከፍተኛ ፍ/ቤት በተሰጠው ትዕዛዝ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አላገኘንም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 96273 በቀን 12/12/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ሐምሌ 7 ቀን 2002 ዓ.ም ለአመልካች ተሰጥቶት የነበረውን የዋስትና ፈቃድ ትዕዛዝ በማንሣቱ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
2. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 45595

ሰኔ 17 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ሕግ-አቶ ደሳላኝ ደንገላ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** 1.ኢዮሲያስ አበራ ገ/ሚካኤል-አልቀረበም፡፡-የሁሉም ጠበቃ አቶ ጎበና እጅጉ ቀረቡ፡፡

2. ለአለም አበራ ገ/ሚካኤል-ቀረቡ፡፡

3. ወ/ሮ ትርንጎ ወ/ሚካኤል -ቀረቡ፡፡

4. አብያለው አበራ ገ/ሚካኤል-ቀረቡ፡፡

5. መላኩ ግዛው ማሩ-ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ከሰ/መ/ቁጥር 54215 ከሆነው ጋር ተጣምሮ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሰው ግድያ ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች በተጠሪዎች ላይ የመሰረተው ክስ ይዘት ሲታይም በ1996 ዓ/ም በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1(ሀ፣ለ)) እና 539(1(ሀ)) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ሟች አቶ የማነ መስፍንና ሟች የትናየት ጌቱ ጥር 12 ቀን 1999 ዓ/ም በነገሌ ወረዳ ላንጋኖ በቀለ ሞላ ሆቴል ልዩ መዝናኛ ስፍራ ውስጥ እያሉ 1ኛ ተጠሪ ሟች የትናየት ጌቱ እጮኛዬ ሆና እያለች ከሟች የማነ መስፍን ጋር ወደ መዝናኛ ሥፍራው ሄዳለች በማለት ከሌሊቱ ወደ 6፡00 አከባቢ ሲሆን ከአዲስ አበባ እስከ መዝናኛ ቦታው በመሄድ በዚያው ሆቴል አልጋ በመያዝ ሟቾችን አይቷቸው ከለያቸው በኋላ ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ ቁጥር ስማቸው ለተጠቀሱት ተጠሪዎች ደውሎ ሟቾችን መግደል እንደሚፈልግ ነግሯቸው፣እነዚህ ተጠሪዎች በእለቱ ከሌለቱ 8፡00 አከባቢ ላይ ተሰባስበው በመወያየት ሲጓዙ አድረው፣ ጥር 13 ቀን 1999 ዓ/ም ከጥዋቱ 12፡30 ሲሆን ወደ ሆቴሉ ሲደርሱ አቶ አበራ ወ/ሚካኤል ፈቃድ ያወጡበትንና ቁጥሩ 678309 የሆነ ኮልት ሽጉጥ ባልታወቀ ሁኔታ ወደ ሆቴሉ በድብቅ ካስገቡና ከ1ኛ ተጠሪ ጋራ ከተመካከሩ በሁዋላ በዚሁ እለት ከጠዋቱ 1፡30 ሲሆን 1ኛ ተጠሪ(ኢዩሲያስ አበራ) ሟቾች ያሉበትን የሆቴሉ አልጋ ቁጥር 9 በአልጋ

በኩል ያለውን መስኮት በመስበር በመግባት፣2ኛ ተጠሪ(ለአለም አበራ) ደግሞ በበር ገብቶ 1ኛ ተጠሪ በክሱ በተጠቀሰው ሽጉጥ ተኩሶ ሟቾችን የተለያየ አካላቸውን በመምታት ሲገድላቸው 2ኛ ተጠሪ አብሮ ገብቶ በሃሳብ ሲረዳው የነበረ ሲሆን ከ3ኛ እስከ 5ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ደግሞ ወንጀሉ በሚፈጸምበት ወቅት በጋራ እነሱን ልኳቸው የወንጀሉን ውጤት በሆቴሉ ቁጥር 9 እና 8 መካከል ቆመው ሲጠባበቁ የነበሩ ከመሆኑም በላይ ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ከሕግ ተጠያቂነት ራሳቸውንም ሆነ 1ኛ ተጠሪን ለማስመለጥ አስበው ወንጀሉ የተፈፀመበትን ሽጉጥ 2ኛ ተጠሪ በሆቴሉ አልጋ ቁጥር 9 ክፍል ውስጥ በጃኬት ጠቅልሎ ይዞ ለ4ኛ ተጠሪ ሲሰጥ ይኸው ተጠሪም ለ3ኛ ተጠሪ በማቀበል በመጡበት መኪና ውስጥ እንዲቀመጥ የደበቁ መሆኑን ዘርዝሮ በአጠቃላይ ተጠሪዎች አስበው፣ተባብረው፣ተረዳድተውና የወንጀሉን ውጤት በመቀበል በቅናት ተነሳስተው ዘግናኝ በሆነ ሁኔታ ሁለት ሰዎችን በግፍ ገድለዋል የሚል ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ 1ኛ ተጠሪ የወንጀል ሕጉን 808(ሀ) ድንጋጌን በመጣስ የተከሰሰ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ተጠሪዎች ክሱ ደርሷቸው በግልጽ ችሎት ከተነበበላቸውና እንዲረዱት ከተደረገ በሁዋላ የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ 1ኛ ተጠሪ ድርጊቱን መፈፀሙን አምኖ መብቱን ጠብቆ የተከራከረ ሲሆን ሌሎች ተጠሪዎች ግን የድርጊቱን አፈጻጸም ክደው ተከራክረዋል፡፡ዐቃቤ ሕግ በበኩሉ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን ያቀረበ ሲሆን ተጠሪዎችም ድርጊቱን እንደአቃቤ ሕግ የክስ አመሰራረት ስለመፈፀማቸው በዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ተረጋግጦባቸዋል ተብሎ እንዲከላከሉ ተደርጎ የመከላከያ ማስረጃዎችን አሰምተዋል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበባቸው ክስ መሰረት የጥፋተኛነት ውሳኔ ሰጥቶ 1ኛውን ተጠሪ በ18(አስራ ስምንት አመት)፣3ኛዋን ተጠሪ(ትርንጎ ወ/ሚካኤልኝ) ደግሞ በ15(አስራ አምስት አመት) ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ሲወሰን 2ኛ፣4ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎችን ግን ክሱን ተከላክለዋል በማለት በነፃ አስተናብቷቸዋል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች በ1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ላይ በተሠጠው የቅጣት ውሳኔ፣በሌሎች ተጠሪዎች ላይ የተሠጠው የነፃ መለቀቅ ውሳኔ ላይ እንዲሁም የአሁኑ 1ኛና 3ኛ ተጠሪዎች በጥፋተኝነት ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት በተለያዩ መዛግብት አቅርበው ጉዳዩ ከታየ በሁዋላ የአሁኑ አመልካች እና የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ይግባኝ ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረ ሲሆን የአሁኗ 3ኛ ተጠሪ ይግባኝ ግን ተቀባይነት አግኝቶ ክርክር ከተደረገበት በሁዋላ 3ኛ ተጠሪ ድርጊቱን መፈፀማቸው በሚገባ አልተረጋገጠባቸውም በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ በነጻ እንዲሰናበቱ ተወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካችና የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው የአሁኑ አመልካች አቤቱታ ተቀባይነት ሲያጣ የ1ኛ ተጠሪ አቤቱታ ግን ተቀባይነት አግኝቶ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ 1ኛ ተጠሪ ድርጊቱን መፈፀሙ የተረጋገጠበት ቢሆንም ድርጊቱ ሊሸፈን የሚገባው በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበው ድንጋጌ ሳይሆን ተራ የሰው ግድያ ወንጀል በሚያስጠይቅበት ድንጋጌ ነው ተብሎ ድንጋጌው ዝቅ ተደርጎለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በሁዋላ ቅጣቱም 16(አስራ ስድስት አመት) እንዲሆን ተድርጎ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡የሰበር አቤቱታው የቀረበውም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በሰ/መ/ቁጥር 45595 በሆነው የሰበር አቤቱታውን ያቀረበው በ1ኛ ተጠሪ ላይ በስር ፍርድ ቤት የተጣለው ቅጣት ተገቢነት የለውም፣ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎችም ከክሱ በነጻ መሰናበታቸው ያላግባብ ነው በሚል ሲሆን በሰ/መ/ቁጥር 54215 የቀረበው የሰበር

አቤቱታ ይዘትም ደግሞ 1ኛ ተጠሪ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድርጊቱ በወ/መ/ሕግ አንቀጽ 540 የሚሸፈን ነው ተብሎ የተሠጠው የሕግ ትርጉም ያላግባብ ነው በሚል ነው፡፡በሁለቱም መዛግብት የቀረቡት የአቃቤ ሕግ የሰበር አቤቱታ ቅሬታ ነጥቦች ተመርምረውም በሰበር ችሎት ሊታዩ የሚገባቸው ናቸው ተብሎ በመታመኑ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጠበቃቸው አማካኝነት የተጻፈ የጽሑፍ መልስ አቅርበዋል፡፡የመልሳቸው መሰረታዊ ይዘትም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆኑት ውሳኔዎችና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ በሰበር ችሎት ሲቀርብ በሁለቱም መዛግብት የተያዙትን ጭብጦች በሚከተለው መልኩ መርምሯቸዋል፡፡

<u>1ኛ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበት የሕግ ድንጋጌና በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው የቅጣት መጠን ተገቢ መሆን ያለመሆኑን በተመለከተ፡-</u>

1ኛ ተጠሪ የተከሰሰው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1(ለ)፣(ሀ)) እና 539(1ሀ) የስር የተመለከተውን በመተላለፍ የትናየት ጌቱ እና የማነ መስፍን የተባሉትን ሰዎች በተመሳሳይ ጊዜና ቦታ በግፍ ገድሏል በሚል ሲሆን ተጠሪ ድርጊቱን መፈፀሙን አምኖ ኃላፊነት የለብኝም፣ኃላፊነት አለብህ ከተባለም ቅጣትን ሊያቀልሉ የሚችሉ ሁኔታዎች በተገኙ ጊዜ የሰው መግደል ወንጀል ሊያስጠይቅ በሚችለው ድንጋጌ መሰረት ነው በማለት መሆኑን ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡አቃቤ ሕግ በበኩሉ የድርጊቱ አፈፃፀም በቅናት እና በጨካኝነት የተፈፀመ ስለመሆኑ ያሳያሉ ያላቸውን ማስረጃዎችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡1ኛ ተጠሪ ራሱ በሰጠው ቃልም ሆነ በአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች በፍሬ ነገር የተረጋገጠው ነጥብ የሚያሳየው ሟች የትናየት ጌቱና ተጠሪ ትዳር ሊመሰርቱ ስምምነት ተድርጎ ጋብቻው ሊፈፀም ሶስት ወራት ያህል በቀሩበት ጊዜ ውስጥ ጥር 12 ቀን 1999 ዓ/ም ከሟች የማነ መስፍን ጋር ወደ ላንጋኖ መዝናኛ በመሄድ በመዝናናት ላይ የነበሩ መሆኑን ተጠሪ ከአዲስ አበባ ወደ ላንጋኖ ሌሊቱን ሄዶ መኖራቸውን አረጋግጦና አጠቃላይ ሁኔታውን ከተመለከተ በሁዋላ በበነጋው ላይ ግን ተጠሪዎችን ከአገኘ በሁዋላ ሟቾች ወደ ተኙበት አልጋ በመስኮት በመግባት ሟቾችን በወቅቱ በያዘው ሽጉጥ ተኩሶ መግደሉ ነው፡፡ተጠሪ ድርጊቱ የተፈፀመው በንዴትና በብሥጭት ነው፣ራሴን ለመከላከል ነው በማለት ያቀረበውን መከራከሪያ ሁሉም የበታች ፍርድ ቤቶች ያልተቀበሉት ጉዳይ ሲሆን የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የ1ኛ ተጠሪ ድርጊት በግፍ ሰው የመግደል ወንጀል ሊያቋቁም የሚችል አይደለም ወደ ሚለው ድምዳሜ የደረሰው ተጠሪ ከሟች የትናየት ጌቱ ጋር እጮኛ ሁኖ ጋብቻ ሊመሰርት ሶስት ወር በቀረው ጊዜ ውስጥ ከሌላ ሰው ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀሟ መረጋገጡና ተጠሪ ከአዲስ አበባ ተነስቶ ላንጋኖ እስኪደርስ ድረስ ሰው ለመግደል ሀሳብ ያለው ስለመሆኑ በዐቃቤ ሕግም ሆነ በፈፀመው ድርጊት የተረጋገጠ አይደለም በሚል ምክንያት ነው፡፡

በመሰረቱ የሰው ግድያ ወንጀል በወንጀል ሕግ አንቀፅ 539(1(ሀ)) መሰረት ድርጊት ፈጻሚውን ሊያስጠይቅ የሚችለው ድርጊቱ ሆነ ተብሎ አስቀድሞ በማሰብና በመዘጋጀት ሲፈፀም ወይም በአንቀጽ 84 ወይም 86 ስር የተመለከቱት አክባጅ ሁኔታዎች በተገኙበት ሁኔታ የወንጀል አድራጊው በተለይ ጨካኝ፣ነውረኛ ወይም አደገኛ መሆኑን ሲያመለክቱ ስለመሆኑ ተጠቃሹ ድንጋጌ



www.chilot.me

በግልጽ ያሳያል፡፡ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው በድንጋጌው ስር የተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች በየራሳቸው መቆም የሚችሉ ነጥቦች ስለመሆናቸው ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ ሚቾችን የገደለው ሚች የትናየት ጌቱ ፍቅረኛው ሁና ለጋብቻ ዝግጅት እየተደረገ ባለበት ጊዜ ከሚች የማነ መስፍን ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት ስትፈፅም አረጋግጩአለሁ በማለት ሲሆን ድርጊቱን የፈፀመውም ከአዲስ አበባ ወደ ላንጋኖ ሂዶ ሲሆን ከአዲስ አበባ ወደ ላንጋኖ ሲሄድም የሌላ ሰው መሣሪያ ይዞ መሆኑ፣ላንጋኖ መዝናኛ ሲደርስም ሚቿ ከሌላ ሰው ጋር መሆኗን ከአዲስ አበባ በሄደበት እለት አረጋግጦ እዚያው ላንጋኖ መዝናኛ አድሮ ጥዋት ላይ የአሁኑ ተጠሪዎች ከቦታው ከደረሱለት በሁዋላ ሚቾች ወደ ተኙበት አልጋ በመስኮት ገብቶ ነው፡፡ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ተጠሪ ቀድሞውኑም ከአዲስ አበባ ሲነሳና እስከ ላንጋኖ ሌሊቱን በመጓዝ ሲደርስ ሰውን ለመግደል ሀሳብና ቅድመ ዝግጅት ያለው ስለመሆኑ በራሱ አረጋጋጭ ሲሆን ይህ ቅድመ ዝግጅቱን አያረጋግጥም ቢባል እንኳ ተጠሪ እዚያው አድሮ ሌሎች ሰዎች ወደ ቦታው ከደረሱ በሁዋላ ድርጊቱን መፈጸሙ ከላንጋኖ መዝናኛ ከደረሰ በሁዋላ ሁኔታውን አይቶና ተገንዝቦ፣አጠቃላይ ሁኔታዉን አውጥቶና አውርዶ ከአሰበና ሊከተል የሚችለውን ውጤት ሙሉ በሙሉ ለመቀበል ዝግጁ ከሆነ በሁዋላ ሲሆን በቅፅበት ደም ሊያፈላ የሚችል ሁኔታ ሲያልፍና መንፈሱ ሲረጋጋ የፈፀመው ድርጊት መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡እነዚህ ፍሬ ነገሮች 1ኛ ተጠሪ የግድያ ወንጀሉን አስቦበትና ቀድሞ ተዘጋጅቶበት በጭካኔ ወይም በአደገኛነት በተለይም በማንአለብኝነት የፈፀመው ስለመሆኑ ያሳያሉ ከሚባሉ በስተቀር በእለታዊ ፀብ እና አለመግባባት ምክንያት የፈፀመው ድርጊት ነው ለማለት የሚያስችሉ አይደሉም፡፡አንድ ሰው እጮኛው የሆነችውና ጋብቻ ለመፈፀም በዝግጅት ላይ ያለች ሴት ጋብቻው ከመፈፀሙ በፊት ከሌላ ሰው ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፅማለች ብሎ ከሴቷ ጋር ግብረ ስጋ ግንኙነት ሲፈፀም ነበር ከተባለው ሰው ጋር ይገኙበታል እስከተባለው ቦታ ድረስ ሌሊቱን ረዥም ጉዞ በመጓዝ ከደረሰና ሁኔታውን ከተመለከተ በሁዋላ ቀላል የማይባል ሰዓት አሳልፎ ሕግና ሥርዓት ባለበት አገር ሁለት ሰዎችን በአንድ ላይ አከታትሎ መግደሉ በማንአለብኝነት፣በቂምና በቅናት መንፈስ ክቡሩን የሰው ሕይወት አጥፍቷል ከሚባል በስተቀር በማናቸውም መመዘኛ ግድያውን ተራ የሰው ግድያ ወንጀል ሊያደርግ የሚችል አይደለም፡፡በመሆኑም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአቃቤ ሕጉ ማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ከሕጉ ጋር ማገናዘብ ሲገባው ያለሕጋዊና በቂ ምክንያት በ1ኛ ተጠሪ ላይ በአቃቤ በኩል ተጠቅሶ የቀረበውን ድንጋጌ መቀየሩ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡በዚህም መሰረት 1ኛ ተጠሪ ለፈመው የሰው ግድያ ወንጀል ሊጠየቅ የሚገባው በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 539(1(ሀ)) ስር እንጂ በአንቀጽ 540 ስር ባለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በ1ኛ ተጠሪ ላይ በወ/ሕ/ቁጥር 539(1ሀ) ስር የሠጡትን የጥፋተኝነት ውሳኔ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀየረው ያላግባብ ሁኖ ስላገኘነው በ1ኛ ተጠሪ (ኢዮስያስ አበራ) ላይ በወ/ሕ/ቁጥር 540 ስር የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(ለ-2)) መሰረት ለውጠን ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 539(1ሀ) ስር ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡

## 2ኛ. በሌሎች ተጠሪዎች(ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ በተጠቀሱት) ላይ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን በተመለከተ፡-

ሁለተኛ ተጠሪ(ለአለም አበራ) በስር ፍርድ ቤት በነፃ የተሰናበተ ሲሆን ለውሳኔው የስር ፍርድ ቤት መሰረት ያደረገው ምክንያትም ተጠሪው የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈጸሙ አልተረጋገጠም፣በመከላከያ ምስክርም ወደ ቦታው የሄደበትን ምክንያት አስረድቷል በሚል ምክንያት ነው፡፡2ኛ ተጠሪ በአቃቤ ሕግ የተከሰሰው ለ1ኛ ተጠሪ ግብረ አበር በመሆን በድርጊት አፈጻጸሙ

ተሳትፏል በሚል ምክንያት ሲሆን በድርጊት አፈፃጸሙ የነበረው ተሳትፎን በተመለከተም ሚቸች ወደ ተኙበት አልጋ 1ኛ ተጠሪ በመስኮት ሲገባ 2ኛ ተጠሪ በአልጋው በር በኩል ገብቷል፣ድርጊቱ ከተፈጸመ በሁዋላም በበር በኩል ወጥቷል በማለት በክሱ ላይ ገልጿል፡፡ይህንኑ የተጠሪን የወንጀል ድርጊት ተሳትፎ ለማረጋገጠም የሰው ምስክሮችን ያቀረበ ሲሆን 1ኛው የአቃቤ ምስክር በወቅቱ በቦታው ላይ የነበረ መሆኑን ገልፆ ሁለት ሰዎች ሲሯሯጡ እንደነበርና አንዱ ሚቸች ወደ ተኙበት አልጋ በበር ሲገባ ሌላው በመስኮት መግባቱን መመልከቱን በአከባቢ ማስረጃነት የመሰከረ ሲሆን 3ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር 2ኛ ተጠሪ ሚቸች ከተኙበት አልጋ ውስጥ ጥይት ከተተኮሰ በሁዋላ በበር በኩል ጃኬቱን ይዞ መውጣቱን መስክሯል፡፡ሌሎች የአቃቤ ሕግ ምስክሮች በሰጡት ቃልም 2ኛ ተጠሪ ድርጊቱ በተፈፀመበት ቦታ የነበረ መሆኑንና 1ኛ ተጠሪን ሌሎች ሰዎች ለመያዝ ሲሞክሩም እንዳይያዝና ጉዳት እንዳይደርስበት ጥረት ሲያደርግ የነበረ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡እንግዲህ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ነጥብ ሲታይ 2ኛ ተጠሪ ሚቸች በተገደሉበት ጊዜና ቦታ በመገኘት 1ኛ ተጠሪ በመስኮት ሲገባ እሱ ደግሞ በቤርጎው በር በመግባት ጥይት ከተተኮሰ በሁዋላ እንደገና በቤርጎው በር ሩጦ የወጣና ጃኬትም ለሌላ ሰው ያቀበለ መሆኑ እንዲሁም 1ኛ ተጠሪን በቦታው የነበሩት ሌሎች ሰዎች ከተኩሱ በሁዋላ ቁም ሲሉትም ይህንኑ ይከላከል የነበረ መሆኑ ነው፡፡እነዚህ ፍሬ ነገሮች ሲታዩ ደግሞ 2ኛ ተጠሪ ሚቸችን ራሱ በቀጥታ ተኩሶ መግደሉ ባይረጋገጥም ሚቸችን ለህልፈት የዳረገውን የተኩስ ተግባር 1ኛ ተጠሪ ሲፈፅም ከዚሁ ተጠሪ ጋር ተባብሮ ሚቸች ወደ ተኙበት አልጋ በበር በኩል መግባቱም ሆነ ከተኩሱ በሁዋላ በበር ሩጦ መውጣቱ በመላ ሀሳቡና አድራጎቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሠጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ መሆኑን የሚያስገነዝቡን ናቸው፡፡ የስር ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪን ነጻ ያደረገበት ምክንያት ድርጊቱን ስለመፈፀሙ አልተረጋገጠም፣በመከላከያም አስረድቷል በሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ ፍርድ ቤቱ ወደዚህ ድምዳሜ የደረሰው በአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር በአግባቡ ባለመያዝ በደፈናው የ2ኛ ተጠሪ የድርጊቱ ተሳትፎ አልተረጋገጠም በማለት ነው፡፡ አንድ ፍርድ ቤት በሕግ በኩል የቀረቡትን ማስረጃዎችን ውድቅ ሊያደርግ የሚገባው በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠውን ነገር ሙሉ በሙሉ በመመዘን እንጂ ከማስረጃዎቹ ውስጥ የተወሰነውን ፍሬ ነገር ብቻ በመያዝ ሊሆን እንደማይገባው ተቀባይነት ያላቸው የማስረጃ ሕግ ፅንሰ ሀሳቦች የሚያስገነዝበን ሐቅ ነው፡፡በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች በ2ኛ ተጠሪ ላይ የድርጊቱን ተሳትፎ አላረጋገጡም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ተጠሪ እንዲከላከል ትዕዛዝ ከሰጠ በሁዋላ ሁሉም የአቃቤ ሕግ ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል አንድ ባንድ ባለማየት ነው፡፡ተጠሪው በመከላከያ ማስረጃ የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን አስተባብሏል የሚለው ድምዳሜም ተጠሪው ወንድሙ የሆነው 1ኛ ተጠሪ ያለበትን ሁኔታ ለማየት ከአዲስ አበባ ወደ ላንጋኖ መሄዱ ተመስክሯል በሚል ምክንያት ነው፡፡ሆኖም የ2ኛ ተጠሪ የመከላከያ ማስረጃ ያረጋገጠው ይኸው ፍሬ ነገር ተጠሪው ላንጋኖ ከደረሰ በሁዋላ የነበረውን የድርጊት ተሳትፎን የሚያስተባብል አይደለም፡፡በመሆኑም ሁለተኛ ተጠሪ(ለአለም አበራ ገ/ሚካኤል) የወንጀል ድርጊቱን በመላ አሳቡና አድራጎቱ የወንጀሉ ድርጊት የሚሰጠውን ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ መሆኑ በአቃቤ ሕግ የአከባቢና የአይን ምስክሮች ተረጋገጦበት እያለ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር በመተው ተጠሪውን የስር ፍርድ ቤት በነጻ ማሰናበቱም ሆነ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች አለመታረሙ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘነው 2ኛ ተጠሪ ላይ የተሰጠውን የነጻ መለቀቅ ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁጥር 195(2(ሀ)) መሰረት ለውጠን 2ኛ ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1(ለ)) እና 539(1(ሀ)) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የተላለፈ ጥፋተኛ ነው ብለናል፡፡



www.chilot.me

ሌላው በአቃቤ ሕግ በኩል የቀረበው የሰበር ቅሬታ በ3ኛ ተጠሪ(ትርንጎ ወ/ሚካኤል) ላይ የተሰጠውን ውሳኔ የሚመለከት ነው።የስር ፍርድ ቤት 3ኛ ተጠሪን በተመለከተ በተከሰሱበት የሕግ ድንጋጌ ጥፋተኛ በማድረግ በአስራ አምስት አመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል።ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤት ደግሞ ተጠሪ በግድያው ወንጀል የነበራቸው ተሳትፎ አልተረጋገጠም በማለት ሙሉ በሙሉ በነጻ እንዲሰናበቱ አድርጓል።ይህ ችሎትም ጉዳዩን ሲመለከተው ማስረጃን የመመዘንና ፍሬ ነገርን የማጣራት ስልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአቃቤ ሕግን ማስረጃ ዝርዝር ይዘት በመመልከት 3ኛ ተጠሪ በግድያው ወንጀል የነበራቸው ተሳፍቶ አልተረጋገጠም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሷል።አቃቤ ሕግ ደግሞ የተጠሪ የወንጀል ተሳትፎ በማስረጃ የተረጋገጠ ነው በማለት ቅሬታውን አቅርቧል።ይሁን እንጂ አቃቤ ሕግ ክሱን ሲመሰርት 1ኛ ተጠሪ ሟቾችን እንደሚገድል ለ3ኛ ተጠሪ ስልክ ደውሎላቸው ይህንኑ ሰምተው ሌሊቱን በመኪና ሲጓዙ አድረው ድርጊቱ ወደተፈጸመበት ቦታ በመድረስ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ከተመካከሩ በሁዋላ ድርጊቱ መፈፀሙን፣ድርጊቱ ሲፈፀምም በቦታው ላይ 3ኛ ተጠሪ ቁመው ውጤቱን ሲጠባበቁ የነበሩ መሆኑን የጠቀሰ ቢሆንም ይህ በአቃቤ ሕግ ማስረጃ አለማረጋገጡን የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ የሚያስገነዝብ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም 3ኛ ተጠሪ ወደላንጋኖ የሄዱበትን ምክንያትና ከሄዱ በሁዋላ ስለግድያው የነበራቸውን ተሳትፎ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በግድያ ወንጀሉ 3ኛ ተጠሪ ተሳትፎ የነበራቸው ስለመሆኑ አልተረጋገጠም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሷል።ይህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ድምዳሜ የማስረጃ ምዘናን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ከተሰጠው የመሰረታዊ ሕግ ስህተት የማረም ስልጣን አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚገባው ሁኖ አልተገኘም።በመሆኑም አቃቤ ሕግ 3ኛ ተጠሪን በተመለከተ በከባድ የግድያ ወንጀል ተጠያቂ ሊሆኑ ይገባል በማለት ያቀረበው ቅሬታ የመሰረታዊ ሕግ ስህተትን መመዘኛ የሚያሟላ ሁኖ ባለማግኘታችን አልፈነዋል።ሆኖም 3ኛ ተጠሪ ድርጊቱ በተፈጸመበት ቦታ የነበሩ፣ተኩስ ከተሰማ በሁዋላም የወንጀል ድርጊቱ ከተፈፀመበት ቤርጎ ውስጥ በሌላ ሰው ወጥቶ የተሰጣቸውን ጃኬት ተቀብለው መኪና ውስጥ በማስገባት ቆልፈው በኋላ መኪናው ተከፍቶ ጃኬቱ ሲታይ ሽጉጥ መገኘቱ በስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ መሆኑ ሲታይ 3ኛ ተጠሪ ሙሉ በሙሉ ነፃ ሊሆኑ ይችላሉ? ወይስ በተረጋገጠባቸው መጠን አግባብነት ባለው የሕግ ድንጋጌ ሊጠየቁ ይገባቸዋል? የሚለውን ጥያቄ የሚያስነሳ ሁኖ አግኝተነዋል።በመሰረቱ አንድ ሰው በአቃቤ ሕግ በኩል የተመሰረተበት ክስ እንደክሱ አመሰራረት ሳይረጋገጥ ቢቀርም የቀረበው ማስረጃ ከቀረበው ክስ ያነሰ የወንጀል ድርጊት በተከሳሽ መፈጸሙ ከተረጋገጠ ተከሳሹ በተመሰከረበት የወንጀል ድርጊት የማይጠየቅበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 113 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው።በተያዘው ጉዳይ 3ኛ ተጠሪ የግድያ ወንጀል ከተፈጸመ በኋላ ሽጉጡ የተጠቀለለበትንና የተሰጣቸውን የግድያ ወንጀል ከተፈጸመበት ቤርጎ የወጣውን ጃኬት ተቀብለው ከመኪና ውስጥ መደበቃቸው የተረጋገጠ ሲሆን ይህም ወንጀል ከተደረገ በሁዋላ ሆነ ብለው ወንጀል አድራጊው ከመከሰስና ከመቀጣት እንዲያመልጥ የረዱት መሆኑን በግልፅ የሚያሳይ ሲሆን አድራጎቱ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 40 መሰረት በአንቀጽ 445 ስር ተጠያቂነት የሚያስከትል ነው።በመሆኑም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 3ኛ ተጠሪን በግድያ ወንጀል ሊጠየቁ አይገባም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰበት መንገድ የማስረጃ ምዘና ሁኖ በዚህ ችሎት ሊታይ የሚችል ባይሆንም ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪ ስለመፈፀማቸው በፍሬ ነገር ደረጃ በሚገባ የተረጋገጠውንና ወንጅሉ ከተደረገ በኋላ ወንጀል አድራጊውን መርዳትን በተመለከተ የተደነገገውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ 3ኛ ተጠሪን ጥፋተኛ ያለማድረጉ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ



www.chilot.me

አግኝተናል፡፡ስለሆነም 3ኛ ተጠሪ በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ የቀረበባቸውን ድንጋጌ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 113(2)መሰረት በመለወጥ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 40 እና 445 ስር የተመለከተውን የተላለፉ ጥፋተኛ ናቸው ብለናል፡፡

ሌላው በአቃቤ ሕግ በኩል የቀረበው ቅሬታ በስር 4ኛ ተከሳሽ(አብያለው አበራ) ላይ የተሰጠውን የነጻ መለቀቅ ውሳኔ የሚመለከት ነው፡፡አቃቤ ሕግ ይህ ተጠሪም በግድያው ወንጀል ሊጠየቅ የሚገባ መሆኑን ጠቅሶ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ይሁን እንጂ የስር ፍርድ ቤትም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤት ይህንኑ ተጠሪ ከግድያ ወንጅሉ ያሰናበቱት በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎችን በመመዘን ስለመሆኑ የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡በመሆኑም ከላይ እንደተጠቀሰው ይህ ችሎት በሕግ ከተሠጠው የመሰረታዊ ሕግ ስህተት የማረም ስልጣን አንፃር ሲታይ በዚህ ረገድ የተሰጠው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ይሁን እንጂ 4ኛ ተጠሪ በግድያ ወንጅሉ የነበረው የተሳትፎ ሁኔታ አልተረጋገጠም የተባለው ማስረጃ ተመዝኖ ቢሆንም ድርጊቱ በተፈጸመበት ቦታ ተገኝቶ ድርጊቱ ከተፈጸመበት የቤርጎ ቁጥር ከድርጊቱ በሁዋላ ወዲያውኑ የወጣውንና ድርጊቱ የተፈጸመበት ሽጉጥ መጠቅለሉ የተረጋገጠበትን ጃኬት ድርጊቱ ከተፈጸመበት ቤርጎ ከወጣው ሰው ተቀብሎ ለ3ኛ ተጠሪ መስጠቱ በአቃቤ ሕግ የአይንና የአካባቢ ማስረጃ የተረጋገጠበት ሲሆን ይህንኑ ፍሬ ነገር ላለመቀበል የሚያስችል ምክንያት የሌለ መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳያል፡፡ስለሆነም 4ኛ ተጠሪ( አብያለው አበራ) ወንጀል ከተደረገ በሁዋላ ወንጀል አድራጊውን በመርዳት ወንጀል መጠየቅ ሲገባው ከዚሁ የወንጀል አድራጎቱ ሁሉ ነፃ መደረጉ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር በመተው በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሳኔ ሊታረም የሚገባው ሁኖ ስለአገኘን 4ኛ ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 40 እና 445 መሰረት ጥፋተኛ ሊሆን የሚገባው ነው ብለናል፡፡

5ኛ ተጠሪን (መላኩ ግዛው ማሩን) በተመለከተ የቀረበውን የአቃቤ ሕግን ቅሬታ ስንመለከተው ደግሞ ይህ ተጠሪ ከድርጊቱ ሙሉ በሙሉ ነፃ የተባለው በጉዳዩ ላይ የቀረቡት ማስረጃዎች ተመዝነው ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃም ከግድያው ባነሰ የወንጀል ድርጊት ሊያስጠይቀው የሚችል የወንጀል ተሳትፎ ስለመኖሩ የክርክሩ ሂደት የማያረጋግጥ ሁኖ ስለአገኘነው በዚህ ረገድ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

## 3. ቅጣትን በተመለከተ

1ኛውን ተጠሪ በግፍ ሰው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ያሉት የበታች ፍርድ ቤቶች ያስተላለፉት የቅጣት መጠን አስራ ስምንት ዓመት ጽኑ እስራት ነው፡፡አቃቤ ሕግ ይህ ቅጣት ተገቢ ያለመሆኑን በመጥቀስ ለበላይ ፍርድ ቤቶች ይግባኙን ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ 1ኛ ተጠሪ ሁለት ሰው በግፍ መግደሉ በሚገባ ተረጋግጧል፡፡ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539(1)ሀ)) ስር ጥፋተኛ የተባለ አጥፊ ሊቀጣ የሚገባው እድሜ ልኩን በፅኑ እስራት ወይም በሞት ነው፡፡በመሠረቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ የወንጀል ህግ የአገሪቱን የወንጀል ህግ ግብ በአዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀጽ 1 ስር ሲደነግግ "የወንጀል ህግ ግብ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ ነው" በማለት ያስቀምጣል፡፡ ህጉ

በአንቀጽ 87 ላይ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ህጉ ሊደርስበት ያሠበውን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በህጉ መንፈስ መሠረት መፈፀም እንዳለባቸው በመርህ ደረጃ ይደነግጋል፡፡ይኸው አንቀጽ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎቹ ምን ጊዜም ሠብዓዊ ክብርን በሚጠብቅ መንገድ መፈፀም እንደሚኖርባቸው ያስገነዝባል፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 88 ሲታይም የቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሣሠንን በተመለከተ ዘርዘር ያሉ ንዑስ ድንጋጌዎችን አካቶ ይዟል፡፡ በዚህ አንቀጽ ስር ያሉ ንዑስ አንቀጾች የሚያሣዩት ፍርድ ቤቱ ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን የሚወሰነው የወንጀል ህጉን ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎችን እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ መሆኑን፣ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ ያነሣሡትን ምክንያቶችና የአሣቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ህግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስን የቅጣት አወሳሳን ደንቡ በግልፅ ያሳያል፡፡ከላይ እንደተገለጸው ቅጣት የሚወሰነው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88(2)፡ስር፡የተመለከቱትን ሁኔታዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ይህ ችሎትም እነዚህ ሁኔታዎችን ተመልክቷል፤አመዛዝኗልም፡፡ተጠሪ ሪኮርድ ያልቀረበበት መሆኑም ያለፈ የሕይወት ታሪኩ መልካም የነበረ መሆኑን እንደሚሳይ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 82(1(ሀ)) መሰረት የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሲሆን ከዚህ ውጪ 1ኛ ተጠሪ የተለየና ልዩ የሆነ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት የለውም፡፡ የቅጣት መጠኑንም በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 179(ሀ) መወሰኑ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ሲጠቃለልም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 1ኛ ተጠሪን ተጠያቂ ያደረጉበት ድንጋጌ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሰረት ያደረገና በምክንያትም የተደገፈ ቢሆንም በቅጣት ረገድ ግን ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ ሊያስቀጣ ከሚችለው የቅጣት መጠንና ከቅጣት ዓይነተኛ ዓላማ አንፃር ሲታይ ተገቢ ባለመሆኑ በተጠሪ ላይ የተጣለው የአስራ ስምንት ዓመት ፅኑ እስራት ቅጣት የቅጣት አወሳሰን መርሆዎችንና የቅጣትን ዓላማ ያልተከተለ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ በመሆኑም የተጠሪ አድራጎት በከባድ የሰው መግደል ወንጀል የሚሸፈንና የቅጣት መጠኑም ከእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ሊወርድ የሚችልበት የሕግ አግባብ የሌለ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

3ኛ ተጠሪን በተመለከተ ይህ ችሎት ጥፋተኛ ያደረጋቸው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 40 እና 445 ስር ሲሆን ቅጣቱ ሊተላለፍ የሚገባውም በዚሁ ድንጋጌ መሰረት ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ ጥፋተኛ የተባለ ሰው ሊቀጣ የሚችለው በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ነው፡፡ ቅጣት የሚወሰነው ደግሞ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88(2) ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን በማመዛዘን ሲሆን ይህ ችሎትም 3ኛና 4ኛ ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት ያስመዘገቡትን የቅጣት አስተያየት ከድርጊቱ አፈጻጸም ጋር አገናዝቦ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሰረት 3ኛ ተጠሪ በጉዳዩ የታሰሩት ማንኛውም ጊዜ የሚታሰብላቸው ሁኖ በሶስት አመት ቀላል እስራት ሊቀጡ የሚገባ ሁኖ አግኝተናል፡፡ ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ በበታች በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሊሻሻል የሚገባው ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡



www.chilot.me

## ው ሣ ኔ

1. በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 14431 ሚያዚያ 01 ቀን 2000 ዓ/ም የተሰጠ ውሳኔ ፣ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 65733 ጳጉሜ 04 ቀን 2000 ዓ/ም የተሰጠው ትእዛዝ ፣ በዚሁ ችሎት በመ/ቁጥር 64223 ህዳር 02 ቀን 2001 ዓ/ም የተሠጠው ውሳኔ ፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 31426 የካቲት 18 ቀን 2001 ዓ/ም የተሰጠው ትእዛዝ እንዲሁም በዚሁ ችሎት በመ/ቁጥር 74006 ታህሳስ 19 ቀን 2002 ዓ/ም የተሠጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2(ለ-2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. 1ኛ ተጠሪ (ኢዮስያስ አበራ) ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 539(1(ሀ)) ሲሆን ቅጣቱም እድሜ ልኩን ጽኑ እስራት እንዲሆን ተወስኗል ፣ 3ኛ ተጠሪ የፈጸሙት ድርጊት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 445 ስር የሚሸፈን ሁኖ ቅጣቱን በተመለከተ በጉዳዩ ላይ የታሰሩት ጊዜ የሚታሰብላቸው ሁኖ በሶስት አመት ቀላል እስራት እንዲቀጡ በማለት ወስነናል፡፡
3. 5ኛ ተጠሪ (መላኩ ግዛው)ን በተመለከተ በነፃ መሰናበቱ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
4. በ1ኛ ተጠሪ ላይ ቅጣቱ ተሻሽሎ የተወሰነ መሆኑን አውቆ ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለማረ/ቤቱ ይገለፅለት ብለናል፡፡ይፃፍ፡፡

ከተባለ በኂላ በ2ኛ እና በ4ኛ ተጠሪዎች ላይ ቅጣት ለመወሰን ይቻል ዘንድ የግራ ቀኙኝ የቅጣት አስተያየት በመጠየቅ ግራ ቀኙ ያቀረቡት የቅጣት አስተያየት በመቅረጸ ደምፅ ተቀርጿል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

1. ግራ ቀኙ ያቀረቡት የቅጣት አስተያየት ከመቅረፀ- ደምጽ ወደ ፅሑፍ ተቀይሮ ከመዝገቡ ጋር ይያያዝ ብለናል፡፡
2. የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት መርምሮ ተገቢውን ቅጣት ለመወሰን ለሰኔ 21 ቀን 2003 ዓ/ም ተቀጥሯል፡፡
3. 2ኛ፣3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎችን የአራዳ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ አቆይቶ ለሰኔ 21 ቀን 2003 ዓ/ም ችሎት እንዲያቀርባቸው ታዝዟል፡፡ ማሰሪያ ዋራንት ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁጥር 45595 እና 54215

ሰኔ 21 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ሕግ ዐ/ህግ ደሣለኝ ደንገላ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1.ኢዮስያስ አበራ ገ/ሚካኤል-አልተጠራም

2. ለአለም አበራ ገ/ሚካኤል-ቀረቡ፡፡

3. ትርንጎ ወ/ሚካኤል-ቀረቡ፡፡

4. አብያለው አበራ ገ/ሚካኤል-ቀረቡ፡፡

5. መላኩ ግዛው -አልተጠራም፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው በ2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ላይ የቅጣት ውሳኔ ለመስጠት ተብሎ ነው፡፡በዚህም መሰረት ጉዳዩን መርምረን ተከታዩን የቅጣት ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ቅ ጣ ት

2ኛ ተጠሪ ለአለም አበራ ጥፋተኛ የተባለው በግፍ ሰው መግደል ወንጀል በሚያስጠይቅበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539(1ሀ) ስር ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ የተባለ አጥፊ ሊቀጣ የሚገባው እድሜ ልኩን በፅኑ እስራት ወይም በሞት ነው፡፡

ቅጣት የሚወሰነው ደግሞ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 88(2) መሰረት ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ ያነሣሡትን ምክንያቶችና የአሣቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ህግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስን መገንዘብ ይቻላል፡ በዚህ መሰረት ይህ ችሎትም እነዚህ ሁኔታዎችን ተመልክቷል፤ አመዛዝኗልም፡፡ 2ኛ ተጠሪ ሪከርድ ያልቀረበበት መሆኑም ያለፈ የሕይወት ታሪኩ መልካም የነበረ መሆኑን እንደሚያሳይ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ይህ ደግሞ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 82(1(ሀ)) መሰረት የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሲሆን ከዚህ ውጪ 2ኛ ተጠሪ የተለየና ልዩ የሆነ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት የለውም፡፡ የቅጣት መጠኑንም በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 179(ሀ) መወሰኑ

ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ሲጠቃለልም 2ኛ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ ሊያስቀጣ ከሚችለው የቅጣት መጠንና ከቅጣት ዓይነተኛ ዓላማ አንፃር ሲታይ ተጠሪ ሊቀጣ የሚገባው በጉዳዩ ላይ የታሰረው ጊዜ የሚታሰብለት ሁኖ በእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ሁኖ አግኝተናል፡፡ 4ኛ ተጠሪን በተመለከተ ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ ሊያስቀጣ የሚችለው በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ነው፡፡ በተጠሪው ላይ ሊተላለፍ የሚገባውን የቅጣት መጠን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 88(2) ስር ከተመለከቱት ሁኔታዎች እና ከቅጣት አላማዎች ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡ በዚህም መሰረት 4ኛ ተጠሪ ሊቀጣ የሚገባው በጉዳዩ ላይ የታሰረው የሚታሰብለት ሁኖ **በ3 (ሶስት) አመት ቀላል** እስራት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ት ዕ ዛ ዝ</u>

1. 2ኛ ተጠሪ ለአለም አበራ ገ/ሚካኤል በጉዳዩ ላይ የታሰረው የሚታሰብለት ሁኖ በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ፣ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ደግሞ በጉዳዩ ላይ የታሰሩት የሚታሰብላቸው ሁኖ እያንዳንዳቸው በሶስት አመት ቀላል እስራት የተቀጡ መሆኑን አውቆ የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ከአራዳ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ በመረከብ በእያንዳንዳቸው ላይ በተላለፈው ቅጣት መሰረት ተከታትሎ እንዲያስፈፅም፡፡ የማሰሪያ ዋራንት ይጻፍ፡፡
2. መዝገቡ ያለቀለት በመሆኑ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ/ 47831

ሰኔ 03 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** 1. መስታወት ጌታነህ ከማረ/ቤት - ቀረበች

2. ግርማ ገዛኸኝ - አልቀረቡም

3. ባዩ ጌታነህ ከማረ/ቤት - ቀረበ

4. በለጠ አስፋ ከማረ/ቤት - ቀረበ

ለሁሉም ጠበቃ ወንድወሰን ተ/ማርያም - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ፌዴራል አቃቤ ሕግ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካቾች ላይ የመሠረተው የወንጀል ክስ በሁለት ምድብ የተከፈለ ሲሆን 1ኛው ክስ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወ/ህ/አንቀጽ 32(1(ሀ)(ለ))እና 539(1ሀ) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ አመልካቾች በሙሉ ሐሳባቸውና አድራጎታቸው በወንጀሉ ስራና በሚሰጠው ዉጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ተበዳዮች ጌታነህ ወ/ማሪያም እና ደስታ ወ/ማሪያም የተባሉት በጥቅምት ወር 1985 ዓ/ም በኢ.ሕ.አ.ዲ.ግ ታጋዮች 1ኛ/ ጌታነህ ወ/የስ ፣ 2ኛ/ መኮንን ጌታነህ ፣ 3ኛ/ በቀለች ወ/አረጋይ የተባሉ ቤተሰቦቻችንን አስገድለውብናል በሚል ቂም በቀል ተነሳስተው ቤት ንብረታቸውን በእሳት አውድመው ከአገር እንዲሰደዱ ካደረጓቸው በኂላ እንደገና በፍርድ ቤት ከሰዋቸው በነፃ ሲሰናበቱ 1ኛዋ አመልካች በተሰጠው የፍርድ ውሳኔ የበቀል ጥማቷ ባለመርካት ከአስር አመት በላይ ተበዳዮቹ የሚኖሩበትን ቦታ ለማወቅ በግብረአበሮቿ አማካኝነት ስትከታተል ቆይታ በ2ኛው አመልካች አማካኝነት ቤታቸውን ካገኘች በኂላ በተጨማሪም የተበዳይን ወንድሞች ቤት ጭምር ራሷ ፈልጋ በማግኘት ከቤታቸው ድረስ እየሄደች ስታጠና ቆይታ የወንጀሉን ሥራ መሪ ተዋናይ በመሆን 3ኛ እና 4ኛ አመልካቾችን ከደብረ ብርሃን ፣ 2ኛ አመልካችን ከአዲስ አበባ በማሰባሰብ የአከባቢው ሰው በስራ የሚሰማራበትንና ጭር የሚልበትን አመቺ ጊዜ አጥንተው ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ/ም ከጠዋቱ ከ4፡00 እስከ 6፡00 ባለው ጊዜ ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 07 ክልል ወደሚገኘው የሚኞች መኖሪያ ቤት በመሄድ ዘመድ ነን ብለው ሕፃናቱን በር ካስከፈቱ በኂላ ጨካኝታቸውንና አደገኛነታቸውን እንዲሁም

ነውረኝነታቸውን በሚገልፅ አስቃቂ ሁኔታ፡- 1ኛ/ ህፃን ፍቅረተ በቀለ እድሜዋ 12 አመት የሆነችውን ፣ 2ኛ/ ሕፃን ሐና በቀለ እድሜዋ 8 አመት የሆነችውንና 3ኛ ሕፃን ነጻነት በቀለ እድሜዋ 1 አመት ከ8 ወር የሆነችውን ከሟች ሕፃን ፍቅረተ በቀለ ጀርባ እንደታዘለች ሶስቱንም ሕጻናት በዱላ ጭንቅላታቸውን እና መላ ሰውነታቸውን እየተፈራረቁ ቀጥቅጠው በግፍ ገድለዋል የሚል ሲሆን 2ኛው ክስ ደግሞ ሁሉም አመልካቾች በ1996 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 669(3(ለ)) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ አመልካቾች ሕገ ወጥ ብልፅግና ለራሳቸው ለማግኘት በማሰብ በቡድን ተደራጅተው በ1ኛው ክስ ላይ በተገለጸው ጊዜና ስፍራ በክሱ ላይ የተመለከተውን የግፍ ግድያ ወንጀል ከፈጸሙ በሁዋላ ንብረትነቱ የአቶ በቀለ ወ/ማሪያም የሆኑ፡- ባለ 14 ኢንች ኤልጂ (LG) ቴሌቭዥን ፣ ሶስት ጋቢዎች ፣ አንድ ሰማያዊ ሸራ ላስቲክ እና አንድ አሮጌ የማዳበሪያ ከረጢት ሰርቀው በመውሰዳቸው ከባድ የስርቆት ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ አመልካቾች ክሱን ክደው በመከራከራቸውም ዐቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስዎችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ከዚህም በኋላ የአመልካቾች የመከላከል መብት ተጠብቆላቸው የመካለከያ ማስረጃዎችን አቅርበው አሰምተዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አመልካቾች የዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ያላስተባበሉ መሆኑን ዘርዝሮ የመከላከያ ማስረጃዎቻቸውን ቃል ውድቅ ያደረገ ሲሆን አመልካቾችን በዐቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሰው በቀረቡባቸው ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ በማድረግ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በቅጣት ረገድም የአሁኗ 1ኛ አመልካችን (መስታወት ጌታነህን) በሞት ፣ ሌሎች አመልካቾችን ደግሞ በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ሲል በድምፅ ብልጫ ወስኗል፡፡ አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት በተሰጠው የጥፋተኝነም ሆነ የቅጣት ውሳኔ ይግባኛቸው ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ በሌላ በኩል ዐቃቤ ሕግ ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተራ በተጠቀሱት አመልካቾች ላይ የተሰጠውን የቅጣት ውሳኔ ሕጋዊነት የለውም ፤ ያነሰ ነው በሚል ምክንያት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የአመልካቾችን የድርጊት አፈጻፀም ከሕጉ ጋር በመመርምር አመልካቾች ሊቀጡ የሚገባው በሞት ነው በማለት የስር ፍርድ ቤትን የቅጣት ውሳኔ አሻሽሎ ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በጥፋተኝነት እና በቅጣት ውሳኔው ላይ ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ድርጊቱን አመልካቾች ስለመፈጸማቸው በወንጀል ሕግ የማስረጃ ምዘና መርህ ባልተረጋገጠበት ሁኔታና በፖሊስና በፍርድ ቤት አመልካቾች ሰጡ የተባሉት የእምነት ቃል በኃይል የተገኘ ሁኖ እያለ የወንጀል ድርጊቱን ፈጽማችኋል ተብሎ የመከላከያ ማስረጃዎችን እንድናቀርብ ብይን መሰጠቱ ያላግባብ ከመሆኑም በላይ የመከላከያ ማስረጃዎች ቃል ውድቅ የተደረገው ያላግባብ ነው ፣ የቅጣቱ ውሳኔም ሕጉን የተከተለ ሳይሆን የተጋነነ ነው በማለት ውሳኔው እንዲታረም ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካቾች እያንዳንዳቸው በሞት እንዲቀጡ ተብሎ የተወሰነው የቅጣት ውሳኔ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ታህሳስ 07 ቀን 2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለበት ወይስ የለበትም? የሚለው ሁኖ አግኝቶታል፡፡



www.chilot.me

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች ሶስቱን ህፃናት ለሕልፈተ- ሕይወት ዳርገዋል ፣ ከባድ የስርቆት ወንጀል ፈጽመዋል ተብሎ በግፍ የሰው ግድያና በከባድ የስርቆት ወንጀል ጥፋተኛ የተባሉበት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 27(2) ለፖሊስ ፣ በወ/መ//ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 35 ደግሞ ለፍርድ ቤት ሰጡ በተባሉት የእምነት ቃል ፣ የድርጊቱን አፈጻጸም መርተው ሲያሳዩ በተነሱት ገላጭ ማስረጃና በጠንካራ አካባቢ የሰው ምስክሮች ቃል ስለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በግልፅ ተጠቅሷል። የአመልካቾች የመከላከያ ምስክሮች ቃል ውድቅ የተደረገውም አመልካቾች የእምነት ቃሉን የሠጡት በኃይል ስለመሆኑ ለማስረዳት እምነት ሊጣልበት የሚችል አይደለም በሚል ምክንያት ነው። እንግዲህ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካቾች ድርጊቱን ፈፀሙ በማለት ድምዳሜ ላይ የደረሱት አመልካቾች እያንዳንዳቸው በድርጊቱ አፈጻጸም ላይ የነበራቸውን ቀጥተኛ ተሳትፎ በሚገባ አቃቤ ሕግ አስረድቷል ፣ በመከላከያ ማስረጃዎቻቸውም አልተደገፉም በሚል ነው።የአመልካቾች ጠበቃ ከሚከራከሩባቸው ነጥቦች ውስጥ የአመልካቾችን የድርጊት ፈጻሚነት በተገቢው መንገድ አቃቤ ሕግ በማስረጃ ያለማስደገፉንና የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን አመልካቾች በመከላከያ ምስክሮች የማስተባበላቸው ሁኔታን የሚመለከቱ ነጥቦች የሚገኙ ሲሆን የበታች ፍርድ ቤቶች ተገቢውን የማስረጃ ምዘና መርህ ተከትለው አመልካቾችን ጥፋተኛ ያደረጉ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የሚያሳየን ሁኖ አግኝተነዋል። በመሆኑም ከዚሁ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መገንዘብ የሚቻለው አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉት በጉዳዩ ላይ የቀረቡት ማስረጃዎች ተመዝነው መሆኑን ነው። እንደሚታወቀው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት አንድ የመጨረሻ ፍርድ ያገኘን ጉዳይ ማረም የሚችለው በውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መኖሩ ሲረጋገጥ ስለመለሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ተመልክቷል። ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ ይህ ሰበር ችሎት ፍሬ ነገርን የማጣራት ወይም ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የሌለው መሆኑን ነው። በተያዘው ጉዳይም የአመልካቾች ጠበቃ አጥብቀው የሚከራከሩባቸው ነጥቦች የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን መሰረት ያደረጉ ሳይሆን የፍሬ ነገርንና የማስረጃ ምዘናን መሰረት ያደረጉ በመሆናቸው በዚህ ችሎት ሊታዩ የሚችሉ ሁነው አላገኘናቸውም።በመሆኑም አመልካቾች የእምነት ቃላቸው በመገደድ የተገኘ ስለመሆኑ ማረጋገጥ ባልቻሉበት ሁኔታና በራሳቸው ምሪት ወንጀሉ የተሰራበትን ቦታና የአፈጻጸሙን ሁኔታ ስለማሳየታቸው በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጦ ባለበት የክርክር ሂደት እንዲሁም ወንጀሉ በአመልካቾች ስለመፈጸሙ ደግሞ በበርካታ ጠንካራ የአካባቢ ማስረጃዎች ተደግፎ በቀረበበት መንገድ አመልካቾች የአቃቤ ሕግ ማስረጃ በሕጉ መመዘኛ የሚያሟላ አይደለም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የሕግ መሰረት ያለው ሁኖ አልተገኘም። አመልካቾች ለድርጊቱ ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ የተወሰነው ወንጀሉ መሰራቱ ወይም መፈጸሙና ተሰራ ወይም ተፈጸመ የተባለው ወንጀል ደግሞ በአመልካቾች መፈጸሙ በማያጠራጥር ሁኔታ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ በመሆኑና ይህም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የሚያሟላ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን ክርክር የምንቀበለው ሁኖ አላገኘነውም። ወደዋናው ጭብጥ ስንመለስም የአመልካቾች መሠረታዊ ክርክር የበታች ፍርድ ቤቶች ያስተላለፉት የሞት ቅጣት የቅጣት አወሣሠኑን በተመለከተ የወንጀል ህጉ ያስቀመጣቸውን መርሆዎች ያላገናዘበ ነው የሚል ነው። እኛም ይህንኑ ቅሬታ ከህጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል።

በመሠረቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ የወንጀል ህግ የአገሪቱን የወንጀል ህግ ግብ በአዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀጽ 1 ስር ሲደነግግ "የወንጀል ህግ ግብ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ

ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ ነው" በማለት ያስቀምጣል፡፡ ህጉ በአንቀጽ 87 ላይ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ህጉ ሊደርስበት ያሠበውን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በህጉ መንፈስ መሠረት መፈፀም እንዳለባቸው በመርህ ደረጃ ይደነግጋል፡፡ ይኸው አንቀጽ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎቹ ምን ጊዜም ሠብዓዊ ክብርን በሚጠብቅ መንገድ መፈፀም እንደሚኖርባቸው ያስገነዝባል፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 88 ሲታይም የቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሣሠንን በተመለከተ ዘርዘር ያሉ ንዑስ ድንጋጌዎችን አካቶ ይዟል፡፡ በዚህ አንቀጽ ስር ያሉ ንዑስ አንቀጾች የሚያሣዩት ፍርድ ቤቱ ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን የሚወሰነው የወንጀል ህጉን ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎችን እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መሆኑን ፣ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ ያነሣሡትን ምክንያቶችና የአሣቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ህግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስንና የቅጣት አወሣሰን ትክክለኛነትና አንድ ወጥነት ለማረጋገጥ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የቅጣት አወሣሠን መመሪያ (Manual) እንደሚወጣ የሚያስገነዝቡን ናቸው፡፡

ከላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንረዳው አቢይ ነጥብ ቅጣቶች መወሠን ያለባቸው የህጉን መንፈስ በመከተል ዓላማዎችንና ግቦቹንም ተፈፃሚ በማድረግ ሀሣብ መሆኑን ነው፡፡ የህጉን መንፈስ ከመተግበር አኳያ ወንጀለኛውን ማዕከል የማድረግ ፅንሰ ሀሣብ አጽንኦት የተሠጠው ጉዳይ ነው፡፡ ዳኞች በፅንሰ ሀሣቡ መሠረት የተሠጣቸውን አመዛዝኖ የመወሰን ስልጣን (Discretion) በስራ ላይ ሲያውሉ ሠብአዊ ክብርን ከማስጠበቅ ዓላማ ጋር መሆን ያለበት ከመሆኑም በላይ ህግ አውጪው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 87/1/ ስር የተመለከቱትን መሠረት በማድረግ ዳኞች የቅጣት ውሣኔ በምን መንገድ መወሠን እንደሚገባቸው በአንቀጽ 88 ስር አስቀምጧል፡፡ በወንጀል ህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ስንመለከትም ዳኞች ከተሠጣቸው የቅጣት ክልል ሣይወጡ የአጥፊውን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ቅጣት እንዲወስኑ ህጉ ስልጣን የሠጣቸው መሆኑ ነው፡፡ ዳኞች አጥፊውን በተመለከተ ከግምት ውስጥ ሊያስገቧቸው የሚገባቸው በርካታ የአጥፊ ፡ ሁኔታዎች ቢኖሩም የቅጣት አወሣሠናቸው መሠረት የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን /degree of individual guilt/ ስለመሆኑ የአንቀጽ 88/2/ ድንጋጌ ይዘትና አቀራረፅ ያስረዳል፡፡ አንቀጽ 88(2) በመጀመሪያ ደረጃ የወንጀል አድራጊውን የአደገኛነት መጠን መሠረት በማድረግ ዳኞች ቅጣት እንዲወስኑ ማድረጉና ይህንን ሲወስኑም በድንጋጌው የተመለከቱትን የወንጀሉን አፈፃፀም የአጥፊውን ያለፈ የህይወት ታሪኩንና የኑሮ ሁኔታ ከግምት በማስገባት በማመዛዘን ለወንጀሉና ለወንጀለኛው የሚገባውን የቅጣት መጠን እንዲወስኑ መደንገጉ የቅጣት ውሣኔዎችንና እርምጃዎችን እየተራራቁ እንዳይወሠኑ የማድረግ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ከመታሠቡም በተጨማሪ ችግሩ የሚቀረፍበትና የሚቀነስበትን ሥርዓትም ህጉ ዘርግቷል፡፡ ዳኞች ቅጣት ሲወስኑ በህጉ አንቀጽ 88(2) ለአጥፊው ተገቢ ነው ያሉትን ቅጣት ከወሠኑ በኋላ በህጉ የተመለከቱትን የማቅለያና የማክበጃ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ቅጣቱን ከፍ ወይም ዝቅ ለማድረግ የሚችሉ ስለመሆኑ ህጉ ያሣያል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ህግ በአንቀጽ 84(1) ከፊደል (ሀ) እስከ ፊደል (ሠ) ድረስ ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን ካስቀመጠ በኋላ በአንቀጹ ንዑስ ቁጥር ሁለት ስር በንዑስ ቁጥር አንድ

ስር የተመለከቱት የማክበጃ ሁኔታዎች በህጉ ልዩ ክፍል ተካተው ሲገኙ በድጋሚ በማክበጃነት ዳኞች እንዳይጠቀሙ ያሣስባል፡፡ ስለሆነም የህጉ አንቀጽ 84 ደግሞ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን የዘረዘረ ሲሆን ዳኞች የህጉን አንቀጽ 183 ባገናዘበ መልኩ ቅጣት የሚያከብዱባቸውን ሁኔታዎች ያሣያል፡፡ ዳኞች ቅጣትን የሚቀንሱትም ሆነ የሚያከብዱት ተገቢ ሁኖ ሲገኝ ስለመሆኑ የአንቀጽ 179 እና 183 ድንጋጌዎች ያሣያሉ፡፡ አንቀጽ 179 የቅነሣውን ገደብ የሚያሣይ ሲሆን ከዚህ መደበኛ ቅነሣ በተጨማሪ ልዩ ቅነሣ ለማድረግ እንደሚቻልም ህጉ በአንቀጽ 180 ስር አስቀምጧል፡፡ በህጉ አንቀጽ 86 ቅጣትን በማቅለልም ሆነ በማክበድ ረገድ ከህጉ አንቀጽ 179፣182 እና ውጪ የሆኑ ምክንያቶች ሲያጋጥማቸው ዳኞች ምክንያታቸውን በመግለፅ ቅጣቶችን ለመቀነስ ወይም ለማክበድ እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡ ግንቦት 09 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ ተግባራዊ በሆነው የቅጣት መመሪያ ውስጥ የተቀመጠው የቅጣት አወሳሰን ሥርዓት እንደተጠበቀ ሁኖ ከላይ ስለቅጣት አወሣሰን በህጉ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ሲታዩ የሚያስገነዝቡን ዓቢይ ነጥብ ቅጣቶችን በመጣልና እርምጃዎችን በመውሠድ ረገድ ዳኞች **አመዛዝነው የመወሠን ከፍተኛ ስልጣን ያላቸው መሆኑን ነው፡፡**

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉት ግዙፍነት ባላቸው ተደራራቢ ወንጀሎች ሲሆን የግድያ ወንጀሉ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 32(1(ሀ)(ለ)) እና 539(1ሀ)) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ በቂም ፣ ጨካኝነት ፣ ነውረኝነት ፣ አሰቃቂና አደገኛነትን በሚያሳይ ሁኔታ ምንም የማያውቁ ጨቅላ ሕጻናትን በግፍ ገድለዋል ተብሎ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ ጥፋተኛ የተባለ አጥፊ ሊቀጣ የሚገባው እድሜ ልኩን በጽኑ እስራት ወይም በሞት ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው ፍርድ ቤት ቅጣት ሲወስን ሊከተላቸው የሚገባቸው የቅጣት አወሳሰን መርሆዎች በሕጉ ላይ ተቀምጠዋል፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአመልካቾች ላይ ያስተላለፈው የሞት ቅጣት ስለመሆኑም ከላይ ገልፀናል፡፡

በመሰረቱ ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት እንዳለውና በሕግ በተደነገገው ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን ሊያጣ እንደማይገባ የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት በአንቀፅ 15 ስር በኃይለ ቃል የደነገገው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በሕጉ አግባብ ከባድ ወንጀል መፈጸሙ በተረጋገጠበት ሰው ላይ የሞት ቅጣት ማስተላለፍ የሚፈቀድ መሆኑን ሕገ መንግስቱ አስቀምጧል፡፡ በሌላ በኩል የሞት ቅጣት ሊተላለፍ የሚገባበትን አግባብ የወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 117 ስር ድንግጎ እናገኛለን፡፡ በዚህ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ መሰረት የሞት ቅጣት የሚወሰነው ወንጀሉ ፍጻሜ ያገኘ ሁኖ እጅግ በጣም ከባድ በመሆኑና ወንጀለኛውም በተለይ አደገኛ በመሆኑ ለወንጀሉ ቅጣት እንዲሆን በሕጉ በግልጽ ተደንግጎ በተገኘ ጊዜ እንዲሁም ለወንጀለኛው ቅጣትን የሚያቀልለት ምክንያት በታጣ ጊዜ እድሜው ቢያንስ አስራ ስምንት አመት የሞላው ሁኖ ሲገኝ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ እድሜ ልኩን በፅኑ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጣ ነው፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሞት ቅጣቱን ለመወሰን የቻለውም ድርጊቱን ለመፈጸም ያነሳሳቸውን ምክንያት ፣ ድርጊቱን ለመፈጸም ለረዥም አመታት ሲደረግ የነበረውን ቅድመ ዝግጅትና እና ድርጊቱ የተፈጸመባቸው ምንም የማያውቁና ከማንኛውም ሰው እንክብካቤ የሚሹ ሶስት ጨቅላ ህጻናት ላይ መሆኑን እንዲሁም የአፈጻጸሙን ዘግናኝነትና አስቃቂነት ከአመልካቾች አደገኛ ባህርይና ቅጣቱ ለሌላው ማህበረሰብ ሊያስተላልፈው ከሚችለው መልዕክት በመነሳት ከመሆኑም በላይ ለአመልካቾች በሕጋዊ ማቅለያነት ሊያዙ የሚችሉ ምክንያቶች የሌሉ መሆኑን በመረዳት መሆኑን ከውሳኔው ይዘት ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተያዘው ምክንያትና የተደረሰው ድምዳሜ በቅጣት አወሳሰን ጊዜ

ግንዛቤ ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ የቅጣት አወሳሰን መሰረታዊ መርሆዎችን ያልተከተለ ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለልም በአመልካቾች ላይ የተጣለው የሞት ቅጣት የወንጀል ሕጉን መሰረታዊ ግብና ዓላማ እንዲሁም የቅጣት አወሳሳን መርሆዎችን ከድርጊቱ አፈጻፀም ጋር ያገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/መ/ቁ 45475 ሰኔ 26 ቀን 2001 ዓ.ም ፤ 45693 ሰኔ 26 ቀን 2001 ዓ/ም እና በመ/ቁጥር 45640 ሰኔ 26 ቀን 2001 ዓ/ም የሰጣቸው ውሳኔዎች በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2)(ለ-2) መሠረት ጸንተዋል፡፡
2. አመልካቾች በሞት እንዲቀጡ ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡ የሞት ቅጣቱ ተፈጻሚነት የሚኖረውም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 117(2) መሰረት በአገሪቱ ርዕሰ ብሔር ከፀና በሁዋላ ይሆናል ብለናል፡፡
3. በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው የሞት ቅጣት የፀና መሆኑን አውቆ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለአዲስ አበባ ማረ/ቤት ይፃፍ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 67947

15/10/2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ አዱኛ አንበሎ - ጠበቃ ሰለሞን እምሩ ከቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌደራል ዐቃቤ ሕግ ወርቅነህ ዘነበ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሁን ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስ በፌ/የከፍተኛ ፍ/ቤት የተጀመረ ሲሆን ቀርቦ የነበረው ክስ፡-

1ኛ ክስ ተከሣሽ በ1996 ዓ.ም የወንጀል ህግ አንቀጽ 693/1/ ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ የቢ.ኤ.ኦሜጋ ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ ማህበር ምክትል ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ይሰራ በነበረበት ወቅት በባንክ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ ያለመኖሩን እያወቀ በ05/2/01 ዓ.ም ከዳሽን ባንክ ጥቁር አንበሣ ቅርንጫፍ ወጪ ሆኖ የሚከፈል ብር 3,000,000 /ሶስት ሚሊዮን ብር / የያዘ ቁጥሩ ኤች 257/638 የሆነ ቼክ ለአቶ ፍትዊ ወልዳይ ፈርሞ ከሰጠ በኋላ በ15/7/01 ዓ.ም ቀርቦ ክፍያ ሣይፈፅሙለት በመመለሱ በፈፀመው ገንዘብ ሣይኖር ቼክ ማውጣት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

2ኛ ክስ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወ.ህ በአንቀጽ 693/1/ ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ የተጠቀሰው የንግድ ድርጅት ምክትል ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ይሰራ በነበረበት ወቅት በባንክ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ አለመኖሩን እያወቀ በ06/2/2002 ዓ.ም ከላይ ከ1ኛ ክስ በተመለከተው ዳሽን ባንክ ቅርንጫፍ ወጪ ሆኖ የሚከፈል ብር 300,000 /ሶስት መቶ ሺ.ህ ብር/ የያዘ ቁጥር ኤች 257/680 የሆነ ቼክ በ1ኛው ክስ ስማቸው ለተጠቀሰው ግለሰብ ፈርሞ ከሠጠ በኋላ ቼኩ በ11/07/01 ዓ.ም ለባንክ ቀርቦ በቂ ገንዘብ የለውም ተብሎ ክፍያ ሳይፈፀምለት በመመለሱ የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ በማውጣት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

3ኛ ክስ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወ/ህግ አንቀጽ 302/1/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ የሌላውን ሠው መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት አስቦ በቦሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 12/13 ክልል ልዩ ቦታው ዳሚና ሩፋ ህንፃ ላይ ከሚገኘው ቢ.ኤ ኦሜጋ ኃ/የተ/የግ ማህበር ውስጥ የማህበሩ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሠራ በእጁ የነበረ ለሥራ አስኪያጅ አቶ በላይነህ ሰርጉአለም ብቻ የሚፈረም የዳሽን ባንክ ጥቁር አንበሣ ቅርንጫፍ ቼክ ውስጥ ሐምሌ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ከቀኑ በግምት 4:00

ሰዓት ሲሆን TF 4948565 የሆነ ቼክ የግል ተበዳይ በላይነህ ሰርጉአለም ፊርማን አስመስሎ ፈርሞ ከማህበሩ ገንዘብ ጠያቂ ለነበረው ሞክሮ ጀነራል ኮንተራክተር 225,477.38/ሁለት መቶ ሃያ አምስት ሺህ አራት መቶ ሰባ ሰባት ብር ከሠላሣ ስምንት ሣንቲም/ እንዲከፍል ለተወካዩ አቶ ኤልያስ ማሞ ከሠጠው በኋላ ቀኑ ይርዘም ቢቻል ሲለው በ17/8/08 የሚለውን እላዩ ላይ በ15/8/08 በሚል አስተካክሎ ለማረጋገጥ በላዩ ላይ የግል ተበዳዩን ፊርማ አስመስሎ ከቀኑ በላይ ፈርሞ በመስጠት በፈፀመው ሃሠተኛ ሠነድ በመፍጠር ሌላው እንዲገለገልበት ማድረግ ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

አመልካች የቀረበባቸውን ክሶች አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደሁም በማለት ተከራክሯል፡፡ በዚሁ መሠረት ከሣሽ ( ዐ/ሕግ ) አሉኝ ያለውን የሠውና የሠነድ ማስረጃ በማቅረብ አሠምቷል፡፡ ተከሣሽ/አመልካች/ መከላከያውን እንዳያቀርብ በተሠጠው መብት መሠረት የሰነድና የሠው ማስረጃ አቅርቦ አሠምቷል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ እና 2ኛ ክስ ተደራራቢ ወንጀል ነው ማለት ስለማይቻል በአንድ አንቀጽ ሥር በወ.መ.ሕግ ቁ 693/1/ ሥር ጥፋተኛ በማድረግ ሶስተኛውን ክስ በክሱ በተመለከተው አንቀጽ 382/1/ ሥር ጥፋተኛ በማለት የጥፋተኛነት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ቅጣትን በተመለከተ ጥፋተኛ በተባሉበት ሁለቱ አንቀጾች ሥር በ1 ዓመት ከ4 ወር ፅኑ እሥራት እንዲቀጡ ከወሰነ በኋላ በሁለት ዓመት የፈተና ጊዜ ገድቧል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት አመልካችም ሆኖ ተጠሪ ይግባኙ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን የአመልካች ቅሬታ ውድቅ ሲደረግ የአሁን ተጠሪ ይግባኝ ግን ተቀባይነት አግኝቶ በዐቃቤ ሕግ በቀረባቸው ሶስቱም ክስ ሥር ጥፋተኛ ነው በማለት ፍርድ ከሠጠ በኋላ ለ1ኛው ድርጊት 4 ዓመት ፅኑ እሥራት ፣ ለሁለተኛ ድርጊት 1 ዓመት ፅኑ እሥራት እና ለ3ኛው ድርጊት 1 ዓመት ፅኑ እሥራት ሆኖ ባጠቃላይ በ6 ዓመት ፅኑ እሥራት እንዲቀጣና በ1ኛ ና 2ኛ ድርጊቶች በተጨማሪ የገንዘብ መቀጮ ባጠቃላይ 11,000/አሥራ አንድ ሺህ ብር/ እንዲቀጣ በማለት ወስኗል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ሲሆን አመልካች ይግባኝ ያቀረበበት የመዝ.ቁ 55773 ንም በመጨመር የቀረበ ነው፡፡ የቅሬታው ፍሬ ሃሣብ በ1ኛ እና 2ኛ ክስ ሥር የተጠቀሰው አቶ ፍትዊ ወልዳይ ላይ የተፈፀመ የማታለል ተግባር የሌለ መሆኑን አቶ ፍትዊ ወልዳይ ለድርጅቱ የኮንስትራክሽን ዕቃዎችንና ቢሮ ሲያከራዩ ድርጅቱ ከደንበኞቹ ገንዘብ ሰብስቦ እስኪሠጣቸው ድረስ ሁለቱ ቼኮች በዋስትና መልክ የተሠጠ እንጅ ባንክ ቤት ሄደው እንዲመነዝሩት አይደለም፣ ተበዳይ የተባሉትም ቼኮቹ በቂ ስንቅ እንደሌላቸው የሚያውቁ ስለመሆኑ ለፍ/ቤቱ አስረድተዋል፣ ቼክ ደግሞ በዋስትና ሊሠጥ የሚችል ሠነድ ስለመሆኑ የሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ በፊት በመዝገብ ቁ 24435 የህግ ትርጉም የሠጠበት በመሆኑ፣ አመልካች ቼኮቹን በፈረሙበት ወቅት ከዋና ሥራ አስኪያጅ በተሠጣቸው ውክልና መሠረት ሲሆን ለባንክ በቀረበበት ጊዜ ግን ውክልናቸው በመውረዱ ተከታትለው ሃሣቡን ማስተካከል የማይችሉ በመሆኑ፣ ቼኩ ለክፍያ ቀርቦ ሊመለስ የቻለው በቂ ስንቅ የለውም በማለት ሣይሆን ሂሣቡ በመዝጋቱ በመሆኑ እና ጥፋተኛ ሊባሉ ይገባል ቢባል እንኳ 1ኛ እና 2ኛ ክስ በአንድ የወንጀል የመሥራት ሃሣብ የተሠራ በመሆኑ እንደሁለት የተለያዩ ወንጀሎች መታየት የለባቸውም የሚል ሲሆን፣ ሶስተኛውን ክስ በተመለከተ የተጠቀሰው ቼክ በአቶ በላይነህ ሠርጉአለም ያልተፈረመ ስለመሆኑ በቴክኒክ ምርመራ ከመረጋገጥ አልፎ በአመልካች ስለመፈረሙ አልተረጋገጠም፣ የሠነድ ማስተካከያ አድርገዋል ቢባል እንኳ የነበረን ዕዳ ከመክፈል አኳያ እንጅ ሀሰተኛ ሠነድ ለመፍጠር ባለመሆኑ በቸልተኝነት አደረጉ ቢባል እንኳ እንደሚያስቀጣ ባለመደንገጉ ጥፋተኛ የሚያደርግ አይደለም ፣ ቼኩ የተሠጠው የድርጅቱን



www.chilot.me

ትክክለኛ ዕዳ ለመክፈል እንጅ ድርጅቱን ለመጉዳት ወይም አመልካች ራሱን ወይም ሌላውን ለመጥቀም ያደረገው ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

ቅጣትን በተመለከተ አመልካች ጥፋተኛ የሚባል ከሆነ እንኳ ከዚህ በፊት ወንጀል ፈፅመው ሪከርድ የሌለባቸው በመሆኑ፣ የቤተሰብ ኃላፊ መሆናቸው፣ አጠቃላይ የጉዳዩ አፈፃፀም እና ያበረከቱት አስተዋጽኦ ታይቶ ቅጣቱ ተሻሽሎ በገደብ እንዲለቀቁ በማለት የቀረበ ነው፡፡

ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ዐቃቤ ሕግ መልስ እንዲሠጥበት ታዞ በቀን 06/10/03 6 ገፅ የጽሑፍ መልስ አቅርበል፡፡ የመልሱ ፍሬ ሃሣብ የቀረበው ቅሬታ የፍሬ ነገር ክርክር እንጂ መሠረታዊ የሕግ ስህተትን የማይመለከት በመሆኑ በሰበር ሰሚ ችሎት የማይታይ በመሆኑ ውድቅ ሆኖ እንዲሠናበት ፣ በ1ኛ እና 2ኛ ክስ ሥር ማታለሉ ከተከፋይ አቶ ፍትዊ ወልዳይ አኳያ ብቻ የሚታይ ከሆነ መታለል የለም ብሎ መከራከር ይቻላል ሆኖም በወ.መ.ሕግ ቁ 692 ሥንመለከት በቼኩ መታለል መፈፀሙን ለማስረዳት ብቸኛው መመዘኛ ቼኩ ለክፍያ ሲቀርብ በቂ ስንቅ የሌለው መሆኑን ማረጋገጥ በቂ ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ የግል ተበዳይ ጠየቀም አልጠየቀም የህጉ አላማና ፍላጎት የሕዝብን ጥቅም ከማስከበር አኳያ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ክርክር አይደለም፣ የተሠጠውም ቼክ በዋስትና የተሠጠ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ነገር የለም፣ ሶስተኛው ክስ ሥርም ፊርማውን ከሥራ አስኪያጁ ጋር አመሣስሎ የፈርመው ተበዳይን ለመጉዳት እንደሆነ ግልፅ በመሆኑ እና የተሠጠው የጥፋተኝነትም ሆኖ ቅጣት የሚነቀፍ ባለመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈፀመበትም ተብሎ እንዲሠናበት በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በቀን 10/10/2003 ዓ.ም 3 ገፅ የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም መዝገቡን መርምሮታል፡፡ በዚሁ መሠረት መፍትሔ ማግኘት ያለባቸው ጭብጦች፡-

1. በ1ኛ እና 2ኛ ክስ ሥር የአመልካች በወ.መ.ሕግ አንቀጽ 693/1/ ሥር ጥፋተኛ የመባሉን አግባብነት ከአጠቃላይ የቼኩ አሠጣጥ ሂደት አኳያ በመመርመር
2. በ3ኛ ክስ ሥር በተጠቀሰው አንቀጽ የወ/መ/ሕ/ቁ 382/1/ ሥር ጥፋተኛ የመባሉን አግባብነትና አጠቃላይ ቅጣት አጣጣሉን በመመልከት አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በዚሁ መሠረት ወደ ተያዙት ጭብጦች ስንመለስ፡- 1ኛ እና 2ኛውን ክስ በተመለከተ በእርግጥ በወ.መ.ሕ.ቁ 692/1/ ሥር ስለማታለል የተሠጠውን ትርጉም በምናይበት ጊዜ "…….የማይገባ ብልፅግና ለራሱ ለማስገኘት ወይም ለሌላ ሠው ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር ፣ የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሠወር ወይም መግለፅ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሠው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም ፣ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላውን ሰው አታሎ የራሱን ወይም የሶስተኛ ወገን የንብረት ጥቅም የመጉዳት አድራጎት እንዲፈፀም ያደረገ እንደሆነ……" በሚል ይደነግጋል፡፡

አሁን በቀረበው ክርክር ላይም የቀረበው ክርክር የተፈፀመ የማታለል አድራጎት የለም፣ ቼኩ በሚሠጥበት ጊዜ በቂ ስንቅ እንደሌለው ተበዳዩም ያውቅ ነበር ገንዘብ ከደንበኞች ተሰብስቦ

እስኪሠጠው ድረስ ለመያዥ የተሠጠ እንጅ ባንክ ቤት ቀርቦ እንዲመነዘር አይደለም የሚል ከመሆኑ አኳያ ተበዳይን መሠረት ያደረገ ማታለል የተፈፀመ ስለመሆኑ ከላይ ከተመለከተው የሕግ ድንጋጌ አኳያ ጥያቄ ውስጥ ሊገባ ይችል ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን የወ.መ.ሕግ ቁ 693/1/ን በምንመለከትበት ጊዜ ርዕሱ " የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት" የሚል ሲሆን በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ ሥር የተደነገገው 693/1/ ማንም ሰው ቼክ በሚያወጣበት ወይም ቼኩ ለባንክ በሚቀርብበት ጊዜ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ ያለመኖሩን እያወቀ ቼክ ያወጣ /የሰጠ / እንደሆነ በሚል ተደንግጓል፡፡ ይሄንን ስለቼክ የሚደነግገውን የወንጀል አንቀጽ ስንመለከት በወንጀለኛ መቀጫ ሕግ ቁ 692/1/ ሥር ከላይ የተመለከተውን የወንጀሉን አፈፃፀም ከግል ተበዳይ/ተታሎአል/ ከሚባል ግለሰብ አኳያ ያልታዬ መሆኑን ነው፡፡ ይሄ ማለት ደግሞ በተለይም የቼክ ሠነድ ለአምጭው ወድያውኑ የሚከፍል እና በንግድ ሕጉ ከተቀመጡት ውስን መቃወሚያዎች ውጪ ሊቀርቡበት የማይገባ በመሆኑ በቼክ አውጪው ላይ ኃላፊነት የጣለ ይመስላል፡፡ ይሄም ማለት ከላይ የተመለከተው የወ.መ.ሕግ ንባብ አንድ ቼክ ያወጣ /የሠጠ/ ሰው በቂ ስንቅ መኖርን ማረጋገጥ እንዳለበትና ቼኩ በተሠጠበት ጊዜ ወይም ለክፍያ በቀረበበት ጊዜ በቂ ስንቅ ያለመኖሩ ብቻ የተጠቀሰውን የወንጀል ኃላፊነት እንደተቋቋመ የሚቀበለው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ አኳያ የግል ተበዳዩ በየትኛውም ተቋም በወንጀል ክስ ያልመሠረተ መሆኑ ሆኖም ግን ቼኩን ለክፍያ ሲያቀርበው በቂ ገንዘብ የለውም ተብሎ መመለሱ እስከተረጋገጠ ድረስ ሕግ አውጪው ደግሞ ቼክን በተመለከተ የተደነገገዉ የማታለል ወንጀል እስከ ተሚላ ድረስ ከኃላፊነት ነፃ ሊያደርገው አይችልም ፡፡

በሌላ በኩል ቼኩ የተሠጠው ለባንክ ቀርቦ እንዲመነዘር ሣይሆን ለዋስትና የተሠጠ ነው በማለት የቀረበውን ክርክር ስንመለከተው ከዚህም ጋር ተያይዞ ከዚህ በፊት ይሄ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ.ቁ 24435 በሆነ መዝገብ ቼክ በዋስትና መያዝ እንደሚቻል የሕግ ትርጉም ሠጥቶበታል በማለት ተያያዥ ክርክር ቀርቧል፡፡ ይሄንን በተመለከተ ቀድሞ የሕግ ትርጉም ተሠጥቶበታል የተባለው መዝገብ አንድ ቼክ ለክፍያ ሲቀርብ /ገንዘብ ስጠየቅ ለቀረቡበት ከሚችሉት መቃወሚያዎች አንድ የግል ግንኙነት /personal Relation/ መኖር ስለመሆኑ በፍትሕብሔር ክርክር ላይ የተያዘ አቋም እንጅ አሁን እየታየ ካለው የወንጀል ኃላፊነት አኳያ ቀጥታ ግንኙነት ያለው ባለመሆኑ ፣ የተባለውም የግል ግንኙነት ከላይ ከተመለከተው የወንጀል ኃላፊነት አኳያ አላፊነቱን ቀሪ የሚያደርግበትን አግባብ ያስረዳ /ያመለከተ/ባለመሆኑ አልፈነዋል፡፡

የአመልካች ኃላፊነት መታየት ያለበት በወ/መ/ሕግ ቁ 693/1/ ወይስ 693/2/ ሥር የሚለውን በተመለከተ ባንክ ቤት የነበረው ሂሣብ የተዘጋው በተደጋጋሚ በቂ ስንቅ ሣይኖር ቼክ በመሠጠቱ ባለው መመሪያ መሠረት የሂሣብ ቁጥሩ መዝጋቱን ያመለከተና ይሄንንም የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ረገድ ያረጋገጡት በመሆኑ በቸልተኝነት የተሠጠ ነው የሚያሠኝ አይደለም ፡፡

1ኛ እና 2ኛው ክስ የተሠራው በአንድ የወንጀል ሐሣብ ነው በሚል የተነሣውን ክርክር በተመለከተ የተፈፀመው በአንድ ቀን ልዩነት ከመሆኑም በላይ የተሠጠበት ዓላማም ለተለያዩ ይሄውም የድርጅቱን ደረጃ ለማሣደግና ለዕዳ መክፈያ በሚል በመሆኑ በአንድ የወንጀል ሃሣብ የሚያሠኝ ሣይሆን በወ.መ.ሕግ ቁ 62 መሠረት በአዲስ ሃሣብ እንደሠራው ይቆጠራል፡፡

ሶስተኛውን ክስ በተመለከተ በቼኩ ላይ የተፈረመው ፊርማ የተበዳይ አለመሆኑ በቴክኒክ ምርመራ የተረጋገጠ በመሆኑ ፈራሚው ማን ሊሆን ይችላል? የሚለው ነጥብ መታየት አለበት፡፡

በዚሁ መሠረት ቼኩን የተቀበለው ሰው ለፍርድ ቤት ቀርቦ በሠጠው የምስክርነት ቃል ቼኩን የሠጠው አመልካች እንደሆነ ፣ ቀድሞ የተፈረመበት እንደሆነና ቀኑ እንዲያጥርለት አመልካችን እንደጠየቀና በጠየቀው መሠረት ቀኑን አሣጥሮ ፖራፍ አድርጎበት የሠጠው መሆኑን መስክሯል፡፡ በዚህ ቼክ ላይ የቴክንክ ምርመራ ሲደረግ ቢያንስ ፖራፍ የተደረገው እንኳ የአመልካች ፊርማ ስለመሆኑ ያልተመለከተ በመሆኑና የበታች ፍ/ቤትም አመልካች የተበዳዩን ፊርማ አስመስሎ ፈርሟል የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ ይሄ ደግሞ የማስረጃ ምዘና በመሆኑ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የደረሰበትን መደምደሚያ መቀበሉ ተገቢ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና አዋጅ ቁ 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ማረም እንጂ ማስረጃን መመዘን ባለመሆኑ በሌላ በኩል አመልካች የተበዳዩን ፊርማ አመሣስሎ ፈርሟል ወይስ አልፈረመም? የሚለው ደግሞ የማስረጃ ምዘና በመሆኑ ነው፡፡

ባጠቃላይ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሠጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ቅጣትን በተመለከተ የአመልካች ቀድሞ ባህርይ መልካም መሆኑ፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑና በበርካታ ማህበራዊ አገልግሎቶች ተሣታፊ መሆኑ ከግምት ውስጥ በማስገባት የተላለፈ በመሆኑ ከዚህም አኳያ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የተላለፈበት የጥፋተኝነት ውሣኔና ቅጣት መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

በዚህ መሠረት ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሠጥተናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 55773 በቀን 20/5/2003 ዓ.ም እና በመዝ.ቁ 55897 በቀን 30/6/2003 እና ሚያዝያ 10 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጠው ፍርድ እና ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ቁ 195/2/ /ለ/2/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በአመልካች ላይ የሠጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔ የሚነቀፍበት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 59356

ሰኔ 03 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች ፡-** ፌዴራል ዐቃቤ ህግ - ዐ/ህግ አበባው መንግስቱ ቀረበ፡፡

**ተጠሪ ፡-** በሪሁን ፍቃዱ - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ የመሰረተው የወንጀል ክስ ተጠሪ በ1996 ዓ/ም በወጣው የወ/ህ/አንቀጽ 540 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ መስከረም 15 ቀን 2002 ዓ.ም ከሌሊቱ በግምት 8፡30 ሲሆን በቂ/ክ/ከተማ ቀበሌ 02/03 ልዩ ቦታው "ኤልሲባር" አካባቢ ሟች ከድር አብዱልቃር ያሽከረክር ከነበረው መኪና ሲወርድ ልትገጨን ነው እንዴ በማለት የሟችን ግንባር በቦክስ መትቶ ከጣለው በሁዋላ በወደቀበት ግንባሩንና ሆዱን ደጋግሞ በመረጋገጥ በብርጭቆ ጭንቅላቱን በመምታት ለከፍተኛ ጉዳት በመዳረግ ከጥቂት ሰዓታት በኂላ ሕይወቱ እንዲያልፍ በማድረጉ ተራ የሆነ ሰው ግድያ ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም የዐቃቤ ሕጉን ክስ በመካዱ ዐቃቤ ሕግ እንደክሱ ሊያስረዱ የሚችሉ ማስረጃዎች ያሉት መሆኑን ገልጾ ማስረጃዎቹ ከተሰሙ በሁዋላ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ድርጊቱን መፈፀሙ ተረጋግጦበታል በሚል ምክንያት እንዲከላከል አድርጎ የመከላከያ ምስክሮች እንዲያሰማ መብቱን ጠብቆለት የመከላከያ ማስረጃዎቹን አሰምቷል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን በመከላከያ ማስረጃዎቹ ያላስተባበለ መሆኑን ዘርዝሮ የመከላከያ ማስረጃዎቹን ቃል ውድቅ ከአደረገ በሁዋላ ተጠሪን በዓቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበበት ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጎ በ3/ሦስት/ አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡ በተጠሪ ላይ በተላለፈው የቅጣት ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የቅጣት ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በቁጥር 3-9590/02 በቀን 11-12-2002 ዓ.ም በተፃፈ 5/አምስት/ ገፅ የሰበር አቤቱታ የበታች ፍርድ ቤቶች በቅጣት አወሳሰን ረገድ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ፈፅመዋል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርቧል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪ ጥፋተኛ ከተባሉት ድንጋጌ

መነሻ ቅጣት ወርዶ ቅጣት መስጠቱ የወ/መ/ሕ/ቁጥር 189/1/ ድንጋጌን ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም ተጠሪ ጥፋተኛ ከተባሉበት ድንጋጌ መነሻ ቅጣት ዝቅ ተደርጎ በሦስት ዓመት ፅኑ እስራት ቅጣት መቀጣታቸው ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የበታች ፍርድ ቤቶች የቅጣት አወሳሰን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት ወይስ የለበትም? የሚለው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ሟች ከድር አብዱልቃድር ያሽከረክር ከነበረው መኪና ሲወርድ “ልትገጨን ነው እንዴ?“ በማለት የሟችን ግንባር በቦክስ መትቶ ከጣለው በሁዋላ በወደቀበት ግንባሩንና ሆዱን ደጋግሞ በመረጋገጥ በብርጭቆ ጭንቅላቱን በመምታት ለከፍተኛ ጉዳት በመዳረግ ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ህይወቱ እንዲያልፍ ማድረጉ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ለወንጀል ድርጊቱ መፈፀም ወይም መሰራቱ እንዲሁም ድርጊቱን የፈጸሙት ወይም የሰሩት ተጠሪ መሆናቸው በሚገባ መልኩ እና በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23 ስር በተመለከተው ድንጋጌ መሰረት የተረጋገጠ ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት በመገንዘብ በቅጣቱ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ሕጋዊነት ተመልክተናል፡፡

የአመልካች መሠረታዊ ክርክር የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ ከሚያስቀጣው ድንጋጌ መነሻ ቅጣት ዝቅ በማለት የሰጡት የሦስት አመት ፅኑ እስራት ቅጣት በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ጉዳዮችና የቅጣት አወሳሰኑን በተመለከተ የወንጀል ህጉ ያስቀመጣቸውን መርሆዎች ያላገናዘበ ነው የሚል ነው፡፡ እኛም ይህንኑ ቅሬታ ከህጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

በመሠረቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ የአገሪቱን የወንጀል ህግ ግብ በአዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀጽ 1 ስር ሲደነግግ “የወንጀል ህግ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለ ወንጀሎችና ስለ ቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ ነው“ በማለት ያስቀምጣል፡፡ ህጉ በአንቀጽ 87 ላይ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ህጉ ሊደርስበት ያሰበውን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በህጉ መንፈስ መሠረት መፈፀም እንዳለበቸው በመርህ ደረጃ ይደነግጋል፡፡ ይኸው አንቀጽ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎቹ ምንጊዜም ሰብዓዊ ክብርን በሚጠብቅ መንገድ መፈፀም እንደሚኖርባቸው ያስገነዝባል፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 88 ሲታይም የቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሳሰንን በተመለከተ ዝርዝር ያሉ ንዑስ ድንጋጌዎችን አካቶ ይዟል፡፡ በዚህ አንቀጽ ስር ያሉ ንዑስ አንቀጾች የሚያሳዩት ፍርድ ቤቱ ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን የሚወስነው የወንጀል ህጉን ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎችን እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለ ቅጣታቸው

የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ መሆኑን፣ ቅጣት ሲወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ ያነሳሱትን ምክንያቶችና የሃሣቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ህግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስንና የቅጣት አወሳሰን ትክክለኛነትና አንድ ወጥነት ለማረጋገጥ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ (manual) እንደሚወጣ የሚያስገነዝቡን ናቸው፡፡

ከላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንረዳው አቢይ ነጥብ ቅጣቶች መወሰን ያለባቸው የህጉን መንፈስ በመከተል ዓላማዎችና ግቦቹንም ተፈፃሚ በማድረግ ሀሣብ መሆኑን ነው፡፡ የህጉን መንፈስ ከመተግበር አኳያ ወንጀለኛውን ማዕከል የማድረግ ፅንሰ ሀሣብ አፅንኦት የተሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ ዳኞች በፅንሰ ሀሣቡ መሠረት የተሰጣቸውን አመዛዝኖ የመወሰን ስልጣን (Discretion) በስራ ላይ ሲያውሉ ሰብአዊ ክብርን ከማስጠበቅ ዓላማ ጋር መሆን ያለበት ከመሆኑም በላይ ህግ አውጪው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 87 እና 1 ስር የተመለከቱትን መሠረት በማድረግ ዳኞች የቅጣት ውሣኔ በምን መንገድ መወሰን እንደሚገባቸው በአንቀጽ 88 ስር አስቀምጧል፡፡ በወንጀል ህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ስንመለከትም ዳኞች ከተሰጣቸው የቅጣት ክልል ሳይወጡ የአጥፊውን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ቅጣት እንዲወስኑ ህጉ ስልጣን የሰጣቸው መሆኑ ነው፡፡ ዳኞች አጥፊውን በተመለከተ ከግምት ውስጥ ሊያስገቡዋቸው የሚገባቸው በርካታ የአጥፊ፣ ሁኔታዎች ቢኖሩም የቅጣት አወሳሰናቸው መሠረት የሚያደርገው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን /degree of individual guilt/ ስለመሆኑ የአንቀጽ 88/2/ ድንጋጌ ይዘትና አቀራረፅ ያስረዳል፡፡ ይህም በሕጉ አግባብ የወጣውና ከግንቦት 09 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ ተግባራዊ የሆነው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ እንደተጠበቀ ሁኖ በቅጣት አወሳሰን ወቅት ዳኞች ሰፊ ስልጣን ያላቸው መሆኑን ጠቋሚ ነው፡፡ አንቀጽ 88/2/ በመጀመሪያ ደረጃ የወንጀል አድራጊውን የአደገኛነት መጠን መሠረት በማድረግ ዳኞች ቅጣት እንዲወስኑ ማድረጉና ይህንን ሲወስኑም በድንጋጌው የተመለከቱትን የወንጀሉን አፈፃፀም የአጥፊውን ያለፈ የህይወት ታሪኩን እና የኑሮ ሁኔታ ከግምት በማስገባት በማመዛዘን ለወንጀለኛው የሚገባውን የቅጣት መጠን እንዲወስኑ መደንገጉ የቅጣት ውሣኔዎችንና እርምጃዎችን እየተራራቁ እንዳይወስኑ የማድረግ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ከመታሰቡም በተጨማሪም ችግሩ የሚቀረፍበትና የሚቀነስበትን ሥርዓትም ህጉ ዘርግቷል፡፡ ዳኞች ቅጣት ሲወስኑ በህጉ አንቀጽ 88/2/ ለአጥፊው ተገቢ ነው ያሉትን ቅጣት ከወሰኑ በኋላ በህጉ የተመለከቱትን የማቅለያና የማክበጃ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ቅጣቱን ከፍ ወይም ዝቅ ለማድረግ የሚችሉ ስለመሆኑ ህጉ ያሳያል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ህግ በአንቀጽ 82/1/ ከፊደል /ሀ/ እስከ ፊደል /ሠ/ ድረስ ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን ካስቀመጠ በኋላ በአንቀጹ ንዑስ ቁጥር ሁለት ስር በንዑስ ቁጥር አንድ ስር የተመለከቱት የማቅለያ ሁኔታዎች በህጉ ልዩ ክፍል ተካተው ሲገኙ በድጋሚ በማቅለያነት ዳኞች እንዳይጠቀሙ ያሳስባል፡፡ የህጉ አንቀጽ 84 ደግሞ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን የዘረዘረ ሲሆን ዳኞች የህጉን አንቀጽ 183 ባገናዘበ መልኩ ቅጣት የሚያከብዱባቸውን ሁኔታዎች ያሳያል፡፡ ዳኞች ቅጣትን የሚቀንሱትም ሆነ የሚያከብዱት ተገቢ ሁኖ ሲገኝ ስለመሆኑ የአንቀጽ 179 እና 183 ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ አንቀጽ 179 የቅነሣውን ገደብ የሚያሳይ ሲሆን ከዚህ መደበኛ ቅነሣ በተጨማሪ ልዩ ቅነሣ ለማድረግ እንደሚቻልም ህጉ በአንቀጽ 180 ስር አስቀምጧል፡፡ በህጉ

አንቀጽ 86 ቅጣትን በማቅለልም ሆነ በማክበድ ረገድ ከህጉ አንቀጽ 179፣ 182 ውጪ የሆኑ ምክንያቶች ሲያጋጥማቸው ዳኞች ምክንያታቸውን በመግለፅ ቅጣቶችን ለመቀነስ ወይም ለማክበድ እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡ እነዚህ ስለቅጣት አወሳሰን በህጉ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ሲታዩ የሚያስገነዝቡን አቢይ ነጥብ ቅጣቶችን በመጣልና እርምጃዎችን በመውሰድ ረገድ ዳኞች አመዛዝነው የመወሰን ከፍተኛ ስልጣን ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ እንግዲህ ህጉ ለዳኞች የሰጠውን አመዛዝኖ የመወሰን ስልጣን ተግባራዊ የሚሆንበትን ሁኔታና በሕጉ የሰፈረውን የቅጣት አጣጣል መርህ ከላይ ተመልክተናል፡፡ ዐ/ህግ በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ቅሬታ ስንመለከተው ከመነሻው ቅጣቱ እንዲወርድ የተደረገው ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሳይኖርና እና የቅጣት ማቅለያው አለ ቢባል እንኳ የወንጀሉ ማቋቋሚያ የሆነው ነገር ስለመሆኑ ጠቅሶ መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን ስንመለከተው የስር ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ቅጣቱን ሲጥል በማቅለያነት የያዘው ድርጊቱ በድንገተኛ አጋጣሚ መፈጸሙን፣ በተጠሪ ላይ ሪኮርድ ያለመቅረቡንና በወቅቱ የነበረው ያልተገባ የሚች መኪና አነዳድ የፈጠረው ጫና ነው የሚሉትን ምክንያቶችን ነው፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪ የተከሰሱትና ጥፋተኛ የተባሉት ተራ በሆነ የሰው ግድያ ወንጀል ሲሆን ድርጊቱ በድንገት የተፈፀመ ነው የሚለው ምክንያት ተጠሪ የተከሰሱበትን የወንጀል ድርጊት የሚያቋቁም ነው ከሚባል በስተቀር በቅጣት ማቅለያነት በድጋሚ ሊወሰድ የሚችል ሕጋዊ ምክንያት አይደለም፡፡ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠውን የወንጀሉን ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር ፍ/ቤቱ ይዞ በቅጣት ማቅለያነት መወሰዱም የወንጀል ህጉ በአንቀጽ 82/2/ ስር ያስቀመጠውን መርህ የሚጻረር ሲሆን ይኸው ሕግ በአንቀጽ 86 ስር ለዳኞች የሰጠውን ስልጣንም መሰረት ያደረገ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡

ፍርድ ቤቱ በወንጀል ህጉ ቁጥር 540 ስር የተመለከተውን መነሻ ቅጣት ተገቢ መስሎ ሲታየው በህጉ አንቀጽ 108/1/ የተመለከተውን የፅኑ እስራት ቅጣት መነሻ ሳይወርድ ማቅለል የሚችል ስለመሆኑ የአንቀጽ 179/ሐ/ ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ከዚህ በህጉ ለዳኞች ከተሰጠው ስልጣን አኳያ ተገቢነት ያለው ውሳኔ ተሰጥቷል ሊባል የሚችለው በጠቅላላ ወይም ልዩ ቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ስር የሚወድቁና የወንጀሉ ማቋቋሚያ ያልሆኑ ማቅላያ ምክንያቶች መገኘታቸው ሲረጋገጥ ነበር፡፡ በተያዘው ጉዳይ ድርጊቱ በድንገተኛ አጋጣሚ የተፈፀመ ነው የሚለው ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት የወንጀል ድርጊቱ መቋቋሚያ ከሚሆን በስተቀር በወ/መ/ሕጉ አንቀጽ 82/2/ እንደተመለከተው በድጋሚ በቅጣት ማቅለያነት ሊያዝ የሚችል አይደለም፡፡ በዚህ ምክንያት የቅጣት ማቅለያ አይሆንም እንጂ ይሆናል ቢባል እንኳ ተጠሪ ሚችን ለሕልፈተ - ሕይወት ሲዳርግ የድርጊቱ አፈፃፀም ከባድ የነበረ መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልፅ የሚያሳይ በመሆኑ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባሉት ድንጋጌ ሊያስቀጣ ከሚችለው መነሻ ቅጣት መውረድም ሆነ መነሻ ቅጣቱን ለመጣል የሚያስችል ሕጋዊና በቂ ምክንያት አይደለም፡፡ ስለሆነም ድርጊቱ በድንገተኛ አጋጣሚ የተፈጸመ ነው የሚለው ምክንያት በቅጣት ማቅለያነት መወሰዱ ከድርጊቱ አፈፃፀም አንጻር ሲታይ የበታች ፍርድ ቤቶች በህጉ ለዳኞች የሚሰጠውን አመዛዝኖ የመወሰን ስልጣንን ሲጠቀሙ በቅጣት አወሳሰን ረገድ ህጉ ያስቀመጣቸውን መሠረታዊ መርሆዎች በተለይም በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 82/2/ እና 189 ስር የተመለከቱትን፤ ጥሰው መገኘታቸውን የሚያሳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡ ተጠሪ የወንጀል ሪኮርድ የሌለባቸው መሆኑም ቅጣቱን ከመነሻው ለመውረድ የሚያስችል አይደለም፡፡ ሲጠቃለልም በተጠሪ ላይ የተጣለው ቅጣት የወንጀል ሕጉን መሰረታዊ ግብና ዓላማ እንዲሁም የቅጣት አወሳሰን መርሆዎች ከድርጊቱ አፈጻጸም ጋር ያገናዘበ ባለመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡



www.chilot.me

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ. 87623 ሚያዝያ 22 እና 26 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 56605 ሐምሌ 09 ቀን 2002 ዓ.ም የጸናው ውሳኔ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2//መ/ መሠረት ተሻሽሎ ተጠሪ ሊቀጣ የሚገባው በጉዳዩ ላይ የታሰረው የሚታሰብለት ሁኖ በአስር አመት ጽኑ እስራት ነው በማለት ወስነናል፡፡
2. ውሳኔው የተሻሻለ መሆኑን አውቆ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለማ/ቤቱ ይፃፍ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 57938

ሐምሌ 14/2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** 1- አቶ አደም አብዱ } የቀረበ የለም

2- አቶ ጀማል አሊ

**ተጠሪ፡-** የፌደራል ሥነ - ምግባርና ፀረ - ሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ሕግ

ዋልተንጉስ ፍቅሬ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አመልካቶች በተከሠሡበት የሙስና ወንጀል የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ መካከል የነበረውን የቅድመ ክስ ክርክር ሂደት ከሠማ በኂላ ወደ ዋና ክስ እንዲገባና የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች እንዲሠሙ የመወሰኑን እና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይሄንኑ ትዕዛዝ የማፅናቱን አግባብነት ለመመርመር የቀረበ ነው፡፡

አመልካቾች ቅሬታቸውን ከሌሎች 3ኛ እና 4ኛ አመልካቾች ከነበሩት እና ጉዳያቸው አያስቀርብም ከተባሉት ጋር ያቀረቡ ሲሆን ሰኔ 23 ቀን 2002 ዓ.ም በ3 ገፅ በተፃፈ አቤቱታ የአሁን አመልካቾችን የሚመለከተው ክፍል ፍሬ ሃሣብ ከሣሽ የአሁን አመልካቾችን ከገቢያቸው በላይ ንብረት አፍርተዋል በማለት ስለተከሣሾቹ የያዘው የሀብት ማስረጃ ሣይኖር በወ/መ/ሕግ ቁ 419/ለ/ መሠረት ክስ ማቅረቡ ያለአግባብ ነው በሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በቀን 21/4/2003 ዓ.ም በሁለት ገፅ የሠጠው የመልስ ፍሬ ሃሣብ አመልካቾች የሉሲ አንጅነሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር አባል ብቻ ሣይሆኑ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ውስጥ ባላቸው ኃላፊነት በመጠቀም ማህበሩ ያለአግባብ ጨረታዎቹን እንዲያሸንፍ አድርገዋል፡፡ ከገቢያቸው ጋር ያልተመጣጠነ ንብረት አፍርተዋል በማለት የከሰሰ ሲሆን ወደ ክሱ ሲገባ በማስረጃ ነጥሮ የሚወጣ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ወደ ዋና ክስ እንድንገባ መወሰኑ በአግባቡ በመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ

መርምሮታል፡፡ በዚሁ መሠረት የወንጀል ጉዳዩን እየተመለከተ ያለው ፍርድ ቤት የቅድመ ክሱን ክርክር በመስማት ወደ ዋናው ክስ ተገብቶ ምስክር እንዲሠማ መወሰኑ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ተይዞ የተያዘው ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህ መሠረት በሙስና ወንጀሎች ላይ የቅድመ ክስ ዝግጅት የሚመራበት አግባብ በአዋጅ ቁ 434/97 አንቀጽ 35 እስከ 41 ድረስ የተዘረዘሩ ሲሆን ሂደቱ ውስጥ ማለፍ አስገዳጅ ያልሆነና እንደ ክሱ ዓይነት ታይቶ የክሱ ጭብጦችና ማስረጃው ዝርዝር ውስብስብ በመሆኑ የፍርድ ሂደቱን ሊያራዝምና ሊያወሣስብ ይቻላል ብሎ ፍርድ ቤቱ ሲገምት ሊያዝ የሚችል ስለመሆኑ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 35 በግልፅ ያስቀምጣል፡፡

የቅድመ ክስ ዝግጅት ዓላማ ለክሱ አወሣሠን ሊረዱ የሚችሉ ጭብጦችን ለመለየት ፣ ባለጉዳዮች ጭብጦችን እንዲረዱ ማድረግ ፣ የክሱን ሂደት ለማፋጠንና ችሎቱ አካሄዱን ለመምራት እንዲችል ለማስቻል ስለመሆኑ በአዋጅ ቁ 434/97 አንቀጽ 36/1/ ሥር የተዘረዘረ ሲሆን የማስረጃዎች ተቀባይነት ላይ እና መደበኛው ክስ ከመጀመሩ በፊት ውሣኔ ሊያገኙ በሚገባቸው የህግ ጥያቄዎች ላይ ውሣኔ የሚሠጥ ስለመሆኑ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 36/2/ ሥር ተደንግጓል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካቾች ከገቢያቸው በላይ ንብረት አፍርተዋል በማለት የተከሠሡ በመሆኑ ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤት የቅድመ ክሱን ሂደት ካዳመጠ በኋላ ወደ ዋና ጉዳዩ ተገብቶ ምስክሮች ይሠሙ በማለት ትዕዛዝ መስጠቱ በአመልካቾች ላይ ከቀረበው ክስ አኳያ ሲታይ የተከሠሱበት ጉዳይ በማስረጃ የሚጣራ ከመሆኑ አኳያ ተፈፀመ ሊባል የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም፡፡ በተጨማሪም በዚህ ቅድመ ክስ ዝግጅት ሂደት ውስጥ መታለፍ ራሱ አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ የተቀመጠ ባለመሆኑና ፍርድ ቤቱ የጉዳዩን ውስብስብነት እየተመለከተ የሚወሰነው ጉዳይ በመሆኑ የቀረበው የወንጀል ክስ በማስረጃ እንዲጣራ መታዘዙ ቅሬታ የሚቀርብበት ሊሆን አይገባም ብለናል፡፡ በዚሁ መሠረት የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ዋና ክስ ተገብቶ ምስክሮች ይሠሙ በማለት የሠጠው ብይን እና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሠጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 54774 ሰኔ 11 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 85874 መጋቢት 09 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጡት ውሣኔ በተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና ማስረጃ ህግ አዋጅ ቁ 434/97 አንቀጽ 40 መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የቅድመ ክስ ዝግጅት ሂደት እንደተጠናቀቀ በወንጀል ክሱ የተመለከቱት ነጥቦች ላይ ምስክሮች እንዲሠሙ መታዘዙ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 63344

ሐምሌ 28 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች ፡-** የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሥነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን አልቀረቡም

**ተጠሪዎች ፡-** 1. ላሉ ሰይድ አከልታ - አልቀረቡም

2. ከማል ሁሴን ዳልቦ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ህዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የዋስትና ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታያው የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪዎች የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 676 ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ ከባድ የእምነት ማጉደልና የሙስና ወንጀል ፈጽመዋል በማለት የወንጀል ክስ አቅርቦባቸዋል፡፡

ተጠሪዎች የዋስትና መብታቸው ተጠብቆ ክርክሩን እንድንቀጥል ይፈቀድልን በማለት አመልክተዋል፡፡ አመልካች ተጠሪዎች የተከሰሱበት የሙስና ወንጀል ከአምስት ዓመት እስከ ሀያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንደሚያስቀጣ የተደነገገ በመሆኑና ከአስር ዓመት በላይ በሚያስቀጣ የሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው የዋስ መብት እንደማይፈቀድለት በአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 የተደነገገ በመሆኑ በዋስትና ወረቀት ሊለቀቁ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4ን በመጥቀስ ተጠሪዎች በማረሚያ ቤት ሆነው እንዲከራከሩ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪዎች የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 ከአስር ዓመት በላይ በሚያስቀጣ የሙስና ወንጀል የተከሰሰ የሚለው ሀረግ አስር ዓመት ዝቅተኛው የቅጣት መነሻ ወይም ከፍተኛ የቅጣት ጣሪያን መሠረት በማድረግ እንደሚወስን ግልጽነት የጐደለው ነው፡፡ ተጠሪዎች የተከሰሱበት የወንጀል ህግ ድንጋጌ ዝቅተኛው መነሻ አምስት ዓመት ከፍተኛው ጣሪያ ሀያ አምስት ዓመት በመሆኑ ተጠሪ ሌላ ዋስትና የሚያስከለክል ተጨማሪ ምክንያት ያላቀረበ ስለሆነ በዋስትና ወረቀት ሊለቀቁ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች የሰበር



www.chilot.me

አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ታህሣስ 11 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ከአርሶ አደር በደረሰኝ የሰበሰቡትን ገንዘብ አንደኛ ተጠሪ ብር 382,895.01 ለመንግስት ገቢ ሣያደርጉ ከባድ የዕምነት ማጉደል ወንጀል የፈጸሙ መሆናቸዉን ሁለተኛው ተጠሪ ከሰበሰቡት ግብር ብር 333,940.91 ለመንግስት ገቢ ባለማድረጋቸዉ ከባድ የዕምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽመዋል በማለት የወንጀል ህግ አንቀጽ 676 ንኡስ አንቀጽ 1ን በመጥቀስ ክስ አቅርበናል፡፡ ከአስር ዓመት በላይ በሚያስቀጣ የሙስና ወንጀል የተከሰሰ ተከሣሽ በዋስትና ወረቀት የማይለቀቅ መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ይህንን ድንጋጌ በተመሣሣይ መንገድ በመተርጎም ተጠሪዎች በዋስ እንዲለቀቁ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች የፍርድ ቤቱ መጥሪያ ደርሷቸው በቀነ ቀጠሮው መልስ ይዘው ያልቀረቡ በመሆኑ መልስ የመስጠት መብታቸዉ ታልፏል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ተጠሪዎች በዋስትና ወረቀት እንዲለቀቁ የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን የአዋጅ 434/97 አንቀጽ 4 መሠረታዊ ይዘትና የዚህን ድንጋጌ ተግባራዊ ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ ፍርድ ቤቶች ሊከተሏቸው የሚገባቸዉ የህግ አተረጓጐም መሠረታዊ መርሆችን ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ የአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 ንኡስ አንቀጽ 1 በሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው በዋስ እንዲለቀቅ ለፍርድ ቤት ማመልከት ይቻላል፡፡ ሆኖም የተከሰሰበት ወንጀል ከአስር ዓመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና መለቀቅ አይችልም በማለት ይደነግጋል፡፡ ድንጋጌው የዋስትና መብት ለተከሣሽ ፍርድ ቤቶች ሊፈቅዱ የማይችሉበትን ሁኔታ አስገዳጅ በሆነ መንገድ የሚደነግግ ነው፡፡

ድንጋጌው ከአስር ዓመት በላይ በሚያስቀጣ የሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው በዋስትና ወረቀት መለቀቅ እንደማይፈቀድለት ይደነግጋል፡፡ ተከሣሹ የከሰሰበት ወንጀል ከአስር ዓመት በላይ የሚያስቀጣ መሆኑን ወይም ከአስር ዓመት በላይ በእስራት የማያስቀጣ መሆኑን ለመወሰን ፍርድ ቤቶች ተከሣሹ የተከሰሰበት የህግ ድንጋጌ የሚደነግገውን ዝቅተኛውን የመነሻ ቅጣት ነው መሠረት የሚያደርጉት ወይም ተከሣሹ በተከሰሰበት ወንጀል በህጉ የተደነገገውን ከፍተኛውን የቅጣት ጣሪያ የሚለውን ነጥብ ለመተርጎም በመጀመሪያ የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ ምግባርና ልዩ የማስረጃ ህግ በልዩ ሁኔታ መደንገግ ያስፈለገበትን ምክንያትና የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ህግን በማወጅ ህግ አውጭው ሊያሳካው የፈለገውን ግብ መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡ ህግ አውጭው የሙስና ወንጀል ያለውን ልዩ ባህሪ ግምት ውስጥ በማስገባት ሙስናን ለማጋለጥ ሙስናን ለመመርመርና የሙስና ክስን ውጤታማ ለማድረግ በማሰብ የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ በመሆኑ በአዋጅ መግቢያ ላይ ግልጽ አድርጓል፡፡ ስለሆነም የአዋጁ ድንጋጌዎች ትርጉምና ተግባራዊ አፈጻጸም ይህንን የህግ አውጭውን መሠረታዊ ግብ የሚያሣካ በሚሆንበት መንገድ መተርጎምና ስራ ላይ ማዋል ፍርድ ቤቶች ሊከተሉት የሚባው አተረጓጐም መርህ ነው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 ድንጋጌ በልዩ ሁኔታ አሁን ያለውን ቅርጽና ይዘት እንዲኖረው ተደርጐ የተደነገገበትን መሠረታዊ ምክንያት ማየት ያስፈልጋል፡፡ አዋጅ ቁጥር 434/97 በአዋጅ ቁጥር 236/93 እና አዋጅ ቁጥር 239/93 የታወጀውን የፀረሙስና ልዩ የሥነ ሥርአት ሕግ የማስረጃ ህግ ለማሻሻል የወጣ የህግ ማእቀፍ ነው፡፡ የአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 በአዋጅ ቁጥር 239/93 አንቀጽ 2 በሙስና ተጠርጥሮ የተያዘ ማናቸውም ሰው የዋስትና መብት አይኖረውም በማለት የተደነገገውን ለማሻሻል ታስቦ የተደነገገ ድንጋጌ ነው፡፡ ድንጋጌው ዓላማ ሁሉንም በሙስና ወንጀል የተከሠሱ ሰዎች የዋስ መብት በህግ ከመከልከል ይልቅ የተከሠሱበት ወንጀል የሚያስከትለውን ከፍተኛውን የቅጣት ጣሪያ መሠረት በማድረግ በቀላል የሙስና ወንጀል የተከሰሰና ከአስር ዓመት በታች በሚያስቀጣ የሙስና ወንጀል የተከሰሱት በዋስትና የሚለቀቁበትና የዋስትና መብታቸው የሚጠበቅበትና በከባድ ሙስና ወንጀሎች የተከሰሱትና የተከሰሱበት ወንጀል ከዓስር አመት በላይ የሚያስቀጣ በሆነ ጊዜ በማረሚያ ቤት ሆነው እንዲከራከሩ ለማድረግ ታስቦ የወጣ ድንጋጌ መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 434/97 ሀተታ ዘምክንያት በግልጽ የሚያሳይ በመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 434/97 ንዑስ አንቀጽ 4 ድንጋጌ ከዚሁ አንፃር መተርጉምና ተፈፃሚ መሆን የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በሶስተኛ ደረጃ የአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 ድንጋጌ ውጤታማ በሚሆንበት መንገድ መተርጐምና ሥራ ላይ መዋል ይኖርበታል፡፡ በወንጀል ህጉ በአንቀጽ 404 ንዑስ አንቀጽ 4 የሙስና ወንጀል እንደሆኑ የተዘረዘሩት የወንጀል ድንጋጌዎች በአብዛኛው ዝቅተኛው የመነሻ ቅጣት ከአስር ዓመት በታች እንደሆነ የድንጋጌዎቹን ይዘትና የሚያስከትሉትን አነስተኛ ቅጣትና ከፍተኛ የቅጣት ጣሪያ በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ተከሳሹ የተከሰሰበትን ዝቅተኛ የቅጣት መነሻ በማድረግ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ትርጓሜ ድንጋጌውን ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ተፈፃሚ የማያደርግና ህግ አውጭው የፀረሙስና ልዩ የሥነ ሥርዐትና የማስረጃ ህግን በማውጣት ለማሳካት የሚፈልገውን ግብ የማያሳካና ህግ አውጭው ድንጋጌውን ሲያውጅ የነበረውን መሠረታዊ ሀሳብ ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ በዝርዝር ባስቀመጥናቸው ምክንያቶች የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ተጠሪዎች የተከሰሱበት የወንጀል ህግ ድንጋጌ ለወንጀል የሚደነግገውን ከፍተኛ የቅጣት ጣሪያ ሣይሆን ዝቅተኛውን የቅጣት መነሻ መሠረት በማድረግ መተርጐም አለበት በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1 የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡

2 ተጠሪዎች የተከሰሱበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 676 ንኡስ አንቀጽ 1 እስከ ሀያ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ በዋስትና ወረቀት ሊለቀቁ አይገባም በማለት በአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 65054

ሐምሌ 14 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

***አመልካች ፡- ብሩክ ሚካኤል  የቀረበ የለም***

***ተጠሪ ፡- ፌዴራል ዐቃቤ ሕግ የቀረበ የለም***

*መዝገቡ ተመረምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡*

***ፍ ር ድ***

ጉዳዩ በወንጀል የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ የተጀመረ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም አመልካች በ1996 ዓ/ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675(1) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ የማይገባውን ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት በማሰብ ጥቅምት 02 ቀን 2002 ዓ/ም በግምት ከቀኑ 4፡00 ሰዓት ሲሆን በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 09 ውስጥ ካለው ኒያላ የቤትና የቢሮ እቃዎች ማምረቻ ድርጅት ውስጥ የድርጅቱ ንብረት የሆነውን አንድ ቱርቦ ቻርጀር ግምቱ ብር 46,000.00(አርባ ስድስት ሺህ ብር) እና አንድ ፒስተርን ሪንግ ግምቱ ብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) በአጠቃላይ ግምቱ ብር 56,000.00(አምሳ ስድስት ሺህ ብር) የሚያወጣ ንብረት ሊጠግን መጥቶ ንብረቶችን  ከዚሁ ስለማይጠገኑ በራሴ ድርጅት ጠግኼ አመጣቸዋለሁ ብሎ ከወሰደ በሁዋላ ሳይመለሱ የቀሩ በመሆኑ ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈፅሟል በማለት ነው፡፡ አመልካችም ክሱ ደርሶትና ተነቦለት እንዲረዳው ከተደረደገ በሁዋላ ስለእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቅ የድርጊቱን አፈፃፀም በተመለከተ የክህደት ቃሉን ሰጥቷል፡፡ አቃቤ ሕግ በበኩሉ አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎች አቅርቦ ካሰማ በሁዋላ አመልካች የመከላከል መብታቸው ተጠብቆላቸው የመከላከያ ምስክሮቻቸውን አሰምተዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በመከላከያ ምስክሮቻቸው የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ሊያስተባብሉ አልቻሉም በሚል ምክንያት ክስ በቀረበባቸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጎ በአንድ አመት ከስድስት ወር እስራት እንዲቀጡ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት የጥፋተኛነት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሲጸና ቅጣቱን በተመለከተ ደግሞ የቅጣት መመሪያውን ያላገናዘበ ነው በሚል ምክንያት ወደ ሰባት ወር ቀላል እስራት ዝቅ ተደርጎ ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ የፍትሓ ብሔር ጉዳይ ከሚሆን በስተቀር በወንጀል የሚያስጠይቅበት አግባብ የለም ፣ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች እንደክሱ አላስረዱም ፣

የመከላከያ ምስክሮች ቃል ውድቅ የተደረገው ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች በወንጀል ጥፋተኛ ተብለው የመቀጣታቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለትም መጥሪያው መድረሱ ተረጋግጦ ያልቀረበ በመሆኑ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነውን ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቋሙት ሕጋዊ ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 414/1996 የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2) በግልፅ ደንግጓል፡፡ እንግዲህ አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ብሎ ለመወሰን ሕጋዊ ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተጣምረው መገኘት የግድ ይላል፡፡ ሕጋዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት አለው ተብሎ የተጠቀሰውን ድንጋጌ ለማቋቋም ሙሉ በሙሉ መሟላት ያለባቸውን ነጥቦች የሚመለከት ሲሆን ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ እንደየቅደምተከተላቸው ከድርጊት ማድረግ ወይም አለማድረግና ከሐሳብ ክፍል ጋር በሕጉ አንቀፅ 24 ፣ 57 እና 58 ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱት ሁኔታዎችን የሚመለከቱ መሆኑ ይታመናል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመጣ አመልካች መውሰዳቸው የተረጋገጠውን እቃ ወደ እጃቸው ያስገቡት ለጥገና በሚል ምክንያት ሲሆን ይህም ከንብረቱ ባለቤት ከሆነው ድርጅት ፈቃድ ያገኘ እንደነበር ፣ ከንብረቱ ባለቤት ከሆነው ድርጅት ውስጥ ሊጠገን ባለመቻሉ ምክንያት ወደራሳቸው ድርጅት ወስደው ለመጠገን ጥያቄ ሲያቀርቡም ድርጅቱ ፈቅዶላቸው አመልካች ንብረቶቹን እንደወሰዱ በአቃቤ ክስና ማስረጃዎች የተገለፀና የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን አመልካችም ግዴታዬን ተወጥቼአለሁ ከማለት በስተቀር ከንብረቱ ባለቤት ድርጅት ጋር የጥገና ውል የነበራቸው መሆኑን የሚክዱት ጉዳይ አይደለም፡፡ እንግዲህ የንብረቶቹ ባለቤት የሆነው ድርጅት ንብረቶቹን ለማስጠገን መስማማቱ ከተረጋገጠና ለጥገና የሄዱት ንብረቶች ተጠግነው ካልተመለሱ ከአመልካች የሚጠይቁት ጉዳይ ፍትሐ ብሔራዊ መፍትሔ  ወይም ውልን መሰረት ያደረገ እንደሚሆን ግልፅ ነው፡፡ በውል መሰረት ግዴታውን ያልተወጣ ተዋዋይ ወገን እምነት አጉድሏል ተብሎ በወንጀል የሚጠየቅ ስለመሆኑ ስለእምነት ማጉደል የሚደነግጉት የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎችም ሆነ ሌሎች ድንጋጌዎች አያሳዩም፡፡ በመሆኑም በሕግ አግባብ ወንጀል ነው ተብሎ ያልተጠቀሰ ድርጊት በወንጀል የማያስጠይቅ መሆኑን ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 23(2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ በግልፅ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡በዚህም መሰረት አመልካች ለጉዳዩ በወንጀል ጥፋተኛ የተባሉት የፍትሐ ብሔር ይዘት ባለው ጉዳይ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የወ/መ/ሕ/አንቀጽ 23(2) እና 675(1) ድንጋጌዎችን የጣሰ ሁኖ በመገኘቱ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 25870 ሕዳር 16 ቀን 2003 ዓ/ም የተሰጠው የጥፋተኛነት ውሳኔ ፣ ይኸው ፍርድ ቤት ሕዳር 23 ቀን 2003 ዓ/ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 101571



www.chilot.me

ጥር 04 ቀን 2003 ዓ/ም የሰጠውን የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(ለ-1)) መሰረት ሙሉ በሙሉ ተሽረዋል፡፡

2. አመልካች በወንጀል የሚጠየቁበት አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት አመልካች በሌላ ወንጀል የማይፈለጉ ከሆነ ዛሬውኑ ከእስር እንዲፈታቸው ታዝዟል፡፡ መፍቻ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 57644

ሐምሌ 25 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች** ፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** ፡- መምህር ዓወት ተካ - አልቀረበም።

**ተጠሪ** ፡- የትግራይ ዐቃቤ ሕግ - አልቀረበም።

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የትግራይ ብሔራዊ ክልል የምሥራቃዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው። ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው። የክርክሩ መነሻ የዞኑ ዐቃቤ ሕግ አመልካች በአንደኛ ተከሳሽ ስሙን በመመዝገብ በሥር ፍርድ ቤት አብረው ክስ ከቀረበባቸው ሌሎች ሦስት ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 የተመለከተውን በመተላለፍ ጳጉሜ 2 ቀን 1998 በአዲግራት ከተማ ቀበሌ 01 ዞን 4 ዓለም መስፍን ሆቴል ፊት ለፊት ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት አቶ ፅጌ ባህታን በድንጋይ አናቱንና ሌላውን ሰውነቱን መትተው የገደሉት ስለሆነ የሰው መግደል ወንጀል ፈፅሟል በማለት ያቀረበው ክስ ነው። አመልካች ዐቃቤ ሕግ በጠቀሰው ቀንና ሰዓት አብረውት ከተከሰሱት ሦስት ሰዎችና ክስ ካልቀረበበት ኃይለማርያም አብርሀ ከተባለ ልጅ አህዋ ሆቴል ከተባለው ሆቴል ሲጠጡ ቆይተው ወደ ቤት በመሄድ ላይ እያሉ ዓለም መስፍን ሆቴል ሲደርስ ሙዚቃ ሰምቶ ቀድሞ ከዓለም መስፍን ሆቴል ሲደርስ ሟች ከሆቴሉ ውስጥ ሲወጣ በር ላይ አግኝቶት ሟች ሂድ አንተ ምናባህ ብሎ እንደገፋው፣ አመልካችም ሟች ወታደር ስለመሰለው ምን አደረግሁህ ጋሼ እንዳለውና ሟች አከታትሎ መትቶት ከአስፋልት ላይ እንደጣለውና መነሳት እንዳልቻለ አመልካችም ኡኡ ብሎ እንደጮኸና ከዚያ በኋላ ሟችን በድንጋይ ማን እንደመታው እንዳላየና ተፈንክቶ ስለነበር ተነስቶ እየተንገዳገደ እንደሄደ በመግለፅ በሟች ግድያ ተካፋይ አይደለሁም ወንጀሉን አልፈፀምኩም በማለት ተከራክሯል።

ተጠሪ አመልካችና ሌሎቹ ተከሳሾች ዋና ወንጀል አድራጊና የወንጀል ተካፋይ በመሆን ሟችን መግደላቸውን ያስረዳልኛል በማለት አምስት ምስክሮችና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቧል። ዐቃቤ ሕግ ክሱን ለማስረዳት ካቀረባቸው ምስክሮች ውስጥ ዐቃቤ ሕግ በአራተኛው ተራ ቁጥር የማስረጃ ዝርዝር ላይ ስሙን የገለፀው ምስክር ሥራው ፖሊስ መሆኑን ገልፆ በሥር ፍርድ ቤት

ሁለተኛ ተከሳሽ እና አራተኛ ተከሳሽ ለፖሊስ ቃል ሲሰጡ የሰማ መሆኑንና ሟች አመልካችን ወድቀው ሟች ከላይ በሥር አንደኛ ተከሳሽ የነበረው አመልካች ከታች ሆነው እንዳገኟቸውና ሁለተኛ ተከሳሽ ሟችን በድንጋይ አናቱን የመታው መሆኑንና አራተኛ ተከሳሽ በእግሩ ሟችን የመታው መሆኑን ሲናገሩ ሰምቻለሁ አንደኛ ተከሳሽ /አመልካች/ መናገሩን አላስታውስም በማለት መስክሮ ተመልሷል፡፡ ዐቃቤ ሕግ በማስረጃ ዝርዝሩ ስሙ በአምስተኛው ተራ ቁጥር የጠቀሰው ምስክር ሥራው ፖሊስ መሆኑን ገልፆ በሥር ሁለተኛና አራተኛ ተከሳሽ የነበሩት ሰዎች ስለወንጀሉ አፈፃፀም ለፖሊስ ቃላቸውን ሲሰጡ የሰማ መሆኑን በዝርዝር መስክሮ የተመለሰ ነው፡፡ ለፖሊስ የተሰጠን ቃል የመሰከረው የዐቃቤ ሕግ ሶስተኛ ምስክር ሁሉም በጠቡ ተሳታፊ መሆናቸውን የመሰከሩ መሆኑንና ሁለተኛና አራተኛ ተከሳሾች በድምፅና በምስል በተቀረፀ ካሴት የሰጡት ቃልና ከአዲግራት ሆስፒታል የተሰጠ ማስረጃ በማስረጃነት የቀረበ መሆኑን ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሁለተኛና አራተኛ ተከሳሾች በወረዳ ፍርድ ቤት የሰጡት የእምነት ቃል ሶስት የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች በቀዳሚ ምርመራ ፍርድ ቤት የሰጡት የምስክርነት ቃልና በማስረጃነት እንደቀረበ የዞኑ ፍርድ ቤት በውሣኔው ገልጿል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችና ሌሎች ተከሳሾች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ብይን ሰጥቶ የአመልካችና የሌሎቹን ተከሳሾች መከላከያ ማስረጃ ከሰማ በኋላ በሥር ሶስተኛ ተከሳሽ የነበረው በነፃ እንዲሰናበት ፍርድ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በሥር ሁለተኛ ተከሳሽና አራተኛ ተከሳሽ የነበሩት ሰዎች በወንጀል ሕግ አንቀፅ 540ን በመተላለፍ የሰው መግደል ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኞች ናቸው በማለት አመልካች በሰባት ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የዞኑን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ አፅንቷል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርቧል፡፡ የክልሉ የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት በአብላጫ ድምፅ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ጥር 14 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ዐቃቤ ሕግ እኔን ሟችን በመግደል ወንጀል የከሰሰኝ ቢሆንም ዐቃቤ ህግ ያቀረበው የሰውና የፅሑፍ ማስረጃ በወቅቱ ሟች እኔን መሬት ላይ ጥሎ እየደበደበኝ እያለ ኡኡታ የሰማሁ መሆኑንና በሥር ሁለተኛ ተከሳሽና አራተኛ ተከሳሽ የነበሩት ሟችን የመቱት መሆኑንና እኔም ከወደቅሁበት ተነስቼ መሄዴን የሚያስረዱ ናቸው፡፡ ሟች መሬት ላይ ጥሎ ሲደበድበኝ የኡኡታና የጩኸት ድምፅ ማሰማቴ በወንጀሉ ድርጊት ተካፋይ ወይም ግብረ አበር የነበርኩ መሆኑን አያስረዳም፡፡ ስለሆነም በወንጀሉ ድርጊት የተሳተፍኩ መሆኔን የሚያሳይ ምንም ዓይነት ማስረጃ ተጠሪ አቅርቦ ባላስረዳበት ሁኔታ ጥፋተኛ ተብዬ መቀጣቴ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በፅሑፍ መልሱን እንዲያቀርብ መጥሪያ ከደረሰው በኋላ በፅሑፍ መልሱን ባለማቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ እንዲታለፍ ችሎቱ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አመልካች ሟችን በመግደል ወንጀል ጥፋተኛ ነው ተብሎ የተወሰነበት የቅጣት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ከላይ የተገለፀውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ዐቃቤ ህግ /ተጠሪ/ ባቀረበው ማስረጃ አመልካች የወንጀሉ ሥራ ዋና ወንጀል አድራጊ /ተካፋይ/ አባሪ ወይም ረዳት መሆኑን የማስረዳት ኃላፊነቱን ተወጥቷል ወይስ አልተወጣም የሚለውን ነጥብ ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1.በተጠሪ ማስረጃ ምስክሮች ስለ አመልካች ያረጋገጡትን ፍሬ ጉዳይ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ታህሳስ 2 ቀን 2001 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ በመጨረሻው ገፅ በአንደኛው ፓራግራፍ "አንደኛ ተከሳሽ ከሟች ጋር ወድቆ ሲመታ እንደነበረ በምስክሮች የተመሰከረ ሆኖ ነገሩ በመጀመሪያ መነሻው ተከሳሽ ነው ወይስ ሟች ያስነሳው የሚለው ባይታወቅም ሟች ተከሳሹን ጥሎ ይመታው እንደነበር ተከሳሽም እየተመታ እንደነበር ምስክሮችን ሰምቶ ፍርድ ቤቱ ተገንዝቦና ተረድቷል በሚል መንገድ በአጭሩ ገልፆታል፡፡ ተጠሪ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረባቸው የምስክሮች ቃልና የሰነድ ማስረጃዎች ሟች አመልካችን ጥሎ እየደበደበው እያለ አመልካች የኡኡታና የጫጫታ ድምፅ ያሰማ መሆኑንና የአመልካች የጩኸት ድምፅ በሰሙትና ከአመልካች ጋር አብረው ያሙት በሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛና አራተኛ ተከሳሾች ሟች ከላይ አመልካች ከታች ሆነው ሟች አመልካችን እየደበደበ እንዳለ ሟችን መሐል ራሱን በድንጋይ እንደመቱት የሚያረጋግጡ መሆናቸው የሥር ፍርድ ቤት ስለ ዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ይዘት በውሣኔው በክርክር ከገለፀው ፍሬ ጉዳይ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ አመልካች ሟች መሬት ላይ ጥሎ እየደበደበው እያለ የኡኡታና የጩኸት ድምፅ በማሰማቱና የአመልካችን ጩኸት ሰምተው የመጡት ሁለተኛና አራተኛ ተከሳሾች በቦታው የደረሱና ሟችን በድንጋይ የመቱት መሆኑን እንጂ ተጠሪ ዐቃቤ ሕግ አመልካች ሟችን ለሞት ያበቃው ድርጊት ሌሎቹ ተከሳሾች ሲፈፅሙ በተግባር ወይም በመላ ሃሳቡ ተካፋይ የነበረ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡

በመሠረቱ ዐቃቤ ሕግ በወንጀል በተከሰሰ ሰው ላይ የሚያቀርበው የወንጀል ክስ የወንጀሉን ዝርዝር ሁኔታ መያዝ እንዳለበት በተለይም ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ለይቶ አውቆ መልስ ለመስጠት እንዲችል ክሱ ወንጀሉንና ሁኔታውን መግለፅ ያለበት መሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀፅ 112 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከት ተጠሪ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ አመልካች በወንጀሉ ድርጊት በምን ሁኔታ እንደተሳተፈ የሚገልፅ አይደለም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካችና ከአመልካች ጋር የተከሰሱት ሌሎች ሰዎች በወንጀሉ ሥራ ያደረጉትን ተሳትፎና በወንጀሉ ተካፋይ ናቸው የሚልበትን ምክንያት በመዘረዘርና ክሱን እንዲያሻሽል በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 119 መሠረት ትዕዛዝ መስጠት ሲገባው የአመልካች የወንጀል ተሳትፎና ተካፋይነት በዝርዝር የማይገልፀውን የወንጀል ክስ ተቀብሎ ማከራከሩ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 112 ድንጋጌን መሠረታዊ ግብ ሳይከተል ክርክሩን የመራው መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. ተጠሪ በወንጀል ክሱ በገለፀው ስፍራና ጊዜ ሟች አመልካችን መሬት ላይ ጥሎ ሲደበድበው አመልካች የኡኡታና የጩኸት ድምፅ ያሰማ ከመሆኑ ውጭ አመልካች ሟችን ለመግደል የሃሳብ ወይም የድርጊት ተካፋይ መሆኑን ተጠሪ የማስረዳት ግዴታውን አልተወጣም፡፡ አንድ ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት በኃላፊነት የሚጠየቀው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 32 ንዑስ አንቀጽ 1 /ከሀ-ሐ/ በተደነገጉት መሠረት በወንጀሉ ሥራ ተካፋይ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀፅ 32 ንዑስ አንቀጽ 1 /ከሀ-ሐ/ በተደነገገው መሠረት ሟችን ለሞት ያበቃውን ድብደባ ሌሎቹ ተከሳሾች ሲፈፅሙ ተካፋይ የነበረ መሆኑ ተጠሪ አላስረዳም፡፡ በተለይም አመልካች ሟችን ሀሳብና አድርጐቱ እንደዚሁም በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ መሆኑን ተጠሪ የማስረዳት ኃላፊነቱን /Burden of proof/ የተወጣ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በውሣኔያቸው አላረጋገጡም፡፡ በአንፃሩ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመልካች ጓደኞች የነበሩት ሁለተኛና አራተኛ ተከሳሽ ሟችን በድንጋይ ሲደበድቡት አመልካች የሟች ጥቃት ሰለባ ሆኖ መሬት ላይ ወድቆ ሟች እየደበደበው የነበረና አመልካችም



www.chilot.me

የኡኡታና የጩኸት ድምፅ እያሰማ እንደነበር ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበውን ማስረጃ ይዘት በማጠቃለል የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሣኔው ካሰፈረው ለመረዳት ችለናል፡፡

አንድ ሰው ከሌሎች ሰዎች ጋር የወንጀል ተካፋይ ሆኗል የሚባለው በወንጀሉ አፈፃፀም የግዙፍ ተግባር፣ የሃሳብና የሕግ ሁኔታዎች በመተላለፍና በወንጀል ሕግ አንቀፅ 32 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት በወንጀሉ ድርጊት ተሳታፊ ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 23 ንዑስ አንቀጽ 2 እና ከወንጀል ሕግ አንቀፅ 32 ንዑስ አንቀጽ 1 በጣምራ በማንበብ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ ሰው ጥቃት እየተፈፀመበት ከመሬት ላይ ወድቆ እየተደበደበ ያለ ሰው የጩኸትና የኡኡታ ድምፅ ማሰማቱን በወንጀልነት የሚፈርጅ የሕግ ድንጋጌ የለም፡፡ አመልካችን ሟች መሬት ላይ ጥሎ ሲደበድበው የጩኸትና የኡኡታ ድምፅ ከመስማቱ ውጭ ሁለተኛና አራተኛ ተከሳሾች ሟችን እንዲገድሉት ያነሳሳ ወይም የወንጀሉ አባሪ ስለመሆኑ አያሳይም፡፡ በአጠቃላይ አመልካችን ሟች በመሬት ላይ ጥሎ እየደበደበው እያለ የጩኸትና የኡኡታ ድምፅ ማስማቱ የወንጀል ግዙፍ ተግባር አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ሟችን የመግደል ሃሳብ የነበረው ወይም በመሳ ሃሣቡ አድራጎቱ የሚሰጠውን ውጤት የራሱ በማድረግ በወንጀሉ ተካፋይ መሆኑን ተጠሪ በቂ ማስረጃ በማቅረብ እንዳላስረዳ ከሥር ፍርድ ቤት የውሣኔ ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ኡኡታና ጩኸት ማሰማቱ ለሟች መሞት ያስከተለ ተግባር ነው ብሎ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 24 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በምክንያትና በውጤት መካከል ግንኙነት እንዳለ ለመደምደም አይቻልም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት ሟች አመልካችን መሬት ላይ ጥሎ ሲደበድበው የጩኸትና ኡኡታ ድምፅ ባያሰማ ኖሮ፣ ሟችን በድንጋይ ደብድበው የገደሉት ሌሎቹ ተከሳሾች ከቦታው አይደርሱም ነበር፡፡ ሌሎቹ ተከሳሾች ጩኸቱን ሰምተው መጥተው ሟች አመልካችን እየደበደበው ባያገኙት ኖሮ ሟችን በድንጋይ አይደበድቡትም ነበር የሚል ሕጋዊ መሠረት የሌለው መነሻ በመያዝ አመልካችን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 32/1/ እና አንቀጽ 540 የተመለከተውን በመተላለፍ ሟችን ለመግደል በተፈፀመው የወንጀል ድርጊት ተካፍሏል በማለት የሰጠው ውሳኔ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 23/1/ ንዑስ አንቀጽ 2፣ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32 ንዑስ አንቀጽ 1፣ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 24 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 141 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘት መንፈስና ዓላማ የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎትም ከላይ በዝርዝር የተገለፀውና የሕግ ስህተት ያለበትን የከፍተኛ ፍርድ ቤት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ማረምና ማስተካከል ሲገባቸው ውሣኔውን በአብላጫ ድምፅ ማፅናታቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

3. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አነስተኛ ድምፅ አመልካች የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32/1/ እና አንቀፅ 540 በመተላለፍ ሳይሆን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 571 በመተላለፍ ጥፋተኛ ተብሎ የቅጣት ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ መሆኑን የገለፀው ሃሳብ ተገቢነት ያለው መሆኑን መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 571 " ማንም ሰው አስቦ ሌላውን ሰው በቅርብ ለሚደርስ የሞት አደጋ ያጋለጠ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ወይም ከሶሶት ወር በማያንስ ቀላል እስራት ይቀጣል" በሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ ተጠሪ ባቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠው ሟች አመልካችን ከመሬት ጥሎ ሲደበድበው አመልካች የኡኡታና ጩኸት ድምፅ ያሰማ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ አመልካች ሟችን ሆን ብሎና አስቦ ለሞት አደጋ ለማጋለጥ የጩኸትና ኡኡታ ድምፅ ያሰማ ስለመሆኑ ለሥር ፍርድ ቤት ባቀረበው ማስረጃ የማስረዳት ግዴታውን አልተወጣም፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረበው ማስረጃ አመልካች ሟችን



www.chilot.me

ለሞት አደጋ ለማጋለጥ በማሰብ የፈፀመው ተግባር መሆኑን የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡ ተጠሪ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀፅ 571 የተዘረዘረውን የወንጀል ድርጊት የፈፀመ ስለመሆኑ በበቂ ማስረጃ ባላስረዳበት ሁኔታ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀፅ 571ን በመተላለፍ በኃላፊነት የሚጠየቅበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡

በአጠቃላይ ተጠሪ በሥር ፍርድ ባቀረበው የወንጀል ክስ በገለፀው ስፍራና ጊዜ ሟች ከመሬት ላይ ጥሎ ሲደበድበው አመልካች የኡኡታና ጩኸት ድምፅ ከማሰማቱ ውጭ አመልካች ሟች በሌሎች ተከሳሾች በድንጋይ ሲደበደብ በወንጀሉ ዋና አድራጊነት /ተካፋይነት/ በአነሳሽነት፣ ወይም በአባሪነት የተሳተፈ መሆኑን ተጠሪ የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነቱን አልተወጣም፡፡ ተጠሪ አመልካች የተከሰሰበትን የወንጀል ድርጊት ወይም ከተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ውጭ የሆነ በወንጀል የሚያስጠይቅ ድርጊት የፈፀመ መሆኑን በበቂ ማስረጃ እንዳላስረዳ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ስላቀረበው ማስረጃ ይዘት በውሣኔው ካስፈረው ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ተጠሪ አመልካች ሟችን ለህልፈት ባበቃው ድርጊት በመሳ ድርጊቱ፣ ወይም ሃሣቡ ተሳታፊ መሆኑን በበቂ ማስረጃ ካላስረዳ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልገው በነፃ እንዲሰናበት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ቁ. 141 መሠረት በነፃ ማሰናበት ሲገባው አመልካች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ በማድረግ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሣኔ ማፅናቱ ከላይ የተገለፁትን የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈፅመዋል በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልል የምስራቃዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ እንደዚሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ፍርድ በማፅናት የሰጡት ውሣኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀፅ 2 /ለ/ -1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ከተከሰሰበት ወንጀል በነፃ ይሰናበታል በማለት በወንጀለኛ ሕግ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀፅ 2/ለ/ -1 መሠረት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

ቤ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 66767

ሐምሌ 28 ቀን 2003ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** ፡- አቶ ተስፋዬ ተሾመ - ጠበቃ ሲሳይ ኃይሉ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ** ፡- የፌደራል ዓቃቤ ሕግ - ማርታ በቀለ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የወንጀል ክስ ሲሆን በፌ/ከፍተኛ ፍርድ በተጠሪ ቀርቦ የነበረው የክስ ይዘት ተከሣሽ/የአሁን አመልካች በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ ቁ.692(1) ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ የማይገባውን ብልፅግና ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት አስቦ የግል ተበዳይ ወይንሸት ወርቁ የከባድ መኪና ካምፒዮ እንደተሸጠለት በወ/ሮ አልማዝ ከበደ የከባድና ቀላል መኪና ዕቃ መለዋወጫ ሱቅ ውስጥ አስቀምጣ እንዳለ ተከሣሽ ወደ ሱቁ ውስጥ የሠሌዳ ቁጥሩ ኮድ 2.35215 አ.አ በሆነ መኪና እያሽከረከረ በመምጣቱ መጀመሪያውኑም ከግል ተበዳይ ጋር የከባድ መኪና ካምፒዮ በብር 45,000 ለመግዛት ከመስማማቱ በኂላ ብር ላምጣ ብሎ መሄዱን እንጂ የግል ተበዳይ ከላይ የተመለከተውን ዕቃ ውሰድ ሳትለው ወ/ሮ አልማዝም የግል ተበዳይ የታለች ብላ ስትጠይቀው ከኂላዬ ናት ከፊትና ኂላ ሆነን ነው የመጣነው በማለት አሳሳች ነገር በመናገር የከባድ መኪና ካምፒዮን ይዞት በነበረው መኪና ውስጥ ጭኖ በመጥፋቱ በፈፀመው የማታለል ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

በቀረበው ክስ ላይ አመልካች በመካድ የተከራከረ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማት ክሱ በቀረበበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ ሥር ጥፋተኛ ነው በማለት በመወሰን የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበል በአንድ ዓመት ከስድስት ወር የእስራት ቅጣት እንዲቀጣ በማለት ወሰኗል፡፡ አመልካች በተሠጠው ውሣኔ ቅር በመሠኘት ይግባኙን ለፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኂላ የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ በማፅናት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

አሁን የቀረበው አቤቱታ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ሲሆን አመልካች በጠበቃቸው በኩል መጋቢት 12 ቀን 2003ዓ.ም የተፃፈ የቅሬታ ፍሬ ሃሣብ ዋናው የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር የሆነው የተከለከለ የወንጀል ድርጊት ስላልተሟላ ድርጊቱ የማያስከስስ በመሆኑ፣ ዓ/ሕግ ያቀረባቸው የሰው ምስክሮች አመልካች ከጥርጣሬ ውጭ የወንጀል ድርጊቱን የፈፀመ ስለመሆኑ የማያረጋግጡ

በመሆኑ፣ አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች ያቀረባቸው የሠውና ሰነድ ማስረጃዎችን በአግባቡ ያልተመለከቱት በመሆኑ እና አመልካች በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.143(2) እና በሕገ-መንግስቱ በተሠጠኝ የመከላከል መብት መሠረት ያቀረብኩትን ተጨማሪ ማስረጃ ያለመቀበላቸው ያለአግባብ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤት የፈፀሙት መሠረታዊ የህግ ስህተት ታርሞ አመልካች በነፃ እንዲሠናበት የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ ቀርቦ መልስ የሰጠ ሲሆን በቀን 22/9/2003 ዓ.ም በ3 ገፅ የተፃፈ የመልስ ፍሬ ሃሣብ አመልካች የፈፀማቸው ተግባር ሕጉ የተረጋገጠው ፍሬ ነገር ስንመለከት በወንጀል ሕጉ የተቀመጠውን የወንጀል አላፊነቱን የሚያቋቁሙትን ተግባራት የሚያሟላ በመሆኑ፣በዓቃቤ ህግ የቀረቡት ማስረጃዎች የተፈፀመውን ወንጀል በአግባቡ ያረጋገጡ በመሆኑና አመልካች በመከላከያ ምስክሮቹ ያላስተባበለ በመሆኑ እና ተጨማሪ የማስረጃ ጥያቄ በተመለከተ የመከላከልን መብት በተመለከተ ቀድሞ በመከላከያዎች ዝርዝር ውስጥ የተጠቀሰ ባለመሆኑ እና ፍርድ ቤቱ የተጠየቀው ተጨማሪ ማስረጃ ነገሩን ለማዘግየት ሣይሆን ለፍትሕ አሠጣጡ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን የሚፈቅድ በመሆኑ በባሕርይው ፍቃጅ እንጂ አስገዳጅ ባለመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ ቀርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደተመረመረውም በመጀመሪያ ደረጃ የቀረቡት የዓቃቤ ሕግ ማስረጃዎች በበቂ ሁኔታ ተፈፀመ የተባለው ወንጀል ስለመፈፀሙ አላስረዱም እና አመልካች ያቀረባቸው ማስረጃዎች በአግባቡ አልታየልኝም የሚሉትን ነጥቦች ስንመለከት ማስረጃን መመዘን ጉዳዩን በመጀመርያ የተመለከተው እና በይግባኝ የያዘው የፍርድ ቤት ሥልጣን በመሆኑ እና የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና በአዋጅ ቁ.25/88 አንቀጽ 10 መሠረት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሲፈፀም ማቃናት በመሆኑ በፍሬ ነገር ረገድ የበታች ፍርድ ቤቶች የደረሱበትን መደምደሚያ መቀበሉ አግባብነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሠረት መታየት ያለባቸው አመልካች የጠየቀው ተጨማሪ ማስረጃ መታለፍ እና በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው ነጥቦች አመልካች ጥፋተኛ የተባለውን የወንጀል ኃላፊነት ስለ ማቋቋሙ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉት ጭብጦች ተይዘው ይሄ ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት የችሎት ሂደት ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው አመልካች የሰውና የሠነድ መከላከያ ምስክሮችን /ማስረጃዎቹን/ ካጠናቀቀ በኋላ የካቲት 26 ቀን 2002ዓ.ም በዋለው ችሎት የተጨማሪ የባለሙያ ምስክር የጠየቁ መሆኑ ተመዝግቦ የማስረጃው ዝርዝርና ምን እንደሚያስረዱለት ሲያቀርብ ለትክክለኛ ፍትሕ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም የሚለው ይታያል በማለት መዝገቡ ለውሣኔ የተቀጠረ መሆኑ፣ ለውሣኔ በተቀጠረበት መጋቢት 20 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተከሣሽ ጠበቃ በቀን 10/7/2002 ዓ.ም በተፃፈ ተጨማሪ የባለሙያ ምስክር የተጠየቀ መሆኑ ተገልፆ አስፈላጊ ሲሆን የሚታዘዝ መሆኑ ተገልጾ አሁንም መዝገቡ ለውሣኔ የተቀጠረ መሆኑን፣ በቀጠሮው ሚያዝያ 18 ቀን 2002ዓ.ም በተመሣሣይ መልኩ የተቀጠረ መሆኑን በመጨረሻውም ለአሁኑ ቅሬታ ምክንያት የሆነው ፍርድ መሠጠቱን መመልከት ይቻላል፡፡ በዚሁ በስተመጨረሻ በተሰጠው ፍርድም የተጨማሪ ማስረጃ ጉዳይ የተነሣ ሲሆን ከሂደቱ ፍርድ ቤት ያለፈው መሆኑን ተረድተናል በማለት ተመልክቷል፡፡ ከዚህ አጠቃላይ ሂደት መገንዘብ የሚችለው መጀመሪያውኑ የተጨማሪው ማስረጃ የመራለት ችሎት ወደ ፊት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ትዕዛዝ ይሰጥበታል በማለት ሲቀጥር መቆየቱ እና



www.chilot.me

በመጨረሻም ፍርድ የሠጠው ችሎት የተጨማሪ ማስረጃ ጉዳይ በማንሣት እንደታለፈ ይቆጠራል ማለቱ ጉዳዩን የተመለከተውና የቀረበውን ጥያቄ ያለመቀበሉን ያመለክታል፡፡

ፍርድ ቤቱ የተጨማሪ ማስረጃን ጥያቄ አልተቀበለውም የሚል መደምደሚያ ላይ ከተደረሰ የታለፈበትን አግባብ ወይም መታለፉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ ተጨማሪ ማስረጃ የተጠየቀው የባለሙያ ምስክርነት ሲሆን በወቅቱ የያዝኩት መኪና የከባድ መኪና ካምፒዮ መጫን የማይችል ስለመሆኑ ያረጋግጣል በማለት ነው፡፡ተጠሪ የሙሉ አመልካች ይዞት የነበረው የቤት መኪና የከባድ መኪና ካምፒዮ መጫን መቻሉ ወይም ያለመቻሉ በጭብጥነት ያልተያዘ ጉዳይ በመሆኑ እና መሸከም እንደሚችል ለማንም ሰው ግልፅ በመሆኑ የተለየ የባለሙያ ምስክርነት የማያስፈልገው በመሆኑ ቢታለፍ በአግባቡ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ችሎቱም የግራቀኙን ክርክር ሲመለከተው አጠቃላይ ክርክሩና የምስክር ሂደቱ አመልካች ከግል ተበዳይና ከዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ጋር የተባለውን የከባድ መኪና ካምፒዮ በእጅ ለማስገባት የተጠቀመባቸውን ስልቶች ወይም ዘዴዎች ላይ ያተከረ እንጂ የመኪናው ዓይነት እና በተለይም አመልካች ይዘውት የመጡት መኪና ዝርዝር ይዘት ወይም የመሸከም አቅም በተመለከተ ጭብጥ ተይዞ በስፋት የተኬደበት አይደለም፡፡ ይሄ ከሆነ ደግሞ ቀድሞ በጭብጥነት ያልተያዘ ጉዳይ ከመሆኑም በላይ ከወ/መ/ሕግ ቁ.143(2) ሥር እንደተመለከተው ተጨማሪ ማስረጃ ፍርድ ቤቱ ለትክክለኛ ፍትሕ አሠጣጥ ተገቢ ነው ብሎ ሲያምን እንጅ አስገዳጅ ካለመሆኑ ጋር ተደምሮ ሲታይ መታለፉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል የሚያሠኝ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህ መሠረት አመልካች በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ስርዓት ህግ እና በህገ መንግስቱ የተሠጡትን መከላከያ ማስረጃ በማቅረብ የመከላከል መብቱን የተጠቀመበት በመሆኑ እና ተጨማሪ ማስረጃ መቀበል ደግሞ አስገዳጅ ሣይሆን ፍርድ ቤቱ ለፍትሕ አሠጣጥ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን የሚሠጥ /የሚፈቀድ/ በመሆኑ በመታለፍ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል የሚያሠኝ ነገር የለም ብለናል፡፡

ወደ ሁለተኛው ጭብጥ ስንመለስ የተረጋገጠው ፍሬ-ነገር አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣበትን የወንጀል ህግ ኃላፊነት ሊያቋቁም ስለመቻሉ መመልከት ተገቢ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት የግል ተበዳይና አመልካች በደላላ ከተገናኙ በኋላ የከባድ መኪናውን ካምፒዮን ያስቀመጠችበት ድረስ በማምጣት የግል ተበዳይ ለአመልካች ካሣየችውና ዋጋውን ከተነጋገሩ በኋላ አመልካች ገንዘቡን ይገኘ እመጣለሁ በማለት ሲሄድ ተበዳይም እስከዚያ የግል ጉዳይ ቦታ ለመድረስ እንደወጣች፣ አመልካች ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ተመልሶ የመጣ መሆኑ፣ የዓቃቤ ሕግ ምሥክሮች የግል ተበዳይስ ብለው ሲጠይቁት ከኋላዬ ነች አብረን ነው የመጣነው፣ ፓርክ ለማድረግ መኪና እያዞረች ነው፣ የመኪና ማቆሚያ ቦታ እየፈለገች ነው፣ እስከዚያ ይጫን ፣ይዘን እንጥፋ በማለት የተለያዩ የማሣመኛ ቃላቶችን በመጠቀም ዕቃውን አስወጥቶ በመጫን የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች የራሳቸውን ሱቅ ሥራ ለመሥራት መለስ ሲሉ ይዞ የጠፋ መሆኑ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጧል፡፡ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ከወ/መ/ሕግ ቁ.692(1) አኳያ ሲታይ አመልካች የማይገባ ብልፅግና ለራሱ ወይም ለሌላ ሠው ለማስገኘት ቀድሞ ከግል ተበዳይ ጋር የመምጣቱን አጋጣሚ በመጠቀም የግል ተበዳይ ከእሱ ጋር ሣትመጣ አብራው እንደመጣች በማስመሠል የባለ ሱቆቹን የተሣሣተ እምነት በመጠቀም፣ ትክክለኛውን ነገር በመደበቅ ካምፒዮኑን ይዞ በመጣው መኪና ላይ ከጫነ በኋላ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች በሌላ ሥራ መጠመድ አጋጣሚ በመጠቀም ይዞት የሄደ በመሆኑ በሕጉ የተቀመጠውን ወንጀል ሕጉ ሥር የወንጀል ኃላፊነቱን የሚያረጋግጡ መመዘኛዎች መሟላታቸውን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም የተፈፀመው ድርጊት የወንጀል ኃላፊነቱን የሚያቋቁሙ በመሆኑ ስለተረጋገጠ በዚህ አንቀጽ ስር ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ በአግባቡ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት



www.chilot.me

ሆኖ አልተገኘም፡፡ የተላለፈበት ቅጣትም የግራቀኙን የቅጣት አስተያየትና አጠቃላይ የቅጣት አጣጣል ሥርዓቶች የተከተለ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተው ውሣኔ ተሠጥቷል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ.58613 የካቲት 29 ቀን 2003ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ.80841 በቀን 12/11/2002 ዓ.ም እና በቀን 15/11/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ፍርድ እና ውሣኔ በወ.መ.ሥ.ሥ.ሕግ ቁ. 195(2)(ለ)(2) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች በተከሠሠበት የማታለል ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ የተጣለበት ቅጣት በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በትውስት የመጣው የመዝ.ቁ.80841 ወደ መጣበት ይመለስ መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሐ.አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 68407

ሐምሌ 14 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ውልታ ደሳለኝ - ጠበቃ ግርማ ሚደቅሣ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** የኦሮሚያ የስነ ምግባርና ፀረ - ሙስና ኮሚሽን ዐ/ሕግ ማንደፍሮ ናታአ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የዋስትና አቤቱታ ሲሆን የቀረበው በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በክልሉ የስነ ምግባርና ፀረ - ሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ሕግ በሙስና ወንጀል ከሌሎች 11 ሰዎች ጋር በተከሰሱበት መዝገብ በካንሰር በሽታ መታመማቸውን ገልፀው ውጪ አገር ሂደው ለመታከም ዋስትና እንዲፈቀድላቸው ያቀረቡት ጥያቄ በተከሰሱበት ወንጀል ዋስትና አይፈቀድም በማለት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር የቀረበ ነው፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከላይ እንደተመለከተው በመወሰኑ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደዚሁም ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የዞኑን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ በማፅናታቸው ሲሆን በቀን 15-9-2003 ዓ.ም በ3 ገፅ የቀረበ የቅሬታ ፍሬ ሃሣብ ባደረብኝ የጉበት ካንሰር በሽታ በአገር ውስጥና ውጪ ስታከም የቆየሁ መሆኑ እየታወቀ፣ በተሰጠኝ በሐኪሞች ቦርድ መሠረት ውጪ አገር ሄጄ እንድታከም ተወስኖ እያለ በቁጥጥር ሥር በመሆኔ መሄድ ያልቻልኩ መሆኑ እየታወቀ፣ በጤንነት ምክንያት ችሎት ቀርቤ መከራከር ያልቻልኩ በመሆኑ፣ ዋስትና ያስከላክላል በማለት የተጠቀሰብኝ አንቀፅ የሕክምና እድል የማግኘት መብቴን የማይነፍገኝ እንጂ የሚነፍገኝ ቢሆን እንኳን የአዋጁ ድንጋጌ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 21 እና 15 እንደዚሁም አንቀፅ 9 ጋር ታይቶ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ ተሽሮ ውጪ አገር ሄጄ መታከም እንድችል እንዲፈቀድልኝ የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ ቀርቦ በቀን 02-10-2003 ዓ.ም በ4 ገፅ የሰጠው የመልስ ፍሬ ሃሣብ አመልካች ዋስትና የተከለከሉት የተከሰሱበት የሙስና ወንጀል ዋስትና የማይፈቅድ በመሆኑ፣ በበታች ፍርድ ቤቶች ያቀረቡት ጥያቄ የዋስትና ጥያቄ እንጂ ሕክምና የማግኘት መብት ባለመሆኑ ሁለቱ ጥያቄዎች ደግሞ መቅረብ ያለባቸው በተለያዩ ሁኔታዎች በመሆኑ አሁን የቀረበው ጥያቄ ተገቢነት የለውም፣ የበታች ፍርድ ቤቶችም ውሣኔ የሰጡት የቀረበው የዋስትና ጥያቄ ተቀባይነት አለው? ወይስ የለውም? በሚለው ነጥብ ላይ በመሆኑ አሁን እየተነሳ ያለው በህይወት የመኖር መብት ጋር ተያይዞ የሕገ-መንግስቱን

አንቀጽ በመጥቀስ የቀረበው ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት የለውም፣ የቀረበው ጉዳይ ከሕገ መንግስቱ ጋር ተያያዥነት አለው ቢባል እንኳ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ-መንግስት አንቀጽ 19 ለተከሰሱ ሰዎች በመርህ ደረጃ የዋስትና መብት የሚፈቅድ ቢሆንም በልዩ ሁኔታ ግን ዜጐች እንደ ወንጀሉ ሁኔታ ዋስትና ሊከለከሉ እንደሚችሉ የሚደነግግ በመሆኑ የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ እንዲፀና በማለት ተከራክሯል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም የቀርበው አቤቱታ የዋስትና መብትን መሠረት ያደረገ ነው? ወይስ የህክምና የማግኘት መብቱን ነው? በሁለቱ ጉዳይ መከተል የሚገባው ሥርዓት አንድ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉት ጭብጦች ተይዞ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሠረት የሙስና ወንጀል እየታየ ያለበት ችሎት ቀርቦ የነበረው አቤቱታ አመልካች በካንሰር በሽታ እየታመሙ መሆናቸውን ገልፀው የዋስትና መብታቸው ተጠብቆ ውጪ አገር ሂደው ለመታከም እንዲቻሉ በሚል የቀረበ ሲሆን ችሎቱም ሰጥቶት የነበረው ትዕዛዝ ዋስትናን በተመለከተ የተሰሱበት ወንጀል ዋስትና አያስጠብቅም፡፡ ሕክምናን በተመለከተ ግን በፖሊስ ክትትል ሥር ሆነው ለመታከም የሚያግድ ነገር የለም በሚል ነበር፡፡ ይሄ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ እስከ ክልሉ ሰበር ችሎት ቀርቦ ፀድቋል፡፡

አሁን ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበው ቅሬታ “…. የተከሰስሽበት የወ.መ.ሕ.ቁ. 407/2/ በአዋጅ ቁ. 434/1997 አንቀጽ 4/1/ መሠረት የዋስትና መብት አይፈቅድም በሚል ምክንያት የውጭ አገር የህክምና ጥያቄን በትእዛዝ እና ውሣኔ ውድቅ አድርገውብኛል፡፡” በሚል ነው፡፡ ከዞኑ ፍርድ ቤት ጀምሮ ሲጠየቅ የነበረውን የዋስትና ጥያቄ በተመለከተ አመልካች የተከሰሱበት የወንጀለኛ መቀጫ ሕግ አንቀጽ 407/2/ን ስንመለከት ከ7 ዓመት ፅኑ እስራት እስከ 15 ዓመት ፅኑ እስራት ሊያስቀጣ የሚችል አንቀጽ በመሆኑና አመልካች በካንሰር በሽታ መታመማቸው በራሱ ከተሻሸለው የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁ. 434/97 አንቀጽ 4/1/ አኳያ ሲታይ ለዋስትና ጉዳይ ከግምት የሚገባበት አግባብ የለም፡፡ ምክንያቱም በዚህ አዋጅ አመልካች የተከሰሱበት አንቀጽ ከ10 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ በሚችል ወንጀል ከሆነ በዋስትና መልቀቅ እንደማይቻል ይደነግጋል፡፡

በሌላ በኩል የተሰጠው ትዕዛዝ ወይም ደግሞ የዋስትና ጥያቄ ውድቅ መደረጉ የአመልካችን ሕክምና የማግኘት መብት ብሎም በህይወት የመኖር ሕገ-መንግሥታዊ መብቷን ተቀባይነት አሳጥቷል ወይ? የሚለውን ነጥብ ስንመለከት በመጀመሪያ ደረጃ በሕግ ጥላ ሥር ያለ ተከሣሽ የመታከም መብት የማይገደብበትና ከዚህ አኳያ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት የተቀመጡት መሠረታዊ መብቶች እንደ ማንኛውም ዜጋ የሚከበርላቸው ስለመሆኑ በሕገ መንግሥቱና አገሪቷ ካፀደቀቻቸው አለም አቀፍ የሰበአዊ መብት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች የዋስትናውን ጥያቄ ውድቅ ሲያደርጉ በሌሎች ሕጎች የተመለከቱትን የመታከም መብቷን ውድቅ ያላደረጉና አሁንም ቢሆን ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላትን የመጠየቅ መብታቸውን የሚነካባቸው ባለመሆኑ አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ የተከሰሱበት ወንጀል ዋስትናን አያስጠብቅም በማለት ያቀረብኩትን የመታከም መብቴን ውድቅ አድርገውብኛል በማለት ያቀረቡት አቤቱታ አግባብነት የለውም ብለናል፡፡

በመሆኑም አመልካች በበታች ፍርድ ቤት አቅርበውት የነበረው አቤቱታ የዋስትና ጥያቄ የነበረ በመሆኑ ፍርድ ቤቶች የተከሰሱበት ወንጀል ዋስትና ይከለክላል በማለት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ በመሆኑና ጉዳዩን የሚመለከተውን አካል በመጠየቅ የመታከም መብታቸውን የሚነካ ባለመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶችም ከላይ በተመለከተው መሠረት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የኦሮሚያ ብሔ/ክ/መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ.ቁ. 129766 በቀን 05-09-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 122550 በቀን 02-9-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 03345 በቀን 08-7-2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በአዋጅ ቁ. 434/97 አንቀጽ 4/1/ እና በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 75/2/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች የተከሰሱበት ወንጀል የዋስትና መብት አያስጠብቅም መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

ቤ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ 48956

መጋቢት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** 1. ወ/ሮ ፍኖተፃድቅ አበራ
2. አቶ ሳመሶን አበራ } ከጠበቃ ማሩ ባዘዘው ጋር ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የጉምሩክ ዐቃቤ ሕግ የቀረበ የለም ከተባለ በኂላ መኮንን አየለ ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰምተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት የቀረበው የከፍተኛው ፍርድ ቤት በአንደኛ አመልካችና በሁለተኛ አመልካች እያንዳንዳቸው ለመኪናው ሊከፈል የሚገባ የነበረውን የቀረጥና የታክስ ግምት ብር 332,005.19 (ሶስት መቶ ሰላሣ ሁለት ሺህ አምስት ብር ከአሥራ ዘጠኝ ሣንቲም) እንዲቀጣ የመወሰነን ህጋዊነትና አግባብነት ለማጣራት ተብሎ ነው፡፡ አመልካቾች ፍርድ ቤቱ በሁለታችን ላይ የጣለው የገንዘብ ቅጣት ለመኪናው ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ እጥፍ በመሆኑ አዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 73ን የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ አመልካቾች ወንጀል በመፈፀማቸው ጥፋተኛ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ስለዚህ ቅጣት የሚወሰነው በአንዳንዳቸው ላይ በመሆኑና የበታች ፍርድ ቤቶች በእያንዳንዳቸው ላይ በህጉ የተመለከተውን ዝቅተኛ የገንዘብ ቅጣት እያንዳንዳቸው እንዲከፍሉ የተሰጠው ውሣኔ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን ስንመረምረው አመልካች በወንጀል ህግ ቁጥር 32/1/ሀ እና አዋጅ ቁጥር 60/89 እንደተሻሻለ አንቀጽ 73(1) በመተላለፍ ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኞች መሆናቸውን ተረድተናል፡፡ አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ በእስራትና በገንዘብ መቀጮ በጣምራ የሚያስቀጣ ወንጀል ነው፡፡ ቅጣት የሚወሰነው የእያንዳንዱን ጥፋተኛ ግላዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደሆነና ወንጀልና የወንጀል ቅጣት ግላዊ መሆናቸውንና ከአንዱ ወደ ሌላው የማይተላለፍ መሆኑ በወንጀል ህግ አንቀጽ 41 ከተደነገገው መሠረታዊ መርህ ለመረዳት የሚቻል ሲሆን የበታች ፍርድ ቤቶችም የገንዘብ መቀጮ የወሰኑት በአንደኛ አመልካች ላይ ያሉትን የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችና በህጉ የተቀመጠውን ዝቅተኛ የገንዘብ መቀጮ መነሻ በማድረግና በማገናዘብ ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች በሁለተኛ አመልካች ላይ የገንዘብ መቀጮ የወሰኑት በሁለተኛው አመልካች ላይ ያሉ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን መነሻ በማድረግና በማገናዘብ ነው፡ ስለሆነም እያንዳንዳቸው ጥፋተኛ ሆነው የተገኙበት የህግ ድንጋጌ በወቅቱ

ለመንግሥት ይከፈል የነበረውን ቀረጥና ታክስ ገንዘብ መነሻ በማድረግ ፍርድ ቤቱ ሊወስን የሚችል መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡

ወንጀል በመፈፀሙ የሚወሰነው የገንዘብ ቅጣት በወንጀል ሕጉ የቅጣት አወሳሰን መርሆችን መሠረት በማድረግ የሚወሰን ነው፡፡ በወንጀል ጥፋተኛ በተባሉ ሰዎች ላይ የሚጣለው የገንዘብ መቀጮ በፍታብሔር መንግሥት ሣይከፈለው የቀረበን ቀረጥና ታክስ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍል ለማድረግ ከሚቀርብ ክስና ከሚሰጥ ውሳኔ በእጅጉ የተለየ ነው፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካቾች እያንዳንዳቸው ለመኪናው ይከፈል የነበረውን ቀረጥና ታክስ መከፈል ያለበት ገንዘብ ለፈፀሙት ወንጀል በመቀጫነት እንዲከፍሉ የሰጡት ውሣኔ የወንጀል ህጉን መሠረታዊ የቅጣት አወሳሰን መርሆች የተከተለና መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ በወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195(2)(ለ-2) መሠረት አጽንተነዋል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ፍርድና ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ፍርዱ የፀና መሆኑን አውቆ እንዲያስፈጽም ለሚመለከተው ክፍል የውሣኔው ግልባጭ ይተላለፍ

ይህ ፍርድ  በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

የሰ/መ/ቁ. 58514

ጥር 9 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ሐንካራ ሐርቃ ሃያሞ

**ተጠሪ፡-** የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የሥነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ህግ

መርዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የአሁኑ አመልካች በወንጀል የተከሰሱበትን ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ባለቤት ሆኖ መገኘት ጉዳይ በሚመለከት በይግባኝ ደረጃ ቀርቦለት የተመለከተው የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰጠው የጥፋተኛነት ፍርድ እና የቅጣት ውሣኔ ላይ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ተብሎ የቀረበውን ክርክር በመጨረሻ ያየው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 39818 በ22/10/2002 የጥፋተኛነቱም ሆነ የቅጣት ውሣኔው እንዲሁም የንብረት መወረስ ውሣኔው በአግባቡ ስለሆነ ፀንቷል በሚል የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በሚል በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10(3) መሠረት የቀረበ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶች ሐምሌ 19 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት የሚያስቀርብ ነው በመባሉ ማመልከቻው ለተጠሪው ተልኮ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በ08/03/2003 ጽፎ ባቀረበው መልስ በዚህ ጉዳይ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ሆነ ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ምንም አይነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም፡፡ አመልካች ለሰበር ባቀረቡት ማመልከቻ ላይ በሥር ፍ/ቤት የህግ ስህተት ተፈጽሟል ብለው የገለጿቸው ምክንያቶች ስለማስረጃ ምዘናና ከጥፋተኛነቱ ውሣኔ በኋላ ስላሉ ጥቃቅን ፍሬ ነገሮች የሚመለከቱ እንጅ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለመኖሩ የሚያስረዱ አይደሉም፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት እንዲህ አይነት የማስረጃ እና የፍሬ ነገር ክርክሮችን በሕጉ የማየት ስልጣን የለውም በማለት የሰበር አቤቱታው ውድቅ ሆኖ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ እንዲፀና ጠይቋል፡፡



www.chilot.me

በአመልካች ጠበቃ በኩልም የመልስ መልስ መቅረቡን መዝገቡ ያሳያል፡፡

ይህ ችሎትም የአሁኑ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 419 ላይ የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ በእጃቸው ገብቶ ተገኝቷል ተብለው በወንጀል የተከሰሱባቸውን ጉዳዮች በሚመለከት በሥር ፍ/ቤት ታይቶ በአመልካች ላይ የተሰጠው የጥፋተኛነትም ሆነ የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን ሲመረምር መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት የሚያስችል ምክንያት የለም፡፡ በተለይ ቅጣቱን በተመለከተ የአሁኑ አመልካች በመንግሥት ሥራ ላይ ሆነው ከብር 182 የወር ደመወዝ ተነስተው በጭማሪና በዕድገት ብር 928 የወር ደመወዝ ላይ ደርሰው በዚህ መጠነኛ ደመወዝ ራሣቸውን ሲያስተዳድሩ እንደቆዩና ባለቤታቸውም ሌላ ህጋዊ ገቢ እንዳልነበራቸው እየተገለፀ ምንጩ ያልታወቀ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ በእጃቸው ገብቶ መገኘቱና ከፍተኛ ግምት ያለው ንብረት ባለቤት ሆነው መገኘታቸው ነገሩን ከባድ ስለሚያደርገው በዚሁ በሕጉ ልዩ ክፍል ከተደነገገው እስከ አምስት አመት ከሚደርሰው የጽኑ እስራት ቅጣት በአራት አመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጡ መወሰኑ ያለአግባብ ቅጣቱ ከብዶባቸዋል ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በመ/ቁ 39816 በ22/10/2002 የሰጠው ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2/ለ/2) መሠረት ፀንቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡***

ራ/ታ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 69899

ሐምሌ 29 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፊሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** 1. ዮሴፍ ሀይሉ ጠቅላላ ንግድ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ አቶ መላኩ ወልደማሪያም- ቀረቡ

2. አቶ ዮሴፍ ሃይሉ - ጠበቃ አቶ መላኩ ወልደማሪያም - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ዓቃቤ ህግ ዓቃቤ ሕግ አቶ ሲሳይ ተድላ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ አመልካቾች የወንጀል ህግ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 15 የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ እና አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 1ን በመተላለፍ አምድሁን ጠቅላላ ንግድ ኃላፊነቱ የግል ማህበር ብቸኛ አስመጭና አከፋፋይ የሆነበትንና ኮሪያ አገር ያለው ኦርዮን ኮርፖሬሽን የንግድ ድርጅት የሚጠቀምበትን “ORIQN” የሚል የንግድ ምልክት ያለበትን 639 ካርቶን ማስቲካዎች በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16/17 የቤት ቁጥር 479 አከማችቶ የተገኘ በመሆኑ ህጋዊ ጥበቃ የተሰጠውን የንግድ ምልክት በማስመሰል ተጠቃሚውን ለማሳሳት የሚናችል ዕቃ የመያዝና የመሸጥ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ያቀረበው ክስ ነው፡፡

አመልካቾች የወንጀል ተግባር አልፈፀምንም በማለት በመከራከራቸው ተጠሪ “ORION” የሚለው የንግድ ምልክት በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የተመዘገበ መሆኑና አምድሁን ጠቅላላ ንግድ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ብቸኛ አስመጭና አከፋፋይ መሆኑንና አመልካቾች ይዘው የተገኙት ማስቲካ “ORION” ከሚለው ማስቲካ ጋር ተመሳሳይነት ያለው መሆኑን ያስረዱልኛል በማለት የጽሑፍና የሰው ማስረጃ አቅርቧል፡፡ አመልካቾች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ፍርድ ቤቱ ብይን ሰጥቶ አመልካቾች ORIQN የሚለው ማስቲካ ህብረተሰቡ ለይቶ የሚያውቀውና  መሳሳትና መሳከር የማይፈጥር መሆኑን ያስረዱልናል በማለት የሰው ምስክሮች አቅርበው አስመስክረዋል እንደዚሁም ማስቲካውን ከቻይና አገር በባንክ በኩል በተከፈተ ሌተር ኦፍ

ክሬዲት ዋጋ ከፍለው ማስገባታቸውና የጉምሩክ ቀረጥና ፎርማሊቲ አሟልተው ወደ አገር ውስጥ ያስገቡ መሆኑን ያሳያሉ ያሉቸውን የሰነድ ማስረጃዎችን በመከላከያ ማስረጃነት አቅርበዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረና ከመከሩ በኋላ አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 1ን በመተላለፍ ህጋዊ ጥበቃ ባለው የንግድ ምልክት ላይ ወንጀል የፈፀሙ ናቸው በማለት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከሰማ በኋላ አንደኛ አመልካች በብር 15,000 /አስራ አምስት ሺህ ብር/ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ ሁለተኛው አመልካች በአምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የወሰነ ሲሆን አመልካቾች ይዘው የተገኙት 639 ካርቶን ማስቲካና 23,000 ፖኬት ማስቲካ ወደ ገበያ እንዳይሰራጩ ይወገዱ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካቾች ሰኔ 7 ቀን 2003 ዓ.ም በፃፈው የሰበር አቤቱታ የንግድ ምልክቱ አላግባብ ጥቅም ላይ ውሎበታል የተባለው ድርጅትና በአገር ውስጥ ያለው ብቸኛ አከፋፋይ “ORION” የሚለውን የንግድ ምልክት በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ያስመዘገቡት አዋጅ ቁጥር 501/98 ከመውጣቱ በፊት ነው፡፡ ይህንን የንግድ ምልክት አዋጅ ቁጥር 501/98 ወጥቶ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ በአዋጅ አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 በሚደነግገው መሠረት ከአሥራ ስምንት ወራት ውስጥ አላስመዘገቡም፡፡ የግል ተበዳይ በአዋጅ በተደነገገው መሠረት ሳያስመዘግቡ ለአራት ዓመት ያህል ከቆዩ በኋላ ህጋዊ ጥበቃ የተሰጠው የንግድ ምልክታችንን አላግባብ ተጠቅመዋል በማለት ክስ ለማቅረብ የሚችሉበት ሁኔታ የለው፡፡ ስለሆነም “ORION” የሚለው የንግድ ምልክት አዋጅ ቁጥር 501/98 ከመውጣቱ በፊት መመዝገቡ የአዋጁን አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1፣ አንቀጽ 48 እና አንቀጽ 29 አንቀጽ 2 መሥፈርት የሚያሟላና ሶስተኛ ወገኖች በሃላፊነት የማያስጠይቅና ውጤት የሌለው ሆኖ እያለ በወንጀል ጥፋተኛ ተብለን መቀጣታችን መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ በሌላ በኩል አመልካቾች ለማጭበርበርና ተጠቃሚውን ለማሳሳት ሆነ ብለንና አስበን የፈፀምነው ተግባር የለም፡፡ ስለዚህ ማስቲካ ከቻይና አገር በማስገባታችን በወንጀል የሚያስጠይቀን አይደለም እንጅ በወንጀል የምንጠየቅ ከሆነም በቸልተኝነት መሆን ሲገባው ሆነ ብለንና አስበን እንደፈፀምን ተቆጥሮ ጥፋተኛ ተብለን መቀጣታችን መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ ሐምሌ 15 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው መልስ ORION የሚለው የንግድ ምልክት የተመዘገበና ህጋዊ ጥበቃ የተሰጠው መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 320/95 ሥልጣን የተሰጠው የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በጽሑፍ አረጋግጧል፡፡ አመልካቾች ተጠቃሚውን የሚያሳስትና የማይሳክር እንደዚሁም በአገር ውስጥ የተመዘገበና ህጋዊ ጥበቃ የሌለው QRIQN የሚል የንግድ ምልክት የለው ማስቲካ በአገር ውስጥ ሚያሰራው ተገኝተዋል፡፡ አመልካቾች QRIQN የሚለውን ማስቲካ ከቻይና አገር በባንክ በተከፈተ ሌተር ኦፍ ክሬዲት የውጭ ምንዛሬ ተፈቅዶላቸው ከፍለው ማስመጣታቸውና ማስቲካውን የጉምሩክ ቀረጥና ፎርማሊቲ አሟልተው ወደ አገር ውስጥ ማስገባታቸው አድራጐታቸው ወንጀል መሆኑን የሚያስቀረው ባለመሆኑ የአመልካቾች ክርክር የህግ መሠረት የለውም፡፡ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 42 ንዑስ

አንቀጽ 1ን በመተላለፍ ህጋዊ ጥበቃ በተሰጠው የንግድ ምልክት ላይ ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኛ ናቸው በማለት የሰጡት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን አንደኛ አመልካችና ሁለተኛ አመልካች በወንጀል ተጠያቂ የሚሆኑባቸው የወንጀል ህግ መርሆዎች የየራሳቸው ልዩ ባህሪያት ያላቸው በመሆኑ በዚሁ አንፃር ጉዳዩን ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. አንደኛ አመልካች የንግድ ድርጅት ሲሆን ሁለተኛ አመልካች የተፈጥሮ ሰው ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 501/98 በህግ ወለድ ሰዎች ላይ የወንጀል ሀላፊነትና ተጠያቂነትን የሚደነግግ የህግ ማዕቀፍ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ አከራካሪ በመሆኑ በመጀመሪያ የከፍተኛው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በሁለተኛው አመልካች ላይ የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ተገቢነትን ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አንድ ሰው ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ተጠያቂ የሚሆነው የግዙፍ ተግባር የህግና የሃሳብ ሁኔታ ተሟልተው ሲገኙ እንደሆነ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡ ሁለተኛ አመልካች የተከሰሱትና ጥፋተኛ የተባሉት በአዋጅ ቁጥር 501/98 ህጋዊ እውቅናና ጥበቃ የተሰጠውን የንግድ ምልክት የሚጐዳ ተጠቃሚውን የሚያሳስትና የሚያሳክር ተግባር ሆን ብለውና አስበው ፈጽመዋል ተብለው እንደሆነ ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ ሁለተኛውን አመልካች በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌን በመተላለፍ በወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ በመጀመሪያ “ORIQN” የሚል የንግድ ምልክት ያላቸውንና በኮሪያ አገር የሚመረቱ ምርቶች ብቸኛ አስመጭ ነኝ የሚለው “አምደሁን ጠቅላላ ንግድ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር “ORION” የሚለው የንግድ ምልክት የአዋጅ ቁጥር 501/98 ህጋዊ ጥበቃና እውቅና ለማግኘት የሚያስችለውን የህግ ሁኔታ /ህጋዊ መስፈርት/ ያሟላ ለመሆኑ ተጠሪ በቂ ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት ግዴታና ሃላፊነቱን ተወጥቷል ወይስ አልተወጣም የሚለውን ነጥብ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡

ይህንን ነጥብ ለማጣራት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን መዝገብ አስቀርበናል፡፡ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ከፃፈው የሰነድ ማስረጃ እንደተረዳነው ጽ/ቤቱ ORION የሚለውን የንግድ ምልክት ለመመዝገብ የቀረበውን አቤቱታ በአዲስ ዘመንና በሄራልድ ጋዜጣ አውጥቶ ተቃዋሚ ባለመቅረቡ የንግድ ምልክቱን መጋቢት 12 ቀን 1998 ዓ.ም በመመዝገብ የምዝገባ ሰርተፊኬት ሰጥቷል፡፡ ጽ/ቤቱ በሰጠው የምዝገባ ሰርተፍኬት የንግድ ምልክቱ እስከ መጋቢት 11 ቀን 2004 ዓ.ም ህጋዊ ጥበቃ እንደሚኖረው የሚገልጽ ቢሆንም ORION የሚለው የንግድ ምልክት ከተመዘገበ በኂላ አዋጅ ቁጥር 501/98ን ህግ አውጭው በማወጅ፣ አዋጁ ከሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ ውሏል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተቀመጡ የንግድ ምልክቶች ይህ አዋጅ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በአስራ አምስት ወራት ጊዜ ውስጥ መመዘገብ ይኖርባቸዋል በሚል መንገድ በመደንገድ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የንግድ ምልክት ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት አቅርበው በማስመዝገብ የባለሃብትነት ሰርተፊኬት አግኝተው የነበሩ ሰዎች አዋጁ ወጥቶ ሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ ባሉት አሥራ አምስት ወራት የማስመዝገብ ግዴታና ሃላፊነት እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡

ይህ የአዋጁ ድንጋጌ ፈቃጅነት ያለው የህግ ድንጋጌ ያለመሆኑን ከድንጋጌው አቀራረጽ፣ መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በተለይም የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ የእንግሊዝኛው ቅጅ “Trade marks deposited before the entry into force of this proclamation shall be submitted for registration with in eighteen month beginning from the entry in to force of this proclamation” በሚል መንገድ የተቀረፀና የተደነገገ

መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ አዋጅ ቁጥር 501/98 ከመውጣቱ በፊት የንግድ ምልክት ያስመዘገበ ማናቸውም ሰው ህግ አውጭው በአዋጁ የሰጠውን ጥበቃና ከለላ ለማግኘትና አዋጁን መሠረት በማድረግ የመብት ጥያቄ ለማቅረብ በመጀመሪያ ህግ አውጭው በአዋጅ ቁጥር 501/98 የደነገጋቸውን አስገዳጅ የህግ ድንጋጌዎች በመፈፀም ህጋዊ ሁኔታዎችን አሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡ ህግ አውጭው በአዋጅ ቁጥር 501/98 አስገዳጅነት ባለው ሁኔታ የደነገጋቸው ድንጋጌዎች በአዋጁ መሠረት መብታቸው እንዲከበርላቸው የሚጠይቁ የህግ ወይም የተፈጥሮ ሰዎች ብቻ ሳይሆን አዋጁን የማስፈፀም ሥልጣንና ሀላፊነት በተሰጠው የመንግስት አካል ማለትም የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ላይ ገዥነትና አስገዳጅነት ያላቸው ናቸው፡፡ ይኸም በመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ጽ/ቤቱ ለግል ተበዳይ ለስድስት ዓመት ህጋዊ ጥበቃ እንዳለው በመግለጽ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ሠቶት በነበረው የምዝገባ ሠርተፍኬት ላይ የበላይነትና ገዥነት ያለውና የግል ተበዳይ የንግድ ምልክቱን አዋጁ ወጥቶ ሥራ ላይ ከዋለ በኂላ በአሥራ ስምንት ወራት ውስጥ እንደገና እንዲያስመዘግብ የሚያስገድድ ድንጋጌ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የግል ተበዳይ የንግድ ምልክቱን አዋጅ ቁጥር 501/98 ከመውጣቱ በፊት ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ከመጋቢት 12 ቀን 1998 ዓ.ም እስከ መጋቢት 11 ቀን 2004 ዓ.ም የሚያገለግል የምዝገባ ሰርተፍኬት ተሰጥቶት የነበረ መሆኑን የሚያስረዱ የሰነድ ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡ ከዚህ ውጭ ተጠሪ በአዋጁ ቁጥር 501/98 ህጋዊ ጥበቃና ከለላ ለማግኘት ህግ አውጭው በአዋጁ አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን አስገዳጅ መሥፈርት ያሟላና በአዋጅ ቀጥር 501/98 አንቀጽ 45 እና አንቀጽ 16 የተደነገጉትን ህጋዊ ሥርዓቶች በማሟላት በአስራ ስምንት ወራት ውስጥ የተመዘገበ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ይኸም በመሆኑ የግል ተበዳይ አምዱሁን ጠቅላላ ንግድ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በኢትዮጵያ ግዛት ብቸኛ አስመጭና አከፋፋይ ነኝ የሚለው “ORION” የሚለው የንግድ ምልክት በአዋጅ ቁጥር 501/98 ህጋዊ ጥበቃና ከለላ ለማግኘት ህጋዊ ሁኔታዎችን ያሟላ መሆኑን ተጠሪ በበቂ ማስረጃ አላረጋገጠም፡፡ ሁለተኛውን አመልካች በወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ አስፈላጊ የሆነው ህጋዊ ሁኔታ ማለትም ከአዋጅ ቁጥር 502/98 በፊት የነበረው ምዝገባና ሠርተፍኬት አዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 በአስገዳጅነት በደነገገው የጊዜ ገደብ ማለትም አዋጁ ወጥቶ ሥራ ላይ መዋል ከጀመረበት ቀን አንስቶ በአስራ ስምንት ወራት ውስጥ የንግድ ምልክቱን ያስመዘገበ መሆኑ በበቂ ማስረጃ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ሶስተኛ ወገኖችን በአዋጅ ቁጥር 501/98 ለንግድ ምልክቱ የተሰጠውን ህጋዊ እውቅና እና ጥበቃ በመተላለፍ የወንጀል ድርጊት ፈጽመዋል ብሎ ለመክሰስም ሆነ በወንጀል ጥፋተኛ ብሎ ለመቅጣት አይቻልም፡፡ በመሆኑም ሁለተኛ አመልካች በወንጀል ህግ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 2 በሚደነግገውና ወንጀል ለማቋቋም አስፈላጊ በመሆናቸው ከሚዘረዝራቸው አስፈላጊ ጉዳዮች ሁለተኛ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን አስገዳጅ መስፈርት ያሟላና ህጋዊ ጥበቃ የተሰጠው የንግድ ምልክትን የሚጥስ ግዙፍ ተግባር የፈፀመ መሆኑን ተጠሪ የማስረዳት ሸክሙን ሳይወጣ የግል ተበዳይ አዋጅ ቁጥር 501/98 ከመውጣቱ በፊት የንግድ ምልክቱ መመዝገቡን ብቻ በመመልከት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 1 የተደነገገውን አስገዳጅ መስፈርት ያላሟላና ህጋዊ ጥበቃ የተሰጠውን የንግድ ምልክት የሚጥስ ግዙፍ ተግባር የፈፀመ መሆኑን ተጠሪ የማስረዳት ሸክሙን ሳይወጣ የግል ተበዳይ አዋጅ ቁጥር 501/98 ከመውጣቱ በፊት የንግድ ምልክቱ መመዝገቡን ብቻ በመመልከት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 አስገዳጅ

የህግ ድንጋጌ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 2 እና የወንጀል ህግ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2ን የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. የአንደኛው አመልካች የወንጀል ተጠያቂነት ሁለተኛው ፓራግራፍ ከተዘረዘሩት ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የአንደኛው አመልካች ሥራ አስኪያጅ የሆኑት ሁለተኛ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን አስገዳጅ መስፈርት በማሟላት የተመዘገበ "የንግድ ምልክት"ን የሚጉዳ የወንጀል ተግባር የፈፀመ መሆኑን ተጠሪ የማስረዳት ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑን ይኸ ሰበር ችሎት አረጋግጧል፡፡ ይኸም በመሆኑ አንደኛ አመልካች በወንጀል በሃላፊነት የሚያስጠይቅ ተግባር ፈጽሟል ከሚል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ በወንጀል ህግ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 ሁለተኛው ፓራግራፍ የተደነገገውን ሁኔታ የማያሟላ በመሆኑ በአንደኛ አመልካች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ቀሪ የሚሆን እንደሆነ ከወንጀል ህግ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 ሁለተኛው ፓራግራፍ መሠረታዊ ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ የገለጽነው ምክንያት እንደተጠበቀ ሆኖ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአንደኛ አመልካች ላይ አዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጸ 1 የተደነገገውን በመተላለፍ የወንጀል ድርጊት ፈጽሟል በማለት የወሰኑት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የሚያስነሳው የህግ ጥያቄ አለ፡፡ ይኸውም የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በሁሉም የወንጀል ድርጊቶች ተጠያቂና ሀላፊ እንደማይሆን የወንጀል ህግ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 "በህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የመንግስት አስተዳደር አካላትን ሳይጨምር በህግ በግልጽ በተደነገገ ጊዜ በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ አነሳሽነት ወይም በአባሪነት በወንጀል ሊቀጣ ይችላል" የማለት የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ የሚሆነው ይህንኑ የሚደነግግ ግልጽ የህግ ድንጋጌ በሚኖርበት ጊዜ ብቻ እንደሆነ ገዥነት ያለውን መርህ በግልጽ ያስቀመጠ በመሆኑ ነው፡፡

ህግ አውጭው በወንጀል ህጉ ወይም በሌሎች የህግ ማዕቀፎች ለምሳሌ በወንጀል ህጉና በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ በወንጀልነት የተፈረጀው አድራጐት የህግ ሰውነት በተሰጠው ድርጅት የተፈፀመ ሲሆን የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በወንጀል የሚጠየቅ ስለመሆኑ በግልጽ የሚደነግግ ድንጋጌ በማወጅ ህግ ወለድ ሰዎች በወንጀል ተጠያቂና ሀላፊ የሚሆኑበትን ሥርዓት እንደሚዘረጋ አግባብነት ያላቸውን የህግ ማዕቀፎች ይዘትና አቀራረጽ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 501/98 የተደነገገውን የተላለፈ የንግድ ህግ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች የወንጀል ተጠያቂና ሃላፊ የሚሆኑ መሆኑን የሚደነግግ ግልጽ የህግ ድንጋጌ የለም፡፡ ተጠሪ የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 1 "ማንኛውም ሰው" የሚለው አገላለጽ የተፈጥሮ ሰውና የህግ ሰውነት ያላቸውን ድርጅቶች የሚያካትት ስለሆነ አንደኛ አመልካች በወንጀል መጠየቁ ተገቢነው በማለት ያቀረበው ክርክር በወንጀል ህግ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን መሠረታዊ መርህ ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ አንደኛ አመልካች ላይ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የወንጀል ህግ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረታዊ መርህን የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡



www.chilot.me

ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው የህግ ምክንያቶች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአመልካቾች ላይ የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአመልካቾች ላይ የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2/ለ/1 መሠረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. ሁለተኛ አመልካች ከተከሰሰበት ወንጀል በነፃ የተሰናበተ በመሆኑ ከእስር እንዲለቀው ለማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡
3. አንደኛ አመልካችና ሁለተኛ አመልካች የወንጀል ሃላፊነትና ተጠያቂነት የሌለባቸው በመሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አንደኛ አመልካች ከቻይና አገር ያስገባው 639 ካርቶንና 23,000 ፓኬት QRIQN የሚል የንግድ ምልክት ያለው ማስቲካ እንዲወገድ የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
4. በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተያዘውና አመልካቾች ከቻይና አገር ያስገቡት ማስቲካ እንዲለቀቅ ወስነናል፡፡
5. ይኽ ውሣኔ መብቴ ተጥሷል የሚል ወገን ህጋዊ ሁኔታዎችን በማሟላት ህጋዊ ጥበቃና ከለላ እንዲሰጠው ጥያቄ ከማቅረብ የሚገደብ አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
6. በትውስት የመጣው መዝገብ ይመለስ ነው፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 55649

መጋቢት 06 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ኤሊያስ ዲጋ ጉዳይ የውብነሽ ማንደፍሮ

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ አሻሽሎ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ ክሱም በሁለት ምድብ የተከፈለ ሆኖ የ1ኛው ክስ ይዘትም ፡- አመልካች በ1996 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/3/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በአሽከርካሪነት ሙያው የሌላውን ሕይወትና ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ እያለበት ጥር 20 ቀን 2000 ዓ/ም ከቀኑ 11፡20 ሲሆን የሰሌዳ ቅጥሩ 3-41980 አ.አ መኪና ይዞ ከቦሌ አየር መንገድ ወደ ዮሴፍ ቤተ ክርስቲያን አቅጣጫ እያሽከረከረ በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01 ልዩ ቦታው ቦሌ ሚካኤል ከተባለ ቦታ ሲደርስ ግልፅ የሆነ ደንብ ተላልፎ ሰው በማይጫንበት አይሱዚ የጭነት መኪና የእቃ መጫኛ ላይ ተጭኖ የነበረውን ጋሻው ተሾመ የተባለውን ሰው ከመኪናው ላይ ጥሎ ሕይወቱ እንዲያልፍ በማድረጉ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል የሚል ሲሆን 2ኛው ክስ ደግሞ ከላይ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ ከመኪናው ወድቆ ጉዳት የደረሰበትን ሰው አፋጣኝ ህክምና እንዲያገኝ ሳያደርግ ከወደቀበት ጥሎት በመሄድ በአደጋ ላይ ያለን ሰው ባለመርዳቱ በ1996 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 575(2(ሀ)) ስር የተመለከተውን ተላልፏል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም የክስ ማመልከቻው ደርሶት ክሱን እንዲረዳው ከተደረገ በኂላ ስለእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቅ በክሱ ላይ ተቃውሞ የሌለው መሆኑን ገልፆ የድርጊቱን አፈፃፀም በተመለከተ ግን የክህደት ቃሉን ሰጥቷል፡፡ ዐቃቤ ሕግ በበኩሉ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ከዚህም በሁዋላ አመልካች የወንጀል ድርጊቶችን ስለመፈፀሙ አቃቤ ሕግ በማስረጃዎቹ ያስረዳበት መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ታምኖበት ይህንኑ እንዲያስተባብል ዕድል ተሰጥቶት አመልካች በሌላ የመከላከያ ማስረጃ ያሰማ ሲሆን የሥር ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በመከላከያ ማስረጃዎቹ የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ያላስተባበለ መሆኑን በመጥቀስ በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሰው በቀረቡት ሁለቱም ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ አድርጎ ወስኗል፡፡ ቅጣቱን በተመለከተም በ1ኛው ክስ በስድስት አመት እና በብር 10,000.00 በሁለተኛው ደግሞ በስድስት ወር ጽኑ እስራትና በብር 1000 በድምሩ በስድስት አመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራትና በብር 11,000.00 (አስራ አንድ ሺህ ብር) አመልካች



www.chilot.me

እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ይግባኙ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195/1/ መሠረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሚያዚያ 29 ቀን 2002 ዓ/ም በተጻፈ አምስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፤ አመልካች የወንጀል ድርጊቶቹን ስለመፈፀሙ ዐቃቤ ሕግ በሕጉ አግባብ አላስረዳም፣ የመከላከያ ማስረጃው ውድቅ የተደረገው ያላግባብ ነው በማለት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ እንዲሰረዝ ወይም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ድንጋጌ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543/2/ ነው ተብሎ የቅጣት ውሳኔው አመልካች የታሰረበትን ጊዜ በቂ በማድረግ እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ የጽሑፍ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች በ1ኛው ክስ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/3/ ስር ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ ባግበቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት የሚታይ ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ይህንኑ ጭብጥ ምላሽ ከመስጠታችን በፊት ግን የአመልካች ጠበቃ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን ፈፅሟል ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተደረሰው ድምዳሜ ከማስረጃ አረዳድና አፈፃፀም አንፃር ስህተት ያለበት ነው በማለት ያቀረቡትን ቅሬታ ከዚህ ሰበር ችሎት ሥልጣን አንፃር ያለውን ተገቢነት ተመልክተናል፡፡ እንደሚታወቀው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት የተሰጠው ስልጣን በማናቸው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖሩ ሲረጋገጥ ይህንኑ ማረም ነው፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለውም የማስረጃ ምዘና ጉዳይ በሰበር ችሎቱ ስልጣን ስር የማይወድቅ መሆኑን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአመልካች ጠበቃ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የማስረጃ አረዳድና አፈፃጸም ግድፈት ተፈፅሟል፣ ይህም የወንጀል ሕጉን አንቀፅ 23/4/ የሚፃረር ነው በማለት በሰበር ማመልከቻው ላይ የዘረዘሩ ቢሆንም በዚህ ረገድ የቀረበው የቅሬታው አጠቃላይ ይዘት ሲታይ ግን የማስረጃ ምዘናን ጉዳይ የሚመለከት በመሆኑ በዚህ ሰበር ችሎት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበው ቅሬታ የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ባለመሆኑ አልፈነዋል፡፡

ወደዋናው ጭብጥ ስንመለስ አመልካች በ1ኛው ክስ ጥፋተኛ የተባለው እቃ በሚጫንበት መኪና ሰው ጭኖ ሲሄድ ሰው ውድቆ እንዲሞት አድርጓል፣ ይህም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543(3) ስር የተመለከተውን የወንጀል ማቋቋሚያ ነጥቦችን የሚያሟላ ነው በሚል ነው፡፡

በሰበር ችሎት ከላይ የተጠቀሰው አጠቃላይ የክርክሩ ሂደት አግባብ ካላቸው የወንጀል ሕግ ድንጋጌ እና የአመልካች ጠበቃና ተጠሪ ለዚህ ችሎት በጽሑፍ ካቀረቡት ክርክር እንዲሁም የስር ፍርድ ቤትን ዋና መዝገብ በማስቀረብ ጉዳዩን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ ተመልክቷል፡፡ በበታች ፍርድ ቤቶች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገርና ከተወሰነው ውሣኔ አንፃርም አመልካችን በወንጀል ጥፋተኛ ለማለት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 543/3/ የተጠቀሱት መስፈርቶች ተሟልተዋል? ወይስ አልተሟሉም? የሚለውን ነጥብ አጣርቷል፡፡ አመልካቹ በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ



www.chilot.me

የተቀጣ በመሆኑ በሕጉ ቸልተኝነት የሚያቋቁሙ መስፈርቶች መሟላት አለመሟላታቸውን ተመልክቷል፡፡ ይህ ችሎት በዋናነት የመረመረው የሕግ ነጥቡን ብቻ ቢሆንም የሕጉን አግባብነት በትክክል ለመመዘን በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች በቅደሚያ ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ጉዳዩ በሥር ፍ/ቤት ሲታይ አመልካች የሰሌዳ ቁጥር 3-41980 አ.አ መኪና ይዞ ከቦሌ አየር መንገድ ወደ ዮሴፍ ቤተ ክርስቲያን አቅጣጫ እያሽከረከረ በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01 ልዩ ቦታው ቦሌ ሚካኤል ከተባለ በታ ሲደርስ የእቃ መጫኛ ላይ ተጭኖ የነበረውን ጋሻው ተሾመ የተባለውን ሰው ከመኪናው ላይ ወድቆ ሕይወቱ እንዲያልፍ ማድረጉ በክሱ ተገለጿል፡፡ ይሁን እንጂ መኪናው የእቃ መጫኛ ሆኖ እያለ ሟችን አመልካች ያሳፈረው ስለመሆኑ በአቃቤ ሕግ ማስረጃ ስለመነገሩ የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ነገር የለም፡፡ በሌላ አገላለጽ ሟችን አመልካች አሳፍሮት ሲጓዝ እንደነበር የሚያሳይ የፍሬ ነገር ድምዳሜ የለም፡፡ ይህ በፍርዱ ሂደት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ሲሆን አመልካች ጥፋተኛ የተባለበትን ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ደግሞ ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 414/1996 የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2/ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ እንግዲህ አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ብሎ ለመወሰን ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተጣምረው መገኘት የግድ ይላል፡፡ ሕጋዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት አለው ተብሎ የተጠቀሰውን ድንጋጌ ለማቋቋም ሙሉ በሙሉ መሟላት ያለባቸው ነጥቦች ሲሆን ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉትን ደግሞ እንደየቅደምተከተላቸው ከድርጊት ማድረግ ወይም አለማድረግና ከሐሳብ ክፍል ጋር በሕጉ የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚመለከቱ ናቸው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ከላይ እንደተገለፀው አመልካች ሟች በመኪና ግጭት እንዲሞት ማድረጉ በፍሬ ነገር ደረጃ አመልካችን ሊያስጠይቅ የሚችለው በየትኛው ድንጋጌ ነው? የሚለው ነው፡፡ አመልካቹ በዓቃቤ ሕግ ክስ የመሰረተበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/3/"ን" በመተላለፍ ጋሻው ተሾመን ገድሏል በማለት ነው፡፡ በዚህ የሕግ ድንጋጌ አንድ ሰው ተጠያቂነት የሚከተልበት የሌላ ሰውን ሕይወት ፣ጤንነት ወይም ደኅንነት የመጠበቅ የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለበት እንደ ሕክሙና ባለሙያ ወይም አሽከርካሪ ያለ ሰው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎችን የገደለ፣ ወይም ወንጀሉን የፈፀመው ግልፅ የሆነ ደንብ /መመሪያን/ ተላልፎ እንደሆነ ወይም የሚያሰክሩ ወይም የሚያፈዙ ንጥረ ነገሮችን ወይም መጠጦችን በመውሰዱ እራሱን ከኃላፊነት ነጻ በሚያወጣ ሁኔታ ውስጥ ካስገባ በኋላ በቸልተኝነት ሰው የገደለ እንደሆነ ስለመሆኑ በሕጉ ተመልክቷል፡፡ የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች ከላይ የተመለከቱት ሲሆኑ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች የተጠቀሰውን ሕግ የሚያቋቁሙ መሆን አለመሆናቸው ለማረጋገጥ ሕጉ ቸልተኝነት አለ የሚለው ምን ምን ሁኔታዎች ሲሟሉ እንደሆነ መመልከቱ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 57 በግልፅ እንደሰፈረው "ለድርጊቱ ኃላፊ ሊሆን የሚገባው ሰው አስቦ ወይም በቸልተኝነት አንድ ወንጀል ካላደረገ በቀር በወንጀል ጥፋተኛ አይሆንም" በአንፃሩ አንድ ሰው "የፈፀመው ድርጊት በሕግ የሚያስቀጣ ቢሆንም ምንም ጥፋት ሳያደርግ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል ምክንያት ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ ነገር የተፈፀመ ወይም የደረሰ ሆኖ ሲገኝ በወንጀል ሕግ ሊፈረድበት አይገባውም በማለት የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 57/2/ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ



www.chilot.me

የሕጉ  አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው በአንድ ድርጊት ምክንያት አንድን ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ነው ለማለት ከሳሽ የሆነው ዓቃቤ ሕግ ድርጊቱ የተፈፀመው  ሆነ ተብሎ ወይም በቸልተኝነት መሆኑን ማስረዳት የሚጠበቅበት መሆኑን ነው፡፡ ድርጊቱ ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኝነት የተፈፀመ መሆኑ ማስረጃ ካላቀረበ ወይም ድርጊቱ ከአቅም በላይ ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ የተፈፀመ መሆኑን የሚያስረዳ  ማስረጃ በተከሣሽ በኩል ከቀረበ የተከሰሰውን ሰው በወንጀል ሕግ ጥፋተኛ ብሎ መፍረድ ከሕጉ መንፈስ ውጪ ነው፡፡ በወንጀል  የተከሰሰ ሰው ቸልተኛ ነበር? ወይስ አልበረም? የሚለው ጥያቄ በወንጀል ሕጉ በአንቀፅ 59 የሰፈረውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የሚወሰን ነው፡፡ የዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ አንድ አሁን ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው በመሆኑም የሕጉን ይዘት እንዳለ ማስቀመጡ ጠቃሚ ነው፡፡ ይኸው፡- ማንም ሰው በቸልተኝነት የወንጀል ተግባር አድርጓል የሚባለው፡-

ሀ) ድርጊቱ በወንጀል ሕግ የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ አይደርስም በሚል ግምት ወይም ባለመማዛዘን፣ ወይም

ለ) ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅ እያለበት ወይም እያቻለ ባለመገመት ወይም ባለማሰብ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ነው፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሠረት አንድ ሰው በቸልተኝነት ወንጀል ፈፅሟል የሚባለው ውጤቱን እያወቀ ውጤቱ አይደርስም ከሚል መነሻ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ወይም ደግሞ የወንጀል ውጤት የሚያስከትል መሆኑን ባያውቅም ውጤቱን ማወቅ ነበረበት ወይም ጥረት ቢያደርግ ውጤቱን ማወቅ ይችል ነበር ማለት ሲቻል ነው፡፡ በመሆኑም ቸልተኝነት አለ ለማለት ሕጉ የሚጠቀምበት ዋነኛ መስፈርት የተከሰሰው ሰው በድርጉቱና በውጠቱ መካከል ያለውን ግንኙነት አስመልክቶ ያለው ወይም ሊኖረው የሚገባው ግንዛቤ ነው፡፡ ድርጊቱን የፈፀመው ሰው የነበረው ዕውቀትና ግንዛቤ ወይም ሊኖረው የሚባው ዕውቀትና ግንዛቤ የሚመዘነው የሰውዬው ዕድሜ፣ ያለው የኑሮ ልምድ ፣ የትምህርት ደረጃው፣ ሥራውና የማህበራዊ ኑሮ ደረጃውን ግምት ውስጥ በማስገባት እንደሆነም የሕጉ አንቀፅ 59/1/ ይደነግጋል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች የሚከራከረው ሟችን ለእቃ ጭነት በሚያገለግለው መኪና እያወቀ ያልጫነው መሆኑንና ተሳፍሮ ያለ መሆኑንም ማወቅ ይችል የነበረ ስለመሆኑ አቃቤ በፍሬ ነገር ደረጃ ያላረጋገጠው መሆኑን  በመጥቀስ ሲሆን ይህ ያለመረጋገጡ ደግሞ ደንብ ቁጥር 279/1956 አንቀጽ 46/1/ ስር የተመለከተውን ጥፗል ለማለት አያስችልም በማለት ነው፡፡

ይሁን እንጂ ሟች አመልካች ሲያሽከረክር በነበረው የአይሱዚ መኪና ተገጭቶ ከዚህ አለም በሞት መለየቱ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ሲሆን ይህ ድርጊት አመልካችን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/3/ መሠረት ሊያስጠይቅ የሚችለው በአሽከርካሪነት ስራው ማድረግ የነበረበትን ጥንቃቄ ሳያደርግ ቀርቶ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 59/1/ የተገለፀውን ያሟላና የትራፊክ ደንቡን መጣሱ የተረጋገጠ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡ በመሆኑንም በክርክሩ ሂደት አመልካች  ሟችን በአይሱዚ መኪና በአንቀጽ 543/3/ ሥር ስለቸልተኝነት የተመለከተውን መመዘኛ በሚያሟላ መልኩ የጫነው መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 543/3/ ሥር ጥፋተኛ ሊባል የሚችልበትን የሕግ አግባብ አላገኘንም፡፡ ይልቁንም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ጉዳይ አመልካች በአሽከርካሪነት ስራው  ማድረግ የነበረበትን ጥንቃቄ ሳያደርግ ቆርቶ ሟችን በመግጨት ለሕልፈት የዳረገው

መሆኑን ሲሆን ይህም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543/2/ ሥር ተጠያቂነት የሚያስከትል ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በበታች ፍርድ ቤቶች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543/3/ ሥር ጥፋተኛ የተባለው ባለተረጋገጠ ፍሬ ነገር በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለአገኘን አመልካች ጥፋተኛ የተባለበትን ድንጋጌ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/113/2/ መሠረት በመለወጥ ድርጊቱ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543/2/ ሥር የሚሸፈንና የሚያስጠይቅ ነው ብለናል፡፡

ሌላው አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች ጥፋተኛ የተባለው የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 575/2/ሀ/ ሥር ሲሆን አመልካች በአሽከርካሪነት ሥራው ማድረግ የነበረበትን ጥንቃቄ ሳያደርግ ቀርቶ ሟችን ከገጨ በኋላ እርዳታ ሳያደርግለት መሸሹ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የሥር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑ በዚህ ረገድ በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አላገኘንበትም ፡፡

ከላይ እንደተገለጸው በ1ኛ ክስ ላይ አመልካች ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው ድንገጌ መለወጥ ያለበት መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ከዚሁ ተያይዞ መታየት ያለበት በዚህ ረገድ ሊጣል የሚገባው የቅጣት መጠን ነው፡፡ አመልካች ሊቀጣ የሚገባው በዚህ ችሎት ጥፋተኛ በተባለበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/2/ መሠረት ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ ጥፋተኛ የተባለ ሰው ሊቀጣ የሚገባው ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ሊደረስ በሚችል ቀላል እስራት እና ከሦስት ሺህ እስከ ስድስት ሺህ ብር ሊደርስ በሚችል መቀጮ ነው፡፡ ቅጣት ደግሞ ሊጣል የሚገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88/2/ ሥር የተመለከቱትን ነጥቦችን በማመዛዘን ነው፡፡ እኛም አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ያስመዘገባቸውን የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች (ሪኮርድ የሌለበትና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑን) ከድርጊቱ አፈጻጸምና ከቅጣት ዓላማ እንዲሁም ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመው ሲገኙ ቅጣት ከሚጣልበት አግባብ (ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184/1/ለ/ ) ጋር በበገናዘብ ጉዳዩን ተመልክተናል፡፡ በመሆኑም አመልካች በሁለቱም ጉዳዮች ሊቀጣ የሚገባው የእስራት መጠን በጠቅላላው አራት አመት ቀላል እስራት ሆኖ የገንዘብ መቀጮው ደግሞ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 90 ይዘትና መንፈስ አንጻር ሲታይ በድምሩ ብር 7000.00 (ሰባት ሺህ) ሊሆን የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች በጉዳዩ ላይ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሊሻሻል የሚገበው ሆኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ ቁጥር 70094 የካቲት 03 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በፍደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 53779 መጋቢት 29 ቀን 2002 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(ለ-2)) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች በ1996 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ህግ አንቀጽ 543(2) እና 575(2(ሀ)) ሥር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የተላለፈ ጥፋተኛ ነው በማለት በጉዳዩ ላይ የታሰረው ጊዜ የሚታሰብለት ሆኖ በጠቅላላው በአራት አመት ቀላል እስራትና በብር 7000.00 (ሰባት ሺህ) እንዲቀጣ በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ተሻሽሎ በተወሰነው ውሳኔ መሠረት ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለማረሚያ ቤቱ ትዕዛዝ ይድረሰው ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

እ/ብ *የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

የሰ/መ/ቁ. 59537

ሚያዝያ 19 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አነዚር ኢብራሂም - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** የቤ/ጉ/ክ/ሥ/ፀ/ሙስና ኮሚሽን ዐ/ሕግ አቶ አብዮት አልቦሮ ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ትዕዛዝ ሰጥተናል፡፡

**ት ዕ ዛ ዝ**

አመልካች በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከሳሽ ሲሆን ተጠሪው ደግሞ ከሳሽ ነበር፡፡ የሥር ከሳሽም በአመልካች (በሥር ተከሳሽ) ሁለት ክሶችን አቅርቧል፡፡ 1ኛ ክስ ተከሳሹ ቀደም ሲል በክልሉ የሥራ አመራር ተቋም ሀላፊ የነበረ ሲሆን ከዚሁ ከተጠቀሰው ተቋም ወደ ክልሉ አቅም ግንባታ ቢሮ ከተዛወረ በኋላ የሥራ አመራር ተቋም በጀት በሆነው በስልክ መስመር ቁጥር 0911254789 በህገ ወጥ መንገድ ተጠቅሞ ብር 4,674.32 የመንግሥት ገንዘብ ወጪ ሆኖ እንዲባክን በማድረጉ በሥልጣን ያለአግባብ በመገልገል በወ/ህ/ቁ 407/1ሐ/ የተመለከተውን ተላልፏል የሚል ሲሆን፤ 2ኛ ክስ ደግሞ ተከሳሹ በሥራ አመራር ተቋም ሥራ አስኪያጅ ሆኖ በሚሠራበት ወቅት በሥራ አጋጣሚ በትውስት በእጁ የገቡትን የመንግስት ንብረቶች እንዲመልስ በተደጋጋሚ ተጠይቆ ጠፍተውብኛል በማለት ያለአግባብ በንብረቶቹ ለመጠቀም አስቦ የሰወራቸው በመሆኑ በወ/ህ/ቁ/አ 413 (1ለ) የተደነገገውን የመሰወርና የወውሠድ ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡

ተከሳሹም ፍ/ቤት ቀርቦ የእምነት ክህደት ቃሉን ሲጠየቅ ወንጀሉን አለመፈፀሙንና ጥፋተኛ አለመሆኑን ክዶ በመከራከሩ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የከሳሽ ማስረጃዎችን ከሰማ በኋላ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 141 መሠረት ተከሳሹን በብይን በነፃ አሰናብቷል፡፡

በተከሣሹ በነፃ መለቀቅ ቅር የተሰኘው የሥር ከሳሽም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በወ/ይ/መ/ቁ 01966 በቀን 24/02/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት በአብላጫ ድምፅ በሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195(1) መሠረት የይግባኝ ባዩን ይግባኝ ባለመቀበል አሠናብቷል፡፡ ይሁን እንጂ አነስተኛው ድምፅ መልስ ሰጪው በሥር ፍ/ቤት ሳይከላከል በነፃ መሠናበቱ ያለአግባብ በመሆኑ መከላከል አለበት ብሏል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚው ችሎት በአብላጫ ድምጽ የከፍተኛውን ፍ/ቤት ብይን በማጽናቱ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት የአሁኑ ተጠሪ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም በመ/ቁ 02083 በቀን 19/11/2002 ዓ.ም

በዋለው ችሎት በአብላጫ ድምፅ በሰጠው ፍርድ ከሳሽ (ይግባኝ ባይ) በሁለቱም ክሶች አስረድቶ እያለ አልተመሠከረበትም በሚል በነፃ መለቀቁ ያለአግባብ ነው በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 142(1) መሠረት እንዲከላከል ወስኗል፡፡ የሰበር ችሎት አነስተኛው ድምጽ ደግሞ ተጠሪው (የሥር ተከሳሽ) ሊከላከል አይገባም ብሏል፡፡

በክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎት ፍርድ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ያለው የአሁን አመልካችም ሐምሌ 30 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ቅሬታ በቀረቡብኝ ሁለት ክሶች የተጠሪ ምስክሮች የወንጀሉን ድርጊት አለመፈፀሜን በሚገባ በማረጋገጥ መስክረው እያሉ የክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎት በአብላጫ ድምጽ በሰጠው ፍርድ እንዲከላከል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ስህተቱ ታርሞ የአብላጫው ድምጽ ፍርድ ተሽሮና አነስተኛው ድምጽ መካላከል የለበትም ያለው ፀንቶልኝ በነፃ እንድሰናበት ይወሰንልኝ ብሏል፡፡

ለዚህ የሰበር ቅሬታ ተጠሪው በቁጥር 01/2003 በቀን 02/05/2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም አንድ ተከሳሽ ወይም ይግባኝ ባይ ወይም የሰበር አቤቱታ አቅራቢ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 184(መ) እና 195 መሠረት የጥፋተኛነት ወይም የቅጣት ውሣኔ ባልተሰጠበት ይግባኝም ሆነ የሰበር አቤቱታ ማቅረብ አይችልም፡፡ አመልካች የሚያነሣቸው ነጥቦች በመከላከያ ማስረጃዎች የሚረጋገጡ እንጂ በሰበር አቤቱታው ባቀረበው ሁኔታ የሚታመንበትና ተቀባይነት የሚያገኝበት አይደለም፡፡ በሁለቱም ክሶች ተጠሪ ባቀረባቸው የሰውና የጽሁፍ ማስረጃዎች ከተገቢው ጥርጣሬ በላይ የተመሠከረበት በመሆኑ የሥር ሰበር ሰሚው ችሎት በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች ተጠሪው ለሰበር ችሎት ለሰጠው መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ክርክሩን አጠናክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው የቀረበ ሲሆን እኛም ይህ ሰበር ችሎት ጉዳዩን የመመርመር ሥልጣን አለው ወይስ የለውም የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10(2) ሆነ በኢ/ፌ/ዲ/ሪ/ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3) ሀ መሠረት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን ማንኛውንም የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን ያለው መሆኑ የተገለፀ ሲሆን በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን በሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት አመልካች የቀረቡበትን ክሶች ይከላከል መባሉ በጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ ተሰጥቶበታል የሚያሰኝ አይደለም፡፡

ስለሆነም የሰበር አቤቱታው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ለመቅረብ ብቁ ባለመሆኑ ውድቅ አድርገን መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ እንዲሆን ብለናል፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡***

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 63727

ሰኔ 13 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** ፡- ፋሲል ታምራት - አልቀረቡም

**ተጠሪ** ፡- የሐዋሣ ከተማ ከፍተኛ መርማሪ ከሣሽ - አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክስ ሲሆን የተጀመረው በአዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት ሲሆን የአሁን ተጠሪ በመግደል ሙከራ ክስ በአመልካች ላይ ባቀረበው መሠረት ነው፡፡ ቀርቦ የነበረው ክስ በአጭሩ፡- ተከሣሽ የወ/መ/ሕ/ቁ. 27 እና 539 /1/ /ሀ/ በመተላለፍ በቀን 06-9-2002 ዓ.ም ከምሽቱ በ4፡00 ሰዓት በሀዋሳ ከተማ መሀል ከተማ ክልል ጸሐይ ሆቴል ፊት ለፊት ባለው አስፋልት መንገድ ላይ አቶ ተስፋአብ ለተሞ ወደሚያሽከርክረው መኪና ተጠግቶ ምስራቅ ሆቴል ልታሰዬኝ ትችላለህ? በማለት ካልተያዘው ተጠርጣሪ ጋር ካነጋገሩት በኂላ ያልተያዘው የግል ተበዳይ እንዳይከላከል ከልሎ ሲያመቻች ተከሣሹ የግል ተበዳዩን በኂይል አንገቱን ሊወጋው ሲል ዞር በማለቱ ቀኝ ጉንጩን ወግቶ የፊት ለፊት 3 ጥርስ ከታች መንጋጋ 5 ጥርሶቹን በሣንጃ ወግቶ ያወላላቀበት በመሆኑ በፈጸመው የመግደል ሙከራ ተከሷል የሚል ነበር፡፡

ተከሣሽ የቀረበበትን ክስ በመካድ ሲከራከር የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ቀርበው ከተሰሙ በኂላ የተከሣሽም መከላከያ ምስክር እንዲቀርቡ ታዘው ከተሰሙ በኂላ በክሱ ላይ የተጠቀሰውን አንቀጽ ወደ 555 /ሀ/ /ለ/ በመለወጥ ጥፋተኛ መሆኑን ፍርድ በመስጠት በ8 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ ፍርድ ቤቱ በሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ እና ቅጣት ላይ ዐቃቤ ህግ ይግባኝ ጠይቆ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ካከራከረ በኂላ ተከሣሽ ጥፋተኛ መሆን ያለበት በወ/መ/ሕ/ቁ. 27 እና 540 መሆን አለበት በማለት ቅጣቱንም በ12 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታውን አቅርቦ ችሎቱም በትዕዛዝ የበታች ፍ/ቤቱን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች ያቀረበው ቅሬታ ፍሬ ሃሣብ የተላለፈበት የጥፋተኝነት ውሣኔና ቅጣት ያለአግባብ በመሆኑ ተሽሮ በነጻ እንዲሰናበት ፣ ይሄ ካልሆነ ደግሞ የተላለፈበት ቅጣት ተሻሽሎ እስከአሁን የታሰረው በቂ ሆኖ እንዲለቀቅ ጠይቋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ቀርቦ በሰጠው መልስ የተላለፈበት የጥፋተኝነት ውሣኔና

ቅጣት በአግባቡ በመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ እንዲሆን ጠይቋል። አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል።

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይሄ ችሎትም የቀረበውን ክርክር ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል።

በዚሁ መሠረት ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ አመልካች ጥፋተኛ መባል ያለበት በከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ ወይስ? በመግደል ሙከራ የነበረ በመሆኑ ይሄ ጉዳይ ከዚሁ አኳያ ታይቶ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

በመጀመሪያ ደረጃ አመልካች በተከሰሱበት የወንጀል ድርጊት ስላልተረጋገጠብኝ በነጻ ልሰናበት ይገባኛል በማለት የተከራከረውን በተመለከተ በዚህ ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ እና ቅጣት ያንሣል በማለት ይግባኝ ያለው ከሣሽ ዐቃቤ ህግ በመሆኑ በዚህ ነጥብ ላይ አመልካች ያቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም። ምክንያቱም በከፍተኛው ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሣኔ ላይ አመልካች ይግባኝ ስለማቅረቡ የሚያመለክት ነገር የለም።

በሁለተኛ ደረጃ የጥፋተኝነት ውሣኔ የተሰጠበትን አንቀጽ በተመለከተ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በዐቃቤ ህጉ ክስ ውስጥ የተመለከተውን የወ/መ/ሕ/ቁ. 27 እና 539 /1/ /ሀ/ ወደ ወ/መ/ሕ/ቁ. 555 /ሀ/ /ለ/ የቀየረው እውነት ለመግደል ሃሳብ ቢኖረው ደጋግሞ በመውጋት ሃሳቡን ከግቡ ለማድረስ ይችል ነበር በሚል ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበኩሉ አመልካች ጥፋተኛ መሆን ያለበት በወ/መ/ሕ/ቁ. 27 እና 540 ስር መሆን አለበት ወደሚል መደምደሚያ የደረሰው አመልካች በያዘው ሣንጃ የተበዳይ አንገት ላይ ለመውጋት የሰነዘረ መሆኑና ተበዳይ በድንገት ዞር በማለቱ ጉንጩ ላይ በመውጋት ከወጋ በኋላ ደግሞ ሣንጃውን ነቅነቅ በማድረግ ባጠቃላይ 8 /ስምንት/ ጥርሶቹን ያረገፈ በመሆኑ እና መጀመሪያ እንደሰነዘረው አንገቱን ቢወጋ ኖሮ የተበዳይ በህይወት የመትረፍ አጋጣሚ ጠባብ የነበረ መሆኑ ስለመረጋገጡ በማስረዳት መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል።

ይሄንን የይግባኝ ሰሚ ችሎት መደምደሚያ ከወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 27/1/ ሁለተኛ ምዕራፍ ጋር ስናመዛዝን… “ወንጀሉ እንደተጀመረ የሚቆጠረው የተደረገው ተግባር በማያጠራጥር ሁኔታና በቀጥታ ወንጀሉን ለመፈጸም ወደ ታሰበበት ግብ ለማድረስ የተደረገ በሆነበት ጊዜ ነው” ይላል።

በእርግጥም አመልካች ቀድሞ አስቦ ሣንጃውን በሰነዘረው መሠረት ተበዳይ ዞር ባይልና በቀጥታ አንገቱን ቢያገኘውና ቢወጋው ኖሮ ሞትን ሊያስከትል እንደሚችል መገመት አያስቸግርም።

አንገት ላይ በሣንጃ መውጋት ደግሞ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወ/መ/ሕ/አንቀጽ 24/1/ ሁለተኛ ምዕራፍ ላይ እንደተመለከተው በነገሮች የታወቀ ወይም የተለመደ ሂደት In the normal course of things…” ሞትን ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ በውጤቱና ምክንያቱ መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት አለ የሚያሰኝ ነው።

ባጠቃላይ ከላይ የተመለከቱትንና ሌሎችንም የድርጊቱን አፈጻጸም ሂደቶች ከግምት በማስገባት የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች ጥፋተኛ መባል ያለበት በመግደል ሙከራ ስር ነው በማለት በወ/መ/ሕ/ቁ. 27 እና 540 ስር ጥፋተኛ ማድረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የተላለፈበት ቅጣትም ከወንጀሉ አፈጻጸም እና ጥፋተኛ ከተባለበት አንቀጽ አኳያ ሲታይ በተመሣሣይ መልኩ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የደ/ብ/ብ/ሕ/ብሔ/ክ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 45137 በቀን 09-3-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 43913 በቀን 06-01-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ ወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ. 195/2/ /ለ/ /2/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. ለአመልካች የውሣኔው ግልባጭ በሀዋሳ ማረሚያ ቤት በኩል ይድረሰው፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

# ፍታብሔር ሥነ - ሥርዓት



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 53844

ጥቅምት 18 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- አቶ ውጅራ ንዳ ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- 1. አቶ ታደሰ መኮንን ጠበቃ ይመኑ ገ/ፃድቅ ቀረቡ

2. አዲስ ዘመን 83 የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር ሊቀመንበር ኪሮስ አምደየሱስ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ተከሳሽ አንደኛ ተጠሪ ከሳሽ በመሆኑን ተከራክረዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ በሥር ተከሳሽ የሆኑት አመልካች እኔ በሊቀመንበርነት የምመራው አዲስ ዘመን 83 የመኖሪያ ቤት የህብረት ሥራ ማህበር አለ በማለት ብር 20,000 /ሀያ ሺ.ህ ብር/ ተቀብለው በመውሰድ በልጽገውበታል፡፡ ተከሳሹ /አመልካች/ ማስጠንቀቂያ ብጽፍላቸውም መልስ አልሰጡኝም ስለሆነም ከእኔ የወሰዱትን ብር 20,000 /ሀያ ሺ.ህ ብር/ ከነወለዱ እንዲከፍሉ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

አመልካች ገንዘቡን ለእኔ በግሌ አልሰጠኝም፡ ገንዘቡን የከፈለው ለቤት ሥራ ማህበር ሲሆን ገንዘቡን ለማህበሩ የከፈለ ስለመሆኑ ደረሰኝ ተሰጥቷል፡፡ እኔ ገንዘብ የተቀበልኩት በወቅቱ የማህበሩ ገንዘብ ያዥ በመሆኔ ነው፡፡ ስለዚህ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ማህበሩ ህጋዊ ሰውነት ያለው ስለመሆኑ በቂ ማስረጃ አልቀረበም በማለት አመልካች ብር 20,000 /ሀያ ሺ.ህ ብር/ ከግንቦት 5 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ይክፈሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አንደኛ ተጠሪን በአንደኛ መልስ ሰጭነት ሁለተኛ ተጠሪን በሁለተኛ መልስ ሰጭነት ስማቸውን በመጥቀስ ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካች ይህንን ውሣኔ በመቃወም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ገንዘቡን እኔ በግለሰብነቴ ሣይሆን የማህበሩ



www.chilot.me

ገንዘብ ያዥ ስለሆንኩ የተቀበልኩት መሆኑን ማስረጃ በማቅረብ ተከራክሬአለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሁለተኛው ተጠሪ በክርክሩ ጣልቃ ለመግባት ጠይቆ ገንዘቡ ለማህበሩ ገቢ መሆኑንና ገንዘቡ እኔን የማይመለከተኝ መሆኑን በጽሑፍ መልስ ሰጥቷል፡፡ ይህንን ሁሉ በማለፍ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ሁለተኛው ተጠሪ አለኝ የሚለውን የሰነድ ማስረጃ በማያያዝ በክርክሩ ጣልቃ ገብ ተከራካሪ ሆኖ እንዲገባ ያመለከተ ቢሆንም የሥር ፍርድ ቤት ማህበሩ ህጋዊ ህልውና የሌለው መሆኑን በማረጋገጥ ጥያቄውን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡ ስለዚህ አመልካች ያቀረበው አቤቱታ የህግ ድጋፍ የለውም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አንደኛ ተጠሪ ለአመልካች ብር 20,000 /ሀያ ሺህ ብር/ የከፈለ መሆኑን ለማስረዳት የቀረበው በአዲስ ዘመን 83 የመኖሪያ ቤት የህብረት ሥራ ማህበር ሥም የታተመ የገንዘብ መሠብሰቢያ ደረሰኝ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ማህበሩ የራሱ የሆነ ማህደር ያለው ስለመሆኑ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ቡራዩ አስተዳደር ማዘጋጃ ቤትና የኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ማህበራዊ ማደራጃና ማስፋፊያ መምሪያ የፃፋቸው ደብዳቤዎች ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሁለተኛ ተጠሪ ገንዘቡ የተከፈለው መሆኑንና ክርክሩ አመልካችን ሳይሆን በቀጥታ እሱን የሚመለከተው መሆኑን ገልፆ በሥር ፍርድ ቤት ታህሣሥ 10 ቀን 2001 ዓ.ም ያመለከተ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤትን መዝገብ በማስቀረብ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛው ተጠሪ የከሳሽን /የአንደኛ ተጠሪን/ ክስና ማስረጃ ወስደው መልስ እንዲያቀርቡና በክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ ከፈቀደ በኋላ ሁለተኛው ተጠሪ ጥር 13 ቀን 2001 ዓ.ም በነበረው ቀነ ቀጠሮ መልስ ይዘው ባለመቅረባቸው የሁለተኛ ተጠሪን ጣልቃ ገብነት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 41 ንዑስ አንቀጽ 3 እና በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 199 መሠረት ሠርዥዋለሁ በማለት ትእዛዝ የሰጠ መሆኑን ችሎቱ አስቀርቦ የሥር ፍርድ ቤት መዝገብና አመልካች በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ቅር በመሰኘት ካቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት የተከተለው የክርክር አመራር ሥርዓትና በመጨረሻም ውሳኔ ሲሰጥ የደረሰበት መደምደሚያ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመመሥረት ጉዳዩን መርምረናል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተጠሪ ታህሣሥ 10 ቀን 2001 ዓ.ም ያቀረቡትን አቤቱታ በመቀበል በክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ ታህሳስ 10 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ ያቀረቡት የጣልቃ ገብነት አቤቱታ አመልካች ገንዘቡን የተቀበለው የማህበሩ ገንዘብ ያዥ በመሆኑና ማህበሩም ገንዘቡ ገቢ የተደረገለት በመሆኑ ከሳሽ /ሁለተኛ ተጠሪ/ ስለማህበር አባልነትና ተመላሽ ገንዘብ መክሰስም ሆነ መከራከር ካለበት ከማህበሩ ጋር መሆን አለበት የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተጠሪ ለአንደኛ ተጠሪ በሥር ከሳሽ ክስና ማስረጃ ይዘው እንዲቀርቡ በተቀጠረበት ቀን ካልቀረቡ የሁለተኛ ተጠሪን መልስ የመስጠት መብት በማለፍ ውሣኔ መስጠት ሲገባው ህጋዊ ህልውና አለህ በክርክሩ ጣልቃ እንድትገባ ተፈቅዷል ያለውን አካል ከክርክር ውጭ እንዲሆን የሰጠው ትእዛዝ የአመልካችን መብት የሚያጣብብና አንድ በክርክር ተካፋይ የሆነ ሰው መልሱንና ማስረጃውን ባያቀርብ ፍርድ ቤቱ በሌለበት ክርክሩን ሰምቶ የሚወስን መሆኑ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 70 የተደነገገውን የሚጥስና የክርክር አመራር ጉድለት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ሁለተኛ ተጠሪ ሕጋዊ ህልውና እንዳለውና በክርክር ጣልቃ መግባት እንደሚችል የሥር ፍርድ ቤት ትእዛዛ ከሰጠ በኂላ ሁለተኛው ተጠሪ ህጋዊ ህልውና እንደሌለውና አንደኛ ተጠሪ በማህበሩ ስም የታተመ ደረሰኝ ተቀብሎ ለከፈለው ብር 20,000 /ሀያ ሺህ ብር/ አመልካች በግሉ ተጠያቂነት አለበት በማለት መጋቢት 16 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፍርድ ቤቱ የማህበሩ ህጋዊ ሰውነት ያለው ስለመሆኑ ታህሳስ 10 ቀን 2001 ዓ.ም ከሰጠው ትእዛዝ ጋር የሚቃረንና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ውሳኔ ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካች ሁለተኛ ተጠሪና በአንደኛ ተጠሪ መካከል የቀረበውንና የሚቀርበውን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343(1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. ከሥር ፍርድ ቤት የመጣው መዝገብ ይመለስ
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 50835

ጥቅምት 16 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**:- ተገኔ ጌታነህ

ሓጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች**:- 1. አቶ ምናሴ ኢትሶ ጠበቃ አሰፋ ንጉሴ ጋር ቀረቡ

2. ወ/ሮ ሸዋዬ በዳሶ ጠበቃ አሰፋ ንጉሴ ጋር ቀረቡ

**ተጠሪ**:- ወ/ሮ ፋንታዬ ተረፈ ጠ/ጌታቸው እንግዳ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ አመልካቾች ተጠሪ ላይ ያቀረቡት ክስ ያላአግባብ የፍርድ ባለመብት የሆኑበት ቤት ይለቀቅልኝ ክስ በሥር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ባለማገኘቱ ነው፡፡

በሥር ፍ/ቤት አመልካቾች ከሳሾች ነበሩ፡፡ የክሱ ምክንያትም ባልና ሚስት የሆኑት የሥር ተከሳሾች በቤቱ ላይ መብት ሳይኖራቸው የባልና ሚስት ንብረት በማስመሰል በፍርድ አፈፃፀም የተረከቡትን ቤት እንዲያስረክቡ /እንዲመልሱ/ ይወሰንልን የሚል ነበር፡፡

የአሁኗ ተጠሪ ሥር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ ሆነው የሰጡት መልስ ቤቱ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ መሆኑ ተረጋግጦ በመ/ቁ. 45803 በ16/7/98 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ በክፍፍል ያገኙት ንብረት መሆኑን ገልፀው የከሳሾች ጥያቄ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1149 መሰረት በይርጋ ቀሪ ሊባል ይገባል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተከሳሾች ቤቱን የያዙት በፍርድ ስለመሆኑ ከሳሾች ያመኑት ጉዳይ ስለመሆኑ ጠቅሶ በሐሰት ማስረጃ ያገኙት ነው የሚሉ ከሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6/1/ መሰረት ከሚጠይቁ በስተቀር ክስ ለማቅረብ አይችሉም በሚል ጥያቄያቸውን ሳይቀበል ቀርቷል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ የሥር ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6/1/ን በመጥቀስ በውሳኔው ያመለከተውን የከሣሽ መብት ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት እንደሌለው ተችቶ ከሳሾች መብታቸውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ከሚጠይቁ በስተቀር አዲስ ክስ ማቅረብ አይችሉም በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ ምክንያት በመለወጥ አጽንቷል፡፡



www.chilot.me

አመልካቾች ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ ያቀረቡት በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፡፡ የቤት ቁጥር 260 የባልና ሚስት ሐብት ነው ተብሎ እንዲከፋፈሉ በመ/ቁ. 45803 ውሳኔ መስጠቱን እንዳወቁ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት አቤቱታ አቅርበው ውሳኔ ከተፈፀመ በኋላ የቀረበ ነው በሚል ውድቅ የተደረገባቸው መሆኑን ጠቅሰው አዲስ ክስ የቀረበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 421 መሰረት ስለመሆኑ ገልፀው የሥር ፍ/ቤቶች ፍትህ የማግኘት መብታቸውን በሚጐዳ ሁኔታ የሰጡት ውሳኔ እንዲታረም ጠይቀዋል፡፡

የሰበር ችሎቱም አቤቱታቸውን መርምሮ የሥር ፍ/ቤቶች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6 እና 358 ጠቅሰው የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ ስለመሆኑ ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ አዝዟል፡፡

የተጠሪ ጠበቃ ሚያዝያ 18 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ በይዘቱም የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካቾችን የዳኝነት ጥያቄ ቀደም ሲል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቀጥር 358 መሰረት ውድቅ መደረጉን ተገንዝበው መወስናቸው በአግባቡ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከተው ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው የአሁኑ ተጠሪ እና ባለቴቷ መካከል የነበረ ጋብቻ በፍች እንዲፈ|ርስ መወሰኑን ተከትሎ የንብረት ክፍፍል ክርክር ተደርጐ በተሰጠ ውሳኔ መሰረት በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቀበሌ 04 የቤ/ቁ. አዲስ የሆነ በ400 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያለ ቤት ተጠሪዋ በፍርድ አፈፃፀም የተረከበች መሆኑን ተከትሎ ይህ ቤት የባልና ሚስቱ ሳይሆን የአመልካቾች ነው ሲሉ አመልካቾች ክስ ማቅረባቸው ተመልክቷል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍ/ቤት ተጠሪና ባለቤቷ በሐሰተኛ ማስረጃ ቤቱን አገኙ የሚሉ ከሆነ የከሳሾች (አመልካቾች) ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6/1/ መሰረት ሊታይ የሚገባ እንጂ አዲስ ክስ መቅረብ አይችልም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡

በመሰረቱ የከፍተኛው ፍ/ቤት ይህ የሥነ ሥርአት ሕጉ ድንጋጌ ተከራካሪ በነበሩ ወገኖች መካከል እንጂ ሦስተኛ ወገን ሊጠቀምበት እንደማይችል ጠቅሷል፡፡ በዚህ ረገድ የ3ኛው ፍ/ቤት የውሳኔው ምክንያት ተገቢነት ያለው እንደሆነም መገንዘብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን አመልካቾች አዲስ ክስ ከማቅረባቸው በፊት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሰረት በዋናው መዝገብ ላይ አቤቱታ አቅርበው ውሳኔው ከተፈፀመ በኋላ የቀረበ ጥያቄ ነው ተብሎ ውድቅ የተደረገባቸው መሆኑ በግልጽ ተጠቅሶ እያለ ከፍተኛው ፍ/ቤት መልሶ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት መብታቸውን ማስከበር ይችላሉ ያለው እርስ በርሱ የሚጋጭ አቋም መሆኑን ያመለክታል፡፡ በአንድ ንብረት ላይ መብት አለኝ፣በክርክሩ ሂደት አልተካተትኩም በሚል ምክንያት መብቴ ተነክቷል የሚል ወገን መብቱን ሊያስከብር የሚችልበትን ሥርአት ሕጉ በየደረጃው ዘርግቷል፡፡

ለዚህም ተጠቃሽ የሚሆኑት ውሳኔው ከመፈጸሙ በፊት ከሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት፤ውሳኔው በአፈፃፀም ሂደት ላይ ሆኖ ንብረቱ ያለአግባብ ተይዞብኛል የሚል ወገን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 418 መሰረት መብቱን ማስከበር የሚችልበት አግባብ ተደንግጓል ከዚህ ባለፈ በንብረቱ ላይ የተሻለ መብት አለኝ የሚል ወገን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 421 አልያም እንደነገሩ ሁኔታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/አንቀጽ 455 መሰረት ክስ መሥርቶ መብቱን ማረጋገጥ እንደሚችል ተመልክቶ እናገኛለን፡፡



www.chilot.me

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካቾች ጥያቄ ያቀረቡበት ንብረት በፍርድ ለ1ኛ ተጠሪ የተላለፈ ስለመሆኑ በክርክር ሂደት የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካቾች ይህ ንብረት የባልና ሚስቱ ሳይሆን የአመልካቾች ነው ሲሉ ያቀረቡት ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 455 በተደነገገው አግባብ ሊስተናገድ የሚችል ስለመሆኑ መረዳት ተችሏል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር እንደማናቸውም ጉዳዮች በማስረጃ ተጣርቶ ውሳኔ ሊይገኝ የሚገባው እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡

ስለሆነም አመልካቾች በንብረቱ ላይ ያላቸውን መብት ለማረጋገጥ ያቀረቡትን ክስ የሥር ፍ/ቤቶች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6 እና 358ን በመጥቀስ ውድቅ ማድረጋቸው ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው እና የጉዳዩን ደረጃ እና የቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 12351 በ29/5/01 የሰጠው ፍርድ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 78780 ጥቅምት 25 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄን ተቀብሎ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ብለን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/1/ መሰረት መዝገቡን ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 52942

ጥቅምት 18 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ገብሩ ኮሬ ጠበቃ ወልደስላሴ ብርቱ

**ተጠሪ፡-** አቶ አመዲዮ ፌዴሬቼ ከጠበቃ መስፍን ጌታቸው ጋር ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በውሉ መሠረት የግልግል ዳኛ ጉዳዩን እንዲመለከት ይወሰን ዘንድ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ቀርቦ በፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት ጉባኤው ተቋቁሞ ጉዳዩን ማየት ከጀመረ በኋላ ጉባኤው የአባላቱን አበል በተመለከተ ትዕዛዝ ሲሰጥ በአበሉ መጠን ቅሬታ ያለው ወገን ሊከተለው የሚገባውን ሥነ ሥርዓት የሚመለከት ነው፡፡

ጉዳዩ በግልግል ጉባኤ እንዲታይና ጉባኤው እንዲቋቋም ለፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረቡት ያሁኑ ተጠሪ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የሽምግልና ዳኛ እንዲሾም ብይን ሰጥቷል፡፡ በዚህም መሠረት ፍ/ቤቱ አንድ ሰብሳቢ ዳኛ ግራ ቀኙ ደግሞ አንድ አንድ የሽምግልና ዳኛ መርጠዋል፡፡ በፍርድ ቤቱ የተሾሙት ሰብሳቢ ዳኛ በግራ ቀኙ ከተሾሙት ዳኞች ጋር በመሆን ስራ ከመጀመራቸው በፊት ስለአበል ክፍያ አተማመን ይረዳቸው ዘንድ የግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር እንዲቀርብ አድርገዋል፡፡ ከዚህም የሽምግልና ጉባኤ አባላት አበል ብር 60,000.00 (ስልሳ ሺህ ብር) እንዲሆንና ግማሹ ቅድሚያ እንዲከፈል ለግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ተገልጾላቸዋል፡፡ ተጠሪ ይህ ሲገለጽላቸው አበሉ ከአቅም በላይ የሆነባቸው መሆኑን ገልፀው ቀነ ቀጠሮ በጉባኤ ከተሰጣቸው በኋላ አባላቱ ጉዳዩን ለማየት የማይችሉ መሆኑንና የተጠሪን በቀነ ቀጠሮ አለመቅረብ በመጥቀስ መዝገቡን ዘግተዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ተጠሪ ሌላ የሽምግልና ጉባኤ እንዲቋቋምላቸው /እንዲሾምላቸው/ እና የተዘጋው መዝገብ እንዲንቀሳቀስላቸው ለስር ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍ/ቤቱም የግልግል ጉባኤው አበሉ ቀድሞ ካልተወሰነ ራሱ መወሰን እንደሚችል፣ ይህም በስራ ሒደት እንደተሰጠ ትዕዛዝ እንደሚቆጠር በትዕዛዙ ቅሬታ ያለው ወገን ማሳረም የሚችለው በይግባኝ እንጂ ሌላ ጉባኤ እንዲቋቋም በማድረግ አለመሆኑንና ተጠሪ እንዲከፈል ትዕዛዝ የተሰጠበትን የጉባኤ አባላት አበል በመክፈል መዝገቡን ከማንቀሳቀሳቸው ውጭ ሌላ የግልግል ዳኛ እንዲተካ ጥያቄ ማቅረብ የለባቸውም በሚል ምክንያት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 318/5/፣ 317/1/ እና 319/1/ ድንጋጌዎችን በዋቢነት በመጥቀስ ተጠሪ ሌላ



www.chilot.me

ዳኛ ተተክቶ መዝገቡ ይንቀሳቀስልኝ ሲሉ ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ብይን ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በዋላ የስር ፍ/ቤት ብይን ተሽሮ የስር ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አነጋግሮ ምትክ የሽምግልና ዳኝነት ጉባኤ እንዲያቋቁም በሚል ተወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ የካቲት 15 ቀን 2002ዓ.ም በፃፉት ሶስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የሽምግልና ጉባኤ አበል በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ክስ ለማቅረብ ከሚጠየቀው የዳኝነት ገንዘብ የተለየ ነው፡፡ በግልግል ዳኝነት ጉባኤ የተከፈተው መዝገብ የተዘጋው በአበል ያለመክፈል ብቻ አይደለም የሚሉትን ምክንያቶች ዘርዝረው ውሳኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የሽምግልና ጉባኤው የአበል መጠንን አስመልክቶ የሰጠው ትዕዛዝ በስራ ሒደት እንደተሰጠ ውሳኔ ስለማይቆጠር ተጠሪ ይግባኝ ማለት አያስፈልጋቸውም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት የተጠሪ ጠበቃ ቀርበው ሐምሌ 19 ቀን 2002ዓ.ም በተፃፈ 3 ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃ በ8/02/03 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ብቻ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ የግልግል ዳኝነት የሚቋቋምበት አይነተኛ ዓላማ ተከራካሪዎቹ ወገኖች ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት በመሄድ የሚያጠፉትን ጊዜና ገንዘብ ለማስቀረት መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ ጉባኤው የሚቋቋመውም በተከራካሪ ወገኖች ስምምነት ሲሆን ተከራካሪዎቹ ባላቸው የመዋዋል ነፃነት ጉዳያቸውን ከፍርድ ቤት ውጪ በግልግል ዳኝነት ለመጨረስ የሚስማሙት ሁኔታ መኖሩ በራሳቸው ፍላጎትና ምርጫ የተቋቋመው ጉባኤ ጉዳያቸውን በተገቢው ጊዜና በአነስተኛ ወጪ ለመወሰን ይችላል የሚል እምነት ኑሯቸው ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ በሕጉ አግባብ በተደረገ የግልግል ስምምነት መሠረት የግራ ቀኙ ጉዳይ /ክርክር/ የግልግል ዳኛ መመልከት ከጀመረ በኂላ ሊከተል የሚገባው ሥነ ሥርዓትን በተመለከተ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ መሠረት ስለመሆኑ የፍ/ህ/ቁጥር 3345 ድንጋጌ ያሳያል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 317/1/ ድንጋጌ ሲታይ ደግሞ የግልግል ዳኛ ክርክሩን መምራት ያለበት በተቻለ መጠን የመደበኛ ዳኝነት አካሄድን ተከትሎ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ የዚህ ድንጋጌ መንፈስ የግልግል ዳኝነት አካሄድ የመደበኛ ፍ/ቤት የዳኝነት አካሄድን መከተል ያለበት ቢሆንም እንደመደበኛ ፍ/ቤት የዳኝነት አካሄድ የጠበቀ ወይም ሁል ጊዜ ጥብቅ የሙግት ሥርዓትን ተከትሎ ሊሆን የማይገባ መሆኑን ነው፡፡

በሌላ በኩል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 318/5/ ድንጋጌ ሲታይ የግልግል ጉባኤ ጉዳዩን ለማየት ሊከፈል የሚገባውን የገንዘብ መጠን በተመለከተ ተገቢ ነው ብሎ ያመነበትን ያህል መወሰን የሚችል መሆኑን ያሳያል፡፡ ጉባኤው ይህንን አይነት ትዕዛዝ ጉዳዩ መታየት ከመጀመሩ በፊት ወይም በኂላ ሊሰጥ የሚችል መሆኑን ድንጋጌው ያስገነዝባል፡፡ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ ጉባኤው ተከራካሪ ወገኖች

የማይሰማሙበትን የአበል መጠን እንዲከፍልሉ የሚል ትዕዛዝ ቢሰጥ በትዕዛዙ ላይ ተቃውሞ ያለው ተካራካሪ ወገን ያለው መፍትሔ ምንድን ነው? የሚለው ነው፡፡ አንድ ሰው በፍርድ ሊያልቅ የሚገባው ጉዳይን ፍርድ ቤት ይዞ ሲቀርብ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መክፈል ያለበት መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 215፣ ከ467 እስከ 479 ድረስ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ የዳኝነት አገልግሎት መክፈል የማይችል ሰው ክስ ለማቅረብ የሚችልበት አግባብ ስለመኖሩም ተጠቃሽ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ አንድ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ለመክፈል የማይችል ሰው በደሃ ደንብ ክስ ለማቅረብ የሚችል ሲሆን ለመክፈል አቅም እያለው ክስ ያቀረበ መሆኑ ከተረጋገጠ ግን መዝገቡ እንደሚዘጋ፣ የተዘጋ መዝገብ ደግሞ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ/ገንዘቡን/ ለመክፈል ዝግጁ እስከሆነ ድረስ የሚንቀሳቀስለት መሆኑን የሥነ ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መንፈስና ይዘት ያስገነዝባሉ፡፡

የግልግል ጉባኤ ከሚቋቋምበት ዋነኛ ዓላማ፣ ጉባኤው ሊከተለው ከሚገባው ሥርዓት እና ስለ ዳኝነት አገልግሎት ክፍያ የተመለከቱት ደንቦች መሠረት ሲሆኑ አንድ ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት እንዲታይለት የተስማማ ሰው በአካሄዱ ቅሬታ እያለው ጉዳዩ በተቋቋመው ጉባኤ እንዲታይ ማድረግ ተገቢነት አለው ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ጉባኤው ጉዳዩን ለማየት ከመጀመሪያውኑ አበሉን መወሰን የሚችል ሲሆን በዚሁ ደረጃ የሚሰጠው ትዕዛዝ ሙሉ በሙሉ የክርክሩ አካል አይደለም ለማለት የማይቻል ቢሆንም በተያዘው ጉዳይ ከላይ ከተመለከቱት ፍሬ ነገሮችና የሕጉ ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በአመልካች መብት ላይ መሠረታዊ የመብት መጣበብ ያስከተለ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ ጉዳዩ በምትክ የጉባኤ አባላት እንዲታይ ማድረግ በአመልካች መብት ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ውጤት የሌለው ከመሆኑ አንፃር ስንመለከተው በውጤት ደረጃ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት የሚያስችል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ውጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሶ/በ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 48608

ህዳር 2 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወጋገን ባንክ (አ.ማ) - ኤፍሬም ፈቃዱ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሀብቶም ረዘነ ከጠበቃ ፊሊጶስ አይናለም ጋር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የትግራይ ክልል የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከተ ነው፡፡ ክርክሩ በብድር የተወሰደ ገንዘብን የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ተጠሪ በብድር የወሰዱትን ብር 200,000 እና ይህ የብድር ገንዘብ የሚወልደው ወለድ በድምሩ 306,185.16 (ሶስት መቶ ስድስት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ አምስት ብር ከአስራ ስድስት ሣንቲም) እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርበው አመልካች መኪና ሸጧል እንደዚሁም ወለዱ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2024(ረ) ይታገዳል የሚሉ መከራከሪያዎችን ያቀረቡ ሲሆን በዋነኛነት እዳዬን ሰርዞልኛል ምክንያቱም በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት በደረሰብኝ ጉዳት ለመክፈል እንደማልችል ተረጋግጧል በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች ተጠሪ በማስረጃነት የጠቀሱት የውስጥ መፃፃፊያ ነው፡፡ እዳው አልተሠረዘም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ አመልካች ተጠሪ የተበደሩትን ብድር የሰረዘላቸው በመሆኑ ዕዳውን ተጠሪ (ተከሳሽ) የመክፈል ሀላፊነት የለበትም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ነሐሴ 19 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የተጠሪ ዕዳ ለጊዜው በተንጠልጣይ ሂሳብ እንዲቆይ (written off) አደረግን እንጅ እዳው የተሰረዘ መሆኑን ለተጠሪ አልገለፅንለትም፡፡ አንድ ዕዳ በተንጠልጣይ ሂሳብ መያዝ (written off) እና አንድን የብድር ዕዳ ሙሉ በሙሉ መሠረዝ የተለያዩ ናቸው፡፡ ፍርድ ቤቱ ይህንን ለማስረዳት ያቀረብናቸውን ማስረጃዎች በተሟላ መልኩ አላየልንም፡፡ ባንኩ ለተጠሪ ያበደረውን ብድር ሙሉ በሙሉ ምህረት አላደረገም፡፡ ተጠሪ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት የተበደሩትን ብድር እንዳይከፍል የፈጠረባቸው

መሰናክል የለም ስለዚህ ተገቢውን ማጣራት ሣያደርግና ሙያዊ በሆኑ ነገሮች የባለሙያ አስተያየት ሣይሰማ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት እኔ በምኖርበት አካባቢ ጦርነት የነበረ መሆኑና በጦርነቱም ውድመት የደረሰ መሆኑ ፍርድ ቤቱ ዕውቅና ሊሰጠው የሚገባው ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ብድር ሲያበድር በመያዣነት ይዞት የነበረውን ተሽከርካሪ በራሱ ፈቃድ በግንቦት ወር 1997 ዓ.ም ነፃ በማድረግ ለቆታል፡፡ ይህም ዕዳውን በምህረት መልክ መሠረዙን የሚያሣይ ነው፡፡ በባንኮች ዝርዝር ፖሊሲና ፕሮሲጀር መሠረት ሁለት አይነት የብድር ዕዳ ሥረዛዎች መኖራቸውን ለመረዳት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው “written off” የሚባለው ሲሆን ሁለተኛው ለዘለቄታው ተበዳሪውን ላለመጠየቅ የሚደረግ የዕዳ ሥረዛ ነው፡፡ አመልካች ለተጠሪ ያደረገው ሁለተኛውን አይነት የዕዳ ስረሳ ነው በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ እኔ ያደረክሁት (written off) እንጅ ለዘለቄታው ተበዳሪው ብድሩን እንዳይከፍልና እንዳይጠየቅ ምህረት አላደረግሁም በማለት የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር በፅሑፍ የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን ችሎቱም የአመልካችንና የተጠሪን የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡ በቃል ክርክሩም አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩት አመልካች የተጠሪን ዕዳ በተንጠልጣይ ሒሳብ እንዲያዝ (written off) ነው ያደረገው ወይስ ተጠሪ በዕዳው እንዳይጠየቅ ለዘለቄታው እዳውን በመሰረዝ ምህረት አድርጎለታል በሚለው ነጥብ ላይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ እኛም በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነውን ይህንን ጭብጥ በአግባቡ ለመፍታት አመልካችና ተጠሪ የሚያቀርቡትን ማብራሪያና ደጋፊ ጽሑፎችን መመልከቱ ብቻ በቂ እንዳልሆነ ተገንዝበናል፡፡

አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበት ነጥብ የባንኮች የዕዳ አመዘጋገብ እና የዕዳ ሥረዛን “ፕሮሲጀርና” አሰራር የሚመለከትና የሙያ ማብራሪያ የሚያስፈልገው ነጥብ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ተከራካሪዎች የሚከራከሩበት ጉዳይ የልዩ አዋቂ ምስክርነትና ማብራሪያ የሚያስፈልገው ሆኖ በሚያገኝበት ሠዓት የልዩ አዋቂ ምስክር በመሰየም ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ማድረግ እንደሚገባው የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 136 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ አመልካች ግንቦት 12 ቀን 1997 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ ዕዳውን ከእኔ በማናቸውም ጊዜ ላለመጠየቅ ሙሉ በሙሉ በመሠረዝ ምህረት አድርጎልኛል በማለት ያቀረቡት ክርክር የባንክ ባለሙያዎችን በመመደብና አስፈላጊም ከሆነ ከብሔራዊ ባንክና ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ስለ ባንኮች የዕዳ አመዘጋገብና የእዳ ሥረዛና የምህረት ፕሮሲጀር ተገቢው ሙያዊ ማብራሪያ እንዲሰጥ በማድረግ አመልካች የተጠሪን ብድር በተንጠልጣይ ሒሳብ ነው የመዘገበው (written off) ነው ያደረገው ወይስ አመልካች የተጠሪን ዕዳ በማናቸውም ጊዜ ቢሆን ላይጠይቅ ሙሉ በሙሉ በመሠረዝ ምህረት አድርጓል የሚለውን ጭብጥ መወሰን ሲገባቸው በጉዳዩ የልዩ አዋቂ ምስክርነትና ማብራሪያ ሣይሰሙ አመልካች የተጠሪን ዕዳ ሰርዟል በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የትግራይ ክልል የምስራቅ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡



www.chilot.me

2. የምስራቃዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች የተጠሪን የብድር ዕዳ በተንጠልጣይ ሒሳብ ነው የያዘው (written off) ነው ያደረገው ወይስ ዕዳውን በማናቸውም ጊዜ ላይጠይቅ ሙሉ በሙሉ በመሰረዝ ምህረት አድርጓል በሚለው ነጥብ ላይ የልዩ አዋቂ በመመደብና በማስመርመር የልዩ አዋቂ የሚያቀርበውን ሙያዊ አስተያየት ከሰማ በኋላ እንድወሰን ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343(1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

*ራ/ታ*



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 49502

ህዳር 01 ቀን 2003 ዓ.ም

*ዳኞች፣* ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

*አመልካች፣* የኢት/ያ የእህል ንግድ ድርጅች አልቀረቡም

*ተጠሪዎች፣* 1ኛ. መርዕድ ተፈራ

2ኛ አያሌው መኮንን ቀረቡ

3ኛ ስለሺ ኃ/ሚካኤል ቀረቡ

4ኛ ወ/ሪት ዙልፋ ከድር አልቀረበችም

5ኛ አቶ ጣሰው ነገዎ ቀረቡ

6ኛ አቶ አሰፋ ቱሉ ጠበቃ አቶ ወንድአወክ አየለ ቀረበ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የአሁን አመልካች ከተራ ቁጥር 1 እስከ 6ኛ የተጠቀሱት ሠራተኞቹ በሥራቸው ምክንያት የብር 154,334.67/100 የገንዘብ ጉድለት አድርሶውብኛል በማለት እያንዳንዱ ሠራተኛ ኃላፊ ሊሆን ይገባዋል የሚልበትን ምክንያት በመጥቀስ ገንዘቡን እንዲተኩለት ባቀረበው ክስ መነሻ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ተመልክቻለሁ በማለት ተጠሪዎች ኃላፊ ሊሆኑ የሚገባበት ምክንያትና ማስረጃ አልተገኘም በማለት በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ቅር ተሰኝቶ የይግባኝ አቤቱታውን ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነትን አላገኘም፡፡

አመልካች የጉዳዩ አካሄድ እንደ ሙግት አመራር ሥርዓቱ ባለመከናወኑ ምክንያት ተገቢውን ዳኝነት አላገኘም የሚለውን የመከራከሪያ ነጥብ በዋነኛነት በመጥቀስ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪዎችም በሥር የተሰጠው ውሣኔ የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም የሚሉበትን ምክንያት ከመግለፅ ጋር ውሣኔው እንዲፀናላቸው ተከራክረዋል፡፡

እኛም ጉዳዩን ተመልክተናል እንደተመለከትነውም የአሁን አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበውን ክስ ለማስረዳት ከቀረበው የኦዲት ምርመራ ውጤት በተጨማሪ የኦዲት ምርመራ ሥራውን ያከናወኑት ባለሙያዎች ሙያዊ የምስክርነት ቃል እንዲሰጡለት በማስረጃነት የቆጠራቸው

መሆኑንና ነገር ግን እነዚህ የሰው ማስረጃዎች ሳይሰሙ ታልፎ ውሣኔ በመስጠቱ ፍትህ እንደተጓደለበት ገልፆ ቅሬታ ሲያቀርብ፤

በተጠሪዎች በኩል በሰበር ከቀረበው ክርክር መካከል እነዚህ ኦዲተሮች ከኦዲት ምርመራ ሰነዱ በተለዩ ምን ሊያስረዱ ይቻላሉ? አንደኛውም ኦዲተር ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል ለመስማት የሚቻልበት መንገድ የለም በማለት ከመከራከራቸው ጋር ተገናዝቦ ሲታይ በእርግጥም የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን ማስረጃዎች በሙሉ አለመሰማቱን አረጋጋጭ ነው፡፡

አመልካች በሰው ማስረጃነት የሙያ ምስክርነት እንዲሰጡለት የጠቀሳቸው ኦዲተሮች ሳይሰሙ የታለፈበት ምክንያት ምን እንደሆነ በውሣኔው ላይ ተገልፆ ባይገኝም ከላይ እንደተመለከተው የምስክርነት ቃል አለመስጠታቸውን ከውሣኔው ይዘት መረዳት ችለናል፡፡

እነዚህ የሙያ ምስክሮች የሚሰጡት የምስክርነት ቃል ጉዳዩን በማስረዳት ረገድ የሚኖረው የማስረዳት ብቃትም ሆነ አግባብነት ቃላቸውን ከሰጡ በኃላ የሚታወቅ በመሆኑ ተጠሪዎች በሰበር ደረጃ ባቀረቡት ክርክር እንደገለፁት የኦዲት ምርመራ ውጤቱን ከያዘው ሰነድ የተለየ አያስረዱም ብሎ ከወዲሁ መደምደም የማይቻል ከመሆኑም በላይ አንድ ተከራካሪ ወገን ያቀረበውን ክርክር ለማስረዳት የማስረጃ አግባብነትና ተቀባይነት መርህ ካለገደው ወይም ካልከለከለው በቀር ዘርዝሮ ያቀረበውን የማስረጃ በዓይነትም ሆነ መጠን የማስረዳት መብት ያለው በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት የእነዚህን ምስክሮች የሙያ ምስክርነት ቃል ሳይቀበል በዝምታ አልፎ ውሣኔ መስጠቱ የሙግት አካሄድ ሥርዓትን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም እንዲሁም ጉድለቱ በጥፋት ወይም በቸልተኝነት የተፈፀመ መሆኑን ለማስረዳት የግምት መነሻ ይሆናል የተባለውና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145 ከፖሊስ ኮሚሽን የቀረበ የተባለው በቁጥር 272179 የተሰየመው ሰነድ ቀርቦ ስለመታየቱም ሆነ ታይቶ ተቀባይነትን አጥቶ ስለመሆኑ የውሣኔው ይዘት የሚያስረዳው ነገር እንዳሌለ ተረድተናል ስለሆነም የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ ከውሣኔ ለመድረስ አመልካች ያቀረበውን ክርክር በማስረጃ የማስረዳት መብቱን ሙሉ በሙሉ ጠብቆ ያከናወነ ስለመሆኑ የውሣኔው ይዘትም ሆነ በሰበር ግራቀኙ ያደረጉት ክርክር ስለማያስረዳ የጉዳዩ አካሄድ ሙሉ የክርክር አመራር ሥርዓትን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 01217 በ10/11/2000 እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 72047 በሐምሌ 07 ቀን 2001 የሰጠው ዳኝነት ተሽሯል፡፡
2. የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 01217 የተመዘገበውን መዝገብ እንደገና አንቀሳቅሶ በአመልካች በኩል ማመልከቻው ላይ የጠቀሰውን ጉዳይ ለማስረዳት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 223 መሠረት አስቀድሞ ዘርዝሮ ያቀረበውን ማስረጃ በሙሉ ሰምቶና አይቶ በጉዳዩ ላይ የመሰለውን እንዲወስን መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሠረት መልሰናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙ ያደረጉት ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ሁለቱም ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡን ዘግተናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

የሰ/መ/ቁ. 53113

ህዳር 03 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** 1. ወ/ሮ አበበች በጅጋ - ጠበቃ አፈወርቅ ደጀኔ ቀረቡ

2. ወ/ሮ ሰብለወንጌል አበበ - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** ዶ/ር ተስፋዬ አካሉ - ጠበቃ ፋንታሁን አበራ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ተከሳሽ በሌለበት የተሠጠ ውሳኔ ተነስቶ ተከሳሹ ባለበት የሚታይበትን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ አግባብን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካቾች ላይ የቤት ሽያጭ ውል ተደርጓል የተባለው እንዲፈርስና ቤቱንም እንዲረከቡ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በመሰረቱት ክስ የአሁኑ አመልካቾች በሌሉበት ታይቶ አመልካቾች በቀድሞ ወረዳ 24 ቀበሌ 13 ውስጥ የሚገኝ ቁጥሩ 1099 የሆነ ቤት ለተጠሪ እንዲያስረክቡ የሚል ውሳኔ ተጠሪ አግኝተዋል፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካቾች ውሳኔውን ለሰጠው ፍርድ ቤት በሌሉበት የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ክርክሩ ባሉበት እንዲታይላቸው አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የአመልካቾች የስር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ ለ1ኛ አመልካች የጋዜጣ ጥሪ የተደረገው ያላግባብ መሆኑን 2ኛ ተጠሪም በሚኖሩበት ቤት መጥሪያው ተለጥፏል የተባለው ባግባቡ አለመሆኑን ዘርዝረው መጥሪያው በአግባቡ ደርሷል ለማለት ስለማይቻል መጥሪያው እንደአልደረሰ ተቆጥሮ በሌለንበት የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ክርክሩ ባለንበት እንዲካሄድ ይደረግልን የሚል ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ተጠሪ በአመልካቾች አቤቱታ ላይ አስተያየት እንዲሰጡበት በማድረግ ክርክሩን መርምሮ የአመልካቾችን አቤቱታ ውድቅ አድርጓል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካቾች ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ትእዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ የካቲት 02 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ለ1ኛ አመልካች የጋዜጣ ጥሪ የተደረገው የመጥሪያ አደራረስ ቅደም

ተከተልን ባልጠበቀ ሥነ ሥርዓት በመሆኑና ይህም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ስለመጥሪያ አደራረስ የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን የሚፃረር በመሆኑ አመልካች በሌሉበት የተሰጠው ውሳኔ ሊነሳ አይገባም ተብሎ የተወሰነው ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ትእዛዝ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካቾች ወደ ጉዳዩ ገብተን እንከራከር በሚል ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ የሆነው ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ ቀርበው ሰኔ 01 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ሁለት ገፅ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ በመልሳቸውም መጥሪያው ለአመልካቾች የደረሰው በሥነ ሥርዓቱ የተቀመጡትንና የሰበር ችሎቱም የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ባገናዘበ መልኩ መሆኑን በማረጋገጥ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የ1ኛ አመልካች ጠበቃም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች በሌሉበት የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳላቸው አቤቱታ ያቀረቡት መጥሪያ በተገቢው ስርዓት ቅደም ተከተሉን ተከትሎ አልደረሰም በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት የአመልካቾችን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው መጥሪያውን አመልካች ቤት ድረስ ተሂዶ እማኞች ባሉበት ማግኘት ሳይቻል ቀርቷል፣ ይህም ብቻ ሳይሆን መጥሪያው በአመልካች ቤት ላይ ተለጥፎ ነበር፤ ሊቀርቡ ባለመቻላቸው በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸዋል፡፡ ይህም ሆኖ ሳይቀርቡ ቀርተዋል፣ አንድ ሰው በአካል ተፈልጎ ካልተገኘ በመኖሪያው ላይ መጥሪያ ተለጥፎ እና በጋዜጣ ተጠርቶ ካልቀረበ መጥሪያው እንደደረሰው እንደሚቆጠር በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አስገዳጅ ውሳኔ ተሰጥቷል፣ አመልካች ታምሜ ወደ ሌላ ቦታ ሄጀ ነበር በማለት የገለፁት ከ10/11/2001 ዓ.ም በኋላ ሲሆን ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ የተወሰነው ከመሄዳቸው በፊት ነው ስለዚህ መጥሪያው ደርሷቸው እንደነበር ፍርድ ቤቱ ስለተረዳና በቂ ምክንያትም ስላላቀረቡ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይህ ችሎትም የስር ፍርድ ቤት ዋናውን ጉዳይ የመራበትን የኮ/መ/ቁጥር 148744 አስቀርቦ ተመልክቷል፡፡ መዝገቡ ሲታይም አመልካች መልሳቸውን ከመዝገቡ ጋር በ17/10/2001 ዓ.ም እንዲያያይዙ እና በ19/10/2001 ዓ.ም ለቃል ክርክር እንዲቀርቡ በ02/10/2001 ዓ.ም ትዕዛዝ መስጠቱን፣ የክፍሉ ቀበሌ ደንብ አስከባሪዎች ነን የሚሉ ሁለት ግለሰቦች በ09/10/2001 ዓ.ም በፃፉትና ማህተም በሌለው ደብዳቤ ቁጥር 1099 ወደሆነው ቤት ሄደን ነበር፣ ወ/ሮ አበበች በጅጋ በቤቱ ውስጥ እንደማይኖሩና የት እንደሚኖሩም የሚያውቅ ሰው አለመኖሩን ጠይቀን የተረዳን መሆናችንን እናረጋግጣለን በማለት ለፍርድ ቤቱ ማረጋገጫ የላኩ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ መገኘቱን የተጠሪ ጠበቃ በ16/10/2001 ዓ.ም በተጻፈ የቃለ መሐላ ማመልከቻ አንደኛ አመልካች በቤቱ ውስጥ አይኖሩም በሚል መጥሪያ ለማድረስ አለመቻሉን ገልጸው በጋዜጣ ማስታወቂያ እንዲጠሩላቸው መጠየቃቸውን 1ኛዋ አመልካች በጋዜጣ ማስታወቂያ እንዲጠሩ ታዝዞም በ8/11/2001 ዓ.ም ስላልቀረቡ ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ መታዘዙን ክሱ ቤት ለመረከብ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 36(4) መሰረት ቤቱን የያዘውን ሰው በተከሳሽነት መካተት አለበት ተብሎ የተሻሻለው ክስ እንዲቀርብ ታዞ ይኸው የተሻሻለው ክስ ለአመልካቾች ተልኳል ተብሎ መመዝገቡን የተላከው መጥሪያ ከስር

ፍርድ ቤት መዝገብ ሲታይም በከሳሽ የፍርድ ባለመብት ዶ/ር ተስፋዬ አካሉና በተከሳሽ የፍርድ ባለእዳ ወ/ሮ ሰብለወንጌል ታደሰ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የሚያወሳ መሆኑንና "ሰዎቹን ስላላገኘን በቤቱ በራፍ ላይ የለጠፍን መሆኑን እንገልፃለን" የሚል ይዘት የያዘ ሁኖ የ1ኛዋን አመልካች ስም ግን የሚጠቅስ አለመሆኑን መጥሪያው በመኖሪያ ቤቷ ላይ ተለጥፏል የተባለችው ሁለተኛ አመልካች ወ/ሮ ሰብለወንጌል ታደሰ በሚል ስም ሲሆን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78 መሰረት ጥያቄውን አልቀበልም ያለው ወ/ሮ ሰብለወንጌል አበበ በሚል መዝግቦ መሆኑን ከመዝገቡ ተረጋግጧል፡፡

የስር ፍርድ ቤት ዋናውን ጉዳይ ከመራበት መዝገብ ከተረጋገጡት፣ ከላይ ከተገለፁት ፍሬ ነገሮች በቀላሉ መገንዘብ የሚቻለው አንደኛ አመልካች በቅድሚያ በአካል ሊሰጣቸው የሚገባን መጥሪያ ባግባቡ እንዲደርሳቸው ሳይደረግ እና በማትኖርበት ቤት ላይም ቢሆን የሷን ስም የሚጠራ መጥሪያ በተገቢው አካል ተለጥፏል ለማለት የማይቻል መሆኑን እንዲሁም ሁለተኛዋን አመልካች በተመለከተ ደግሞ የአባቷ ስም ተለውጦ የፍርድ አፈፃፀም መጥሪያ እንጂ ከተጠቃሹ ጉዳይ ጋር አግባብነት ያለው መጥሪያ አለመለጠፉ በሚገባ መረጋገጡን ነው፡፡

ወደ ሕጉ ስንመጣ፤ በመሰረቱ የመጥሪያ አሰጣጥ ዘዴና ቅደም ተከተሉ እንዲሁም መጥሪያው ለማን እንደሚሰጥ የሚመለከተው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ክፍል ዓይነተኛ ዓላማ ከሆኑት መካከል አንዱ ተከራካሪ ወገኖችን እኩል የመከራከር መብት እንዲኖራቸው በማድረግ ጉዳዩን ፍትሐዊ በሆነ አኳኋን ለመወሰን ማስቻል መሆኑን ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ መጥሪያ የሚደርስበትን ተገቢ መንገድና ለማን መድረስ እንዳለበት ማረጋገጥ ይገባዋል፡፡ መጥሪያ በተገቢው መንገድ ደርሶት ተከራካሪ ወገን ካልቀረበ ወይም መጥሪያን አልቀበልም ካለ ፍርድ ቤቱ ሊከተለው የሚገባው ስርዓትም በሕጉ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ከእነዚህም ድንጋጌዎች መካከል አንዱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 70(ሀ)፣ 103፣ 104፣ 105፣ 106 እና 107 ስር የተመለከተው ሲሆን በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት ተከሳሽ በሌለበት ክርክሩ ታይቶ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችለው መጥሪያው በአግባቡ የደረሰው መሆኑ ሲረጋገጥ ወይም መጥሪያውን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆኑ ወይም ሊገኝ ያልቻለ መሆኑ ሲረጋገጥ ወይም መጥሪያውን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆኑ ወይም ሊገኝ ያልቻለ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ ድንጋጌዎቹ መጥሪያው በትክክል ያልደረሰው መሆኑ ከተረጋገጠ ጉዳዩ ተከሳሽ በሌለበት እንዲታይ የማይታዘዝ ስለመሆኑ ያስገነዝባሉ፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 70(ሀ) ድንጋጌ ስር ላይ "መጥሪያው በትክክል መድረሱ" የሚለው ሐረግ መኖሩም የሚያሳየው ስለመጥሪያ አሰጣጥና አደራረስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 94 እስከ 110 ድረስ የተመለከቱት ሁኔታዎች በአግባቡ መሟላታቸውን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ አንድ ተከሳሽ በሌለበት ጉዳዩ ታይቶ ውሳኔ ከተሰጠውም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78 መሰረት መፍትሔ መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት መፍትሔ ሊጠየቅ የሚችለው አቤቱታ አቅራቢው በሚያቀርበው አቤቱታ ላይ የጥሪው ትዕዛዝ "በሚገባ ያልደረሰው" መሆኑን በመጥቀስ ይህንኑ ማረጋገጥ ሲችል ነው፡፡ ከእነዚህ ሁሉ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው አንድ ሰው የመከራከር መብቱን እንደተወው የሚቆጠረው መጥሪያው በሕጉ በተዘረጋው ሥርዓትና ቅደም ተከተል መሰረት ደርሶት ክርክር ያለው መሆኑን እያወቀ ሳይቀርብ ሲቀር ብቻ መሆኑን ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ በሕጉ የተዘረጋውን ስርዓት ተከትሎ አማራጭ የመጥሪያ አደራረስ ሥርዓት ከፈጸመ መጥሪያው ለተከሳሹ እንደደረሰ እንደሚቆጠርና በቂና ሕጋዊ ምክንያት ካለው ብቻ ወደ ክርክሩ እንዲገባ የሚፈቀድ መሆኑን ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያስገነዝባል፡፡ ስለሆነም



www.chilot.me

ማንኛውም ውሳኔ መስጠት ያለበትም በሕጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሰረት መጥሪያው መድረሱ በሚገባ የተረጋገጠና የተከሳሽ የመከራከር መብት የተጠበቀ መሆኑ ሲታወቅ ሊሆን ይገባል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ከላይ ከስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች የሚያሳዩት 1ኛ አመልካችን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ ወደ ጋዜጣ ጥሪ የሄደበት አካሄድ ቅድሚያ ሊፈጸም የሚገባውን ሥርዓት በአግባቡ አሟጦ ሳይጨርስና ተገቢ ያልሆነ መግለጫ ስለቀረበለት ከመሆኑም በላይ ክሱ ተሻሽሎ ከቀረበ በኂላም ቢሆን የአመልካቿ ስም ተጠቅሶ መጥሪያው መላኩ ሳይረጋገጥ ነው፡፡ የሁለተኛዋ አመልካችም የአባት ስም ተለውጦ የፍርድ አፈፃፀም መጥሪያ እንጂ ከዋናው ጉዳይ ጋር አግባብነት ያለው መጥሪያ ያልተለጠፈላቸው መሆኑን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ በግልፅ ያሳያል፡፡ የጋዜጣ ጥሪና በተከሳሽ መኖሪያ ላይ በአግባቡ መጥሪያ እንዲለጠፍ ማድረግ ውጤታቸው መጥሪያው እንደደረሰ የሚያስቆጥር የሚሆነው ተከሳሽ መገኘት አለመቻሉ በሚገባ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ የተገለፁትና በስር ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 148744 የተረጋገጡት ፍሬ ጉዳዮች ለአመልካቾች መጥሪያው እንደሕጉ አነጋገር በሚገባ ያልደረሳቸው መሆኑን የሚያረጋግጡ ሁነው አግኝተናል፡፡ ይህ በተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካቾች ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቶ ገብተን እንከራከር ሲሉ ያቀረቡትን ጥያቄ በበታች ፍርድ ቤቶች ውድቅ የሆነው በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕጉ ስለመጥሪያ አደራረስ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ከመከራከር መብት ጋር ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ትእዛዙ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 148744 ህዳር 08 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 86844 ህዳር 23 ቀን 2002 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾች በሌሉበት ታይቶ የተሠጠው ውሳኔ ባሉበት እንዲታይ ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ የሆነው ስለመጥሪያ አደራረስ ሥርዓት የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ከመከራከር መብት ጋር ባላገናዘበ መልኩ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካቾች በሌሉበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 78(2) መሰረት ተነስቶ ባሉበት እንዲታይ ብለናል፡፡
4. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አመልካቾች ባሉበት በመመልከት የግራ ቀኙን ጉዳይ ሠምቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

*ራ/ታ*



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 53607

ህዳር 14 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጉስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች ፡-** የምጥን መንደር መኖሪያ ቤቶች የህብረት ሥራ ማህበር ጠበቃ ዜና ደባሱ ቀረበ

**ተጠሪዎች ፡-** 1. ወ/ሮ ባየች አይገምት - በሌሉበት

2. ወ/ሮ ሽዋሰገድ አይገምት - በሌሉበት

3. ወ/ሮ ሃና መኰንን - ከጠበቃ ይልማ አቻሜ ጋር ቀረበች

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ በሁከት ይወገድ ክስ መነሻነት ክርክር ተካሂዶ የተሰጠውን ውሳኔ መሠረት በማድረግ የተጀመረውን የአፈጻጸም ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው የአሁኑ አመልካች የሁከት ይወገድልኝ ክስ በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ መስርቶ ክርክር ከተደረገ በኂላ፣ የፍርድ ባለመብት ሆኖአል፡፡ በውሳኔው 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ በአመልካች ይዞታ ላይ ሁከት የፈጠሩ መሆናቸውን ስለመረጋገጡ ተመልክቶአል፡፡ አመልካች የአፈጻጸም መዝገቡን ያስከፈተው በውሳኔው መሠረት የፍርድ ባለዕዳ የሆኑት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ ይዞታውን ለቀው እንዲወጡላት ትዕዛዝ ለማስጠት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ 3ኛ ተጠሪ አፈጻጸም በተጠየቀበት ቦታ ይዞታ ያለኝ እኔ ነኝ በማለት መቃወሚያ በማቅረብዋ የክርክሩ ተካፋይ ልትሆን ችላለች፡፡ አፈጻጸሙን የጀመረው የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን ጥያቄ በመቀበል እንደውሳኔው እንዲፈጸም ትዕዛዝ ሰጥቶ የነበረ ሲሆን የአሁንዋ 3ኛ ተጠሪ ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረብዋ ትዕዛዙ ተሽሮአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርቦ ክርክሩ በዚህ ደረጃም ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም የሰበር ችሎቱ የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ አፅንቶአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች መጋቢት 3 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ባለመቅረባቸው ክርክሩ የተሰማው እነሱ በሌሉበት ነው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ



www.chilot.me

የተደረገው የሥር ፍ/ቤቶች የ3ኛ ተጠሪን መቃወሚያ በመቀበል የመወሰናቸውን አግባብነት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ከሥር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ ባጭሩ እንዳመለከትነው ለአፈጻጸሙ መሠረት የሆነው ውሳኔ በተሰጠበት ክርክር ተጠሪ ተከራካሪ ወገን አልነበረችም፡፡ አመልካች በ1ኛ እና በ2ኛ ተጠሪዎች ላይ ክስ የመሠረተው በሕጋዊ መንገድ በያዝኩት መሬት ላይ ሁከት ፈጥረውብኛል፡፡ ስለዚህም ያለ አግባብ የያዙትን መሬት ለቀው ይወጡ ዘንድ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም ተጠሪዎች (ተከሳሾች) ስፋቱ በካሬ ሜትር ተለክቶ ለአመልካች በተሰጠው መሬት ውስጥ ገብተዋል በሚል ምክንያት ከሕግ ውጪ የያዙትን መሬት እንዲለቁ ወስኖአል፡፡ ፍ/ቤቱ ይህን የመሰለ ውሳኔ ሊሰጥ የቻለው መሬቱ በአመልካች የተሰጠ መሆኑን በማረጋገጥ ነው፡፡ 3ኛ ተጠሪ ክርክሩ ውስጥ የገባችው ከዚህ በኋላ ብቻ ሳይሆን መቃወሚያዋን ያቀረበችውም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.418 የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የአፈጻጸም ክርክር በቀጠለበት መዝገብ ስለመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ከሰጡአቸው ውሳኔዎች ለመገንዘብ ችለናል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እና የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የተጠሪን መቃወሚያ በመቀበል የሰጡት ውሳኔ እንዳየነው ክርክር የተነሳበት መሬት ለተጠሪ የተሰጠ ነው ወይም የተጠሪ ይዞታ ነው የሚል እንድምታ ያለው ነው፡፡ ይህ ውሳኔ በይዘቱ ሲታይ በአመልካች እና በ1ኛና በ2ኛ ተጠሪዎች መካከል በተነሳው ክርክር መነሻነት የተሰጠውን ውሳኔ የሚሽር ነው፡፡

ጉዳዩ የፍትሐብሔር ክርክርን የሚመለከት በመሆኑ የሚመራው በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሠረት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ የክስ አቀራረብን፣ የክርክር አመራርን፣ አወሳሰን እና አፈጻጸምን የሚመለከቱ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ይዞአል፡፡ በዋናው ክርክርም ሆነ በአፈጻጸም ሂደት መብታችን ተነክቶአል የሚሉ ሦስተኛ ወገኖች መቃወሚያ የሚያቀርቡበት እና መብታቸውን የሚያስከብሩበት ሥርዓት በዚሁ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ተካቶአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ሦስተኛ ተጠሪ ለጉዳዩ ሦስተኛ ወገን በመሆንዋ እና መብቴ በአፈጻጸሙ ሂደት ተነክቶአል ብላ በማመንዋ በአፈጻጸም ደረጃ ባለው ክርክር ላይ መቃወሚያ ማቅረብ የሚያስችለውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.418ን መሠረት በማድረግ ክርክሩ ውስጥ ገብታለች፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም መቃወሚያው የቀረበበትን ሥርዓት በትክክል ቢገነዘቡም፤ አፈጻጸሙ የቀጠለበት መሬት የማን ይዞታ ነው ወይም በመሬቱ ላይ የተሻለ መብት ያለው የትኛው ወገን ነው የሚል የንጥጥር አይነት ጭብጥ በመያዝ ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ ፍ/ቤቶቹ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.418 መሠረት የቀረበውን መቃወሚያ ለመወሰን የተከተሉት አካሄድ አግባብነት ያለው ነው ወይ? የሚለውን ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ የሚሆነውም እዚህ ላይ ነው፡፡

በዋናው ክርክርም ሆነ በአፈጻጸም ሂደቱ መብታችን ተነክቶአል ብለው የሚያስቡ ሦስተኛ ወገኖች መቃወሚያቸውን የሚያቀርቡበት ሥርዓት በሥነ-ሥርዓት ሕጉ ስለመዘርጋቱ ቀደም ሲል ተመልክተናል፡፡ በዋናው ክርክር የሚሰጠው ውሳኔ እና በውሳኔው መሠረት ለማስፈጸም የሚደረገው ሂደት የተለያዩ በመሆናቸው በሚቀርቡት መቃወሚያዎች ላይ የሚሰጡት ውሳኔዎችም የተለያዩ ናቸው፡፡ መቃወሚያ አቅራቢው መብቱ የተነካው በአፈጻጸም ሂደቱ ከሆነ ከአፈጻጸም ሂደቱ ጋር የተያያዘ መፍትሄ ነው የሚሰጠው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.418 መሠረት በሚቀርብ መቃወሚያ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.419 ተመልክቶአል፡፡ በዚህ መሠረት መቃወሚያው ተቀባይነት ያገኘ ከሆነ በአፈጻጸም የተያዘው ንብረት በከፊል ወይም በሙሉ እንዲለቀቅ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡ ከዚህ አልፎ በአፈጻጸም የተያዘው ንብረት ለአንዱ ወይም ለሌላው ተከራካሪ ወገን ይገባል

የሚል ዳኝነት አይሰጥም፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ በዋናው ክርክር የተሰጠውን ውሳኔ የሚሽር ወይም የሚያሻሽል ውሳኔ አይሰጥም፡፡ የዚህ አይነት ውሳኔ መስጠት የሚቻለው ዋናውን ውሳኔ በመቃወም አቤቱታ ሲቀርብ ነው፡፡ ይህ ደግሞ እራሱን የቻለ የአቀራረብ ሥርዓት እና የክርክር አመራር ሂደት ያለው ነው፡፡ በዚህ ረገድ ተገቢው ድንጋጌም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.358 የተመለከተው ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ 3ኛ ተጠሪ በዚህ ቁጥር 358 መሠረት ወይም ዋናውን ውሳኔ በመቃወም አቤቱታ አላቀረበችም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ግን ዋናውን ውሳኔ የሚሽር ነው፡፡ ከዚህ የተነሳም ፍ/ቤቶቹ የሰጡት ውሳኔ (አቤቱታ የቀረበበት) በሕጉ አተገባበር/አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ.09838 መስከረም 27 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ 11818 የካቲት 30 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በቀድሞው ውሳኔ መሠረት የተጀመረው አፈጻጸም የሚቀምበት አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

   መዝገቡ ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

ራ/ታ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 42714

ኀዳር 8 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፍትሕና ሕግ ጉዳዮች ቢሮ - ተስፋዬ ዘመድኩን ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1. የሽቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት ገ/ማርያም ዋዴሮ ቀረበ

2. አመሃ ጥበቡ ቀረበ

3. በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ የቤቶች ማስተላለፍ ጽ/ቤት - ሽምሱ ስሩር ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከቤት ባለቤትነት መብት ጋር ተያይዞ የተነሣውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው አመልካች የክርክሩ ተካፋይ የሆነው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት መቃወሚያ በማቅረቡ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ላይ ክስ አቅርቦ ከተከራከሩ በኋላ፣ ክስ ያቀረበበትን ቤት እንዲረከብ ውሣኔ አሰጥቶአል፡፡ አመልካች መቃወሚያ ያቀረበው ቤቱ ከጅምሩ የአስተዳደሩ ሲሆን ዋጋ ተቀብሎ ለ1ኛ ተጠሪ በሽያጭ ያስተላለፈው በመሆኑ ቀደም ሲል የተሰጠው ውሣኔ መብቴን ይነካል በማለት ነው፡፡ ፍ/ቤቱም መቃወሚያውን ከመረመረ በኋላ፣ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ጥር 12 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው አመልካች መብቴ ተነክቶአል በማለት ያቀረበው የመቃወሚያ ክርክሩ ሣይሰማ ውድቅ መደረጉ አግባብ ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች ባቀረበው መቃወሚያ መሠረት የክርክሩ ተካፋይ በመሆን ሊያቀርበው ይችል የነበረውን የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር ክርክር እንዲያሰማ አልተደረገም፡፡ በሰበር አቤቱታው እንደገለፀው በጉዳዩ ያገባኛል የሚለው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ. 2/95 እና በአዋጅ ቁ. 4/2000 /እንደተሻሻለ በአንቀጽ 29 መሠረት የተቋቋመ የአስተዳደሩ አስፈፃሚ አካል በመሆኑ ነው፡፡ በተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 29/3/ መሠረት የከተማውን አስተዳደርና የነዋሪዎችን መብትና ጥቅም በሚመለከቱ ጉዳዮች ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር መብት የተሰጠው መሆኑንም በክርክሩ ገልጾአል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 በተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት መቃወሚያ ያቀረበው ለክርክሩ መሠረት ከሆነው ቤት ጋር በተያያዘ ያለውን የከተማውን አስተዳደር የነዋሪዎች መብትና ጥቅም ለማስከበር በሚል እንደሆነም ተገንዝበናል፡፡

አስቀድሞ የተሰጠውን ውሣኔ ለማስነሣት መቃወሚያ ማቅረብ የሚችል ወገን በክርክሩ ውስጥ መግባት የሚገባው ሆኖ ነገር ግን ተካፋይ ያልነበረ፤ ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድም መብቱን የሚነካበት የሆነ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 ተደንግጎአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው አመልካች በአስተዳደሩ የአስፈፃሚ አካልነቱ ሊያስጠብቀው የሚገባው የአስተዳደሩና የነዋሪዎች መብትና ጥቅም እንዳለ በመግለጽ መቃወሚያውን አቅርቦአል፡፡ መቃወሚያው የቀረበለት ፍ/ቤት ግን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 360/2/ በተደነገገው መሠረት ክርክሩን አልሰማም፡፡ አቤቱታውን ውድቅ ያደረገው ቀደም ሲል በተሰጠው ውሣኔ መብቱ ከተነካ "በሕግ አግባብ ውሣኔውን ከሚያስለውጥ በቀር … በዚህ ረገድ ሊያቀርበው የሚችለው የመቃወም አቤቱታ … የለም" የሚል ምክንያት በመስጠት ነው፡፡ ይህን አይነቱ አካሄድ አግባብ ያለውን የሥነ ሥርዓቱን ድንጋጌ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ አይደለም፡፡ አመልካች ቀድሞ በተሰጠው ውሣኔ መብቴ ተነክቶአል ማለቱ እስከተረጋገጠ ድረስ ውሣኔውን ለማስለወጥ የሚችለው መቃወሚያውን በማቅረብ ነው በፍ/ቤቱ ግንዛቤ ሣያገኝ ቀርቶአል የምንለውም ይህ ነው፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ በሥነ - ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 71179 ህዳር 10 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 75281 ጥር 7 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡

2/ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን የመቃወሚያ አቤቱታ ተቀብሎ በጉዳዩ ሥረ ነገር ግራ ቀኝ ወገኖችን አከራክሮ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት ብለናል፡፡

3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 46281

ታህሣሥ 28 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፣ ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፣ ወ/ሮ አበባዬ አቢ ደራ ወርቅ ጠበቃ ተስፋዬ ርቀቱ ቀረበ

ተጠሪ፣ ይገረም ፈዬ አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ በሰበር ችሎቱ እንዲመረመር የተያዘው ጭብጥ ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሠረተው ክስ ተቀባይነት የለውም ተብሎ ከተወሰነ በኃላ ክሱን ሲመሠረት የከፈለውን የዳኝነት ገንዘብ ተጠሪ ትተካለት የተባለው በአግባቡ ነው ወይ? የሚል ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው ተጠሪ ክስ የመሠረተው ብር 30,000 ግምት ያለው ባህር ዛፍ ቆርጣ ስለወሰደችብኝ ገንዘቡን ትክፍለኝ ዘንድ ይወሰንልኝ በማለት ነው አመልካች ለክሱ በሰጠችው መልስ ክሱን በመካድ የተከራከረች ሲሆን ፍ/ቤቱም የአመልካችን ክርክር በመቀበል የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጓአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ውሣኔውን በመቃወም ይግባኙን ለሚሰማው የበላይ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ለክሱ ምክንያት የሆነው ባህርዛፍ ስለመቆረጡ በማስረጃ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ አትከፍልም በማለት በአንድ በኩል ሲወስን በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ለዳኝነት የከፈለውን ብር 1718.50 አመልካች ትተካለት ብሎአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ግንቦት 27 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በመቀጠልም ግራቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር በጭብጥነት ከተያዘው ነጥብ አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

እንደምንመለከተው ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሠረተው ክስ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ባየው ፍ/ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተቀባይነትን አላገኘም፡፡ ክሱ ሙሉ በሙሉ ውድቅ በመደረጉም በክሱ የተመለከተውን ብር 30,000 አመልካች ልትከፍልህ አይገባም ተብሎ ተወስኖአል፡፡ ለዳኝነት ተከፈለ የተባለው ብር 1718.50 ሊከፈል የቻለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 215 መሠረት ነው በሥነ ሥርዓት ሕጉ በተለየ ሁኔታ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ክሶች ሁሉ ዳኝነት ሊከፈልባቸው እንደሚገባ በተጠቀሰው ቁጥር 215/1 አመልክቶአል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የቻልነው

የዳኝነት ገንዘብ የመክፈል ግዴታ የከሣሹ ወገን እንደሆነ ነው በእርግጥ በክርክር ወቅት ወይም ክርክሩን ለማካሄድ የሚወጡ ወጪዎች ስለወጪና ኪሣራ በሚመለከት በተደነገገው በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ በስምንተኛው መጽሐፍ ሥር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር እየታዩ በየትኛው ተከራካሪ ወገን እንደሚሸፈኑ በፍ/ቤቱ ውሣኔ የሚሰጥበት ሁኔታ እንዳለ ይታወቃል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ ቁ 462 እንደተመለከተው በሌላ አኳኋን በግልፅ ካልተደነገገ በቀር በክሱ ምክንያት የወጣውን ወጪና ኪሣራ የትኛው ወገን ሊከፍለው እንደሚገባ ፍ/ቤቱ ተገቢ በመሰለው ሁኔታ ሊወሰን ይችላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ያለአግባብ በአመልካች ላይ ክስ መመስረቱ ተረጋግጦ ጥያቄው ውድቅ እንዲሆን ከመወሰኑ አልፎ በአመልካች በኩል የተፈጸመ ኪሣራ ሊያስከፍል የሚችል ድርጊት /ጥፋት/ ስለመኖሩ በሥር ፍ/ቤት ውሣኔ አልተመለከተም ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ለተጠሪ ኪሣራ የምትከፍልበት የሕግ አግባብ አይኖርም ሕግ ሳይፈቅድ ረቺ የሆነውን ወገን ለተረቺ ኪሣራ እንዲከፍል መወሰን ደግሞ ሕጉን በተሳሳተ ሁኔታ መተረጎም ወይም መተግበር ነው፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በጋምቤላ ሕዝቦች ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በ28/07/2001 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሻሽሎአል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ የዳኝነት ገንዘቡን እንድትተካ የምትገደድበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ግራቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

   መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

ም.አ



www.chilot.me

ሰ/መ/ቁ 47960

ታህሣሥ 12 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ታከለ ባልቻ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ አዜብ ፀጋዬ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የሱማሌ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ዕቃንና ሰውን በየብስ ለማጓጓዝ በተደረገ ውል ምክንያት ለደረሰ ጉዳት ሊከፈል የሚገባውን የካሣ መጠን የሚመለከት ነው፡፡ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት የመለያ ቁጥሩ 2612 የሆነ ሻርፕ የፎቶና የፊልም ማባዥያ ማሽን ከሻርፕ ጄኔራል ትሬዲንግ ብር 200,000/ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ገዝቼ ንብረትነቱ የተከሳሽ/የአሁኑ አመልካች/ የሆነ የመለያ ቁጥሩ 3-12334 አይሱዙ መኪና እኔንና ዕቃውን ጅጅጋ እንዲያደርስ ተዋውለን ዕቃውን ጭኖ ወደ ጅጅጋ ስንጓዝ ሐምሌ 18 ቀን 1999 ዓ.ም. ከአዋሽ አስር ኪሎ ሜትር ዕርቀት ከምትገኘው "መድን" ተብሎ ከሚጠራው መንደር አካባቢ መኪናው በመገልበጡ የፊልምና የፎቶ ማሽን ወድሟል፡፡ ስለሆነም በአደጋው ብር 200,000/ሁለት መቶ ሺህ ብር ማሽኑ በመውደሙ የደረሰብኝን ኪሣራ እንዲከፍል ይወሰንልኝ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአደጋው እግሬን የተሰበርኩ በመሆኑ ለደረሰብኝ ጉዳት ካሣ ብር 30,000/ሠላሳ ሺህ ብር/ ለህክምና ያወጣሁትን ብር 40,000/አርባ ሺህ ብር/ እና በመታመሜ ምክንያት የቀረብኝን ገቢ ብር 30,000/ሠላሳ ሺህ ብር/ በድምሩ ተከሣሽ/የአሁኑ አመልካች/ ብር 300,000/ሦስት መቶ ሺህ ብር/ እንዲከፍለኝ በማለት ተጠሪ ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርበው ማሽኑ እየሠራ ነው፡፡ ከሣሽ/ተጠሪ/ ለህክምና ብር 40,000/አርባ ሺህ ብር/ ያወጡ መሆኑን ያቀረቡት ማስረጃ የለም ማሽኑ አዲስ ወይም ያገለገለ መሆኑ አልተረጋገጠም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

የከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ ባደረጉት የዕቃና ሰው መጓጓዝ ውል መሠረት ከሳሽ/ተጠሪ/ ማሽኑን ጭነው ወደ ጅጅጋ ሲሄዱ አደጋው የደረሰ መሆኑን ተከሳሹ/አመልካች/ ያመኑ መሆኑንና የሚያከራክረው መሠረታዊ ጭብጥ የካሣው መጠን መሆኑን በውሣኔው ከገለፀ በኋላ



www.chilot.me

ቁጥሩ 2612 የሆነው ሻርፕ የፎቶና የፊልም ማባዥያ ማሽን ተጠሪ ብር 200,000/ሁለት መቶ ሺህ ብር/ የገዙት መሆኑን የሚያረጋግጥና ማሽኑ የወደመ መሆኑን በመግለፅ ሻጩ ሻርፕ ጀኔራል ትሬዲንግ ማሽኑን ካየ በኂላ በፅሑፍ እንዳረጋገጠ በመጥቀስ፣ ጉዳቱ በድንገተኛ አደጋ የደረሰ በመሆኑ አመልካች ለተጠሪ ብር 180,000/አንድ መቶ ሰማኒያ ሺህ ብር/ ይክፈል ለህክምና፣ ለጉዳት ካሣና ተጠሪ ለቀረበት ገቢ ብር 54,00/ሃምሣ አራት ሺህ ብር/ ተከሳሽ ለከሳሽ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ሻርፕ ጄኔራል ትሬዲንግ ማሽኑን ከተረከበና ካየ በኂላ በማሽኑ ላይ የደረሰበት ጉዳት የለም ብለው በቃል ሲናገሩ ሰምተናል የሚል የአመልካችን ሁለት ምስክሮች ቃል ሰምቷል፡፡ ከዚያ በኂላ አመልካች ማሽኑ ጉዳት አልደረሰበትም ስለዚህ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ ብር 180,000/አንድ መቶ ሰማኒያ ሺህ ብር/ እንድከፍል የሰጠው ውሣኔ አላግባብ ነው በማለት ውሣኔውን አሻሽሎ አመልካች ለተጠሪ ብር 25,000/ሃያ አምስት ሺህ ብር/ ለህክምና ለደረሰባት ጉዳት ካሣ እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ችሎት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ሐምሌ 29 ቀን 2001 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የፎቶና የፊልም ማባዥያ ማሽኑ ብልሽት እንደደረሰበት የቀረቡት ማስረጃ ሀሰተኛ ማስረጃ መሆኑን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀርበው የምስክርነት ቃል በሰጡ ሁለት ምስክሮች አረጋግጫለሁ፡፡ አደጋው የደረሰው ሹፌሩን ሽፍቶች ሊያስገድዱት መሀል መንገድ ውስጥ በመግባታቸውና ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በመሆኑ ለደረሰው ጉዳት ሃላፊ ነህ መባሉ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት የወሰነው የካሣ መጠን የንግድ ህግ ቁጥር 597ን የሚቃረን ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት እንዳለ ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ማሽኑ የወደመ መሆኑ በፅሑፍ ከተገዛበት ድርጅት የተሰጠን ማስረጃ እያለ ስለ ማሽኑ ምንም አይነት ሙያ በሌላቸው ሁለት ምስክሮች ቃል አስተባብያለሁ በማለት ያቀረቡት ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም፡፡ አመልካች ለሥር ፍርድ ቤት የላነሱትን መከራከሪያ ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል ነው አደጋው የደረሰው በማለት የቀረቡት ክርክር በህግ በኩል ተቀባይነት የሌለውና በማስረጃ ያልተረጋገጠ ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ሰኔ 20 ቀን 2002 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች የካቲት 1 ቀን 2002 ዓ.ም. የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አመልካች ለተጠሪ መክፈል ያለበት የካሣ መጠን አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ውሣኔ ለመስጠት ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ ብር 200,000/ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ዋጋ ያለውን ሻርፕ የፎቶና የፊልም ማባዥያ ማሽን ከአዲስ አበባ ወደ ጅጅጋ ለማድረስ ዋጋ ከፍለው በአመልካች ንብረት በሆነው መኪና ላይ የጫኑ መሆኑና ንብረትነቱ የአመልካች የሆነው መኪና የመገልበጥ አደጋ የደረሰበት ስለመሆኑ አመልካችና ተጠሪ የማይካካዱበት ነጥብ ነው፡፡ ይኸም አመልካች



www.chilot.me

የተጠሪን ዕቃ በየብስ ትራንስፖርት በማጓጓዝ፣ ከመድረሻው ሥፍራ ማለትም ጅጅጋ ከተማ ለማድረስ፣ ተጠሪ በበኩላቸው የትራንስፖርት ግልጋሎት ክፍያ ለመክፈል ውል የነበራቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ አደጋው ከደረሰ በኂላ በአመልካች መኪና ላይ ተጭኖ የነበረውን ማሽን ተጠሪ ከገዙበት ሻርኘ ጄኔራል ትሬዲንግ ወስደው ለማሣየት በመስማማት የፎቶና የፊልም ማባዥያ ማሽኑን ለሻርኘ ጄኔራል ትሬዲን ወስደው ያስረከቡ መሆኑ በተጠሪም ሆነ በአመልካች በኩል በቀረበው ክርክር ተገልጿል፡፡

የከፍተኛ ፍርድ ቤት አደጋው ስለደረሰበት ማሽን ዋጋ፣ እና አጠቃላይ ባህሪይ በማሽኑ ላይ ስለደረሰው ጉዳይ የሚያውቀው ሻርኘ ጄኔራል ትሬዲንግ ማሽኑ በአደጋው ምክንያት በደረሰበት ጉዳት ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጭ የወጣ መሆኑን በፅሑፍ የሰጠውን ማረጋገጫ በመቀበል፣ አመልካች ለተጠሪ ብር 180,000/አንድ መቶ ሰማኒያ ሺህ/ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሻርኘ ጄኔራል ትሬዲንግ በማሽኑ ላይ ስለደረሰው ጉዳት ማሽኑን ከመረመረ በኂላ የሰጠው የሙያ አስተያየት ታዓማኒነት የለውም የሚል ከሆነ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 136(1) በሚደነግገው መሠረት ስለማሽኑ ልዩ ዕውቀት ያለው ባለሙያ በመመደብ እንዲመረመር ማድረግ ይገባው ነበር፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ስለ ማሽኑ ዕውቀትና ክህሎት ያለው ድርጅት ማሽኑን ከአደጋው በኂላ መርምሮ በፅሑፍ የሰጠውን የሙያ ማረጋገጫ ማሽኑን ለሻርኘ ጄኔራል ትሬዲንግ ስናደርስ ማሽኑ ደህና ነው በማለት የድርጅቱ ሠራተኞች ሲናገሩ ሰምተናል የሚሉ ስለ ማሽኑ ልዩ ዕውቀትና ሙያ የሌላቸው ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል በመቀበል በሻርኘ ጄኔራል ትሬዲንግ በማሽኑ ላይ ስለደረሰው ጉዳት የቀረበውን የሙያ ማረጋገጫ ውድቅ ማድረጉ፣ ልዩ ዕውቀትና ክህሎትን መሠረት በማድረግ አንድ ጉዳይ ተመርምሮ የተሰጠ የሙያ አስተያየትን ለማስተባበል የሚቻለው በጉዳዩ የተሻለ የሙያ ዕውቀትና ክህሎት ያለው ባለሙያ ጉዳዩን መርምሮ በሚያቀርበው የሙያ አስተያየት "ነው" የሚለውን የማስረጃ ህግ መርህና የፍትሐብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 136(1) ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘትና መንፈስና ዓላማ ጋር የማይጣጣም ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሙያ ምርመራ በማድረግ የቀረበን ማረጋገጫ መሠረት በማድረግ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ የሻርኘ ጄኔራል ትሬዲንግ ሠራተኞች ማሽኑ ደህና ነው በማለት ሲናገሩ ሰምተናል የሚሉ ሁለት ምስክሮችን ቃል መሠረት በማድረግ መሻሩ ስህተት ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ሆኖ ስላገኘነው አመልካች በዚህ በኩል ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

አመልካች አደጋው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በማለት ያቀረበው ክርክር ለሥር ፍርድ ቤት ያልቀረበና በይግባኝና በሰበር ደረጃ ያላነሱት በመሆኑ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም የመለያ ቁጥሩ 2612 የሆነው የተጠሪ ማሽን ጅጅጋ ለማድረስ ዋጋ ተቀብሎ ከጫነ በኂላ የማሽኑ ደህንነት በተጠበቀበት ሁኔታ ያላደረሰና መንገድ ላይ በደረሰው አደጋ ማሽኑ መሉ በሙሉ ከአገልግሎት ውጭ በመሆኑ አመልካች ለተጠሪ ብር 180,000/አንድ መቶ ሰማኒያ ሺህ ብር/ እንዲከፍል የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ማፅናቱ ዕቃን በየብስ ትራንስፖርት ስለማጓጓዝ የወጡትን የንግድ ህግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ በመሆኑ የአመልካችን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

2. አመልካችና ተጠሪ የዕቃ ማጓጓዥያ ውል ብቻ ሣይሆን ተጠሪን ከአዲስ አበባ እስከ ጅጅጋ ለማጓጓዝ አመልካቹ ተስማምቶ እየተጓዙ እያለ መኪናው በደረሰበት የመገልበጥ አደጋ በተጠሪ ላይ ሃያ ፐርሰንት(20%) ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ በኢትዮ ተቢብ ሆስፒታል በተሰጠ የፅሑፍ ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን ከፍተኛው ፍርድ ቤት በውሣኔው ውስጥ ገልጿል፡፡ አመልካች



www.chilot.me

ተጠሪ ለደረሰባቸው ጉዳት የህክምና ወጭ በሚል ብር 9,000/ዘጠኝ ሺህ ብር/ ለአመልካች የከፈሉ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ሊከፍል የሚገባውን የካሣ መጠን ያሰላው ከውል ውጭ የሚደርስ ሃላፊነት ህግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ሆኖም አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል የሚገባው የካሣ መጠን መሰላት የሚገባው በንግድ ህግ አንቀፅ 597 ድንጋጌዎች መሆን ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በንግድ ህግ አንቀፅ 597 ንዑስ አንቀፅ 1 አንድ ሰውን ለመጓጓዝ ውል የተዋዋለ ሰው በጉዞ ወቅት በሰውየው ላይ ለደረሰው ጉዳት መክፈል የሚገባው የካሣ መጠን ከብር 40,000/አርባ ሺህ ብር/ መብለጥ እንደሌለበት ይደነግጋል፡፡

አመልካች ተጠሪ ብር 9,000/ዘጠኝ ሺህ ብር/ ለህክምና ወጭ እንዲሆን የሰጡ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ከሆነ ከላይ በጠቀስነው የህግ ድንጋጌ መሠረት አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉት የሚገባው ቀሪ የካሣ ገንዘብ ብር 31,000/ሠላሳ አንድ ሺህ ብር/ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በንግድ ህግ ቁጥር 597 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ሣያሻሻል ተጠሪ በአመልካች መኪና ሲጓዙ ለደረሰባቸው ጉዳት አመልካች ካሣ ብር 54,000/ሃምሣ አራት ሺህ ብር/ ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ይህንን የውሣኔ ክፍል በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት በማሻሻል፣ አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው የአካል ጉዳት ሊከፍል የሚገባው ብር 40,000 /አርባ ሺህ ብር/ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 9,000/ዘጠኝ ሺህ ብር/ የከፈሉ መሆኑ ስለተረጋገጠ አመልካች የሚቀርበት የብር 31,000/ሠላሳ አንድ ሺህ ብር/ ብቻ ነው በማለት ወስነናል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በገለፅናቸው ምክንያቶች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በተጠሪ ማሽን ላይ ለደረሰው ጉዳት አመልካች ለተጠሪ ብር 180,000/አንድ መቶ ሰማኒያ ሺህ ብር/ ይክፈል በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው የአካል ጉዳት የሚከፍለውን የካሣ መጠን በማሻሻል አመልካች ለተጠሪ ከዚህ በፊት ከከፈለው ብር 9,000 /ዘጠኝ ሺህ ብር/ በተጨማሪ ብር 31,000/ሠላሳ አንድ ሺህ ብር/ ብቻ ሊከፍል የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በአጠቃላይ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል የሚገባው ብር 211,000/ሁለት መቶ አሥራ አንድ ሺ ብር/ ብቻ ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የሱማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ ብር 211,000/ሁለት መቶ አሥራ አንድ ሺህ ብር/ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ግራቀኙ ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፤

ዘቢ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 58540

ጥር 27 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ኪድስ ሊንክ ኢንተርናሽናል - ጠበቃ ቶማስ ገ/አብ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ**፡- ሲስተር ገነት ወንድሙ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 377/96"ን" መሠረት ያደረገ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ከአመልካች ጋር የመሠረቱት የስራ ቅጥር ውል ከሕግ ውጪ የተቋረጠባቸው መሆኑን ገልፀው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም የስራ ቅጥር ውሉ የተቋረጠው የአመልካች እናት ድርጅት በመክሰሩ ምክንያት መሆኑን በመግለጽ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ብሎ ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ካናዳ የሚገኘው የአመልካች ድርጅት እናት መስሪያ ቤት ስለመክሰሩ የአመልካች ድርጅት በማስረጃዎች አረጋግጠዋል፣ የተጠሪ ምስክሮች ቃል ግን ይህንኑ የአመልካች ማስረጃዎች ያረጋገጡትን ፍሬ ነገር የሚያስተባብል አይደለም የሚል ምክንያት በመያዝ የስራ ውሉ የተቋረጠው በሕጉ አግባብ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ ተጠሪ ሊከፈላቸው የሚገባው የስራ ስንብት ክፍያና የ29 ቀናት የዓመት ፈቃድ ክፍያ ብቻ እንዲከፈል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በማለት በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሮ የስራ ስንብቱ ከሕግ ውጪ የተከናወነ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት ከሰጠው ክፍያ አይነት በተጨማሪ የካሣ እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ተወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም የስራ ስንብቱ ሕገወጥ ነው የተባለው በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ውጪ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ ከስራ መሰናበት የነበረባቸው በቅነሣ መልክ መሆን ይገባው ነበር ተብሎ የስራ ስንብቱ ከሕገ ውጪ ነው በማለት መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ



www.chilot.me

ተደርጓል። በዚህም መሠረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጽሑፍ ባቀረቡት ክርክር በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ የሻረው የአመልካች ድርጅት ጠቅላላ ስራ መዘጋቱ በበቂ ማስረጃ አልተረጋገጠም፣ ስራው እየቀዘቀዘ ነው እንዳይባል ደግሞ በቅነሣ መልክ ስንብቱን አላከናወነም በማለት መሆኑን ነው። ከሁሉም በላይ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው አመልካች ድርጅት ማዕከል ውስጥ በወቅቱ አንድ ህፃን ብቻ መቅረቱ በግራ ቀኙ ማስረጃዎች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። ከሁሉም በላይ የአመልካች ድርጅት እናት መስሪያ ቤት በመክሰር ላይ ያለ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በሚገባ ማረጋገጡን የውሣኔው ግልባጭ ያስረዳል። የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንኑ የስር ፍርድ ቤትን ድምዳሜ ውድቅ ያደረገው በተገቢው መንገድ ሣይረጋገጥ የተያዘ ድምዳሜ ነው በማለት ነው። ይሁን እንጂ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤትን ድምዳሜ ውድቅ ያደረገው በደፈናው በተገቢው ሣይረጋገጥ ነው በሚል ከመሆኑ ውጪ ተገቢ ያልሆነበትን፣ በጉዳዩ ላይ የቀረቡት የአመልካች ማስረጃዎች የሰጡት ቃል ተቀባይነት የማይኖርበትን  ህጋዊ ምክንያት ሣይጠቅስ ነው። የበላይ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሊሽር የሚችለው ሕጋዊና በቂ ምክንያት ሲኖረው ስለመሆኑ ስለ ፍርድ አሰጣጥ የሚደነግጉት ከቁጥር 341 ጀምረው ያሉት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ያሣያሉ። ያለሕጋዊ ምክንያት የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ በበላይ ፍርድ ቤት ሊሻር አይገባም። በመሠረቱ የበላይ ፍርድ ቤት በበታች ፍርድ ቤት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችንም የማይቀበልበትን ምክንያት በግልጽ ጽፎ ውድቅ ማድረግ እንጂ በደፈናው በተገቢው አልተረጋገጡም በማለት ሊያልፈው አይገባም። በመሆኑም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የደረሰበትን ድምዳሜ ያልተቀበለበት አግባብ የዳኝነት አካሄዱን ያልተከተለ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል። በፍሬ ነገር ደረጃ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ሕጋዊ አይደለም ሊባል የሚችልበት ምክንያት የለም ከተባለ ደግሞ የተሰጠውን ውሣኔ ሕጋዊነት መመልከቱ ተገቢ ይሆናል። የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የተቀጠሩበት ስራ መቀዝቀዙን በሚገባ ያረጋገጠ ሲሆን አንድ አሰሪ ስራው በመቀዝቀዙ ምክንያት ሰራተኛውን ሊያሰናብተው የሚችልበት አግባብ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት ተዘርግቷል። በተያዘው ጉዳይም የተጠሪ ስንብት በአዋጁ አንቀጽ 24/4/ መሠረት ሕጋዊ እንጂ ሕገ ወጥ ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም። በመሆኑም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ አመልካች ተጠሪን በቅነሣ ሥርዓት ያሰናበታቸው መሆኑን አላስረዳም በማለት የያዘው ምክንያት የሕግ ድጋፍ የሌለው ነው። በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ነገር ተጠሪ ጋር በተመሣሣይ ሁኔታ ተቀጥረው ስራ በመስራት ላይ የሚገኙ ሰራተኞች ስራውን እየሰሩ ስለመሆኑ የተረጋገጠበት ሁኔታ የለምና። በአጠቃላይ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ የሻረው በሕጉ አግባብ ባለመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሥነ ሥርዓትም ሆነ የመሠረታዊ ሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል።



www.chilot.me

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 87901 ሰኔ 24 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 58407 ታህሣሥ 07 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 57378

ጥር 23 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች:- ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** :- ወ/ሮ አስቴር አርአያ - ቀረቡ

**ተጠሪ** :- ወ/ሮ አምሳለ በላይ - ጠበቃ ሽመልስ ሄይስ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ወ/ሮ አምሳለ በላይ የካቲት 11 ቀን 2001 ዓ.ም. በተሰጠ ውሣኔ በዶ/ር አለኸኝ መኮንንና በወ/ሮ አስቴር አርአያ ላይ ገንዘብ በማስወሰን የፍርድ ባለመብት የሆንኩበት ይፈፀምልኝ ብለው ባስከፈቱት የአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር 92421 የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግንቦት 4 ቀን 2002 ዓ.ም. የፍርድ ባለመብት በሌላ መዝገብ ባለዕዳ ሆነው በመ/ቁ. 63974 በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አፈፃፀሙ እየታየ ስለሆነ በዚህ ችሎት የተሰጠው ፍርድ ተቻችሎ እንዲፈፀም የፍርድ አፈፃፀም ማመልከቻው ከትዕዛዙ ጋር ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለ8ኛ ችሎት ይተላለፍ በሚል የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም በዚሁ ትዕዛዝ ላይ ይግባኙ የቀረበለት የፍዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 56661 ሰኔ 14 ቀን 2002 ዓ.ም. ይግባኝ የተባለበት ትዕዛዝ ጉድለት የለበትም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በሚል ምክንያት የቀረበ ነው፡፡

አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲፈፀም አፈፃፀም የተጠየቀበት የገንዘብ ፍርድ እና በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አፈፃፀም የተጠየቀበት የገንዘብ ፍርድ ተቻችሎ እንዲፈፀም ለከፍተኛው ፍ/ቤት የቀረበውና ወደ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይተላለፍ በሚል የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶች ሰኔ 17 ቀን 2002 ዓ.ም. በተጻፈ ማመልከቻ ገልፀው አቅርበዋል፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ ተብሎ በመታዘዙ ማመልከቻው ለአሁኗ ተጠሪ ተልኮ ቀረበው መልስ እንዲሰጡበት የተደረገ ሲሆን በተጠሪዋ በኩል በጽሑፍ የቀረበው መልስም ለአመልካች እንዲደርሳቸው ተደርጎ በጽሑፍ የመልስ መልስ ሰጥተውበታል፡፡

በዚህ ጉዳይ በአንድ በኩል የአሁኗ ተጠሪ በአሁኗ አመልካች እና በሌላ አንድ ሰው ላይ ገንዘብ በማስወሰን በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አፈፃፀም የጠየቁበት ፍርድ በሌላም በኩል የአሁኗ አመልካች በአሁኗ ተጠሪ ላይ ብቻ ገንዘብ በማስወሰን በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አፈፃፀም የጠየቁበት ፍርድ መቻቻል ሊደረግበት እንዲችል ለከፍተኛው ፍ/ቤት የቀረበው የአፈፃፀም ጥያቄ ወደ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተላልፎ ይታይ በሚል የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት መኖር አለመኖሩ ሲመረመር፡-

በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 397/1/ ላይ እንደተመለከተው በዚህ ጉዳይ ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች በየበኩላቸው ክስ አቅርበው አንዱ በአንዱ ላይ የፍርድ ባለገንዘብ መሆናቸው የተረጋገጠ ሲሆን ሁለቱም እንደፍርዱ እንዲፈፀምላቸው ለፍ/ቤት የአፈፃፀም ማመልከቻና ለማቅረብ የአፈፃፀም መዝገብ አስከፍተዋል፡፡ ልዩነት የታየው የአሁኗ አመልካች የአፈፃፀም ማመልከቻውን ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርበው የአፈፃፀም መዝገብ ማስከፈታቸው እና የአሁኗ ተጠሪ ደግሞ የአፈፃፀም ማመልከቻውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማቅረብ የአፈፃፀም መዝገብ ያስከፈቱ ሆኖ መገኘታቸው ላይ ቢሆንም ፍርዱ በአንድ ፍ/ቤት ዘንድ ሊፈፀም የሚችል ነው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ በመረዳት ፍርዱ መቻቻል ሊደረግበት እንዲችል አፈፃፀሙ በአንድ ፍ/ቤት እንዲታይ በአሁኗ ተጠሪ በኩል የቀረበው የአፈፃፀም ማመልከቻ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቀረበው የአፈፃፀም ማመልከቻ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንዲተላለፍ አድርጓል፡፡ የአሁኗ ተጠሪ የአፈፃፀም ማመልከቻ ያቀረቡበት ፍርድ ገንዘቡን የአሁኗ አመልካችና ሌላው የፍርድ ባለዕዳ በአንድነትና በነጠላ ይክፈሉ ተብሎ የተወሰነ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ስለመቻቻሉም ጥያቄ አፈፃፀሙን በዝርዝር በማየት የሚወሰነው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች አንዱ በሌላው ላይ ያስወሰነው በፍርድ የበሰለ ገንዘብ በመቻቻል መፈፀም እንዲችል የአሁኗ ተጠሪ የአፈፃፀም ማመልከቻ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንዲተላለፍ ማድረጉ የሕግ ስህተት ያለበት አይደለም፡፡

የአሁኗ አመልካች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1838 እና 1839ን በመጥቀስ ማቻቻል እንዲደረግ ባለዕዳው የሚፈልግ መሆኑ መረጋገጥ አለበት በሚል ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተም በፍርድ የበሰለው የገንዘብ ዕዳ መቻቻል አፈፃፀም የሚመራው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 397 መሠረት ስለሆነ ወደ ፍትሐብሄር ሕጉ ድንጋጌዎች የሚወሰድ ጉዳይ አይደለም፡፡ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 397/1/ የሚጠይቃቸው ቅድመ ሁኔታዎች የተሟሉ ሆነው ከተገኙ ማቻቻሉ መፈፀም ይኖርበታል፡፡ በዚህ ጉዳይ መቻቻሉ እንዲፈፀም በሕጉ ላይ የተመለከቱት መሠረታዊ የሆኑት ነገሮች ተሟልተው ስለሚገኙ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ክርክር በሕጉ ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡

ሌላው አመልካች የአሁኗ ተጠሪ የአፈፃፀም ማመልከቻ ባቀረቡበት ፍርድ ገንዘቡን እንድከፍል የተወሰነው በእኔ ላይ ብቻ ሣይሆን በዶ/ር አለኸኝ መኮንንም ላይ ስለሆነ እኔ በተጠሪዋ ላይ ካስፈረድኩት ገንዘብ ጋር መቻቻል ሊደረግበት አይችልም በሚል ያነሱትን የተቃውሞ ክርክርም በሚመለከት በአንድነትና በነጠላ ይክፈሉ ተብሎ የተወሰነ መሆኑን ተጠሪዋ በጽሑፍ በአቀረቡት መልስ ላይ የገለፁት ሲሆን አመልካችም በጽሑፍ በሰጡት የመልስ መልስ ላይ በአንድነትና በነጠላ ይከፈል መባሉን አልካዱም፡፡ በአንድነትና በነጠላ ይክፈሉ ተብሎ የተወሰነ ሆኖ ከተገኘ የፍርድ ባለመብቷ በሕጉ የአንደኛው የፍርድ ባለዕዳ ንብረት ብቻ ተሽጦ ወይም አፈፃፀሙ በአንደኛው የፍርድ ባለዕዳ ላይ ብቻ ቀጥሎ ገንዘቡ እንዲከፈላቸው መጠየቅ ይችላሉ፡፡ መቻቻሉም በተመሣሣይ መንገድ ተፈፃሚ የሚሆን ነው፡፡ የአሁኗ አመልካች በተጠሪዋ ላይ ብቻ አስፈርደው የአፈፃፀም ማመልከቻ ያቀረቡበት ገንዘብ የአሁኗ ተጠሪ አመልካችና ሌላ ሁለተኛ ሰው በአንድነትና በነጠላ

ይክፈሉ ተብሎ ተወስኖ አፈፃፀም ከጠየቁበት ገንዘብ ጋር እንዲቻቻል ከተደረገ በኋላ አመልካች በሕጉ ያላቸው መፍትሄም ሆነ አማራጭ ሁለተኛው የፍርድ ባለዕዳ በድርሻቸው ያለውን ገንዘብ እንዲተኩላቸው መጠየቅ ስለሆነ ተጠሪ በእኔና በሌላ ሁለተኛ ሰው ላይ በፍርድ ያስወሰኑት ገንዘብ እኔ በተጠሪዋ ላይ ብቻ ካስወሰንኩት ገንዘብ ጋር መቻቻል እንዲፈፀም ሊደረግ አይገባም በሚል ያቀረቡት ተቃውሞ ተቀባይነት የለውም፡፡

አመልካች የአሁኗ ተጠሪ የአፈፃፀም ማመልከቻውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲያቀርቡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 386 መሠረት ለእኔም ማመልከቻው ተልኮልኝ ቀርቤ መልስ እንድንሰጥ መደረግ ሲገባው ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንን የመሰማት መብቴን አልፎ መቻቻል እንዲደረግ የተጠሪ የአፈፃፀም ማመልከቻ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይተላለፍ ያለው ያለአግባብ ነው ብለው የገለጹትን በተመለከተም አሁንም ቢሆን ፍርዱ እንዳይፈፀም የሚቃወሙበት የሕግ ምክንያት ስለመኖሩ ያስረዱት ነገር ስለሌለ በፍርድ ተወስኖ ባለቀ ጉዳይ ላይ እንደገና መልስ እንድሰጥ መደረግ ነበረበት የሚለው ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ሁለት ፍርዶች በማቻቻል እንዲፈፀሙ በማድረጉ ሂደት ሊያነሱት የሚገባ ጥያቄ ካለ ማቅረብ የሚገባቸው የአፈፃፀሙን ጉዳይ በማየት ላይ ለሚገኘው ፍ/ቤት ነው፡፡

በአጠቃላይ ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች አንዱ በሌላው ላይ በፍርድ ያስወሰኑትን ገንዘብ የአፈፃፀም ጥያቄዎች በአንድ ፍርድ ቤት ታይተው በማቻቻል እንዲፈፀሙ የአሁኗ ተጠሪ ለከፍተኛው ፍ/ቤት አቅርበውት የነበረው የአፈፃፀም ማመልከቻ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንዲተላለፍ በሚል የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት የሌለ ሆኖ ስለተገኘ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 56661 ሰኔ 14 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 51223

የካቲት 24 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች ፡-** ዳሽን ባንክ ነገረ ፈጅ ትንሳኤ ተፈራ - ቀረቡ

**ተጠሪ ፡-** ወ/ሮ ሀመልማል መኮንን ጠበቃ አቶ ተስፋዬ ታደሠ - ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ በግራ ቀኙ ከተነሣው ክርክር አንፃር በማየት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 የተመለከተውን ሥነ-ሥርዓታዊ ድንጋጌ አፈፃፀምን በሚመለከት በሥር የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠውን ትርጉም አግባብነት ለማየት በሚል የቀረበ ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ የአሁን ተጠሪ በሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 126261 በአሁን አመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ሲሆን ይዘቱም ባጭሩ፡-

ከወ/ሮ ፅዮን መኮንን በዳሽን ባንክ መሣለሚያ ቅርንጫፍ ብር 55,907.02 የተላከልኝን ገንዘብ ባንኩ ለሌላ ግለሰብ ከፍሏል፡፡ ይህም ክፍያ የሥራ ግዴታውን በአግባቡ ካለመወጣቱ የተነሣ የተፈፀመ ስለሆነ ሊከፍለኝ ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካችም በተከሣሽነት ቀርቦ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 244/2/ መሠረት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን በማስቀደም በዚህ ጉዳይ ወ/ሮ ፅዮን መኮንን ከሰውን የድሬዳዋ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ገንዘቡን የመክፈል ግዴታ እንደሌለብን በመግለፅ ወስኖ አሰናብቶናል፡፡ የአሁን አመልካች ጥያቄ ከወ/ሮ ፅዮን መኮንን የመነጨ ስለሆነ አስቀድሞ ዳኝነት ባገኘው ጉዳይ ላይ ዳግመኛ ክስ ማቅረብ እንደማይቻል ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 ስለተደነገገ ክሱ ውድቅ ነው የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

ፍ/ቤቱም ይህንኑ ክርክር በማስረጃነት ከቀረበው ከመ/ቁጥር 23357 ፍርድ ይዘት ጋር አገናዝቦ ከመረመረ በኂላ እንደ አመልካች ክርክር አስቀድሞ ውሣኔ ባገኘ ጉዳይ ዳግመኛ የቀረበ ክስ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

በአኳያው ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ጉዳዩን ተመልክቶ በሁለቱም መዝገቦች ያሉት ተሟጋቾች የተለያዩ ናቸው፣ የመብታቸውም ጥያቄ እራሱን የቻለ ነው እንዲሁም ጭብጡም የተለያየ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 የተመለከተው ድንጋጌ ለዚሁ ጉዳይ ተፈፃሚነት የለውም



www.chilot.me

የሚል ትርጉም ከሰጠ በኋላ በዋናው ጉዳይ ዘልቆ የአሁን አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከሕጋዊ ወለድ ጋር ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡

ጉዳዩ በሁለተኛ የይግባኝ ደረጃ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አከራካሪ የሆነውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያው ክርክርም ሆነ በዋናው ጉዳይ የተሰጠውን ውሣኔ መርምሮ በተመሳሳይ አተረጓጉም ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበውም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 ጋር በተያያዘ በግራ ቀኙ ለተነሣው ክርክር ይግባኝ ሰሚዎች ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍ/ቤቶች የሰጡት ትርጉም አግባብነት በሚለው ነጥብ ላይ ግራ ቀኙን በሰበር አድምጦ አስፈላጊውን ትርጉም ለመስጠት በሚል ነው፡፡

በዚህ ነጥብ ላይ ግራ ቀኙ በፍሬ ነገርም ሆነ ስለ ሕጉ ያቀረቡት ክርክር በሥር ፍ/ቤቶች ካቀረቡት በይዘቱ የተለየ ባለመሆኑ በዚህ ፍርድ ላይ በድጋሚ ማስፈሩ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ዓይነት ከላይ ባጭሩ የመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነው የወ/ሮ ሀመልማል ክስ በኮ/መ/ቁ. 126261 በሆነው መዝገብ ከመቅረቡ በፊት ገንዘቡን በሃዋላ ለወ/ሮ ሀመልማል መኮንን ላኩ የተባሉት ወ/ሮ ፅዮን መኮንን ይህንኑ ገንዘብ ብር 55,907.02 በሃዋላ ለወ/ሮ ሀመልማል እንዲከፍልልኝ ግዴታ ገብቶ ገንዘቡን ከተቀበለ በኋላ ለተላከለት ሰው አልከፈለም ስለዚህ ገንዘቡን ይመልስልኝ በማለት በአሁን አመልካች ላይ ክስ አቅርበው ገንዘቡን አስተላላፊ ነው የተባለው ባንክ ገንዘቡን በማስተላለፍና ለተላከለት ሰው ክፍያን በመፈፀም ረገድ ካለበት የሥራ ግዴታ አንፃር ያደረገው ተግባር ሁሉ ታይቶ ተከሣሽ ግዴታውን በመወጣት በኩል ተግባሩን በአግባቡ ፈፅሟል፡፡ ገንዘቡን የመመለስ ግዴታ የለበትም ተብሎ በመ/ቁ. 23357 ተወስኗል፡፡

ይህ ውሣኔ ከተሰጠ ከሦስት ወር ተኩል በኋላ ደግሞ እንደገና ገንዘቡ ተላከላቸው የተባሉት የአሁን ተጠሪ ከወ/ሮ ፅዮን የተላከልኝን ብር 55,907.02 ባንኩ ለእኔ መክፈል ሲገባው ለሌላ ግለሰብ ከፍሏል ይክፈለኝ በማለት ክስ አቅርበውበታል፡፡

በዚህም ሁለተኛ ክስ ላይ ሊነሳ የሚችለው ጭብጥ ገንዘብ አስተላላፊው በገባው ግዴታ መሠረት ገንዘቡን ለተላከለት ሰው ለመክፈል የሚጠበቅበትን ተግባር አከናውኗል ወይስ አላከናወነም? የሚለው በመሆኑና የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ጠቅላይ ፍ/ቤት በተሳሳተ መንገድ ወደ ፍሬ ነገሩ ጉዳይ ዘልቀው በመገባታቸውም የተነሣ በግራ ቀኙ መካከል የተነሣው አከራካሪ ነጥብ ይህው ስለመሆኑ የውሣኔው ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ስለሆነም በመ/ቁ. 23357 ሆነ በመ/ቁ. 126261 የተነሣው የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ጭብጥ ተመሳሳይ ነው፡፡ ተከራካሪ ወገኖችም የተለያዩ ሰዎች ይሁን እንጂ የወ/ሮ ሀመልማል ገንዘብ የመጠየቅ መብት የሚመነጨው ከገንዘብ ላኪዋ በመሆኑና ገንዘብ ላኪዋ ባቀረቡት ክስ ረቺ ሆኖ በተገኙ ጊዜ እንዲሁም ገንዘብ ተቀባይ የፍርዱ ተጠቃሚ የሚሆኑ ወገን ናቸው፡፡ ተመሳሳይ ዳኝነት ከአንድ ተከሣሽ የሚጠይቁ ወገኖች በመፈራረቅ የተለያዩ ክስ በማቅረብ በተከሣሹ ላይ አላስፈላጊ እንግልት እንዳያደርሱ በማሰብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ በአንቀጽ 5/1/ ላይ ከተከራካሪዎቹ መብት ያገኙ ሦስተኛ ወገኖች በዚያው ነገር ሁለተኛ ክስ ለማቅረብ እንደማይችሉ ተደንግጓል፡፡ የእነዚህ ለመጀመሪያው ጉዳይ ተከራካሪ ከሆኑት ወገኖች መብት ያገኙ ሦስተኛ ወገኖች እጣ ፈንታ በመጀመሪያው የክስ ውጤት ላይ የተወሰነ ውሣኔውም ኀጂ ከሆነ

ስለአስከተለው ኃላፊነት በቅድሚያ በተከራከረው ወገን ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር እንጂ ዳግመኛ ክስ በዚያው በአንድ ተከሣሽ ላይ እንዲቀርብ የተፈቀደበት ሥርዓት አይደለም፡፡

በዚህም የሕግ ይዘትና የሕጉ መሠረተ ሀሳብ መነሻ በሁለቱም ጉዳዮች በከሣሽነት የተሰየሙት ወገኖች ተመሳሳይ ወገኖች እንደሆኑ የሚቆጠሩ ናቸው፡፡

ከሁሉም በላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 የተቀመጠው ድንጋጌ ክርክሮችን ሥርዓት ባለው መንገድ እንዲመሩ በማድረግ በተቻለ ፍጥነት በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጭ ታይተው እንዲቋጩ በማድረግ ረገድ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ የያዘውን ዓላማ ተከትሎ የተዘረጋ ሥርዓት እንደመሆኑ መጠን አንድ አስቀድሞ የተሰጠ ፍርድ ወደ ፊት ለሚነሱት ክርክሮች ያለውን ውጤት ለይቶ ደንግጓል፡፡ ይህንንም ድንጋጌ አስመልክቶ የትርጉም ጥያቄ ከተነሣ ልንሰጠው የሚገባው ትርጉም ከዚሁ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ዓላማ የራቀ ሊሆን አይገባም፡፡ ከዚህ አንፃር ለሁለቱም ጉዳዮች መነሻ የሆነው አንድ የተላከ ገንዘብ ሆኖ እያለ በሁለቱም ጉዳዮች ለተነሣው ክርክር ዕልባት ለመስጠት በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ ባንኩ በአግባቡ የሥራ ግዴታውን ተወጥቷል ወይስ አልተወጣም? የሚለው መሆኑ እየታወቀ እና ላኪ እና ተቀባይ የሚጠይቁት ዳኝነት በይዘቱ ተመሳሳይ ሆኖ እያለ በጊዜ ቅደም ተከተል በመፈራረቅ አንድን ተከሣሽ ሁለት ጊዜ በአንድ ጉዳይ በተለያዩ ፍ/ቤት በተለያዩ ጊዜ ለሙግት በሚደረግ አኳኋን የክርክሩ አንኳር ነጥብ ሲያያዝ በጭፍጫፊ የቃላት አጠቃቀም በመመራት ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 እንደተመለከተው አስቀድሞ በፍርድ እንዳለቀ ሊቆጠር የሚችል አይደለም በሚል የተሰጠው ትርጓሜ የድንጋጌውን ይዘትም ሆነ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ዋነኛ ዓላማን መሠረተ ያደረገ ሆኖ ስላላገኘነው ትርጉሙ መሠረታዊ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና በጠቅላይ ፍ/ቤት እንደቅደም ተከተሉ በኮ/መ/ቁ. 74189 ጥር 25 ቀን 2001 ዓ.ም. እና በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 45987 ህዳር 09 ቀን 2002 ዓ.ም. የተሰጠው ፍርድ እና ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 126261 በ10/03/2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. በአሁን አመልካች ላይ የቀረበውና ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነው ክስ አስቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ ዳግመኛ የቀረበ ሆኖ ስላገኘነው ክሱ ውድቅ ነው፡፡ ውድቅ ሊሆን በሚገባው ክስ ምክንያት ብር 55,907.02 /ሃምሣ አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባት ብር ከዜሮ ሁለት ሣንቲም/ ይክፈል በሚለው ፍርድ ሊገደድ አይችልም፡፡ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡ በዚህ ሰበር ክርክር ምክንያት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 53421

ቀን የካቲት 22 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች ፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ወርቅነሽ ዋሴ -ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ባንተይርጋ ወርቁ - ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው ፍርድን ለማስፈፀም ሲባል በተሸጠ ቤት ላይ የአሁን አመልካች ቤቱ የእራሴ ንብረት ነው፡፡ የፍርድ ባለዕዳ ንብረት እንደሆነ ተቆጥሮ የተሸጠው ያለአግባብ ስለሆነ የሐራጅ ሽያጩ ፈርሶ የቤቱ ባለመብትነቴ ይረጋገጥልኝ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 447 (4) አንጻር ተቀባይነት ያለው መሆኑንና አለመሆኑን ለይቶ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት ሲባል ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ የአሁን ተጠሪ አቶ ባንተይርጋ ወርቁ እና ባለቤታቸው የነበሩት በዚህ ጉዳይ በፍርድ ባለዕዳነት የተሰየሙት ወ/ሮ አየሁብርሃን ወዳጆ በመካከላቸው የነበረውን ጋብቻ ካፈረሱ በኋላ በፍቺ ውጤቱ ይህ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን በወ/ሮ አየሁብርሃን ወዳጆ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው በቦራዩ ከተማ ቀበሌ ለኩ ኮታ በዕድገት የመኖሪያ ቤት ሥራ ማህበር ተደራጅተው ያፈሩት የመኖሪያ ቤት የባልና ሚስት የጋራ ሀብት መሆኑን ገልፀው እንዲካፈሉ ተስማምተው ስምምነታቸው በፍ/ቤት በመ/ቁ 12592 ሚያዚያ 11 ቀን 1986 ዓ.ም. በተሰጠው ውሳኔ መሠረት ፀድቋል፡፡

በዚህ ውሳኔ መሠረት ለማስፈፀም የአሁን ተጠሪ የፍርድ ባለመብት፤ ሚስት የነበሩት ወ/ሮ አየሁብርሃን ወዳጆ ባለዕዳ በመሆን የተሰየሙበት የአፈጻጸም መዝገብ በአ/ፈ/መ/ቁ በኮ/መ/ቁ 17831 ተከፍቶ አፈጻጸሙ ቀጥሎ ሐምሌ 20 ቀን 1997 ዓ.ም. የፍርድ ባለዕዳ ባሉበት ቤቱ ክፍት ሆኖ በመቆየቱ የፍርድ አፈጻጸም መምሪያ ባለሙያ፣ ከቀበሌና ከፖሊስ ጽ/ቤት በተገኙ አባላት አማካኝነት ቤቱ ተገመተ፡፡ ነገር ግን ግምቱ ቦታውን አላካተተም ተብሎ የመሬት አስተዳዳር የመሬቱን ዋጋ እንዲለካ በድጋሚ ሲታዘዝ የፍርድ ባለዕዳም ቤት የላትም የሚል መልስ መስጠቱን፤ ይህ በእንዲህ እንዳለ የአሁን አመልካች በሽያጭ አስተላለፈልኝ የሚሏቸው አቶ ቦጋለ ደገፋ በአፈጻጸም ይሸጥ በተባለው ቤት ላይ መብት አለኝ በማለት በዚሁ የአፈጻጸም መዝገብ ጣልቃ ገብተው በመከራከራቸው በኮ/መ/ቁ 17831 ሐምሌ 04 ቀን 2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት አቶ ቦጋለ የማህበር ማረጋገጫ ካርታ አቀረቡ እንጂ ቤቱ የግላቸው ስለመሆኑ የሚገልፅ ማስረጃ አላቀረበም፡፡

መብት የላቸውም በማለት አሰናብቷቸዋል። አቶ ቦጋለ በአፈጻጸም ጉዳይ የተያዘው ንብረት የእኔ ነው በማለት አቤቱታ ሲያቀርቡ የፍርድ ባለዕዳ የነበሩት እና ቤቱ በስማቸው ተመዝግቦ ይገኝ የነበሩት ወ/ሮ አየሁብርሃን ወዳጆ እኔና ባለቤቴ የነበረው የአሁን ተጠሪ የጋራ ቤት የሌለን ስለሆነ ቤቱ ለአቶ ቦጋለ ደገፋ ቢለቀቅ አልቃወምም የሚል መልስ ሰጥተው እንደነበሩ የክርክሩ አመጣጥ ያስረዳል።

የአሁን አመልካችም ይህ ክርክር የተነሳበትን ቤት ከፍርድ ባለመብትም ሆነ ከፍርድ ባለእዳ ጋር ግንኙነት ከሌላቸው ከአቶ ቦጋለ ነሐሴ 07 ቀን 2001 ዓ.ም. ገዝቻለው ስመ ሀብትነቱም በካርታ ቁጥር Bur/74/93/10 በ11/12/2001 ወደ እኔ ተዛውሯል። የፍርድ ባለዕዳ ሳልሆን ንብረቴ ላይ የአፈጻጸም ትዕዛዝ ተለጠፈብኝ በማለት በአፈጻጸም መዘገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት ሰኔ 02 ቀን 2002 ዓ.ም. አቤቱታ ሲያቀርቡ ቤቱን ሸጠልኝ የሚሏቸው ግለሰብ አቶ ቦጋለ ደገፋ በዚህ መዝገብ ተመሳሳይ ጥያቄ አቅርበው ውድቅ የተደረገባቸው መሆኑን መነሻ አድርገው አሰናብቷቸዋል።

በዚህ ትዕዛዝ ላይ የይግባኝ  አቤቱታ ሲያቀርቡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 87938 በ12/4/2002 በዋለው ችሎት ቤቱ በሐራጅ መሸጡን ስለተረዳሁ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት የቀረበውን አቤቱታ መርመሮ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘሁትም፤ለሥር ፍ/ቤት ያመልክቱ  የሚል ዳኝነት ሰጥቶበታል በሚል ለዚህ ሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውን አቤቱታ የሐራጅ ሽያጩ ፈርሶ ቤቱን ልረከብ በማለት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 445 መሠረት አፈጻጸሙን በያዘው ፍ/ቤት ጥያቄ ማቅረባቸውን የጉዳዩ አመጣጥ ያስረዳል።

አፈጻጸሙን የያዘው ፍ/ቤትም በኮ/መ/ቁ 17831 በ27/4/2002 በዋለው ችሎት ከላይ እንደተመለከተው የጉዳዩን አጀማመር፤ በመካከል አፈጻጸሙን ያሰናከሉትን ሙግቶች ሁሉ ከጠቀሰ በኋላ ንብረቱ የፍርድ ባለዕዳዋ የነበረ ስለመሆኑ በንብረት አገማመት ጊዜ በባለቤትነት የነበራቸውን ተሳትፎ የአሁን አመልካች በዚሁ ጉዳይ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት ዳኝነት ጠይቀው መሰናበታቸውን ሁሉ መሠረት በማድረግ አመልካች ያቀረቡት ተቃውሞ ተቀባይነት የለውም። በማለት ወስኗል።

ይህም ውሳኔ የይግባኝ አቤቱታ ቀርቦበት ተቀባይነት ባለማግኘቱ ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል። መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል የሚልበት ዋና የመከራከሪያ ነጥብ የንብረቱ ባለቤት እኔ ስለመሆኔ የቤቱ ስም ሀብትነት በእኔ ተመዝግቦ ይገኛል። የፍርድ ባለዕዳና የፍርድ ባለገንዘብ የተሸጠው ቤት ያልነበራቸው መሆኑን የቡራዩ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት አረጋግጠውልኛል የሚሉ ናቸው።

የአሁን ተጠሪም በሥር ፍ/ቤቶች ከነበረው ክርክር አንስቶ የተሰማቸውን ነጥቦች በማድረግ ንብረት የባልና የሚስት የጋራ ሀብት ስለሆነ ለክፍፍል በአፈጻጸም እንዲሸጥ መደረጉ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል።

የጉዳዩ አጀማመር እና የክርክሩ ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን፤እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል። እንደመረመርነውም በቅድሚያ ሊታይ የሚገባው ነጥብ ሆኖ ያገኘነው በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት እንዲሸጥ በተከበረ ንብረት ላይ የቀዳሚ መብት አለኝ በሚል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት በአፈጻጸም ጉዳዩ ጣልቃ ገብቶ ተከራክሮ ክርክሩ ውድቅ ከተደረገ

በኋላ እንደገና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 444-447 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት በዚያው የአፈጻጸም መዝገብ ገብቶ ለመመርመር የሚያስችለው መብት አለው ወይስ የለውም? የሚለው ነው፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 ሆኖ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ባለው የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 447(4) የተመለከቱት ድንጋጌዎች ግብ ተመሳሳይ ሆኖ የሚለያዩበት ነጥብ ቢኖር እንዲሸጥ በተከበረው ንብረት ልዩ መብት አለኝ በሚል የቀረበው አቤቱታ መቼ ቀረበ በሚለው ላይ ነው፡፡ በቁጥር 418 አቤቱታ የሚቀርበው ከመሸጡ በፊት ሲሆን በቁጥር 447-(4)የሚቀርበው ደግሞ ከተሸጠ በኋላ መሆኑ ብቻ ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘት ግን ተመሳሳይ ነው ይኸውም በሐራጅ ለማሸጥ የተከበረው ንብረት ወይም ደግሞ ተከብሮ የተሸጠው ንብረት የፍርድ ባለዕዳ ሳይሆን የእኔ ነው የሚል በመሆኑ ነው፡፡ ይህም ከሆነ በተመሳሳይ ክርክር ነጥብ በአንድ ጉዳይ እንደ አመልካች ባለ አቀራረብ ፍ/ቤቱ ሁለት ጊዜ ሊያስተናግድ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ ይህ ዓይነት አቀራረብ ክርክርን ሥርዓት ባለው መንገድ በመምራት ማስተናገድ ይገባል ከሚለው የሙግት አመራር አላማ ጋርም የሚጣረስ ነው በዚህም ምክንያት አፈጻጸሙን የያዘው ፍ/ቤት የአሁን አመልካች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 445-446ን በመጥቀስ ዳኝነት የጠየቀበት ጉዳይ ቀደም ሲል በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት ጥያቄ ቀርቦበት ዳኝነቱ ያረፈበት ጉዳይ ስለሆነ  በድጋሚ ሊታይ የሚችልበት አግባብ የለም በሚል የሰጠውን ውሳኔ መሠረት ማድረጉ በአግባቡ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ንብረቱ ከተሸጠ በኋላም ቢሆን በዚያው የአፈጻጸም መዝገብ ለሁለተኛ ጊዜ ያቀረቡት ክርክር ይታይ እንኳ ቢባል ይህ ክርክር ያስነሰውን ንብረት አመልካች ከአቶ ቦጋለ ደገፋ ከመግዛታቸው በፊት በፍርድ አፈጻጸም ተይዞ ሻጭ የተባሉት በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት ሊያዝብኝ አይገባም በማለት ተከራክረው በፍርድ ከተረቱ በኋላ ነሐሴ 07 ቀን 2002 ዓ.ም. ገዛሁ የሚል በመሆኑ ይህ ከሆነ በኋላ የተላለፈው የግዥ ተግባር አስቀድሞ የተጀመረውን የአፈጻጸም ጉዳይ ሊያቋርጠው የሚችል አይደለም፡፡ በተለይም ሻጭ የተባለው አቶ ቦጋለ በአፈጻጸም ጉዳይ ጣልቃ ገብተው በተከራከረ ጊዜ የፍርድ ባለዕዳ ንብረቱ ይለቀቅለት የእኔና የፍርድ ባለመብት የጋራ የሆነ ቤት አይደለም የሚለውን ገልፀው መከራከራቸውን እና አመልካችም ይህንኑ ቤት በግዥ አገኝሁ የሚሉት ቤቱ በአፈጻጸም ምክንያት በፍ/ቤት ከተያዘ በኋላ እንደመሆኑ መጠን ጥያቄያቸው ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 354 አንጻር ሲታይ የህግ መሠረት ያለው አይደለም፡፡

ስለሆነም በዚህ ሁሉ ምክንያት የአሁን አመልካች እንደአባባላቸው ቤቱን በሽያጭ አግኝተው የስመ ሀብቱም ዝውውር ወደ እርሳቸው ተዛውሮ ከሆነ ይህ ሁሉ ሥርዓት የተፈፀመው አስቀድሞ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት መሆኑ ታውቆ ፍርድ ያረፈበት፣በአፈጻጸም ተመርቶ በሐራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ የተለላፈበት፤ በሐራጅ እንዲሸጥ  በሂደት ላይ እያለ የአሁን አመልካች ሸጡልኝ የሚሏቸው ሻጭ በአፈጻጸም ጉዳይ ጣልቃ ገብተው ከተረቱ በኋላ የተደረገ የግዥ ተግባር በመሆኑ በእጅ የተያዘውን የሐራጅ ሽያጭ ለማስቆም የሚያስችል መብት የሌላቸው በመሆኑ፤ እንዲሁም የአመልካች የአቤቱታ አቀራረብም ሥርዓቱን የተከተለ ሆኖ ባለመገኘቱ የሥር ፍ/ቤቶች በአሁን አመልካች አቤቱታ መነሻ የሰጠው ዳኝነት በአግባቡ የተሰጠ እንጂ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡



www.chilot.me

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ በመ/ቁ 88606 ጥር 12 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠውን የመጨረሻ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1)መሠረት አፅንተናል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም መዝገቦቹ ይመለሱ
3. የካቲት 30 ቀን 2002 ዓ.ም. የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 55973

የካቲት 21 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- ወ/ሮ አፀደ ኤዶ ጠበቃ አቶ ተስፋዬ ታደሠ - ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- አቶ ትኩ ዋቅሹም ጠበቃ አቶ ይመኑ ገብረፃድቅ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ከ1966 ዓ.ም. እስከ 1987 ዓ.ም. እንደ ባልና ሚስት ስንኖር ያፈራናቸው የጋራ ሀብት አለ፡፡ ስለሆነም የጋራ ሀብቴን እንዲያካፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት አሉ የሚሉትን ንብረት ከተራ ቁጥር 1 እስከ ተራ ቁጥር 6 ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ ጥቅምት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. በተጻፈ መልስ ንብረቶቹን በግሌ ያፈራኋቸው ናቸው፡፡ ከሣሽ /አመልካች/ የጋራ ንብረት ስለሆነ ያካፍለኝ በማለት ያቀረበችው ክስ ተገቢ አይደለም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ በኋላ በሥር ተከሣሽ የሆኑት ተጠሪ ቀደም ሲል በፍ/ቤቱ ያቀረቡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ ያልተካተተበትና ጉዶሎ ስለሆነ መልሴን እንዳሻሽል ይፈቀድልኝ በማለት ህዳር 2 ቀን 2001 ዓ.ም. በተጻፈ ማመልከቻ አመልክተዋል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ተከሣሽ /ተጠሪ/ መልሳቸውን አሻሽለው እንዲያቀርቡ ፈቅዶላቸዋል፡፡ ተጠሪ /ተከሣሽ/ ታህሣስ 28 ቀን 2001 ዓ.ም. በተጻፈ የተሻሻለ መልስ የከሣሽ /አመልካች/ የተከሣሽ /ተጠሪ/ ግንኙነት 1987 ዓ.ም. ተቋርጧል፡፡ ስለሆነም የባልና የሚስት የጋራ ንብረት ክፍያ ጥያቄ በአሥር ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ቀሪ የሚሆን ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ስለሆነም የከሣሽ /አመልካች/ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ይሆናል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ አሻሽለው ባቀረቡት መልስ ላይ ያቀረቡትን የይርጋ ጊዜ ገደብ መቃወሚያ በመቀበል የከሣሽ /አመልካች/ የጋራ ንብረት ክፍያ ጥያቄ በአሥር ዓመት ይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡



www.chilot.me

አመልካች ግንቦት 4 ቀን 2002 ዓ.ም. በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የጋራ ንብረት እንዲያካፍለኝ ላቀረብኩት ክስ ተጠሪ በጽሑፍ ሙሉ መልስ ከሰጡና ግራ ቀኛችን የቃል ክርክርና ምስክሮች ተሰምተው ጉዳዩ ለውሣኔ ቀጠሮ ከተሰጠው በኋላ ተጠሪ መልሱን ለማሻሻል አቤቱታ አቀረቡ፡፡ የሥር ፍ/ቤት ከፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 91 መሠታዊ ድንጋጌ ከሚፈቅደው ውጭ ተጠሪ መልሱን እንዲያሻሽል የፈቀደ ሲሆን በተሻሻለው መልስ አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ ሆኖ መቅረብ የነበረበትን የይርጋ ክርክር አካትቶ አቀረቡ፡፡ የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኛችን ክርክር ከተጠናቀቀና ምስክሮች ከተሰሙ በኋላ ተጠሪ ያቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ ተቀብሎ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የሰጠው ብይን የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244/1/ እና የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 91/1/ የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ መልሴን ለማሻሻል ጥያቄ ያቀረብኩት የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ አካትቶ ለማቅረብ እንደሆነ ለሥር ፍ/ቤት ገልጨአለሁ፡፡ የሥር ፍ/ቤትም በዚሁ ጥያቄ አምኖበት መልሴን እንዳሻሽል ፈቅዶልኛል፡፡ የሥር ፍ/ቤት የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ብይን የሰጠው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 17937 የሰጠውን የሕግ ትርጉም በመከተል ነው፡፡ ስለሆነም የበታች ፍ/ቤቶች የፈፀሙት የሕግ ስህተት የሌለ በመሆኑ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ሆኖ እንድሰናበት በማለት ታህሣስ 11 ቀን 2003 ዓ.ም. የተጻፈ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ በማካተት መልሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ መፍቀዱና በተሻሻለው መልስ ያቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ መሠረት አድርጎ ጉዳዩ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተከሣሽ የቀረበበትን ክስ ለመቃወም የሚችልበት የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ ለክሱ ከሚሰጠው ዝርዝር መልስ በፊት ወይም ከመከላከያ መልሱ ጋር ማቅረብ እንዳለበትና ፍ/ቤቱም በመጀመሪያ የክሱ መቃወሚያ ላይ ከሣሽ የሚሰጠውን መልስ በመቀበል ብይን መስጠት እንደሚገባው በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 245 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ አንድ ጉዳይ በይርጋ የጊዜ ገደብ ይታገዳል የሚለው መከራከሪያ ተከሣሽ በመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያነት መቅረብ ያለበት መሆኑ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 ንዑስ አንቀጽ 2/ረ/ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ተከሣሽ በመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያነት ሊያቀርበው ይገባው የነበረውን የይርጋ መቃወሚያ ሣያካትት የመከላከያ መልሱን ካቀረበ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1856 ንዑስ አንቀጽ 1 በሚደነግገው መሠረት የይርጋ መከራከሪያውን እንደተወው የሚቆጠር መሆኑን የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 ንዑስ አንቀጽ 2/ረ/ እና የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 245 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1856 ንዑስ አንቀጽ 1 ያጣመረ ይዘት፣ መንፈስና ዓላማን በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

የመጀመሪያ ክስ የሚሰማው ፍ/ቤት ተከሣሽ የመከላከያ መልሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ የሚፈቅደው ተከሣሽ መልሱን አሻሽሎ ማቅረቡ ጉዳዩን ለመወሰን አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው (Necessary for the Purpose of the Real Question in Dispute) መሆኑ በፍታብሔር ሥነ-

ሥርዓት ሕግ ቁጥር 91 ንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 91 ንዑስ አንቀጽ 1 ተከሣሽ በፍትብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 ድንጋጌዎች መሠረት በመጀመሪያ የክስ መቃወሚያነት ያላቀረበውን በተለይም በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 ንዑስ አንቀጽ 2/ረ/ መሠረት ማቅረብ የሚባውንና የተወውን የይርጋ ጊዜ ገደብ መከራከሪያ አካትቶ እንዲያቀርብ የሚፈቅድ ድንጋጌ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ድንጋጌው ክርክሩ በሚሰማበት ጊዜ የክሱ ወይም የመከላከያ መልሱ መሻሻል በክርክር የተያዘውን ጉዳይ ለመወሰን አስፈላጊ ሆኖ ባልተገኘበት ሁኔታ ፍ/ቤት ክስ ወይም መልስ እንዲሻሻል መፍቀድ የሌለበት መሆኑን የሚያስቀምጥ ነው፡፡ ስለሆነም የበታች ፍ/ቤት አመልካችና ተጠሪ የጽሑፍና የቃል ክርክር ካደረጉና ግራ ቀኙ ምስክሮቻቸውን አቅርበው ካሰሙ በኋላ ተጠሪ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 ንዑስ አንቀጽ 2/ረ/ መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያነት ሊያቀርብ ይገባው የነበረውን የይርጋ መቃወሚያ አካትቶ ለማቅረብ የመከላከያ መልሱን ለማሻሻል የቀረበውን ጥያቄ ተቀብሎ ተጠሪ የመከላከያ መልሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ የሰጠው ትዕዛዝ የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 91 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት፣ መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ አሻሽሎ ባቀረበው የመከላከያ መልስ ውስጥ በማካተት ያቀረበውን የይርጋ መከራከሪያና የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በመቀበል የሰጠው ትዕዛዝ የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 ንዑስ አንቀጽ 2/ረ/ እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1856 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244/3/ ንዑስ አንቀጽ 2 የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ከላይ የዘረዘርነው የሕግ ስህተት ያለበትን ውሣኔ በይግባኝ አይቶ ማረም ሲገባው የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ የከፍተኛው ፍ/ቤት ማጽናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካች ክስ ቀሪ እንደማይሆን በመገንዘብ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 341 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 56795

የካቲት 21 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ሙባረክ ከድር - ጠበቃ አቶ ወንድም ጥላሁን ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1ኛ. ሚ/ር ሙዋንጋ ሲርል - አልቀረቡም

2ኛ. ወ/ሮ አሰለፈች ሰይድ በሌሉበት የሚታይ

3ኛ. ወ/ሪት አስቴር ጉግሳ " "

4ኛ. አቶ አወል ሽበሺ " "

5ኛ. አቶ መሐመድ ሺበሺ ወኪል አቶ ሙሣ መሐመድ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 158 መሠረት በንብረት ላይ የተሰጠ የዕግድ ትዕዛዝ እንዲነሳ አቤቱታ ያቀረበ ወገን በጉዳዩ ላይ ተከራክሮ ዳኝነት እንዳገኝ የሚቆጠር ወገን ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ዳኝነት የመጠየቅ መብት የለውም በሚል በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ትርጉም ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ተመልክቶ አግባብነቱን ለማየት በሚል የቀረበ ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ህዳር 25 ቀን 1999 ዓ.ም. በተጻፈ የክስ አቤቱታ

ከሚች ወ/ሮ አረጋሽ ሺበሺ ጋር ከ1968 ዓ.ም. ጀምሮ በግሪክ አገር ጋብቻ ፈጽመን እየኖርን እያለ ሚች ኢትዮጵያ መጥታ ሞታለች የእኔም ባልነት በፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡ የጋራ ሀብት 1ኛ በየካ ክ/ከተማ ቀበሌ 13/14 የሚኘውን ቁጥሩ አዲስ/የፋይል ቁጥር ሊዝ 06 የሆነ ቤት፣ 2ኛ በቦሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 15 ቀበሌ 15 የቤት ቁጥር አዲስ የሆነ ጅምር ቤት፣ 3ኛ በሚች ስም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራዳ ቅርንጫፍ የሚገኝ መጠኑ ያልታወቀ ገንዘብ ስለአለ ግማሽ ድርሻ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት የጠየቀበት ነው፡፡

በዚህ የክስ ማመልከቻ በተጠሪነት የተሰየመ ወገን ስላልነበር ክሱ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሟች ወራሾች ካሉ ቀርበው ክርክር ያደርጉ ዘንድ ጥሪ ሲያደርግ የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ህዳር 20 ቀን 2000 ዓ.ም. በተጻፈ መልስ ከሣሽ የሟች አሠሪ እንጂ ባል አይደለም እርሱም ከሟች ቀድሞ የሞተ ስለሆነ የጥብቅና ውክልናው ዋጋ ያለው አይደለም ተጣርቶ ውድቅ ይደረግልን፤ ሟች ንብረቷን በሙሉ በኑዛዜ አስተላልፋለች፡፡ ክስ የቀረበበት ንብረት የሟች የግል ንብረቷ መሆኑንም አረጋግጣለች፡፡ ስለሆነም የጋራ ሀብት መሆኑ ሳይረጋገጥ የቀረበው ክስ አግባብነት የለውም በማለት ሲከራከሩ፤ የአሁን 4ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው እኛም የሟች ወራሾች ስለሆን የንብረቱ ተካፋይ ልንሆን ይገባል የሚል መልስ ጥቅምት 20 ቀን 2000 ዓ.ም. በተጻፈ ሰጥተዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ ደረጃ ላይ እያለ የአሁን አመልካች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 158 እና 205 ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ሐምሌ 20 ቀን 2001 ዓ.ም. በተጻፈ አቤቱታ ግማሽ ድርሻ ከተጠየቀበት ንብረቶች መካከል በየካ ክ/ከተማ ቀበሌ 13 ክልል በካርታ ቁጥር ሊዝ/06/8328/02 8388 ተመዝግቦ የሚታወቀው ቤት የሟች የወ/ሮ አረጋሽ ሺበሺ የግል ንብረት የነበረ ሲሆን ሟች ይህንኑ ቤታቸውን ለ2ኛ ተከሣሽ ለአሁን 3ኛ ተጠሪ በግልፅ ኑዛዜ አስተላልፋልኝ የአሁን ተጠሪም የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸው በደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ተረጋግጦ ከተወሰነ በኋላ የቤቱ የይዞታ ማረጋገጫ ወረቀት በስማቸው መስከረም 09 ቀን 1999 ዓ.ም. ከተዛወረ በኋላ ለአሁን አመልካች በሽያጭ አስተላልፈውል፡፡ የቤቱ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታም ሆነ ንብረቱ በእጄ ይገኛል፡፡ ስለሆነም የአሁን 1ኛ ተጠሪ መብት በሌለው ንብረት ላይ የዕግድ ትዕዛዝ ማሰጠቱን ስለተረዳሁ በዚሁ ንብረት ላይ የተሰጠውን የዕግድ ትዕዛዝ የተከበረው ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 158 መሠረት እንዲነሳ ያድርግልኝ የሚል ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም በኮ/መ/ቁ. 50497 አቤቱታ በቀረበበት ዕለት ሐምሌ 20 ቀን 2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ዕግድ የሰጠበትን ንብረት ስለመግዛታቸው በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት የተረጋገጠ ውል ከመቅረቡ በቀር 3ኛ ወገኖችን ለመመለስ እንዲቻል ስለመመዝገቡ አላስረዱም፡፡ ስለሆነም የዕግድ ይነሳልኝ አቤቱታ ለከሣሽ ደርሶ መልስ ይስጡበት በማለት ማዘዝ ሳያስፈልግ አቤቱታው ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል የሚል ትዕዛዝ ሰጥቶበታል፡፡

ከዚህም በኋላ ክርክሩ በከሣሽና በተከሣሾች መካከል ቀጥሎ ከተጠናቀቀ በኋላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ጥር 10 ቀን 2002 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የአሁን 1ኛ ተጠሪ ባልነት በአዲስ አበባ የመ/ደ/ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡ የጠበቃው ውክልናም በግሪክ አገር ኢምባሲና በውጭ ጉዳይ ሚ/ር በኩል ተረጋግጦ ቀርቧል፡፡ ጉዳዩም በኢትዮጵያ ፍ/ቤትም ሆነ ሕግ መሠረት ይዳኛል፡፡ ተከሣሾች የጋራ ሀብት ናቸው የተባሉት ንብረቶች የሉም በሚል አልተከራከሩም፡፡ ስለዚህ ንብረቶቹ የጋራ ሀብት ናቸው፡፡ ግማሽ ድርሻ የመካፈል መብት አላቸው በማለት ወስኗል፡፡

ይህ ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ የአሁን አመልካች ይህን ውሣኔ ለሰጠው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በ25/5/2002 ዓ.ም. በተጻፈ አቤቱታ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ክርክር ባስነሳው ንብረት ላይ ያላቸውን መብት ለማስከበር ዝርዝር የፍሬ ነገርና የሕግ ክርክር በማቅረብ ዳኝነት ሲጠይቁ ፍ/ቤቱ በኮ/መ/ቁ. 50497 የካቲት 03 ቀን 2002 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የአሁን አመልካች ከዚህ በፊት ተመሳሳይ አቤቱታ አቅርበው ይህ ፍ/ቤት ሐምሌ 20 ቀን 2001 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ ውሉ በማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ ያልተመዘገበ ስለሆነ በ3ኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ አይሆንም

በማለት የተሰናበቱ ስለሆነ በይዘቱ ተመሳሳይ አቤቱታ በድጋሚ ማቅረባቸው አግባብ አይደለም በሚል ትዕዛዝ አሰናብቷቸዋል፡፡

በዚህ ትዕዛዝ ቅር ተሰኝተው የይግባኝ አቤቱታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ይኸው ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 54796 በ11/9/2002 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የከፍተኛ ፍ/ቤቱ የሰጠው ብይን የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት መዝገቡን በመዘጋቱ የአሁን አመልካች ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውን የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ጥቅል ይዘቱ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የካቲት 03 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ እና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ የሰጠው ዳኝነት በንብረቱ ላይ ያለኝን የመፋለም፣ የመከራከር መብት ያለ ሥርዓቱ የነፈገኝ ስለሆነ ይታረምልኝ የሚል ሆኖ ዝርዝሩም፡- ከዚህ በፊት በባለቤትነቴ በንብረቱ ላይ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ እንዲነሳልኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 158 መሠረት አቤቱታ አቀረብኩ እንጂ ሙሉ ክርክር ያቀረብኩበት አቤቱታ አይደለም፡፡

የሚች ወ/ሮ አረጋሽ ሺበሺ ንብረት በኑዛዜ ለአሁን 3ኛ ተጠሪ ተላልፎ የ3ኛ ተጠሪ የኑዛዜ ወራሽነት በፍ/ቤት ከተረጋገጠ በኋላ የንብረት ስመ-ሀብትነት ወደ ስሟ መዞሩን፣ ከዕዳና ዕገዳ ነፃ መሆኑን በማረጋገጥ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በተደረገ ውል በግዥ የተላለፈልኝ ንብረት ነው፡፡ ይህም የሽያጭ ውል ከቤቱ ማህደር ጋር ተያይዞ የሚገኝ ሲሆን የንብረት /የይዞታ/ ማረጋገጫ ካርታ እና ንብረቱ በእጄ ይገኛል፡፡ ይህ ንብረት የጋራ ሀብት ነው እንኳ ቢባል አንደኛው ተጋቢ ያለ ሥልጣኑ ወደ ሌላ ወገን አስተላልፎ ከተገኘ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 69 የተመለከተው ድንጋጌ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የአሁን 1ኛ ተጠሪ ይህንኑ የሽያጭ ውል አላስፈረሰም፡፡ ከሚች ሌላ የሀብት ድርሻ ላይ በማካካሻነት ከሚጠይቁ በቀር ሀብቱን ሊከተሉ አይችሉም፡፡ በመሆኑም በሕግ መሠረት በሽያጭ ያኘሁት ሀብት ያለአግባብ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ነው የሚል ውሣኔ መሰጠቱን ስረዳ ስለ ጉዳዩ ዝርዝር የፍሬ ነገርና የሕግ ክርክር በማቅረብ የመከራከር መብቴን ያስጠበቁበት የሕግ መሠረት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 የተመለከተው ሆኖ እያለ ክርክር የማሰማት መብቴን የሚነፍግ ዳኝነት መሰጠቱ ሥነ-ሥርዓታዊ ባለመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

በዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ ተጠሪዎች ቀርበው እንዲከራከሩ ጥሪ ሲተላለፍ ከተራ ቁጥር 2 እስከ 4ኛ ድረስ የተዘረዘሩት በጥሪው መሠረት ያልቀረቡ በመሆኑ ጉዳዩ እነርሱ በሌሉበት እንዲታይ ሲደረግ 1ኛ ተጠሪ በጠበቃው አማካኝነት፡- ሐምሌ 20 ቀን 2001 ዓ.ም. እና ጥር 25 ቀን 2002 ዓ.ም. በተፃፈ አቤቱታ አመልካች ያቀረበው ጥያቄ አርዕስቱና የሕግ አንቀጹ ተለያዩ እንጂ ይዘቱ አንድ ነው፡፡ የኑዛዜ ሠነድ የተባለው ተሽሯል፡፡ ስለሆነም በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ዳኝነት የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በማለት ሲከራከር፤

5ኛ ተጠሪ በበኩሉ ሻጯ ቤቱን በስሟ ያዞረችው የቤቱ ባለቤት ሚች ወ/ሮ አረጋሽ በኑዛዜ ሰጥተውኛል በማለት ነው፡፡ ነገር ግን ኑዛዜው በፍ/ቤት ተሰርዟል፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 69 የተመለከተው ድንጋጌ የውርስ ሀብት ክፍፍልን አይመለከትም፡፡ የሰበር አቤቱታው ተቀባይነት የለውም የሚል መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ የሰጠበት ሲሆን በይዘቱ ከዚህ በፊት ካቀረበው የተለየ አይደለም፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭር ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡



www.chilot.me

እንደመረመርነውም የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 መሠረት ያቀረበውን ዝርዝር የፍሬ ነገር እና የሕግ ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም በማለት የከፍተኛው ፍ/ቤት ለሰጠው ዳኝነት መሠረት አድርጎ የያዘው ይህ አቤቱታ በይዘቱ ከዚህ በፊት በ20/11/2001 ዓ.ም. ቀርቦ ዳኝነት ከተሰጠበት በይዘቱ የተለየ አይደለም። ተመሳሳይ አቤቱታ ሆኖ ስለተገኘ በድጋሚ ሊታይ የሚችልበት አግባብ የለም የሚለውን በመንተራስ ነው። ይሁን እንጂ የአሁን አመልካች ሐምሌ 20 ቀን 2001 ዓ.ም. በተጻፈ አቤቱታ ለፍ/ቤቱ የጠየቀው ዳኝነት በጉዳዩ ላይ የክርክር ተካፋይ ሆኖ በተከራካሪነቱ አቋም ያቀረበው ክርክር ሳይሆን በሌሎች ተከራካሪ ወገኖች መካከል በተነሳው ሙግት ሳቢያ በንበረቴ ላይ ጊዜያዊ የማገጃ ትዕዛዝ መሰጠቱን ተረድቻለሁ፣ ይኸው ትዕዛዝ ይነሳልኝ በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 158 መሠረት ዳኝነት የጠየቀበት ነው።

ፍ/ቤቱም ከፍርዱ በፊት ጊዜያዊ ማገጃ ትዕዛዝ የሰጠበት ንብረት የአመልካች ንብረት ነው ለማለት የሚያበቃውን የንብረት ምዝገባ ሥርዓት ያሟላ ባለመሆኑ በዚህ ጊዜያዊ ማገጃ ትዕዛዝ ይነሳልኝ አቤቱታ ላይ ሌሎች ተከራካሪ ወገኖች መልስ እንዲሰጡበት ማድረግ ሳያስፈልግ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት በዕለቱ ዕለት አቤቱታው በቀርበበት አግባብ ዳኝነት የሰጠበት እንጂ የአሁን አመልካች በንብረቱ ላይ ያለውን መብት በሚያሳይ አኳኋን ሙሉ የፍሬ ነገርና የሕግ ክርክር አቅርቦ በዚሁ ክርክር ላይም የከሣሽና የተከሣሾች ክርክር ተሰምቶ ዳኝነት የተሰጠበት ትዕዛዝ አይደለም።

ይልቁንም የዚህ ትዕዛዝ መነሻ ሌሎች ተከራካሪ ወገኖች በከሣሽነትና በተከሣሽነት በሚከራከሩበት ጉዳይ ስለሚሰጠው ፍርድ አፈፃፀም ዋስትና ይሆን ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ 3ኛ መጽሐፍ ምዕራፍ 5 ሥር በተመለከቱት ሁኔታዎች በአንድ ንብረት ላይ ጊዜያዊ የማገጃ ትዕዛዝ በተሰጠ ጊዜ በዚህ ትዕዛዝ ላይ ቅሬታ ያላቸው ወገኖች በሚስተናገዱበት ሥርዓት መሠረት የቀረበ ጥያቄ እና የተሰጠ ዳኝነት እንደመሆኑ መጠን ለጉዳዩም ተፈፃሚነት ያላቸው ድንጋጌዎች በዚህ የሕግ ክፍል የሚገኙት ናቸው።

ከእነዚህም ድንጋጌዎች መካከል ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ንብረት በተከበረ ወይም ታግዶ እንዲቆይ በተደረገ ጊዜ መብት አለን የሚሉ እንደአሁኑ አመልካች ያሉ ሦስተኛ ወገኖች አቤቱታ ባቀረቡ ጊዜ የአቤቱታው አግባብነት የሚመረመረው በፍርድ አፈፃፀም ላይ ያለው ንብረት የሦስተኛ ወገን መብት ያለበት መሆኑ በሚመረመርበት ዓይነትና ሁኔታ (በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418-421) በተመለከተው መሠረት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 153/3/ ተመልክቷል። ይህም ዓይነት ምርመራ በንብረቱ ላይ ሦስተኛ ወገኖች ያላቸውን መብት ለመለየት ሲባል ቀለል ያለና አጭር ሥርዓትን የሚከተል እንጂ ሙሉ የክርክር አካሄድን (Ordinary Judicial Proceeding) የሚጋብዝ ባለመሆኑ በጊዜያዊ ማገጃ ትዕዛዝ እንዲነሳ የቀረበ ጥያቄ ውድቅ በተደረገ ጊዜ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 421 መሠረት ለክርክሩ መነሻ በመሆነው ንብረት ላይ ክስ የማቅረብ መብትን በማይነፍግ ሁኔታ ተደንግጓል።

በዚህም በተያዘው ጉዳይ የከፍተኛው ፍ/ቤት ሐምሌ 20 ቀን 2001 ዓ.ም. በተጻፈ የቀረበለትን ጊዜያዊ የንብረት ማገጃ ትዕዛዝ ይነሳልኝ ጥያቄ ብቻ እንደቀረበለት በዚህ ጥያቄ ላይ ሌሎች ተከራካሪ ወገኖች /ከሣሽና ተከሣሾች/ መልስ መስጠት የማያስፈልጋቸው ሆኖ አልተገኘም በማለት በአጭር ሥርዓት ተመልክቶ ትዕዛዝ የሰጠበት እንጂ አመልካች የክርክር ተካፋይ ሆኖ በጉዳዩ ላይ የሚመለከታቸው ወገኖች ሁሉ ያላቸው ክርክርና ማስረጃ ተሰምቶ የተሟላ የሙግት ሥርዓትን በመከተል የተሰጠ ዳኝነት ባለመሆኑ በዚሁ ንብረት ላይ የአሁን አመልካች አለኝ



www.chilot.me

የሚለውን መብት ለማስከበር የመደመጥ መብቱ ተከብሮ ዳኝነት ማግኘት ይችል ዘንድ አዲስ ክስ ለማቅረብ የሚከለክለው ሥርዓት አልተገኘም፡፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት የተዘረጋው ሥርዓት አስቀድሞ በተሰጠው ውሣኔ መብቱ የሚነካበት ወገን ባለበት እንደገና ውሣኔ እንዳልተሰጠበት ተቆጥሮ እንደገና ክርክር የሚጀምርበት ሥርዓት በመሆኑ በውጤት ደረጃ አዲስ ክስ ከማቅረብ ተለይቶ የሚታይ አይደለም፡፡ ይህም ሲባል አሁን የተነሣውን ክርክር መነሻና መድረሻ መሠረት በማድረግ ለጉዳዩ አግባብነት ካለው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ክፍል አንፃር በማየት የአሁን አመልካች ክርክር ባስነሳው ንብረት ላይ ያለው የመሟገት መብት የተጠበቀ ነው ለማለት እንጂ በማንኛውም ጉዳይ ቢሆን በአንድ ጉዳይ ላይ ክርክር መጀመሩን ያወቀ ወገን የክርክሩን ውጤት ጠብቆ መብቱን የሚነካበት ሆኖ ባገኘው ጊዜ ከውሣኔ በኋላ የመሟገት መብት አለው በማለት ለፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 የተለጠጠ ትርጉም ለመስጠት ተፈልጎ አይደለም፡፡ ይህ ዓይነት አተረጓጎም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግን መሠረታዊ ዓላማ የተከተለ ባለመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የከፍተኛው ፍ/ቤት ሐምሌ 20 ቀን 2001 ዓ.ም. የቀረበለት ጥያቄ እና ለጥያቄው የሰጠው ዳኝነት ከጊዜያዊ የማገጃ ትዕዛዝ አነሳስ ጋር የተያያዘ መሆኑ እየታወቀ አስቀድሞ ሙሉ ክርክር ተደርጎበት ዳኝነት እንዳገኘ ጉዳይ በመቁጠር አመልካች በንብረቱ ላይ ያለውን መብት ለማስከበር ሲል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ያቀረበው የተሟላ የፍሬ ነገርና የሕግ ክርክር አስቀድሞ ዳኝነት ከተሰጠበት ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ በድጋሚ ሊታይ የሚችል አይደለም፡፡ ተቀባይነት የለውም በሚል የተሰጠው ትርጉም መሠረታዊ የሆነ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት እና ከፍተኛው ፍ/ቤት እንደ ቅደም ተከተሉ በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 54796 በ11/9/2002 እና በኮ/መ/ቁ. 50497 ጥር 10 ቀን 2002 ዓ.ም. የተሰጠ ትዕዛዝ እና ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአሁን አመልካች ክርክር የቀረበበትን ንብረት በየካ ክ/ከተማ ቀበሌ 13/14 የሚገኘውንና ቁጥሩ አዲስ የሆነውን በካርታ ቁጥር ሊዝ/06/8328/02/8388 አስመልክቶ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት በቀረበው የፍሬ ነገርና የሕግ ክርክር መሠረት ጉዳዩ እንደገና ታይቶ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ሆኖ ስለተገኘ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚሁ መሠረት አከራክሮ ይወስን ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341 መሠረት መልሰናል፡፡

በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙ ያደረጉት ክርክር ላስከተለው ውጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ

የሰ/መ/ቁ. 52546

ታህሣሥ 13 ቀን 2003 ዓ.ም

*ዳኞች፣* ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

***አመልካች፡-*** እነ አቶ በቀለ አማረ /ሁለት ሰዎች/ 1ኛው አመልካች ቀረቡ

***ተጠሪ፡-*** ወ/ሮ ብዙነሽ ግርማ ጠበቃ ጉታ ጫካ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ጋብቻን መሠረት ያደረገ የንብረት ክፍፍል ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካቾች ላይ በአርሲ ዞን ጢዮ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ከአመልካቾች አባት ጋር ተጋብተው ሲኖሩ ባለቤታቸው ከዚህ አለም በሚያዚያ 07 ቀን 1981 ዓ.ም በሞት መለየታቸውን በሟች ስም የተመዘገበ የጋራ ቤት እንዳላቸው ተጠሪ ቤቱን በአደራ እያስተዳደሩ አመልካቾች ድርሻቸውን እንዲካፈሉ ቢጠይቁም ሳይከፋፈሉ መቆየታቸውን አመልካቾችን በማክበር የንብረቱን ክፍፍል ሳይጠይቁ መቆየታቸውን በመግለጽ አመልካቾች ድርሻቸውን እንዲካፈሉ እና የእርሳቸውም ድርሻ እንዲሰጣቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረቡት ክርክር ጉዳዩ በእርቅ ያለቀ መሆኑን የሚጠቅስ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ አባታቸው ቤቱን ተጠሪን ከማግባታቸው በፊት የሰሩት የግል ሀብት መሆኑን ሟች ቤቱን በተመለከተ ያደረጉት ኑዛዜ አለመግባባት በመፍጠሩ ወራሾች ስለቤቱ አጠባበቅና ክፍፍል በተመለከተ ግንቦት 21 ቀን 1981 ዓ.ም የእርቅ ስምምነት ማድረጋቸውንና ተጠሪ የልጆቻቸው ሞግዚት በመሆን ፈርመው እና ስምምነቱ በፍርድ ቤቱ ፀድቆ ያለ በመሆኑ ክስ ሊቀርብ እንደማይገባ በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳ ፍርድ ቤትም ተጠሪ ከአመልካቾች አባት ጋር ሚስት በመሆኑ አብረው እስከኖሩና አመልካቾች ቤቱ የአባታቸው የግል ሀብት መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ እስካላቀረቡ ድረስ ሟችና ተጠሪ በጋራ የሚጠቀሙበት ቤት የጋራ ሀብት መሆኑንና ተደረገ የተባለውም የእርቅ ስምምነት በወራሾች መካከል የተደረገ በመሆኑ በተጠሪ ላይ ተፈፃሚነት የለውም የሚል ምክንያት በመያዝ ተጠሪ የቤቱ ግማሽ ድርሻ ይገባቸዋል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት



www.chilot.me

ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች ጠበቃ የካቲት 04 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ቤቱ ከጋብቻ በፊት የተሰራ መሆኑን የሚያስረዱ ማስረጃዎች ተቆጥረው እያለ ሳይሰሙ ውሣኔ መስጠቱ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የአመልካቾች አባት እና ተጠሪ ከመጋባታቸው በፊት የአመልካቾች አባት የሰሩት ቤት ስለሆነ የጋራ ሊባል አይገባም በማለት አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ክርክር አቅርበው ቤቱ ከጋብቻ በፊት የተሰራ ስለመሆኑ ያስረዱልናል በማለት የቆጠሯቸው ምስክሮች ሳይሰሙ የስር ፍርድ ቤቶች ቤቱ የጋራ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግንቦት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ አምስት ገፅ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ በመልሳቸውም የአመልካቾች ጥያቄ በይርጋ ቀሪ እንደሚሆንና ጋብቻው መቼ እንደተፈጸመ ገልጸው ያልተከራከሩ መሆኑን በመጥቀስ ማስረጃ ሳይሰማ ውሣኔ ተሰጥቷል የሚለው ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃም በመልስ መልሳቸው ላይ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ክስ ሊመሰርቱ የቻሉት አከራካሪው ቤት ከአመልካቾች አባት ጋር በጋብቻ ተሳስረው በነበሩበት ጊዜ የተፈራ መሆኑን ገልፀው አመልካቾች ተጠሪ የአውራሻቸው ሚስት የነበሩ መሆኑን ሳይክዱ የሚከራከሩት አከራካሪው ንብረት ተጠሪ ከሟች አባታቸው ጋር ጋብቻ ከመፈፀማቸው በፊት የተሰራ በመሆኑ የጋብቻ ውጤት አይደለም በማለት መሆኑን ነው፡፡

ከላይ እንደተገለፀው አመልካቾች አከራካሪው ንብረት የተፈራው አውራሻቸው ከተጠሪ ጋር ጋብቻ ከመመስረታቸው በፊት ነው በማለት ቢከራከሩም ተጠሪ ግን ቤቱ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ ንብረት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

በአመልካቾች ክርክር እንደተገለፀው ቤቱ ከጋብቻ በፊት በአውራሻቸው ስለመፈራቱ ተጠቅሶ ይህንኑ ፍሬ ነገር ለማስረዳት ምስክሮችን ቆጥረዋል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካቾች የቆጠሯቸው ማስረጃዎች በስር ፍርድ ቤት አልተሰሙም ፍ/ቤቱ በቂ የሆነ ማጣራትም አላደረም፡፡

በግራቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የተካደ ወይም ያልተማመኑበት የፍሬ ነገር ነጥብ የሚነጥረው በማስረጃ ነው፡፡ በግራቀኝ ተከራካሪ ወገኖች የተቆጠረና ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ማስረጃ በአግባቡ መስማት አንዱና ዋነኛው የፍርድ አመራር ስርዓት መሠረታዊ መርህ ነው፡፡ በእርግጥ በተከራካሪ ወገን የቀረበ ማስረጃ ሁሉ ያለምንም ምክንያት መሰማት አለበት ማለት እንዳልሆነ የማስረጃ ደንቦች የሚያሳዩን ጉዳይ ነው፡፡ የተቆጠረው ማስረጃ ለተያዘው ክርክር አግባብነት የሌለው ሆኖ ከተገኘ ውድቅ የሚደረገው እንዲሁ በደፈናው ሣይሆን ምክንያቱን በግልጽ በጽሑፍ በማስፈር ነው /የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ 138/፡፡ በተያዘው ጉዳይ እንደምናየው የስር ፍ/ቤቶች ወደ ውሣኔ ያመሩት በአመልካቾች የተቆጠረውን ማስረጃ አስቀርበው ሣያዩ እና ሣይመረምሩ ነው፡፡ ማስረጃው ቤቱ

የተሰራበትን ጊዜና ሁኔታ ያረጋግጣሉ የተባሉት የሰው ምስክሮች ሲሆኑ ምስክሮች የሚሰጡት ቃል ደግሞ ቤቱ የጋብቻ ውጤት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ለመፍታት አግባብነት ያለው ማስረጃ ነው፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ የምስክሮችን ቃል ሳይሰማና ክብደቱን ከተያዘው ጭብጥ ጋር አገናዝቦ ሣይመረምር ብቃት ያለው ማስረጃ አይደለም ወደሚለው መደምደሚያ ሊደርስ አይችልም አይገባምም፡፡ አንደ ሰው ለቀረበበት ክስ መከላከያ ማስረጃ ለጉዳዩ አግባብነት እስካለው ድረስ ማሰማት የሕግ ስርዓቱ /Due Process of law/ የግድ የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ መብትም ነው፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ማስረጃ ተቆጥሮ እያለ ማስረጃው ሳይሰማ ወደፍርድ ማምራት አይቻልም፡፡ ፍርድ ሊሰጥ የሚገባው የክርክር አመራር ሥርዓት በተገቢው መንገድ ከተሟላ በኃላ ነው፡፡ የመከላከያ ማስረጃ በሥነ ሥርዓቱ አግባብ ተቆጥሮ እያለ ይኸው ሳይሟላ የሚሰጥ ፍርድ አካሄዱ የተሟላ ነው ሊባል አይችልም፡፡ የፍርድ አካሄዱ ያልተሟላ ውሣኔ ደግሞ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

እነዚህን ሁኔታዎች ደምረን ስንመለከት ፍ/ቤቱ ወደ ውሣኔ ያመራው ምንም ዓይነት ማስረጃ ሣይሰማ እንደሆነ ነው፡፡ በግልጽ የቀረበን ክርክር በተቆጠረው ማስረጃ ወይም አግባብነት ባለው መንገድ ሣያጣሩ/ሣያነጥሩ/ መወሰን ደግሞ ዋነኛው መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀም ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔም የአመልካቾችን የመከላከያ ማስረጃ ማሰማት መብት ያልጠበቀ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአርሲ ዞን ጢዮ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 08970 ግንቦት 18 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 16409 ጥቅምት 21 ቀን 2001 ዓ.ም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት በመ/ቁጥር 71266 ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ.ም እንዲሁም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 90774 ህዳር 14 ቀን 2002 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የጢዮ ወረዳ ፍርድ ቤት በተከፈተው መዝገብ ቁ 08970 ክርክሩ እንዲቀጥል በማድረግ እና በአመልካቾች የተቆጠሩትን ማስረጃዎች በመስማት እንዲሁም የተጠሪንም ማስረጃ የማሰማት መብት በመጠበቅ ክርክሩን መርምሮ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 343/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 55078

ታህሣሥ 25 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፣** ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች -** ማበርፋይድ ኃ/የተ/የግል ማህበር

**ተጠሪዎች -** 1. አሸናፊ አለሙ

2. በለጠ እሸቱ

3. አብዮት ጉግሳ

4. ወንድወሰን ጌቱ

5. አባይነህ ደምሴ

6. ሰሎሞን ይገዙ

7. ኤልያስ አክመል

8. ሳህሌ ከበደ

9. እንግዳ ደበሌ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኞች መካከል የተነሳውን የሥራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክር በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪዎች አመልካችን የከሰሱት የሥራ ውላችን ከሕግ ውጪ አቋርጦብናል በማለት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ተጠሪዎች ያለበቂ ምክንያት ከሥራ በመቅረታቸው ነው በማለት ተከራክሮአል ከዚህም በተጨማሪ 1ኛ፣3ኛ፣5ኛ፣ 7ኛ፣ 8ኛ እና 9ኛ ተጠሪዎች ክርክሩ ሊሰማ በተቀጠረበት ዕለት በመቅረታቸው ምክንያት ከክሱ ውጪ እንዲሆኑ ከተደረጉ በኃላ ክርክሩ ውስጥ እንዳሉ በመቁጠር መመዝገባቸው ትክክል አይደለም በማለት አመልካች መከራከሩን ተመልክተናል፡፡ ከዚህ በኃላ ፍ/ቤቱ በአመልካች የቀረበውን ክርክር ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግ ተጠሪዎች የተለያዩ ክፍያዎች እንዲያገኙ ወስኖአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሚያዚያ 13 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው 1ኛ፣3ኛ፣5ኛ፣7ኛ፣8ኛ እና 9ኛ ተጠሪዎች ከክሱ ውጪ እንዲሆኑ ትዕዛዝ ከተሰጠ በኃላ እነሱ ሳይጠይቁ የሥር ፍ/ቤት ትዕዛዙን በማንሳት እነሱንም በመጨመር ውሣኔ መስጠቱ በአግባቡ ነው? የሚለውን ጭብጥ ለመመርመር ነው 2ኛ 4ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎችን በሚመለከት እንደውሣኔው እፈጽማለሁ በማለት የአመልካች ጠበቃ ተጠሪዎች ግን በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ባለመቅረባቸው ክርክሩ በሌሉበት ተሰምቶአል፡፡

በአመልካች የቀረበውን አቤቱታ መነሻ በማድረግ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በዝርዝር ተመልክተናል በእርግጥም ከሣሾች ሆነው በፍ/ቤቱ መዝገብ የተመለከቱት ዘጠኙም ተጠሪዎች ቢሆኑም ክርክሩ ሊሰማ ቀነ ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት የቀረቡት ግን 2ኛ 4ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች እንደሆኑ እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ይህን ሁኔታ በመገንዘብ እንደዚሁም የአመልካች ጠበቃ ያቀረበውን አቤቱታ በመስማት 1ኛ፣ 3ኛ፣ 5ኛ፣ 7ኛ፣8ኛ እና 9ኛ ተጠሪዎችን /ተከሣሾችን/ ከክሱ ውጪ እንዲሆኑ አድርጎ እንደነበር ከውሣኔው ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ይህ በአንድ በኩል የሆነው የክርክሩ ሂደት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በሚቀጥለው ቀነቀጠሮ ፍ/ቤቱ ትዕዛዙን በማንሳት ተጠሪዎቹ በክርክሩ ውስጥ እንዳሉ በመቁጠር ቀሪውን የክርክር ሂደት አጠናቆ ውሣኔ እንደሰጠ ተገንዝበናል፡፡

በበኩላችን እንደምናየው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት 1ኛ፣ 3ኛ፣ 5ኛ 7ኛ፣ 8ኛ እና 9ኛ ተጠሪዎችን በተመለከተ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 73 በተደነገገው መሠረት ትዕዛዝ ሰጥቶ ከክሱ ውጪ እንዲሆኑ አድርጎአል ከዚህ በኃላ ተጠሪዎቹ ክርክሩ ውስጥ እንዳሉ በማድረግ የወሰነው ደግሞ ጉዳዩን ቀጥሎ ባለው የሥነ ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌ /ቁ 74/ ከተቀመጠው ሥርዓት ውጪ በሆነ ሁኔታ እንደሆነ ከውሣኔው ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ተጠሪዎቹ እነሱን በተመለከተ የተሰጠው ትዕዛዝ እንዲነሳላቸው አላመለከቱም ከሁሉ በላይ ደግሞ ተጠሪዎቹ በየግላቸው ከአመልካች ጋር ባላቸው የሥራ ውል መሠረት ክርክር አልተደረገም፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ተጠሪዎቹ የክርክሩ ተካፋይ እንደሆኑ አድርጎ በመወሰኑ ውሣኔው ከሥነ ሥርዓት ሕጉ አተገባበርም ሆነ ለውሣኔው መሠረት ሊሆን የሚገባውን ፍሬ ነገር ከመጨበጥ አንፃር ሲታይ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 13664 ሐምሌ 15 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና ይህን ውሣኔ በማፅናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 83507 የካቲት 18 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካች 1ኛ፣3ኛ፣5ኛ፣7ኛ፣8ኛ እና 9ኛ ተጠሪዎችን በሚመለከት በሥር ፍ/ቤቶች በተሰጠው ውሣኔ እንዲፈጽም አይገደድም በማለት ወስነናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

ም.አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 52193

ታህሣስ 27 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- የኮንስትራክሽንና የቢዝነስ ባንክ አ.ማ - ነ/ፈጅ ነጋ አበበ ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡-1. ወ/ሮ መድኃኒት ኃይሉ } ጠበቃ መኮንን ይማም ቀረቡ

2. አቶ ጌታቸው ተሰማ

መዝገቡ በአዳሪ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን የፍርድ ባለመብት የሆነው የአሁኑ ተጠሪዎች በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የአፈፃፀም ማመልከቻ እስከዚህ ሰበር ችሎት እንዲከፈላቸው የተወሰነው ብር 1,307,607.00 /አንድ ሚሊዮን ሦስት መቶ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሰባት ብር/ ከተለያዩ ወጪዎች ጋር እንዲፈጸምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የተጠሪዎች አፈፃፀም መዝገብን በመቀበል እንደፍርዱ የማይፈጸምበትን ምክንያት አመልካች ቀርቦ እንዲያስረዳ ወይም እንደፍርዱ ፈፅሞ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ የአሁኑ አመልካች ቀርቦ ተጠሪዎች በ27/07/1985 እና በ07/04/1986 ዓ.ም. በተፈረሙ የብድር ውሎች ከአመልካች ላይ የወሰዱትን ገንዘብ በውሉ መሠረት ከሚያስከትለው ወለድ፣ የኢንሹራንስ ክፍያ እና ሌሎች ልዩ ልዩ ወጪዎች ጋር ብር 858,457.38 /ስምንት መቶ ሃምሣ ስምንት ሺህ አራት መቶ ሃምሣ ሰባት ብር ከሠላሣ ስምንት ሣንቲም/ እና አመልካች ሆቴል ቤቱን በጨረታ ከገዛው በኋላ ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ ምክንያት በየደረጃው ባሉት ፍርድ ቤቶች ሆቴል ቤቱን እንዳይረከብ በማሳገድ ያላግባብ ስለተጠቀሙት አመልካች ሆቴል ቤቱን በወቅቱ ተረክቦ ቢሆን ኖሮ ከሆቴል ቤቱ ሊያገኝ የነበረውን የቤት ኪራይ ብር 604,000.00 /ስድስት መቶ አራት ሺህ ብር/ በድምሩ ብር 1,460,457.38/ አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ስልሣ ሺህ አራት መቶ ሃምሣ ሰባት ብር ከሠላሣ ስምንት ሣንቲም/ ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚያስከትለው ወለድ እና ከክሱ ወጪ እና ኪሣራ ጋር እንዲከፍሉት በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀጥታ ክስ ማቅረቡን በመግለጽ አፈፃፀሙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 377 መሠረት እንዲቆምለት ወይም ገንዘቡ ታግዶ እንዲቆይለት አፈፃፀሙን ለያዘው ፍርድ ቤት አመልክቷል፡፡ አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤትም አመልካች ያቀረበውን አቤቱታና እግድ ውድቅ በማድረግ አመልካች በፍርዱ መሠረት ፈጽሞ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ

ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ጥር 18 ቀን 2002 ዓ.ም. በጻፉት አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች የአፈፃፀም ትዕዛዝ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡

ይዘቱም ባጭሩ፡-

አመልካች ከተጠሪዎች የሚፈለግ ዕዳ መኖሩን ገልፆ ቀጥታ ክስ በመመስረት ጉዳዩ እየታየ ባለበት ሁኔታ ተጠሪዎች የከፈቱት የአፈጻጸም መዝገብ እንዳይቀም መደረጉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 377 ድንጋጌን መሠረት ያላደረገ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች የፍርድ ባለመብት በሆኑት ተጠሪዎች ላይ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ በቀጠሮ ላይ ባለበት ሁኔታ አፈፃፀሙ የመቀጠሉ አግባብነት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 377 አንፃር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የጽሑፍ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅም የመልስ መልሳቸውን በጽሑፍ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አመልካች በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመሠረተው ቀጥታ ክስ በመ/ቁጥር 64235 በሆነው ታይቶ ግንቦት 26 ቀን 2002 ዓ.ም. ውድቅ መሆኑን፣ እንዲሁም በዚሁ ውሣኔ ላይ አመልካች ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቀርቦ በመ/ቁጥር 57640 በሆነው የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ መጽናቱ ተረጋግጧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ፍርድ በተፈረደበት ማናቸውም ሰው ላይ ፍርድ የተፈረደለት ወገን ክስ ያቀረበበት እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ የገመተውን በቂ ዋስትና ወይም መያዣ እንዲሰጥ ካደረገ በሁዋላ ለክርክሩ ውሣኔ እስከሚሰጠው ድረስ አፈፃፀሙ ታግዶ እንዲቆይ ትዕዛዝ መስጠት እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 377 ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው በቀድሞው ክስና በአፈፃፀሙ ጊዜ በቀረበው ክስ ተከራካሪ የሆኑት ወገኖች ተመሳሳይ መሆን እንደሚገባቸው ነው፡፡ አመልካች ለተጠሪዎች እንዲከፍል በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ የተሰጠው የተጠሪዎችን ሆቴል ከግምቱ ውጪ ሸጧል በሚል ምክንያት ሲሆን ይህ ውሣኔ እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ፀንቷል፡፡ አመልካች ከዚህ በሁዋላ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሠረተው በብድር ውሉና በሐራጅ ገዝቼዋለሁ በሚለው ቤት የቀረበትን ጥቅም በመዘርዘር ነው፡፡ አፈፃፀሙ እንዲታገድ የጠየቀውም ይህንኑ ክስ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 377 ዓላማ የፍርድ ባለመብት የሆነ ወገን አፈፃፀሙን በሚቀጥልበት ጊዜ የፍርድ ባለዕዳው በበኩሉ በፍርድ ባለመብቱ ላይ ክስ አቅርቦ ሲገኝ ምናልባት በክርክሩ ረቺ ቢሆን ፍርዱን ጎን ለጎን ለማስፈጸም እንዲቻል ለማድረግ መሆኑ ይታመናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች የፍርድ ባለመብት በሆኑት ተጠሪዎች ላይ ክስ የመሠረተው አስቀድሞ ታይቶ በተወሰነው ጉዳይ ሳይከፈለኝ የቀረ ዕዳ አለ፣ በጨረታ የተሸጠውን

ሆቴል ደገሞ በጊዜው በመረከብ አከራይቼ ላገኝ እችል የነበረውን ጥቅም አስቀርተውብኛል በሚል ሲሆን ይህ አካሄድ መጨረሻ ላይ ጎን ለጎን ሊፈፀም የሚችል ፍርድ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 377 ድንጋጌ ዓላማ ስር የሚወድቅ አይደለም፡፡ አመልካች ያቀረበውን ቀጥታ ክስ በመጀመሪያ ደረጃ ሲመለከተው የነበረው ፍርድ ቤትም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት የአመልካችን ክስ ውድቅ ማድረጋቸው ተረጋግጧል፡፡ አመልካች አሁን የቀረው የመጨረሻ እድሉ ጉዳዩን በሰበር ማሳየት ነው፡፡ በሰበር ሰሚው ችሎት ጉዳዩ የሕግ ነጥብ አለበት የሚባል ከሆነም አመልካች ሥርዓቱን ጠብቆ ለተጠሪዎች የሚከፍለው ገንዘብ እንዲከበርለት ከሚጠይቅ በስተቀር አሁን የሥር ፍርድ ቤት የያዘውን አፈጻጸም ሙሉ በሙሉ እንዲቆም የሚያስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ በአሁኑ ደረጃ ሲታይ ስህተት ነው ለማለት የሚያስችል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1) በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡

2) በዚህ ሰበር ችሎት የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>**ት ዕ ዛ ዝ**</u>

በዚህ ችሎት የካቲት 16 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 61846

ግንቦት 29 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** ፡- ወ/ሮ ፋጡማ ጀማል - ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- ወ/ሮ ፋጡማ ኡስማን ከጠበቃ መሐመድ ሀሰን ጋር - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78 መሠረት የሚስተናገደውን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት ሲሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78 መሠረት አቤቱታውን ያቀረቡት የአሁኑ አመልካች ናቸው፡፡ የአመልካች የአቤቱታ ይዘትም ባጭሩ፡- አመልካች በከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በነበረው የይግባኝ ክርክር የክርክሩ ተካፋይ መሆን ሲገባቸው ሣይከራከሩበት በቀድሞ አወቃቀር በወረዳ 08 ፣ ቀበሌ 02 ክልል ወስጥ በሚገኝና ቁጥሩ 102 በሆነው የግል የመኖሪያ ቤታቸው ላይ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሣኔ መብታቸውን የሚጐዳ ከመሆኑም በላይ በተከሰሱበት ጉዳይ የመከላከል ህገ መንግስታዊ መብታቸውን የሚጋፋ በመሆኑ አመልካች በሌሉበት የተሰጠው ውሣኔ ተነስቶ የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ ይደረግላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታው ጋርም ከውጭ አገር የነበሩ መሆኑን የሚያሣዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አያይዘው አቅርበዋል፡ አቤቱታው የቀረበለት ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤትም አመልካች አቤቱታውን ያቀረቡት ጉዳዩ ውሣኔ ካገኘ ከስድስት ዓመት በሁዋላ ከመሆኑም በላይ ጉዳዩ የቤተሰብ እንደመሆኑ መጠን አልሰሙም ነበር ለማለትም የሚቻል አይደለም በሚል ምክንያት የአመልካች አቤቱታን ውድቅ አድርጐ ብይን ሰጥቷል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸው ለፌዴራሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ በከፍተኛው ሸሪዓ ፍርድ ቤት በነበረው የይግባኝ ክርክር አመልካች በወኪላቸዉ አማካኝነት የክርክሩ ተካፋይ የነበሩ መሆኑ መረጋገጡን ጉዳዩ የቤተሰብ ከመሆኑም በላይ አመልካች ይኖሩበት ከነበረው ውጪ አገር ወደ ኢትዮጵያ ሲመላለሱ የነበረ መሆኑ መረጋገጡን በምክንያትነት በመያዝ በይግባኙ ክርክር ውሣኔ ከተሰጠ ከስድስት ዓመት በሁዋላ ጉዳዩ ባለሁበት ይታይልኝ ተብሎ የቀረበው የአመልካች ጥያቄ በህጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልቀረበና በበቂና ህጋዊ ምክንያት ያልተደገፈ ነው በማለት የከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤትን ብይን አጽንቶታል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህኑን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት ሲታይም የክርክሩ ተካፋይ ሣይሆኑ በግል ገንዘባቸው በገዙት ቤት ላይ ተገቢ



www.chilot.me

ያልሆነ ውሣኔ ማረፉን ገልጸው የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ ባሉበት እንዲታይላቸው ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ ማድረጋቸው ህጋዊ አለመሆኑን በመዘርዘር ውሣኔው እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የአመልካች አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት ሊታይ የሚችልበት አግባብ መኖር ያለመኖሩን ሣያረጋግጡ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78 መሠረት ወደ ክርክሩ ለመግባት በቂ ምክንያት የላትም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጐአል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጐላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሁፍ ክርክር አድርገዋል፡፡ ከላይ የተመለከተው የክርክሩ አመጣጥ ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እንዲሁም ከፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት ካስቀረብነው የመ/ቁጥር 51/93 እና 4640/2001 ፣ ከፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ካስቀረብነው መ/ቁጥር 68/2002 ጋር አዛምደን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም ተጠሪ በሌሉበት የተሰጠው ውሣኔ ሊነሣ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ መመልከቱ ተገቢ ሁኖ አግኝተነዋል፡፡

የፍታብሔር ክርክሮች የሚመሩት በ1958 ቱ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ መሠረት ነው፡፡ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የክርክር አመራር ስርዓትም በዚህ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀጽ 6/1/ ድንጋጌ በግልጽ ያሣያል፡፡ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ አካቶ ከያዛቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የተከራካሪ ወገኖች በክርክሩ ወቅት ያለመቅረብና ውጤቱ ነው፡፡ በዚህም መሠረት መጥሪያ ተልኮለት በተገቢው መንገድ የደረሰው መሆኑ በተረጋገጠበት ተከሣሽ /መልስ ሰጪ/ ላይ ፍ/ቤቱ ሊከተለው የሚገባው ሥርዓት ጉዳዩ ተከሣሹ/መልስ ሰጪ በሌለበት የሚሰማበት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 70/ሀ/ ስር ተመልክቷል፡፡ ሌላው በሥነ ሥርዓት ህጉ የተመለከተው ሥርዓት ተከሳሹ ሊከተለው የሚገባው መፍትሔ ነው፡፡ ክርክሩ በሌለበት እንዲቀጥል የተደረገበት ተከሣሽ በተከታዩ ቀነ ቀጠሮ ቀርቦ በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት በመጀመሪያ ቀነ ቀጠሮ ያለመቅረቡን ካስረዳ መከላከያውን አቅርቦ የመከራከር መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 72 ያስገነዝባል፡፡ እንዲሁም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78/1/ አንድ ተከሣሽ /መልስ ሰጪ/ በክርክሩ ላይ ቀርቦ መልስ ሣይሰጥ ወይም ተገቢውን መከራከሪያ ሣያቀርብ በመቅረቱ በሌለበት አንድ ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ የተሰጠ ከሆነ ውሣኔው ወይም ትዕዛዙ መሰጠቱን በተረዳው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ትዕዛዙ ወይም ውሣኔው እንዲነሣለት የማመልከት መብት እንዳለው ተደግንጓል፡፡ አቤቱታ አቅራቢ በዚህ መሠረት ማመልከቻ በሚያቀርብበት ጊዜ የጥሪው ትዕዛዝ በሚገባ ያልደረሰው መሆኑን ወይም ክርክሩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ቀርቦ መከራከሪያውን ያላሰማው ወይም መልስ ያልሰጠው በበቂ ምክንያት መሆኑን ፍርድ ቤቱ የተረዳ እንደሆነ የተከሣሹ /የመልስ ሰጪ/ አቤቱታ ላንደኛው ወገን ተከራካሪ እንዲደርሰው ካደረገና ተገቢውን ኪሣራ ወይም መቀጮ እንዲከፍል ካዘዘ በኋላ ትዕዛዙን ወይም ብይኑን በማንሣት ክርክሩን እንደገና መስማት እንዳለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78/2/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያሣያል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በሌለሁበት በግል ንብረቴ ላይ ውሣኔ ተሰጥቶብኛል የሚሉት ጥር 09 ቀን 1995 ዓ.ም ሲሆን ይኸው ውሣኔ ተነስቶ ወደ ክርክሩ ልገባ ይገባል በማለት አቤቱታ ያቀረቡት ደግሞ ነሐሴ 19 ቀን 2001 ዓ.ም ነው፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት የስር ፍርድ ቤቶች መዛግብት መገንዘብ የተቻለው ደግሞ የአሁኗ አመልካች ወ/ሮ ኑሪያ ኡስማን /የሟች ሚስት/ እና ሌሎች አምስት የሚሆኑ የሟች ጀማል ሐምዛ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች መሆናቸውን ገልጸው በሸሪዓ ህግ መሠረት የውርስ ንብረቱን ለመከፋፈል ንብረቱን ይዘዋል፣ የሟች ሁለተኛ ሚስት



www.chilot.me

ናቸው ባሏቸው የአሁኗ ተጠሪ ላይ ክስ መስርተው የስር ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢ ነው ያለውን ውሣኔ ከሰጠ በሁዋላ ተጠሪ የአሁን አመልካች በግል የገዛሁት ንብረቴ ነው በሚሉት ቤት ላይ የተሰጠውን የውሣኔ ክፍል በመቃወም ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አቅርበው የስር ከሣሾች የነበሩት፤ የአሁኗ አመልካች ጭምር በወ/ሪት ቀመሪያ ጀማል አማካኝነት ተወክለው የይግባኝ ክርክሩ ተካሂዶ አከራካሪው ንብረት ላይ ተገቢ ነው የተባለ ውሣኔ የተሰጠበት መሆኑን ነው፡፡ አመልካች ራሣቸው የክርክሩ ተካፋይ ባይሆኑም በህጉ አግባብ የወከሏቸው እህታቸዉ ወ/ሪት ቀመሪያ ጀማል የክርክሩ ተካፋይ የነበሩ መሆኑን ከላይ የተጠቀሱት መዛግብት በሚገባ ያረጋግጣሉ፡፡ ይህም የሚያሣየው አመልካች በህጉ አግባብ የክርክሩ ተካፋይ የነበሩ መሆኑን ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ አንድ ሰው በውሣኔው ላይ የሚኖረውን ቅሬታ በይግባኝ ወይም በሰበር ስርዓት ማሣረም እንጂ ጉዳዩ በሌለሁበት ታይቷል፡፡ ባለሁበት ሊታይልኝ ይገባል በማለት አቤቱታ የሚያቀርብበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78 ድንጋጌ ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ ሲታይም አከራካሪው ንብረት የክርክሩ ምክንያት የነበረ መሆኑንና አመልካችም በህጉ አግባብ ተወክለው የነበሩ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የሚያሣይ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት የአመልካች አቤቱታ ሊስተናገድ ይገባ ነበር ሊባይ የሚችል ባለመሆኑ ተገቢነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በአጠቃላይ አመልካች በሌለሁበት የተሰጠው ውሣኔ ይነሣልኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ውድቅ መደረጉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78 ስር የተመለከተውን መመዘኛ መሠረት ያደረገ ሲሆን አመልካች የግል ቤቴ ላይ ተገቢ ያልሆነ ውሣኔ ተሰጥቷል በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ደግሞ በይዘቱ በዋና ጉዳይ ላይ የቀረበ በመሆኑ የክርክሩን አመራር ስርዓት ካልሆነ በስተቀር የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በስረ ነገር ስልጣናቸው ስር የሆኑ ጉዳዮች የሚቀርብላቸዉን አቤቱታና ክርክር የሚወስኑት የሸሪዓ ህግን መሠረት በማድረግ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 188/92 በአንቀጽ 6/1/ በግልጽ የተደነገገ በመሆኑ አንድ ሰው ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ክስ ወይም አቤቱታ ሲያቀርብና ተገቢ የተባለ ውሣኔ ከተሰጠ ሥነ ሥርዓታዊ ከሆነው ጭብጥና ጥያቄ ውጭ የሆኑት ጉዳዮች ለዚህ ሰበር ችሎት ለማቅረብ የሚቻልበት አግባብ የሌለ በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሁኖ አላገኘንም፡፡ በዚህም መሠረት በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሥነ ሥርዓት ህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 68/2002 ሐምሌ 28 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. አንድ ተከራካሪ ወገን በህጉ አግባብ በተወከለው ሰው የክርክሩ ተካፋይ መሆኑ ከተረጋገጠ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78 መሠረት በሌለሁበት የተሰጠ ውሣኔ ሊነሣልኝ ይገባል ለማለት አይችልም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት ጥር 19 ቀን 2003 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፤ ለሚመለከታቸው አካላት ይጻፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 55842

መጋቢት 23 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች ፡-** የኦሮሚያ ከተሞች ፕላን ኢንስቲትዩት - ነ/ፈጅ ለገሠ ለማ ቀረቡ

**ተጠሪ ፡-** 1. አቶ ካሣ ጭርሳ
2. አቶ ሽፈራ ሔምቤ
3. አቶ አክሊሉ ካሣ
(1-3) ቀረቡ

4. የቡሌ ሆራ ከተማ አስተዳደር - ነ/ፈጅ ፈቃዱ ኤሌማ ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ፍርድን መቃወም የሚቻልበትና አቤቱታው የሚስተናግድበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች በአሁኑ ከ1ኛ እስከ 3ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ባሁኑ 4ኛ ተጠሪ ላይ ያስፈረዱት ፍርድ የአመልካችን መብትና ጥቅም የሚነካ በመሆኑ ፍርዱ እንዲነሳለት ባቀረበው አቤቱታ መነሻ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤትም አመልካችንና ተጠሪዎችን በአፈፃፀም መዝገቡ ላይ እንዲከራከሩ በማድረግ አመልካች ዋናውን ውሳኔ በይግባኝ ሳያሸር አፈፃፀሙን ሊቃወም አይችልም፣ ውሉ የሚፈርስበት ምክንያትም የለም በማለት አፈፃፀሙ ሊቀጥል ይገባል ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ትእዛዝ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለቦረና ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የሰበር አቤቱታውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የአፈጻጸም ትእዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ግንቦት 04 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት አራት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች በተሰጠው ትዕዛዝ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ አመልካች በሕጉ በተሰጠው ስልጣን ለክልሉ ከተሞች እንደየደረጃቸው ከተማ አቀፍ መዋቅራዊ ፕላን እና የአካባቢ ልማት ፕላን (City wide structure plan and local development plan) እየሰራና እያሰራ ስራ ላይ እንዲውል የማድረግና ስራ ላይ መዋሉን የመቆጣጠር ኃላፊነቱንና ተግባሩን ለመወጣት የሚችል ሁኖ እያለ

ይህንኑ ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት በማድረግ ተጠሪዎች ከከተማው ፕላን ውጪ ቦታ ሊወስዱ አይገባም በማለት ያቀረበው የፍርድ ተቃውሞ ተቀባይነት ያጣው ያላግባብ መሆኑንና አቤቱታው የቀረበውም ዋናውን ፍርድ በመቃወም ሁኖ እያለ በአፈፃፀም መዝገብ ላይ እንደቀረበ ተደርጎ ትእዛዝ መስጠቱ ተገቢነት የሌለው መሆኑን፣ ዋናውን ፍርድ ሕጋዊ አይደለም በማለትም ተገቢው ክርክርና ማስረጃ ቀርቦ እያለና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 145 መሰረትም አግባብነት ያለው ማስረጃ በፍርድ ቤቱ እገዛ እንዲቀርብ ጥያቄ ቀርቦ እያለ ይኸው ታልፎ በዋናው ጉዳይ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ሊሻር አይገባም ተብሎ የተሰጠው ትእዛዝ ሥነ ሥርዓታዊ አይደለም በማለት ዘርዝረው የአፈጻጸም ትዕዛዝ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የአመልካች የፍርድ ተቃውሞ አቤቱታ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ በዚህም መሰረት ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው መልሳቸውን በፅሑፍ አቅርበዋል፣ አመልካችም የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሰረቱ አንድ የፍትሐብሔር ክርክር የሚመራበት ሥርዓት የሚገዛው በ1958ቱ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጋችን እና በክልሎች ስራ ላይ ባሉት አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሆኑ እሙን ነው፡፡ የ1958ቱ የፍትሐብሔር ስነ ሥርዓት ሕጋችን ከያዛቸው ስርዓቶች መካከል በፍርድ ላይ የሚቀርበው ተቃውሞ እና በፍርድ አፈጻጸም ጊዜ በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት ላይ የሚቀርበው ጣልቃ ገብነትን የሚገዙት ድንጋጌዎች ይገኙበታል፡፡ እነዚህ አቤቱታዎችን የሚገዙት ድንጋጌዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 እና 418 ስር የተመለከቱት ናቸው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 አንድ የክርክሩ ተካፋይ መሆን የሚገባው ሰው የክርክሩ ተካፋይ ሳይሆን ውሳኔ ተሰጥቶ ከሆነ እና ውሳኔውም ያረፈው በአንድ የክርክሩ ምክንያት በሆነ ንብረት ላይ ሁኖ ይህንኑ የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነ ወገንን መብትና ጥቅም የሚነካ መሆኑ ከተረጋገጠ ፍርዱ ይኸው ወገን ባለበት እንዲታይና እንዲነሳለት የሚደነግግ ነው፡፡ አቤቱታው የሚቀርብበት ሥርዓትም በቁጥር 359 ስር በተመለከተው መንገድ መሆን እንደአለበት የተቀመጠ ሲሆን ይህ ድንጋጌ የመቃወሚያ አቤቱታ አቀራረብ በክስ አመሰራረት አይነት ሁኖ የማስረጃ ዝርዝር ሁሉ ይህንኑ ስርዓት ማሟላት እንደአለበት ያስገነዝባል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 መሰረት የሚቀርበው አቤቱታ ደግሞ ለፍርድ ማስፈጸሚያ እንዲሆን የተያዘ ወይም የተከበረ ንብረት የፍርድ ባለእዳው ንብረት አይደለም፣ የራሴ ንብረት ነው የሚል ወገን አቤቱታውን የሚያቀርብበትን አግባብ የሚደነግግ ድንጋጌ ነው፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት አቤቱታ አቅራቢ የሚሆን ወገን በሕጉ አግባብ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት አቤቱታውን ማቅረብ ያለበት ሲሆን ስርዓቱን ጠብቆ ያልቀረበን አቤቱታ ደግሞ ፍርድ ቤቱ ሊቀበል የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን በፍትሐብሔር ስነ ስርአት ስለ ክርክር አመራር የተመለከቱት ድንጋጌዎች የሚያሳዩን ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች አቤቱታውን ያቀረበው በዋናው ጉዳይ ላይ የተሰጠው ፍርድ መብትና ጥቅሜን ይነካል በሚል ሲሆን አቤቱታውን የስር ፍርድ ቤት ያስተናገደው ግን በፍርድ አፈጻጸም መዝገብ ላይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአመልካች የፍርድ ተቃውሞ አቀራረብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 ድንጋጌን መሰረት ያደረገ ሳይሆን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358ን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታ

በአፈጻጸም መዝገብ የሚቀበልበት ሥርዓት የሌለ ሲሆን አመልካች ባቀረበው አቤቱታ መሰረት በዋናው ጉዳይ የተሰጠውን ፍርድ በያዘው መዝገብ ላይ ማስተናገድ ነበረበት፡፡

ከክርክሩ ሂደት መረዳት እንደተቻለው አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ እንዳይከራከር በስር ፍርድ ቤቱ የተከለከለው በአፈጻጸም መዝገብ አቤቱታውን እንደአቀረበ ተቆጥሮ ከመሆኑም በላይ ተጠሪዎች ከፍርድ ባለእዳው ነው ከተባለው 4ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት ውል ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለውን ደንብ የሚጥስ አይደለም፣ ውሉ ሲመሰረትም አመልካች አልተመሰረተም፣ በዋናው ጉዳይ ላይ የተሰጠው ፍርድ በይግባኝም አልተለወጠም በሚል ነው፡፡ በእርግጥ እነዚህ ሁለት አካላት በአንድ መንግስታዊ መዋቅር (በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስተዳደር) ስር የሚገኙ አካላት ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በአንድ የክልል መንግሥታዊ መዋቅር ስር መገኘታቸው ብቻ አከራካሪውን የመሬት ይዞታ በተመለከተ ተመሣሣይ ጥቅምን የሚወክሉ አካላት ናቸው ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ አይደለም፤ እነዚህ ሁለት አካላት የክልሉ መስተዳድሩ የተለያዩ እርከኖች ወይም አካላት ሆነው የየራሳቸው ሕጋዊ ሰውነት፣ ስልጣንና ተግባር እንዳላቸው የሚታመን ነው፡፡ ይህ ነጥብ በስር ፍርድ ቤት ግንዛቤ ውስጥ ያልገባ ከመሆኑም በላይ አመልካች በክርክሩ ቀደም ብሎ ከቀረበው ክርክር አመልካቹ የተለየ ሌላ ክርክር ሊያቀርብ አይችልም የተባለውም ቢሆን ክርክራቸው ተመሣሣይና አንድ አይነት ጥቅም የሚወክል መሆኑና አለመሆኑ የሚታወቀው አመልካቹ አግባብነት ባለው የስነ ስርዓት ድንጋጌ ያቀረበው አቤቱታ ተገቢነት ካለው መዝገብ ጋር ታይቶ፣ ወደ ክርክሩ እንዲገባ ተደርጎ የሚያቀርበውን የክርክር አይነትና የሚወክለውን ጥቅም የአሁኑ 4ኛ ተጠሪ አቅርቦት ከነበረው ክርክር በማነፃፀር የሚታወቅ እንጂ አስቀድሞ ተመሣሣይ ክርክር አለው፣ ውሉ አግባብነት ያለውን ደንብ የሚጥስ አይደለም የሚል ግምት በመያዝ አይደለም፡፡

በመሰረቱ ከላይ እንደተጠቀሰው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት የሚቀርበው አቤቱታ በቁጥር 359 ስር በተመለከተው መንገድ መቅረብ ያለበት ነው፡፡ ድንጋጌው የአቤቱታው አቀራረብ የክስ አቀራረብ ሥርዓቱን ሊከተል እንደሚገባ የሚያሳይ ሲሆን እንዲህ ከሆነ ከሣሽ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 222 መሠረት አዘጋጅቶ ከሚያቀርበው የክስ ማመልከቻ ጋር በክሱ መሰማት ወቅት ለጉዳዩ ማስረጃ ይሆኑኛል የሚሏቸውን የሠውም ሆነ የጽሁፍ ማስረጃዎችን ዝርዝርና ዋናውን ወይም ትክክለኛ ግልባጮቻቸውን ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁ 223 ድንጋጌ የደነገገ ከመሆኑ ጋር ተጣምሮ ሲታይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት የሚቀርበው አቤቱታም ይህንኑ መከተል ያለበት መሆኑ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በተለይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 137/3/ የሠነድ ማስረጃዎችን በተመለከተ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን ከአቤቱታው ጋር በማያያዝ ወይም ከቀነ ቀጠሮ በፊት ወይም በመጀመሪያው ቀን ቀጠሮ ካልቀረበ በቀር ማስረጃው ሊቀርብ ወይም ይቅረብልኝ ተብሎ ሊጠየቅ እንደማይችል ተመልክቷል፡፡ ይሄው ጥያቄ ተቀባይነት የሚያገኘው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 256 ስር በተመለከተው አኳኋን ማስረጃዎቹ ሣያቀርቡት የቀሩት ከባድና በቂ በሆነ ምክንያት መሆኑን ፍ/ቤቱ ሲረዳ ብቻ ነው፡፡ የማስረጃ አቀራረብን በተመለከተ በሥነ ሥርዓት ህጉ የተመለከተው ሌላው ደንብ የይግባኝ ሠሚውን ፍ/ቤት ሥልጣን የሚመለከት ነው በዚህም መሠረት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 345 ድንጋጌ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በራሱ አስተያየት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ማናቸውም ዓይነት ሠነድ ወይም ምስክር ወይም ሌላ ዓይነት ማስረጃ በተጨማሪነት እንዲቀርብለት የማዘዝ ህጋዊ ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ ያሣያል፡፡ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145(1) ድንጋጌም በሌላ ፍ/ቤት የሚገኝ ሠነድ የፅሁፍ ማስረጃ ወይም ፍርድ የተሠጠበት መዝገብ

ለውሣኔው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፍ/ቤቱ በራሡ አነሣሽነትም ሆነ በተከራካሪዎቹ ጠያቂነት እንዲቀርብለት ማዘዝ የሚችል ስለመሆኑ ያስረዳል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው አመልካች በዋናው ጉዳይ ላይ በተሰጠው ፍርድ ላይ ያቀረበው ተቃውሞ ያላግባብ በአፈጻጸም መዝገብ ላይ ተያይዞ ጉዳዩ ከመታየቱም በላይ ዋናውን ፍርድ ለመቃወምና ለማሻር የሚያስችላቸውን ማስረጃዎች ዘርዝሮ ከማቅረቡም በተጨማሪ በፍርድ ቤቱ እገዛ መሰረት የሚቀርብለት ማስረጃ መኖሩንም ጠቅሶ እያለ ይህ ማስረጃ ሳይታይለት አቤቱታው ውድቅ መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልፅ ያሳያል፡፡ እንዲህ ከሆነ በአመልካች የተጠቀሡው ማስረጃ ሳይቀርብ በዋናው ጉዳይ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በአመልካች መብት ወይም ጥቅም ላይ የሚያስከትለው ችግር የለውም ወደሚለው ድምዳሜ ሊያደርስ አይችልም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ተቃውሞ አግባብነት ባለው መዝገብ ሳይቀበልና ተገቢ ማስረጃዎችን ሁሉ ሳይመለከት ውድቅ በማድረግ መወሰኑ የክርክሩን አመራር ከላይ በተመለከቱት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ የተቃውሞ አቀራረብና የማስረጃ አቀራረብ ደንቦች መሠረት አለመምራቱንና፣ በውጤቱም አመልካች በሕጉ የተጣለውን ኃላፊነትና ተግባሩን እንዳይወጣ የሚያደርግ በመሆኑ ውሳኔው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ ትእዛዝ የሠጡት አመልካች አቤቱታ ባላቀረበበት ሥርዓትና አቤቱታው ሊቀርብ በማይችልበት መዝገብ ከመሆኑም በላይ የአመልካች አቤቱታ የተስተናገደው የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓት ድንጋጌዎች በማይደግፉት፣ የፍርድ አካሄዱ ባልተሟላ ሁኔታ በመሆኑ በእየርከኑ ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሠጠው ትዕዛዞች ሙሉ በሙሉ ሊሻሩ የሚገባና የአመልካች አቤቱታ በዋናው የፍርድ መዝገብ ላይ ቀርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሠጥ ማድረጉ አግባብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የቡሌ ሆራ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 05757 የካቲት 09 ቀን 2002 ዓ.ም የሠጠው ትዕዛዝ የቦረና ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 5196 መጋቢት 16 ቀን 2002 ዓ.ም የሠጠው ትእዛዝ እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 103608 ሚያዝያ 14 ቀን 2002 ዓ.ም የሠጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የአቀረበው አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት የሚስተናገድ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 04136 በሆነው ላይ የአመልካችን አቤቱታ በመቀበልና ለተጠሪዎች እንዲደርስ በማድረግ እንዲሁም አመልካች በሕጉ አግባብ ሊቀርቡልኝ ይገባል በማለት የዘረዘራቸውን ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎችን ሁሉ በማስቀረብ፣ በጉዳዩ ላይ ቀድሞ የተሰጠው ውሳኔ የሚሻር መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 65930

14/10/2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች ፡-** የሱ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ አቶ ግሩም አየለ ቀረቡ

**ተጠሪ ፡-** 1- አቶ ደጀኔ በቀለ - ቀረቡ

2- አቶ አሸናፊ አብርሃም አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የአሁን ተጠሪዎች በሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከሣሾች የነበሩ ሲሆን አመልካች ደግሞ ተከሣሽ ነበር፡፡ ክሱም በተከሣሽ ድርጅት ተቀጥሬን እየሠራን ተከሣሽ ያለአግባብ የሥራ ውላችን እንዲቋረጥ ያደረገ ስለሆነ በህጉ መሠረት የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍለን ይወሰንበት የሚል ነው፡፡

ተከሣሽም ለክሱ በሰጠው መልስ ከሣሾች በምርት ማምረቻ ማሽን ከመጠን በላይ ነዳጅ በመጨመርና ማሽኑ በፍጥነት እንዲሠራ በማድረጋቸው ሙቀት ጨምሮ የማሽኑ ኩሽኔታ ከመቃጠሉም በላይ በሰርኩሌሽን ዴስክ ብልሽት ደርሶ በቀጣይ ፈረቃ ማሽኑ የቆመ በመሆኑ በተከሣሽ ድርጅት ላይ ባደረሱት ጉዳት የተነሣ ከሥራቸው እንዲሠናበቱ ተደርገዋል ብሏል፡፡

የሥር የፌ/የ/መደ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ በሰጠው ፍርድ ከሣሾች በአሠሪው ንብረት ላይ በከባድ ቸልተኝነት ጉዳት እንዲደርስ ያደረጉ በመሆናቸው ውሉ እንዲቋረጥ የተደረገው በህጋዊ መንገድ ነው ብሏል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የመረመረው የሥር የፌ/ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ ማሽኑ የተበላሸው ይግባኝ ባዮች /የሥር ከሣሾች / ለቀጣዩ ፈረቃ ተረኞች በ2፡00 አስረክበው ማሽኑም ሥራውን እያከወነ ቆይቶ 5፡30 ሲሆን የቆመ በመሆኑ እንዲሁም የማሽኑን ሁኔታ የሚቆጣጠር ኮምፕዩተር ተበላሽቶ ስለነበር ጉዳቱ የደረሰው በይግባኝ ባዮች ነው ለማለት አይቻልም ሲል ይግባኝ ባዮች ወደ ሥራቸው እንዲመለሡና መልስ ሰጪ /የአሁኑ አመልካች/ የ6 ወር ደመወዛቸውንም እንዲከፍል ፈርዷል፡፡

በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ፍርድ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን በዋናነት የጠቀሳቸው የቅሬታ ነጥቦችም፡-



www.chilot.me

- ተጠዎች በአመልካች ንብረት ላይ ብር 2,000,000 የሚገመት ጉዳት በማድረሣቸው ምክንያት የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከሥራ የተሠናበቱት በህጋዊ መንገድ ነው ሲል የወሰነውን ከፍተኛው ፍ/ቤት መሻሩ፣
- በልዩ ባለሙያዎች /Experts/ የተሰጠውን የምስክርነት ቃል ከፍተኛው ፍ/ቤት ከሙያው ወጪ ውድቅ ማድረጉ፣
- ከፍተኛው ፍ/ቤት ለተጠሪዎች ካሣ ብቻ ይከፈላቸው ማለት ሲገባው ወደ ሥራ ይመለሡ ማለቱ ያለአግባብ ነው የሚሉ ናቸው፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሰጡት መልስ የአመልካችና የተጠሪዎች ምስክሮች ተመሣሣይ ሥራ ያላቸውና በጊዜው ሥራ ላይ ሆነው ሁኔታውን የተመለከቱ እንጂ ለሙያዊ ምስክርነት ያስፈልጋሉ ተብለው የተጠሩ አይደሉም፡፡ ለቀጣዩ ፈረቃ ማሽኑን አስረክበን ከሄድን ከ5፡00 ቆይታ በኂላ ለደረሰው ጉዳት ተጠሪዎች ተጠያቂዎች አይደለንም በማለት የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ የተገለፀ ሲሆን እኛም በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የነበረው የሥራ ውል የተቋረጠው በህጋዊ መንገድ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ይዘን የግራ ቀኙን ክርክር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የአመልካች ማሽን በደረሰበት ጉዳት መቆሙን ተጠሪዎችም የሚያምኑት ጉዳይ ሲሆን ዋናውና አከራካሪ የሆነው ጉዳይ ግን በማሽኑ ላይ ጉዳት የደረሰው በተጠሪዎች ፈረቃ ነው? ወይስ ተጠሪዎች ለቀጣዩ ፈረቃ ሠራተኞች አስረክበው ከወጡ በኂላ ነው? የሚለው ነው፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ አመልካች ተጠሪዎች በፈረቃቸው ወቅት ያለአግባብ ነዳጅ በመጨመርና ማሽኑም ከሚገባው በላይ ፍጥነት እንዲጨምር በማድረጋቸው በተፈጠረ ሙቀት የተነሣ በተለያዩ የማሽኑ ክፍሎች ጉዳት ደርሷል የሚል ሲሆን ጉዳቱ ግን የታወቀው ከኮምኘዩተር በተገኘው መረጃ መሠረት ሆኖ በቀጣይ ፈረቃ የሚሠሩ ሠራተኞች ሥራ ላይ ባሉበት ጊዜ ነው ብሏል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው ማሽኑ በራሳቸው ፈረቃ አለመበላሸቱንና ብልሽቱም የደረሰው በቀጣዩ ፈረቃ በመሆኑ ለደረሰው ጉዳት ሃላፊነት የለብንም ሲሉ ይከራከራሉ፡፡

የሥር የፌ/የ/መደ/ፍ/ቤትም ከግራ ቀኙ የቀረበውን የፍሬ ነገር ክርክር ለማጣራት ማስረጃዎችን የሰማ ሲሆን በአመልካች በኩል የቀረቡት ልዩ ዕውቀት ያላቸው /Experts / ምስክሮች ሲሆኑ በተጠሪዎች በኩል የቀረቡት ምስክሮች ደግሞ ልዩ አዋቂዎች ያልሆኑ በቀጣዩ ፈረቃ ሲሠሩ የነበሩ የማሽኑ ኦፐሬተሮች ናቸው፡፡

ልዩ አዋቂዎች የሚባሉት በትምህርት ፣ በሥልጠና እና በልምድ ዕውቀት ያካበቱ ሰዎች ሲሆኑ እነዚህን ሰዎች ፍ/ቤቱ በሚጠራበት ጊዜ በተፈለገው ጉዳይ አግባብ የሆነ ዕውቀት ያላቸው ስለመሆኑ ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ይህም ሲባል የኤክስፐርት ምስክርነት ለምሳሌ በኢንጅነሪንግ /engineering/ የሚያስፈልግ ከሆነ መጣራት ያለበት በዚሁ በኢንጅነሪንግ ሙያ ዕውቀት ያለው ሰው መሆን ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም በአርክቴክቸር /architecture/ ቴክኒዮሎጂ /technology / እና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ የልዩ አዋቂዎች ምስክርነት አስፈላጊነት በፍ/ቤቱ ሲታመን ወይም ተከራካራዎቹ ቀርበው እንዲሰሙ በጠየቁ ጊዜና ፍ/ቤቱም የልዩ አዋቂዎች ምስክርነት ጉዳዩን ለማብራራት ወይም ለክርክሩ ውሣኔ አሰጣጥ ተገቢ ነው ካለ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን ልዩ አዋቂዎች ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ይህ ከዚህ በላይ የተገፀው ሁኔታ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 136/1/ ሥር የተደነገገ ሲሆን የምስክርነት ቃላቸውን የሚሰጡ ልዩ አዋቂዎችም የሚሰጡት የምስክርነት ቃል በገለልተኝነት የሚሰጥ መሆን ይኖርበታል፡፡ በዚህ በተያዘውም ጉዳይ የአሁኑ አመልካች ባቀረባቸው የልዩ አዋቂ ምስክሮች ገለልተኝነት /impartiality of experts/ ከተጠሪዎች በኩል የቀረበ ክርክር የሌለ ሲሆን በአንድ የፍትሃብሄር ጉዳይ ልዩ አዋቂዎች/Experts / እና ልዩ አዋቂዎች ያልሆኑ ምስክሮች ቀርበው በተሰሙ ጊዜ " In the civil context … lay evidence should not be preferred to expert evidence with out good reason " የሚለውን የማስረጃ ምዘና መርህ መከተል ይገባል፡፡

ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው የማስረጃ ምዘና መርህ መገንዘብ የሚቻለው ዳኞች በልዩ አዋቂዎች የተሰጠውን ምስክርነት ተቀባይነት የለውም በማለት ሊወስኑ የሚችሉት ይህንኑ የልዩ አዋቂዎችን ምስክርነት ተቀባይነት ሊያሳጣ የሚችል በቂ ምክንያት መኖሩ ከተረጋገጠ ብቻ ነው፡፡ የልዩ አዋቂዎችን ምስክርነት ተቀባይነት ለማሳጣት በቂ ምክንያት ከሌለ ግን ልዩ አዋቂ ያልሆኑ ምስክሮች ከሰጡት ምስክርነት ይልቅ በልዩ አዋቂዎች የተሰጡት ምስክርነት ተመራጭነት ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል ልዩ አዋቂዎች ከሰጡት ምስክርነት ልዩ አዋቂ ያልሆኑ ምስክሮች የሰጡት ምስክርነት አሳማኝ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ የልዩ አዋቂዎችን የምስክርነት ቃል ውድቅ በማድረግ ልዩ አዋቂዎች ያልሆኑት ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል ዳኞች እንዳይቀበሉ የሚከለክላቸው የህግ መርህ የለም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የአመልካች የልዩ አዋቂ /Experts / ምስክሮች ስለብልሽቱ የቴክኒዮሎጂ ውጤት የሆነውን ኮምፒዩተር በማንበብ በሙቀት መጨመርና ከመጠን በላይ በሆነ ፍጥነት ማሽኑ እንዲሠራ በመደረጉ የተነሣ ብልሽት የደረሰበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ይህን አግባብ ባለው ባለሙያ የተሰጠውን ምስክርነት ውድቅ ለማድረግ ምንም በቂ ሁኔታ ባልተገኘበት የሥር ከፍተኛው ፍ/ቤት ውድቅ በማድረግ ለጉዳዩ ይግባኝ ባዮች /ያሁን ተጠሪዎች/ ሀላፊት የለባቸውም ያለውና የሥራ ስንብቱም የተደረገው በህገወጥ መንገድ በመሆኑ የ6 ወር ደመወዝ ተከፍሎአቸው ተጠሪዎች ወደ ሥራቸው ይመለሱ በሚል የወሰነው መሠረታዊ የሆነ የማስረጃ ምዘና መርህን ያልተከተለ ስለሆነ ውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የሥር የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 93713 በቀን 26/04/2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 62045 በቀን 11/8/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የነበረው ውል የተቋረጠው በህጋዊ መንገድ ነው ተብሏል፡፡
4. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡
5. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ ይሁን፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 59953

ሰኔ 02 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች:- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** :- ወ/ሮ ዓለምነሽ አበበ-

**ተጠሪ** :- አቶ ተስፋዬ ገሠሠ-

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ፍቺን ተከትሎ የተነሳውን የባልና ሚስት የንብረት ክፍፍል ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች በተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የክሱ ይዘትም ባጭሩ:-ከተጠሪ ጋር ከ1970 ዓ/ም ጀምሮ አብረው እንደባልና ሚስት ከኖሩ በኂላ ታህሳስ 25 ቀን 1977 ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የፈጸሙት ጋብቻ ከሚያዚያ 18 ቀን 1994 ዓ/ም በፍቺ መፍረሱን፣በጋራ የሠሩትን ቤት ቁጥር 398ሀ1 የሆነን ቤት እንዲከፋፈሉ አመልካች ተጠሪን ጠይቀው ተጠሪ ፈቃደኛ ካለመሆናቸውም በላይ ከ1989 ዓ/ም እስከ 1992 ዓ/ም በወር ብር ከ800.00(ስምንት መቶ ብር)፣ከ1992 እስከ 1997 ዓ/ም ብር 900.00፣ከ1997 ዓ/ም ጀምሮ በአመት ብር 20,000.00 ተጠሪ ቤቱን እያከራዩ ገቢውን ለአመልካች ሊከፍሏቸው ያልቻሉ መሆኑን ገልፀው በቤቱ ኪራይ የሚገኘውን ገቢ እንዲያካፍሏቸውና ቤቱን በስምምነት ሽጠው ለመከፋፈል ፈቃደኛ ካልሆኑ በሐራጅ ተሽጦ እንዲከፋፈሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት በማንሳት የተከራከሩት ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ ያገኘ ነው በሚል ነው፡፡ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በተጠሪ በኩል በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበውን መቃወሚያ በጭብጥነት ይዞ ጉዳዩን በመመርመር ጉዳዩ ውሳኔ ያረፈበት ጉዳይ በመሆኑ ድጋሚ ክስ ሊቀርብበት የማይገባ ነው በማለትና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 እና 244(2(ለ)) ድንጋጌዎችን በዋቢነት በመጥቀስ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ ሙሉ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በአሜሪካን አገር የሚገኝ ፍርድ ቤት በግልፅ ዳኝነት የሰጠበት ስለሆነ ዳግመኛ ዳኝነት መጠየቅ አይቻልም በማለት መዝገቡ የተዘጋው የተሰጠው ዳኝነት ኢትዮጵያ ያላችሁንም የማይንቀሳቀስ ንብረት ያጠቃልላል የማይል ሁኖ እያለ በተሳሳት ትርጉም ፍርድ አርፎበታል መባሉ



www.chilot.me

ያላግባብ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርመሮም አመልካች በኢትዮጵያ የሚገኘውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመካፈል ያቀረቡት አቤቱታ ዳግመኛ የተጠየቀ ዳኝነት ነው በማለት ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም የአሜሪካን አገር የሚገኘው ፍርድ ቤት በሁሉም የጋብቻ ውጤቶች ላይ ውሳኔ ያሳረፈ መሆኑን ጠቅሰው በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግብብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማዛመድ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የፍቺ ውሳኔም ሆነ የንብረት ውሳኔ የተሰጠው በአሜሪካ ሀገር ሜሪላንድ እስቴት ሞንትጎመሪ ካውንት ፍርድ ቤት በቤተሰብ ሕግ ቁጥር 21746 በሆነ በ25/08/94 ገቢ የሆነበት ማስረጃ መኖሩን፣ይህ ማስረጃ ግራ ቀኙ ንብረታቸውን በጋራ እርካታ ላይ በተመሰረተ ሁኔታ እንደተከፋፈሉና በማንኛውም ወገን የንብረት ባለመብትነት ይገባኛል ጥያቄ ለዳኝነት እንዳይቀርብ የታዘዘ ስለመሆኑ እንደሚያሳይ፣ከዚህ በተጨማሪ ባለጉዳዮቹ የገንዘብ ነክ ፍርድን በጋራ በራሳቸው ፈቃድ እንደተው መታዘዙን እንደሚገልፅ የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ መግለፁን፣በውጪ አገር የተሰጠ ውሳኔም በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ትክክለኛነቱ ተረጋግጦ የቀረበ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ማረጋገጡን ነው፡፡እንግዲህ የስር ፍርድ ቤት የውጪ አገር ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ ጋብቻቸውንም ሆነ የንብረትና የገንዘብ ክርክራቸውን በአሜሪካን አገር ፍርድ ቤት በስምምነት ቀርበው ውሳኔ ያሰጡ መሆኑን በመገንዘብ የአመልካችን ጥያቄ ዳግመኛ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው በማለት ውሳኔ መስጠቱን  የውሳኔው ግልባጭ የሚያሳይ ነው፡፡

በመሠረቱ የፍትሐብሔር የክርክር አመራር ሥርዓት ዓይነተኛ ዓላማ የክርክርን ሂደት ለማቀላጠፍና አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ መቋጫ ለማበጀት መሆኑ ይታመናል፡፡ የፍትሐብሔርን ክርክር አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ እልባት እንዲደረግበት በማቀድ ከተደነገጉት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ጽንሰ ሐሣቦች አንድ የመጨሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች /Res judicata/ የሚለው ሲሆን ይህ ጽንሰ ሀሣብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 5  ስር በግልጽ ተቀምጧል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሠረት የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች ማለት በማናቸውም መልክ በሕግ በተቋቋመ ፍ/ቤት ቀርበው የመጨረሻ ውጤት የገኙ ጉዳዮችን የሚሸፍን መሆናቸውንና በፍርድ፣ በብይን፣በውሣኔ፣በትእዛዝ፣ወይም በጊዜያዊ አገልግሎት ባለው ትእዛዝ የመጨረሻ ውጤት አግኝተው በሌላ መልክ ለመንቀሣቀስ የማይችሉ የክርክር ነጥቦችን ሁሉ የሚያጠቃልል ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 ስር በተመለከተው አኳኋን አንድ ጉዳይ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት መረጋገጥ ካለባቸው ሁኔታዎች ውስጥ ቀደም ሲል ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የነበሩ ጉዳዮች በድጋሚ በቀረበው ክስም ላይ በቀጥታ በፍሬ ነገር ጭብጥ ሆነው መቅረባቸው፣ቀደም ሲል የነበረውን ክርክር አሁን በክርክር ተሣታፊ በሆኑ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወይም ተላልፎላቸው በነበረ ወገኖች መሆኑንና እነዚህ ጉዳዮች ቀደም ሲል በተካሄደው ሙግት የመጨረሻ ፍርድ ያረፈባቸው መሆኑን ነው፡፡

ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ በመጨረሻ ፍርድ መቃወሚያነት ሲቀርብ ተቀባይነት የሚኖረው ይኸው ጉዳይ በድጋሚ በቀረበው ክርክር ላይ መቅረቡ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የሚለው ሐረግ አጠቃላይ ይዘቱ ሲታይም በመጀመሪያው ክርክር ላይ በአንደኛው ወገን ተጠይቆ በሌላኛው ወገን የተካደ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የታመነና በዚሁ ላይ የፍርድ ውሣኔ ያረፈበት የክርክር ነጥብ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም በመሆኑም በድጋሚ በቀረበው ክስ በቀድሞው ክርክር ተሣታፊ በነበሩ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወገኖች የሚካሄድ መሆኑና በሁለተኛው ክስም የተያዘው የፍሬ ነገር ጭብጥ ከመጀመሪያው ጋር ተመሣሣይ ሆኖ የመጨረሻ ፍርድ ያረፈበት መሆኑ ከተረጋገጠ እንዲሁም ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ አርፎበታል የሚል ተቃውሞ በተከራካሪ ወገን ከተነሣ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 እና 244(2) ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች አሻሽለው በ08/03/2001 ዓ.ም ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ጋብቻው መፍረሱን ገልጸው በኢትዮጵያ ውስጥ ያለና በጋራ የሠሩትን ቤት ቁጥር 398ሀ1 የሆነን ቤትና በቤቱ የተገኙትን ፍሬዎች እንዲከፋፈሉ አመልካች ተጠሪን ጠይቀው ተጠሪ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል በሚል ምክንያት ነው፡፡ በአሜሪካን አገር ተሰጠ የተባለው ውሳኔ ግራ ቀኙ ንብረታቸውን በጋራ እርካታ ላይ በተመሰረተ ሁኔታ እንደተከፋፈሉና በማንኛውም ወገን የንብረት ባለመብትነት ይገባኛል ጥያቄ ለዳኝነት እንዳይቀርብ የታዘዘ ስለመሆኑ እንደሚያሳይ፣ከዚህ በተጨማሪ ባለጉዳዮቹ የገንዘብ ነክ ፍርድን በጋራ በራሳቸው ፈቃድ እንዲተው መታዘዙን እንደሚገልፅ የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ በግልጽ አስፍሮታል፡፡ ይሁን እንጂ የውጪ አገሩ ፍርድ ኢትዮጵያ ውሥጥ ያለውን ንብረት እንደተከፋፈሉ ወይም በራሳቸው ፈቃድ እንደተው የሚያሳይ አይደለም፡፡ ከላይ እንደተገለፀው አንድ ጉዳይ የመጨረሻ ፍርድ ተሰጥቶበታል የሚባለው በመጀመሪያው ክርክር ላይ በአንደኛው ወገን ተጠይቆ በሌላኛው ወገን የተካደ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የታመነና በዚሁ ላይ የፍርድ ውሣኔ ያረፈበት የክርክር ነጥብ ሲሆን ነው፡፡በመሆኑም አንድ ጉዳይ በፍርድ አልቋል የሚለው ተቃውሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 እና 244(2) ድንጋጌዎች መሰረት ተቀባይነት የሚኖረው በሕጉ የተመለከቱት መመዘኛዎች መሟላታቸው በቅድሚያ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ ግን ግራ ቀኙ በጋብቻ ጊዜ ኢትዩጵያ ውስጥ ያለውን ንብረት በተመለከተ በውጪ አገር ባለ ፍርድ ቤት ውሳኔ ያገኙ ስለመሆኑና ይህም ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ከቁጥር 456 እስከ 461 የተደነገጉት ድንጋጌዎች በሚያሳዩት መልኩ በኢትዩጵያ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነትን ሊያገኝ የሚችልበትን ሁኔታ በግልፅ መሟላቱ ሳይረጋገጥ የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው በማለት የአመልካችን ዳኝነት ውድቅ ማድረጋቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 118249 መጋቢት 17 ቀን 2002 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 92036 ነሐሴ 11 ቀን 2002 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘውን የማይንቀሳቀስ ንብረትና ፍሬውን ለመካፈል ያቀረቡት አቤቱታ ዳግመኛ የተጠየቀ ዳኝነት አይደለም ብለናል፡፡



www.chilot.me

3. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 118249 የቀረበውን ክርክር ቀጥሎ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1)መሰረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 57360

ሐምሌ 15 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ/ማ - ሜሮን ሰሎሞን ቀረበች

**ተጠሪ**፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ዮናስ ለሜሳ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የማቅረቢያው ጊዜ ያለፈበት ይግባኝ ይከፈት ዘንድ እንዲፈቀድ የቀረበውን ጥያቄ መነሻ ያደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ የማስፈቀጃ ጥያቄው የቀረበው ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሲሆን፣ ጥያቄ አቅራቢው የአሁኑ ተጠሪ ነበር፡፡ የይግባኝ ማቅረቢያው ጊዜ ሊያልፍበት የቻለው ወይም ይግባኙን በሥነ ሥርዓት ሕጉ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ሊያቀርብ ያልቻለው ጉዳዩን ይዞ ሲከታተል በነበረው ነገረ ፈጁ ስህተት /ጥፋት/ እንደሆነም በማመልከቻው ላይ ገልጾአል፡፡ ፍ/ቤቱም ይህን መነሻ በማድረግ የአሁን አመልካች መልስ ሰጪ ን አስቀርቦ ክርክሩን ከሰማ በኋላ ጊዜው ያለፈው በነገረ ፈጁ ጥፋት ነው፡፡ ነገረ ፈጁም በዚህ ምክንያት የዲሲፕሊን እርምጃ ተወስዶበታል የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት የተጠሪን ጥያቄ ተቀብሎአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሰኔ 17 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገው የይግባኝ ማስፈቀጃው ጥያቄ በበቂ ምክንያት የተደገፈ ነው በሚል በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 326/2/ ከተቀመጠው ድንጋጌ ጋር ተገናዝቦ ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡

በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ተጠሪ የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ያቀረበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 323/2/ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ይግባኙን ባለማቅረቡ ከፍ/ቤቱ ፈቃድ ለማግኘት ነው፡፡ ጊዜ ካለፈ በኋላ ይግባኝ እንዲከፈት ጥያቄ የሚቀርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 325 በተደነገገው መሠረት ሲሆን፣ ጥያቄው ተቀባይነት ያለው ስለመሆን አለመሆኑ የሚመረመረው /የሚመዘነው/ ደግሞ

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 326 መሠረት ነው፡፡ ጥያቄው ተቀባይነት አለው ወይንስ የለውም? የሚለው ነጥብ ሊወሰን የሚገባው እንደየአግባቡ በንኡስ ቁ/1/ ወይም /2/ መሠረት እንደሆነም ግልፅ ነው በንዑስ ቁ /1/ እንደተመለከተው አመልካቹ ወይም የፈቃድ ጥያቄ አቅራቢው ይግባኙን በጊዜው ለማቅረብ ያልቻለው በበቂ ምክንያት መሆኑ ፍ/ቤቱን ማሣመን ከቻለ ይግባኙን በአሥር ቀናት ውስጥ እንዲያቀርብ ይፈቀድለታል፡፡ በዚህ ረገድ ምክንያቱ በቂ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ፍሬ ነገር በፍ/ቤቱ የሚመዘን ከመሆን አልፎ በሕጉ የተቀመጠ የታወቀ /የተለየ/ መስፈርት የለም፡፡ በንዑስ ቁ./2/ የተቀመጠው ድንጋጌ ግን አመልካቹ ያቀረበው ምክንያት በንኡስ ቁ./1/ አባባል ሊስተናገድ የማይገባ ወይም ተቀባይነት የሌለው ነው የሚባልበትን አግባብ የሚያመለክት ነው፡፡ በፈቃድ መጠየቂያው ማመልከቻ ላይ የተገለፀው ምክንያት ይግባኙን በጊዜው ማቅረብ ያልቻለው በአመልካቹ ጠበቃ ወይም ነገረ ፈጁ ወይም በወኪሉ ያለመቅረብ እና በእነዚሁ ጉድለቶች መሆኑን የሚያመለክት ከሆነ ምክንያቱ በንኡስ ቁ./1/ እንደተነገረው በቂ ነው ሊባል እንደማይገባ ድንጋጌው በግልጽ ያመለክታል፡፡ በዚህ ምክንያትም የይግባኝ ይከፈትልኝ ጥያቄው ተቀባይነት ለማግኘት አይችልም በማለት ግልጽ ድንጋጌ ሕጉ አስቀምጦአል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ ይግባኙን በጊዜው ያላቀረበው በነገረፈጅ ጉድለት ምክንያት እንደሆነ በፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻው አረጋግጦአል፡፡ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኙ እንዲከፈት የፈቀደው ነገረ - ፈጁ ሥራውን በታማኝነት እና በተገቢ የሥራና የሙያ ሥነ ምግባር አልፈፀሙም የሚል ምክንያት በመስጠት እንደሆነ ከውሣኔው ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በእኛ እምነት ሕጉ ግልጽ ነው፡፡ የነገረፈጁን ወይም የጠበቃውን ወይም የወኪሉን በታማኝነት ሥራውን አለመሥራት ወይም አለመሥራት እንደመስፈርት ተወስዶ በሕጉ አልተቀመጠም፡፡ ለምዘና የሚቀርብ ፍሬ ነገርም አይደለም፡፡ ይህ ሁኔታ በአመልካቹ /የይግባኝ ማስፈቀጃ ጥያቄ አቅራቢው/ እና በነገረፈጁ በጠበቃው ወይም በወኪሉ መካከል ለሚነሣ የኃላፊነት ክርክር አወሳሰን አግባብነት ይኖረው እንደሆነ ነው እንጂ ይግባኙ ይከፈትልን በሚለው ወገን እና በተቃራኒው ይግባኙ ሊከፈት አይገባም በሚለው ተከራካሪ ወገን መካከል የሚነሣ አይደለም፡፡

ፍ/ቤቶችም የቀረበላቸውን ጉዳይ መወሰን ያለባቸው በሕጉ መሠረት እንደሆነ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ግልጽ የሆነውን ሕግ በመተላለፍ የሚሰጠው ውሣኔ የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ ውሣኔው ከሕጉ አተረጓጎም /አተገባበር/ አንፃር ሲታይ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው የሚሆነው፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ በዚህ መሠረትም ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 54164 ግንቦት 11 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. ተጠሪ ያቀረበው የይግባኝ ይከፈት ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 326/2/ እንደተደነገገው ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 62173

ሐምሌ 11 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች ፡-** ወ/ሪት ቤቴልሔም ታደሰ - ጠበቃ ዳንኤል ግርማ ቀረቡ

**ተጠሪ ፡-** 1. ወ/ሮ ሐና ታደሰ - የቀረበ የለም

2. አቶ ተስፋዬ አበበ - የቀረበ የለም

3. አቶ ተስፋዬ ጎይቴ - ከጠበቃ መላኩ ወ/ማርያም ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አንድ ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 መሰረት የመጨረሻ ፍርድ ያገኘ ጉዳይ ነው ሊባል የሚችልበትን የሥነ ሥርዓት ሕግ አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው አመልካች ነሀሴ 11 ቀን 2001 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካች በክሳቸው ላይ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 07 ክልል ውስጥ የሚገኝና የቤት ቁጥሩ 261 የሆነውን ፣ የአመልካች ድርሻም ጭምር ያለበትን መኖሪያ ቤት ለአሁኑ 3ኛ ተጠሪ ነሀሴ 12 ቀን 1998 ዓ/ም በተደረገ የቤት ሽያጭ ውል የሸጡት መሆኑን ፣ ይህ የሽያጭ ውል አመልካችን የሚጎዳና ሕገወጥ መሆኑን ጠቅሰው ውሉ እንዲፈርስላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መልስም ውሉ መደረጉን ሳይክዱ የሕጉን ፎርማሊቲን ያልጠበቀና ረቂቅ በመሆኑ ቢፈርስ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን የገለፁ ሲሆን የአሁኑ 3ኛ ተጠሪ በበኩላቸው በጉዳዩ ላይ 1ኛ ተጠሪ ባሁኑ 3ኛ ተጠሪ ላይ የውል ይፈረስልኝ ጥያቄ አቅርበው አመልካች የጣልቃ ልግባ ጥያቄ ሲያቀርቡ ፍርድ ቤቱ ውድቅ ያደረገባቸው መሆኑንና ውሉም ሊፈርስ አይገባም ተብሎ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ጭምር የፀና መሆኑን ጠቅሰው ጉዳዩ ዳግም ክስ ሊቀርብበት አይገባም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ አመልካች ያቀረቡት የውል ይፍረስልኝ ክስ ቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ በመሆኑ ዳግም ክስ ሊቀርብበት የሚገባው አይደለም በማለት የአመልካችን ክስ ዘግቶታል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ልግባ

የሚለውን ጥያቄ አቅርበው አቤቱታቸው ውድቅ የሆነው 1ኛ ተጠሪ ከ3ኛ ተጠሪ ክስ በመሰረቱበት ጊዜ የጠየቁት ዳኝነት አመልካች ጣልቃ ልግባ በማለት ከጠየቁት ጋር የተለየ ምክንያት ያለው በመሆኑ ሊስተናገድ አይገባም ተብሎ ሲሆን አመልካች በሌላ መንገድ መብታቸውን ከማስከበርም የማያግዳቸው መሆኑ ተገልፆ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12928 ብይን ሰጥቶ እያለ ከዚሁ ብይን ውጪ በሆነ መንገድ ጉዳዩ ቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የስር ፍርድ ቤት የአመልካች ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 መሰረት ውድቅ ነው በማለት የሰጠው ብይን በመ/ቁጥር 12928 ከሰጠው ብይን አንፃር ሲታይ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም በስር ፍርድ ቤት ከሰጡት መልስ ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለው መልስ አቅርበዋል ፣ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሯል፡፡

በመሠረቱ የፍትሐብሔር የክርክር አመራር ሥርዓት ዓይነተኛ ዓላማ የክርክርን ሂደት ለማቀላጠፍና አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ መቋጫ ለማበጀት መሆኑ ይታመናል፡፡ የፍትሐብሔርን ክርክር አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ እልባት እንዲደረግበት በማቀድ ከተደነገጉት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ጽንሰ ሐሣቦች አንዱ የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች /Res judicata/ የሚለው ሲሆን ይህ ጽንሰ ሀሣብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 5 ስራ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች ማለት በማናቸውም መልክ በሕግ በተቋቋመ ፍ/ቤት ቀርበው የመጨረሻ ውጤት ያገኙ ጉዳዮችን የሚሸፍን መሆናቸውንና በፍርድ፣ በብይን ፣ በውሣኔ ፣ በትእዛዝ ፣ ወይም በጊዜያዊ አገልግሎት ባለው ትእዛዝ የመጨረሻ ውጤት አግኝተው በሌላ መልክ ለመንቀሣቀስ የማይችሉ የክርክር ነጥቦችን ሁሉ የሚያጠቃልል ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 ስር በተመለከተው አኳኋን አንድ ጉዳይ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት መረጋገጥ ካለባቸው ሁኔታዎች ውስጥ ቀደም ሲል ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የነበሩ ጉዳዮች በድጋሚ በቀረበው ክስም ላይ በቀጥታ በፍሬ ነገር ጭብጥ ሆነው መቅረባቸው ፣ ቀደም ሲል የነበረውን ክርክር አሁን በክርክር ተሣታፊ በሆኑ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወይም ተላልፎላቸው በነበረ ወገኖች መሆኑንና እነዚህ ጉዳዮች ቀደም ሲል በተካሄደው ሙግት የመጨረሻ ፍርድ ያረፈባቸው መሆኑን ነው፡፡

ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ በመጨረሻ ፍርድ መቃወሚያነት ሲቀርብ ተቀባይነት የሚኖረው ይኸው ጉዳይ በድጋሚ በቀረበው ክርክር ላይ መቅረቡ ሲረጋገጥ ነው ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የሚለው ሐረግ አጠቃላይ ይዘቱ ሲታይም በመጀመሪያው ክርክር ላይ በአንደኛው ወገን ተጠይቆ በሌላኛው ወገን የተካደ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የታመነና በዚሁ ላይ የፍርድ ውሣኔ ያረፈበት የክርክር ነጥብ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም በመሆኑም በድጋሚ በቀረበው ክስ በቀድሞው ክርክር ተሣታፊ በነበሩ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወገኖች የሚካሄድ መሆኑና በሁለተኛው ክስም የተያዘው የፍሬ ነገር ጭብጥ ከመጀመሪያው ጋር ተመሣሣይ ሆኖ የመጨረሻ ፍርድ ያረፈበት መሆኑ ከተረጋገጠ እንዲሁም ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ አርፎበታል የሚል ተቃውሞ በተከራካሪ ወገን ከተነሣ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 እና 244(2) ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በ11/12/2001 ዓ.ም ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ድርሻቸው ባለው መኖሪያ ቤት ላይ የተደረገው የሽያጭ ውል የሚጎዳቸውና ሕገ ወጥ መሆኑን ጠቅሰው ውሉ እንዲፈርስላቸው ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን እህታቸው የሆኑት የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ባሁኑ 3ኛ ተጠሪ ላይ በመሰረቱት የውል ይፈረስልኝ ክርክር ስርዓቱን ጠብቀው የጣልቃ ልግባ አቤቱታ አቅርበው የስር ፍርድ ቤት የአመልካች ጥያቄና የ1ኛ ተጠሪ ጥያቄ የተለያዩ ምክንያቶችን መሰረት ያደረገ ነው በሚል ምክንያት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎ አመልካች በተናጠል መብቷን ማስከበር እንደሚችሉ ገልጾ አመልካችን ስለማሰናበቱ የስር ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 12928 በግልጽ ያሳያል፡፡ ከዚህ በሁዋላ አመልካች የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ በተናጠል ሲያቀርቡ ደግሞ 1ኛ ተጠሪ በ3ኛ ተጠሪ ላይ የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ አቅርበው ተቀባይነት እንዳጡ ፣ የአመልካች ጥያቄም ተመሳሳይ እንደሆነና በ1ኛ ተጠሪ በቀረበው አቤቱታም የክርክሩ ተሳታፊ ሁነው ተቀባይነት እንዳጡ ተገልፆ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 መሰረት መዝገባቸው ተዘግቶባቸዋል፡፡ ከዚህ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መገንዘብ የሚቻለው የስር ፍርድ ቤት አመልካች በ1ኛ ተጠሪ በቀረበው ክስ የክርክሩ ተሳታፊ ነበሩ ከማለት በስተቀር በመ/ቁጥር 12928 የተሰጠው ብይን ይዘቱ ምን እንደነበር በግልፅ ያልመዘገበውና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ጋር አዛምዶ ያልተመለከተው መሆኑን ነው፡፡ አመልካች የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ በሥርዓቱ መሰረት አቅርበው የስር ፍርድ ቤት በተናጠል ሊያቀርቡ የሚገባውና 1ኛ ተጠሪ ካቀረቡት ምክንያት የተለየ ምክንያት ያለው ነው በማለት ብይን የሠጠበት ጉዳይ ቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በዚህ ችሎት እምነት አመልካችና 1ኛ ተጠሪ የቤት ሽያጭ ውል እንዲፈረስ የጠየቁት የተለያዩ ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ ነው ቢባልም የውል ይፍረስልኝ ጥያቄው ውጤት ግን አመልካችና 1ኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ አለን የሚሉትን መብት መጠበቅ በመሆኑ አመልካች ትክክለኛውን መድረክና ስርዓት በመምረጥ የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ በጣልቃ ገብነት አቅርበዋል ፣ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በያዘው መዝገብ አስተናግዶ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት ነበረበት፡፡ ፍርድ ቤት በፈጠረው ስህተት ተከራካሪ ወገን ተቀጪ የሚሆንበትና በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 መሰረት የተከበረለትን ፍትህ የማግኘት መብት የሚጣበበት አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ራሱ በመ/ቁጥር 12928 የሰጠውን ብይን ይዘት ባግባቡ ሳይመረምር የአመልካችን ጥያቄ ይዘት ከ1ኛ ተጠሪ ጥያቄ ይዘት ጋር መመሳሰሉን ብቻ በመመልከት የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 መሰረት መዝጋቱ መሰረታዊ የሆነ የሥነ ሥርዓት ሕግ ግድፈት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 15316 የካቲት 29 ቀን 2002 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 92343 ነሐሴ 24 ቀን 2002 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 15316 በሆነው ክርክሩን ቀጥሎ የግራ ቀኙን ፍሬ ነገር ክርክርና ማስረጃ በመስማት በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡



www.chilot.me

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ሃ/ዲ                                        የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ. 63699

15/11/2003

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አፔኖ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ድርጅት ጠበቃ አቶ በረከት ቡሽራ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ጥሩነህ ይመር አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ተጠሪ ለሥር የጋምቤላ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በተከሣሽ ድርጅት /በአሁኑ አመልካች ድርጅት/ በዘበኝነት ተቀጥሬ እየሠራሁ የቆየሁ ቢሆንም በህመም ምክንያት ሥራዬን ያቆምኩ ስለሆነ ተከሣሽ አንዳንድ ያልከፈላቸውን ክፍያዎች እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ ብለዋል፡፡

ተከሣሽ ድርጅት በበኩሉ በሰጠው መልስ ከሣሽ በድርጅቱ ከታህሣሥ ወር 2001 እስከ ጥቅምት 2002 ለአሥራ አንድ ወራት በጥበቃ ሥራ ከቆዩ በኂላ በራሣቸው ፈቃድ ከተከሣሽ ድርጅት የተሰናበቱ ሲሆን በሰጡት አገልግሎት መሠረት የስንብት ክፍያ የተከፈላቸው በመሆኑ ሌሎች የሚከፈላቸው ክፍያዎች የሉም በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር የከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቱም በሰጠው ፍርድ ተከሣሽ የስንብት ክፍያ ለከሣሽ መክፈሉን በማረጋገጥ ሌሎች ክፍያዎችን በሚመለከት ግን ከሣሽ በግልጽና በዝርዝር ያልጠየቁና በማስረጃ አስደግፈው ያላቀረቡ በመሆናቸው ሊከፈላቸው አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የጋምቤላ ከተማ ዙሪያ ፍ/ቤት በበኩሉ በሰጠው ውሣኔ ይግባኝ ባይ በመልስ ሰጪ ድርጅት ለአንድ ዓመት የሠሩ መሆናቸው ስለተረጋገጠ መከፈል ያለባቸው ክፍያዎች ማለትም የትርፍ ሰዓት ክፍያ የዓመት ዕረፍትና የበዓላት ቀን ክፍያ የተከፈላቸው ስለመሆኑ በማስረጃ ስላልተረጋገጠ መልስ ሰጪ ሊከፍላቸው ይገባል ብሏል፡፡

በከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ያለው ያሁን አመልካችም ለዚህ ችሎት ባቀረበው አቤቱታ ተጠሪ በደፈናው አንዳንድ ያልተከፈሉኝ ጥቅማ ጥቅሞችን አመልካች እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለታቸው ብቻ የትርፍ ሰዓት የዓመት ዕረፍት እና የበዓላት ቀን ክፍያ በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈላቸው መወሰኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ስለ ክስ አቀራረብ

የተደነገጉትን መርሆዎችንና ስለማስረጃ አቀራረብ ሥርዓትን መሠረት ያላደረገ ስለሆነ ውሣኔው ሊሻር ይገባል ብሏል፡፡

ተጠሪው ለሰበር አቤቱታ መልስ ለመስጠት ባለመፈለጋቸው መብታቸው የታለፈ ሲሆን እኛም የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ለተጠሪው የትርፍ ሰዓት ክፍያ፣ እንዲሁም የዓመት ዕረፍትና የበዓላት ቀናት የሠሩባቸው ታስቦ በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈላቸው መወሰኑ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የሥራ ክርክር የፍትሐብሔር ባሕሪ ስላለው ክርክሩ መመራት ያለበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ መሠረት መሆን ይኖርበታል፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 222 በክስ ጽሑፍ ላይ ስለሚሠፍሩ ነገሮች የተደነገገ ሲሆን በዚሁ በተጠቀሰው የሕግ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር /1/ በፊደል /ረ/ አንድ ክስ ለክሱ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች መያዝ እንዳለበት ተገልጿል፡፡ ከዚህ ሌላም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 80/1/ እንደተጠቀሰው ከሣሽ የሚጠይቀውን ሁሉ ዘርዝሮ በክሱ ወይም በአቤቱታው ማቅረብ እንደሚኖርበት በማያሻማ ሁኔታ ተጠቅሷል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን ተጠሪው ያልተከፈሉኝን ክፍያዎች አመልካች ይክፈሉኝ ከሚል ውጪ መክፈል ያለበትን ክፍያዎች በሕጉ መሠረት በዝርዝር ግለጽ አድርገው አላቀቡም፡፡ በግልጽ በዝርዝር ባልቀረበ ጉዳይ ደግሞ ሌላኛው ወገን እንዲከራከርበት ማድረግ የተጠቀሱትን የፍትሐብሔር ሥነ ሥ/ሕ/ድንጋጌዎች መጣስ ይሆናል፡፡

ግለጽነት የጎደው ክስ ወይም አቤቱታ በቀረበ ጊዜ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 91/1/ እንደተጠቀሰው ፍርድ ከመስጠቱ በፊት ከተከራካሪ ወገኖች በሚቀርበው ጥያቄ ወይም ፍ/ቤቱ በራሱ አነሣሽነት ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት አስፈላጊ መሆኑን ከተረዳ ክሱ ወይም አቤቱታው እንዲሻሻል ለማዘዝ ይችላል፡፡ ሆኖም በዚህ በያዝነው ጉዳይ በዚህ መልኩ ክሱ እንዲሻሻል አልተደረገም፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ ተጠሪው እንዲከፈላቸው የሚጠይቁት የዓመት ዕረፍት፣ የበዓላት ቀን እና የትርፍ ሰዓት ክፍያዎች ለየትኛው ጊዜ እንደሆኑ ተለይተው ባልቀረቡበት እንዲሁም በእነዚህ ጊዜያት ተጠሪው የትርፍ ሰዓት ሥራ እና በበዓላት ቀናት የሠሩ ስለመሆናቸው፣ የዓመት ዕረፍት ያልተጠቀሙበት መኖር አለመኖሩ ማረጋገጫ ባለቀረበበት አመልካች እነዚሁኑ ክፍያዎች እንዲከፍሉ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት መወሰኑ በፍትሐብሔር ሥ/ሥ ስለ ክስ አቀራረብ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ባልተከተለ ሁኔታ ከመሆኑም ሌላ ተጠሪው ክሱን በማስረጃ ሣያስረዱ የተወሰነ በመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የሥር የጋምቤላ ከተማና ዙሪያ ከፍተኛ ፍ/ቤት በቀን 10/2/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የሥር የጋምቤላ ከተማ አስተዳደር የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03436 በቀን 28/10/2002 የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. አመልካች ለተጠሪ የዓመት ዕረፍት፣ የበዓላት ቀናት፣ ትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያዎችን በገንዘብ ተለውጦ ሊከፍላቸው አይገባም ብለናል፡፡
4. አመልካች የዚህን ፍ/ቤት ወጪ የራሱን ይቻል፡፡
5. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

ሃ/ዲ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 61227

ሐምሌ 14 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ነገረ ፈጅ ክበሩ ደበበ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪዎች፡-** 1. አቶ ኃይሉ አምቦ
2. ወ/ሮ እታገኝ ወርቁ } አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ቀባንክ ብድር ጋር ተያያዥነት ያለው ክርክር ሲሆን የተጀመረው በደቡብ ብሔ/ብ/ሕ/ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁኑ አመልካች ከሳሽነት ነው፡፡ ቀርቦ የነበረው ክስ 1ኛው ተከሣሽ በተደረገው የብድር ውል የእህል ንግድ ለመሥራት ብር 30,000 የተበደረና 2ኛ ተከሳሽም የ1ኛ ተከሳሽ ባለቤትና ውሉ እንዲፈቅድ ስምምነታቸውን ገልፀዋል፣ ለዋስትናም በሚዛን ተፈሪ ከተማ ያለው የመጋዘን ቤትና የመኖሪያ ቤት ባንኩ በመረከብ ከዕዳቸው ላይ ቀንሷል፣ ይሄም ሆኖ በውሉ መሠረት ዋና ገንዘብ ብር 8,112.49 እና ወለድ 6,433.37 በድምሩ ብር 14,545.86 የሚፈለግባቸው በመሆኑ የቀረበ ክስ ነው፡፡ ተከሣሾች በሰጡት መልስ ከሳሽ በዕዳው ምክንያት ንብረቱን የተረከበ በመሆኑ የቀረውን ዕዳም ከፍሎ ለመጨረስ ጊዜ ይሰጠን በማለት የመለሱ በመሆኑና በቃል ክርክር ወቅት ከሳሽ ንብረቶችን በእጅ ካስገባ በኋላ ተከሣሾች ኃላፊነት መውሰድ የለብንም የሚል ክርክር ያነሱና በወቅቱ በባንክ ነገረፈጅ ቀርቦ የነበረው ክርክር ንብረቱን የተረከብን ቢሆንም ወደ ገንዘብ ተሽጦ ያልተለወጠ በመሆኑ የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱ ከላይ እንደተመለከተው ከክርክሩ በኋላ ከሳሽ ከላይ የተመለከቱትን መጋዘንና መኖሪያ ቤት ብረከብም ወደ ገንዘብ አልተለወጠም በማለት የተነሳው ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት ሐምሌ 09/1994 ዓ.ም ከተረከቡበት ጊዜ ጀምሮ በግምቱ መጠን ያለባቸው ሆኖ ተቀናሽ መሆን ይገባዋል በማለት የንብረቶቹ ግምት በአጠቃላይ ብር 41,209 ነው በማለት አመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ በማያያዝ ከሳሽ ንብረቱን እስከተረከበበት ጊዜ ድረስ በተከሣሾች ላይ ያለው ዕዳ ብር 41 /አርባ አንድ/ ብቻ በመሆኑ ውሣኔውን እስከሰጠበት ድረስ ያለውን ወለድ በማስላት ወይም በማሰብ ብር 85.28 /ሰማኒያ አምስት ብር ከሃያ ስምንት ሣንቲም/ ብቻ ይቀራል በማለት ወስኗል፡፡



www.chilot.me

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ አፅንቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን የአመልካች ነገረ ፈጅ ጥቅምት 08 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የቅሬታ ፍሬ ሃሣብ ባንኩ በመያዣ የያዛቸውን ንብረቶች በአዋጅ ቁ. 97/90 እና አዋጅ 216/92 መሠረት የተረከባቸውንና የተረከበበትን የንብረት ግምትም ከዕዳው ላይ በማቀናነስ ቀሪውን ዕዳ ለመጠየቅ የቀረበ ክስ ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ ከጭብጡ በመውጣት የሂሣብ ስሌት ውስጥ በመግባት የወሰነው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተሽሮ በክሳችን መሠረት እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች በቀን 02-5-2003 ዓ.ም የሰጡት 2 ገፅ የመልስ ፍሬ ሃሣብ አመልካች መጋዘን እና መኖሪያ ቤቱን ከተረከበ በኋላ ሰባት ዓመት ቆይቶ ንብረቶቹንም እያከራዩ ሲጠቀሙ ቆይተው በተሳሳተ ስሌት ቀሪ ዕዳ አለባችሁ በማለት ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ እንዲፀና በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ ቀርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም ከግራ ቀኙ የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደተመረመረውም ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤት ተገቢውን ማጣራት ካደረገ በኋላ የተሰጠ ውሣኔ ነው? ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ ተይዞ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ አኳያ የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከተው በመጀመሪያ ደረጃ ለዕዳው መክፈያ በአንደኛ ደረጃ ዋስትና የተያዙት መጋዘን ቤት እና መኖሪያ ቤት ባንኩ የተረከበው አጠቃላይ ግምታቸው ብር 41,209 ስለመሆኑ እና ሐምሌ 9/1994 ዓ.ም ባንኩ የተረከባቸው መሆኑ አላከራከረም፡፡ አመልካቹ ንብረቶቹን ከተረከበበት ቀን ጀምሮ በንብረቱ ግምት መጠን ዕዳውን ተቀናሽ ማድረግ ሲገባው ንብረቱን ብንረከብም ተሸጦ ወደ ገንዘብ የተለወጠ ባለመሆኑ ሊቀነስ አይገባም በማለት በከፍተኛው ፍርድ ቤት በቃል ክርክር ወቅት የተነሣውን ነጥብ በተመለከተ በዚህም ችሎት ለማጣራት የአመልካች ነገረ ፈጅ ተጠይቀው በወቅቱ የቀረበው የአመልካች ተወካይ የፈፀሙት የክርክር ስህተት እንጂ ባንኩ ንብረቱን ሲረከብ በግምቱ መጠን ዕዳውን የሚቀንስ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም በወቅቱ በከፍተኛው ፍርድ ቤት በቃል ክርክር ወቅት በአመልካች ነገረ ፈጅ በኩል ተነስቶ የነበረውን ክርክር ፍርድ ቤቱ ውድቅ በማድረግ ባንኩ ንብረቶቹን በዕዳው ምክንያት ከተረከበበት ቀን ጀምሮ በግምቱ መጠን ዕዳው የሚቀነስ መሆኑን የወሰነ በመሆኑ በዚህ ነጥብ ላይ ተጠሪዎች ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

በመሆኑም በዚህ ጉዳይ ላይ አከራካሪው ነጥብ አመልካቹ ለዋስትና የተያዙትን መጋዘንና መኖሪያ ቤት በተረከበበት ሐምሌ 09 ቀን 1994 ዓ.ም ወቅት በተጠሪዎች ላይ የነበረው ዕዳ ስንት የነበረ ስለመሆኑ፣ በወቅቱ የነበረው ዕዳ አመልካች ንብረቱን ሲረከብ የንብረቶቹ ግምት መጠን ከተጠሪዎች ዕዳ ላይ ሲቀናነስ ምን ያህል ዕዳ የሚቀርባቸው ስለመሆኑ እና አመልካች /ባንኩ/ ንብረቶቹን ከተረከበ በኋላ በግራ ቀኙ መካከል በነበረው ውል መሠረት የቀረው ዕዳ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ያለው ስሌት ስንት ይሆናል የሚሉት ነጥቦች እንደሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ይሄንን በተመለከተ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በዋስትና የተያዙትን ንብረቶች ስረከብ የነበረው ዕዳ ተቀናንሶ ብር 41 ብቻ በተጠሪዎች ላይ እንደሚቀር ይሄው ዕዳ ውሣኔ እስኪሰጥበት ቀን ድረስ በቀሪው ዕዳ ላይ ወለድ ታስቦ ብር 85.28 ብቻ እንደሚቀርባቸው ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ ወደ ዕዳው ስሌት ሊገባ የቻለው በግራ ቀኙ መካከል በነበረው ክርክር በኃላፊነት መጠን ስሌት ላይ ክርክር በመፈጠሩ ምክንያት መሆኑ ከክርክሩ አጠቃላይ ሂደት



www.chilot.me

መገንዘብ ይቻላል፡፡ የዕዳው ሒሳብ ስሌትን በተመለከተ አጠራጣሪ ሁኔታ ከተፈጠረ ዳኞች በራሳቸው የሂሣብ ስሌቱን ለመሥራት ሳያስፈልግ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 136 /1/ /2/ መሠረት ልዩ አዋቂ /ኤክስፐርት/ በመመደብ እንዲሰሩት ማድረግ እንደሚቻል ያመለክታል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ያለመፈፀማቸው አሁን እየተነሣ ላለው የስሌት ስህተት አለ የሚለውን ሊያስቀር የሚችል ነው፡፡ በዚህ መሠረት ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤት የዕዳውን ስሌት መሥራቱ አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነ ከላይ በተመለከተው በልዩ አዋቂ ማሰራት ሲገባው ፍርድ ቤቱ በራሱ ስሌት የደረሰበት መደምደሚያ መሠረታዊ የክርክር ማጣራት ሂደትን ከላይ እንደተመለከተው የተከተለ ባለመሆኑ እና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይሄንን ሳያጣራ ማለፉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የደቡብ ብሔ/ብ/ሕ/ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ. 32725 በቀን 14-12-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ. 07373 በቀን 28-12-2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከላይ በፍርድ ሐተታው በተመለከተው መሠረት በተጠሪዎች ላይ የቀረውን ዕዳ በልዩ አዋቂ /ኤክስፐርት/ እንዲጣራ ካደረገ በኋላ ተገቢ የሆነውን ውሣኔ እንዲሰጥ በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 343 /1/ መሠረት መልሰናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 61637

ሐምሌ 11 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- ዶ/ር አልሑሴን በድልገዋድ - ጠበቃ 1. በሻዳ ገመቹ ቀረቡ፡

2. ጥላሁን ምትኩ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ**፡- 1. ወ/ሮ ገነት ሐድጎ
2. አቶ ታደሰ ጥላሁን- } ጠበቃ ንዋይ ዘርጌ ዓይናለም /ዶ/ር/ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ፍርድ ቤት እግድ የሠጠበት የማይንቀሳቀስ ንብረት እግዱ ተጥሶ ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት በተደረገ ሽያጭ ውል ለሶስተኛ ወገን ንብረቱ ተላልፎ ሲገኝ ያለውን ውጤት የሚመለከት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻና ይዘትም የሚከተለው ነው፡፡ አመልካች አቶ ጥበቡ እሸቴ በተባሉት ግለሰብ ላይ ብር 1,598,470.00 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ አራት መቶ ሰባ ብር) ለማስከፈል በኮ/መ/ቁጥር 56345 በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሰኔ 05 ቀን 1999 ክስ መስርተው የፍርድ ባለመብት መሆናቸውን አረጋግጠው እንደ ፍርዱ እንዲፈፀምላቸው የአፈጻጸም ማመልከቻ ለፍርድ ቤቱ አቅርበው አሁን ለክርክሩ መሰረት በሆነው ቤት ላይ ሐራጅ ወጥቶ አፈጻጸሙ እንዲቀጥል ባቀረቡት ማመልከቻ መሰረት ፍርድ ቤቱ እግድ ተሰጥቶበት የነበረ መሆኑን ተገንዝቦ የሐራጅ ማስታወቂያውን አውጥቶ አፈጻጸሙን በመምራት እንዳለ የአሁኑ ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 መሰረት የተቃውሞ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች የተቃውሞ ምክንያት የሆነው ነገር ለአፈጻጸሙ መሰረት የሆነውና በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 ክልል ውስጥ የሚገኘው ቁጥሩ 274 የሆነውን መኖሪያ ቤት በሕግ አግባብ በተደረገ የሽያጭ ውል ከአቶ ጥበቡ እሸቴ የገዙትና ስመ ሀብቱንም ወደራሳቸው ያዞሩት መሆኑን የሚገልፅ ሁኖ አፈጻፀሙ በንብረታቸው ላይ ሊቀጥል አይገባም የሚል ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ በቀረበው የተጠሪዎች አቤቱታ ላይ አመልካች መልስ እንዲሰጡበት አድርጓል፡፡ አመልካች በሰጡት መልስም ዋናውን ክስ በአቶ ጥበቡ እሸቴ ላይ ሲመሰርቱ ክሱ ለቀረበለት ፍርድ ቤት ባቀረቡት የእግድ አቤቱታ መሰረት ሰኔ 06 ቀን 1999 ዓ/ም በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 ክልል ውስጥ ቁጥሩ 274 የሆነ መኖሪያ ቤት በግለሰቡ ስም የሚታወቅ መሆኑ ተጣርቶ በማናቸውም መንገድ ለሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ በማለት ያዘዘ ሲሆን ይኸው የእግድ

ትዕዛዝ ለቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ደርሶት በቤቱ ማህደር መያያዙንና ይህ የእግድ ትዕዛዝ በሕግ አግባብ ያልተነሳ መሆኑን ዘርዝረው እግዱ በተጭበረበረ መንገድ ተነስቷል ተብሎ በተገለፀበት ሁኔታና ጊዜ የተከናወነው የሽያጭ ውል ሕጋዊ ባለመሆኑ የተጠሪዎች ተቃውሞ ተቀባይነት የለውም፣ አፈጻጸሙ በቤቱ ላይ መቀጠል አለበት በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ በዚህ መልክ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በአከራካሪው ቤት የፍርድ ቤት እግድ መተላለፉ የተረጋገጠ ቢሆንም በሕግ አግባብ ሳይነሳ እንደተነሳ ተደርጎ ትእዛዝ ተላልፎ እግዱ ተነስቷል ተብሎ በተገለጸበት ሁኔታና ጊዜ የሽያጭ ውሉ በውልና ማስረጃ ፅ/ቤት ተደርጎ ስመ ሀብቱ ሁሉ ወደ ተጠሪዎች መዛወሩን፣ እግዱ በመጣሱ ተጠያቂ ሊሆን የሚችለው ደግሞ እግዱን የጣሰው ወገን እንጂ ገዥ ሊሆን እንደማይገባ ዘርዝሮና የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 156፣ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1566 እና የአዋጅ ቀጥር 334/95 አንቀጽ 15(2) እና 27(1) ድንጋጌዎችን በዋቢነት በመጥቀስ ቤቱ በሐራጅ ሊሸጥ አይገባም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ታህሳስ 07 ቀን 2003 ዓ.ም ተሻሽሎ በተፃፈ አምስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት አመልካች በሕግ አግባብ አስከብረው የነበረና በሕግ አግባብ እግዱ ሳይነሳ በተጭበረበረ መንገድ የተነሳ መሆኑ በግልጽ ተረጋግጦ እያለ ሽያጩ ቀሪ ሊሆን አይገባም፣ እግዱን የጣሰው ወገን እንጂ ገዥ ተጠቂያነት የለበትም ተብሎ መወሰኑ የእግድን ዓላማና ውጤቱን ያላገናዘበና ሕጋዊነት የሌለው ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሐራጅ እንዲሸጥ የተባለው ቤት ለሁለተኛ ተጠሪ በግዥ ተላልፏል ተብሎ ሐራጁ እንዲቋረጥ የስር ፍርድ ቤቶች የመወሰናቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጐ ተጠሪዎች ጥር 17 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ሦስት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የመልሳቸው ይዘትም ባጭሩ፡- ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ሽያጩ የተከናወነው እግዱ የተነሳ መሆኑ በተረጋገጠበትና በውልና ማስረጃ በተደረገ የሽያጭ ውል ሁኖ ስመ - ሐብቱም ለገዥው የዞረ በመሆኑ ሽያጩ ሕጋዊ አይደለም ሊባል የሚችልበት ምክንያት ስለሌለ የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች ጠበቃም በተጠሪዎች መልስ ላይ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይህ ችሎትም የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን የመራበትን መዝገብ ቁጥር 67884ን አስቀርቦ የክርክሩን ሂደት ተመልክቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በአቶ ጥበቡ እሸቴ ላይ የገንዘብ ይከፈለኝ ክስ ሰኔ 05 ቀን 1999 ዓ.ም መስርተው አሁን እያከራከረ ያለው እና ሌላ ቤት ሰኔ 06 ቀን 1999 ዓ/ም በፍርድ ቤት ትእዛዝ እንዲከበር ያደረጉ መሆኑን፣ ይህ የእግድ ትዕዛዝም ለሚመለከታቸው አካላት መተላለፉ የተረጋገጠ ቢሆንም እግዱ መነሳቱን ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ስለማስተላለፉ ያሳያል የተባለ ማስረጃ በመኖሩ ምክንያት ውልና ማስረጃ ፅ/ቤት በተደረገው የሽያጭ ውል መጋቢት 10 ቀን 2001 ዓ/ም አከራካሪው ቤት ለተጠሪዎች መተላለፉን፣ ከዚህም በኋላ ተጠሪዎች የስመ ሃብቱን ወደ

ራሳቸው አዙረው እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮች መሆናቸውን ነው፡፡ የአመልካች ክርክር መሰረቱም የፍርድ ቤት እግድ ያለበትን ቤት በተጭበረበረ መንገድ እግዱ ተነስቷል ተብሎና እግዱ የተነሳው ከፍርድ ቤት ከወጣ ትዕዛዝ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ሽያጩ መከናወኑም ሆነ የቤቱን ስመ - ሃብት ገዢዎች ማዞራቸው ሽያጩን ሕጋዊ አያደርገውም በሚል ምክንያት ስለመሆኑም ተገንዝበናል፡፡ እኛም በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ከሕጉ ጋር በሚከተለው መልኩ በማዛመድ ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ በፍርድ ቤት የእግድ ትዕዛዝ የሚሰጠው በክርክሩ ሂደት ረቺ የሚሆነው ወገን ለፍርድ አፈጻጸም ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር እንዲያስችለው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 154 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መንፈስና ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ሲሆን የፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ደግሞ ሊከበር የሚገባ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ፍርድ ደግሞ ሊፈጸም የሚገባው በፍርድ ባለእዳውና በሕግ አግባብ እንዳይያዙ ከሚጠቀሱት ንብረቶች/መብቶች ውጪ ባሉት የፍርድ ባለእዳ ንብረቶች/መብቶች ስለመሆኑ በቁጥር 378 ተከታዮቹ በተመለከቱት የፍትሐ ብሔር ስነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ አንድ ሰው በሕግ አግባብ ለሌላ ሰው ሊያስተላለፍ የሚችለው መብትም በሕግ አግባብ ገደብ ያልተደረገበትንና ያለውን መሆኑ እሙን ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የስር የፍርድ ባለእዳ የሆኑት አቶ ጥበቡ አከራካሪውን ቤት የሸጡት በፍርድ ቤት የተላለፈው እግድ በፍርድ ቤቱ መነሳቱን አረጋገጠው ባይሆንም የፍርድ ቤቱ የእግድ ትዕዛዝ የተነሳ መሆኑን የሚያሳይና ከፍርድ ቤቱ የወጣ መሆኑን የሚገልፅ ማስረጃ በቤቱ ማህደር ተያይዞ በመገኘቱ ሲሆን እግዱን የጣሰው አካል ማን እንደሆነም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ አይደለም፡፡ የፍርድ ቤቱ እግድ የተነሳ መሆኑ ከተረጋገጠ በኂላ ሽያጩም ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት የተደረገ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ሽያጩ ሲከናወን አቶ ጥበቡ እሸቴ የአከራካሪው ቤት ባለሃብት ሲሆኑ በዚሁ ሰፊው መብታቸው ደግሞ በሕግ ያልተገደቡ መብቶቻቸውን መጠቀም የሚችሉ መሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1204፣1206፣1184 እና 1185 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ድንጋጌ መሰረት ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የምስክር ወረቀት ሲሰጥ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሰው የማይንቀሳቀሰው ንብረት ባለሃብት ሁኖ ሊቆጠር እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ከላይ የተገለጹትን ድንጋጌዎች ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ጋር አጣምረን ስንመለከት የባለሃብትነት የምስክር ወረቀት የያዘ ሰው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ስር የተመለከቱት ሁኔታዎች መኖራቸው እስካልተረጋገጡ እና ሌሎች ሕጋዊ ክልከላዎች እስከሌሉ ድረስ ሃብቱን በሕጉ አግባብ ከሸጠ ተግባሩ ሕገ ወጥ የሚባልበት ምክንያት የለውም፡፡ አንድ ሰው በሕግ ጥበቃ የተደረገለትን መብት በሕጋዊ መንገዶች ለሌላ ለማስተላለፍ መብት አለውና፡፡ በዚህ መንገድ መብቱ የተላለፈለት ሰውም በሕግ ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በቤቱ ላይ እግድ ማሰጠታቸው የተረጋገጠ ቢሆንም ከዚህ በሁዋላ ደግሞ እግዱ መነሳቱ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች እግዱ ከፍርድ ቤት በወጣ ትዕዛዝ የተነሳ አይደለም በማለት ከመከራከራቸው ውጪ ለእግዱ መጣስ ወይም የይነሳልኝ ጥያቄው የቀረበው ወይም እግዱ ስለመነሳቱ የሚገልጸው ደብዳቤ ጋር ተጠሪዎች ያላቸው ግንኙነት ስለመኖሩ ያቀረቡት ክርክርም ሆነ ማስረጃ አለመኖሩን የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳያል፡፡ ከሻጭ ጋር የመመሳጠር ሁኔታ ስለመኖሩ ያልተረጋገጠበትና የተለየ ግንኙነት የሌለው ሰው በቤቱ ላይ እግድ መነሳቱን የሚያሳይ ማስረጃ ከሚመለከተው የቤቱ ማህደር አይቶና ይህን ማስረጃ በመመልከት ንብረቱን ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት የሚገዛ ገዥ ሽያጩን ያከናወነው ከሕግ ውጪ ነው ሊባል የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በቤቱ ላይ ሕጋዊ መብት የሌለው ሰው

ሽያጩን አከናውኖ ሲገኝም ትክክለኛው ባለሃብት ሊጠይቅ የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጐ የገዛውን ገዥ ሊሆን አይገባም፡፡ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጎ በሕጋዊ ተግባር መብት ያገኘ ሰው ከራሱ እውቅና ውጪ ለተፈፀመ ሕገ ወጥ ተግባር ተጠያቂ ማድረግ የግብይት ሥርዓቱንም ጭምር ዋስትና የሚያሳጣው ይሆናል፡፡ ከሁሉም በላይ የፍርድ ቤት እግድ ተጥሶ ሲገኝ ኃላፊነት ሊወስድ የሚገባው የእግድ ትዕዛዙ እንዲጣስ ምክንያት የሆነ ተግባር የፈፀመ አካል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 156 ድንጋጌ ይዘት ያስገነዝባል፡፡ በውልና ማስረጃ ጽ/ቤትም በሕግ የባለቤትነት መብት ማረጋገጫ የሚሰጥባቸውን ንብረቶች ለማስተላለፍ የሚዘጋጁ ሰነዶች ከመዘጋጀታቸው በፊትም ሰነድ አረጋጋጩ ንብረቱ በመያዣነት ያልተሰጠ ወይም በፍርድ ቤት ያልታገደ መሆኑን ሊያረጋገጥ እንደሚገባ አዋጅ ቁጥር 334/95 አንቀጽ 15(2) ድንጋጌ በኃይለ ቃል አስቀምጦ እናገኛለን፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች አከራካሪውን ቤት የገዙት በሕግ ፊት ተቀባይነት ያለውን ማስረጃ ከያዙት ግለሰብ ሆኖ ሽያጩም የተከናወነው ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት ሲሆን በዚህ ጊዜም የፍርድ ቤቱ እግዱ ስለመነሳቱ የሚያረጋገጥ ማስረጃ ከቤቱ ማህደሩ ጋር በመገኘቱ በመሆኑ የአከራካሪው ቤት ሽያጭ ውል ቀሪ የሚሆንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ተጠሪዎች በቤቱ ላይ በሕግ አግባብ በተፈጸመ የሽያጭ ውል ያቋቋሙት የባለሃብትነት መብት ያላቸው መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን አመልካች ያላቸው መፍትሄ የእግዱን ትእዛዝ በጣሰው አካል ላይ ተገቢውን ጥያቄ በተገቢው አካል አቅርበው  የደረሰባቸው ጉዳት ካለ መብታቸውን ማስከበር እንጂ አፈጻጸሙ በአከራካሪው ቤት እንዲቀጥል ማስደረግ ሊሆን አይገባም፡፡ አመልካች በሰ/መ/ቁጥር 21270 እና 29269 የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ለጉዳዩ ተፈፃሚነት አለው በማለት ያቀረቡት ክርክርም በተጠቀሱት መዛግብት ላይ የተሰጠው የሕግ ትርጉም ከመያዣ ቀዳሚ መብት ጋር የተያየዘ በመሆኑና በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ ደግሞ በፍርድ ቤት የተሰጠ እግድ ከገዥው እውቅና ውጪ ተነስቷል ተብሎ ማረጋገጫ በመቅረቡ እግድ የተላለፈበት የማይንቀሳቀስ ንብረት በውልና ማስረጃ ፅ/ቤት በተደረገ የሽያጭ ውል ለሶስተኛ ወገን ተሸጦ ቢገኝ ውሉ በሕግ ስለሚኖረው ጥበቃ የሚመለከት በመሆኑ ከላይ የተጠቀሱት አስገዳጅ የሰበር ሰሚ ችሎት የሕግ ትርጉሞች ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው አይደሉም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካች ክርክር የምንቀበልበትን ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡

ሌላው የአመልካች ጠበቆች የሚከራከሩበት ነጥብ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአከራካሪው ቤት ላይ የተደረገው ሽያጭ ሕጋዊ የሚሆንበት አግባብ የለም፣ በማለት ሐራጁ እንዲቀጥል ትዕዛዝ ከሰጠ በሁዋላ ችሎቱ ላይ የነበሩት ዳኛ ሲለወጡ በሽያጭ ውሉ ላይ ክርክር ተደርጎ የቀድሞው ትዕዛዝ ተመሳሳይ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ችሎት ቀሪ እንዲሆን መደረጉ ሥነ ሥርዓቱን የተከተለ አይደለም በማለት ነው፡፡ እኛም ይህንኑ ክርክር መሰረት አድርገን የስር ፍርድ ቤትን መዝገብ አስቀርበን ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪዎች በአከራካሪው ቤት ላይ ሕጋዊ መብት አለን በማለት ወደ ክርክሩ የገቡትና በግራ ቀኙ መካከል ክርክር ተደርጎ የሽያጭ ውሉ ሕጋዊ ነው ተብሎ ውሳኔ የተሰጠው ሕዳር 11 ቀን 2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት እንጂ ከዚህ ቀን በፊት በነበረው የክርክር ሂደት አለመሆኑን አረጋግጠናል፡፡ አንድ ሰው በሕግ አግባብ የክርክሩ ተሳታፊ ባልሆነበት ሁኔታ የተሰጠ ብይን ይኸው ሰው መብት አለኝ በሚል ሥርዓቱን ጠብቆ ሲቀርብ ሌላ ወገን ተከራክሮ ተገቢ ትዕዛዝ ተሰጥቶበታል በሚል ምክንያት ብቻ በሌላ ወገን ላይ የተሰጠ ትእዛዝ ተፈጻሚነት ሊኖረው ይገባል የሚል ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ እንዲህ ከሆነ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ሁለት ጊዜ የተለያየ አቋም መያዙ ስነ ሥርዓቱን የተከተለ አይደለም በማለት የሚቀርበው ቅሬታ እውነትነትና ሕጋዊ መሰረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

በአጠቃላይ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ስለእግዱ መጣስ ተጠሪዎች ያደረጉት ድርጊት አለመኖሩንና የሽያጭ ውሉም እግዱ በተነሳበት ሁኔታና ጊዜ በተገቢው አካል ዘንድ የተከናወነ መሆኑን በማረጋገጥ የሠጡት ውሳኔ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 67884 ሕዳር 11 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 51156 መስከረም 24 ቀን 2003 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡፡

2. በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 ክልል ውስጥ የሚገኘው ቁጥሩ 274 የሆነውን መኖሪያ ቤት ላይ የተደረገው ሽያጭ ውል ሊፈረስ አይገባም፣ አፈጻጸሙ በቤቱ ላይ ሊቀጥል አይገባም ብለናል፡፡

3. አመልካች በእግዱ መጣስ ተግባር የደረሰባቸው ጉዳት ካለ የሚመለከተውን አካል በመክሰስ መብታቸውን ከማስከበር ይህ ውሣኔ አያስቀርም ብለናል፡፡

4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 54632

29/09/2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ራውዳ ሙሜ - ጠበቃ አበራ ማረኝ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አምባሳደር አብደላ አብዱራህማን - ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የባልና ሚስት ክርክር ሲሆን የተጀመረው በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ክስ ነው፡፡ ቀርቦ የነበረው ክስ በአጭሩ በመካከላችን የነበረው ጋብቻ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 64296 ሚያዝያ 30 ቀን 1998 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሣኔ ፈርሷል፡፡ የጋራ ንብረት ክፍፍልን በተመለከተ ተከሳሽ ካናዳ ቶሮንቶ ከተማ 4725 የቤት ቁጥር 1614 የሆነውን ኮንዶምኒየም ተከሳሽ እንዲወስዱና በአ/አበባ ን/ስል/ላ/ክ/ከተማ ቀበሌ 05 የቤት ቁጥር 1775 የሆነውን ደግሞ ከሣሽ እንድወስድ የሚል ሃሳብ አቅርቤ ተከሳሽ ከሣሽ ያልተሳተፍኩበትን በካናዳ ፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ በማቅረብ ለፍ/ቤቱ በማመልከታቸው በከፍተኛው ፍ/ቤት እንዲታይ የሚል ውሣኔ በመስጠቱና በይግባኝም በመጽናቱ የቀረበ ነው፡፡ የተባለው የካናዳ ፍ/ቤት ውሣኔ ከሳሽ በሌለበት የተሰጠ የጋራ ንብረቱን በሙሉ ለአንደኛ ወገን የሚሰጥና የካናዳን ሕገ መንግስት የሚፃረርና ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ከላይ ባቀረብኩት የክፍፍል ሃሳብ መሰረት እንዲወሰን በሚል ጠይቋል፡፡

ክሱ ለተከሳሽ ደርሶ በሰጡት መልስ የከሳሽና የተከሳሽ ጋብቻ ከመፍረሱም በላይ የካናዳ ፍ/ቤት ሰኔ 23 ቀን 1998 ዓ.ም በዋለው ችሎት በቀረበበት የንብረት ክርክር የካናዳውም ሆነ በአ/አበባ የሚገኘው ቤት ለተከሳሽ እንዲሰጥ የተባለ በመሆኑ አሁን የቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 5 መሠረት ተቀባይነት የለውም በማለት የካናዳ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ መሠረት አፈፃፀም የማቅረብ መብቴ ተጠብቆ የደረሰው ኪሣራ እንዲከፈለኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤት ከላይ እንደተመለከተው ከክርክር በኂላ የፍች ውጤት መታየት የሚገባው ጋብቻ በተመሰረተበት ሀገር ህግ በመሆኑ እና በካናዳ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ሁሉንም ንብረት ለአንድ ወገን ብቻ የተደረገ በመሆኑ በኢትዮጵያ ህገ መንግስት አንቀጽ 34 መሠረት ባልና ሚስት በፍች ውጤት ላይ ያላቸውን እኩል ህገ መንግስታዊ መብት የሚነካ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም



www.chilot.me

በማለት እኩል እንዲከፋፈሉ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርዱ ቤቱም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 337 መሠረት አጽንቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች በጠበቃቸው አማካኝነት መጋቢት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በ2 ገጽ በፃፉት ማመልከቻ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡ የቅሬታው ፍሬ ሃሳብ በዚህ ጉዳይ ቀድሞ በካናዳ ፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ እያለ በማለፍ የበታች ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ እንድሻርልን የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በጠበቃ በኩል ጥቅምት 29 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ 2 ገጽ መልስ በካናዳ ተሰጠ የተባለው ፍርድ ያልተከራከርኩበትና የአንደኛውን ተከራካሪ ወገን መብት የሚስጥ መሆኑን ፍ/ቤቱ በመገንዘብ ውድቅ ያደረገው በመሆኑ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ እንዲፀና በማለት ተከራክሯል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ክርክር አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም በግራ ቀኙ የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘበ መርምሮታል፡፡ በዚሁ መሠረት በግራ ቀኙ መካከል ያለው ጋብቻ በፍርድ ቤት ውሣኔ መፍረስ ተከትሎ ያለው የንብረት ክፍፍል ክስ ቀድሞ በፍርድ ያለቀ ጉዳይ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ተይዞ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ይሄንን ጉዳይ ስንመረምረው አመልካች ቀድሞ በፍርድ አልቋል የሚሉት በካናዳ ፍርድ ቤት ተሰጠ የተባለውና በኢትዮጵያም ሆነ በካናዳ የሚገኙትን መኖሪያ ቤቶች ለአመልካች ወስኗል የተባለውን ፍርድ ነው፡፡

አንድ የውጭ ሃገር ፍርድ ከአገራችን የፍትሐብሔር ስነ ሥርዓት እይታ አኳያ ሲታይ የክሱ መጀመር ወይም ከተወሰነ በኂላ ለአፈፃፀም ቢቀርቡ ያላቸው ተቀባይነት በተመለከተ አግባብነት ያላቸው የሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 8/2/ እና በውጭ አገር የተሰጠ ፍርድ ወይም ብይን ስለሚፈፀምበት ሁኔታ የሚደነግገው ከአንቀጽ 456 እስከ 461 ሥር የተደነገጉት ናቸው፡፡ የመጀመሪያውን አንቀጽ ማለትም አንቀጽ 8/2/ በምናይበት ጊዜ በውጭ አገር ክስ መጀመሩ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተቀብሎ ከመመልከት እንደማያግደው የሚያመለክት በመሆኑ በዚሁ እናልፈዋለን፡፡ ከላይ በሁለተኛ ደረጃ የተመለከቱትን የህግ ድንጋጌዎች በምናይበት ጊዜ አንድ የውጭ ሃገር ፍርድ የመጨረሻ ውሣኔ ተሰጥቶበት መቅረቡ ብቻ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ሊያስገኝለት የማይቻል ስለመሆኑና የተለያዩ መመዘኛዎችን ማሟላት እንዳለበት ይደነግጋሉ፡፡ የተመለከተው ፍርድ ደግሞ በሥነ ሥርዓት ሕጉ ላይ የተጠቀሱትን መመዘኛዎች ያሟላል ወይስ አያሟላም ማለት ደግሞ የሚቻለው የተሰጠው ፍርድ ይጠቅመኛል ወይም መብት ያጐናጽፈኛል ባይ የአፈፃፀም ማመልከቻ ከላይ በተጠቀሱት የሥነ ሥርዓት ሕጐች መሠረት ብታቀርብ ኖር እንጂ ለቀረበባቸው ክስ እንደመከራከሪያ በማቅረብ አይደለም፡፡

በመሆኑም በካናዳ ፍርድ ቤት ተሰጠ የተባለው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 456 እስከ 416 በተመለከተው አግባብ ተቀባይነቱ ለፍርድ ቤት ቀርቦ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካችም ይሄንን ባለፍፀሙበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 5 መሠረት የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ ጉዳይ ነው በማለት የቀረቡት መከራከሪያ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ከዚህ አኳያ የተነሳውን ተቃውሞ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለመሆነም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 51738 የካቲት 17 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 71195 ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ ያላቸውን የጋራ ንብረት በኢትዮጵያ የፌዴራል ቤተሰብ ህግ መሠረት እኩል ይካፈሉ መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በግራ ቀኙ ላይ በዚህ ችሎት ለደረሰው ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 43453

15/3/2002 ዓ.ም.

**ዳኞች** ፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሠ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች** ፡- አንበሳ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት ነ/ፈጅ ፋሲካ በለጠ

**ተጠሪ** ፡- 1. ወ/ሮ ዘነበወርቅ ከበደ } ጠበቃ ይፍሩ ወ/ጻዲቅ

2. አቶ ኢብራሂም አብዱጃቢር

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች በተጠሪዎችና በሥር 3ኛ ተከሣሽ ላይ በቀረበው ክስ የሠ.ቁ. 3-15306 የሆነውን የከተማ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ ንብረትነቱ የ1ኛ እና 2ኛ ተከሣሾች የሆነ መኪና በ3ኛ ተከሣሽ አማካይነት ሲሽከረከር በፈጸመው ጥፋት በከሣሽ አውቶቡስ ላይ ጉዳት ደርሷል፡፡ ከሣሽ አውቶቡሱን ብር 43,392.55 ወጭ አድርጎ ከማሰራቱም በላይ መኪናው ለጥገና በመቆሙ ብር 68,742.52 ከሣሽ ገቢ ሳያገኝ ቀርቷል፡፡ በመሆኑም ተከሣሾች ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ብር 112,149.67 ከነወለዱ እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ጠይቋል፡፡

2ኛ እና 3ኛ ተከሣሾች ቀርበው 1ኛ ተከሣሽ ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን ገልጸው አደጋው የደረሰው በ3ኛ ተከሣሽ ጥፋት ሳይሆን የከሣሽን መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ሾፌር በፈፀመው ጥፋት ስለሆነ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ የተጠየቀውም የካሳ መጠን የተጋነነ ነው በማለት መልስ ሠጥተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ 2ኛ እና 3ኛ ተከሣሾች /የአሁን ተጠሪዎች/ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አቅርበው አደጋው የደረሰው የከሣሽን መኪና ሲያሽከረክር በነበረው ሹፌር ጥፋት ስለሆነ የእኛ ንብረት በሆነው የሠ.ቁ. 1-01766 መኪና ላይ ጉዳት የደረሰ ስለሆነ ለእጅ ዋጋ፣ ለመለዋወጫና የተቋረጠ ጥቅም በድምሩ ብር 16,900 የከሣሽ ተከሣሽ እንዲከፍል ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

የከሣሽ ተከሣሽም ጉዳቱ የደረሰው በተከሣሽ ተከሣሾች ሹፌር ጥፋት ስለሆነ ካሣ የመክፈል ግዴታ የለብኝም በማለት መልስ ሠጥቷል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሠማ በኋላ ከሣሽ በማስረጃነት ያቀረበው የፖሊስ የምርመራ መዝገብ በአደጋው ቦታ በተነሳው ፕላን መሠረት ጥፋቱ የ3ኛ ተከሣሽ እንደሆነ ያስረዳል፡፡ በሌላ በኩል ተከሣሾች ያሰሟቸው ምስክሮች አደጋው የደረሰው የተከሣሾች መኪና በቆመበት የከሣሽ

መኪና መትቶ በመግጨቱ መሆኑን በቦታው ተገኝተው በዓይናቸው እንዳዩ ገልጸዋል፡፡ የከሣሽ ማስረጃ የፖሊስ ምርመራ ሪፖርት ከአደጋው በኋላ ከነበረው ሁኔታ የተዘጋጀ በመሆኑ እና የተከሣሾች ማስረጃ ደግሞ በቦታው የነበሩ ሰዎች ቃል ስለሆነ ፍ/ቤቱ በተከሣሾች ማስረጃ ላይ የበለጠ እምነት ጥሎ አደጋው የደረሰው የከሣሽን መኪና ሲያሽከረክር በነበረው ሾፌር ጥፋት ስለሆነ ከሣሽ ኃላፊ ነው ካለ በኋላ የካሳ ክፍያውን መርምሮ ተከሣሾች በአደጋው ምክንያት ብር 9,600 ጥቅም ተቋርጦብናል ቢሉም ይህንን የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረቡም ነገር ግን መኪናው የታክሲ አገልግሎት የሚሰጥ እንደመሆኑ መጠን ገቢ ሊቋረጥ እንደሚችል ስለሚታመን በርትዕ ብር 2,000 ሺህ እንዲከፍል ለእጅ ዋጋና ለመለዋወጫ የተከፈለን በተመለከተ ተከሣሾች ማስረጃ ያቀረቡ ስለሆነ ይህንኑ ጨምሮ በጠቅላላው ብር 10,300 ከወጭና ኪሣራ ጋር ከሣሽ ለ2ኛ እና 3ኛ ተከሣሾች እንዲከፍል ወስኗል፡፡ ከሣሽ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ተከራክረው ፍ/ቤቱ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ 2ኛ ተጠሪ በትራፊክ ፖሊሱ ኘላን ላይ ጥፋታቸውን በማመን በሰነዱ ላይ በፈረመበት ሁኔታና የተሸከርካሪው ባለቤት ናቸው የተባሉትም ጥፋቱን በመቀበል በካሳው መጠን ላይ ከአመልካች ጋር ለመደራደር ጥያቄ ማቅረባቸው በተረጋገጠበት ሁኔታ ጥፋት የፈፀመው የአመልካች ሾፌር ነው ተብሎ መወሰኑ አግባብነቱ ለሰበር ቀርቦ ሊመረመር እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ በሥር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረው በአግባቡ ነው ወይንስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበውን ክስ ውድቅ በማድረግ በተጠሪዎች በኩል የቀረበውን የተከሣሽ ከሣሽነት ክሱ ተቀብሎ ውሣኔ የሰጠው ከፍ ብሎ እንደተመለከተው ተጠሪዎች ያሰሟቸው ምስክሮች አደጋው የደረሰው የተጠሪዎች መኪና በቆመበት የአመልካች መኪና መጥቶ በመግጨቱ መሆኑን በቦታው ስለነበሩ በዓይናቸው እንዳዩ የገለጹ ስለሆነና በአመልካች በኩል የቀረበው የባለሙያ ሪፖርት የተጠሪዎችን መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ሹፌር ጥፋት መፈጸሙን ቢያረጋግጥም የምስክሮቹ ቃል ይበልጥ ዕምነት የሚጣልበትና ክብደት የሚሰጠው ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡

በማስረጃ ዓይነቶች ክፍፍል የአንድን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር ለማስረዳት ሊቀርብ የሚችሉት ማስረጃዎች ቀጥተኛ ማስረጃ /direct evidence/ ወይም የአካባቢ ማስረጃዎች /circusmstantial evidence/ ተብለው፣ ሊመደቡ የሚችሉ ሲሆን ምስክሮች በስሜት ሕዋሳታቸው አማካይነት የተፈለገው ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖሩ እናውቃለን በማለት የሚሰጡት የምስክርነት ቃል ቀጥተኛ ማስረጃ ተብሎ ይወሰዳል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአካባቢ ማስረጃ የሌሎች ፍሬነገሮችን መኖር ወይም አለመኖር በማስረዳት ለክርክሩ ግምት መውሰጃ መሠረት የሆነውን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር በተዘዋዋሪ መንገድ ለማስረዳት የሚቀርብ ማስረጃ እንደሆነ በመስኩ ከዳበረው ሥነ ሕግ /Jurisprudence/ መገንዘብ ይቻላል፡፡

አመልካች ክሱን ለማስረዳት ያቀረበው ማስረጃ አደጋው ከደረሰ በኂላ በአደጋው ሥፍራ በተገኘ ባለሙያ /ኤክስፐርት/ አማካይነት የተዘጋጀ የባለሙያ ሪፖርት ነው፡፡ የባለሙያ ሪፖርት የኤክስፐርት ማስረጃ ተብሎ ሊወሰድ የሚችል ሲሆን አንድ ኤክስፐርት የሚሰጠው ቃል በፍ/ቤት እንዲረጋገጥ የተፈለገውን ጉዳይ በቀጥታ አይቻለሁ ወይንም ጉዳዩ በቀጥታ ሊረጋገጥ የሚችልበት በማንኛውም የስሜት አካሎች አማካይነት ተረድቻለሁ በማለት ሳይሆን በሙያው ሊረጋገጡ የሚችሉትን ነገሮች ተመራምሮ ውጤቱን ወይም ግኙቱን የሚገልጽ ስለሆነ የኤክስፐርት ማስረጃ በአካባቢ ማስረጃ ሥር ሊመደብ እንደሚችል ከዳበረው ሥነ-ሕግ መረዳት ይቻላል፡፡ የኤክስፐርት ማስረጃም ለፍ/ቤት በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤቱ ይህን ማስረጃ ሳይጠረጥረው ባለበት ሁኔታ የሚቀበለው ሣይሆን እንደማንኛውም ማስረጃ የሚመዘን ነው፡፡

የተጠሪዎች መኪና ቆሞ ባለበት በአመልካች መኪና የተገጨ ስለመሆኑ ተጠሪዎች የቆጠሯቸው ምስክሮች አረጋግጠዋል፡፡ በአመልካች በኩል የቀረበው የባለሙያ ሪፖርት ጥፋቱ የተጠሪዎችን መኪና ሲያሽከረክር በነበረው ሹፌር የተፈጸመ መሆኑ ቢረጋገጥም የባለሙያ ማስረጃ የኤክስፐርት ማስረጃ እንደመሆኑ መጠን ኤክስፐርቱ መጨረሻ ላይ የሚደርስበት መደምደሚያ /ግኙት/ ሙያዊ አስተያየት /opinion/ እንጂ ፍሬ ነገር /fact/ ሊሆን አይችልም፡፡ የኤክስፐርቱ የሚደርስበት የመጨረሻ አስተያየት ከሚኖረው ሙያዊ ዕውቀት አድማስ ከሚታገዝበት መሣሪያና ከመሳሰሉት ጋር የተሟላና ሙሉ ዕምነት የሚጣልበት ማስረጃ /conclusive evidence/ ሊሆን ስለማይችል በዓይን ምስክሮች የተነገረን ፍሬ ነገር ለማስተባበል የሚያበቃ አቅም አይኖረውም፡፡ ይህ ሰበር ችሎትም ቀደም ሲል በሰበር መ.ቁ. 14981 የኤክስፐርት ማስረጃ ሙሉ ዕምነት ሊጣልበት የሚችል ማስረጃ እንዳልሆነ የሕግ ትርጉም ሠጥቶበታል፡፡ ከዚህም ሌላ የኤክስፐርት ማስረጃ በማስረጃነት በቀረበ ጊዜ ይበልጥ ተቀባይነት የሚኖረው ከቀጥተኛ ማስረጃ ጋር በተጣጣመ ጊዜ እንጂ ቀጥተኛ ማስረጃውን በሚፃረር ጊዜ የበለጠ ክብደት የሚሰጠው ለቀጥተኛ ማስረጃው ስለሆነ የኤክስፐርት ማስረጃው ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይችል መገንዘብ ስለሚቻል የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በቀጥተኛው ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ጥፋት የተፈጸመው የአመልካችን መኪና ሲያሽከረክር በነበረው ሹፌር አማካይነት ነው ሲል የደረሰበት መደምደሚያ ከማስረጃ አቀራረብ መሠረታዊ መርህ አኳያ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

በሌላ በኩልም የተጠሪዎች ሾፌር ጥፋተኛ በተደረገበት በባለሙያ አስተያየቱ ላይ ፊርሞ መገኘቱ እንደዚሁም ተጠሪዎች ይህንኑ ተቀብለው ለአመልካች ካሣ ለመክፈል ተደራድረው ነበር መባሉ የኤክስፐርት ማስረጃውን ከቀጥተኛ ማስረጃው የበለጠ ተቀባይነት ሊያደርገው ስለማይችል ውጤቱን ሊቀይረው የሚችል ሆኖ አላገኘውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 08549 በ28/6/2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 67409 በ8/3/2001 ዓ.ም. የሰጠውን ፍርድ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት አጽንተነዋል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ጽ/ሸ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 14981

ግንቦት 04 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሠ

አብዱልቃድር መሐመድ

ጌታቸው ምህረቱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሰ

**አመልካች** ፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ

**ተጠሪ** ፡- ወ/ሮ ሃዋ መሐመድ

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የባለሙያ አስተያየት የመጨረሻ ማስረጃ (conclusive evidence) መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

አመልካች ለም/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ አቶ መሐመድ አብዱራህማን ከባንኩ ለወሰዱት ብድር ተጠሪ ንብረታቸውን በዋስትና ስላስያዙ ተበዳሪው በሚፈለግባቸው ዕዳ ተጠሪ በዋስትናቸው መሠረት ግዴታቸውን እንዲወጡ ጠይቋል፡፡ ተጠሪም የገቡት የዋስትና ውል አለመኖሩን በመግለጽ የተከራከሩ ሲሆን ፍ/ቤቱም በዋስትና ሠነዱ ላይ ያለው ፊርማ የተጠሪዋ አለመሆኑን በፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ በመረጋገጡ ተጠሪ ሊጠየቁ አይችሉም በማለት ወስኗል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይግባኙን ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም በባለሙያ የሚሰጥ አስተያየት የመጨረሻ ማስረጃ (conclusive evidence) ነው ወይ? የሚለውን የሕግ ነጥብ ለመመርመር ጉዳዩን ለሰበር ችሎት አስቀርቧል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በጽሑፍ ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ ከተገቢው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በዚህ መዝገብ ዋነኛው አከራካሪ የሆነው ተጠሪ ንብረታቸውን በማስያዝ የዋስትና ግዴታ የመግባታቸው ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪዋ ለተሰጠው ብድር የዋስትና ግዴታ መግባታቸውን ለማስረዳት የዋስትና ሠነዱን እንዲሁም ምስክሮችን አቅርቧል፡፡ ምስክሮቹም ተጠሪ በዋስትና ውሉ ላይ የፈረሙ ለመሆኑ ባል የሌላቸው መሆኑን ከቀበሌ ማስረጃ አቀርበው እንደነበር አረጋግጠዋል፡፡ ነገር ግን ተጠሪ ፊርማውን የካዱ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ፊርማው በፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ ክፍል እንዲመረመር አድርጎ በሠነዱ ላይ ያለው ፊርማ የተጠሪዋ አለመሆኑን የሚያረጋግጥ ውጤት ለፍ/ቤቱ ቀርቧል፡፡ ፍ/ቤቱም ፊርማው የተጠሪ አለመሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ስለቀረበ የሰው ማስረጃው ፋይዳ ከሌለው መሠማታቸው ስህተት ነው በማለት የመስክሮቹን ቃል ሙሉ በሙሉ ውቅድ በማድረግ ተጠሪን ከተጠያቂነት ነፃ አድርጓቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት የባለሙያ አስተያየት ተቃራኒ ማስረጃ ሊቀርብበት የማይችል የመጨረሻ ማስረጃ መሆን አለመሆኑን መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡

በአገራችን ራሱን የቻለ የማስረጃ ሕግ ባለመኖሩ በዚህ ጉዳይ በቀጥታ ተፈፃሚነት ያለው ድንጋጌ ሊጠቀስ ባይችልም በሌሎች አገሮች ተቀባይነት ካገኘው የማስረጃ ሕግ መርህ ግን መረዳት የሚቻለው የባለሙያ አስተያየት ብቻውን ለመቆም የሚችል ወይም በተቃራኒ ማስረጃ ሊስተባበል የማይችል ሳይሆን ይልቁንም ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር ተገናዝቦ ብቃቱና ተአማኒነቱ ሊመዘን የሚገባ መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም ምንም እንኳን በባለሙያ አስተያየቱ መሠረት የሚያቀርበው የሣይንሳዊ ጥናትና ምርመራ ውጤትን ቢሆንም ሣይንስ በራሱ ፍፁም እርግጠኛነት የሌለውና ሙሉ እምነት የሚጣልበት አይደለም፡፡ ይህም በመሆኑ የባለሙያ አስተያየት ብቻ እንደበቂ ማስረጃ ተቆጥሮ ሌሎች ማስረጃዎችን ያለበቂ ምክንያት ተቀባይነት ማሳጣቱ ወደ ተሣሣተ መደምደሚያ ሊያደርስ የሚችል ይሆናል፡፡

በተያያዘው ጉዳይም ቢሆን ፍ/ቤቱ የቀረበለትን የፖሊስ ምርመራ ውጤት ብቻ ተቀብሎ የምስክሮቹ ቃል ተቀባይነት ወይም ተአማኒነት ሊያጣ የሚገባበትን በቂ ምክንያት ሣይገልፁ የምርመራ ውጤቱ በመቅረቡ ብቻ በደፈናው የሰው ማስረጃ ፋይዳ የለውም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ስህተት መሆኑን ተረድተናል፡፡

በሌላ በኩል ፍ/ቤቱ ከግራ ቀኙ የቀረቡትን ማስረጃዎች እንዲሁም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት ጠቃሚ ነው የሚለውን ማስረጃ አስቀርቦ መመርመር የሚችል ቢሆንም የጠሪን ምስክሮች እንዲቀርቡ በማድረግ የምስክርነት ቃላቸውን ከሰማ በኋላ የባለሙያ አስተያየት በመቅረቡ ብቻ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 207 መሠረት የምስክርነት ቃሉን ውድቅ ማድረጉ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን የተከተለ አካሄድ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም የተጠቀሰው የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌ ከሥነ-ሥርዓት ውጪ ክስ ሲቀርብ ወይም በክሱ ውስጥ ከደንብ ውጪ የሆነ ተግባር ሲፈፀም ስህተቱን ለማረም የተቀመጠ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ምስክሮቹ በአመልካቹ የተቆጠሩ በመሆናቸው ቀርበው መሰማታቸው ስህተት አልነበረም፡፡ በአመልካች ባይቆጠሩ እንኳን ፍ/ቤቱ ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት ጠቃሚ ናቸው ብሎ ካመነ እንዳይሰሙ የሚከለክል ሥርዓት የለም /የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 264 ይመለከቷል/፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ምስክሮቹ የሰጡት ምስክርነት ተአማኒነት የለውም ካለ ይህንኑ ገልፆ ውድቅ ከሚያደርገው በቀር ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የሥነ-ሥርዓት ድነጋጌ መሠረት በማድረግ የሰው ማስረጃውን ውድቅ ማድረጉ ስህተት ነው፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍ/ቤቶች የባለሙያ አስተያየቱን እንደመጨረሻ ማስረጃ (conclusive evidence) አድርገው በመውሰድ የሰው ማስረጃውን ውድቅ በማድረጋቸው የሕግ ስህተት ፈጽመዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

3. የም/ሸዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24190 ግንቦት 28/1995 የሰጠው ውሣኔ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00894 ታህሣስ 13/1996 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡
4. ተጠሪ በዋስትና ባስያዙት ንብረት ግምት ልክ ለሚፈለገው የዕዳ መጠን ተጠያቂ ናቸው፡፡
5. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ በመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 44238

ጥር 09 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ማሞ ደምሴ ወኪል ወ/ት አዲስ ማሞ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ አያሌው ገ/እግዚአብሔር
2. ወ/ሮ ታየች ብርሃኑ
} በሌሉበት
3. ወ/ሮ ከበቡሽ በጅጋ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 349 መሠረት የሚቀርበውን የተወሰደ ነገር የማስመለስ ጥያቄንና አፈፃፀሙን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪዎች ላይ በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ በሐረር ከተማ ቀበሌ 14 ውስጥ የቤት ቁጥር 700 የሆነ መኖሪያ ቤትን በሚመለከት ክርክር ላይ የነበሩ መሆኑንና ክርክሩም በመ/ቁጥር 84/88 ታይቶ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቤቱን የአሁኑ አመልካች ለ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እንዲያስረክቡ የሚል ውሳኔ ተስጥቶ ፍርዱ እንዲፈፀም በመ/ቁጥር 14/90 በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ቤቱን አመልካች ያስረከቡ ቢሆንም በቀጥታ ክስ ላይ በተሰጠው ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኂላ በጉዳዩ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በመ/ቁጥር 5390 ጥር 29 ቀን 1999 ዓ.ም ሙሉ በሙሉ መሻሩን በመግለፅ ቤቱን ተጠሪዎች መልሰው እንዲያስረክቡ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ 3ኛ ተጠሪ ጉዳዩ ቀደም ብሎ በፍርድ ያለቀ ነው፣ አመልካች በቤቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም (ባለቤት አይደሉም)፣ ቤቱን በሕግ አግባብ በተደረገ የሽያጭ ውል ከባለቤቶቹ ገዝቼ ቤቱን በመረከብ ስመሃብቱን በማዛወር እየተጠቀምኩ የምገኝ በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የ3ኛ ተጠሪን ክርክር ባለመቀበል ውድቅ አድርጎ ቤቱን ለአሁኑ አመልካች ሊያስረክቡ ይገባል ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡ በዚህ ብይን የአሁኗ 3ኛ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ከዚህም በኂላ 3ኛ ተጠሪ ይግባኛቸውን ለሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ



www.chilot.me

ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ በተለያዩ ጊዜያትና በተለያዩ መዛግብት የቀረቡትን ክርክሮችና የተሠጡትን ውሳኔዎችን ይዘት በመመርመር ለአሁኑ አመልካች መብት የሚሰጥ ውሳኔ አለመሰጠቱን እና የአሁኗ 3ኛ ተጠሪ ቤቱን በሕግ አግባብ መግዛታቸውን በመግለፅ የበታች ፍርድ ቤቶችን ብይን ሽሮ አመልካች ቤቱን የሚረከቡበት አግባብ የለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች መጋቢት 04 ቀን 2001 ዓ.ም በተጻፈ ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የቤት ሽያጭ ውል ይፍረስ ጥያቄ ቀርቦ በበላይ ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ ተጠሪዎች ይግባኝ ብለው ተቀባይነት ባላገኙበት ሁኔታ 3ኛ ተጠሪ ቤቱን በሕግ አግባብ ገዝተዋል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ሥነ ሥርዓታዊ ባለመሆኑ ሊሻር ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ለተጠሪዎች በተገቢው መንገድ ጥሪ ሲደረግ 1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች ሳይቀርቡ በመቅረታቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን 3ኛ ተጠሪ ግን ቀርበው የጽሑፍ መልሳቸውን ታህሳስ 07 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ሰጥተዋል፡፡ አመልካችም 3ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ላይ የመልስ መልሳቸውን በጽሑፍ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን በበታች ፍርድ ቤቶች ከተደረጉት ክርክሮችና ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እንዲሁም አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አብይ ነጥብ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ወይስ አልተፈፀመም የሚለው ሁኖ አግኝቶታል፡፡ ለዚሁ ጭብጥ ምላሽ ለመስጠት ይቻል ዘንድም በጉዳዩ ላይ የተደረጉትን ክርክሮችን በእየእርከኑ ባሉት ፍርድ ቤቶች የተሰጡትን ውሳኔዎችን መመልከቱ አስፈላጊ ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ አመልካች ከአቶ አያሌው ገ/እግዚአብሔር (ከአሁኑ 1ኛ ተጠሪ) ጋር ያደረገው የቤት ሽያጭ ውል እንዲጸድቅላቸው ስመ ሀብቱ እንዲዞርላቸው ይወሰን ዘንድ በጊዜው ለነበረው ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበው አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤቱም ተቃዋሚ ካለ እንዲቀርብ በጋዜጣ ጥሪ አድርጎ ባለመቅረቡ ውሉን በማፅደቅ ስመ ሀብቱ በአሁኑ አመልካች እንዲዞር ውሳኔ የሰጠ ሲሆን በዚህ ውሳኔ መሰረት ከመፈፀሙ በፊት ቤቱን ሸጠ የተባለው ግለሰብ፣ የግለሰቡ ሚስት(ወ/ሮ ታየች ብርሃኑ) እና የአሁኗ 3ኛ ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት ፍርዱን በመቃወም አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱም የተቃውሞ አቤቱታቸውን በመቀበል ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የቤት ሽያጭ ውሉ ሻጭ የሆኑትን ግለሰብ (አቶ አያሌው ገ/እግዚአብሔር) ሚስት ወ/ሮ ታየች ብርሃኑ ፈቃድ የሌለበት በመሆኑ ፈራሽ ነው በሚል የቀድሞውን ውሳኔ በመሰረዝ ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካች ይግባኛቸውን ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ተቀባይነት ባያገኙም የሰበር አቤቱታቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ጉዳዩ ከታየ በኋላ አመልካች መጀመሪያውኑ የቤት ሽያጭ ውል ይፅደቅልኝ በማለት ለአውራጃ ፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለው ነው በሚል ምክንያት መዘጋት ሲገባው ጉዳዩ መታየቱ ያላግባብ ነው በሚል ምክንያት በበታች ፍርድ ቤቶች የሽያጭ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ አመልካች ውሉ በፍርድ ቤት ውሳኔ ይጽደቅልኝ በማለት ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት ቤቱን ተረክበው የነበሩ ሲሆን ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ ከተወሰነ በኋላ የአሁኑ 1ኛ



www.chilot.me

እና 2ኛ ተጠሪዎች ቤቱን አመልካች ያስረክበን በሚል ጥያቄ አቅርበው ፍርድ ቤቱ አመልካች ቤቱን ለእነዚህ ተጠሪዎች እንዲያስረክቡ በማለት ግንቦት 26 ቀን 1989 ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቶ በዚህ ውሳኔ መሰረት የአፈጻጸም መዝገብ ተጠሪዎች አቅርበው አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች መስከረም 20 ቀን 1990 ዓ.ም አስረክበዋል፡፡ ከዚህም በኋላ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በጋራ ሁነው ለአሁኗ 3ኛ ተጠሪ ሰኔ 17 ቀን 1984 ዓ.ም በተደረገና ሐምሌ 22 ቀን 1984 ዓ.ም በፍርድ ቤት በተመዘገበ የሽያጭ ውል ቤቱን ሸጠው 3ኛ ተጠሪ ቤቱን በመረከብ ስመ ሀብቱን ሁሉ አዙረው መጠቀም ቀጥለዋል፡፡ ይሁን እንጂ ግንቦት 26 ቀን 1989 ዓ.ም 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ያገኙት ፍርድ በአሁኑ አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርቦበት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ የስረ ነገር ሥልጣን ሳይኖር የተሰጠ ውሳኔ ነው በሚል ምክንያት የተሻረ ሲሆን የአሁኗ 3ኛ ተጠሪም በዚህ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቀርቦበት ተቀባይነት ያላገኘ መሆኑን ችሎቱ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ ችሏል፡፡ ከዚህ በኋላ ነው እንግዲህ የአሁኑ አመልካች አከራካሪው ቤት ላይ የስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በበላይ ፍርድ ቤት የተሻረ ስለሆነ ተጠሪዎች በፍርድ ኃይል የተረከቡትን ቤት መልሰው ያስረክቡኝ በሚል ጥያቄ ያቀረቡት፡፡

በመሰረቱ የተወሰደ ነገር ለማስመለስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 349(1) መሰረት አቤቱታ የሚቀርበው ይግባኝ የተባለበት ፍርድ ወይም ውሳኔ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተለወጠ ወይም የተሻሻለ የሆነ እንደሆነ ሲሆን ይኸው ሲረጋገጥ ማናቸውም ተከራካሪ ወገን ነገሩን በመጀመሪያ ደረጃ ላየው ፍርድ ቤት ሲያመለክት የተሻሻለው ወይም የተለወጠው ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ክርክር የተነሳበት ነገር ወደ ነበረበት ሁኔታ ለመመለስ እንዲችል በመጀመሪያው ፍርድ መሰረት የተወሰደው ንብረት ወይም ገንዘብ ለባለመብቱ እንዲመለስ ወይም የተከራካሪዎቹ ወገኖች መብት በይግባኙ ፍርድ መሰረት እንዲስተካከል ተስማሚ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ ፍርድ ቤቱ መስጠት ያለበት መሆኑ በዚሁ ድንጋጌ ስር ተመልክቷል፡፡ ተጠቃሹ የንዑስ ቁጥር 3 ድንጋጌ ስር አቤቱታው የሚቀርብበትን ሥርዓት አስቀምጧል፡፡ ይኸውም ለማስመለስ የሚቻለውን ሀብት ወይም ለማስተካከል የሚቻለውን መብት ለማስፈጸም ሌላ የክስ መዝገብ መክፈት አስፈላጊ አለመሆኑ በሕጉ ተመልክቷል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 349(1) መሰረት የተወሰደን ንብረት ለማስመለስ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሠጠው ውሳኔ በይግባኝ መሻሻል ወይም መለወጥ እና ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ንብረት ይመለስልኝ የሚለው አቤቱታ አቅራቢ የንብረቱ ባለመብት መሆን መረጋገጥ ስለመሆናቸው ከድንጋጌው ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የምንችለው ነጥብ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ቤቱን ከ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ በግዥ አግኝቼአለሁ፣ እነዚህ ተጠሪዎች ቤቱን የተረከቡበት ፍርድ በበላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሯል ቢሉም አመልካች በየትኛውም የክርክር መስመር ወይም ደረጃ የአከራካሪው ቤት ባለንብረት መሆናቸው ተረጋግጦ የተሰጠ ፍርድ የሌለ መሆኑን ከላይ የተመለከተው የክርክሩ አመጣጥ በግልፅ ያሳያል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 349 መሰረት አቤቱታ የሚያቀርበው ወገን ደግሞ የንብረቱ ባለመብት የሆነ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ የአሁኗ 3ኛ ተጠሪ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ውሳኔ በከፍተኛው ፍርድ ቤት የስረ ነገርን ስልጣን መሰረት ባደረገ ምክንያት በመሻሩ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ተቀባይነት ያለማግኘታቸውም የአሁኑን አመልካች የአከራካሪው ቤት ሕጋዊ ባለንብረት ናቸው ወደሚለው ድምዳሜ ሊያደርስ የሚችል ሕጋዊ ምክንያት አይደለም፡፡ ይልቁንም 3ኛ ተጠሪ የቤቱ ሕጋዊ ባለቤት ናቸው ከተባሉት ከአሁኑ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች (ባልና ሚስት) ቤቱን ከአመልካች ከተረከቡ በኋላና አመልካችም በየደረጃው በነበሩት



www.chilot.me

ፍርድ ቤቶች ክርክር ሲያደርጉ በቤቱ ላይ በሕጉ አግባብ የእግድ ትዕዛዝ ባላሰጡበት ሁኔታ ስልጣን ባለው አካል ፊት በሕጉ አግባብ በተደረገው የሽያጭ ውል ቤቱን ገዝተውና ተረክበው እንዲሁም ስመ ሀብቱን በማዛወርና ለውጦችንም በማድረግ ለበርካታ ጊዜያት የሚጠቀሙበት መሆኑ መረጋገጡ ሦስተኛ ወገን የሆኑት ግለሰብ እጅ የገባን ንብረት አመልካች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 349ን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ጥያቄ የማቅረብ መብት የሌላቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች በሕጉ አግባብ ከ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ጋር ያደረጉት ግንኙነት ካለና በዚህ ግንኙነት መሰረት ወጪ ያደረጉት ገንዘብ ካለም እነዚህን ተጠሪዎች ከሚጠይቁ በስተቀር ቤቱን ከ3ኛ አመልካች ሊወስዱ የሚችሉበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ጉዳዮችንና የትኛው ወገን ከቀድሞ ባለቤቶች ጋር ሕጋዊ ግንኙነት መስርቷል ከሚለው ጥያቄ ምላሽ እና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 349 ድንጋጌ መንፈስና ይዘት ጋር ያገናዘበ ነው ከሚባል በስተቀር ሊነቀፍ የሚችልበትን መሰረታዊ የሕግ ነጥብ አላገኘንም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01169 ታህሳስ 07 ቀን 2001 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

*ራ/ታ*



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 56130

ጥር 26 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡** - ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ሊሲ ታነሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - አብይ ስንታየሁ /ስራ አስኪያጅ/ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪዎች፡-** 1. ወ/ሮ መዓዛ አስፋው - አልቀረቡም፡፡

2. አቶ ክብሮም ሙሉ - አልቀረቡም፡፡

3. አቶ አየለ ኮሮሶ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪዎች ከድል የቆዳ ፋብሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጋር ተከራክረው የፍርድ ባለመብት መሆናቸውን ገልፀው የአፈፃፀም መዝገብ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከፍተዋል፡፡ አፈፃፀሙን የያዘው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የፍርድ ባለዕዳው የሚገኝበት የምስራቅ ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በባለዕዳው ስም የሚገኘውን ንብረት በማሸጥ ብር 250,000 /ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ ብር/ ለፍርድ ባለመብቶቹ እንዲያስከፍል በማለት በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 371 እና በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 392/1/ሀ መሠረት ውክልና ሰጥቷል፡፡

ከዚህ በኂላ አፈፃፀሙ በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀጥሏል፡፡ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቆዳ ፋብሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ንብረት እንደሚሸጥ የጨረታ ማስታወቂያ አውጥቷል፡፡ በሀራጅ ማስታወቂያው መሠረት ሽያጭ ፈጽሟል፡፡ ስለ ሽያጭ ሒደቱም ውክልናውን ለሰጠው ፍርድ ቤት ሪፖርት አድርጓል፡፡ አመልካች በዕዳ የተሸጠው የእኔ ንብረት ነው ሽያጩ የተከናወነው የካቲት 14 ቀን 2001 ዓ.ም ነው፡፡ እኔ በማይመለከተኝ ዕዳ ንብረቴ መሸጡን ያወቅሁት ገዥው ስመ ንብረቱን ለማዛወር እንቅስቃሴ ሲያደርግ ነው፡፡ ስለዚህ የሀራጅ ሽያጩ እንዲሰረዝልኝ በማለት አመልክተዋል የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች ውድቅ አድርጐታል፡፡ የመጀመሪያው አቤቱታው መቅረብ ያለበት በውክልና ቤቱን

ላሸጠው ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆን አለበት በማለት የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 374 ንዑስ አንቀጽ 1ን በመጥቀስ የወሰነ ሲሆን፣ ሁለተኛው አቤቱታው ሽያጩ በተከናወነ በሁለት ወር ውስጥ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 447 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አቤቱታው አልቀረበም በማለት ነው፡፡ አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካች ይግባኝ ፍሬ ነጥብ የሌለው መሆኑን በመግለጽ በፍታብሔር የሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ግንቦት 13 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የጨረታ ማስታወቂያው የፍርድ ባለዕዳውን ስም በግልጽ መያዝ ሲገባው "የቆዳ ፋብሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር" በሚል ስያሜ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ወጥቷል፡፡ የፍርድ ባለዕዳው በትክክል ባልተገለፀበት ሁኔታ የእኛ ንብረት ላይ የሃራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ ያወጣ መሆኑን አውቀን ልንከታተል እና በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 447/1/ በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ሀራጁ እንዲሰረዝ ለማመልከት የምንችልበት ሁኔታ የለም፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች ጥያቄያችንን ተቀብለው ሁኔታውን አጣርተው መወሰን ሲገባቸው ባለዕዳ ባልሆንበት ፍርድ ንብረታችን እንዲሸጥ መደረጉና ሽያጩ ይፀናል ማለታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው ጥያቄው መቅረብ ያለበት በውክልና ንብረቱን በሸጠው ፍርድ ቤት መሆን ይገባዋል፡፡ ይህንንም በተለያዩ ምሁራን የተፃፉ የህግ ትንታኔዎችን በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የምስራቅ ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሸጥ የታዘዘው በተለይ በአዋሳኝ የተገለፀው ቦታ የአመልካችን ንብረት አይደለም፡፡ የተሸጠው የባለዕዳው ንብረት ነው፡፡ አመልካች በስም ስህተት የእኔ ንብረት ነው የተሸጠው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተገቢ አይደለም በሀራጅ የተሸጠው ንብረት በእነ አዜብ ሙሉ አውራሽ በአቶ ሙሉ በአቶ ደረጃ ደመቀና በአቶ ስለሺ ሀይሌ በተቋቋመው ድል የቆዳ ፋብሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሥር የተያዘ ነበር፡፡ ይህ የንግድ ማህበር ሳይፈርስ እንደፈረሰ በማስመሰል ሊሲ ታነሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በሚል ስም ይዘነዋል እያሉ የሚያቀርቡት ክርክር የህግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የሀራጅ ሽያጩ እንዲሰረዝ አቤቱታውን ማቅረብ ያለበት ሀራጁን እንዲያስፈጽም ለተወከለው ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥና የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 447 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥያቄውን አላቀረበም በማለት የሰጡት ውሣኔ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን የህግ ድንጋጌ መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉት ጭብጦች እልባት ማግኘት ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

1. የመጀመሪያውን ጭብጥ ለመወሰን በዚህ መዝገብ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የተከተለውን አሠራርና የህጉን ድንጋጌ ማገናዘብ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሞጆ ከተማ የሚገኘው የቆዳ ፋብሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ይዞታና ንብረት በማሸጥ ለፍርድ ባለመብቶች ብር 250,000 /ሁለት መቶ ሀምሳ ሺህ ብር/ እንዲከፍል ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውክልና ሰጥቷል፡፡ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ



www.chilot.me

ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጥቅምት 3 ቀን 2001 ዓ.ም በሰጠው ውክልና መሠረት "የቆዳ ፋብሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር" ንብረት በጋዜጣ ማስታወቂያ እንዲወጣ በማድረግ ንብረቱን በሀራጅ ሸጧል፡፡ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ንብረቱን በሀራጅ የካቲት 14 ቀን 2001 ዓ.ም ከሸጠው በኋላ አመልካች ለፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አቤቱታ በማቅረቡ፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካቾችን አቤቱታ ከተቀበለ በኋላ ስለ ሀራጁ አካሄድ ጉዳዩን በውክልና ያስፈፀመው የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማብራሪያ እንዲሰጠው ታህሳስ 26 ቀን 2002 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጥቶ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥር 20 ቀን 2002 ዓ.ም አምስት ገጽ ማብራሪያ ልኮለታል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማብራሪያ ከደረሰው በኋላ የካቲት 2 ቀን 2002 ዓ.ም አመልካች አቤቱታውን ማቅረብ ያለብህ ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ቤት ፍርድ ነው በማለት ወስኗል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ይህንን ብይን መስጠት የነበረበት የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማብራሪያ እንዲሰጠው ከመጠየቁ በፊት አመልካች አቤቱታውን ወዲያውኑ እንዳቀረበ መሆን ነበረበት፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታ ተቀብሎ ጉዳዩን ለማጣራት ረጅም ጊዜ ከወሰደ በኋላ አመልካች ወደ ምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ እንዲያቀርብ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በዋቢነት የጠቀሰው የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 374 ንዑስ አንቀጽ 1 አፈፃፀሙ በውክልና የሚያከራክረው ፍርድ ቤት የስልጣን ወሰንን የሚገልጽ እንጅ የሃራጅ ሽያጭ ተከናውኖ ካለቀ በኋላ ጉዳዩን በውክልና ካስፈፀመው ፍርድ ቤት ሙሉ ማብራሪያ የተሰጠው ወካዩ ፍርድ ቤት የሀራጅ ሽያጩ ይሰረዝልኝ ጥያቄ ሲቀርብለት ጉዳዩን እንዳያከራክር እና ውሣኔ እንዳይሰጥ የሚከለክል ድንጋጌ አይደለም፡፡ ድንጋጌም ሁለቱም ፍርድ ቤቶች እኩልና አቻ ስልጣን ያላቸው መሆኑን የሚደነግግ ድንጋጌ ነው፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ ተቀብለው ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን እንደሌላቸው በመግለጽ የሰጠውን ብይን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 447 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው የሁለት ወር የጊዜ ገደብ በአፈፃፀም ክርክሩ ተሳታፊ የነበረ የፍርድ ባለመብት፣ የፍርድ ባለዕዳ ወይም በሀራጅ ንብረቱን የገዛው ሰው የሀራጅ ሽያጩ እንዲሰረዝ በሁለት ወር ውስጥ መጠየቅ እንዳለበት የሚደነግግ የህግ ድንጋጌ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ የፍርድ ባለዕዳ ያልሆኑ የሦስተኛ ወገን ንብረት በሀራጅ በተሸጠ ጊዜ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው የሀራጅ ጨረታ ማስታወቂያው በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 423 የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ ያሟላ በሆነ ጊዜና የሀራጅ ማስታወቂያው በሚሸጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 414 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 425 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት የተለጠፈ መሆኑ ሲረጋገጥና የንብረቱ ባለሀብት ነኝ የሚለው ሰው የሀራጅ ሽያጭ በንብረቱ ላይ እየተካሄደ መሆኑን የሚያውቅ ወይም ማወቅ የሚገባው ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ የፍርድ ባለዕዳ የሆነው ድል የቆዳ ፋብሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሲሆን በጋዜጣ የወጣው የሀራጅ ማስታወቂያ "የቆዳ ፋብሪካ ኃላፊነቱ የግል ማህበር" በሚል ስያሜ መሆኑንና የሀራጅ ማስታወቂያው በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 423 በሚደነግገው መሠረት የፍርድ ባለዕዳውን ስም በትክክል የሚገልጽ አለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ንብረቴ ነው የሚለው የማይንቀሳቀስ ንብረት በሃራጅ እየተሸጠ መሆኑን ለማወቅ የሚችልበት ሁኔታ የነበረ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት አላጣራም፡፡ የሀራጅ ማስታወቂያው በህጉ የተደነገገውን መስፈርት የማያሟላ በሆነበት ሁኔታ የሀራጅ ሽያጩ በፍርድ ባለዕዳው ድል የቆዳ



www.chilot.me

ፋብሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ንብረት ላይ ሳይሆን በእኔ ንብረት ላይ ነው የሚለው የሚለውን የአመልካች ጥያቄ ለመወሰን አግባብነት ያለው የህግ ድንጋጌ የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 447/1/ ሳይሆን የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 453 ድንጋጌ ነው፡፡

አመልካች የፋብሪካውን ስመ ንብረት ሐራጅ አሸናፊ ሆኖ ወደ ገዛው ሰው ለማዛወር የሚደርገውን እንቅስቃሴ በመቃወም ንብረቱ የፍርድ ባለዕዳው ሳይሆን የእኔ ሀብት ስለሆነ ልለቅ አይገባኝም የሚል አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችል የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 453 ንዑስ አንቅጸ 1 ይደነግጋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የአመልካች አቤቱታ ለፍርድ ባለመብትና ንብረቱን ለገዛው ሰው እንዲደርስ በማድረግና ግራ ቀኙ የሚከራከሩበትን ቀነ ቀጠሮ በመያዝ ማከራከር እንዳለበት የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 453 ንዑስ አንቀጽ 2 የሚደነግግ ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 453 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ተገቢ ነው የሚለውን ውሣኔ የማስጠት ግዴታና ሀላፊነት አለበት፡፡ በያዝነው ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታና ማስረጃ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 453 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በመቀበል የግራ ቀኙን ክርክር በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 453 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በመስማት በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 453 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት መወሰን ሲገባው ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 447 ንዑስ አንቀጽ 1 በመጥቀስ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታና ማስረጃ እንደዚሁም የተጠሪዎችን መልስና ማስረጃ በመቀበልና የሚያቀርቡትን ክርክር በመስማት በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 453 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 54080

ጥቅምት 19 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች ፡-** እነ አቶ ላሪ ሮላንድ ቻፕማን ጠበቃ ከድር ቡሎ ቀረበ

**ተጠሪ ፡-** አቶ ዜና ወልደማሪያም የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካቾች በስር ፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሌለንበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ክርክሩ ባለንበት ይታይልን በማለት ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ የተደረገው ያላግባብ ነው በሚል በጠበቃቸው አማልካኝነት መጋቢት 15 ቀን 2002ዓ.ም የተፃፈ ሶስት ገጽ የሰበር አቤቱታቸውን ስላቀረቡ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ የተጠሪ ጠበቃ ቀርበው ሐምሌ 13 ቀን 2002ዓ.ም በተፃፈ ሶስት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ በመልሳቸውም ላይ መጥሪያ በአግባቡ ደርሶ ተገቢው ሰው ለክርክር ሳይቀርብ በመቅረቱ ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ ውሳኔ የተሰጠ ስለሆነ እና በፍርዱ መሠረት ከፊሉም የተፈፀመ በመሆኑ የፍርድ አፈፃፀሙን ለማጓተት የቀረበ አቤቱታ በመሆኑ ውድቅ ሊሆን የሚገባው መሆኑን ገልፀው የበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያደረጓቸውን የጽሁፍ ክርክሮች ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

እንደሚታወቀው የፍትሐብሔር ክርክሮች የሚመሩት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት ነው፡፡ ይኸው የሥነ ሥርዓት ሕግ አካቶ ከያዛቸው ጉዳዩች ውስጥ አንዱ የተከራካሪ ወገኖች በክርክሩ ወቅት ያለመቅረብና ውጤቱ ነው፡፡ በዚህም መሠረት መጥሪያ ተልኮለት በተገቢው መንገድ የደረሰው መሆኑ በተረጋገጠበት ተከሳሽ ላይ ፍ/ቤቱ ሊከተለው የሚገባው ሥርዓት ጉዳዩ ተከሳሹ በሌለበት የሚሰማበት ስለመሆኑ በፍ/ብሥ/ሥ/ሕ/ቁ 70/ሀ/ ስር ተመልክቷል፡፡ ሌላው በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተመለከተው ሥርዓት ተከሳሹ ሊከተለው የሚገባው መፍትሔ ነው፡፡ ክርክሩ በሌለበት እንዲቀጥል የተደረገበት ተከሳሽ በተከታዩ ቀነ ቀጠሮ ቀርቦ በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ ያለመቅረቡን ካስረዳ መከላከያውን አቅርቦ የመከራከር መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 72 ያስገነዝባል፡፡ እንዲሁም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 78/1/ አንድ

ተከሳሽ በክርክሩ ላይ ቀርቦ መልስ ሳይሰጥ ወይም ተገቢውን መከራከሪያ ሳያቀርብ በመቅረቱ በሌለበት አንድ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ የተሰጠ ከሆነ ውሳኔው ወይም ትዕዛዙ መሰጠቱን በተረዳው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ትዕዛዙ ወይም ውሳኔው እንዲነሳለት የማመልከት መብት እንዳለው ተደንግጓል፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 2 ደግሞ ተከሳሽ የጥሪው ትዕዛዝ በሚገባ ያልደረሰው መሆኑን ወይም ክርክሩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ቀርቦ መከራከሪያውን ያላሰማ ወይም መልስ ያልሰጠው በበቂ ምክንያት መሆኑን ለፍርዱ ቤቱ ያስረዳ እንደሆነ ተከሳሹ በሌለበት እንዲታይ የተሰጠው ብይን ወይም ትዕዛዙ እንደሚነሳለትና ክርክሩ እንደገና እንደሚሰማለት ይደነግጋል፡፡ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78/1/ እና /2/ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው ተከሳሽ በቀነ ቀጠሮ ያልቀረበው በበቂ ምክንያት መሆኑን ፍርድ ቤቱ ከተረዳው ተከሳሹ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ የተሰጠውን ትዕዛዝ ወይም ብይን በማንሳት ክርክሩ ተከሳሹ ባለበት እንዲቀጥል ማድረግ ያለበት መሆኑን ነው፡፡ የድንጋጌው ዓላማም የተከሳሹን የመከራከር መብት ለመጠበቅ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም፡፡ በመሆኑም ተከሳሹ ቀና ልቦና ያለው መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ በቂ ምክንያት የሚለው የድንጋጌው ሐረግ መታየትና መተግበር ያለበት የተለያዩ ነባራዊ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት የተከሳሹን የመከራከር መብት በሚጠበቅ መልኩ ነው፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስመንለስም አመልካቾች በቀጠሮው ቀን ስላለመቅረባቸው ያቀረቡት ማስረጃ የቤተሰብ ጤና ችግር መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን የሥር ፍ/ቤትም ይህ ማስረጃ ተቀባይነት የለውም ወደሚለው ድምዳሜ አልደረሰም፡፡ የስር ፍ/ቤት በቀደመው ቀነ ቀጠሮ የቀረቡትን የአመልካቾችን ጠበቃ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ለመቆም የሚያስችል የጥብቅና ፈቃድ የላቸውም በማለት ተገቢውን ፈቃድ አሟልተው እንዲመጡ ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቶ ጠበቃቸው አልቀረቡም፡፡ አመልካቾቹም በቤተሰባቸው የጤና መታወክ ችግር ምክንያት በተለዋጩ ቀነ ቀጠሮ አልቀረቡም፡፡ የስር ፍ/ቤት የአመልካቾችን ጉዳዩ ባለንበት ይታይልን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው በጠበቃ መወከል ትችሉ ነበር በሚል ምክንያት ነው፡፡ በመሠረቱ በጠበቃ መወከል ግዴታ ሳይሆን መብት ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት ከላይ እንደተገለፀው የአመልካቾች ቤተሰብ የጤና ችግር በወቅቱ መድረሱን ያረጋግጣል የተባለውን የህክምና ማስረጃ ተቀባይነት ሰጥቶ በጠበቃ መወከል ትችሉ ነበር በሚል ምክንያት አመልካቾች በሌሉበት እንዲታይ የተሰጠውን ትዕዛዝ ሳያነሳ መቅረቱ የፍትሐብሔር ሥነ ስርዓት ዓላማንና የአመልካቾችን የመከራከር መብት ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም የአመልካቾች ጠበቃ ተገቢውን ፈቃድ አልያዙም በሚል ምክንያት አመልካቾችን መወከል አይችሉም ተብሎ ከተሰናበቱ በኋላና አመልካቾችም በቤተሰብ የጤና መታወክ ችግር ምክንያት በተለዋጩ ቀጠሮ አለመቅረባቸው ተረጋግጦ እያለ በተከራካሪ ወገን ፈቃድ ላይ የተመሰረተውን በጠበቃ የመወከል መብት እንደ አማራጭ በመውሰድ አመልካቾች ወደ ክርክሩ ሊገቡ አይገባም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 33470 ጥር 12 ቀን 2002ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 89198 ጥር 28 ቀን 2002ዓ.ም የፀናው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾች በሌሉበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ባሉበት እንዲታይ ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ የሆነው አመልካቾች ያቀረቡት ማስረጃ ተቀባይነት ያለው መሆኑና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78/2/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ከመከራከር መብት ጋር ባላገናዘበ መልኩ ነው ብለናል፡፡



www.chilot.me

3. አመልካቾች ተከሳሽ ሆነው በሌሉበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ አመልካቾች ባሉበት ክርክሩን አቅርበው ግራ ቀኙ ባለቡት ጉዳዩ እንደገና በስር ፍ/ቤት ታይቶ ይወሰን በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78/2/ መሠረት ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ሶ/በ**

የሰ/መ/ቁ. 44522

ታህሣሥ 15 ቀን 2003

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገብረሥላሴ

ፀጋዬ አስማማው

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ጭላሎ ሥራ ተቋራጭ የተወሰነ የግል ማህበር አልቀረበም

**ተጠሪ፡-** አፍሪካ ኢንጅነርስ ኮንስትራክሽን ጠበቃ አቶ ተሰማ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የማሽነሪ ኪራይ ውል አፈፃፀምን የተመለከተ ነው ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ከሣሽ በመሆን አንድ ግሬደር በሰዓት ሁለት መቶ ሃምሣ ብር ላንድሮለር በሰዓት ሁለት መቶ ብር አንድ ዶዘር በሰዓት አራት መቶ ብር ሊከፍል የአሁን አመልካች /ተከሣሽ/ የወሰደ መሆኑን ገልዖ ያልተከፈለ የማሽነሪ ኪራይ ብር 1,327,500.00/አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሃያ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ብር/ ያለበት ስለሆነ እንዲከፍለኝና ማሽነሪዎቹን እንዲያስረክበኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ ከሣሽ /ተጠሪ/ የጠየቀው ማሽነሪዎቹ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በዝናብና በጎማ አለመኖር ለቆሙበት ሰዓት በመሆኑና የሠሩበት ሠዓት በሹፌሮቹ ተረጋግጦ የቀረበ ባለመሆኑ ክሱ ተገቢ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሣሽ /ተጠሪ/ ያቀረበውን ክስ የሚያስረዳ ማስረጃ ያቀረበ በመሆኑና አመልካች /ተከሣሽ/ የኪራይ ገንዘብ ትክክል አይደለም በማለት ከሚከራከር በስተቀር ክርክሩን የሚያስረዳ ማስረጃ ያላቀረበ በመሆኑ አመልካች በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ሒሣቡ በባለሙያ ተጣርቶ መቅረብ እንዳለበት በማመን አመልካች አንድ ባለሙያ ተጠሪ አንድ ባለሙያ እንዲመርጡና ሒሣቡን ሁለቱ ባለሙያዎች በጋራ አጣርተው እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ሁለቱ ባለሙያዎች በጋራ ሒሣብ እንዲያጣሩ የተሰጡትን ትእዛዝ ወደ ጎን በመተው አመልካች የመረጠው ባለሙያ ሒሣቡን ለብቻው በማጣራት አመልካች ለተጠሪ ያልከፈለው ብር 54,267.17 /ሀምሣ አራት ሺህ ሁለት መቶ ሥልሣ ብር ከአሥራ ሰባት ሣንቲም/ ነው በማለት የሒሣብ ሪፖርት ለብቻው ያቀረበ ሲሆን በተጠሪ



www.chilot.me

የተመረጡት ባለሙያ በበኩላቸው አመልካች በተጠሪ ያልከፈለው ቀሪ ሒሣብ ብር 1,327,005 /አንድ ሚሊዮን ሦስት መቶ ሃያ ሰባት ሺህ አምስት ብር/ አለበት በማለት የብቻውን የሒሣብ ሪፖርት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአመልካች የተመረጠው ባለሙያ ያቀረበው ጥቅል የሒሣብ ሪፖርት መሆኑና በተጠሪ በኩል የተመረጡት ባለሙያ ዝርዝር የሒሣብ ሪፖርት ያቀረቡ መሆኑን በመግለጽ በተጠሪ የተመረጠው ባለሙያ ያቀረበው የሒባብ ሪፖርት አሣማኝነት አለው በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማጽናት አመልካች ለተጠሪ ብር 1,327,005 እንዲከፍል ወስኗል፡፡

አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የኪራይ ሒሣቡ በባለሙያ ሣይጣራ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ መሰጠቱ በአግባቡ መሆኑን በማመን ሒሣቡ በባለሙያ እንዲጣራ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በባለሙያዎቹ ሒሣቡን በጋራ በማጣራት የሚስማሙባቸውን ሒሣብ ተስማምተው የተለያዩበትን ሒሣብ የልዩነታቸውን ምክንያት በመግለጽ በጋራ ማቅረብ ሲገባቸው ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከሰጠው ትእዛዝ ውጭ ለየብቻ ሠርተው ካቀረቡት ሪፖርት ውስጥ የአንደኛውን ባለሙያ ሪፖርት በመተው ሌላውን ተቀብሎ የሰጠው ውሣኔ ስለ ልዩ አዋቂ ምስክር የተደነገገውን የማያሚላና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ለዚህ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በቃል ክርክር ባቀረቡት መልስ ችሎት ሒሣቡን በዝርዝርና በሚያሣምን ሁኔታ ሠርቶ ያቀረበለትን ባለሙያ በመቀበል ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በጋራ ሒሣቡን እንዲያጣሩና ሪፖርት እንዲያቀርቡለት ትእዛዝ የሰጣቸው ባለሙያዎች ለየብቻ ሒሣብ በማጣራት ያቀረቡትን ሪፖርት በመቀበል የአንደኛውን ባለሙያ የሒሣብ መግለጫ ውድቅ በማድረግና የሌላውን ትክክለኛ ነው በማለት ውሣኔ መስጠቱ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከላይ የተያዘውን ጭብጥ እልባት ለመስጠት በአገራችን የሕግ ሥርዓት ልዩ አዋቂ ምስክር በፍርድ ቤቱ የሚሾምበትን ምክንያት በዝርዝር ማየት ያስፈልጋል፡፡ የኮመንሎው የሕግ ሥርዓት በሚከተሉ አገሮች ተከራካሪዎች ልዩ አዋቂ ምስክሮቻቸውን በራሣቸው የማቅረብና በተከራካሪዎች ምርጫና ክፍያ የማይቀርበው ልዩ አዋቂ ምስክር የቆጠራቸውን ተከራካሪ ሊረታ የሚችልበትን ሁኔታ ከሙያ አንፃር አቀነባብረው የሚያቀርቡ የሲቪል ሎው በሚከተሉ አገሮች የልዩ አዋቂ ምስክር የሚመድበው በፍርድ ቤት ሲሆን የልዩ አዋቂ ምስክሩ በማናቸውም ተከራካሪ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ ከሙያ አንፃር ማጣራት የሚገባውን ነገር አጣርቶ ለፍርድ ቤቱ የሚያቀርብና የሙያ አበልም የሚታሰብለት በፍርድ ቤቱ በኩል እንደሆነ የሕግ ሥርዓቱን የሚከተሉ የሥነ ሥርዓት ሕግጋት በማየት ለመረዳት ይችላል፡፡

የአገራችን የሕግ ሥርዓት የሲቪል ሎው የሕግ ሥርዓት የሚከተሉ አገሮች የሚከተሉትን መሠረታዊ መርህ የሚያራምድ ሲሆን አከራካሪ ጉዳይ የሚያጣሩ ልዩ አዋቂዎች /ባለሙያዎች/ ጉዳዩን አጣርተው እንዲቀርቡ የሚሾመው ፍርድ ቤቱ እንደሆነ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 136 ተደንግጓል፡፡ ፍርድ ቤቱ የሚሾማቸው ልዩ አዋቂ ምስክሮች ከተከራካሪዎቹ አንደኛውን ለመደገፍ ሣይሆን ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ትእዛዝ የሙያ ሥነ ምግባር የሚጥልባቸውን ግዴታ ተከትለው ገለልተኛ ሆነው ፍሬ ጉዳዩን በመመርመር ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ



www.chilot.me

አለባቸው። በፍርድ ቤቱ የተመደቡ ልዩ አዋቂ ምስክሮች የሙያ ምግባር የሚጥስ ወይም ገለልተኛ በመሆን ከሙያ አንፃር ጉዳዩን መርምረው ማቅረባቸው አከራካሪ በሚሆንበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ በሌላ ባለሙያ እንዲጣራ ማድረግ ይጠበቅበታል። በያዝነው ጉዳይ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ባለሙያዎቹን ሲመድብ ነፃና ገለልተኛ የሆኑ ባለሙያዎች በመምረጥ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 136/1/ መሠረት ባላቸው ልዩ የሒሣብ እውቀት ሒሣቡን መርምረው መመደብ ሲገባው አመልካች የራሱን ባለሙያ እንንዲያቀርቡ ማድረጉ ተገቢነት አልነበረውም። ይግባኝ ሰሚው ችሎት ባለሙያዎቹ በጋራ ሒሣቡን ሠርተው እንዲያቀርቡ የሰጣቸውን ትእዛዝ ባለሙያዎቹ አላከበሩም። ባለሙያዎቹ የፍርድ ቤቱ ልዩ አዋቂ ምስክር ሆነው ከተሰሙ በኂላ ከሁሉም በላይ ለፍርድ ቤቱ ትእዛዝና መመሪያ ተገዥ በመሆን የሙያ ሥራቸውን ማከናወን አለባቸው የልዩ አዋቂ ሒሣብ አጣሪዎች የችሎቱ ትእዛዝና በመመሪያ መጣስ አመልካች የመደበው ባለሙያ የአመልካችን ክርክር በመደገፍ የሒሣብ ሪፖርት ተጠሪ የመረጠው ባሉሙያ ተጠሪን በመደገፍ የሒሣብ ሪፖርት አቅርበዋል።

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሁለቱም ምስክሮች ችሎቱ ከሰጣቸው ትእዛዝና መመሪያ ውጭ ሒሣቡን በተናጠል ሠርተው ሲያቀርቡለት የሁለቱንም ሪፖርት ውድቅ በማድረግ ሂሣቡ በሌላ ባለሙያ ወይም ኦዲት ለማድረግ በተቋቋመ ሕጋዊ ድርጅት በኩል ተጣርቶ እንዲቀርብ ትእዛዝ መስጠት ነበረበት። ይግባኝ ሰሚው ችሎት በሰጣቸው ትእዛዝና መመሪያ ተመርተው ሒሣቡን ያላጣሩ መሆኑን እያወቀና ችሎቱ ከሰጣቸው ትእዛዝ ውጭ ሁለቱም ባለሙያዎች በተናጠል የመሰላቸውን ሁለት የሂሣብ መግለጫ ካቀረቡለት በኂላ በአመልካች በኩል የተመረጠው ባለሙያ የቀረበው ጥቅል ሒሣብ ስለሆነ አሣማኝ አይደለም ከተጠሪ የተመረጠው ባለሙያ ያቀረበው ዝርዝር ሪፖርት ስለሆነ አሣማኝ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ስለ ልዩ አዋቂ አጣሪ አመዳደብና አሠራርና የተዘረጋውን ሥርዓትና የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 136 ድንጋጌን የሚቃረን በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል።
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ብቃት ያለው ገለልተኛ የሒሣብ ባለሙያ ወይም ፈቃድ ያለው የኦዲት ድርጅት በመመደብ ሒሣቡ ተጣርቶ እንዲቀርብ በማድረግ ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል።
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 58487

መጋቢት 22 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- ወ/ሮ አባይነሽ ገ/ህይወት - ወኪል ወ/ት ትዕግስት ደመወዝ - ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- ወ/ሮ እታገኝ ደሣለኝ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ ለሰበር የቀረበው ክርክር በፍትሐብሔር ክስ ክርክሩ ሊሰማ በተወሰነው ቀን ቀጠሮ ከሣሽ ወገን አልቀረበም ተብሎ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ተከሣሽ ተሰናብተዋል በተባለበት ጉዳይ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74/2/ መሠረት እንደገና ክሱ እንዲታይ ሣይጠየቅ በቀጥታ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኙ ቀርቦ ሊታይ የሚችል ስለመሆን አለመሆኑ የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው ደቡብ ጐንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሆኖ ከሣሽ የነበሩት የአሁኗ አመልካች ናቸው፡፡ ተከሣሾች የነበሩት ደግሞ ሀብታሙ ጌትነት እና የአሁኗ ተጠሪ ናቸው፡፡

1ኛው ተከሣሽ ሀብታሙ ጌትነትና የአሁኗ ተጠሪ እናትና ልጅ ናቸዉ፡፡ ከሣሽ ሁለቱን እናትና ልጅ በአንድነት የከሰሷቸው ልጅየው ሰርቆ ወስዷል የተባሉትን የተለያዩ የወርቅ ጌጣጌጦች ዋጋ ብር 13,490 እንዲከፍሏቸው ነው፡፡ የአሁኗ ተጠሪ ልጃቸው ሰርቋል በተባለው ወርቅ ጉዳይ ገንዘቡን ሊከፍሉ ይገባል ተብሎ የተከሰሱት በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2125 መሠረት ሃላፊነት አለባቸው በሚል ምክንያት ነው፡፡ ሁለቱ ተከሣሾች ክሱ ደርሷቸው በጽሁፍ መልስ ሰጥተው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ክርክሩ ሊሰማ በተወሰነው ቀን ቀጠሮ ከሣሿ የአሁኗ አመልካች ባለመቅረባቸውና የአሁኗ ተጠሪም በጽሁፍ በሰጡት መልስ ሃላፊ ልሆን አይገባም ብለው ክደው በመከራከራቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 ጋር በማገናዘብ መርምሮ የአሁኗ ተጠሪ ሃላፊነት የለባቸውም ወደሚለው ጭምር የገባ ቢሆንም በእርሳቸው ላይ ክሱ አይቀጥልም ብሎ አሰናብቷቸዋል፡፡ በመጨረሻም ፍርድ በሚለው የተወሰነውና መዝገቡም ሣይዘጋ የቆየው አንደኛው ተከሣሽ በጽሁፍ በሰጠው መልስ ወንጀሉን ስለመሠረቱ ማመኑ በፍትሐብሔር የቀረበበትን ክስም እንዳመነ ይቆጠራል ተብሎ በመወሰዱ ሲሆን በተሰጠው ፍርድም በክሱ ለተጠየቀው ገንዘብ ሃላፊነት አለበት ተብሎ ተወስኗል፡፡ የአሁኗ አመልካች 2ኛዋ ተከሣሽ የአሁኗ ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ታይቶ ከክሱ እንዲሰናበቱ የተደረገበትን የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ፍርድ በመቃወም በቀጥታ ለአማራ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን አቅርበው ፍ/ቤቱ



www.chilot.me

ግራ ቀኙ እንዲቀርቡ አድርጐ ክርክሩን ከሰሙ በኋላ መርምሮ በሰጠው ውሣኔ የአሁኗን ተጠሪ በሚመለከት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጨረሻ አጠቃሎ በሰጠው ፍርድ ክርክሩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀነ ቀጠሮ ከሣሿ ስላልቀረቡና ተከሣሿም በጽሁፍ በሰጡት መልስ ክሱን ስለካዱ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ታይቶ ተሰናብተዋል ስላለው ያነሣው ነገር ሣይኖር በቀጥታ ወደ ሃላፊነቱ ክርክር በመግባት በወቅቱ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ለሰረቀው ወርቅ በፍትሐብሔር በኩል ስላለው ሃላፊነት የልጁ እናት የአሁኗ ተጠሪ በፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 2125/1/ መሠረት ሃላፊነት አለባቸው ብሎ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት በመሻር ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ብር 13,490 ለአሁኗ አመልካች ሊከፍሉ ይገባል በሚል ወስኗል፡፡

ቀጥሎ ጉዳዩ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ ክርክሩን መርምሮ በሰጠው ፍርድ የደቡብ ጐንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኗ ተጠሪ በሚመለከት የክሱን መዝገብ የዘጋው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ስለሆነ ከሣሽም የአሁኗ አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.74/2/ መሠረት የክሱ መዝገብ ይከፈትልኝ የሚል ጥያቄ ሣያቀርቡ በቀጥታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን ያቀረቡት ትክክል አይደለም፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ወደ ፍሬ ነገሩ መግባት አልነበረበትም፤ ይግባኙን መቀበሉም የስነስርዓት ህጉን የተከተለ አይደለም በማለት በዚሁ ስነስርዓት ምክንያት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ አጽንቶታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የአማራ ክልላዊ መንግስት የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80/3/ መሠረት የቀረበ ሲሆን ጉዳዩም ለሰበር ችሎት የሚያስቀርብ ነው በመባሉ ግራ ቀኙ እንዲቀርቡ ተደርጐ መልስ እና የመልስ መልሱን በጽሁፍ በመለዋወጥ ክርክራቸውን አድርገዋል፡፡

ጉዳዩም ከህጉ ጋር ተገናዝቦ ተመርምሯል፡፡

ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የደቡብ ጐንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሁለተኛ ተከሣሽ የነበሩት የአሁኗን ተጠሪ በሚመለከት የክሱን መዝገብ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ነው የዘጋው ለማለት ይቻላል አይቻልም? የአሁኗን ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ነው ያሰናበታቸው የሚባል ሆኖ ከተገኘስ ከሣሽዋ የአሁኗ አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74/2/ መሠረት የመዝገብ ይከፈትልኝ ጥያቄ ሣያቀርቡ በመጨረሻ በተሰጠው ፍርድ መነሻ በቀጥታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረቡ ስነስርዓት ህጉን የተከተለነው የሚባል ነው ወይንስ አይደለም? የሚለውን በተመለከተ፡-

ከሣሽ የሆኑት የአሁኗ አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ክርክሩ በቃል ሊሰማ በተወሰነው ቀነ ቀጠሮ ሣይቀርቡ መቅረታቸውንና ሁለተኛ ተከሣሽ የነበሩት የአሁኗ ተጠሪ ደግሞ በጽሁፍ በሰጡት መልስ ሃላፊ ልሆን አይገባም ብለው ክሱን ሙሉ በሙሉ በመካድ መከራከራቸውን የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጨረሻ የሰጠው ፍርድ ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ የቀረበው ኮፒው የሚያስረዳ ሲሆን ፍ/ቤቱ በዚህ ፍርድ ላይ የአሁኗን ተጠሪ ክዶ የመከራከር ሁኔታ የተመለከተው የአሁኗ አመልካች ክርክሩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀነ ቀጠሮ ባለመቅረባቸው ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 ጋር በማያያዝ ነው፡፡ ፍ/ቤቱ በፍርዱም ላይ የጀመረው ከሣሽ ለቃል ክርክር ስላልቀረቡ መዝገቡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ተመርምሯል በማለት ነው፡፡ ቀጥሎም 2ኛዋ ተከሣሽ በጽሁፍም ሆነ



www.chilot.me

በቃል ሃላፊ ልሆን አይገባም ብለው ስለመከራከራቸው ከሣሽ ደግሞ በቃል ክርክሩ ላይ ቀርበው በዚህ ላይ ተቃውሞ እንዳላቀረቡ በመግለጽ 2ኛዋ ተከሣሽ ሃላፊነት የለባቸውም ብለናል በማለት ከክሱ አሰናብቷቸዋል፡፡ ከዚህም የአጻጻፍና የአገላለጹ ሁኔታ እንጅ 2ኛዋን ተከሣሽ የአሁኗን ተጠሪ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያሰናበታቸው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ መዝገቡ ወዲያውኑ ያልተዘጋው 1ኛ ተከሣሽ ክሱን አምኗል ተብሎ በመቀጠሉና ፍ/ቤቱም ውሣኔ ሊሰጥበት በማቆየቱ ነው፡፡ የአሁኗን ተጠሪ በሚመለከት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት የክሱ መዝገብ ተዘግቷል ለማለት የሚቻል ሆኖ ስለተገኘ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት የሰበር ክርክር ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡ ተጠሪን በተመለከተ የክሱ መዝገብ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ተዘግቷል የሚባል ሆኖ ከተገኘ ከሣሽዋ የአሁኗ አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74/2/ መሠረት ጥያቄ በማቅረብ እንደገና መዝገቡ ተከፍቶ ነገሩ እንዲቀጥል ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

አመልካች ይህንን ሣይፈጽሙ ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት በተሰናበቱበት ላይ በቀጥታ ይግባኝ ለማቅረብ የሚያስችላቸው ስነስርዓት የለም፡፡ የአማራ ክልላዊ መንግስት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔም ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

## ው ሣ ኔ

1ኛ/ የአማራ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 0469 ሐምሌ 5 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡

2ኛ/ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 59085

መጋቢት 05 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ብርሃኔ አዱላ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ግርማ አብዲሣ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለመመርመር ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜን አስመልክቶ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 323(2) የተደነገገውን ድንጋጌ አፈፃፀም ከግራ ቀኙ ክርክር አንፃር ተመልክቶ ተገቢውን ትርጉም ለመስጠት በሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካች ባቀረበቺው የአፈፃፀም ክስ መነሻ የጋምቤላ ከተማ ዙሪያ ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ 01161 መጋቢት 27 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ዳኝነቱን በትዕዛዝ መልክ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ትዕዛዝ ላይ የአሁን አመልካች ቅር ተሰኝተው ሚያዝያ 18 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ትዕዛዝ የተሰጠበት የመዝገብ ግልባጭ እንዲሰጣቸው ስለመጠየቃቸውና በጥያቄው መሠረት ግንቦት 11 ቀን 2002 ዓ.ም ግልባጩ እንደተሰጣቸው ትዕዛዙን በሰጠው ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ 01161 ግንቦት 11 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሸኚ ላይ ከተዘረዘረው መረዳት ችለናል፡፡

እንዲሁም ይህ ግልባጭ ከደረሳቸው በኂላ ሰኔ 02 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ ዝርዝር የይግባኝ አቤቱታ አዘጋጅተው ይግባኙን እንዳቀረቡ ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በአፈ/ይ/መ/ቁ 00978 ሰኔ 03 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ከሰጠው ዳኝነት ተገንዝበናል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው ለይግባኙ ምክንያት የሆነው ዳኝነት መቼ ተሰጠ፤ ይግባኝ ባይ ቅሬታ እንዳላቸው ገልፀው ግልባጭ እንዲሰጣቸው መቼ ጠየቁ፤ በጥያቄው መሠረት የመዝገቡን ግልባጭ ፍ/ቤቱ መቼ ሰጣቸው፤ ግልባጩ ከተሰጣቸው በኂላ የይግባኝ ቅሬታ አዘጋጅተው ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መቼ አቀረቡ፤ የሚለውን አስመልክቶ ለማረጋገጥ ማስረጃ ሆነው የቀረቡት በፍ/ቤቶች የተሰጡት ማረጋገጫዎች ከመሆናቸውም በላይ ተጠሪ ይህንን ለማስተባበል የሚያስችል የተለየ ክርክር አላቀረበም፡፡



www.chilot.me

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም የአመልካች የይግባኝ መዝገብ እንደቀረበለት ለይግባኙ ምክንያት የሆነው ዳኝነት የተሰጠበትን መጋቢት 27 ቀን 2002 ዓ.ም እና የይግባኝ ቅሬታ የቀረበበትን ሰኔ 02 ቀን 2002 ዓ.ም በፍሬ ነገር ረገድ የቀረቡትን ጊዜዎች መነሻ በማድረግ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 323(2) የተመለከተው የሁለት ወር የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በኋላ የቀረበ የይግባኝ መዝገብ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት መዝገቡን ዘግቶ አሰናብቷል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ዳኝነት የይግባኝ አቤቱታን አቀራረብ ጊዜን አስመልክቶ ከተቀመጠው ድንጋጌ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ሲል የበኩሉን ዳኝነት ሰጥቶበታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን፤ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ለጉዳዩ አግባብነት ባለው ድንጋጌ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 323(2) ላይ የይግባኝ አቤቱታ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መቅረብ የሚገባው ይግባኝ የሚባልበት ጉዳይ በተፈረደ በ60 ቀን ውስጥ ነው በማለት ተደንግጓል፡፡ የዚህን ድንጋጌ አነጋገር በቀጥታ ከወሰድን በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ይግባኝ የሚባልበት ፍርድ በተፈረደ በ60 ቀን ጊዜ ውስጥ መሆን ይኖርበታል ወደሚለው መደምደሚያ የሚያደርሰን በመሆኑ ተከራካሪው ወገን ግልባጭ በመጠየቅና በማግኘት ረገድ ያሳየው ጉድለት ሳይኖር ፍ/ቤቶች ባላቸው አሠራር ምክንያት የባከነውን ጊዜ ሁሉ በስሌት ውስጥ የሚያስገባ ሆኖ ስለሚገኝ ድንጋጌው ትርጉም የሚያስፈልገው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ድንጋጌው ሥነ ሥርዓታዊ እንደመሆኑ መጠን ሥነ ሥርዓታዊ ድንጋጌዎችን ሥራ ላይ በምናውልበት ጊዜ ትርጉም ካስፈለገ በተለይ የሥነ ሥርዓት ህግ ግብን መሠረት በማድረግ ውጤታማ እና ትርጉም ባለው አኳኋን ተግባራዊ ፋይዳውን በማየት ሌሎች መሠረታዊ ህጎችን ከምንተረጉምበት መደበኛ የአተረጓጎም ዘዴ በተለየ ሁኔታ ልንተረጉም ስለሚገባ ይህ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 323(2) ድንጋጌ በግልፅ የተቀመጠ ስለሆነ ትርጉም ሳያስፈልገው እንዳለ በሥራ ላይ ሊውል ይገባል የሚያሰኝ አይደለም፡፡

ስለሆነም ፍርድ እንደተፈረደበት ይግባኝ እንደሚጠይቅ ገልፆ የይግባኝ መጠየቂያ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ የመዝገብ ግልባጭ እስኪሰጠው ድረስ ያለው ጊዜ ለይግባኝ ማቅረቢያ ተብሎ ከተሰጠው 60 ቀን ስሌት ውስጥ ሊካተት አይገባውም፡፡

ይህ በፍ/ቤት አሠራር ምክንያት የባከነው ጊዜ ከይግባኝ ጥያቄው አቅም ውጭ የሆነና እንደበቂ ምክንያት ስለሚቆጠር የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ እንዳለፈበት በይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ አማካኝነት ይግባኙ እንዲቀርብ ያድርግ የሚለውን መስመር መከተል ይኖርብናል እንዳይባል ከላይ እንደተጠቀሰው አስቀድሞ ውጤቱ ለሚታወቅ ጉዳይ ትርጉም አልባ የሆነ ሥርዓት እንዲፈፀም ለማድረግ ብቻ ከሚሆን በቀር ተግባራዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ አይገኝም፡፡

ስለሆነም ይህ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 323(2) የተመለከተው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ይሰላ ከተባለ ፍርዱ በተፈረደበት ቀን እና ይግባኝ ጠያቂው የይግባኝ አቤቱታ ሊያቀርብ እንደሚፈልግ ገልፆ የመዝገብ ግልባጭ በጠየቀበት ጊዜ መካከል የባከነውን ጊዜ፣ የመዝገብ ግልባጭ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ የይግባኝ አቤቱታውን አዘጋጅቶ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እስካቀረበበት ድረስ የባከነውን ጊዜ በማስላትና በመደመር 60 ቀን ማለፉ እና አለማለፉ እንዲለይ በማድረግ ሊሆን ይገባል፡፡

ከዚህም አንፃር አሁን በእጅ ያለውን ጉዳይ ስንመለከት ፍርዱ ከተፈረደበት ከመጋቢት 27 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ የይግባኝ መጠየቂያ ለፍ/ቤቱ እስከቀረበበት እስከ ሚያዝያ 18/2002 ድረስ ያለው ጊዜ ሲታሰብ 21 ቀናት ያለፉ እንዲሁም ግልባጩ በአመልካች እጅ ከደረሰበት ከግንቦት 11 ቀን ጀምሮ የይግባኝ ቅሬታ ተዘጋጅቶ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እስከቀረበበት እስከ ሰኔ 02 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ 21 ቀናት ብቻ በድምሩ 42 ቀናት ብቻ ያለፉ እንጂ በህጉ የተቀመጠውን የ60 ቀን ጊዜ የተላለፈ ሆኖ ባለማግኘታችን የአመልካች የይግባኝ ጉዳይ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በኋላ የቀረበ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም በሚል የጋምቤላ ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሰበር ሰሚው ችሎት የሰጡት ዳኝነት ድንጋጌውን በመተርጎም ረገድ ትክክለኛውን የትርጉም መስመር የተከተለ ሆኖ ስላላገኘነው የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የጋምቤላ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአፊ/ሰ/መ/ቁ 00005 ሐምሌ 01 ቀን 2002 ዓ.ም እና ጠቅላይ ፍ/ቤቱ በአፊ/ይ/መ/ቁ 00978 በ03/10/2002 ዓ.ም የሰጡትን ትዕዛዞች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ሽረናል፡፡
2. የአመልካች የይግባኝ አቤቱታ የማሰማት መብታቸው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜውን ያለፈ ሆኖ አልተገኘም፡፡
3. የአመልካችን የይግባኝ ጉዳይ ተቀብሎ እንደ ሥርዓቱ ማየት ይቀጥል ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሠረት ወደ ጋምቤላ ከተማ ዙሪያ ከፍተኛ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡
4. ይህ የሰበር ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡን ዘግተናል፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

ራ/ታ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 59294

መጋቢት 19 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች** :- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** :- አቶ በቀለ ጃፋር - ቀረቡ

**ተጠሪ** :- እነ ወ/ሮ ሙሉነሽ ማሞ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክርክርን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪዎች ናቸው፣ ተከሣሽ ደግሞ አመልካች ነበሩ፡፡ ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ይዘቱ ሲታይ የእናታችንን የውርስ ሀብትና ይዞታ አመልካች ይዞ ስለሚገኝ እንዲለቅልን ይወስንልን የሚል ሲሆን የአሁን አመልካች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረቡት የውርስ ሀብት ይገባናል ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ የውርስ ሀብቱን ያልያዙ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የሱልልታ ወረዳ ፍርድ ቤትም በአመልካች በቀረበው የይርጋ መቃወሚያ ብይን ሳይሰጥ በማለፉ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅረበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት በአመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ብይን ሳይሰጥ ማለፉ ሥነ ስርዓቱን የተከተለ አይደለም በማለት በስር ፍርድ ቤት የተፈፀመውን የስነ ስርአት ግድፈት በማረም በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ብይን እንዲሰጥ ጉዳዩን መልሶታል፡፡ ከዚህም በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የአመልካች ማስረጃ እንዲሰሙ ያዘዘ መሆን ያለመሆኑን ማብራሪያ እንዲሰጥና ትእዛዙንም አመልካች አድርሰው ማብራሪያውን እንዲያቀርቡ የስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሰጥቶ አመልካች ይህንኑ ትዕዛዝ አልፈፀሙም፣ ይልቁንም ቀድሞ ዘርዝረው ያላቀረቡትን የመከላከያ ማስረጃ ዝርዝር አቅርበዋል በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡



www.chilot.me

አመልካች ነሐሴ 11 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፉት ሦስት ገፅ የሠበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ብይን ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የፅሑፍ መልሳቸው ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ወሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ አመልካች ተጠሪዎች ባቀረቡባቸው የውርስ ንብረት ይልቀቅልን የዳኝነት ጥያቄ የይርጋ ክርክር አንስተው የሥር ፍርድ ቤት በዚሁ ላይ ብይን ሳይሰጥ በማለፉ የበላይ ፍርድ ቤት በአመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ተገቢው ብይን እንዲሰጥ ለስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከመለሰለት በሁዋላ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ብይን ለመስጠት ማስረጃ መስማት እንደአለበት የስር ፍርድ ቤት አምኖ ተገቢ ነው ያለውን ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ወደዚህ ድምዳሜ የደረሰው ይግባኙን ተመልክቶ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ተገቢው መጣራት ተደርጎ ብይን ሊሰጥበት ይገባል በማለት ውሣኔ የሰጠው የበላይ ፍርድ ቤት ተገቢው መጣራት ተደርጓል ሲል ማስረጃ ተሰምቶ መሆን ያለመሆኑን ማብራሪያ እንዲሰጥበት፣ ይህንኑም አመልካች ተከታትለው እንዲያስፈፅሙ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቶ አመልካች ይህንኑ ትዕዛዝ ሳያስፈፅሙ አዲስ የማስረጃ ዝርዝር አቅርበዋል በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሰረት ያደረገው የጊዜ ማለፍ ሲሆን ይህ የጊዜ ማለፍ ደግሞ ተጠሪዎች ካቀረቡት ክስ ባሕርይ እና ክስ ከተመሰረተበት ጊዜ አንፃር ታይቶ አግባብነት ባለው ሕግ ምላሽ የሚሰጠው ከመሆን ውጪ የተከሣሽ ማስረጃ ሊሰማ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለው ነው፡፡ ተጠሪዎች የጊዜውን ማለፍ አምነው የይርጋ ጊዜውን ሊያቋርጡ የሚችሉ ሕጋዊ ምክንያት ያላቸው ስለመሆኑ ጠቅሰው ተከራክረው አመልካች ይህንኑ ሊያስተባብል የሚችል ክርክርና ማስረጃ ያላቸው ስለመሆኑ ጠቅሰው መከራከራቸውን የሚያሳይ የክርክር ሂደትም የለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ብይን እንዲሰጥ ይግባኙን የተመለከተው የበላይ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሲሰጥም በጊዜው ማለፍ ላይ ማስረጃ እንዲሰማ ብሎ የገለፀው ነገር የሌለ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም በአመልካች በኩል የይርጋ ጊዜ አልፏል በሚል የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው መሆን ያለመሆኑን የክሱን አይነትና ክሱ የቀረበበትን ጊዜ ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማዛመድ ብይን የሚሰጥበት ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤት የሰው ማስረጃ መቅረብ አለበት ያለበት አግባብ ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖረው መሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ ይህ ደግሞ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 244/2/ሠ/ እና 234 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ እንዲሁም አላማቸውን ያላገናዘበ ከመሆኑም በላይ የአመልካችን የመከራከር መብት ያጣበበ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ ከተመለሰለት በሁዋላ መዝገቡን የዘጋበት ሥርዓት መሰረታዊ የሆነ የሥነ ስርዓት ሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በሱልልታ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12832 ጥር 06 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00520 መጋቢት 09 ቀን 2002 ዓ.ም.፣ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 103687 ሐምሌ



www.chilot.me

03 ቀን 2002 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካች ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የተጠሪዎችን የክስ አይነትና ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለውን ሕግ መሰረት በማድረግ ተገቢው ብይን ከሚሰጥበት በስተቀር የአመልካች የመከላከያ ማስረጃ እንዲሰማ የሚደረግበት ህጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. የሱልልታ ወረዳ ፍርድ ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ ጉዳዩን ከዚህ በፊት ባላዩት ዳኛ እንዲታይ በማድረግና በአመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ተገቢውን ብይን በመስጠት ጉዳዩን እንዲዳኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341/1/ መሰረት ተመልሶለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ግራ ቀኙ ለአደረጉት ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ጽ/ሸ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 62330

ሚያዚያ 03 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ዋልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ነጋ ዱፍሣ

**አመልካች፡-** አቶ አዱኛ አጃው የቀረበ የለም፡፡

**ተጠሪ፡-** ቀስቅስ አየነው የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የከብቶች ግምት ይከፈለኝ ጥያቄን የሚመለከት ስሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪና ለጉዳዩ ዋስትና ገብተውላቸዋል በሚሏቸው ግለሰብ ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካች የስር ክስ ይዘትም ባጭሩ፡- የግላቸው የሆኑት ሶስት ከብቶች ጠፍተውባቸው ተጠሪን ጠርጥረው በሽማግሌ ሲጠይቋቸው በቤተክርስቲያን ለመማማል ፈቃደኛ ከሆኑ በኋላ እንደገና አልምልም፣ ወስጀአለሁ በማለት አምነው መስከረም 25 ቀን 2000 ዓ/ም በተደረገ ስምምነት መሰረት ብር 8000.00 (ስምንት ሺህ ብር) ለመክፈል መስማማታቸውን፣ ተጠሪ ይህንኑ ባይከፍሉ ደግሞ በስር ሁለተኛ ተከሣሽ የነበሩት አቶ ባበዩ ሲሳይ የተባሉት ግለሰብ የዋስትና ግዴታ መግባታቸውን፡ ሆኖም በውሉ መሰረት ገንዘቡ ያልተከፈላቸው መሆኑን ዘርዝረው የከብቶቹ ግምት የሆነው ብር 8000. (ስምንት ሺህ ብር) እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም ጉዳዩ ቀድሞ በማህበራዊ ፍ/ቤት ቀርቦ ውድቅ የተደረገ መሆኑን ገልጸው ክሱ በድጋሚ ሊቀርብ እንደማይገባ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሱ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ ውሉን በሃይል የፈረሙ መሆኑን ገልፀው ሕጋዊ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የተጠሪን መከራከሪያ ውድቅ አድርጎ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ ብቻቸውን እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላም ተጠሪ ይግባኛቸውን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸውን ከክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበውም ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ጉዳዩ ቀድሞ የማሕበራዊ ፍርድ ቤት ቀርቦ ያለቀ ነው በሚል ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር እቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም ለክሱ መሠረት የሆነው የመስከረም 25 ቀን 2000 ዓ.ም ውል ሆኖ እያለ በ1998 ዓ/ም በቀበሌ ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ አግኝቷል ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው በማለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ እንዲሻር ዳኝነት



www.chilot.me

መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ በመታመኑ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የጽሑፍ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የአመልካች ክስ በቀበሌ ማሕበራዊ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ሆኖ አግኝተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መዝገንዘብ የተቻለው አመልካች ለክሳቸው መሰረት ያደረጉት መስከረም 25 ቀን 2000 ዓ.ም ተደረገ የተባለውን ውል ሲሆን የቀበሌ ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ውሳኔ ስለመስጠቱ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተገለፀው በ1998 ዓ/ም ተደረገ የተባለው ስምምነት መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ መስከረም 25 ቀን 2000 ዓ.ም የተደረገ ውል ስለመኖሩ ሳይክዱ በኃይል የተደረገ ነው በማለት የሚከራከሩ ሲሆን ይህንኑ እንዲያስረዱ እድል ተሰጥቷቸው በቀነ ቀጠሮው እለት ችሎት ሳይቀርቡ የቀሩ መሆኑን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ ከመዘገበው ተገንዝበናል፡፡

በመሠረቱ የፍትሐብሔር የክርክር አመራር ሥርዓት ዓይነተኛ ዓላማ የክርክርን ሂደት ለማቀላጠፍና አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ መቋጫ ለማበጀት መሆኑ ይታመናል፡፡ የፍትሐብሔርን ክርክር አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ እልባት እንዲደረግበት በማቀድ ከተደነገጉት የፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ጽንሰ ሐሳቦች አንዱ የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች /Res judicata/ የሚለው ሲሆን ይህ ጽንሰ ሀሣብ በ1958ቱ የፍትሐ ብሔር ሥነ ስርዓት ሕጋችን ውስጥ በቁጥር 5 ድንጋጌ ስር በግልጽ ተቀምጦ እናገኘዋለን፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች ማለት በማናቸውም መልክ በሕግ በተቋቋመ ፍ/ቤት ቀርበው የመጨረሻ ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮችን የሚሸፍን መሆናቸውንና በፍርድ፣ በብይን፣ በውሣኔ፣ በትእዛዝ፣ ወይም በጊዜያዊ አገለግሎት ባለው ትእዛዝ የመጨረሻ ውጤት አግኝተው በሌላ መልክ ለመንቀሣቀስ የማይችሉ የክርክር ነጥቦችን ሁሉ የሚያጠቃልል ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 5 ሥር በተመለከተው አኳኋን አንድ ጉዳይ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት መረጋገጥ ካለባቸው ሁኔታዎች ውስጥ፡- ቀደም ሲል ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የነበሩ ጉዳዮች በድጋሚ በቀረበው ክስም ላይ በቀጥታ በፍሬ ነገር ጭብጥ ሆነው መቅረባቸው ፣ቀደም ሲል የነበረው ክርክር አሁን በክርክር ተሳታፊ በሆኑ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወይም ተለለፎላቸው በነበረ ወገኖች መሆኑንና እነዚህ ጉዳዮች ቀደም ሲል በተካሄደው ሙግት የመጨረሻ ፍርድ ያረፈባቸው መሆኑን ነው፡፡

ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ በመጨረሻ ፍርድ መቃወሚያነት ሲቀርብ ተቀባይነት የሚኖረው ይኸው ጉዳይ በድጋሚ በቀረበው ክርክር ላይ መቅረቡ ሲረጋገጥ ነው፡፡ “ … ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ …” የሚለው ሐረግ አጠቃላይ ይዘቱ ሲታይም በመጀመሪያው ክርክር ላይ ከአንደኛው ወገን ተጠይቆ በሌላኛው ወገን የተካደ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የታመነና በዚሁ ላይ የፍርድ ውሣኔ ያረፈበት የክርክር ነጥብ ነው፡፡ በመሆኑም በድጋሚ በቀረበው ክስ በቀድሞው ክርክር ተሣታፊ በነበሩ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወገኖች በሚካሄድ መሆኑና በሁለተኛው ክስም የተያዘው የፍሬ ነገር ጭብጥ ከመጀመሪያው ጋር ተመሣሣይ ሆኖ የመጨረሻ ፍርድ ያረፈበት መሆኑ ከተረጋገጠ እንደሁም ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ አርፎበታል የሚል

ተቃውሞ በተከራካሪ ወገን ከተነሣ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 እና 244(2) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በ15/07/2000 ዓ.ም ለሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ መሠረት ያደረጉት ከተጠሪ ጋር መስከረም 25 ቀን 2000 ዓ/ም ተደረገ የተባለውን ውል ሲሆን ይህ ውል በ1998 ዓ.ም ቀበሌ ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ሊቀርብ እንደማይችል የጊዜው ቅደም ተከተል በራሱ አስረጂ ነው፡፡ ተጠሪ መስከረም 25 ቀን 2000 ዓ/ም የተደረገውን ውል ስለመኖሩ የካዱት ሳይሆን ውሉ በሕግ ጥበቃ ሊደረግለት አይገባም ያሉትን የኃይል ተግባር ጠቅሰው ቢከራከሩም በማስረጃ ያረጋገጡት ፍሬ ነገር አለመኖሩን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ነጥብ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች በአቤቱታ ጽሑፋቸው የገለፁትና የዘረዘሩት ፍሬ ነገር በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ቀርቦ ነበር ከተባለው ጉዳይ ጋር ሲነፃፀር የተለየ ፍሬ ነገር ነው፡፡ በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 መሠረት የመጨረሻ ፍርድ ያረፈበት ጉዳይ ነው ሲል የበታች ፍ/ቤቶችን ውሳኔ መሻሩ ባግባቡ ባለመሆኑ ውሳኔው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የአማራ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ/ 4248 ጥቅምት 11 ቀን 2003 ዓ.ም የሠጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በሰሜን ጎንደር አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 25638 ታህሳስ 06 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 25316 ጥቅምት 03 ቀን 2003 ዓ/ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/348(1) መሰረት ጽንቷል፡፡
3. አመልካች መጋቢት 15 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የአቤቱታ ጽሑፍ (ክስ) መሠረት ያደረጉት መስከረም 25 ቀን 2000 ዓ.ም ተደረገ የተባለውን ውል በመሆኑ የመጨረሻ ፍርድ ያገኘ ጉዳይ አይደለም ብለናል፡፡
4. ተጠሪ ብር 8000.00 (ስምንት ሺ.ህ ብር) ከመጋቢት 15 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ከሚታሰብ ዘጠኝ ከመቶ /9%/ ወለድ ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ብ



www.chilot.me

# ባንክና
# ኢንሹራንስ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 41535

ጥቅምት 3 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**:- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች**:- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ተሾመ መኩሪያ ቀረበ

**ተጠሪዎች**:- 1. ግሎሪ የኃላነቱ/የተ/የግል ማህበር -ጠበቃ ዓብደላ ዓሊ ቀረቡ

2. ማታዶር አዲስ ጎማ - ማርዩ ማንደፍሮ ቀረቡ

3. ኩሪፍቱ ኃ/የተ/የግል ማህበር

4. ብርሃነ በርሀ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የኔ ባልሆነ ሐሰተኛ ፊርማ እና ማህተም መሠረት ተደርጎ ከኔ የባንክ ሂሣብ ላይ ገንዘብ ወጪ ሆኖብኛል በማለት 1ኛ ተጠሪ ያቀረበውን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ የሁሉንም ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከእነወለዱ ለ1ኛ ተጠሪ ይክፈል በማለት በአንድ በኩል ሲወስን፤ በሌላ በኩል ደግሞ 4ኛ ተጠሪ ገንዘቡን ለአመልካች ይተካለት በማለት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በውሣኔው ባለመስማማት ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የነበረ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ይግባኝ የተባለበት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ህዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚልባቸውን ምክንያቶች በመግለጽ ውሣኔው ይታረምለት ዘንድ ጠይቆአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት የቀረቡት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ብቻ ሲሆኑ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪ ባለመቅረባቸው ክርክሩ የተሰማው በሌሉበት ነው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው ገንዘቡ ከባንክ ወጪ ሊሆን የቻለው የ1ኛ ተጠሪ ሠራተኛ በሆነው 4ኛ ተጠሪ ሆኖ ሣለ አመልካች ለገንዘቡ መውጣት ኃላፊ ነው መባሉ አግባብ ነው ወይ? የሚለውን ጭብጥ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ



www.chilot.me

መሠረትም ግራ ቀኝ ወገኖች ጭብጡን በማስመልከት ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር እና ከተሰጠው ውሣኔ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው ለክሱ ምክንያት የሆነው ገንዘብ በተጭበረበረ መንገድ ከባንክ ሊወጣ የቻለው የ1ኛ ተጠሪ ሠራተኛ በሆነው በ4ኛ ተጠሪ አማካይነት ነው፡፡ 4ኛ ተጠሪ የ1ኛ ተጠሪን ምክትል ሥራ አስኪያጅ ፊርማ እና የኩባንያው /1ኛ ተጠሪ/ ማህተም አስመስሎ በተዘጋጀ ሲፒዮ እና የክፍያ መጠየቂያ ለባንኩ /አመልካች/ እንዳቀረበ፣ ይህን ሰነድ ያቀረበው በሁለት የተለያሉ ጊዜያት ማለትም የብር 420,000 ክፍያ የታዘዘበት የመጀመሪያው በጃንዋሪ 8 ቀን 2005 /እ.ኢ.አ/ ታህሣሥ 30 ቀን 97 ዓ.ም/፤የብር 347,206.63 ክፍያ የታዘዘበት ሁለተኛው ደግሞ በማርች 17 ቀን 2005/እ.ኢ.አ. መጋቢት 8 ቀን 97 ዓ.ም/ እንደሆነ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጦአል፡፡ ክፍያዎቹም የተፈፀሙት እንደዚሁ እንደአመጣጡ ነው፡፡

1ኛ ተጠሪ ክሱን የመሠረተው ታህሣሥ 25 ቀን 99 ዓ.ም ሆኖ ለገንዘቡ በተጭበረበረ መንገድ መውጣት ኃላፊነት መውሰድ ያለበት ባንኩ ነው በማለት የተከራከረውም የሚጠበቅበትን ጥንቃቄ አላደረገም፡፡ የሰነዶቹን ትክክለኛነት ሣያረጋግጥ እና እኔን /ከሣሽን/ ሣያሣውቅ ከፍሎአል የሚሉትን ምክንያቶች መሠረት በማድረግ ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ገንዘቡን ለታዘዘላቸው ወገኖች እንዲተላለፍ/ እንዲከፈል/ ያደረግሁት የባንኩን የተለመደ አሠራር እና ሥርዓት በመከተል ተገቢውን ጥንቃቄ ከወሰድኩ በኂላ ነው፡፡ በሰነዶቹ ላይ ያለው ፊርማ እና ማህተም ትክክል አለመሆኑን ለመጠራጠር ወይም ለማወቅ የምችልበት የተለየ ሁኔታ አልነበረም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በሕጉ እና በተለመደው አሠራር መሠረት ለ1ኛ ተጠሪ የባንክ ወርሃዊ የሂሣብ መግለጫ እየላከለት እና ከሂሣቡ ላይ ገንዘቡ መቀነሱን ሲያሣውቀው እንደቆየ፤ ይህም ሁኔታውን ለማወቅ የሚያስችለው ሆኖ ሳለ 1ኛ ተጠሪ ግን የራሱ ሠራተኛ ላይ ጥንቃቄ አለማድረጉን በመግለፁም ተከራክሮአል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ባየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተደረገው የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር ተጠቃሎ ሲታይ ከላይ የተመለከተው ሲሆን፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም "ተከሣሽ ባንክ ለክሱ መሠረት የሆነውን ሲፒዮ በከሣሽ ስም ሲዘጋጅ እና ክፍያ ሲፈፀም ተገቢውን የተለመደ የባንክ አሰራር ተከትሎአል አልተከተለም?" የሚል ጭብጥ በመያዝ ክርክሩን መርምሮአል፡፡ በውሣኔው ላይ በግልጽ እንዳመለከተው ከቀረበለት ማስረጃ አንፃር አመልካች /ባንኩ/ ተገቢውን የተለመደ የባንክ አሠራር አልተከተለም፣ ገንዘቡን የከፈለው ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ እና ቅን ልቦናን ተከትሎ አይደለም እሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርስ አልቻለም፡፡ አመልካችን ኃላፊ በማድረግ ሊወስን የቻለው የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መ.ቁ. 25306 በሰጠው ውሣኔ የገንዘቡ አደራ ጠባቂ የሆነው ባንክ አደራ አስቀማጭ የሆነው ባለሂሣብ ሣይጠይቅ ወይም ሕጋዊ ትእዛዝ ሣይሰጥበት ገንዘቡ በተጭበረበረ መልኩ ወጪ ከሆነ የተጭበረበረው አደራ አስቀማጩ ባለሂሣብ ሣይሆን፣ አደራ አስቀማጩ ባንክ ነው በማለት ለሥር ፍ/ቤቶች ገዢ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶአል በማለት እና ከሣሽ በተከሣሽ ባንክ ካለው ሂሣቡ ውስጥ ያለእሱ ትእዛዝ እና እውቅና ወጪ እንደሆነበት ሰነዱን በማስመርመር አረጋግጦአል የሚል ምክንያት በመስጠት ነው፡፡

ቀደምሲል እንደተገለፀው ለባንኩ የቀረቡት ሰነዶች በማስመሰል የተዘጋጁ እንጂ እውነተኛ አይደሉም ስለተባሉ ነው 1ኛ ተጠሪ ወደ ክስ ያመራው በመሆኑም አከራካሪ የሚሆነው እና በውሣኔ እልባት ማግኘት ያለበት ሰነዶቹ የተጭበረበሩ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለው ሣይሆን፣ አመልካች



www.chilot.me

ሰነዶቹን መሠረት በማድረግ ክፍያ የፈፀመው የባንኩን የተለመደ አሠራር ሣይከተል እና ተገቢውን ጥንቃቄ ሣያደርግ ነው ወይ? የሚለው ነው፡፡ ይህ ነጥብ የፍሬ ነገር ጭብጥንም የሚመለከት በመሆኑ የሚነጥረው በማስረጃ ነው፡፡ ጭብጡን በማስረጃ የማንጠር ሥልጣን ያለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ተገቢውን ጥንቃቄ ሣያደርግ ወይም የባንኩን የተለመደ አሠራር ሣይከተል ገንዘቡ እንዲከፈል አድርጎአል እሚል መደምደሚያ ላይ አልደረሰም፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ ረገድ ኃላፊ ሊያደርገው የሚችል ጥፋት ወይም የሕግ /የሥርዓት/ ጥሰት አልፈፀሙም ማለት ነው፡፡

በመቀጠል የሚታየው የሰበር ችሎቱ ሰጠው የተባለው የሕግ ትርጉም ነው፡፡ በሰበር መ.ቁ. 25306 የተሰጠውን ውሣኔ አስቀርበን ተመልክተነዋል፡፡ በመጀመሪያ የተገነዘብነው በዚህ መዝገብ /ቁ.25306/ የነበረው ክርክር እና የተያዘው ጭብጥ አሁን በያዝነው ጉዳይ ከተነሣው ክርክር እና ጭብጥ የተለየ እንደሆነ ነው፡፡ በሰበር መ.ቁ. 25306 ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ክስ በፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ ሣይኖር ውሣኔ እንደተሰጠ በማስመሰል እና የተጭበረበረ የፍ/ቤት ትእዛዝ በማቅረብ ገንዘብ ከባንክ ወጪ ሆኖአል የሚል መነሻ ያለው ነው፡፡ ተከሣሾች የነበሩትም ፍ/ቤት እና ባንክ ናቸው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የተገነዘብነው እና ዋናው ቁም ነገር ደግሞ የሰበር ችሎቱ በተጭበረበረ መንገድ ከባንክ ገንዘብ ወጪ በሆነ ቁጥር ያለምንም ምክንያት ባንኩ ኃላፊ ይሆናል የሚል የሕግ ተርጉም አለመስጠቱን ነው፡፡ እንደሚታወቀው ክርክሮች የሚወሰኑት እንደ የግል ባህሪያቸው እየታየ ነው፡፡ በአንድ ጉዳይ የተነሣውን ክርክር እልባት ለመስጠት የተሰጠ ውሣኔ በሌላ ጉዳይ ለተነሣው ክርክርም እልባት ለመሰጠት ያስችላል ብሎ ሙሉ በሙሉ መደምደም ትክክልም ተገቢም አይደለም፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ወደ ድምዳሜ የደረሰው የሰበር ችሎቱ ለውሣኔው መሠረት ያደረገው የፍሬ ነገር እና የሕግ ምክንያት በዝርዝር ሣይመለከት እንደሆነ ነው በበኩላችን መገንዘብ የቻልነው፡፡ በመሆኑም የሰበር ችሎቱ በሰጠው የሕግ ትርጉም ነው በሚል አመልካችን ኃላፊ ማድረጉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ቀደም ሲል ተሰጠ በተባለው ውሣኔም ሆነ በሰበር ችሎቱ እምነት ባንክ በተጭበረበረ መንገድ ለወጣ ገንዘብ በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችለው የተለመደውንና ተገቢውን የባንክ አሠራር ሣይከተል ወይም ተገቢውን ጥንቃቄ ሣያደርግ ከፍሎ ከተገኘ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ባንኩ / አመልካች/ ገንዘቡን የከፈለው አሠራሩንና ሥርዓቱን ተከትሎ ነው፡፡ ስለዚህም አመልካችን ኃላፊ በማድረግ የተሰጠው ውሣኔ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 51654 ሚያዝያ 28 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 38080 ህዳር 8 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ እንዲከፍል የሚገደድበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ የቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 50199

ታህሳስ 27 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ግሎባል ኢንሹራንስ ኩባንያ አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** አቶ አያሌው ወርቁ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የመድን ውልን የተመለከተ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው ተጠሪ በመሠረቱት ክስ ነው፡፡ የተጠሪ የክስ ምክንያት አመልካች የመድን ሽፋን የሰጠው የተጠሪ ንብረት የሆነ ታርጋ ቁጥር 3-10953 የሆነ መኪና የመኪናው ሹፌር ረዳት የነበረው አቶ በሪሁን ገ/ሚካኤል ፈቃድ ሳይሰጠው ቁልፍ ሰርቆ ለማሽከርከር ሲሞክር መኪናውን ከቴሌኮሙንኬሽን ፖል ጋር በማጋጨት ጉዳት ስላደረሰበት ለጥገና እና ሌሎች ወጪዎች የወጣ በድምሩ ብር 146,998.50 አመልካች እንዲከፍል እንዲወሰን የሚል ሲሆን በአመልካች በኩል ስር ፍ/ቤት የቀረበው ክርክር ለመኪናው የመድን ሽፋን የሰጠ መሆኑን አምኖ መኪናው ላይ ጉዳት የደረሰው ረዳቱ መንጃ ፈቃድ ሳይኖረው ሲያሽከረከር በመሆኑ እና ይህም በመድን ውሉ ክፍል 1 እና 2 መድን ሰጪን በሃላፊነት የማያስጠይቅ ስለመሆኑ እና ረዳት የመኪናውን ቁልፍ ሰርቋል ሊባል አይችልም በሚል ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኂላ መድን ሰጪ በመድን ውል ማግለያ አንቀጽ መሠረት ከሃላፊነት ሊድን የሚችለው የሹፌሩ ረዳት መኪናውን ያሽከረከረው ተጠሪ /ከሳሽ/ አውቀውና ፈቅደው ስለመሆኑ አመልካች ማስረዳት ሲችል ብቻ ነው፤ ነገር ግን በዚህ ረገድ አመልካች /ስር ተከሳሽ/ አላረጋገጠም በማለት ሃላፊነት አለበት ሲል ወስኗል፡፡ እንዲሁም ጉዳት የደረሰው በተጠሪ ሠራተኛ ጥፋት ስለሆነ በንግድ ሕግ አንቀጽ 664/1/ መሠረት አመልካች ለደረሰው ጉዳት መድን የመሰጠት ሃላፊነት አለበት ብሏል፡፡ በዚሁ አግባብ ክስ የቀረበበት ገንዘብ እንዲከፍል ፈርዷል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳት ያደረሰው ሰራተኛ የመንጃ ፈቃድ አለው ወይስ የለውም? እና የመድን ፖሊሲ ክፍል 1ና2 ማግለያ ሁኔታ በአግባቡ ተተርጉሟል ወይስ አልተተረጎመም የሚሉትን ነጥቦች ለመመርመር ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ ጠበቃ መጋቢት 15 ቀን 2002ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅረበዋል፡፡ በይዘቱም ሲታይ የመኪናው ሹፌር ረዳት ተጠሪ ሳይፈቅዱና ሳይስማሙ የመኪናውን ቁልፍ ሹፌሩ ደብቆ ካስቀመጠበት አንስቶ ለማሽከርከር ሲሞክር አደጋ የደረሰ ስለመሆኑ በመግለጽ ለደረሰው አደጋ የማግለያ አንቀጹ ተፈፃሚነት ሊኖረው እንደማይገባ እንዲሁም በንግድ ህግ አንቀጽ 664/1/ መሠረት አመልካች ሃላፊ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከተው ነው፡፡

እኛም ለዚህ ሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘውን ጭብጥ መሠረት አድርገን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው አመልካች ለተጠሪ መኪና የመድን ሽፋን መስጠቱ አላከራከረም፡፡ የተጠሪ መኪና ላይ ጉዳት የደረሰው በሹፌሩ ረዳት እንደሆነም ተረጋግጧል፡፡ የሹፌር ረዳት መኪናውን ለማሽከርከር የሚያስችለው የመንጃ ፈቃድ እንደሌለውም በስር ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡

ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ክስ ሲያቀርብም ሆነ እዚህ ሰበር ችሎት ሲከራከር የሹፌር ረዳት የመኪናውን ቁልፍ ሰርቆ ነበር መኪናውን ሊያሽከረክር የሞከረው በማለት ነው፡፡ እነዚህን በስር ፍ/ቤቶች የተረጋገጡትን እና የቀረቡት ክርክሮች መሠረት በማድረግ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የመድን ውል ክፍል 1 እና 2 በአግባቡ ተተርጉሟል ወይስ አልተተረጎመም የሚለውን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የመድን ውል ፖሊሲ ለክፍል 1ና2 ልዩዎች በሚል "ኩባኒያው ለሚከተሉት ማንኛቸውም ክፍያ የመክፈል ሃላፊነት አይኖርበትም" በሚለው ርዕስ ስር በንዑስ አንቀጽ ሁለት ------ በመድን ገቢው ወይም በመድን ገቢው እውቅናና ስምምነት በሌለ ግለሰብ ከፈቃድ ሰጪ ባለስልጣን ወይም በሌላ ሕግና ደንብ ለማሽከርከር ፈቃድ ሳይኖረው ወይም በአስካሪ መጠጦችና እጾች ተፅዕኖ ስር ሆኖ ሲሽከረከር በሚፈጠርና በሚደረስ አደጋ፣ ጉዳት፣ ብልሽትና ኃላፊነት በማለት ያመለክታል፡፡

አመልካች በዚህ የማግለያ አንቀጽ መሠረት ሃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡ የተጠሪ መኪና ላይ ጉዳት የደረሰው በሹፌሩ ረዳት ሲሽከረከር መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የሹፌሩ ረዳት መንጃ ፈቃድ የለውም፡፡ ከፍ ሲል በተጠቀሰው የማግለያ አንቀጽ መኪናው መንጃ ፈቃድ በሌለው ሰው ሲሽከረከር ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ መድን ሰጪው ሃላፊነት እንደሌለበት ተጠሪ ፈቅዶ ውል ገብቷል፡፡ በሌላ በኩል መኪናውን ያሽከረከረው ረዳት የተጠሪ እውቅናና ስምምነት ሳይኖር ስለመሆኑ ለማስረዳት ተጠሪ ስር ፍ/ቤት ያቀረቡት የፍሬ ነገር ክርክር የመኪናውን ቁልፍ ረዳቱ ሰርቆ ነበር የሚል ሲሆን እንደ ክርክሩ አቀራረብ የመኪናው ቁልፍ በረዳቱ የተሰረቀ ስለመሆኑ ተጠሪ በማስረጃ አላረጋገጠም፡፡

ተጠሪ እንደክሱ አቀራረብ ፍሬ ነገሩ ስለመኖሩ ማስረዳት ግዴታ እንዳለበት የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 2001/1/ ይዘት ያመለክታል፡፡ ተጠሪ የማስረዳት ግዴታውን ባልተወጣበት ሁኔታ ረዳቱ መኪናውን ያሽከረከረው በተጠሪ እውቅናና ስምምነት ስለመሆኑ አመልካች አላስረዳም ሲል የስር ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ከተጠቀሰው ሕግ መንፈስና ይዘት ጋር የሚጣጣም አይደለም፡፡

ስለሆነም መኪናው ከተጠሪ ፈቃድና ስምምነት ውጪ ተሰርቆ በረዳቱ ይሽከረከር የነበረ ስለመሆኑ ተጠሪ ሳያስረዳ በተቃራኒው አመልካች የማስረዳት ግዴታ እንዳለበት የስር ፍ/ቤት የወሰደው አቋም የስር ከሳሽ /ተጠሪ/ የማስረዳት ሸክምን ያለአግባብ ወደ ተከሳሽ /አመልካች/ ያስተላለፈ ስለሆነ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ ነው ለማለት ችለናል፡፡

በሌላ በኩል የሥር ፍ/ቤት ለውሳኔው ምርኩዝ ያደረገው የንግድ ሕግ ቁጥር 664/1/ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ ይዘት መሠረት መድን ገቢው ሃላፊ የሚሆንባቸው ሰዎች ባደረጉት ጥፋት ምክንያት ለሚደርስ ጉዳት መድን ሰጪው መድን የሚሆን ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ መኪናው ላይ ጉዳት የደረሰው መንጃ ፈቃድ በሌለው የሹፌሩ ረዳት መኪናው ሲሽከረከር ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ መኪናው በማንኛውም ሰው ቢሆን መንጃ ፈቃድ በሌላው ሰው ሲሽከረከር ጉዳት ከረደሰበት መድን ሰጪው ሃላፊነት እንደሌለበት በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ውል ማግለያ አንቀጽ ላይ በግልጽ የተመለከተ ስለመሆኑ ከፍ ሲል ተመልክተናል፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለው በመኪናው ላይ ጉዳት ያደረሰው የተጠሪ ተቀጣሪ በሆነ ሠራተኛ ቢሆንም በማግለያ አንቀፁ መሠረት ረዳቱ መንጃ ፈቃድ የሌለው በመሆኑ ብቻ እንኳ አመልካች መድን የመስጠት ሃላፊነት የሌለበት መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ መንጃ ፈቃድ የሌለው ሰው ባለሞተር ተሽከሪካሪ ማሽከርከር እንደማይችል ይልቁንም ድርጊቱ በወንጀል ጭምር እንደሚያስጠይቅ በሕግ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ሕጉ በዚህ መልክ ሲደነገግ ጥበቃ ሊያደርግ የፈለገው ለባለ ንብረቱ ጥቅም ብቻ ሳይሆን ለማህበረሰቡ /ለሕዝብ/ አጠቃላይ ደህንነትም ጭምር እንደሆነ መገንዘብ አዳጋች አይደለም፡፡ በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ ጋር ስናያይዘው የተጠሪ መኪና ላይ ጉዳት የደረሰው ሚያዝያ 6 ቀን 1999ዓ.ም ሲሆን በዚህ ጊዜ ሥራ ላይ የነበረው የትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/97 አንቀጽ 22 ላይ እንደተደነገገው ያለመንጃ ፈቃድ ባለሞተር ተሽከርካሪ መንዳት እንደማይፈቀድ እና ባለንብረቱም ይህንን መፍቀድ እንደሌለበት በግልጽ ተደንግጎ እናገኛለን፡፡

በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 29 እንደተመለከተው አዋጁንና አዋጁን ለማስፈፀም ተብሎ የወጡትን ደንቦች የተላለፈ ሰው የወንጀል ሕግ መሠረት እንደሚሰማ ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም ጉዳት አደረሰ የተባለው የሹፌሩ ረዳት በተጠሪ ስር የሚሆን ሰው ነው በሚል ምክንያት አመልካች የመድን ሃላፊነት አለበት ተብሎ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ የማግለያ አንቀፁን የውል ድንጋጌ መንፈስ በአግባቡ ያላገናዘበና በሌሎች ሕጎች ለሕዝብ ጥቅም ተብለው የተደነገጉትን ሕጎች ዓላማና ግብ ያላጤነ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ተችሏል፡፡



www.chilot.me

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 127331 ታህሳስ 3 ቀን 2001ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 76377 ነሐሴ 25 ቀን 2001ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ የመክፈል ሃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

ሶ/በ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 65632

ሐምሌ 13 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች** ፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** ፡- ሕብረት ባንክ /አ.ማ/ - ነገረ ፈጅ ንጉሴ ኪዳኔ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ** ፡- አቶ ዓሊ አብዱ - ጠበቃ አቶ ደምሴ ልዑልሰገድ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ በፍርድ የተወሰነላቸው ገንዘብ እንዳለ በመግለፅ ወሐቢይ መሐመድ የአፈፃፀም ክስ አቅርበዋል፡፡ በአፈፃፀሙ ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነ የሰሊጥ ማበጠሪያ ማሽን ድርጅት መጋዘን የተያዘ በመሆኑ አመልካች በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ በሰሊጥ ማበጠሪያ ድርጅቱ መጋዘን የብድር መያዣ በመሆኑ የቀዳሚነት መብት አለኝ፡፡ ሌሎች የፍርድ ባለመብቶች የሰሊጥ ድርጅቱ ሲሸጥ ከእኔ የተረፈ ገንዘብ ከተገኘ በተረፈው ላይ ብቻ ነው ፍርድ የማስፈፀም መብት ያላቸው የሚል ጥያቄ አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ጥያቄ ተቀብሎ የሀራጅ ማስታወቂያው በሬድዮና በቴሌቪዥን እንዲነገር ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ የሀራጅ ማስታወቂያው ሳይነገር የቀረ መሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ያሳያል፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 97/90 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በመያዣነት የያዘውን የሰሊጥ ማበጠሪያ ድርጅት መጋዘን ሸጦ ቀሪ ገንዘብ ከተገኘ ለሌሎች የፍርድ ባለመብቶች ለማከፋፈል እንዲችል ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ እንዲሰጥለትና መያዣውን በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በሐራጅ ለመሸጥ የተጀመረው አፈፃፀም እንዲቆም ጥያቄ አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ጥያቄ በመቀበል አመልካች በአዋጅ ቁጥር 97/90 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት መያዣውን እንዲሸጥ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች በመያዣ የያዘውን የሰሊጥ ማበጠሪያ ድርጅት መጋዘን እንዲሸጥ እድል ተሰጥቶት ጨረታ ማስታወቂያ ካወጣ በኋላ የተወው በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መያዣውን በራሱ የመሸጥ መብቱን ትቷል፡፡ ስለሆነም የሐራጅ ሥርዓቱ መከናወን ያለበት አፈፃፀሙን በጀመረው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኩል እንጂ በአመልካች በኩል መሆን የለበትም በማለት ወስኗል፡፡



www.chilot.me

አመልካች የካቲት 15 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች መያዣውን የመሸጥ መብቱን ከፈቃዱ ለቋል በሚል የተሳሳተ የሕግ ትርጉም በመስጠት በአዋጅ ቁጥር 97/90 መያዣውን በመሸጥ ብድራችንን የመሰብሰብ መብታችንን የሚያሳጣ ውሣኔ ወስኗል፡፡ ይኸም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰሊጥ ማበጠሪያ ድርጅቱን ለመሸጥ የመጀመሪያ ሐራጅ እንዲወጣ ካደረገ በኋላ አመልካች መያዣውን በአዋጅ ቁጥር 97/90 እንዲሸጥ በማለት የሰጠውን ትዕዛዝ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሻረው ባግባቡ ነው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፤ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ያቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች መያዣውን የመሸጥ መብቱን በፍላጎቱ ትቶቷል፡፡ ሁለተኛ መያዣውን በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት ለመሸጥ ያቀረበው ጥያቄ ተገቢነት የለውም በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የፍርድ ባለዕዳ የሆኑትን የተጠሪ ሰሊጥ ማበጠሪያ ድርጅት መጋዘኖች በመያዣነት የያዘ መሆኑ አመልካችና ተጠሪ የሚካካዱበት ነጥብ አይደለም፡፡ የመንግስትም ሆነ የግል ባንኮች ለአበደሩት ብድር ዋስትና እንዲሆን የያዙትን የማይንቀሳቀስ ንብረት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በሐራጅ በመሸጥ ለአበደሩት ብድር መክፈያነት ሊያውሉ የሚችሉበት ሥልጣንና ኃላፊነት በአዋጅ ቁጥር 97/90 በሕግ አውጭው ተሰጥቷቸዋል፡፡ ሕግ አውጭው በአገሪቱ የሚገኙ ባንኮች በውል የያዙትን የመያዣ ንብረት ራሳቸው በሐራጅ ሸጠው ዕዳቸውን ለመሰብሰብ የሚያስችላቸው ሥልጣን የሰጠበት ዋነኛው ምክንያት የገንዘብ ተቋማቱ መያዣውን በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በማሸጥ ያበደሩትን ገንዘብ ለማስመለስ በሚጥሩበት ጊዜ የተለያዩ ችግሮች ስለሚያጋጥሟቸውና በዚህ ምክንያት ዕዳቸውን ለመሰብሰብና መያዣውን በወቅቱና በዋጋቸው ለመሸጥ የማይችሉ በመሆናቸው መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 97/90 መግቢያ ላይ በግልፅ አስቀምጧል፡፡ ሕግ አውጭው የገንዘብ ተቋማቱ በመያዣ የያዙትን ንብረት በሐራጅ ሲሸጡ በፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ከአንቀፅ 394 እስከ አንቀፅ 449 ያሉትን ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው የመከተል ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን በአዋጁ አንቀፅ 6 ከመደንገጉም በላይ በሽያጭ ሂደቱ ሕግን በመተላለፍ ሽያጩን ቢፈፅም ባንኩ በባለ ዕዳው ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ተጠያቂነት ያለበት መሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 7 በግልፅ ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም አመልካች በመያዣነት የያዘውን የተጠሪ ሰሊጥ ማበጠሪያ ድርጅት መጋዘን በራሱ በሐራጅ የመሸጥና ዕዳውን የመሰብሰብ መብት ያለው መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀፅ 3 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ አመልካች ይህንን በሕግ የተሰጠውን ሥልጣን ለመጠቀም የፍርድ ቤት ውሣኔም ሆነ ፈቃድ አያስፈልገውም፡፡ አመልካች ከዚህ በፊት መያዣውን የመሸጥ መብቱን በፈቃዱ ትቶታል የሚለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክንያት ሕግ አውጭው ከጅምሩ አዋጅ ቁጥር 97/90 በማወጅ ባንኮች መያዣቸውን ለመሸጥ የሚያስችላቸውን ሥልጣንና ኃላፊነት የሰጠበትን መሠረታዊ ዓላማ ያላገናዘበና የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በመያዣነት የያዘውን የተጠሪን የሰሊጥ ማበጠሪያ ድርጅት መጋዘን በአዋጅ ቁጥር 97/90 ራሱ መሸጥ አይችልም፡፡ የሐራጅ ሽያጩ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኩል ይፈፀም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 47076

መስከረም 25 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አፍሪካ ኢንሹራንስ /አ.ማ/ ነ/ፈጅ ሜሮን ሰለሞን ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ጣይቱ አመዴ አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ በንብረት ላይ የሚደርስ ጉዳት ለመሸፈን የተደረገ የመድን ውል ነው፡፡ ተጠሪ ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበው የክስ ማመልከቻ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-27956 አ.አ የሆነ ኤፍ ኤስ አር አይሱዚ መኪና እንዳላቸውና መኪናው በአደጋ ምክንያት ጉዳት በደረሰበት ተከሳሹ /አመልካች/ እስከ ብር 300,000 /ሶስት መቶ ሺህ ብር/ የመድን ሽፋን ለመስጠት በመስማማቱ ተጠሪ የአረቦን ክፍያ ሲከፍሉ የቆዩ መሆኑን የተጠሪ መኪና ህዳር 10 ቀን 1999ዓ.ም በመውደቁ ተጠሪ አመልካች መኪናውን እንዲያስጠግን ወዲያውኑ ያሳወቁ መሆኑን ሆኖም አመልካች ሙሉ በሙሉ ሊተካ የሚገባውን የመኪናውን አካል በአዲስ ለመተካት ባለመፈለጉና መኪናው ሳይጠገን 198 ቀናት የቆየ በመሆኑ የመኪናውን አካል እንዲተካና መኪናውን ለመጠገን ከሚያስፈልገው ምክንያታዊ ጊዜ በላይ የቆመ በመሆኑ በቀን ብር 1500 /አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር/ ሒሳብ አመልካች ውሉን ባለመፈፀሙ ምክንያት የደረሰብኝን ጉዳት ካሳ /የቀረ ገቢ/ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት በተከሳሽነት ቀርቦ መኪናው አዲስ እቃ ተገዝቶ ካልተተካለት በማለት ተጠሪ /ከሳሽ/ በፈጠሩት ችግር ምክንያት ሳይጠገን የቆየ በመሆኑ ኃላፊነቱ የከሳሽ /ተጠሪ/ ነው፡፡ በመድን ፖሊሲው መሠረት የተቋረጠ ጥቅም የመክፈል ኃላፊነት የሌለብን በመሆኑ የከሳሽ ጥያቄ የህግ ድጋፍ የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

የስር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃና ክርክር ከሰማ በኋላ መኪናው ሳይጠገን ለመቆየቱ የአመልካች /የተከሳሽ/ ጥፋትና ኃላፊነት ነው በማለት ከደመደመ በኋላ ተከሳሽ /አመልካች/ በመድን ውሉ መሠረት የከሳሽን መኪና ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ ባለማስጠገኑ ምክንያት ከሳሽ /ተጠሪ/ ያቀረቡትን ገቢ የመሸፈን ግዴታና ኃላፊነት አለበት፡፡ ስለሆነም የመኪናውን መጠን የሚያስፈልገውን



www.chilot.me

ገንዘብ ብር 139,000 /አንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ብር/ እና መኪናው ፍርድ እስከተሰጠበት ቀን ድረስ ያስገኝ የነበረው ገቢ በቀን በብር 1500 ታስቦ ብር 588,000 /አምስት መቶ ሰማኒያ ስምንት ሺ ብር/ እንዲከፍል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ሁለት ጭብጦችን መስርቷል የመጀመሪያው ጭብጥ የከፍተኛው ፍ/ቤት አመልካች መኪናውን ለማስጠገን አስፈላጊ የሆነውን ብር 139,000 /አንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ብር/ ለተጠሪ ይክፈል በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት ወስኗል፡፡ ሁለተኛው ጭብጥ መኪናውን ለማስጠገን የሚፈጀው ምክንያታዊ ጊዜ ምን ያህል ነው የሚል ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የከፍተኛው ፍ/ቤት አርባ አምስት ቀናት ብቻ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት መኪናውን ለማስጠገን የሶስት ወራት ጊዜ ይፈጃል ከዚህ በተጨማሪ መኪናው በቀን የሚያስገኘው ገቢ ብር 1300 እስከ ብር 1500 ስለሆነ ሒሳቡ መሰላት ያለበት በዝቅተኛው መጠን በብር 1300 መሆን አለበት በማለት ካሻሻለ በኋላ መኪናው ከየካቲት 6 ቀን 1999ዓ.ም ጀምሮ በቀን ብር 1300 /አንድ ሺህ ሶስት መቶ ብር/ እየታሰበ ጉዳዩ በይግባኝ ውሳኔ እስካገኘበት ግንቦት 26 ቀን 2001ዓ.ም ድረስ ይከፈል በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔን በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካች ሰኔ 24 ቀን 2001ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የክስ ማመልከቻ ከማቅረባቸው በፊት አመልካች የመኪናውን አካል እንዲቀይርልኝ የማይቀይር ከሆነ መኪናው ሙሉ ውድመት እንደደረሰበት ተቆጥሮ የመድን ውሉ ሙሉ ገንዘብ ብር 300,000 /ሶስት መቶ ሺህ ብር/ ይክፈለኝ የሚል እንደሆነ ለአመልካች በጽሑፍ በሰጡት ማስጠንቀቂያ አሳውቀዋል፡፡ በዚህ መሠረት የመኪናውን ጋቢና ስፖንዳ በማስቀየር ወይም በማስጠገን የሚስተካከል ስለመሆኑ በባለሙያ አስጠንተን ሊጠገን የሚችል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የስር ፍ/ቤቶች መኪናውን ለመጠገን እና ለማስተካከል ከሚያስፈልገው በላይ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጡት ውሳኔ ተጠሪ መኪናውን ለማስጠገን ከሚያስፈልገው በላይ እንዲካስ የሚያደርግና መሠረታዊ መርህ የሚጥስ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ በሁለተኛ ደረጃ አመልካች መኪናው ላይ በደረሰው ጉዳት ምክንያት ተጠሪ የቀረበትን ገቢ የመክፈል ኃላፊነት እንደሌለበት በመድን ፖሊስው በግልጽ ተገልጾ እያለ የእኛን ምስክሮች ሳይሰማ ተጠሪ ጉዳቱን የመቀነስ ኃላፊነታቸውን የተወጡ መሆን አለመሆኑን ሳይመዝን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1802ን በመጣስ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የበታች ፍ/ቤቶች ለመኪናው ማስጠገኛ ከሚያስፈልገው በላይ እንዲካስ ወስነዋል በማለት የቀረበው አቤቱታ የበታች ፍ/ቤቶች ፍሬ ጉዳዩን በማጣራትና በማስረጃ በማረጋገጥ የደረሱበትን መደምደሚያ የሚመለከት በመሆኑ የሰበር አቤቱታ የሚቀርብበትና የሚታይ ነጥብ አይደለም፡፡ በእኔ በኩል የጠየቅሁት መኪናው ላይ አደጋ በመድረሱ ምክንያት የቀረብኝን ገቢ /Consequential loss/ እንዲከፍለኝ ሳይሆን አመልካች መኪናውን አስነትቶ ወስዶ በማቆም በመድን ውሉ መሠረት በምክንያታዊ ጊዜ ውስጥ አሰርቶ ማስረከብ ሲገባው መኪናውን አሰርቶ ባለማስረከቡ የደረሰብኝን ኪሳራ የሚመለከት በመሆኑ የአመልካች ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች በጸሑፍ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የተጎዳውን የመኪና ክፍል በአዲስ ለመተካት የሚያስችል ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔና አመልካች መኪናውን



www.chilot.me

ባለማስጠገኑ ተጠሪ ያቀረባቸውን ጥቅም በሙሉ ይክፈል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ መስርተናል፡፡

1. የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ በተጠሪ መኪና አካል ላይ የደረሰው ጉዳት በጥገና የሚስተካከል ሳይሆን አዲስ እቃ ገዝቶ በመተካት ሊስተካከል የሚችል መሆኑን በገለልተኛ ባለሙያ እንደተረጋገጠና ጉዳቱ በጥገና ሊስተካከል የሚቻል ነው በማለት ሐሳብ የሰጡት የአመልካች ኤክስፐርቶች መሆናቸውን በመግለጽ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመኪናው ላይ የደረሰው ጉዳት አዲስ እቃ በመግዛትና በመተካት ሊስተካከል የሚችል ጉዳት ነው፡፡ ስለሆነም ጉዳቱን ለማስተካከል አስፈላጊ የሆነውን ብር 139,000 /አንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ብር/ አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት የወሰነው ፍሬ ጉዳዩን በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት ፍሬ ጉዳዩን በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን የሰጠው ውሳኔ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ፀንቷል፡፡ ስለሆነም አመልካች የበታች ፍ/ቤቶች ማስረጃ በመመዘን ሒደት ሰርተውታል የሚለውን ስህተት የማጣራትና የማረም ስልጣን ይህ ችሎት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ያልተሰጠው በመሆኑ አመልካች መኪናው እንዲጠገንና እንዲስተካከል ለማድርግ ብር 139,000 ለተጠሪ እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ በመኪናው የደረሰውን ጉዳት ለማስተካከል ከሚያስፈልገው መጠን በላይ ነው በማለት ያቀረበውን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

2. ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ተጠሪ አመልካች በመድን ውሉ መሠረት ባለመፈፀሙና መኪናውን ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ አስጠግኖ ባለመስጠቱ የቀረብኝ ገቢ ክርክሩ እስከተቋጨበት ጊዜ ድረስ ያለው ታስቦ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ ይህ የተጠሪ ጥያቄ ተጠሪ መኪናቸው በአደጋው ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ ምክንያት ያቀረባቸውን ጥቅም አመልካች እንዲከፍላቸው የቀረበ የ /Consequential loss/ ጥያቄ በመሆኑና የዚህ አይነት ጥያቄ በመድን ውሉ እንደማይሸፈን ግልጽ የፖሊሲ ድንጋጌ ያለ በመሆኑ ተገቢ አይደለም በማለት አመልካች ተከራክሯል፡፡ በእኛ በኩል እንደተረዳነው ተጠሪ የጠየቁት መኪናው በአደጋው በመጎዳቱ ምክንያት ያቀረባቸውን ጥቅም አመልካች እንዲሸፍንና እንዲከፍላቸው አይደለም፡፡ የተጠሪ ክስ መሠረታዊ ይዘት አመልካች መኪናውን ከወደቀበት ካነሳ በኋላ ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ መኪናውን አስጠግኖ የማስረከብ የውል ግዴታ አለበት፡፡ አመልካች ይህንን የውል ግዴታውን በወቅቱ ባለመፈፀሙ ምክንያት የደረሰብኝን ኪሳራ እንዲከፍል ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች የበታች ፍ/ቤቶች ከመድን ፖሊሲው ድንጋጌ ውጭ /Consequential loss/ እንድንከፍል ተወስኖብን በማለት ያቀረቡት ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የተጠሪ ክርክር ውልባለመፈፀሙ ምክንያት የደረሰብኝ ኪሳራና ጉዳት በውሉ መሠረት ግዴታውን ያልፈፀመው አመልካች ይክፈለኝ የሚልና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1790 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1791ን መሠረት ያደረገ መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ሆኖም እዚህ ላይ ሊታይ የሚገባውና የበታች ፍ/ቤቶች በአግባቡ ያላዩዋቸው መሠረታዊ የህግ ነጥቦች አሉ፡፡ ይኸውም አመልካች በመድን ውሉ መሠረት መኪናውን በምክንያታዊ ጊዜ ውስጥ በማስጠገን የማያስረክባቸው መሆኑን ካወቁ ተጠሪ መኪናው ተጠግኖ ለስራ ባለመሰማራቱ ምክንያት የሚያደርሰውን ኪሳራ/ጉዳት/ ለመቀነስ አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን የመፈፀም ግዴታ አለባቸው ወይስ የለባቸውም? ተጠሪ ጉዳቱን ለመቀነስ አስፈላጊውን ጥረት ካላደረጉ ሊከፈላቸው የሚገባው የካሳ መጠን ምን ይሆናል የሚሉት ናቸው፡፡

ሌላቸው ተዋዋይ ወገን የውል ግዴታውን ያልፈፀመለት ሰው ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት የሚደረሰውን የጉዳት ኪሳራ የመቀነስ ግዴታ እንዳለበት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1802 ተደንግጓል፡፡

የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1802 "የጉዳት ኪሳራን የመቀነስ ግዴታ" በሚል ርዕስ ስር በንዑስ አንቀጽ 1" ውል አልተፈፀመልኝም የሚለው ወገን ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት የሚደርሰው ኪሳራ ያነሰ እንዲሆን ተገቢ የሆነውን ጥንቃቄ ሁሉ ማድረግ አለበት ይኸውም ይህንን የሚያደርገው ጥንቃቄ አስቸጋሪና ብዙ ወጭ እንዲያደርግ የማያስገድደው ሲሆን ነው" በማለት ይደነግጋል፡፡ ጉዳት የደረሰበትን መኪና ለመጠገን አስፈላጊ የሆነው ምክንያታዊ ጊዜ ሶስት ወር/ዘጠና ቀናት/ እንደሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በማረጋገጥ ወስኗል፡፡ የተጠሪ መኪና ጉዳት የደረሰበት ህዳር 3 ቀን 1999ዓ.ም በመሆኑ አመልካች በመድን ውሉ መሠረት መኪናውን ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ ያስጠግነዋል ብለው መጠበቅ ያለባቸው እስከ የካቲት 10 ቀን 1999ዓ.ም ነው፡፡ ተጠሪ ከየካቲት 11 ቀን 1999ዓ.ም በኋላ አመልካች መኪናውን በመድን ውሉ መሠረት ባለማስጠገኑ ምክንያት የሚደርሰውን የኪሳራ /ጉዳት/ ለመቀነስ የበኩላቸውን እንቅስቃሴ ማድረግና መኪናውን በሶስት ወር ውስጥ በግል ወጫቸው አስጠግነው ወደ ስራ እንዲስማራ የማድረግ ህጋዊ ግዴታ ያለባቸው መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1802 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ እስካቀረቡበት ጊዜ ድረስም ሆነ ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ እስከተወሰነበት ግንቦት 26 ቀን 2001ዓ.ም ድረስ መኪናውን በግል ወጭ ለማስጠገንና መኪናው ተጠግኖ ለስራ ባለመሰማራቱ ምክንያት የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ ያደረጉት እንቅስቃሴ የለም፡፡ ይህም ተጠሪ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1802 ንዑስ አንቀጽ 1 የተጣለባቸውን የጉዳት ኪሳራን የመቀነስ ግዴታ ያልተወጡ መሆኑን ያሳያል፡፡

ተጠሪ መኪናው ባለመጠገኑ ምክንያት የሚደርስባቸውን ኪሳራ መኪናውን በራሳቸው ወጭ በማስጠገን ለመቀነስ እየቻሉ ይህንን ግዴታቸውን ካልተወጡ የሚከፈላቸው የኪሳራ መጠን እንዲቀንስ አመልካች ለመከራከር የሚችል መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1802 ንዑስ አንቀጽ 2 "ይህንን ጥንቃቄ በቸልተኝነት ሳያደርግ ቢቀር ውሉን ያልፈፀመው ሰው የሌለውን ወገን ቸልታ መከራከሪያ አድርጎ ኪሳራው እንዲቀንስለት ለመጠየቅ ይችላል" በማለት በግልጽ ይደነግጋል፡፡ አመልካች የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1802ን በመጥቀስ የተከራከረ ሲሆን የበታች የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት መኪናው በመድን ውሉ መሠረት አስጠግኖ ባለማስረከቡ ተጠሪ የደረሰባቸውን ኪሳራ ለመቀነስ ያደረጉት እንቅስቃሴ አለመኖሩንና የጉዳት ኪሳራ የመቀነስ ግዴታቸውን ተጠሪ ያልተወጣ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የካሳውን መጠን መወሰን ሲገባቸው መኪናውን ለማስጠገን ከሚያስፈልገው ምክንያታዊ ጊዜ ከየካቲት 8 ቀን 1999ዓ.ም ጀምሮ ጉዳዩ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እስከተወሰነበት ግንቦት 26 ቀን 2001ዓ.ም ድረስ በየቀኑ 1300 /አንድ ሺህ ሶስት መቶ ብር/ እየታሰበ አመልካች ለተጠሪ ካሳ እንዲከፍል በማለት የሰጠው ውሳኔ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1802 የተደነገገውን የጉዳት ኪሳራን የመቀነስ ግዴታ ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም ተጠሪ መኪናውን ለማስጠገን አመልካች ከሚወስድበት ምክንያታዊ ጊዜ ማለትም ከየካቲት 11 ቀን 1999ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት 10 ቀን 1999ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ መኪናውን በግሉ በማስጠገን መኪናው ያለስራ በመቆሙ ምክንያት የሚደርስበትን ኪሳራ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1802/1/ መሠረት መቀነስ ሲገባው ይህንን ግዴታውን ያልተወጣ በመሆኑ ኪሳራ የሚከፈለው ጉዳዩ በይግባኝ ውሳኔ እስካገኘበት ጊዜ ድረስ ሳይሆን በራሱ ወጭ መኪናውን በማስጠገን ኪሳራውን ለመቀነስ የሚያስፈልገው ምክንያታዊ ጊዜ ማለትም የሶስት ወር ወይም የዘጠና ቀናት ብቻ መሆን ይገባዋል በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወሰነውን የካሳ መጠን



www.chilot.me

በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1802/2/ እና በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት በማሻሻል ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1/ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡

2/ አመልካች ለመኪናው ማስጠገኛ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትና በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የተወሰነውን ብር 139,000 /አንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ብር/ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ከሰጠበት የካቲት 3 ቀን 2000ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ለተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ብለናል፡፡

3/ አመልካች መኪናውን ባለማስጠገኑ ተጠሪ ለደረሰባቸው ጉዳት የዘጠና ቀናት ገቢ በቀን በብር 1300 /አንድ ሺህ ሶስት መቶ ብር/ ታስቦ ብር 117,000 /አንድ መቶ አስራ ሰባት ሺህ ብር/ ጉዳዩ በዚህ ፍ/ቤት ውሳኔ ካገኘበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ይክፈል ብለናል፡፡

4/ በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሶ/በ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 56010

ሐምሌ 29 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

**ተጠሪዎች፡-** 1. ቃድሮ ኑሬ

2. ወ/ሮ ይባ ሄቦ

3. ቱሪ ዋሪቱ

4. ወ/ሮ ሃጆ ዱቤ

5. ከድር ቢፍቱ

6. ወ/ሮ ሽምሲያ ዓብዱልቃድር

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የክርክሩን መነሻ በብድር የተሰጠን ገንዘብ ለማስመለስ የቀረበ ክስ ሆኖ በዚህ ሰበር ችሎት እንዲወሰን ተይዞ የቀረበው ጭብጥ ክሱ በይርጋ ቀሪ የሆነ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነው፡፡ ክሱ /ክርክሩ/ የጀመረው በምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ነው፡፡ በክሱ እንደተመለከተው 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ከባንኩ ገንዘብ በብድር የወሰዱ ናቸዉ፡፡ ሌሎች ተጠሪዎች ደግሞ ለብዱሩ አመላለስ የዋስትና ግዴታ ገብተዋል፡፡ ብድሩ የተወሰደው በ24-7-88 ዓ.ም በተፈረመው ውል እንደሆነ መመለስ የነበረበት በ24-7-89 ዓ.ም መሆኑን ተበዳሪዎች ገንዘቡን ለመመለስ ባለመቻላቸው አመልካች በዋስትና የያዘው የ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ቤት በአዋጅ ቁ. 97/90 መሠረት አስገምቶ ሐራጅ ማወጣቱን ፣ የሐራጅ ማስታወቂያ ከማውጣቱ በፊትም በ19-5-92 ዓ.ም ለተጠሪዎች ማስጠንቀቂያ ጽፎ የነበረ መሆኑን በወጣው የሐራጅ ማስታወቂያ መሠረት ቤቱን የሚገዛ ሰው ባለመገኘቱ አመልካች በቀረበው ግምት ብር 52,525.10 ቤቱን መረከቡን በመጨረሻም አመልካች በቀሪ የሚፈለገውን ገንዘብ ይከፈለው ዘንድ በ21-2-2001 ዓ.ም ክስ መመስረቱን ክሱን የሰማው ፍ/ቤት በሰጠው ብይን ላይ በዝርዝር ተመልክቶአል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው ለክሱ በሰጡት መልስ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና ሌሎች የመከራከሪያ ነጥቦች አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ወደሌሎች የመከራከሪያ ነጥቦች

ከማለፉ በፊት ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድርጐአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤትም ብይኑ ጉድለት የለበትም ብሎአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ግንቦት 10 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በመቀጠልም በጭብጥነት የተያዘውን ነጥብ ግራ ቀኙ ወገኖች ካሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው ተጠሪዎች የብድሩን ገንዘብ በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ባለመክፈላቸው አመልካች በ92 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ ሰጥቶአቸዋል፡፡ ሆኖም በተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ መሠረትም ገንዘቡን ሊከፍሉ ባለመቻላቸው በዋስትና በያዘው ቤት ላይ በአዋጅ ቁ. 97/90 መሠረት የሐራጅ ማስታወቂያ ያወጣ ቢሆንም ቤቱን የሚገዛ ሰው ባለመገኘቱ ለጉዳዩ አፈጻጸም አግባብ ባለው የሥነ -ሥርዓት ህግ መሠረት ቤቱን በግምቱ ልክ ተረክቦአል፡፡ አመልካች ቤቱን የተረከበው ሚያዝያ 20 ቀን 96 ዓ.ም ስለመሆኑም በተጠሪዎች መልስ ጭምር ተረጋግጦአል፡፡ አመልካች ቤቱን ቢረከብም በዚህ ረገድ ተከፈለ ሊባል የሚችለው ዕዳ በተጠሪዎች ላይ የሚፈለገውን አጠቃላይ ዕዳ የሚሸፍንለት ሆኖ ባለማግኘቱ ቀሪው ዕዳ እንዲከፈለው በመጠየቁ ክስ መስርቶአል፡፡ አመልካች ቤቱን በግምቱ ልክ ተረክቦ ቀሪ ዕዳ የሚፈልግ መሆኑን ባረጋገጠበት ጊዜ እና ክስ በመሰረተበት ቀን /ጊዜ/ መካከል ያለው ጊዜ ሲታሰብ አስር ዓመት አልሞላም፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም ይህንኑ ስለመገንዘባቸው ከተሰጠው ብይን ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ይህም ሆኖ የይርጋውን ጊዜ ያሰሉት ብድሩ ከተወሰደበት ቀን ጀምሮ በመሆኑ የአስር ዓመትን የይርጋ ጊዜ መሠረት በማድረግ ክስ የማቅረቢያ ጊዜው አልፎአል እሚል መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል፡፡

በበኩላችን እንደምናየው አመልካች በዋስትና የያዘውን ቤት በአዋጅ ቁ. 97/90 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ሸጦ ለብድሩ መክፈያ ከማድረጉ በፊት ያልተከፈለ ቀሪ የብድር ገንዘብ የሚኖር ስለመሆኑ እርግጠኛ መሆን ይችል ነበር ለማለት አይቻልም፡፡ በመጀመሪያ ማድረግ የነበረበትም በመያዣነት የያዘውን ቤት ሸጦ ገንዘቡን መሰብሰብ እንደመሆኑ አመልካቹ ይህንኑ ፈጽሞአል፡፡

ተጠሪዎችን ቀሪ የብድር ገንዘብ ይክፈሉኝ በማለት ሊከስ የሚችለው በእርግጥም ያልተከፈለ ቀሪ ዕዳ መኖሩን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከያዘ በኋላ ነው፡፡ የይርጋ ቀን መቆጠር የሚጀምረው ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ወይም በውሉ የሚሰጠው መብት ከተሰራበት ቀን ጀምሮ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕግ/ቁ. 1846 ተደንግጉአል፡፡

አመልካች ለብድር ገንዘቡ አመላለስ ዋስትና እንዲሆን የያዘውን ቤት በግምቱ ልክ ከተረከበ በኋላ ቀሪ ዕዳ እንደሚፈልግ እርግጠኛ የሆነው ከሚያዝያ 20 ቀን 96 ዓ.ም በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም በተጠሪዎች ላይ ክስ መመስረት የሚችለው ከዚህ በኋላ ነው፡፡ የይርጋ ጊዜው መቆጠር የሚጀምረውም ከሚያዝያ 20 ቀን 96 ዓ.ም ጀምሮ ስለሆነ ክሱ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ያለው ሲታሰብ ጊዜው አላለፈበትም፡፡ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ከዚህ አንጻር ሲታይም በህጉ አተረጓጐም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡



www.chilot.me

**ው ሣ ኔ**

1. የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 04301 መስከረም 21 ቀን 2002 የሰጠው ብይን እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 77420 መጋቢት 7 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ አልሆነም ብለናል፡፡ በመሆኑም የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩን በተጀመረው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ በክሱ ስረ ነገር ላይ ግራ ቀኝ ወገኖች የሚያቀርቡለትን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተገቢውን ይወስን ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/1/ መሠረት ወስነናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

# የዳኝነት ሥልጣን



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 54697

መስከረም 24 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሓጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-**1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማት አስተዳደር ባለስልጣን
2. የቂርቆስ ክፍለ ከተማ መሬት ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት } ነ/ፈጅ ተስፋዬ ዘመድኩን ቀረበ

**ተጠሪ፡-** ድንቅ ስራ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ ሞላ ዘገዬ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሊዝ ውልን መሰረት አድርጐ ለአንድ ሰው የተሰጠ ቦታ ለሌላ ሰው ሲሰጥ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው አካል የትኛው ነው? የሚለውን የሕግ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ማህበር ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በአዲስ አበባ ከተማ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/19 በተለምዶ ባንቢስ አጠገብ ስፋቱ 1194 ካ.ሜ የሆነ ቦታ ላይ ሕንፃ ለመስራት ቦታውን ከአሁኑ 2ኛ አመልካች ጋር የሊዝ ውል በመፈረም ቦታውን በመረከብ ስራ ከጀመረ በሁዋላ 1ኛ ተጠሪ ከመስከረም 25 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ምንም ዓይነት የቦታ ጥያቄ እንዳያስተናግድ ታግዶ ሳለ፣አስፈላጊውን መረጃዎች ሳይቀርቡለት ከተጠሪ መሬት ጋር አጐራባች ለሆኑት የሆቴል ዲልፓል ባለቤት ለሆኑት ለአቶ ዳመና ሲማ ቦታውን እንዲወስዱ፣ተጠሪ ቦታውን እንዲያስረክብ መወሰኑን፣አመልካቾች በሕግ ከተሰጣቸው ሥልጣን ውጪ ተጠሪ በሊዝ ውል መሰረት የወሰደውን የልማት ቦታ በመቀማት ለሌላ ግለሰብ ለመስጠት የወሰኑትን እንዲያርሙ ቢጠየቁ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን በመግለጽ ከዚህ አድርጐታቸው እንዲቆጠቡ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾችም ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችንና የፍሬ ነገር ክርክሮችን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል፡፡ በሚል ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የቀረቡትን የአመልካቾችን መከራከሪያ ነጥቦችን በመመርመር ጉዳዩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ አይደለም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ ተጠሪ ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት



www.chilot.me

ቅሬታውን አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ጉዳዩን የማየት ሥረ ነገር ስልጣን የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ናቸው በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች ነገረ ፈጅ ሚያዝያ 01 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት አምስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ጉዳዩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶችም ሆነ በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ስር የማይወድቅ የአስተዳደር አካሉ ሥልጣን ነው በማለት መከራከራቸውንና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ እንዲታረም ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ጉዳዩ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ስረ ነገር ሥልጣን ስር የሚወድቅ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጐ ተጠሪ መስከረም 04 ቀን 2003 ዓ.ም በጠበቃቸው አማካኝነት በተፃፈ ሦስት ገጽ ማመልከቻ የጽሁፍ መልሱን አቅርቧል፡፡ የአመልካቾች ነ/ፈጅም መስከረም 14 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመልጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀረብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ፣በቀድሞው አጠራር በወረዳ 15 ቀበሌ 34 ክልል ውስጥ በተለምዶ አጠራር ባምቢስ አጠገብ ስፋቱ 1194 ካ.ሜትር ቦታ ለማልማት በቅድሚያ ሰኔ 28 ቀን 1996 ዓ.ም ከአዲስ አበባ አስተዳደር የመሬት አስተዳዳር ባለስልጣን ጋር በተፈረመ ጊዜያዊ መተማመኛ ውል ቀጥሎም መስከረም 25 ቀን 1998 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ከተማ የቂርቆስ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ጋር በተፈረመ የከተማ ቦታ የሊዝ ውል አድርገው ቅድሚያ የሊዝ ክፍያ ተከፍሎ ካርታ እና የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቅት የተሰጣቸው ሁኖ እያለ በውሉ መሰረት ግዴታቸውን አልተወጡም ወይም የውሉ ጊዜ አብቅቷል ባልተባለበት ሁኔታ እንዲሁም ለመንግስት ልማት የሚፈለግ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ መሬቱን አመልካቾች ከተጠሪ ነጥቀው ለሆቴል ዲሊኦፖል ባለቤት ግለሰብ ለመስጠት ደብዳቤ የፃፉላቸው መሆኑን ጠቅሰው የአመልካቾች እርምጃ ከሕግ ውጪ ነው በማለት ተጠሪ የሚከራከሩ መሆኑን፣አመልካቾች በበኩላቸው ይህ ለተጠሪ የተሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሊዝ ቦርዱ ከተጠሪ ጋር የነበረው የሊዝ ውል እንዲቋረጥ በመወሰኑ መሰረዙን ገልፀው ጉዳዩ በፍርድ ቤት ሊዳኝ የማይችል መሆኑን ጠቅሰው የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም ተጠሪ ጉዳዩ የሊዝ ውል እንጂ የአስተዳደር ውል ባለመሆኑ መዳኘት ያለበት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ነው የሚለውን ክርክር፣አመልካቾች ደግሞ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ይታያል ከተባለም መታየት ያለበት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሳይሆን በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ነው የሚል ክርክር በስር ፍርድ ቤት አቅርበው የነበሩ መሆኑንም ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37/1/ ድንጋጌ በግልጽ የሚያሳየው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚሁ የሕገ መንግስት ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ ፍርድ ቤቶች አንድን

ጉዳይ(አቤቱታ) ተቀብለው ውሳኔ መስጠት የሚችሉት ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በሕግ ለሌላ አካል ያልተሰጠ ጉዳይ በሚሆንበት ጊዜ እንደሆነ መሆኑን ነው፡፡ በሕግ ተለይተው በአስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲቋጩ በተባሉ ጉዳዮች ላይ መደበኛ ፍርድ ቤት የመዳኘት የስረ ነገር ስልጣን ስለሌለው በሕጉ መሰረት ለአንድ አስተዳደር አካል ቀርቦ አስተዳደራዊ ውሳኔ የተሰጠበትን ጉዳይ ወይም ለአስተዳደር መቅረብ የሚገባውን ጉዳይ ፍርድ ቤት ሊያስተናግደውም ሆነ አከራክሮ ውሳኔ ሊሰጥበት አይችልም፡፡ ለአንዳንድ የመንግስት አካላት በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን የሚሰጡት ሕጎች መጠበቅና መከበር ያለባቸው ሲሆን የዳኝነት አካል ስልጣንም በሕግ የተወሰነ ስለሆነ ሕግ የመተርጐም ስራው በሕጉ በተመለከተው አድማስ የሚመራ ይሆናል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.4 ድንጋጌ የሚያሳየውም ፍርድ ቤቶች በሌላ ሕግ በግልጽ በታገዱ ጉዳዮች ላይ አከራክሮ የመወሰን ስልጣን የሌላቸው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በአስተዳደራዊ ውሳኔ የመጨረሻ እልባት እንዲያገኙ በሕግ ተለይተው የተቀመጡ ጉዳዮችን ፍርድ ቤቶች የመዳኘት ስልጣን የሌላቸው መሆኑ ሊስተዋል የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ(ክርክር) መሰረት ያደረገው ከአመልካቾች ጋር ባደረጉት የሊዝ ውል የተሰጠውን መሬት ከሕግ ውጪ ተወስዶ ለሌላ ግለሰብ እንዲሰጥ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ በዚህ መልኩ የሚቀርበውን የዳኝነት ጥያቄ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ የመጨረሻ እልባት የሚሰጥበት መሆኑን ወይም ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤት ሊታይ የማይገባው መሆኑን የሚደነግግ ሕግ አለ በሚል በአመልካቾች የሚቀርበው ክርክር መሰረት ያደረገው አዋጅ ቁጥር 272/1994 ነው፡፡ በዚህ አዋጅ የሊዝ ቦታ የሚሰጥበትና ውሉ የሚቋረጥበት አግባብ ተዘርግቷል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 15፣16 እና 17 ድንጋጌዎች ሲታዩ የሊዝ ውል የሚቋረጥበትንና ካሳ የሚከፈልበትን አግባብ፣ጉዳዩን ሊመለከቱ የሚችሉ ወገኖችንና የይግባኝ አቀራረብን ሥርዓት ደንግገው እናገኛለን፡፡

በተያዘው ጉዳይ የሊዝ ውል እንዲቋረጥ ተደርጓል የሚባለው ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ነው በሚል ምክንያት በመሆኑ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያላቸው የአዋጅ ቁጥር 272/94 ድንጋጌዎች አንቀጽ 15/1/ለ/ እና 16 ናቸው፡፡ የአንቀጽ 15/1/ለ/ ድንጋጌ የከተማ ቦታ የሊዝ ይዞታ ቦታው ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ለሌላ ስራ ወይም አግልግሎት እንዲውል ሲወሰን ሊቋረጥ እንደሚችል የተመለከተ ሲሆን በአንቀጽ 16/1/ደግሞ አግባብ ያለው አካል ለሕዝብ ጥቅም ይውላል ተብሎ በሚወስነው መሰረት ለሚመለከተው አካል የማስለቀቂያ ትእዛዝ ወይም ማስጠንቀቂያ በጹሑፍ በመስጠት የሚፈልገውን የከተማ ቦታ ማስለቀቅና መረከብ እንደሚችል አስቀምጧል፡፡ የአዋጅ አንቀጽ 17/1/ ድንጋጌ ሲታይም በአንቀጽ 16 መሰረት የማስለቀቅ ትእዛዝ የደረሰው ወይም ትእዛዝ በተሰጠበት ንብረት ላይ መብት ወይም ጥቅም አለኝ የሚል ወገን የካሣም ሆነ ማንኛውንም ለፍርድ ሊቀረብ የሚገባው ሌላ አቤቱታ ከዝርዝር ምክንያቱ እና ማስረጃው ጋር ትእዛዙን ለሰጠው አካል የማቅረብ መብት እንዳለው ያስገነዝባል፡፡ በዚህ መልኩ ቀርቦ የታየ ጉዳይም በአንቀጹ ንኡስ ቁጥር ሁለት ስር የተመለከተው ተገቢ ዳኝነት የሚሰጥበት ሲሆን በውሳኔው የማይስማማ ሰው ለጉባኤው ይግባኙን ማቅረብ እንደሚችል በአንቀጽ 18/1/ ስር ተደንግጐ ያለ ከመሆኑም በላይ ይህ አካል የሚሰጠው ውሳኔ ካሣ አነሰኝ፣ ወይም ካሣ በዛብኝ ወይም ካሳ ተከለከልኩ በሚሉ ክርክሮች ላይ ካልሆነ በስተቀር በሕግም ሆነ በፍሬ ነገሮች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ስለመሆኑ የተጠቀሰው አንቀጽ ንኡስ ቁጥር ሦስት ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለው በሊዝ የተሰጠ ቦታን የሚመለከተው አካል ማስለቀቅ የሚችለውና ጉዳዩ ላይ ጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ እና

በፍርድ ቤት ሊቀርብ የማይገባው ቀድሞ የቦታ ማስለቀቁ እርምጃ የተወሰደው ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ነው፡፡

አዋጅ ቁጥር 272/94 አንቀጽ 2/7/ ስር ለህዝብ ጥቅም ትርጉም አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሰረት የሕዝብ ጥቅም ማለት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሕዝቦች በመሬት ላይ ያላቸውን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና የከተማ ልማትን በቀጣይነት ለማጐልበት አግባብ ያለው አካል በመሪ ፕላን ወይም በልማት እቅድ የሕዝብ ጥቅም ብሎ የሚወስነው ነው በሚል ትርጓሜ የተቀመጠ ሲሆን አዋጅ ቁጥር 455/97ም ተመሳሳይ ይዘት ያለውን ትርጉም በአንቀጽ 2/5/ ስር ይዞ እናገኛለን፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች ጉዳዩ ከሕዝብ ጥቅም ጋር የተገናኘ በሚል ያቀረቡት ክርክር በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያላገኘው መሬቱ ሊሰጥ የታሰበው ሆቴል ለሕዝብ ጥቅም የሚለውን ትርጉም በሚያሟላ መልኩ የሚታወቅ ስለመሆኑ አላስረዱም በሚል ነው፡፡ ይህ ግልጽ የማስረጃ ጉዳይ መሆኑን የምንገነዘበው ሲሆን ፍሬ ነገርን የማጣራትና የማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካቾች ክርክር በማስረጃ የተደገፈ አለመሆኑን አረጋግጧል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እ 25/1988 አንቀጽ 10 የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሲፈፀም ማረም በመሆኑ የአመልካቾች ያቀረቡት ክርክርና ማስረጃ አሳማኝ ነው? ወይስ አይለም? የሚለውን ጉዳይ የሚመለከተው ሆኖ አላገኘውም፡፡ በተለይ አመልካቾች የተጠሪ ቦታ የሚወሰድ መሆኑን የገለፁት ተጠሪ በሊዝ በወሰዱት ቦታ ላይ የፈለጉትን ግንባታ ቢያካሂዱ በስተጀርባ ያለውን የአቶ ዳመና ሲማ ንብረት የሆነውን ዲሊኦፖል ሆቴል ስለሚጋረድ በሆቴሉ ሥራ ላይ እንቅፋት ይፈጥራል በሚል ምክንያት ስለመሆኑ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ ሆኖ አግኝተናል፡፡ እንዲህ ከሆነ ቦታው ላይ የተሻለ ልማት የሚካሄድ መሆኑን፣በከተማው መዋቅራዊ ፕላን ቦታ ላይ የሚካሄደውን ግንባታ ለሆቴሉ ለመስጠት ማስፈለጉን አመልካቾች ያላረጋገጡት ጉዳይ ሲሆን በሊዝ አዋጅና ደንብ መሰረት የገባውን ውል ባለማክበሩ ወይም መሬቱ መንግስት ለሚያካሄደው የልማት ሥራ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በቀር መሬት በሊዝ የተከራየ ሰው የሊዝ ዘመኑ ከማለቁ በፊት መሬቱ የማይወሰድበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 3/2/ ከመደንገጉ ጋር ተዳምሮ ሲታይ የአመልካቾች ክርክር ተቀባይነት የሚያገኝ ሁኖ አልተገኘም፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው ጉዳዩ በፍርድ ቤት የሚታይ ነው ከተባለ ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች የትኞቹ ናቸው የሚለው ነጥብም ምላሽ የሚያስፈልገው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ይህንኑ ነጥብም ምላሽ የሚያስፈልገው ሆኖ አግኝተናል፡፡ ይህንኑ ነጥብ ለመመለስ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ ይዘቱ ምን እንደሆነ ማየቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ተጠሪ የአመልካቾችን እርምጃ ሕገ ወጥ ነው በማለት የሚከራከሩት ከሊዝ አዋጁና ደንብ ውጪ የተፈጸመ ነው በማለት ነው፡፡ ተጠሪ ከአመልካቾች ጋር የሊዝ ውል ያላቸው መሆኑና ተያያዥ ማስረጃዎችም ያላቸው መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ አመልካቾች ደግሞ የተጠሪ የሊዝ ውል እንዲቋረጥ ተደርጐ ካርታና የይዞታ ምስክር ወረቀት መሰረዙን ገልጸው የሚከራከሩ መሆኑን የክርክር ሂደቱ ያሳያል፡፡ በመሆኑም ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ ተጠሪ ከአመልካቾች ያገኙት የሊዝ ቦታ ምስክር ወረቀት የተሰረዘው በአግባቡ ውሉን መሰረት ባደረገ መልኩ ነው ወይም ከውሉና አግባብነት ካላቸው ሕጐች ውጪ ነው? የሚለው ነው፡፡

የከተማው አስተዳደር ካርታ የመስጠት፣የመሰረዝ፣የማሻሻል፣የማምከን፣ የማገድ እና አሻሽሎ የመስጠት ሙሉ ስልጣን ያለው ቢሆንም የሊዝ ውልን መሰረት አድርጐ የተሰጠውን ካርታና የምስክር ወረቀት መልሶ ከሕግ ውጪ ሰርዞ ሲገኝ በእርምጃው ላይ ቅሬታ ያለው ወገን

ጉዳዩን ለፍርድ ቤት እንዲያቀርብ የሚከለከልበት ስርዓት የሌለ ስለመሆኑ  የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አግልግሎት አካላት ስልጣንና ኃላፊነትን ለመደንገግ የወጣው፣ክርክሩ ሲጀመርም ሆነ ከተጀመረ በኋላ በስራ ላይ ያለው ሕግ ያሳያል፡፡ ይልቁንም የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41/1/ሀ/ እና/መ/ ድንጋጌዎች ሲታዩ የተያዘውን ጉዳይ አይነት የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤት ተቀብሎና አከራክሮ ለመወሰን የስረ ነገር ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ ያስገነዝባሉ፡፡ አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት በአማራጭ ባቀረቡት ክርክርም ይህንኑ ደግፈው ሲከራከሩ የነበሩ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ቀርቦ ሊታይ ይገባል ሲባል የተያዘው ጭብጥ ሰበር ችሎቱ ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንፃር ለማየት ተብሎ ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶባቸዋል ተብለው ሊጠቀሱ የሚችሉት መዛግብት የመ/ቁጥር 17712 እና በመ/ቁጥር 27604 በተያዘው ጉዳይ ካለው ፍሬ ነገር እና የሕግ ክርክር ሙሉ በሙሉ ግንኙነት አላቸው ሊባሉ የሚችሉ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም የተጠሪ ክስ መሰረቱ የሊዝ ውል ሆኖ ውሉ ተጥሷል በሚል ዳኝነት የጠየቁ ናቸውና፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካቾች ክርክር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የተጠሪ ጥያቄ የክፍለ ከተማው አስተዳደር ከሕግ ውጪ በሊዝ የተወሰደ ቦታ ለመውሰድ ካርታና የምስክር ወረቀት በመሰረዝ ሕገ ወጥ እርምጃ ወስዷል በማለት በሊዝ ውል ያገኙት የንብረት መብታቸው (የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40/6/ ይመልከቷል) በፍርድ እንዲጠበቅላቸው የሚጠይቅ በመሆኑ በፍርድ ቤት ሊያስተናግድ የሚገባው እና ውሳኔ የሚሰጥበት ጉዳይ በመሆኑ እና መታየት ያለበትም በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ጉዳዮች ፍርድ ቤቶች በመሆኑ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበት ድምዳሜም ከአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41/1/ሀ/ እና/መ/ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንፃር ህጋዊ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህ ምክንያት በውሳኔው ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 48336 ጥር 04 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ት እ ዛ ዝ</u>

ይህ ችሎት ሐምሌ 14 ቀን 2002 ዓ.ም ሰጥቶት የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 48316

ጥቅምት 04 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ዘነበች ተመስገን - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ መሠረት አበራ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ ከቀኛዝማች ተመስገን ዳልኬሮ መስከረም 20 ቀን 1960 ዓ.ም በተደረገላቸው የስጦታ ውል በወረዳ ሶስት ቀበሌ 47 ውስጥ የሚገኝ ቁጥሩ 790 የሆነ ቤት ተሰጥቷቸው ሥጦታው ፀድቆና ቤቱ ያላግባብ የተወሰደ መሆኑ ተረጋግጦ በስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ሕዳር 20 ቀን 1970 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ እንዲመለስላቸው የታዘዘ ቢሆንም ተጠሪ ቤቱ ሊመለስላቸው ያልቻለ መሆኑን ገልፀው ቤቱ እንዲመለስላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም ለክሱ በሰጠው መልስ አመልካች ክስ ለመመስረት የሚያስችላቸው መብት ወይም ጥቅም የሌላቸው መሆኑን ቤቱን ከሀያ አመት በላይ በእጁ አድርጎ የሚያስተዳድረው እና ግብርም የከፈለበት በመሆኑ ክሱ በይርጋ እንደሚቋረጥ ጉዳዩ በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እየታየ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የተከራከረ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃም የአመልካች ክስ በማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን ገልጾ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ መሆኑን ገልጾ መዝገቡን ቢዘጋውም የአሁኗ አመልካች በዚሁ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን ያለው መደበኛ ፍርድ ቤት ነው በሚል ምክንያት ቀደም ብሎ የተሰጠው የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ ጉዳዩ ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ተመልሶለታል፡፡ ጉዳዩ የተመለሰለት የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን እንደገና መርምሮ የአሁኑ ተጠሪ ያቀረባቸውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችን ውድቅ አድርጎ በፍሬ ነገር ደረጃም የአመልካችን ክርክር ተቀብሎ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ተጠሪ ለአመልካች እንዲያስረክብ ሲል ወስኗል፡፡ በዚሁ ውሳኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ አመልካች ጉዳዩን ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አቅርበው ጉዳዩ እየታየ ባለበት ሁኔታና ውጤቱ ሳይታወቅ በፍርድ ቤት

ክስ መመስረታቸው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 8 ድንጋጌ አኳያ ተገቢነት የለውም በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ በመሻር ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላም አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታቸው መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ መሆኑ ተረጋግጦ ከተወሰነ በኋላ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እንደመደበኛ ፍርድ ቤት የማይቆጠር ሁኖ እያለ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 8 ተጠቅሶ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሻሩ ስነ ስርአቱን የጠበቀ ስላልሆነ ሊለወጥ ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታዘዙ የተጠሪ ነገረ ፈጅ ቀርበው ጥር 13 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ የፁሑፍ መልሳቸውን ያቀረቡ ሲሆን አመልካች በበኩላቸው ጥር 14 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች አከራካሪው ቤት ይመለስልኝ ጥያቄን በመደበኛ ፍርድ ቤት ክስ የመሰረቱበት ሲሆን ከዚሁ ጎን ለጎን ደግሞ ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አቤቱታቸውን አቅርበው ጉዳዩ እየታየ መሆኑን አልካዱም፤ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት አቤቱታቸው በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቢቀርብም ይኸው አካል እንደ መደበኛ ፍርድ ቤት ሊታይ አይገባውም ባሁኑ ጊዜም ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለኝም በማለት አቤቱታቸውን ያልተቀበለው መሆኑን በመግለፅ ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ወገን ጉዳዩን ማቅረብ ያለበት ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 110/87 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 193/92 እና 572/2000 ያሳያሉ፡፡ ይህ አካል ጉዳዩ ሲቀርብለት በሕጉ አግባብ የሚሰጠው ውሳኔ እንደ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊቆጠር የሚችልና ለአፈፃፀምም የሚቀርብ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ይህ አካል በሕግ ተለይቶ በተሰጠው ጉዳይ ላይ የዳኝነት ሥልጣን ያለው አካል ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 110/87 ስለኤጀንሲው ስልጣንና ተግባሩ በአንቀፅ 4 ስር በግልፅ ያስቀመጠ ሲሆን የዚሁ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ፊደል "ለ" ከአዋጁ ውጪ የተወሰዱ ንብረቶችን በተመለከተ የቀረቡለትን የመብት ጥያቄዎችና ሁኔታዎች በአዋጁ መሰረት ይመረምራል፣ ለምርመራው አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን ከማናቸውም የመንግስት ወይም የግል መስሪያ ቤት፣ ድርጅት ወይም ተቋም እንዲሁም ከማንኛውም ግለሰብ ለማግኘት የምስክር ቃል ለመቀበል ወይም የፅሁፍ ማስረጃን እንዲያቀርብለት ለማዘዝ እንደሚችል የተገለፀ ሲሆን በዚሁ ንኡስ ድንጋጌ ፊደል "ሐ" ስር ደግሞ ከአዋጁ ውጭ የተወሰደን ንብረት ባለቤትነት በተመለከተ በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ መረጃዎችን እያጣራ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፣ ውሳኔው እንዲፈፀም አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል በሚል ተደንግጓል፡፡ ሌላው በአዋጁ አንቀፅ 9 ስር ከአዋጁ የማይቃረን ህግ ወይም መመሪያ ተፈጻሚነት እንዳለው በሚያስገነዝብ መልኩ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ሁሉ መረዳት የሚቻለው ይኸው አካል ጉዳዩን ሲመለከት የተለያዩ የማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ሥርዓቶችን ሊከተል

የሚችል መሆኑና አግባብነት ባላቸው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ሊመራ የሚችል መሆኑን ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ያለው የየትኛው አካል ነው የሚል ክርክር ቀርቦ ባለበት ሁኔታ አንድ ጉዳይ ለሁለት የዳኝነት አካላት የሚቀርብበት አግባብ የለም፡፡ አንድ ጉዳይ በተመሳሳይ ጊዜ በሁለት የዳኝነት ሥልጣን ባላቸው አካላት መቅረብ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ድንጋጌ አላማን የሚፃረር ነው፡፡ በመሆኑም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቀርቦ ሳያልቅ በፍርድ ቤት መቀጠሉ ያላግባብ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ መሻሩ በአግባቡ ነው፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ጉዳዩ በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ታይቶ ተገቢው ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ አመልካች ለሚመለከተው ፍርድ ቤት በሕጉ አግባብ ክርክራቸውን ከመቀጠል የማይገድብ መሆኑን የተገነዘብን ሲሆን አመልካች በአሁኑ ወቅት የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አቤቱታቸውን ያልተቀበለው መሆኑን በዚህ የሰበር ክርክር ደረጃ የገለፁ ስለሆነ ይህንኑ መሰረት በማድረግ ለስር ፍርድ ቤት ክርክራቸውን ከመቀጠል በስተቀር የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሠጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት የሚያስችል ሁኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 58727 ሕዳር 16 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመ/ቁጥር 44907 ሰኔ 19 ቀን 2001 ዓ.ም በትእዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ያቀረቡት አቤቱታ እልባት አግኝቶ ከሆነና እልባት የተሰጠበት አግባብም በፍርድ ቤት ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ከሆነ ይህ ውሳኔ ክርክራቸውን በስር ፍርድ ቤት ከመቀጠል የሚያግዳቸው አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

*ራ/ታ*



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 54577

ህዳር 01 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- የኢት/ያ መድን ድርጅት - ነገረፈጅ ክንፈ ታደለ ቀረበ

**ተጠሪ**፡- አቶ ሰለሞን ያዕቆብ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር መዝገብ ሊቀርብ የቻለው አንድ የፌዴራል ፍ/ቤቶች የሆነን ጉዳይ በሕገ መንግሥቱ በተሰጠው የውክልና ሥልጣን መሠረት በክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ በታዩ ጊዜ የይግባኝ ክርክሩን ተመልክቶ ለመወሰን የይግባኝ ሰሚነት ሥልጣን ያለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው ወይስ የዚያው ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት? ለሚለው የሕግ ጥያቄ አግባብነት ያለው የሕግ ትርጉም ለመስጠት ሲባል ነው፡፡

የጉዳዩ መነሻ ከውል ውጪ በሚደርስ ኃላፊነት ክስ ምክንያት የአሁን ተጠሪ ባቀረበው የገንዘብ ክርክር የአሁን አመልካች በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ገብቶ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለትም የአላባ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበለትን ጉዳይ ከመረመረ በኋላ ኃላፊ የሆነውን ወገን ለይቶና የካሣ መጠኑን ወስኖ የአሁን አመልካች በገባው የዋስትና ሽፋን መሠረት ለተጠሪ ይክፈል በማለት በመወሰኑ ምክንያት የኢት/ያ መድን ድርጅት ኃላፊነትና የካሣ መጠኑን አስመልክቶ በተሰጠው ውሣኔ ቅር ተሰኝቶ የይግባኝ አቤቱታውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ በዚህም የይግባኝ ቅሬታ መነሻ የአሁን መልስ ሰጭ ቀርቦ እንዲከራከር ሲደረግ በመጀመሪያ ደረጃ ያቀረበው የይግባኝ ክርክር የፍ/ቤቱን የይግባኝ ሥልጣን የሚመለከት ነው፡፡

ከውሣኔው ግልባጭ ይዘት እንደምንረዳው ለክርክሩ መሠረት ያደረገው ከዚህ ቀደም በተመሣሣይ ጉዳይ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መ/ቁ. 20465 ሰኔ 26 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ በክልል ፍ/ቤት በውክልና ሥልጣን የታዬ ጉዳይ በይግባኝ ተቀብሎ የማስተናገድ ሥልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እንጂ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አይደለም በማለት የወሰነ ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 454/97 መሠረት ይህም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ጉዳይ ተቀብሎ ለማየት የሚያስችለው ሥልጣን የለውም የሚለውን ነው፡፡

የይግባኙ ጉዳይ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ በሚመለከት የሚከተለውን ዳኝነት ሰጥቷል፡

ክርክር ባስነሣው ጉዳይ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች የሁለት የተለያዩ ክልል ኗሪ ናቸው፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/2/ መሠረት ጉዳዩ የፌዴራል ነው የፌዴራል የሆነውን ጉዳይ የክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት በውክልና ሥልጣኑ ተመልክቶ ከወሰነ ክሱ የሚታይበትን ክልል ጨምሮ በአምስቱም ክልሎች ተሰጥቶ የነበረው የውክልና ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 322/95 የተነሣ ስለሆነ በዚህ መንገድ በተሰጠው ውሣኔ ላይ የሚቀርበውን የይግባኝ ክርክር ተቀብሎ ለማስተናገድ ሥልጣን ያለው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት እንጂ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አይደለም የሚለውን ትንታኔ ምርኩዝ በማድረግ በሥልጣን ረገድ የቀረበውን የመከራከሪያ ነጥብ በኮ/መ/ቁ. 67947 ሚያዚያ 05 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውድቅ አድርጎታል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ የማየት ሥልጣን አለኝ ሲል በሰጠው ውሣኔ የአሁን መልስ ሰጭ ቅር ተሰኝተው የይግባኝ አቤቱታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በማቅረባቸው ይህ ችሎት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በመ/ቁ.46679 በ04/5/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት በተመሣሣይ ጭብጥ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ. 20465 ሰኔ 26 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ትርጉም መሠረት የአሳባ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍ/ቤት ባገኘው የውክልና ሥልጣን ተመልክቶ ውሣኔ በሰጠበት የፌደራል ጉዳዩ የሚቀርበውን የይግባኝ ክርክር ተመልክቶ የመዳኘት ሥልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ስለሆነ የአሁን አመልካች የይግባኝ አቤቱታውን በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ማቅረቡ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለሆነም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ ከሚያቀርብ በቀር ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ማቅረብ አይችልም በማለት ውሣኔውን ሽሮታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔውን ለመሻር መሠረት ያደረገው የሰበር ሰሚ ውሣኔ ለዚህ ጉዳይ ተዘማጅነት የለውም፡፡ በዚህ ጉዳይ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች የተለያዩ ክልል ኗሪ በመሆናቸው ጉዳዩ የፌዴራል ነው የፌዴራል የሆነን ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ተቀብሎ ለማስተናገድ የሚከለክለው ሕግ የለም ስለሆነም ከጉዳዩ ጋር ተገቢነት የሌለውን የሰበር ውሣኔ ጠቅሶ የሰጠው ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በዚህ የሰበር ቅሬታ መነሻ መልስ ሰጭ ቀርቦ በሥር ፍ/ቤቶች አቅርቦት የነበረውን ክርክር በማጠናከር ውሣኔው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም ከይግባኝ ስልጣን ጋር በተያያዘ የተነሣውን የሕግ ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነው ጉዳይ ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5 አኳያ የፌዴራል ጉዳይ ስለመሆኑ በግራ ቀኙ መካከል የተካደ ነጥብ አይደለም፡፡

አከራካሪ የሆነው ጉዳይ የአሳባ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍ/ቤት በውክልና ሥልጣኑ ተመልክቶ በሰጠው ውሣኔ ላይ ሊቀርብ የሚገባውን የይግባኝ ክርክር ተቀብሎ የማስተናገድ ሥልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ነው ወይስ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት? የሚለውን ጥያቄ አስመልክቶ በኢት/ያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ራፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80፣ 78/2/ እና አንቀጽ 78/2/

ተከትሎ ከወጣው አዋጅ ቁጥር 322/95 ጋር በማጣቀስ ሊሰጥ የሚገባውን የሕግ ትርጓሜ ላይ ያተኮረ ነው፡፡

በሕገ- መንግሥቱ አንቀጽ 78/2/ እንደተደነገገው ክርክር የተነሣበትን ክልል ጨምሮ በአምስቱም ክልሎች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለመደራጀቱ በአዋጅ ቁጥር 322/95 ተደንግጓል፡፡

በዚሁ አዋጅ መሠረት የተደረገው አደረጃጀት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ብቻ የተወሰነ እንጂ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን ጨምሮ ያደራጀ ባለመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 78/2/ ሁለተኛ ክፍል ላይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በክልሎች እንዲደራጅ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ካልተወሰነ ለክልል ፍ/ቤቶች የተሰጠው የውክልና ሥልጣን እንደፀና የሚዘልቅ መሆኑ በመደንገጉ፣ በሕገ- መንግሥቱ አንቀጽ 80/4/ እንደተመለከተው የእነዚህ ክልሎች የከፍተኛ ፍ/ቤቶች በፌዴራል ጉዳይ እንደ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሆነው በዳኝነት የማየት የውክልና ሥልጣናቸው የተነሣ አይደለም ሕገ መንግሥታዊ መሠረት ያለው ነው፡፡

ከዚህ አንፃር በአንድ በኩል በእነዚህ ክልሎች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተደራጀ መሆኑን ጠቅለል ባለ መልኩ ብቻ በአዋጅ ቁጥር 322/95 የተደነገገ በመሆኑ የተነሣ፤ በሌላ በኩል ከላይ እንደተገለፀው የክልል ከፍተኛ ፍ/ቤቶች በፌዴራል ጉዳይ ላይ የተሰጣቸው ሕገ መንግሥታዊ የውክልና ሥልጣን እንደፀና ያለ ለመሆኑና በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80/5/ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን በውክልና የማየት ሥልጣን ያለው መሆኑ፣

እንደ አሁኑ ባለው ጉዳይ የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በውክልና ሥልጣኑ ተመልክቶ ውሣኔ የሰጠበትን ጉዳይ ተቀብሎ ለማስተናገድ ሥልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ወይስ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ነው? የሚለውን ጥያቄ ያስነሣል፡፡

በእነዚህ ክልሎች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ብቻ ተለይቶ በአዋጅ ቁጥር 322/95 የተደራጀ እንደመሆኑ መጠን የዚህ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሥልጣን ወሰን በይግባኝ ተመልክቶ የመወሰንን ሁሉ የሚጨምር ስለመሆኑና አለመሆኑ በሕጉ በግልጽ ሊሰፍር ይገባ እንደነበረ የክርክሩ ይዘት ያስረዳል፡፡

ይሁን እንጂ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በፌዴራል ጉዳይ ላይ ያለው የውክልና ሥልጣን ጠቅለል ባለመንገድ በሕገ - መንግሥቱ አንቀጽ 80/2/ ላይ ይቀመጥ እንጂ በሕገ- መንግሥቱ አንቀጽ 80/2/ እና 80/5/ እንደቅደም ተከተሉ በመጀመሪያ ደረጃ በሚነሳ የክርክር ጉዳይ እንደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ደረጃ ባለክርክር ደግሞ እንደ ፌዴራል ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት ሆኖ መመለከት እንደሚችል ዘርዘር ባለ ሁኔታ ያለው የውክልና ሥልጣን አይነት ተለይቶ ተቀምጧል፡፡

በመሆኑም የክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፌዴራል ጉዳይ በሕገ- መንግሥቱ አንቀጽ 80/2/ የተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን አሁንም ያልተነካና በዚህ መንገድ ታይቶ በሚሰጥ ውሣኔ ላይ ይግባኙ ለማን ይቀርባል የሚለውን ጥያቄ የአዋጅ ቁጥር 322/95 ጥቅል አነጋገር ጥያቄ የሚያስነሣ ቢሆንም፤ እንዲሁም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው የውክልና ሥልጣን በሁለት የክርክር እርከን ዓይነት ተለይቶ በሕገ- መንግሥቱ አንቀጽ 80/2/ እና 80/5/ በግልጽ የተሰጠ እስከሆነ ድረስ በአዋጅ ቁጥር 322/95 የተደራጀው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሥልጣን የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች

በሕገ- መንግሥቱ አንቀጽ 80/2/ መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ የሚቀርቡትን የፌዴራል ጉዳይ ክርክሮችን ተቀብለው እንዲያስተናግዱ ተሰጥቷቸው የነበረውን ሥልጣን የወሰደ፤ የተካ እንጂ ለክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች በሕገ - መንግሥቱ አንቀጽ 80/5/ መሠረት በይግባኝ ያላቸውን ሥልጣን ሁሉ ያስቀረ አይደለም ብሎ ለመተርጎም የሚያበቁ በቂ መነሻዎች ናቸው፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በክልሎች የተደራጀ መሆኑ በአዋጁ በግልጽ እስከተደነገገ ድረስ በይግባኝ ደረጃ ያለውን ሥልጣን ሁሉ የሚጨምር ነው እንዳይባል ከአንድ የፌዴራል ጉዳይ የሚመነጭን የመጀመሪያ ደረጃ ክርክር በክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲታይ አድርጎ የይግባኙን ጉዳይ ለማከራከር በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80/5/ መሠረት የውክልና ሥልጣን የተሰጠው መሆኑ እየታወቀ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትን ወደ ጎን ትቶ ወይም አስቀርቶ ይግባኙ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሊቀርብ ይገባል የሚለው መደምደሚያ ትርጉም አልባ ከመሆኑም በላይ የሕጎችን ዐውደ ንባብ ትርጓሜ ያልተከተለ፤ አዋጁ ውጤት እንዲኖረውና በአዎንታዊ መንገድ ታይቶ ሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የሚያስችል የአተረጓጎም መንገድ ሆኖ አይገኝም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የአላባ ልዩ ወረዳ ፍ/ቤት በተሰጠው የውክልና ሥልጣን መሠረት ተመልክቶ ውሣኔ በሰጠበት የፌዴራል ጉዳይ ላይ የአሁን አመልካች ቅሬታ ካለው የይግባኝ አቤቱታውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ከሚያቀርብ በቀር የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ ለማየት የሚያስችለው ሥልጣን የለውም ሲል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ. 46679 በ04/5/2002 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰ/መ/ቁ. 46679 በ04/5.2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

2/ የሰበር አመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ መዝገቡ ዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 56118

ኀዳር 16 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- የኢት/ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን - ነ/ፈጅ አቶ ዓለምሰገድ ፍትህአወቅ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ** ፡- ወ/ሮ ወርቅነሽ ወ/ማርያም በሌለበት የሚታይ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የአ/አበባ ከተማ ማኀበራዊ ፍ/ቤቶች አመልካች የኢትዮጵያ ኤሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ተከራካሪ የሆነበትን ጉዳይ ተመልክተው ለመወሰን የሚያስችል ሥልጣን አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚለውን ጭብጥ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር አገናዝቦ ለመተርጎም ሲባል ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ የአሁን ተጠሪ የስልክ አገልግሎት ክፍያና የስልክ ቀፎ እንዲመለስለት አመልካች ክስ መሥርቷል፡፡ በክሱ የተካተተውም የገንዘብ መጠን ከብር 5000.00 በታች በመሆኑ ለአዲስ አበባ ከተማ ማኀበራዊ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ሁለቱንም ወገኖች ካከራከረ በኂላ የመጨረሻ ወርሃዊ ክፍያ ስለመፈፀሙ ደረሰኝ ከቀረበ ከዚህ ወር በፊት ላሉት አገልግሎቶች ተገቢው ክፍያ እንደተፈፀመ ይቆጠራል የሚለውን መሠረት አድርጎ ወስኖበታል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ይህንኑ ውሣኔ በማጽናት ስላሰናበተው የሰበር አቤቱታውን ለአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡

ይኸው ሰበር ሰሚው ችሎትም ወደ ጉዳዩ ዘልቆ ከመግባቱ በፊት ክሱ በአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ቀርቦ ሊታይ የሚገባው ነው ወይስ አይደለም? የሚለው የሥልጣን ጉዳይ በቅድሚያ ሊመረመር የሚገባው ነጥብ መሆኑን ጠቅሶ የአሁን አመልካች በፌዴራል መንግሥቱ የተመዘገበ አካል ነው፡፡ ይህን መሰል ወገን ተከራካሪ የሆነበትን ጉዳይ ተመልክተው የመዳኘት ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስለመሆናቸው በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/6/ ሥር ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም የፌዴራል የሆነውን ጉዳይ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ተመልክተው ለመወሰን ከሕግ የመነጨ ሥልጣን የላቸውም በማለት በየደረጃው የተሰጠውን ውሣኔ ሽሮ አሰናብቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህ ከላይ የተጠቀሰው ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 361/95 ለማኅበራዊ ፍ/ቤቶች የተሰጣቸውን ሥልጣን ያገናዘበ አይደለም በሁለቱም አዋጆች ላይ ሥልጣንን በሚመለከት ግጭት አለ እንኳ ቢባል አግባብነት ያለውን አተረጓጎም ልንከተል ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር ከዚህ ቀደም ተከተል አንፃር ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው አዋጅ ቁጥር 361/95 እንጂ አዋጅ ቁጥር 25/59 አይደለም፡፡ ስለሆነም የሕግ ስህተቱ ይታረምልን በማለት ነው፡፡

እኛም በዚህ የሰበር ቅሬታ መነሻ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

የፌዴራል ፍ/ቤቶች የወል የፍትሐብሔር ሥልጣንን በሚደነግገው በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/6/ መሠረት በጉዳዩ የተካተተው የገንዘብ መጠን ምንም ይሁን ምን በፌዴራል መንግሥቱ የተመዘገበ የንግድ ድርጅት ወይም ማኅበር ተከራካሪ የሆነበትን ማናቸውም ጉዳይ ተቀብለው ለማስተናገድ ብቸኛ ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ናቸው፡፡ ከሥልጣን ጋር በተያያዘ ሥራ ላይ የሚገኘው የሕግ ዘርፍ ይህ ብቻ ቢሆን ኖሮ ይህ ጉዳይ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ሥልጣን ሥር ሊወድቅ የሚቻል ስለመሆኑ ባላከራከረ ነበር፡፡

ይሁን እንጂ የአ/አበባ ከተማ ፍ/ቤቶችን ለማደራጀት በወጣው አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 50 ላይ ደግሞ ተከራካሪ ወገን ማንም ይሁን ማን እስከ ብር 5000.00 ሊደርስ የሚችለውን የገንዘብ ክርክር ጉዳይ በአ/አበባ ከተማ ሥር እስከተነሣ ድረስ የአ/አበባ ከተማ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች ተቀብለው ለመወሰን ሥልጣን የተሰጣቸው በመሆኑ ከላይ ከፍ ሲል በአዋጅ ቁጥር 25/85 የተመለከተውን ድንጋጌ ከዚሁ አዋጅ ይዞታ ጋር ተገናዝቦ ሊታይ ይገባዋል፡፡ በሁለቱም አዋጆች መሠረት አሁን የቀረበውም ጉዳይ ለየትኛው የፍ/ቤት አደረጃጀት ሊቀርብ ይገባዋል? የጉዳዩ ባለቤት ማን ነው? የሚል ጥያቄ ከተነሣ አንድ ወጥ የሆነ ምላሽ አያገኝም፡፡ በሁለቱም ሕጎች መካከል ቅራኔ እንዳለ እንረዳለን፡፡ ይህም ከሆነ ጉዳዩን ተቀብሎ ለማስተናገድ ሥልጣን የሚኖረው በአንደኛው መስመር የተደራጀው ፍ/ቤት ሊሆን ስለሚገባው ይህንኑ ለይቶ ለመወሰን ተገቢውን የሕግ አተረጓጎም ዘዴ መከተል የግድ ይላል፡፡ ከእነዚህም የአተረጓጎም ዘዴዎች መከተል አንዱ አንድን ጉዳይ ይኸውም ክርክር ያስነሳውን ጉዳይ ተቀብሎ ለመወሰን ሥልጣን ያላቸው የትኞቹ ፍ/ቤቶች ናቸው የሚለውን አስመልክቶ በእኩል ደረጃ በሚገኙ ሕጎች /አዋጆች/ በተለያዩ ሁኔታ ደንግገው ከተገኙ ከጊዜ ቀደም ተከተል አንፃር በኋላ የወጣው ሕግ ከፊተኛው በልጦ ተፈፃሚነት ይኖረዋል የሚለው የትርጉም መርህ በመሆኑ ጉዳዩ በአዋጁ ቁጥር 361/95 ሥር የሚታቀፍ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በተለይም በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/6/ ድንጋጌ መሠረት ይህን መሰል ጉዳይ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ሥር እንደሚወድቅ እየታወቀ ሕግ አውጪው ዘግይቶ ሥልጣንን የገንዘብ መጠን ወሰን አበጅቶ በሌላ አነስተኛ የፍርድ መድረክ ሥር ቀርቦ እንዲታይ ማድረጉ በክርክር ምክንያት የሚወጣው ወጪና የሚባክነው ጊዜ ክርክሮች ከያዙት የገንዘብ መጠን ጋር የተመጣጠነ ሊሆን እንደሚገባው ታሳቢ በማድረግ የፌዴራል ፍ/ቤቶችን ሥልጣን ቀንሶ ለመስጠት ሲባል የወጣ ሕግ መሆኑን ያመለክታል በተለይም ይህንኑ የትርጉም መስመር ይበልጥ የሚያጠናክረው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ሥልጣን ተፈፃሚ ከሚሆንበት ከድሬደዋ ከተማ ጋር በተያያዘ የድሬዳዋ ከተማ ቻርተርን ለማቋቋም በወጣው በአዋጅ ቁጥር 416/96 አንቀጽ 41 ሥር ስለ ቀበሌ ማኅበራዊ ፍ/ቤቶች ሥልጣን ሲደነገግ ከተላላፊ የገንዘብ ሰነዶች እና ከኢንሹራንስ ጉዳይ በቀር ሌሎች ግምታቸው እስከ ብር 2500.00 ድረስ ያሉትን ገንዘብ ነክ ክርክሮች ለማየት ሥልጣን ያላቸው የማኅበራዊ ፍ/ቤቶች ናቸው በማለት ከዚህ

ቀድሞ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5 ሥር የፌዴራል ጉዳይ መሆኑን ለመለየት መነሻ ከሆኑት 10 ንዑስ ጉዳዮች መካከል ተላላፊ የገንዘብ ሰነድና የኢንሹራንስ ጉዳዮች ሊያስነሱ ከሚችሉት የተወሳሰበ የሕግ ጥያቄ አንፃር ሁለቱን ብቻ በመለየት የፌዴራል ሆነው እንዲቀሩ በሌሎች ጉዳዮች የሚነሳው ክርክር ግን ግምቱ እስከ ብር 2500.00 እስካልበለጠ ድረስ ከፌዴራል ፍ/ቤቶች ወጥተው በድሬዳዋ ከተማ ቀበሌ ማኀበራዊ ፍ/ቤቶች እንዲታዩ መደረግ በገንዘቡ መጠን ትይዩ የሚታይበትን ፍ/ቤት እና የክርክር ደረጃ ለመለየት ሆን ተብሎ የወጣ ሕግ መሆኑን አስረጂ ነው፡፡

የአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 50 ይዘት ከዚሁ ተለይቶ የሚታይ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመሆኑም ከሥልጣን አደላደል አንፃር የሕግ ጥበቃ የተደረገለት የአሁን አመልካች ሥልጣን አለው በማለት በቀበሌ ማኀበራዊ ፍ/ቤት የቀረበው ጉዳይ በፌዴራል ፍ/ቤቶች እንጂ በአ/አበባ ፍ/ቤቶች ሥልጣን ሥር የሚወድቅ አይደለም በሚል የአ/አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ትርጓሜ ሕጎቹ ከወጡበት ዘመን አንፃርም ሆነ የሕግ አውጪውን ሃሣብ ከመፈለግ አንፃር ሊሰጥ የሚገባውን የሕግ አተረጓጎም ዘይቤ ያልተከተለ ስለሆነ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 12124 በ12/6/2002 ዓ.ም. የተሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ ሽረናል፡፡
2. ክርክር ያስነሳው ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ ከአዲስ አበባ የቀበሌ ማኀበራዊ ፍ/ቤት ሥልጣን የሚጀምር ስለሆነ ከቀበሌ ማኀበራዊ ፍ/ቤት ጀምሮ በየደረጃው የተሰጡትን ውሣኔዎች በማገናዘብ ለአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታ መነሻ የቀረበለትን ጉዳይ መርምሮ ተገቢውን ፍርድ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሠረት ወስነናል፡፡

በዚህ ሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ ያደረጉት ክርክር ስላስለከተለው ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 55299

መጋቢት 19 ቀን 2003ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- ዓለም ገብሩ አልቀረቡም (ማ/ቤት ስለሆኑ)

**ተጠሪ** ፡- ትግራይ ዐቃቤ ህግ አልቀረቡም VC ስለማይሠራ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የትግራይ ክልል ምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ተገልያ ለሰበር ስለቀረበ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ለዞኑ ዐቃቤ ህግ ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ተጠሪ አመልካች ከሌሎች ግብረአበሮቹ ጋር በመሆን በወንጀል ህግ 32/3/ አንቀፅ 671 /1/ /ሀ/ /ሰ/ የማይገባውን ጥቅም ለማግኘት አስበው በቡድን የጦር መሣሪያ በመያዝ በህዳር ወር 2000ዓ.ም ከቀፍታ ወረዳ ሁመራ ወደ ሀገረ ኤርትራ በመሻገር ከሁለት ኤርትራውያን ሰባት መቶ ዶላር /700 ዶላር/ በመዝረፍ የዘረፋ ወንጀል ፈፅሟል፡፡

በኢፌድሪ የወንጀል ህግ አንቀፃ 27/1/ 32/1/ /ሀ/ /ለ/ ከሌሎች ግብረአበሮቹ ጋር ቡድን በመፍጠር ትጥቅ ይዘው ከሁመራ ወደ ሀገረ ሱዳን ሐምዳይት ከሚባል ቦታ ለዘረፋ ከሄዱ በኃላ በሱዳን ወታደሮች ተኩስ ተከፍቶባቸው ስለሸሹ የመዝረፍ ሙከራ ወንጀል ፈፅሟል፡፡ ከ1994ዓ.ም እስከ 1999ዓ.ም ብዛቱ ያልታወቀ ማር ቅቤ በርበሬና ሽሮ ይዞ ከሁመራ በህገወጥ መንገድ ወደ ሱዳን ሐምዳይት የወሰዱ በመሆኑ በተደጋጋሚ የአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀፅ 66/1/ን በመተላለፍ የኮንትሮባንድ ወንጀል ፈፅሟል፡፡ ይህንን ወንጀል በ2000ዓ.ም ዕቃዎችን በህገወጥ መንገድ ወደ ሱዳን በመወሰድ በህገወጥ መንገድ ኮንትሮባንድ ወንጀል ፈፅሟል፡፡ በወንጀል ህግ አንቀፅ 481/1/ሀ የተመለከተውን በመተላለፍ 1800 ጥይት በአራት ብር ከህምሣ ሣንቲም ገዝቶ በአምስት ብር ሸጧል፡፡ ከሌሎች ጋር በመሆን ቁጥሩ 7862 የሆነ ሁለት እግሯ ከላሽን ጠመንጃ ደብቆ በማስቀመጡ ተከስሷል በማለት የወንጀል ክስ አቅርቦበታል፡፡ አመልካች የወንጀሉን ድርጊት አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡ ዐቃቤ ህግ ከሳሽ መደበቁንና በሥር ስድስተኛ ተከሳሽ ከነበረው ሰው ቤት የተገኘ መሆኑን እናውቃለን የሚሉ፣ ምስክሮችንና አመልካች ለፖሊስ ቃሉን ሲሰጥ ሰምተናል የሚሉ ምስክሩችን በማቅረብ አስመስክሮአል አመልካች ለፖሊስ ቃል የሰጠሁት በተፅዕኖ



www.chilot.me

ነው በማለት የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ ከመዘነ በኃላ አመልካች የተከሰሰበትን አራት ወንጀሎች የፈፀመ ጥፋተኛ ነው ብሎ በአሥር ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ፍርድ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ፍርድ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ በመሆኑ ጉዳዩን የማየት የሰበር ሥልጣን የለኝም በማለት አቤቱታውን ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች ሚያዚያ 4 ቀን 2002ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የወንጀል ክሱ የቀረበውን የታየው ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን በሌለው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ክሱ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መታየት ያለበት እና በክልል ደረጃ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መታየት ነበረበት፡፡ ስለዚህ በዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ታይቶ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ዐቃቤ ህግ በወንጀል ህግ አንቀፅ 18 /1/ሀ እና አንቀፅ 19/3/ የተቀመጡትን ሁኔታ ሣያሟላ ያቀረበውና ለፖሊስ በተፅዕኖ ከሰጠሁት የተከሳሽነት ቃል ውጭ ሌላ ማስረጃ ያላቀረበበት ሆኖ እያለ ጥፋተኛ ተብዬ የተሰጠው የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የካቲት 17 ቀን 2003ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ከኢትዮጵያ ግዛት ውጪ በፈፀመው ወንጀል በኢትዮጵያ ፍርድ ቤትም መከሰሱም ሆነ ጥፍተኛ ተብሎ መቀጣቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ጥፋተኛ ከተባለባቸው አራት ወንጀሎች መካከል አንደኛው ወንጀል በኤርትራ ግዛት ክልል ውስጥ ገብቶ ሰባት መቶ የአሜሪካን ዶላር ከሁለት ኤርትራዊያን ዘርፏል የሚል ሲሆን ሁለተኛው በሱዳን ግዛት ክልል ሐምዳይት ከተባለ ቦታ መሣሪያ ታጥቆ ከግብረአበሮቹ ጋር በመሄድ የዘረፋ ወንጀል ለመፈፀም ሲሞክር በሱዳን መከላከያ ሀይል ተኩስ ተከፍቶበት የተመለሰ በመሆኑ የዘረፋ ወንጀል ለመፈፀም ሞክሯል የሚል ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ወንጀሎች በኢትዮጵያ ግዛት ክልል ውስጥ ወይም ኢትዩጵያዊ በሆነ ዜጋ ላይ የተፈፀሙ ወንጀሎች አይደሉም፡፡ እነዚህ ሁለት ወንጀሎች የሱዳን ግዛት ክልልና በሱዳናዊ ዜጎች ላይ የተፈፀመ የዘረፋ ሙከራ ወንጀልና በኤርትራ ግዛት ክልል ውስጥ በኤርትራዊያን ላይ የተፈፀመ የዘረፋ ወንጀሎች መሆናቸውን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ እነዚህ ወንጀሎች አመልካችና ግብርአበሮቹ የሌላውን ሉዓላዊ መንግስት የግዛት ክልል በመጣስ የተፈፀሙ መሆኑን የወንጀል ህጉን አንቀፅ 263 እና አመልካች ጥፋተኛ የተባለበትን የወንጀል ህግ አንቀፅ 71 በጣምራ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 25/1988 በውጭ አገር መንግስት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን የማየት የዳኝነት ሥልጣን ያለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆኑን ከአዋጁ አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 1 እና የአዋጁን አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 2 በጣምራ በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 2 የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደሆነ በግልጽ ይደነግጋል፡፡ ይህም የትግራይ ምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በኤርትራ ግዛት ክልልና በሱዳን ግዛት ክልል ፈፅሚቸዋል የተባሉ የወንጀል ክሶችን የማየት የዳኝነት ሥልጣን የሌለው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ከቀረቡለት ክሶች ሁለቱን የወንጀል

ክሶች የማየት የዳኝነት ስልጣል የሌለው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዐቃቤ ህግ በጉዳዩ የመጀመሪያ የዳኝነት ሥልጣን በህገ መንግስቱ በተሰጠው በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲያቀርብ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 110 መሠረት ትዕዛዝ መስጠት ሲገባው ጉዳዩን ለማት የዳኝነት ሥልጣን ሣይኖረው የቀረበለትን የወንጀል ክስ በማየት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የዳኝነት ሥልጣን ሣይኖረው ጉዳዩን በማየት በአመልካች ላይ የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በይግባኝ ሣያርምና ሣያስተካክል ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የትግራይ ክልል ምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ፍርድ ተሽሯል፡፡
2. ይህ ውሣኔ ዐቃቤ ህግ የዳኝነት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት የወንጀል ክሱን ከማቅረብ የሚገድበው አይደለም ብለናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

ቅ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 56893

መጋቢት 22 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች** ፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አቤቱታ ምርመራና ክስ አቀራረብ ንዑስ ሥራ ሒደት

**ተጠሪዎች** ፡-
1. ወ/ሪት ፍሬህይወት ፍቃዱ
2. ወ/ሮ ሰላም ጥላሁን
3. አቶ ረዘነ ብሥራት
4. አቶ እስራኤል ቶላ
5. ወ/ሪት አጃኤባ አህመድ
6. ወ/ሪት ትዕግስት ጌትነት
7. ወ/ሪት ሰላማዊት ስዩም
8. አቶ ታደሰ ግርማ - ጠበቃ ፍሬው ካሣሁን ቀረቡ
9. ወ/ሪት ዘበናይ ተሻገር
10. ወ/ሪት ሰሚራ ጀማል
11. ወ/ሪት ሀይማኖት ዓለሙ
12. አቶ አብርሀም ታደሰ

አመልካች በመዝገብ ቁጥር 56893 ስማቸው ከተራ ቁጥር 1 እስከ አስረኛው ተራ ቁጥር በተጠቀሰው ተጠሪዎች ላይ የቀረበው የሰበር አቤቱታና የተደረገውን ክርክር አመልካች በመዝገብ ቁጥር 56894 ስማቸው ከአስራ አንደኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ተራ ቁጥር ከተጠቀሰው ተጠሪዎች ጋር ካደረገው ክርክር ጋር በማጣመር መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።



www.chilot.me

# ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ስማቸው ከተራ ቁጥር 1 እስከ ተራ ቁጥር 10 የተጠቀሱት ተጠሪዎች በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 13165 ያቀረቡትን የይግባኝ ቅሬታ በመመርመር የሰጠው ውሣኔና ስማቸው አስራ አንደኛና አሥራ ሁለተኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ተጠሪዎች በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 13138 ያቀረቡትን ይግባኝ በመመርመር የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት በሁለት መዛግብት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ውድቅ መደረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበው አቤቱታ የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ተገልፆ ለሰበር ችሎት ስለቀረበ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች በሁሉም ተጠሪዎች ላይ መጋቢት 17 ቀን 2002 ዓ.ም. ፅፎ የወንጀል ክስ አቅርቧል፡፡ የአመልካች የወንጀል ክስ ይዘትም ስማቸው ከተራ ቁጥር 1 እስከ ተራ ቁጥር 4 የተጠቀሱት ተጠሪዎች በአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 28/1/ለ አንቀፅ 33 እና አንቀፅ 46/3/ መጋቢት 11 ቀን 2000 ዓ.ም. በተደረገው ፍተሻ ጫት ሲያስቅሙና ሺሻ ሲያስጨሱ ከነሺሻ ዕቃው የተገኙ በመሆኑ ከተፈቀደላቸው ንግድ ፈቃድ ውጭ የመነገድ ሕግ የመጣስ ተግባር ፈፅመዋል፡፡ ስማቸው ከተራ ቁጥር 5 እስከ ተራ ቁጥር 12 የተጠቀሱት ተጠሪዎች በአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀፅ 21(1) እና አንቀፅ 46(1) የተመለከተውን በመተላለፍ ጫት በማስቃምና ሺሻ በማስጨስ ገንዘብ እየሰበሰቡ የተገኙ በመሆኑ ያለንግድ ፈቃድ በመነገድ የህግ መጣስ ተግባር ፈፅመዋል የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ ተጠሪዎች ጥፋተኝነታቸውን ያመኑ በመሆኑ የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተከሰሱበትን ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኞች ናቸው በማለት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በተናጠል ያላቸውን የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርቡ ካደረገ በኋላ እያንዳንዱን ተጠሪ ጥፋት ጋር ተመጣጣኝ ነው በሚለው በእስራትና በገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ስማቸው ከተራ ቁጥር 1 እስከ ተራ ቁጥር 10 የተጠቀሱት ተጠሪዎች የሥር ፍርድ ቤት በሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የይግባኝ መዝገብ ቁጥር 13165 ያቀረቡ ሲሆን አስራአንደኛና አሥራሁለተኛ ተጠሪ ይግባኛቸውን በመዝገብ ቁጥር 13138 አቅርበዋል፡፡ የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በሁለቱ መዝገቦች ተጠሪዎችና አመልካች ያቀረቡትን ክርክር ከሰማ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 67/89 የወንጀል ቅጣት የሚያስከትሉ ድንጋጌዎችን በመጣስ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን አስመልክቶ የሚቀርቡ የወንጀል ጉዳይ የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች አይቶ የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 67/89 ሆነ በሌላ ህግ አልተሰጣቸውም፡፡ ስለሆነም የወንጀል ክሱ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይገባል በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታውን በሁለት መዛግብት ለአዲስ አበባ አስተዳደር ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን የከተማው ሰበር ችሎት የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የህግ ስህተት የሌለበት መሆኑን በመግለፅ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች በተጣመሩት መዛግብት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀፅ 41(2)ሀ የከተማው ፍርድ ቤቶች የፋይናንስ መሰል ድርጊቶች ላይ የተፈፀሙ ወንጀሎችን የማየት ሥልጣን እንዳላቸው ደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ የአዲስ አበባ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ህግን

የማስከበርና የመቆጣጠር ሥራ በሚሠሩበት ጊዜ ያጋጠማቸውን የህግ ጥሰት በከተማው ፍርድ ቤቶች ክስ አቅርቦ ለማስቀጣት በሚችሉበት መንገድ መተርጎም ይገባዋል፡፡ ስለሆነም የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን የለውም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲሻርልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

አንደኛ ሶስተኛና ስምንተኛ ተጠሪዎችና አስራ አንደኛና አሥራ ሁለተኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው ባቀረቡት መልስ አዋጅ ቁጥር 67/89ን በመተላለፍ የተፈፀመ የወንጀል ጉዳይ የማየት ሥልጣን የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች አይደለም፡፡ በህግ በግልፅ ባልተደነገገ ወንጀል መከሰሳችንም ሆነ ጥፋተኛ ተብለን መቀጣታችን የህጋዊነት መርህን የሚጥስ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና የሰበር ችሎቱ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ሌሎቹ ተጠሪዎች በሌሉበት ጉዳዩ ታይቷል፡፡ አመልካች በህግ ረገድ ያለውን ክፍተት የሰበር ችሎት ህጉን በመተርጎም ተገቢውን ማስተካከያ ሊያደርግ ይገባዋል የሚል ይዘት ያለው የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች በተጠሪዎች ተፈፀመ የተባለውን ወንጀል ለማየትና ለመወሰን የሚያስችል የዳኝነት ሥልጣን አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ይህንን ጭብጥ ለመወሰን የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የወንጀል የዳኝነት ሥልጣንን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 41 ንኡስ አንቀጽ 2 የከተማው የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን በአዋጅ አንቀጽ 52 በተመለከቱት የፋይናንስ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ወንጀሎችን አይተው እንደሚወስኑ የሚደነግግ ሆኖ አግኝተዋል፡፡ አመልካች ተጠሪዎች የተከሰሱበት ጉዳይ የደንብ መተላለፍ ተግባር እንደሆነ በማድረግ የሚከራከር ቢሆንም አዋጅ ቁጥር 67/89 የተደነገጉ የወንጀል ሃላፊነት የሚያስከትሉ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ወንጀል ፈፅሞ መገኘት እንደወንጀሉ ክብደት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ እስራትና በገንዘብ መቀጮ የሚያስቀጣ መሆኑ የአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 46 ድንጋጌዎችን በማየት ለመገንዘብ የሚቻል በመሆኑ አመልካች ተጠሪዎች የተከሰሱት በደንብ በመተላለፍ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር ህጋዊ መሠረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪዎች የተከሰሱትና በሥር ፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብለው የቅጣት ውሣኔ የተወሰነባቸው በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በአዋጅ አንቀጽ 52 በተመለከቱት በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ ጉዳዮች የሚመለከቱ ወንጀሎችን ፈፅመዋል ተብለው እንዳልሆነ አመልካች ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው የወንጀል ክስ ይዘትና የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ ከሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ተጠሪዎች የተከሰሱትም ሆነ በሥር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የተሰጠባቸው በአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 46 እና ሌሎች ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ወንጀል ፈፅመዋል በሚል ምክንያት ነው፡፡ የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቀጥር 67/89ን በመተላለፍ የተፈጸሙ ወንጀሎች የማየትና ዳኝነት ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 67/89 እና በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 2 አልተሰጣቸውም፡፡ ህግ አውጭው የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች የዳኝነት ሥልጣን እንዲኖራቸው ሀሣብና ፍላጐቱ ቢኖረው ኖሮ ጉዳዩን የማከራከርና የመወሰን ሥልጣን ያላቸው መሆኑን በህግ ማዕቀፎቹ በግልፅ በመደንገግ የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ አስተዳደር

ፍርድ ቤቶች ናቸው ብሎ ግልፅ ያደርገው ነበር፡፡ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አዋጅ ቁጥር 67/89ን በመተላለፍ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን የማየት የዳኝነት ሥልጣን ለአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ያልተሰጣቸው ሆኖ እያለ አመልካች ይህ የሰበር ችሎት በትርጉም የዳኝነት ሥልጣን ለአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ነው ብሎ እንዲወሰንለት ያቀረበው አቤቱታ የህግ አተረጓጎም መርህን የሚጥስና ህግ ከውጭው አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀፅ 41 ንዑስ አንቀጽ 2 የደነገገበትን መሠረታዊ ዓላማ የማያሣካ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ ስለሆነም የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እና የከተማው ሰበር ችሎት የከተማው ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 67/89ን በመተላለፍ የተፈፀሙ ወንጀሎችን የማየት የዳኝነት ሥልጣን የላቸውም በማለት የወንጀል ክሱ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 110ን መሠረት በማድረግ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከተማው የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ተጠሪዎች ፈፅመውታል የሚለውን ወንጀል የማየት የዳኝነት ሥልጣን ላለው አካል የወንጀል ክሱ እንዲቀርብ ከማድረግ ይኼ ውሣኔ አያግደውም ብለናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 64703

ሐምሌ 29 ቀን 2003ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** ፡- ሻምበል ለታይ ገ/መስቀል - ጠበቃ ሣህሉ ሀብቴ - ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- በቂርቆስ ክፍለ ከተማ የወረዳ 1 አስተዳደር ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ ቴዎድሮስ ጸሀዬ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 14640 ታህሳስ 14 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይሻርልኝ በማለት ጥር 05 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች በማቅረባቸው ነው፡፡

የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ አመልካች ነሀሴ 12 ቀን 2002 ዓ/ም ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፅፈው ያቀረቡት ክስ ሲሆን ይዘቱም ተጠሪ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ውስጥ የሚገኝ ቁጥሩ 067 የሆነውን ቤት በወር ኪራይ እየከፈልን በመኖር ላይ እንዳለን ከቀድሞ ባለቤቴ ጋር አብሮ መኖር ስላልቻልን በመ/ቁጥር 142006 በሆነው ሚያዚያ 30 ቀን 2001 ዓ.ም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጋብቻችን እንዲፈርስ ውሳኔ ተሰጥቷል ፣ እንዲሁም ከፍቺው በኂላ የወለድናቸውን ልጆች ለማሳደግ የሞግዚትነት ስልጣን የተሰጠኝ በመሆኑ በባለቤቴ ስም ተመዝግቦ የነበረውን የመንግስት ቤት ኪራይ ተጠቃሚነት በስሜ ዞሮ እንድጠቀምበት ከፍቺው ጋር ፍርድ ቤቱ ውሳኔ የሠጠ በመሆኑ የፍርድ ቤቱን የውሳኔ ግልባጭ ለተጠሪ በማድረስ የስም ዝውውሩን በመጠባበቅ ላይ እንዳሉ የኮንዶሚኒየም ቤት ከቀድሞ ባለቤትሽ ጋር የደረሰሽ በመሆኑ ቤቱን እንድትለቂ የሚል ማስጠንቀቂያ በተጠሪ የተሰጣቸው መሆኑንና ለባለቤታቸው የኮንዶሚኒየም ቤት የደረሳቸው መሆኑን ከፍቺው በሁዋላ የተረዱ መሆኑን ገልፀው በተጠሪ የተፈጠረው ሁከት እንዲወገድላቸው ፣ የቤቱ የኪራይ ስምም እንዲዞርላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም የመንግስት ቤት ኪራይ ተጠቃሚነትን የኮንዶሚኒየም ቤት በባለቤታቸው ስም ትዳር ፅንቶ ባለበት ጊዜ ደርሶአቸው እያለ ሊጠይቁ እንደማይገባ ገልፆ ተግባሩ ሁከት አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለተከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን መርምሮ የአመልካች ተግባር እንደሁከት

ተግባር ሊቆጠር የሚችል አይደለም በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የአመልካች ተግባር ሁከት ነው ተብሎ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሯል፡፡ ከዚህም በኋላ ተጠሪ የሰበር አቤቱታውን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የኮንዶሚኒየም ቤት ለቀድሞ ባለቤታቸው መድረሱን ያወቁት ከፍቺው በኋላ ሁኖ እያለ ኮንዲሚኒየም መድረሱን በመገናኛ ብዙሃን በግልጽ የእጣ አወጣጥ ስነ ስርዓት የተደረገና በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ለሕዝብ ይፋ የሆነ ጉዳይ በመሆኑ የሕግ ግምት የሚወሰድበት ጉዳይ ነው ተብሎ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ግራ ቀኙ በጽሁፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ጉዳዩ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ሥልጣን ስር የሚወድቅ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በክሱ የጠየቁት ዳኝነት የተከራይነት ስም እንዲዞርላቸው የሚመለከት ብቻ ሳይሆን የተጠሪ ማስጠንቀቂያ መስጠት የሁከት ተግባር በመሆኑ ሊወገድ ይገባል የሚገባው ጉዳይ መሆኑን ጭምር ነው፡፡ የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የሰበር ሰሚ ችሎትም የተጠሪ ተግባር ሁከት ነው በማለት ዳኝነት ሰጥተዋል፡፡

ተጠሪ ደግሞ ቤቱን ለማስለቀቅ ለአመልካች የሰጠው ማስጠንቀቂያ የሁከት ተግባር አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመረምረው የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ስልጣንና ሐላፊነት በአዋጅ ቁጥር 361/1995 በአንቀጽ 41 የተዘረዘረ ሲሆን የከተማ ነክ ፍርድ ቤት ንብረትነቱ የከተማው አስተዳደር የሆነ ቤት ላይ የሚነሱ ክርክሮችን አይቶ የመወሰን ስልጣን እንዳለው በአዋጅ አንቀጽ 41(1)(ረ) በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ከዚህም የምንረዳው የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ንብረትነታቸው የከተማው አስተዳደር ለመሆናቸው ክርክር በማይቀርብባቸው ቤቶች ላይ የሚነሱ የይዞታ ፣ የኪራይ እና ሌሎች ክርክሮችን አይተው የመወሰን ስልጣን ያላቸው መሆኑን ነው፡፡

ሆኖም ክርክር የተነሳበት ቤት የከተማው አስተዳደር ነው? ወይስ የሌላ ግለሰብ? ወይም ድርጅት? የሚል መሰረታዊ ክርክር ያለበት ከሆነ የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ይህንን የቤት ባለቤትነት ጥያቄ አስመልክቶ በከተማው አስተዳደርና በሌሎች ሰዎች መካከል የሚደረግ ክርክር በዳኝነት አይተው ለመወሰን የሚያስችል የሥረ ነገር ስልጣን የሌላቸው መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41 (1) (ረ) ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የቤቱን ሕጋዊ ባለቤትነት አስመልክቶ በአመልካች በኩል ክርክር የቀረበበት ሳይሆን የተጠሪን ባለቤትነትን በማመን በቤቱ ላይ የተከራይነት መብታቸው እንዲረጋገጥላቸው በፍርድ ቤት ውሳኔ ተሰጥቶ እያለ አመልካች ለተጠሪ በትዳር ጊዜ የኮንዶሚኒየም ቤት በባል ስም ደርሷቸዋል ተብሎ ቤቱን እንዲለቁ የተሰጣቸው

ማስጠንቀቂያ የሁከት ተግባር በመሆኑ ሊወገድ ይገባል በማለት በመሆኑ የጉዳዩ መሰረታዊ ጭብጥም የተጠሪ ተግባር ሁከት ነው? ወይስ አይደለም? የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ የቤት ይዞታ አይደለም እንጂ ነው ቢባል እንኳ የከተማው አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የቤት ይዞታ ክርክርን በተመለከተ የዳኝነት ስልጣን በሕጉ የተሰጣቸው ሁከት ይወገድልኝ በሚል የሚቀርብ የዳኝነት ጥያቄን መሰረት ባደረገ መልኩ ሲቀርብ አይደለም፡፡ የቦታ ይዞታ ክርክርን በተመለከተም የዳኝነት ሥልጣን ለፍርድ ቤቶቹ በሕጉ የተሰጠው ከከተማው መሪ ፕላን አፈፃጸም ጋር በተያያዘ እንደሆነ አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41((ሀ)) ይይደነግጋል ፣ እንዲሁም በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 18552 በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2(1)መሰረት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ስለሆነም የሁከት ይወገድልኝ ክስ ከከተማው መሪ ፕላን ጋር እስካልተያያዘ ድረስ በከተማው ፍርድ ቤቶች የስነ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቅ አይደለም፡፡ አንድ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከማየቱ በፊት የስረ  ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለው መሆኑን ማረጋገጥ ያለበት ሲሆን የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን በተከራካሪ ወገኖች ባይነሳም በማናቸውም የክርክር ደረጃ ፍርድ ቤቱ በራሱ ሊያነሳው የሚገባው ጉዳይ መሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 እና 231 (1(ለ)) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የሥረ ነገር የዳኝነት ስልጣን በሌለው ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ ደግሞ በመርህ ደረጃ እንዳልተሰጠ የሚቆጠር ነው፡፡ ስለሆነም በየደረጃው ያሉ የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን ሣይኖራቸው ጉዳዩን ሰምተውና አከራክረው የሰጡት ውሣኔ ህጋዊ አስገዳጅነት የሌለውና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 07101 መስከረም 05 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፣ የከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 14292 ጥቅምት 19 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የከተማ ነክ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 14640 ታህሳስ 14 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ የሥረ ነገር ስልጣን ሳይኖራቸው የተሰጡ ውሳኔዎች በመሆናቸው ሙሉ በሙሉ ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. አመልካች ያቀረቡት የሁከት ይወገድልኝ ጥያቄን ሥልጣኑ ለሚፈቅድለት ፍርድ ቤት ወይም አካል አቅርበው ተገቢውን ዳኝነት የመጠየቅ መብታቸውን ይህ ውሣኔ አይገድብባቸውም ብለናል፡፡
3. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 63417

ሐምሌ 15 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** ፡- አቶ ትዕዛዙ አርጋው - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ** ፡- የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ ም/ቤት - አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የአሁኑ አመልካች ለሥር የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ የአሁኑ ተጠሪ /የሥር ተከሳሽ/ በሕገ ወጥ መንገድ ከሥራዬ በማገዱ ምክንያት ያልከተፈለኝ ውዝፍ ደመወዝ ብር 114,788 እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ ብለዋል፡፡

የሥር ተከሳሽም በዋናነት ሁለት መቃወሚያዎችን አቅርቧል፡፡ መቃወሚያዎቹም ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የሥረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን የለውም፣ የከሳሽ ክስ በይርጋ ይቋረጣል የሚሉ ናቸው፡፡

የሥር ፍ/ቤት ተከሳሽ ያቀረቧአቸውን የመቃወሚያ ነጥቦች ከመረመረ በኋላ ከሳሽ የሲቪል ሰርቪስ ሠራተኛ በመሆናቸው በክልሉ የሲቪል ሰርቪስ አዋጅ ቁጥር 29/95 አንቀጽ 71 መሠረት ክሱ መቅረብ ያለበት ለአስተዳደር ፍ/ቤት እንጂ ለመደበኛ ፍ/ቤት ባለመሆኑ ፍ/ቤቱ ሥልጣን የለውም ሲል የከሳሹን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡፡

የሥር ከሳሽም ለክልሉ የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍ/ቤት ጉዳዩን ያቀረቡ ሲሆን የአስተዳደር ፍ/ቤቱ በአስተዳደር መ/ቤት የዲስፐሊን ኮሚቴ የተሰጠ ውሣኔ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ከፀደቀ በኋላ በይግባኝ የሚቀርቡ ጉዳዮችን የማየት ሥልጣን ያለው ሲሆን የይግባኝ ባይ ቅሬታም ይኸንኑ ሥነ ሥርዓት ሳይጠብቅና በአሰሪው መ/ቤት የተሰጠ የዲስፐሊን ኮሚቴ ውሣኔ በሌለበት በ3ኛ ወገን /በክልሉ ም/ቤት/ ውሣኔ ከሥራ የተሰናበቱ በመሆናቸው የአስተዳደር ፍ/ቤቱ ጉዳዩን አከራክሮ ለመወሰን ሥልጣን የለውም በማለት ክሱን ሳይቀበል ቀርቷል፡፡

የአሁን አመልካችም በክልሉ የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ፍ/ቤት በተሰጠ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም መልስ ሰጪውን መጥራት ሳይስፈልግ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት የይግባኙን መዝገብ



www.chilot.me

በመዝጋት ይግባኝ ባዩን አሰናብቷል፡፡ የአሁኑ አመልካችም በሥር የአስተዳደር ፍ/ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚው ችሎት ብይን ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት የሰበር አቤቱታቸውን ለሥር የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም በማለት የሥር ፍ/ቤቶችን ብይን አጽንቷል፡፡

አመልካች የሰበር አቤታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡትም በሥር የአስተዳደር ፍ/ቤትና በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ብይንና በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ፍርድ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል በሚል ሲሆን በዋናነት የጠቀሱትም የቅሬታ ነጥብ፣ ተጠሪው አመልካችን ከሥራ አግዶ ካቆየ በኂላ ማሰናበቱ አግባብ ባለመሆኑ ጉዳዩን አከራክሮ እንዲወስኑ በሚል ለአስተዳደር ፍ/ቤትም ሆነ መደበኛ ፍ/ቤቶች ክስ ባቀርብም አለመቀበላቸው አመልካች ፍትሕ እንዳላገኝ የሚያደርግ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

ተጠሪው በበኩሉ በሰጠው መልስ አመልካች የክልሉ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ሆነው በሹመት በሚሰሩበት ወቅት በታማኝነት ማገልገል ሲገባቸው በፀረ ልማትና አፍራሽ በሆኑ ተግባራት ላይ ተሰማርተው በመገኘታቸው በተሰጠው የፖለቲካና የአስተዳደር ውሣኔ ከሥራቸው እንዲሰናበቱ የተደረገው በአግባቡ ነው በማለት የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ሲል ተከራክሯል፡፡

ከሥር ጀምሮ የተደረገው ክርክር ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው አጥሮ የቀረበ ሲሆን እኛም በሥር የአስተዳደር ፍ/ቤት ብይንም ሆነ በየደረጃው ባሉ የክልሉ ፍ/ቤቶች ብይንና ፍርድ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለ? ወይስ የለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከቀረበው ክርክር መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካች ቀደም ሲል የመንግስት ሠራተኛ በመሆናቸው በክልሉ የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ መሠረት የሚተዳደሩ ቢሆንም የክልሉ መስተዳደር ም/ቤት ተመርጠው በተሰጣቸው ሹመት መሠረት የክልሉ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ በመሆን እየሰሩ ፈጽመዋል በተባሉት ፀረ ልማትና አፍራሽ ተልዕኮ ከሥልጣናቸው ወይም ከሹመታቸው የሾሟቸው አካል አንስቶአቸዋል፡፡

ይህ በመሆኑ ቀደም ሲል ሲሰሩበት ከነበረው የመንግስት መ/ቤት ለቀው በተሰጣቸው ሹመት ላይ እያሉ በተወሰደባቸው የፖለቲካ እርምጃና የአስተዳደር ውሣኔ ከሥራቸው በመነሳታቸው ጉዳይ በክልሉ የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ መሠረት ሊታይ የሚገባ መሆን አለመሆኑን መመርመር ተገቢ ይሆናል፡፡

በክልሉ የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ መሠረት ለአስተዳደር ፍ/ቤት በይግባኝ የሚቀርበው ጉዳይ አስቀድሞ መታየት ያለበት ሰራተኛው በሚሰራበት የመንግስት መ/ቤት ውስጥ በተቋቋመው የዲስፕሊን ኮሚቴ ነው፡፡ አመልካች ግን ከፍ ተብሎ እንደተገለፀው የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ በመሆናቸው በሥራቸው ያሉ የመንግስት ሠራተኞች የዲስፕሊን ግድፈት ሲፈጽሙ የመ/ቤቱ የዲስፕሊን ኮሚቴ ውሣኔን ሊያፀድቁ ሊያሻሽሉ ወይም ውድቅ በማድረግ እንደገና እንዲታይ የማድረግ ሥልጣን ያላቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም ራሳቸውን እንደ ሠራተኛ በመቁጠር የፖለቲካ ውሣኔን ለአስተዳደር ፍ/ቤት የሚያቀርቡበትና ጉዳያቸውን በክልሉ የመንግስት ሠራተኞች አሰተዳደር አዋጅ እንዲታይ የሚጠይቁበት ሁኔታ የለም፡፡

በሌላ በኩል ተጠያቂነት አንዱ የመልካም አስተዳደር ማዕቀፍ ሲሆን በኢ/ፌ/ዲ/ሪ/ሕገ መንግስት አንቀፅ 12/2/ ማንኛውም ኃላፊና የሕዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ እንደሚሆን በግልጽ የተደነገገ ሲሆን ተጠያቂነቱ ለሕግ እና ለመረጠው ሕዝብ ጭምር ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ በተያዘውም ጉዳይ አመልካች የቢሮው ኃላፊ በነበሩበት ወቅት ፈጽመዋል ለተባሉት ድርጊቶች የሕዝብ ውክልና ያለው የክልሉ ም/ቤት ከሥልጣናቸው ወይም ከሹመታቸው አንስቷል፡፡ ይህን የፖለቲካ ውሣኔ አመልካች በፍ/ቤት ለማስለወጥ ማቅረባቸው ያለአግባብ ሲሆን የፖለቲካ ውሣኔዎችን /political actions/ ፍ/ቤቶች ተቀብለው አከራክረው ተገቢውን ፍርድ ለመስጠት የዳኝነት ሥልጣንም አይኖራቸውም፡፡

በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ጉዳዩን አከራክሮ ለመወሰን የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን የለንም ሲሉ በሰጡት ብይንም ሆነ ፍርድ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አላገኘንም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የክልሉ የአስተዳደር ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ/አስ/ፍ/ቤት 17/02/2001 በቀን 30/04/2001 ዓ.ም የሰጠው ብይን፣ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 01721 በቀን 19/05/2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 01732 በቀን 30/03/2003 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ፀንተዋል፡፡
2. የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ያቀረቡትን ክስ ለማየት የዳኝነት ሥልጣን የለንም ሲሉ የወሰኑት በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ



www.chilot.me

የሰ.መ.ቁ 63627

ሐምሌ 14 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- ሼህ አሸራቅ ሰይድ - ጠበቃ ዝኑር አብዱልወሀብ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** የቡታጅራ ከተማ ቀበሌ 02 አስተዳደር - አበበ ነጋሽ ቀረቡ፡፡

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል የጉራጌ ዞን የቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅት ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ የቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔውን እንዲያስፈፅምለት የሰጠው ውክልና ነው፡፡ ኤጀንሲው ሕዳር 17 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈና ቁጥር 05/1506/88/8402/2002 በሆነ ደብዳቤ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 371 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አማካኝነት እንዲፈፀም ስለመጠየቅ የሚል ርዕስ ያለውና በይዘቱም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በጉራጌ ዞን ቡታጅራ ከተማ ልዩ ከፍተኛ ቀበሌ 02 ክልል ውስጥ የሚገኝ ቁጥሩ 112 የሆነ መኖሪያ ቤት ከሼህ አሸራቅ ሰይድ ከአዋጅ ውጭ የተወሰደባቸው በመሆኑ እንዲመለስላቸው መስከረም 7 ቀን 2002 ዓ.ም በቁጥር 05/1506/339/2000 የተሰጠውን ውሣኔ ለሚመለከታቸው አካላት አሳውቀናል፡፡ ሆኖም በኤጀንሲው ውሣኔ መሠረት ያልተፈፀመላቸው መሆኑን ባለጉዳዩ ካቀረቡት ማመልከቻ ስለተረዳን በአዋጅ ቁጥር 146/9/ እና አዋጅ ቁጥር 110/87 መሠረት ውሣኔያችንን ፍ/ቤቱ እንዲያስፈፅምልን የሚል መሆኑን የሥር ፍ/ቤቱ በውሣኔው አስፍሮታል፡፡ ከዚህ ደብዳቤ ጋር ኤጀንሲው ቤቱ እንዲመለስ የሰጠውን የውሣኔ ግልባጭ እንደላከ ከገለፀ በኋላ ተጠሪ በመቃወሙ ኤጀንሲው በቡታጅራ አካባቢ ፍ/ቤት ውሣኔውን እንዲያስፈፅምለት የሰጠው ውክልና ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ለጉዳዩ አግባብነት አላቸው የሚላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች ከዘረዘሩና ከተረጐሙ በኋላ የኤጀንሲውን ውሣኔ የማስፈፀም ሥልጣን ያለው የሚኒስቴሮች ምክር ቤትና ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንጂ ፍርድ ቤት የኤጀንሲውን ውሣኔ የማስፈፀም ሥልጣን የለውም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ



www.chilot.me

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ እንዲያይላቸው አመልካች አመልክተው ይግባኛቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አመልካች ለክልሉ ሰበር ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጓል፡፡

አመልካች የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅት ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 371 በሰጣቸው ውክልና መሠረት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ በውሣኔው መሠረት የማይፈፀምበትን ምክንያት በመጠየቅ ውሣኔውን ማስፈፀም ወይም ሌላ ተገቢ ነው የሚለውን የአፈፃፀም ትዕዛዝ መስጠት ሲገባው በአዋጅ ቁጥር 146/9 እና በአዋጅ ቁጥር 110/87 ድንጋጌዎች የተዛባ ትርጉም በመስጠት ሥልጣኑ የጠቅላይ ሚኒስትሩ እንጂ የፍርድ ቤት አይደለም በማለት የሰጠውን ትዕዛዝ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ማፅናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ፍርድ ቤት ግለሰቦችን እንጂ የአስተዳደር አካላትን በአፈፃፀም የማስገደድ እና የኤጀንሲውን ውሣኔ እንዲያስፈፅም እንዲያደርግ ኤጀንሲውን መወከል አይችልም፡፡ ስለዚህ የክልሉ ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ሥልጣን የለንም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለውም በማለት መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በሰጠው የአፈፃፀም ውክልና መሠረት የኤጀንሲውን ውሣኔ የማስፈፀም ሥልጣን ፍርድ ቤቱ የለውም በማለት የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን ከአዋጅ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶችን አስመልክቶ የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በሕግ የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረታዊ ባህርይ መመልከት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የኤጀንሲው ሥልጣንና ኃላፊነት በተለያዩ የሕግ ማዕቀፎች የተዘረዘረ ሲሆን በያዝነው ጉዳይ አግባብነት ባለው አዋጅ ቁጥር 110/87 አንቀፅ 4/ሐ/ ከአዋጅ ውጭ የተወሰደን ንብረት ባለቤትነት በተመለከተ ከቀረቡት ጥያቄዎች መረጃዎችን እያጣራ ተገቢውን ውሣኔ እንደሚሰጥና ውሣኔውም እንዲፈፀም አስፈላጊውን እርምጃ እንደሚወስድ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አዋጅና የሕግ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለው አንድ ንብረት ከአዋጅ ውጭ የተወሰደ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጉዳይ የማጣራት ማስረጃ የማሰባሰብና የመመዘን ንብረቱ ከአዋጅ ውጭ የተወሰደ ነው ብሎ ሲያምን ለባለቤቱ እንዲመለስ የመወሰን ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 110/87 ለኤጀንሲው የተሰጠው መሆኑን ነው፡፡ ይህ በሕግ ለኤጀንሲው የተሰጠው ሥልጣን ተራ ሕግ የማስፈፀም ሥልጣን አይደለም፡፡ ለኤንጀሲው በዚህ አዋጅ የተሰጠው ሥልጣን ይህን ልዩ ጉዳይ በማየትና በማስረጃ በማጣራት ውሣኔ የመስጠት ወይም የዳኝነት ሥልጣን ነው፡፡ በሕገ መንግስቱ አንድ ሰው በፍርድ የሚያልቅ ጉዳይ በፍ/ቤቱ ወይም በሌላ የዳኝነት ሥልጣን በሕግ ለተሰጠው አካል አቅርቦ የማስወሰን እና ፍትሕ የማግኘት መብት እንዳለው አንቀጽ 37 በግልጽ ይደነግጋል፡፡ ኤጀንሲው ከአዋጅ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶችን በተመለከተ አከራክሮና አጣርቶ የመወሰን ሥልጣን በሕግ ተሰጥቶቷል፡፡ ስለሆነም ኤጀንሲው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ድንጋጌ አገላለፅ ከፍ/ቤት ውጭ ከአዋጅ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶችን በተመለከተ አከራክሮ የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን በሕግ የተሰጠው የመንግስት አካል ነው፡፡

የኢትዮጵያ ፐራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ከአዋጅ ውጭ የተወሰደ ንብረት ለባለቤቱ እንዲመለስ የመወሰን ብቻ ሳይሆን ውሣኔውንም ለማስፈፀም አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 110/87 አንቀፅ 74/ሐ/ ተሰጥቶታል፡፡ በፍርድ ቤት ወይም በሕግ ዳኝነት ሥልጣን በተሰጠው ሌላ አካል የተሰጠው ውሣኔ የሚፈፀመው ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት /ወይም/ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን በተሰጠው አካል ወይም እንደ ፍርዱ እንዲያስፈፅም በታዘዘው ፍርድ ቤት እንደሆነ ከፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 371 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ማናቸውም የመንግስት ተቋም ኤጀንሲው በአዋጅ ቁጥር 110/87 የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት ለመወጣት እንዲችል ተገቢውን ትብብር የማድረግ ግዴታ ያለበት መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 110/87 አንቀፅ 7 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 146/1991 አንቀፅ 26 /2/ ፍርድ ቤቶች ከአዋጅ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶችን ለባለቤታቸው እንዲመለሱ ኤጀንሲው የሰጠውን ውሣኔ የማስፈፀምና በንብረቱ ላይ ያለውን ባለይዞታ እንዲለቅ ለመወሰን እንደሚችሉ ነገር ግን ይዞታው ወይም ንብረቱ የእኔ ነው ወይም በህግ መሰረት የተወሰደ ነው የሚል መቃወሚያ ቢቀርብላቸው ሊያስተናግዱ እና አከራክረው ሊወስኑ እንደማይችሉ ይደነግጋል፡፡ በሌላ አነጋገር የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 87 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማን በሚያሳካ መንገድ የአዋጅ ቁጥር 110/87 እና የአዋጅ ቁጥር 146/91 አንቀፅ 28 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌዎች መተርጎምና ስራ ላይ መዋል ያለባቸው ሲሆን ፍርድን ስለማስፈፀምና ፍርድ እንዲፈፀም ውክልና ስለመስጠት ከፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 371 ጀምሮ ያሉት አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 37 እና የሥነ ሥርዓት ሕጉ ከታወጀ በኋላ የወጡ ልዩ የህግ ማዕቀፎች አዋጅ ቁጥር 110/87 እና 146/91 ለማስፈፀም በሚያግዝ መልኩ መተርጎምና ሥራ ላይ መዋል ይገባቸዋል፡፡

2. ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የኢትዮጵያ ፐራይቬታይቬሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ አከራካሪው ቤት አመልካች ከአዋጅ ውጪ የተወሰደባቸው መሆኑን በማጣራት ቤቱ ለአመልካች እንዲመለስ የወሰነበትን የውሳኔ ግልባጭ በማያያዝ፣ ውሳኔውን እንዲያስፈፅምለት ለቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ህዳር 17 ቀን 2002 በተፃፈ ደብዳቤ ውክልና ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ በስህተት ነው ቤቱ የተመለሰው የሚል መቃወሚያ ማቅረቡንና የመንግስት አካላት የኤጀንሲው ውሳኔ ከደረሳቸው በኋላ አለመፈፀማቸውን መነሻ በማድረግ የኤጀንሲውን ውሳኔ የማስፈፀም ሥልጣን የለኝም ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡

በመሰረቱ ተጠሪ የኤጀንሲው ውሳኔ የተሳሳተ ነው ወይም በተሳሳተ ማስረጃ መሠረት የተሰጠ ነው ካለ የፍትሐብሔር ሥነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 6 በሚደነግገው መሠረት አቤቱታውን ውሳኔውን ለሰጠው ኤጀንሲ አቅርቦ ከሚያሳርም በስተቀር አፈፃፀሙን ለያዘው ፍርድ ቤት መቃወሚያ መቅረብ የማይችል መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 146/91 አንቀፅ 28(2) ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል መንግስት በህግ በኩል እንደ አንድ ሰው የሚቆጠር መሆኑና በክልል በዞንና በወረዳና በከተማ አስተዳዳሮችና በገጠር ቀበሌዎች ያሉ የመንግስት አካላት ከተፈጥሯዊ ባህሪያቸው ጋር የሚስማሙ መብቶች ያሏቸውን ግዴታዎች ያሉባቸው መሆኑ ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 394 እና 395 ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ስለሆነም የቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪም ሆነ ሌላ በዞኑ የሚገኝ የመንግስት አካል በኤጀንሲው ውሳኔ መሠረት የማይፈፅመበትን ህጋዊ ምክንያት በመስማት ተገቢውን ትዕዛዝ የመስጠት ስልጣን እያለው በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 37 የተደነገገውን ፍትህ የማግኘት መብት፣ ከአዋጅ ቁጥር 146/9/ አንቀፅ 28/2 እና ከአዋጅ ቁጥር 110/87


www.chilot.me

እንደዚሁም አግባብነት ያላቸው የስነ ሥርዓት ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ለማስፈፀም የሚያስችል ሥልጣን እንደሌለው አድርጎ የሰጠው ትርጉምና ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ ማፅናታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የጉራጌ ዞን ቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የጉራጌ ዞን የቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የኢትዮጵያ ፕራይቬታዜሽንና የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲን ውሳኔ የማስፈፀም የዳኝነት ሥልጣን አለው በማለት ወስነናል፡፡
3. የጉራጌ ዞን ቡታጅራ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በማሰማት ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 341(1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

ቤ/መ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 59723

ሰኔ 16 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አብዱልፈታህ መሐመድ - ጠበቃ ጥበቡ ተስፋዬ - ቀረበ

ተጠሪ፡- ኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ፍትሕ ጽ/ቤት የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በገቢ ግብር አዋጅ ቁ 286/94 አንቀጽ 96 እና በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁ 285/94 አንቀጽ 49 እንደዚሁም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 349/1/ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ወንጀል ተፈጽሞአል በማለት ተጠሪ ባቀረበው ክስ መነሻነት የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኝ ወገኖቹን ክርክር ከሰማ በኂላ ተከሣሽ የነበረውን የአሁኑ አመልካችን ጥፋተኛ ነው ብሎአል፡፡ በዚህ መሠረትም በአመልካች ላይ ተገቢ ነው ያለውን ቅጣት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በቅጣቱ አወሳሰን ላይ ባለመስማማት ተጠሪ ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ አፅንቶአል፡፡ በመጨረሻም ተጠሪ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ በማቅረቡ በዚህ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ በመቀጠልም ችሎቱ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡትን የቅጣት ውሣኔ በመሻር አመልካች በስድስት ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኖአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ነሐሴ 24 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች የተጨማሪ እሴት ታክስን በተመለከተ የሚቀርቡ የወንጀል ክሶችን ለማየት ሥልጣን አላቸው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ጭብጥ ግራ ቀኝ ወገኖች ካሰሙት ክርክር ፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ እንዳመለከትነው አመልካች የተከሰሰው በሁለት የተለያዩ አዋጆች የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ወንጀል ፈጽሞአል ተብሎ ነው፡፡ አዋጆቹ የተለያየ ስያሜ እና ተግባር ያላቸው ሲሆኑ ፣ የመጀመሪያው የገቢ ግብር አዋጅ ፤ ሁለተኛው ደግሞ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ናቸው፡፡ የዳኝነት ሥልጣን ጥያቄ ያስነሳው የተጨማሪ እሴት ታክስን መሠረት በማድረግ



www.chilot.me

የቀረበው ክስ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የተነሳው ጥያቄ መታየት ያለበት የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶችን የዳኝነት ሥልጣን በሚመለከት ከተደነገገው የቻርተሩ/የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁ 361/95 አንቀጽ 41 አንፃር ነው፡፡ በተጠቀሰው አንቀጽ 41/2/ የፍ/ቤቶቹ የወንጀል /የደንብ መተላለፍ የዳኝነት ሥልጣን በዝርዝር ተቀምጦአል፡፡ በዚህ መዝገብ ለተያዘው ጉዳይ አወሳሰን ተገቢነት ያለው ድንጋጌ በፊደል /ሀ/ ሥር የተመለከተው ሲሆን፣ ይዘቱም ፍ/ቤቶቹ በቻርተሩ አንቀጽ 52 በተመለከቱ የፋይናንስ ጉዳዮች ላይ በሚነሱ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ሥልጣን ያላቸው መሆናቸውን ይገልጻል፡፡

የቻርተሩ አንቀጽ 52 የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ሥልጣን በዝርዝር የሚያመለክት ሆኖ የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ /4/ እና /5/ም ለተያዘው ክርክር አግባብነት እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ንኡስ አንቀጽ /4/ የከተማው አስተዳደር በራሱ የሚወሰነው እና የሚሰበሰበው የንግድ ትርፍ /የገቢ / ግብር ፣ የኤክሳይዝ ታክስ እና የተርን ኦቨር ታክስ ብቻ እንደሆነ ሲያመለክት ፤ ንኡስ አንቀጽ /5/ ደግሞ በከተማው ከሚኖሩ ግለሰብ ነጋዴዎች እና በከተማው ባለቤትነት ሥር ከሚገኙ የልማት ድርጅቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚሰበሰበው የፌዴራል መንግስት እንደሆነ እና በመጨረሻ ታክሱ የሚሰጠው ለከተማው አስተዳደር መሆኑን ያመላክታል፡፡ እነዚህን ድንጋጌዎች አንድ ላይ አድርገን ስንመለከት መገንዘብ የምንችለው የተጨማሪ እሴት ታክስን የመሰብሰብ ሥልጣን ለከተማው አስተዳደር በሕግ አለመስጠቱን ነው፡፡ ታክሱን የመሰብሰብ ሥልጣን ካልተሰጠው ደግሞ ታክሱን የመክፈል ግዴታ ያለባቸውን ሰዎች የመከታተል፣ በታክስ ሕጉ አፈጻጸም ረገድ ጥፋት ፈጽመዋል የሚባሉትንም የመክሰስ ሥልጣን ተሰጥቶታል ሊባል አይችልም፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ከታክሱ አሰባሰብ ወይም ደግሞ ከታክሱ አዋጅ አፈጻጸም ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ሊከታተላቸው የሚገባው ታክሱን የመሰብሰብ ሥልጣን የተሰጠው የፌዴራል መንግስቱ ነው፡፡ ይህን የማስፈጸም ሥልጣን የተሰጠው የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን እንደመሆኑ የወንጀል ክሱ መቅረብ ያለበት በባለሥልጣኑ ዓቃቤ ሕግ ነው፡፡

ጉዳዩ የፌዴራል መንግስቱ ሥልጣን ነው ከተባለም ክሱ መቅረብ ያለበት ለፌዴራል ፍ/ቤት ነው፡፡ በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ በመተላለፍ ተፈጽሞአል የተባለውን ወንጀል በሚመለከት የቀረበላቸውን ክስ ያዩት በሕጉ ሥልጣን ሳይሰጣቸው ነው ለማለት ችለናል፡፡ ፍ/ቤቶቹ በአዋጅ ቁ 361/95 አንቀጽ 52/4/ እና /5/ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች የተረጎሙበት አግባብ ትክክል አይደለም፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 30746/02 ሚያዝያ 5 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ 13473 ሰኔ 8 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ 13785 ነሐሴ 14 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሻሽለዋል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁ 285/94ን በመተላለፍ በሚቀርቡ የወንጀል ክሶች ላይ የዳኝነት ሥልጣን የላቸውም በማለት ወስነናል፡፡ በዚህ መሠረትም በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ላይ በመመሥረት በአመልካች ላይ የተሰጠው የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሣኔ ብቻ ተሽሮአል፡፡ መዝገቡ ተዘግቶአል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 55162

የካቲት 22 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ዩኒሊበር ፒ.ኤል.ሲ.ፐርት ሰንላይት ዊራል ሜርሲ ሳይድ - ጠበቃ ተሾመ ገ/ማርያም - ቀረበ

**ተጠሪ፡-** ጌት እሸት ዲተርጀንት ማምረቻና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግል/ማህበር - ጠበቃ አድማሱ መአዛ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ተፈጽሞብኛል በማለት አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበውን ክስ መነሻ በማድረግ የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክሱ የቀረበው ለንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን ጽ/ቤት ሆኖ ኮሚሽኑም የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ከሣሽ /የአሁኑ አመልካች/ ያቀረበውን ጥያቄ ተቀብሎአል፡፡ በዚህ መሠረትም ተጠሪ በንግድ አሰራር አዋጅ ቁ.329/95 አንቀፅ 10/2/ሀ/ የተደነገገውን በመተላለፍ አመልካች የሚጠቀምበትን የንግድ ምልክት አስመስሎ በመለጠፍ ምርቱን መሸጡን እንዲያቆም፤ ለዚህ ድርጊቱም በአዋጁ አንቀፅ 26/1/ መሠረት ብር 10,000/አስር ሺህ ብር/ መቀጫ እንዲከፍል ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ውሣኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን ፍ/ቤቱም የንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን ጉዳዩን ለማየት /ለመዳኘት/ ስልጣን የለውም በማለት ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ ሽሮአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤትም በበኩሉ ክርክሩን ከሰማ በኋላ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡አመልካች ሚያዝያ 12 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ በስር ፍ/ቤቶች በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቦአል፡፡ ስህተቱ ይታረምለትም ዘንድ ጠይቆአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሠማው ጉዳይ የንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽን የዳኝነት ስልጣን ስር አይወድቅም የተባለው በህጉ አግባብ ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኙ ወገኖች ያሠሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከስር ጀምሮ የተደረገውን የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር እና የተሰጡትን ውሣኔዎች ይዘት በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ ከዚህም በቅድሚያ ልንገነዘብ የቻልነው አመልካች ክስ የመሰረተው የንግድ

ምልክት ምዝገባና ጥበቃ መብትን ለማስከበር ወይም የንግድ ምልክት ባለቤትነት መብትን ለማረጋገጥ ሳይሆን ፣ ከህግ አግባብ ውጪ ተፈጽሞብኛል ያለውን የማይገባ የንግድ ውድድር እንዲገታለት /እንዲቆም/ እና ተጠሪም ለዚህ ድርጊቱ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድበት በመጠየቅ እንደሆነ ነው፡፡ ክሱን የሰማው የንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽንም የቀረበለት የዳኝነት ጥያቄ የተፈጸመውን እና በመፈጸም ላይ ያለውን ያልተገባ የንግድ ውድድር እንዲቆም፣ ተጠሪም በአዋጁ መሠረት እርምጃ ይወሠድበት የሚል እንደሆነ በመገንዘቡ የንግድ ምልክት ጥበቃን /አዋጅ ቁ. 501/98/ በሚመለከት የሚነሣውን ክርክር የመዳኘት ስልጣን የለህም በማለት ከተጠሪ ቀርቦለት የነበረውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ በጉዳዩ ስረ ነገር ላይ አከራክሮ ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ የስር ከሣሽ /አመልካች/ ክስ የንግድ ምልክት ባለቤትነት ማዕከል ያደረገ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ጉዳዩ በኮሚሽኑ የዳኝነት ስልጣን ስር አይወድቅም በማለት ወስኖአል፡፡

የኮሚሽኑ ውሣኔ እንዳየነው የተመሰረተው በንግድ አሰራር አዋጅ ቁ. 329/95 አንቀጽ 10 እና 15 በተቀመጡት ድንጋጌዎች ላይ ነው፡፡ አመልካችም ክሱን የመሰረተው በእነዚህ ድንጋጌዎች እና ያልተገባ የንግድ ውድድርን በሚመለከት በንግድ ህግ ቁ. 133 የተቀመጠውን ድንጋጌ በመጥቀስ ነው፡፡ ተጠሪ የፈጸመው እና እየፈጸመው ነው ያለውን ድርጊትም በዝርዝር በመግለጽ አቅርቦታል፡፡ የንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን ያልተገባ የንግድ ውድድርን በሚመለከት የሚነሣውን ክርክር የመዳኘት ስልጣን ያገኘው በአዋጅ ቁ. 329/95 አንቀጽ 15 መሠረት ነው፡፡

በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1/ሀ/ እና /ሰ/ እንደተመለከተው ኮሚሽኑ ከማንኛውም ወገን የሚቀርቡለትን አቤቱታዎች የአዋጁ ድንጋጌዎችን የመተላለፍ ድርጊት ተፈጽሞአል በሚል እስከቀረቡ ድረስ አቤቱታዎቹን የመመርምር እና በመጨረሻም እንደአግባቡ አስተዳደራዊ እርምጃዎች እና /ወይም የቅጣት ውሣኔ የመስጠት ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በዚህ ረገድ አግባብነት ያላቸው ማለትም ለአቤቱታው መቅረብ መነሻ ሊሆኑ የሚችሉት የአዋጁ ድንጋጌዎችም ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድርን በተመለከተ ዝርዝር ነገሮችን የያዘው አንቀጽ 10 ፣ ገበያን በበላይነት ያለአግባብ ስለመጠቀም በሚል የተደነገገው አንቀጽ 11 'ን' መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአዋጁን ዓላማ በዝርዝር ያስቀመጠው አንቀጽ 3 'ንም' መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ የአዋጁ ዓላማ :-

/1/ ለነጻ ገበያ ውድድር እንቅፋት የሆኑ ድርጊቶችና ተገቢ ያልሆኑ የንግድ ስራዎች እንዳይፈጸሙ በመከላከልና በማስወገድ ተገቢ የንግድ ውድድር እንዲሰፍን ለማድረግ እና

/2/ በንግድ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች አቅርቦት እና ስርጭት ላይ ገደብ የሚፈጥሩ ድርጊቶችን በመከላከልና በማስወገድ የተጠቃሚውን ህብረተሰብ ጥቅም ማስጠበቅ ነው፡፡

በሚል በዝርዝር ተቀምጦአል፡፡

ቀደም ሲል እንዳመለከትነው ተጠሪ በአዋጅ ቁ. 329/95 አንቀጽ 10/2//ሀ/ የተቀመጠውን ድንጋጌ ስለመተላለፉ በአመልካች ክስ ተገልጾአል፡፡ የድርጊቱ አፈጻጸም ምን እንደሚመስልም በክሱ በዝርዝር ተመልክቶአል፡፡ የተጠቀሰው አንቀጽ 10/2/ሀ/ በሌላው የንግድ ድርጅት ወይም በንግድ ድርጅቱ ተግባሮች፣ በተለይም ድርጅቱ ከሚያቀርበው ምርት ወይም አገልግሎት ጋር በተገናኘ ሁኔታ ማደናገርን ያስከተለ ወይም ሊያስከትል የሚችል ማናቸውም ድርጊት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ሆኖ እንደሚቆጠር ያመለክታል፡፡ ተጠሪ ፈጽሞታል ወይም እየፈጸመው ነው ተብሎ

በአመልካች ክስ የተነገረውም ይኸው በድንጋጌው የተመለከተው ድርጊት ነው፡፡ የአመልካች የክስ መነሻ ተጠሪ እኔ የምጠቀምበትን የንግድ ምልክት አመሣስሎ በመለጠፍ ምርቱን እየሸጠ ነው የሚል ነው በአጠቃላይ የአመልካች በአዋጅ ቁ. 329/95 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የመተላለፍ ድርጊት ተፈጽሞብኛል በሚል ብቻ የሚያቆም ሣይሆን፣ ተፈጻሚ የሚላቸው ድርጊቶች ከህጉ ጋር ያላቸውን ግንኙነት /አግባብነትም/ በግልጽ እና በዝርዝር የሚያሣይ ነው፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ ከንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ መብት አከባበር አንጻር የሚታይ ነው /አዋጅ ቁ 501/98/ ለማለት የቻለው ተጠሪ የአመልካችን የንግድ ምልክት አመሣስሎ በመለጠፍ ምርቱን እየሸጠ ነው የሚለውን በአመልካች ክስ የተቀመጠውን አባባል አጉልቶ በማውጣት እንደሆነ ከውሣኔው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡

በበኩላችን እንደምንገነዘበው በተያዘው ጉዳይ የንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን የዳኝነት ስልጣን አለው ወይም የለውም? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በዋናነት መታየት ያለበት የክሱ አጠቃላይ ይዘት እና የተጠየቀው ዳኝነት ነው፡፡ ሌላው በመቀጠል መታየት ያለበት ጉዳይ አመልካች እና ተጠሪ በንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ብቻ ሣይሆኑ፣ ተመሣሣይነት ያለው ዕቃም ለገበያ እያቀረቡ ናቸው፡፡ አመልካች ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ተፈጽሞብኛል የሚለውም ተጠሪ የሱ ያልሆነውን የንግድ ምልክት /አመልካች ባለቤት የሆነበትን/ አመሣስሎ በሚሸጠው ምርት መያዣ ዕቃ ላይ በመለጠፍ እየሸጠ /ለገበያ እየቀረበ/ ነው በማለት ነው፡፡ ድርጊቱ ያልተገባ ውድድር ነው እየተባለ ያለውም አመልካች ከሚያቀርበው ምርት ጋር ማደናገርን አስከትሎአል ስለተባለ ወይም ሊያስከትል የሚችል ሆኖ በመታየቱ ነው፡፡ በመሆኑም በክሱ አቀራረብ ወይም በክርክር ሂደት ስለንግድ ምልክት በመነሣቱ ጉዳዩ የንግድ ምልክት ባለቤትነት መብት ወይም ምዝገባና ጥበቃን የሚመለከት ነው ማለት አይችልም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት የደረሱበት መደምደሚያ የህግ መሠረት የለውም፡፡ ጉዳዩ በንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው፡፡

በመጨረሻም ተጠሪ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያለበትን ምክንያት አይተናል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ እንደተመለከተው የንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽንን የዳኝነት ስልጣን በሚመለከት ብቻ ነው ተጠሪ ቅሬታውን ያሰማው፡፡ ከዚህ ባለፈ ኮሚሽኑ በስረ ነገር አጣርቶ በደረሰው መደምደሚያ ላይ ክርክር /ይግባኝ/ አላቀረበም፡፡ በመሆኑም ከዚህ በኋላ በስረ ነገር ላይ የሚደረግ ክርክር የለም፡፡ ጉዳዩ በህጉ አተረጓጎም ረገድ የተፈጸመውን መሠረታዊ ስህተት ማረም ከዚሁ የሚቋጭ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 67927 ሚያዝያ 15 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 46554 የካቲት 25 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ላይ የመሰረተው ክስ በንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው ብለናል፡፡ ስለዚህም ኮሚሽኑ በን.አ.አ.ኮ/1-2-58 መጋቢት 26 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ጸንቶአል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሣቸውን ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 37964

ጥር 27 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፣** ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

በላቸው አንሺሶ

አሊ መሐመድ

***አመልካች*** - የአቶ መሐመድ ሁሴን ወራሾች

1. አቶ ዓሊ መሐመድ
2. ዶ/ር ዘምዘም መሐመድ ሁሴን
3. ወ/ሮ ሮዛ መሐመድ ሁሴን

} ጠበቃ አቶ ወንድሜነህ ዳኘው ቀረቡ

***ተጠሪዎች*** - 1. የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ነ.ፈጅ አቶ ደስታ ሊበን

2. አቶ ኃይለስላሴ ገ/መድህን አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው በተደረገው ምርመራ መሠረት ተገቢውን ለመሥራት ሲሆን በዚሁ መሠረት የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የግራቀኙን ጉዳይ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ተቀብለው ለማየት ሥልጣን የላቸውም በጉዳዩም ላይ ቢሆን የአሁን አመልካቾች ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም በሚል ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ አግባብነት ለጉዳዩ ተፈፃሚነትካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት ሲባል ነው፡፡

ይህንን ጉዳይ ፍ/ቤቶች ተቀብለው ለማስተናገድ የሚያስችላቸው ሥልጣን አላቸው ወይስ የላቸውም? እንዲሁም አመልካቾች በጉዳዩ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚሉትን ሁለት አከራካሪ ነጥቦች ለመለየት ከእነዚህ ጭብጦች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የፍሬ ነገርም ሆነ የህግ ክርክሮች በእነዚህ ጭብጦች ላይ ከታች ባሉት ፍ/ቤቶች በየደረጃው የሰጡት ውሣኔዎች እና ግራቀኙም በጉዳዩ ላይ በሰበር ደረጃ ያቀረቡትን ክርክር ባጭር ባጭሩ ለመጥቀስ ያህል የአሁን አመልካቾች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በከሣሽነት ያቀረቡት የክስ አቤቱታ የአውራሻችን ንብረት የሆነው በኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት በቁጥር 785 በቀበሌው ቁጥር 786 ከሚታወቀው ቤት ውጭ ሌላ ቤት ስላልነበራቸው አዋጅ ቁጥር 47/67 በወጣበት ጊዜ በቅጽ 004 ተረክበው እያለ ከዚህ ዓለም በሞት በተለዩበት ጊዜ በ1970 ዓ.ም አስረክባችሁ እንደገና ትጠይቃላችሁ በሚል በማስገደድ ቅጽ 003 እንዲሞላ አድርገው እንደ አዋጁ ያልተወረሰውን ንብረት ወስደውብናል ይህንኑ የንብረት ባለቤትነት መብት ለማስከበር ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ጥያቄ



www.chilot.me

ብናቀርብም እነዚህን ቅጾች መነሻ በማድረግ ጉዳዩ በእኔ ሥልጣን ሥር የሚወድቅ አይደለም በማለት አሰናብቶናል ስለሆነም በአዋጁ መሠረት ያልተወረሰውን ንብረት በጥንቃቄና በኃይል ወስዶ ከህግ ውጭ ለ3ኛ ተጠሪ አሳልፎ የሰጠ ስለሆነ ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1994 ዓ.ም ድረስ ያለውን የቤት ኪራይ ብር 390,000 ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ያለውን ደግሞ የመጠየቅ መብታችንን ከማስጠበቅ ጋር ንብረቱን እንዲያስረክቡ ይድረግልን የሚል ነው፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ የቤቱ ባለቤት ስለመሆናቸው ማስረጃ ያላቀረቡ ስለሆነ በጉዳዩ ላይ የመክሰስ መብት የላቸውም ቅፅ 004 ከተሞላ በኃላ መልሰው በቅፅ 003 አስረክበዋል፡፡ ቅጽ 004 እንደቋሚ የባለቤትነት ማስረጃም አያገለግልም፡፡ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በቅፅ 003 በትርፍነት ተሞልቶ ማስረከባቸውን አረጋግጦ አቤቱታውን አልተቀበለውም፡፡ በመሆኑም ቤቱ ሊመለስላቸው አይገባም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

የአሁን 2ኛ ተጠሪም በበኩሉ ከከሣሾች ጋር የውል ግንኙነት ስለሌለኝ እኔን የመክሰስ መብት የላቸውም ጉዳዩን ማየት የሚችለው ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ነው ኤጀንሲው በሰጠው ውሣኔ ቅር ከተሰኙ ለኤጀንሲው ሥራ አመራር ቦርድ ያቀርባሉ እንጂ ፍ/ቤቱ ሊመለከት አይችልም ቤቱ በአዋጅ የተወረሰ ነው በአዋጁ መሠረት ተገቢውን ካሣ ከሚጠይቁ በቀር እኔን ከቤቱ ለማስወጣት የሚያስችል መብት የላቸውም የንግድ ድርጅቱንም በህግ አግባብ ገዝቻለሁ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ክሱ የቀረበበት የከፍተኛው ፍ/ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ያለው የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እንጂ ፍ/ቤት አይደለም በሚል የቀረበውን ክርክር አስመልክቶ የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 110/87 መሠረት ከአዋጅ ውጭ በትዕዛዝና በቀላጤ የተወረሱ ንብረቶችን እንጂ ከሣሽ ያቀረቡትን ከህግ ውጭ ቤት ተወርሶብኛል የሚልን ጥያቄ ለመመልከት ሥልጣን የሌለው በመሆኑ ተቃወሚቸው ተቀባይነት የለውም፡፡

ዋናውን ጉዳይ በሚመለከት ቤቱ በተወረሰበት ወቅት ሌላ ቤት የሌላቸው መሆኑን 1ኛ ተከሣሽ የአሁን 1ኛ አመልካች በ18/10/72 ዓ.ም ለከሣሾች የኪራይ ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ከፃፈው ደብዳቤ ለመረዳት ተችሏል፡፡ የከሣሾች አውራሽ ክስ የቀረበበትን ቤት ሌላ ቤት ስለሌላቸው በአዋጁ መሠረት ቤቱ ተፈቅዶላቸዋል ተብሎ በ21/3/68 ዓ.ም ቅፅ 004 የሞሉ ሲሆን በሌላ በኩል በ1970 ዓ.ም ቤቱ ትርፍ ነው ተብሎ ቅፅ 003 ተሞልቷል፡፡ ነገር ግን በዚሁ ቅፅ 003 በተሞላበት ፎርም ላይ ክስ የቀረበበት ቤት ትርፍ ነው ተብሎ ከተሞላው ቤት ሌላ የመረጡት ቤት አልተገለፀም ይህም ከሣሾች አንድ ቤት ብቻ ያላቸው መሆኑን ያመለክታል ተከሣሾች ከሣሾች ቤቱን በቅፅ 003 ሞልተው ቤቱ በትርፍነት ተወርሷል በማለት ይከራከሩ እንጂ አዋጁን አስፈፃሚ እንደመሆናቸው መጠን የአዋጁን መንፈስ የሚቃረኑ ከሆነ ህገወጥ ናቸው የማይባሉበት ምክንያት አይኖርም ተከራይ ነኝ የሚለው የአሁን አመልካች ድርጅቱን ከ1ኛ መልስ ሰጭ ተከራይቼ እየተገለገልኩበት እገኛለሁ የሚለው ክርክሩ ክርክር ከተነሳበት ቤት ጋር የሚገናኝ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም በመሆኑም ከላይ በተገለፁት ምክንያቶች በአዋጁ መሠረት ሊወረስ የሚገባው ትርፍ ቤት ከሆነ ብቻ ስለሆነ ቅጽ 003 ተሞልቶ ተወርሷል የሚለው ክርክር ህጋዊ መሠረት ስለሌለው እና ከህግ ውጭ መወረሱን ስለሚያስረዳ ተከሣሾች ቤቱን ሊመልሱ ይገባል ቤቱ በኪራይ ያስገኘውን የገንዘብ መጠን አስመልክቶ የቀረበ ክርክር ስለሌለም ከብር 390,000 /ሶስት መቶ ዘጠኛ ሺህ/ ጋር ለከሣሾች ያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ እና 2ኛ ተጠሪዎች በተናጠል ያቀረቡትን የይግባኝ መዝገብ አጣምሮ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 24633 የካቲት 28 ቀን 2000



www.chilot.me

በዋለው ችሎት ከሣሾች በአዋጅ ቁጥር 110/87 መሠረት ሥልጣን ላለው ለፕራይቬይታይዜሽን ኤጀንሲ ቤቱ እንዲመለስላቸው ጠይቀው ቤቱ በቅጽ 003 ተሞልቶ በመሰረዙ ምክንያት ጥያቄያቸው ተቀባይነት ማጣቱን የክስ ማመልከቻቸው እያስረዳ ሥልጣን ያለው አካል ውሣኔ ያሰፈረበትን ነጥብ ቤቱ ከህግ ውጭ የተወረሰ ነው በማለት ከፍተኛው ፍ/ቤት መወሰኑ በሌለው ሥልጣን ነው፣

ከዚህም በተጨማሪ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ቤቱ ትርፍ ነው አይደለም ሊወረስ ይገባል አይገበም? ብሎ የመወሰን ሥልጣን ያለው የሥራና ከተማ ቤቶች ሚ/ር ስለመሆኑ በአዋጁ ተጠቅሶ እያለ ከሣሾች ትርፍ ቤት ሳይኖራቸው የተወረሰባቸው ያለአግባብ ነው ማለቱ በሌለው ሥልጣን በመሆኑ እንዲሁም ቤቱ ከተወረሰ በኃላ በአዋጅ ቁጥር 47/67 ሆነ ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 292/18 መሠረት ቤቱ እንዲመለስላቸው በወቅቱ አጠራር ለሥራና ቤቶች ሚ/ር አመልክተው እንዲመለስላቸው ተወስኖ ውሣኔው በሚ/ሩ የፀደቀበትን ማስረጃና በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1195/1/ መሠረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነታቸውን ለማወቅ የተሰጣቸው የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ስላላቀረቡ ከሣሾች ከመነሻውም ቢሆን ክስ በቀረበበት ሐብት ላይ ጥቅም ወይም መብት ያላቸው መሆኑን ስላላረጋገጡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33/2/መሠረት በቤቱ ላይ ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም፡፡

ስለሆነም በእነዚህ ነጥቦች ላይ ያቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መቀበል ሲገባው አልፎ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሣኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነው የአሁን አመልካቾች በዚህ የጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ተፈፅሟል የሚሉትን የህግ ስህተት ለማሳየት ዝርዝር የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ሲሆን ፍሬ ቃሉም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በቤቱ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችላቸው መብት የላቸውም በማለት የሰጠው ውሣኔ ያቀረብነውን የፍሬ ነገር ክርክርና ማስረጃ መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡

እንዲሁም የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ማስረጃዎችን አጣርቶ ቅጽ 003 የተሞላው ከህግ ውጭ መሆኑን በኤክስፐርቶች ካረጋገጡ በኃላ ቤቱ ሊመለስ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ ሆኖም የኤጀንሲው ሥራ እስኪያጅ ቅጽ 003 በህግ አግባብ ያልተሞላ ቢሆንም ሰነዱ ህጋዊነት አለው ወይስ የለውም የማለት ሥልጣን ለኤጀንሲው አልተሰጠውም ስለዚህ ሰነዱ በህግ ውጤት የለውም ቤቱ ሊመለስ ይገባል ለማለት አይችልም ከማለት ውጭ ቅፅ 003 በህግ አግባብ የተሞላ እና ቅጽ 004ን የሻረ ነው አላለም ስልጣን የለኝም ማለት በጉዳዩ ላይ ውሣኔ ተሰጠ ማለት አይደለም ስለሆነም ማንኛውም ሰው በህገ መንግስቱ የተረጋገጠለትን መብት ያለህግ የግል ንብረቱን ማጣት የለብኝም በማለት መብቱን ማስከበር የሚችለው በፍ/ቤት ዳኝነት በመጠየቅ በመሆኑ ኤጀንሲው የመጨረሻ ውሣኔ ባልሰጠበት ጉዳይ የቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ ፍ/ቤት የማየት ሥልጣን አለው የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎችም በየፊናቸው ለሰበር አቤቱታው መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡ በይዘቱም በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት እና በይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡትን መልስና ቅሬታ የሚያጠናክር የጠቅላይ ፍ/ቤቱ የሰጠውን ዳኝነት ትክክለኛነት የሚያስገነዝብ በመሆኑ በድጋሚ ማስፈሩ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

አመልካቾችም በመልስ መልሳቸው በፅሑፍ ያቀረቡት ክርክር በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤቶች የቀረበውን የሚያብራራ እና የሚያጠናክር ነው፡፡

እንግዲህ የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ይህንን ጉዳይ የከፍተኛው ፍ/ቤት ተመልክቶ ለመወሰን ሥልጣን የለውም በሚል ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠውን ዳኝነት በማስቀደም ተመልክተናል፡፡

በኢት/ያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስት አንቀጽ 37 እንደተደነገገው አንድን ጉዳይ ተመልክቶ ዳኝነት ለመስጠት ሥልጣን የተሰጠው ለሌላ የዳኝነት አካል ከሆነ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የላቸውም ለሌላ በህግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል መቅረብ የሚገባው ጉዳይ ለፍ/ቤቶች በቀረበ ጊዜ ጉዳዩ በየትኛው የክርክር ደረጃና በየትኛውም የፍ/ቤት እርከን ቢገኝም በሥልጣን ምክንያት ክርክሩ ሊቋረጥ እና ቀሪ ሊሆን እንደሚገባ ይኸው ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ ሆነ በዝርዝር ህጉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 231/1/ /ለ/፣ 9/2/፣ 244/3/ እና 328/3/ ተመልክቷል፡፡

በዚህም መሠረት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በይግባኝ የቀረበለትን ጉዳይ ከፍ/ቤቶች ሥልጣን አንፃር መመርመሩ አግባብ ቢሆንም ይህ ጉዳይ ቀደም ሲል ለፐራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቀርቦ የታየና ውሣኔ ያገኘ ጉዳይ ስለሆነ ፍ/ቤቶች ተቀብሎ ለማስተናገድ የሚያስችላቸው ሥልጣን የለውም በሚል የሰጠው ዳኝነት ስለጉዳዩ ግራቀኙ በፍሬ ነገር ረገድ ያቀረቡትን ክርክር መሠረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም ይኸውም ለዚሁ ውሣኔ እንደመነሻ ያደረገው ጉዳዩ ለፐራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቀርቦ ውሣኔ ያገኘ ስለመሆኑ የከሣሾች የክስ ማመልከቻ በግልፅ ያስረዳል የሚለውን በመያዝ ነው ይሁን እንጂ የከሣሾች የክስ ማመልከቻ ክሱ ቀርቦለት የነበረው የፐራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ መምሪያ ቤቱ በአዋጁ መሠረት ያልተወረሰ መሆኑን አረጋግጦ እንዲመልስልን የወሰነልን ቢሆንም ዋና ስራ አስኪያጅ ጉዳዩ በኤጀንሲው ሥልጣን ሥር የማይወድቅ መሆኑን ጠቅሶ ሥልጣን የለኝም ብለናል የሚለውን የሚጠቅስ እንጂ እንደይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ የሚናገር አይደለም፡፡

አመልካቾችም ይህንኑ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ በመንቀፍ በሰበር አቤቱታቸው ገፅ 4 የመጨረሻ ክፍል ላይ ኤጀንሲው ጉዳዩን ተመልክቶ ውሣኔ የሰጠበት ጉዳይ ሳይሆን ሥልጣን የለኝም በማለት ነው ያሰናበተን በማለት ላቀረቡት ቅሬታ 1ኛ መልስ ሰጭ በሰጠው መልስ ገፅ 3 የመጨረሻ ክፍል የፐራይቨታይዜሽን ኤጀንሲም ቢሆን ይህን የማጣራትም ይሁን ትክክለኛነቱን ወይም ህገ ወጥነቱን የመመርመር ሥልጣን የሌለው መሆኑን በመግለፅ መዝገቡን ዘግቶታል ቤቱ የተወረሰው ከአዋጁ ውጭ ነው በማለት ቤቱ እንዲመለስላቸው በኤጀንሲው የተሰጠ ውሣኔ የለም በማለት ጉዳዩ በኤጀንሲው በኩል ቀርቦ ክርክር ተደርጐ ማስረጃ ተመርምሮ ተገቢውን ዳኝነት ያረፈበት ሳይሆን ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት የዘጋው መሆኑን ሁሉ አረጋግጧል ይህ ሆኖ እያለ ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት በጉዳዩ በኤጀንሲው ታይቶ ዳኝነት ያረፈበት ጉዳይ ነው የሚለውን መነሻ አድርጎ ጉዳዩን የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የማየት ሥልጣን አልነበረውም በማለት የሰጠው ዳኝነት የግራቀኙን ክርክር መሠረት ያደረገ ባለመሆኑ የተነሣ የተሳሳተ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 110/87 እንደተመለከተው ጉዳዩ በፐራይቬታዜሽን ኤጀንሲ ሥልጣን ሥር የሚወድቅ አይደለም ተብሎ መመለሱ ከተረጋገጠ እና አሁንም ቢሆን ይህን ጉዳይ አይቶ ለመወሰን ሥልጣኑ ለሌላ የዳኝነት አካል የተሰጠ ነው የሚል የህግ ክርክር እስካልቀረበ ድረስ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ድንጋጌ ይህንኑ ጉዳይ በፍ/ቤት ቀርቦ እንዳይታይ የሚከለክል አይደለም በዚህ ረገድ የሥር ጠቅላይ ፍ/ቤት ሥልጣኑን አስመልክቶ የሰጠው ትርጓሜ የግራቀኙን ክርክር ይዘት ካለማገናዘብም ሆነ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌ አንፃር ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

እንዲሁም ትርፍ ቤት ነው ወይስ አይደለም? ሊወረስ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውንም ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት አዋጁን ለማስፈፀም ሥልጣን በተሰጠው አካል



www.chilot.me

ከሚታይ በቀር የፍ/ቤቶችን ዳኝነት የሚጠይቅ ጉዳይ ባለመሆኑ ፍ/ቤቱ ሥልጣን የለውም በሚል በሁለተኛ ደረጃ የሰጠውንም ትርጉም እንደተመለከትነው ከሣሾች ያቀረቡትን የክርክር ይዘት ያገናዘበ አይደለም የከሣሾች የክስ መነሻ አውራሻችን አዋጅ ቁጥር 47/67 በወጣበት ጊዜ ከዚህ ክርክር ካስነሳው ቤት ሌላ ትርፍ ቤት የሌላቸው መሆኑን በማረጋገጥ አዋጁን ለማስፈፀም ሥልጣን በተሰጠው አካል ተረጋግጦ በ21/03/68 ዓ.ም ቅፅ 004 ተሞልቶ ቤቱ ሳይወረስ በአባታችን ባለቤትነት ዘልቆ ቆይቷል በባለቤትነት መብታቸውም እየተገለገሉበት እያለ በ1970 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን ምክንያት በማድረግ እኛን ወራሾችን ከቤት አስመጥተው እንደተወረሰ አድርገው ቅጽ 003 በመሞላት ያልተወረሰን ንብረት ተወስዶብናል በማለት ቤቱን ለማስመለስ አዋጁን ለማስፈፀም ሥልጣን የተሰጠው አካል ያደረገውን የፈቃድ ተግባር መነሻ በማድረግ የሚከራከሩ መሆኑን ያገናዘበ አይደለም በእነዚህ ፍሬ ነገሮች በመመሥረት የቀረበው የቤት ይመለስልኝ አቤቱታ ከመነሻውም በፍርድ ሊያልቅ የሚችል አይደለም ከሚል መደምደሚያ ለመድረስ የሚያስችል የህግ መሠረትም አላገኘንበትም ከዚህም ነጥብ አንፃር ቢሆን ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ተቀብለው ለመወሰን የሚያስችል ሥልጣን የላቸውም የሚለው ትርጉም ህጋዊ መሠረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሶስተኛውና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሣኔ ለመሻር በምክንያትነት የጠቀሰውን የክስ ምክንያት የላቸውም የሚለውንና የዳኝነት አግባብነት የአሁን አመልካቾች በክስ ማመልከቻቸው ላይ ከገለፁት የክስ ምክንያት እና የማስረጃ ዝርዝር ጋር ተገናዝቦ ሊታይ ይገባዋል፡፡

አመልካቾች በሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት የክስ ማመልከቻና የማስረጃ ዝርዝር ላይ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ከአዋጅ ቁጥር 47/67 በፊት ሀብትነቱ የአባታቸው የአውራሻቸው የነበረ መሆኑን አዋጁ እንደወጣም በአዋጁ መሠረት ትርፍ ቤት የሌላቸው መሆኑ ሥልጣን በተሰጠው አካል በቅፅ 004 ተረጋግጦ ህዳር 21 ቀን 1968 ተሞልቶ ተሰጥቷቸው በባለቤትነት በይዞታቸው እያለ በ1970 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን በ1970 ዓ.ም የቤቱ ባለቤት ከዚህ ዓለም በሞት እንደተለዩ በተደራቢ ቅፅ 003 የአሁን 1ኛ ተጠሪ እንደተረከበው ጠቅሰዋል ይህም ስለመሆኑ በየደረጃው የተሰጠው ውሣኔም ያስረዳል፡፡

እንዲሁም አመልካቾች በክስ ማመልከቻቸውና በሰበር ደረጃ በተደረገው ክርክር እንደገለፁት በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ የተደረገው ክርክርና ማስረጃ ከተሰማ በኋላ መምሪያው የሰጠው ውሣኔ በሥልጣን ምክንያት ቀሪ ይሁን እንጂ የቤቱ አወራረስ እንደ አዋጁ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን አስመልክቶ የኤጀንሲው ኤክስፐርቶች አረጋግጠው መምሪያው እንዲመለስ አድርጎ ነበር ለሚለው ክርክራቸው ተጠሪውም ይህ ውሣኔ የመ/ቤቱ የበላይ ውሣኔ አይደለም ተፈፃሚነት የለውም የተቋም ውሣኔ እንደሆነ አይቆጠርም በሚል ተከራከሩ እንጂ በፍሬ ነገር ረገድ ሐሰት ነው አልተባለም የሚል ማስተባበያ አላቀረቡበትም ስለጉዳዩ በሌላ የዳኝነት ሰጭ አካል በተደረገ ክርክር የተረጋገጠ ጉዳይ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ክርክር በቀረበ ጊዜ ያለው ተቀባይነት ምን ያህል ነው? የሚለው አከራካሪ ነጥብ እንዳለ ሆኖ አሁን ለተያዘው የመክሰስ መብት አላቸው ወይስ የላቸውም የሚለውን ለመለየት ግን አግባብነት ያለው በመሆኑ እነዚህ ፍሬ ነገሮችና የከሣሾች የማስረጃ ዝርዝር በጉዳዩ ላይ ክስ የማቅረብ መብት ያላቸው ለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33/2/ አንፃር ሲታዩ በቂ መነሻዎች ናቸው፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ መብትና ግዴታን ወደ ተግባር ለመለወጥ የሚረዳ መሣሪያ እንደመሆኑ ክስ የሚያቀርብ ወገን ክስ የሚያቀርብበት ጉዳይ ከህግ በመነጨ መብት የተደገፈ ተከሣሹም መብቱን

ለማሟላት በህግ ግዴታ የተጣለበት መሆኑን ሊያሳይ ይገባዋል በሚል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33/2/ እና /3/ የተቀመጡት ድንጋጌዎች ተገቢ ያልሆነ ክስ እንዳይቀርብ መገደቢያዎች ከመሆኑ አንፃር ስታይ በዚህ ጉዳይ ከሣሾች በጉዳዩ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ያላቸው ስለመሆኑ በክሳቸው የገለፁት የክስ ዝርዝር እና ማስረጃ አረጋገጭ ናቸው ጉዳዩን ለማስረዳት በብቸኝነት መቅረብ የሚገባው የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ነው ለማለትም አያስችልም፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ በተመሳሳይ ጉዳይ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት ተመልክቶ ከዚህ በፊት የመክሰስ መብት የለም በሚል ስለተረጋገጠው በዚያው አንፃር ይታይልን በማለት በሰበር መ/ቁ 14094 በአመልካች የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና በአቶ ሰለሞን ወረደ መካከል የነበረውን ጉዳይ በመጥቀስ ሁለተኛ አመልካች ያቀረበውን ክርክር ተመልክተናል፡፡ በተመሳሳይ ጉዳይ የሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው የህግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ ላለ ፍ/ቤት የአስገዳጅነት ባህሪ የሚኖረው ጉዳዮች በፍሬ ነገር እና በማስረጃ አቀራረብ ተመሳሳይ ሆነው በተገኙ ጊዜ ለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 454/97 አስረጂ ነው በሰበር መ/ቁ 14094 በተነሳው ጉዳይ ቤቱን በውርስ ይገባኛል ሲል ክስ ያቀረበው ወገን ከአዋጅ ቁጥር 47/67 በፊት የነበረን ካርታና የቤት ሥራ ፈቃድ መሠረት በማድረግ የቀረበ ከመሆኑ በቀር በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ሊወረስ የማይገባበትን ምክንያት አዋጁን መሠረት በማድረግ ያቀረበው ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም ከአዋጁ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የህግ ጥያቄ ሊያስነሳ የሚችል ለመሆኑ መነሻ የሚሆኑ የፍሬ ነገሩና የማስረጃ ጉዳይ የቀረበበት አይደለም በክርክርና በማስረጃ ረገድ ሁለቱም የተለያዩ ናቸው ስለሆነም በተመሳሳይነት የሚወሰንበት አግባብ አላገኘንበትም በዚህ ሁሉ ምክንያት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ክስ የቀረበለት ፍ/ቤት ጉዳዩን ለመመልከት የሚያስችለው ሥልጣን የለውም በሚል እና በጉዳዩም ቢሆን አመልካቾች ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት የላቸውም በሚል የሰጠው ትርጉም የግራቀኙን የክርክር ይዘትና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ባለማገናዘብ የተሰጠ ትርጉም በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/መ/ቁ 24633 የካቲት 28 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾች ክስ ባቀረቡበት ጉዳይ ክስ የማቅረብ መብት አላቸው ጉዳዩንም ተመልክቶ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ የሰጠው በሥልጣኑ ስር የሚወድቅ ሆኑ በመገኘቱ ነው ብለናል፡፡
3. ጉዳዩ የሚያስከስስ እና በስር ፍ/ቤት ስልጣን ስር የሚወድቅ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33/2/ ሆነ በሥልጣን ምክንያት ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የሚቋጭ ስላልሆነ በቀሪው ጉዳይ ላይ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በይግባኝ ሥልጣኑ ተመልክቶ ተገቢውን ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 341 መሠረት ጉዳዩን መልሰናል፡፡

በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙ ላደረሱት ክርክር ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 51790

ግንቦት 16 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** ፡- 1. እነ ወልዳይ ዘሩ (61 ሰዎች) - ጠበቃ ዳንኤል ብርዬ ቀረቡ

2. አቶ ቴዎድሮስ ይልማ - የቀረበ የለም

3. አቶ አማረ ተረፈ - " "

4. እነ አቶ ጀማል አህመድ (ሶስት ሰዎች) - የቀረበ የለም

5. አቶ ትግስቱ ጥላሁን - የቀረበ የለም

6. አቶ ቀዳማዊ ረታ - የቀረበ የለም

7. እነ አቶ አሰለፈው ገድፍ (ሁለት ሰዎች) የቀረበ የለም

8. እነ አሸናፊ አማረ (ሁለት ሰዎች) - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ እስከዳር አዘዘው ቀረቡ፡፡

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ በመ/ቁጥር 51789፣ 51792፣ 51794፣ 51798፣ 53301፣ 53460 እና 57247 ከቀረቡት ጉዳዮች ጋር ተመሳሳይ የሕግ ጥያቄ ያለበት በመሆኑ መዝገቦችን አንድ ላይ አጣምረን በመመርመር ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37/1/ መሠረት ሠራተኛን በልዩ ሁኔታ ከሥራ ስለማሰናበት የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት ሲሆን በዚሁ ፍርድ ቤት አቤቱታ ያቀረቡት የአሁኑ አመልካቾች ናቸው፡፡ የአመልካቾች አቤቱታ ይዘት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እየተገበረ ባለው የመሠረታዊ አሰራር ሂደት ለውጥ ምክንያት ምደባ ሳያገኙ የቀሩ በመሆኑ እረፍት እንዲወስዱ መደረጉንና ለአስራ አንድ ወራት ደመወዝ ሲከፍላቸው ቆይቶ ሐምሌ 01 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውላቸው ተቋርጦ ከስራ መሰናበታቸው ከሕግ ውጪ መሆኑን ገልፀው ወደ ስራ እንዲመለሱ፣ ይህ የማይሆን ከሆነ



www.chilot.me

ከስራቸው የተሰናበቱበትን ምክንያት በአግባቡ በመግለፅ የአመልካችን የመሰማት መብት ተግባራዊ በማድረግ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጣቸው ይወሰንላቸው ዘንድ የይግባኝ አቤቱታውን ማቅረባቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ በተደረገለት ጥሪ መሠረት የአሁኑ ተጠሪ ቀርቦም እርምጃው በአዋጅ ቁጥር 578/2000 አንቀፅ 19/1/ለ/ እና በደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37/1/ መሠረት የተከናወነ በመሆኑ ተገቢ ነው በማለት የአመልካች ይግባኝ ውድቅ እንዲሆን ገልፆ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የአስተዳደር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የአመልካቾችን ይግባኝ በድምጽ ብልጫ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኛቸውን በተለያዩ መዛግብት ቢያቀርቡም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/337 መሠረት ይግባኛቸው ተሰርዞባቸዋል የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

ከላይ በተጠቀሱት መዛግብት አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡ ሲሆን የአቤቱታቸው መሠረታዊ ይዘትም አመልካቾች የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት ያረጋገጠልን የመደመጥ መብት ሳይከበር የተሰጠ የባለስልጣኑ መስሪያ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ጉዳያቸው ባግባቡ እንዲጣራ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት አመልካቾች የተሰናበቱት በሕጉ አግባብ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37/1/ እና /2/ አንጻር ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን የግራ ቀኙ የቃል ክርክር መጋቢት 10 ቀን 2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት በተወሰኑ መዛግብት ሲያሰሙ በተወሰኑ መዛግብት ደግሞ የጽሑፍ ክርክር ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢና ጉምሩክ ባለስልጣን ሠራተኞች መስሪያ ቤቱ በአዲስ መልክ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ተብሎ ሲዋቀር የባለስልጣኑ መስሪያ ቤት የሰራተኞችን መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37/1/"ን" በመጥቀስ አመልካቾችን ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑን ሲሆን አመልካቾች ይህ የተጠሪ እርምጃ ሕጋዊ አይደለም፣ በሕገ መንግስቱ የተከበረውን የመሰማት መብት የሚጥስ ነው በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሠረቱ ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37/1/ ድንጋጌ በግልፅ የሚያሳየው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚሁ የሕገ መንግስት ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ ፍርድ ቤቶች አንድን ጉዳይ (አቤቱታ) ተቀብለው ውሳኔ መስጠት የሚችሉት ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በሕግ ለሌላ አካል ያልተሰጠ ጉዳይ በሚሆንበት ጊዜ እንደሆነ መሆኑን ነው፡፡ በህግ ተለይተው በአስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲቋጩ በተባሉ ጉዳዮች ላይ መደበኛ ፍርድ ቤት የመዳኘት የስረ ነገር ስልጣን ስለሌለው በሕጉ መሠረት ለአንድ አስተዳደር አካል ቀርቦ አስተዳደራዊ ውሳኔ የተሰጠበትን ጉዳይ ወይም ለአስተዳደር መቅረብ የሚገባውን ጉዳይ ፍርድ ቤት ሊያስተናግደውም ሆነ አከራክሮ ውሳኔ ሊሰጥበት አይችልም፡፡ ለአንዳንድ የመንግስት አካላት በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን የሚሠጡት

ሕጎች መጠበቅና መከበር ያለባቸው ሲሆን የዳኝነት አካል ስልጣንም በሕግ የተወሰነ ስለሆነ ሕግ የመተርጎም ስራው በሕጉ በተመለከተው አድማስ የሚመራ ይሆናል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 4 ድንጋጌ የሚያሳየውም ፍርድ ቤቶች በሌላ ህግ በግልጽ በታገዱ ጉዳዮች ላይ አከራክሮ የመወሰን ስልጣን የሌላቸው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በአስተዳደራዊ ውሳኔ የመጨረሻ እልባት እንዲያገኙ በህግ ተለይተው የተቀመጡት ጉዳዮችን ፍ/ቤቶች የመዳኘት ስልጣን የሌላቸው መሆኑ ሊስተዋል የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሠረት የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 79/1/ እና 37 ድንጋጌዎች አንድ ላይ ሲታዩ ፍ/ቤቶች አንድን ጉዳይ ተቀብለው ለማየትና ለመወሰን ሥልጣን የሚኖራቸው ጉዳዩ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው (Justiciable matter) ሆኖ ከተገኘ ብቻ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አዋጅ ቁጥር 578/2000 የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንን ያቋቋመ ሕግ ሲሆን በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 19/1/ለ/ ድንጋጌ የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 ቢኖርም የባለስልጣኑ ሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት ይመራል በሚል በኃይለ ቃል ተደንግጎ ይገኛል ፡፡ በዚሁ ሥርዓት መሠረትም የሚኒስሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 ያወጣ ሲሆን በዚህ ደንብ አንቀጽ 37/1/ ስር በደንቡ በሌላ ሁኔታ የተደነገገ ቢሆንም ዋና ዳይሬክተሩ በሙስና የተጠረጠረውንና እምነት ያጣበትን ማንኛውንም ሠራተኛ መደበኛውን የዲስኘሊን እርምጃ አፈጻጸም ሥርዓት ሳይከተል ከሥራ ማሰናበት እንደሚችል የተደነገገ ሲሆን የዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ ከላይ በተመለከተው ስርዓት መሠረት ከስራ የተሰናበተ ሰራተኛ በየትኛውም የፍርድ አካል ውሳኔ ወደ ስራ የመመለስ መብት እንደማይኖረው አስገዳጅነት ባለው መልኩ አስቀምጧል፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሰራተኞች የሚተዳደሩት አዋጅ ቁጥር 578/2000 "ን" ተከትሎ በወጣው ደንብ ቁጥር 155/2000 መሠረት እንደሆነ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በደንቡ አንቀፅ 37/1/ መሠረት የሥራ ስንብት ቢፈፀም በዳኝነት በፍ/ቤት እንደማይታይ በተጠቀሰው ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ በመርህ ደረጃ ሕግ የማውጣት ሥልጣን በሥልጣን ክፍፍል መርህ መሠረት የሕግ አውጪው አካል ስለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በሕግ አውጪው የመንግስት አካል የሚወጡ ሕጎች ቀዳሚዊ (primary legislations) ተብለው የሚታወቁ ሲሆን ሌሎቹ እንደአስፈላጊነታቸው አግባብ ባለው አካል የሚወጡ ሕጎች የበታች ህጎች (subsidiary legislations) ተብለው የሚታወቁ ናቸው፡፡ ሕግ አውጪው የመንግሥት አካል በተለያዩ ቴክኒካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ምክንያቶች ቀዳሚውን ሕግ ለማስፈጸም የሚያስችሉ ዝርዝር ሕጎች ያስፈልጋሉ ብሎ ባመነ ጊዜ ተገቢ ነው ላለው አካል የበታች ሕጎችን እንዲያወጣ ሥልጣን ሲሰጥ ይስተዋላል፡፡ ይህ አሰራር በሕግም በምክንያትም የተደገፈ እና የዳበረ ልምድ ስለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣው ደንብ ቁጥር 155/2000 ሕግ አውጪው በሰጠው ስልጣን መሠረት የወጣ ሲሆን በደንቡ አንቀጽ 37 መሠረት ደግሞ ሰራተኛው ከስራ የሚሰናበትበትን አግባብ ደንግጓል፡፡ በመሆኑም ወደ ስራ የመመለስ ወይም የመደመጥ መብት በፍርድ የሚያልቅ ጉዳይ አለመሆኑን የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ ከላይ እንደተገለጸው አንድ ጉዳይ በፍርድ ሊያልቅ የሚችለው ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በሕግ ለሌላ አካል ያልተሰጠ ጉዳይ በሚሆንበት ጊዜ እንደሆነ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካቾች የተሰናበቱት ሕግ አውጪው በዘረጋው ሥርዓት መሰረት ሲሆን አመልካቾች ከጠየቁት ዳኝነት አንጻር (ወደ ስራ መመለስ ወይም የመደመጥ መብት መከበር) ሲታይ ጥያቄው በፍርድ ሊያልቅ የሚችል (justiciable matter) አይደለም፡፡



www.chilot.me

በመሆኑም የአስተዳደር ፍርድ ቤት ጉዳዩ በፍርድ ቤት ሊታይ የሚችል አይደለም በሚል ምክንያት የአመልካቾችን የይግባኝ ቅሬታ በአብላጫ ድምፅ ውድቅ ማድረጉ በአመልካቾች ከተጠየቀው ዳኝነት (ወደ ስራ እንድንመለስ ወይም የመደመጥ መብታችን ይጠበቅልን ከሚለው) አንፃር ሲታይ በአዋጅ ቁጥር 578/2000 አንቀጽ 19/1/ለ/ እና ከሚኒስተሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37(1 እና 2) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ እንዲሁም አላማን የተከተለና ለአስተዳደር አካሉ በሕጉ አግባብ የተሰጠውን ስልጣን (executive prerogative) ያከበረ ነው ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ያለ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት በይ/መ/ቁጥር 00827/2001 ነሐሴ 18 ቀን 2001 ዓ/ም ጳጉሜ 02 ቀን 2001፣ በይ/መ/ቁጥር 00831/2001 ነሐሴ 18 ቀን 2001 ዓ/ም በይ/መ/ቁጥር 00839/2001 ነሐሴ 26 ቀን 2001 ዓ.ም፣ 00833/2001 ነሐሴ 26 ቀን 2001 ዓ.ም፣ በይ/መ/ቁ 00826/2001 ነሐሴ 21 ቀን 2001 ዓ.ም እና በይ/መ/ቁጥር 00828/2001 ነሐሴ 13 ቀን 2001 ዓ/ም እና በይ/መ/ቁጥር 00830/2001 መጋቢት 08 ቀን 2002 በአቶ አሸናፊ አማረና በአቶ አወቀ ተሻለ ጉዳይ ተሰጥተው በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የፀኑት ውሳኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 348(1) መሠረት ጸንተዋል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ተጣምረው እንዲታዩ ከተባሉት መዛግብት ጋርም ይያያዝ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

እ/ብ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 47682

መጋቢት 6 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች -** ኤም. ኤ. ሸሪፍ ኃ/የተ/የግል ማህበር - ጠበቃ ይማጅ ዩኒስ - ቀረቡ

**ተጠሪ -** ታይስ ኃ/የተ/የግል ማህበር - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የማይገባ የንግድ ውድድር ተፈጽሞአል በማለት የአሁኑ ተጠሪ የመሠረተውን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ክሱ የቀረበው ለንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽን ጽ/ቤት ሲሆን፣ ኮሚሽኑ ከሣሽ እና በወቅቱ ተከሣሾች የነበሩት የአሁኑን አመልካች እና አቶ መሐመድ አደም የተባለውን ግለሰብ አከራክሮአል፡፡ በመጨረሻም ተከሣሾች ከከሣሽ የንግድ ምልክት ጋር ተመሣሣይነት ያለውን ምልክት በመጠቀም ምርታቸውን ሲሸጡ ተገኝተዋል፡፡ ይህ ደግሞ ተጠቃሚውን ህብረተሰብ ግራ የሚያጋባና የሚያደናግር ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ነው እሚል መደምደሚያ ላይ ደርሰናል፡፡ በዚህ መሠረትም ተከሣሾች ድርጊቱን እንዲያቆሙ፣ 1ኛ ተከሣሽ የነበረው /የአሁኑ አመልካች/ ብር 15,000 መቀጫ እንዲከፍል፣ 2ኛ ተከሣሽ የነበረው ግለሰብ ደግሞ በማስጠንቀቂያ እንዲታለፍ በማለት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ የተሰማ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም ኮሚሽኑ ጉዳዩን ለማየት የዳኝነት ሥልጣን የለውም በማለት ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ ሽሮአል፡፡ በመጨረሻም ተጠሪ በበኩሉ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ በዚህ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ በመቀጠልም ፍ/ቤቱ የንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽን ጉዳዩን ያየው በንግድ አሠራር አዋጅ ቁጥር 329/95 በተሰጠው ሥልጣን ነው የሚል ምክንያት በመስጠት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ ሽሮአል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 21 ቀን 2001 ዓ.ም. በጻፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታውን አቀርቦአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ በሕጉ አግባብ የተሰጠ ነው ወይ? በሚለው



www.chilot.me

ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በሆኑም ግራ ቀኝ ወገኖች በጭብጡ መሠረት ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ የተደረገውን የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር እና የተሰጡትን ውሣኔዎች ይዘት በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ ከዚህም በቅድሚያ ልንገነዘብ የቻልነው ተጠሪ ክስ የመሠረተው የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ መብትን ለማስከበር ወይም የንግድ ባለቤትነት መብትን ለማረጋገጥ ሳይሆን፣ ከሕግ አግባብ ውጪ ተፈጽሞብኛል ያለውን የማይገባ ውድድር /የንግድ ውድድር/ እንዲገታለት እና አመልካችም ለዚህ ድርጊቱ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድበት በመጠየቅ እንደሆነ ነው፡፡ ክሱን የሰማው የንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽንም ባቀረበለት የዳኝነት ጥያቄ የተፈፀመውን እና በመፈፀም ላይ ያለውን ያልተገባ የንግድ ውድድር እንዲቆም፤ አመልካችም በአዋጁ መሠረት እርምጃ ይወሰድበት የሚል እንደሆነ በመገንዘቡ የንግድ ምልክት ጥበቃን /አዋጅ ቁ. 501/98/ በሚመለከት የሚነሳውን ክርክር የመዳኘት ሥልጣን የለህም በማለት ከአመልካች ቀርቦ የነበረውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ በጉዳዩ ሥረ ነገር ላይ አከራክሮ ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ የሥር ከሣሽ /የአሁኑ ተጠሪ/ ክስ የንግድ ምልክት ባለቤትነትን ማዕከል ያደረገ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ጉዳዩ በኮሚሽኑ የዳኝነት ሥልጣን ሥር አይወድቅም በማለት ወስኖአል፡፡ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ባለመስማማቱ በአዋጅ ቁ. 329/95 እና በአዋጅ ቁጥር 501/98 መካከል ያለውን ልዩነት በዝርዝር በማመልከት ጉዳዩ በንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽን የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ ነው እሚል መደምደሚያ ላይ ደርሶአል፡፡

በበኩላችንም እንዳየነው የኮሚሽኑ ውሣኔ የተመሠረተው በንግድ አሠራር አዋጅ ቁ. 329/95 አንቀጽ 10 እና 15 በተቀመጡት ድንጋጌዎች ላይ ነው፡፡ ተጠሪም ክሱን የመሠረተው በእነዚህ ድንጋጌዎች የተመለከተውን መሠረት በማድረግ ሲሆን ተፈፀመ ወይም እየተፈፀመ ነው ያለውን ድርጊትም በዝርዝር ገልጾ አቅርቦታል፡፡ የንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽን ያልተገባ የንግድ ውድድርን በሚመለከት የሚነሳውን ክርክር የመዳኘት ሥልጣን ያገኘው በንግድ አሠራር አዋጅ ቁ. 329/95 አንቀጽ 15 መሠረት ነው፡፡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ እና /ሰ/ እንደተመለከተው ኮሚሽኑ ከማንኛውም ወገን የሚቀርቡለትን አቤቱታዎች የአዋጁ ድንጋጌዎችን የመተላለፍ ድርጊት ተፈጽሞአል በሚል እስከቀረቡ ድረስ አቤቱታዎቹን የመመርመር እና /ወይም የቅጣት ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በዚህ ረገድ አግባብነት ያላቸው ማለትም ለአቤቱታ መቅረብ መሠረት ሊሆኑ የሚችሉት የአዋጁ ድንጋጌዎችም ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድርን በተመለከተ ዝርዝር ነገሮችን የያዘው አንቀጽ 10፣ ገበያን በበላይነት ያለ አግባብ ስለመጠቀም በሚል የተደነገገው አንቀጽ 11"ን" መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአዋጁን ዓላማ በዝርዝር ያስቀመጠው አንቀጽ 3 "ንም" መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ የአዋጁ ዓላማ፡-

1) ለነፃ ገበያ ውድድር እንቅፋት የሆኑ ድርጊቶችና ተገቢ ያልሆኑ የንግድ ሥራዎች እንዳይፈፀሙ በመከላከልና በማስወገድ ተገቢ የንግድ ውድድር እንዲሰፍን ማድረግ እና
2) በንግድ ዕቃዎች አገልግሎቶች አቅርቦት እና ሥርጭት ላይ ገደብ የሚፈጥሩ ድርጊቶችን በመከላከልና በማስወገድ የተጠቃሚውን ህብረተሰብ ጥቅም ማስጠበቅ ነው፡፡

በሚል በዝርዝር ተቀምጦአል፡፡

ቀደም ሲል እንዳመለከትነው አመልካች በአዋጅ ቁጥር 329/95 አንቀጽ 10/2/ሀ/ የተቀመጠውን ድንጋጌ ስለመተላለፉ በተጠሪ ክስ በዝርዝር ተመልክቶአል፡፡ የድርጊቱ አፈፃፀም ምን



www.chilot.me

እንደሚመስልም በክሱ ተገልጾአል፡፡ በዚህ ረገድ የተጠቀሰው አንቀጽ 10/2/ሀ/ በሌላው የንግድ ድርጅት ወይም በንግድ ድርጅቱ ተግባሮች በተለይም ድርጅቱ ከሚያቀርበው ምርት ወይም አገልግሎት ጋር በተገናኘ ሁኔታ ማደናገርን ያስከተለ ወይም ሊያስከትል የሚችል ማናቸውም ድርጊት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ሆኖ እንደሚቆጠር ያመለክታል፡፡ አመልካች ፈጽሞታል ወይም እየፈጸመው ነው ተብሎ በተጠሪ ክስ የተነገረውም ይኸው በድንጋጌው የተመለከተው ድርጊት ነው፡፡ የተጠሪ የክስ መነሻ አመልካች እኔ የምጠቀምበትን የንግድ ምልክት አመሳስሎ በመጠቀም ምርቱን ለገበያ እያቀረበነው የሚል ነው፡፡ በአጠቃላይ የተጠሪ ክስ በንግድ አሠራር አዋጅ ቁ. 329/95/ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የመተላለፍ ድርጊት ተፈጽሞብኛል በሚል ብቻ የሚያቆም ሳይሆን ተፈጸመ /እየተፈጸመ ነው/ የሚለው ድርጊት ከሕጉ ጋር ያለውን ግንኙነት /አግባብነት/ም በግልጽ በዝርዝር የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች ጉዳዩ ከንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ መብት አከባበር አንፃር በማየት ነው ኮሚሽኑ ሥልጣን የለውም በማለት እየተከራከረ የመጣው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም አመልካች የተጠሪን የንግድ ምልክት አመሳስሎ በመጠቀም ምርቱን ለገበያ እያቀረበ ነው የሚለውን በተጠሪ ክስ የተቀመጠውን አባባል ብቻ አጉልቶ በማውጣት ጉዳዩ ከንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁ. 501/98 አንፃር ነው መታየት ያለበት እሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርስ እንደቻለ ከውሣኔው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡

በእርግጥም የክርክሩ አነሳስ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ወደያዘው መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ ከሆነ ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን የሚኖረው የንግድ አሠሪር አጣሪ ኮሚሽን ሳይሆን የፌዴራል መደበኛ ፍ/ቤት እንደሆነ ከአዋጅ ቁ. 501/98 አንቀጽ 49 መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይሁንና ወደ ድምዳሜ ከመደረሱ በፊት የተያዘውን ክርክር አጠቃላይ ይዘት እና ተጠሪ በክሱ የጠየቀውን ዳኝነት በአግባቡ መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ በበኩላችን እንደምንገነዘበው በተያዘው ጉዳይ የንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽን የዳኝነት ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በዋናነት መታየት ያለበት የተጠሪ የክስ ምክንያት /መነሻ/ እና በመጨረሻ የተጠየቀው ዳኝነት ነው፡፡ ሌላው በመቀጠል መታየት ያለበት ጉዳይ አመልካች እና ተጠሪ በንግድ ሥር ላይ የተሰማሩ ብቻ ሳይሆኑ ተመሣሣይነት ያለው ዕቃም ለገበያ እያቀረቡ ናቸው የሚለው ነው፡፡ ተጠሪ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ተፈጽሞብኛል የሚለውም አመልካች የሱ ያልሆነውን የንግድ ምልክት /ተጠሪ ባለቤት የሆነበትን/ አመሳስሎ በመጠቀም ምርቱን ለገበያ እያቀረበ /እየሸጠ/ ነው በማለት ነው፡፡ ድርጊቱ ያልተገባ ውድድር ነው እየተባለ ያለውም ተጠሪ ከሚያቀርበው ምርት ጋር ማደናገርን አስከትሎአል ስለተባለ ወይም ሊያስከትል የሚችል ሆኖ በመታየቱ ነው፡፡ በመሆኑም በክርክር ሂደት ወይም በክሱ አቀራረብ ስለ ንግድ ምልክት በመነሳቱ ጉዳዩ የንግድ ምልክት ባለቤትነት መብት ወይም ምዝገባ ጥበቃን የሚመለከት ጉዳይ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን ክርክር መቀበሉ ትክክል አይደለም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የደረሰበት መደምደሚያ ግን የጉዳዩን ይዘት ከሕጉ ጋር ያገናዘበ የሕግ መሠረት ያለው ነው፡፡ ጉዳዩ በእርግጥም በንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽን የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ ነው፡፡

በመጨረሻም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የዳኝነት ሥልጣንን በመሚመለከት የተነሳውን ክርክር ከወሰነ በኋላ በሥረ ነገር ረገድ ያለውን ክርክር በሥር ፍ/ቤት እንዲታይ አለማድረጉ ተገቢ ነው ወይ? የሚለውን ነጥብ ተመልክተናል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በጉዳዩ የመጨረሻ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እንደመሆኑ ከንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽን ጀምሮ የተካሄደውን ክርክር ነው የመረመረው፡፡ በአጣሪ ኮሚሽኑ እና በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጡት ውሣኔዎችም በዚህ ሂደት ይመረመራሉ፡፡ በእርግጥ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ትኩረት አድርጎ የወሰነው በዳኝነት



www.chilot.me

ሥልጣን ረገድ የተነሳውን ክርክር ብቻ በመያዝ በመሆኑ ወደ ጉዳዩ ሥረ ነገር አልገባም፡፡ የንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽን ግን በሥረ ነገር ረገድ የተነሳውን ክርክር ጭምር በመመርመር ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም በተመሣሣይ ሁኔታ በሁለቱም ነጥቦች ላይ ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ ለዚህም ነው የንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽን የሰጠውን ውሣኔ ማፅናቱን በግልጽ በውሣኔው ላይ የገለጸው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 342 እንደተደነገገው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ በተባለበት መዝገብ ውስጥ የሰፈረው ማስረጃ በቂ ነው የሚል ግምት ከያዘ የነገሩን ጭብጥ በማሻሻል ወይም በመለወጥ ተገቢ መስሎ የታየውን የመጨረሻ ፍርድ ሊሰጥ ይችላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የሆነውም ይኸው ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነቱ ከንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽን ጀምሮ የተደረገውን ክርክር የተሰማውን ማስረጃ በመመርመር የመጨረሻ ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ የንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽን በመቃወሚያውም ሆነ በጉዳዩ ሥረ ነገር ላይ የሰጠው ውሣኔ ትክክል ሆኖ ስላገኘውም ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ በመሆኑም ውሣኔው በሕጉ አተገባበር ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት የለም፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ውሣኔ**</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 41022 ሚያዚያ 26 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቶአል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ



www.chilot.me

# የንግድ ሕግ

የሰ/መ/ቁ. 40173

ጥቅምት 5 ቀን 2003

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

ብርሃኑ አመነው

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች** ፡- አምባሰል የንግድ ሥራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር የቀረበ የለም

**ተጠሪ** ፡- አቶ አብዱልቃድር ጁሀር የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር ያለአግባብ መበልፀግ በሚል መነሻ አመልካች ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በሚል የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት አለበት በማለት አቤቱታ ስለቀረበበት ነው፡፡

የክርክሩ አጀማመር ሲታይ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገ የሰሊጥ ሽያጭ ውል መነሻ ተጠሪ ለአመልካች የገንዘብ ክፍያ የሰጠው ቼክ ከፋይ ባንክ ዘንድ ቀርቦ በቂ ስንቅ የሌለው መሆኑ ተረጋግጦ በቼኩ መሠረት በአመልካች በኩል ቀርቦ የነበረው ክስ በንግድ ሕግ ቁጥር 881 መሠረት በይርጋ ጊዜ ገደብ ቀሪ በመባሉ በንግድ ሕግ ቁጥር 799 መሠረት ተጠሪ በአመልካች ሀብት ያለአግባብ በልጽጓል በሚል መነሻ ብር 2,448,250 ከጥር 10 ቀን 1989 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 14% ወለድ ጋር እንዲከፍል እንዲወሰን ሲል አመልካች ክስ መመሥረቱን መዝገቡ ያስረዳል፡፡

ክሱን በመጀመሪያ የዳኝነት ሥልጣን የተመለከተው የአማራ ብ/ክ/መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ክሱን በብይን ውድቅ አድርጓል፡፡ ለብይኑ የሰጠው ምክንያትም በአንድ በኩል አመልካች ቀደም ሲል በቼክ መነሻ ያቀረበው ክስ በይርጋ ታግዷል ከተባለ በኂላ ይህንኑ ቼክ መሠረት አድርጎ ያለአግባብ መበልፀግ በሚል የክስ ምክንያት በንግድ ሕግ ቁጥር 799 መሠረት ክስ ማቅረቡ ቀድሞ ከቀረበው ክስ ጋር ተመሣሣይ በመሆኑ ፍ/ቤት በይርጋ ቀሪ ነው ባለው ጉዳይ እንደገና ክስ ማቅረቡ ተገቢነት እንደሌለው፣ በሌላ በኩል ክስ የቀረበበት ገንዘብ መክፈያ ጊዜ ጥር 10 ቀን 1989 ዓ.ም ሆኖ ክስ የቀረበው ጥር 25 ቀን 1999 ዓ.ም መሆኑን በመጥቀስ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1845 መሠረት 10 /አሥር ዓመት/ ጊዜ አልፎበታል የሚሉ ናቸው፡፡

አመልካች በዚህ ቅር ተሰኝቶ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኂላ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን አጽንቷል፡፡

የሰበር አመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ የሥር ፍ/ቤት ለንግድ ሕግ አንቀጽ 799 የተሣሣተ ትርጉም እንደሰጠ፣ የክሱ አቀራረብ ጊዜን በተመለከተ በመ/ቁ. 50554 ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ፍ/ቤቱም በጉዳዩ ላይ ሥልጣኑ በውክልና ለአማራ ብ/ክ/ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠ መሆኑን ጠቅሶ ጥር 23 ቀን 1999 ዓ.ም በብይን መዝገቡን የዘጋ ስለሆነ የይርጋ ጊዜው አቆጣጠር በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1851/2/ መሠረት ተቋርጧል፤ ከዚህም በተጨማሪ የቼኩ መክፈያ ቀን የካቲት 20 ቀን 1989 ዓ.ም ቢሆንም ቼክ ቆርጦ ከሰጠ በኋላ ተጠሪው ከዚሁ በቼክ ከተሰጠው ገንዘብ ውስጥ ሚያዝያ 21 ቀን 1989 ዓ.ም ብር 70,000 /ሰባ ሺህ ብር/ እና ሰኔ 10 ቀን 1989 ዓ.ም ብር 60,000 /ስልሣ ሺህ/ ለአመልካች የከፈለ መሆኑን በመጥቀስ ይርጋ ጊዜው መታሰብ ያለበት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ መሆን እንዳለበት በመዘርዘር የሥር ፍ/ቤት ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጠው ብይን እንዲሻር አመልክቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የአመልካችን አቤቱታ መርምሮ አመልካች አለአግባብ መበልፀግን መሠረት በማድረግ ያቀረበው ክስ በንግድ ሕግ ቁጥር 799 መሠረት በድጋሚ የቀረበ ነው ሲል የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ትርጉም እና ብያኔ ተገቢነትን ለመመርመር ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

የተጠሪ ጠበቃ ሐምሌ 16 ቀን 2001 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ ይ/ባይም በቼክ ክስ ቀርቦ በይርጋ ከታገደ በኋላ በንግድ ሕግ ቁጥር 799 ሌላ ክስ እንዲቀርብ መፍቀድ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 አኳያ የተከለከለ ስለመሆኑ የክፍያ ጊዜንም በሚመለከት ክፍያ የሚፈፀመው ጥር 10 ቀን 1989 ዓ.ም ሆኖ ክስ የቀረበው ጥር 24 ቀን 1999 ዓ.ም በመሆኑ የአሥር /10/ ዓመት ጊዜ ያለፈ ስለመሆኑና በመ/ቁ. 50554 የቀረበውን ክስ ፍ/ቤቱ ሥልጠን የለኝም በሚል የተዘጋ ስለሆነ በሰበር መ/ቁ. 16648 በተሰጠው ውሣኔ መሠረት ይርጋ ማቋረጫ ምክንያት ሊሆን አይችልም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

የአመልካች ጠበቃ አቤቱታውን አጠናክሮ የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል የተመለከተ ነው፡፡ ችሎቱም የተያዘውን ጭብጥ መሠረት በማድረግ ከሕጉ አገናዝቦ መርምሮታል፡፡

እንደመረመርነውም በዚህ ችሎት ውሣኔ እንዲሰጥበት የተያዙት ጭብጦች ሁለት ናቸው፡፡ እነዚሁኑ በየተራ እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

የመጀመሪያው ጭብጥ የሥር ፍ/ቤት የንግድ ሕግ ቁጥር 799 አፈፃፀምን አስመልክቶ የሰጠው ትርጉም አግባብ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በተመለከተ ነው፡፡

በዚህ ረገድ ከመዝገቡ መረዳት የተቻለው ተጠሪ ለአመልካች ቆርጦ የሰጠው ቼክ ለባንክ ቀርቦ በቂ ስንቅ የለውም ከተባለ በኋላ ይህንኑ ገንዘብ ተጠሪ እንዲከፍል እንዲወስን አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ መሥርቶ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ የቼኩ የክፍያ ቀን የካቲት 20 ቀን 1989 ዓ.ም ሆኖ በቼኩ ክስ የቀረበው ነሐሴ 21 ቀን 1989 ዓ.ም በመሆኑ ክሱ በንግድ ሕግ ቁጥር 881 መሠረት የስድስት /6/ ወር የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የቀረበ ነው በሚል በመ/ቁ. 11774 በ4/10/96 ውሣኔ መስጠቱን ከዚያም በኋላ ያለአግባብ መበልፀግ በሚል የክስ ምክንያት ለቼኩ መሰጠት ምክንያት የሆነውን ውል እና ያልተከፈለ ቼክ ማስረጃ በማድረግ አመልካች በመ/ቁ. 50554 በ19/3/99 ዓ.ም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ ማቅረቡን እና ፍ/ቤቱም የተጠሪን መልስና

መቃወሚያ ከተቀበለ በኋላ በ23/5/99 ዓ.ም ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን የሌለው ስለመሆኑ ጠቅሶ በብይን መዝገቡን መዝጋቱን ነው፡፡

ከዚህ በኋላ ነው እንግዲህ አመልካች በአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ክስ የመሠረተው የክሱ ምክንያትና ይዘትም ከፍ ሲል ከተጠቀሰው ከመ/ቁ. 50554 ጋር ተመሣሣይና አንድ ነው፡፡

በዚህ መልክ የቀረበውን ክስ የተመለከተው የአማራ ብ/ክ/መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት የአመልካችን ክስ ላለመቀበል የሰጠው ምክንያት በቼክ ክስ ቀርቦ በይርጋ ቀሪ ነው ከተባለ በኋላ ይህንኑ የክስ ምክንያትና የገንዘብ መጠን መሠረት በማድረግ ያለአግባብ መበልፀግ የሚል ክስ ማቅረብ እንዲቻል የንግድ ሕግ ቁጥር 799 ድንጋጌ የሚፈቅድ አይደለም የሚል ነው፡፡

የዚህ ዓይነት ድምዳሜ የሕጉን ይዘትና ግላማ ያገናዘበ መሆን ወይም አለመሆኑን ለመረዳት የድንጋጌውን ይዘት እንመለከታለን፡፡

የአንቀጽ 799ን ይዘት ከማየታችን በፊት ግን አጠቃላይ ስለቼክ የተመለከቱ ጉዳዮችን በአጭሩ እንዳስሣለን፡፡

በመሠረቱ ቼክ የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ሐተታ የሌለበት ትእዛዝ የያዘና ቼኩም እንደቀረበ የሚከፈል ስለመሆኑ በንግድ ሕግ ቁጥር 827/ሀ/ እና 854 ሥር ተመልክቷል፡፡

እንዲሁም ቼኩ የወጣበት ቀን ከግምት ሣይገባ ቼኩ ከተፃፈበት ቀን አንስቶ በሚከተሉት ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለክፍያ መቅረብ እንዳለበት አልፎም በቼኩ አውጭውና ሌሎች ተገዳጆች ላይ አምጪው ክስ ለመመሥረት የሚችለው ቼኩን ለማቅረብ ከተወሰነው ጊዜ ባሉት ቀጣይ ስድስት ወራት ጊዜ ስለመሆኑ የንግድ ሕጉ ድንጋጌ ቁጥር 854 እና 881/1/ ይዘት ያስገነዝባሉ፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች የሚቀርቡት በንግድ ሕጉ አንቀጽ 640 እና 868/ሐ/ በተመለከተው መሠረት የቼኩ አውጪና ሌሎች የጀርባ ፊርሚና እሺ ባይ በቼኩ ለተመለከተው ገንዘብ አከፋፈል ኃላፊ መሆናቸው የተደነገገውን ተከትሎ ስለመሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡

እነዚህን የሕጉ ድንጋጌዎች ተከትሎ ክፍያ ያልተፈፀመ እንደሆነ የአምጪው መብት ምን ሊሆን ይገባል የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ ምላሽ የሚሰጠን የንግድ ሕጉ አንቀጽ 799 ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ስለሐዋላ ወረቀት በተመለከተ የተደነገገው ክፍል ውስጥ የሚገኝ ቢሆንም በቼክ ላይም ተፈፃሚነት እንዳለው የንግድ ሕጉ አንቀጽ 886 በግልጽ ያመለክታል፡፡

ስለሆነም የንግድ ሕጉ አንቀጽ 799ን ይዘት ለመረዳት ይቻል ዘንድ እንጠቅሣለን፡፡

<u>799፡ ያላግባብ ስለመበልፀግ የሚቀርብ ክስ፡-</u> 799/1/ በሐዋላ ወረቀት ላይ የተመሠረቱት ግዴታዎቸቸው ጊዜያቸው በማለፉ ወይም በይርጋ ምክንያት የቀሩ ቢሆኑም እንኳ አውጪውና እሺ ባዩ ሕግ በማይፈቅደው አኳኋን ያለአግባብ በመበልፀግ ባገኙት ጥቅም መጠን ለአምጪው ኃላፊዎች ናቸው" ይላል፡፡

ድንጋጌው ንዑስ ቁጥሮች ቢኖሩትም ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው ይኸው ነው፡፡

ከዚህ ድንጋጌ በግልፅ መረዳት የሚቻለው በቼኩ የተመለከተው ክፍያ ሣይፈፀም ጊዜ ያለፈበት እንደሆነ ወይም በይርጋ ቀሪ ነው የተባለ እንደሆነ የቼኩ አምጪ የቼኩ አውጪ ወይም እሺ ባይ ያለአግባብ በበለፀጉበት መጠን ኃላፊ ስለመሆናቸው ነው፡፡

ይህ ድንጋጌ ግልጽ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት ይህንኑ ግልጽ የሆነውን የሕጉ ድንጋጌ ከንግድ ሕግ ቁጥር 881/ሪ/ በማጣቀስ የሰጠው ትርጓሜ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

አንድ የሕግ ድንጋጌ ግልጽ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ትርጓሜ እንደማያሻው የሕግ አተረጓጎም መርህ ያስረዳል፡፡ ስለሆነም ቼኩን መሠረት አድርጎ በሕጉ በተቀመጠው ጊዜ ክፍያ ያልተጠየቀበት ወይም በይዞታ የታገደ የሆነ እንደሆነ ይህንኑ ቼክ እንደተራ ሰነድ በማስረጃነት በማቅረብ ያለአግባብ መበልፀግ በሚል የክስ ምክንያት መክሰስ የሚቻል መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ አመልካችም የዚህን የንግድ ሕግ ቁጥር 799 መሠረት በማድረግ ክስ የመሠረተ ስለመሆኑ ከመዝገቡ ይዘት መረዳት ተችሏል፡፡

ስለዚህም ክሱን በመጀመሪያ የተመለከተው የሥር ፍ/ቤት የንግድ ሕግ ቁጥር 799ን አስመልክቶ የተሣሣተ ትርጉም የሰጡ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች በመ/ቁ. 50554 በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ የይርጋ ጊዜ ያቋርጣል ወይንስ አያቋርጥም? የሚለው ነው፡፡

በዚህ ረገድ የአማራ ብ/ክ/ጠ/ፍ/ቤት ለውሣኔው የሰጠው ምክንያት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት መ/ቁ.50554ን የዘጋው ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን የለኝ በሚልም ምክንያት መሆኑን በመጥቀስ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት የቀረበው ክስ የይርጋ ጊዜን ለማቋረጥ የሚያስችል አይደለም በሚል ስለመሆኑ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡

አመልካች የይርጋ ጊዜው በከፍተኛው ፍ/ቤት በቀረበ ክስ ምክንያት ስለመቋረጡ እና የጊዜውም ስሌት ቼኩ ሊከፈል ከሚገባበት የካቲት 20 ቀን 1989 ዓ.ም ጀምሮ መታሰብ እንዳለበት አጥብቆ ተከራክሯል፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ የተጠሪ ጠበቃ በሰጡት መልስ የይርጋ ጊዜ መታሰብ ያለበት ከጥር 10 ቀን 1989 ጀምሮ ስለመሆኑ ጠቅሰው ይህ ደግሞ ክስ እስከቀረበበት ጥር 24 ቀን 1999 ዓ.ም የአሥር ዓመት ጊዜ ያለፈው መሆኑና ሥልጣን በሌለው ፍ/ቤት የቀረበው ክስ ይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ማቋረጫ ምክንያት ሊሆን እንደማይገባ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር መ/ቁ. 16648 ታህሣሥ 20 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ በመጥቀስ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ በአግባቡ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡

እኛም ይህንኑ የግራ ቀኙን ክርክር ከሕጉ አገናዝበናል፡፡ በመሠረቱ የክፍያው ጊዜ ጥር 10 ቀን 1989 ዓ.ም ስለመሆኑ የሥር ፍቤት በውሣኔው አረጋግጧል፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች በመ/ቁ. 50554 በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የመሠረተው ክስ ፍ/ቤቱ ሥልጣን የለውም ሲል ክሱን መዝጋቱ የይርጋ ጊዜ ያቋርጣል ወይንስ አያቋርጥም የሚለውን ጭብጥ በተመለከተ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 36730 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ማገናዘብ ተገቢ ይሆናል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል በመ/ቁ. 16648 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/4/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በመለወጥ በመ/ቁ. 36730 አስገዳጅ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በይዘቱም ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ሥልጣን የለኝም በሚል ክሱን ቢዘጋውም የይርጋ ጊዜ ማቋረጫ ሊሆን እንደሚባ ለዚህም የሕግ መሠረቱ

የሥልጣን ጉዳይ መለየት በዋነኛነት የፍ/ቤቱ ኃላፊነት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር አንቀጽ 9፣ 23/1/ለ እና 231/1/ለ ድንጋጌዎችን እንዲሁም ሕገ መንግሥታዊ መብት የሆነውን ፍትህ የማግኘት መብት መሠረት በማድረግ ነው፡፡

ስለሆነም የዚህ ሰበር ችሎት ውሣኔ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ለዚህ ጉዳይም ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/4/ን ይዘት መሠረት በማድረግ ስንመለከተው የሥር ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1851/ለ/ ጠቅሶ የሰጠው ውሣኔ አግባብነት የለውም፡፡

በመሆኑም አመልካች በመ/ቁ. 50554 ያቀረበው ክስ ህዳር 19 ቀን 1999 ዓ.ም ሲሆን ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ በብይን የዘጋው ጥር 23 ቀን 1999 ዓ.ም ስለመሆኑ ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ክሱ የ10 ዓመት ጊዜ ገደብ ጥር 10 ቀን 1999 ዓ.ም ቢሆንም አመልካች አስቀድሞ ህዳር 19 ቀን 1999 ዓ.ም በመ/ቁ. 50554 የመሠረተው ክስ የይርጋ ጊዜውን አቋርጧል፡፡

ስለሆነም አመልካች በአማራ ብ/ክ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ጥር 24 ቀን 1999 ዓ.ም የመሠረተው ክስ በይርጋ ጊዜ ያልታገደ መሆኑን ከፍ ሲል ከተመለከቱት መዛግብትና የሰበር ችሎቱ ውሣኔ ይዘት በማገናዘብ ለመረዳት ችለናል፡፡ ሲጠቃለል አመልካች ያቀረበው ያለአግባብ መበልፀግ የክስ ምክንያት ቀደም ሲል በቼክ ክስ ቀርቦበት በይርጋ የታገደ ነው በሚል እና ክሱም የአሥር ዓመት የይርጋ ጊዜ አልፎበታል ሲል የአማራ ብ/ክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ብይን እና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይህንኑ ማጽናቱ ከፍ ሲል በዝርዝር በተመለከቱት ምክንያቶች መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 11300ጥቅምት 27 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 34738 ግንቦት 22 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካችን ክስ ተቀብሎ በፍሬ ነገር ረገድ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ብለን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሐግ ቁጥር 341/1/ መሠረት መዝገቡን ለአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 48242

ጥቅምት 4 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ መድህን ድርጅት - ጽጌረዳ ተሻገር ቀረበች

**ተጠሪዎች፡-** 1. ቦጋለ መስቀሌ
2. ሚሊዮን ቦጋለ } ጠበቃ ብሥራት መኮንን ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፍዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማጽናት በመ.ቁ. 65456 ግንቦት 17 ቀን 2001 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ጉዳዩ 1ኛ ተጠሪ ያለበትን የብር 107,440 ዕዳ ለመክፈል እንዲያስችለው በ2ኛ ተጠሪ አማካይነት የቃል ኪዳን ሰነድ ፈርሞ ቢሰጠኝም በገባው ቃል መሠረት አልከፈለኝም በማለት አመልካች የመሠረተውን ክስ መነሻ ያደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ 2ቱም ተጠሪዎች ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ዕዳውን እንዲከፍሉ ወይም ፍ/ቤቱ ኃላፊነቱ የማን እንደሆነ ለይቶ ገንዘቡ እንዲከፈለው እንዲወስንለት ስለመጠየቁም ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ተጠሪዎችም ለክሱ በሰጡት መልስ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል፡፡ በውክልና ሰነዱ ላይ ያለው ፊርማ የ2ኛ ተጠሪ አይደለም፡፡ ስለዚህ በቀረበው ክስ በኃላፊነት ልንጠየቅ አይገባም በማለት በጋራ ሲከራከሩ፤ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ በተለይ ባቀረበው ክርክር በውክልና ሠርተሃል እየተባልኩ ለገንዘቡ አከፋፈል ተጠያቂ የምሆንበት ምክንያት የለም ብሎአል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ 2ኛ ተከሣሽ ፊርማውን በመካዱ ፊርማው እንዲመረመር ቢታዘዝም፤ ከሣሽ ዋናውን ሰነድ ሊያቀርብ አልቻለም የሚል ምክንያት በመስጠት ክሱን ውድቅ አድርጎአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በበኩሉ ክርክሩን የሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 4 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቦአል፡፡ በበኩላችንም ይህን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው አመልካች ዋናውን የውክልና ሰነድ አላቀረበም በማለት ክሱ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በሌላም በኩል ተጠሪዎች ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖ እያለ መቃወሚያችን ውድቅ በመደረጉ በሕጉ አተረጓጎም መሠረታዊ ስህተት

ተፈጽሞአል በማለት መስቀልኛ አቤቱታ በማቅረባቸው በዚህ ረገድም የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ሰምተናል፡፡ በመቀጠልም ክርክሩን አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ተጠሪዎች ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት አቅርበውት የነበረው መቃወሚያ የሥር ፍ/ቤቶች ያልተቀበሉት ቢሆንም፤ተጠሪዎች ግን መቃወሚያው ውድቅ የተደረገው ከሕጉ ውጪ ነው በማለት እየተከራከሩ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የንግድ ሕግ ድንጋጌ መሠረት አድርገው ወስነዋል የሚል የመከራከሪያ ነጥብም አንስተዋል፡፡ አመልካች ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ድንጋጌ የንግድ ሕግ ቁ. 817/1/ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ የተወሰነው የክስ ማቅረቢያ ጊዜ ሦስት ዓመት ሲሆን ክሱ የቀረበው ደግሞ ይህ ጊዜ ከማለፉ በፊት በመሆኑ የተጠሪዎች የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው በማለት ተከራክሮአል፡፡

ለክሱ መነሻ የሆነው የቃል ኪዳን ሰነድ ተፈርሞ በተሰጠበት ጊዜ እና ክሱ በቀረበበት ጊዜ መሐል ያለው ጊዜ ሲታይ የሦስት ዓመት ጊዜ አለማለፉ እርግጥ ነው፡፡ አከራካሪ የሆነው የይርጋው መቃወሚያ ለመወሰን ተገቢ የሆነው ድንጋጌ የትኛው ነው? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ የተስፋ /ለመክፈል ቃል የሚሰጥበት/ ወረቀትን ወይም ሰነድን በሚመለከት በንግድ ሕጉ አራተኛ መጽሐፍ በአንቀጽ 2 ሥር ያሉት ድንጋጌዎች አግባብነት እንደሚኖራቸው በንግድ ሕግ ቁ. 825 በመመልከቱ ተጠሪዎች ወደ ቁ. 817 በመሄድ እና አግባብነት ያለው ድንጋጌ ንዑስ ቁ. /2/ እንደሆነ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ ለዚህ ክርክራቸው ምክንያት ያደረጉት የሰነዱ አውጪ ነን፤ በሰነዱ አውጪ ላይ የሚቀርበውን ክስ በሚመለከት ግልጽ ድንጋጌ ያለው በንዑስ ቁ. /2/ ላይ ነው የሚል ነው፡፡

ለተያዘው የይርጋ ክርክር አወሳሰን ተገቢነት አለው በማለት በግራ ቀኝ ወገኖች የተጠቀሰው የንግድ ሕግ ቁ. 817 የሃዋላ ወረቀትን መሠረት በማድረግ የሚቀርበው ክስ በይርጋ ቀሪ ስለሚሆንበት ሁኔታ የሚደነግግ ነው፡፡ ንዑስ ቁ. /1/ ክሱ በሦስት ዓመት ይርጋ ቀሪ እንደሚሆን ሲያመለክት፤ ንኡስ ቁ. /2/ ደግሞ ክሱ በአንድ ዓመት ይርጋ ቀሪ እንደሚሆን ያመለክታል፡፡ እዚህ ላይ በጥንቃቄ መታየት ያለበት የጊዜዎቹ መርዘም ወይም ማጠር ሣይሆን፣ በሁለቱ ድንጋጌዎች /ንኡስ ቁጥሮች/ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው? የሚለው ነው፡፡ የመጀመሪያው ክሱ በእሺ ባዩ ላይ የሚቀርብ እንደሆነ ገልጾ መቅረብ ያለበት ከመክፈያው ቀን አንስቶ በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ሁለተኛው ማለትም ንኡስ ቁ. /2/ ደግሞ ክሱ የሚቀርበው በጀርባ በፈረሙ ሰዎችና በአውጪ ላይ መሆኑን በአንድ በኩል ሲገለጽ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የሐዋላ ወረቀቱ / ሰነዱ/ በሚገባው ጊዜ እንቢታ ማስታወቂያ የተደረገበት ወይም "ያለኪሣራ የሚመለስ" የሚል ቃል ያለበት እንደሆነ ያመለክታል፡፡ እነዚህ በንኡስ ቁ./2/ የተጨመሩ ሁኔታዎች በንኡስ ቁ./1/ የሉም፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪዎች የተከሰሱት የሰነዱ አውጪ በመሆናቸው እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በዚህ ሰነድ መሠረት ግንኙነት የተፈጠረው በተጠሪዎች እና በአመልካች መካከል ብቻ እንደሆነ ግን ልብ ሊባል ይገባል፡፡ በሰነዱ የተመለከተውን ገንዘብ ለመክፈል"እሺ" ባዮች ተጠሪዎች እንደሆኑም መታወቅ አለበት፡፡ በሰነዱ ላይ በንግድ ሕግ ቁ. 817/2/ የተመለከቱት ሁኔታዎች አሉበት አልተባለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች ከእነሱ ውጪ ሌላ ሰው ያለ ይመስል የይርጋ መቃወሚያቸን መታየት ያለበት በንኡስ ቁ./2/ መሠረት ነው በማለት መከራከራቸው አግባብ አይደለም፡፡ በመሆኑም ክሱ የቀረበው በይርጋ ቀሪ ከሆነ በኋላ ነው በማለት ያቀረቡት መቃወሚያ በሥር ፍ/ቤቶች ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡



www.chilot.me

በመቀጠል የተመለከትነው አመልካች ባቀረበው አቤቱታ መነሻነት የተያዘውን ጭብጥ ነው፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረገው በ2ኛ ተጠሪ የተካደው በውክልና ማስረጃ ላይ ያለውን ፊርማ ለማስመርመር አመልካች ዋናውን የውክልና ሰነድ ለማቅረብ አልቻለም በማለት ነው፡፡ እንደሚታወቀው የውክልና ማረጋገጫ ሰነድ የሚመለከተው ወካዩንና ተወካይን ብቻ ነው፡፡ አመልካች በዚህ ጉዳይ ወካይም ተወካይም አይደለም፡፡ በመሆኑም የውክልናው ሰነድ ዋናውን አቅርብ ሊባል የሚገባው ወካይ ወይም ተወካይ እንጂ ሦስተኛ ወገን የሆነውን አመልካችን አይደለም፡፡ በሥር ፍ/ቤት ከተደረገው ክርክር ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው ፍ/ቤቱ የውክልናውን ዋና ሰነድ አመልካች ማቅረብ አልቻለም ከማለት አልፎ ውክልናውን አረጋግጦ ሰነዱን ከሰጠው የመንግሥት መሥሪያ ቤት በተጠሪዎች መካከል የውክልና ግንኙነት የለም የሚል ማረጋገጫ አላገኘም፡፡ ይልቁንም ዋናው የውክልና ሰነዱ የሚገኘው በተጠሪዎች ዘንድ እንደሆነ የሚመለከተው መንግሥታዊ አካል እንደገለፀለት በአመልካች ክርክር ተመልክቶ እያለ ይህንኑ በዝምታ ማለፉን ነው የተገነዘብነው ከሁሉ በላይ ደገሞ ተጠሪዎች ዋናውን ሰነድ በማቅረብ የማስረዳት ሸክማቸውን ሣይወጡ የማስረዳት ሸክሙን ወደአመልካች በማዞር ወደብይን በማምራቱ በሕጉ አተገባበር ረገድ መሠረታዊ ስህተት መፈፀሙን ነው መገንዘብ የቻልነው፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1/ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 75930 ታህሣሥ 22 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 65456 ግንቦት 17 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡

2/ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረገው ተጠሪዎች የውክልና ስልጣኑን በተመለከተ የማስረዳት ሸክማቸውን ባልተወጡበት ሁኔታ መሆኑን ተገንዝቦ ወደ ክሱ ሥረ- ነገር በመግባት ተጠሪዎች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ የማይከፍሉበት አግባብ አለ ወይስ የለም በሚለው ጭብጥ ላይ ግራ ቀኝ ወገኖች ካከራከረ በኂላ ተገቢውን ይወሰን ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት ብለናል፡፡

3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸው ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 52269

ጥቅምት 17 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- 1. አቶ ከድር ሀጅ ሁሴን አልቀረቡም

2. ሊስ ኮሌጅ አክሲዮን ማህበር አልቀረቡም

**ተጠሪ** ፡- አቶ ጁሀር አልይ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ የአክሲዮን ድርሻን የሚመለከት ነው፡፡ተጠሪ 148,000 /አንድ መቶ አርባ ስምንት ሺህ ብር/ ዋጋ ያለው አክሲዮን ባለቤት እንዳልሆንኩ የወሰኑበት ውሣኔ ተሰርዞ የአክሲዮን ባለመብት መሆኔ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ይህንን ገንዘብ ተጠሪ በአይነት ወይም በገንዘብ ገቢ አላደረገም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ብር 100,000, የከፈሉ መሆኑ በመመሥረቻ ጽሑፍ የተገለፀ ሲሆን ብር 95,000 የከፈሉ ስለመሆኑ ደግሞ ሉሲ ኮሌጅ አክስዮን ማህበር የሰጣቸው ማስረጃ ቀርቧል፡፡ ይህንን ድርሻ በቃለ ጉባዔ እንዳልተከፈለ ለመቀየር መሞከራቸው ሕጋዊ ውጤት የለውም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ የአክሲዮን ማህበሩ ሲቋቋም ከጠቅላላ ካፒታል ብር 100,000 ከዚያ በኋላ ብር 95,000 መክፈላቸው ተረጋግጧል፡፡ ይህንን መብት ለማሻሻል የተሰጠው ውሣኔ የሕግ መሠረት የለውም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ተጠሪ ክስ ያቀረበው ውሣኔ ከተላለፈ በኋላ አንድ ዓመት አሣልፎ ነው፡፡ እኛ ያነሣነውን የይርጋ መቃወሚያ አላግባብ ውድቅ ተደርጎብናል፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲሻርልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የአክሲዮን ማህበር ቃለ ጉባዔ ጉዳዩን በአጀንዳነት ይዞ ያስተላለፈው ውሣኔ የለም፡፡ የእኔን አክሲዮን ድርሻ ዝቅ አድርጎ በቃለ ጉባዔው መመዝገቡ የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት የለም



www.chilot.me

የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ የአመልካችን የይርጋ መቃወሚያ በተመለከተም የራሱን የመከራከሪያ ነጥብ አቅርቧል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች ለመመሥረቻ ጽሑፍና በአክሲዮን ሼር ሰርቲፊኬት የተገኘውን መብት በማስመልከት ዝቅ ለማድረግ የአክሲዮን ማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ የተሰጠው ውሣኔ በአንድ ዓመት ይርጋ ይገደባል በማለት ያቀረቡትን ክርክር የበታች ፍርድ ቤቶች ያለፉት በመዝገቡ ዋና የመከራከሪያ ጭብጥ የሆነውን ነጥብ አጠቃላይ ባህሪና የንግድ ሕግ ቁጥር 359/1/ ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓለማ በማገናዘብ መሆኑን ለመረዳት ችለናል፡፡

ተጠሪ በዚህ መዝገብ ያቀረቡት ክስ የባለአክስዮኖች ጉባዔ የሰጠው ቃለ ጉባዔ እንዲሻሻልን ወይም ቀሪ እንዲሆን ሣይሆን በመሠረታዊነት የአክሲዮን ማህበሩ መሥራችነታቸውና ለአክሲዮን ማህበሩ በተረጋገጠ ማስረጃ ክፍያ የፈፀሙባቸው የአክሲዮን ድርሻ የሚጎዳ ተግባር ባአክሲዮን ማህበሩ እየተፈፀመ ስለሆነ ይህንን መብታቸውን ለማስከበር ነው፡፡ በዚህ መንገድ የሚቀርብ ክስ በንግድ ሕግ ቁጥር 416/2/ የሚሸፈንና ቀሪ የሚሆን አይደለም በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሣኔ ተገቢ ሆኖ ስላገኘነው በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት አጽንተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 55077

ኀዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- ወ/ሮ ጥሩወርቅ ዘገት - ጠበቃ አቶ በጋሻው ኃ/ገብርኤል ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ** ፡- አቶ ግደይ አብርሃ - ጠበቃ አቶ ተስፋዬ ወረደ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፣ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ በቼክ ምክንያት የተነሣን ክርክር የሚመለከት ሆኖ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቼክ ቼኩን ለመስጠት ምክንያት ከሆነውና ግራ ቀኙ የካቲት 09 ቀን 2001 ዓ.ም. ካደረጉት ውል አንፃር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ በመለየት የሥር ፍ/ቤት የሰጡትን ዳኝነት አግባብነት ለማየት ሲባል የቀረበ ነው፡፡

ምንም እንኳ የአሁን አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ በዋስትና በተሰጠውና ፊርማው የእኔ ባልሆነ ቼክ በሚል እንደ አዲስ የፍሬ ነገር ክርክር ያቅረቡ እንጂ ይኸው ቼክ በእርሳቸው ለተጠሪ የተሰጠ ስለመሆኑ ከሥር ፍ/ቤት ጀምሮ የተደረገው ክርክርና የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ አስረጅ ናቸው፡፡

ሆኖም ለቼኩ ምክንያት የሆነው ግራ ቀኙ የካቲት 09 ቀን 2001 ዓ.ም. ከግንባታ ሥራ ጋር በተያያዘ ያደረጉት ስምምነት ስለመሆኑ በግራ ቀኙ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡

አከራካሪ የሆነውና የሥር ፍ/ቤቶችን ዳኝነት አግባብነት ለማየት ያስፈለገው ቼኩ በክፍያ ሰነድነቱ ብቻ ተለይቶ የሚታይ ነው ወይስ ለቼኩ መሰጠት መነሻ ከሆነው የግራ ቀኙ ስምምነት ጋር የሚለውን ከንግድ ሕግ ቁጥር 717 አንፃር ለማየት በሚል ነው፡፡

ይህንን ጉዳይ በሚመለከት የሥር ፍ/ቤት መመርመር ሳያስፈልገው ቼኩ በላዩ ላይ የያዘውን የገንዘብ መጠን እና ከቼኩ መስጠት በኂላ አመልካች በተለያየ ጊዜ የፈፀሙትን ክፍያ አቀናንሶ ቀሪውን ብር 180,000.00 /አንድ መቶ ሰማንያ ሺህ/ ብር ከህጋዊ ወለድ ጋር አመልካች ይክፈሉ ሲል ወስኗል፡፡

ሆኖም ለዚህ ቼክ ምክንያት የሆነው የግራ ቀኙ ያደረጉት ውል መሆኑን የአሁን አመልካች በመከላከያነት ያቀረቡት ሲሆን ተጠሪ ይህንኑ የካዱት አይደለም ይህም ከሆነ ከቼኩ በስተጀርባ

ያለው የስምምነት ጉዳይ ከቼኩ ጋር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ሆኖ ሳለ የሥር ፍ/ቤት በቼኩ ላይ ብቻ ተወስኖ የሰጠው ዳኝነት በንግድ ሕግ ቁጥር 717 የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት ያደረገ አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በዚሁ መሠረት የተሰጠው ዳኝነት አግባብ አለመሆኑን ጠቅሰው ቼኩ ከውሉ ጋር ተጣቅሶ ሊታይ ይገባዋል የሚለውን ክርክር በሚመለከት አመልካች ቼኩ የተሰጠው ተጠሪ እንደውሉ ግዴታውን የሚፈጽሙ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ ነገር ግን ተጠሪ በውሉ መሠረት ግዴታቸውን አልተወጡም፣ ሥራው ግድፈት አለበት ይህንኑ ከግንባታ ፈቃድ ውጭ የሚለውን አላስተካከለም በማለት ያቀረብኩት ሳይታይልኝ ታልፏል በማለት ላቀረቡት ክርክር ተጠሪ በተራው በውሉ መሠረት የግንባታ ሥራው ተፈጽሞ የአማካሪ መሐንዲሱ ባለበት በ22/6/2002 አመልካች ፈርመው ተረክበዋል፡፡ ለዚህም በማስረጃነት ሰነዱ ቀርቧል በማለት መልስ ሲሰጥ አመልካች ለዚሁ ማስተባበያ የሚሆን የፍሬ ነገር ክርክር ኀዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም. የተፃፈ የመልስ ልስ ያቀረቡ ሲሆን የክርክሩ ይዘት ቼኩ ዋጋ እንዳይኖረው የሚያደርግ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ እንደ አባባላቸው ከሆነም እንደውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት እራሱን የቻለ አቤቱታ እንዲያቀርቡ ከሚረዳ በቀር ክርክር ያስነሳውን የቼክ ጉዳይ ከንግድ ሕግ ቁጥር 717 አንፃር እንዲታይ በማድረግ በዚህ ነጥብ ላይ በሥር ፍ/ቤት ታይቶ ውሣኔ እንዲሰጥበት ለማድረግ የሚያበቃ ክርክር አይደለም፡፡ ይኸው ጉዳይ ተጣርቶ እንዲወሰን ወደ ሥር ፍ/ቤት ለመመለስ የሚቻልበት ምክንያት ካልተገኘ ደግሞ የሥር ፍ/ቤት ይህንኑ ማጣራት ሳያስፈልገው በቼኩ ላይ ተመርኩዞ ውሣኔ መስጠቱ ከውጤት አንፃር የሕግ ስህተት ፈጽሟል ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ ይህንን ሁሉ በማየት የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና የከፍተኛው ፍ/ቤት እንደቅደም ተከተሉ በኮ/መ/ቁ. 144516 በ28/9/2001 ዓ.ም. እና በመ/ቁ. 85254 የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጡትን ፍርድ እና ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንተናል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ነው ብለናል፡፡
3. የዚህ ክርክር ሁኔታ እስከሚታወቅ ድረስ የሰበር መ/ቁ. 55077 አፈፃፀሙ ታግዶ እንዲቆይ በሚል ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፤ ይፃፍ፡፡

ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 52667

ታህሳስ 12 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች:- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች :-** ኒያላ ኢንሹራንስ አ.ማ ነ/ፈጅ ፅዮን በላይ ቀረቡ

**ተጠሪ :-** የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ በባህር ላይ እቃ ሲጓጓዝ ለደረሰ ጉዳት የካሳ አከፋፈልን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ የደንበኛቸው ንብረት የሆነና የመድን ሽፋን የሰጠባቸውን ሀምሳ ሳጥን መስታወት ከቻይና በመጫን ጅቡቲ ወደብ ለማድረስ በተዋዋለው ውል መሠረት ጅቡቲ ወደብ ካደረሳቸው አምሳ ሳጥን መስታወት ውስጥ አስር ሳጥን መታወት ላይ በአኗኗር ችግር ምክንያት ጉዳት ደርሶበታል፡፡ እኔ ለደንበኛያ የመስታወቱን ዋጋ ብር 101,465 /አንድ መቶ አንድ ሺህ አራት መቶ ስልሳ አምስት ብር/ የከፈልኩ በመሆኑ ይህንን ገንዘብ ተከሳሽ /የአሁን ተጠሪ/ እንዲተካ ውሳኔ ይሰጥልኝ ለማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ የእቃዋቹን ደህንነት በማረጋገጥ ያልጫንኩ በመሆኑ ሐላፊነት የለብኝም፡፡ ለእቃዎቹ ጉዳት ሐላፊ ነህ የምባል ከሆነ የእቃዎቹ ዋጋ ስለማይታወቅ በጥቅል ብር 500 /አምስት መቶ ብር/ ብቻ ታስቦ እንዲከፈለው ይወሰንልን በማለት ተከራክሯል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በእቃው ላይ ጉዳት የደረሰው በኮንቴነሩ ላይ በተደረገው ደካማ አያያዝ በመሆኑን በሰርቬይ ሪፖርት የተረጋገጠ በመሆኑ ተከሳሽ /ተጠሪ/ በእቃዎቹ ላይ ለደረሰው ጉዳት ሐላፊነት አለበት በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የካሳውን መጠን በተመለከተ የእቃው ዋጋ ያልታወቀ በመሆኑ በባህር ህግ አንቀጽ 198 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ለአንድ ሳጥን ብር 500 /አምስት መቶ ብር ሒሳብ ለአስሩ ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ ተጠሪ ለአመልካች ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ አመልካች የካቲት 8 ቀን 2002ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የአመልካች ደንበኛ ለተጠሪ የጭነት ትዕዛዝ የሰጠው የእቃውን ትክክለኛ ዋጋ፣ ከባንክ "በሌትር ኦፍ ክሬዲት" ክፍያ የተፈፀሙትን ሰነድ



www.chilot.me

በመግለጽና ሰነድን በማያያዝ ነው፡፡ ለመስተዋቱ 21,499.94 የአሜሪካን ዶላር የተከፈለ መሆኑን ተጠሪ ያውቃል፡፡ ተጠሪም በሰጡት ቢል ኦፍ ሌዲንግ የኤል ሲ ቁጥር /L/C No.NIB /HGB/ 044/2007/ ክፍያ የተፈፀመበት እቃ መሆኑን ገልጿል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ እቃውን ሲጭኑ በባንክ በኩል በተከፈተ "ኤል ሲ" ለእያንዳንዱ መስተዋት ምን ያህል የውጭ ምንዛሬ እንደተከፈለት ያውቅ ስለነበር ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የባህር ህግ 198 ንዑስ አንቀጽ 3 ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች የባህር ህግ ቁጥር 198 ንዑስ አንቀጽ 2ን በመጥቀስ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው የአመልካች ደንበኛና የእኛ ግንኙነት በባህር ላይ እቃ ማጓጓዥን የሚመለከት ነው፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች የባህር ህጉን መሠረት በማድረግ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የአመልካች ደንበኛ ለተጠሪ የሚጭነው እቃ በውጭ ምንዛሬ በባንክ በኩል ክፍያ የተፈፀመበትን የኤል.ሲ. ዶክመንት የሰጠውና ተጠሪም ለአመልካች ደንበኛ በሰጠው የባህር እቃ መጫኛ ሰነድ /ቢል ኦፍ ሌዲንግ/ ለእቃዎቹ በባንክ በኩል ክፍያ የተፈፀመበትን የኤል. ሲ. ቁጥር ማለትም /L/C No.NIB /HGB/ 044/2007/ የጠቀሰ መሆኑን አመልካች በሰበር አቤቱታው የገለፀ ሲሆን ተጠሪ ለአመልካች የሰጠሁት /ቢል ኦፍ ሊዲንግ/ ለእቃው የአመልካች ደንበኛ በንብ ባንክ በኩል የውጭ ምንዛሬ የከፈለበትን "ሌተር ኦፍ ክሬዲት" ቁጥር አይጠቅስም፣ የባንክ ሌተር ኦፎ ክሬዲት ሰነድ ከጭነት ማዘዣው ጋር አልተሰጠንም የሚል መልስ አላቀረበም፡፡ ይህም የአመልካች ደንበኛ በንብ ባንክ በኩል ለእቃዎቹ በውጭ ምንዛሬ የከፈልኩትን የሌተር ኦፍ ክሬዲት ለተጠሪ የቀረበለት መሆኑን እንዳመነ የሚያስቆጥረው መሆኑ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት 234 ንዑስ አንቀጽ 1 /ሠ/ የተደነገገ በመሆኑ ተጠሪ የአመልካች ደንበኛ የሆነውን አምሳ ሳጥን መስታዎት ስጭን የእያንዳንዱ ሳጥን መስታወት ዋጋ በነጠላና የእቃው ዋጋ በጥቅል ስለማላውቀው ለእቃው መክፈል የሚገባኝ ካሳ በጥቅል ብር 500 /አምስት መቶ ብር/ መሆን ይገባዋል በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የአመልካች ደንበኛ በተጠሪ የጭነት ትዕዛዝ ለሰጠበት እቃ የተከፈለው ዋጋ በውጭ ምንዛሬና በንብ ባንክ በኩል በተከፈተ ሌተር ኦፈ ክሬዲት እንደሆነ ይህንንም ተጠሪ በቢል ኦፍ ሌዲንግ ላይ የገለፀ መሆኑ ያልተስተባበለና ያልተካደ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ ለእቃው በባንክ በኩል በውጭ ምንዛሬ ክፍያ የተፈፀመበትን ሰነድ ተጠሪ የማያውቀውና በባህር ማጓጓዥያ ሰነድ ላይ የባንኩን "ሌተር ኦፍ ክሬዲት ቁጥር" የተገለፀው ከሆነ የባህር ህግ አንቀጽ 198 ንዑስ አንቀጽ 1 ለጉዳዩ አግባብነትና ተፈፃሚነት ያለው ድንጋጌ አይደለም፡፡ ለዚህ ጉዳይ አግባብነትና ተፈፃሚነት ያለው ድንጋጌ በባህር ህግ አንቀጽ 198 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ተጠሪ ለእቃዎቹ በንብ ባንክ በኩል በተከፈተ "ሌተር ኦፍ ክሬዲት" የተከፈለውን የውጭ ምንዛሬ ክፍያ አውቆና "የሌተር ኦፍ ክሬዲቱን" ቁጥር ለአመልካች ደንበኛ በሰጠው "ቢል ኦፍ ሊዲንግ" የእቃ መጫኛ ሰነድ ገልጾ እያለ የባህር ህግ ቁጥር 198 ንዑስ አንቀጽ 1ን በመጥቀስ የእቃው ዋጋ ስለማይታወቅ የአንድ ሳጥን መስታዎት ዋጋ ብር 500 /አምስት መቶ ብር/ ሒሳብ ተጠሪ ለአመልካች ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ ይክፈል በማለት የሰጠውን ውሳኔና ከፍተኛው ፍ/ቤት ሳያርም ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡



www.chilot.me

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካች ደንበኛ በንብ ባንክ በኩል በከፈቱት "ሌተር ኦፍ ክሬዲት" በእቃዎቹ የከፈሉትን ዋጋ በማጣራትና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች አስቀርቦ በመመርመር ተጠሪ ለአመልካች ሊከፈለው የሚገባውን የካሳ መጠን እንዲወስን ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሶ/በ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 57288

መጋቢት 19 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ሰለሞን ፍቅሬ ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- 1. አቶ አሸበር ታደሰ ቀረቡ

2. ሽብሩ አራርሶ
3. ጌታቸው ገልቹ
4. ጥሩነሽ ዲያሶ
5. ወርቁ ፍንጢ

(2–5) ጠበቃ አዲስ ወልዴ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 መሰረት በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት ላይ መብት አለን ባዮች አቤቱታ የሚያቀርቡበትንና አቤቱታው የሚመረመርበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች የፍርድ ባለመብት በመሆን ባሁኑ 1ኛ ተጠሪ ላይ በፍርድ ባለእዳነታቸው የአፈፃጸም ማመልከቻ በጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከአስከፈተ በሁዋላ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች በአሁኑ 1ኛ ተጠሪ በፍርድ ያገኘው ገንዘብ እንዲፈፅምለት አቤቱታ አቅርቦና የፍርድ ባለእዳውም ፍርዱ የማይፈጸምበትን ምክንያት ያላስረዱ በመሆኑ የፍርድ ባለመብት የሆነው አመልካች ከአክሲዮን ማህበሩ ንብረት ንብረቱ ተገምቶ የባለእዳው ድርሻ በጨረታ ተሸጦ ለእዳው ገቢ እንዲሆን አፈፃጸሙን ለያዘው ፍርድ ቤት አመልክቶ አፈፃጸሙ በቀጠለበት ሁኔታ የአሁኑ ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች አፈፃጸሙ በአክሲዮን ማህበሩ ሊቀጥል የማይገባበት ምክንያት ዘርዝረው አፈጻጸሙ እንዲቆም ከላይ በተጠቀሰው ስነ ስርዓት መሰረት አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡የስር ፍርድ ቤት በእነዚህ ተጠሪዎች የቀረበውን ተቃውም ለአመልካችና ለፍርድ ባለእዳ(የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ) እንዲደርስ አድርጎአል፡፡አመልካችና የፍርድ ባለእዳም የተቃውሞ አቤቱታ አቅራቢዎች ተቃውሞ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም የሌላቸው መሆኑንና የተቃውሞ አቤቱታውም የቀረበው የአፈጻጸም ሂደቱን ለማስናከል ስለመሆኑ ጠቅሰው አቤቱታው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡



www.chilot.me

ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት የጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የተቃውሞ አቤቱታ አቅራቢ የሆኑት የአሁኑ ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች የአክሲዮን ማህበሩ አባል መሆናቸውን መስከረም 18 ቀን 1999 ዓ/ም የማህበሩ አባላት ከአካሄዱት ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ላይ መረዳት ይቻላል በሚል ምክንያት አመልካችና 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አልፎ በዋናው ጉዳይ ላይ ብይን ሰጥቷል፡፡ በዋናው ጉዳይ ላይ የሠጠው ብይንም ሰላም እሸት የተባለ ፋብሪካ በአንድ አባል ድርሻ ምክንያት ሊሸጥ ይችላል ወይስ አይችልም? የሚል ጭብጥ ተይዞ ፋብሪካው የጋራ ንብረት ነው፣የ1ኛ ተጠሪ እዳ የግሉ ሁኖ በግሉ የሚጠየቅበት እንጂ የማህበሩ አባላት ሁሉ የሚጠየቁበት ጉዳይ አይደለም፣ለግለሰብ እዳ ደግሞ መያዝ የሚቻለው የባለእዳውን ድርሻ ብቻ ስለመሆኑ በንግድ ሕጉ ተመለክቷል የሚሉትን ምክንያቶችን በመዘርዘር ንብረቱ በጨረታ ሊሸጥ የሚገባው ሁኖ አልተገኘም፣ሆኖም የቀረበው የፋብሪካ ግምት ብር 582,637.20 (አምስት መቶ ሰማኒያ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ሰላሳ ሰባት ብር ከሃያ ሳንቲም) መነሻ ሁኖ ለማህበሩ አባላት ተከፋፍሎ የፍርድ ባለእዳው በፋብሪካው ያላቸውን ድርሻ የማህበሩ አባላት ለፍርድ ባለመብት ሰጥተው ፋብሪካውን ሊያስቀሩት ይገባል በማለት የጨረታ ሂደቱ እንዲቆም ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪዎች ሕጋዊ የማህበሩ አባላት ናቸው ተብሎ የተወሰነው ተቀባይነት ባለው ማስረጃ አይደለም፣የማህበሩ አባላት ቁጥርም አራት እንጂ አምስት አይደለም፣የፋብሪካው የመሃንዲስ ግምት መነሻ ተደርጎ የፍርድ ባለእዳ ድርሻን የማህበሩ አባላት ለአመልካች ከፍለው ፋብሪካውን ያስቀሩ ተብሎ መወሰኑንም የወቅቱን የገበያ ዋጋ ባላገናዘበ መልኩ ከመሆኑም በላይ የአመልካችን ፍርድ ይፈጸምልኝ መብቱን የሚያጣብብ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 መሰረት በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ገብተው ለመከራከር የሚያስችላቸው መብት አላቸው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውንና ተያያዥ ነጥቦችን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡በዚህም መሰረት ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው መልሳቸውን በጹሑፍ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በቅድሚያ ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ጠበቃ የአመልካች ክርክር በፍሬ ነገር ላይ የተመሰረተ እንጂ በሕግ ስህተት ላይ ያልተመሰረተ በመሆኑ በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው አይደለም በማለት ያቀረቡትን ተቃውሞ ተመልክተናል፡፡ይህ ሰበር ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት የተሰጠው ሥልጣን በማናቸውም የመጨረሻ ፍርድ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈፀሙ ሲረጋገጥ ማረም መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለውም ሰበር ችሎቱ የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ክርክርን መሰረት ያደረገ ጉዳይ መመልከትና ማረም የማይችል መሆኑን ነው፡፡ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት ክርክር እያቀረበ ያለው ለጉዳዩ የቀረበው ማስረጃ ተቀባይነት የሌለው ነው፣የአከራካሪው ንብረት የጋራ ባለሃብቶች እነማን እንደሆኑ በሕጉ አግባብ ሊቀርብ የሚችል



www.chilot.me

ማስረጃ አይደለም በሚል እንጂ ማስረጃው ታዓሚነነት የሌለው ነው በሚል አይደለም፡፡እንዲህ ከሆነ ለጉዳዩ በሕጉ ተለይቶ የተቀመጠ ማስረጃ መቅረብ ያለመቅረቡና የንብረቱ የጋራ ባለሃብቶች እነማን ናቸው? የሚለው ጥያቄ የማስረጃ ምዘና ሳይሆን በሕገ መንግስቱ ፣በንብረትና በንግድ ሕጎች እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ባላቸው አዋጆች መሰረት ታይቶ ምላሽ የሚያገኝ የሕግ ጥያቄ በመሆኑ በሰበር ችሎት የሚታይ ስለሆነ በዚህ ረገድ የቀረበው ተቃውሞ ተቀባይነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡

ወደዋናው ጉዳይ ስንመለስም ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ በቀዳሚነት የተያዘው ጭብጥ ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 መሰረት በጉዳዩ ጣልቃ ገብተው ለመከራከር የሚያስችላቸው መብት አላቸው ሲል የስር የጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወሰነው ተቀባይነት ያለውን ማስረጃ መሰረት በማድረግ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ አመልካችና 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን ውድቅ ያደረገው ተጠሪዎች የማህበሩ አባል ስለመሆናቸው ማህበሩ መስከረም 18 ቀን 1999 ዓ/ም ከአደረገው ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ተገንዝቤአለሁ በሚል ምክንያት መሆኑን በውሳኔው ላይ በግልፅ አስፍሯል፡፡አከራካሪው ፋብሪካ በአክሲዮን የተቋቋመ ኃላ.የተ.የግል ማህበር መሆኑ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠ ነው፡፡አክሲዮን ማህበሩ ሲቋቋም ከ1ኛ እስከ 3ኛ ተራ ከተጠቀሱት ተጠሪዎች ጋር በመሆን አባል የነበሩት አቶ ጸጋዬ ሐጎስ የተባሉ ሰው መሆናቸው ያላከራከረ ሲሆን ግራ ቀኙ እየተከራከሩ ያሉት የማህበሩ የጋራ ባለሃብቶች ቁጥር፣አቶ ጸጋዬ በማህበሩ ያላቸው የአክሲዮን መጠንና ለ4ኛ እና ለ5ኛ ተጠሪዎች አክሲዮናቸውን ማስተላለፍ አለማስተላለፋቸው እንዲሁም እነዚህ ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው ከአቶ ጸጋዬ የገዙት የአክሲዮን መጠን፣ይኸው የአክሲዮን ማስተላለፍ ሁኔታ በሕጉና በማህበሩ መመስረቻ ፁሑፍና መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተከናወነ መሆን ያለመሆኑን ጉዳይ ነው፡፡

በመሰረቱ የአክሲዮን ድርሻ አንድ የተፈጥሮ ወይም ሕግ ወለድ ሰው ካፒታሉ አስቀድሞ በታወቀ በአክሲዮን በተከፍፈለና ለዕዳውም ንብረቱ ብቻ ዋስትና በሆነ የአክሲዮን ማህበር ውስጥ ያሉትንና በባለቤትነት የያዛቸውን አክሲዮኖች ብዛትና ዋጋ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ አንድ ባለአክሲዮን በአክሲዮን ማህበሩ ውስጥ በባለቤትነት የያዛቸው አክሲዮኖች የራሣቸው ልዩ ባህሪና ውጤት ያላቸው ግዙፍ ያልሆኑ ሃብቶች ናቸው፡፡ በአገራችን ዕውቅና እና ጥበቃ የተሰጣቸው ሁለት አይነት አክሲዮኖች የራሣቸው ልዩ ባህሪና ውጤት ያላቸው እንዳሉ የንግድ ሕግ ቁጥር 325 (1) ይደነግጋል፡፡

የመጀመሪያው አይነት አክሲዮኖች "ለአምጭው ተብሎ የተፃፈባቸው አክሲዮኖች ናቸው፡፡ ለአምጭው ተብሎ የተፃፈበት አክሲዮን እንደማንኛውም ተላላፊ የንግድ ሰነዶች ናቸው፡፡ ለአምጭው ተብሎ የተፃፈባቸውን አክሲዮኖች ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ እንደማንኛውም ተላላፊ የንግድ ሰነድ የአክሲዮን ድርሻ ማረጋገጫ ሰነዱን /ሼር ሰርተፊኬቱን/ አሳልፎ በመስጠት ያለአንዳች አይነት አሰራር /ፎርማሊቲ/ ማከናወን እንደሚቻል ከንግድ ሕግ ቁጥር 340(1) ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ሁለተኛዎቹ አይነት አክሲዮኖች የባለአክሲዮኑ ስም የተፃፈባቸው አክሲዮኖች ናቸው፡፡ የባለአክሲዮኑ ስም የተፃፈበቸው አክሲዮኖች እንደማንኛውም ተላላፊ የንግድ ሰነድ የአክሲዮን ድርሻ ማረጋገጫ ሰነዱን /ሼር ሰርተፊኬቱን/ አሳልፎ በመስጠት ብቻ ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ አይቻልም፡፡ ስም የተፃፈባቸውን አክሲዮኖች ለማስተላለፍ አክሲዮኖቹ ለሌላ ሰው የተላለፉ መሆኑን በአክሲዮን

ማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት በሚገኘው የአክሲዮን መዝገብ ማስመዝገብ አስፈላጊ እንደሆነ ከንግድ ሕግ ቁጥር 341 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ክርክር የቀረበበት የንግድ ድርጅት አይነቱ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሲሆን የዚህ አይነት ማህበር አክሲዮኖች ለሌላ ሰው የሚተላለፉበት አግባብ በንግድ ሕጉ ከቁጥር 522 እስከ 524 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡የን/ሕ/ቁጥር 522 በተለይ ሲታይም የአክሲዮኖቹ መተላለፍ በጹሑፍ የተረጋገጠ መሆን እንዳለበት፣መተላለፉም በአክሲዮኖቹ መዝገብ ላይ ካልተጻፈ በቀር ለማህበሩና ለሶስተኛ ወገኖችን መቃወሚያ ሊሆን እንደማይችል በሕጉ በአስገዳጅነት ተደንግጓል፡፡የን/ሕ/ቁጥር 523 በመተዳደሪያ ደንቡ ተቃራኒ ቃል ከሌለ በቀር አክሲዮኖች በማህበተኞቹ መካከል ያለገደብ ሊተላለፉ የሚችሉ መሆኑን፣አክሲዮን ለባእድ ሰው የሚተላለፍበትን አግባብም የተወሰነ ስለመሆኑ ያሳያል፡፡የዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር ሶስት ደግሞ ማህበርተኞቹ አክሲዮኑ እንዲተላለፍ የተስማሙበት ውሳኔ በንግድ መዝገብ ላይ እንዲመዘገብ የሚያስፈልግ ስለመሆኑ ኃይለ ቃል ባለው አገላለፅ አስቀምጧል፡፡እንግዲህ በህጉ ረገድ ኃ.የተ.የግል ማህበር የአክሲዮን ድርሻ የሚተላለፍበት አግባብ በግልፅ ከተቀመጠ የአንድ የማህበሩ አባል የአክሲዮን ድርሻ ለሌላ መተላለፍ አለመተላለፉ መረጋገጥ ያለበት በሕጉ የተመለከቱት ሁኔታዎች መሟላታቸውን በሚያሳይ ማስረጃ ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ የአቶ ጸጋዬ የአክሲዮን ድርሻ ለ4ኛ እና ለ5ኛ ተጠሪዎች መተላለፉን ያሳያል የተባለው መስከረም 18 ቀን 1999 ዓ/ም የማህበሩ አባላት ያደረጉት ቃለ ጉባኤ ነው፡፡ሆኖም ይኸው ማህበረተኞቹ የተሰማሙበት ውሳኔ በንግድ ሕግ ቁጥር 523(3) አግባብ በንግድ መዝገብ ላይ እንዲመዘገብ የተደረገ መሆን ያለመሆኑን የስር ፍርድ ቤት በተገቢው መንገድ አላረጋገጠም፡፡ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች የአክሲዮኑ መተላለፍ የማህበሩን መመስረቻ ጹሁፍና መተዳደሪያ ደንብ ባገናዘበ መልኩ የተከናወነ መሆኑን ገልጸው ቢከራከሩም የመስከረም 18 ቀን 1999 ዓ/ም ቃለ ጉባኤ ግን በሕጉ አግባብ እንዲመዘገብ የተደረገ ስለመሆኑ ተረጋግጧል የሚል ክርክር በዚህ ሰበር ችሎት በሰጡት መልስ ላይ ያነሱ ሲሆን አመልካች ደግሞ ይህ እውነትነት የሌለው መሆኑን ጠቅሶ የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡እንዲህ ከሆነ የስር ፍርድ ቤት ቃለ ጉባኤውን በሕጉ አግባብ የተመዘገ መሆኑን ሳያጣራ ማስረጃነቱን ዋጋ ሰጥቶ ውሳኔ መስጠቱ የፍርድ አካሄዱን የተሟላ ባደረገ መልኩ አይደለም፡፡በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚገለጸው እንደተጠበቀ ሁኖ ቃለ ጉባኤው በማስረጃነቱ ሕጋዊ ዋጋ ሊሰጠው የሚችለው በማህበርተኞቹ ስምምነት የተደረሰበት በመሆኑ ብቻ ሳይሆን በንግድ መዝገብ መመዝገቡም በሚገባ ሲረጋገጥ ነው፡፡አንድ ፍርድ ቤት በተከራካሪ ወገኖች የሚቀርበውንና ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ማስረጃ በመቀበል ፍትሐዊ ዳኝነት መስጠት ያለበት መሆኑን በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ላይ ስለማስረጃ አቀራረብና አቀባበል እንዲሁም ስለፍርድ አሰጣጥ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝቡን ሐቅ ሲሆን አግባብነት ያለው ማስረጃ ሳይቀርብና ጉዳዩ በአግባቡ ሳይጣራ የሚሰጠው ውሳኔ የፍርድ አካሄዱን የተሟላ የማያደርግና በዳኝነት አሰጣጥ ሥርዓት ተቀባይነት የሌለው አካሄድ ነው፡፡በመሆኑም ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ የተከራካሪ ወገኖች ሲሆን ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ማስረጃ መቅረብን ማረጋገጥና ወደ እውነት መድረስ ደግሞ ፍርድ ቤቱ ራሱ በማስረጃ አቀራረብ ረገድ ተካራካሪ ወገኖችን ማገዝና ተገቢውን ማጣራት ማድረግ ያለበት መሆኑ የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓቱ የግድ የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ስለሆነም መስከረም 18 ቀን 1999 ዓ/ም የማህበሩ አባለት አደረጉ የተባለው ቃለ ጉባኤ የተመዘገበ መሆን ያለመሆኑ በተገቢው መንገድ ሳይጣራ ቃለ ጉባኤው መኖሩ ብቻ በመረጋገጡ ይኸው የሰነድ ማስረጃ እንዳለ የማስረጃነት ዋጋ በበታች ፍርድ ቤቶች መሰጠቱ በማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ረገድ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሁኖ አግኝነተናል፡፡በዚህም ምክንያት ይህ ሰነድ ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት



www.chilot.me

እንደገና ተጣርቶ በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበው መቃወሚያ እንዲታይ ማድረጉ ተገቢ ሁኖ አግኝተናል፡፡

በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት አጣርቶ የሚደርሰው ውጤት ከዚህ በፊት የደረሰበትን ድምዳሜ የማያስለውጠው ከሆነ የስር ፍርድ ቤት የፋብሪካውን የመሃንዲስ ግምት መነሻ ተድርጎ በማህበሩ አባላት እንዲከፋፈልና የፍርድ ባለእዳውን ድርሻ የሥር ተቃውሞ አቅራቢ የሆኑ የማህበሩ አባላት ለአመልካች ከፍለው ፋብሪካውን እንዲያስቀሩ ተብሎ የጨረታው ሂደት እንዲቆም የመደረጉን አግባብነትም ከወዲሁ መመልከቱ አስፈላጊ ሁኖ አግኝተናል፡፡የስር ፍርድ ቤት የፍርድ ባለእዳው አክሲዮን ድርሻ በማህበሩ አባላት ለአመልካች እንዲከፋፈልና ፋብሪካውን እንዲያስቀሩ ብሎ መወሰኑ ማህበሩ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እንደመሆኑ መጠን ሊቋቋም የሚችለው የመቀራረብና የመተማመን ሁኔታዎች ባላቸው ሰዎች መካከል ነው የሚለው እሳቤ ሲያዝ ከዚሁ የማህበሩ ልዩ ባሕርይ አንፃር ሲታይ ተገቢ ነው ቢባል እንኳ የፋብሪካ ዋጋ ሊሆን የሚችለው ግን የመሐንዲሱ ግምት ሳይሆን የወቅቱ የገበያ ዋጋ ነው፡፡በመሆኑም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አባል የሆነ የአንድ የማህበር አባል የግል እዳ ከአለበት አክሲዩኑ ለእዳው እንዳይሸጥ የሚከለክል ሕግ የሌለ መሆኑ ከን/ሕ/ቁጥር 522፣523 እና 524 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡እነዚህ ድንጋጌዎች ከማህበሩ ልዩ ባሕርይ አንፃር የአንድ የማህበሩ አባል አክሲዮን ሲሸጥ ቅድሚያ መብት ለማህበሩ አባላት እንዲሰጥ ከሚያሳዩ በቀር የማህበሩ አባላት አክሲዩኑን ወይም የማህበሩ ንብረት በመሐንዲስ ግምት መሰረት እንዲያስቀሩት መብት የሚሰጡ አይደሉም፡፡የአንድ ንብረት ሕጋዊ ባለቤት መሆኑ የተረጋገጠ ሰው ንብረቱ በእዳ ምክንያት ሲሸጥ የወቅቱን የገበያ ዋጋ እንዳያገኝ የሚደረግበት የሕግ አግባብ የለም፡፡የፍርድ ባለእዳ ንብረት በጨረታ የሚሸጥበት አግባብ በፍትሓ ብሔር ሥነ ሥርኣት ሕጋችን የመደንገጉ አንዱ ዓላማም የንብረቱን የገበያ ዋጋን በማረጋገጥ የፍርድ ባለመብትና የፍርድ ባለእዳን መብት ለመጠበቅ ነው፡፡የአንድን ንብረት የመሐንዲስ ግምት እንደትክክለኛ የገበያ ዋጋ መውሰድ የማይቻል ሲሆን በመሐንዲሱ ግምት ብቻ ንብረቱ እንዲሸጥ ማድረግ የንብረቱ ባለቤትን መብት ከማጣበቡም በላይ የንብረቱ ግምት ከፍርድ ባለእዳው ከሚፈለገው ገንዘብ ያነሰ ከሆነ የፍርድ ባለመብትን መብት ጭምር የሚያጣብበት አጋጣሚ ሰፊ እንደሚሆን ይታመናል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የፋብሪካውን ግምት መነሻ በአደረገ መልኩ ፋብሪካው ለማህበርተኞቹ እንዲከፋፈልና የፍርድ ባለእዳውን ድርሻ ተጠሪዎች ከፍለው ፋብሪካውን ያስቀሩ በማለት የደረሰበት ድምዳሜም ሕጋዊ መሰረት የሌለው ነው፡፡በአጠቃላይ ከላይ በተመለከቱት ዝርዝር ምክንያቶች በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 03309 የካቲት 26 ቀን 2002 ዓ/ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 77893 መጋቢት 21 ቀን 2002 ዓ/ም በትእዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሸሯል፡፡
2. ክርክር ያስነሳው ማህበር አባላቱ ስንት እንደሆኑ፣እንያንዳንዱ አባል ያለውን የአክሲዮን ብዛት፣4ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች የማህበሩ አባል መሆን ያለመሆናቸውን፣በሕጉ አግባብ ተቀባይነት ያለው ቃለ ጉባኤ መኖር ያለመኖሩን(የመስከረም 18 ቀን 1999 ዓ/ም ቃለ ጉባኤ በሕጉ አግባብ መመዝገብ አለመመዝገቡን)፣እነዚህ ተጠሪዎች አባል ሁነው ከሆነም እያንዳንዳቸው የገዙት የአክሲዮን ብዛት ስንት እንደሆነ እና ሌሎች ለጉዳዩ ፍትሓዊ አወሳሰን አግባብነት አላቸው የሚላቸውን ጭብጦችን በመያዝና ማጣራቶችን በማድረግ አመልካች ተጠሪዎች ጣልቃ



www.chilot.me

ለመግባት የሚችሉ አይደሉም በማለት ያቀረበውን ተቃውሞ እንዲመረምርና ተገቢ ነው ያለውን ብይን እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት ለጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መልሰንለታል፡፡ይጻፍ፡፡

3. በዚህ ችሎት ግራ ቀኙ ለአደረጉት ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 56480

ሰኔ 14 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**:- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** :- የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ - አ.ማ ጠበቃ ማረን ወንዴ ቀረቡ

**ተጠሪ** :- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - ነ/ፈጅ ተመስገን ማሞ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ባህር ላይ በሚደረግ የእቃ ጉዞ ለሚደርሰው ጉዳት ኃላፊነት ያለበትን ወገን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ መጋቢት 25 ቀን 1999 ዓ/ም የመሰረተው ክስ ይዘት ፤ ንብረትነቱ የደንበኛው የቻይና የኤሌክትሪክ ዋየርና ኬቤል አስመጪና ላኪ ድርጅት የሆነው ኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ከቻይና ሻንጋይ ወደብ በጅቡቲ ይርጋለም ዲላ ሀገረ ማርያም ፕሮጀክት ድረስ ተጓጉዞ እስኪመጣ ድረስ ለሚያጋጥም አደጋ በፖሊሲ ቁጥር ኤስ ኤን141 ኤም አር ኦኤ/10776102 የባህር ላይ ጉዞ የመድን ሽፋን መስጠቱን ፣ አመልካች እቃውን ከቻይና ሻንጋይ ወደብ አጓጉዞ ጅቡቲ ለማድስ ግዴታ መግባቱን ፣ አመልካች እቃውን ለተጠሪ ደንበኛ ከማስረከቡ በፊት ጅቡቲ ወደብ ላይ በሚራገፍበት ወቅት የመድን ሽፋን የተሰጠው የኤሌክትሪክ ኃይል ማስለተላለፊያ ጥፋት በሆነ ቸልተኝነት ክሬኑ ተበጥሶ ከባህር ውስጥ መውደቁንና ፣ አመልካች እቃውን አደጋ እንደደረሰ ወዲያውኑ ከባህር እንዲወጣ ማድረግ ሲገባው ከባድ በሆነ ቸልተኝነት በባህር ውስጥ ሳይወጣ ለስድስት ሰዓታት በባህር ውስጥ መቆየቱን ፣ በዚህም ምክንያት ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት መሆኑ በባለሙያዎች መረጋገጡን ፣ ተጠሪም ባለበት የመድን ግዴታ መሰረት ለተጎዳው እቃ እና ጥገናውን ለማከናወን አስፈላጊ ከሆኑ ወጪዎች ጋር በድምሩ ብር 253,827.04 (ሁለት መቶ ሃምሳ ሶስት ሺህ ስምንት መቶ ሃያ ሰባት ብር ከዜሮ አራት ብር) ወጪ አድርጎ ደንበኛውን መካሱን ፣ አመልካች ይህንኑ ገንዘብ እንዲከፍል ቢጠየቅም ኃላፊነትን በማመን ከብር 500.00 (አምስት መቶ ብር) በላይ እንደማይከፍል ማሳወቁን ገልፆ አመልካች ኃላፊነት አለበት ተብሎ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብና ሌሎች ወጪዎችን እንዲተካ እንዲወሰንለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የተጠሪ ክስ በሁለት አመት ይርጋ የታገደ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድ ደግሞ አመልካች በውሉ መሰረት ጅቡቲ ወደብ እቃውን በማድረስ የማጓጓዝ ግዴታውን የተወጣና ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን ፣ እቃውን ለማራገፍ ጥቅም ላይ የሚውለውን ክሬን የአመልካች በማስመሰል አመልካችን ኃላፊነት አለበት በማለት ተጠሪ



www.chilot.me

ማቅረቡ አግባብነት የሌለው መሆኑን ፣ የክሬኑን ብቃት የማረጋገጥ ኃላፊነት የባለሃብቱ እንጂ የአመልካች አለመሆኑን ፣ አመልካች የሌላ ሰው ንብረት ባደረሰው ጉዳት ሊጠይቅ እንደማይችልና ሊጠየቁ የሚገባቸው የጅቡቲ ወደብ አስተዳደርና/ወይም ትራንዚት አገልግሎት አ.ማ እና ወይም ፔይድ(PAID) የተባለው ጫኝና አራጋፊ ድርጅት መሆኑን ፣ አመልካች ሊከሰስ አይገባውም እንጂ ኃላፊነት አለበት ቢባል እንኳን ተጠሪ የጠየቀውን ተመዛዛኝ ያልሆነ(non-equivalent) ኪሳራ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ፣ የቀረበው ገንዘብ መጠንና ማስረጃዎቹ ሕጋዊነት የጎደላቸውና ተቀባይነት የሌላቸው ሲሆን ተጠሪ ስራዎችን አጫርቶና አወዳድሮ በአነስተኛ ዋጋ አለማሰራቱ ተገቢ አለመሆኑን ፣ አመልካች ብር 500 ለመክፈል የፃፈው ደብዳቤ ግዴታውን እንዳመነ እንዳማያስቆጥረው መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ወድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ አመልካችን ለክሱ ሃላፊ በማድረግ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ ብር 253,827.04 ክሱ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ 9% (ዘጠኝ ከመቶ) ወለድ እና ለክሱ ከወጡ የተለያዩ ወጪዎች ጋር እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ባጭሩ፡- ክሱ በሁለት አመት ይርጋ የታገደ ከመሆኑም በላይ አመልካች እቃውን ከቻይና ሻይንጋይ ወደብ በማጓጓዝ ጅበቲ ወደብ ማድረሱ ተረጋግጦ እያለና ይህም በውሉ ያለውን ግዴታውን መውጣቱን የሚያሳይ ሁኖ እያለ በክሬን ችግር ደረሰ ለተባለው አደጋ ኃላፊ ተብሎ ውሳኔ መሰጠቱ በባህር ሕግ ቁጥር 138፣196፣197 ስር የተመለከተውን ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ለክሱ ኃላፊነት አለበት ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በፅሑፍ በሰጠው መልስ አመልካች እቃውን ለማስረከብ በውሉ ግዴታ ገብቶ እንደውሉ ያልፈፀመ መሆኑና በባህር ሕጉ ቁጥር 138፣196 እና 197 ድንጋጌዎች መሰረት ኃላፊቱን ያልተወጣና ኃላፊነቱንም በጽሑፍ ያመነ በመሆኑ ለክሱ ኃላፊ ተብሎ መወሰኑ የሚነቀፍበት አግባብ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና አመልካችና ተጠሪ በጽሑፍ ያቀረቡት ክርክር በአጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የተጠሪ ደንበኛ ንብረት የሆነውን የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ከቻይና ሻንጋይ ወደብ ጅቡቲ አጓጉዞ ለማድረስ ውል መግባቱንና ጅቡቲ ወደብ ማድረሱን ፣ እንዲሁም ይኸው እቃ ከመርከቡ በመውረድ ላይ እያለ ክሬኑ ተበጥሶ ውሃ ውስጥ ወድቆ የቆየና ጉዳትም የደረሰበት መሆኑን ያልካደው ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪ ደንበኛ የማጓጓዣ ሰነድ( Bill of lading) መረከቡም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ አመልካች ላይ ክስ ሊመሰርት የቻለው ባለበት የመድን ውል ለደንበኛው በንብረቱ ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሳ ከከፈለ በኋላ ገንዘቡ እንዲተካለት ነው፡፡ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ኃላፊነት የለብኝም በማለት ሲሆን ለዚህ በቅድሚያ የሚያቀርበው ክርክር የይርጋ ጊዜ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ረገድ አመልካች ያነሳው ክርክር አመልካቹ ታህሳስ 07 ቀን 1998 ዓ/ም ከፃፈው ደብዳቤ ይዘትና በይርጋው ጊዜ አቆጣጠር ላይ ሊያስከትለው ከሚችለው

ውጤት አንፃር ሲታይ የሚገባው ነው፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች ታህሳስ 07 ቀን 1998 ዓ/ም የጻፈው ደብዳቤ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በማመን የኃላፊነት መጠኑ ግን ከብር 500.00(አምስት መቶ ብር ) በላይ ሊሆን እንደማይችልና ይህንኑ የገንዘብ መጠን ተጠሪ ከአመልካች የፋይናንስ መመሪያ እንዲወስድ የገለፀ መሆኑን እንዲሚያሳይ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች እዳውን ማመኑ ተጠሪ ከደንበኛው ካለው ግንኙነት ፣ እንዲሁም አመልካች ከተጠሪ ደንበኛ ካለው ግንኙነት አንፃር በሕጉ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ያልተቋረጠ መሆኑን የባህር ሕግ ቁጥር 203 ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1851 ጋር አዳምሮ በማንበብ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑን አመልካች ይርጋን መሰረት በማድረግ የሚያቀርብ የኃላፊነት ክርክር ታህሳስ 07 ቀን 1998 ዓ/ም ከፃፈው ደብዳቤ ይዘት አኳያ ሲታይ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ሌላው አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያውን ከቻይና ሻንጋይ ወደብ ጅቡቲ አጓጉዞ ለማድረስ ውል የገባና በውሉ መሰረትም ጅቡቲ ወደብ ያደረሰ በመሆኑ እቃው ከመርከብ በክሬን ሲወርድ ለደረሰበት የመውድቅ አደጋ ኃላፊነት የለብኝም በሚል ሲሆን ይህንም በምክንያት የሚያስደግፈው ክሬኑ የራሱ ንብረት ያለመሆኑን በመጥቀስ ነው፡፡

በመሰረቱ በባህር ላይ እቃ አመላለሽ ያለበትን ኃላፊነት በተመለከተ የባህር ሕጉ በቁጥር 196 ስር ያስቀመጠ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሰረት እቃ አመላላሽ ሁለት ዋና ዋና ግዴታዎች አሉት፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ አንድን መርከብ በሙሉ በመከራየት(ቻርተር ፓርቲ) እቃን የሚያጓጉዝ ባለመርከብ ስላለበት ግዴታ የባህር ሕጉን ቁጥር 138 በማጣቀስ የሚደነግግ ሲሆን የአንቀፁ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ በመርከቡ ላይ የተጫኑትን እቃዎች በጥንቃቄና በሚገባ ለመጫን ፣ ለአጠባበቃቸው በሚገባ አቀማመጥ እንዲደረደሩ፣ ስለጉዞዋቸው ፣ ስለ ጥበቃቸው ፣ ስለ መልካም አያያዛቸውና ስለ ማራገፉ መልካም አፈፃፀም ግዴታ ያለበት መሆኑን በአስገዳጅ ሁኔታ ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም አጓዡ በሕጉ የተጣሉበትን እነዚህን ግዴታዎች ካልተወጣ ሃላፊነት ያለበት መሆኑን የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ ያስረዳል፡፡ በጭነት ማስታወቂያ ደረሰኝ ውስጥ አመላላሹ አላፊነት የለበትም ተብሎ የተደረገው ውል የማይፀና ስለመሆኑም የባህር ሕግ ቁጥር 205 በግልፅ ይደነግጋል፡፡ የአመላላሹ መከላከያ ሊሆኑ የሚችሉ ሕጋዊ ምክንያቶች በባህር ሕጉ ቁጥር 197 ስር የተመለከቱት ምክንያቶች ናቸው፡፡ ከላይ የተመለከቱት የባህር ሕግ ድንጋጌዎች የአመላላሽን አላፊነት ሊያስከትሉና ቀሪ ሊያደርጉ የሚችሉ ሕጋዊ ምክንያቶች የሚደነግጉ ሲሆን አላፊነትን በተመለከተ ቀሪ ከሚያደርጉ ምክንያቶች አንዱ አመላላሽ እቃውን በአግባቡ ማስረከቡን መረጋገጡ ስለመሆኑም ያስገነዝባሉ፡፡ የእቃው እርክክብ ተፈጽሟል የሚባለው ደግሞ መቼና በምን ሁኔታ ሲፈጸም እንደሆነም ድንጋጌዎቹ በተለይ ከባህር ሕጉ ቁጥር 180(3) ጋር ተዳምረው ሲነበቡ ያሳያሉ፡፡ በዚህም መሰረት በጭነት ማስታወቂያ ደረሰኝ የተረጋገጠ የማመላለሻ ውልን የሚመለከቱ ልዩ ድንጋጌዎች የሚጸኑት በተለይ በመርከብ ላይ በተጫኑት የንግድ እቃዎች የጭነት ማስታወቂያ ደረሰኝ ወይም ይህን በመሰለ ሌላ አይነት ሰነድ በተረጋገጡ የጭነት ማመላለሻ ውሎች ብቻ መሆኑ ፣ የመርከብ መከራየት ውል ሰነድ ባለው ጉዳይ ላይ ተፈጻሚ እንደማይሆን ፣ ነገር ግን መርከቡ የተከራየው በኪራይ ሰነድ(በቻርተር ፓርቲ) የሆነ እንደሆነ የሚሰጠው የጭነት የማስታወቂያ ደረሰኝ ወይም ይህን የመሳሰለው ሌላ ሰነድ በአመላላሹና በሰነድ አምጪው መካከል ያለው ግንኙነት ከሚመራበት ጊዜ አንስቶ በዚሁ በሚሰጠው የጭነት ማስታወቂያ ደረሰኝ ላይ ድንጋጌዎቹ ተፈጻሚ እንደሚሆኑ ፣ የሚፀኑትም እቃዎቹ ከመርከብ ላይ ከተጫኑበት አንስቶ እስከሚራገፉበት ጊዜ ብቻ ስለመሆኑ የተጠቀሰው ድንጋጌ ያሳያል፡፡ የዚህ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር ሶስት በተለይ ሲታይም

"…..ከመርከቡ ላይ ከተጫኑበት አንስቶ እስከሚራገፉበት ጊዜ ብቻ ነው፡፡" በሚል በኃይል ቃል ማስቀመጡ አመላላሹ በማራገፍ ሂደት ለሚከሰቱ ጉዳቶቹም ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በግልጽ የሚሳይ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ በአመልካችና በተጠሪ ደንበኛ መካከል የተደረገው የማጓጓዣ ውል አንቀፅ 4(1(i) እቃዎቹን ማጓጓዝ ፣ መጫን ፣ ማራገፍ ፣ ማከማቸትና መጋዘን ማስቀመጥ ስራዎች ለሌሎች ወገኖች በውል አሳልፎ የመስጠት መብት እንዳለው በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠ መሆኑ እነዚህ ግዴታዎች የአመልካች ጭምር መሆናቸውን የሚያሳይ ሲሆን ይኸው ውል በአንቀጽ 5(ሀ(i)) ላይም የአጓጓዡን ሃላፊነት ሲዘረዝር እቃዎቹ በባህር ላይ በሚጓጓዙበት ወቅት የአጓጓዡ ኃላፊነት የማራገፉ ስራ እስከተፈፀመ ድረስ እንደሚዘልቅ በግልፅ መደንገጉን ተጠሪ አጥብቆ የሚከራከርበት ነጥብ ሲሆን በአመልካች በኩል የማስተባበያ ክርክር ካለመቅረቡ አንፃር ሲታይ የአመልካች ኃላፊት እቃውን በጥንቃቄ የማራገፍ ግዴታን ሁሉ የሚያጠቃልል መሆኑን የሚያስገነዝብ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በአጠቃላይ አመልካች አጓጓዥነቱንና እቃው ከመርከብ ወደ ውሃ በመውደቅ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ሳይክድ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ያቀረበው ክርክር በበቂ ማስረጃና ሕግ ያልተደገፈ መሆኑን በማረጋገጥ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰጠው መሆኑን የተገነዘበን በመሆኑ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 85940 ሐምሌ 18 ቀን 2000 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 71281 የካቲት 25 ቀን 2002 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ውጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 57932

ሰኔ 30 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** ፡- ተክሉ ካሣ ገብረየስ - ጠበቃ ስንታየሁ ባህሩ - ቀረበ

**ተጠሪ** ፡- ማርኮባርዚ - በሌለበት

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በመዝገቡ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ ቼክን መሠረት ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ሲሆን ፣ የአሁኑ ተጠሪ እና ማባ /maba/ ኋ/የተ/የግ/ማህበር የተባለ ድርጅት ደግሞ ተከሣሾች ነበሩ፡፡ ክሱ በሁለት ቼኮች የታዘዘውን ብር 219,000 አልተከፈለኝም እና ሁለቱም ተከሣሾች ገንዘቡን ይከፍሉኝ ዘንድ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ የማህበሩ ስራ አስኪያጅ እንደሆነ የቼኩ አውጪ ማህበሩ መሆኑን ቼኮቹ ወደ ታዘዘው ባንክ ሲወሰዱ የማህበሩ /2ኛ ተከሣሽ/ ሂሣብ የተዘጋ መሆኑን መገለጹም በክሱ ተመልክቶአል፡፡ ተከሣሾች በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ባለመቅረባቸዉ ክርክሩ በሌሉበት ታይቶ መወሰኑንም የስር ፍ/ቤቶች ከሰጡት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት ጉዳዩን ካየ በኋላ የአሁኑ ተጠሪን ከክሱ በነጻ በማሰናበት 2ኛ ተከሣሽ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከእነወለዱ እንዲከፍል ወስኖአል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች የተጠሪን ከክሱ በነጻ መሰናበት በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የነበረ ሲሆን ፣ ፍ/ቤቱም ይግባኝ የተባለበት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሐምሌ 2 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡

ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ባለመቅረቡ ክርክሩ የተሰማው በሌለበት ነው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገው ተጠሪ የኩባንያው /በስር 2ኛ ተከሣሽ/ ስራ አስኪያጅ ቢሆንም ፤ ፈርሞ ለሰጠው ቼክ በኃላፊነት አይጠየቅም የመባሉን አግባብነት ከንግድ ህግ ቁ. 530 አንጻር ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡

በዚህ መሠረትም ከስር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡



www.chilot.me

አመልካች ክስ የመሰረተው በቼኩ አውጪ ኩባንያ ላይ ብቻ ሣይሆን ቼኩን ፈርሞ በሰጠው የኩባንያው ስራ አስኪያጅ /ተጠሪ/ ላይ ጭምር ነው፡፡ በሰበር አቤቱታ ማመልከቻው ላይም እንደገለጸው ስራ አስኪያጁን አጣምሮ የከሰሰው በስራ አስኪያጅነቱ ብቻ ሣይሆን የኩባንያው የባንክ ሂሣብ መዘጋቱን እና ለቼኮቹ ክፍያ የሚሆን ኩባንያው የሚያዝበት ገንዘብ እንደሌለ እያወቀ ሆነ ብሎ ቼኮቹን ፈርሞ በመስጠት ጥፋት ፈጽሞአል በማለት ጭምር ነው፡፡ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በውሣኔው እንዳመለከተው ቼኮቹ ባንክ ቀርበው ሊከፈሉ ያልቻሉት የኩባንያው የባንክ ሂሣብ በመዘጋቱ ምክንያት ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ይህን ለማለት የቻለው ባንኩ የሰጠው ማረጋገጫ በአስረጂነት ቀርቦለት ከዚሁ በማረጋገጡ እንደሆነም ከውሣኔው ለመገንዘብ ችለናል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ፍ/ቤቱ ተጠሪ በስራ አስኪያጅነቱ ለፈረመው ቼክ ሃላፊ አይሆንም እሚል መደምደሚያ ላይ መድረሱን ተመልክተናል፡፡

እንደምናየው የቼኮቹ ባለቤት /አውጪ/ የሆነው ኩባንያ የባንክ ሂሣብ ስለመዘጋቱ ባቀረበው ማስረጃ ተረጋግጦአል፡፡ ኩባንያው ራሱን የቻለ ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ቢሆንም ስራውን የሚያንቀሣቅሰው በስራ አስኪያጅ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ አመልካች ቼኮቹ በስራ አስኪያጁ ተፈርመው በተሰጡበት ጊዜ ሁሉ ኩባንያው የሚያዝበት ገንዘብ በባንክ ሂሣቡ እንዳልነበረ አስረድቻለሁ በማለት የተከራከረ ሲሆን ፣ ተከሣሾቹ በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ቀርበው አልተከላከሉም፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ተጠሪ የኩባንያው ሂሣብ መዘጋቱን እያወቀ ነው ቼኮቹን ፈርሞ የሰጠው የሚለው የአመልካች ክርክር እውነት አይደለም ወደሚለው መደምደሚያ የሚደረስበት ምክንያት እንደሌለ ነው የተረጋገጠው ይህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪ ጥፋተኛ ወይም ስህተት ፈጽሞአል ማለት ነው፡፡

የኩባንያ ስራ አስኪያጅ በንግድ ህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ወይም የማህበሩን /ኩባንያውን/ የመተዳደሪያ ደንብ በመጣስም ቢሆን በስራ አስኪያጅነታቸው በሰሩዋቸው ጥፋቶችም ፣ ስህተቶችም ቢሆን በማህበሩ እና በሶስተኛ ወገኖች ፊት በየራሣቸው ወይም በአንድነት ሣይከፋፈል እንደነገሩ ሁኔታ ሀላፊዎች እንደሚሆኑ በንግድ ህግ ቁጥር 530 ተደንግጓአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የኩባንያ /ማህበር/ ስራ አስኪያጅ የሆነው ተጠሪ ኩባንያውን ለመምራት ስልጣን ያለው /የነበረው/ ሰው እንደሆነ በመረጋገጡ እና ጥፋትም በመፈጸሙ ለፈረማቸው ቼኮች በሃላፊነት የማይጠየቅበት የህግ ምክንያት የለም፡፡ ይልቁንም በተጠቀሰው የንግድ ህጉ ድንጋጌ እንደተመለከተው እሱም በግሉ ሃላፊ ነው የሚሆነው፡፡ የስር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ረገድ ያረጋገጡትን እውነታ ከህጉ ጋር አገናዝበው ባለማየታቸው ተጠሪን ነጻ በማድረግ የደረሱበት መደምደሚያ የተሣሣተ ሊሆን ችሎአል፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 16058 ታህሣስ 27 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 89973 ሚያዝያ 5 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪም ክስ የቀረበበትን ገንዘብ የመክፈል ሃላፊነት አለበት በመሆኑም ተጠሪ እና ማባ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንዲከፈል የወሰነውን ገንዘብ በአንድነት እና በነጠላ ይክፈሉ በማለት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

የሰ/መ/ቁ. 58931

ሐምሌ 15 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** ፡- የንግድ ኢንዲስትሪ ሚኒስቴር - ነ/ፈጅ ዮናስ ከበደ ቀረበ

**ተጠሪ** ፡- ታይገር ሎጂስቲክ እና የንብረት ጥበቃ ኃ.የተ.የግል ማህበር - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአመልካች መስሪያ ቤት በአዋጅ ቁጥር 67/89 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 376/96 መሰረት የሚሰጣቸው የንግድ ስራ ፈቃድ ጉዳዮች ውድቅ የሚደረጉበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ነው፡፡ ክሱ የተመሰረተውም ባሁኑ አመልካችና ታይገር ሴኩሪቲ ኃ.የተ.የግል ማህበር በተባለ ድርጅት ላይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች መስሪያ ቤት ላይ የመሰረተው የክስ ይዘት ባጭሩ፡- ድርጅቱ ታይገር ሎጅስቲክና የንብረት ጥበቃ( Tiger Logistic and property Protection) በሚል የንግድ ስያሜ ከአመልካች መስሪያ ቤት የንግድ ስራ ፈቃድ ቁጥር ኢ.አይኤ(ኦኤል) 2047/08 በቀን 02/05/2000 ዓ/ም በሕጋዊ መንገድ ተሰጥቶት እየተንቀሳቀሰ ባለበት ሁኔታ በዚሁ ተመሳሳይ ስም ታይገር ሴኩሪቲ በሚል አላማ ላይ የተሰማራ ድርጅት ፈቃድ ወስዶ በአዋሳ ከተማ ከ2000 ዓ/ም ጀምሮ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር(Unfair trade Competition) በማድረግ በአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 14(4(ሀ)) ስር ከተመለከተው መንፈስ ውጪ የተጠሪን ድርጅቶችን ደንበኞች በማደናገር የድርጅቱን ገቢ እየቀነሰ እንደሚገኝ ፣ አመልካች መስሪያ ቤትም ሁኔታውን እንዲያርም ተጠይቆ ተገቢውን ምላሽ ያልሰጠና ተመሳሳይ የንግድ ስያሜ የተሰጠው የሥር ሁለተኛ ተከሳሽም ጉዳዩን በድርድር ሊፈታው የማይችል መሆኑንና በአመልካች መስሪያ ቤት ጉዳዩ እልባት እንዲያገኝ ፍላጎት ያለው መሆኑን ገልጾ ሁኔታው እንዲታረምና እንዲሰረዝ እንዲወሰን እንዲሁም ኪሳራው በቁርጥ እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች በተከሳሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስም የንግድ ስራ ፈቃድ የተሰጠበትን አሰራር በአዋጅ ቁጥር 67/89 እንዲሁም ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 376/96 የተከተለ መሆኑን ፣ ለተጠሪ ድርጅትና ለስር ሁለተኛ ተከሳሽ የተሰጠው የንግድ ስራ ፈቃድ ተመሳሳይ ላልሆኑ ስራዎች የተሰጠ መሆኑን ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ሁለተኛ ተከሳሽም ቀድሞ የንግድ ስራ ፈቃድ የወሰደው ራሱ መሆኑና ተጠሪ ከተሰጠው የንግድ ስራ ፈቃድ ውጪ እየሰራ የሚገኝ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ክሱ

የቀረበለት ፍርድ ቤትም የአመልካችን መከራከሪያ ነጥቦችን ሕጋዊ አይደሉም በማለት ውድቅ አድርጎ የስር ሁለተኛ ተከሳሽ የንግድ ድርጅቱን ስያሜ እንዲቀይር ፣ የአሁኑ አመልካችም የስር ሁለተኛ ተከሳሽን የንግድ ድርጅት ስያሜ እንዲሰርዝ ፣ ሁለተኛ ተከሳሽም ታይገር የምትለዋን ስያሜ እንዳይጠቀም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች መስሪያ ቤት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የመስጠት ስልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 16(2) ስር የተደነገገ ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ከዚሁ ድንጋጌ ውጪ በሆነ መንገድ የንግድ ድርጅቱ ስያሜ እንዲሰረዝ መወሰናቸው ያላግባብ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለጉዳዩ መነሻ የሆነው የንግድ ስያሜ ተመሳሳይ ስለሆነ እና ያልተገባ የውድድር ስሜት እየፈጠረ ስለሆነ ይቀየር መባሉ ከአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 16(2) ድንጋጌ አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ ቀርቦ አመልካች የስር ሁለተኛ ተከሳሽ የሆነው ድርጅት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ተቀብሎ በተቀመጠበት ሁኔታ የሰበር አቤቱታውን ማቅረቡ ተገቢ ያለመሆኑንና በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔም ምንም የሕግ ስህተት የሌለበት መሆኑን በመዘርዘር መልሱን የሠጠ ሲሆን አመልካች ደግሞ በሕጉ አግባብ የተሰጠውን ስልጣን በመጠቀም ለፈፀመው ድርጊት የስር ፍርድ ቤት የሠጠውን የሕግ ስህተት በሕግ አግባብ ማሳረም መብቱ መሆኑን ዘርዝሮና የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሰረቱ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 20 መሰረት የንግድ ስራ ፈቃድ የመስጠት ስልጣን ያለው ሲሆን ይህንኑ ስልጣን ተግባራዊ ሲያደርግ የሚያስፈልጉትንና ሊከተላቸው የሚገባቸው ስርዓቶች በአዋጅ ቁጥር 67/89 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 376/96 ስር ተደንግገው እናገኛለን፡፡ አዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 14 የንግድ ስም ለማስመዝገብ መሟላት ስላለባቸው ነገሮችና ለምዝገባ የቀረበው የንግድ ስም ቀደም ሲል ከተመዘገበበት የንግድ ስሞች ጋር አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይና አሳሳች አለመሆኑን ወይም ለመልካም ጠባይ ወይም ሥነ ምግባር ተቃራኒ አለመሆኑን በአዋጁ አግባብ አለው በተባለው ባለስልጣን ከተረጋገጠ በሁዋላ የንግድ ስሙ የሚመዘገብ ስለመሆኑ በአመልካቹ ወጪ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ በማድረግ ሊመዘግብ የሚችልበትን አግባብ አዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 14(4) ድንጋጌ ደንግጎ ያለው ጉዳይ ሲሆን ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 376/96 ደግሞ የንግድ ስም ከዳታ ቤዝ ተጣርቶ የጋዜጣ ማስታወቂያ ሳያስፈልገው እንደሚመዘገብ ያስገነዝባል፡፡ የአሁኑ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረውም የአሁኑ ተጠሪ ታይገር ሎጂስቲክስ እና ንብረት ጥበቃ ኃ.የተ.የግል ማህበር የሥራ መስክ በላቀ ደረጃ የሎጂስቲክ ፣ የንብረት ጥበቃ ስልጠና እና የምክር አገልግሎት የሆነው እና የውጪ ኢንቬስቴር 70% ድርሻ የያዘ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ዋና ምዝገባ እና የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጠው መሆኑን ፣ የስር ሁለተኛ ተከሳሽ የተሰማራበት የንግድ ስራ መስክ በደቡብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ የተሰጠው የንግድ ስራ ፈቃድ ለሀገር ውስጥ ባለሀብት በተፈቀደ “ የጥበቃ ሥልጠና ” እና “የጥበቃ አገልግሎት” በመሆኑ አመልካች ሁለቱን የንግድ ማህበራት የተሰማሩበት የንግድ ስራ ጠባይ ፈጽሞ



www.chilot.me

አለመመሳሰሉንና በአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 16(2) የንግድ ስም መዝገብ የመግባት ውጤት ተገቢውን ማጣራት ከአደረገ በሁዋላ ምዝገባውን መፈፀሙን ነው፡፡ እንግዲህ በሕጉ የተዘረጋው ስርዓት ከላይ የተመለከተው ከሆነ እና አመልካች ተግባሩን ሕጋዊ ነው የሚልባቸው ምክንያቶች እነዚህ ከሆኑ በሕግ ረገድ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 16(2) ስር የተደነገገውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ምዝገባውን መፈጸም አለመፈፀሙን ነው፡፡ የዚህ ድንጋጌ ይዘት ሲታይ በንግድ ሕጉ ቁጥር 137 እና 138 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የንግድ ስም ቀድሞ የተመዘገበ መሆኑ ብቻውን በንግድ ስራ ጠባዩ ፈፅሞ ለማይመሳሰል የንግድ ስራ እንዳይመዘገብ ሊከለክል አይችልም በማለት በአስገዳጅ ሁኔታ የተደነገገ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ አመልካች እንደተገለፀው ተጠሪ የንግድ ስራ የወሰደበት ስራ እና የስር ሁለተኛ ተከሳሽ የንግድ ስራ የማይመሳሰሉ መሆናቸውን በሕጉ መሰረት በተሰጠው ስልጣን ማጣራቱን ገልፆ የተከራከረ ሲሆን የበታች ፍርድ ቤቶች የአሁኑ ተጠሪ እና የስር ሁለተኛ ተከሳሽ የንግድ ድርጅት ስም ይመሳሰላል ወደሚለው ድምዳሜ ከመድረሳቸው ውጪ ስራው አይመሳሰልም በማለት በአመልካች በኩል የቀረበውን ክርክር ተቀባይነት የሌለበት መሆኑን የሚያሳይ ሕጋዊ ምክንያት በውሳኔአቸው ላይ አልገለፁም፡፡ በመሆኑም አንድ የአስተዳደር አካል ድርጊት ውድቅ ሊደረግ የሚገባው ከሕግ ውጪ መሰራቱ ተረጋግጦ እንጂ ያለሕጋዊ ምክንያት ሊሆን አይገባም፡፡ ያለሕጋዊ ምክንያት ተግባሩን ተገቢ አይደለም ብሎ እንዲስተካከል በማለት መወሰን በሕግ የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር ባግባቡ እንዳይተገበር የሚያደርግ ጭምር ነው፡፡ በሌላ በኩል የስር ሁለተኛ ተከሳሽ በጉዳዩ ላይ ስርዓቱን ጠብቆ ይግባኝ ያለማቅረብ የአመልካችን አቤቱታ አቀራረብ ሕጋዊ አይደለም ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ ምክንያቱም አመልካች በሕጉ ተለይቶ የተሰጠውን ሥልጣን ባግባቡ ማከናወኑን እና አንድ ወጥ አሰራር ያለ መሆኑን ማረጋገጥ የራሱ ኃላፊነት ነውና፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 16(2) ስር የተመለከተውን መመዘኛ መሰረት ማድረግ ሲገባው የውል ስም የሆነውን ታይገር የሚለውን ቃል ብቻ በመመልከት የተጠሪ የንግድ ስያሜና የስር ሁለተኛ ተከሳሽ ስያሜ የሚመሳሰልና ያልተገባ ውድድር የሚፈጥር ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 141884 ሚያዚያ 08 ቀን 2001 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 81997 ግንቦት 04 ቀን 2002 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች እርምጃ በአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 16(2) እና አዋጅ ቁጥር 376/96 መሰረት ሲታይ ሕጋዊ ነው ብለናል፡፡ አመልካች የስር ሁለተኛ ተከሳሽ የንግድ ድርጅት ስያሜን እንዲሰርዝ የሚገደድበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 24435

የካቲት 04 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች** ፡- ሀጂ መሐመድ አደም

**ተከሣሽ** ፡- አቶ ፍፁም ግርማ

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የሚተላለፍ ሠነድ ላይ የግል ግንኙነትን መሠረት በማድረግ የሚቀርብን መቃወሚያ ይመለከታል፡፡ ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የቀረበው አቤቱታ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ለተጠሪ 0574420 የሆነ ብር 55,000 ሺህ የያዘ ቼክ የሰጡ ቢሆንም ለክፍያ ለባንክ ሲቀርብ በቂ ገንዘብ የለም ተብሎ ተመልሶላቸዋል፡፡ አመልካች ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ብር 25,000 ከፍለው ብር 30,000 ይቀርባቸዋል፡፡ በመሆኑም ይህንኑ ገንዘብ ከወለዱ ጋር ይክፈሉኝ ሲሉ ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም ቀርበው ቼኩ የተሰጠው በተጠሪና በአቶ ሙሣ መሐመድ መካከል ለነበረው አለመግባባት የሽምግልና ጉባኤ ባቀረበው ሃሣብ መሠረት ለሁለቱ ተከራካሪዎች መተማመኛ እንዲሆን በመሆኑ ክሱን ለመከላከል እንዲፈቀድላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ቼክ ግልጽ የሆነ የክፍያ ትዕዛዝ ብቻ የሚይዝ በዚህ ትዕዛዝ እንደቀረበ ክፍያ የሚፈፀምበትና ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በአውጪው ላይ የክፍያ ሃላፊነት የሚፈጥር የገንዘብ ሰነድ እንጂ የዋስትና ሰነድ ስላልሆነ ለመከላከል ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ገንዘቡን ከወለድ ጋር እንዲከፍሉ ወስኖባቸዋል፡፡

አመልካች ይህንን ውሣኔ በመቃወም ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡት የይግባኝ ቅሬታም ተቀባይነት ሣያገኝ ቀርቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ሲሆን ይህ ችሎትም ክሱ በይርጋ ሊታገድ የሚገባው መሆን አለመሆኑን እንዲሁም አመልካች ክሱን ሊከላከሉ የሚገባቸው መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ይግባኙ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ያደረገ ሲሆን ግራ ቀኙ በነዚህ ነጥቦች ላይ ክርክራቸውን አሰምተዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ክሱ በይርጋ ይታገዳል ወይስ አይታገድም የሚለውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች ቼኩን ለተጠሪ የሰጡት ጥር 30 ቀን 1997 ዓ.ም. መሆኑን ከመዝገቡና ከግራ ቀኙ የቃል ክርክር ጭምር መረዳት ተችሏል፡፡ ቼክ የወጣበት ቀን ከግምት ሳይገባ በቼክ ላይ ከተፃፈው ቀን አንስቶ በሚከተሉት 6 ወራት ውስጥ እንዲከፈል መቅረብ እንዳለበት በንግድ ሕግ ቁጥር 855 ሥር ተመልክቷል፡፡ በዚሁ ሕግ ቁጥር 881/1/ ሥር ደግሞ በቼክ የሚገደዱ ሰዎች ላይ አምጪው ክስ ማቅረብ



www.chilot.me

የሚችለው ቼኩን ለማቅረብ የተወሰነው ጊዜ ካለፈ ጀምሮ እስከ ስድስት ወር ድረስ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም አምጪው ክስ ማቅረብ የሚችለው ቼክ ከተፃፈበት ቀን አንስቶ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ቼክ የተፃፈው ጥር 30/1997 መሆኑ በግራ ቀኙ ያልተካደ ሲሆን ክስ የቀረበው ደግሞ ታህሣሥ 10/1998 መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ቼኩ ተጽፎ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ቀን 1 ዓመት አያልፍም፡፡ ቼኩ ተጽፎ ከተሰጠ ጀምሮ ለባንክ እንዲከፈል እስከቀረበበት ድረስ 6 ወር አልፏል እንዳይባል ደግሞ ቼኩ የተሰጠው ጥር 30/1997 መሆኑና ለክፍያ የቀረበው ሐምሌ 29/1997 መሆኑን ግራ ቀኙ ተማምነዋል፡፡ በመሆኑም ከጥር 30/1997 እስከ ሐምሌ 29/1997 ዓ.ም. 6 ወር ስለማያልፍ በንግድ ሕጉ ቁጥር 855 ሥር የተመለከተው የይርጋ ጊዜም ቢሆን ስለማያልፍ አመልካች ይርጋን አስመልክቶ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

በመቀጠል አመልካች ክሱን ሊከላከሉ ይገባል አይገባም የሚለውን ነጥብ እንመለከታል፡፡

በመሠረቱ ቼክ የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ሐተታ የሌለበት ትዕዛዝ የያዘና ቼኩም እንደቀረበ የሚከፈል መሆኑ በን/ሕ/ቁ. 827/ሀ/ እና 854 ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ቼኩ የታዘዘለት ሰው /አምጪው/ ቼኩን ይዞ እንደቀረበ ቼኩ ሊከፈል ይገባዋል፡፡ አውጪውም ሆነ የጀርባ ፈራሚዎቹ ለቼኩ አከፋፈል ኃላፊዎች በመሆናቸው /የን/ሕ/ቁ. 640 እና 868 /ሐ/ ይመለከቷል/ ቼክ ባልተከፈለ ጊዜ ተጠያቂዎች ይሆናሉ፡፡ ቼክ እንደ ገንዘብ ወደተለያዩ ሰዎች በቀላሉ ሊተላለፍ የሚችል ባህሪ ስላለው የቼክ አከፋፈል ላይ ማንኛውም መቃወሚያ ሊቀርብ አይችልም፡፡ ሕጉ ለይቶ ባስቀመጣቸው ጉዳዮች ካልሆነ የቼክ ክፍያ በማንኛውም ምክንያት ሊቆምና ሊታገድ አይችልም፡፡ ነገር ግን የተወሰኑ ሁኔታዎች ባጋጠሙ ጊዜ አውጪው ወይም ፈራሚዎቹ ቼክ ሊከፈል የማይገባበትን መቃወሚያ ሊያነሱ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም አግባብነት ያላቸው የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች በመቃወሚያነት እንዲቀርቡ የፈቀድዋቸውንና የከለከሉዋቸውን ጉዳዮች ለመለየት የሕጉን ድንጋጌዎች እንዳለ መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ለዚሁ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያላቸው ድንጋጌዎች የንግድ ሕጉ አንቀጽ 717 እና 850 ሲሆኑ የአንቀጽ 717 ይዘት የሚከተለው ነው፡፡

<u>717 *መቃወሚያ*</u>

1. *ዕዳ ከፋዩ ሰነዱን በያዘው ሰው በሁለቱ የግል ግንኙነቶች ላይ በተመሠረቱት፣ በሰነዱ አፃፃፍ ፎርምና እንዲሁም በሰነዱ ላይ በተፃፉት ቃሎች ካልሆነ ሌላ መቃወሚያ ሊያቀርብበት አይችልም፡፡*

2. *እንዲሁም ፊርማን በማስመሰል የተሰራ፣ ችሎታ ወይም ሰነዱ ሲወጣ የውክልና ሥልጣን ባለመኖሩ ወይም ክስ ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑት ሁኔታዎች ባለመሟላታቸው የተነሱትን መቃወሚያዎች ለማቅረብ ይችላል፡፡*

3. *አምጪው ይህን ሰነድ ባገኘበት ጊዜ ዕዳ ከፋዩን ለመጉዳት እያወቀ ያደረገው ካልሆነ በቀር ከዚህ በፊት ሰነዱን ይዘው ከነበሩት ሰዎች ጋራ በግል ግንኙቶች ላይ በተመሠረቱ ክርክሮች ዕዳ ከፋዩ ሰነዱን የያዘውን ሰው ሊቃወመው አይችልም፡፡*

<u>717 Defenses</u>

1/ The debtor may only set up against the holder of the instrument defenses based on their personal relations. Defenses of form and those based on the text of the instrument.

2/ He may set up defenses based on falsification of signature, lack of capacity or power of representation at the time of issue of the instrument or on the absence of the necessary conditions for bringing the proceeding.

3/ The debtor may not set up against the holder of the instrument defenses based on his personal relations with previous holders unless the holder in acquiring the instrument has knowingly acted to the detriment of the holder.

ከዚህ ሕግ ድንጋጌ ይዘት ሕጉ ለሚተላለፉ ሰነዶች የሚሰጠው ጥበቃ እንደተጠበቀ ሆኖ ተዘርዝረው በተገለፁ ሁኔታዎች በነዚህ ሰነዶች የተከሰሰ ሰው አንዳንድ መቃወሚያዎችን በማቅረብ ከእዳው ራሱን ነፃ ማድረግ እንደሚፈቅድ መገንዘብ ይችላል፡፡ የግል ግንኙነት መቃወሚያ ሊሆኑ ከሚችሉ ጉዳዮች አንዱ ሲሆን ከዚሁ ድንጋጌ ንኡስ ቁጥር አንድና ሶስት መገንዘብ እንደሚቻለው ሕጉ የግሉ ግንኙነት መቃወሚያ ሊሆኑ የሚችልበትንና የማይችልበትን ሁኔታ ለይቶ አስቀምጧል፡፡ በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ አንድ ላይ በዕዳ ከፋዩና ሰነዱን በያዘው ሰው መካከል ያለው የግል ግንኙነት በመቃወሚያነት ሊቀርብ የሚችል ሲሆን በዕዳ ከፋዩና /በተከሣሹ/ ቀድመው ሰነዱን ይዘው በነበሩ ሰዎች መካከል ያለ የግል ግንኙነት ግን በመርህ ደረጃ መቃወሚያ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም፡፡ በመሆኑም የግል ግንኙነት ምን ማለት ነው? የሚለው ጥያቄ እንደተጠበቀ ሆኖ የግል ግንኙነት እንደመቃወሚያ መቅረብ የሚችለው ይኸው የግል ግንኙነት በከሣሹና በተከሣሹ መካከል ያለ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው ቼክም ሆነ ሌሎች የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች በንግድ ልውውጥ ሂደት የመተላለፍ ባሕርይ ያላቸው በመሆኑ ከከሣሹና ከተከሣሹ በተጨማሪ ሌሎች ሰዎች በሂደት በፊርማ አስተላልፈዋቸው ወይም ተቀብለዋቸው ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ጠቃሚ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ሂደት የሚኖረው የግል ግንኙነት አንድ ብቻ ሳይሆን በእያንዳንዱ ቼኩን ፈርሞ ባስተላለፈና በተቀበለ ሰው መካከል በርካታ የግል ግንኙነቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ከነዚህ በርካታ የግል ግንኙነቶች /Personal relations/ መካከል ሕጉ በመቃወሚያነት እንዲቀርብ የሚፈቅደው በተከሣሹና ሰነዱን ይዞ በመጣው ሰው መካከል ያለውን የግል ግንኙነት ብቻ ነው፡፡ ተከሣሹ ሰነዱን ይዞ ከመጣው ሰው ሣይሆን ቀድመው ሰነዱን ይዘው ከነበሩ ሰዎች ጋር የነበረውን የግል ግንኙነት እንደመቃወሚያ በማቅረብ ክፍያውን አልፈጽምም እንዲል ሕጉ አይፈቅድለትም፡፡ ይህ መሠረታዊ መርህ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 717 /1 እና 3/ ላይ ብቻ ሳይሆን በንግድ ሕጉ አንቀጽ 752 እንዲሁም አንቀጽ 850 የተካተተ ነው፡፡ ቼክን የሚመለከተው አንቀጽ 850 በተለይ "አምጪው ቼኩን ሲያገኝ ያውም ባለዕዳውን ለመጉዳት ካላደረገ በቀር በቼኩ መሠረት የተከሰሱት ሰዎች ከአውጪው ጋራ ወይም በፊት አምጪ ከሆኑት ጋራ በግል ግንኙነታቸው ላይ በተመሠረቱት ልዩነቶች አምጪውን ሊቃወሙት አይችሉም" በማለት በቼክ የተከሰሰ ሰው መቃወሚያ ሊሆነው የሚችለው ከአምጪው /holder/ ወይም ቼኩን ከያዘው ሰው ጋር ያለው የግል ግንኙነት እንጂ ከቼኩ አውጪ /drawer/ ወይም ቼኩን ቀድመው ይዘው ከነበሩ ሰዎች /previous holders/ ጋር ያለውን የግል ግንኙነት እንዳልሆነ ይደነግጋል፡፡ የንግድ ሕግ አንቀጽ 850 የእንግሊዝኛው ትርጉም " Persons sued on a cheque cannot set up against the holder defenses founded on their personal relations with the drawer or with previous holder. unless the holder in acquiring the cheque has knowingly acted to the detriment of debtor" በሚል ነው፡፡



www.chilot.me

ሕጉ የግል ግንኙነት በመቃወሚያነት የሚቀርብበት ሁኔታ ሌሎች መቃወሚያዎች ከሚቀርቡበት ሁኔታ ልዩነት አበጅቷል፡፡ ይህን ልዩነት የንግድ ሕጉን አንቀጽ 717 ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች በመመልከት መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለው ሕጉ በግል ግንኙነት ያስቀመጠው ዓይነት ገደብ በሌሎች መቃወሚያዎች ላይ አላስቀመጠም፡፡ አንቀጽ 717 በመቃወሚያነት የሚቀበላቸው ሌሎች ጉዳዮች /የሰነዱ አፃፃፍ፣ በሰነዱ የተፃፉ ቃሎች ምክንያት የሚነሱ መቃወሚያዎች /717/1/ ወይም በማስመሰል የተሰራ ፊርማ፣ ችሎታ ወይም ሥልጣን አለመኖር፣ ክስ ለማቅረብ አስፈላጊ ሁኔታዎች አለመሟላት /717/2// የግድ በአምጪውና በተከሰሰው ሰው መካከል ብቻ የሚነሱ መሆናቸውን የሚገልጽ ድንጋጌ የለውም ይልቁንም እነዚህ ጉዳዮች መኖራቸውን ባረጋገጠ በማንኛውም ተከሣሽ ሊነሱ የሚችሉ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በመሆኑም በ717 ከተገለጹት መቃወሚያዎች መካከል የግል ግንኙነት /Personal relation/ ከሣሹንና ተከሣሹን ብቻ የሚመለከት ሆኖ ሲገኝ ሌሎች መቃወሚዎች ግን ሌሎችን በሂደቱ ላይ የነበሩትን ሰዎች የሚመለከት እንኳን ቢሆን በቃወሚያነት ማንሳት ይቻላል፡፡ በሌላ አነጋገር ሌሎቹ መቃወሚያዎች ቼኩን ተከትለው የሚሄዱ ሲሆን፣ የግል ግንኙነት ግን በሁለቱ /ከሣሽና ተከሣሽ/ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ነው፡፡ በመሆኑም በአንቀጽ 717 የሚታዩት መቃወሚያዎች ሁለት ገጽታ ያላቸው ናቸው፡፡ በአንድ በኩል ማንኛውም በቼክ የተከሰሰ ሰው ሊያነሳቸው የሚችል፣ አምጪውም ቢሆን እነዚህ መቃወሚያዎች አንተን የሚመለከቱ አይደሉም ሊል የማይችልባቸው በመሆናቸው ሰነዱ እስካለ ድረስ እሱን ተከትለው የሚሄዱ በሌሎች የሕግ ሥርዓቶችና በሕግ ጽንሰ ሃሣብ real defense በመባል የሚታወቁ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሰነዱ ይመለከታቸዋል ከሚባሉ ሰዎች መካከል የተወሰኑ ሰዎች ብቻ ካልሆኑ በቀር ሌሎቹ እንዲያነሱዋቸው የማይፈቀዱ በሕግ ሳይንስና በሌሎች የሕግ ሥርዓቶች Personal defense /in personal defense/ በመባል የሚታወቁ መቃወሚያዎች ናቸው፡፡ መቃወሚያዎችን /defense/ ብቻ ሳይሆን መብቶችን Personal እና Real ወይም rights in personal እና rights in rem/ ብሎ መከፋፈል በሁሉም የሕግ ሥርዓቶች ያለ በኛም የሕግ ሥርዓት በተለያዩ ሁኔታዎች የተካተተ ነው፡፡

በመሆኑም በንግድ ሕጉ የተለያዩ አንቀጾች በተለይም በአንቀጽ 717፣ 752 እንደሁም 850 የተገለፀውና የግል ግንኙነትን የሚመለከተው መቃወሚያ ሊታይ የሚገባው ከዚህ አንፃር ነው፡፡ ቼክ ለአምጪው የሚከፈል የንግድ ልውውጥን ለማቀላጠፍ ተብሎ የተዘጋጀ ሰነድ መሆኑ እሙን ነው፡፡ የአፈፃፀሙ ሂደት የንግድ ሂደትን እንዳያውክና እንዳያስተጓጉል መደረግ እንዳለበትም እሙን ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን ቼክ የሚሰጠው በአመዛኙ በንግድ ልውውጥና በግብይት ሂደት በመሆኑ ይህን ታሳቢ በማድረግ ሕጉ ያስቀመጣቸውን መቃወሚያዎች በአግባቡ ማስተናገድ ተገቢ ነው፡፡

በቼክ የተከሰሰ ሰው ከሌሎች በቼኩ ከተጠቀሙ ወይም ካስተላለፉ ሰዎች ጋር ያለውን የግል ግንኙነት ማንሣት ባይፈቀድለትም ከአምጪው ጋር ያለውን የግል ግንኙነት ግን ማንሳት ይፈቀድለታል፡፡ የግል ግንኙነት ምንድነው የሚለው ደግሞ ሊተረጎም የሚገባው ከላይ ከተመለከትነው፣ የንግድ ሕግን ዓላማ የሚያሳካና ከተለመደው አተረጓጎም አንፃር እንጂ ከዚህ ባፈነገጠ መንገድ ሊሆን አይገባውም፡፡ በመሆኑም የግል ግንኙነት ማለት ከሚመለከታቸው ሁለት ሰዎች ውጪ በሌሎች ሰዎች ሊነሳ የማይችል ግንኙነትን ለማመልከት እንጂ ከንግድና ከግብይት ውጪ የሚከሰቱ ግላዊ ግንኙነቶች ለማመልከት የተቀመጠ ነው ተብሎ ሊተረጎም አይገባውም፡፡ የግል ግንኙነት /Personal relation/ በተለምዶ in personal በመባል የሚታወቀውን ከሕግ ወይም ከውል የሚመነጭ በሁለት ሰዎች መካከል የተፈጠረ ግንኙነት ማለት ነው፡፡

የንግድ ሕጉ አንቀጽ 850 በቼክ የተከሰሱ ሰዎች ቼኩን ካዘጋጀው /አምጪው/ ወይም ቼኩን ቀድመው ይዘው ከነበሩት ሰዎች /Personal holder/ ጋር የነበረውን የግል ግንኙነት ቼኩን ይዞ በመጣ ሰው /holder/ ላይ እንዳያነሳ ከሚከላከል በቀር ተከሣሹ ቼኩን ካመጣው ሰው ጋር ያለውን የግል ግንኙነት እንዳያነሳ የሚከለክል አይደለም፡፡ ይልቁንም ለሁሉም ሰነዶች ተፈፃሚነት ያለውና ከላይ የተመለከትነው አንቀጽ 717/1/ በሁለቱም መካከል ያለ የግል ግንኙነት መቃወሚያ ሊሆን እንደሚችል በግልጽ ያስቀመጠው ነው፡፡ ይህ የሕግ ይዘት በቼክ የተከሰሰ ሰው በቼኩ ላይ የተገለፀውን ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ላለመክፈል መብት የሚሰጠውን ከውል የመነጨ ግንኙነት እንደመከላከያ እንዲያቀርብ የሚፈቅድለት ነው፡፡ ቼክ አብዛኛውን ጊዜ የሚሰጠው ከውል ወይም ከሕግ የመነጨ ግዴታን ለመፈፀም /in consideration/ እንደመሆኑ ለግዴታው መነሻ የሆኑ ጉዳዮችን በማስመልከት መከላከያ እንዲሆኑ መፍቀድ ተገቢም ነው፡፡ ይህ አሠራር የሁለቱም ወገን ማስረጃን ለመመዘን ዕድል በመስጠት እውነት እንዲወጣ ከማገዙም ባሻገር የተለያዩ ክሶች እንዳያቀርቡ ስለሚያደርግ ወጪ ቆጣቢም ነው፡፡

የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረቡትን መቃወሚያ ውድቅ ያደረገው የንግድ ሕጉ አንቀጽ 827/840 እንዲሁም 854 ቼክ እንደቀረበ ክፍያ የሚፈፀምበትና ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በአውጪው ላይ የክፍያ ኃላፊነት የሚፈጥር የገንዘብ ሰነድ እንጂ የዋስትና ሰነድ አለመሆኑን ይደነግጋል በማለት ነው፡፡ በመሠረቱ እነዚህ የተጠቀሱት የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች ቼክ በዋስትና ሊሰጥ የማይችል መሆኑን አይደነግጉም፡፡ ቼኩ የሚሰጥበት ምክንያት በሰጪውና በተቀባዩ የሚወሰን እንጂ በሕጉ የተዘረዘረ አይደለም፡፡ ሕጉ ቼክ ላምጪው ወዲያው የሚከፈል መሆኑን መግለፁ ደግሞ መከላከያና መቃወሚያ የማይቀርብበት ሰነድ ነው ማለት አይደለም፡፡ የሕጉ ዓላማ ይህ ቢሆን በማያሻማ ሁኔታ በ717 በተዘዋዋሪ መንገድ ደግሞ በአንቀጽ 850 መቃወሚያ የሚቀርብባቸውን ሁኔታዎች አይደነግግም ነበር፡፡

በመሆኑም ፍርድ ቤቱ ተከሣሽ ያቀረቡትን መቃወሚያ አልቀበልም ያለው ከሕጉ ድንጋጌ ውጪ በመሆኑ ሊሻር የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ቼኩ በዋስትና የተሰጠ መሆኑን በመገለፁ የአሁን አመልካች ከከሳሽ ጋር የዋስትና ውል ግንኙነት ያላቸው መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ይህ ውል ደግሞ በመካከላቸው የግል ግንኙነት መኖሩን ስለሚያሳይ በመቃወሚያነት መቅረብ የሚችል ነው፡፡ የቀረበው መቃወሚያ የተጠየቀውን ገንዘብ ላለመክፈል በቂ ምክንያት መሆን አለመሆኑ የሚታወቀው ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን በአግባቡ ካከራከረ በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤት መቃወሚያውን ተቀብሎ ክርክሩን ሊያስተናግድ የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 62028 የካቲት 28/98 የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 45409 በ22/7/98 የሰጠው ትዕዛዝ በድምጽ ብልጫ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች መከላከያቸውን አቅርበው ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩ ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ተመልሷል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡



www.chilot.me

## የሁለተኛው ዳኛ የሐሣብ ልዩነት

በዚህ ጉዳይ በሰበር መ/ቁጥር 24435 እና በሰበር መ/ቁጥር 26438 አከራካሪ የሆኑት ጭብጦች፣

1ኛ/ በንግድ ሕግ ቁጥር 717/1/ የተደነገገው በዕዳ ከፋዩና ሰነዱን በያዘው ሰው መካከል ያለውና በሕጉ መሠረት መቃወሚያ እንዲቀርብበት የሚፈቀደው ግንኙነት የዋስትና ግንኙነትንም ይጨምራል? ወይንስ አይጨምርም?

2ኛ/ ይኸው በቁጥር 717/1/ የተፈቀደው የግል ግንኙነት /Personal relations/ መቃወሚያ ገደብ ሊኖረው ይገባል? ወይንስ አይገባም? የሚሉት ናቸው፡፡

## የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተም፣

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1920 መሠረት የዋስትና ግዴታ ማለት ዋሱን ባለዕዳውንና ባለገንዘቡን የሚያካትት ግዴታ ነው፡፡

በንግድ ሕግ ቁጥር 717/1/ መሠረት መቃወሚያ እንዲቀርብበት የሚፈቀደው ግንኙነት ግን በዕዳ ከፋዩና ሰነዱን በያዘው ሰው <u>በሁለቱ መካከል</u> ባለው የግል ግንኙነት ላይ ብቻ የሚመሠረት ነው፡፡

ስለሆነም፣ በዋሱ፣ በባለዕዳውና በባለገንዘቡ የሦስትዮሽ የጋራ ግንኙነት ላይ የሚመሠረተው የዋስትና ግንኙነት በተቃጠሹ ሕግ ውስጥ የሚካተት አይደለም፡፡

የዚህን ምክንያት ከያዝነው ጉዳይና ከሕጉ አንፃር እንመልከት፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካቹ በቼክ የቀረበባቸውን ክስ ለመከላከል በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የኮ/መ/ቁጥር 62028 የሰጡት ምክንያት የሚከተለው ነው፡፡ ይኸውም፣ ተጠቃሹን ቼክ ለከሳሹ /ለአሁን መልስ ሰጭ/ የሰጠሁት መክፈል ያለብኝ ዕዳ ኖሮ ሣይሆን በከሣሽና በአቶ ሙሣ መሐመድ /ልጃቸው መሆኑ ነው/ መካከል ለነበረው አለመግባባት የሽምግልና ጉባኤ ባቀረበው ሃሣብ መሠረት ለሁለቱ ተከራካሪዎች <u>መተማመኛ</u> እንዲሆን እንጂ ለክፍያ የተሰጠ ቼክ አይደለም የሚል ነው፡፡

አመልካቹ በማስፈቀጃ ማመልከቻው በገለጹት መሠረት <u>በተፋጠነ ሥነ ሥርዓት</u> የቀረበባቸውን የቼክ ክስ ለመከላከል የሚፈልጉት በራሣቸውና በመልስ ሰጭው <u>በሁለቱ</u> መካከል ባለው የግል ግንኙነት ላይ ተመሥርተው ሣይሆን በሣቸው፣ በልጃቸውና በመ/ሰጪው መካከል ባለው የሦስቱ የጋራ ግንኙነት ውስጥ ለመተማመኛ የተሰጠ ቼክ መሆኑን በማስረዳት ነው፡፡ በአመልካቹና በመልስ ሰጪው መካከል ባለው የሁለቱን የግል ግንኙነት በተመለከተ ግን ቼኩን ዕዳ ኖሮብኝ ለክፍያ የሰጠሁት አይደለም ብለዋል፡፡

የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤቱ ቼክ በአውጪው ላይ የክፍያ ኃላፊነትን የሚፈጥር የክፍያ ሰነድ እንጂ የዋስትና ሰነድ ባለመሆኑ ተከሣሹ ክሱን ለመከላከል ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡ የተከሰሱበትን የገንዘብ መጠን ይከፍላሉ ብሎ ወስኗል፡፡

ሕጉን በተመለከተም፣ በተጠቃሹ የንግድ ሕግ ቁጥር 717/1/ መሠረት መከላከያ እንዲቀርብበት የሚፈቀደው በሁለቱ፣ በዕዳ ከፋዩና ሰነዱን በያዘው ሰው የግል ግንኙነት ላይ

የተወሰነ መሆን ስለሚገባው፣ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1920 በተደነገገው መሠረት ዋስትና ከዋስትና ሰጪውና ከዋስትና ተቀባዩ የግል ግንኙነት ሰፋ ብሎ ባለዕዳውንም የሚጨምር የሦስት ወገኖች ግንኙነት በመሆኑ፣ በንግድ ሕግ ቁጥር 840 መሠረት አውጪው ዋስ የሚሆነው ለቼኩ አከፋፈል በመሆኑ፣ /The drawer guarantees payment/ ከዚህ የዋስትና ኃላፊነት ለመዳን የሚፃፈው ቃል ሁሉ እንዳልተፃፈ የሚቆጠር በመሆኑ፣ /any provision by which the drawer releases himself from this guarantee shall be of no effect/ ተብሎ የተደነገገ በመሆኑ የአመልካቹ /አውጪው/ ዋስትና ለአምጪው /ለመልስ ሰጪው/ መሆን ሲገባውና አውጪው ሦስተኛ ወገን ለሆነው ልጃቸው ሰጥቻለሁ የሚሉት ዋስትና መተማመኛ ወዘተ እንዳልተፃፈ መቆጠር ሲገባው፣ በድምጽ ብልጫው ተቀባይነት ማግኘቱ ተገቢ ባለመሆኑ ተለይቻለሁ፡፡

## ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-

በዚህ ጭብጥ ላይ ተከራካሪዎቹ ወገኖች ዕዳ ከፋዩና ሰነዱን የያዘው ሰው መሆናቸው አከራካሪ አልሆነም ልዩነቱ ያለው በንግድ ሕግ ቁጥር 717/1/ በተደነገገው መሠረት በዕዳ ከፋዩና ሰነዱን በያዘው ሰው መካከል ያለው የግል ግንኙነት /personal relation/ ምን ያሕል ሰፋ ብሎ መተርጎም አለበት? የሚለው ላይ ነው፡፡

ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁጥር 39902 ኀዳር 8/97 የሰጠው ውሣኔ ነው፡፡ የፍሬ ነገር ክርክሩ ደግሞ፣ በአመልካቹ በአቶ ሰለሞን ታደሰና በመልስ ሰጭው በአቶ ሽኩር ብርሃን መካከል ያለው የሴቶች ቦርሣን የንግድ ንግኙነት የሚመለከት ነው፡፡ አመልካቹ አከራካሪ በሆነው ቼክ ላይ የተፃፈው 83,760 ብር እንዲከፈላቸው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ክስ ሲያቀርቡ መ/ሰጪው ለመከላከል እንዲፈቀድላቸው የጠየቀው፣ በሁለቱ መካከል የሴቶች ቦርሣ ንግድ የነበረ መሆኑን በመግለጽ ሲሆን እነዚህ አመልካቹ የሸጡላቸው ቦርሣዎች ወደሀገር ውስጥ በኮንትሮባንድ የገቡ ናቸው ተብሎ ከመ/ሰጪው ጋር ከሚሠሩት ከአቶ ሥራጅ ኢብራሂም እጅ የተወረሱና አቶ ሥራጅም ኮንትሮባንድ ይዘህ ተገኝተሃል ተብሎ በደንብ መተላለፍ ተከሰው በዋስትና ስለተለቀቁ ለተወረሰ ዕቃ ገንዘቡን ልከፍል አይገባኝም የሚል ነው፡፡ መ/ሰጭው እንዲከላከሉ ከተፈቀደላቸው በኂላ አቶ ሥራጅ ኢብራሂምንና ሌሎች በሽምግልናው ላይ ነበሩ የተባሉ ግለሰቦችን ቃል በምስክርነት እንዲያሰሙ ተደርጎ መ/ሰጪው ዕዳውን ሊከፍሉ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡

የአመልካቹ ጠበቃ በሰበር አቤቱታ ማመልከቻ ቼኩን ከዕቃ ሽያጩ ጋር ተጠቅሶ መስጠቱን የሚመለከት የሽያጭ ውል በሌለበት ሁኔታ የቼክ ክስ በምስክር የሚስተባበል ከሆነ በተፋጠነ ሥነ ሥርዓት የሚመራ መሆኑ ቀርቶ ከመደበኛው የብድርና አደራ ግንኙነት ደረጃ በታች መሆኑን /የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2472ትን ይመለከቷል፡፡/ ስለሚያሳይ ሊታይም የሚገባው ነው ብለዋል፡፡

ሕጉን በተመለከተም፣ የአብዛኛው ድምጽ አስተያየት፣ ቼክ አብዛኛውን ጊዜ የሚሰጠው ከውል ወይም ከሕግ የመነጨ ግዴታን ለመፈጸም /in consideration/ የሚሰጥ በመሆኑ ለግዴታው መነሻ የሆኑ ጉዳዮችን በማስመልከት መከላከያ እንዲሆኑ መፍቀድ ተገቢ ነው የሚል ነው፡፡

በአነስተኛው ድምጽ አስተያየት ግን፣ በንግድ ሕግ ቁጥር 717/1/ መሠረት በግራ ቀኙ መካከል ያለው የግል ግንኙነት ለመከላከያነት ሊፈቀድ ይገባል ቢባልም የግል ግንኙነቱ በጣም ሰፋ ተደርጎ መተርጎም የለበትም የሚል ነው፡፡ ቼኩን ባመጣው ባለገንዘብና ቼኩን ባወጣው ባለዕዳ መካከል ያለው የግል ግንኙነት /ቤተሰባዊ፣ የንግድና ሌሎችም ተመሣሣይ ግንኙነቶች/ በጠባቡ መታየት አለበት፡፡ አመልካቹ በቼኩ እንዲከፈላቸው ክስ ሲያቀርቡ መ/ሰጪው የሸጠልኝ ዕቃ ሦስተኛ

ሰው እጅ ከገባ በኂላ ኮንትሮባንድ ነው ተብሎ ስለተያዘ በቼኩ መክፈል የለብኝም የሚለውን ክርክሩን መቀበል የግል ግንኙነታቸውን በጣም ሰፋ አድርጎ መተርጎም ነው፡፡ ይህን የግል ግንኙነት መከላከያ በጣም ሰፋ አድርጎ መተርጎም ደግሞ፣ በንግድ ሕግ ቁጥር 840 የቼኩ አውጪ ለአከፋፈሉ ዋስ ነው፡፡ አውጪውን ከዚህ ዋስትና ኃላፊነቱ ለመዳን የሚፃፈው ቃል ሁሉ እንዳልተፃፈ ይቆጠራል ተብሎ ከተደነገገው ጋር የሚጋጭ ነው፡፡

የግል ግንኙነት ትርጉሙ በጣም የሚጠብ ከሆነም በንግድ ሕግ ቁጥር 717/1/ ላይ የተሰጠውን የመከላከል ፈቃድ የሚነሣ እንዳይሆን በሁለቱ ወገኖች መካከል ባለው <u>የጠበቀ</u> ግንኙነት ላይ ብቻ መፈቀዱ ባግባቡ ይመስለኛል፡፡

ስለዚህ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁጥር 62028 የካቲት 28/98 የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሳይኖርበት በመሻሩ፣ በኮ/መ/ቁጥር 39902 ኅዳር 8/97 በዚሁ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ከመሠረታዊ የሕግ ስህተቱ ጋር እንዲፀና በመደረጉ ስላልተስማማሁ በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 50537

ግንቦት 02 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሀመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** ፡- ሲ/ር መዓዛ ዮሴፍ ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- ዶ/ር ዮሴፍ ደነቀው ጠበቃቸው አቶ ሙሉቀን ሊበን ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የአሁኑ የሰበር ተጠሪ ለሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ፍሬ ቃሉ ከተከሣሽ /ያሁኗ የሰበር አመልካች / ጋር ጕፋ ገብርኤል ከፍተኛ ክሊኒክ ኃ/የተ/የግል ማህበር አቋቁመን በድርጅቱ መመስረቻ ጽሁፍ ከተገለፀው ካፒታል በተጨማሪ የህክምና መሳሪያዎችን በመግዛት በሁለት ቦታዎች የክሊኒክ ሥራ እየሠራን ቆይተን ከጊዜ በኋላ ከተከሣሽ ጋር ተግባብተን መሥራት ያልቻልንና ተከሣሽ ከሣሽን ከማህበር በማግለል ድርጅቱን ይዘው ለብቻቸው እየተጠቀሙ ስለሆነ ማህበሩ በፍ/ቤት ውሣኔ ፈርሶ የንብረት አጣሪ ተሹሞ የሚገባኝ ድርሻ እንዲከፈለኝ አመለክታለሁ የሚል ነው፡፡

የሥር ተከሣሽም የክስ መቃወሚያና በፍሬ ነገር ላይ በአማራጭ መልስ አቅርበዋል፡፡ ያቀረቡት የክስ መቃወሚያም ከሣሽ ከማህበሩ ለመውጣት ባቀረቡት ተደጋጋሚ ጥያቄ መሠረት ጉዳዩ በሽማግሌዎች ሲታይ ቆይቶ ሰኔ 24 ቀን 1998 ዓ/ም በተደረገው ስምምነት ከሣሽ በዓይነት ያዋጡትን ንብረትና ብር 60,000 /ስድሣ ሺህ ብር/ ወስደው ጉዳዩ በሽምግልና ያለቀ በመሆኑ ከማህበሩ ከወጡ በኋላ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብትና ጥቅም ስለሌላቸው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ብለዋል፡፡

ተከሣሽ በፍሬ ነገሩ ላይ በአማራጭ በሰጡት መልስ ከከሣሽ ጋር ማህበሩን አቋቁመናል የማህበሩም ካፒታል ማህበሩ ሲቋቋም ብር 40,000/አርባ ሺህ ብር/ ሲሆን ከሣሽና ተከሣሽ እያንዳንዳችን ብር 20,000 ማምጣት የሚጠበቅብን ቢሆንም ከሣሽ ገንዘብ አልያዝኩም በማለታቸው ሌላ ጊዜ ይከፍላሉ በማለት በእምነት የከሣሽ ድርሻ ብር 20,000 እንደተከፈለ ተደርጐ በመመስረቻ ጽሁፍ ተሞልቷል፡፡ ሆኖም ገንዘቡን ሳይከፍሉ ቀርተዋል፡፡ በከሣሽ ተደጋጋሚ ጥያቄ ምክንያት ሽማግሌዎች ተመርጠው ጉዳዩን ሲያዩ ከቆዩ በኋላ በ24/10/98 ዓ/ም በተደረገው ስምምነት መሠረት 60,000 ብር እና በአይነት ንብረት ወስደው ከወጡ በኋላ ጉዳዩን በግልግል ለመጨረስ ተከሣሽ እንቢተኛ በመሆን ድርጅቱን በግላቸው እየተጠቀሙ ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ሐሰተኛ ነው፡፡

በመተዳዳሪያ ደንባችን የአንዱ ማህበርተኛ ከማህበሩ መውጣት ማህበሩን አያፈርሰውም በሚል የተስማማን ስለሆነና ከሣሽም ድርሻቸውን ወስደው ከማህበሩ የወጡ በመሆናቸው ማህበሩ ፈርሶ ሂሣብ አጣሪ ተሹሞና ሂሣቡ ተጣርቶ ድርሻዬ ይከፈለኝ ያሉትም የሚቻል አይደለም በማህበሩም ምንም አይነት ድርሻ የላቸውም፡፡ ማህበሩ በከሣሽ ጥያቄ እንዲፈረስ ውሣኔ የሚሰጥ ከሆነ ደግሞ ከሣሽ ከማህበሩ እወጣለሁ ብለው የወሰዱትን ብር 60,000 እና ሌሎች በዓይነት የወሰዱአቸውን ንብረቶች እንዲመልሱና ለማህበሩ ጽ/ቤት ኪራይ ብር 114,000 እንዲሁም ከሣሽ የፈረሙበት የማህበሩ ዕዳ ብር 207,536.85 በድምሩ ብር 321,536.85 ከግል ገንዘቤ እየከፈልኩ ስለምገኝ እንደማህበሩ ዕዳ እንዲቆጠር፣ የማህበሩ አባል ተከሣሽ ብቻ ስለሆንኩኝ በንግድ ህግ ቁጥር 511/1/ መሠረት የማህበሩ አባላት ቁጥር ከ2 በታች ስለሆነ ማህበሩ በፍ/ቤት ውሣኔ እንዲፈርስ እጠይቃለሁ ብለዋል፡፡

የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤትም አጣሪ በመሾም የማህበሩ ንብረት እንዲጣራ ካደረገ በኋላ የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር ከሣሽ ለማህበሩ ባዋጡት የገንዘብ መጠን ድርሻቸው ሲሰላ 36.63 ከመቶ ስለሚሆን በጠቅላላው 83,081.04 ብር ተከሣሽ ለከሣሽ እንዲከፍሉና ማህበሩም በንግድ ህግ አንቀጽ 511/1/ መሠረት እንዲፈርስ ወስኗል፡፡

ይህ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ በአሁኗ የሰበር አመልካች ይግባኝ ጠያቂነት ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ቀርቦ ክርክር ከተካሄደበት በኋላ ከፍተኛው ፍ/ቤትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት የሥር የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔን አጽንቷል፡፡

በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ቅር የተሰኙት የሰበር አመልካችም ባቀረቡአቸው የቅሬታ ነጥቦች፡-

- ጉዳዩ በሽምግልና ታይቶ ውሣኔ አግኝቷል በሚል በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 244/2/ረ/ መሠረት ያቀረብኩትን መቃወሚያ የሥር ፍ/ቤት ውድቅ ማድረጉ ያለአግባብ ነው፣
- ማህበሩ ይፈርሣል ከተባለም ወደ ነበርንበት ልንመለስ ሲገባ ተጠሪው ብር 60,000 እና የህክምና መገልገያዎች እንዲሁም የጽ/ቤት ዕቃዎችን ከማህበሩ ወስደው ወጥተው ባሉበት በተጨማሪ ብር 83,081.04 አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑ ያለአግባብና የሽምግልና ስምምነቱን ያላገናዘበ ነው፣
- በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 17/2/ መሠረት አንድ ማህበርተኛ ከማህበሩ በመውጣቱ ምክንያት ማህበሩ እንደማይፈርስ ተገልጾ እያለ ከስምምነታችን ውጪ የተሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የለውም፣
- ማህበሩ ከፈረሰ ተጠሪውና አመልካች ለማህበሩ ዕዳ ብር 321,536.85 በጋራ ተጠያቂዎች መሆን ሲገባንና ተጠሪውም ዕዳውን ባላስተባበሉበት የሥር ፍ/ቤቶች በምን ምክንያት ዕዳውን እንዳለፉ በውሣኔያቸው አልጠቀሱም ከዚህ ሌላ ማህበሩ ሲፈርስ ትርፍና ኪሣራ ሳይለይ ለተጠሪው ብር 83,081.04 አመልካች እንዲከፍል ሲወሰን የአመልካች ድርሻ ምን እንደሆነ ሳይወሰን ታልፏል፣ ሂሣቡን ያጣሩት ሰዎች ቀደም ሲል ጉዳዩን በሽምግልና ከማየታቸው ውጪ በሂሣብ አጣሪነት እንዲሠሩ አመልካች ሳልፈቅድ ፍ/ቤቱ እንዲያጣሩ ያደረገ ሲሆን ምንም አይነት የሂሣብ ሞያ የሌላቸው ናቸው በማለት የሥር ፍ/ቤቶች የፈፀሙት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡

የሰበር ተጠሪ በበኩላቸው በሰጡት መልስ፡- አመልካች ለአጣሪዎች ያላቀረቡአቸውን ክርክሮች ሪፖርቱ ለሥር ፍ/ቤት ከቀረበለት በኋላ ያቀረቡ በመሆናቸው ተጠሪ አግባብነት ያላቸውን

የማስተባበያ ማስረጃዎች በማቅረብ እንዳልከላከል ያደረገ ከመሆኑም ሌላ አዲስ ክርክር በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 329 መሠረት ተቀባይነት የለውም፣ የሂሣብ አጣሪዎች የሂሣብ ዕውቀት የላቸውም በሚል የቀረበው ክርክርም ቢሆን ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ምክንያቱም አጣሪዎች የተለየ ሞያ ክህሎት እንዲኖራቸው የሚያስገድድ ህግ የለም፡፡ አጣሪዎቹ የተሾሙትም አመልካች ተጠሪ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ቀርበን ባመለከትነው መሠረት ነው፡፡ ጉዳዩ በሽምግልና የተጠናቀቀ ነው ላሉትም ስምምነቱ የማህበሩን መፍረስ የሚመለከት ካለመሆኑም በላይ አንድ የማህበር አባል በሀገሪቱ ህግና በማህበሩ ደንብ መሠረት ማህበሩ እንዲፈርስና ከንብረቱ ድርሻው እንዲከፈለው የመጠየቅ መብቱን የሚያስቀር ወይም የሚያሣጣ አይደለም፡፡ ተጠሪው በማህበሩ ባለኝ 50% ድርሻ ታስቦ ሊከፈለኝ የሚገባውን ገንዘብ በህግ የመጠየቅ መብት ቢኖረኝም ለሰላም ሲባል አነስተኛ ቀመር ተቀብያለሁ፡፡ የማህበሩ ካፒታል ብር 40,000 ሲሆን እኔም ድርሻዬን በሙሉ ከፍያለሁ፣ የከፈልኩ ስለመሆኔም አጣሪው አረጋግጧል፡፡

የማህበሩ ሀብት እና ዕዳ ተጣርቶ ቀደም ሲል ከተቀበልኩት የካሣ ክፍያ በተጨማሪ ብር 83,081.04 የሚገባኝ መሆኑን አጣሪዎች በማረጋገጣቸው ፍ/ቤቱም ተቀብሎ አጽድቆታል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው ማህበሩ ያለበት ዕዳ ፣ ሀብት እና ሁለቱም የማህበሩ አባላት ከማህበሩ ካፒታል በተጨማሪ ገቢ ያደረግነው ገንዘብ ተመዛዝኖ ነው፡፡

አጣሪዎች ሂሣቡንም የሠሩት እስከ 24/10/1998 ባለው ጊዜ ብቻ ሲሆን ከዚህ ከተጠቀሰው በኋላ የተገኘው ሀብትም ሆነ የመጣው ዕዳ በ24/10/98 አመልካችና ተጠሪ ባደረግነው ስምምነት መሠረት እንዲሰላ በፍ/ቤትም ሆነ በአጣሪዎች ዘንድ የተስማማን በመሆኑ በዚህ ነጥብ ላይ ተጠሪን የሚጠቅም ወይም በሀላፊነት የሚያስጠይቅ ነገር የለም ሲሉ በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለመኖሩን በመጥቀስ ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ እንደተመለከተው የቀረበ ሲሆን እኛም የሚከተለውን ጭብጦች ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

- የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በፊት በሽምግልና ተጠናቅቋል ወይስ አልተጠናቀቀም?
- አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ የተወሰነባቸውን ገንዘብ ሊከፍሉ ይገባል ወይስ አይገባም?

የመጀመሪያውን ጭብጥ በሚመለከተ፡- አመልካች የሚከራከሩት ጉዳዩ በሽምግልና ሲታይ ቆይቶ ሰኔ 24 ቀን 1998 ዓ/ም ስምምነት የተደረሰ በመሆኑና ተጠሪዉም በዚሁ ስምምነት መሠረት ብር 60,000 ፣ የህክምና መሣሪያዎች እና ሌሎች የጽ/ቤት ቁሳቁሶችን ወስደው ከማህበሩ የወጡ በመሆናቸው በተጠናቀቀ ጉዳይ ክስ ማቅረብ አይችሉም በማለት ለክርክራቸውም የጠቀሱት የፍትሃብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁ 244/12/ረ/ ነው፡፡

በእርግጥ የተጠቀሰው የፍብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 244/2/ረ/ ክስ የተነሣበት ነገር በሽምግልና ታይቶ በስምምነት የተፈፀመ ከሆነ ወይም ለዕርቅ የተቀጠረ ከሆነ ክሱን መቃወም እንደሚቻል የሚደነግግ ነው፡፡ ይህ ችሎትም አመልካች እንደሚሉት በእርግጥ የግራ ቀኙ ክርክር በሽምግልና ታይቶ በስምምነት ተፈጽሟል ወይስ አልተፈፀመም የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ለመወሰን ሰኔ 24 ቀን 1998 በግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የተፈረመ ቃለ ጉባኤና ብር 60,000 ለተጠሪ የተከፈለበትን ሠነድ ይዘት ተመልክቷል፡፡



www.chilot.me

ቃለ ጉባኤውም አመልካችም ሆነ ተጠሪ ለማህበሩ የተለያዩ ወጪዎችን ማውጣታቸውን የሚገልጽ ሲሆን የሰበር አመልካች ግን ከተጠሪው የበለጠ ወጪ ማውጣታቸውን ይገልጻል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቃለጉባኤ ድርጅቱ ከተቋቋመ በኋላ፣ በሥራ ሂደት ወይም በመጀመሪያ አካባቢ በድርጅቱ የተፈሩ ወይም የተገዙ ቋሚ ዕቃዎችን በሚመለከት እስከ 24/10/98 ድረስ ተከፍሎ ያልተጠናቀቀ ዕዳ እና የተከፈለው ተሰልቶ ለተጠሪ የሚገባ ክፍያ ያዋጡት መጠን በመቶኛ ተሠልቶ እንዲሰጣቸው ያልተከፈለ የተጠሪ ደመወዝ እንዲከፈላቸው በቅድመ ክፍያ የተከፈለው የቤት ኪራይ ገንዘብ ቅድመ ክፍያ የተፈፀመበት ወራት ተለይቶ የተጠሪ ድርሻ እንዲመለስላቸው እና ተጠሪው ድርሻቸውን በማስተላለፍ ከማህበሩ ስለሚወጡ ካሣ ብር 60,000 አመልካች እንዲከፍሉ ማህበሩ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 24/10/1998 በማህበሩ ላይ ያለውን ዕዳ በተመለከተ ድርጅቱን በማስቀረት ይዘው የሚያዙት አመልካች በሚያቀርቡት እና በተጠሪው ምትክ በሚገባ ግለሰብ ይሸፈናል የሚሉትንና ባጠቃላይ ከተራ ቁጥር 1-9 የተጠቀሱትን ነጥቦች ያካተተ ነው፡፡

አመልካች ግን ለተጠሪው ብር 60,000 /ስልሳ ሺህ ብር/ የተከፈላቸው በመሆኑንና በአይነት የህክምና መሣሪያዎችን ወስደዋል በሚል ነው አጥብቀው እየተከራከሩ ያሉት ብር 60,000 ለተጠሪ የተከፈለበት ሠነድም ቢሆን ሌሎች ክፍያዎች በቃለጉባኤው በተገለፀው መሠረት የሚከናወኑ መሆናቸውን በግልጽ ይናገራል፡፡ ይህ ሆኖ ሣለ አመልካች ቃለጉባኤው ተጠሪው ከማህበሩ የሚደርሣቸውን አጠቃላይ ድርሻ ያላስቀመጠና ገና ሂሣብ ተጣርቶ የሚፈፀም መሆኑን እየገለፀ ባለበት ብር 60,000 /ስልሳ ሺህ ብር/ እና የህክምና መሣሪያዎችን በአይነት ተጠሪው ወስደው በስምምነት ተጠናቅቋል ሲሉ ያቀረቡት መቃወሚያ ከፍትሃብሄር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 244/2/ረ/ መንፈስ ውጪ በመሆኑ ያለአግባብ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የሥር ፍ/ቤቶች ውድቅ በማድረጋቸው የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡

2ኛን ጭብጥ በሚመለከት፡- አጣሪው ጥቅምት 21 ቀን 2001 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ ሽኚነት በ24/10/2000 ዓ/ም የተዘጋጀ ቃለጉባኤ /ሪፖርት / ለሥር የመ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ሪፖርቱም መሠረት ያደረገው ቀደም ሲል ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ የማጣራቱ ሥራ ሰኔ 24 ቀን 1998 ዓ.ም የተደረገውን የሽምግልና ስምምነት መሠረት ያደረገ መሆን እንዳለበት በገለፀው መሠረት ነው ብሏል፡፡

ይህ ችሎትም እንደተረዳው በ24/10/98 ዓ/ም በተደረገው የሽምግልና ስምምነት መሠረት አጣሪው የማጣራቱን ሥራ አከናውኗል፡፡ የማጣራቱ ሥራም የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች ያቀረቡአቸውን ማስረጃዎች ጭምር በመመዘን የተሰራ ስለመሆኑ ሪፖርቱ ያመለክታል፡፡

ለድርጅቱ ሥራ በብድር የተገዙና ዕዳቸው ተከፍሎ ያልተጠናቀቁ ቋሚ ዕቃዎችን በሚመለከትም እስከ ሽምግልና ስምምነት ድረስ መከፈሉ በማስረጃ የተረጋገጠ ተጠሪው ባዋጡት ድርሻ መጠን ተሰልቶ ገንዘብ እንዲሠጣቸው በብድር ተገዝቶ ክፍያው የተጠናቀቀው ፎቶ ሜትር የተባለው የህክምና መሣሪያ ክፍያው የተጠናቀቀው የሽምግልና ስምምነት ከተደረገበት ቀን በፊት መሆኑ በመረጋገጡ ለተጠሪው ባዋጡት መጠን ድርሻቸው እንዲሰጥ የተወሰነ ሲሆን ሌሎች ዕቃዎችን በሚመለከት የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች በ10/6/99 ዓ.ም የተፈራረሙበት ደረሰኝ ከተጠሪው በኩል በመቅረቡ ተጠሪው ባዋጡት የገንዘብ መጠን ተሰልቶ ድርሻቸው እንዲከፈል ተወስኗል፡፡ ያሁን አመልካችም እነዚህን በ10/6/99 ዓ/ም በተደረገው ውል የተዘረዘሩትን ንብረቶች እንዲያስቀሩ ተደርጓል፡፡

የቤት ኪራይም ቢሆን የአጣሪው ሪፖርት እንደሚያመለክተው ኪራይ ከ23/4/98 እስከ 23/4/99 ድረስ ብር 39,000 የተከፈለ ሲሆን ተጠሪው ከሰኔ 24 ቀን 1998 ጀምረው ከድርጅቱ ስለተሠናበቱ ከሐምሌ 1998 - ታህሣሥ 99 ዓ.ም ያለው የ6 ወራት ታስቦ ባዋጡት መጠን ድርሻቸውን አመልካች እንዲከፈሉ ሲደረግ ይህም ክሊኒክ ቁጥር 1 የተባለውን የሚመለከት ነው፡፡ ቁጥር 2 የተባለውን ክሊኒክ በሚመለከት ደግሞ ከመስከረም 19 ቀን 1998 ዓ/ም እስከ መስከረም 19 ቀን 1999 ድረስ የ12 ወር ብር 24,000 የቤት ኪራይ የተከፈለ ሲሆን ከአመልካች ጋር የተገለገሉበት እስከ 24/10/1998 ዓ/ም በመሆኑ ሐምሌና ነሐሴ 1998 የ2 ወር በቅድሚያ የተከፈለ በወር በብር 2000 ሂሣብ ተጠሪው ባዋጡት የገንዘብ መጠን ተሰልቶ ድርሻቸውን አመልካች እንዲከፈሉ መወሰኑን ሪፖርቱ ያመለክታል፡፡ ለዚሁ ለቁጥር 2 ክሊኒክ ተጨማሪ ግንባታ ቅድመ ክፍያ ብር 30,000 እንደተከፈለ ተቆጥሮ ከመስረከም 19 ቀን 1998 - ሰኔ 24 ቀን 1999 ድረስ ለ9 ወራት አመልካችና ተጠሪ በጋራ የተጠቀሙበት ስለሆነ የ51 ወራት በወር በብር 500 ሂሣብ ተጠሪው ባዋጡት መጠን ድርሻቸውን እንዲያገኙ ተብሏል፡፡

ደመወዝን በሚመለከት አጣሪው ከመቼ ጀምሮ መከፈል እንዳለበት በግልጽ የተቀመጠ ነገር የግራ ቀኙ አከራካሪዎች ባለማቅረባቸው የተነሣ አመልካች ድርጅቱ ሥራውን ከጀመረበት ቀን አንስቶ ከ2 ወር በኋላ መሆን አለበት ያሉትን አጣሪው በመቀበልና ድርጅቱ ሥራ የጀመረው 17/4/1999 በመሆኑ ከየካቲት 18 ቀን 1997 — 24/10/98 ድረስ የ16 ወራት ደመወዝ ማናቸውም የመንግስት ግብር ተቀንሶና ቀደም ሲል ተጠሪው በብድር የወሰዱት ብር 37,000 ተቀናሽ ተደርጐ የሚደርሣቸውን ድርሻ አመልካች እንዲከፍሉ በሚል በሪፖርቱ ገልጿል፡፡

እንግዲህ እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ልዩ ልዩ ክፍያዎች ናቸው ተጠቃልለው ብር 83,081.04 ሳንቲም የሆኑት አጣሪው በዚህ ዓይነት በጥልቀት የቀረቡለትን ማስረጃዎች በመመርመር አግባብነት ያላቸውን በመቀበልና አግባብነት የሌላቸውን በመጣል የተጠቀሰውን ገንዘብ የሰበር አመልካች እንዲከፍሉ በሪፖርት የገለፀውና የሥር ፍ/ቤቶች በየደረጃው የቀረበላቸውን ጉዳይ በመመርመር ገንዘቡን አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የወሰኑት፡፡

አመልካች ብር 60,000 በ24/10/98 ዓ/ም በተደረገ ስምምነት መክፈላቸውን በመግለጽ ያቀረቡት የመከራከሪያ ሀሣብም ቢሆን ብር 60,000 / ስልሳ ሺህ / የተከፈለው ካሣ በሚል ስለሆነና በዚሁ ስምምነት ሌሎች ሂሣቦች ለወደፊት ተሰልቶ የሚቀርቡና ክፍያ የሚፈፀምባቸው መሆኑ የተገለፀ በመሆኑ በስሌቱ መሠረት እንዲከፍሉ የተጠየቁትን ገንዘብ መክፈል አይገባኝም ማለታቸው ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

በሌላ በኩል የማህበሩን ዕዳ በሚመለከት ምንም ሳይባል ታልፏል ያሉትም ቢሆን የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች ሰኔ 24 ቀን 1998 ዓ/ም በተፈራረሙት ቃለ ጉባኤ ገጽ 6 በቁጥር "7 ድርጅቱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ይህ ውል እስከ ተደረገበት እለት ድረስ በድርጅቱ ላይ ያለውን ዕዳ በተመለከተ ድርጅቱን በማስቀረት ይዘው የሚጓዙት አመልካች በሚያቀርቡትና በተጠሪው "ሼር" ምትክ በሚገባው ግለሰብ የሚሸፈን ይሆናል" ተብሏል፡፡ በዚህ መልክ ስምምነት ላይ የተደረሰ ከሆነ ደግሞ እንደገና አመልካች ተጠሪው ለማህበሩ ዕዳ ተጠያቂ ሊሆኑ ይገባል ያሉት ከተፈረመው ስምምነት ጋር የሚጋጭ ይሆናል፡፡

የማህበሩን መፍረስ በሚመለከት አመልካች ባቀረቡት ክርክር ተጠሪ ድርሻቸውን ይዘው ከማህበሩ የወጡ በመሆናቸው በተጠሪው ጥያቄ መነሻ ማህበሩ ሊፈርስ አይገባም ካሉ በኋላ

የማህበሩ አባላት ከሁለት በታች በመሆኑ እንዲፈርስ ጠይቀዋል የሥር ፍ/ቤትም ማህበሩ እንዲፈርስ የወሰነው ከዚህ በላይ በተጠቀሰው የክርክር ሂሣብ መነሻ ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ የመሠረቱት ማህበር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሲሆን ማህበሩ ሊመሠረት የሚችለው ደግሞ በንግድ ህግ አንቀጽ 510/2/ እንደተጠቀሰው ማህበርተኛው ከሁለት ያላነሠና ከአምሣ ያልበለጠ ከሆነ ነው፡፡

በዚህ በተጠቀሰው ማህበር ደግሞ አባላቱ አመልካችና ተጠሪ ብቻ ሲሆኑ ተጠሪው ከማህበሩ ከተሠናበቱ አመልካች ብቻ ይቀራሉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በህጉ ከተጠቀሰው አነስተኛ ቁጥር በታች በመሆኑ መፍረሱ የግድ ነው፡፡

በመሆኑም የሂሣብ አጣሪ ያቀረበውን ሪፖርት መነሻ በማድረግ የሥር የመ/ደ/ፍ/ቤት ከውሣኔው በፊት ተጠሪ የተቀበሉትን ብር 60,000/ስድሳ ሺህ/ እና በሂሣብ አጣሪ ተሠልቶ የቀረበውን ብር 83,081.04 /ሰማንያ ሶስት ሺህ ሰማንያ አንድ ከዜሮ አራት ሳንቲም/ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉና የንግድ ማህበሩም እንዲፈርስ የሰጠውን ውሣኔ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ያፀናው በአግባቡ ስለሆነ በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የሥር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በኮ/ቁ 26095 በቀን 01/7/2001 ዓ/ም በዋለው ችሎት እንዲሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 78493 በቀን 10/03/2003 በዋለው ችሎት የሰጡት ፍርዶች ፀንተዋል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ ቀደም ሲል ከከፈሉት ብር 60,000/ስድሳ ሺህ/ በተጨማሪ ብር 83,081.04/ሰማንያ ሶስት ሺህ ሰማንያ አንድ ከዜሮ አራት ሳንቲም/ እንዲከፍሉ የተወሰነባቸው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ አመልካችና ተጠሪ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ ይሁን፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 49295

መጋቢት 22 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ነ/ፈጅ ናሆም ሽዋንግዛው ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- 1- የቻይና ዋንቦ ኢንጂሪንግ ኮርፖሬሽን ጠበቃ ዱቺ ፈለቀ ቀረቡ

2- ታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበር ጠበቃ መኮንን ሽፈራው ቀረቡ

የሰ/መ/ቁጥር 49321 የሆነ መዝገብ ከዚህ መዝገብ ጋር ተጣምሮ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመድን ውልን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ በሰ/መ/ቁጥር 49295 በአመልካች በ2ኛ ተጠሪና በአቶ ዮናስ ተስፋዬ ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በአሁኑ አመልካች የመድን ዋስትና የተሰጠው የ1ኛ ተጠሪ ኤሌክትሪክ ትራንስፎርመር ንብረትነቱ የአቶ ዮናስ ተስፋዬ በሆነ ተሽከርካሪ በአሁኑ 2ኛ ተጠሪ አስጫኝነት ከጅቡቲ ወደብ ተጭኖ ወደ ደብረ ብርሃን ሲሄድ መኪናው የመገልበጥ አደጋ ደርሶበት በትራንስፎርመሩ ላይ ከባድ ጉዳት መደረሱን ገልፆ የአሁኑ አመልካች በመድን ውሉ መሠረት የአሁኑ ሁለተኛ ተጠሪ ደግሞ ወኪል ሁኖ በማስጫኑ የስር ሶስተኛ ተከሣሽ የነበሩት ግለሰብ /አቶ ዮናስ ተስፋዬ/ ደግሞ አጓዥ በመሆኑ ኃላፊነት እንደአለባቸው ጠቅሶ ለደረሰው ጉዳት ብር 2,223,293.80 /ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃያ ሶስት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና ሶስት ብር ከሰማኒያ ሳንቲም/ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በስር ከሣሽ በኩል ለቀረበበት ክስ በሰጠው መከላከያ መልስ ፡- ከከሣሹ ጋር የመሰረተው የመድን ዋስትና ውል የባህር መድን ዋስትና ውል በመሆኑ ጉዳዩ የሚገዛው በባሕር ሕጉ እንጂ በንግድ ሕጉ አለመሆኑን በትራንስፎርመሩ ላይ ጉዳት የደረሰው ተሽከርካሪው መጫን ከሚችለው አቅም በላይ በመጫኑ ይህም የተደረገው በከሣሹ ወኪል በሆነው ታብትራ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በመሆኑና ወኪል ያደረገው ወካዩ እንዳደረገው ስለሚቆጠር እንዲሁም በመድን ውሉ ላይ በግልፅ መድን ሰጭውን ከኃላፊነት ነፃ የሚያደርገው እንደሆነ ገልጾ ኃላፊነት

የለብኝም በንግድ ሕጉ መሠረትም የእምቢታ ማስታወቂያ በሰባት ቀናት ውስጥ ለመድን ሰጪው ያለመገለፁ የመዳረግ መብቱን ያሳጣው በመሆኑም መድን ሰጪው ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን እንዲያሳይ እንዲሁም የኃላፊነት መጠኑም ቢሆን የተጋነነ እና በተገቢው ማስረጃ ያልተደገፈ መጠኑን ጠቀሶ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ በስር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተከሣሽ የነበረው ታብትራ ኃላ.የተ.የግል ማህበር በበኩሉ ከተከሣሾች ጋር ተጣምሮ መከሰስ የሌለበት መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስቶ የተከራከረ ሲሆን በኃላፊነት ረገድ ደግሞ በተሰጠው የውክልና ስልጣን መሠረት በውሉና በሕጉ አግባብ ግዴታውን የተወጣ መሆኑን ገልጾ ክሱ ውደቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ሶስተኛ ተከሣሽ የነበሩት ግለሰብ /አቶ ዮናስ ተስፋዬ / በበኩላቸው ከአንድ አንጓዥ በሚጠበቅ መልኩ ትራንስፎርመሩን ጭነው ለስር ከሣሽ ያስረከቡ መሆኑንና በጊዜውም በሕጉ አግባብ መሠረት የእቢታ ማስታወቂያ /Protest/ ሳይፃፍላቸው ከስምንት ወራት በሁዋላ ጉዳቱ ደርሷል በማለት ጥያቄ መቅረቡ ሕጋዊ አለመሆኑን ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በሁዋላ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የባሕር ሕጉ መሆኑን ጠቅሶ የኢትዮጵያ መድን ድርጅትንና አቶ ዮናስ ተስፋዬን ከኃላፊነት ነጻ ሲያደረጋቸው ታብታራ ኃ/የተ/የግል ማህበርን ለጉዳዩ ኃላፊ በማድረግ በከሣሽ የተጠየቀውን ገንዘብ ያህል እንዲከፍል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የስር ከሣሽ የኢትዮጵያ መድን ድርጅትና አቶ ዮናስ ተስፋዬ ከኃላፊነት ነፃ መባላቸው ያለአግባብ ነው በማለት ታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበር ደግሞ ኃላፊነት የለብኝም በማለት በየፊናቸው ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ መዛግብቱ ተጣምረው ታይተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሕግ የንግድ ሕጉ ሁኖ የስር ፍርድ ቤት የኢትዮጵያ መድን ድርጅትን ከኃላፊነት ነፃ መደረጉ ያላግባብ ነው ታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበር ከመድን ሰጪና ከአቶ ዮናስ ተስፋዬ ጋር ተጣምሮ መከሰሱም ያላግባብ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሽሮ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ለክሱ መሠረት የሆነውን ገንዘብ ለከሣሽ /ቻይና ወንቦ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን /እንዲከፍል መድን ሰጪው ገንዘቡን ለከሣሽ ከፍሎ የስር ሁለተኛ እና ሶስተኛ ተከሣሾችን የመክሰስ መብቱ የተጠበቀ መሆኑ ተገልጾ ተወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ሲሆን የሰበር አቤቱታ የቀረበው በሁለት መዛግብት ነው፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 49295 አመልካች የሆነው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ሲሆን የሰበር ተጠሪ የሆኑት የስር ከሣሽና የስር ሁለተኛ ተከሣሽ ናቸው፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 49321 አመልካች የሆነው የስር ከሣሽ ሲሆን የሰበር ተጠሪ የሆነው ደግሞ የስር ሁለተኛ ተከሣሽ የነበረው ታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበር ነው፡፡

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ነገረ ፈጅ መስከረም 11 ቀን 2002 ዓ/ም በጻፋት ስምንት ገፅ የሰበር አቤቱታ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለ የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ፡- ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የባህር ሕግ ሁኖ እያለ ከውሉ መሠረታዊ ይዘት ውጪ የንግድ ሕጉ ተፈፃሚነት አለው መባሉ ያላግባብ ከመሆኑም በተጨማሪ መድን ድርጅቱ የስር ሁለተኛና ሶስተኛ ተከሣሾችን በመክሰስ የመዳረግ መብቱን ሊያስከብር ይችላል ተብሎ መወሰኑ ከስነ ሥርዓት ውጪ ከመሆኑም በላይ በውጤት ደረጃ የመድን ድርጅቱን መብት ሊያስጠብቅ የሚችልበት ከሕግም ሆነ ከውል የመነጨ ምክንያት የሌለ መሆኑን ጠቅሰው ውሣኔው ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የቀረበው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው የባህር ሕጉ ሳይሆን የንግድ ሕጉ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለመመረር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ



www.chilot.me

የተደረገ ሲሆን ተጠሪ የሆኑት የስር ከሣሽና የስር ሁለተኛ ተከሣሽ ቀርበው የፅሑፍ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የስር ከሣሽ የሆነው ድርጅት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ መስረከረም 18 ቀን 2002 የተፃፈ ሁኖ መሰረታዊ ይዘቱ የስር ሁለተኛ ተከሣሽ የነበረው ድርጅት /ታቭትራ ኃ/የተ/የግል ማህበር / ከስር ተከሣሾች ጋር ተጣምሮ መከሰስ የለበትም ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ያለግባብ ነው የሚል ሲሆን ይኸው አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ በመታዘዙም ግራ ቀኙ የጽሑፍና የቃል ክርክር እንዲያደርጉ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች እንዲሁም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 37799 ከሰጠው የሕግ ትርጉም ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

1. <u>በኢትዮጵያ መድን ድርጅትና በቻይና ዋንቦ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን መካከል ያለውን የመድን ዋስትና በተመለከተ ተፈፃሚነት ስላለው ሕግ፡-</u>

መድን ሰጪ የሆነው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ከቻይና ዋንቦ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ጋር የመድን ውል ያለው ስለመሆኑ ሳይክድ ጉዳዩ ሊገዛ የሚገባበትን ሕግ ለይቶ ክርክር አቅርቧል፡፡ በመድን ሰጪ በኩል ለጉዳዩ አግባብነት አለው ተብሎ የተጠቀሰው ሕግ የባህር ሕጉ ነው፡፡ መድን ገቢ የሆነው የቻይና ዋንቦ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ደግሞ በንግድ ሕጉ ጉዳዩ ሊገዛ የሚችል ነው በማለት ምክንያቶችን ጠቅሷል፡፡ ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ ያደረጉትን የመድን ውል እንደተመለከተው የባህር ጉዞ ፖሊስ የሚባል መሆኑን ከሰነዱ የተገነዘበ ሲሆን በኢንሹራንስ ውል ላይ በተራ ቁጥር 1.4 እስከ 7 ከተዘረዘሩት የአደጋ መንስኤዎች በስተቀር የጉዞው ሽፋኑ እቃው ከሚመጣበት የቻይና ሀገር እስከ እቃው የሚደርስበት የኢትዮጵያ ግዛት ደብረ ብርሃን ድረስ ለሚደርስ ማንኛውም ጉዳት ስለመሆኑ በውሉ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ጉዳይ ደግሞ እቃው በሰሌዳ ቁጥር 3-26454 ኢት ተሳቢ ቁጥር 3-02979 ኢት የጭነት መኪና ከጅቡቲ ወደብ ተጭኖ በመሬት ሲጓጓዝ በአፋር ብሔራዊ ክልል ኤሊዳር ከተማ መኪናው ተገልብጦ የመድን ዋስትና በተገባለት እቃ ላይ ጉዳት መድረሱ ሲሆን የመድን ውሉ በአንቀጽ 19 ስር ኢንሹራንሱ የሚገዛው በኢትዮጵያ ሕግና ልማድ ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የመድን ውሉ ይዘት ከላይ በተመለከተው መልኩ ስለመሆኑ ግልፅ ማስተባበያ ክርክር ሳያቀርብ የውሉን ርዕስና የባህር ኢንሹራንስ መሰረታዊ ባህሪያትን እንዲሁም የዓለም አቀፍ ልምድን መሠረት አድርጎ ክርክር አቅርቧል፡፡ በእርግጥ የባህር ኢንሹራንስ መሠረታዊ ባህርይ ሲታይ ኢንሹራንሱ የሚገባው በባህር ላይ ለሚደርስ አደጋ ላይ፡፡ የባህር ሕጉ አንቀፅ 292/1/ ሲታይም ግባቸው ሕጋዊ ለሆነው የገንዘብ ግምት ዋጋ ላላቸውና ሊደርስ የሚችል የባህር አደጋ ለሚያስፈራቸው ነገሮች ሁሉ ኢንሹራንስ ሊደረግላቸው እንደሚችል የተደነገገ ሲሆን የዚሁ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ በባህር አደጋ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ካልሆነ በቀር ማንም ሰው በኢንሹራንስ የሚገኘውን ጥቅም ለመጠየቅ አይችልም በማለት ይገልፃል፡፡ የባህር ሕጉ ስለኢንሹራንስ ውል የተደነገጉትን ድንጋጌዎች የሚያስቀምጠው አንቀጽ ሰባት ምዕራፍ አንድ በቁጥር 288 ስር ዋናው ዓላማ በባህር የሚደርሰውን አደጋ ወይም ከዚሁ ጋር ተጨማሪ የሆኑትን አደጋዎችም ለማረጋገጥ ቢሆን እንኳ ማንኛውም የኢንሹራንስ ውል በዚሁ ክፍል በተደነገጉት ውሣኔዎች ይመራል በማለት ደንግጓል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለው የባህር ሕጉ ተፈፃሚነት የሚኖረው በባህር አደጋ ሲደርስ ስለመሆኑ ነው፡፡ የባህር አደጋ የሚባለው ደግሞ በባህር ላይ ዘረፋ እና የመሳሰሉ ሁነው የባህር ክልል ውስጥ የሚደርሱ አደጋዎች ናቸው፡፡ የባህር ሕጉ ከመግቢያው ጀምሮ ሲታይ የባህርን

ጉዳይ የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚገዛ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት የባህር ሕጉ ድንጋጌዎችና የሕጉ መግቢያ ይዘትና መንፈስ ሲታይ የባህር ሕግ የተፈፃሚነት አድማሱ የባህርን ጉዳይ ለሚመለከቱ ጉዳዮች ነው፡፡ ለክርክሩ አግባብነት ያላቸው የባህር ሕጉ ድንጋጌዎች ይዘታቸውና መንፈሳቸው ከላይ የተመለከተው ሲሆን የንግድ ሕጉ አንቀጽ 655 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ሲታይም ለጉዳዩ ጭብጥ አወሳሰን ምላሽ የሚሠጥ ሁኖ ይገኛል፡፡ ይህ ድንጋጌ ስለኢንሹራንስ የተመለከቱት የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች የተፈፃሚነት ወሰንን የሚያሳይ ሲሆን በንዑስ ቁጥር አንድ በንግድ ሕጉ ስለኢንሹራንስ የሚደነግገው አንቀጽ ሶስት ተፈፃሚ የሚሆነው በመሬት ፣ በወንዝና በአየር ለሚደርሱ አደጋዎች መሆኑን ሲጠቅስ የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር ሁለት ደግሞ በንግድ ሕጉ ስለኢንሹራንስ የተመለከተው አንቀጽ በባሕር ሕግ የሚተዳደረውን የባህር ኢንሹራንስን የማይመለከት ስለመሆኑ አስገዳጅነት ባለው መልኩ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው የውሉ አርዕት የባህር ኢንሹራንስ ነው ተብሎ በተዋዋይ ወገኖች መገለጹ ውሉ በባህር ሕጉ እንዲገዛ ፍላጎት ስላላቸው በዚሁ መልኩ ውሉ መገዛት ያለበት ሳይሆን የውሉ ይዘትና አደጋው የደረሰበት ቦታ በራሱ ውሉ የሚገዛበትን የሕግ አግባብ ለመለየት የሚያስችል መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የተዋዋይ ወገኖች ፍላጎት ከውሉ አጠቃላይ ይዘት ታይቶ ውላቸው የሚገዛበት ሕግ መለየቱ የውል አተረጓጎም ደንቦች የግድ የሚሉት ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይም የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ለቻይና ዋንቦ ኮርፖሬሽን የሠጠው የመድን ውል በአርስት ደረጃ የባህር ጉዞ ፖሊሲ /Marine insurance / በሚል የተጠቀሰ ቢሆንም የውሉ አንቀጽ 1 እና 19 ይዘት ሲታይ ግን በውሉ በግልፅ ከተገለሉት አደጋዎች ውጪ በመሬት ላይ ለሚደርሱ ሌሎች አደጋዎች ሁሉ መድኑ የተገባ በመሆኑ በባህር ሕጉ ቁጥር 288 ፣ 292 እና በመግቢያው ላይ እንዲሁም በን/ሕ/ቁጥር 655 ድንጋጌ መንፈስ እና ይዘት ሲታይ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው ሕግ የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ ሁኖ ስለአገኘነው በዚህ ረገድ የቀረበው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ክርክር ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የሰጠው የሕግ ትርጉም መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

2. **ኃላፊነትን በተመለከተ፡-** የቻይና ዋንቦ ኮርፖሬሽን የኢትዮጵያ መድን ድርጅትን ሊከስ የቻለው በመድን ውሉ መሠረት ሲሆን ታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበርን ደግሞ የእቃ ማጓጓዝ ውልን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በቻይና ዋንቦ ኮርፖሬሽንና በታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበር የተደረገው ውል እቃውን በማጓጓዝ ደብረ ብርሃን ከተማ ለማድረስ ሲሆን በውሉ አንቀጽ 3.6 ላይ እቃው ሲጓጓዝ በመንገድ ላይ ለሚደርስበት ማንኛውም ጉዳት ታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበር ኃላፊነት ለመውሰድ ስለመሆኑ ቻይና ዋንቦ በዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው ክርክር ላይ ጠቅሷል፡፡ ታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበር ባቀረበው ክርክርም ከቻይና ዋንቦ ጋር የመጓጓዣ ውል መፈራረሙን ሳይክድ ስራውን በስር ፍርድ ቤት ሶስተኛ ተከሣሽ ለነበረው ለአቶ ዮናስ ተስፋዬ የሰጠ መሆኑን ይህም ግለሰብ በራሱ አሽከርካሪ እቃውን አስጭኖ ሲያመጣ ጉዳቱ የደረሰ መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡ እንግዲህ የቻይና ዋንቦ ኮርፖሬሽን ከታብተራ ኃ/የተ/የግል ማህበር ጋር ያደረገው ስምምነት ሲታይ የትራንዚት አገልግሎትና የትራንስፖርት ስምምነት የሚል ስለመሆኑ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በውሣኔው ላይ ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ግንኙነቱ የሚገዛውም በደንብ ቁጥር 37/1990 ነው፡፡ በዚህ ደንብ አንቀጽ 2/1/ ስር እቃ አስተላላፊ በአገር ውስጥ ወይም በአለም አቀፍ ደረጃ እቃ ተቀባይነት ወይም እቃ ላኪነት በመወከል የጉምሩክ የወደብ ወይም ሌሎች ስርዓቶች አስፈፅሞ ገቢ ወይም የወጪ እቃዎችን ወደብ እንዲገቡ ወይም እንዲወጡ የሚያደርግ ሲሆን እቃን የማጓጓዝና የማስረከብን ስራም እንደሚጨምር ተቀምጧል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ጠቅላላ ይዘት ሲታይም እቃ አስተላላፊው ስራውን የሚያከናውነው እቃ ላኪዎችን ወይም ተቀባዮችን በመወከል ስልጣን



www.chilot.me

መሆኑን የሚያስገነዝብ ቢሆንም በደንቡ አንቀጽ 3/6/ እና 7 ድንጋጌዎች ስር ያሉት ሁኔታዎች ሲታዩ ደግሞ የእቃ መጓጓዝ ተግባሩ እንዴት ሊከናወን እንደሚገባ ያመላክታሉ፡፡ በደንቡ አንቀጽ 3/6/ ድንጋጌ ስር እቃ አስተላላፊ የራሱን የትራንስፖርት አገልግሎት ካለው የእቃ ማጓጓዙን ተግባር የሚያከናውነው እንደ አጓጓዥ ሁኖ እንጂ በውልክና አለመሆኑን በግልፅ ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል ግን የራሱ ትራንስፖርት ከሌለው ወይም ባለእቃው የራሱን ማጓጓዣ ካላቀረበ እቃ አስተላላፊው ማጓጓዣ ተከራይቶ እቃውን እንደሚያጓጉዝ በደንቡ አንቀጽ 3 ንዑስ ቁጥር ሰባት ድንጋጌ ስር ተመልክቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ በአንቀጹ ንኡስ ቁጥር ስድስት እንደተመለከተው የማጓጓዝ ስራውን እንደ አጓጓዥ ሆኖ እንደሚሰራ አያስቀምጥም፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተው እቃ አስተላላፊ ስራውን ሁሉ የሚያከናውነው በውክልና ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበር የማጓጓዝ ተግባሩን ያስፈጸመው በአቶ ዮናስ ተስፋዬ ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ሲሆን ታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበር የማጓጓዝ ተግባሩን ያከናወነው በውክልና ተግባሩ እንጂ ራሱ በሰራው የማጓጓዝ ስራ አይደለም፡፡ እንዲህ ከሆነ ታብትራ ኃላፊነቱ የሚኖረው በደንብ ቁጥር 37/1990 አንቀጽ 12 ስር በተመለከተው ሁኔታ ነው፡፡ በዚሁ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ስር እቃ አስተላለፊ ወይም የመርከብ ወኪል ተግባሩን ባለማከናወኑ ጥፋት ቢፈጽም በተለይም እቃው ቢጠፋበት ቢጎድልበት ወይም እቃውን በወቅቱ ባያስረክብ ተጠያቂ የሚሆን መሆኑ የተቀመጠ ሲሆን የዚሁ ድንጋጌ የእንግሊዝኛው ቅጂም፡ " the Frieght forwarder shall be liable for defaults in the performance of his duties, in particular he shall be liable for loss of or shortage of or damage to the goods or delay in delivery of the goods." የሚል ነው፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የኢትዮጵያ መድን ድርጅትን ለጉዳቱ በመድን ውሉ መሠረት ኃላፊ በማድረግ ካሳውን ለቻይና ዋንቦ ኮርፖሬሽን ከፍሎ ታብትራን ኃ.የተ.ግል ማህበር ወይም አቶ ዮናስ ተስፋዬን በን/ሕ/ቁጥር 683/3/ መሠረት እንዲጠይቅ መብቱን የጠበቀለት መሆኑን ውሣኔው ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ በቻይና ዋንቦ ኮርፖሬሽንና በታብትራ ኃ.የተ.የግል ማህበር መካከል ያለው የእቃ ማጓጓዝ ተግባር የሚፈጸመው በውክልና ግንኙነት /እቃ አስተላላፊነት ነው፡፡/ በዚህ መልኩ ለሚፈፀም ተግባር እቃ አስተላላፊ የሚጠየቀው ደግሞ በደንቡ አንቀጽ 12/2/ ስር በተመለከተው ሁኔታ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት እቃ አስተላላፊ ተግባሩን በጥንቃቄ ማከናወን እንደአለበት የተቀመጠ ሲሆን የጥንቃቄው መለኪያ ሲታይም እቃ አስተላላፊው በገባው ውል ግዴታ መሠረት እቃውን በማጓጓዝ ለባለንብረቱ የማስረከብ ኃላፊነትን የሚሸፍን መሆኑ በድንጋጌው ከሰፈሩት አመላካች ነጥቦች የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ አንድ እቃ አስተላላፊ እቃዎችን አጓጉዞ ለባለንብረቱ ካላስረከበ በሕጉ አግባብ ኃላፊነቱን የሚያስቀሩ ሁኔታዎችን እስካላስረዳ ድረስ ጥፋት እንደፈፀመ የሚቆጠር መሆኑን የተጠቀሰው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ በን/ሕ/ቁጥር 683/3/ ስር ወደ ተመለከተው ድንጋጌ ስንመለስ ደግሞ፡- ሌላ ተቃራኒ የውል ቃል ቢኖርም በክፋት ያደረጉት ካልሆነ በቀር ኢንሹራንስ ሰጪው በኢንሹራንስ ገቢው ወደ ታች የሚቆጠሩ ተወላጆች ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ወኪሎች ፣ ሰራተኞች ወይም ከእርሱ ጋር ዘወትር አብረው በሚኖሩት ሰዎች ላይ ኢንሹራንስ ሠጪው በምትክነት ክስ ለማቅረብ እንደማይችል ተቀምጧል፡፡ የድጋጌው የእንግሊዝኛ ቅጂም "Notwithstanding any provision to the contrary, the insurer may not claim against the ascendants, descendants, agents or employees of the insured person nor against persons living with him, unless such persons have acted maliciously.." በማለት ይደነግጋል፡፡

የዚህ ድንጋጌ አቀራራጽና ይዘት ሲታይ ኢንሹራንስ ሰጪ ክስ ሊያቀርብባቸው የማይቻላቸው ወገኖች ከኢንሹራንስ ገቢው ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያላቸውና ለራሳቸው ጥቅም ሳይሆን ለኢንሹራንስ ገቢው ጥቅም በሚሰሩ ወገኖች ላይ መሆኑን የሚስገነዝብ ነው፡፡ ስለሆነም



www.chilot.me

እነዚህ ወገኖች ከወካዩ ጋር ካላቸው የጠበቀ ግንኙነትና ስራቸውን የሚያከናውኑት ደግሞ ለወካዩ ጥቅም እስከሆነ ድረስ በደንብ ቁጥር 37/90 ስለእቃ አስተላለፊ ከተሰጠው ትርጉም ጋር እኩል ተደርገው ሊወሰዱ የሚገባ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የእቃ አስተላላፊነት ተግባር የሚከናወነው በውክልና ስልጣን መሠረት ቢሆንም እቃ አስተላላፊው ለእራሱ ጥቅም የሚሰራ ነውና፡፡ በመሆኑም እቃ አስተላላፊነት በን/ሕ/ቁጥር 683/3/ ስር "ወኪሎች" በሚል ከተዘረዘሩት ወገኖች ስር ሊካተት የሚችል አይደለም፡፡ በን/ሕቁጥር 683/3/ ስር የተመለከቱት ወገኖች የሚፈፅሙት ተግባር የመድን ሰጪውን በምትክነት እንዲገባና ሃላፊነቱን እንዲወስዱ የሚያደርገው ተግባሩ በክፋት የተደረገ/Have acted maliciously/ መሆኑ ከተረጋገጠ ይህም የጥፋቱ አፈፃፀም መለኪያው በደንብ ቁጥር 37/1990 አንቀጽ 12 ስር ከተመለከተው የወኪሎች ተግባር ጥፋት ጋር ሲነጻጸር የጠበቀ መሆኑን የድንጋጌው አቀራረፀ ያሳያል፡፡ ይኸውም አንድ ድርጊት በክፋት የተፈጸመ ነው የሚባለው ምንም ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖር በአንድ ሰው መብት እና ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ ሆነ ተብሎ ሲፈፀም መሆኑ ታዋቂው የሄኔሪ ብላክስ የሕግ መዝገብ ቃላት "Malicious Act is an intentional, wrongful act performed against another without legal justification ." በማለት ከሰጠው ትርጉም የምንገነዘበው ሲሆን ከደንብ ቁጥር 37/90 አንቀጽ 12 ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጥፋት ደግሞ ከውል አፈጻጸም ጋር ተያይዞ ግዴታ ሳይፈጸም ሲቀር የሚነሳና ኃላፊነት የሚያስከትል፣ ሕጉም ምክንያቶችን አመልካችነት ባለው ሁኔታ የጠቀሰ በመሆኑ ጥፋቱ የሚፈፀመው ሰፋ ባሉ አጋጣሚዎች መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሰው መዝገበ ቃላት ጥፋትን ሲተረጎም "Default is the omission or failure to perform a legal or contractual duty." በማለት ያስቀመጠው ሲሆን ይህም ትርጉም ጥፋቱ ከውል አፈጻጸም ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ነው በማለት የገለፅነውን አባባል የሚያጠናክር ነው በመሆኑም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በን/ሕ/ቁጥር 683/3/ መሠረት ታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበርን ለመጠየቅ ይችላል ብሎ ሲወስን መሰረት ያደረገው ሕግ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 37799 ላይ የእቃ አስተላላፊ በክፋት ለፈጸመው ተግባር ካልሆነ በስተቀር የሚጠየቅበት አግባብ የለውም በማለት የን/ሕ/ቁጥር 683/3/ "ን" መሠረት በማድረግ የሰጠው ትርጉምም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ሕግ መሠረት በማድረግ የተሰጠ ሁኖ ስለአገኘነው በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2/2/ መሠረት መለወጥ ያለበት ነው፡፡

ሌላው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ካሣውን ከፍሎ ታብትራ ኃ/የተ/የግ ማህበርን እንዲጠይቅ ውሣኔ የተሠጠበትን የክርክር ሂደት አግባብነቱን መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው በእነዚህ ወገኖች መካከል የሚነሳው ክርክር የሚገዛው በአዋጅ ቁጥር 37/90 ሲሆን የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ለቻይና ዋንቦ ኮርፖሬሽን በሰጠው የመድን ውል መሠረት በእቃ አስተላላፊው ላይ የሚያቀርበው ክርክር እቃው አቅም በሌለው መጓጓዣ ላይ በመጫኑ ጉዳቱ መድረሱን የሚያሳይ ሲሆን ታብትራ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ደግሞ በክሱ ውስጥ ተሳታፊ የሚሆንበት ወይም በጣምራ የሚከሰስበት አግባብ የሌለ መሆኑን ጠቅሶ በመከራከሩ ይህንኑ የእቃ አስተላላፊ ክርክር የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት እንዳለ ተቀብሎ በስር ፍርድ ቤት የክሱ አመሰራረትም ሆነ የክርክሩ አመራር ስነ ሥርዓቱን የተከተለ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ ታብትራ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው መልስም የመከራከር መብቱ መጣበቡን ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ተገንዝቦ የሰጠው ውሣኔ ተገቢ መሆኑንና በጭብጥ አመሰራረትም ሆነ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ካለው ድንጋጌ አንጻር አንድ ተከሣሽ ሌላ ተከሣሽ ለሰጠው መከራከሪያ መልሱን የሚሰጥበት አግባብ በኢትዮጵያ የሙግት አመራር ሥርዓት ውስጥ የሌለ መሆኑን ዘርዝሮ ተከራክሯል፡፡ እኛም እንደተመለከትነው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በቻይና ዋንቦ ኮርፖሬሽን ላይ የሚያነሳው ክርክር የመድን ውሉንና የንግድ ሕጉን መሠረት ያደረገ ቢሆንም ቻይና ዋንቦ ከእቃ

አስተላላፊው ጋር የሚያቀርበውን ክርክር ደግሞ መድን ድርጅቱ በውሉ በሚያገኘው የመዳረግ መብት በእቃ አስተላላፊው ላይ ከማቅረብ የሚከለክለው ሕግ የለም፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም መድን ድርጅቱ እቃ አስተላላፊውንና አጓዡን የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀለት ነው ያለው በእነዚህ ወገኖች የቻይና ዋንቦ ኮርፖሬሽን ሊያነሳ የሚችለውን ክርክር ሁኖ እነዚህ ወገኖች ደግሞ ለመድን ድርጅቱ ጥያቄ ኃላፊነት የሌለባቸው መሆኑን የሚያሳይ ክርክር ሊያቀርቡ የሚችሉት በቻይና ዋንቦ ላይ ወይም ታብትራ ከአቶ ዮናስ ተስፋዬ ላይ ፣ ወይም ዮናስ ተስፋዬ ደግሞ በታብትራ ላይ ሊያነሱ የሚችሉትን ክርክር ነው፡፡ ለጉዳዩ አወሳሰን ደግሞ ከመድን ውሉ ጀምሮ ሁሉም ወገኖች በመካከላቸው ያደረጉት ስምምነት አግባብነት የሚኖረው ይሆናል፡፡ የመዳረግ መብት አጠቃላይ ፅንሰ ሀሣብ ሲታይም የመጨረሻ ኃላፊነት ያለውን ወገን በመለየት ካሣውን የከፈለው ወገን ገንዘቡ እንዲተካለት ማድረግ ነው ፡፡ ፍርድ ቤቶች በመድን ውሉ መሠረት ኃላፊነት ያለው ወገን ኃላፊ የማሆንበትን ምክንያት ገልፆ የሚከራከር ከሆነ ይህንኑ እንዲያስረዳ እድል መስጠት አለባቸው፡፡ እንዲሁም በክርክሩ ውስጥ የሚገባ ወገን ካለና ኃላፊነቱ የማን እንደሆነ እንዲለይ ከሣሽ ጥያቄ ከአቀረበም ይህንኑ በተገቢው መንገድ በመመራት ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ይገባቸዋል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁጥር 36/5/ ፣ 39 ፣ 40 ፣ እና 43 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስም ይህንኑ የሚያሳይ ነው፡፡ ግልፅ የሆነ ክርክር ቀርቦ ባለበት ሁኔታ እነዚህ ድንጋጌዎች በአግባቡ ሳይተገበሩ የሚሰጠው ውሣኔ በክርክር አመራር ስርዓት ተቀባይነት አለው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የመድን ውሉ መኖሩን ሳይክድ ኃለፊነት የሌለበት መሆኑን ጠቅሶ የሚከራከረው መድን የተገባለት እቃ ላይ ጉዳት የደረሰው አቅም በሌለው መኪና ላይ በመጫኑ ምክንያት ነው የሚል ክርክር ሲሆን ይኸው ተግባር እቃ አስተላላፊውን በደንብ ቁጥር 37/1990 አንቀፅ 12/2/ መሠረት ሊያስጠይቅ የሚችል መሆን ያለመሆኑ ፣እቃ አስተላላፊው አጓዡ /አቶ ዮናስ/ ኃላፊነት ያለው መሆን ያለመሆኑን ሊያስረዳ የሚችል መሆን ያለመሆኑ አጓዥ የተባሉት አቶ ዮናስ ተስፋዬ ለጉዳቱ የማይጠየቁበት የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ክርክር ያለ መሆን ያለመሆኑ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ጭብጦች መለየት ያለባቸው የኢትየጵያ መድን ድርጅት ካሣውን ለቻይና ዋንቦ ኮርፖሬሽን ከከፈለ በኂላ ሳይሆን አሁን በቀረበው ክርክር መሆኑን የክርክሩ ይዘት ያስገነዝባል፡፡ የታብትራ ኃ/የተየግል ማህበር ጠበቃ አንድ ተከሣሽ ላቀረበው ክርክር ሌላው ተከሣሽ መልስ እንዲሰጥበት የሚያስችል የክርክር ስርዓት በኢትዮጵያ የሙግት አመራር ሥርዓት የለም፣ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሠጠው ውሣኔም ይህንኑ ያገናዘበ ነው በማለት ለሰበር ችሎት በሰጡት መልስ ላይ ተከራክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ የፍትሓ ብሔር ክርክር ላይ በክርክር አመራር እና እውነትን በማውጣት ረገድ የፍርድ ቤት ሚና ሲታይ እጅጉን ከፍተኛ መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቀጥር 39 ፣ 40 ፣ 91 ፣ 136 ፣ 241 ፣ 246 ፣ 247 ፣ 248 ፣ 256 ፣ 265 ፣266፣ 272 እና ሌሎች በርካታ በዋቢነት የሚጠቀሱ ድንጋጌዎች ያሉ በመሆኑ አንድ ተከሣሽ በሚያቀርበው ክርክር ላይ ሌላው ተከሣሽ መልስ /ክርክር / እንዲያቀርብበት ማድረግ ሥርዓቱ የሚደግፈው አይደለም ሊባል የሚችል አይሆንም፡፡ ዋናውና ቁልፉ ነገር የተከራከሪ ወገኖች የመከራከር መብት መጠበቅ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የታብትራ ጠበቃ ያቀረቡትን ክርክር የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤት የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ባቀረበው ክርክር ታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበርም ሆነ አቶ ዮናስ ተስፋዬ ክርክር እንዲያቀርቡ አድርጎ ሙግቱን አለመመራቱን በማረም ጉዳዩን እንደገና እንዲመለከተው ማድረግ ሲገባው መድን ድርጅቱን ከወዲሁ ለጉዳቱ ኃላፊ በማድረግ ሌላ ክስ አቅርቦ መብቱን ሊያስከብር ይችላል በማለት የሰጠው ውሣኔ የመድን ድርጅቱ የመድን ውሉንም ሆነ በደንብ ቁጥር 37/1990 እንዲሁም አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት የሚያቀርበውን ክርክር ከወዲሁ ዋጋ ሊያሳጣ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩን ከክርክሩ ይዘት

ተገዝበናል፡፡ በዚህም ምክንያት ኃላፊነቱን በተመለከተ የተሰጠው ውሣኔ የክርክር አመራር ስርዓቱ በአግባቡ ሳይከናወን የተሰጠ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ ጉዳዩ ሲጠቃለልም ከላይ በተመለከቱት ክርክር ምክንያቶች መሠረት በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ ተሽሮ ክርክሩ እንደገና መመራት ያለበት ሁኖ ስለተገኘ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1- በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 39888 ሰኔ 25 ቀን 2001 ዓ/ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2- የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔም ተገቢነት የለውም ብለናል፡፡
3- ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 37799 ላይ በደንብ ቁጥር 37/1990 መሠረት በራሱ ማንንዣ እቃ የማያስተላላፍ ሰው ለመድን ሰጪ ሊጠይቅ የሚችለው በን/ሕ/ቁጥር 683/3/ መሠረት የክፋት ተግባር የፈፀመ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው በማለት የሰጠው የህግ ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2/2/ መሠረት ተለውጦ እንደዚህ አይነት ግንኙነት ሊገዛ የሚገባው በደንብ ቁጥር 37/1990 አንቀጽ 12/2/ በተመለከተው ሁኔታ ነው ብለናል፡፡
4- የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደገና ተመልክቶ የስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሣሾች/ታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ዮናስ ተስፋዬ /በኢትዮጵያ መድን ድርጅት በቀረበው ክርክር ተገቢ ነው የሚሉትን ክርክር እንዲያቀርቡ አድርጎ እንዲሁም እነዚህ ተከሣሾች እርስ በራሳቸው የሚያቀርቡት ክርክር ካለም በመቀበል እና ማስረጃ ካላቸውም ከሰማ በሁዋላ ጉዳዩን ከደንብ ቁጥር 37/1990 አንቀጽ 12 እንዲሁም አቶ ዮናስ ተስፋዬ ከታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበር ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚገዛውን ውልና ሕግ በመለየት ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343/1/ መሠረት ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡
5- በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሰባት ዳኞች ፊርማ አለበት



www.chilot.me

# አምሯዊ ንብረት



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 57179

የካቲት 22 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች** ፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- ኢትዮ ሴራሚክ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - አልቀረቡም

**ተጠሪዎች** ፡- 1. የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ነገረ ፈጅ አቶ አጥናፉ ደምሴ ቀረቡ

2. ኦቮርጊጋ ቴክኖሎጅ ሊሚትድ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች አንደኛ ተጠሪ በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን ይግባኝ በማየት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ አንደኛ ተጠሪ ሁለተኛ ተጠሪ ያቀረበውን የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥያቄ በመቀበል ሁለተኛ ተጠሪ በአራት ማዕዘን ውስጥ ዙሪያውን በአስር ኮከቦች የተከበበ " ETHIO CEMENT " የሚለው የንግድ ምልክት ለመመዝገብ የሰጠው ውሣኔ ነው፡፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ ዓለም አቀፍ ምድብ ያለው የሲሚንቶ ምርት ግልጋሎቱ በአራት ማዕዘን ውስጥ ዙሪያውን በአስር ኮከቦች የተከበበና መካከሉ " ETHIO CEMENT " የሚል ፅሑፍ ያለበት የንግድ ምልክት በአንደኛው ተጠሪ እንዲመዘገብለት ቁጥሩ 1912 በሆነ ማመልከቻ ጠይቋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ የንግድ ምልክቱን ከመመዝገቡ በፊት መቃወሚያ የሚያቀርብ ወገን ካለ መቃወሚያውን እንዲያቀርብ መጋቢት 15 ቀን 2000 ዓ.ም. በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ማስታወቂያ አውጥቷል፡፡ አመልካች "ኢትዮ ሲሚንቶ" በሚለው የንግድ ሥም የኢንቨስትመንት ፈቃድ በማውጣት የሲሚንቶ ፋብሪካ ለማቋቋም ጥረት እያደረገ መሆኑን በመግለፅ ሁለተኛ ተጠሪ እንዲመዘገብለት ያቀረበው የንግድ ምልክት ከአመልካች የንግድ ስም ጋር አንድ አይነት በመሆኑና ሁለቱም ድርጅቶች የሲሚንቶ ምርት ለተገልጋዩ የሚያቀርቡ በመሆናቸው ተጠቃሚውን የሚያደናግር በመሆኑ የንግድ ምልክቱ ሊመዘገብ አይገባውም የሚል መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ኢትዮ ሲሚንቶ /ETHIO CEMENT/ የሚለው ሀረግ የአመልካች የንግድ ስም መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያቀረበለት መሆኑን ገልዖ ሆኖም አመልካች ይህንን ሀረግ በንግድ ምልክትነት ስላላስመዘገበ፣ የሁለተኛ ተጠሪ የንግድ ምልክት ETHIO CEMENT የሚለው ሀረግ ብቻ ሣይሆን ዙሪያውን ያሉት ኮከቦች አካል ሆኖ ያቀረበ በመሆኑና አመልካች " ETHIO CEMENT " የሚለውን ሀረግ ከሌላ ሊመዘገብ ከሚችል ምልክት ጋር



www.chilot.me

ማስመዝገብና መጠቀም ስለሚችል የአመልካች መቃወሚያ የህግ መሠረት የለውም በማለት፣ ሁለተኛ ተጠሪ እንዲመዘገብለት የጠየቀውን የግንድ ምልክት በመመዝገብ ዕውቅናና ጥበቃ ሰጥቷል፡፡

አንደኛ ተጠሪ በተሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔው የይግባኝ ቅሬታ የቀረበበት አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ ያቀረቡትን መልስና የአመልካችን የመልስ መልስ ከሰማ በኋላ አንደኛ ተጠሪ ውሣኔ ሲሰጥ ያቀረባቸውን ምክንያቶች በመቀበል አንደኛ ተጠሪ በአራት ማዕዘን ውስጥ በአስር ኮከቦች የተከበበ " ETHIO CEMENT " የሚል ፅሑፍ ያለበት የንግድ ምልክት የሁለተኛ ተጠሪ ንብረትና የንግድ ምልክት መሆኑን በማረጋገጥ መመዝገቡ የአመልካችን መብትና ጥቅም ስለማይነካ የንግድ ምልክቱ አይሰረዝም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ሰኔ 10 ቀን 2002 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ለሁለተኛ ተጠሪ በንግድ ምልክትነት የተመዘገበው " ETHIO CEMENT " የሚለው ሀረግ የአመልካች የንግድ ስምና መጠሪያ ሆኖ አግባብነት ባላቸው አካላት ተመዝግቧል፡፡ አንደኛ ተጠሪ የሁለተኛው ተጠሪን የንግድ ምልክት ሲመዘግብ አመልካች በንግድ ስሙ አምርቶ ፅፎ ለገበያ የሚያቀርበውን የሲሚንቶ ምርት ሁለተኛ ተጠሪ የንግድ ምልክት አድርጎ ለተገልጋዩ በሚያቀርበው የሲሚንቶ ምርት ላይ በንግድ ምልክትነት እንዲጠቀምበት ፈቃድ ሰጥቷል፡፡ ይህ ተጠቃሚውን ህብረተሰብ የሚያሣስትና የሚያደናግር ሲሆን የአንደኛ ተጠሪ ውሣኔ የንግድ አሠራር አዋጅ 329/95 እና የንግድ ምልክት ጥበቃና አሠራር አዋጅ 501/1998 መሠረታዊ ግብና ዓላማ በሚያሣካ መንገድ ተጣጥመው ሥራ ላይ እንዲውሉ የሚያደርግ አይደለም፡፡ ስለሆነም እኔ በንግድ ስምና መጠሪያነት የምገለገልበትን " ETHIO CEMENT " ሁለተኛ ተጠሪ የንግድ ምልክት አድርጎ እንዲጠቀም አንደኛ ተጠሪ የሰጠው ዕውቅና የአዋጅ ቁጥር 329/1995 ድንጋጌዎች እና የአዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀፅ 5 እና ሌሎች ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

አንደኛ ተጠሪ የንግድ ስም በአንድ ድርጅት መጠሪያነት የሚያገለግል ሲሆን ዓላማው አንደኛውን የንግድ ድርጅት ከሌላው የንግድ ድርጅት ለመለየት ነው፡፡ የንግድ ስም የሚመዘገበው በንግድ ሚኒስትር ወይም በክልል ንግድ ቢሮዎች ነው፡፡ የንግድ ምልክት የአንድን ሰው ምርት ወይም አገልግሎት ከሌላው ሰው ለመለየት የሚያገለግል ነው፡፡ የንግድ ምልክት ጥበቃ የሚያደርገውና የሚመዘገበው በአዋጅ ቁጥር 501/1998 ሲሆን ይህንን ተግባር አንደኛ ተጠሪ እንዲያከናውን በአዋጅ ቁጥር 320/1995 ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ የንግድ ድርጅቶች የንግድ ስያሜያቸውን በንግድ ምልክትነት በማስመዝገብ ወይም በመጠቀም ባለቤት መሆን እንደሚቻል አዋጅ ቁጥር 501/98 በአንቀፅ 5/1/ እና በአንቀፅ 7/2/ በግልፅ የተደነገገ ቢሆንም አመልካች የንግድ ስማቸውን በንግድ ምልክትነት አላስመዘገቡም፡፡ አንደኛ ተጠሪ ጥበቃ የሰጠውና የመዘገበው ለኮከቦቹ እንጅ " ETHIO CEMENT " ለሚለው ሀረግ አይደለም፡፡ ስለዚህ የሰበር አቤቱታው የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ውድቅ ሆኖ እንድሰናበት በማለት ታህሣሥ 13 ቀን 2003 ዓ.ም. በፅሑፍ መልስ ሰጥቷል፡፡

ሁለተኛው ተጠሪ በበኩሉ የንግድ ስምና የንግድ ምልክት የተለያዩ ናቸው፡፡ አመልካች ሲሚንቶ አምርቶ መሸጥ ስላልጀመረ በሚያመርተው ሲሚንቶ ላይ የሚያስቀምጠው የንግድ ምልክት ምን እንደሆነ ገና አልታወቀም፡፡ እኔ የአመልካችን የንግድ ስያሜ በንግድ ምልክትነት አልተጠቀምኩም፡፡ አመልካች ምርት ማከፋፈል አልጀመረም ስለዚህ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ በመሠረዝ እንዲያሰናብተን በማለት ጥር 30 ቀን 2003 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ ሰጥቷል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን

መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አንደኛ ተጠሪና ይግባኝ ሰሚው የከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተጠሪ እንዲመዘገብለት ያቀረበው "የንግድ ምልክት" አመልካች የንግድ ስሙን በንግድ ምልክትነት ስላላስመዘገበ ወይም የንግድ ስሙ የሚያመርተውን የሲሚንቶ ምርት ለተጠቃሚው ማቅረብ ያልጀመረ በመሆኑ መቃወሚያ ሊያቀርቡበት አይችልም በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መመርመር ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን አመልካችና ተጠሪ ለማምረትና ለመስጠት የሚፈልጉትን አገልግሎት አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች በተለይም ከንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1989 በአዋጅ ቁጥር 328/1995 እንደተሻሻለ አግባብነት ያላቸውን የንግድ ህግ ድንጋጌዎች የንግድ አሠራር አዋጅ ቁጥር 329/1995 ከአንደኛው ተጠሪ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 320/1995 እና ከአዋጅ ቁጥር 501/1998 ድንጋጌዎች ማገናዘብና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተከተለውን የህግ አተረጓጎም ተገቢነት መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች በአዋጅ ቁጥር 67/1989 በአዋጅ ቁጥር 329/1995 እንደተሻሻለው በአንቀፅ 16 ንዑስ አንቀፅ 1 በሚደነግገው መሠረትና የንግድ ህግ አንቀፅ 135 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 2 በሚደነግጉት መሠረት "ኢትዮ ሲሚንቶ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር" በሚል የንግድ ስም ተመዝግቦ የሲሚንቶ ማምረቻ ፋብሪካ በማቋቋምና ሲሚንቶ በማምረት ለአገር ውስጥ ገበያና በተሻሻለው የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁ. 328/1995 አንቀፅ 32 መሠረት ምርቱን ወደ ወጭ አገር ለመላክ የሚችል የንግድ ድርጅት ስለመሆኑ አመልካች ለአንደኛ ተጠሪ ካቀረባቸው ማስረጃዎችና በይግባኝ እና በሰበር ካቀረበው ክርክር ለመገንዘብ ችለናል፡፡ አመልካች ይህንን ተግባሩን ሲያከናውን በንግድ ህጉና በንግድ ሥራ አዋጅ 329/1995 መሠረት ተገቢው ጥበቃ የሚሰጠው ሲሆን በንግድ ሥራ አዋጅ ቁ. 329/1995 እና በሌሎች ህጎች የተደነገጉትን ግዴታና ሀላፊነቶች በአግባቡ መወጣት ይጠበቅበታል፡፡ ይህም በመሆኑ አመልካች ፋብሪካውን በመገንባት ያመረተውን ሲሚንቶ ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ሲያቀርብ በንግድ ሥራ አዋጅ ቁጥር 329/95 አንቀፅ 21 በተደነገገው መሠረት ስለ አመረተው ምርት መግለጫ የመለጥፍ ግዴታ አለበት፡፡ በምርቱ ላይ የሚለጥፈው መግለጫ በአዋጅ ቁጥር 329/95 አንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገውን መያዝ እንደሚገባውና በተለይም አመልካች የሲሚንቶ ምርቱን አሽጎ ለገበያ ሲያቀርብ በአዋጅ ቁጥር 329/95 አንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ /3/ በሚደነግገው መሠረት የዕቃውን የተጣራ ክብደት፣ የፋብሪካው ወይም የአሻጊው ስምና አድራሻና ዕቃው አገልግሎት መስጠት የሚያበቃበትን ቀን እና ዕቃው የተመረተበትን ቀን በምርቱ ላይ የመፃፍ ግዴታና ሀላፊነት እንዳለበት ከላይ ከተጠቀሰው የህግ ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህም የምንረዳው አመልካች የፋብሪካውን ግንባታ አጠናቅቆ የሲማንቶ ምርት በማምረት ለገበያ ሲያሠራጭ ሲሚንቶውን ያመረተው “ኢትዮ ሲሚንቶ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር“ መሆኑን በመግለፅ የመለጠፍ ህጋዊ ግዴታና ኃላፊነት ያለበት መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 329/95 አንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ በግልፅ የተደነገገ መሆኑ ነው፡፡ አመልካች ከዚህ በፊት የሲሚንቶ ምርት በንግድ ስሙ በመጠቀም ያላሰራጨ ቢሆንም ምርት ሲጀምር የንግድ ስሙንና አድራሻውን አሽጎ በሚያቀርበው የሲሚንቶ ምርት ላይ የመግለፅ /የመፃፍ/ ህጋዊ ግዴታና ኃላፊነት አለበት፡፡

በሌላ በኩል ሁለተኛው ተጠሪ የሚሠራው ሥራ የሲሚንቶ ምርት ስርጭት ጋር የተገናኘ መሆኑ ሁለተኛው ተጠሪ ለአንደኛ ተጠሪ ባቀረበው አቤቱታ የተገለፀ ሲሆን፣ ሁለተኛው ተጠሪ በአራት ማዕዘን ውስጥ ሆኖ በአስር ኮከቦች የተከበበና /ETHIO CEMENT/ የሚለው ሀረግ ያለበት የንግድ ምልክት አንደኛ ተጠሪ ብቸኛ ባለሀብትና ተጠቃሚ መሆኑን በማረጋገጥ እንዲመዘግብለት፣ ጥያቄ አቅርቧል፡፡ ይህ የሁለተኛው ተጠሪ የንግድ ምልክት በአራት ማዕዘን ምስል ውስጥ በአስር

ኮከቦች መካከል የሚፃፍ ቢሆንም በአዋጅ ቁጥር 329/95 አንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ መሠረት አመልካች በሚያመርተውና አሽጎ በሚሸጠው የሲሚንቶ ምርት ላይ መግለፅ ህጋዊ ግዴታው ከሆነው የአመልካች የንግድ ስም / ኢትዮ ሲሚንቶ/ በእንግሊዝኛው " ETHIO CEMENT " PRIVATE LIMITED ጋር አንድና ተመሣሣይ ነው፡፡ ተጠሪ በንግድ ምልክትነት በሚያመርተውና በሚያሰራጨው የሲሚንቶ ምርት ላይ እንዲለጥፍ በአንደኛ ተጠሪ የተመዘገበለት የንግድ ምልክት አመልካች በህግ ተገድዶ በምርቱ ላይ መግለፅ ከሚገባው የንግድ ስያሜ ጋር የሚመሳሰል ተመሣሣይ " ETHIO CEMENT " የሚል ሀረግ ያለው ነው፡፡

የንግድ ሥራ አዋጅ መሠረታዊ ዓላማ ለነፃ ገበያ ውድድር እንቅፋት የሆኑ ድርጊቶችና ተገቢ ያልሆኑ የንግድ ሥራዎች እንዳይፈፀሙ በመከላከልና በማስወገድ ተገቢ የንግድ ውድድር እንዲሰፍን ማድረግ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 329/95 አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 1 ተደንግጓል፡፡ በዚህ አዋጅ መሠረት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ማለት በንግድ ሥራ ኦዲት ውስጥ በተለያዩ መንገዶች ተወዳዳሪን ለማጥፋት ያለመ ማንኛውም ድርጊት ወይም ተግባር ሁሉ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር እንደሆነ እንደሚቆጠር በአዋጅ ቁጥር 329/95 አንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ 1 በመርህ ደረጃ የተደነገገ ሲሆን፣ በሌላው የንግድ ድርጅት ወይም በንግድ ድርጅቱ ተግባሮች በተለይም ድርጅቱ ከሚያቀርበው ምርት ወይም አገልግሎት ጋር በተገናኘ ሁኔታ ማደናገርን ያስከተለ ወይም ሊያስከትል የሚችል ማናቸውም ድርጊትና የአንድ ድርጅት ወይም የድርጅቱን ተግባሮች በተለይም ድርጅቱ ከሚያቀርበው ምርት ወይም አገልግሎት ጋር በተገናኘ ሁኔታ የሕዝብ ግንዛቤን ያዛባ ወይም ሊያዛባ የሚችል ማናቸውም ድርጊት ተገቢ ያልሆኑ የንግድ ውድድሮች እንደሆኑ በአዋጅ አንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ 2/ሀ/ እና /ሐ/ በግልፅ ተደንግጓል፡፡

በተመሣሣይ ሁኔታ የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ መሠረታዊ ግብ ዕቃ በማምረት እና በማከፋፈል ወይም አገልግሎት በመስጠት የንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሰዎችን መልካም ስም እና ዝና መጠበቅና በተመሣሣይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች መካከል መሣከርን ማስወገድ መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 501/1998 መግቢያ በመጀመሪያው ፓራግራፍ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንደኛ ተጠሪ የፖተንትና የንግድ ምልክት የምዝገባ ወረቀት ማመልከቻዎችን ተቀብሎ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅን መሠረታዊ ግብና ዝርዝር ድንጋጌዎች እንደዚሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መመርመር ወይም እንዲመረመር የማድረግ ግዴታና ኃላፊነት ያለበት መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 320/95 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም አንደኛ ተጠሪ " ETHIO CEMENT " የሚል ሀረግ ያለበትን የንግድ ምልክት እንዲመዘግብለት ሁለተኛ ተጠሪ ሲጠይቀው "ኢትዮ ሲሚንቶ" በእንግሊዝኛው " ETHIO CEMENT " በሚል የንግድ ስም የሚጠራው አመልካች በሚያመርተውና አሽጎ በሚሸጠው ሲሚንቶ ላይ ይህንን የንግድ ስሙን የመፃፍና የመግለፅ ግዴታና ኃላፊነት በአዋጅ ቁጥር 329 በአንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ የተጣለበት መሆኑንና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ በአንድ በኩል በአራት ማዕዘን ምስል ውስጥ ሆኖ በአስር ኮከቦች መካከል የተፃፈ " ETHIO CEMENT " የሚል ሀረግ ያለው የንግድ ምልክት ያለበት ሲሚንቶ በሁለተኛው ተጠሪ የሚቀርብ መሆኑና በሌላ በኩል " ETHIO CEMENT " ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የሚለው የአመልካች የንግድ ስም የተፃፈበት የሲሚንቶ ምርት ሊቀርብለት የሚችል መሆኑን የማገናዘብ ሀላፊነት አለበት፡፡

እነዚህ ሁለት ምርቶች ለተጠቃሚው በሚቀርቡበት ጊዜ የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ የወጣበትን መሠረታዊ ዓላማ በሚፃረር መንገድ በሁለተኛው ተጠሪና የአመልካች ምርት መካከል መሣከርን የሚፈጥርና በአዋጅ ቁጥር 329/95 አንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ 2/ሀ/ እና /ሐ/



www.chilot.me

ክልከላ የተደረገበት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ምክንያትና መንስኤ የሚሆኑ በመሆኑ አንደኛ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 320/95 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገውን አግባብነት ያላቸውን ህጎች ሣይመረምር የአመልካችን የንግድ ስም በውስጡ የሚያካትተውን የሁለተኛ ተጠሪ የንግድ ምልክት ተቀብሎ መመዝገቡ ህግ አውጭው በአዋጅ ቁጥር 329/95 እና በአዋጅ ቁጥር 501/98 በንግድ ሥራ ለተሰማራው ሰውም ሆነ ለተገልጋዩ ህብረተሰብ ለመስጠት ያሰበውን ህጋዊ ጥበቃና ዋስትና በተሟላ ሁኔታ ተፈፃሚ ለማድረግ የማያስችል የህግ አረዳድና አተገባበር ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛው ተጠሪ የአመልካች የንግድ ስም የተካተተበትን የንግድ ምልክት በመመዝገብ የሰጠው ዕውቅና ከላይ በዝርዝር ይዘታቸው፣ መሠረታዊ ዓላማና ግባቸው የዘረዘርናቸውን ተያያዥነት ያላቸው የህግ ማዕቀፎችና ድንጋጌዎች ያላገናዘበና መሠረት ያላደረገ፣ እንደዚሁም በአዋጅ ቁጥር 320/95 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት አግባብነት ያላቸውን ሌሎች የህግ ማዕቀፎችና ድንጋጌዎች ሣይመረምርና ሣያገናዝብ የሰጠው ውሣኔ በመሆኑ በይግባኝ ሊታረም የሚገባው ሆኖ እያለ በይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት መፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. አንደኛ ተጠሪና በከፍተኛው ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተጠሪ ያቀረበውና የአመልካችን የንግድ ስም የሚያካትተውን የንግድ ምልክት እንዲመዘገብ የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ሁለተኛ ተጠሪ የአመልካችን የንግድ ስም " ETHIO CEMENT " የሚለውን ሀረግ ከንግድ ምልክቱ በማውጣትና በሌላ በመተካት የንግድ ምልክቱን ሠርቶ ካላቀረበ በስተቀር የንግድ ምልክቱ ሊመዘገብና ህጋዊ ጥበቃ ሊሰጠው አይገባም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ጽ/ሽ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 59025

ግንቦት 19 ቀን 2003 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታሁ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች ፡-** የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረቶች ጽ/ቤት -ነ/ፈጅ አጥናፉ ደምሴ ቀረቡ

**ተጠሪ ፡-** አቶ ጥበበ አየለ - ጠበቃ ታገል ጌታሁን ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በአመልካች መስሪያ ቤት በአዋጅ ቁጥር 501/98 መሠረት በሚሰጡት ውሳኔዎች ቅሬታ ያለበት ወገን አቤቱታውን ሊያቀርብ የሚገባበትን ፍርድ ቤት የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበሩት ተጠሪ ናቸው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች መስሪያ ቤት ላይ የመሰረቱት የክስ ይዘት ባጭሩ፡- RISING የሚለውን የንግድ ምልክት እንዲመዘግብልኝ አመልክቼ ማመልከቻዬን ያላግባብ ያልተቀበለኝ ስለሆነ የንግድ ምልክቱን እንዲመዘግብልኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ ማየት እንደማይችል ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥብን ውድቅ አድርጓል በፍሬ ጉዳዩ ላይም ተጠሪ የንግድ ምልክቱ እንዲመዘገብላቸው ሲል ወስኗል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ያደረገው አመልካች መስሪያ ቤት በፍርድ ቤት ሊከሰስ እንደሚችል አዋጅ ቁጥር 501/98 ይደነግጋል በሚል ምክንያት ነው ፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም የአመልካች መስሪያ ቤት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የመስጠት ስልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 17 ስር የተደነገገ ሆኖ በውሳኔው ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ደግሞ ይግባኙን ማቅረብ ያለበት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 49 ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከተሰጠው የይግባኝ ስልጣን ድንጋጌዎች ጋር አጣምሮ በማንበብ መረዳት የሚቻልና በጉዳዩ ላይ በስራ ላይ የነበሩትና ሌሎች ተዛማጅ ሕጎችም ሆነ ያለው አሰራር አየመልካች መስሪያ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ በይግባኝ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይቀርብ የነበረ አሁንም እየቀረበ ያለ መሆኑን በግልጽ የሚያሳዩ ሁነው እያለ ጉዳዩን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ቀጥታ ክስ መመልከቱ ተገቢነት የለውም በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው



www.chilot.me

ተመርምሮም በስር ፍርድ ቤት የቀረበውን የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥያቄ ተቀብሎ የተጠሪን የንግድ ምልክት እንዲመዘግብ የተሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በቀጥታ ክስ አስተናግዶ ፍርድ የሰጠበትን አግባብ ከአዋጅ ቁጥር 320/1995 ፣ 501/98 እና 25/1988 አንፃር ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የጽሁፍ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ ተጠሪ በጽሁፍ መልሳቸው በተመሳሳይ ጉዳይ በመ/ቁጥር 56938 በሰበር ችሎት የአመልካች የሰበር ቅሬታ ለሰበር ችሎቱ አያስቀርብም ተብሎ መዘጋቱን ፣በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 17/2/ ስር ይግባኝ የሚለው ቃል መቀመጡ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ የተቀመጠውን የይግባኝ ቃል ትርጉም በመያዝ ሳይሆን ቅሬታ በሚል ቃል መንፈስ ነው የሚሉትንና ሌሎች ነጥቦችን በማንሳትና በዋቢነትም አግባብነት አላቸው ያሏቸውን ሕጎችና ድንጋጌዎችን በመጥቀስ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ አንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ስልጣን አለው? ወይስ የለውም የሚለው ሆኖ አኝቶታል፡፡

በመሠረቱ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 320/1995 አንቀጽ 6/1/ መሠረት የንግድ ምልክት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ማመልከቻዎችን በመቀበል አግባብ ባለው የአእምሯዊ ንብረት ሕግ መሠረት ምርመራ በማካሄድ ውሳኔ የመስጠትና በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 36 መሠረት በተመዘገበ የንግድ ምልክት ላይ የሚነሱ ክርክሮችን በማየት ፈራሽ የማድረግ ስልጣን የተሰጠው መሆኑን የተጠቀሱት ድንጋጌዎች በግልፅ ያስገነዝባሉ፡፡ የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 17/1/ ድንጋጌ ሲታይም የአመልካች መስሪያ ቤት ስለንግድ ምልክቱ ምዝገባ በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ቅሬታውን ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል አስቀምጧል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 49 ሲታይ ደግሞ ስልጣን ያለው ፍርድ ቤትን ያሳያል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት በአዋጁና አዋጁን ለማስፈጸም በአዋጁ አንቀጽ 47 መሠረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ የተመለከቱ ጉዳዩችን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮችንና ተዛማጅ ጉዳዮችን የማየት ስልጣን የሚኖራቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸው በሚል የሚደነግግ ነው፡፡ እንግዲህ በሕጉ ረገድ ያለው የውሳኔ አሰጣጥና የይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን ሕጉ አመልካች መስሪያ ቤት በሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት (The right to Appeal) እንዳለው በግልፅ ከማስቀመጡ ውጪ ይግባኙ በፌዴራሉ ፍርድ ቤቶች በየትኛው እርከን ለሚገኝ ፍርድ ቤት እንደሚቀርብ ግልጽና አሻሚነት በሌለው አነጋገር አያስቀምጥም፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜ ሕጉን መተርጎም ተገቢ ይሆናል፡፡

የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 17/1/ ድንጋጌ ርእሱ ሲታይ አማርኛው "ይግባኝ የማቅረብ መብት" በሚል የተቀመጠ ሲሆን የእንግሊዝኛው ቅጂ ደግሞ "The right to Appeal" በሚል የተቀመጠ ነው፡፡ እንግዲህ ሕጉ በይዘቱና በቅርጹ ይህን የሚመስል ከሆነ ይግባኝ የሚለው የሕጉ አገላለፅ ለየትኛው ፍርድ ቤት ነው ጉዳዩ መቅረብ ያለበት የሚለውን ጥያቄ ይፈታ ዘንድ የይግባኝ ትርጉሙንና የአቀራረብ ሥርዓቱን በአጠቃላይ ማየቱን፣ የአመልካች መስሪያ ቤትን ለማቋቋም

የወጣውን ሕግና ለመስሪያ ቤቱ ስልጣን የሚሰጡ ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ሕጎች የሚያስቀምጡትን የይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት መመልከቱና ግንዛቤ መውሰዱ ተገቢ ይሆናል፡፡

ታዋቂው የ" Black's Law Dictionary" ይግባኝ የሚለውን ቃል ሲተረጎም A proceeding undertaken to have a decision reconsidered by bringing it to a higher authority, especially, the submission of a lower court's or agency's decision to a higher court for review and possible reversal. በሚል ያስቀምጣል፡፡ ከዚሁ መገንዘብ የሚቻለው ይግባኝ በበታች አካል የተሰጠ አንድ ፍርድን ወይም ውሳኔን በመቃወም ለበላይ ፍርድ ቤት አቤቱታ በማቅረብ የስር ፍርዱ /ውሳኔ/ እንደገና የሚታይበትን ወይም እንዲጣራ የሚደረግበትን ወይም ሊለወጥ የሚችልበትን ሥርዓት የሚያመላክት መሆኑን ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 320/1/ የተመለከተው ድንጋጌ ሲታይም በፍትሓብሔር ወይም በሌሎች ሕጎች ውስጥ በሌላ ሁኔታ እንዲፈጸም የሚያዝ ድንጋጌ ከሌላ በቀር ከሳሽ ወይም ተከሳሽ በፍትሐ ብሔር ፍርድ ቤት በተወሰነበት የመጨረሻ ፍርድ ላይ ይግባኝ ለማለት የሚችሉ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የይግባኝ ትርጉም በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከራካሪ የነበረና በተሰጠው ፍርድ ቅር የተሰኘ ወገን ይህንኑ ቅሬታውን ለበላይ ወይም ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርቦ የበታች ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ እንዲሻሻል ፣ እንዲለውጥ ወይም በጠቅላላው ውድቅ እንዲሆንና ዳኝነቱ ለእሱ እንዲሰጠው ለመጠየቅ የሚያስችል ሥርዓት ነው፡፡ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 ደግሞ የይግባኝ ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ተመልክተዋል፡፡ በሌላ በኩል አዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 17/1/ ድንጋጌ ስለንግድ ምልክት ምዝገባ ፅ/ቤቱ በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ቅሬታውን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል ብሎ ሲያስቀምጥ "የመጨረሻ ውሣኔ" የሚለው ሐረግ አቀራረፁና ይዘቱ የሚያሳየው በጉዳዩ ላይ ይግባኝ የሚቀርብበት መሆኑን እንጂ ቀጥታ ክስ የሚቀርብበት አለመሆኑን መገንዘብ የሚቻል መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም አመልካች የተቋቋመው አእምሯዊ ንብረትን የሚገዙ ብሔራዊ ሕጎችን የሚያስፈፅም ወይም ተፈፃሚነታቸውን የሚከታተል እንዲሁም አስፈላጊውን አቅም በመገንባት ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት የሚሰጥ መንግስታዊ አካል ማቋቋሙ በማስፈለጉ መሆኑን አዋጅ ቁጥር 320/95 በመግቢያው ያስቀመጠው ጉዳይ ሲሆን የዚሁ አዋጅ አንቀፅ 2 ደግሞ "አእምሮአዊ ንብረት" እና "ፓተንት" የሚሉትን ቃላት ትርጉም አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሠረት አእምሯዊ ንብረት ማለት የሰው ልጅ አእምሮ ውጤት በሆኑ የፈጠራ ሥራዎች ላይ ያለ ሕጋዊ መብት ሲሆን ፓተንትን፣ የንግድ ምልክትን፣ የምስክር ወረቀትንና ኮፒ ራይትን እንደሚጨምር በአዋጁ አንቀፅ 2/1/ ድንጋጌ የተቀመጠ ሲሆን ፓተንት ማለት ደግሞ የፈጠራ ስራን ለማስጠበቅ የሚሰጥ መብት ሲሆን በፈጠራ በአነስተኛ ፈጠራና በኢንዱስትሪያዊ ንድፍ በአዋጅ ቁጥር 123/87 መሠረት በፈጠራ በአነስተኛ ፈጠራና በኢንዳስትሪያዊ ንድፍ የሚሰጠውን የአስገቢ ፓተንት የግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀትና የኢንዱስትራያዊ ንድፍ የምዝገባ የምስክር ወረቀትን እንደሚጨምር በአንቀጽ 2/2/ ስር በግልፅ ሰፍሮ እናገኛለን፡፡ ይህ መስሪያ ቤት ከሚያስፈጽማቸው ሕጎች መካከል አንዱ አዋጅ ቁጥር 410/1996 ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2/9/ እና 15/ ድንጋጌዎች ሲታዩም በአዋጁ በሚገዙ ጉዳዮች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን የመመልከት ስልጣን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣን ስለመሆኑ በግልፅ ያሳያሉ፡፡፡ በሌላ በኩል የፈጠራ፣ የአነስተኛ ፈጠራና የኢንዱስትሪያል ንድፍ አዋጅ ቁጥር 123/1987 ስር የይግባኝ ስልጣኑ የማዕከላዊ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣን ስለመሆኑ አንቀፅ 2/1፣ እና 54 ድንጋጌዎች በአንድ ላይ ሲነበቡ የሚያሳዩት ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ የሚቻል ሆኖ አግኝተናል፡፡ እነዚህ ሕጎች በአመልካች መስሪያ ቤት ይፈጸማሉ ተብለው ከተጠቀሱት ሕጎች መካከል ሲሆኑ አመልካች መስሪያ ቤት በሚሰጠው ውሳኔ ይግባኙ የሚቀርበው በግልፅ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ

ቤት መሆኑን ያሳያሉ። ከላይ እንደተገለጸው አመልካች መስሪያ ቤትን ያቋቋመው አዋጅ ቁጥር 320/1995 መስሪያ ቤቱን ለማቋቋም ያስፈለገበትን ሲገልፅ አእምሯዊ ንብረትን የሚገዙ ብሔራዊ ሕጎችን የሚያስፈፅም ወይም ተፈፃሚነታቸውን የሚከታተል አካል ማቋቋም በማስፈለጉ መሆኑን በግልፅ ያስፈረ ሲሆን ይህ ምክንያት አመልካች መስሪያ ቤት ተመሳሳይ የአእምሯዊ ንብረት ጉዳዮችን ለማስተናገድ ስልጣን የተሰጠው አካል ከመሆኑ ተዳምሮ ሲታይ ጽ/ቤቱ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ይታያሉ፣ ወይም በተወሰኑት ይግባኝ በተወሰኑት ደግሞ ቀጥታ ክስ ይቀርብባቸዋል ብሎ መደምደም የአመልካች መስሪያ ቤትን ሥልጣንና ተግባር ውጤት ያለው ማድረግ ያስችላል ተብሎ የማይታሰብ መሆኑን አመልካች መስሪያ ቤት የሚያስፈጽማቸው ሕጎች አውደ ንባብ (contextual interpretation) የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው። በመሆኑ አመልካች መስሪያ ቤት በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሠረት በሚሰጣቸው ውሳኔዎች ቅሬታ ያለው ወገን በሕግ የተሰጠው መብት ይግባኝ ማቅረብ እንጂ ቀጥታ ክስ መመስረት አይደለም። በሕጉ የተዘረጋው ሥርዓት ይግባኝ ከሆነ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 እና አግባብነት ባላቸው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት በጉዳዩ ላይ የይግባኝ ሥልጣን ያለው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው። የተጠሪ ጠበቃ በሰ/መ/ቁጥር 56938 በቀረበው ተመሳሳይ ጉዳይ በሰበር ችሎቱ አጣሪ ችሎት በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ መወሰኑን ገልፀው ይህ ጉዳይም በተመሳሳይ መልኩ ሊስተናገድ እንደሚገባው ያቀረቡትን ክርክር ስንመለከተውም ሦስቱ ዳኞች የሚሰጡት የሰበር ትዕዛዝ /ውሳኔ/ አስገዳጅነት የሌለው መሆኑን አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2/1/ ድንጋጌ በግልፅ የሚያሳይ በመሆኑ ይህ ችሎት የሚቀበለው አይሆንም። በመሆኑም በሰ/መ/ቁጥር 56938 የተሰጠው ትዕዛዝ ይህን ጉዳይ በተመሳሳይ መንገድ ለመወሰን የሚያስገድድ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን የተጠሪ ጠበቃ ክርክርን አልፈነዋል።

ሲጠቃለልም የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀፅ 6፣17፣36፣እና 49 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ ከይግባኝ ትርጉምና አመልካች መስሪያ ቤት ከተቋቋመበት አላማና አመልካች መስሪያ ቤት የሚያስፈፅማቸው ከአዋጅ ቁጥር 501/98 ውጪ ያሉት ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ሕጎች ከዘረጉት የይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት አንጻር ሲታይ በንግድ ምልክት ምዝገባ ጉዳይ ላይ አመልካች መስሪያ ቤት በሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ያለው መብት በይግባኝ ሥርዓት የማስከበር እንጂ በቀጥታ ክስ የሚስተናገድ አለመሆኑን ፣ ይግባኙ መቅረብ ያለበት ደግሞ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆኑን የሚያስረዳ ሆኖ አግኝተነዋል። በመሆኑም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በቀጥታ ክስ ለማየት አይችልም ተብሎ በአመልካች በኩል የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አዋጅ ቁጥር 501/98 አመልካች መስሪያ ቤት ሊከሰስ እንደሚችል ይደነግጋል በሚል በደፈናው ውድቅ ማድረጉና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ ሳያርም ማለፉ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል። በዚህም መሠረት ተከታዩን ወሰነናል።

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 153240 በ13/4/2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 89864 በ03/10/2002 ዓ/ም የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/348/1/ መሠረት ተሽሯል።



www.chilot.me

2. የንግድ ምልክት ምዝገባ አቤቱታ ላይ አመልካች በሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ያለው መብት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ማቅረብ እንጂ ቀጥታ ክስ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማቅረብ አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

እ/ብ



www.chilot.me

# ውክልና



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 38721

ህዳር 27 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፣** ተሻገር ገብረስላሴ

ብርሀኑ አመነው

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ካፕቴን ዩናስ ህሉፍ - አልቀረቡም

**ተጠሪዎች፡-** 1. አቶ እስጢፋኖስ ኪዳኔ - ቀረቡ

2. ወ/ሪት ሄለን ኪዳኔ

3. ወ/ሮ አዜብ ኪዳኔ

4. ወ/ሪት አስቴር ኪዳኔ

(2–4) አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ጉዳዩ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሁለት ጊዜ ቀርቦ ታይቶ ውሣኔ ተሰጥቶበታል፡፡

በሥር ፍርድ ቤት ክርክሩ የተጀመረው አንደኛ ተጠሪ ጥር 21 ቀን 1995 ዓ.ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ የአባትና የእናታቸው የጋራ ሀብት የሆነውንና በውርስ የተላለፈላቸውን በቀድሞው አጠራር በወረዳ 21 ቀበሌ 10 የሚገኘውና ቁጥሩ 383 የሆነውን ቤት የአሁን አመልካች /የሥር ተከሣሽ/ በመጀመሪያ ተከራይቶ ይኖርበት ነበር፡፡ ቤቱን እንዲለቅልኝ ብጠይቀው ገዝቸዋለሁ በማለት ለመልቀቅ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ቤቱን እንዲያስረክበኝና የቤቱን ኪራይ ክስ ካቀረብኩበት ቀን ጀምሮ እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት የክስ ማመልከቻ በማቅረቡ ነው፡፡ የሥር ተከሣሽ የአሁን አመልካች ሟች አቶ ኪዳኔ ተስፋሐዋሪያት ሌሎች ልጆች ስላሏቸው በክርክሩ እንዲገቡ ትዕዛዝ ይሰጥልኝ፡፡ ቤቱን የሟች ወኪል ከሆነችው የከሣሽ /የአንደኛ ተጠሪ/ እህት በውል የገዛሁት ስለሆነ ውሉ እንዲፈርስ በፍርድ ሣይወሰንብኝ ቤቱን ይልቀቅልኝ በማለት ክስ ሊቀርብብኝ አይገባም ውሉ መመዝገብ የሚያስፈልገው ለሶስተኛ ወገን እንጂ ለተዋዋይ ወገኖች አይደለም፡፡ አንደኛ ተጠሪ የእናቴ የጋራ ሀብት ነው የሚለውን በተመለከተ ውሉ እንዲፈርስ መጠየቅ አይችልም የሚል ክርክርና



www.chilot.me

ሌሎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኃላ አመልካች ከሟች ኪዳኔ ተስፋሁዋሪያት ወኪል ጋር መጋቢት 27 ቀን 1991 ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል በፍታብሐር ህግ ቁጥር 1923/1/ መሠረት ያልተፈፀመና እንደረቂቅ የሚታይ በመሆኑ ተከሣሽ የአሁን አመልካች ቤቱን ለአንደኛ ተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡

ከዚህ በኂላ ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአንደኛ ተጠሪንና የአመልካችን ክርክር ሰምቶ ጥር 4 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ በመቃወም የካቲት 15 ቀን 1997 ዓ.ም የተፃፈ የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡ አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ተጠሪዎች ባቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ የተጠሪዎች ወላጅ እናት ጥቅምት 1 ቀን 1990 ዓ.ም ወላጅ አባታቸው ሀምሌ 1 ቀን 1991 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ መሆኑን ገልፀው በአባታቸው ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤት ከአባታቸው በተሰጠ የውክልና ሰነድ አራተኛ ተጠሪ መጋቢት 27 ቀን 1991 ዓ.ም በተፃፈ ውል ለአመልካች ሽጠውላቸዋል፡፡ ስለዚህ እኛ በክርክሩ ሳንሳተፍ የሽያጭ ውሉ የእኛ መብት ያለበትን ቤት አንደኛ ተጠሪ እንዲረከብ የተሰጠው ውሣኔ እንዲሰርዝልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች በፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ መነሻ የይርጋና የውል ፎርም ክርክሮች ያቀረቡ ሲሆን የሥር ፍ/ቤት የይርጋው ክርክር በሥር ተከሣሽ /አመልካች/ ያልተነሣ በመሆኑ በፍርድ መቃወም አመልካቾች በኩል መነሳቱ ተገቢ አይደለም በማለትና ሌሎቹን የመከራከሪያ ነጥቦችን ውድቅ በማድረግ በተጠሪዎች አባት ወኪል አራተኛ ተጠሪና በአመልካች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል የህጉን ፎርም የማያሟላ በመሆኑ ጥር 4 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠሁትን ውሣኔ የምሠርዝበት ወይም የምሽርበት ምክንያት የለም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን ይግባኝና ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች ያቀረቡትን ይግባኝ በመዝገብ ቁጥር 37810 በማጣመር በአንደኛ ተጠሪ በአመልካች እንደዚሁም በሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎችና በአንደኛ ተጠሪ መካከል የተደረገውን ክርክር መርምሮ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ቤቱን የተጠሪዎች ወላጅ አባት ለአራተኛ ተጠሪ በሰጡት ውክልና መሠረት መጋቢት 21 ቀን 1991 ዓ.ም ሽጠው ሟች ሀምሌ 1 ቀን 1991 ዓ.ም የሞቱ በመሆኑ የውሉን ፎርም አንደኛ ተጠሪ በመከራከሪያነት ሊያነሣው አይችልም በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አንደኛ ተጠሪ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የመልስ ሰጭዎችን ማለትም የአመልካችን የሁለተኛ ተጠሪ የሶስተኛ ተጠሪና የአራተኛ ተጠሪን የቃል ክርክር ለማሰማት ለሀምሌ 10 ቀን 2000 ዓ.ም ቀጠሮ ሰጥቶ የአመልካች ጠበቃ በፅሑፍ መልስ ሰጥቷል፡፡ የሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎችን የቃል ክርክር መስማት ባለመቻሉ ክርክሩን ለመስማት ለታህሣሥ 3 ቀን 2000 ዓ.ም ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ቀን ይግባኝ ባዩ አንደኛ ተጠሪ ባለመቅረቡ አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ተጠሪዎች መዝገቡ እንዲዘጋላቸው በመጠየቃቸው ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎችን አሰናብቷል ከዚህ በኃላ አመልካችና አንደኛ ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክር መርምሮ ውሉ በህጉ የተደነገገውን ፎርም አያሟላም በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማፅናት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ውሉ በህጉ የተመለከተውን ፎርም የማያሟላ በመሆኑ አመልካች ቤቱን ለአንደኛ ተጠሪ እንዲያስረክብ በማለት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ የህግ ስህተት አለበት በሌላ በኩል የጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አንደኛ ተጠሪ በሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ይግባኝ በሚሰማበት ቀን ቀጠሮ ባለመቅረቡ የአንደኛ ተጠሪን ይግባኝ በመሰረዝ ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪን አሰናብቷቸዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ መዝገቦችን በማጣመር የወሰነ በመሆኑ ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች ባቀረቡት ይግባኝ መነሻ የሽያጭ ውሉ የፀና ነው በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ እንዲፀና የቀረበና የአንደኛ ተጠሪ ይግባኝ ከተሰረዘ በኃላ እኔ ያቀረብኩትን መልስ መነሻ በማድረግ ውሉ ፎርሙን አላሟላም ብሎ መወሰኑ እርስበርሱ የሚቃረን ነው፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የሰጠው ውሣኔ የህግ ሥርዓቱን ያልተከተለ በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ አንደኛ ተጠሪ በበኩሉ ጥቅምት 4 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ህግ በመተርጎም ረገድ የፈፀመው የህግ ስህተት የለም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ይህ ሰበር ችሎት የሰጠውን የህግ ትርጉም ተከትሎ ነው ውሣኔ የሰጠው ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎችንም ያሰናበታቸው የእነርሱ በተከራካሪነት መቀጠል የሚያመጣው የፍርድ መዛባት የሌለ በመሆኑ ነው፡፡ የአመልካች የሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች ክርክር ተመሳሳይ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በአመልካች ላይ የሰጠው ውሣኔ ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎችን ክርክር የሚቋጭ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው ጥቅምት 4 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአንደኛ ተጠሪን ይግባኝ በመሠረዝ እኛን አሰናብቶናል አንደኛ ተጠሪ ይህ ትዕዝዝ እንዲነሣ ወይም እንዲሰርዝ የሰበር አቤቱታ ያላቀረቡ በመሆኑ እኛን በተመለከተ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ውሣኔ መሆኑን በማረጋገጥ ውሣኔ እንዲሰጥልን በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በፅሑፍ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ለሰበር በግራቀኙ የቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪዎች የሟች ወ/ሮ ለተስላሴ ኃይሉና የሟች አቶ ኪዳኔ ተስፋሐዋሪያት ልጆችና የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ናቸው፡፡ አንደኛ ተጠሪ ሟች አቶ ኪዳኔ ተስፋሐዋሪያት በወኪላቸው አራተኛ ተጠሪ በኩል ከአመልካች ጋር ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል እንዲፈርስና ቤቱን እንድረከብ በማለት ከፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከ ሰበር ችሎት ባቀረቡት ክርክር የሚከራከሩ ሲሆን ሁለተኛ ተጠሪ፣ ሶስተኛ ተጠሪና አራተኛ ተጠሪ በበኩላቸው ሟች አባታችን በወኪሉ አራተኛ ተጠሪ በኩል የፈፀመው የቤት ሽያጭ ውል የሚፈርስበት ምክንያት የለም፣ውሉ አይፈርስም በማለት የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ እኛን በተመለከተ የመጨረሻና የፀና ነው በማለት የተከራከሩ መሆኑን ከሥር ጀምሮ እስከ ሰበር ችሎት ካቀረቡት ክርክር ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች በመዝገብ ቁጥር 37810 የቤት ሽያጭ ውሉ ሊፈርስ አይገባውም በማለት ያቀረበውን የይግባኝ ቅሬታና ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎሪች የሥር ፍርድ ቤት ውሉ ረቂቅ ነው በማለት የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም በመዝገብ ቁጥር 46139 ያቀረቡትን ይግባኝ በማጣመር በመዝገብ ቁጥር 37810 መርምሮ ውሉ ሊፈርስ አይገባም አመልካችም ለአንደኛ ተጠሪ ቤቱን የማስረከብ ግዴታ የለበትም በማለት ውሣኔ መስጠቱን ይህንን ውሣኔ በመቃወም አንደኛ ተጠሪ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካችን አንደኛ መልስ ሰጭ ሁለተኛ ተጠሪን ሁለተኛ መልስ ሰጭ ሶስተኛ ተጠሪ ሶስተኛ መልስ

ሰጭ አራተኛ ተጠሪን አራተኛ መልስ ሰጭ በማድረግ የይግባኝ ቅሬታ አቅርበው የነበረ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በይግባኝ በተደረገው ክርክር አንደኛ መልስ ሰጭ የነበሩት አመልካች የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው የይግባኝ ባዩ አንደኛ ተጠሪ የይግባኝ ቅሬታ የህግ መሠረት የለውም የሚል የፅሑፍ መልስ ሀምሌ 10 ቀን 1999 ዓ.ም ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያቀረቡ መሆኑንና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ መልስ ሰጭ የነበሩትን ከተራ ቁ 2-4 ተጠሪዎች የቃል ክርክር ለመስማት ቀነ ቀጠሮ በያዘበት ታህሣሥ 3 ቀን 2000 ዓ.ም አንደኛ ተጠሪ /ይግባኝ ባዩ/ ባለመቅረቡ መዝገቡ እንዲዘጋላቸው በመጠየቃቸው ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎችን እንዳሰናበታቸው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 28090ን በማስቀረብ ለማረጋገጥ ችለናል፡፡

በዚህ መዝገብ ከፍሬ ጉዳይ፣ ከተከራካሪዎቹ መሠረታዊ ባህሪና በክርክር የያዙት አቋምና አንደኛ ተጠሪ ያቀረበው ይግባኝ በሚሰማበት ቀነ ቀጠሮ ባለመቅረቡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝና በሰበር አመልካች አንደኛ ተጠሪና ከሁለተኛ እስከ አራተኛ ተራ ቁጥር ስማቸው የተጠቀሱ ተጠሪዎች ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ መሻሩ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ለጉዳዩ እልባት መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. ጉዳዩን እንደመረመርነው የተጠሪዎች ወላጅ አባት አቶ ኪዳኔ ተስፋሐዋሪያት ለአራተኛ ተጠሪ በስማቸው የተመዘገበ የማይንቀሣቀስ ንብረት የመሸጥ የመለወጥና ለሶስተኛ ወገን ለማስተላለፍ የሚያስችል ልዩ የውክልና ሥልጣን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2205 ንዑስ 1 መሠረት ሰጥተው የነበረ ስለመሆኑ አከራካሪ አይደለም አራተኛ ተጠሪ ይህንን የውክልና ስልጣን በመጠቀም የክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት መጋቢት 21 ቀን 1991 ዓ.ም ለአመልካች የሸጡ መሆኑን ይህም አቶ ኪዳን ተስፋሐዋሪያት በህይወት እያሉ የተፈፀመ መሆኑን ግራቀኙ ካቀረቡት ክርክር ለመንዘብ ችለናል፡፡ አራተኛ ተጠሪ ለአቶ ኪዳኔ ተስፋሐዋሪያት ከሰጧቸው የውክልና ሥልጣን ሣያልፉ በሟች አቶ ኪዳኔ ተስፋሐዋሪያት ስም የፈፀሙት የቤት ሽያጭ ውል በፍ/ሕግ ቁጥር 2189 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በሿሚው በሟች አቶ ኪዳኔ እንደተፈፀመ የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ አራተኛ ተጠሪ መጋቢት 21 ቀን 1991 ዓ.ም ለወኪላቸው ለአራተኛ ተጠሪ በሰጡት ሥልጣን መሠረት የፈፀሙት የቤት ሽያጭ ውል የፈቃድ ወይም የፎርም ጉድለት ቢኖርበት ይህንን ጉድለት ለአራተኛ ተጠሪ የውክልና ሥልጣኑን የሰጡት አቶ ኪዳኔ መከራከሪያ ሊያደርጓቸው የሚችሉ ስለመሆን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2189/2/ ይደነግጋል፡፡

አራተኛ ተጠሪ ወኪላቸው በመሆን የፈፀማቸውን ሽያጭ የፎርም ጉድለት ያለበት ስለሆነ ይፍረስልኝ የሚል ጥያቄ ሣያቀርቡ ቆይተው አቶ ኪዳኔ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ መሆኑን በአንደኛ ተጠሪ በአመልካችና በሌሎች ተጠሪዎች ካደረጉት ክርክርና ባቀረቧቸው ማስረጃዎች የተረጋገጠ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ አንድ ሰው ለሌላ ሰው በሰጠው ፍፁም የውክልና ሥልጣን መሠረት የተከናወነውን ተግባር ለማፍረስና መከራከሪያ ሊያደርገው የሚችለው ወካዩ ራሱ እንደሆነ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2189 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ የጣምራ ንባብ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ሟች አቶ ኪዳኔ ወኪላቸው አራተኛ ተጠሪ በሰጡት የውክልና ሥልጣን መሠረት የፈፀማችው የቤት ሽያጭ ውል የህጉን ፎርም አያሟላም ብለው መከራከሪያ የማድረግ መብት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2189/2/ የተሰጣቸው ቢሆንም በህይወት በነበሩበት ጊዜ ይህንን መብታቸውን አልተጠቀሙበትም አንድ ተወካይ ወካዩ ከሰጠው የሥልጣን ወሰን ሣያልፍ

የሠራው ሥራ ላይ የሚታዩ የፍቃድ ጉድለቶችን እንደመከራከሪያ አድርጎ ለማንሣት የሚችለው ወካዩ ብቻ እንደሆነ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2189/2/ የተደነገገ በመሆኑ ወካዩ ይህንን መብት ሣይጠቀምበት ካለፈ ወራሾቹ የሟች ወኪል የውክልና ሥልጣን ወሰኑን ሣያልፍ የሰራውን ተግባር የሚቃወሙበት ህጋዊ መሠረት የለም፡፡ በመሆኑም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በዚህ መዝገብ አራተኛ ተጠሪ የሟች አቶ ኪዳኔ ወኪል በመሆን ከተሰጣት የውክልና ሥልጣን ወሰን ሣታልፍ የፈፀመችው የቤት ሽያጭ ውል አቶ ኪዳኔ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2189/2/ መሠረት መከራከሪያ ሣያደርጉ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ መሆኑን ሣያገናዝቡ አንደኛው ተጠሪ ያቀረበውን ክስ በመቀበል የቤት ሽያጭ ውሉ እንዲፈርስና አመልካች ለአንደኛ ተጠሪ ቤቱን እንዲያስረክብ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. ይግባኝ ሰሚው ችሎት አንደኛ ተጠሪ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ያቀረበውን ይግባኝ በሚሰማበት ወቅት አንደኛ መልስ ሰጭ የነበረው ተጠሪ ሀምሌ 10 ቀን 1999 ዓ.ም በፅሑፍ መልስ ሰጥቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የቃል ክርክር ለመስማት ቀነ ቀጠሮ በያዙበት ታህሣሥ 3 ቀን 2000 ዓ.ም ይግባኝ ባይ የነበረው አንደኛ ተጠሪ ባለመቅረቡ በይግባኝ ክርክሩ ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ መልስ ሰጭዎች የነበሩት ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች መዝገቡ እንዲዘጋላቸው በማመልከታቸው በእነርሱ በኩል የይግባኝ ክርክር ተቋርጦ የተሰናበቱ መሆኑን በመግለፅ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ለይግባኝ በፅሑፍ መልስ የሰጠውና አንደኛ መልስ ሰጭ የነበረው አመልካች በይግባኝ ይግባኝ ባይ የነበረው አንደኛ ተጠሪ ያቀረበውን ይግባኝ በመቃወም መልስ የሰጠ መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ይግባኙ በሚሰማበት ቀን ይግባኝ ባይ ካልቀረበና መልስ ሰጭዎች ቀርበው በፅሑፍም ሆነ በቃል የሰጡት መልስ ይግባኝ ባይ ያቀረበውን ቅሬታ የሚደግፍ ካልሆነ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በፍታብሐር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 32/2/ እና በፍታብሐር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 73 በሚደነገገው መሠረት ይግባኙን ሙሉ በሙሉ በመሠረዝ ሁሉንም መልስ ሰጭዎች ማሰናበት ይገባዋል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች አንደኛ መልስ ሰጭ በመሆን በፅሑፍ የሰጠው መልስ የአንደኛ ተጠሪን የይግባኝ ቅሬታ የሚነቅፍ ሆኖ እያለ የአንደኛው ተጠሪ በሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች ላይ ያቀረበው የይግባኝ ክርክር እንዲቋረጥና ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች እንዲሰናበቱ ያደረገ ሲሆን በሌላ በኩል የአመልካችን መልስ መነሻ በማድረግ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ መሻሩ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 32/2/ና የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 73 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘት መንፈስና ዓላማ ያልተከተለ ትዕዛዝና ውሣኔ የሰጠ መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ የዚህም ትዕዛዝና ውሣኔ ውጤት የከፍተኛው ፍርድ ቤት በአንድና ተመሳሳይ ጭብጥ የሰጠውን ውሣኔ ለአመልካች ባደረገው የይግባኝ ክርክር መነሻ የሚሽር ለሁለተኛ ሶስተኛ አራተኛ ተጠሪዎች የአንደኛ ተጠሪ ይግባኝ የተሠረዘና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ የሚያፀና እርሱ በርሱ የሚቃረን ውጤት የሚያስከትልና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ በዘረዘርናቸው የህግ ምክንያቶች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ምክንያቱ ተለውጦ ፀንቷል፡፡
3. አመልካች ለአንደኛ ተጠሪ ክርክር የተነሳበትን ቤት የማስረከብ ግዴታና ሃላፊነት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

ም.አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 59568

ሚያዝያ 5 ቀን 2003ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

**አመልካች**፡- አቶ ቴዎድሮስ ተስፋዬ ጠበቃ ሰመረ አሰፋ ቀረቡ

**ተጠሪዎች**፡- 1. አቶ ሙሉ አርጌ ቀረቡ

2. ህፃን ሐና ሙሉ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የደቡብ ክልል ወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ ህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ተገልፆ ለሰበር ስለቀረበ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ በሰበር መዝገብ ቁጥር 58065 ከተዘረዘሩት ንብረቶች ውስጥ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-33129 ኢት፣ የሆነው የፍስሽ ጭነት ማመላለሻ መኪናን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀርቦ ንብረቱ የሆነውን ከላይ ቁጥሩ የተገለፀውን መኪና አንደኛ ተጠሪ እንዲሸጥ እንዲለወጥ እና እንዲያስተዳደር ውክልና የሰጠው መሆኑንና ውክልናውን ያሰረዘው መሆኑን ገልፆ ንብረቱን እንዲመልስልኝና በመኪናው ተሠርቶ የተገኘውን ገንዘብ እንዲከፍለኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አንደኛ ተጠሪ አመልካች በሰጠው ውክልና ሥልጣን መሠረት መኪናውን ለሁለተኛ ተጠሪ በብር 1,250,000/አንድ ሚሊዬን ሁለት መቶ አምሳ ሺህ ብር/ የሸጠው መሆኑንና ገንዘቡንም የአመልካች ወኪል ለሆኑት አቶ ታፈሰ አርጌ ያስረከበ መሆኑን በመግለፅ ተከራክራል፡፡ አንደኛ ተጠሪ በሥር ጣልቃ ገብ ተከራካሪ ሆነው በመቅረብ የመኪናውን ብር 1,500,000 /አንድ ሚሊዬን አምስት መቶ ሺህ ብር/ ከፍለው የተረከቡና የሚጠበቅባቸው ቀሪ ገንዘብ ብር 50,000 /ሀምሣ ሺህ ብር/ መሆኑን በመጥቀስ ተከራክረዋል፡፡ አቶ ታፈሰ አርጌ በሥር ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ ተከራካሪ ሆነው ቀርበው አመልካች ገንዘብ ለመቀበል የሚያስችል ውክልና ያላቸው መሆኑን ገልፀው የመኪናውን ዋጋ ከአንደኛ ተጠሪ በመቀበል የካቲት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ መተማመኛ 1,200,000 /አንድ ሚሊዬን ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ለአመልካች የሰጡት መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ ሌላኛው ጣልቃ ገብ ወ/ሮ ገነት ደምሴ መኪናው የጋራ ንብረት ሆኖ እያለ ወደ አመልካች መዛወሩን በመቃወም ጣልቃ ገብ ሆነው ተከራክረዋል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ለአንደኛ ተጠሪ የውክልና ሥልጣን ለመስጠት የውክልና ውሉ ረቂቅ የተፃፈው ሀምሌ 11 ቀን 1999ዓ.ም መሆኑን የውክልና ሥልጣን የሚሰጠው ሰነድ ለውልና ማስረጃ ቀርቦ የተረጋገጠው መስከረም 28 ቀን 2000ዓ.ም መሆኑን አንደኛ ተጠሪ ለሁለተኛ ተጠሪ የመኪና ሽያጭ ውል ያደረገው ነሐሴ 12 ቀን 1999ዓ.ም መሆኑን በውሣኔው ካስፈረ በኃላ አንደኛ ተጠሪ አመልካች ውክልናው ሥልጣን እንደሚሰጠው በቅን ልቦና በማሰብ የውክልና ሰነድ ረቂቅ ከተፃፈ ከሀምሌ 11 ቀን 1999ዓ.ም በኃላና የውክልና ሰነድ በውልና ማስረጃ ቀርቦ ሣይመዘገብ በፊት ነሐሴ 11 ቀን 1999 ዓ.ም የፈፀመው የሽያጭ ውል በቅን ልቦና የተደረገ በመሆኑ የፀና ነው በማለት በድምፁ ብልጫ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የይግባኝ ውሣኔውን በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ ተሰርዞበታል፡፡ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የቀረበው የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎበታል፡፡

አመልካች አንደኛ ተጠሪ ለህፃን ልጁ ለሁለተኛ ተጠሪ መኪናውን የሸጠው እኔ የውክልና ሥልጣን ከመሰጠቴ በፊት ነው፡፡ ስለዚህ በመኪልነት ሥልጣን ይሰጠኛል በሚል በቅን ልቦና የፈፀመው ህጋዊ ተግባር ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ያመለከተ ሲሆን አንደኛ ተጠሪ መኪናውን ሽጨ ገንዘቡን ለአመልካች ወኪል ሰጥቻለሁ፡፡ አመልካች ገንዘቡን ተቀብሏል ስለዚህ ውሉ እንዲፈርስ የሚያመለክትበት ህጋዊ ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡ ሁለተኛ ተጠሪ በበኩላቸው በ1982 ዓ.ም የተወለዱና ህፃን እንዳልሆኑ በመግለፅ ንብረቱን በአግባቡ የገዛሁት በመሆኑ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅረበዋል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች አንደኛ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን መኪና ሁለተኛ ተጠሪ የሸጠው የውክልና ስልጣን የተሰጠበት ረቂቅ ሰነድ ከተፃፈ በኃላ በቅን ልቦና በመሆኑ የሽያጭ ውሉ የፀና ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም; የሚለው ጭብጥ መመርመር ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ይህንን ጭብጥ ለመወሰን አንደኛ ተጠሪ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-3312927 የሆነውን መኪና የማስተዳደር የመሸጥና የመለወጥ ሥልጣኑን ያገኘበትን መንገድና መኪናውን የሸጠበትን ጊዜ እንደዚሁም አመልካች መኪናው ከተሸጠ በኃላ ፈጽሟቸዋል ለማለት አንደኛ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ጣልቃገብ የነበሩት አቶ ታፈሰ አርጌ ያነሱትን ክርክና ፍርድ ቤቶቹ የያዙትን ጭብጥና የሰጡትን ውሣኔ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የሌላ ሰው እንደራሴ በመሆን ሥራዎችን የመፈፀም ሥልጣን የሚገኘው ከህግ ወይም ከውል እንደሆነ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2179 መሠረታዊ መርህ ሆኖ ተደንግጓል፡፡ አንደኛው ተጠሪ ከላይ ቁጥሩ የተገለፀውን የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ መኪና የማስተዳደር የመሸጥና የመለወጥ የውክልና ሥልጣን ያገኘው በህግ የተደነገገን ድንጋጌን መሠረት በማድረግ ሣይሆን አመልካች ወኪሉ እንዲሆን ተስማምቶ በውልና ማስረጃ አስመዝግቦና አረጋግጦ በሰጠው የውል ሰነድ መሆኑን ግራቀኙ አልተካካዱም፡፡ ግራቀኙ የሚከራከሩት አመልካች ለተጠሪ የሰጠው የውክልና ሰነድ ህጋዊ ውጤት የሚኖረው ረቂቁ ከተፃፈበት ከሀምሌ 11 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ነው; ወይስ የውክልና ሰነዱ በአመልካች ከተፈረመበትና በውልና ማስረጃ ተመዝግቦና ተረጋግጦ ከተሰጠበት ከመስከረም 28 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ነው; በሚለው ነጥብ ላይ ነው፡፡

ስለ ውሉ አፃፃፍ ህጉ አንድ አይነት ፎርም እንዲደርግ ያስገደደ እንደሆነ ውሉን የሚፈፀምበት ሥልጣን በዚሁ አይነት ፎርም ለወኪል ሥልጣን መስጠት እንዳለበት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2080 የሚደነግግ መሆኑንና ውክልና በግልፅ ወይም በዝምታ ሊሰጥ የሚችል መሆኑን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2200 ንዑስ አንቀፅ 1 የሚደነግግ መሆኑን በመመልከት አንደኛ ተጠሪን አመልካች ረቂቁ ከተፅፈበት ሀምሌ 11 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ እንደወከለውና አንደኛ ተጠሪም መኪናውን በቅን ልቦና የአመልካች ወኪል ነኝ በሚል ውክልና ሰነድ በውልና ማስረጃ ከመረጋገጡ በፊት ነሐሴ 12 ቀን 1999 ዓ.ም አንደኛ ተጠሪ ከሁለተኛ ተጠሪ ጋር ያደረገው የመኪና ሽያጭ ውል በተሰጠው ውክልና መሠረት እደፈፀመው የሚቆጠር ነው በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና የሰበር ችሎት አፅንተውታል፡፡

ሆኖም ይህ የበታች ፍርድ ቤቱች የሰጡት ውሣኔ ስለ ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 334/1995 በአንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 1 እና በአንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 1/ለ/ የተደነገገውን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 334/1995 አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 1 አዋጁ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት ላይ ተፈፃሚነት ያለው መሆኑ "የተፈፃሚነት ወሰን" በሚለው ርዕስ ሥር በግልፅ ደንግጓል፡፡ ፍርድ ቤት ማስረጃ የመመዘን የመመርመርና የመቀበል ህገ መንግስታዊ ሥልጣን ያላቸው አካላት በመሆናቸው ይህንን አዋጅ የመተግበር ግዴታ ያለባቸው መሆኑ የአዋጅ ቁጥር 334/95 አንቀፅ 3/1/ ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 50 ንዑስ አንቀፅ 7 ጋር በጣምራ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 334/95 አንቀፅ 5 በህግ መሠረት ካልተረጋገጡና ካልተመዘገቡ ህጋዊ ውጤት እንደማይኖራቸው ከተዘረዘሩት ሰነዶች አንደኛው የውክልና ሥልጣን መስጫ ሰነድ እንደሆነ በአንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 1/ለ/ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም አመልካች የውክልና ሰነዱን ፈርሞና በውልና ማስረጃ አስመዝግቦ እና አረጋግጦ መስከረም 28 ቀን 2000ዓ.ም ለአንደኛ ተጠሪ የውክልና ሥልጣን ከመስጠቱ በፊት አንደኛ ተጠሪ የውክልና ሰነድ ረቂቅ የተጻፈው ሀምሌ 11 ቀን 1999 ዓ.ም ነው በማለት የፈፀመው ተግባር በወኪልነት ሥልጣኑ እንደፈፀመው የማይቆጠርና ወካዩ/አመልካች/ በግልፅ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ካላፀደቀው በስተቀር አመልካችን የማያስገድድ በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው የህግ ትርጉምና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ረቂቅ ሰነዱን መሠረት በማድረግ አንደኛ ተጠሪ ነሐሴ 12 ቀን 1999ዓ.ም የአመልካች መኪናን ለመሸጥ ያደረገው ስምምነት ህጋዊ ውጤት የሚኖረው አመልካች የመኪና ሽያጭ ውሉን በግልፅ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሲያፀድቀው መሆኑን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2090/1/ ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤት የአመልካች ወኪል የሆኑት አንደኛ ተጠሪ መኪናውን የሸጡትና ገንዘቡን የአመልካች ሌላው ወኪል ለሆኑት አቶ ታፈሰ አርጌ የሰጡ መሆኑን በማንሣት ያቀረቡትን ክርክርና የአመልካች ወኪል የነበሩት አቶ ታፈሰ አርጌ መኪናው ተሸጦ ገንዘቡን ተቀብለው ለአመልካች የሰጡ መሆናቸውን በማመን ያቀረቡትን ክርክር በመመልክት የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ሆኖም የሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪ የውክልና ሥልጣን ሣይኖራቸው የፈፀሙትን የመኪና ሽያጭ ውል አመልካች በግልፅ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ መኪናው መሸጡን የተቀበለው መሆኑን የሚያሣይ ተግባራትን በመፈፀም አፅድቆታል ወይም አላፀደቀውም; የሚለውን ጭብጥ በመመሥረት በግራ ቀኙ በኩል ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ በመመዘን የሰጠው ውሣኔ የለም፡፡

አመልካች የመኪናውን ሽያጭ በግልፅ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ አፅድቆታል ወይስ አላፀደቀውም; የሚለውን ነጥብ ለመወሰን በአንደኛ ተጠሪና በአመልካች መካከል የተደረገውን ክርክርና ማስረጃ መመርመሩና መመዘኑ ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ አመልካች መኪናውን አንደኛው ተጠሪ እንደሸጠው የሚያውቅና ከመኪናው ዋጋ ውስጥ 1,200,000 /አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ከአንደኛው ተጠሪ ተቀብዬ ወስጄ ለአመልክች የካቲት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በተፈረመ መተማመኛ ሰጥቸዋለሁ በማለት በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ጣልቃ ገብ ተከራካሪ የሆኑት አቶ ታፈሰ አርጌ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ በማጣራት በመመርመርና በመመዘን ውሣኔ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች የመኪናው የሽያጭ ዋጋ ከሆነው ገንዘብ ውስጥ ብር 1,200,000 /አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ ብር/ የካቲት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ መተማማኛ ተቀብሏል ወይስ አልተቀበለም; የሚለው ነጥብ አመልካች የመኪናውን መሸጥ የሚያውቅ የነበረና ዋጋውን ተቀብሎ ሲጠቀምበት የቆየ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመወሰን አስፈላጊ ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 248 በሚደነግገው መሠርት በክርክሩ ተካፋይ የሆኑት ተከራካሪ ወገኖች ያቀረቡትን የመከላከያ መልስና የፅሑፍ ማስረጃ በመመርመር መያዝ የሚገባውን ጭብጥ ሁሉ በመያዝ ጉዳዩን አጣርተው ያልወሰኑ በመሆኑ ውሣኔያቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የደቡብ ክልል የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የደቡብ ክልል የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሥር አንደኛ ጣልቃ ገብ ተከራካሪ የነበሩት አቶ ታፈሰ አርጌን ወደ ክርክሩ እንዲገቡ በማድረግ አመልካች አንደኛ ተጠሪ ከሸጠው የመኪና ዋጋ ገንዘብ ውስጥ ብር 1,200,000 /አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ከአቶ ታፈሰ አርጌ ተቀብሎ ወስዷል ወይስ አልወሰደም; አመልካች ገንዘቡን ተቀብሎ እንደወሰደ ቢረጋገጥ አመልካች አንደኛ ተጠሪ የውክልና ሥልጣን ሣይኖረው መኪናውን ነሀሴ 12 ቀን 1999 ዓ.ም ለሁለተኛ ተጠሪ ለመሸጥ የተስማማውን ውል እንዳፀደቀው ይቆጠራል; ወይስ አይቆጠርም; የሚለውን ጭብጥ በማጣራትና የግራቀኙን ክርክር በመስማትና ማስረጃ በመመዘን ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልስን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቅ/መ



www.chilot.me

## የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎችን /ከቅጽ 8 - 10 / ዝርዝር የሚያሳይ ስንጠረዥ

### ቅጽ - 8

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት** | | | | 1 |
| 1 | ዳኝነት ባልተጠየቀበት ጉዳይ የሚሰጥ ፍርድ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 182(2) | 33945 | አቶ ሣልህ ሁሴን እና ደግፌ ደርቤ | ጥቅምት 20/2001 | 2 |
| 2 | ማንኛውም ክርክር ሊወሰን የሚገባው በቀረበው ማስረጃ እና በህጉ መሰረት ብቻ ስለመሆኑ | 36848 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና መኰንን ግርማይ (ሦስት ሰዎች) | ጥቅምት 11/2001 | 5 |
| 3 | በክርክር ሂደት ተቃዋሚ ወገን መጠራት ያለበት ምስክር ከመሰማቱ በፊት ስለመሆኑ | 35946 | እነ አቶ ማማሽ ወ/ስላሴ (ሁለት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ ሰብለ ወንድይራድ (ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 27/2001 | 7 |
| 4 | መጥሪያ ለምስክር እንዲደርስ በሚል ፍ/ቤቶች ሊልኩ የሚችሉበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 103 | 36479 | ጉደር አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ኃይሉ ወልዱ | ጥቅምት 25/2001 | 9 |
| 5 | በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ የተወሰነበት ተከራካሪ ፍ/ቤት ህጉን አስመልክቶ በሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለማለት የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78 | 36412 | ተስፋሁን ዋኘው እና በጃክ አግሮ ኮሜርሻል ኢንተርኘራይዝ | ጥቅምት 13/2001 | 12 |
| 6 | የቃል ክርክር ለመስማት እና የጽሁፍ መልስ ለመቀበል በሚል ፍ/ቤቶች በአንድ ቀጠሮ ሁለት ተግባራትን ለማከናወን የሚሰጡት ትዕዛዝ ከሥነ-ሥርዓት ውጪ ስለመሆኑ | 36380 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ታረቀኝ ገ/ፃዲቅ | ጥቅምት 18/2001 | 16 |
| 7 | የበላይ ፍ/ቤቶች ውሣኔን ወደጉን በመተው በሥር ፍ/ቤቶች የሚሰጥ ትዕዛዝ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ | 37725 | እነ በቀለ ድሪብሣ (ሁለት ሰዎች) እና የምክር በሪሁን | ጥቅምት 6/2001 | 18 |
| 8 | በግልፅ የቀረበን ክርክር በተቆጠረ ማስረጃ ወይም አግባብነት ባለው መንገድ እንዲጣራ/እንዲነጥር/ ሣይደረግ የሚሰጥ ውሣኔ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ | 37105 | ሚድሮክ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ ማህበር እና ሰለሞን አበበ ኮከብ | ጥቅምት 25/2001 | 21 |
| 9 | ተከራካሪ ወገኖች የይግባኝ መብታቸውን አስቀርተዋል /ትተዋል/ ለማለት የሚቻለው የነገሩን አካባቢያዊ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ በተረዱበት ደረጃ እርስ በርሳቸው ስምምነት ባደረጉ ጊዜ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 350(1) እና (2) | 37678 | ድራጋዶስ ጄ ኤንድ ፒ.ጆይንት ቬንቸር እና ሳባ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር | ህዳር 18/2001 | 23 |
| 10 | በሥር ፍ/ቤት ዳኝነት ያልተጠየቀበት ጉዳይ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ታይቶ ሊወሰን የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1), 182(2) | 37762 | ገወኔ ኢንተርኘራይዝ ኃ/ተ/የግ/ማህበር እና አቶ የሱፍ ይማም | ታህሣሥ 9/2001 | 26 |
| 11 | ከሥራ ውል ጋር በተያያዘ የሚጠየቁ ክፍያዎች ሳይነጣጠሉ በአንድ ላይ መቅረብ ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216(4), 5 | 38601 | የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት እና ወ/ሮ ከድጃ ሳቢር | ታህሣሥ 14/2001 | 30 |
| 12 | • ክርክር ከሚካሄድበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ መብትና ጥቅም እንዳለ የተረጋገጠ እንደሆነ በክርክር ጣልቃ ለመግባት በቂ ምክንያት ስለመሆኑ<br>• በውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ ጥያቄ (ተቃውሞ) | 37742 | ወ/ሮ አልማዝ ጉንፌ ኦሪቲ እና ወ/ሮ ፀሐይ ሊበን | ታህሣሥ 7/2001 | 32 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አለማቅረብ ሚስት/ባል የሆነን ወገን የጋራ ነው በሚለው ንብረት ላይ ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር የሚያግድ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41 | | | | |
| 13 | በአንድ መንግስታዊ መዋቅር ሥር የሚገኙ ሁለት ራሳቸውን የቻሉና የህግ ሰውነት ያላቸው ተቋሞች የመንግሥትን ጥቅም የሚያስጠብቁ አካላት በመሆናቸው ብቻ እንደ አንድ መቆጠር የሌለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358<br>አዋጅ ቁጥር 1/1995,18/1997,2/1995,4/2000 | 37502 | የአዲስ ከተማ አስተዳደር ፍትህና ህግ ጉዳዬች ቢሮ እና እነ ወ/ሮ የኃላሸት ገመዳ ቤኛ (ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ 2/2001 | 34 |
| 14 | ፍ/ቤቶች ለክርክር ፍትሐዊነት ተገቢ ነው ብለው ሲያምኑ ማናቸውንም አይነት ማስረጃ አስቀርበው መመርመር ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 145,345,327/3/ | 29861 | ወ/ሮ ህጽአት ፍስሐጽዬን እና እነ ወ/ሮ አልማዝ ተረፈ (ሁለት ሰዎች) | ጥር 14/2001 | 37 |
| 15 | የክርክር ዋነኛ ጭብጥ በሆነ ጉዳይ ላይ አከራክሮ የሰጠውን ውሣኔ ፍ/ቤት በድጋሚ "ስህተት ለማረም" በሚል ምክንያት ሊለውጥ ወይም ሊያሻሽል ስላለመቻሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 208 | 37303 | ኤ.ሲ.ዲ አይ/ቮካ-ኢትዮጵያ እና እነ ሃይደር አሊ (ስምንት ሰዎች) | ጥር 26/2001 | 41 |
| 16 | ዳኝነት የሚጠየቅበት መብትና ጥቅም በግልጽ ተለይቶ ያልተመለከተበት አቤቱታ የክስ ምክንያት እንደሌለው የሚቆጠር በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33, 231 | 38419 | የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 19/20 አስ/ጽ/ቤት እና አቶ ያሲን ጀማል | የካቲት 5/2001 | 43 |
| 17 | ፍ/ቤቶች የቀረበላቸውን ክርክር መሠረት በማድረግ አግባብነት ያለውን ጭብጥ ሳይመሰርቱ የሚሰጡት ውሣኔ ህጋዊ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ | 37391 | የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና እነ ስዩም ማሞ (ሁለት ሰዎች) | የካቲት 3/2001 | 46 |
| 18 | በፍ/ቤት በመካሄድ ላይ ባለ ክርክር የግድ ተካፋይ መሆን የሚገባቸው ወገኖች በሚሰጠው ውሣኔ ጥቅማቸው /መብታቸው/ ሊነካ የሚችል የሆነ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.40 | 39540 | ናስ ፋድስ የድ/ዳ/ጨ/ጨ/ፋብሪካ ተከራይ እና እነ ስንዱ ደጀኔ (ዘጠና ሦስት ሰዎች) | የካቲት 26/2001 | 48 |
| 19 | አንድ ጉዳይ ከዚህ ቀደም በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.5 | 36780 | ወ/ሮ አወጣሽ አብርሃ እና አቶ ገ/ኪዳን እንግዳ | መጋቢት 3/2001 | 51 |
| 20 | ነዋሪነታቸው በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሣ ክርክርን የክርክሩ ምክንያት የሆነው ንብረት የሚገኘው ወይም ውል የተደረገው በአንደኛው ክልል እንኳን ቢሆን የመዳኘት ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስለመሆናቸው<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 5(2) | 36460 | መሐመድ ሰዓዳይ ረጃ እና እነ አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ ፈረጀ (ሰባት ሰዎች) | መጋቢት 24/2001 | 59 |
| 21 | በተከራካሪ ወገኖች የተጠየቀን ዳኝነት አስመልክቶ ግልጽ ፍርድ አለመስጠት ስህተት ስለመሆኑ | 39144 | አቶ ልዑልሰገድ ቦኔ እና ኢትዮ ሴዘር ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል ማህበር | መጋቢት 24/2001 | 62 |
| 22 | የቀረበበትን ክስ ያመነ ተከሣሽ ባመነው መሠረት ውሣኔ ለመስጠት የሚከለክል በቂ የህግ ምክንያት እስከሌለ ድረስ ውሳኔ መስጠት የሚገባ ስለመሆኑ | 38597 | እነ ጋሻው መንግስቴ ካሣ (ሁለት ሰዎች) እና ናይል ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር | ሚያዝያ 6/2001 | 65 |
| 23 | በአንድ ዘንግ የሚመደቡ ተከራካሪዎች እና አንድ ጭብጥ ላይ የሚቀርቡ ክርክሮች ተጣምረው እንዲታዩ ያለማድረግ መሠረታዊ የሥነ-ሥርዓት ግድፈት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 11(5) | 40024 | ሽራተን አዲስ እና እነ አቶ እያሱ መገርሣ | ሚያዝያ 29/2001 | 67 |
| 24 | የሥር ፍ/ቤቶች የፈፀሙትን ሥህተት ለማረም በሚል በሥር ፍ/ቤት ተከራካሪ ከነበሩ ወገኖች መካከል አንዱ ወገን ያቀረበውን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ሌላኛው ወገን ሳይጠራና ሳያከራከር ውሣኔ መስጠት ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) | 34504 | አቶ አበባው የሺ.ድንበር እና አቶ ካሣ በቀለ | ሚያዝያ 6/2001 | 71 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 25 | በሥር ፍ/ቤት ያልተነሣን ክርክር መሠረት በማድረግ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሚሰጠው ውሣኔ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 329(1), 182(2) | 37761 | ገብረመስቀል ንጉሴ እና አዲስ ልብስ ስፌት አ.ማ | ሚያዝያ 20/20001 | 73 |
| 26 | ክስ በሚሰማበት የቀጠሮ ዕለት የይግባኝ ባይ አለመቅረብ ጋር በተያያዘ መዝገብ ሊዘጋ የሚችለው መልስ ሰጪው ይግባኙን ሙሉ በሙሉ ክዶ የተከራከረ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ | 38181 | የኢትዮጵያ መንግዶች ባለስልጣን እና እነ ወ/ሮ ትዕግስት ወንድይፍራው (ሁለት ሰዎች) | ግንቦት 4/2001 | 76 |
| 27 | ፍ/ቤት ተከራካሪ ወገን ያቀረበው የሰነድ ማስረጃ የሚጠቅም ያልሆነ እንደሆነና የሰው ምስክር በተጨማሪነት የቆጠረ እንደሆነ ፍትሐዊ የሆነ ውሣኔን ለመስጠት የምስክሮችን ቃል መስማት ያለበት ስለመሆኑ | 42706 | ላየን ሴኩሪቲ ኩባንያ እና አቶ ጥላሁን ገ/እግዚአብሔር | ግንቦት 25/2001 | 78 |
| 28 | በአንድ ፍ/ቤት የተሰጠን ፍርድ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት መለወጥ ወይም መሻሻል ተከትሎ ማናቸውም ተከራካሪ ወገኖች ፍርዱ ከመሰጠቱ በፊት ወደነበሩበት እንዲመለሱ የሚሰጥ ትዕዛዝ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ እንጂ የግድ የሚሰጥ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 349(1) | 37741 | አቶ መኮንን ዘውዴ እና እነ<br>አቶ ተሾመ ሽፈራው (ሦስት ሰዎች) | ሰኔ 4/2001 | 80 |
| 29 | ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቶች የቀረበላቸውን ጉዳይ ለማስተናገድ ስልጣን ያላቸው ወይም የሌላቸው መሆኑን በመመርመር ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 9(2) | 38452 | የአ.አ ከተማ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>አቶ አለም ገብሩ | ሰኔ 11/2001 | 82 |
| 30 | አንድን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማንሣት ስልጣን የለኝም ያለ ፍ/ቤት ጉዳዩ በበላይ ፍ/ቤት ታይቶ በፍሬ ጉዳዩ ላይ እንዲያከራክር ጉዳዩ የተመለሰለት እንደሆነ ሌላ ተጨማሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን መሠረት በማድረግ ጉዳዩን ለማየት አልችልም ማለት የማይገባው ስለመሆኑ | 39014 | አለሙ መግራ<br>እና<br>እምነቱ እንዳሻው ህንፃ ተቋራጭ | ሰኔ 23/2001 | 84 |
| 31 | የይግባኝ ማመልከቻ ማቅረቢያ ጊዜው ያለፈበት ተከራካሪ ወገን የሚያቀርበው የማስፈቀጃ ማመልከቻ በበቂ ምክንያት የተደገፈ መሆን/አለመሆኑን ፍ/ቤቶች በጥሞና መመርመር ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 326(1) | 38145 | ወ/ሮ አያልነሽ ዘገየ<br>እና<br>አቶ ተስፋዬ ደምሴ | ሰኔ 30/2001 | 86 |
| 32 | አንድ ተከራካሪ ወገን በማስረጃነት የሚጠቅሳቸው ምስክሮች፣ ሰነዶች ወይም ሌላ አስረጂዎች (የሙያ) ማስረጃው በፍ/ቤቱ በኩል በጭብጥነት ተይዞ ከሚፈታው ፍሬ ነገር ጋር አግባብነት ያለው እና በህግ ተቀባይነት ያለው እስከሆነ ድረስ ቀርቦ መሰማት ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 111, 249 እና 257 | 38683 | የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት<br>እና<br>አቶ ሣህሉ ወ/ማርያም | ሰኔ 25/2001 | 88 |
| 33 | ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በአግባቡ ሳይመረምሩ እና ለውሣኔያቸው በቂ ምክንያት ሣይሰጡ መሻር የማይችሉ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 182(1) | 38844 | የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን<br>እና<br>ጋድ ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህ | ሰኔ 25/2001 | 90 |
| 34 | ተከራካሪ ወገኖች በፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲቀርብላቸው የሚጠይቁት ማስረጃ የተያዘውን ጉዳይ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ዕልባት ለመስጠት የሚያስችል እስከ ሆነ ድረስ ጥያቄውን ፍ/ቤቶች ሊቀበሉት የሚገባ ስለመሆኑ | 36979 | ቤዛ አማካሪ መሀንዲሶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ሚስተር ሽሬሃሪ ብራማቫሪ ጉፓል | ሐምሌ 23/2001 | 94 |
| 35 | ሦስተኛ ወገኖች በፍ/ቤት በመካሄድ ላይ ባለ ክርክር እንዲገቡ የሚያስፈልግበት ሁኔታ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43 | 41544 | ሰላም የህዝብ ማመላለሻ (አ.ማ) እና ኒያላ ኢንሹራንስ አ.ማ | ሐምሌ 8/2001 | 96 |

| | አሰሪና ሰራተኛ | | | | 98 |
|---|---|---|---|---|---|
| 36 | የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ የሆነ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀፅ 2/ሰ/ | 35197 | አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ<br>እና ኤፍሬም ንዋየማሪያም | ጥቅምት 13/2001 | 99 |
| 37 | ለፕሮጀክት ሥራ የተቀጠሩ ሠራተኞች የተቀጠሩበት የፕሮጀክት ሥራ ሲጠናቀቅ የሥራ ውላቸው የሚቋረጥ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 10/1//ሠ//ሀ/ | 35621 | ሰንሻይን ኮንስትራክሽን እና<br>እነ አቶ ፍቃዱ ገቢሣ<br>(ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 11/2001 | 102 |
| 38 | በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ.377/96 ባልተሸፈነ ጉዳይ ላይ በአሠሪና በሠራተኛ መካከል የተደረገ የህብረት ስምምነት መፈፀም ያለበት ስለመሆኑ | 36692 | አንበሳ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት እና ተስፋዬ መኰንን | ጥቅምት 25/2001 | 104 |
| 39 | ሠራተኞች ለሚፈፅሙት ጥፋት በህብረት ስምምነት የተለያዩ የቅጣት ደረጃዎች የተቀመጡ በሆነ ጊዜ አሰሪው በሠራተኛው የተፈፀመውን ጥፋት ክብደት በመመዘን ይመጥናል የሚለውን ቅጣት መወሰን የሚችል ስለመሆኑ | 37027 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን<br>እና ወ/ት አሰለፈች ደስታ | ጥቅምት 11/2001 | 106 |
| 40 | አንድ ድርጅት እንደስራው ፀባይ በህግ ከተደነገገው ማፅቀፍ ሳይወጣ/ሳይጥስ/ የሥራ ሰዓቱን ማሻሻል ስለመቻሉ<br>አዋጅ 377/96 አንቀፅ 61/1/ | 36518 | ሜታ አቦ ቢራ አ.ማ እና<br>እነ ሳሙኤል ተፈራ (አራት ሰዎች) | ጥቅምት 4/2001 | 108 |
| 41 | የአሰሪ ንብረት የሆነን ገንዘብ ማጉደል ያለማስጠንቀቂያ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27/1/ተ/ | 35484 | የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና<br>አቶ ደረጀ ማሞ | ህዳር 25/2001 | 110 |
| 42 | አሰሪ ሠራተኛውን በማምንት ዕረፍቱ ሥራ እንዲሰራ ለማድረግ የሚችል ስለመሆኑ | 37815 | አለማየሁ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ<br>እና አቶ አብዮት በፈቃዱ | ህዳር 2/2001 | 112 |
| 43 | በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ ውስጥ “የሥራ ቀናት” የሚለው ሃረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(3) | 36377 | የኢትዮጵያና የጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት እና ተሾመ ኩማ | ህዳር 2/2001 | 114 |
| 44 | የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም/ እና የጡረታ አበል ተጠቃሚ የሆነ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ ለማግኘት መብት የሌለው ስለመሆኑ | 37048 | የሚድሮክ ኮንስትራክሽን ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና አቶ ሣህሉ ምትኩ | ህዳር 2/2001 | 116 |
| 45 | በወንጀል ጉዳይ ተከሶ ነፃ መውጣት በራሱ አንድን ሠራተኛ ወደ ቀድሞ ሥራ ለመመለስ መብት የሚሰጥ ስላለመሆኑ | 37256 | አዲስ አበባ የምግብ አዳራሽ አስተዳደር እና ወ/ሮ የውብዳር ጥላሁን | ህዳር 4/2001 | 119 |
| 46 | ለአምስት ተከታታይ ቀናት በሥራ ገበታ ላይ ያለበቂ ምክንያት አለመገኘት ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ሊያሰናብት የሚችል ስለመሆኑ | 37402 | የንኮማድ ኃ/የተ/የግል/ማህበር<br>እና አቶ ቡሽራ በቀለ | ህዳር 11/2001 | 122 |
| 47 | ከሥራ ጋር በተገናኘ በሚፈፀም ድርጊት መነሻነት በሠራተኛው ላይ በፖሊስ የሚደረግ ምርመራ የይርጋ ጊዜን የማያቋርጥ ስለመሆኑ | 37573 | የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት እና<br>አቶ መሐመድ አደን | ህዳር 16/2001 | 125 |
| 48 | የሥራ ውል በስምምነት ተቋረጠ ለማለት የሚቻለው ስምምነቱ በፅሁፍ የተደረገ እንደሆነ ስለመሆኑ | 37575 | ቃሊቲ ባሌስትራ ማምረቻ<br>እና ብርሃኑ ልደት ወልዴ | ህዳር 2/2001 | 127 |
| 49 | በአሰሪ በተደረገ የሥራ ዝውውር ቅሬታ አድሮብኛል በሚል ምክንያት ከሥራ መቅረት የህግ ድጋፍ የሌለው ስለመሆኑ | 37778 | አዲስ መለዋወጫ ዕቃዎች አስመጪ አከፋፋይ አ.ማ<br>እና አቶ ካሣሁን ከበደ | ህዳር 4/2001 | 129 |
| 50 | በአሰሪና በሠራተኛ መካከል የሥራ ውል ግንኙነት አለ ለማለት የሚቻልበት አግባብ | 03171 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፓሬሽን እና<br>ወ/ት ትርሲት ደገፋ | ህዳር 16/2001 | 132 |
| 51 | አዲስ መዋቅርን ተግባራዊ ያደረገ ተቋም/ድርጅት/ ሠራተኞቹን “ራሱ ባወጣው መስፈርት” መሰረት ሊመድብ ስለመቻሉ | 36210 | አቃቂ መለዋወጫ ዕቃዎችና መሣሪያዎች አ.ማ እና አቶ ኃይለ ሳልቫቶር | ህዳር 2/2001 | 136 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 52 | • አንድ ሠራተኛ በአሰሪው ንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል በሚል ያለማስጠንቀቂያ ሊሰናበት የሚችልበት አግባብ<br>• በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ ውስጥ "የአሰሪ ንብረት" በሚል የተገለፀው ሐረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27/1//ሸ/ | 34669 | አድማስ ኮሌጅ እና ሠለሞን ሙሉአለም | ታህሣሥ 2/2001 | 138 |
| 53 | የተረከበው የአሠሪ ንብረት የጠፋበት ሰራተኛ ንብረቱን ለግል ጥቅሙ ወይም ለሌላ ሶስተኛ ወገን ጥቅም ያዋለው ያለመሆኑን ካላስረዳ በቀር የንብረቱ መጥፋት ሠራተኛውን ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ለማሰናበት የሚያስችል በቂ ምክንያት ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(መ)(ቀ) 14(2)(ለ)(2) | 39118 | ደሣለኝና ቤተሰቡ ኃላ/የተ/የግል ማህበር<br>እና<br>አቶ በፈቃዱ በላይ | ታህሣሥ 23/2001 | 141 |
| 54 | በህብረት ስምምነት ወይም በሌላ አካኂን የተወሰነ የሥራ ውል የሚቋረጥበት ምክንያት ካለ በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ያልተመለከተ ቢሆንም ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 3787/96 አንቀፅ 27/1/ | 36591 | ማታዶር አዲስ ጎማ አ.ማ<br>እና<br>ደረጀ ኡመታ | ታህሳስ 14/2001 | 144 |
| 55 | የሥራ መሪ በሆነ የሥራ መደብ ላይ በጊዜያዊነት መስራት ግለሰቡን የሥራ መሪ ከመሆን የሚያስቀረው ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 3/2/ /ሐ/ | 36894 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ሙላት ታረቀኝ | ታህሳስ 30/2001 | 146 |
| 56 | ለተወሰነ ጊዜ በተደረገ የሥራ ውል ግንኙነት ለሠራተኛው የሚከፈል የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ተዋዋይ ወገኖች በስምምነታቸው ባስቀመጡት መልክ የሚፈፀም ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 35/2/ | 37201 | ማታዶር አደስ ጎማ አክሲዮን ማህበር እና እነ አቶ ኤልያስ በቀለ<br>(አስራ አራት ሰዎች) | ታህሣሥ 30/2001 | 148 |
| 57 | የጥበቃ ሥራን የሚሠራ ሠራተኛን በተመለከተ የሥራ ውሉ ያለአግባብ ተቋርጧል በሚል ሲወሰን በአሠሪውና ሠራተኛው መካከል ሊኖር የሚገባው ከፍተኛ መተማመን የሚሻክር በመሆኑ ሰራተኛው ወደ ሥራ እንዲመለስ የሚሰጥ ውሳኔ ተገቢ ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43 | 37454 | ሰላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል እና ከበደ ሰይፉ | ታህሣሥ 16/2001 | 151 |
| 58 | ወደ ሥራ እንዲመለስ የተፈረደለት ሠራተኛ ለመመለስ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቶ የሥራ ክርክሮችን የሚወስነው አካል ሠራተኛው አግባብነት ያላቸውን ክፍያዎች ተከፍሎት ከሥራ እንዲሰናበት ሊወሰን የሚችለው በመጀመሪያው ፍርድ መሠረት ያልተፈፀመ እንደሆነ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43/3/ | 38255 | አበባ ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና<br>አለምሰገድ ኃይሉ | ታህሣሥ 23/2001 | 154 |
| 59 | የሥራ ውሉን በፍቃዱ ያቋረጠ ሠራተኛ የህብረት ስምምነት የሚፈቅድለት ከሆነ ኘሮቪደንት ፈንድና የሥራ ስንብት የማግኘት መብት የሚኖረው ስለመሆኑ | 37551 | አቶ ድካምየለህ ጥበቡ እና አርሾ የህክምና ላብራቶሪ ኃ/የተ/የግል/ማህበር | ታህሣስ 9/2001 | 157 |
| 60 | የስራ ውል የተቋረጠው ከህግ ውጪ ነው ተብሎ በተወሰነ ጊዜ የስራ ውሉ የተቋረጠበት ወገን/ሠራተኛ/ ሊወሰኑለት የሚገቡ ክፍያዎች | 34476 | ኩመላ በጅሣ እና ብሔራዊ አስጐብኚና ጉዞ ወኪል | ታህሳስ 2/2001 | 160 |
| 61 | አንድ የሥራ ዘርፍ የአሠሪው ቋሚ ሥራ ቢሆንም በዚሁ ዘርፍ ሠራተኞችን ለተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል ቀጥሮ ሊያሰራ የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 10(1)(ሐ) | 40305 | የኢትዮጵያ ፐልኘና ወረቀት አ.ማ<br>እና<br>እነ አቶ ታመነ ጫላ | ታህሣሥ 21/2001 | 163 |
| 62 | አንድ ሠራተኛ ይሰራው የነበረ የሥራ መደብ መሰረዝ ወይም አለመኖር ለሥራ ውሉ መቋረጥ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 28(1) (መ) | 40804 | ዳንዲቦሩ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ እና እነ ተክሉ ኡርጌ ኢደኤ<br>(ሁለት ሰዎች) | ጥር 26/2001 | 165 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 63 | አንድ ሠራተኛ ወደ ሥራ ሲሄድና ከሥራ ወጥቶ ወደቤቱ ሲመለስ አሰሪው በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት ሲጠቀም አደጋ የደረሰበት መሆኑ ከተረጋገጠ ሦስተኛ ወገኖች ለአደጋው ያደረጉት አስተዋፅኦ መኖር አሰሪው የጉዳት ካሣ ላለመክፈል እንደመከላከያ ሊሆነው ስላለመቻሉ እና የጉዳት ካሣው በጉዳት የተነሣ ህይወቱን ላጣው ሠራተኛ ጥገኞች የሚከፈልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 95/2/, 96/1/, 98/2/, 97/1/, 107/1//ሐ/, 110/ 112 | 36194 | ዶ/ር ማንደፍሮ እሸቴ<br>እና<br>ፍሬድሪክ ኤቨርት<br>ሲቲፍቱንግ | ጥር<br>28/2001 | 167 |
| 64 | በድርጅት ውስጥ በተደረገ የመዋቅር ማሻሻያ የሥራ መደብ የተሰረዘ እንደሆነ የሥራ መደብ የተሰረዘበትን ሠራተኛ በማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የሚቻልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 28(1)(መ) | 38811 | ርሆቦት ሆሊ ሴቪየር ኃ/የተ/የግል ማህበር እና<br>አቶ አማረ አድማሱ | የካቲት<br>17/2001 | 173 |
| 65 | በአንድ ድርጅት ውስጥ ያለ የሥራ መደብ በሌላ 3ኛ ወገን እንዲከናወን አስተላልፎ መስጠት (out sourcing) የስራ ውል ለማቋረጥ ህጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 28 | 38435 | ኤስ.ኦ.ኤስ የህፃናት መንደር እና እነ አቶ ከበደ ኩምሣ (ስድስት ሰዎች ) | የካቲት<br>17/2001 | 175 |
| 66 | ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የሥራ ውል የሚቋረጠው ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስለመሆኑ | 38023 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና ብርሃኑ ደስዬ | የካቲት<br>17/2001 | 178 |
| 67 | በአሰሪያቸው ላይ ክስ አቅርበው ያስፈረዱ ሠራተኞች የአሰሪውን ንብረት በዋስትና ከያዙ ባለገንዘቦች ይልቅ የቅድሚያ ክፍያ መብት ያላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 167<br>አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 3<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. አንቀጽ 2857(1)<br>አዋጅ ቁ. 186/94 አንቀጽ 80<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ- መንግስት አንቀፅ 13(2) | 40921 | አቢሲንያ ባንክ (አ.ማ)<br>እና<br>አብዱ አህመድ<br>(ሁለት መቶ ስልሣ ስድስት ሰዎች) | የካቲት<br>26/2001 | 180 |
| 68 | የአንድ ሠራተኛን ድርጊት ከባድ ቸልተኝነት ነው ለማለት የሥራውን ባህሪ ከግምት ውስጥ ማስገባት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ | 41115 | ሜድሮክ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል/ማህበር እና<br>አቶ ሞገስ ሽፈራው | የካቲት<br>26/2001 | 183 |
| 69 | አሠሪ የአንድን ሠራተኛ ደሞዝ እና ሌሎች ጥቅማጥቅም ሣይነካ በተመሳሳይ የሥራ መደብ ላይ አዛውሮ ሊያሠራ የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 13(2) እና (7) | 40938 | ሙገር ሲሚንቶ<br>ኢንተርፕራይዝ<br>እና<br>አቶ ኃይሉ መንግስቱ | መጋቢት<br>24/2001 | 186 |
| 70 | አንድ ሠራተኛ የአሠሪው ንብረት የሆነን ገንዘብ ማጉደሉ የተረጋገጠ እንደሆነ አሠሪው ሠራተኛውን በፍ/ብሔር ክሶ ገንዘቡን የማስመለሱ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ሊያቋርጥ የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1)(መ) | 42292 | የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ ከበደ አቡነቱ | መጋቢት<br>24/2001 | 188 |
| 71 | በአሠሪው ወደሌላ ቦታ ተዛውሮ እንዲሠራ የተደረገ ሠራተኛ ዝውውሩን በወቅቱ ሣይቃወም የተዛወረበት የሥራ ገበታ ላይ ለ5 ተከታታይ ቀናት የቀረ እንደሆነ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያበቃ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27 (1)(ለ) | 41623 | አበባ ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና አቶ ሣሙኤል ኪዳኔ | መጋቢት<br>8/2001 | 191 |
| 72 | • ከ30 ቀናት በላይ ሠራተኛን ከሥራ የማገድ ተግባር ሠራተኛን እንደማሰናበት የማይቆጠር ስለመሆኑ<br>• አሠሪው ከ30 ቀናት በላይ ሠራተኛው ለታገደበት ጊዜ ደሞዝ እንዲከፍል የሚደረግበት አግባብ<br>• ከሥራ ያለአግባብ ታገድኩኝ በሚል የቀረበን ክስ በማስተናገድ ላይ ያለ ፍ/ቤት በክርክሩ | 41411 | ሙሉሙል ዳቦ መጋገሪያ ድርጅት<br>እና<br>አቶ በለጠ ተገኝ | ግንቦት<br>11/2001 | 193 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሂደት ሠራተኛው ከሥራ የተሰናበተ መሆኑን ካወቀ የተያዘው ጭብጥ እንዲሻሻል እና ጭብጡ እንዲስተካከል በማድረግ ጉዳዩን ማየት ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(4) | | | | |
| 73 | • አንድ ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ ቋሚ የአካል ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ ከጉዳቱ በኂላ የቀድሞ ስራውን መስራት መቀጠሉ ብቻ አሰሪውን የጉዳት ካሣ ከመክፈል ነፃ የማያወጣው ስለመሆኑ<br>• በሥራ ላይ ከሚደርስ ጉዳት ጋር በተገናኘ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ውስጥ የተመለከተውና "የመስራት ችሎታ" የሚለው ሃረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ እና የጉዳት ካሣ መጠንና ሊወሰን የሚችልበት የህግ አግባብ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 109, (1) እና (3) , 107, 99(1), 102(3)<br>አዋጅ ቁ.345/95 አንቀጽ 33 | 43370 | የግብርና ምርት ማሣደጊያዎች አቅራቢ. ድርጅት<br>እና<br>አቶ ጌታቸው ገድሌ | ግንቦት 12/2001 | 196 |
| 74 | • የድርጅት ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የአሰራር ዘዴዎችን ለመለወጥ ወይም በአዲስ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም የሠራተኛ ቅነሣ የሚደረግበት አግባብ<br>• ቅነሣ የሚደረግበትና ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 28(2)(ሐ), 29(3) | 42752 | እነ ወ/ት ማሚ አሠፋ (ሰላሳ ስድስት ሰዎች)<br>እና<br>ብሔራዊ አስጎብኚ የጉዞ ወኪል(NTO) | ግንቦት 12/2001 | 199 |
| 75 | በሠራተኛ እጅ የሚገኙ የአሠሪ ንብረቶች መመለስ ወይም አለመመለስ ጉዳይ ሠራተኛው የሥራ ውሉ በተቋረጠ ጊዜ የሚያነሣቸውን ልዩ ልዩ ክፍያዎችን ለማስተናገድ ግምት ውስጥ መግባት ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 36, 38 | 39464 | ሐረር ቢራ አክሲዮን ማህበር<br>እና<br>አቶ አብዱልቃድር አብዱረዛቅ | ግንቦት 25/2001 | 202 |
| 76 | ቀድሞ ይሰራበት የነበረን የሥራ መደብ በመሰረዙ ምክንያት ሠራተኞችን በማሰናበት ፋንታ በክፍያ አነስተኛ ወደሆነ ሌላ የሥራ መደብ እንዲሰሩ ያደረገ አሠሪ ለሠራተኞቹ በቀድሞው ደመወዝ መሠረት እንዲከፍል የሚገደድበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ | 41786 | የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና እነ አቶ አሰፋ አቤቦ (ሦስት ሰዎች) | ግንቦት 26/2001 | 204 |
| 77 | በጥበቃ ሥራ የተቀጠረ ሠራተኛ እንዲጠብቅ የተሰጠው የአሰሪ ንብረት የጠፋ እንደሆነ ሰራተኛው ለንብረቱ መጥፋት አስተዋጽኦ ያለማድረጉን ማረጋገጥ ካልተቻለ በስተቀር በሃላፊነት ሊያስጠይቀው የሚችል ስለመሆኑ | 39650 | የየረር በር ምስራቅ ፀሐይ ቅዱስ ዑራኤል ቤ/ክ እና እነ ቄስ ሰሬነው ደሣለኝ | ግንቦት 27/2001 | 207 |
| 78 | በተጭበረበረ ማስረጃ ሥራ የተቀጠረ ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ የማጭበርበር ድርጊቱ የታወቀ/የተደረሰበት/ ከሆነ ማጭበርበሩ የተከሰተው ሥራውን በማከናወን ላይ እንዳለ ተቆጥሮ ሊያስናብተው የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27(1) (ሐ) | 39543 | የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት<br>እና<br>አቶ በረከት ተ/ማርያም | ግንቦት 4/2001 | 209 |
| 79 | ለፕሮጀክት ሥራ የተቀጠሩ ሠራተኞች ቅነሣ በሚካሄድበት ወቅት አሰሪው በአዋጅ ቁ.377/96 ላይ የተመለከተውን የሠራተኞች ቅነሣ ሥነ-ሥርዓት መከተል የማይጠበቅበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 30(1) | 39042 | ዮቴክ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ጀማል መሐመድ | ግንቦት 26/2001 | 211 |
| 80 | የሥራ መደብ ዝውውርን በመቃወም ቅሬታን በማሰማት ላይ መሆን በስራ ቦታ ላይ ላለመገኘት እንደ በቂ ህጋዊ ምክንያት የሚወሰድ ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ለ) | 38189 | ሮፖክ ኢንተርናሽናል ኃላ/የተ/የግል ማህበር እና ይደርሳል አእምሮ | ግንቦት 27/2001 | 213 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 81 | አሠሪ የሥራ መሪ የሆነን ሠራተኛውን ያሰናበተው ያለበቂ ምክንያት ቢሆንም እንኳን ተገቢ የሆነ ካሣ ለመክፈል ከሚገደድ በስተቀር ሠራተኛውን ወደ ሥራ እንዲመልስ ሊገደድ የማይችል ስለመሆኑ | 37982 | የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻ እና ማከፋፈያ ድርጅት እና አቶ ታደሰ ዘነበ | ሰኔ 16/2001 | 216 |
| 82 | ለሥራ ማስኬጃነት የተቀበሉትን የአሰሪ ገንዘብ አጉድሎ መገኘት ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(መ) | 41720 | የእንጨት መሠንጠቂያና መገጣጠሚያ ድርጅት እና ረዲ እንዳለ | ሰኔ 9/2001 | 219 |
| 83 | የሥራ ውል የተቋረጠው በህጉ አግባብ ነው ተብሎ የተወሰነ እንደሆነ የሥራ ስንብትና የካሣ ክፍያ የማይከፈል ስለመሆኑ | 39861 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ሣምሶን በለጥካቸው | ሰኔ 18/2001 | 221 |
| 84 | በቃል ከሥራ ተሰናበትኩ በሚል ክስ የሚያቀርብ ሠራተኛ አሰሪው ከሥራ ያሰናበተው ስለመሆኑ የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ | 43610 | ናይኮ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ ሰለሞን ተሰማ | ሐምሌ 21/2001 | 224 |
| 85 | አሠሪ የሆነ ወገን የሥራ ቅልጥፍናን፣ ውጤታማነትን፣ የኢንዱስትሪ ሰላምን ወይም ሌሎች ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት አንድን ሠራተኛ የተቀጠረበትን ደመወዝና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች በጠበቀ ሁኔታ አዛውሮ ለማሰራት የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 2 (1), 4 | 44033 | መንበረ ፓትሪያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት እና አቶ ይበልጣል አጥናፉ | ሐምሌ 22/2001 | 226 |
| 86 | በህግ ወይም በሕብረት ሥምምነት የተመለከተው የጡረታ እድሜ ሣይደርስ በመንግሥት መመሪያ በጡረታ እንዲገለሉ የተደረጉ ሠራተኞችን በተመለከተ አሰሪ ልዩ ልዩ ክፍያዎች ለመክፈል የማይገደድ ስለመሆኑ | 42906 | የኢትዮ-ጃፓን ጨርቃ ጨርቅ አ.ማ እና እነ ትዕግስት ማሞ (ሰማንያ አንድ ሰዎች) | ሐምሌ 21/2001 | 228 |
| 87 | የኮንስትራክሽን ሥራ የሚሰራ ድርጅት የሥራው መጠን በቀነሰ ጊዜ ሠራተኞችን ለማሰናበት የማስጠንቀቂያና ሌሎች የቅነሳ ሥነ-ሥርዓቶችን ሳይከተል ቅነሳ ለማካሄድ የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 30 | 42075 | አፍሪካዊት የህንፃ ስራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና እነ አቶ እንድሪስ ዓሊ | ሐምሌ 16/2001 | 231 |
| 88 | የሥራ ውል □ንደተቋረጠ የጡረታ አበል ለማግኘት መብት ያለው ሠራተኛ የሥራ ስንብት የማይከፈለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 39<br>አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2(2) (ሰ) | 39808 | ናዝሬት ሣሙና ፋብሪካ እና ዘውዱ ኃ/ማርያም | ሐምሌ 21/2001 | 233 |
| 89 | የሥራ መሪ ከሠራተኛ ሊለይ የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3, አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2 | 42901 | የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻ እና ማከፋፈያ ድርጅት እና ወ/ሮ ንግስት ለጥይበሉ | ሐምሌ 21/2001 | 235 |
| 90 | በአሰሪና ሠራተኛ መካከል በሚካሄድ የሥራ ክርክር የሚያዘው ጭብጥ አሰሪው ገንዘብ ይከፈለኝ በሚል በሠራተኛው ላይ ክስ ባቀረበ ጊዜ ከሚያዘው ጭብጥ ጋር አንድ አይነት ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ | 39471 | ኤርሚያስ ሙሉጌታ እና በከልቻ ትራንስፓርት አ/ማ | ሐምሌ 29/2001 | 237 |
| 91 | በሃይማኖት ተቋም ውስጥ መንፈሳዊ(ሃይማኖታዊ) አገልግሎት የሚሰጥ ሰራተኛ ከተቋሙ ጋር ያለው የስራ ግንኙነት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ የሚሸፈን ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 | 18419 | ሐመረወርቅ ቅ/ማሪያም ቤ/ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት እና እነ ዲያቆን ምህረት ብርሃን (ስድስት ሰዎች) | ግንቦት 4/1998 | 239 |
| | **ቤተሰብ** | | | | 242 |
| 92 | የውርስ ሀብት ክፍፍልን መነሻ ያደረገ ክስ የግዴታ ውርስ ከተጣራ በኋላ መቅረብ የሌለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 1000(1) | 34703 | እንዳሻው ፍቃዱ እና እነ ወንድማገኝ ፍቃዱ(ሰባት ሰዎች) | ጥቅምት 11/2001 | 243 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 93 | ኑዛዜ ሲነበብ የነበሩ ሰዎች ኑዛዜው አይፀናም በሚል የሚያቀርቡት የመቃወም አቤቱታ ኑዛዜው በተነበበ በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 973 | 36604 | ወ/ሮ ፅጌ መንግስቱ እና እነ አቶ ወንድይራድ መንግስቱ(ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 25/2001 | 245 |
| 94 | ከጋብቻ በፊት የግል የነበረን ንብረት መነሻ በማድረግ በጋብቻ ጊዜ በግብይት የተገኘ ንብረት የግል ሆኖ ሊቀጥል የሚችለው በፍ/ቤት ቀርቦ የፀደቀ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 58(2), 57, 62(2) | 37275 | ሻ/ባሻ ገዛኸኝ ድልነሣው እና<br>ወ/ሮ ተዋበች ደመቀ | ጥቅምት 18/2001 | 247 |
| 95 | ግልፅ ኑዛዜ ህጋዊ እንዲሆን መሟላት ያለበት ፎርማሊቲ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 | 36777 | አቶ ወንድም አገኝ ዘውዱ እና እነ አቶ ታፈሰ ወንድአፈራሽ(ሶስት ሰዎች) | ጥቅምት 25/2001 | 251 |
| 96 | ህፃናትን ማዕከል ያደረጉ ክርክሮች የልጆችን ጥቅም ባስጠበቀ መልኩ መስተናገድ ያለባቸው ስለመሆኑ | 35710 | ወ/ሮ እፀገነት እሸቱ እና ወ/ሮ ሰላሚዊት ንጉሴ | ታህሣስ 16/2001 | 253 |
| 97 | የስጦታ ውል የተፈፀመው ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ፊት ከሆነ ይኼው ግለሰብ እንደ ምስክር ተደርጐ ባይፃፍም ምስክር ተደርጐ ሊቆጠር የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443,881,882 | 37562 | አቶ ሣሙኤል ፈረንጅ እና አቶ ግርማ ታፈሰ (ሁለት ሰዎች) | ጥር 28/2001 | 258 |
| 98 | ጋብቻ ህጋዊ ውጤት የሚኖረው በህግ አግባብ ተፈፅሟል ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 28(3) | 41896 | ወ/ሮ ታደለች ዋለልኝ እና እነ ወ/ሮ አዲስዓለም ፀጋ (ሦስት ሰዎች) | የካቲት 26/2001 | 261 |
| 99 | የሟች እዳን ለመክፈያ በአፈፃፀም ሊያዝ የሚገባው በውርስ የተገኘውን ሀብት እንጂ የወራሾች የግል ሃብት ስላለመሆኑ | 38691 | አቶ ለገሰ ቢራቱ እና አቶ ደረጀ ጅማ ገርግሶ | የካቲት 24/2001 | 263 |
| 100 | የአንደኛው ተጋቢ ስምምነት ሣይኖር የጋራ የሆነ የማይንቀሣቀስ ንብረት በሌለኛው ተጋቢ የተሸጠ እንደሆነ ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢ ካወቀበት ቀን ጀምሮ በ 6 ወር ውስጥ እንዲሁም በማናቸውም ሁኔታ ደግሞ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ለመጠየቅ ስለመቻሉ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 69(2) | 38126 | ዲያቆን ኃይለጊዮርጊስ ወንድምሲያምረኝ እና እነ ወ/ሮ የሺ ተፈሪ (ሁለት ሰዎች) | መጋቢት 22/2001 | 266 |
| 101 | በኑዛዜ የተገኘ ንብረት በ10 (አሥር) ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልተጠየቀ በስተቀር በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ | 38152 | የወ/ሮ ገነት ዳምጤ ወራሾች እና እነ አቶ ይልማ አስፋው | ሚያዝያ 29/2001 | 268 |
| 102 | የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በሥር ፍ/ቤት የተሰጠን ፍርድ ከመረመረ በኋላ የጉዳዩን ጭብጥ በመያዝ ወደ ሥር ፍ/ቤት የመለሰው እንደሆነ አስቀድሞ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ፍርድ እንደሌለ የሚያስቆጥረው ስለመሆኑ | 37313 | እነ አቶ መሐሪ ተ/ማሪያም (ሁለት ሰዎች) እና የወ/ሮ ገነት መኮንን ወራሾች (ሁለት ሰዎች) | ግንቦት 18/2001 | 271 |
| 103 | ወራሽ የሆኑ ወገኖች የሚያቀርቧቸውን ተገቢነት ያላቸው ማስረጃዎች በሙሉ አሰባስቦ በመስማት ያልተከናወነ የውርስ ማጣራት ሪ□ርት በህግ አግባብ የተከናወነ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 241, 270 እና 345 | 42525 | እነ አቶ አብዱልዋሲቅ አርጋው እና<br>ወ/ሮ አልዋያ አባበሊስ | ግንቦት 27/2001 | 274 |
| 104 | የተናዛዡ ህጋዊ ንብረት ባልሆነ ነገር ላይ የተደረገ ኑዛዜ በፍ/ቤት ቢፀድቅም እንኳን የኑዛዜ ሰነዱ ዋጋ የማይኖረው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 865 | 32817 | ወ/ሮ አልማዝ ዘውዴ እና እነ ወ/ሮ ቴቱ ዘውዴ(ሦስት ሰዎች) | ሰኔ 11/2001 | 277 |
| 105 | የገበያ ዋጋን መሠረት ያላደረገና የግንባታ ዋጋ ግምት ላይ ብቻ ተመርኩዞ የሚደረግ የውርስ ሀብት ክፍፍል ፍትሐዊ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ | 40510 | ቴዎድሮስ መንበሩ እና ገ/ህይወት ታደሰ | ሰኔ 23/2001 | 281 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 106 | ጋብቻ በሁለት የተለያዩ ሥርዓቶች የተፈፀመ ቢሆንም አንድ ጊዜ በህግ አግባብ የተደረገ ፍቺ በቂና ሙሉ ህጋዊ ውጤት የሚያስከትል ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 75(ሐ) | 40781 | ፍቅረስላሴ ካህሣይ እና ወ/ሮ ሮማን ታደሠ | ሐምሌ 30/2001 | 283 |
| 107 | በውርስ ሃብት ክፍፍል ላይ ተወላጅ የሆነ ሰው ከሩብ በላይ ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ ክፍፍሉ እንዲቀር ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ሕ/ቁ. 11/22,913,1060,1037-1051,942 | 18394 | ወ/ሮ ዝናሽ በቀለ ማንደፍሮ እና ወ/ሮ ሐረገወይን በቀለ | መጋቢት 21/1999 | 286 |
| | **ውል** | | | | 290 |
| 108 | የደረሰው ወይም ይደርሣል ተብሎ የሚጠበቀው ኪሣራ በጉዳት ኪሣራ ሊካስ የሚችል በሆነ ጊዜ ውሉን አስገድዶ ለማስፈፀም የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1776 | 35472 | አቶ መሐመድ ካሣሁን እና አቶ ሰለሐዲን ኑር | ጥቅምት 6/2001 | 291 |
| 109 | የፍ/ብ/ህ/ቁ.1723"ን" መስፈርት አላሟላም በሚል ውል እንዲፈርስ የተደረገ እንደሆነ ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት እንዲመለሱ ውሣኔ ሊሰጥ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723,1815 | 34803 | መ/ር መኳንንት ወረደ እና እነ መስከረም ዳኛው (አራት ሰዎች) | ጥቅምት 11/2001 | 294 |
| 110 | ከአንሻርነት ውል ጋር በተያያዘ ለሚኖር የጉዳት ሃላፊነት ካሣ ሊወሰን የሚችልበት አግባብ<br>የንግድ ህግ ቁጥር 595, 596, 597<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1790, 2090, 2091, 2092, 2141, 2102 | 32854 | ወ/ሪት ማርታ አድማሱ እና እነ አቶ በረከት ሰብስቤ (ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 20/2001 | 307 |
| 111 | የተከራዩትን ቤት ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት ለውል ማፍረስ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ | 36520 | የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ይብራህ ግርማይ | ጥቅምት 27/2001 | 310 |
| 112 | መሐይምነትን ወይም ዓይነስውርነትን መሠረት በማድረግ ውል እንዲፈርስ የሚቀርብ አቤቱታ በአሥር ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1719,1845 | 29363 | ወ/ሮ ወርቅነሽ አምዴ እና አቶ ጥላሁን አርምዴ | ህዳር 18/2001 | 313 |
| 113 | የማይንቀሣቀስ ንብረት የሽያጭ ውል ተደረገ የሚባለው በውል ውስጥ ያሉ ወገኖች በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበው የሽያጭ ውሉን ከተፈራረሙበት ቀን ጀምሮ እንጂ የአስተዳደር ጉዳዩች ተጣርቶ የመስሪያ ቤቱ ማህተም ካረፈበት ቀን አንስቶ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723(1), 2015(ሀ) | 36740 | አቶ አብዱልዋሐብ ኢብራሂም እና እነ ወ/ት መሰለች ከፍያለች (ሁለት ሰዎች) | ህዳር 23/2001 | 316 |
| 114 | በማኅበር በመደራጀት የተሠራ ቤትን ለሶስተኛ ወገን ከማስተላለፍ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የሚነሣ ክርክርን አስመልክቶ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1723 ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1723 | 36294 | ወ/ሮ ሠናይት ገነሜ ገንታ እና እነ በቀለ ገመዳ ዳኖ (ሁለት ሰዎች) | ህዳር 9/2001 | 319 |
| 115 | በአሰሪ ወይም በ3ኛ ወገን ወጪ ትምህርትን ተከታትሎ ለማገልገል በሚል የተገባን ውል (ስምምነት) የጣሰ ሰው ግዴታውን በአማራጭ ሊወጣ የሚችል ስለመሆኑ | 33473 | ወ/ሮ ሃርሴማ ሰለሞን እና የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ | ህዳር 16/2001 | 322 |
| 116 | የዕቃ አስተላላፊነት ሃላፊነትና ተግባር ዕቃን የማጓጓዝና የማስረከብ ሥራን የሚያካትት ስለመሆኑ | 32571 | አቶ ሚፍታህ ከድር እና የባህር ትራንዚት አገልግሎት | ታህሣሥ 9/2001 | 326 |
| 117 | ክርክር የሚካሄድበት ጉዳይን አስመልክቶ በህግ ተለይቶ የተቀመጠ የይርጋ ጊዜ የሌለ እንደሆነ ስለ ውሎች በጠቅላላ በሚለው ክፍል የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚነት የሚኖረው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677፣1845 | 34940 | ወ/ሮ ሐጅራ አብሮ እና አቶ ሐሺም ሐጂ አሊዩ | ታህሣስ 28/2001 | 329 |
| 118 | • ፍ/ቤት የቀረበለትን የውል ይሰረዝልኝ፣ ጥያቄ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ወደጉን በመተው የውል የፎርማሊቲን የተመለከተ ጭብጥ በማንሣትና ምክንያቱን በመለወጥ ውሣኔ መስጠት የማይገባው ስለመሆኑ<br>• በፍ/ብሔር ሕግ ሥነ-ሥርዓት መሰረት ጭብጥ ለመመስረት የሚቻልበት አግባብ | 32299 | እነ አቶ ሰለሞን ከተማ (ሁለት ሰዎች) እና እነ ሴንትራል ቬኑ /የተ/የግል ማህበር (አራት ሰዎች) | ጥር 7/2001 | 331 |
| 119 | በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1161 ላይ ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ ነገር ጋር በተያያዘ በቅን ልቦና ዋጋ ሰጥቶ ስለመዋዋል የተመለከተው ድንጋጌ የንግድ መደብርን በተመለከተ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1161<br>የንግድ ሕግ ቁ. 124 | 34586 | አቶ አያሌው ድልነሳው እና እነ ወ/ሮ ብርቅነሽ ሽዋረግ (አራት ሰዎች) | ጥር 28/2001 | 336 |
| 120 | በውል ግንኙነት ውስጥ የራስን ግዴታ ሳይወጡ ሌላው ወገን ግዴታውን አልተወጣም በሚል የሚቀርብ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1757 | 39568 | አቶ ሽንቁጤ ተ/ማርያም እና አቶ ገብሬ ጉንጤ | መጋቢት 24/2001 | 339 |
| 121 | የማይንቀሳቀስ ንብረት ሻጭ በውሉ መሠረት የመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ለገዥ ያላሳወቀ እንደሆነ ገዥ ውሉ እንዲፈፀምለት የመጠየቅ መብቱ በ10 ዓመት ይርጋ የሚታገድበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1731(1), 1732, 1789 እና 1845 | 38935 | እነ አቶ ወልደፃዲቅ ብርሃኑ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ስንታየሁ አያሌው | መጋቢት 3/2001 | 343 |
| 122 | በፍ/ብሔር ጉዳዮች የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1846 | 36756 | አቶ ፀጋዬ ምትኩ እና እነ ወ/ሮ አበበች ምትኩ (ሁለት ሰዎች) | መጋቢት 17/2001 | 348 |
| 123 | ለብድር በዋስትና መልክ የተሰጠን ንብረት ለተበዳሪው መመለስ ብድሩ እንደተከፈለ የሚያስቆጥር ስለመሆኑ | 41571 | ማህደር አእምሮ እና ላእከ ገ/መድህን | ሰኔ 2/2001 | 351 |
| 124 | በህግ ፊት በማይፀና ውል አማካኝነት የተሣሠሩ ወገኖችን ወደ ነበሩበት ይመለሱ በሚል ውሣኔ መስጠት የሚቻለው መመለሰሱ አንደኛውን ወገን በእጅጉ የሚጎዳ ወይም ለሌላኛው ያልተገባ ጥቅም ሊያስገኝ የሚችል አለመሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ | 39336 | ኒያላ ኢንሹራንስ አ/ማ እና እነ አዱኛ እጅጉ (ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 7/2001 | 354 |
| 125 | በፍ/ቤት በንብረት ላይ የሚሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ከፍርድ የመነጨ የመያዣ መብት ተቋቁሟል ለማለት የሚያበቃ ስለመሆኑ | 39170 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ ክንዴ አፍራሶ (ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 2/2001 | 357 |
| 126 | የባለዕዳውን ዕዳ ለባለገንዘብ የከፈለ ወገን በባለገንዘቡ መብቶች ላይ በመዳረግ (subrogation) ባለገንዘቡ የነበረውን መያዣን መሰረት ያደረገ የቀዳሚነት መብት ሊሰራበት የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1968 - 1974 | 39778 | ሕብረት ባንክ አ/ማ እና አቢሲኒያ ባንክ አ/ማ | ሐምሌ 30/2001 | 361 |
| 127 | ፈራሽ የሆነን የስጦታ ውል ተከትለው የተሰሩ ስራዎችን ቀሪ ማድረግና ተዋዋዬችን ወደነበሩበት ቦታ መመለስ የሚቻለው በቅን ልቦና የተዋዋለ 3ኛ ወገን መብትን የማይጎዳ በሆነ ጊዜ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1815,1816,1817 | 41116 | ፍሌንስቶን ኢንጅነሪግ እና እነ ወ/ት ሐና ተስፋዬ (ስድስት ሰዎች) | ሐምሌ 30/2001 | 368 |
| 128 | የአክስዮን ድርሻ በመያዣነት እንደተሰጠ ሊቆጠር የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2863 - 2874 | 39256 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ ሞሣ ነጋሽ (ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 2/2001 | 371 |
| 129 | በብድር የተሰጠን ገንዘብ እጥፍ ለመቀበል በሚል የሚደረግ የብድር ስምምነት የህግ መሰረት የሌለው ስለመሆኑ | 43372 | አቶ ደረሱ አለሙ እና አቶ ሙሊሣ ወርቁ | ሐምሌ 22/2001 | 379 |
| 130 | ስልጣን ያለው የአስተደደር አካል የማይንቀሳቀስ | | | | |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ንብረት ባለሀብትነቱን አውቆለት የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት ከሰጠው ሰው ጋር የተደረገ የንብረቱ የመያዣ ውል የተሰጠው የምስክር ወረቀት የተሰረዘ ቢሆን እንኳን መያዣ ተቀባዩ በቅንልቦና አለመሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር የፀና ሆኖ የሚቀጥል ስለመሆኑ | 41388 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ አቶ ከፍያለው ሞልቶት (ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 30/2001 | 381 |
| 131 | የማይንቀሣቀስ ንብረት ገዥ ውል እንዲፈፀምለት ሻጭን የመጠየቅ መብቱ በፍርድ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ በአስር ዓመት ጊዜ ውስጥ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 384(ሀ)<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2892(3) | 39725 | እነ ወ/ሮ አለምሸት ካሣሁን (ሦስት ሰዎች) እና አቶ ሽመልስ እንዳለ | ሐምሌ 23/2001 | 384 |
| 132 | የማይንቀሣቀስ ንብረትን በተመለከተ የሚደረግ የስጦታ ውል የማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ ቢሆንም በህግ የፀና ውል ተደርጐ ሊወሰድ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443, 881, 1723(1) | 39803 | አቶ አለሽኝ ገ/ህይወት እና እነ እማሆይ አጢነሽ በቀለ (ሦስት ሰዎች) | ሐምሌ 2/2001 | 387 |
| | **አፈፃፀም** | | | | 390 |
| 133 | በፍርድ አፈፃፀም ምክንያት የማይንቀሣቀስ ንብረት በሐራጅ ጨረታ ተካሄዶ ሽያጭ የተፈፀመ እንደሆነ ሽያጩ ሊፈርስ የሚችለው በአሻሻጥ ሥርዓቱ የተነሣ መብት ወይም ጥቅም ያለው ሰው ላይ ቀጥተኛ ጉዳት መድረሱ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 445 | 31963 | አቶ አብዱልሐኪም ሁሴን እና እነ አቶ ቀነኒ ሁንዴ (ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 20/2001 | 391 |
| 134 | የፍርድ ባለመብት ባለመቅረቡ የተዘጋ የአፈፃፀም መዝገብ ፍርድ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በ10(አሥር) ዓመት ይርጋ ካልታገድ በቀር ሊንቀሳቀስ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 384 | 35018 | በዛብህ አበበ እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | ጥቅምት 18/2001 | 394 |
| 135 | •የፍርድ አፈፃፀም ክርክር የሚጀመረው የፍርድ ባለመብት የሆነ ወገን በፍርዱ መሰረት እንዲፈፀምለት የአፈፃፀም ማመልከቻ ሲያቀርብ ስለመሆኑ<br>•የፍርድ አፈፃፀም ማመልከቻ መቅረብ ያለበት ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት ወይም የአፈፃፀም የውክልና ስልጣን ለተሰጠው ፍ/ቤት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 371,372, 378/1/ | 21359 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ተገኝ ማንደፍሮ (ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 28/2001 | 396 |
| 136 | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥሮች 358 እና 418 ተፈፃሚ የሚሆኑበት አግባብ | 32143 | መሐመድ አስማኤል ተርቢ እና መሐመድ አህመድ ኑር | ጥቅምት 18/2001 | 400 |
| 137 | የአንድ ንብረት ወቅታዊ ዋጋ ማለት ንብረቱ ለጨረታ ሽያጭ ቀርቦ የሚያወጣው ዋጋ ስለመሆኑ | 37503 | አቶ ወልደዮሐንስ ኃብተየስ እና ወ/ሮ ያምሮት ሸዋረጋ | መጋቢት 24/2001 | 402 |
| 138 | የማይንቀሣቀስ ንብረት በሐራጅ ጨረታ ሊሸጥ የሚችልበት ሥነ- ሥርዓት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 426,428(2) | 39175 | ወ/ሮ በለጡ ጋሼ እና እነ አንዱአለም ቴድሮስ (ሦስት ሰዎች) | መጋቢት 24/2001 | 404 |
| 139 | በቀጥታ ክስ ወቅት የተገመተ የንብረት ግምት በአፈፃፀም ወቅት በአይነት ካልተገኘ እና የንብረቱ ዋጋ በልጦ ከተገኘ አፈፃፀሙ ሊሆን የሚገባው ንብረቱን በአይነት ለመተካት በሚያስችል የወቅቱ ዋጋ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378, 392 | 39485 | የህፃን ሠላማዊት ቴድሮስ ሞግዚት እና መምህር ሚካኤል ግደይ | መጋቢት 17/2001 | 407 |
| 140 | በህግ አግባብ በፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ በይግባኝ እስካልተሻረ ድረስ የሞራል ወይም የህሊና አስተሳሰብን መሠረት በማድረግ ብቻ ዋጋ አልባ ሊደረግ የማይችል ስለመሆኑ | 38041 | ታደሠ ገ/መስቀል እና እነ ሙሉጌታ ዘካርያስ (ሰባት ሰዎች) | መጋቢት 22/2001 | 410 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | **ወንጀል** | | | 1 |
| 1 | በወንጀል ጉዳይ የክስ ሂደት የዐቃቤ ህግ ማስረጃ ከነሙሉ ይዘቱ ሊመዘን የሚገባ ስለመሆኑ | 35697 | የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ እና ከበደ ወርቅነህ | ጥቅምት 20/2001 | 2 |
| 2 | • በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ የተሻሻሉና የተለወጡ ሁኔታዎች ከነባሩ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ጋር በቀጥታ ተጣምረው ሥራ ላይ ሊውሉ የሚገባ ስለመሆኑ<br>• በወ/ሕ/ አንቀጽ 543(3) የተከሰሰ ሰው የዋስ መብት የሚከለከል ስለመሆኑ<br>የወ/ሕግ አንቀፅ 543 የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 63 | 35695 | የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ እና አቶ ተመስገን አዲስ | ህዳር 11/2001 | 5 |
| 3 | በተወሰነበት ፍርድ ላይ ይግባኝ እንደሚል ፍላጐቱን አሳውቆ እያለ ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት በኩል በተከሰተ መጓተት የይግባኝ ጊዜው ያለፈበት ፍርደኛ የሚያቀርበው የማስፈቀጃ አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ | 39722 | ግርማ ሃይሌ እና ዐቃቤ ህግ | ታህሣሥ 23/2001 | 7 |
| 4 | የዳኝነትን ሥራ በማከናወን ወቅት የሚፈፀሙ ስህተቶች እና ጥፋቶች ሁሉ ዳኛን በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል ወንጀል ሊያስጠይቁ የማይችሉ ስለመሆናቸው<br>አዋጅ ቁ. 214/74 | 33075 | አቶ ብርቁ ገላነው እና የአማራ ብ/ክ/መ/የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን | ጥር 19/2001 | 9 |
| 5 | አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉ የሚቋቋምበት ህጋዊ፣ ግዙፍዊና፣ ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተጣምረው ሲገኙ ብቻ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2 | 38161 | እነ ጀሚላ መሐመድ ሐጉስ እና የፌዴራል የመ/ደ/ዐ/ህግ | የካቲት 19/2001 | 11 |
| 6 | በወንጀል ድርጊት ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው ንብረት የሆነ ንግድ መደብር ጋር በተገናኘ ፍ/ቤቶች የንግድ መደብሩን በውስጡ ከያዘው ሸቀጦች በመለየት (በመነጠል) የሚሰጡት ትዕዛዝ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ | 44594 | የፌ/ሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ህግ እና እነ ካፋ መሐመድ (አራት ሰዎች) | ሐምሌ 15/2001 | 13 |
| 7 | በወንጀል ጉዳይ በእስራት እንዲቀጣ የተወሰነበት ሰው የእስራት ቅጣቱን ሳይፈፀም በገደብ እንዲቆይ ወይም እንዲለቀቅ ሊደረግ የሚችለበት አግባብ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 82,192,194 | 46382 | እነ ዳንኤል ገ/ዮሐንስ (አራት ሰዎች) እና የፌዴራል ዐቃቤ ህግ | ሐምሌ 28/2001 | 16 |
| 8 | አንድ ተከሣሽ በተፈፀመ ወንጀል ላይ ተካፋይ ነበር ለማለት ተከሣሹ በሙሉ ፈቃዱና ዕውቀቱ በወንጀል ድርጊቱ ተሣታፊ የነበረ መሆኑ መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32, 33, 630, 25 | 44031 | ወ/ሮ ፈለቀች ኃ/ገብርኤል እና የኦሮሚያ ክልል ፍትህ ቢሮ | ሐምሌ 30/2001 | 19 |
| 9 | ከተሽከርካሪ ጋር በተያያዘ በድንገተኛ አደጋ | | ፋሲል ብርሃኑ እና ዓቃቤ | ሐምሌ | |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ለሚከሰት የሰው ህይወት መጥፋት አሽከሪካሪው በቸልተኝነት ወንጀል በማድረግ ሊጠየቅ የማይችል ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ አንቀፅ 59(1), 543(2) እና (3)፣57 (2) | 42703 | ሕግ/የኦሮሚያ ክልላዊ ብሔራዊ መንግስት/ | 22/2001 | 22 |
| **ንብረት** | | | | | 27 |
| 10 | የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት ካርታ በማቅረብ ብቻ የሚረጋገጥ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195 | 36320 | ወ/ሮ ዘውዱ ገ/ስላሴ እና ወ/ሮ ህይወት ባህታ | ጥቅምት 18/2001 | 28 |
| 11 | የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተገናኘ የንብረቱ ትክክለኛ ዋጋ ተደርጐ ሊወሰድ የሚገባው ንብረቱን ለመገንባት የወጣው ወጪ (BooK value) ብቻ ሣይሆን ንብረቱ በወቅቱ ለገበያ ቀርቦ ሊያወጣ የሚችለው ዋጋ ( market value) ጭምር ስለመሆኑ | 35003 | አቶ አሸናፊ አብዱልቃድር እና እነ ወ/ሮ ሽቶ አብዱራሂም (አራት ሰዎች) | ህዳር 9/2001 | 30 |
| 12 | አንድ ተከራካሪ ተገቢነት ያለው የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ አቅርቧል ለማለት ለክርክር መንስኤ የሆነውን ንብረት በእጅ አድርጎ መገኘትና በዚሁ ንብረት ላይ በእውነት ለማዘዝ እንዲችል የንብረቱ አያያዝ ያልተቋረጠ የተረጋገጠበት ... ያልተቋረጠ ... በማናቸውም መንገድ ህገ-ወጥ በሆነ ሁኔታ ያልተገኘ መሆን ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140, 1149(1) | 36645 | ረዳት ሳጂን አያኖ አንጀሎ እና እነ ወ/ሮ አለሚቱ ጫሌቦ | ህዳር 11/2001 | 32 |
| 13 | የጋራ ንብረትን ለመካፈል በሚደረግ ሽያጭ የጋራ ባለንብት የሆነ ወገን የቅድሚያ ግዥ መብት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1261(2), 1386 — 1409 | 37297 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ እታለም ተስፋ | ታህሣሥ 2/2001 | 36 |
| 14 | የጋራ ሀብት የሆነ ንብረት በመያዣ የተያዘ በመሆኑ የቅድሚያ መብት ያለ ቢሆንም የጋራ ባለሀብት የሆነ ወገን ንብረቱ በግልፅ ጨረታ ቀርቦ የሚያወጣውን ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ግማሽ በመክፈል ማስቀረት የሚችል ስለመሆኑ | 37298 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ አለምነሽ ዋቅጂራ | ታህሣስ 2/2001 | 39 |
| 15 | የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታን ለማቅረብ አቤቱታ አቅራቢው ክርክር የቀረበበት ንብረት ባለሀብትነቱን ሳይሆን ባለይዞታነቱን ብቻ ማስረዳት ያለበት ስለመሆኑ | 38228 | ሐጂ መሐመድ አወል ረጃ እና እነ አቶ ዲኖ በሺር (ሁለት ሰዎች) | ታህሣስ 7/2001 | 41 |
| 16 | ባለመሬቱ ሳይቃወም በሌላ ሰው መሬት ላይ ህንፃ የሰራ ሰው የህንፃው ባለሀብት ሊሆን የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1179 | 36638 | በላይ አበበ እና እነ አበራሽ ዋቅጅራ (ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ 21/2001 | 43 |
| 17 | በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የመያዣ መብት ያለው ባንክ በንብረቱ ላይ ሊኖረው የሚችለው የመብት አድማስ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059/1/, 3088/1/, 3110/ሐ/ | 36013 | ወ/ሮ ዘምዘም ኑሩ እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ | ታህሣሥ 21/2001 | 46 |
| 18 | የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ የሚያቀርብ ወገን የሁከት ተግባር ፈጽሟል ከሚባለው ሰው የተሻለ የይዞታ መብት ያለው መሆኑን በቅድሚያ ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140, 1149 | 39940 | ወ/ሮ ነጂባ ነጋሽ እና ወ/ሮ ዚያዳ ዴታሞ | ግንቦት 27/2001 | 50 |
| 19 | ንብረትነታቸው የመንግስት የሆኑ ቤቶችን በተመለከተ የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ መንግስትን ወክሎ የመከራከር መብት ያለው | 38169 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና የወ/ሮ ንጋቷ ዘለቀ ወራሽ | ግንቦት 12/2001 | 52 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33(2) | | አቶ እሸቱ ቦጋለ | | |
| 20 | የይዞታ መብት ፍፁም ስላለመሆኑ እና በህግ አግባብ ይዞታው የተወሰደበት ሰው ተገቢ የሆነ ካሣ የመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140, 1149(1), (2)<br>አዋጅ ቁ. 7/1986 አንቀጽ 2(5), 21, 22, 24, 23<br>በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ- መንግሥት አንቀጽ 40 (8)<br>አዋጅ ቁ. 455/1997 | 39539 | የአዲስ አበባ አስተዳደር ግብርና ቢሮ<br>እና<br>እነ አቶ አበበ ዓባይ(ዘጠኝ ሰዎች) | ሐምሌ 30/2001 | 54 |
| 21 | ከህግ የሚመነጭ የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለሀብትነትን አስመልክቶ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723 ተፈፃሚነት የማይኖረው ስለመሆኑ | 38666 | የኢትዮጲያ ልማት ባንክ<br>እና<br>ባላንባራስ ተስፋዬ ገ/እየሱስ | ሐምሌ<br>9/2001 | 57 |
| | **ከውል ውጭ ኃላፊነት** | | | | 60 |
| 22 | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 2143 ላይ የጉዳት ካሣን አስመልክቶ የቀረበው የይርጋ ድንጋጌ የሞት ጉዳትን የሚያካትት ስለመሆኑ | 34544 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና ወ/ሮ ፋጤ ዓሊ | ጥቅምት 11/2001 | 61 |
| 23 | ማንም ሰው ሥራው በሚያደርሰው ጉዳት ምክንያት ጥፋት ባይኖርበትም ከውል ውጭ ሃላፊነት ሊከተልበት የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2066- 2089(2069(1)) | 33201 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>ሼል ኢትዮጵያ | ጥቅምት 27/2001 | 63 |
| 24 | ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው (ልጅ) ሃላፊነትን የሚያስከትል ሥራ የሰራ እንደሆነ ወላጆች በፍ/ብሔር በሃላፊነት ሊጠየቁ የማይችሉ ስለመሆናቸው<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2125, 2124 | 31721 | ወ/ሮ ብዙነሽ ኃ/ዮሐንስ<br>እና<br>ወ/ሮ ስንታየሁ እሸቱ | ጥቅምት 25/2001 | 65 |
| 25 | የጉምሩክ ባለሥልጣን ተግባር ህጋዊ ነው ሊባል የሚችለው በህጉ መሠረት ሊሟሉ የሚገቡትን ሁኔታዎች አሟልቶ ሲገኝ እንጂ በማናቸውም ጥርጣሬ ምክንያት የግለሰብን ንብረት በመያዝ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.60/89 አንቀጽ 6, 58<br>አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 2(28)<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 26(1)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1193(1),(2), 2027, 2035, 2054, 2118 | 31171 | አብልሃሚድ የሱፍ እና የምስራቅ ቀጠና ጉምሩክ ጽ/ቤት | ጥቅምት 27/2001 | 67 |
| 26 | ጉዳት መድረሱ የተረጋገጠ ከሆነና ጉዳቱ በተጉጂው የወደፊት ህይወት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያሳድር እንደሚችል ምክንያታዊ እርግጠኝነት ያለ እንደሆነ ካሣ ርትዕን መሠረት በማድረግ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ | 35034 | እነ ወ/ሮ ጥሩቀለም ደሴ እና እነ ወ/ሮ ጽጌ ከፍያለው | ጥቅምት 6/2001 | 70 |
| 27 | ከውል ውጭ በሆነ ግንኙነት የሰው ህይወት የጠፋ እንደሆነና ለጉዳቱ መንስኤ (ምክንያት) የሆነው ወገን ሃላፊነት የተረጋገጠ ከሆነ በጠፋው የሰው ህይወት የተነሣ ጉዳት የደረሰበት ሰው የሞተው ሰው ምን ያህል ጥቅም ያስገኝለት እንደነበር ወይም ምን ያህል ተጨማሪ ዕድሜ ሊኖር እንደሚችል ያላስረዳ ቢሆንም እንኳን ፍ/ቤት የጉዳት ካሣውን በርትዕ ሊወስን የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2102 | 34314 | ወ/ሮ ግምጃ ጎበና እና እነ አቶ ወንድወሰን ወልዴ (ስድስት ሰዎች) | ህዳር 11/2001 | 73 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 28 | የጉምሩክ ባለሥልጣን ያለአግባብ በቁጥጥሩ ሥር አድርጐ ለሚያቆየው ንብረት በባለንብረቱ ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ በኃላፊነት ሊያስጠይቀው የሚችል ስለመሆኑ | 31704 | አቶ አማረ መጃ እና የድሬዳዋ ስጋር ጉምሩክ | ጥር 29/2001 | 76 |
| 29 | በጥቅም ላይ ባልተመሰረተ ግንኙነት በመኪና ተሣፍሮ የሚሄድ ተሣፋሪ ላይ ለሚደርስ አደጋ የመኪናው ባለቤት ካሣ የመክፈል ሃላፊነት የማይኖርበት ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2089 | 38457 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>ተመኘሁ እንደሻው | ሰኔ 2/2001 | 79 |
| | | | **የዳኝነት ስልጣን** | | 81 |
| 30 | የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የውርስ አጣሪ የመሾም ሥልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ እና በአዲስ አበባ መስተዳደር ውስጥ የውርስ አጣሪ ይሾምልኝ ጥያቄን የማየት የዳኝነት ሥልጣን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41(1) (ሸ)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 996(1) | 35657 | እነ ወ/ሮ እመቤት መክብብ እና አቶ በድሉ መክብብ | ጥቅምት 6/2001 | 82 |
| 31 | የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች ለክርክር መነሻ የሆነው ክስ በገንዘብ ሊተመን የማይችል የመብት ጥሰትን የተመለከተ በሆነ ጊዜ የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 50(1), 39 | 36338 | ገ/መስቀል ደመወዝ<br>እና<br>ወ/ሮ አፀደ መኰንን | ጥቅምት 25/2001 | 86 |
| 32 | የቅኔ መምህርነት ቀጥተኛ የሆነ መንፈሣዊ ሥራ በመሆኑ በሥራ ክርክር ችሎቶች ሊስተናገድ የሚችል ስላለመሆኑ | 34440 | መንበረፓትሪያክ ጠቅላይ ጽ/ቤት እና<br>መጋቢ ሚስጢር መዝገቡ በላይነህ | ጥቅምት 6/2001 | 88 |
| 33 | የከተማ ነክ ፍ/ቤቶች የቤት ባለቤትነት ክርክር የቀረበበትን ጉዳይ ለማየት ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41(1)(ሪ) | 33841 | አቶ አስጨናቂ ረጋሣ እና<br>እነ አቶ ገዛኸኝ ነጋሽ<br>(ስድስት ሰዎች) | ጥቅምት 6/2001 | 91 |
| 34 | በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ በወታደርነት በማገልገል ላይ የሚገኙ የሠራዊት አባላት ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ የወንጀል አቤቱታዎችን ለማስተናገድ ወታደራዊ ፍ/ቤቶች ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.27/88, አዋጅ ቁ. 343/94 አንቀፅ 2(9),26(1) | 33368 | ሻምበል አሰፋ በላይ ዘገየ<br>እና<br>ወታደራዊ አቃቤ ህግ | ህዳር 9/2001 | 93 |
| 35 | የአ.አ ከተማ ነክ ፍ/ቤቶች በከተማው አስተዳድር ሥር ካሉ ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮችን ብቻ ለማየት ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ | 34788 | የሟች አቶ ሰለሞን ሳሙኤል ወራሾች እና ማርታ ሰለሞን (2 ሰዎች) | ህዳር 2/2001 | 96 |
| 36 | በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ይሰጠኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በፍርድ ቤት ቀርቦ ዳኝነት ሊሰጥበት የሚችል ስላለመሆኑ | 31906 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና የአቶ መርስኤ መንበሩ ወራሾች | ህዳር 4/2001 | 99 |
| 37 | በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ከተወረሱና በቀላጤ ከተያዙ ቤቶች ውጭ ያሉ ቤቶችን አስመልክቶ የሚነሣ የቤት ክርክር ጉዳዮችን ፍርድ ቤቶች ማየት የሚችሉ ስለመሆናቸው<br>አዋጅ ቁ.47/67<br>አዋጅ ቁ. 110/87 | 37281 | አቶ አበበ ዓሊ እና እነ የ08 ቀበሌ ገ/ማህበር<br>(ሦስት ሰዎች) | ታህሣሥ 16/2001 | 103 |
| 38 | በውጭ አገር የሚገኝ ንብረትን አስመልክቶ የሚቀርብ ክርክርን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ማስተናገድ ስለመቻሉ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 37, አዋጅ | 37339 | ወ/ሮ ንግስት ኃይሌ እና<br>አቶ ለገሠ ዓለሙ | ጥር 28/2001 | 106 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቁጥር 25/88 አንቀፅ(4) | | | | |
| 39 | ወደ ቀድሞ የሥራ መደብ እንድመለስና ለመደቡም የተሰጠው ልዩ ጭማሪ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በሚል የሚቀርብ ጥያቄ የወል ሥራ ክርክር ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ142(1) (ሀ) | 37016 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>አቶ ተስፋዬ ማሞ | የካቲት 3/2001 | 109 |
| 40 | ከጉምሩክ ፖሊስ አባላት ጋር በተያያዘ የሚነሱ የሥራ ክርክሮችን ለማየት የሚያስችል ስልጣን ለመደበኛ የሥራ ክርክር ችሎቶች ያልተሰጠ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 368/96 , አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 8(2) , መመሪያ ቁ.4/1996 | 39085 | የኢትዮትያ ጉምሩክ ባለስልጣን<br>እና እነ ወ/ር አስረሳች ወርቅነህ<br>(ሰማንያ ሰባት የጉምሩክ ፓሊሶች) | የካቲት 3/2001 | 111 |
| 41 | ቀደም ብሎ የተሰጠን የፍች ውሣኔ ወደጐን በመተው አዲስ የተደረገን ጋብቻ ህገ ወጥ ነው ማለት የማይቻል ስለመሆኑ | 38745 | እነ ወ/ሮ ሣሊያ ኢብራሂም (ሁለት ሰዎች) እና ሐጂ ሰማን ኢሣ | መጋቢት 10/2001 | 113 |
| 42 | የሸሪዓ ፍ/ቤቶች የይዞታ ክርክርን ማስተናገድ የማይችሉ ስለመሆናቸው | 36677 | ወ/ሮ ሻምሺ የኑስ እና ወ/ሮ ኑሪያ ማሚ | ሚያዝያ 30/2001 | 116 |
| 43 | የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመቀጮ እና ወለድ ላይ የሚቀርብ ይግባኝን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው ስለመሆኑ | 37866 | ሙሉጌታ አባይ እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን | ግንቦት 19/2001 | 119 |
| 44 | የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶችም ሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳዬችን ለማየት የሚያስችል ስልጣን በህግ ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ | 41608 | እነ ሙላቱ አንበርብር<br>እና ወ/ት ታመነች ዮሴፍ መና | ሐምሌ 22/2001 | 121 |
| | **ባንክና ኢንሹራንስ** | | | | 123 |
| 45 | ዕቃዎችን ለሚያጓጉዝ የጭነት መኪና የተገባ የመድን ዋስትና ጋር በተያያዘ በመኪናው ላይ ተሣፍሮ ሲሄድ ለነበረና አደጋ ለደረሰበት ሰው መድን ሰጪው የጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የሌለበት ስለመሆኑ | 42139 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና ብያን ኡመር | ሰኔ 30/2001 | 124 |
| 46 | ኢንሹራንስ ሰጪ በውሉ መሠረት ከፈፀመ በኂላ በተሸሸገ ወይም በሀሰት ቃል የቀረበ ጉዳይ አጋጥሟል በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ የተሸሸገውን ወይም በሐሰት የቀረበውን ቃል ካወቀበት ቀን ጀምሮ ባለው ሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ 674(1),(2) | 42309 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>የኢትዮጵያ መድን ድርጅት | ሰኔ 30/2001 | 126 |
| | **ውክልና** | | | | 128 |
| 47 | አደራ ተቀባይ የሆነ ወገን በአደራ የተቀበለውን ዕቃ መመለስ ያለበት ለአደራ ሰጪው ወይም ይቀበልልኝ ብሎ ላመለከተው ሰው ስለመሆኑ | 38289 | ወ/ሮ ነጂሃ ድዋሌ ዋይስ<br>እና አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማ | ሰኔ 23/2001 | 129 |
| 48 | መንግስታዊ የሆነ ተቋም በሚከሰስበትም ሆነ በሚከስበት ክርክር የሚቀርብ ሰነድ የፕሮቶኮል ቁጥር እንዲሁም ስለአቤቱታው ጽሁፍ ትክክለኛነት በሚመለከተው ኃላፊና በወኪሉ መፈረም ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 80, 92, 93 እና 92(3) | 43875 | በወላይታ ዞን የቦዲቲ ከተማ ማዘጋጃ ቤት እና አቶ ወንድሙ ኃይሌ | ሐምሌ 16/2001 | 131 |
| 49 | የዕቃ አስተላላፊ አካል እንደ አጓዥ ሆኖ የሚቆጠረው ከወደብ የተረከበውን ዕቃ በራሱ ማጓጓዣ ካጓጓዘ ብቻ ስለመሆኑ<br>ደንብ ቁ.37/90 አንቀጽ 2(1), 3(6),(7)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2251 | 37799 | የባህርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት<br>እና<br>የኢትዮጵያ መድን ድርጅት | ሐምሌ 29/2001 | 134 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የንግድ ህግ .ቁ. 683(3) | | | | |
| 50 | በወኪል በኩል የሚፈፀም የመኪና ጭነት ውል በአስጫኙ እና በመኪናው ባለቤት መካከል እንደተደረገ የሚቆጠር ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 566 እና የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2251 | 34621 | ኒያላ ኢንሹራንስ አ/ማ<br>እና<br>አቶ ሐጎስ ገ/መድህን | ሐምሌ 30/2001 | 136 |
| **የንግድ ሕግ** | | | | | 140 |
| 51 | የንግድ ድርጅት በህግ አግባብ ለባለመብቶች ሊከፋፈል የሚችልበት ሁኔታ<br>የንግድ ህግ ቁጥር 127 | 33954 | ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ እና<br>አቶ ዘውዱ ቢረዳ | ጥቅምት 20/2001 | 141 |
| 52 | የእሽሙር ማህበር መፍረስ በንብረት ክፍፍል ረገድ የሚያስከትለው ውጤት | 33470 | ወ/ሮ እጅጋየሁ ታደሰ እና<br>መገርሳ ጉደታ | ህዳር 2/2001 | 144 |
| 53 | የጋራ ሀብት የሆነ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እንደሌላ ማናቸውም ንብረት ባለበት ሁኔታ በዓይነት ሊከፋፈል ወይም ደግሞ በሃራጅ ሊሸጥ የማይችል ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 542 | 34945 | ወ/ሮ መስታወት በላቸው<br>እና አቶ ሰገሠ ሣህሉ | ህዳር 2/2001 | 146 |
| 54 | የንግድ መደብርን የተከራየ ወገን ይህንኑ የንግድ መደብር ለሌላ ሶስተኛ ወገን ያለአከራዩ ፈቃድ ማከራየት ስለመቻሉ<br>የንግድ ህግ ቁጥር 145 | 31264 | ወ/ሮ እመቤት መኰንን<br>እና<br>ወረዳ 20 ቀበሌ 29<br>አስ/ጽ/ቤት | ጥር 5/2001 | 148 |
| 55 | በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1161 ላይ ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ ነገር ጋር በተያያዘ በቅን ልቦና ዋጋ ሰጥቶ ስለመዋዋል የተመለከተው ድንጋጌ የንግድ መደብርን በተመለከተ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1161<br>የንግድ ሕግ ቁ. 124 | 34586 | አቶ ያለው ድልነሳው<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ብርቅነሽ ሽዋረግ<br>(አራት ሰዎች) | ጥር 28/2001 | 151 |
| 56 | ቼክን አስመልክቶ ክስ በቀረበ ጊዜ የተከሰሰው ወገን የቀረበበትን ክስ ለመከላከል እንዲፈቀድለት የሚያቀርበው ምክንያት ፈቃድ ሊያሰጥ የሚችል መሆን ያለመሆኑን አግባብነት ካላቸው ህግጋት አኳያ መታየት ያለበት ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 717<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 284, 285 | 43315 | ብራንድ ኒው የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ማዕከል<br>እና<br>አቶ መስፍን ታደሰ | ግንቦት 18/2001 | 154 |
| **አእምሯዊ ንብረት** | | | | | 156 |
| 57 | አንድን የሥነ-ጥበብ(ኪነ-ጥበብ) ሥራ ያለባለቤቱ ፈቃድ ኦርጅናሉ ወይም ቅጅው ለህዝብ እንዲታይ ማድረግ የኮፒ ራይት ህግ ጥሰት የሚያስከትል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1791, 1771(1), 1790, 2090-2123<br>አዋጅ ቁ. 410/96 አንቀፅ 7 | 42253 | መምህር ሙሉ<br>ኃይለሥላሴ<br>እና<br>ዘመናዊ ማተሚያ ቤት | ሐምሌ 8/2001 | 157 |
| **ልዩ ልዩ** | | | | | 160 |
| 58 | የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መዋቅር ባልተዘረጋባቸው ክልሎች የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ወክለው/ተክተው/ ክርክሮችን ማስተናገድ ያለባቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 139/1//ለ/,154/1/,153,140 | 21214 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ<br>አቶ ለማ ኩማ<br>(ሦስት ሰዎች) | ህዳር 4/2001 | 161 |
| 59 | • የጡረታ መዋጮ በመዘግየቱ ምክንያት | | | | |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በአዋጅ ቁ. 345/95 መሠረት ተጨማሪ ክፍያ ሊከፈል የሚችልበት አግባብ<br>• የጡረታ መዋጮ በ2 ዓመት ውስጥ እንደተከፈለ የህግ ግምት ሊወሰድበት የሚችል የክፍያ ዓይነት ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024(ሠ)<br>አዋጅ ቁ. 345/95 አንቀጽ 7(3), 52(1),56 | 35391 | የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ<br>እና<br>አንበሣ ጫማ አ/ማ | ህዳር 25/2001 | 163 |
| 60 | የጥብቅና ፈቃድን ለማግኘት በህጉ የተቀመጡት መስፈርቶች ራሣቸውን ችለው መታየት ያለባቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 199/92 አንቀጽ 8(1) | 37375 | አቶ ሽምሱ ከድር አህመድ<br>እና<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፍትህ ሚኒስቴር | ህዳር 11/2001 | 166 |
| 61 | በከባድ የወንጀል ጉዳይ የተከሰሱ እና በራሣቸው ወጪ ጠበቃ ለማቆም ያልቻሉ ግለሰቦችን በተመለከተ ጉዳዩን የሚያየው ፍ/ቤት የግለሰቦችን በጠበቃ የመወከል ህገ-መንግሥታዊ መብት መከበሩን በቅድሚያ ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ 13 (1) | 37050 | ሻምበል ሁሴን አሊ እና የሱማሌ ክልል ዐ/ሕግ | ታህሣሥ 30/2001 | 168 |
| 62 | ከዘር የወረደ ርስት ነው በሚል የመሬት ባለቤት ለመሆን የሚቀርብ ክስ ህገ-መንግስታዊ ያልሆነና ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ | 38237 | አቶ በርገና ሽፈራው እና እነ አቶ አብራሃም ሽፈራው(አራት ሰዎች) | ታህሣሥ 21/2001 | 171 |
| 63 | በወንጀል ጉዳይ የተሰጠ ውሣኔ በተመሳሳይ ጉዳይ በፍ/ብሔር ለቀረበው ክስ በማስረጃነት ለመወሰድ ብቃትና አግባብነት ያለው ስለመሆኑ | 37184 | የሰሜን ቀጠና ጉምሩክ እና እነ ቄስ ብርሃን ንዋይ (ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ 9/2001 | 174 |
| 64 | የመንግሥት መሥሪያ ቤት በጨረታ አማካኝነት የሽያጭ ውል አካሄዷል ተብሎ ሊገደድ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1688(2), 3167(1), 1688(2), 3168 | 37163 | የአዋሽ ተፋሰስ ባለስልጣን እና ህያብ ገ/መድህን ብረታ ብረት ማቅለጫ ፋብሪካ | ታህሣሥ 23/2001 | 179 |
| 65 | አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ምንነት፣ የሚደረጉበት መንገድና ለአፈፃፀም የሚቀርቡበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3318, 3324, 3325, 3346, 1731<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 315, 319, 350, 357 | 38794 | አቶ ሙክሚል መሐመድ እና አቶ ሚፍታህ ከድር | መጋቢት 24/2001 | 182 |
| 66 | አስተዳደራዊ የሆኑ መስፈርቶች ባልተሟሉበት ሁኔታ ካርታ እንዲሰጥ የሚወስን ውሣኔ ተገቢ ስላለመሆኑ | 39529 | ቦሌ ክ/ከተማ የመሬትና ልማት አስተዳደር እና እነ ወ/ሮ ግምኟ በዳኔ (ስድስት ሰዎች) | ግንቦት 11/2001 | 186 |
| 67 | ግምቱ ከብር 10,000 ብር በላይ ለሆነ የአፈፃፀም ክስ ሊከፈል የሚገባው ዳኝነት 25 ብር ብቻ ስለመሆኑ<br>የህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁ. 177/1945 አንቀጽ 2(ሠ) | 40752 | እነ ወ/ሮ ኤክራም መሃመድ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ዘኪ መሐመድ | ሐምሌ 28/2001 | 189 |
| 68 | ከፌዴራል መንግስት የልማት ድርጅት ሠራተኞች የሚሰበሰብ የሥራ ግብር ምንም እንኳን ሥራው የሚካሄደው በክልሎች ቢሆንም ወይም ሠራተኞቹ የክልል ነዋሪዎች ቢሆኑም ገቢ የሚደረገው ለፌዴራሉ መንግስት ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 96(3)<br>አዋጅ ቁ. 33/85 አንቀጽ5(2)(ሐ)<br>ደንብ ቁ. 109/96 | 40133 | የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን እና በሶማሌ ብ/ክ/መ የፊደልቱ ወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ገቢዎች ጽ/ቤት | ሐምሌ 2/2001 | 191 |
| | **አሰሪና ሰራተኛ** | | | | 195 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 69 | የግንባታ ዕቃዎች እጥረት አጋጥሟል በሚል የሚደረግ የሥራ ስንብት ህገ-ወጥ ነው ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 26,28,30 | 41385 | ጊጋ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር እና እነ ተረፈ ዘርጋው (ስድስት ሰዎች) | ጥቅምት 3/2002 | 196 |
| 70 | የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት አድርጐ ከሚቀርብ ክርክር ጋር በተገናኘ በግልፅ ዳኝነት ተጠይቆበት ውሣኔ ሣይሰጥ ከተጠየቀት ዳኝነት መካከል ወደ ሥራ የመመለስ ጉዳይ ላይ ብቻ ውሣኔ ከተሠጠና ሠራተኛው ወደ ሥራ መመለስ ሳይፈልግ ቢቀር ቀድሞ ዳኝነት በጠየቀባቸው ነገር ግን ውሣኔ ባላረፈባቸው ነጥቦች ላይ ዳኝነት ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 43(3) | 42361 | ወ/ት ትዕግስት ንጉሴ<br>እና<br>ኤስ.ኦ.ኤስ<br>ኢንፋንት<br>ኢትዮጵያ | ጥቅምት 5/2002 | 198 |
| 71 | በትርፍ ሰዓት በሌላ መሥሪያ ቤት ሰርተሃል በሚል ሠራተኛን ያለማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የሚያስችል የህግ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ 377/96 አንቀፅ 27 | 42818 | አቢሲኒያ ባንክ አ.ማ እና ወ/ር ሙለታ ገዳ | ጥቅምት 10/2002 | 200 |
| 72 | አሰሪ በግልፅ ባልፈቀደበት ሁኔታ በሁለት ቦታ በተመሳሳይ ጊዜ መስራት ሠራተኛውን የማታለል ተግባር እንደፈፀመ የሚያስቆጥረው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 27(1)(ሐ) | 41767 | የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን እና<br>አቶ አድማስ ደምሳቸው | ህዳር 8/2002 | 202 |
| 73 | አሰሪ የእድገት አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት እና መለኪያ መስፈርቶችን አዘጋጅቶ በሠራተኞቹ መካከል በክፍያ ረገድ ልዩነት ማድረግ ስለመቻሉ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 14(1)(ረ)<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት 42(1)(መ) | 42923 | የኢትዮጵያ<br>ቴሌኮሙኒኬሽን<br>ኮርፖሬሽን<br>እና<br>ወ/ሮ ነጃት አባስ | ህዳር 22/2002 | 204 |
| 74 | ሥራውን በገዛ ፈቃዱ የሚለቅ ሰራተኛ የስንብት ክፍያ ለማግኘት የሚችለው ቢያንስ የ5 ዓመት አገልግሎት ያለው እንደሆነ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2(ሽ) | 44410 | ወ/ሮ ሳይላ ረዲ እና<br>ድሬ ኢንዱስትሪዎች<br>ኃ/የተ/የግል ማህበር | ኅዳር 01/2002 | 207 |
| 75 | በአሠሪና ሠራተኛ ሕጉ "በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት" ወይም "በስራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ" በሚል የተቀመጠው ሐረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 95/2/,97,96 | 47807 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ፀሐይነሽ<br>ፈንታው<br>(ሁለት ሰዎች) | ታህሳስ 06/2002 | 210 |
| 76 | አሰሪ ሠራተኞቹን በማስተዳደር ረገድ የሚፈፅማቸውን ስህተቶች በራሱ አነሣሽነት ሊያርም የሚችል ስለመሆኑ | 45889 | የኢትዮጵያ<br>ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፓሬሽን<br>ደቡብ ሪጅን እና ሳሙኤል<br>ቁለቦ | ታህሣሥ 20/2002 | 213 |
| 77 | በክርስትና ሃይማኖት ተቋም ውስጥ በዲያቆንነት ሥራ ከማገልገል ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ የሥራ ክርክር ጉዳዮች በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት ሊስተናገዱ የማይችሉ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 | 47806 | የሆህተሰማይ ቅድስት ማሪያም ቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት እና ዲያቆን አያሌው አዲሱ | ታህሣሥ 20/2002 | 215 |
| 78 | በጡረታ የተገለሉና ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሠራተኞች ቋሚ ሠራተኞች የሚያገኟቸውን ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞችን የማግኘት መብት የሌላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 10 | 47469 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ስዩም ገብረፃዲቅ(ሃያ ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ 15/2002 | 217 |
| 79 | በሥራ ክርክር ጉዳይ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1853 ላይ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ | 47784 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>አለምፀሐይ አያና | ታህሣሥ 20/2002 | 220 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁ. 377/96 164(3)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1853,1852 | | | | |
| 80 | በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ መሠረት የሥራ ግንኙነት በአንቀፅ 30 መሠረት ሲቋረጥ አሰሪ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታ የሌለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 30, 28(2) | 49057 | አስመላሽ እና ልጆቹ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ዮሐንስ እሺበል | ጥር 5/2002 | 223 |
| 81 | የጡረታ መብት ያለው እና መደበኛ የጡረታ ዕድሜው ደርሶ የተሰናበት ሰራተኛ የስንብት ክፍያ ለማግኘት መብት የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2/2(ሰ) እና (ሸ) | 46276 | ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት እናእነ ኃይሌ ይማም (ሁለት ሰዎች) | የካቲት 11/2002 | 225 |
| 82 | • አንድ ድርጅት በመክሰሩ ወይም በሌላ ምክንያት ለዘለቄታው በመዘጋቱ የሥራ ውል ሲቋረጥ ሠራተኞች የስንብት ክፍያ ሊከፈላቸው የሚገባ ስለመሆኑ<br>• ድርጅት ለዘለቄታው እንዲቆም የሚያደርግ ሁኔታ ሲከሰት ማስጠንቀቂያ ለሠራተኞች መሰጠት ያለበት ስለመሆኑ | 42985 | ውድ መጣስ ኑሮ አስመጪና ላኪ ድርጅት እና እነ አቶ ሁነኛው ሰጠ (አስራ አንድ ሰዎች) | የካቲት 25/2002 | 227 |
| 83 | የጠብ አጫሪነት ኃይለ ቃልና ዛቻ አዘል ንግግር በሥራ ቦታ ላይ ማድረግ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ የሚያሰናብት ጥፋት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1)(ረ) | 49958 | ግዩን ትራቭልና ቱርስ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ዳንኤል አስፋው | የካቲት 12/2002 | 229 |
| 84 | በሞት ምክንያት የሥራ ውል ሲቋረጥ ለሠራተኛው ጥገኞች ስለሚከፈል ካሣ፣ ካሣው የሚከፈልበትና የሚሰላበት ሁኔታ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 110 | 40529 | የህፃን ዮናታን ነጋ ተሻገር ጠ/ጥ.ጋቡ ጌጤ እና አቶ ለገሠ አበራ | የካቲት 10/2002 | 231 |
| 85 | በአሰሪና ሰራተኛ በኩል በአጠቃላይ ለፕሮጀክት ሥራ በሚል የተደረገ የሥራ ውል በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ አንቀጽ 10(1)(ሀ) መሰረት የተደረገ እንደሆነ ተደርጎ የሚወሰድ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 10(1)(ሀ) | 48648 | የፃልቁ የትምህርትና የተቀናጀ የልማት ማህበር እናእነ አቶ ታጠቅ ደጀኔ (ሁለት ሰዎች) | የካቲት 24/2002 | 234 |
| 86 | ሠራተኞችን ለማበረታታት በሚል የሚደረግ የደመወዝ (ጥቅማጥቅም) ጭማሪን መሠረት በማድረግ ጭማሪውን የሚፈቅደው መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የሥራ ውሉ የተቋረጠ ሠራተኛ የሚጠይቀው መብት የሌለ ስለመሆኑ | 47825 | የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ (አ.ማ) እና እነ አቶ ዘርዓየሁ ሰሜ (ሁለት ሰዎች) | የካቲት 25/2002 | 236 |
| 87 | አንድ ሠራተኛ በሥራ ላይ ከሚፈፅመው ጥፋት ጋር በተያያዘ ከሥራ ታግዶ ሊቆይ ስለሚችልበት ሁኔታ በህብረት ስምምነት ሊወሰን የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 | 47535 | የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት እና አቶ እንግዳው ላቀው | መጋቢት 20/2002 | 238 |
| 88 | • የአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ አሰሪና ሰራተኛ ስምምነት ሊያደርጉባቸው የሚችሉበት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ጥፋትንና ጥቅምን በተመለከተ የተለያየ አቋም የያዘ ስለመሆኑ<br>• አሰሪና ሠራተኛ በህብረት ስምምነታቸው ውስጥ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት በሚል የተስማሙበት ድንጋጌ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 134(2), 27(1)(ሸ) | 49750 | በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02/01 የመዝናኛ ክበብ እና አቶ ማስረሻ ሁሴን | መጋቢት 30/2002 | 240 |
| 89 | አሠሪ የሠራተኛውን የሥራ ውል ያቋረጠበትን ምክንያት በፅሁፍ አለመግለፁ | 49797 | አልሀበሽ ሹገር ሚልስ ኃ/የተ/የግል ማህበር | መጋቢት 30/2002 | 242 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ብቻ ስንብቱ ህገ- ወጥ ነው ለማለት የሚያስችል ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(2) | | እና<br>ተገኜ ገ/ሃዋሪያት | | |
| 90 | በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ ውስጥ "እንደ ጥፋቱ ክብደት በሥራው ላይ የማታለል ወይም የማጭበርበር ተግባር መፈፀም" በሚል የቀረበው አባባል (አነጋገር) ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1)(ሐ) | 50009 | የአዲስ አበባ ሂልተን ሆቴል<br>እና<br>አቶ ዮናስ ጥላሁን | መጋቢት 6/2002 | 244 |
| 91 | አሠሪና ሠራተኛ የሥራ ውል መቋረጥ ጋር በተያያዘ በሥራ ውሉ ላይ የሚያመለክቱት ሁኔታ የአሰሪና ሠራተኛ ህጉን እስካልተፃረረ ድረስ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ | 50205 | የኢትዮጵያና ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት<br>እና<br>አቶ ምናለ በሪሁን | መጋቢት 20/2002 | 246 |
| 92 | የሥራ ውል በተቋረጠ ጊዜ አሰሪው ከሠራተኛው በህግ አግባብ የሚፈልገው/ የሚጠይቀው ዕዳ ያለ እንደሆነ ለሠራተኛው የሥራ ልምድ ምስክር ወረቀት ከመስጠት ባሻገር የሥራ መልቀቂያ (ክሊራንስ) ለመስጠት የማይገደድ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 515/99 አንቀፅ 78 (1),87 | 48476 | የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት እና አቶ ደረጀ መኮንን | ሚያዝያ 12/2002 | 248 |
| 93 | ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ የሚደርስበትን ጉዳት ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ወይም ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት በማለት ለመለየት የሚቻልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 101 (2) | 49273 | አቶ ደረጀ ውለታው<br>እና<br>ዋሊያ ሌዘርና ሌዘር ፕሮዳክትስ ኃ/የተ/የግል ማህበር | ሚያዝያ 27/2002 | 250 |
| 94 | • አንድ ሰው በአፈፃፀም ሊገደድ የሚችለው በህግ አግባብ የተፈረደ ፍርድ ሲኖር ብቻ ስለመሆኑ<br>• በግልፅ ፍርድ ያላረፈበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሊፈፀም የሚችል ፍርድ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378 | 50148 | እነ አቶ ወርቁ ደረጀ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ አባርኪሮ ሁመድ | ሚያዝያ 4/2002 | 252 |
| 95 | ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ ከሠራተኛው ጋር ያለው ግንኙነት ሠራተኛው ወደ ሥራ ቢመለስ ችግር ውስጥ እንደሚወድቅ በአሠሪው ስለተገለፀ ብቻ ሠራተኛው ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት በሚል የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43/3/ | 49931 | የጎሸና እርግብ መለስተኛና አነስተኛ የሕዝብ ማመላለሽ ባለንብረቶች ማህበር<br>እና<br>አቶ ተሰማ ኃይሉ | ሚያዝያ 21/2002 | 254 |
| 96 | የድርጅት መዋቅራዊ ለውጥ ያደረገ ተቋም በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ መሠረት ሠራተኞቹን አዲስ በሚያወጣው የሥራ መደብ ላይ ተመርኩዞ የሥራ ምደባ ሊያከናውን የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 28 | 50838 | ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት<br>እና እነ አቶ አማረ አበራ (ሰባት ሰዎች) | ሚያዝያ 12/2002 | 256 |
| 97 | ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ አሰሪ ሠራተኛው የፈፀመውን ድርጊት መሠረት አድርጐ ለማሰናበት የሚችለው የሥራ ውሉን ለማቋረጥ ምክንያት የሆነው ነገር መከሰቱን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠሩ ሰላሳ ቀናት ውስጥ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(3) | 45746 | ጉደር አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል/ማህበር<br>እና<br>አቶ በለጠ ጫላ | ሚያዝያ 6/2002 | 258 |
| 98 | ሠራተኛ የተረከባቸውን ንብረቶች አላስረከበም ወይም አጉድሏል በሚል የሥራ ውሉ በተቋረጠ ጊዜ የሚጠይቃቸውን ተገቢ ክፍያዎች ሊጠይቅ አይችልም በሚል በአሠሪው የሚቀርብ ክርክር ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ | 44405 | ፊንፊኔ የቤትና የቢሮ ዕቃዎች ፋብሪካ ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና አቶ ደጃ ደምሴ ጎበና | ግንቦት 19/2002 | 260 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 36,37,38 | | | | |
| 99 | ወደ ሥራ እንዲመለስ ፍርድ የተሰጠ እንደሆነና በአሰሪው ችግርም ሆነ በሠራተኛው ፍላጎት በፍርዱ መሠረት ወደ ሥራ ለመመለስ ሠራተኛው ያልፈለገ ከሆነ ሠራተኛው የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ በምትክነት በሰጠው መብት መሠረት በመመለሱ ፈንታ ካሣ እንዲከፈለው አፈፃፀሙን ለያዘው ችሎት ጥያቄውን ባቀረበ ጊዜ ሊስተናገድ የሚገባው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 43(3) | 53064 | አቶ ደሬሳ ኮቱ<br>እና<br>የአምቦ ገበሬዎች የህብረት ሥራ ዩኒየን | ግንቦት 17/2002 | 263 |
| 100 | በድርጅት ውስጥ የተከሰተ ተጨባጭ ችግርን ለመቅረፍና የድርጅቱን ትርፋማነት ለማስቀጠል በሚል በተመሳሳይ ሙያና ደረጃ ላይ ካሉ ሠራተኞች መካከል ተለይቼ ወደ ሌላ የሥራ መደብ ስለተዛወርኩኝ እንድመለስ ይወሰንልኝ በማለት የሚቀርብ አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለው ስለመሆኑ | 50182 | የአዲስ አበባ ቁራዎች ድርጅት እና አቶ አበበ ተፈራ ይልማ | ግንቦት 13/2002 | 265 |
| 101 | የሥራ ውል የተደረገው ለተወሰነ ጊዜ ወይም ሥራ ነው በሚል ክርክር በቀረበ ጊዜ ይህንኑ የማስረዳት ሸክም የሚኖር ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 9 | 44218 | የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ታጁ አባጋሮ (ሃያ አንድ ሰዎች) | ግንቦት 13/2002 | 267 |
| 102 | አንድ አሰሪ በሥራ ላይ ጉዳት የደረሰበትን ሰራተኛ ወደ ውጭ አገር ልኮ ስለሚያሳክምበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 124,105 | 46363 | ሚሲኒ ኮንስትሩቶሪ ኤስ.ፒ.ኤ<br>እና<br>አቶ ትግሉ ፍሬህይወት | ግንቦት 19/2002 | 270 |
| 103 | • ከአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት ጋር በተገናኘ ሁለቱ ወገኖች አዋጅ ቁ. 377/96 "ን" ወደ ጎን በማድረግ በሌላ አገር ህግ ለመዳኘት ስምምነት ያደረጉ በመሆኑ ብቻ ጉዳዩ የግለሰብ አለም አቀፍ ህግ ጥያቄን ያስነሳል በሚል በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊስተናገድ የማይገባ ስለመሆኑ<br>• አዋጅ ቁ. 377/96 የውጭ አገር ድርጅት ሆኖ በኢትዮጵያ ተመዝግቦ በሚሰራ የበጐ አድራጐት ድርጅት ላይ ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3/3/ /ለ/ | 50923 | ፋውንዴሽን አፍሪካ<br>እና<br>አቶ አለሙ ታደሰ | ግንቦት 19/2002 | 273 |
| 104 | ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ የሚነሣው የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚሰላው የሥራ ቀናትን ብቻ በማስላት ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 163(2) | 51912 | የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት እና ወ/ሮ ሶፋኒት አጥናፉ | ሰኔ 7/2002 | 276 |
| 105 | • በአሰሪ የተፈፀመው የሥራ ስንብት ህገ-ወጥ ቢሆንም ከሥራ ግንኙነቱ ፀባይ የተነሣ ከፍተኛ ችግር የሚፈጠር በሆነ ጊዜ ሠራተኛውን ወደ ሥራ ከመመለስ ይልቅ ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት ማድረግ ተገቢ ስለመሆኑ<br>• የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ አንቀፅ 43(3) በአንድ በኩል የሠራተኛን የሥራ ዋስትና በሌላ በኩል ደግሞ የኢንዱስትሪን ሰላም በማመዛዘን ትርጉም ሊሰጠው የሚገባ ስለመሆኑ | 55189 | አዲስ አበባ ሂልተን ሆቴል<br>እና<br>አቶ ዘላለም መንግስቱ | ሰኔ 30/2002 | 279 |
| 106 | በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ ‹‹… ውሉ የሚቋረጥበት ምክንያት መከሰቱን ካወቀበት…›› በሚል የተመለከተው ሃረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(3) | 53358 | የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና አቶ ጥላሁን ኩማ | ሰኔ 18/2002 | 281 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 107 | አንድ የሥራ ውል ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ የተደረገ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 9,10 | 43160 | እነ እንደገና ተሾመ<br>(ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>ኒው ጄኔሬሽን ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ነቀምቴ ቅርንጫፍ | ሰኔ<br>22/2002 | 283 |
| 108 | በማናቸውም ምክንያት የሥራ ውል ሲቋረጥ ሠራተኛው ያልወሰደው የዓመት እረፍት ፈቃድ በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈል የሚገባ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 77(5) ,24(2) | 52459 | እነ ወ/ሮ ሙሉ ታደሰ<br>እና አለሙ መራ<br>ኮንስትራክሽን ጠቅላላ ብረታ ብረት ሥራ ድርጅት | ሐምሌ<br>16/2002 | 285 |
| 109 | በክረምት ወቅት የማስተማር ሥራ እንዲሠራ የሚያዝ ግልፅ ደንብ ወይም መመሪያ የሌለ እንደሆነ ወይም አስተማሪው በክረምት ወራት ለማስተማር የገባው የውል ግዴታ (ስምምነት) በሌለ ጊዜ በክረምት ወቅት ሥራን ለመስራት ፈቃደኛ አልሆነም በሚል ከሥራ ሊሰናበት የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 13(1) | 45170 | የቅድስት ማሪያም አፀደ ህፃናት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት<br>እና<br>መ/ት ሲሳይ ሙሉጌታ | ሐምሌ<br>8/2002 | 287 |
| | **የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት** | | | | 289 |
| 110 | በክርክር የግድ ተካፋይ ሊሆኑ የሚገባቸው ወገኖች እና የፍ/ቤት ሚና<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 39,(1),40(2) | 43424 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና እነ አቶ መስፍን /ስምንት ሰዎች/ | ጥቅምት<br>10/2002 | 290 |
| 111 | የቃል ክርክር እንዲሰማ በተቀጠረበት ዕለት ግራ ቀኝ የሆኑ ወገኖች ያልቀረቡ እንደሆነ መዝገቡ መዘጋት ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 69(2) | 43410 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ሰላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል | ህዳር<br>30/2002 | 293 |
| 112 | አንድን ፍሬ ነገር ለማስረዳት ተለይቶ የተመለከተ ማስረጃ እንዲቀርብ ህጉ ካላስገደደ በቀር ይህንን ፍሬ ነገር በማንኛውም የማስረጃ ዓይነት ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ | 47551 | ንግድ ማተሚያ ድርጅት እና አቶ ካሱ ሙላት | ታህሣሥ<br>6/2002 | 295 |
| 113 | ጣልቃ በመግባት በክርክር ተሳታፊ ለመሆን ጠይቆ የተፈቀደለትና የጣልቃ ገብነት አቤቱታውን ለተከራካሪ ወገኖች ማድረስ ሲገባው ይህን ባለመፈፀሙ መብቱ ከተሰረዘበት በኋላ ፍ/ቤቱ በሰጠው ውሣኔ ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሠረት የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41,358 | 40229 | ወ/ሮ ኸይሮ መሐመድ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ መዲና በያን<br>(ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ<br>15/2002 | 297 |
| 114 | በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ትዕዛዝ የተሰጠበት ተከራካሪ ወገን ፍ/ቤቱ ለጉዳዩ የመጨረሻ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት አቤቱታው ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70(ሀ), 78,69,72 | 43731 | ሲ.ጂ.ሲ.አቨርሲስ ኮንስትራክሽን ኢትዮጵያ ሊሚትድ እና ሰለሞን እንዳለ | ታህሣሥ<br>8/2002 | 299 |
| 115 | • በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 280 መሠረት መዝገብ ሊዘጋ የሚችልበት አግባብ<br>• ተከራካሪ ወገኖች በአቤቱታቸው ዳኝነት የሚጠይቁበትን ፍሬ ነገር በአግባቡ ከገለፁ ትክክለኛውን የህግ ድንጋጌ አለመጥቀሳቸው መብታቸውን የሚያስቀር ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 280,69(2), 70(መ), 71(2) | 39581 | አቶ ውብሸት ካሣዬ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ማዕድን ሃብት ኮርፖሬሽን | ጥር<br>25/2002 | 302 |
| 116 | ተከራካሪ ወገኖች በአቤቱታቸው ላይ የጠቀሷቸውን የሰው ማስረጃዎች ሊለውጡ (ሊቀይሩ) የሚችሉበት አግባብ | 45984 | ፕሮፌሰር ረዳ ተ/ኃይማኖት እና አቶ ልመንህ ተፈራ | ጥር<br>26/2002 | 304 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 223/2/,234 | | | | |
| 117 | የክርክር ጭብጥ የሚመሰረተው ከሳሽ የሚያቀርበውን ክስና ማስረጃ በተከሳሽ የቀረበውን የመከላከያ መልስና ማስረጃ እንዲሁም ፍ/ቤቱ የቃል ምርመራ ሲያደርግ የሚያገኘውን ፍሬ ጉዳይ መሠረት በማድረግ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 241,248 | 47252 | ወ/ሮ ፑሽፓላት ጆሴፍ<br>እና<br>አቶ ሠይፈ ጎሣዬ | የካቲት 26/2002 | 307 |
| 118 | ዳኝነት እንደገና እንዲታይ (Review of judgement) በሚል የሚቀርብ አቤቱታ አስቀድሞ በተሰጠ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የተባለበት ነው በሚል ምክንያት ብቻ ውድቅ ሊደረግ የማይገባ ስለመሆኑ (ከዚህ ቀደም በሰበር ችሎት የተሰጠው የሕግ ትርጉም የተለወጠ ስለመሆኑ)<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1)(ሀ),(ለ) | 43821 | ወ/ሮ ትርሃስ ፍስሀዬ እና ወ/ሮ ዘነበች በሪሁን | ጥር 5/2002 | 310 |
| 119 | ዳኝነት በድጋሚ እንዲታይ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ላይ በተሰጠ ትእዛዝ/ብይን ላይ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6(3)(4) | 42871 | የቀድሞ ወረዳ 07 ቀበሌ 32 አስተዳደር ጽ/ቤት እና ወ/ሮ ጆሮ ዋቅጅራ | ጥር 12/2002 | 315 |
| 120 | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 421 መሠረት ክስ ለመመስረት የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418,421 | 37214 | አቶ ተስፋዬ አለሙ እና እነ ሐጂ ይማም ሙዘይን(ሦስት ሰዎች) | የካቲት 25/2002 | 318 |
| 121 | በፍ/ብሔር ክርክር አንድ መብት ወይም ግዴታ አለ ብሎ የሚከራከር ወገን መብቱ ወይም ግዴታው ስለመኖሩ የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ | 44634 | አቶ ታዬ ሆሳዕና እና ወ/ሮ መሠረት ወልደየስ | የካቲት 22/2002 | 320 |
| 122 | ፍ/ቤቶች ለቀረበላቸው ክስ ምክንያት የሆነው ነገር መቋረጡን ወይም ጨርሶ መቅረቱን በክሱ ሂደት በማንኛውም ደረጃ በቂ በሆነ ማስረጃ በተገነዘቡ ጊዜ ክሱን ሊዘጉት የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 280 | 45371 | የገነተ-ጽጌ ቅ/ጊዮርጊስ ማህበር በኩር ሰንበቴ<br>እና<br>እነ አቶ ማሞ ተሠማ (ሦስት ሰዎች) | የካቲት 8/2002 | 322 |
| 123 | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 216 መሠረት በድጋሚ ክስ እንዳይቀርብ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 216(3) | 36776 | መብራቱ፣ተ/ማሪያም፣ገ/ማ ሪያም የሽርክና ማህበር እና አቶ መብራቱ ዓንዳይ | መጋቢት 7/2002 | 324 |
| 124 | ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር በዋናው ጉዳይ ላይ የራሱን ውሣኔ ካሣለፈና የበላይ የሆነ ፍ/ቤት ደግሞ የይግባኝ ውሳኔውን ባለመቀበል የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በደፈናው በማፅናት የሚሰጠው ውሣኔ የተከራካሪ ወገን የይግባኝ መብት የሚያጣብብና የሥነ-ሥርዓት ህግ ደንብን የሚጥስ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 341,342,343 | 44545 | ክፍሉ መሓሪ<br>እና<br>በላይ ከመላ | መጋቢት 7/2002 | 326 |
| 125 | የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለሰጠው ብድር በመያዣነት የያዘ ባለገንዘብ ባንክ መብቱ በይርጋ እስካልታገደ ድረስ የያዘውን ንብረት በጨረታ ለመሸጥ የሚገደድበት ተለይቶ በህግ የተቀመጠ የጊዜ ገደብ የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 97/90<br>አዋጅ ቁ. 216/92 አንቀፅ 2<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሀ/ቁ. 394 - 449 | 44883 | አቶ ፈንታ ምህረቱ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | መጋቢት 8/2002 | 328 |
| 126 | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43 ሊተረጉም የሚችልበት አግባብ | 39799 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና ወ/ሮ ገነት ስዩም | መጋቢት 21/2002 | 331 |
| 127 | • በተከራካሪ ወገኖች የሚቆጠሩ ማስረጃዎች ሳይሰሙ የሚቀሩት ለተያዘው ጉዳይ | 43845 | የገቢዎችና ጉምሩክ | መጋቢት 20/2002 | 334 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አግባብነት የሌላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ<br>• ፍ/ቤቶች ተከራካሪ ወገኖች የቆጠሩትን ማስረጃ ሳይሰሙ ወደ ጐን በመተው አቤቱታቸውን በበቂ ማስረጃ አላስረዱም በሚል የሚደርሱበት መደምደሚያ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ | | ባለስልጣን<br>እና ጌታይዳ ኃ/የተ/የግል ማህበር | | |
| 128 | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 208 መሠረት በሥር ፍ/ቤት የተደረገ እርማትን መነሻ በማድረግ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አስቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ ለመለወጥ የሚያስችለው የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 208,209,320,(1) ,348(1) | 44931 | ወ/ሮ ሰዓዳ ኢድሪስ<br>እና<br>አቶ ረሺድ ቡባ | መጋቢት 20/2002 | 337 |
| 129 | የፍ/ቤትን ክብርንና የዳኝነት ሥርዓቱን መልካም አመራር ለማስጠበቅ ሲባል የማንኛውም ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ በችሎት ውስጥ በሚገኝ ማንኛውም ሰው ላይ ቅጣት ሊወሰን የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 480 | 48237 | ወ/ሮ ሰኢዳ ሁሴን ይመር<br>ተጠሪ፡የለም | መጋቢት 6/2002 | 339 |
| 130 | ክስ የቀረበለት ፍ/ቤት ወደ ጉዳዩ ሥረ-ነገር ገብቶ ተከሳሽ የሆነን ወገን በሌለበት ባለዕዳ የሚያደርግ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ተከሳሹ በአግባቡ ስለመጠራቱ ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 97, 95(3) | 50022 | 5 ብራዘርስ ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና ዓብደላ ኢብሮ ዩሴፍ | መጋቢት 29/2002 | 341 |
| 131 | የንብረት ክፍፍል እንዲደረግ በፍርድ ቤት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በውሳኔው ወቅት ንብረቱን በእጁ አድርጐ የሚገኘው ወገን የንብረቱን ስመ ሐብት ወደ ሌላ ሦስተኛ ወገን አዛውሮ ሲገኝ ፍርድ ቤቶች ሊከተሉት ስለሚገባው አካሔድ | 45038 | እነ ወ/ሮ አለሚቱ ጓዱ<br>(ሁለት ሰዎች)<br>እና ወ/ሮ አስረስ አህመድ | መጋቢት 23/2002 | 343 |
| 132 | • ሐሰተኛ ቃል ተሰጥቷል በሚል ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 481 መሠረት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ሊሰጥ የሚችልበት አግባብ<br>• በአንድ የወንጀል ድርጊት ነፃ የተባለ ሰው እንደገና ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ተደርጐ የሚቀጣበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 481 የወንጀል ህግ ቁ. 452(1) | 43005 | እነ አቶ አውግቸው እርገጤ<br>(ሦስት ሰዎች)<br>ተጠሪ፡የለም | ሚያዝያ 19/2002 | 345 |
| 133 | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6 መሠረት ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ ለሰጠ ፍ/ቤት አቤቱታ ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6 | 45839 | ወ/ሮ ይርጋለም ከበደ እና<br>እነ ወ/ሮ ፅጌ ሚካኤል<br>(አምስት ሰዎች) | ሚያዝያ 5/2002 | 348 |
| 134 | በፍ/ብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ መሠረት ተጨማሪ ማስረጃ ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 256, 345, 327 | 39853 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>እነ የአፋር ነፃ አውጪ ግንባር (ሁለት ሰዎች) | ሚያዝያ 21/2002 | 350 |
| 135 | አቤቱታ የቀረበበት ጉዳይ ከማስረጃ ምዘና ጋር የተያያዘና የፍሬ ነገር ክርክር ላይ ያተኮረ እንደሆነ በሰበር ችሎት ሊስተናገድ የማይችል ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 80(3), አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀፅ 10 | 41526 | ትራንስ አፍሪካ ትራንስፖርት አ.ማ<br>እና<br>ሙሉ ኤሌክትሮኒክስ ኢንጅነሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር | ግንቦት 2/2002 | 353 |
| 136 | ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በእርቅ ለመጨረስ የተስማሙና ይሄንኑም ስምምነት ለፍ/ቤት በማቅረብ ያስፀደቁ በሆነ ጊዜ | 52752 | እነ ከድር ሐጂ ሁሴን<br>(ሁለት ሰዎች) እና እነ<br>አቶ አሚን ዑስማን | ሰኔ 16/2002 | 355 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስምምነቱ እንደ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተቆጥሮ መፈፀም ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 277 | | (ሁለት ሰዎች) | | |
| 137 | ፍ/ቤቶች የቀረበላቸው አቤቱታ የክስ ምክንያት አለው ወይም የለውም ብሎ ለመወሰን በክስ ላይ የተገለፀው ነገር ቢረጋገጥ ከሳሽ የሆነው ወገን የጠየቀውን ዳኝነት ለማግኘት ህግ ይፈቅድለታል ወይስ አይፈቅድለትም የሚለውን ጥያቄ መመርመር ያለባቸው ስለመሆኑ | 45247 | አቶ ደጀኔ በላቸው እና<br>አቶ ነስሩ አወል | ሰኔ<br>17/2002 | 358 |
| 138 | ሁለት ሰዎች ተጣምረው በተከሰሱ ጊዜ አንደኛው ወገን ጉዳዩ በሌለበት ከታየ በኋላ ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተፈቀደለት እንደሆነ ሌላኛው ተከሳሽ አስቀድሞ ያነሳቸውን መቃወሚያዎች በድጋሚ ልታነሣና ልትከራከር አትችልም ሊባል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 | 49857 | ወ/ሮ ፈትለወርቅ መንገሻ ፋንታ<br>እና<br>ወ/ሮ በላይነሽ ወ/ኪዳን | ሰኔ<br>30/2002 | 361 |
| 139 | በግልፅ ያልተካደ ፍሬ ነገር እንደታመነ ይቆጠራል የሚለው የሥነ- ሥርዓት ህግ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው ተከሳሽ ቀርቦ ክርክሩን ባሰማ ጊዜ ስለመሆኑና ድንጋጌው የካሣ ጥያቄ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 235(2),83 | 48632 | አቶ ሙልሳ በየቻ<br>እና<br>አቶ ደበሌ በየቻ | ሰኔ<br>14/2002 | 363 |
| 140 | ክስ የቀረበበት ወገን ክሱን ለማስተባበል የሚቆጥራቸው ማስረጃዎችን ተቀብሎ አለመስማት የመከላከል ህጋዊ መብትን የሚያጣብብ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ5 223, 234, 137, 249, 256 | 49660 | እነ መንበረ መንግስት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ት/ቤት (ሁለት ሰዎች)<br>እና መምህር ሲሳይ ደጀኔ | ሰኔ<br>22/2002 | 365 |
| 141 | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(1) መሠረት በድጋሚ ክስ ማቅረብ የማይቻለው በቀደመው ክርክር የተያዘው ጭብጥና የፍሬ ነገር ክርክር ተመሳሳይ መሆኑና የተከራካሪ ወገኖች አንድነት በመኖሩ ብቻ ሣይሆን በፍሬ ጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 | 52525 | ወ/ሮ የትምወርቅ ሰብስቤ<br>እና<br>አቶ ሽዋረጋ ደመቀ | ሰኔ<br>29/2002 | 368 |
| 142 | የሥር ፍ/ቤት በመቃወሚያ ላይ የሰጠውን ውሣኔ የሚለውጥ ውሣኔ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠ እንደሆነ በግራ ቀኝ ወገኖችን በኩል የሚቀርቡ የፍሬ ነገር ክርክሮችንና ማስረጃ በአግባቡ ለመስማት ብሎም የተከራካሪዎችን ይግባኝ መብት ላለማጣበብ ሲባል ጉዳዩ ወደ ሥር ፍ/ቤት መመለስ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 341(1) | 43331 | አቶ ገመቹ ቡቻላ<br>እና<br>አቶ በቀለ ኩማ (ቡቻላ) | ሐምሌ<br>19/2002 | 370 |
| 143 | ስልጣን ለሌለው የዳኝነት አካል ክስ ማቅረብና ክርክር ማካሔድ የይርጋ ጊዜን የሚያቋርጥ ስለመሆኑ ( ከዚህ ቀደም የሰበር ችሎት በተቃራኒው የሰጠው የህግ ትርጉም የተለወጠ ስለመሆኑ።)<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 138, 147, 164(1)<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 9, 23,(1) (ለ) ,231,(1)(ለ), 278(3)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1851 (ለ),1852(1) | 36730 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን<br>እና<br>አቶ አማረ ገላው | ሐምሌ<br>30/2002 | 372 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁ. 454/97 አንቀፅ 2(4) | | | | |
| 144 | • በፍ/ብሔር ጉዳይ ተከሣሽ ለሆነ ወገን ከፍ/ቤት የሚላከውን መጥሪያ ለተከሳሹ ሊደርስ የሚችልበትን የተሻለ አማራጭ መንገድ በመለየት ሊላክ የሚገባ ስለመሆኑ<br>• የመኖሪያ አድራሻው በግልፅ ለሚታወቅ ተከሳሽ ፍ/ቤቱ የሚልከውን መጥሪያ በፍ/ቤቱ ቅጥር ግቢ ብቻ እንዲለጠፍ በማድረግ ተከሳሹ አልቀረበም በሚል በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ<br>• መጥሪያ በአግባቡ እንዲደርሰው ያልተደረገ ተከሳሽ በሌለበት ታይቶ የተሰጠበት ውሣኔ እንዲነሣለት የሚያቀርበው አቤቱታ ተገቢነት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 105(1), 78, | 50376 | ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ገሰሰ<br>እና<br>በአራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 07/08 አስተዳደር ጽ/ቤት | ሐምሌ 12/2002 | 378 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ቤተሰብ | | 1 |
| 1 | በጋብቻ ውል ላይ ባልና ሚስት "መተዳደሪያችን" ነው በሚል ያመለከቷቸው ንብረቶች የጋራ ንብረት ተደርገው የሚቆጠሩ ስለመሆናቸው | 38544 | አቶ ብሩክ ኃ/እየሱስ እና ወ/ሮ ፋናዬ አበበ | ጥቅምት 5/2002 | 2 |
| 2 | • በጋብቻ ላይ የተደረገ ጋብቻ ከጅምሩ ውጤት አልባ ነው (void ab initio) ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ<br>• የጋብቻ ውል ተጋቢዎች ንብረታቸውን በተመለከተ ጋብቻው የሚያስከትለውን ውጤት ስምምነት የሚያደርጉበት ሰነድ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 42,44,33,11 | 39408 | አርጋው አባቴ እና የወ/ሮ አስቴር አበጋዝ ወራሾች (ስድስት ሰዎች) | ጥቅምት 24/2002 | 5 |
| 3 | የውርስ ሀብትድርሻ ክፍፍል ጥያቄ በይርጋ የሚታገድበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1080(3) | 40418 | ተስፋዬ ሞላ እና እነ እሸቱ ምነ (ሦስት ሰዎች) | ጥቅምት 10/2002 | 7 |
| 4 | አባትነት በፍርድ ውሣኔ ሊታወቅ የሚችልበት አግባብ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 43 | 42682 | እነ ወ/ሮ ፋንታነሽ በላይ (ሦስት ሰዎች) እና ሞላ ደምሴ | ጥቅምት 10/2002 | 9 |
| 5 | ፀንቶ ባለ ጋብቻ ውስጥ የተወለደ ልጅ አባት በጋብቻ ውስጥ ባል የሆነው ወገን ስለመሆኑና የዚህን ሰው አባትነት ለመቃወም የሚቻልበት አግባብ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 144,126,167,168,173 | 40624 | እነ ወ/ሮ መብራት ታደሰ (አራት ሰዎች) እና አቶ ኤፍሬም ዘውዴ | ጥቅምት 12/2002 | 11 |
| 6 | የጋራ የሆነን የውርስ ሀብት ከፍቃዱ ውጪ እንዲሸጥ የተደረገበት ወራሽ ከሽያጩ ዋጋ ድርሻውን ለማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1266,1060(1) | 41857 | አሕመድ ሑሴን እና እነ ወ/ሮ የኔዓለም ተመስገን (ሦስትሰዎች) | ጥቅምት 24/2002 | 14 |
| 7 | አባትነት በፍርድ ውሣኔ ሊታወቅ የሚችልበት አግባብ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 43 | 42682 | እነ ወ/ሮ ፋንታነሽ ሲሳይ (ሦስት ሰዎች) እና ሞላ ደምሴ | ጥቅምት 10/2002 | 17 |
| 8 | ከጋብቻ በፊት የግል የነበረ ንብረት በተጋቢዎች የጋብቻ ውል መነሻነት የጋራ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ | 42766 | እነ ወ/ት ሡናይት ኃ/ማሪያም እና ወ/ሮ አበበች ወርቁ | ጥቅምት 10/2002 | 19 |
| 9 | ልጅነትን በማረጋገጥ በፍ/ቤት የሚሰጥ ውሣኔ የህግ ግምት የሚፈጥር እንጂ አስገዳጅነት ያለው እና የመጨረሻ ማስረጃ ተደርጐ መወሰድ የሌለበት ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 154,155,156,157 | 42648 | ወ/ሮ ዘነበች በያን እና ወ/ት ብርቅነሽ ከበደ | ታህሣሥ 6/2002 | 21 |
| 10 | አባትነት በህግ አግባብ ሊታወቅ የሚችልባቸው ሁኔታዎች<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 126,1(1),(2),128(1),130(2),125,106(1),<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 35(2) | 44612 | ወ/ሮ ዘውዴ ወ/ጊዮርጊስ እና ወ/ት ኤልሣቤጥ ኪዳኔ | ጥቅምት 10/2002 | 23 |
| 11 | • በውርስ ሕግ ውስጥ የተመለከቱ የይርጋ ድንጋጌዎች ሊተረጐሙ የሚችሉበት | 38533 | እነ ወ/ሮ ጽጌ | ህዳር | 27 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አግባብ<br>• የወራሽነት መብትን በሕግ በተመለከተ ጊዜ ውስጥ ያረጋገጡ ወራሾች የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄን በማናቸውም ጊዜ ማቅረብ የሚችሉ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996,1000(1),1000(2),1060,1062 | | ወልደመስቀል (ስድስት ሰዎች) እና አቶ ስዩም ክፍሌ | 8/2002 | |
| 12 | ልጅነት ሊረጋገጥ የሚችልበት አግባብ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 156,168,158,169 | 42569 | እነ የዳግማዊ ታዲዩስ ሞግዚትና አስተዳዳሪ (ሁለት ሰዎች) እና የሃና ታዲዮስ ሞግዚትና አስተዳዳሪ | ታህሣሥ 212002 | 30 |
| 13 | ኑዛዜ ሊተረጎም የሚገባው ቃላቶቹና መልዕክቱ ግልፅ ሣይሆን ሲቀር ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 810(2) | 47487 | አቶ ሐይለራጉኤል ደበላ እና<br>እነ ወ/ሪት አለምፀሐይ ፈለገ (ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ 27/2002 | 33 |
| 14 | የስጦታ ውል ሊተረጐም የሚገባው በውሉ ውስጥ የሚገኘን አንድ ሃረግ ነጥሎ በማውጣት ሳይሆን የውሉን አጠቃላይ ይዘት በመመልከት ስለመሆኑ | 41893 | ወ/ሮ ዮዲት ኃይሉ እና እነ ወ/ሪት ገነት አረጋይ (ሦስት ሰዎች) | ታህሣሥ 21/2002 | 36 |
| 15 | የምትክ ወራሽነት ተጠቃሚዎችን ስለመለየት<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 842,843,844(3) | 47957 | እነ አቶ ተፈሪ ሐጉስ (ሦስት ሰዎች) እና<br>አቶ ተስፋይ ገ/እግዚአብሔር | ጥር 5/2002 | 39 |
| 16 | • የስጦታ ውል ገደብ ያለበት ወይም ግዴታ የተጣለበት እንደሆነ በውሉ ውስጥ የተመለከተው ግዴታ አልተፈፀመም በሚል ፈራሽ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ<br>• በፍ/ብ/ህ/ቁ. 244(1) ላይ የተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ በስጦታ ውል ውስጥ የተመለከተ ግዴታ አልተፈፀመም በሚል ውሉ እንዲፈርስ ሲጠየቅ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2452(1),2464(1),2441(1) | 42346 | እነ አቶ ፍስሐ መንግስቱ (ሁለት ሰዎች) እና<br>ወ/ሮ አለምነሽ ፍስሐ | የካቲት 9/2002 | 41 |
| 17 | የጉዲፈቻ ስምምነት የሕፃናትን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል ሊፈርስ የሚችል ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 195(2) | 44101 | ሚስስ ፍራንስዊስ ፖስተር እና<br>እነ ሚ/ር ዱክማን ቬኖ (ሁለት ሰዎች) | የካቲት 24/2002 | 44 |
| 18 | የውርስ ንብረት በሆነ ቤት ላይ ድርሻ አለን የሚሉ ወገኖች ንብረቱን ህጋዊ የሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ይዞ ከነበረ ሰው በመግዛት ስመ ሀብቱን ወደራሱ ስም አዛውሮ የሚገኘን ሰው ለመጠየቅ የማይችሉ ስለመሆኑ | 46527 | ወ/ሮ ገነት በቀለ እና<br>ወ/ሮ ትዕግስት አሰፋ | የካቲት 24/2002 | 48 |
| 19 | ከውርስ ጋር በተያያዘ በቤት ላይ ህጋዊ መብት የሌለው ሰው ሽያጭ አከናውኖ ሲገኝ ትክክለኛው ባለሃብት መብቱን ሊጠይቅ የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጐ የገዛውን ገዥ ሣይሆን ሻጩን ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 997,2882, 2884,1060(1),1266 | 47378 | አቶ አለማየሁ ከተማ እና<br>እነ ወ/ሮ ላቀች አይተንፍሱ (ሦስት ሰዎች) | የካቲት 24/2002 | 50 |
| 20 | ኑዛዜ በፍ/ቤት መፅደቁ በንብረት ላይ ያለ የባለቤትነት መብትን የሚያረጋግጥ ስላለመሆኑ | 42482 | እነ አቶ ፍሬዘውድ ተካ ጉጂ (ሁለት ሰዎች) እና<br>አቶ ሰለሞን ኃ/ማሪያም | የካቲት 3/2002 | 53 |
| 21 | የልጆች ቀለብ አከፋፈል ሁኔታ ጋር በተያያዘ ክፍያ ተግባራዊ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ | 45819 | አቶ ካሣ ፋንታ እና ወ/ሮ እስካዳር ግጨው | የካቲት 12/2002 | 55 |
| 22 | በትዳር ወቅት የተወሰደ ብድር የአንደኛው ተጋቢ ፈቃድ የሌለበት ቢሆንም ፈቃዱን ያልሰጠው ተጋቢ የብድር ስምምነቱ እንዲፈርስ | 45202 | አቶ ድንቁ ወርዶፋ እና | መጋቢት 8/2002 | 57 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ያላደረገ እንደሆነ ወይም ደግሞ ለትዳር ጥቅም አለመዋሉን ማስረዳት ያልቻለ ከሆነ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ የህግ ግምት የሚወሰድ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 68(መ) | | ወ/ሪት ኤደን ድንቁ ወርዶፋ | | |
| 23 | በተጭበረበረ መንገድ ወራሽነትን አሳውጆ የውርስ ንብረት አካል የሆነን ቤት ስመ ሃብት ወደ ራሱ አዙሮ የሚገኝ ሰው ጋር የሽያጭ ውል በተደረገ ጊዜ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ በሚል ትክክለኛ ወራሾች የሚያቀርቡት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍብ/ህ/ቁ. 2882, 2884, 997 | 45370 | እነ አቶ ዳንኤል አበበ (ሁለት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ ሙሉ ወልደየስ (ሁለት ሰዎች) | መጋቢት 21/2002 | 61 |
| 24 | የስጦታ ውል ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠሩ 10 (አስር) ዓመታት ውስጥ ለአፈፃፀም ያልቀረበ እንደሆነ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1676(1),1845 | 42691 | አቶ አደፍርስ በቀለ እና አቶ ይቁም በቀለ | መጋቢት 22/2002 | 64 |
| 25 | • በውርስ ሕግ ውስጥ የተመለከቱ የይርጋ ድንጋጌዎች ሊተረጐሙ የሚችሉበት አግባብ<br>• የወራሽነት መብትን በሕግ በተመለከተ ጊዜ ውስጥ ያረጋገጡ ወራሾች የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄን በማናቸውም ጊዜ ማቅረብ የሚችሉ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ.<br>996,1000(1)1002,1060,1062 | 44237 | እነ ወ/ሮ ሙሉሸዋ ቦጋለ (አራት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ መስፍን ቦጋለ | መጋቢት 20/2002 | 66 |
| 26 | ሞግዚት የሆነ ሰው በሞግዚትነት የሚያስተዳድራቸውን ልጆች ሀብት የሆነን ንብረት ለልጆቹ መልካም አስተዳደግ ሲል ሊሸጠው የሚችል ስለመሆኑ<br>የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ ቤተሰብ ህግ አንቀፅ 292 | 46490 | እነ ወ/ሮ ቦጋለች ደባልቄ (አራት ሰዎች) እና ወ/ሮ መሠረት በለጠ | መጋቢት 21/2002 | 69 |
| 27 | በባልና ሚስት የጋራ ንብረት ላይ የተደረገ የሽያጭ ውል በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ አለመፍረሱ ስለሚያስከትለው ውጤት | 51295 | አቶ ዮሐንስ ጡእማይ<br>እና<br>ወ/ሮ ምህረት ገብሩ | መጋቢት 6/2002 | 72 |
| 28 | ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው ባለስልጣን ፊት የሚደረግ ኑዛዜ በህግ የተቀመጠውን ፎርማሊቲ አሟልቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 882 | 49851 | ወ/ሮ ታሪኳ አበበ የህፃን ሮቤል ንጉሤ ሞግዚት ተጠሪ፡የለም | ሚያዝያ 4/2002 | 75 |
| 29 | ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ የሆነ ሰው እና ከህግ ውጪ ከውርስ የተነቀለ ያለኑዛዜ ወራሽ የውርስ ሃብትን ሊከፋፈሉ የሚችሉበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 939(3) ,850,,911(1) 912(1) | 43069 | አቶ አማረ ረታ እና አቶ ሰለሞን ካሣዬ | ሚያዝያ 6/2002 | 78 |
| 30 | የጉዲፈቻ ውል እንዲፈርስ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 195(1),(2) | 52691 | እነ ቤተ ዛታ ችልድረንስ ሆም አሶሴሽን (ሦስት ሰዎች)<br>ተጠሪ፡የለም | ሚያዝያ 22/2002 | 81 |
| 31 | ኑዛዜ መኖሩን የማስረዳት ሸክም (ግዴታ) የተጠቃሚዎች ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 896,897 | 53279 | ወ/ሮ ትእግስት ግርማ የእነ አቤል ወርቁ ሞግዚት<br>እና<br>አቶ ኤፍሬም መንግስቱ | ሰኔ 8/2002 | 84 |
| 32 | በኑዛዜ የውርስ ሀብት ክፍፍል መደረግ ጋር በተያያዘ ወራሽ የሆነ ወገን ሊደርሰው ከሚገባው የውርስ ሀብት መጠን ከአንድ አራተኛ በታች እንዲደርሰው የተደረገ መሆኑ | 50901 | ወ/ሮ እልፌ ኃይሌ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ትዕግስት ደበሌ | ሰኔ 10/2002 | 87 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ካልተረጋገጠ በስተቀር ኑዛዜውን እንዲፀና በማድረግ የተናዛዥን ፍላጐት ማክበርና መጠበቅ የሚያስፈልግ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 910, 913 1123(1) | | (ሦስት ሰዎች) | | |
| 33 | በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ ስለመኖሩ ለማስረዳት የሚችሉት በግንኙነቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች ብቻ ናቸው ለማለት የሚያስችል የሕግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 98,99,106 | 46613 | ወ/ሮ ኑኑ ሽህሞሎ<br>እና<br>ወ/ሮ አስገደች ጫኔ | ሰኔ<br>24/2002 | 91 |
| 34 | በተከራካሪ ወገኖች ዳኝነት የተጠየቀበትን ጉዳይ ፍ/ቤቶች በግልፅ በመቀበል ወይም ባለመቀበል ውሣኔ ሊሰጡበት የሚገባ ስለመሆኑ | 51866 | ወ/ሮ ደጅይጥኑ አለማየሁ<br>እና ወ/ሮ አዛለች ደበበ | ሐምሌ<br>2/2002 | 94 |
| 35 | ከኮንዶሚኒየም ቤት ባለቤትነት ጋር በተያያዘ ከጋብቻ በፊት በአንደኛው ተጋቢ በተደረገ ምዝገባ የተነሣ የቤት ዕጣው የወጣው ብሎም የቤት ሽያጭ ውል የተደረገው በጋብቻ ወቅት መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ለቤቱ መገኘት ምክንያት የሆነው ተጋቢ ቤቱ የግል መሆን አለበት በሚል የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 62(2) | 51893 | እንዳልካቸው ዘለቀ<br>እና<br>ወ/ሮ ብዙዓለም መንግስቱ | ሐምሌ<br>8/2002 | 96 |
| 36 | በፍ/ቤት የተሰጠ የኑዛዜ ወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የውርስ ሃብት ማጣራት ሳይደረግ የተሰጠ ነው በሚል ምክንያት ብቻ ሊሰረዝ የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ | 50836 | ወ/ሮ ቅድስት ተካ<br>እና<br>ወ/ሮ የኔነሽ ተካ | ሐምሌ<br>13/2002 | 99 |
| 37 | ከውርስ ሃብት ክፍፍል ጋር በተያያዘ ተጠቃሚው በኢንሹራንስ ውል ላይ ባልተገለፀበት ጊዜ የሟች ባል ወይም ሚስት የኢንሹራንስ ገንዘቡን ከወራሾች ጋር ሊካፈሉ የሚችሉበት አግባብ<br>የንግድ ህግ ቁጥር 705,701(1)(ሀ)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 827 | 44561 | ወ/ሮ ገነት በላይ<br>እና አቶ ያፌት ተክሉ | ሐምሌ<br>28/2002 | 101 |
| 38 | ከውርስ ሃብት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የውርስ ሃብቱን በእጅ አድርጐ በመገልገል ላይ ያለ ተከራካሪ የሆነ ወራሽ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ንብረት በጋራ ይዞ የቆየ ሰው ላይ የሚያነሳው የውርስ ጥያቄ በይርጋ ታግዷል ሊባል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ | 44025 | እነ ወ/ሪት ፀሐይ ሐይሌ<br>(አራት ሰዎች) እና ወ/ሮ<br>ፈልቃ ቤኛ | ሐምሌ<br>22/2002 | 110 |
| 39 | ወራሽ የሆነ ወገን በውርስ ሃብት ክፍፍል ድርሻው ላይ ከሩብ የበለጠ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን በመግለፅ አውራሽ ባደረገው ኑዛዜ መሠረት ክፍፍል እንዳይፈፀም መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1123(1) | 47622 | ወ/ሮ ትዕግስት ነጋሽ እና<br>እነ ወ/ሮ መንበረ ስላሴ<br>ተኼሌ<br>(አምስት ሰዎች) | ሐምሌ<br>30/2002 | 112 |
| 40 | የምትክ ወራሽነት ተጠቃሚዎችን ስለመለየት<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 842,843,844(3) | 45587 | እነ ወ/ሮ አተረፈች ዘውደ<br>(ሁለት ሰዎች)<br>እና አቶ ዘውዱ ወሰኔ | ሐምሌ<br>29/2002 | 115 |
| 41 | በተዘዋዋሪ መንገድ ተወላጅን ከውርስ ያለ በቂ ምክንያት መንቀል የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 938,842,915 | 42546 | አቶ ተስፋልደት ኪዳኔ<br>እና እነ ወ/ሮ ዘሀቡ ይመር<br>(ሦስት ሰዎች) | ሐምሌ<br>28/2002 | 118 |
| | **ውል** | | | | 123 |
| 42 | በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የመያዣ መብት ውጤት የሚኖረው ከተፃፈበት ቀን ጀምሮ እስከ አሥር ዓመት ድረስ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3058 | 44800 | አቶ አብዱራዛቅ ሐሚድ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ጥቅምት<br>05/2002 | 124 |
| 43 | ውል በተዋዋይ ወገኖች መካከል ሊኖር የሚገባውን የቅንነትና የመተማመን ግንኙነት | 42897 | አቶ አየለ ሐብተየስ እና | ህዳር | 127 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | መሠረት በማድረግና ጉዳዮቹ ውስጥ ያለውን ልማዳዊ ሥርዓት በመከተል በቅን ልቦና ሊተረጐም የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1732(1) | | እነ ሚ/ር ኖቼራ ጃካርሎ (ሁለት ሰዎች) | 10/2002 | |
| 44 | ለጨረታ ማስከበሪያ በሚል የሚያዝ ገንዘብ ጨረታውን ባዘጋጀው አካል ሊወሰድ የሚችለው ተወዳዳሪው ጨረታውን ባሸነፈው መጠን ሆኖ በጨረታው መሠረት ውል ለመፈፀም ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ስለመሆኑ | 40947 | አቶ መዝገቡ መድህኔ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር | ህዳር 15/2002 | 131 |
| 45 | ተከራካሪ ወገኖች ባላነሱበት ሁኔታ ፍ/ቤት የውል አፃፃፍ ሥርዓትን (ፎርማሊቲን) መሠረት በማድረግ በግራ ቀኝ ወገኖች መካከል የተካሄደን ውል ፈራሽ ነው በሚል የሚሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723,1808(2) | 43825 | የህፃን ኮከቤ ተረፈ ሞግዚትና አስተዳዳሪ እና እነ አቶ አያሌው ካሳዬ (ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ 6/2002 | 133 |
| 46 | • የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2026(1) ለባንኮችና ለደንበኞቻቸው መብት ልዩ ጥበቃ የሚያደርገው የፍ/ብ/ሀ/ቁ. 2473(2) ድንጋጌን ዋጋ በሚያሳጣ መንገድ ተፈፃሚ ሊሆን የማይገባ ስለመሆኑ<br>• የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2026(1) በባንኮችና በሌሎች አበዳሪ ተቋማት እና ደንበኞቻቸው መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ተፈፃሚነት የሌለው የህግ ድንጋጌ ስለመሆኑ<br>• ባንኮች ለደንበኞቻቸው ያበደሩትን የብድር ወለድ ያልተከፈለ መሆኑን በሰው ምስክር፣ የሰነድና ሌላ ማስረጃ በማቅረብ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024(1) ስር የተደነገገውን የህሊና ግምት ለማስተባበል የሚችሉ ስለመሆኑ | 29181 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ልየው ቸኮል (ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ 20/2002 | 135 |
| 47 | በፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 2024/ረ/ መሰረት እንደተከፈለ ሊቆጠር የሚችለው በብድር የተሰጠ ገንዘብ ሳይሆን የተሰጠ ገንዘብ ላይ የሚታሰብ ወለድ ክፍያ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024 | 35758 | እነ አቶ ገብረመድኀን አየናቸው (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ሰብስቤ ኃይሌ | ታህሣሥ 20/2002 | 142 |
| 48 | የወለድ አግድ ውል ህጋዊ ነው ሊባል የሚችለው የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ መቋቋምን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን በመከተል የተደረገ እንደሆነ ስለመሆኑና በዚህ መሰረት ያልተደረገ መሆኑ ውሉን ፈራሽ ሊያደርገው የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3118,3045,3052 | 45422 | እነ አቶ ፈታኒ ባየህ (ሰባት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ አስራት ባየህ (ሦስት ሰዎች) | ጥር 13/2002 | 147 |
| 49 | የስልክ አገልግሎት ከማግኘት ጋር በተያያዘ በአገልግሎት የክፍያ መጠን ላይ በአገልግሎት ሰጪውና በአገልግሎት ተቀባዩ መካከል አለመግባባት በተፈጠረ ጊዜ የተጠየቀው የአገልግሎት ሒሳብ በእርግጥም ስልኩን በይዞታው ስር አድርጐ የሚጠቀምበት ወገን በተገለገለው መጠን የተመዘገበ ስለመሆኑ በባለሙያ እንዲጣራ በማድረግ እልባት መስጠት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1732 | 48967 | አቶ ሳዲቅ ሐሰን እና የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን | ሰኔ 30/2002 | 151 |
| 50 | መዋዕለ ነዋይን በማፍሰስ ግንባታን ለማካሄድ የከተማ ቦታን ከመንግስት ተረክቦ ግንባታን በተገቢው ጊዜ ለማጠናቀቅ አለመቻል ሊያስከትል የሚችለው ውጤት የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ደንብ ቁ. 41/97 አንቀፅ 8(3) የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ አዋጅ ቁ. 51/94 | 46052 | ዶ/ር አሸብር ወ/ጊዮርጊስ እና የቦንጋ ማዘጋጃ ቤት ከፋ ዞን | ጥር 19/2002 | 154 |
| 51 | ከቤት ኪራይ ውል ጋር በተያያዘ የኪራይ | 46394 | ወ/ሮ ስንቄ መስፍን እና | የካቲት | |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ውልን ለማቋረጥ በቂ ናቸው ሊባሉ የሚችሉ ተከራይ የሚፈፅማቸው የግንባታ አይነቶች<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2953,2954,1732 | | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | 11/2002 | 157 |
| 52 | ፍ/ቤት ተከራካሪ ወገኖች ወለድን አስመልክቶ በውላቸው ካመለከቱት ሃሳብ ውጪ የራሱን ስሌት መሠረት በማድረግ ውሣኔ መስጠት ስላለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ/. 1731,2478 | 45559 | የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ (አ.ማ) እና እነ የአቶ ኃይሉ ፈይሳ ወራሾች (ሁለት ሰዎች) | የካቲት 25/2002 | 160 |
| 53 | ከሽያጭ ጋር በተያያዘ ውል ሲመሰረት ጉድለት የነበረበት መሆኑ ቢረጋገጥም ከውሉ መመስረት በኂላ በተሸጠው ንብረት ላይ ተዋዋይ ወገኖች ተጨማሪ ግንባታ ያካሄዱና ወደ ነበሩበት ለመመለስ አዳጋች ሁኔታ ያለ መሆኑ ከታመነ ውሉ ሊፀና የሚገባው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1817(1) | 47800 | ወ/ሮ እመቤት ደርበው እና አቶ ታደሰ ሰዳሚ | የካቲት 25/2002 | 162 |
| 54 | ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የሚቆጠር የኪራይ ውል አከራይ የሆነ ወገን ለተከራይ ማስታወቂያ በመስጠት ምክንያቱን መግለፅ ሳያስፈልገው የኪራይ ውሉን ሊያቋርጥ ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2966(1) | 40336 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና የወ/ሮ አሰገደች ካሣሁን ወራሽ ሄኖክ ሣሙኤል | መጋቢት 22/2002 | 164 |
| 55 | በሌላ ሰው ድካም ወይም የሌላ ሰው ሃብት በሆነ ነገር በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ ሰው አላግባብ ጥቅም ባገኘበት መጠንና ባደረሰው ጉዳት መጠን ኪሣራ ሊከፍል የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2162 | 43381 | ወ/ሮ ፎዚያ ሁሴን እና አቶ ውብሸት ተ/ወልድ | መጋቢት 10/2002 | 166 |
| 56 | ከሳሽ የሆነ ወገን ክስ ለማቅረብ ምክንያት የሆኑትን ሁሉ በአንድ ላይና በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ለመክሰስ የሚችል (የሚገባው) የነበረ ቢሆንም ሊጠይቅ ይገባው ከነበረው ቀንሶ ያቀረበው በፍ/ቤት ፈቃድ የሆነ እንደሆነ የቀረው መብት ላይ በድጋሚ ክስ ለመመስረት የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216(4) | 43992 | እነ አቶ ይልማ አንበሴ (አራት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ እመቤት መንገሻ (አምስት ሰዎች) | መጋቢት 6/2002 | 168 |
| 57 | ከሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ ሻጭ የሚያቀርበው የውል ይፍረስልኝ ክስ ገዥ ውል እንዲፈፀምልኝ በሚል ሊያቀርብ የሚችለው አቤቱታ ላይ የሚቆጠረውን የይርጋ ጊዜ የሚያቋርጥ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845,1851 | 43636 | ወ/ሮ አልማዝ ተሰማ እና እነ አቶ በየነ ወ/ሚካኤል (ሁለት ሰዎች) | መጋቢት 22/2002 | 173 |
| 58 | የኪራይ ውልን መሠረት በማድረግ ቤትን የያዘ ወገን የኪራይ ውሉን በቅድሚያ ሣያስፈርስ የባለቤትነት ጥያቄን መሠረት በማድረግ በኪራይ ውሉ አልገደድም በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ | 46947 | አቶ ዘነበ ኃ/ማሪያም እና እነ ወ/ሮ አባይነሽ ዘለቀ (ሦስት ሰዎች) | መጋቢት 7/2002 | 175 |
| 59 | ከእጅ በእጅ ሽያጭ ጋር በተያያዘ ገገር የሽያጩን ዋጋ የከፈለበትን ደረሰኝ ይዞ መገኘቱ የገዛውን ንብረት እንደተረከበ የሚያሳይ የመጨረሻ (conclusive) ማስረጃ ነው ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2266,2278(1) እና (2) | 45545 | ወ/ሮ ሸዋዬ ኑርዬ እና ምን አዩ ኃ/የተ/የግል ማህበር | መጋቢት .22/2002 | 178 |
| 60 | በፍ/ብሔር ጉዳይ ህጋዊ ጥበቃ ሊደረግለት የሚችል ዋስትና የሚደረግበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1922 | 47971 | ወ/ሮ ጅቦኒ ቱና እና ወ/ሮ ብርቂ ኢርክታ | ሚያዝያ 5/2002 | 181 |
| 61 | ከኪራይ ውል ጋር በተያያዘ ተከራይ የሆነ | | አቶ ብርሃነ ገብረሐይሉ | | |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ወገን የተርን ኦቨር ታክስ የመክፈል ግዴታ በህግ የተጣለበት እንደሆነ አከራይ የሆነው ወገን ይህንኑ ክፍያ ለመፈፀም ይቻል ዘንድ ተከራዩን ለመጠየቅ ስለመቻሉ<br>አዋጅ ቁ. 308/95 አንቀፅ 2(3,5,7,8,9,12),6 | 48358 | እና<br>አንሲዩን ኮንትር ላፋም | ሚያዝያ<br>7/2002 | 183 |
| 62 | • አንድ ሰው ብድሩን አለመክፈሉን አምኖ በሚከራከርበት ሁኔታ የፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 2024(ረ) ተፈፃሚነት የማይኖረው ስለመሆኑ<br>• 2024(ረ) ዋና ብድርን ሣይሆን ለብድር የሚከፈል ወለድን የሚመለከት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024(ረ) | 44691 | አቶ ሽባባው ወሌ<br>እና<br>አቶ ሙሉጌታ ዓባይ | ሚያዝያ<br>8/2002 | 186 |
| 63 | አንድ ውል ህግን የሚፃረር /የሚቃረን/ ነው በሚል እንዲፈርስ የሚቀርብ ጥያቄ በአሥር ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845 | 48094 | እነ ሙና እንድሪስ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ልማት ባንክ | ግንቦት<br>10/2002 | 188 |
| 64 | በአሰሪና ሠራተኛ መካከል በተደረገ ስምምነት መሠረት አሰሪው ሠራተኛው በውጭ አገር ትምህርቱን እንዲከታተል ለማስቻል የሚያስፈልጉ ወጭዎችን ደመወዝን ጨምሮ ለመክፈል ሠራተኛው ደግሞ ትምህርቱን ሲያጠናቅቅ አሠሪውን ለማገልገል ውል ገብቶ ሠራተኛው ግዴታውን ለመፈፀም ያልቻለ በሆነ ጊዜ አሠሪው የጉዳት ኪሣራ የመጠየቅ / የመከፈል/ መብት ያለው ስለመሆኑ | 49453 | የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲቲዩት እና<br>አቶ ተፈሪ ማሞ | ግንቦት<br>19/2002 | 192 |
| 65 | የሽያጭ ውል በህግ የተቀመጠውን የአፃፃፍ ሥርዓት ባለመከተሉ ፈራሽ ሲሆን ንብረት የመመለስ ግዴታ ያለበት ወገን ንብረቱን ለውጦ ወይም በንብረቱ ላይ ወጪ አውጥቶ ከሆነ ባወጣው ወጪ መጠን ሊጠይቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1818 | 49326 | ወ/ሮ እታፈራሁ<br>ኃ/ማሪያም እና<br>እነ መምህር በቀለ ታችበሌ<br>(ሁለት ሰዎች) | ሰኔ<br>28/2002 | 195 |
| 66 | በፍ/ብሔር ጉዳይ (ክርክር) የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምርበትን ጊዜ ለመወሰን የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ/. 1846 | 42700 | የባህርና ትራንዚት<br>አገልግሎት ድርጅት እና<br>አደጋ መከላከልና ዝግጁነት<br>ኤጀንሲ | ሐምሌ<br>12/2002 | 198 |
| 67 | የእቁብ ገንዘብ ይከፈለኝ ጥያቄ በይርጋ ደንብ የሚገዛ እንጂ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2024 ሥር በተመለከተው የህሊና ግምት የሚሸፈን ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024 | 46019 | የአቶ ደሣለው ፋንታ<br>ወራሾች<br>እነ ሙሉጌታ ደሣለው እና<br>አየለ ደበላ | ሐምሌ<br>20/2002 | 202 |
| 68 | አንድ የስጦታ ውል በኃይል ወይም በተንኮል ተግባር ተደርጓል በሚል ስለሚፈርስበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2442(3),1698,1699,1704,1706 | 49900 | እነ ወ/ሮ ሐመልማል<br>ዓለሙ(ሁለት ሰዎች)<br>እና ወ/ሮ ሀረገወይን ዘለቀ | ሐምሌ<br>19/2002 | 206 |
| **አፈፃፀም** | | | | | 210 |
| 69 | የውርስ ንብረት በጨረታ እንዲሸጥ ለማድረግ መነሻ ዋጋን ለመወሰን የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1083,1084 | 43888 | አቶ ፀሐይ ወንድም እና<br>እነ አቶ አያለው መለስ<br>(ሁለት ሰዎች) | መጋቢት<br>23/2002 | 211 |
| 70 | አንድ ተጋቢ በግሉ ያመጣው ዕዳ ከሌለኛው ተጋቢ የጋራ ንብረት እንዲከፈል የሚደረገው ዕዳውን ያመጣው ተጋቢ ዕዳውን ለመክፈል አለመቻሉ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ<br>የደቡ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ እና የፌዴራል መንግስት የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ | 39837 | አቶ ስመንጉስ አሰፋ<br>እና<br>መ/ት ምህረት ክበበው | ግንቦት<br>3/2002 | 213 |
| 71 | አንድ ንብረት በፍርድ አፈፃፀም የተነሣ ሊያዝ የሚችለው በተሰጠው ፍርድ ባለዕዳ የሆነው | 46143 | ወ/ሮ ድልበጌ ራሕመቶ<br>እና እነ የባህር ትራንዚት | ሐምሌ<br>2/2002 | 215 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ወገን ሃብት መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ | | አገልግሎት ድርጅት(ሁለት ሰዎች) | | |
| | **ወንጀል** | | | | 217 |
| 72 | የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የንግድ ድርጅት ሠራተኛ፣ ሥራ አስኪያጅ እንዲሁም ድርጅቱ በወንጀል ጉዳይ ክስ ቀርቦባቸው ኃላፊ ሊሆኑ የሚችሉበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀፅ 56(1)(3)<br>አዋጅ ቁ. 609/2001 አንቀፅ 50(ለ)(1),22(1)<br>የወንጀል ህግ አንቀፅ 23(3),34(1) | 48850 | እነ አቶ ታረቀኝ ገ/ጊዮርጊስ (ሦስት ሰዎች)<br>እና<br>የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን | ታህሣሥ 8/2002 | 218 |
| 73 | በግድያ ወንጀል የተከሰሰ ሰው የፈፀመው የግድያ ድርጊት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539(1)(ሀ) ሥር የሚያስጠይቅ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ<br>የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539(1)(ሀ),84,86 | 45927 | የኦሮሚያ ክልል ዓቃቤ ሕግ<br>እና<br>መሰረት መኮንን | ጥር 19/2002 | 221 |
| 74 | በወንጀል ጉዳይ የቀረበ ክስ በዐቃቤ ህግ ምስክሮች ተሟልቶ አለመቅረብ የከሳሽ መዝገቡን የማንቀሳቀስ መብት ተጠብቆ መዘጋት በቀረበው ወንጀል ላይ ተፈፃሚ የሚሆነውን የይርጋ ጊዜ ተግባራዊ ከመሆን የሚያግደው ስላለመሆኑ | 45572 | ወ/ሮ ዘነበች ሽብሩ እና ፌ/ዐ/ህግ | የካቲት 26/2002 | 224 |
| 75 | ህጋዊ መካላከልን ከመጠን በማሳለፍ የተፈፀመ የሰው መግደል ተግባር በወንጀል ህግ ቁጥር 541(ሀ) የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 540, 541 | 43501 | እነ ረዳት ሳጅን ሺጋ ተካ ሞላ (ሦስት ሰዎች) እና የኦሮሚያ ክልል ዓ/ሕግ | መጋቢት 15/2002 | 225 |
| 76 | በወንጀል ሕግ ቁጥር 543 እና 567 መሰረት አንድ ሰው በአንድ ጊዜ ሊጠየቅ ስለሚችልበት አግባብ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543,567 | 44235 | ቄስ ጌታቸው ተሾመ<br>እና ዓቃቤ ሕግ | መጋቢት 28/2002 | 229 |
| 77 | አንድ ሰው የማታለል ተግባር ፈፅሟል በሚል በወንጀል ሊጠየቅ የሚችልበት አግባብ<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 692(1) | 46189 | ሐረገወይን ተፈራ እና ፌዴራል ዐቃቤ ሕግ | ሚያዝያ 20/2002 | 232 |
| 78 | ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ ጥፋተኛ የተባለ ተከሳሽ የዘወትር ፀባይ መልካም የነበረ መሆኑ በተናጠል (በራሱ) ቅጣትን ለማቅለል የሚያስችል ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 82(1) (ሀ) | 53612 | እነ አቶ ፍስሐ ዓባይ(ሁለት ሰዎች) እና የገቢዎችና ጉምሩክ ዓ/ህግ | ሚያዝያ 25/2002 | 234 |
| 79 | በወንጀል ጉዳይ ክስ ቀርቦ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ከተሰጠ በኂላ ወንጀለኛው በይቅርታ የተለቀቀ መሆኑ አስቀድሞ የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ እንዳልነበረ የሚያስቆጥር (በሪከርድነት እንዳይያዝ የሚያደረግ) ስላለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 230 | 41248 | ቡርቂሶ ዋቆ<br>እና<br>ዐቃቤ ሕግ | ሰኔ 23/2002 | 237 |
| 80 | በሥር ፍ/ቤት የተሰጠ የቅጣት ውሣኔ ላይ አነሰ ወይም በዛ በሚል በግልፅ ይግባኝ ባልተጠየቀበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቅጣትን ከፍ ወይም ዝቅ በማድረግ ውሣኔ ሊሰጥ የማይገባ ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 195(መ) | 48617 | ተስፋዬ አደላ<br>እና<br>ዐቃቤ ሕግ | ሰኔ 18/2002 | 239 |
| 81 | • ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ ተከራካሪ ወገኖች የማስረዳት ሽክማቸውን ተወጥተዋል ለማለት የሚቻልበት አግባብ<br>• በፍ/ቤት ፊት ቃለ- መሃላ በመፈፀም የተሰጠ የምስክር ቃል እውነት ነው በሚል የሚወሰደው ግምት ሊፈርስ የሚችል | 51706 | አቶ ግርማ ትኩ<br>እና<br>የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | ሐምሌ 21/2002 | 242 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 111 | | | | |
| **ንብረት** | | | | | 251 |
| 82 | የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣ ተሰጥቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3041,3052 | 38681 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እማሆይ ፀሐይቱ አምበሉ | ጥቅምት 3/2001 | 252 |
| 83 | ለረጅም ጊዜ በመንግስት ቁጥጥር ሥር የነበረ ቤትን ይለቀቅልኝ በሚል አቤቱታ የሚያቀርብ ወገን ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተፈቀደለት ስለመሆኑ ወይንም ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ከሆነም ለሚመለከተው አካል ጥያቄውን አቅርቦ ውሳኔ አግኝቶ ባለመብትነቱን ሳያረጋግጥ የሚያቀርበው ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁጥር 47/67 | 45161 | እነ እናኑ ጀንበሬ (ሁለት ሰዎች) እና የደሴ ከተማ ቀበሌ 03 ጽ/ቤት | ታህሣሥ 24/2002 | 255 |
| 84 | የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚቀርብ የመፋለም ክስ በይርጋ ቀሪ ነው (ቀሪ ሆኗል) ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 1677,1845,1206,1188-1192 | 43600 | ዳዊት መስፍን እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | ጥር 05/2002 | 257 |
| 85 | የአዋጅ ቁጥር 47/67 በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተሰጠን ካርታ መሰረት በማድረግ ክሥ ለመመስረት የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 47/67 | 48699 | አቶ አምሣለ ጀመሪ እና አቶ ፍርዱ ገበያሁ | ሚያዝያ 21/2002 | 262 |
| 86 | በአንድ ቤት ውስጥ ሲኖር ያልነበረ ወይም ቤቱን በእጁ አድርጐ ሲያዝበት ያልነበረ ሰው የሚያነሣው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1149 | 43081 | አቶ ሣሙኤል ጦናሮ እና እነ ወ/ሮ አይሻ አርጌሳ (አራት ሰዎች) | ግንቦት 6/2002 | 266 |
| 87 | በሃይል ቤቱ ተይዞብኛል እንዲለቀቅልኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ነው ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1206,1149 | 42861 | ወ/ሮ አጤነሽ አበበ እና አቶ ማንተጋፋቶት አጥላው | ሰኔ 28/2002 | 268 |
| 88 | • አንድን ንብረት በአደራ ለማስተደደር (ለመጠበቅ) የተረከበ ወገን አደራ ሰጪው ንብረቱ እንዲመለስ በጠየቀው ጊዜ ወዲያውኑ መመለስ ያለበት ስለመሆኑ<br>• ንብረትን በአደራ የሰጠ ወገን ንብረቱ እንዲመለስለት ከመጠየቅ ጋር በተያያዘ በህግ የተቀመጠ የጊዜ ገደብ (ይርጋ)የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2781 (1)(2),2779, 2989(1) | 48048 | ወ/ሮ ገብርኤላ ኒካላ ቶማስ ናክሶ እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | ሐምሌ 22/2002 | 270 |
| 89 | ከማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተያያዘ የጉዳት ኪሣራን ጉዳት ለሚደርስበት ወገን በመክፈል የመንገድ መተላለፊያ ( servitude right) መብት ሊከበር የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1221 | 48783 | ወ/ሮ ሶፊያ ሁሴን እና እነ የአራዳ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር (ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 27/2002 | 273 |
| **ከውል ውጭ ኃላፊነት** | | | | | 276 |
| 90 | የጉዳት ኪሣራ የሚከፈለው ጉዳት ስለመድረሱ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2090,2091 | 39601 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ገዛኸኝ መንግስቱ | ጥቅምት 5/2002 | 277 |
| 91 | ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳቱ ከመድረሱ በፊት ገቢ ያልነበረው መሆኑ በርትዕ ሊከፈለው የሚገባውን ካሣ የሚያስቀር ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2102 | 42962 | አቶ አየለ አድማሱ እና አቶ አጀቡ ሹሜ | ታህሣሥ 28/2002 | 279 |
| 92 | በወንጀል ጉዳይ ተከስሶ ጥፋት የሌለበት መሆን | 43843 | ዶ/ር ተስፋነሽ በላይ | መጋቢት | 282 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በራሱ በተመሳሳይ ጉዳይ በፍትሐብሔር ከቀረበ ክስ ነፃ ለመውጣት እንደ በቂና የመጨረሻ መስፈርት የሚወሰድ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2149 | | እና<br>አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ | 21/2002 | |
| 93 | ለተወሰነ ጊዜም ሆነ ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ሠራተኛ ከውል ውጭ በሆነ ግንኙነት በሥራ ወቅት በሌሎች ሰዎች ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት አሠሪ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2130, 2131, 2132 | 45735 | አቶ ደረጀ ቸርነት<br>እና<br>ወ/ሮ ሕይወት የኃላሸት | መጋቢት<br>21/2002 | 285 |
| 94 | በአሰሪና ሠራተኛ ክርክር ችሎት ሠራተኛው የፈፀመው ድርጊት ከሥራ ለማሰናበት በቂ አይደለም ተብሎ መወሰኑ አሰሪው በሠራተኛው ላይ በፍ/ብሔር ጉዳይ ሊያቀርብ የሚችለውን ክስ የሚያስቀር የመጨረሻ ፍርድ /ውሣኔ/ ስላለመሆኑ | 44588 | የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት እና እነ ኃይለየሱስ ቱኪ (አራት ሰዎች) | ሚያዝያ<br>4/2002 | 290 |
| 95 | ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ህይወቱ ካለፈ ሰው ጋር በተገናኘ የሚከፈለው የጉዳት ካሣ መብቱን የሚጠይቀው ሰው ዕድሜ ከአስራ ስምንት ዓመት በላይ በመሆኑ የተነሣ ብቻ ካሳው ሊከፈለው አይገባም ለማለት የሚያስችል የሕግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2095/1/ | 50225 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና<br>እነ ወ/ት ዝናሽ አሰፋ<br>(ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ<br>5/2002 | 293 |
| | **የዳኝነት ስልጣን** | | | | 295 |
| 96 | የአ.አ ከተማ መስተዳድር ምክር ቤት የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ደብተርን ለመሰረዝ የሚያስችል ስልጣን ያለው ስለመሆኑ | 34665 | እነ አቶ ናትናኤል ዘውገ (ሁለት ሰዎች)እና እነ ወ/ሮ እግዜሩ ገ/ህይወት(ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት<br>12/2002 | 296 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 97 | የከተማ ቦታ ያለአግባብ ተወስዶብኝ በሊዝ ለሌላ ተሰጥቷል በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የቦታውን መውሰድ ውሣኔ ለሰጠው አካል በቅድሚያ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑና በሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ለቦታ ማስለቀቅ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቅረብ ያለበትና ይኼው አካል የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 272/1994 | 46220 | የደቡብ ክልል የሐዋሣ ከተማ ማዘጋጃ ቤት<br>እና የሐዋሳ ደብረ ምህረት ቅ/ገብርኤል ገዳም | ጥር<br>18/2002 | 298 |
| 98 | በውጪ አገር ሕግ መሰረት የተቋቋመና በኢትዮጵያ ውስጥ ያልተመዘገበ የንግድ ድርጅት ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት በኢትዮጵያ ፍ/ቤት ቀርቦ ሊዳኝ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 27(1), አዋጅ 25/88 አንቀጽ 11(2)(ሀ) | 42928 | የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን<br>እና ድራጋዶስ ኮንስትራክሽን | ጥር<br>12/2002 | 300 |
| 99 | በብልጫ የተከፈለ የቀረጥ ገንዘብ ለባለገንዘቡ ሊመለስ የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀፅ 53(1),55 | 42866 | ብርሃነ ጥዑም እና<br>የጉምሩክ ባለስልጣን | መጋቢት<br>20/2002 | 302 |
| 100 | የሥራ መደብ ወይም እድገት ይሰጠኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የወል የሥራ ክርክርን የሚመለከት ስለመሆኑ | 48111 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና አቶ ቂጤሳ ገብሬ | ሚያዝያ<br>13/2002 | 305 |
| 101 | በውድድር አሸንፌ ያገኘሁትን የሥራ መደብ እድገት ይሰጠኝ በሚል የሚቀርብ የሥራ | 52600 | የኢትዮጵያ ቆዳ አክሲዮን ማህበር | ሚያዝያ | 308 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ክርክር የግል የሥራ ክርክር በመሆኑ በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ቦርድ የሚታይ ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 | | እና<br>አቶ ተስፋዬ ኃይሌ | 12/2002 | |
| 102 | የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች በከተማው የሚገኝ ቤት ባለቤትነቱ የማን ነው ከሚል ጉዳይ ጋር ተያይዞ የሚነሣ ክርክርን ለማየት ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁ. 416/19 አንቀፅ 33 | 47134 | የድሬዳዋ አስተዳደር ቀበሌ 06 አስተዳደር ጽ/ቤት እና ወ/ሮ ፋንታዬ ምትኩ | ግንቦት 6/2002 | 310 |
| 103 | • የክርክሩ የገንዘብ መጠን ከ5000 ብር በታች የሆነ ጉዳይን በሙሉ ተቀብሎ ለማስተናገድ የአዲስ አበባ ከተማ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች በሕግ ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ<br>• የሥረ-ነገር ሥልጣን በሕግ ባልተሰጠው የዳኝነት አካል (ፍ/ቤት) የተሰጠ ፍርድ የማይፀና ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 5(6),5(9)<br>አዋጅ ቁ. 361/95 | 52041 | የእርሻ መሣሪያዎችና የቴክ/አ/ማህበር<br>እና<br>የኢት/መድን ድርጅት | ሰኔ 29/2002 | 313 |
| 104 | በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ የንግድ ማህበር (ድርጅት) ጋር በተያያዘ የሚነሣ ክርክርን ለማስተናገድ ስልጣን የተሰጠው ለፌዴራል ፍ/ቤቶች ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀፅ 5(6) | 43912 | አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ እና<br>እነ የአቶ ኢብራሂም ሙሣ ወራሾች (ሁለት ሰዎች) | ሰኔ 15/2002 | 315 |
| 105 | በሰዎች ወይም በሚንቀሳቀስ ሀብት ላይ ለደረሰ ጉዳት ካሣ ለማግኘት የሚቀርብ ክስን ለማስተናገድ የግዛት ክልል ሥልጣን ስለሚኖረው ፍ/ቤት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 27 | 48018 | አቶ ተከተል ዘካሪያስ እና እነ ወ/ሮ አስቴር ታደሰ(ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 7/2002 | 317 |
| 106 | በሸሪአ ፍ/ቤት በሚካሄድ ክርክር ላይ ጣልቃ ገብቶ መከራከር በፍ/ቤቱ ለመዳኘት ስምምነትን እንደመስጠት የሚያስቆጥር ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 188(92) አንቀፅ 5(1) | 45806 | አቶ ፍፁም በረታ እና እነ ወ/ሮ ሶፊያ ዱላ(አራት ሰዎች) | ሐምሌ 8/2002 | 319 |
| 107 | • በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ እጅግ አስፈላጊ የህዝብ አገልግሎት ድርጅቶች ተብለው ከተዘረዘሩት ተቋማት ጋር ተያይዞ የሚቀርብ የሠራተኞች ደመወዝና ጥቅማጥቅም ጥያቄን የያዘ የውል የሥራ ክርክር ካልሆነ በስተቀር የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ለማስተናገድ የሥረ-ነገር ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ<br>• መሰል ጉዳዬችን ለማየት በህግ ስልጣን የተሰጠው በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚሰየም ቦርድ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 466/97 አንቀፅ 2(2)<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 142(1)(ሀ),(2),(3),136(2) | 49152 | የኮንስትራክሽን ሥራዎችና ቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ድርጅት መሠረታዊ ሠራተኛ ማህበር<br>እና<br>የኮንስትራክሽን ሥራዎችና ቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ድርጅት | ሐምሌ 7/2002 | 324 |
| **ባንክና ኢንሹራንስ** | | | | | 328 |
| 108 | በብድር ለተሰጠ ገንዘብ በመያዣነት የተያዘ ንብረት መድን የተገባለት ሆኖ አደጋ የደረሰበት እንደሆነ አበዳሪው ንብረቱን በመያዣ የያዘበት ብድር ዋጋ ዋስትና ከተገባለት የገንዘብ መጠን ያነሰ እንኳን ቢሆን መድን ሰጪው እንዲከፍለው ሊጠይቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2858 | 38572 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ጥቅምት 17/2002 | 329 |
| 109 | ባንክ በመያዣ መልክ የያዘውን የተበዳሪ ንብረት በአዋጅ ቁ. 97/90 መሠረት በመሸጥ | 44164 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና | ታህሣሥ 8/2002 | 332 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ላይ እያለ በሌላ በኩል ደግሞ በተበዳሪው ላይ በፍ/ቤት ክስ መስርቶ ዕዳው እንዲከፈለው ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ | | አቶ ሐሰን ኢብራሂም | | |
| 110 | የኢንሹራንስ ውልን መሠረት በማድረግ የሚቀርብ ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 674(1),754(1) | 46778 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ | የካቲት 24/2002 | 336 |
| 111 | የመድን ሰጭ ኃላፊነት በመድን ውሉ ላይ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን ሊበልጥ የማይችል ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 665(2) | 46808 | አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ እና ወ/ሮ ጫልቱ ሚደግሳ | ሚያዝያ 6/2002 | 339 |
| 112 | ለአንድ ንብረት መድን የገባ ሰው በንብረቱ ላይ የደረሰው ጉዳት ሙሉ ውድመት ሊባል የሚችል ቢሆንም ካሣ ሊከፈለው የሚችለው ጉዳት በደረሰ ጊዜ ዕቃው ከሚያወጣው ዋጋ ሳይበልጥ ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 678 | 48698 | አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ እና አቶ ሣሙኤል አለሙ | ግንቦት 19/2002 | 341 |
| 113 | መድን ሰጪ የሆነ ወገን በመድን ገቢው እግር በመተካት ባለዕዳ የሆነ ወገን ላይ ጥያቄ ባነሣ ጊዜ ባለዕዳው ከመድን ገቢው ጋር የሚፈጠር አለመግባባትን ከፍርድ ቤት ውጪ በሽምግልና ለመጨረስ የተስማማን በመሆኑ መድን ሰጪው በፍርድ ቤት ክስ መስርቶ ሊጠይቅ አይችልም በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ የህግ መሠረት የሌለው ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 683(1) | 39902 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና ወ/ሮ ብሬ ሞሲሳ | ሰኔ 18/2002 | 344 |
| 114 | አስቀድሞ የተደረገ ነገር ግን ባለመታደሱ ምክንያት የተቋረጠ (ያበቃ)ን የመድን ውል መሠረት በማድረግ ሊጠየቅ የሚችል የጉዳት ካሣ ስላለመኖሩ<br>የንግድ ህግ ቁ. 666(2) እና (3) | 52910 | አቶ አንዳርጌ ታደሰ እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት | ሐምሌ 28/2002 | 347 |
| **ጉምሩክ(ግብር)ታክስ** | | | | | 349 |
| 115 | • የንግድ ቤቶችን የማከራየት እንቅስቃሴ ከታክስ ነፃ ከሆኑ ግብይቶች የማይመደብ ስለመሆኑ<br>• የንግድ ቤት ኪራይ የመክፈል ግዴታ ያለበት ወገን የተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈል ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀፅ 8 | 39574 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ ወ/ሮ ምልእተ ፀጋ ቢዘን (ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 3/2002 | 350 |
| 116 | የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ያልተከፈለን ቀሪ ቀረጥ ሊያስከፍል የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ.60/89 አንቀፅ 57(1),48,53(1) | 45882 | የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና እነ ወ/ሮ እጅጋየሁ አራምዴ (ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ 6/2002 | 352 |
| 117 | የጉምሩክ አዋጅን በመተላለፍ ከሚፈፀም የወንጀል ድርጊት ጋር በተያያዘ የኮንትሮባንድ ተግባር ሃይልን በመጠቀም ወይም ከሌሎች ጋር በማበር የተፈፀመ እንደሆነ አዋጅ ቁ. 60/89 ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ | 44862 | አሸናፊ አበበ እና የጉምሩክ ባለስልጣን | ጥር 5/2002 | 355 |
| 118 | የጉምሩክ ሕግን በመተላለፍ ወንጀል ፈፅሟል በሚል የተጠረጠረ ሰው ክስ ሊቀርብበት የሚገባውና ጉዳዩ መታየት ያለበት በአዲሱ የወንጀል ህግ ሣይሆን የጉምሩክ አዋጆችን መሠረት በማድረግ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 60/89 | 48693 | ነኢማ አወል እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን | ጥር 5/2002 | 357 |
| 119 | የንግድ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ የሆነ ሰው የድርጅቱን አስተዳደራዊ ሥራ ለሌላ ሰው | 54061 | አቶ መስፍን ሽፈራው እና የኢትዮጵያ ገቢዎች | ሚያዝያ | 359 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የወከለ መሆኑ ድርጅቱ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብይት በመፈፀም ወንጀል ጥፋተኛ በተባለ ጊዜ ከሚቀርብበት የወንጀል ተጠያቂነት ነፃ የማያደርገው ስለመሆኑ | | ባለስልጣን | 26/2002 | |
| 120 | • የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሕግ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባሩን በተገቢው ጊዜና ሁኔታ ባለማከናወኑ በሌላ ሰው ንብረት ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>• የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሕግ በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት ግዴታውን ለመወጣት ሲንቀሳቀስ በቁጥጥሩ ሥር አድርጐት ከሚቆየው ንብረት ጋር በተያያዘ የተቋረጠ ጥቅም ወይም የጉዳት ካሣ ሊከፍል የሚችልበት የሕግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ 60/98 አንቀጽ 6(5), 58,74<br>አዋጅ ቁ 368/95 አንቀጽ 78 | 49889 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት<br>እና<br>አቶ ዛኪ ሰይድ | ሰኔ 28/2002 | 361 |
| 121 | የግብር ይግባኝ ጉባኤ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ የተፈቀደው ጊዜና ስሌቱ<br>አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 43(1) | 48621 | አቶ አብደላ ሁሴን ከለር ላብራቶሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን | ሰኔ 30/2002 | 365 |
| **ውክልና** | | | | | 368 |
| 122 | ባንክ በሐዋላ ለማድረስ የተቀበለውን ገንዘብ ለተገቢው ሰው አልደረሰም በሚል ኃላፊነት አለበት ሊባል የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ እና የተለመደውን አሰራር ሳይከተል የቀረ እንደሆነ ወይም መጭበርበሩ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ | 48269 | አቶ ሽረፈዲን አብደ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | የካቲት 24/2002 | 369 |
| 123 | ወኪል የሆነ ሰው የውክልና ሥራውን በሚሰራበት ጊዜ የራሱን ወይም ከራሱ ጋር ቤተሰባዊ ወይም ሌላ ጥብቅ ግንኙነትና ትስስር ያለው ሰውና የወካዩ ጥቅም ሊጋጭ የሚችልበት አጋጣሚ እንዳይፈጠር መከላከል ያለበት ወይም በተፈጠረ ጊዜ አስቀድሞ ለወካዩ ማሳወቅ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2187(1)2198,2208,2209 | 50440 | አቶ ሃብቱ ወልዱ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ መሰሉ ደስታ (ሁለት ሰዎች) | ግንቦት 16/2002 | 371 |
| **የንግድ ሕግ** | | | | | 375 |
| 124 | • የእሽሙር የሽርክና ማህበር ተመስርቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ<br>• በግለሰቦች መካከል በውል የሚፈጠር የሽርክና ማህበር የንግድ ሕግ በሚያዘው መሰረት አይነቱ ተለይቶ ተመዝግቦ የማይገኝ በሆነ ጊዜ እንደ የእሽሙር የሽርክና ማህበር ተደርጐ ሊወሰድ የሚችል ስለመሆኑ<br>የንግድ ሕግ ቁጥር 211,212,219 | 46358 | ወ/ሮ ብርሃን ፀጋዬ እና እነ አቶ ሚካኤል ፋስሐ (ሁለት ሰዎች) | የካቲት 25/2002 | 376 |
| 125 | ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማህበር ሥራ አስኪያጅ የሆኑ ሰዎች ማህበሩን ሲያስተዳድሩ በሰሩት ያልተገባ ስራ ምክንያት በኃላፊነት ሊጠየቁ የሚችሉበት አግባብ<br>የንግድ ሕግ ቁጥር 580 | 39608 | ወ/ሮ አስቴር አርአያ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አምሳለ በላይ (ሁለት ሰዎች) | የካቲት 11/2002 | 378 |
| **አእምሯዊ ንብረት** | | | | | 381 |
| 126 | አንድን መፅሐፍ ከተፃፈበት ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ የተረጐመ ሰው እንደ ድርሰት አመንጪ ተቆጥሮ የሞራልና የቁሣዊ ጉዳት ሊወሰንለት | 44520 | አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት<br>እና | ጥቅምት 10/2002 | 382 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለመቻሉ<br>አዋጅ ቁ.410/96 አንቀፅ 2(2),6(1) | | ዶ/ር ጌታሁን ሽብሩ | | |
| **ልዩ ልዩ** | | | | | 385 |
| 127 | ለዋስትና የተያዘ ገንዘብን የአስያዢን ማንነትን ማረጋገጥ እስከተቻለ ድረስ ገንዘቡን ያስያዘበት ደረሰኝ ኮፒን ያቀረበ እንኳን ቢሆን የተያዘው ገንዘብ መመለስ ያለበት ስለመሆኑ | 53459 | አቶ ማሞ ገ/ማሪያም<br>ተጠሪ፡የለም | ሚያዝያ 12/2002 | 386 |
| 128 | • በአስፈፃሚ አካላት የሚወጡ የተለያዩ መመሪያዎች በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው የወጡ ወይም በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጁ አለመሆናቸው ህጋዊ ውጤት እንዳይኖራቸው የሚከለክል ስላለመሆኑ<br>• አዋጅን መሠረት በማድረግ የወጡ መመሪያዎችን የሚፃረር ድርጊት መፈፀም በኃላፊነት ሊያስጠይቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 83/86 አንቀፅ 39(2),1, 2, 59(1)(ሸ)<br>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁ. ሲ.ቲጂ 001/97 | 43781 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን<br>እና<br>አቶ ዳንኤል መኮንን | ሐምሌ 14/2002 | 388 |
| 129 | • የሕግ ክርክሮችን በሰበር ማየት /ማስተናገድ/ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠ ስልጣን (power) ስለመሆኑ<br>• በግልግል ዳኝነት (arbitration) የታየ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ተዋዋይ ወገኖች የይግባኝ መብትን ለማስቀረት የሚያደርጉት ስምምነት ጉዳዩን በሰበር ችሎት ከመታየት የማያግድ ስለመሆኑ (ከዚህ ቀደም በሰበር ችሎት የተሰጠው የሕግ ትርጉም የተለወጠ ስለመሆኑ፡፡)<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3 (ሀ), አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 (4), አዋጅ ቁጥር 25/88, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 350(2) 351 እና 356 | 42239 | ብሔራዊ ማዕድን ኮርፖሬሽን ኃ/የተ/የግ/ ኩባንያ እና<br>ዳን ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ | ጥቅምት 20/2003 | 393 |



www.chilot.me

ቅጽ 11

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| **ቤተሰብ** | | | | | |
| 1. | • ባል ሁለት ሚስቶችን በአንድ ጊዜ አግብቶ የሚኖር በሆነ ጊዜ በመካከላቸው የሚፈራ ንብረት ለተጋቢዎቹ ሊከፋፈል የሚችልበት አግባብ<br>• ሚስቶች ጋብቻ እንደተፈፀመ ከሚቆጠርበት ጊዜ ጀምሮ ከባል ጋር ያፈሩትን ሀብት ብቻ መካፈል ስለመቻላቸው<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ 213/96 አንቀጽ 62/1/ | 50489 | ወ/ሮ ዘይነባ ከልፋ<br>እና<br>ወ/ሮ ከድጃ ሲራጅ | መስከረም 24/2003 | |
| 2. | የኮንዶሚንየም ቤት ለማግኘት የተደረገ ምዝገባ ከጋብቻ በፊት ቢሆንም ዕጣ የወጣው ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ ከሆነ ተጋቢዎቹ የመካፈል መብት የሚያገኙ ስለመሆኑ | 46606 | አቶ ገ/ሥላሴ ጫኔ<br>እና<br>ወ/ሮ አብረኸት ተጫኔ | ጥቅምት 02/2003 | |
| 3. | ወራሽ የሆነ ሰው ወራሽ ባልሆነ ሰው ላይ ንብረቴ ይለቀቅልኝ በሚል የሚያቀርበው ክስ /አቤቱታ/ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው ይርጋ የሚቆጠረው ወራሽነት ከተረጋገጠበት ቀን አንስቶ ሳይሆን ንብረቱ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ | 47201 | እነ በላቸው አስፋው<br>እና<br>ወ/ሮ መኪያ አወል | ጥቅምት 05/2003 | |
| 4. | የጋብቻ ውል አስገዳጅ የህግ ድንጋጌን እስካልተቃረነ ድረስ በፍቺ ምክንያት የሚከተለውን የተጋቢዎች የንብረት ክፍፍል እልባት በመስጠት ረገድ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 42, 47, 73, 44 | 47889 | እነ ወ/ሮ ሠላማዊት አስራት /አምስት ሰዎች/<br>እና<br>ወ/ሮ መሠረት ዘውዴ | ጥቅምት 04/2003 | |
| 5. | በሁለት የተለያዩ ከተሞች የሚገኙ ቤቶች የጋብቻ ፍቺን ተከትሎ ለባልና ሚስት ሊከፋፈሉ የሚችሉበት አግባብ | 49171 | ዶ/ር ደስታ አቡኑ በለጡ<br>እና ሲ/ር አስቴር ካሣ ወልደየስ | ጥቅምት 16/2003 | |
| 6. | የውርስ ሀብትን አስመልክቶ የሚቀርብ ክስ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ገደብ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1851/ለ/ መሰረት ሊቋረጥ የሚችልባቸው ሁኔታዎች ስለመኖራቸው<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1851 | 49359 | ወ/ሮ ቀለሚ ወርቅነህ<br>እና<br>ሻምበል ጌታሁን ገብሬ | ጥቅምት 04/2003 | |
| 7. | • ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት የሚኖሩ ሰዎች ግንኙነታቸው በንብረት ረገድ ያለውን ውጤት በተመለከተ በውል ሊወሰኑ ስለመቻላቸው<br>• በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያለ የአላባ የመጠቀም መብት ጥቅም ተቀባዩ ሲሞት የሚቋረጥና ለወራሾቹ የማይተላለፍ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1731, 1322/1/ | 53663 | እነ አቶ ጊላጋብር ገብረህይወት /ሦስት ሰዎች/<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አረጋሽ አብረሃ /ሁለት ሰዎች/ | ጥቅምት 29/2003 | |
| 8. | የኑዛዜ መኖርን የማስረዳት ሸክም ስላለበት ወገንና ኑዛዜውን ለማስረዳት ሊቀርቡ ስለሚገቡ ማስረጃዎች<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 896, 897 | 49831 | ወ/ሪት ሮማን ግዛው<br>እና<br>አቶ ግርማ አብርሃም | ጥቅምት 02/2003 | |
| 9. | በኑዛዜ ላይ ስለሚቀርብ የመቃወም አቤቱታ እና ተፈፃሚነት ስላለው የይርጋ ደንብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 973, 974 | 53223 | እነ አቶ ሐዲስ ዓለመስላሴ<br>እና<br>ወ/ሮ ብሌን ዓለመስላሴ | ጥቅምት 15/2003 | |
| 10. | • የጋብቻ መኖርን አስመልክቶ ቀዳሚና ዋናው ማስረጃ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ስለመሆኑ<br>• በማንኛውም ሥርዓት የተፈፀመ ጋብቻ በክብር መዝገብ ሹም ፊት ቀርበው ሊመዘገቡ የሚችሉና በዚህ መልኩ የሚገኘው ሰነድ የጋብቻ መኖርን ለማረጋገጥ ብቃት ያለው ስለመሆኑ<br>• በዚህ መልኩ በክብር መዝገብ ሹም ፊት የተመዘገበ ጋብቻ ውጤት አለው ለማለት የሚቻለው ምዝገባው ከተከናወነበት ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን የጋብቻው ሥርዓት ከተፈፀመ ዕለት | 54258 | ወ/ሮ ዘነበች በቀለ<br>እና<br>አቶ ዮናስ ፀጋዬ | ህዳር 02/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አንስቶ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/1992 አንቀጽ 28/3/ | | | | |
| 11. | • በትዳር ወቅት የተወሰደ /በአንደኛው ተጋቢ/ ብድር ለትዳር ጥቅም እንደዋለ የሚገመት ስለመሆኑና ከዚህ ተቃራኒ የሚከራከር ተጋቢ ገንዘቡ ለትዳር ጥቅም ያልዋለ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>• ደመወዝ የተጋቢዎች የጋራ ሃብት ነው በሚል ሊወሰድ የሚችለው ተጋቢዎቹ በጋብቻ ባሉበት ወቅት የትዳርን ወጪ ከመሸፈን አኳያ መሆን ያለበት ስለመሆኑ<br>• ተጋቢዎች ከህጋዊ ፍቺ በፊት ተለያይተው በቆዩባቸው ግዜያት በግል ያገኙት ደመወዝ የጋራ ነው ለማለት የሚቻል ስላለመሆኑ<br>• በጋብቻ ወቅት የተወሰደና በፍቺ ወቅት ተከፍሎ ያላለቀ ዕዳ እንደ የጋራ ዕዳ የሚወሰድ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ 213/92 አንቀጽ 62/1/ | 56184 | ወ/ሮ ኑን ስንታየሁ ጉዝ<br>እና<br>አቶ ተስፋዬ ወ/ሚካኤል | ህዳር<br>02/2003 | |
| 12. | ባል/ሚስት በጡረታ መልክ የሚያገኘውን ክፍያ ሌላ ባል/ሚስት ባገባ ጊዜ የሚቋረጥ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 209/55 አንቀጽ 21<br>አዋጅ ቁ. 345/95 አንቀጽ 35/2/ | 52569 | ወ/ሮ ሙሉወርቅ ዋቹ<br>እና<br>ማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን | ህዳር<br>13/2003 | |
| 13. | • የውርስ ሃብት እንዲጣራ በሚል በንብረቱ ላይ የተሰጠው ትዕዛዝ ከሚች ጋር ህጋዊ ግንኙነት ባልነበረበት ሁኔታ ነው በሚል ክርክር በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤቶች ይህንን እንደ ጭብጥ በመያዝ እልባት ሊሰጡበት የሚገባ ስለመሆኑ<br>• በዚህ ጉዳይ ላይ ፍ/ቤት የሚሰጠው ብይን ጊዜያዊ አገልግሎት እንዳለው ትዕዛዝ የሚወሰድ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 320/3/, 247/1/ | 46726 | ነጋሲ አየለ ኢትቻ<br>እና<br>እነ ሳሙኤል ዮሃንስ ገ/እግዚአብሔር /ሁለት ሰዎች/ | ታህሳስ<br>13/2003 | |
| 14. | • ጋብቻ ሳይኖር እንደ ባልና ሚስት መኖርን ማስረዳት የሚቻልበት አግባብና ይሄው ግንኙነት በህግ ጥበቃ ያለው ነው ለማለት የሚቻልበት ሁኔታ<br>• ጋብቻ ሳይኖር እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት በንብረት ረገድ ውጤት ሊያስከትል የሚችለው ግንኙነቱ፡ ሦስት ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ የፀና ከሆነና በዚሁ ጊዜም የተፈራ ንብረት ያለ እንደሆነ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 106/2/, 95 | 50580 | ዶ/ር አለልኝ መኮንን<br>እና<br>ወ/ሮ አስቴር አርአያ | ታህሳስ<br>14/2003 | |
| 15. | • ሚች ካለው ሀብት እጅግ አነስተኛ የሆነ መጠን ያለው ንብረት ለተወላጁ እንዲሰጠው የተናዘዘ እንደሆነ ተናዛዡ በተዘዋዋሪ መንገድ ተወላጁን እንደነቀለው የሚቆጠር ስለመሆኑ<br>• የሚች ኑዛዜ ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ በሆነ ጊዜም የተነቀለ ተወላጅ ከኑዛዜ ተቀባዩ ጋር እኩል ሊካፈል የሚገባው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 951, 938, 939, 937, 912 | 54385 | አቶ ፍቃዱ ሽፈራው<br>እና<br>አቶ ግሩም ኤድሚያስ | ጥር<br>27/2003 | |
| 16. | • የጋብቻ ውል በአግባቡ ተደርጓል ሊባል የሚችልበት አግባብ<br>• የጋብቻ ውል በሚል በተጋቢዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት ከነሙሉ ይዘቱ ሊታይና ተፈፃሚ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 40 እና ተከታታዮቹ 73, 46/1/<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 826/2/ 2427 2428 857 | 56157 | እነ ወ/ሮ ፀሐይ ተሰማ /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>የህፃን አማኑኤል ወንደሰን ሞግዚት | ጥር<br>09/2003 | |
| 17. | አባትነት በፍርድ ሊነገር የሚችልባቸው ሁኔታዎች ላይ ሳይንሳዊ የደም ምርመራ (DNA test) በማስተባበያ ማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል ስለመሆኑና ፍ/ቤቶች ተከራካሪ ወገኖች በዚህ ረገድ የሚያቀርቧቸውን አቤቱታዎች በአግባቡ ሊያስተናግዱ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92<br>አንቀጽ 144, 143 /ሠ/, 145 | 62041 | ጥሩወርቅ ወርዶፋ<br>እና<br>ጥሩነሽ ወርዶፋ | የካቲት<br>11/2003 | |
| 18. | ማየት የተሳናቸው ሰዎች የሚያደርጉት ኑዛዜ በውል አዋዋይ | 50971 | አቶ ሃይሌ ስሙጋ | የካቲት | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ፊት ካልሆነ በስተቀር አይፀናም ለማለት የሚያስችል የህግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881/3/, 1728/3/, 340, 343/2/ | | እና<br>ሰላማዊት ተኮላ | 25/2003 | |
| 19. | ከውርስ ሃብት ጋር በተያያዘ ወራሽ የሆነና አካለመጠን ያልደረሰ ሰው ላይ የይርጋ ጊዜ ሊቆጠር የሚገባው አካለመጠን ከደረሰበት ወይም በመብቱ መጠቀም ከቻለበት ጊዜ አንስቶ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845 | 57114 | ወ/ሮ ሃና ፀጋዬ<br>እና<br>ወ/ት ጣዕሙ ደስታ | ግንቦት<br>03/2003 | |
| 20. | በጋብቻ ውስጥ የተወለድኩ በመሆኔ ልጅነቴ እንዲረጋገጥልኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ህጋዊ መሰረት ያለውና ፍ/ቤቶችም ተቀብለው በፍሬ ነገር ረገድ ሊጣሩ የሚገቡትን በማጣራት መወሰን ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37/1/ | 57607 | ኤርምያስ ኬስታንትኖስ ግሊፐትስ<br>እና<br>ሰለሞን ኬስታንቲኖስ ግሊፐትስ | ግንቦት<br>30/2003 | |
| 21. | • ኑዛዜ አድራጊ “ስታመም አላስታመመኝም ” በሚል ምክንያት ተወላጅን በኑዛዜ ለመንቀል የሚያስችለው ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>• ኑዛዜ በተደረገበት ንብረት ሚች መብት የሌለው በሆነ ጊዜ ሊከተል ስለሚችለው ውጤት<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1047, 938, 939, 915, 912 | 57836 | ወ/ሮ አስናቀች ደሳለኝ<br>እና<br>የድርሐ አርያም ቅዱስ ሩፋኤል ቤተክርስቲያን | ግንቦት<br>17/2003 | |
| 22. | • ኑዛዜ ህጋዊ አይደለም እንዲሻር በሚል ተቃውሞ እስከቀረበ ድረስ በየትኛውም ህጋዊ መስፈርት መሰረት ፍ/ቤት ኑዛዜውን ውድቅ ሊያደርገው ስለመቻሉ<br>• በኑዛዜ ላይ የነበሩ ምስክሮች የሚሰጡት የምስክርነት ቃል ስለሚኖረው ዋጋ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881-883 | 59268 | ወ/ሪት ዝባድ ታዬ<br>እና<br>እነ ብፁአን ታዬ<br>/ሦስት ሰዎች/ | ግንቦት<br>03/2003 | |
| 23. | ከውርስ ጋር በተገናኘ በህግ ወራሽ የሆኑ ሰዎች ሚችን ለመውረስ ያልተገቡ ናቸው ሊባል የሚችልበት ሁኔታ ሚች በኑዛዜው ከውርስ ሊነቅላቸው ከሚችልበት ሁኔታ የተለየ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 838, 937/1/, 938/2/, /3/ | 49713 | እነ የጥሩነሽ አየለ ወራሾች /አራት ሰዎች/<br>እና<br>ወ/ሮ ወጋየሁ ሠለሞን | ሚያዝያ<br>03/2003 | |
| 24. | • ተናዛዥ የሆነ ሰው ተወላጁ የሆነ ሰው በውርስ ሊደርሰው ከሚገባው ድርሻ ከሩብ በላይ ጉዳት እንዲደርስበት ለማድረግ የሰጠው ምክንያት በቂ መሆን ያለመሆኑ በዳኞች ሊመረመር የሚገባው ስለመሆኑ<br>• “ስላልረዱኝ ወይም ስላልጠየቁኝ” የሚል ምክንያት በመስጠት ተወላጅን ሊደርሰው ከሚገባው የውርስ ድርሻ ሩብ በላይ ጉዳት እንዲደርስበት ለማድረግ የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 913, 1123 | 55648 | እነ ወ/ሮ እቴቱ ሽፈራው /ሦስት ሰዎች/<br>እና<br>እነ ወ/ሮ መንበረ ሽፈራው /ሦስት ሰዎች/ | ሚያዝያ<br>20/2003 | |
| 25. | የልጅ አባት ነህ የተባለ ሰውን በተመለከተ የመካድ ክስ ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 177/3/ | 61677 | አቶ ፈቃደ መክብብ<br>እና<br>አቶ ዳንኤል ብስራት | ሚያዝያ<br>18/2003 | |
| 26. | ከጋብቻ በሞት መፍረስ ጋር በተገናኘ የሚቀርብ የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው ይርጋ መቆጠር የሚጀምረው ጋብቻው ከፈረሰበት ዕለት አንስቶ እንጂ ወራሽነት ከተረጋገጠበት ቀን ጀምሮ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1846, 826/1/ | 59539 | እነ አቶ ስዩም ወ/መስቀል /አራት ሰዎች/<br>እና<br>ወ/ሪት አምሳለ ሙሉነህ | ሰኔ<br>29/2003 | |
| 27. | አስቀድሞ የተደረገን የጋብቻ ውል በማሻሻል የተደረገ የጋብቻ ውል ህጋዊ ተቀባይነት እንዲኖረው ፍ/ቤት ቀርቦ መጽደቅ ያለበት ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 47/1-3/ | 60725 | አቶ አብርሃ የኂላሸት<br>እና<br>ወ/ሮ አበባ ዘመን | ሰኔ<br>27/2003 | |
| 28. | ባልና ሚስት በፍቺ ወቅት የጋራ ንብረታቸውን ለመካፈል ስምምነት ላይ ያልደረሱ ከሆነና ንብረቱ በአይነት ሊካፈል የማይችል እንደሆነ ንብረቱ ተሸጦ የተገኘውን ዋጋ እኩል እንዲካፈሉ መደረግ ያለበት እንጂ በእጣ እንዲካፈሉ ሊወሰን የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 103/1/ | 61788 | ወ/ሮ ጥሩወርቅ ለማ<br>እና<br>ታፈሰ ተሰማ | ሰኔ<br>14/2003 | |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 29. | በሁለት ሰዎች መካከል የጋብቻ ሁኔታ መኖሩን ለማረጋገጥ የሚያዝ ጭብጥ በሁለቱ ሰዎች መካከል ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት የመኖር ሁኔታ ስለመኖሩ ለማረጋገጥ በሚል ከሚያዘው ጭብጥ የተለየ ወይም አንድ አይነት ነው ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ<br>የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 | 60691 | ወ/ሮ ገዛችን ገብሩ<br>እና<br>ወ/ሮ ዓለምነሽ በየነ | ሐምሌ<br>12/2003 | |
| 30. | አባትነትን /ልጅነትን/ ከማረጋገጥ ጋር በተያያዘ በሚቀርብ አቤቱታና ክርክር የዲኤን.ኤ (DNA) ምርመራ እንዲደረግለት በመጠየቅ ክርክር የሚያቀርብ ወገን ለዚሁ የህክምና ማስረጃ የሚያስፈልገውን ወጪ የመሸፈን ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 259/1/ | 63195 | ገረመው ሙሜቻ<br>እና<br>ወ/ሮ አሰፋ ነበበ | ሐምሌ<br>26/2003 | |
| 31. | ጋብቻ ሳይፈርስ የትዳር ግንኙነቱን ትቶ የሄደ ተጋቢ ጋብቻውን ትቶ በሄደበት ወቅት የተፈራን ንብረት የጋብቻ ውጤት ነው በማለት የክፍያ ጥያቄ ሲያቀርብ በጋብቻ ወቅት የተፈራን ንብረት የጋራ ይሆናል በሚለው የህግ ግምት ተጠቃሚ ሊሆን የማይገባ ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40/1/ | 43988 | ወ/ሮ ሰኒያ ሼሳ<br>ተማም<br>እና<br>እነ ወ/ሮ በላይነሽ<br>ማቴቦ /ሁለት ሰዎች/ | መስከረም<br>24/2003 | |
| 32. | ወደ ሌላ አገር ለሥራ በሄደበት ወቅት ህይወቱ ያለፈ ሰው ጋር በተያያዘ የግለሰቡ መደበኛ መኖሪያ ኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ውርሱ በኢትዮጵያ ውስጥ መከፈት ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/በ/ህ/ቁ. 826/1/ | 65621 | እነ ወ/ሮ ታደለች<br>መንግስቱ /አምስት<br>ሰዎች/<br>እና<br>ተጠሪ፡ የለም | ሰኔ<br>27/2003 | |
| 33. | • የውርስ ሀብት ይጣራልኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በሦስት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ/<br>• ከውርስ ሀብት ክርክር ጋር በተገናኘ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ንብረቱ በእጅ ከተደረገበት ጊዜ እንጂ ስመሃብቱ ከተዛወረበት ጊዜ አንስቶ ስላለመሆኑ / | 52407 | እነ ወ/ሮ ውለታ ደስታ<br>ወ/ማርያም /ሁለት<br>ሰዎች/<br>እና<br>ወ/ሮ እቴቴ ደስታ | ህዳር<br>24/2003 | |
| 34. | • የውርስ ሃብት አጣሪ ሪፖርት በፍ/ቤት መጽደቅ ውጤት<br>• በፍ/ቤት የፀደቀ የውርስ ሃብት አጣሪ ሪፖርትን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 አግባብ ተቃውሞ ሊቀርብበት ይገባል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 | 45905 | ሚስስ ሚላን ፒሲጂ<br>ማልጂ<br>እና<br>እነ ሃንድሬ ፒስ<br>ማልጂ /ሁለት ሰዎች/ | ጥቅምት<br>03/2003 | |
| 35. | ከጋብቻ በፊት አንደኛው ተጋቢ የግል መኖሪያ ቤት ኖሮት ከጋብቻ በኂላ ሌሎች ተጨማሪ ቤቶችና ግንባታዎች ተካሂደዋል በሚል ከጋብቻ በፊት በስሙ ተመዝግቦ የሚገኘው ቤት በጨረታ ተሸጦ ለተጋቢዎቹ እንዲካፈል በሚል የሚሰጥ ውሣኔ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ | 53814 | እነ አቶ ነስሩ ሰማን<br>/ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>ወ/ሮ ሙህሊሳ ኒጋኒ | ጥቅምት<br>05/2003 | |
| 36. | በፍ/ብ/ህ/ቁ. 881 መሰረት የተደረገ ግልጽ ኑዛዜ ላይ ያለው የተናዛዡ የጣት አሻራ በተመለከተ ክርክር በቀረበ ጊዜና በፎረንሲክ ምርመራ ለማረጋገጥ ካልተቻለ በኑዛዜው የተገኙ ምስክሮች ቀርበው እንዲመሰክሩ ማድረግ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881, 1677/1/, 2007/2/, 897/1/, 896 | 54013 | ወ/ሮ አስመረት ነጋሲ<br>እና<br>ወ/ሮ ጽጌረዳ ስዩም | ጥር<br>12/2003 | |
| 37. | • በጋብቻ ውስጥ የሚወለድ ልጅ አባት ባል እንደሆነ የህግ ግምት ሊወሰድ የሚችልበት አግባብ<br>• የዚህ የህግ ግምት የሚቋቋምበት አግባብ እና እንደ ማስረጃ ተወስዶ በፍ/ቤት እውቅና ሊያገኝ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 126, 143 | 54024 | አቶ ገ/ሊባኖስ ረዳ<br>እና<br>ወ/ሮ አዜብ አሰፋ | ጥር<br>10/2003 | |
| 38. | አካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ሞግዚት የልጁ ሀብት የሆነን የማይንቀሳቀስ ንብረት ያለ ፍርድ ቤት ፈቃድ ለመሸጥ የማይችል ስለመሆኑ<br>የኦ/ብ/ክ/መ/ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 69/95 አዋጅ ቁ. 83/96 አንቀጽ 294, 316<br>የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 277/1/, 292 | 54827 | እነ ሮም ወርቁ<br>ተስፋዬ /አምስት<br>ሰዎች/<br>እና<br>አሰግድ ሸነገለኝ | ሚያዝያ<br>21/2003 | |
| 39. | አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ሞግዚት የልጁ ንብረት የሆነን | 54129 | አቶ ከፍያለው በቀለ | ህዳር | |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የማይንቀሳቀስ ንብረት በሽያጭ ለ3ኛ ወገን ለማስተላለፍ በህግ ስልጣን ያልተሰጠው ስለመሆኑ | | እና<br>ወጣት ሶፊያን<br>አብዱልቃድር | 01/2003 | |
| 40. | • ከውርስ በዝምታ ወይም ያለበቂና ህጋዊ ምክንያት የተነቀለ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ከጠቅላላ የኑዛዜ ተጠቃሚ ጋር እኩል ወራሽ ሆኖ የሚችን የውርስ ሃብት ሊካፈል የሚገባ ስለመሆኑ<br>• "በህይወቴ ላይ ከፍተኛ ችግር ፈጥረውብኛል" የሚል ምክንያት በመስጠት ብቻ ተወላጅን ለመንቀል የማይቻል ስለመሆኑ<br>• ሟች ካለው ሃብት እጅግ አነስተኛ የሆነ ንብረት /ሀብት/ ለተወላጁ በኑዛዜ የሰጠ እንደሆነ በውጤት ደረጃ ተወላጁ የተነቀለ መሆኑን መገንዘብ የሚቻልና ተወላጁ ከሌሎች የጠቅላላ ኑዛዜ ተጠቃሚዎች ጋር እኩል መካፈል ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 912, 938, 939, 915, 1014, 1123 | 58338 | እነ አቶ ዳንኤል ጽጌ<br>/ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>የህፃን አሳለፈ ጽጌ<br>ሞግዚት | ሚያዝያ<br>06/2003 | |
| 41. | • የውርስ ሃብት አጣሪ የሆነ ሰው የሟችን ንብረት በማጣራት ረገድ ሊኖረው የሚችለው የስልጣን አድማስ<br>• በወራሾች መካከል አንድን ንብረት በተመለከተ የውርሱ ሃብት አካል ስለመሆኑ ክርክር በተነሳ ጊዜ አጣሪው ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ማስረጃ በሪፖርቱ ላይ በማስፈር ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍ/ቤት ማቅረብ እንጂ ማስረጃዎቹን በራሱ መዝኖ አከራካሪው ንብረት የውርሱ ሃብት አካል ነው ወይም አይደለም በማለት ውሣኔ ለመስጠት ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 956 | 66727 | ወ/ሪት ዝናሽ ዘውዱ<br>እና<br>የወ/ሮ መድሐኒት ካሣ<br>ወራሽ እነ ወ/ሮ<br>ደብሪቱ ስዩም | ሐምሌ<br>29/2003 | |
| 42. | ከጋብቻ በፊት በአንደኛው ተጋቢ የተፈራ ቤት በጋብቻ ወቅት እድሳት የተካሄደለት መሆኑ ብቻ ንብረቱን የባልና ሚስቱ የጋራ ሃብት የማያደርገው ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 42/1/, 57 | 45207 | ወ/ሮ አየለች ከበደ<br>እና<br>በላቸው ዋለ | ሰኔ<br>16/2002 | |
| 43. | • ተወላጅ የሆነ ሰው ከውርስ ተነቅሏል ሊባል የሚችለው ተናዛዡ ንብረቱን በጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ ለሌሎች ተወላጆች ወይም ሌሎች ሰዎች የሰጠ እንደሆነ ስለመሆኑ<br>• ሟች ያለው አንድ የታወቀ ንብረት ብቻ ሆኖ ይህንኑ ከተወላጆቹ መካከል አንዱን ወይም ሁሉንም ሳያካትት ለሌሎች ሰዎች በኑዛዜ የሰጠ እንደሆነ ተነቀልኩ የሚል ወገን ኑዛዜው ላይ ተቃውሞ ሊያነሳ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 937-939, 842/2/, 915 | 47917 | እነ ወ/ሮ<br>መልካምሥራ አለበል<br>/አራት ሰዎች/<br>እና<br>ወ/ሮ አንለይ ሊበን | ግንቦት<br>05/2003 | |
| | **አሠሪና ሠራተኛ** | | | | |
| 44. | • በህብረት ስምምነት ውስጥ በሌላ አኳኋን ካልተገለፀ በስተቀር የህብረት ስምምነት ከተፈረመበት ዕለት አንስቶ የሚፀና ስለመሆኑ<br>• የህብረት ስምምነት በሚመለከተው አካል ፊት ቀርቦ እንዲመዘገብ የሚደረገው ድርድር ተደርጐበት ከተፈረመበት በኋላ ለመሆኑ<br>• በተደራዳሪ ወገኖች በተሟላና በአግባቡ ያልተፈረመ የህብረት ስምምነት በፍርድ ሃይል እንዲመዘገብ የሚደረግበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 124-135 | 54451 | የፊንጫ ስኳር ፋብሪካ<br>እና<br>የፊንጫ ስኳር ፋብሪካ<br>መ/ሰ/ማህበር | መስከረም<br>27/2003 | |
| 45. | አንድ ሰራተኛ ለሥራ ከሚጠቀምበት መሳሪያ ብልሽት መከሰት ጋር በተገናኘ በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችለው አሰሪው ግዴታና ኃላፊነቱን በአግባቡ የተወጣ እንደሆነ ስለመሆኑ<br>የአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 12/1//ሀ/ | 48945 | አቶ አየለ አበበ<br>እና<br>የፊንፊኔ የደን ድርጅት | ህዳር<br>27/2003 | |
| 46. | የህብረት ስምምነት የሌለው አሰሪ ሰራተኛው የዲሲፕሊን ጉድለት ፈጽሟል የሚልበትን ጉዳይ ለማጣራትና ለመመርመር ሰራተኛውን ከአንድ ወር ሳልበለጠ ጊዜ ለማገድ | 53985 | ዳሽን ባንክ አ.ማ<br>እና<br>አቶ ዘነበ ድንቁሳ | ህዳር<br>13/2003 | |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለመቻሉ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/4/ | | | | |
| 47. | በህብረት ስምምነት ላይ ከተመለከቱ ሁኔታዎች ውጪ ሰራተኛን ያለአግባብ አዛውሮ የማሰራት ተግባር ህጋዊ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ | 54326 | አንበሳ ጫማ አ.ማ<br>እና ወ/ሮ እትሁን<br>አያሌው | ህዳር<br>03/2003 | |
| 48. | በስራ ላይ ከሚደርስ ጉዳት ጋር በተያያዘ የአሰሪው ኃላፊነት በጥፋት ላይ ያልተመሰረተ (strict liability) ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 96, 97 | 57068 | የኢትዮጵያ መድን<br>ድርጅት<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ሰናይት<br>መጫ /ሦስት ሰዎች/ | ህዳር<br>28/2003 | |
| 49. | ከስራ ተሰናበትኩ በማለት አቤቱታ የሚያቀርብ ሠራተኛ በእርግጥም ስለመሰናበቱ አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በማቅረብ የማስረዳት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ | 57541 | የቻይና መንገድና<br>ድልድይ ሥራ<br>ድርጅት<br>እና<br>ግርማ ቡሽራ | ህዳር<br>14/2003 | |
| 50. | በአዋጅ በተቋቋመ የት/ት ተቋም ውስጥ በሚገኝና በራሱ ገቢና በጀት የሚተዳደርና ሠራተኞችን ቀጥሮ በሚሠራ ክበብ ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ሊስተናገዱ የሚገባ ስለመሆኑ እና ተቋሙን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ተፈፃሚ ይሆናል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96<br>አዋጅ ቁ. 515/96<br>አዋጅ ቁ. ደንብ ቁጥር 61/96 | 46075 | አቶ ንጉስ ሃዱሽ<br>እና<br>የመቀሌ ዩኒቨርስቲ<br>ተማሪዎች ዲን | ታህሳስ<br>25/2003 | |
| 51. | ከሥራ ክርክር ጋር በተገናኘ አሰሪና ሠራተኛው ያደረጉት የሥራ ቅጥር ውልን አስመልክቶ ክርክር ቢነሳ ጉዳዩን የሚገዛው ከኢትዮጵያ ሌላ /ውጭ/ የሆነ አገር ህግ መሆኑንና የሥራ ቦታውም ቢሆን ከኢትዮጵያ ውጪ እንዲሆን የተስማሙ እንደሆነ ጉዳዩ በአጠቃላይ የአለም አቀፍ የግለሰብ ህግ (private international law) ጥያቄን የሚያስነሳ በመሆኑ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለው ፍ/ቤት የትኛው ነው?፣ በየትኛው አገር ህግ መሰረት?፣ የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ስልጣን ያለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 11/2/ | 60685 | አቶ በዛብህ እሸቴ<br>እና<br>ሳሊኒ ኮንስትራክሽን | የካቲት<br>21/2003 | |
| 52. | አንድ ሰራተኛ በአሰሪው ታግዶ /የሥራ ውሉ ተቋርጦ/ በነበረበትና ባልሰራበት ዓመት አሰሪው ለሌሎች ሠራተኞች የከፈለውን የቦነስ ክፍያ ለመክፈል የማይገደድ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43, 45/5/, 53 | 59320 | ጊዮን ሆቴሎች<br>ድርጅት<br>እና<br>አቶ ስለሺ አምዴ | ግንቦት<br>15/2003 | |
| 53. | አሰሪ ሠራተኛው ጥፋት እንደፈፀመ አውቆ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የማሰናበት እርምጃ አለመውሰዱ ስንብቱን ህገ ወጥ የሚያደርገው ቢሆንም ሠራተኛውን ወደ ሥራው እንዲመልስ ላይገደድ የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43/3/ | 64079 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ<br>ኃይል ኮርፖሬሽን<br>እና<br>አቶ ጌትነት መኮንን | ግንቦት<br>17/2003 | |
| 54. | በሥራ ላይ ከሚደርስ ጉዳት ጋር በተያያዘ የጉዳቱን አይነትና መጠን መለየት የሚቻልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 109/3/ /ሀ/ለ/ 101/2/ 100 96/1/ 99/1/ | 60464 | የኦሮሚያ መንገዶች<br>ባለስልጣን<br>እና<br>አቶ ግርማ ወዩሳ | መጋቢት<br>06/2003 | |
| 55. | ከአሰሪና ሠራተኛ ክርክር ጋር በተያያዘ አሰሪው ሠራተኛው የሚጠይቀውን የገንዘብ ክፍያ በማመን የፃፈው ደብዳቤ ሠራተኛው መብቱን ለማስከበር በሚያቀርበው የክፍያ ጥያቄ ላይ የሚቆጠረውን ይርጋ የሚያቋርጥ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 164/3/<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1852/1/ | 63635 | አቶ ጉልላት ወልዴ<br>እና<br>የሽቀጦች ጅምላ | ሰኔ<br>27/2003 | |
| 56. | • አንድ ሠራተኛ ቦነስ ወይም ድጐማ ሊያገኝ የሚችለው ከአሰሪው ጋር በሚደረግ /በሚኖር/ ስምምነት እንጂ በህጉ አሠሪ ለሠራተኛው በቦነስ ድጐማ እንዲከፍል በአስገዳጅነት የተመለከተ ነገር የሌለ ስለመሆኑ | 64758 | እነ ተመስገን ገ/እየሱስ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ሰኔ<br>17/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | • የቦነስና ድጐማ አሰጣጥና አፈፃፀምን በተመለከተ በህብረት ስምምነት የተመለከተ ደንብና መመሪያ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 4, 12, 13, 53 | | | | |
| 57. | •አንድ ሠራተኛ አሰሪው በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ መሰረት ሊከፍለው የሚገባውና ያልከፈለው ክፍያ መኖሩን /እንዳለ/ በተረዳ ጊዜ አሰሪውን የመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ<br>•የአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት በቀጠለበት ሁኔታ ሠራተኛው በአንድ ወቅት ሊከፈለኝ /ሊጠበቅልኝ/ ይገባል በማለት ያቀረበው የመብት ወይም የክፍያ ጥያቄ በፍርድ ቤት ውድቅ መደረጉ በሌላ ጊዜ መብቱን ከመጠየቅ የሚያግደው ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 12<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5, 216 | 66242 | ወ/ሮ ሙሉ ደምሴ<br>እና<br>ሸራተን አዲስ | ሐምሌ<br>13/2003 | |
| 58. | በአዋጅ ቁ. 147/91 መሠረት በተቋቋመ ማህበር ውስጥ ላሉ ሰራተኞች አዋጅ ቁ. 377/96 ተፈፃሚ ስለመሆኑ | 59579 | ወ/ሮ አሞኘሽ ገብሬ<br>እና<br>የአቃቂ መለዋወጫ ዕቃዎች የእጅ መሣሪያዎች አ/ማ ሠራተኞች የገንዘብና ቁጠባ ብድር ኃ/የተ/የግ/ማህበር | ግንቦት<br>16/2003 | |
| 59. | የጡረታ መብት ያለው የመንግስት ልማት ድርጅት ሠራተኛ ሊያገኝ ስለሚገባው ካሣ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 9/1/ | 65427 | ሜታ አቦ ቢራ አ.ማ<br>እና<br>ወ/መድህን ቢረዳ | ግንቦት<br>15/2003 | |
| 60. | ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ ሠራተኞች እየሠሩ የሚገኙትን ሥራ በተመለከተ የሥራ ውል አላደሱም ወይም ለማደስ ፈቃደኛ አይደሉም በሚል ለማሰናበት የሚያስችል የህግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ | 62370 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን<br>እና<br>እነ አቶ እዮብ መለሰ /አራት ሰዎች/ | ታህሳስ<br>26/2003 | |
| 61. | • በአዋጅ ቁ. 377/96 መሰረት የሠራተኛ ማህበር ለማቋቋም የሚቻልበት አግባብ<br>• የሰራተኛ ማህበር ለማቋቋም መብት የተሰጣቸው በአዋጅ ቁ. 377/96 የሚተዳደሩ ሰራተኞች ብቻ ስለመሆናቸው<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 114, 115, 118, 2/4/, 113<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 42/1/ /ሀ/, 31 | 55731 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሰራተኛ ማህበር<br>እና<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ማህበራዊ ጉዳይ ሚንስቴር | የካቲት<br>22/2003 | |
| 62. | • የሠራተኛ ደመወዝ ሊቀነስ የሚችለው በህግ፣ በህብረት ስምምነት፣ ወይም በሥራ ደንብ በተወሰነው መሰረት ወይም በፍ/ቤት ትዕዛዝ ብቻ ስለመሆኑ<br>• አሰሪ የሠራተኛን ደመወዝ በራሱ ውሣኔ ሊቀንስ፣ ሊይዝ ወይም የዕዳ ማቻቻያ ሊያደርግ የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 59/1/ | 59666 | የኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>አቶ አቡ ጉበና | ግንቦት<br>04/2003 | |
| 63. | • የደረጃ እድገት በድርጅት ውስጥ በሥራ ላይ ባለ የእድገት አሰጣጥ ስርዓት እና ደንብ መሰረት የሚካሄድ ስለመሆኑ<br>• የደመወዝ ጭማሪ ሊገኝ የሚችለው በእድገት ወይም አሰሪው የደመወዝ ጭማሪ ማድረግ የሚችልበት አግባብ ኖሮት ሲጨመር ስለመሆኑ<br>• በመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ (BPR) መሠረት የተደረገ የሥራ ምደባ የደመወዝ ጭማሪ የማያስገኝ ስለመሆኑ | 64821 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃየል ኮርፖሬሽን<br>እና<br>አያሌው ሕብስት | ግንቦት<br>01/2003 | |
| 64. | ከአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በፍ/ቤት የተሰጠ ፍርድ እንዲፈፀም የሚቀርብ አቤቱታ ፍርድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ | 53527 | የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት<br>እና<br>አቶ በዳሶ መልካቶ | መስከረም<br>27/2003 | |
| 65. | ሚች ከቀበሌ ተከራይቶት የነበረን መኖሪያ ቤት ወራሽነትን በማረጋገጥ ብቻ በቤቱ ውስጥ የመኖር ህጋዊ መብት ሊገኝ የማይችል ስለመሆኑና ተቀባይነት ያለው የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ ሊቀርብ ስላለመቻሉ | 57045 | የልደታ ክ/ከተማ ቀበሌ 12 አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና<br>አቶ ተስፋዬ አሰፋ | ጥር<br>25/2003 | |
| 66. | የመከላከያ ሰራዊት አባል ያልሆነ የመንግስት ሰራተኛ | 61872 | የኢትዮጵያ ፕልፕና | የካቲት | |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በፍቃዱ ሥራ በለቀቀ ጊዜ የስንብት ክፍያ ሊያገኝ የሚችልበት አግባብ<br>የመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁ. 345/95 | | ወረቀት አ/ማ<br>እና<br>አብዱልቃድር አደም | 10/2003 | |
| 67. | ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለውና በባለሃብትነት ሊያዝ የሚችልን የአሰሪ የሆነ ነገር ላይ ሠራተኛው ሆን ብሎም ሆነ በቸልተኝነት በማናቸውም ሁኔታ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/1/ሸ/ | 64988 | ዳሽን ባንክ አ/ማ<br>እና<br>አቶ ሃይሉ ሽመልስ | ግንቦት 30/2003 | |
| 68. | • የመንግስት ሰራተኞች አዋጅን መሰረት በማድረግ የሚነሳ ክርክር የሚስተናገድበት ህግና የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ<br>• ይግባኝ ለማቅረብ ጊዜ ያለፈበትን አቤቱታ ተቀብሎ ለማስተናገድ የሚቻልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 515/99 አንቀጽ 76/2/<br>አዋጅ ቁ. 6/2000 አንቀጽ | 61843 | ሰይፉ ናስር<br>እና<br>የአ.አ ከተማ አስተዳደር ፍትህና ህግ ጉዳዮች | መጋቢት 23/2003 | |
| 69. | ለተወሰነ ጊዜና ሥራ የተቀጠረ ሠራተኛ ጊዜው ደርሶ መሰናበቱ ምንም እንኳን ሌሎች ሠራተኞች በእሱ ምትክ የተቀጠሩ ቢሆንም ህገ ወጥ ነው ለማለት የማይችል ስለመሆኑ | 57337 | አድቬንቲስት የልማት ተራድኦ ድርጅት<br>እና<br>አቶ ገበየሁ ወ/ሚካኤል | ሰኔ 15/2003 | |
| 70. | በአሰሪና ሰራተኛ ስምምነት የሚዘጋጅ የህብረት ስምምነት ውስጥ የተካተቱ ሠራተኛን ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ለማሰናበት የሚያስችሉ ምክንያቶች ጥፋትን መሰረት ማድረግ ያለባቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/1//ተ/ | 64734 | ካንትሪ ክለብ ዴበሎበር የረር ቪው የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት<br>እና<br>እነ አቶ በቀለ ለማ /ሦስት ሰዎች/ | ሰኔ 16/2003 | |
| 71. | የግንባታ ሥራ ተቋራጭ ድርጅት ከ3ኛ ወገን ጋር ባደረገው የግንባታ ሥራ ውል መነሻነት የቀጠረውን ሰራተኛ የግንባታ ሥራው ውል በመቋረጡ ምክንያት ማሰናበቱ ህገ ወጥ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 24/4/, 4/1/, 10, 9 | 66306 | አምሳሉ ወረዳ ኮንስትራክሽን አ/ማ<br>እነ<br>እነ አቶ መሐመድ ሰይድ /ስድስት ሰዎች/ | ሰኔ 03/2003 | |
| 72. | የወንጀል ድርጊት ፈጽሟል በሚል በመጠርጠሩ የተነሳ ከሥራ ታግዶ የነበረና በኋላም የተሰናበት ሠራተኛ በወንጀል ተከስሶ ጥፋተኛ መሆኑ ተረጋግጦ የተሰጠ የፍ/ቤት ውሣኔ ያልቀረበ በመሆኑ ብቻ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑና ጉዳዩን በማስተናገድ ላይ የሚገኝ ፍ/ቤት የሠራተኛውን ስንብት አግባብነት ለመወሰን ማናቸውንም ማስረጃ አስቀርቦ በመመልከት ለጉዳዩ እልባት መስጠት ያለበት ስለመሆኑ | 59906 | የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት<br>እና<br>ኃይለማርያም ሻረው | የካቲት 09/2003 | |
| 73. | ከሥራ ጋር ባልተገናኘ /ተፈጥሮአዊ/ ሞት ምክንያት የሥራ ውል ሲቋረጥ የሥራ ስንብት ክፍያ የማይከፈል ስለመሆኑ | 18495 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>ወ/ሮ አሚናት ገበየሁ | መጋቢት 18/1999 | |
| 74. | • የቦነስ ክፍያ ለሠራተኛ የሚከፈለው በሥራ ላይ ያለ ሰራተኛ ወደፊት በርትቶ እንዲሰራ ለማበረታታት ብቻ ሳይሆን በሥራ ላይ በነበረበት ወቅት የሰራው ሥራ ለአሰሪው ትርፋማ ውጤት በማስገኘቱ የትርፉ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል ጭምር ስለመሆኑ<br>• የቦነስ ክፍያ ተጠቃሚ ለመሆን ሠራተኛው ድርጅቱ /ተቋሙ/ ትርፋማ ውጤት ባስገኘበት ዓመት በሥራ ላይ የነበረና አስተዋጽኦ ያደረገ መሆን ያለበት ስለመሆኑ | 20869 | አቶ አዲሱ አቦሴ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን | ሰኔ 30/1998 | |
| | **ንብረት** | | | | |
| 75. | ቤትና ቦታዬን ያለአግባብ ተነጠቅሁ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በፍ/ቤት ታይቶ ፍርድ ሊሰጥበት የማይችል አስተዳደራዊ ጉዳይ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ<br>ኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37 | 48217 | ወ/ሮ አባዲት ለምለም<br>እና<br>እነ የዛለአንበሳ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት | ጥቅምት 03/2003 | |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 4 | | /ሁለት ሰዎች/ | | |
| 76. | የመሬት ይዞታ ለህዝብ ጥቅም ሲባል በተወሰደ ጊዜ ካሣ የሚከፈለው በተወሰደው ይዞታ ላይ ንብረት የነበረ መሆኑ እንዲሁም ንብረቱን ለመተካት ከሚያስፈልገው ወጪ ጋር ተመጣጣኝነት ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 401/96 አንቀጽ 9/1/, 10<br>አዋጅ ቁ. 455/97 | 52496 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>እነ አቶ ከድር ኃሌጅንሶ /አስራ ሁለት ሰዎች/ | ጥቅምት 16/2003 | |
| 77. | • አንድ ሰው የንብረት ባለቤት የሚሆነው በጉልበቱ፣ በፈጠራ ችሎታው ወይም በገንዘቡ ንብረትን ያፈራ እነደሆነ ስለመሆኑ<br>• የፍርድ ባለዕዳ የሆነ ሰው ንብረቱ ለፍርድ ማስፈፀሚያነት እንዳይውል አስቦ አካለ መጠን ባልደረሰ ህፃን ልጁ ስም ማዞሩ ብቻ ከኃላፊነት ሊያድነው የሚያስችል ስላለመሆኑና ይህ በመሆኑም ሊፈፀም የሚችል ፍርድ የለም ሊባል የማይችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195, 1196<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40/2/ | 55081 | ወ/ሪት ራሔል ሥነ ፀሐይ<br>እና<br>አቶ መስፍን ታምራት | ጥቅምት 18/2003 | |
| 78. | • መንግስት አንድን የግል ንብረት ለህዝብ ጥቅም በሚወስድበት ጊዜ ሊከተለው ስለሚገባው ሥነ ሥርዓት<br>• ለህዝብ ጥቅም ሲባል ንብረቱ የተወሰደበት ሰው የተሰጠው ግምት ከንብረቱ ዋጋ ጋር ተመጣጣኝ አይደለም በሚል ለፍ/ቤት የሚቀርብ አቤቱታ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ ያለበት ሰለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1460-1488 | 50810 | እነ አቶ ፀጋዬ መሠረት /ሰባ ዘጠኝ ሰዎች/<br>እና<br>የመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን | ጥቅምት 30/2003 | |
| 79. | የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተያያዘ ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ስመ ሃብት ይዞ መገኘት የንብረቱ ባለቤት አድርጐ የማያስቆጥር ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195, 1196 | 47139 | አቶ የሱፍ ሁሴን<br>እና<br>አቶ አደን አብደላ | ህዳር 30/2003 | |
| 80. | አዋጅ ቁ. 47/67 ከመውጣቱ በፊት የተደረገ የመሬት ኪራይ ውል ህጋዊ አስገዳጅነት ሊኖረው የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 47/67 | 48086 | እነ ወ/ሮ አሰለፈች ወልደሚካኤል /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>ቶታል ኢትዮጵያ አክሲዮን ማህበር | ህዳር 03/2003 | |
| 81. | • ፍ/ቤቶች በሚቀርቡላቸው አቤቱታዎች ላይ ህግን ተፈፃሚ ለማድረግ የቀረበውን የክስ አርእስት ብቻ ሳይሆን ይዘት ጭምር መመልከት የሚገባቸው ስለመሆኑ<br>• ከንብረት ባለቤትነት ጋር በተያያዘ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1149/1/ መሰረት ሁከት የተፈጠረበት ሰው እንዲወገድለት ይዞታው የተወሰደበት ሰው ደግሞ እንዲመለስለት በሚል ዳኝነት የሚጠየቀው አቤቱታ የቀረበበት ንብረት ተገምቶ ተገቢው ዳኝነት ከተከፈለበት በኂላ ስለመሆኑና በጥቅሉ የተፈጠረ ሁከት እንዲወገድ (cessation of interference) እንደሆነ ተቆጥሮ ልክ አቤቱታቸው በገንዘብ የማይገመቱ አቤቱታዎች አይነት ሊስተናገድ የማይገባ ስለመሆኑና የይርጋ ደንብ ተፈፃሚ የማይሆን ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1149/2/<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 16, 226/3/ | 49985 | ሻለቃ አሰፋ አየለ ደምሴ<br>እና<br>ፍቃዱ ሙሉጌታ | ህዳር 28/2003 | |
| 82. | መሬት በፍ/ብሔር ግንኙነት የተፈጠረን ዕዳ ለመክፈል ጥቅም ላይ ሊውል የማይችል ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40/3/<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1678/2/ | 49200 | አቶ ጋሻው በጉሰው<br>እና<br>አቶ አለበል መከተ | ህዳር 01/2003 | |
| 83. | የከተማ መሬት ይዞታን እንዲለቅ የተደረገ ባለይዞታ በተወሰነለት የካሣ መጠን ላይ ካልተስማማ አቤቱታውን ማቅረብ ያለበት በከተማው አስተዳደር ሥር ለተቋቋመ የመሬት ነክ አቤቱታ ሰሚ አካል ስለመሆኑ እና በመደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ ሊታይ የሚችለው በይግባኝ ብቻ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 11/2/, /4/ | 57271 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና ጃዳ ብሩ | ታህሳስ 27/2003 | |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 84. | • የማይንቀሳቀስ ንብረት /ህንፃ/ ግንባታ ሥራ ጋር በተገናኘ ተፈፃሚ ስለሚሆኑ ድንጋጌዎች<br>• የሥራ ተቋራጭነት ውል ተፈጸሚል /አለ/ ለማለት የሚቻልበት አግባብ<br>• የግንባታ ሥራ ውል በልዩ ፎርም መደረግ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3019-3040 | 47526 | ዛፍኮ ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና<br>ብሔራዊ መሐንዲሶች ስራ ተቋራጭ ድርጅት | ግንቦት 15/2003 | |
| 85. | • የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በቅን ልቦና የተደረገ ነው በሚል ምክንያት ብቻ በህግ ጥበቃ ሊደረግለት የማይችል ስለመሆኑ<br>• በህግ ፊት በማይፀና ሁኔታ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት የምስክር ወረቀት የያዘ ሰው ይህንኑ ንብረት ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት የሚያደርገው የሽያጭ ውል ህጋዊ ነው ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ<br>• የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሽያጭ ለ3ኛ ወገን ለማስተላለፍ መብት ከሌለው ሰው እያወቀ የሽያጭ ውል የፈፀመ ገዢ በቅን ልቦና የተደረገ ነው በሚል የሕግ ጥበቃ የሚደረግበት ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195, 1196, 2882-2884 | 60720 | ወ/ሮ ሄርያ መሐመድ ግርግቦ<br>እና<br>አቶ ሽምሱ የሱፍ | ግንቦት 15/2003 | |
| 86. | ተከራይ ለሆነ ወገን በተከራየው የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የባለቤትነት ወይም ሌላ መብት አለን በማይሉ 3ኛ ወገኖች አድራጐት ለሚነሳ ሁከት አከራይ ዋስትና እንዲሰጥ የማይገደድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2914/1/, /2/, 2913/1/, /2/<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 158 | 63042 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>አቶ ሰለሞን ነጋሽ | ግንቦት 01/2003 | |
| 87. | ለህዝብ ጥቅም ሲባል ይዞታውን እንዲለቅ የተደረገ ሰው በመሬቱ ላይ የሰፈረውን ንብረት ለመተካት ከሚከፈለው ካሣ በተጨማሪ በይዞታው ላይ የነበረው ንብረት በመፍረሱ የተነሳ የተቋረጠ ገቢ /የታጠ ጥቅም/ ካሣ ሊከፈል የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 455/97 አንቀጽ 2/1//ለ/, 7/1/2/ ደንብ ቁ. 135/99 | 63352 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>አቶ ቱሌ አብዶ | ሐምሌ 13/2003 | |
| 88. | • ተከራይ በይዞታው ያለውን የማይንቀሳቀስ ንብረት አከራይ ባለበት ዕዳ ምክንያት ባለገንዘብ የሆነ ወገን ንብረቱን መረከቡ በተከራዩ ላይ የሁከት ተግባር ፈጽሟል የማያስብል ስለመሆኑ<br>• የተከራዩ እና በንብረቱ ላይ መብት ያለው ባለገንዘብ የሚኖራቸው ተነፃፃሪ መብት<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140 1149 2933/1/ 2899 2931<br>አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 6 | 62858 | ፓዝ ፋይንደር ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ<br>እና<br>እነ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ /ሁለት ሰዎች/ | ግንቦት 16/2003 | |
| 89. | ለህዝብ ጥቅም ሲባል በሚመለከተው የአስተዳደር አካል እንዲፈርስ መረጃ የደረሰው በመሆኑ ቤቱን ያፈረሰ ሰው የአስተዳደር አካሉ የዲዛይን ለውጥ አድርጐ ቤቱ ከፈረሰ በኂላ የግለሰቡን ይዞታ /ንብረት/ መፍረስ የማያስፈልግ መሆኑን መግለፁ ካሣ የመክፈል ግዴታውን ቀሪ የማያደርግ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 322/97<br>አዋጅ ቁ. 455/97 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት art. 40/2/ | 62293 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>እነ አቶ መስፍን ጀንበሩ /ሁለት ሰዎች/ | ግንቦት 15/2003 | |
| 90. | • አንድ ሰው የሌለውን ነገር ሸጦ በተገኘ ጊዜ ገገርው በህግ ሊያገኝ ስለሚገባው መፍትሔ<br>• በሌለ መብት መሥራት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2884/1/ /2/, 2282-2285, 1716 | 51034 | ታሪክ ጌታቸው<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አልጋነሽ ተጠምቀ /ሁለት ሰዎች/ | የካቲት 22/2003 | |
| 91. | • የኮንዶሚንየም ቤትን ዋጋ አጠቃላይ የከፈለ የኮንዶሚንየም ቤት ባለቤት በፍርድ የተወሰነበት የሌላ ሰው ዕዳ ያለበት በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቶች ቤቱ በአፈፃፀም ተሸጦ ለዕዳው መክፈያነት እንዲሆን ለማዘዝ የሚችሉ ስለመሆኑ<br>• የኮንዶሚንየም ቤት ባለሀብት የሆነ ሰው በራሱ ፈቃድ | 56011 | አቶ ሳሙኤል ታደሰ<br>እና<br>ወ/ሮ እጥፍወርቅ ኃይለማርያም | መጋቢት 23/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቤቱን ለመሸጥ ለመለወጥ ወይም ለ3ኛ ወገን ለማስፈላለፍ የሚችለው ያለበትን የቤቱን ዋጋ አጠናቅቆ ከከፈለበት ጊዜ ጀምሮ አምስት ዓመት ካለፈ በኋላ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 19/97 አንቀጽ 21, 14/2 | | | | |
| 92. | • በህጋዊ መንገድ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሽያጭ ውል ያገኘ ገገር የሚመለከተውን የአስተዳደር አካል የስም ዝውውር እንዲፈጽምለት በፍ/ቤት ለመክሰስ የሚችል ስለመሆኑ<br>• የሚመለከተው የአስተዳደር አካል በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነት ካልተወጣ ገዥ መብቱን ለማስከበር ክስ ማቅረብ የሚገባው በዚሁ የአስተዳደር አካል ላይ ስለመሆኑ<br>የአማራ ብ/ክ/መ/አዋጅ ቁ. 91/96 እና ደንብ ቁጥር 12/2000 | 49428 | እነ ወ/ሮ ከበቡሽ ልሳነወርቅ /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>እነ አቶ ፀዳሉ አዳነ /ሁለት ሰዎች/ | ህዳር 28/2003 | |
| **ጉምሩክ /ቀረጥ/ ግብር** | | | | | |
| 93. | በስህተት ለጉምሩክ የተከፈለ ቀረጥ ተመላሽ የሚደረገው ስህተቱ መኖሩን ባለስልጣን መ/ቤቱ ያወቀና ዕቃውም የጉምሩክ ስነ ስርዓትን አጠናቅቆ ወደ አገር ከገባበት ወይም ወደ ውጭ አገር ከተላከበት ቀን ጀምሮ ባለው 6 ወር ውስጥ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 15<br>አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 53, 55 | 53749 | የአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ<br>እና<br>አቶ አዱኛ አበሉ | ጥቅምት 18/2003 | |
| 94. | ከቀረጥ ነፃ በሆነ መልኩ ለግል አገልግሎት እንዲውል የገባ መኪናን ለንግድ ማዋል በወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 73/1/, 78 | 54203 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን<br>እና<br>ወ/ሮ ሙሉእመቤት ኃ/ሚካኤል | ህዳር 27/2003 | |
| 95. | ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ዕቃዎችን አስመልክቶ ስለሚካሄድ የቅድመ ጭነት ምርመራ ሥርዓት እና በዕቃው ላይ ስለሚከፈል ግብር /ታክስ/<br>አዋጅ ቁ. 173/91 አንቀጽ 6/1/, 4/1/ | 50375 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ለተብርሀን አድሀኖም /ሁለት ሰዎች/ | ህዳር 13/2003 | |
| 96. | የተጨማሪ እሴት ታክስ ህግን ተላልፏል በሚል በወንጀል የተከሰሰ ስራ አስኪያጅ የሆነ ሰው ድርጊቱ ሲፈፀም በቦታው አልነበረም ወይም አያውቅም በሚል ምክንያት ከወንጀል ኃላፊነት ነፃ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 56/1/ 55<br>አዋጅ ቁ. 609/209 አንቀጽ 22/1/ 50/ለ//1/ | 51090 | እነ ዘ ቲዊንስ ባርና ሬስቶራንት ኃ/የተ/የግ/ማህበር /ሁለት ሰዎች/<br>እና የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን | ታህሳስ 12/2003 | |
| 97. | • የጉምሩክ ባለስልጣን ኮንትሮባንድ እንደተፈፀመበት በበቂ ሁኔታ የጠረጠረውን ተሽከርካሪ በቁጥጥሩ ሥር አድርጐ ለሚያደርገው ማጣራት ለባለንብረቱ የተቋረጠ ጥቅም እንዲከፍል የማይጠየቅ ስለመሆኑ<br>• ባለስልጣኑ በቁጥጥሩ ሥር የሚያውላቸው ተሽከርካሪዎች የተያዙበትን ጉዳይ ለማጣራት ከሚያስፈልገው ተገቢና ምክንያታዊ ጊዜ በላይ የሆነ እንደሆነ የሚያስጠይቀው ስለመሆኑ<br>• በባለስልጣኑ ቁጥጥር ሥር የቆዩ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ የተቋረጠ ገቢ ይከፈለን በሚል አቤቱታ በቀረበ ጊዜ ፍርድ ቤት የተጠየቀውን ገቢ ህጋዊነት እና ትክክለኛነት በማረጋገጥ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 6/5/ 58/1//1<br>አዋጅ ቁ. 368/95 | 43996 | የሰሜን ምስራቅ ጉምሩክ ሚሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት<br>እና<br>በረከት አሰፋ | ጥር 10/2003 | |
| 98. | • አንድ ግብር ከፋይ ለተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ግብር ከፋይነት ተመዘገበ የሚባለው በባለሥልጣኑ ከተመዘገበበት ዕለት ወይም ምዝገባው እንደሚፀና ከተገለፀበት ጊዜ ጀምሮ | 59851 | አቶ አለሙ ጋባ<br>እና<br>የፌዴራል ገቢዎችና | የካቲት 11/2003 | |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለመሆኑ<br>• የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ተመዝጋቢ የሆነ ሰው ከተመዘገበበት ዕለት ጀምሮ ለሚያደርገው ግብይት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ለተጠቃሚው ወዲያውኑ ያልሰጠ መሆኑ በወንጀል የሚያስጠይቀው ስለመሆኑ<br>• እውቅና ያልተሰጠው የሽያጭ መመዝገቢያ መጠቀም በወንጀል የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 471/98 አንቀጽ 5<br>አዋጅ ቀ. 285/94 አንቀጽ 64, 3/1/ና/2/, 22/1/<br>አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 117<br>ደንብ ቁጥር 139/99 አንቀጽ 22<br>መመሪያ ቁጥር 46/99 | | ጉምሩክ ባለስልጣን | | |
| 99. | • በጉምሩክ አዋጅ ቁ. 368/95 /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 74 ሥር ጥፋተኛ የተባለ ተከሳሽ ሊጣልበት ስለሚችለው የቅጣት አይነትና መጠን<br>• በኮንትሮባንድ ዕቃ ሲያጓጉዝ የተገኘ ተሽከርካሪ ሊወረስ የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 60/89<br>አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 64/4/, 74 | 48628 | የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓ/ሕግ<br>እና<br>አቶ በርሄ ሐጐስ | ግንቦት 05/2003 | |
| 100. | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አስቀድሞ በዋስትና ለሌላ ሰው ያልተሰጡ የግብር ከፋይ ንብረቶች ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 80/1/, 78/1/ | 57100 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስለጣን በጅማ ቅ/ጽ/ቤት<br>እና<br>እነ አቶ አዳራ ሰይድ /ሁለት ሰዎች/ | ግንቦት 30/2003 | |
| 101. | የተሽከርካሪ ባለንብረትና ሹፌር በመሆን የኮንትሮባንድ ወንጀል በተሽከርካሪ በመታገዝ የተፈፀመ ስለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ የግለሰቡን የወንጀል ጥፋተኝነት ውሣኔ ተከትሎ ተሽከርካሪው እንዲወረስ ትዕዛዝ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀጽ 91/2/, 2/1/ | 64819 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን<br>እና<br>አቶ አንተነህ ካሣዬ | ሰኔ 30/2003 | |
| 102. | ከቀረጥ ነፃ፣ በቅናሽ ቀረጥ ወይም በጊዜያዊነት ከቀረጥ ነፃ የገባን ዕቃ ህግን በሚቃረን መልኩ የቀረጥ ነፃ መብቱ ከተሰጠበት ምክንያት ውጪ መጠቀም /ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት/ የወንጀል ኃላፊነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 60/89<br>አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 73/1/ /ሀ/ /ለ/ /2/ | 58266 | ወ/ሮ አልማዝ ደሴ<br>እና<br>የጉምሩክ ዓ/ህግ | ሰኔ 03/2003 | |
| 103. | • አንድ ዕቃ /ንብረት/ ኮንትሮባንድ ነው ወይም የጉምሩክ ስርዓት ያልተፈፀመበት ነው በሚል በቁጥጥር ስር ሊውል የሚችልበት አግባብ<br>• የጉምሩክ ሥርዓት ያልተፈፀመበትን ዕቃ ወደ ጉምሩክ ክልል ማስገባት ወይም ከጉምሩክ ክልል ማስወጣት ዕቃው ኮንትሮባንድ እንዲባል የሚያደርግ ስለመሆኑና የኮንትሮባንድ ወንጀልን የሚያቋቁም ስለመሆኑ<br>• "የጉምሩክ ክልል" በሚል የተጠቀሰው ሃረግ አጠቃላይ የኢትዮጵያ የግዛት ክልልን የሚያመላክት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ 622/2001 አንቀጽ 2/17/, 12/4/, 13/1/, 91/1/, 2/7/ | 60400 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን<br>እና<br>ኤፍታታ እና ቢኤም ኤም ኃ/የተ/የግ/ማህበር | ሐምሌ 12/2003 | |
| 104. | በህግ አግባብ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት የተፈፀመበት ዕቃ/ንብረት/ የኮንትሮባንድ ዕቃን ለማሳለፍ በሽፋንነትና በከለላነት ያገለገለ መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ የጉምሩክ ባለስልጣን ይህን በሽፋንነትና በከለላነት ያገለገለውን ዕቃ ለመውረስ ስልጣን የተሰጠው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 6/5/ 58/1/ /ለ/ 16-18<br>አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 22 | 65656 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት<br>እና<br>ወ/ሪት ትዕግስት ጥላሁን | ሐምሌ 26/2003 | |
| 105. | የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበት ዕቃን በማጓጓዝ የተያዘ ተሽከርካሪ እንዲወረስ ሳይታዘዝ የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀጽ 104/3/ /ሀ/ አንቀጽ 91/1/ | 57243 | የሚሌ ገቢዎች እና ጉምሩክ እና<br>አቶ ደረጀ ከፍያለው | መስከረም 27/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ሲ.ማ | | |
| 106. | • ማንኛውም ሰው በመቀጠር ምክንያት በሚያገኘው ማናቸውም ገቢ ላይ የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>• በደረሰ የአካል ጉዳት ወይም በሞት አደጋ ምክንያት ከሚሰጥ የካሣ ክፍያ በስተቀር ሌሎች በማናቸውም ሁኔታ የሚከፈሉ የካሣ ክፍያዎች ከግብር ነፃ ናቸው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>• ከሥራ መሰናበት ጋር በተገናኘ ለሰራተኞች የሚሰጥ የመልሶ ማቋቋሚያ የድጋፍ ክፍያ የሥራ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ነው ለማለት የሚያስችል የህግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 10/1/, 2/10/, 1/11/ | 65330 | የኢፌዴሪ ፍትህ ሚኒስቴር<br>እና<br>እነ አቶ ተክሌ ጋረደው /ስድስት ሰዎች/ | ሰኔ 30/2003 | |
| 107. | በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ውሣኔ ቅሬታ ያለው ግብር ከፋይ ይግባኙን ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ለማቅረብ የሚችለው በጉባኤው የተወሰነበትን ግብር ይግባኝ ሙሉ በሙሉ ሲከፍል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 112/4/<br>አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 43/4/ | 59711 | ሸበል ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓ/ህግ | ሰኔ 14/2003 | |
| **ከውል ውጭ ኃላፊነት** | | | | | |
| 108. | ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት በመኪና ላይ ጉዳት በደረሰ ጊዜ የመኪናው ባለቤት በደረሰው ጉዳት የተነሳ ሊከተል የሚችለውን ኪሣራ ለመቀነስ ተገቢውን ጥረት የማድረግ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2091, 2097/1/ /2/ | 54021 | አቶ ዱላ ያሲን<br>እና<br>ወ/ሮ አበበች እሸቱ | ህዳር 03/2003 | |
| 109. | የህንፃ ተቋራጭ ሠራተኛ በመሆን በሚሠራው ህንፃ ላይ ሥራውን በማከናወን ላይ እያለ ከህንፃው ወድቆ ጉዳት የደረሰበት ሰው የሚሰራውን ህንፃ ባለቤት ከውል ውጭ የሆነ ግንኙነትን መሰረት በማድረግ የጉዳት ካሣ ሊጠይቅ የሚችልበት የህግ መሠረት የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2077 | 52595 | ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ሻሎም ተስፋዬ /አራት ሰዎች | ታህሳስ 15/2003 | |
| 110. | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የዘረጋቸው የኤሌክትሪክ መስመር ገመዶች ለሚያደርሱት ጉዳት ከኀላፊነት ነፃ ሊሆን የሚችለው ጉዳቱ የደረሰው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በተጐጂው ጥፋት መሆኑን በማስረዳት ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2086/2/ | 57904 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን<br>እና<br>አቶ ወልዱ ገ/ስላሴ | ታህሳስ 15/2003 | |
| 111. | ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ተፈፃሚ ከሚሆነው የይርጋ ጊዜ ጋር በተገናኘ ለደረሰው ጉዳት ምክንያት የሆነው ድርጊት በወንጀል የሚያስቀጣና ጥፋት መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ አጥፊው በወንጀል ጉዳይ ክስ ያልቀረበበትና ያልተቀጣ እንኳን ቢሆን በወንጀል ህጉ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚ ሊደረግ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143 /1/ እና /2/ | 58920 | አለምነው አበበ አካሌ<br>እና<br>ህብረት ኢንሹራንስ አ.ማ | የካቲት 22/2003 | |
| 112. | ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ፍ/ቤቶች የጉዳት ካሣን አስመልክቶ የሚሰጡት ውሣኔ በይግባኝ ሊለወጥ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2152, 2153 | 53598 | አቶ ይልማ ደጀኔ<br>እና<br>ወ/ሮ መዲና ዲታሞ | ግንቦት 19/2003 | |
| 113. | የባንክ ሥራ አስኪያጅ የሆነ ሰው ጥፋት ፈጽሟል በሚል በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችልበት ብሎም ላደረሰው ጉዳት ካሣ እንዲከፍል ሊደረግ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2524/2/, 1676/1/, 1790/2/, 2090 | 44427 | አቶ ለገሰ ጥቀኔር<br>እና<br>ንብ ኢንተርናሽናል አ.ማ | መጋቢት 09/2003 | |
| 114. | • አንድ ሰው የሌላውን ሰው የሥራ ድካም ወይም በሌላው ሰው ሀብት በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ እንደሆነ አላግባብ ባገኘው ጥቅም መጠን ለባለሀብቱ ወይም በጉልበቱ ለደከመው ሰው የመካስ ግዴታ ያለበት | 59698 | አቶ ሚኪያስ ከበደ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ምስራቅ ንጉሴ /ሁለት ሰዎች/ | መጋቢት 06/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለመሆኑ<br>• አንድ ሰው ባለዕዳ መሆኑን ያመነ እንደሆነ ዕዳው የታመነለት ሰው ባለዕዳው ዕዳውን ያመነበትን ምክንያት የማስረዳት /የማረጋገጥ/ ግዴታ የሌለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2162 2164 2019 | | | | |
| 115. | • በህክምና ጉድለት ሀላፊነት ሊከተል የሚችልበትና ካሣ የሚከፈልበት አግባብ<br>• የጉዳት ካሣን ለመወሰን የጉዳቱን ልክ በማስረጃ ለማረጋገጥ አዳጋች ሲሆን በርትዕ ለመወሰን የሚቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2090, 2102 | 64590 | ሜሪስቶፕስ ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ<br>እና<br>ወ/ት ሠናይት ዓለማየሁ | ሚያዝያ 18/2003 | |
| 116. | የትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጥ ተሽከርካሪ ተሳፋሪ በመሆን ሲጓዙ ለሚደርስ ጉዳት አጓጓዥ ከኃላፊነት ነፃ ሊሆን የሚችልባቸው ልዩ ሁኔታዎች፣ ኃላፊ በሆነ ጊዜ የኃላፊነቱ መጠን እንዲሁም አጓጓዥ በህግ ከተደነገገው የጉዳት ካሣ መጠን በላይ በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችልባቸው ሁኔታዎች<br>የንግድ ህግ ቁ. 595, 596, 599, 588, 597<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2130, 2092, 2091 | 67973 | አቶ በቀለ ወልቻም<br>እና<br>አቶ ጥበቡ ጣራ | ሐምሌ 25/2003 | |
| 117. | • መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ልዩ የምዝገባና የባለሀብትነት ስም ዝውውር የሚያስፈልገው ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ ንብረት ስለመሆኑ<br>• የባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤትነት /ባለሃብትነት/ ወደ ሌላ ሰው ተላልፏል ሊባል የሚችልበት አግባብ<br>• መኪኖች እና ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ለሚያደርሱት ጉዳት በኃላፊነት ስለሚጠየቀው ወገን<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1186/1/ /2/, 2081/1/, 2082/2/, 2083/1/, 2267/2/, 2324/1/<br>አዋጅ ቁ. 256/60 አንቀጽ 6<br>አዋጅ ቁ. 468/97 አንቀጽ 21<br>ደንብ ቁ. 360/61 አንቀጽ 6 7/1/ /3/, 8, 11/1/ /2/, 42-45 | 24643 | ወ/ሮ አስናቀች ወ/ማርያም<br>እና<br>አቶ አለማየሁ አህመድ | ሐምሌ 29/2000 | |
| 118. | ባለሞተር ተሽከርካሪ ከሚያደርሰው ጉዳት ጋር በተያያዘ የመጨረሻው ኃላፊነት (ultimate liability) የሚወድቀው መኪናው ሲሽከረከር የነበረው ባለቤቱ በቀጠረው ሹፌር እንኳን ቢሆን በወቅቱ በመኪናው ሲገለገል የነበረው ሰው ላይ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2082/1/, 208/1/, 2083/1/ | 55228 | አቶ አብራር ሳቢር<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አለምፀሐይ ወሰኔ /ሁለት ሰዎች/ | ጥር 25/2003 | |
| 119. | ከውል ውጭ የሌላ ሰው ሃብት የሆነን ነገር በመያዝ ለተገለገለበት ጊዜ ክፍያ እንዲከፈል በሚል የቀረበ አቤቱታ ጋር በተያየዘ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024 ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024 | 54518 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>እነ ፀሐይ ዘሙይ /ሁለት ሰዎች/ | የካቲት 14/2003 | |
| 120. | • ለአካለ መጠን ያልደረሱ ህፃናት ላይ ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ጉዳት ሲደርስ የጉዳት ካሣ መከፈል የሚገባው ስለመሆኑና የካሣ አወሳሰኑ ስሌት<br>• በገንዘብ ለመተመን የሚያዳግት የአካል ጉዳት በደረሰ ጊዜ ካሣ በርትዕ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2090, 2091, 2092/2/, 2095/2/ | 38117 | አቶ ብርሃኑ ፈይሳ ቢፍቱ<br>እና<br>እነ ናይል ኢንሹራንስ /ሁለት ሰዎች | ሐምሌ 09/2001 | |
| | **አፈፃፀም** | | | | |
| 121. | በዕዳ ምክንያት በፍ/ቤት የተከበረ ንብረት እንዲሸጥ በተደረገ ጊዜ ንብረቱን ያስከበረው ወገን የሚኖረው መብት ከሽያጭ ገንዘቡ ላይ የቀዳሚነት መብት ያላቸው ባለገንዘቦች የሚተርፍ ካለ መውሰድ ነው እንጂ ንብረቱን በሽያጭ ውል የተነሳ ባለቤት የሆነን ወገን መጠየቅ ወይም ንብረቱን የመከተል ስላለመሆኑ | 48042 | ጉና ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ<br>እና<br>እነ ቡሬ ባጉና የማዕድን ውሃ ፋብሪካ /ሦስት ሰዎች/ | ጥቅምት 03/2003 | |
| 122. | የአፈፃፀም ክስና መጥሪያው ደርሶት የፍርድ ባለዕዳ ሳይቀርብ | 53943 | እነ ወ/ሮ አስካለ | ህዳር | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በሚቀርበት ጊዜ ፍርድ ቤቶች የሚከተሉት ሥርዓት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70/ሀ/"ን" ድንጋጌ መሰረት ያደረገ ስላለመሆኑ እና የተሰጠን ትዕዛዝም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78 መሠረት ለማስነሳት የሚቻልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70/ሀ/, 78 | | ደሣለኝ /ሁለት ሰዎች/ እና እነ ወ/ሮ የትምወርቅ ታደሰ /ሁለት ሰዎች/ | 16/2003 | |
| 123. | በአንድ የፍርድ ባለዕዳ ላይ ከአንድ በላይ የሆኑ ባለገንዘቦች አፈፃፀም ሊቀጥል የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403, 378 | 40945 | ኮለኔል ግርማ ሃይለስላሴ እና አቶ አስማማው መንግስቱ | ጥር 13/2003 | |
| 124. | ፍርድን የሚያስፈጽም የአፈፃፀም ችሎት የተሰጠውን ፍርድ በአግባቡ ለማስፈፀም ተስማሚ ነው ብሎ የገመተውን ትዕዛዝ ለመስጠት የሚያስችል ስልጣን ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 392/1/ | 62804 | እነ አቶ ብርሃን ገ/እግዚአብሔር እና ወ/ሮ ለታይ ገ/ጊዮርጊስ | ሰኔ 15/2003 | |
| 125. | በፍ/ብሔር ክርክር የተፈረደበት ሰው የፍርዱ አፈፃፀምን ለማሰናከል የተንቀሳቀሰ መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ እስከ ስድስት ወር በሚደርስ እስራት ሊቀጣ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 389/1//ሀ//ለ/ | 63754 | አቶ ዓለም ባህታ እና ወ/ሮ ኑኑሽ ሽህምሎ | ሰኔ 15/2003 | |
| 126. | • ፍርድን የሰጠ ፍርድ ቤት ፍርዱ በውክልና እንዲፈፀም ለሌላ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ባስተላለፈ ጊዜ በውክልና ፍርድ ለማስፈፀም ስልጣን የተሰጠው ፍርድ ቤት ፍርድ ከሰጠው ፍርድ ቤት ማረጋገጫ እንዲላክለት ለመጠየቅ የሚችለው የፍርዱ ወይም ትዕዛዙ ግልባጭ ትክክለኛነት የሚያጠራጥር ስለመሆኑ በቂ ምክንያት ካለው ብቻ ስለመሆኑ<br>• ፍርድን በውክልና እንዲያስፈጽም ትዕዛዝ የደረሰው ፍርድ ቤት ስለፍርዱ ትክክለኛነት ወይም በግልባጮቹ ላይ ስለሰፈረው ነገር ሌላ መግለጫና ማብራሪያ ሳይጠይቅ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ማስፈፀም ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 373/2/ 371/1/ | 66988 | አቶ ቀደመ ተሾመ እና አቶ ኢብራሂም ሐመዱ | ሐምሌ 25/2003 | |
| 127. | ፍርድን የሰጠ ፍ/ቤት ፍርዱ እንዲፈፀምለት ለሌላ ፍ/ቤት የውክልና ስልጣን ስለሚሰጥበት አግባብና የፍርድ አስፈፃሚ ፍ/ቤት የስልጣን አድማስ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 371-455 | 64354 | አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ እና ወ/ሮ ኡልባሬ ሰማን | ሰኔ 13/2003 | |
| 128. | ፍርድ የማይፈፀመው ፍርዱ በይግባኝ ስርዓት የተለወጠ እንደሆነ ወይም ፍርዱን ላለመፈፀም ህጋዊ ምክንያቶች ያሉ እንደሆነ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378, 386 | 59301 | መምህርት አታቱ ከበደ እና ስቴፕስ አት.ኢዲኬሽናል ኃ.የተ.የግል ማህበር | ግንቦት 04/2003 | |
| 129. | በአፈፃፀም ደረጃ የሚገኝ ጉዳይ ጋር በተገናኘ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78/1/ ያለው አግባብነት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78 /1/ | 52110 | እነ ወ/ሮ ይህደጋ ሳሙኤል /ሁለት ሰዎች/ እና እነ ወ/ሮ አሰፉ ሳሙኤል /አራት ሰዎች/ | ታህሳስ 26/2003 | |
| 130. | • በክርክር ሂደት ተሳታፊ ያልነበረና ፍርድ ያልተሰጠበት ሰው ንብረት በፍርድ አፈፃፀም ሲያዝበት /በሃራጅ ሲሸጥበት/ ሊከተለው ስለሚገባው አካሄድ<br>• በፍርድ ሊያዝ ስለሚችል ንብረት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 447/1/, 418, 234/1/ /ሠ/, 235/2/, 414/2/, 423, 425, 443, 453/1/ /3/ | 58009 | እነ አቶ ስለሺ ወርቅነህ /ሦስት ሰዎች/ እና እነ አቶ ሁሪሳ ደመሳ /ሁለት ሰዎች/ | ጥር 262003 | |
| 131. | ከግብርና ተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር በተያያዘ በአፈፃፀም ደረጃ የሚቀርብ የቀዳሚነት መብት ይከበርልኝ ጥያቄ የህግ መሰረት ያለውና ሊስተናገድ የሚገባ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 32/1/<br>አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 80/1/ | 48997 | የቦሌ ክ/ከ/ገቢዎች መምሪያ እና እነ አቶ መዓዛ ሽፈራው /ሁለት | ጥቅምት 16/2003 | |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418 | | ሰዎች/ | | |

# ልዩ ልዩ

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 132. | በጤና ጥበቃ ሙያ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ከጤና ሥነ ምግባር ጉድለት ጋር በተያያዘ በጤና ባለሙያዎች መማክርት ጉባኤ ክስ በቀረበባቸው ጊዜ በተገቢው መንገድ መልስ የመስጠትና የመሰማት መብታቸው ሊጠበቅ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የኢትዮጵያ ጤና ባለሙያዎችን መማክር ጉባኤ ማቋቋሚያ የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 76/94 አንቀጽ 16/1/ /2/ | 56934 | እነ አሰገደች የእናቶች እና የህፃናት ሆስፒታል<br>እና<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር | መስከረም 26/2003 | |
| 133. | በውጭ አገር የተደረጉ ሰነዶች (foreign documents) በኢትዮጵያ ውስጥ ህጋዊ ተቀባይነት ሊያገኙ የሚችሉበት አግባብ<br>አዋጅ ቁጥር 334/95 አንቀጽ 26/1/ | 32282 | ሚ/ር ካርሎ ካስቴሊ<br>እና<br>የወ/ሮ ዘውዴ ደሚኒኮ ውርስ አጣሪ አቶ ታምራት ኪዳነ ማርያም | መስከረም 25/2003 | |
| 134. | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተሻሻለ አዲስ የባንክ ስራ ፈቃድና የዳይሬክተሮች እና የዋና ሥራ አስፈፃሚ ሹመትን አስመልክቶ የሚያወጣው መመሪያ ህጋዊ መሰረት ያላቸውና በተግባር ሊውሉ የሚገባ ስለመሆኑ<br>መመሪያ ቁጥር ኤስቢቢ/39/ 2006 አንቀጽ 5.1.4 አንቀጽ 5.1.5<br>አዋጅ ቁ. 83/89<br>አዋጅ ቁ. 84/86 | 44226 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ<br>እና<br>እነ ህብረት ኢንሹራንስ ኩባንያ /ሦስት ሰዎች | ታህሳስ 15/2003 | |
| 135. | የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ በህግ ከተጣለበት የጡረታ አበል የመክፈል ግዴታው ጋር በተያያዘ የአንድን ሰው ባልነት /ሚስትነት/ በማረጋገጥ የተሰጠ ውሣኔን የመቃወም መብት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ህ/ቁ. 358 | 53221 | የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ<br>እና<br>ንጋት ወ/ሰንበት | ታህሳስ 27/2003 | |
| 136. | የጥብቅና ፈቃድ ክልከላ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የሚቀርብ አቤቱታ ለሚመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ቀርቦ ታይቶ የሚወሰን እንጂ በቀጥታ ክልከላ እንዲወገድ በሚል ለፍ/ቤት አቤቱታ የሚቀርብበት ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 199/92 አንቀጽ 29/1/ | 59261 | የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር<br>እና<br>አቶ ታዬ በዛብህ ፊኖ | ጥር 24/2003 | |
| 137. | በህገ መንግስቱ አንቀጽ 40/8/ መሰረት ለተወሰደ ንብረት የሚጠየቅ ካሣ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1143 እና 2143 በሁለት ዓመት ይርጋ የማይታገድ ስለመሆኑ | 59979 | የኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና አቶ ከበደ ወዳጆ | የካቲት 09/2003 | |
| 138. | የቡና ላኪነት ፈቃድ አውጥቶ በግብይት ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው የቡና ጥራት ቁጥጥርና ግብይት አዋጅን ጥሷል በሚል በወንጀል ህግ አንቀጽ 34/1/ መሰረት ሊጠየቅ የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 602/2000 አንቀጽ 14/3/, 15/3/ ደንብ ቁ. 159/2001<br>የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር መመሪያ | 58008 | እነ ኤርሰዶ ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ | ግንቦት 16/2003 | |
| 139. | በጡረታ የተገለለ ሰው በሌላ ሥራ ላይ በተቀጠረበት ጊዜ መንግስት ለጡረተኞች ያደረገውን የጡረታ ጭማሪ መሰረት በማድረግ አሰሪው የደመወዝ ጭማሪ እንዲያደርግለት የሚያቀርበው ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ | 60025 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን<br>እና<br>እነ አቶ ወለዬ በየነ /አራት ሰዎች/ | ግንቦት 02/2003 | |
| 140. | • ጠበቃ የደንበኛውን ጉዳይ "እስከመጨረሻ ድረስ በመያዝ ለመከራከር" በሚል የሚያደርገው ስምምነት ጉዳዩ ሊያስኬድ የሚችል እስከሆነ ድረስ በአንድ ፍ/ቤት ሳይወሰን በይግባኝና በሰበር ደረጃ ሁሉ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ የሚኖርበት ስለመሆኑ<br>• ጠበቃ ከደንበኛ ጋር ባለው ግንኙነት ደንበኛው ማድረግ ያለበትን ነገር ከህግ አንፃር የማስረዳትና ግልጽ የማድረግ ብሎም የማማከር ኀላፊነት ያለበት ቢሆንም በአንፃሩ | 60353 | አቶ ባልቻ ወ/ፃድቅ<br>እና<br>አቶ ግርማ ቀለታ | ግንቦት 04/2003 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አከራካሪ ጉዳይ በሌለበት ሁኔታ ክስና ክርክር ለማቅረብ የማይገደድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1732<br>ደንብ ቁ. 57/92 አንቀጽ 28, 8/2/ | | | | |
| 141. | የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በህግ የተሰጠውን ስልጣን መሰረት በማድረግ አስቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ በድጋሚ በማየት የተለየ ውሣኔ በሰጠ ጊዜ የተለወጠውን /የተሻረውን/ ውሣኔ መሰረት በማድረግ የተከናወኑ ተግባራትን ለማስተካከል ወይም የተከራካሪ ወገኖችን መብት ለማስተካከል ተገቢ የሆነ ትዕዛዝ ለመስጠት የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 349, 6 | 60508 | እነ ወ/ሮ ሮዛ አባተ /አራት ሰዎች/<br>እና<br>የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | ግንቦት 15/2003 | |
| 142. | በፌዴራል ፍ/ቤቶች በጥብቅና ለመስራት የሙያ ፈቃድ የሚሰጥበት አግባብ | 67280 | የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚ/ር<br>እና እነ አቶ ተስፋዬ በርሄ /አምስት ሰዎች/ | ግንቦት 15/2003 | |
| 143. | የኢትዮጵያን ዜግነት በመተው የኤርትራን ዜግነት መርጦ የያዘ ሰው "የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ የውጭ ዜጋ" ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 270/94 አንቀጽ 2/2/<br>ደንብ ቁ. 101/96 አንቀጽ 2/1/ | 55238 | እነ የየካ ክ/ከተማ አስተዳደር /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>ወ/ሮ ህዳት ፍስሃ ጽዮን | መጋቢት 09/2003 | |
| 144. | • ጠበቃ የሆነ ሰው ደንበኛውን ወክሎ ለፍ/ቤት የሚያቀርበው አቤቱታ እውነት ስለመሆኑ በቅድሚያ የማረጋገጥ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>• ማንኛውም ጠበቃ የህግ ሙያውን በሚያከናውንበት ጊዜ ሁሉ ለደንበኛው፣ ለሌሎች የህግ ባለሙያዎች፣ ለተከራካሪ ወገኖች፣ ለፍርድ ቤት፣ ለሙያው ብሎም በአጠቃላይ ለህብረተሰቡ ኃላፊነቱን በቅንነት፣ በታማኝነት እና በእውነተኛነት የመወጣት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 92/1/<br>የፌዴራል ፍ/ቤቶች ጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ ቁ. 57/92 አንቀጽ 3 29/2/ 56/4/ /6/ | 67146 | ሻምበል ተሾመ ደምሴ<br>እና<br>የፍትህ ሚኒስቴር ዓ/ህግ | ሐምሌ 01/2003 | |
| 145. | እጣው ከመድረሱ በፊት አባልነቱን ያቋረጠ የእቁብ አባል ለእቁብ የከፈለውን ገንዘብ ይመለስልኝ በሚል የኃላፊነት ጥያቄ ሊያቀርብባቸው ስለሚችሉ አካላት | 55794 | አቶ ለማ አበበ<br>እና ወ/ሮ ሃና አሰፋ | ጥር 24/2003 | |
| 146. | • በፍርድ ቤት የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ፀንቶ ባለበት ወቅት እግድ የተሰጠበት ንብረት ተሸጦ በተገኘ ጊዜ የፍርድ ባለመብት የሆነ ወገን ሊኖረው ስለሚችለው መፍትሔ<br>• የፍርድ ቤትን የእግድ ትዕዛዝ አለማክበር /መጣስ/ ኃላፊነትን የሚያስከትል ተግባር ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2028, 2035, 2126 | 54567 | የባህር ዳር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት<br>እና<br>እነ የባህር ዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ /ሦስት ሰዎች/ | የካቲት 10/2003 | |
| 147. | • በአንድ በቀረበ ክርክር ላይ የተሰጠው ውሣኔ የቀረቡትን ማስረጃዎች ይዘት ወይም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠውን ነጥብ ከሕጉ ጋር በአግባቡ ተዛምዶ አልታየም በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የሕግ ነጥብ /ክርክር/ እንጂ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ተብሎ በሰበር ችሎት ሊስተናገድ የሚችል አይደለም ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>• የሰበር ችሎት በሥር ፍ/ቤቶች የቀረበን ማስረጃ ክብደትና ተዓማኒነት ለመመርመር በህግ ስልጣን ያልተሰጠው ስለመሆኑ | 44804 | ወ/ሮ ሰናይት ተመስገን<br>እና<br>ወ/ሮ እጥፍወርቅ በቀለ | ጥቅምት 04/2003 | |
| 148. | በወንጀል ድርጊት በኤግዚብትነት ተይዞ የነበረ ወርቅ ከተሸጠ በኂላ ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ከተሻረ ሻጩ አካል የወርቁን ዋጋ መክፈል ያለበት በተሸጠበት ወቅት በነበረው ዋጋ ስለመሆኑ | 58822 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓ/ሕግ<br>እና አይንሽምስ ሁሴን | መጋቢት 05/2003 | |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 149. | • የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በአንድ ወቅት በአንድ ጉዳይ /ጭብጥ/ ላይ የሰጠው የህግ ትርጉም እንደተለወጠ /እንደተሻሻለ/ ሊቆጠር የሚችለው በተመሳሳይ ጭብጥ ላይ በህግ አግባብ የተለየ ግልጽ ትርጉም በሰጠ ጊዜ ብቻ ስለመሆኑ<br>• የውርስ ይጣራልኝ አቤቱታ ተቀብሎ ማስተናገድ ብሎም የውርስ አጣሪ መሾም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች በህግ ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ/ /የሰ/መ/ቁ. 35657፣ 42015፣51329 ይመለከቷል/<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41<br>አዋጅ ቁ. 454/97 አንቀጽ 2/4/ | 52530 | እነ አቶ ሰናይ ልዑልሰገድ /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ትዕግስት ኃይሌ | ህዳር 14/2003 | |
| 150. | የይርጋ መርህ ክስን በተወሰነ የጊዜ ገደብ ቀሪ የሚሆንበትን አግባብ የሚመለከትና ንብረትን በመያዝ ወይም ባለይዞታ በመሆን የባለሀብትነት መብት ከሚገኝበት መርህ የሚለይ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1168, 1808 | 53328 | ዓብዱል መሐመድ እና ወ/ሮ ዘበናይ ኃይሌ | ጥቅምት 18/2003 | |
| 151. | • የድምጽ ብክለት ተከስቷል ለማለት የሚቻለው የሚሰማው ድምጽ ከመጠን በማለፉ በሌሎች ላይ ሁከት የሚፈጥር መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ<br>• የድምፁ ብክለት (Nuisance) ተፈጥሮብኛልና እንዲወገድ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በሁለት ዓመት ይርጋ ታግዷል ሊባል የማይችል ስለመሆኑ<br>• አንድ ሥራን ለመስራት የንግድ ፍቃድ የሰጠ አካል ሥራው የሚፈጥረው የድምጽ ረብሻ አለ በሚል የንግድ ፈቃዱን የሚሰረዝበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 67/89 አንቀጽ 10<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1225, 1226, 1149 | 42824 | አቶ ብርሃነ ተሰማ<br>እና<br>እነ አቶ ታምራት ኪዳኔ /ሁለት ሰዎች/ | ህዳር 08/2002 | |
| 152. | • የአስተዳደር አካል የሰጠው ውሣኔ ወይም የወሰደው እርምጃ ህገ ወጥ መሆኑን እስካረጋገጠ ድረስ ውሣኔውን ለማረም /እንዲስተካከል ለማድረግ/ ስለመቻሉ<br>• በተሳሳተ መንገድ በተሰጠ አስተዳደራዊ ውሣኔ ቅን ልቦና አድሮበት ለኪሣራ የተዳረገ ሰው ኪሣራ ለመጠየቅ ስለመቻሉ<br>• በስህተት በተሰጠ የግንባታ ፈቃድ ግንባታ ያካሄደ ሰው የአስተዳደር አካሉ ስህተቱን በማረም ግንባታው እንዲፈርስ መግለጫ በሰጠ ጊዜ የሚያቀርበው የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ የህግ መሰረት የሌለው ስለመሆኑ | 57044 | እነ የልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 04/14 ጽ/ቤት /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>አቶ ታሪኩ ኡርጌሳ | ጥር 25/2003 | |
| 153. | • ለዳኝነት የቀረበው ጉዳይ በባህሪይው ከአንድ በላይ የሆኑ የህግ ስርዓቶችን ለጉዳዩ አወሳሰን የሚጋብዝና የየትኛው ሥርዓት ህግ ተመራጭ ሊሆን ይገባል የሚል ጥያቄን የሚያስነሳ እንደሆነ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የፍ/ብሔር ስልጣኑ ሊታይ የሚችል ስለመሆኑ<br>• ተዋዋይ ወገኖች በማናቸውም ሁኔታ የአገሪቱን ህግ ወደ ጐን በማድረግ ወይም በሚፃረር መልኩ ስምምነት ስላደረጉና ክርክር ስለተነሳ ብቻ አንድ ጉዳይ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ህግ ጥያቄን/private international law issue/ የሚያስነሳ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>• በሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ ካልተወሰነ በቀር አዋጅ ቁጥር 377/96 የውጭ አገር ድርጅት ሆኖ በኢትዮጵያ ተመዝግቦ በሚሰራ ድርጅት ላይ ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3/3//ለ/<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 11/2/ /ሀ/ | 54121 | ሲ.ኤ.ኤስ ኮንስልቲንግ ኢንጂነርስ ሳልዝ ጊተር ጂ.ኤም.ቢ.ኤች<br>እና<br>አቶ ካሣሁን ተወልደብርሃን | ህዳር 01/2003 | |
| 154. | • የክስ ይዛወርልኝ (change of Venue) ጥያቄ ከተከራካሪ ወገኖች የሚነሳ ስለመሆኑና ፍ/ቤትም ጥያቄውን ሊያስተናግድ የሚችለው በህግ የተመለከቱት መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ስለመሆኑ | 66945 | የእንግሊዝ ህፃናት አድን ድርጅት<br>እና<br>አቶ ገአስ አስማን | ሰኔ 02/2003 | |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | • የክልል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ክሶችን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣናቸው ለማስተናገድ የሚችሉ ስለመሆናቸው<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 136/3/, 138/2/, /1/, 139/1/ /ሀ/<br>አዋጅ ቁ. 322/95 አዋጅ ቁ. 25/88 | | | | |
| 155. | ለብድር በመያዣነት የተሰጠ የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣ ውሉ መሰረት በህጉ አግባብ በዋስትና ከመያዙ በፊት በሽያጭ ለሦስተኛ ወገን ተላልፎና ስመ ሃብቱ ለገገርው ተላልፎ በተገኘ ጊዜ ሊኖር ስለሚችለው ውጤት<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3051/2/ | 65688 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>አቶ ንጉሴ በያን | ሐምሌ 27/2003 | |
| 156. | የቀበሌ ባለአደራ ቦርድ ህጋዊ ሰውነት ያለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 14/1//ረ/, 66/1/<br>አዋጅ ቁ. 2/95 አንቀጽ 52 | 53551 | የቀበሌ 10 ባለአደራ ቦርድ<br>እና<br>አቶ ዳንኤል አድርሴ | መስከረም 25/2003 | |
| 157. | ይዞታን አስመልክቶ ከሚነሳ የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ጊዜ መቆጠር ያለበት አቤቱታ አቅራቢው የይዞታ መብቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከሚመለከተው አካል ካገኘበት ቀን ጀምሮ እንጂ አቤቱታ የቀረበበት ድርጊት መፈፀም ከጀመረበት ዕለት አንስቶ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140, 1149, 1146/1/, 1144/2/ | 60392 | አቶ ጌትነት የኔ<br>እና<br>አቶ እዮብ ቢንያም | ታህሳስ 26/2003 | |



www.chilot.me